## ማውጫ


ክፍል ሃያ ሁለት ... 1
ማዕድንና ኢነርጂ ... 1
ሀ/ ማዕድን ... 1
አዋጅ ቁጥር 1144/2011 ... 1
የማዕድን ግብይትን ለማስተዳደር የወጣ አዋጅ ... 1
አዋጅ ቁጥር 678/2002 ... 27
የማዕድን ሥራዎች አዋጅ ... 27
ደንብ ቁጥር 182/1986 ዓ.ም ... 76
ስለ ማዕድን ሥራዎች የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ... 76
ለ/ ኢነርጂ ... 104
አዋጅ ቁጥር 295/1978 ... 104
የነዳጅ ሥራዎችን ለማስተዳደር የወጣ አዋጅ ... 104
ደንብ ቁጥር 49/1991 ዓ.ም ... 117
የኤሌክትሪክ ሥራዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ... 117
አዋጅ ቁጥር 247/1993 ዓ.ም ... 146
የነዳጅ ዋጋ ማረጋጊያ ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ ... 146
አዋጅ ቁጥር 317/1995 ... 148
የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ ... 148
አዋጅ ቁጥር 810/2006 ... 158
የኢነርጂ አዋጅ ... 158
ደንብ ቁጥር 447/2011 ... 179
የኢነርጂ ደንብ ... 179
አዋጅ ቁጥር 838/2006 ... 230
የነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች አቅርቦት ሥራ መቆጣጠሪያ አዋጅ ... 230
አዋጅ ቁጥር 981/2008 ዓ.ም ... 242
የጂኦተርማል ሀብት ልማት አዋጅ ... 242
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 453/2011 ... 272
ስለ ጂኦተርማል ሀብት ልማት የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ... 272
ክፍል 23 ... 325
ትራንስፖርትና መገናኛ ... 325

ሀ/ የመንገድ ትራንስፖርት ........ 325
የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 261/1955 ........ 325
የተሽከርካሪ መኪናዎች ክብደትና ልክ መወሰኛ ደንብ ........ 325
የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 361/1961 ........ 334
የ1961 ዓ.ም የባለሞተር ተሽከርካሪዎች ፍጥነት ወሰን ደንብ ........ 334
አዋጅ ቁጥር 468/1997 ........ 340
ትራንስፖርትን ስለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ........ 340
አዋጅ ቁጥር 547/1999 ........ 356
በየብስ የዕቃ ማጓጓዝ ሥራን ለመደንገግ ተሻሽሎ የወጣ አዋጅ ........ 356
አዋጅ ቁጥር 548/1999 ........ 377
የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አዋጅ ........ 377
አዋጅ ቁጥር 589/2000 ........ 397
የመንገድ ልማት ፕሮጀክቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ ........ 397
አዋጅ ቁጥር 681/2002 ........ 399
ስለተሽከርካሪ መለያ፣ መመርመሪያና መመዝገቢያ አዋጅ ........ 399
ደንብ ቁጥር 205/2003 ........ 419
ብሔራዊ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ምክር ቤትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 419
ደንብ ቁጥር 206/2003 ........ 423
የተሽከርካሪ መለያ፣ መመርመሪያና መመዝገቢያ ክፍያ ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 423
ደንብ ቁጥር 208/2003 ........ 428
የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ........ 428
አዋጅ ቁጥር 811/2006 ........ 507
የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የዲመሬጅ ክፍያ ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ........ 507
አዋጅ ቁጥር 843/2006 ........ 514
የክፍያ መንገዶች አዋጅ........ 514
ደንብ ቁጥር 340/2007 ........ 518
በክብደት ላይ የተመሠረተ ዓመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 518
አዋጅ ቁጥር 1048/2009 ........ 524
የባቡር ትራንስፖርት አስተዳደር አዋጅ........ 524

ደንብ ቁጥር 348/2008 ........ 555
የባቡር ትራንስፖርት ትራፊክ እና ደህንነት መቆጣጠርያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ...... 555
አዋጅ ቁጥር 1074/2010 ........ 582
የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ ........ 582
ደንብ ቁጥር 450/2011 ........ 602
የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድና ተያያዥ አገልግሎቶች ክፍያን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 602
ለ/ የአየር ትራንስፖርት ........ 604
አዋጅ ቁጥር 432/1997 ........ 604
የኢትዮጵያ የአቪዬሽን ሴኩሪት አዋጅ ........ 604
አዋጅ ቁጥር 616/2001 ........ 614
የሲቪል አቪዬሽን አዋጅ ........ 614
አዋጅ ቁጥር 957/2008 ........ 662
የኢትዮጵያ የአውሮፕላን አደጋ እና የአደጋ አጋጣሚ ምርመራ አዋጅ ........ 662
ሐ/ የባህር ትራንስፖርት ........ 677
ደንብ ቁጥር 1/1988 ........ 677
ስለመርከብ ምዝገባ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 677
ደንብ ቁጥር 37/1990 ........ 678
የዕቃ አስተላላፊነት እና የመርከብ ውክልና ሥራ ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 678
አዋጅ ቁጥር 549/1999 ........ 684
የማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ........ 684
ደንብ ቁጥር 454/2012 ........ 693
በማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን ለሚሰጡ አገልግሎቶች የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 693
አዋጅ ቁጥር 588/2000 ........ 694
ደረቅ ወደብ ለባለዕቃው ስለሚኖረው ኃላፊነት ለመወሰን የወጣ አዋጅ ........ 694
መ/ ፖስታና ቴሌኮሙኒኬሽን ........ 698
አዋጅ ቁጥር 464/1997 ........ 698
የቴሌኮሙኒኬሽን የኤሌክትሪክ ኃይል አውታሮችን ደህንነት ለመጠበቅ የወጣ አዋጅ ........ 698
አዋጅ ቁጥር 1148/2011 ........ 701
ስለ ኮሙኒኬሽን አገልግሎት የወጣ አዋጅ ........ 701
ክፍል ሃያ አራት ........ 736

ኮንስትራክሽንና ከተማ ልማት ........ 736

አዋጅ ቁጥር 177/1991 ........ 736

ስለኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ምዝገባና ቁጥጥር የወጣ አዋጅ ........ 736

አዋጅ ቁጥር 624/2001 ........ 739

የኢትዮጵያ የሕንፃ አዋጅ ........ 739

ደንብ ቁጥር 243/2003 ........ 764

የሕንጻ ደንብ ........ 764

አዋጅ ቁጥር 370/1995 ........ 793

የጋራ ሕንፃ ባለቤትነት አዋጅ ........ 793

አዋጅ ቁጥር 574/2000 ........ 807

የከተማ ፕላን አዋጅ ........ 807

ክፍል ሃያ አምስት ........ 825

የከተማ ቦታና የገጠር መሬት አስተዳደር ........ 825

አዋጅ ቁጥር 1161/2011 ........ 825

ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት፣ ካሣ የሚከፈልበት እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ አዋጅ ........ 825

ደንብ 472/2012 ........ 843

ለህዝብ ጥቅም ሲባል መሬት ሲለቀቅ ስለሚከፈል ካሳ እና ተነሺ ስለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ........ 843

አዋጅ ቁጥር 456/1997 ........ 870

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ........ 870

አዋጅ ቁጥር 721/2004 ........ 881

የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የወጣ አዋጅ ........ 881

አዋጅ ቁጥር 818/2006 ዓ.ም ........ 904

የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባ አዋጅ ........ 904

ደንብ ቁጥር 323/2006 ........ 929

የከተማ ካዳስተር ቅየሳ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 929

ደንብ ቁጥር 324/2006 ........ 944

የከተማ መሬት ይዞታ ማረጋገጥ እና ምዝገባ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ 944

## ክፍል ሃያ ሁለት

## ማዕድንና ኢነርጂ

### ሀ/ ማዕድን

### አዋጅ ቁጥር 1144/2011

### የማዕድን ግብይትን ለማስተዳደር የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት ድንጋጌ መሰረት የተፈጥሮ ሀብት ባለቤት በመሆኑ፤ የማዕድን ሀብትም ከተመረተ በኋላ ያለውን የግብይትሥርዓት በሕግ እንዲመራ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የሁሉንም ዓይነት ማዕድን ግብይት ለማስፋፋት፣ ሕጋዊ ሥርዓት ለማስያዝና ለመቆጣጠር የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ የሚያስፈልግ ሆኖ በመገኘቱ፤

የማዕድን ግብይት ሥርዓትን ዘመናዊ በማድረግ ዘርፉ ለኢኮኖሚ የሚያበረክተውን አስተዋጽዖ ለማሳደግ የሚያስችል የግብይት ሥርዓት መፍጠር አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት፤

በማዕድን ግብይቱ ላይ የሚሳተፉ አካላት ሚና ሥልጣንና ተግባር መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55 (1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የማዕድን ግብይት አዋጅ ቁጥር 1144/2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. “ማዕድን” ማለት ማናቸውም ዋጋ ያለው በጠጣር፣ በፈሳሽ ወይም በጋዝ መልክ በተፈጥሮ በመሬት ላይ ወይም ውስጥ፣ በውኃ ውስጥ ወይም ስር የሚገኝ በጂኦሎጂ ሂደት ወይም ሁኔታዎች የተፈጠረ ሲሆን ቀደም ሲል ተቆፍሮ በወጣና ተራፊ

የተቆለለ ማዕድን አዘል አፈር ወይም ከቀሪ የማዕድን ክምችት ውስጥ የተመረተ ማዕድንን ይጨምራል፤ ሆኖም የሚከተሉትን አይጨምርም፡-

ሀ) ከውስጡ ማዕድን ለማውጣት ከሚውል እንደ ጨዋማ ውኃ በስተቀር፤ ለኢንዱስትሪ፣ ለመታጠቢያ፣ ለመዝናኛ፣ እና ለሕክምና የሚውል የጂኦተርማል ውኃ እና ሌላውን ውኃ፣

ለ) አግባብ ባለው የነዳጅ ሕግ ትርጓሜ የሚካተቱ የተፈጥሮ ዘይት እና ጋዝ፣

ሐ) ከነዳጅ አዘል አለት የተመረቱ ውጤቶችን፤

2. "የከበረ ማዕድን" ማለት እንደ ፕላቲንየም፣ ወርቅና ብር የመሰለ የከበረ ብረት ነክ ማዕድን ወይም እንደ አልማዝ፣ ሩቢ፣ ኤመራልድ፣ ሳፋየር ያለ ከከበረ ድንጋይ የተመረተ ሲሆን፣ ሚኒስቴሩ በመመሪያ የከበረ ማዕድን ብሎ የሚሰይመውን ማናቸውንም ሌላ ማዕድን ይጨምራል፤

3. "በከፊል የከበረ ማዕድን" ማለት ለማስዋቢያነት የሚውል ወጥ ወይም በተፈጥሯዊ አንድነት የተጣመረ እንደ ሮዶላይት፣ ኦሊቪን፣ ኦፓል፣ ጃዲያትና ላዙራይት የመሰለ ማዕድን ሲሆን፣ የከበሩ ማድናትን ሳይጨምር ሚኒስቴሩ በመመሪያ በከፊል የከበረ ማዕድን ብሎ የሚስይመውን ማንኛውንም ሌላ ማዕድን ይጨምራል፤

4. "ብረት ነክ ማዕድን" ማለት እንደ ብረት፣ መዳብ፣ ነሐስ፣ እርሳስ፣ ክሮማይት፣ ኒኬል፣ ታንታለም እና ማንጋኒስ የመሰለ ማዕድን ሲሆን፣ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናትን ሳይጨምር ሚኒስቴሩ በመመሪያ ብረት ነክ ማዕድን ብሎ የሚሰይመውን ሌላ ማዕድን ይጨምራል፤

5. "የግንባታ ማዕድናት" ማለት ማናቸውም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለኮንስትራክሽን በግብዓትነት የሚያገለግል እንደ ዕብነበረድ፣ ግራናይት፣ ላይምስቶን፣ ባዛልት፣ አሸዋ፣ ጠጠር፣ ኢግኒምብራይትና የሸክላ አፈር የመሰለ ማዕድን ሲሆን፣ ሚኒስቴሩ በመመሪያ የኮንስትራክሽን ማዕድን ብሎ የሚሰይመውን ሌላ ማዕድንን ይጨምራል፤

6. "የኢንዱስትሪ ማዕድን" ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለኢንዱስትሪ በግብዓትነት የሚያገለግል እንደ ካኦሊን፣ ቤንቶናይት፣ ኳርትዝ፣ የድንጋይ ከሰል፣ ላይምስቶን፣ ፖታሽ፣ ጂፕሰም፣ ፑሚስ፣ የሸክላ አፈርና ግራፋይት የመሰለ ማንኛውም ማዕድን ሲሆን፣ ብረት ነክና የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናትን ሳይጨምር ሚኒስቴሩ

በመመሪያ የኢንዱስትሪ ማዕድን ብሎ የሚሰይመውን ማንኛውንም ሌላ ማዕድን ይጨምራል፤

7. “ግብይት” ማለት ማዕድናትን ለንግድ ዓላማ ለመግዛት፣ ለመያዝ፣ ለማጓጓዝ፣ በዕደ ጥበብ ሙያ ለማዘጋጀት፣ ለማጣራት፣ ለማቅለጥ፣ በሀገር ውስጥ ለመሸጥ ወይም ወደ ውጪ ሀገር ለመላክ የሚከናወን ማናቸውም ተግባር ነው፤
8. “አቅራቢነት” ማለት በሀገር ውስጥ የተመረቱ ወርቅና ብር ማዕድናትን ከሕጋዊ አምራች በመግዛት ለብሔራዊ ባንክ አካል፤ ከወርቅና ብር ውጪ ያሉ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናትን ለላኪዎች ወይም የመቅረጽ የዕደ ጥበብ ፈቃድ ላላቸው እና ከነዚህ ከተጠቀሱት ውጪ ያሉትን ማዕድናት ለተጠቃሚዎች የመሸጥ ሥራ ነው፤
9. “ዕደ ጥበብ” ማለት ከከበሩ ወይም በከፊል ከከበሩ ወይም ከብረት ነክ ማዕድናት በማንጠር ወይም በመቅረጽ ወይም የሁለቱን ውጤት አጣምሮ ሌላ ቅርጽ በማስያዝ ማዕድናት የመጨረሻ ቅርጻቸውን እንዲይዙ የማድረግ ሥራ ነው፤
10. “ማንጠር” ማለት የከበሩ ብረት ነክ ማዕድናትን ለተጠቃሚ ፍጆታ በሚሆን መልኩ ማቅለጥ፣ ቅርጽ ማውጣትና ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ማከናወን ነው፤
11. “መቅረጽ” ማለት የከበሩና በከፊል የከበሩ የጌጣጌጥ ማዕድናትን የመጨረሻቸውን ቅርጽ እንዲይዙ ለማድረግ የሚከናወን የመቁረጥ፣ ቅርጽ የማውጣት፣ የማለስለስና ሌሎች ተመሳሳይ ሥራዎችን ማከናወን ነው፤
12. “ማጣመር” ማለት በማንጠር ወይም በመቅረጽ ሥራ የተሰራ ያለቀለት ወይም በከፊል ያለቀለት ጌጥ በመጠቀም የሁለቱ ጥምረትና ውጤት የሆነ የመጨረሻ ቅርጽ ያለው ጌጥ የማምረት ሥራ ነው፤
13. “ማቅለጥ” ማለት ወርቅ፣ ብር ወይም ብረት ነክ ማዕድናትን ለሽያጭ ሊቀርቡ በሚችሉ መልኩ አቅልጦ የተፈለገውን ቅርጽ የማስያዝ ሥራ ነው፤
14. “ማጣራት” ማለት የብረት ነክ ማዕድናትን ጥራት ለመጨመር ከውስጣቸው ያለውን አላስፈላጊ ንጥረ ነገር ማስወገድ ወይም አብረው ያሉ ተያያዥ ማዕድናትን ለመለየት የሚከናወን ተግባር ነው፤
15. “ፈቃድ” ማለት በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የሚሰጥ ማንኛውም የማዕድናት ግብይት ለማከናወን የሚያስችል የንግድ ፈቃድ ነው፤
16. “የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት” ማለት በማዕድናት ግብይት ሥራ ላይ ለመሳተፍ የሚያስችል የንግድ ፈቃድ ለማግኘት ብቁ ስለመሆኑ የሚሰጥ ሠነድ ነው፤

17. “ማሰናዳት” ማለት ማዕድናት የመጨረሻ ቅርጻቸውን እንዲይዙ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ማጠብ፣ ማቅለጥ፣ ማንጠር፣ መፍጨት፣ መቁረጥ፣ ቅርጽ ማውጣት፣ ማስዋብ፣ እና ሌሎች ተያያዥ ሥራዎችን ማከናወን ነው፤
18. “የውጭ ባለሀብት” ማለት የውጭ ካፒታል ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት ኢንቨስት ያደረገ የውጭ ዜጋ ወይም በውጭ ዜጎች ባለቤትነት የተያዘ ድርጅት ሲሆን እንደ ውጭ ባለሀብት መቆጠር የፈለገ መደበኛ ነዋሪነቱ በውጭ ሀገር የሆነ ኢትዮጵያዊን ይጨምራል፤
19. “የሀገር ውስጥ ባለሀብት” ማለት የኢንቨስትመንት ካፒታል በሥራ ላይ ያዋለ ኢትዮጵያዊ ወይም መንግሥትንና የመንግሥት የልማት ድርጅትን እንዲሁም እንደ ሀገር ውስጥ ባለሀብት መቆጠር የፈለገ በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆነ የውጭ ሀገር ዜጋን ይጨምራል፤
20. “ላኪነት” ማለት ወርቅና ብር ሲሆን የመጨረሻ ቅርጻቸውን የያዙ፣ ሌሎች ማዕድናት ሲሆን በጥሬ ወይም በከፊል የተሰናዳውን ከአምራች፣ ከዕደ ጥበብ ወይም ከአቅራቢነት ባለፈቃድ በመግዛት ወደ ውጭ ሀገር የመላክ ሥራ ነው፤
21. “ማስተላለፍ” ማለት መሸጥ፣ በዕዳ ማስያዝ፣ ማውረስ፣ መዳረግ ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ አንድ ሰው ያለውን መብትና ግዴታ የሌላ ሰው እንዲሆን ማድረግ ነው፤
22. “ተረፈ ምርት” ማለት ማዕድናት ሲሰናዱ የሚገኙ ስብርባሪ፣ ውዳቂ፣ አሰር፣ ዝቃጭ፣ ቆሻሻ አዘል ድፍርስ፣ ቆሻሻ፣ አመድ የመሳሰሉት ሲሆኑ ዋጋ ያላቸውና ዋጋ የሌላቸውን እንዲሁም በአካባቢ ላይ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ወይም ጉዳት የማያደርሱትን ያካትታል፤
23. “የግል መጠቀሚያ” ማለት ለንግድ ዓላማ ሳይሆን ግለሰብ በጌጥ መልክ የሚጠቀምበት የመጨረሻ ቅርፁን ያያዘ ወርቅና የከበረ ብረት ነክ ማዕድን፣ የከበረ የጌጥ ማዕድን ወይም በከፊል የከበረ ማዕድን ነው፤
24. “ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን” ማለት እንደ አግባቡ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል ነው፤
25. “የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪ ባለሥልጣን" ማለት እንደአግባቡ ሚኒስቴሩ ወይም የማዕድን ዘርፍ ሥራ የሚመለከተው የክልል አካል ነው፤
26. “ሚኒስቴር” ማለት የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር ነው፤

27. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 (1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤
28. “ባንክ” ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነው፤
29. “የፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ዘመን” ማለት በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ፈቃድ ወይም የምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ የሚቆጠር የአንድ አመት ጊዜ ነው፤
30. “የበጀት ዓመት” ማለት በኢትዮጵያ አቆጣጠር ከሐምሌ 01 ቀን ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን ያለው ጊዜ ነው፤
31. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
32. “የመጨረሻ ቅርጽ” ማለት በማዕድናት ላይ ዕሴት በመጨመር ለግል ማስዋቢያ ወይም ማስጌጫ እንዲያገለግል የተዘጋጀ ያለቀለት የማዕድናት ምርት ውጤት ነው
33. ማንኛዉም በወንድ ጾታ የተገለጸው ድንጋጌ ሴትንም ይጨምራል፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

1. ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ድሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ግዛት ውስጥ በሚካሄድ በማናቸውም መንገድ በሚመረቱ ማዕድናት ግብይት ሥራ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የማዕድን ሥራዎች አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ ያመረተውን ማዕድን በሀገር ውስጥ ወይም በውጭ ሀገር ለመሸጥ በዚህ አዋጅ የተጠቀሰው ፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አያስፈልገውም፡፡

4. <u>ዓላማ</u>

የዚህ አዋጅ ዓላማ የሚከተሉት ናቸው፡-

1. ለሚመረተው ማዕድን ጠንካራ የግብይት ሥርዓት በመፍጠር የሀገሪቷ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ውስጥ የጎላ አስተዋጽኦ እንዲኖረው ለማድረግ፣
2. የማዕድኑን የግብይት ሥርዓት ወቅታዊ አድርጎ በማደራጀት ግብይቱን ከሕገወጥ ተጽዕኖዎች ለመከላከል፣
3. በማዕድን ግብይት ዘርፉ የሚሰማሩ ባለሀብቶች መብትና ግዴታቸውን ተረድተው በሕጉ አግባብ መመራት እንዲችሉ ለማድረግ፤

4. የማዕድን ግብይት ሥርዐቱ የአካባቢና ማኅበራዊ ጥበቃና እንክብካቤ መረሆዎችን በዘላቂነት በጠበቀ ሁኔታ መተግበሩን ለማረጋገጥ፣

## ክፍል ሁለት

## ስለ ፈቃድ እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

### 5. የፈቃድ ወይም የምስክር ወረቀት አስፈላጊነት

1. ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሰረት የማዕድን ግብይት ፈቃድ በማዉጣት የማዕድን ግብይት ማካሄድ ይችላል፡፡
2. ማንኛዉም የማዕድን ግብይት የንግድ ፈቃድ እንዲሰጠው የሚጠይቅ ሰው ፍቃዱ የሚሰጠው ከብቃት ማረጋገጫ መስክር ወረቀት ሰጪ ባለስልጣን የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሲያቀርብ ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ አንድ

## ፈቃድ ስለ መስጠት

### 6. የፈቃድ ዓይነቶች

በዚህ አዋጅ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት የሚከተሉት የማዕድን ግብይት ፈቃዶች ይሰጣሉ ፡-

1. የማዕድን አቅራቢነት ፈቃድ፣
2. የማዕድን ዕደ ጥበብ ፈቃድ፣
3. የማዕድን ማጣራት ፈቃድ፣
4. የማዕድን ማቅለጥ ፈቃድ፣
5. የማዕድን ንግድ ፈቃድ፣
6. የማዕድን ላኪነት ፈቃድ፣

### 7. የማዕድን አቅራቢነት ፈቃድ

1. የማዕድን አቅራቢነት ፈቃድ በሚከተለው ሁኔታ በየማዕድን ዓይነቱ ተለይቶ ይሰጣል፡፡

ሀ) የኮንስትራክሽን ወይም የኢንዱስትሪ ማዕድን ሲሆን ማዕድኑን ከሕጋዊ አምራች የመግዛት፣ ለሽያጭ የመያዝ፣ የማዘዋወር፣ በሀገር ውስጥ ለተጠቃሚ ወይም የላኪነት ፈቃድ ላላቸው ሰዎች የመሸጥ መብት ይሰጣል፤

ለ) ከወርቅ ወይም ከብር ውጭ ያሉ የከበሩ ወይም በከፊል የከበሩ ማዕድናት ሲሆን ማዕድኑን ከሕጋዊ አምራች የመግዛት፣ ለሽያጭ የመያዝ፣ የማዘዋወርና በሀገር ውስጥ የላኪነት ፈቃድ ላላቸው ወይም የዕደ ጥበብ ሥራ ፈቃድ ላላቸው ሰዎች አሳማኝ ምክንያት ከሌለው በስተቀር ከ 60 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የመሸጥ መብት ይሰጣል፤

ሐ) የወርቅ ወይም የብር ሲሆን፣ ማዕድኑን ከሕጋዊ አምራች የመግዛት፣ ለሽያጭ የመያዝ፣ የማዘዋዋርና በሀገር ውስጥ 30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለባንክ ወይም ሕጋዊ ሥልጣን ላለው አካል የመሸጥ መብት ይሰጣል፤

መ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ ሀ፣ ለ ወይም ሐ ከተጠቀሱት ውጪ ላሉት ማዕድናት የሚሰጥ የአቅራቢነት ፈቃድ፣ ማዕድኑን ከሕጋዊ አምራች የመግዛት፣ ለሽያጭ የመያዝ፣ የማዘዋወር በሀገር ውስጥ ለተጠቃሚ ወይም የላኪነት ፈቃድ ላላቸው ሰዎች የመሸጥ መብት ይሰጣል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተጠቀሱት ፈቃዶች ሲሰጡ በየማዕድን ዓይነቱ ተለይተው የሚሰጡ ሲሆን ለአንዱ የማዕድን ዓይነት የተሰጠው ፈቃድ ለሌላ የማዕድን አቅራቢነት አያገለግልም፡፡

8. <u>የማዕድን ዕደ ጥበብ ፈቃድ</u>

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት የማዕድን ዕደ ጥበብ ፈቃድ ዓይነቶች ይሰጣሉ፡-

ሀ) የማንጠር ፈቃድ፣

ለ) የመቅረጽ ፈቃድ፣ወይም

ሐ) የማጣመር ፈቃድ፣

2. የማንጠር ዕደ ጥበብ ፈቃድ ወርቅ ወይም ብርን ሕግ በሚወስነው መሠረት የመግዛት፣ የመያዝ፣ የማጓጓዝ፣ የተበላሹ ወይም የተሰበሩትን የመግዛት እና የመጠገን፣ የማንጠር ሥራ የማከናወን እና ምርቱን በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር

የመሸጥ መብት ይሰጣል፡፡ ሆኖም ይህ ባለፈቃድ ጥሬ ማዕድናት ገዝቶ ጌጣጌጥ መሥራትና መሸጥ አይችልም፡፡

3. የመቅረጽ ዕደ ጥበብ ፈቃድ ከወርቅ፣ ከብርና ከፕላቲንየም ውጪ ያሉትን የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት የመግዛት፣ የመያዝ፣ የማጓጓዝ፣ የመቅረጽ ሥራ የማከናወን እና ምርቱን በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የመሸጥ መብት ይሰጣል፤

4. የማጣመር ዕደ ጥበብ ፈቃድ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ያለቀላቸው ማዕድናትን የመግዛት፣ የማጓጓዝ፣ የመያዝ እና በማጣመር ጌጣጌጥ ሰርቶ ምርቱን በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገር የመሸጥ መብት ይሰጣል፤ ሆኖም ይህ ባለፈቃድ ጥሬ ማዕድናት ገዝቶ ጌጣጌጥ መሥራትና መሸጥ አይችልም፡፡

9. <u>የማዕድን ማጣራት ፈቃድ</u>

የማዕድን ማጣራት ፈቃድ በሀገር ውስጥ የተመረቱ ወይም ከውጭ ሀገር የገቡ ወርቅ ወይም ብር ወይም ሌሎች ብረት ነክ ማዕድናትን ከማዕድን ማምረት ባለፈቃድ፣ ከባንክ ወይም ሌላ ሕጋዊ ፈቃድ ካለው ሰው ተቀብሎ የማጣራት ሥራ በማከናወን መልሶ የማስረከብ ወይም የመሸጥ መብት ይሰጣል፡፡

10. <u>የማዕድን ማቅለጥ ፈቃድ</u>

የማዕድን ማቅለጥ ፈቃድ በሀገር ውስጥ የተመረቱ ወይም ከውጪ የገቡ ብረት ነክ ማዕድናትን የማቅለጥና ተፈላጊውን ቅርጽ የማስያዝ ሥራ የማከናወን መብት ይሰጣል፡፡

11. <u>የማዕድን ንግድ ፈቃድ</u>

1. የማዕድን ንግድ ፈቃድ ከከበሩና በከፊል ከከበሩ ማዕድናት ተሰርተው የመጨረሻ ቅርፃቸውን የያዙ ጌጣጌጦች በጅምላ ገዝቶ በችርቻሮ በሀገር ዉስጥ የመሸጥ መብት ይሰጣል ፡፡
2. የማዕድን ንግድ ፈቃድ በእያንዳንዱ የማዕድን ዓይነት ተለይቶ የብቃት ማረጋገጫ ለተሰጠበት የማዕድን ዓይነት ብቻ ይሆናል፡፡

## 12. የማዕድን ላኪነት ፈቃድ

1. የማዕድን ላኪነት ፈቃድ የመጨረሻ ቅርፃቸዉን የያዙ የወርቅና የብር ማዕድናትን ፣ በጥሬ ፣ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የተሰናዱ የከበሩ እና በከፊል የከበሩ ማዕድናትን እንዲሁም በጥሬዉና እሴት የተጨመረባቸዉን ሌሎች ማዕድናትን ወደ ዉጭ ሀገር የመላክ መብት ይሰጣል፡፡

2. የማዕድን ላኪነት ፈቃድ በእያንዳንዱ የማዕድን ዓይነት ተለይቶ የብቃት ማረጋገጫ ለተሰጠበት የማዕድን ዓይነት ብቻ ይሆናል፡፡

## 13. ፈቃድ ለማግኘት ብቁ ስለመሆን

1.አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የንግድ ሥራ ማካሄድ የሚችል ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንብና መመሪያዎች የተገለጹትን ተፈላጊ ሁኔታዎችን የሚያሟላ ከሆነ በዚህ አዋጅ የተጠቀሱትን ፈቃዶች ማግኘት ይችላል፡፡

2.የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ ቢኖርም፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ ከተጠቀሱት የፈቃድ ዓይነቶች ውስጥ የአቅራቢነት ወይም የወርቅና የብር ማቅለጥ ፈቃድ ለውጭ ባለሀብት አይሰጥም፤

ለ) በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃዱ የተሰረዘበት ሰው ፈቃዱ ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ ለሁለት ዓመታት ሌላ ፈቃድ ማግኘት አይችልም፤

ሐ) የማዕድን ማምረት ባለፈቃድ ለሆነ ሰው የማዕድናት አቅራቢነት ፈቃድ አይሰጠውም፡፡ ይህ አዋጅ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የማዕድን ማምረት ፈቃድ ላለው ሰው የተሠጠ የአቅራቢነት ፈቃድ ይህ አዋጅ ሥራ ላይ ከዋለ ከ 120 ቀን በኋላ በፈቃዱ ላይ ያለው መብት ቀሪ ይሆናል፡፡

## 14.ስለፈቃድ ማመልከቻ

በሌሎች ሕጎች የተደነገጉ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆኖው ለፈቃድ የሚቀረብ ማመልከቻ በጽሑፍ ሆኖ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፡፡

1. ማመልከቻው ለማዕድን አቅራቢነት ፈቃድ ሲሆን፡-
   ሀ) የአመልካቹ ስም፣ የሥራ አድራሻና ዜግነት፣
   ለ) ሊሰማራበት የፈለገውን የማዕድን ዓይነት፣
   ሐ) ማዕድኑን ሊገዛበትና ሊሸጥበት ያቀደበት ሥፍራ፣
   መ) እንደማዕድኑ ዓይነት የሚወሰን ሆኖ ቋሚ የማከማቻ ቦታ እና የመሥሪያ ቦታ ስለመኖሩ ማረጋገጫ ፣
   ሠ) የንግድ ዕቅዱን፣
   ረ) በንግድ ህጉ መሰረት ለንግድ ዕቅዱ ማሰፈፀሚያ የሚያስፈልግ ካፒታል መኖሩን ማረጋገጫ፣
2. ማመልከቻው ለማዕድን ዕደ ጥበብ ፈቃድ ሲሆን፡-
   ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ)፣ (ሠ)፣ እና (ረ) የተመለከቱትን፣
   ለ) አላስፈላጊ ተረፈ ምርቶችን የሚያስወግድበት ሥርዓት፣
   ሐ) በአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ አዋጅ መሠረት የተዘጋጀ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት ሰነድ፣
3. ማመልከቻው ለማዕድን ማጣራት ፈቃድ ሲሆን፡-
   ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ)፣ (መ)፣ (ሠ)፣ እና (ረ) የተመለከቱት፣
   ለ) የማጣሪያ ተቋሙን ለማቋቋም ያለው ችሎታና ልምድ፣
   ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ (ሐ) የተጠቀሰውን፡፡
4. ማመልከቻው ለማዕድን ማቅለጥ ፈቃድ ሲሆን፡-
   ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ 1 በ (ሀ)፣ (ለ)፣ (መ)፣ (ሠ)፣ እና (ረ) የተመለከቱትንና፣
   ለ) ማዕድናትን ለማቅለጥ ያለው የቴክኒክ ብቃት፣
   ሐ) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 (ሐ) የተጠቀሰውን፡፡
5. ማመልከቻው ለማዕድን ንግድ ፈቃድ ሲሆን
   ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ (ሀ) ፣ (ለ) (ሐ) ፣(መ) ፣ (ሠ) እና (ረ) ሥር የተመለከቱትን፤

ለ) የሚሸጠውን ማዕድን ያለውን ጥራትና መጠን ለተጠቃሚዎች ወይም ለደንበኞች የሚያሳውቅበትን ሁኔታ፤

ሐ) የማዕድን ንግድ የሚያከናውንበት ቦታ እንዳለው የሚያሳይ ማስረጃ፣

6. ማመልከቻው ለማዕድን ላኪነት ሲሆን

ሀ) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ (ሀ) ፣ (ለ) ፣ (ሐ) ፣ (መ) እና (ሠ) ሥር የተመለከቱትን፤

ለ) ለመላክ ያቀደው ማዕድን የሚያገኝበት ቦታ፤

ሐ) የ እድ ጥበብ ስራ ላይ የተሰማራ ከሆነ ያለውን ፈቃድ ቁጥር

15. <u>ፈቃድ ስለመስጠት</u>

1. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማመልከቻውን ከተቀበለና አመልካቹ ተገቢ ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላቱን ካረጋገጠ በኋላ ተገቢውን ክፍያ በማስከፈል ለአመልካቹ ፈቃዱን ይሰጠዋል፡፡
2. የቀረበው ማመልከቻ ተቀባይነት ካላገኘ ወይም አመልካቹ በሕጉ መሰረት ፈቃድ ሊሰጠው የማይገባ ከሆነ ፈቃዱ አይሰጥም፡፡
3. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ፈቃዱን የማይሠጥ ከሆነ በ 10 ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ለአመልካቹ ከነምክንያቱ ማሳወቅ አለበት፡፡

16. <u>ስለፈቃድ ዘመን እና እድሳት</u>

1. ማንኛውም ፈቃድ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለአንድ ዓመት የፀና ይሆናል፡፡
2. ፈቃድ የተሰጠው ሰው ፈቃዱን ለማሳደስ አስፈላጊ የሆኑትን ሁኔታዎች ካሟላና የዚህን አዋጅ ወይም ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የወጡ ደንብ እና መመሪያዎችን እንዱሁም አግባብነት ያላቸው ሌሎች ሕጎች በመተላለፍ ለመሰረዝ የሚያበቃ ጥፋት ካልፈጸመ በስተቀር ተገቢውን ክፍያ በመክፈል ለአንድ አመት ጊዜ የማሳደስ መብት ይኖረዋል፤
3. ማንኛውም ፈቃድ የተሰጠው ሰው በእያንዳንዱ ፈቃድ ዘመን ማብቂያ ላይ ፈቃዱን ማሳደስ አለበት፤ ሆኖም በቅጣት ሊታደስ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡
4. ማንኛውም ፈቃድ የተሰጠው ሰው ለዕድሳት በሚቀርብበት ወቅት የወቅቱን በጀት ዓመት ግብር ስለመክፈሉ ከግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

## 17.<u>የባለፈቃድ ግዴታዎች</u>

1. አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች የተደነገጉ ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

   ሀ) እንደማእድኑ ዓይነት የገዛውን፣ ያስቀመጠውን፣ ያጣራውን፣ ያቀለጠውን፣ የሸጠውን ወይም ወደ ውጭ ሀገር የላከውን ማዕድን በተመለከተ መዛግብትና ማኅደር የመያዝ፤

   ለ) በየአመቱ የበጀት ዘመኑ በተጠናቀቀ በ 45 ቀናት ውስጥ ያካሄደውን ግብይት በተመለከተ ለፍቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሪፖርት የማቅረብ፤

   ሐ) በሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ባላቸው ሌሎች አካላት የወጡ የአሰራር፣ የደኅንነትና የጤንነት ደረጃዎች አፈጻጸም በተመለከተ በየሶስት ወሩ ሪፖርት የማቅረብ፤

   መ) በመመሪያ ከተወሰነው በላይ ማዕድን ያለማከማቸት፤

   ሠ) ሥራውን በሚያከናውንበት በማናቸውም ጊዜ ፈቃዱን እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ይዞ የመገኘት ፤

   ረ) በፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ሰጪ ባለሥልጣን ወይም ሕገ ወጥ ንግድና ኮንትሮባንድ ለመቆጣጠር ሕጋዊ ሥልጣን በተሰጣቸው አካላት በሚሰየም ተቆጣጣሪ ፈቃዱን እንዲያሳይ ሲጠየቅ የማሳየት ፤

   ሰ) የያዘውን ማዕድን ምንጭ ለተቆጣጣሪዎች የማሳየት ፡፡

   ሸ) የሥራ ቦታዉን ሲቀይር በቅድምያ ለፈቃድ ሰጪዉ አካል የማሳወቅ

2. የአቅራቢነት ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

   ሀ) በእያንዳንዱ የበጀት ዓመት መጠኑ ከፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ጋር በሚደረገው ስምምነት የሚወሰነውን ወርቅና ብር ለባንኩ ወይም በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብ፤

   ለ) ከወርቅና ከብር ውጪ ያሉ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት በሀገር ውስጥ በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ ላላቸው የመሸጥ፤

   ሐ) የኮንስትራክሽን እና የኢንዱስትሪ ማዕድናትን በሀገር ውስጥ በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ ላላቸው ወይም ለተጠቃሚ የመሸጥ ፤

   መ) የሚያቀርባቸውን ማዕድናት ሕጋዊ ምንጭና አካባቢያቸውን የማሳወቅ፤

ሠ) ሥራውን የሚመራበት ቋሚ አድራሻ የማዘጋጀት እና ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የማሳወቅ፤

ረ) ፈቃድ በወሰደበት ክልል ውስጥ ብቻ ማዕድን የመግዛት፤

ሰ) ወርቅና ብር ሲሆን አቅራቢያው በሚገኘው ግዢ ማዕከል ባንክ ወይም ሕጋዊ ሥልጣን የተሰጠው አካል ድረስ፣ ከወርቅ ወይም ብር ውጪ ያሉትን የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ሲሆን የላኪነት ፈቃድ ወይም መቅረጽ ባለፈቃድ እስካለበት ቦታ ድረስ፣ ሌሎች ማዕድናትን ቀጣይ ገዢ ወይም ተጠቃሚ እስካለበት ቦታ ድረስ ብቻ ይዞ የመንቀሳቀስ፣

ሸ) ማዕድን ሲገዛና ሲሸጥ ሕጋዊ ደረሰኝ የመጠቀም፣

ቀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ለ) መሰረት በየአመቱ ከሚያቀርበው ሪፖርት በተጨማሪ የገዛቸውንና የሸጣቸውን ማዕድናት በተመለከተ በየ 3 ወሩ ለክልል ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን ሪፖርት የማቅረብ፡፡

3. የዕደ ጥበብ ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

ሀ) ለሥራ የሚያስፈልገውን ጥሬ ወረቅ ወይም ብር ከባንክ ወይም ሕጋዊ ሥልጣን ከተሰጠው አካል ብቻ የመግዛት፣

ለ) የገዛውን ወርቅ ወይም ብር በጥሬ መልኩ ለማንኛውም ሰው ያለማስተላለፍ፣

ሐ) ከወርቅና ብር ውጪ የሆኑ ሌሎች ማዕድናት ሲገዛ ምንጩ ሕጋዊ መሆኑን የማረጋገጥ፣

መ) በሚያመርታቸው የማዕድናት ውጤቶች ላይ ሊለዩ የሚችሉ የራሱ የሆነ ምልክት የማድረግ፣

ሠ) ማንኛውም ሰው ምርቱን በሚገዛበት ወቅት ምልክቱን እንዲለይ፣ ጥራቱንና ብዛቱን እንዲያውቅ የማድረግና ለዚህም ለተገልጋዩ ማረጋገጫ የመስጠት፣

ረ) በመመሪያ ከተወሰነው በላይ የወርቅና ብር ክምችት ሲኖረው ለባንኩ ወይም ሕጋዊ ሥልጣን ላለው አካል የመሸጥ፡፡

4. የማዕድን ማጣራት ባለፈቃድ በሚያጣራው ማዕድን ላይ ሊለዩ የሚችሉ የራሱ የሆነ ምልክት የማድረግ፣ ጥራቱንና መጠኑን እንዲታወቅ የማድረግና ለዚህም ለተገልጋዩ ማረጋገጫ የመስጠት ግዴታ አለበት።

5. የማዕድን ማቅለጥ ባለፈቃድ በሚያቀልጠው ማዕድን ምርት ላይ ሊለዩ የሚችሉ የራሱ የሆነ ምልክት የማድረግ፤ መጠኑን የመግለጽ ለዚህም ለተገልጋዩ ማረጋገጫ የመስጠት ግዴታ አለበት።
6. የማዕድን ንግድ ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-
   ሀ) ከዕደ ጥበብ ባለፈቃዶች የሚረከባቸውን ምርቶች ተገቢው ምልክት እንዳላቸው የማረጋገጥ ፤
   ለ) ከዕደ ጥበብ ባለፈቃዶች የሚረከባቸውን ምርቶች ይዞታቸውን ያለመቀየር ወይም ከሌላ ማዕድናት ጋር ያለመቀላቀል፤
   ሐ) ተጠቃሚ ወይም ደንበኛው ከእሱ የሚገዛውን ምርት ጥራትና መጠን ማወቁን የማረጋገጥ ለዚህም ማረጋገጫ የመስጠት፡፡
7. የማዕድን ላኪነት ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-
   ሀ) የሚልከው ጥሬ ማዕድን ከሆነ ማዕድኑን ያገኘበትን ሕጋዊ ምንጭ የማሳየት፤
   ለ) የሚልከው ሙሉውን ወይም በከፊል ያለቀለት ማዕድን ከሆነ ሕጋዊ ምንጩን ከማሳየት በተጨማሪ ማዕድኑን ያሰናዳውን ሰው ስምና የፈቃድ ቁጥሩን የያዘ ማስረጃ የማቅረብ ፤
   ሐ) ማዕድናት ወደ ውጪ ሲልክ ተገቢውን የባንክ ሕግ የማክበር፤
   መ) ወደ ውጪ የሚላከው ወርቅ ወይም ብር ሲሆን በጌጥ መልክ የተሰሩ የመጨረሻ ቅርፃቸውን የያዙ ብቻ የመላክ፤
   ሠ) ጥሬ ወይም በከፊል ያለቀለት ወይም የመጨረሻ ቅርጹን የያዘ ማዕድን ሲገዛና ሲሸጥ ሕጋዊ ደረሰኝ የመጠቀም፤
   ረ) እንደ አግባብነቱ የገዛውን ወይም ወደ ውጭ ሀገር የላከውን ማዕድን በተመለከተ መዛግብትና ማኅደር የመያዝ፡፡

18. <u>ፈቃድ ማስተላለፍ</u>

ከማዕድን አቅራቢነት ፈቃድ በስተቀር ሌሎች ፈቃዶችን ፈቃድ ሰጪውን ባለሥልጣን አስቀድሞ በማስፈቀድ ማስተላለፍ ይቻላል፡፡ ፈቃድ የሚተላለፈው በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ይሆናል።

19. **ፈቃድ ስለማገድና ስለመሰረዝ**

1. አግባብነት ያላቸው ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ ፈቃድ ባለፈቃዱ፡-
   ሀ) አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት መያዝ የሚገባውን መዛግብትና ማኅደሮች ካልያዘ፤
   ለ) ሕጋዊ የግብይት ሰነድ ሳይጠቀም ማዕድን ከገዛ ወይም ከሸጠ ወይም ካስተላለፈ፤
   ሐ) በፈቃዱ ላይ ከተገለፀው ክልል ወጪ ሲሰራ ከተገኘ፤
   መ) ተቆጣጣሪዎች ወደ ሥራ ቦታ እንዳይገቡ ከከለከለ ወይም ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም መዝገቦች፣ ማኅደሮች ወይም ሌሎች ሰነዶች እንዳያዩ ካደረገ፤ ወይም
   ሠ) የአካባቢን፣ ጤንነትንና ደኅንነትን የሚመለከቱ ግዴታዎችን ከጣሰ፤ፈቃዱ ይታገዳል፡፡
2. አግባብነት ያላቸው ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ ፈቃድ ባለፈቃዱ፡-
   ሀ) ባለፈቃዱ ሥራውን በራሱ ፍቃድ የተወ እንደሆነ፤
   ለ) ፈቃዱን ያገኘው የሀሰት መረጃዎችን በማቅረብ ሲሆን፤
   ሐ) በዚህ አዋጅ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ፈቃዱን ሳያሳድስ ከቀረ፤
   መ) በፈቃዱ ላይ ባልተመለከቱ ማዕድናት ግብይት ሥራዎች ላይ ተሰማርቶ ከተገኘ፤
   ሠ) በፈቃዱ የተፈቀደለትን ማዕድን ፈቃድ ከሌለው ሰው ከገዛ ወይም የገዛውን ማዕድን ፈቃድ ለሌለው ሰው ከሸጠ ወይም ካስተላለፈ፤
   ረ) በተሰጠው ፈቃድ ከሚሰራው ሥራ ጋር በተያያዘ ሕገወጥ ግብይት ካካሄደ ወይም የማጭበርበር ተግባር ከፈጸመ፤
   ሰ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች መሠረት ፈቃድ ለማገድ ምክንያት የሆኑትን ሁኔታዎች በደንብ በሚወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማስተካከል ካልቻለ፤ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡

20. **ስለፈቃድ ክፍያ**

በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ ለመስጠት፣ ለማሳደስና ለሌሎች ተያያዥ አገልግሎቶች የሚጠየቀው ክፍያ በፈቃድ ሰጪዉ ባለስልጣን እየተሰራበት ባለው ሕግና አሰራር ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**ምዕራፍ ሁለት**

**ስለ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት**

21. **የብቃት ማረጋጋጫ የምስክር ወረቀት ዓይነቶች**

በማዕድን ግብይት ስራ የሚከተሉት የብቃት ማረጋጋጫ የምስክር ወረቀቶች ይሰጣሉ፡-

1. የማዕድን አቅራቢነት ብቃት የማረጋጋጫ የምስክር ወረቀት፤
2. የማዕድን ዕደ ጥበብ ብቃት የማረጋጋጫ የምስክር ወረቀት፤
3. የማዕድን ማጣራት ብቃት የማረጋጋጫ የምስክር ወረቀት፤
4. የማዕድን ማቅለጥ ብቃት የማረጋጋጫ የምስክር ወረቀት፤
5. የማዕድን ንግድ ብቃት ማረጋጋጫ የምስክር ወረቀት፤
6. የማዕድን ላኪነት ብቃት ማረጋጋጫ የምስክር ወረቀት፤

22. **የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ብቁ ስለመሆን**

1. ማንኛውም በንግድ ሕግ መሠረት የንግድ ሥራ ማካሄድ የሚችል ሰው በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንብና መመሪያዎች የተገለጹትን ተፈላጊ ሁኔታዎችን የሚያሟላ ከሆነ በዚህ አዋጅ የተጠቀሰውን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት ይችላል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም፡-
   ሀ) የማዕድን ንግድ ወይም የላኪነት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለውጭ ባለሀብት አይሰጥም፤
   ለ) በዚህ አዋጅ መሠረት የምስክር ወረቀቱ የተሰረዘበት ሰው የምስክር ወረቀት ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ ለሁለት ዓመታት ሌላ የምስክር ወረቀት ማግኘት አይችልም፤

3. በዚህ አዋጅ መሠረት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ሥራውን ከመጀመሩ በፊት አግባብ ካለው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ተገቢ ሁኔታ በመሟላት ፈቃድ መውሰድ አለበት፡፡

23. <u>ስለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማመልከቻ</u>

የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ በጽሑፍ ሆኖ መያዝ ያለበት መስፈርት እንደአግባቡ ፍቃድ ለማግኘት በዚህ አዋጅ አንቀፅ 14 የተደነገጉት እና ሌሎች ሚኒስትሩ በመመርያ የሚወስናቸው ይሆናል፡

24.<u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት</u>

1. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሰጪው ባለሥልጣን ማመልከቻውን ከተቀበለና አመልካቹ ተገቢ ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላቱን ካረጋገጠ በኋላ ተገቢውን ክፍያ በማስከፈል ለአመልካቹ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡
2. የቀረበው ማመልከቻ ተቀባይነት ካላገኘ ወይም ለአመልካቹ በሕጉ መሰረት የምስክር ወረቀት ሊሰጠው የማይገባ ከሆነ የምስክር ወረቀቱ አይሰጥም፡፡
3. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የምስክር ወረቀት የማይሰጥ ከሆነ በ 5 ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ለአመልካቹ ከነምክንያቱ ማሳወቅ አለበት፡፡

25. <u>ስለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ዘመን እና እድሳት</u>

1. ማንኛውም የምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለአንድ ዓመት የፀና ይሆናል፡፡
2. የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው የምስክር ወረቀቱን ለማሳደስ አስፈላጊ የሆኑትን ሁኔታዎች ካሟላና የዚህን አዋጅ ወይም ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የወጡ ደንብ እና መመሪያዎችን በመተላለፍ ለመሰረዝ የሚያበቃ ጥፋት ካልፈጸመ በስተቀር ተገቢውን ክፍያ በመክፈል ለአንድ አመት ጊዜ የማሳደስ መብት ይኖረዋል፤
3. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለቤት በያንዳንዱ የምስክር ወረቀት ዘመን ማብቂያ ላይ ማሳደስ አለበት፡፡ ሆኖም በቅጣት ሊታደስ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡አለበት፡፡ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡
4. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለቤት ለዕድሳት በሚቀርብበት ወቅት የወቅቱን በጀት ዓመት ግብር ስለመክፈሉ ከግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

26. <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለማገድና ስለመሰረዝ</u>

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የምሥክር ወረቀት ባለቤቱ-
    - ሀ) አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት መያዝ የሚገባውን መዛግብትና ማኅደሮች ካልያዘ፤
    - ለ) ሕጋዊ የግብይት ሰነድ ሳይጠቀም ማዕድናትን ከገዛ ወይም ከሸጠ ወይም ካስተላለፈ፤
    - ሐ) ተቆጣጣሪዎች ወደ ሥራ ቦታ እንዳይገቡ ከከለከለ ወይም ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም መዝገቦች፣ ማኅደሮች ወይም ሌሎች ሰነዶች እንዳያዩ ካደረገ የምስክር ወረቀቱ ይታገዳል፡፡
2. በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለቤቱ፡-
    - ሀ) ሥራውን በራሱ ፍቃድ የተወ እንደሆነ፤
    - ለ) የምስክር ወረቀቱን ያገኘው የሀሰት መረጃዎችን በማቅረብ ከሆነ፤
    - ሐ) በዚህ አዋጅ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የምስክር ወረቀቱን ሳያሳድስ ከቀረ፤
    - መ) በምስክር ወረቀት ላይ ባልተመለከቱ ማዕድናት ግብይት ሥራዎች ላይ ተሰማርቶ ከተገኘ፤
    - ሠ) በብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ የተፈቀደለትን ማዕድን ፈቃድ ከሌለው ሰው ከገዛ ወይም ፈቃድ ለሌለው ሰው ከሸጠ ወይም ካስተላለፈ፤
    - ረ) በተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከሚሰራው ሥራ ጋር በተያያዘ ሕገወጥ ግብይት ካካሄደ ወይም የማጭበረበር ተግባር ከፈጸመ፤
    - ሰ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማገድ ምክንያት የሆኑትን ሁኔታዎች በደንብ በሚወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማሰተካከል ካልቻለ፤የምስክር ወረቀቱ ይሰረዛል፡፡

27.<u>ስለብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ክፍያ</u>

በዚህ አዋጅ መሠረት የምስክር ወረቀት ለመስጠት፣ ለማሳደስ ወይም ለሌሎች ተያያዥ አገልግሎት የሚጠየቀው ክፍያ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ሲሆን ከዚህ በፊት ይሰራባቸው የነበሩት የክፍያ ሥርዓቶች ደንቡ ሥራ ላይ እስከሚውልበት ቀን ድረስ ተፈጻሚነቱ ይቀጥላል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለ አስተዳደር

### 28. ፈቃድና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመስጠትና የማስተዳደር ሥልጣን

1. የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡-
   ሀ) ፈቃድ የመስጠት፣ የማደስ፣ የመሰረዝ እና የግብይት ሥርዓቱ በአግባቡ መከናወኑን የመከታተልና የመቆጣጠር፤
   ለ) የማዕድን ማጣራት ፈቃድ፣ የብረትና ብረት ነክ ማዕድናት ማቅለጥ ፈቃድ እና የማዕድናት ላኪነት ፈቃድ የመስጠት፤
   ሐ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የማዕድናት ግብይት ሕጋዊነትን የመቆጣጠር እና ሕገወጥ የማዕድናት ግብይት ፈጻሚዎች ለሕግ እንዲቀርቡ የማድረግ፡፡
   መ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን አስፈላጊነቱ ለታመነባቸው ማዕድናት የገበያ ማዕከል የማቋቋም፤
2. የሚኒስቴሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡-
   ሀ) የማዕድን ማጣራት ብቃት ማረጋገጫ፣ የብረትና ብረት ነክ ማዕድናት ማቅለጥ ብቃት ማረጋገጫ እና የማዕድናት ላኪነት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመስጠት፤
   ለ) የማንጠር፣ የመቅረጽ፣ የማጣመር እና የማጣራት ሥራዎች የሚያከናውኑበትን የአሠራር ደረጃ የማውጣትና የማስፈጸም፤
   ሐ) ከሀገር በሚወጡና በሚገቡ ማዕድናት ላይ የቤተ-ሙከራ ምርመራ መደረጉን የማረጋገጥና የቁጥጥር ፍተሻ የማድረግ፤
   መ) በአለም አቀፍ ደረጃ ዋጋቸው በግልጽ የማይታወቅ ማዕድናት ለሽያጭ ሲቀርቡ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ዋጋቸውን የመወሰን፤
   ሰ) በደረጃ ተለይተው ለውጭ ገበያ ለሚቀርቡ ማዕድናት ደረጃ ማውጣት፡፡
3. ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባር ውስጥ አስፈላጊነቱ የታመነበትን ውስን ሥራ አግባብነት ላላቸው የፌዴራልና የክልል አካላት በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ( ለ ) እና ንዑስ አንቀጽ 2 ( ለ ) ከተዘረዘሩት ውጭ ያሉት ፈቃዶችና የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቶች በክልሎች ይሰጣሉ፡፡

29. <u>ስለ ክትትልና ቁጥጥር</u>

1. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪው ባለስልጣን የሚመድባቸው ተቆጣጣሪዎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክርወረቀት ባለቤት ስራ ቦታ የመግባት፣ ናሙና የመውሰድ፣ የክትትልና ቁጥጥር ስራዎችን የማከናወን ስልጣን ይኖራቸዋል።
2. ተቆጣጣሪዎች ስራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት ሊኖራቸው የሚገቡ ግዴታዎች በደንብ ይወሰናል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>
## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

30. <u>የባንክ ኃላፊነት</u>

ባንኩ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

1. በባሕላዊና በልዩ አነስተኛ ማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃዶች የሚመረተውን የወርቅ ወይም የብር ማዕድናት ከአምራቾች ወይም ከአቅራቢዎች የመግዛት፣
2. የዕደ ጥበብ ባለፈቃዶች የሚያስፈልጋቸውን የወርቅ ወይም የብር ማዕድናት በሽያጭ የማቅረብ፣
3. አቅራቢዎችን ሊያበረታቱ የሚችሉ የክፍያ ሁኔታዎች እንዲመቻቹ ፣ የግዢ ማዕከላት ተደራሽነት እንዲኖራቸው እና የግብይት ሥርዓቱ የተቀላጠፈ እንዲሆን የማድረግ፣

31. <u>የማዕድናትን ናሙናዎች በጊዜያዊነት ወደ ውጭ ሀገር ስለመላክ</u>

1. የማዕድን ዕደ ጥበብ ባለፈቃድ የመጨረሻ ቅርጻቸውን የያዙ ወርቅና ብር ወይም በከፊል ወይም ሙሉ ለሙሉ ያለቀላቸው የሌሎች ማዕድናት ናሙናዎችን ለማስተዋወቅ ዓላማ በባንኩ መመሪያ መሠረት በጊዚያዊነት ወደ ውጭ ሀገር መላክ ይችላል፤

2. የማዕድናት ላኪነት ፈቃድ ባለቤት የመጨረሻ ቅርጻቸውን የያዙ ወርቅና ብር እንዲሁም ሌሎች ማዕድናትን በጥሬ፣ በከፊል ወይም ሙሉ ለሙሉ የተሰናዱ ናሙናዎችን በባንኩ መመሪያ መሠረት ለማስተዋወቅ ዓላማ በጊዜያዊነት ወደ ወጭ ሀገር መላክ ይችላል፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተመለከተው ቢኖርም የዕደ ጥበብ ወይም የላኪነት ፈቃድ ያለው ሰው የመጨረሻ ቅርጽ የያዙ ወርቅ እና ብር እንዲሁም ሌሎች ማዕድናትን በጥሬ፣ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የተሰናዳውን ለማስተዋወቅ ዓላማ ወደ ውጪ መላክ የፈለገ ከሆነ በሚከተለው ሥነ ሥርዓት መሠረት ይሆናል፡-

   ሀ) አመልካቹ የዓለም አቀፍ ዋጋ ላላቸው በዋጋቸው እንዲሁም ዓለም አቀፍ ዋጋ ከሌላቸው ደግሞ ሚኒስቴሩ በሚተምነው መሠረት የባንክ ዋስትና ያስይዛል፤

   ለ) ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ መሠረት የማዕድናት ናሙናዎቹ ወደ ውጭ ሀገር ሲላኩና ወደ ሀገር ውስጥ ሲመለሱ ዓይነታቸውን፣ ጥራታቸውንና መጠናቸውን ያረጋግጣል፤

   ሐ) በዚህ አንቀጽ መሠረት ወደ ውጭ ሀገር የተላኩት የማዕድናት ናሙናዎች በዘጠና ቀናት ውስጥ በሙሉ ወይም በከፊል ካልተመለሱ ባንኩ እና ሚኒስቴሩ በባንክ የተያዘው የዋስትና ገንዘብ ወደ ሚመለከተው የመንግሥት አካል ገቢ እንዲሆን ያደርጋሉ፤

   መ) ተመላሽ የሆኑት ናሙናዎች ቀደም ሲል ከተላኩት ጋር በመጠን፣ በጥራት ወይም በዓይነት አንድ ዓይነት አለመሆናቸውን ሚኒስቴሩ ካረጋገጠ የዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ /ሐ/ ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ ሆኖም እንደ ማዕድኑ ዓይነትና ባሕሪይ በምርመራ ወቅት ከመጠናቸው የተወሰነውን ያህል ሊቀንሱ የሚችሉ ማዕድናት ዝርዝር በደንብ ይገለጻል፡፡

32. <u>እሴት መጨመር</u>

ዝርዝሩ እንደ ማዕድናቱ እና እንደ ፈቃዱ ዓይነት የሚወሰን ሆኖ የግብይት ባለፍቃድ ማዕድናት በተሻለ ዋጋ መሸጥ እንዲችሉ፣የማለስለስ ፣የማስዋብ የማጣመር፣ ቅርጽ የማውጣት እና ሌሎች መሰል ተግባራትን ማከናወን አለበት፡፡

## 33.ተረፈ ምርት

1. የዕደ ጥበብ ፣ የማጣራት፣ የማቅለጥ ሥራዎች ሲከናወኑ የሚፈጠሩት ዋጋ የማያወጡ የአካባቢ ብክለት የሚያስከትሉ ተረፈ ምርቶችን ባለፈቃዱ በአግባቡ ማስወገድ አለበት፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው ተረፈ ምርት ዋጋ የሚያወጣ ከሆነ ጥቅም ላይ የሚውልበትን አግባብ ሚኒስቴሩ በመመሪያ ይወስናል፡፡

## 34. ስለግል መጠቀሚያ

ማንኛውም ሰው ፈቃድ ሳያስፈልገው የመጨረሻ ቅርጹን የያዘ የግል መጠቀሚያውን ማዕድን መያዝ፣ ማጓጓዝ፣ ይዞ ከሀገር መውጣት ወይም ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት ስለሚችልበት ሁኔታ፣ መጠንና ጥራት በደንብ ይወሰናል።

## 35. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው የዚህን አዋጅ አዋጁን ለማስፈጸም የሚወጡ ደንብና መመሪያዎችን በማስፈጸም ሂደት አግባብ ካለው ባለሥልጣን ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## 36. የተከለከሉ ተግባራት

ከዚህ በታች የተመለከቱትን ተግባራት መፈፀም የተከለከለ ነው፡፡

1. በዚህ አዋጅ እና አግባብነት ያለቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት የተሰጠ የፀና ንግድ ፈቃድ ሳይኖረው የማዕድን ግብይት ማከናወን፤
2. ማንኛውም ባለፈቃድ በፈቃዱ ያልተመለከቱትን ሥራዎች ማከናወን፤
3. የአቅራቢነት ባለፈቃድ ወርቅ ወይም ብርን ከባንኩ ወይም በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል ውጭ ማስተላለፍ፣ የተሳሳተ ጥራት ያለው ወርቅ ወይም ብር መሸጥ ወይም በማናቸውም ሁኔታ ለባንኩ ወርቅ ወይም ብርን ከመሸጥ ጋር በተያያዘ የማታለል ተግባር መፈፀም፤
4. ማንኛውም የማዕድናት ንግድ ፍቃድ ባለቤት አግባብ ባለው የዕደ ጥበብ ባለፈቃድ ያልተመረተን ምርት መሸጥ፣ በዕደ ጥበብ ባለፈቃድ የተመረተን ምርት ጥራቱን ወይም መጠኑን በሚያበላሽ መልኩ መቀያየር፣ ወይም ተጠቃሚ ወይም ደንበኛ የሚገዛውን ምርት ጥራትና መጠን ሊገባው ወይም ሊያውቀው በማይችለው ሁኔታ ማከናወንና የጽሑፍ ማረጋገጫ መግለጫ አለመስጠት፤

5. ማንኛውም የዕደ ጥበብ ባለፈቃድ ከባንክ ወይም ሌላ ሕጋዊ ሥልጣን ከተሰጠው አካል ውጭ ወርቅና ብርን መግዛት ወይም የገዛውን ወርቅና ብር በጥሬ መልኩ ለሌላ ማስተላለፍ፤
6. ማንኛውም ባለፈቃድ የከበሩ ወይም በከፊል የከበሩ ማድናትን በመመሪያ ከሚወሰነው በላይ ማከማቸት፤
7. ማንኛውም የላኪነት ወይም የዕደ ጥበብ ፈቃድ ባለቤት ለማስተዋወቅ ወይም ለየቤተ ሙከራ ፍተሻ ተግባር በጊዜያዊነት ከሀገር ያወጣቸውን የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት በዚህ አዋጅ ድንጋጌ ከተመለከተው ውጪ ሳይመልስ መቅረት፤
8. ማንኛውም የዕደ ጥበብ ባለፈቃድ በሚያመርታቸው ጌጣጌጦች ላይ በዚህ አዋጅ በተመለከተው መሠረት ተገቢውን ምልክት አለማድረግ ወይም የሚሸጣቸውን ምርቶች ተጠቃሚ ወይም ደንበኛው ጥራቱንና መጠኑን ሊገባው ወይም ሊያውቀው በማይችልበት ሁኔታ ማድረግና ተገቢውን የጽሑፍ ማረጋገጫ አለመስጠት፤ጥራት የሚያጎድሉ ባዕድ ነገሮችን መጨመር
9. የላኪነት ፈቃድ ባለቤት የቤተ ሙከራ ውጤቱ የማይታወቅ ጥራቱ የተጓደለ ማዕድን ለሽያጭ ወይም ለማስተዋወቅ ዓላማ ወደ ውጭ መላክ፤
10. በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረትና በኢንዱስትሪው የሚፈለገውን ተገቢውን የቴክኒክ ዝግጅት ሳያደርጉ የዕደ ጥበብ ሥራውን ማከናወን፤
11. በሚኒስቴሩ ወይም በሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ስለደህንነትና ስለአካባቢ ጥበቃ የወጡትን የአሰራር ደረጃዎችን መጣስ፤
12. ማንኛውም የማዕድን ማጣራት ፈቃድ ባለቤት የተሳሳተ የማጣራት ውጤት ማስተላለፍ ወይም የማጣራት ሥራውን ከተገቢው ደረጃ በታች ማከናወን፤
13. በዚህ አዋጅ ወይም አዋጁን ተከትሎ በሚወጣ ደንብ መሰረት ለግል መጠቀሚያ ከተፈቀደው በላይ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናትን መያዝ፣ ማከማቸት፣ ማጓጓዝ፣ ከሀገር ማውጣት ወይም ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣
14. ማኛውም የማዕድን ማቅለጥ ፈቃድ ባለቤት ከማዕድን ማቅለጥ ጋር በተያያዘ ሥራውን በአግባቡ አለማከናወን ወይም የማታለል ተግባር መፈጸም፣
15. የዚህ አዋጅ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚወጣ ደንብ፣ መመሪያ መጣስ፡፡

## 37. ቅጣቶች

1. ማንኛውም ሰው ተገቢ ፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖረው፡-
   ሀ) በከበሩ ወይም በከፊል በከበሩ ወይም ብረት ነክ ማዕድናት ግብይት ሥራ ላይ ከተሰማራ በእጁ የሚገኘው ማዕድናትና ተያያዥ መሣሪያዎች ወይም ማሽኖች የሚወረሱበት ሆኖ ከ 50ሺ - 100ሺ ብር ገንዘብ ቅጣት እና እስከ 7 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፤
   ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ሀ) ከተጠቀሰው ማዕድን ውጭ በሌሎች የማዕድን ዓይነት ግብይት ሥራ ላይ ከተሰማራ በእጁ የሚገኘው ማዕድናት የሚወረሱበት ሆኖ ከ 30ሺ - 50ሺ ብር ይቀጣል፤እና እስከ 1 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፤
2. ማንኛውም ባለፈቃድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 2፣ 6 እና 7 ሥር የተደነገገውን የተላለፈ ከብር 30ሺብር - 50ሺ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጫ እና እስከ 7 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፤
3. ማንኛውም ባለፈቃድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 3 እና 5 ሥር የተደነገገውን የተላለፈ ከሥራው ጋር ተያያዥነት ያላቸው መሳሪያዎችና ማሽነሪዎች እንዲሁም ማዕድኑ የሚወረስና ድርጅቱ የሚዘጋ ሆኖ ከብር 50ሺ - ብር 150ሺብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጫ እና እሰከ 10 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፤
4. ማንኛውም ባለፈቃድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 4፣ 8፣ 9፣ 10 እና 12 ሥር የተደነገገውን የተላለፈ ከብር 50ሺ- ብር 80ሺ በሚደርስ የገንዘብ መቀጫና እሰከ 10 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፤
5. ማንኛውም ባለፈቃድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 11 ሥር የተደነገገውን የተላለፈ የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ ጉዳይ ላይ የተቀመጡትን የጥፋት ውሳኔዎች ተግባራዊ ይሆናሉ፤
6. ማንኛውም ባለፈቃድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 13 የተደነገገውን የጣሰ ማዕድኑ ይወረሳል፡፡

7. ማንኛውም የማዕድን ማቅለጥ ባለፈቃድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 14 የተደነገገውን የማታለል ተግባር ከፈፀመ ከብር 100ሺ.- ብር 150ሺ. በሚደርስ የገንዘብ መቀጫና እስከ 10 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፤
8. ማንኛውም የማዕድን ማቅለጥ ባለፈቃድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 14 የተደነገገው ሥራውን በአግባቡ ባለማከናወን ለሚያደርሰው ጉዳት ከ 50ሺ.- ብር 100ሺ. በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤
9. ማንኛውም የማንጠር ዕደ ጥበብ ባለፈቃድ ከግለሰብ በግዢ የሚሰበስባቸውን የተበላሹ ወይም የተሰበሩ የወርቅና ብር መጠን በዚህ አዋጅ በተመለከተው መሠረት ሪፖርት አለማድረግ ከብር 20ሺ.- ብር 30ሺ. በሚደርስ የገንዘብ መቀጫና እሰከ 3 ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል፡፡

38.<u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

ከከበሩ ማዕድናት ዉጪ በሆነ የማዕድን ግብይት ላይ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎቾ ተፈፃሚ የሚሆነው አዋጁ ከጸናበት ቀን ጀምሮ ከስድስት ወር በኃላ ይሆናል፡፡

39.<u>የተሻሩ ሕጎች</u>

1. የከበሩ ማዕድናት ግብይት አዋጅ ቁጥር 651/2001 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

40. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዐስ አንቀጽ 1 መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

41.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሀሴ 9 ቀን 2011 ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 678/2002

## የማዕድን ሥራዎች አዋጅ[1]

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት የመንግሥትና የሕዝብ መሆኑ የተደነገገ በመሆኑና መንግሥትም ይህን ሀብት የመጠበቅ ኃላፊነት የተጣለበት በመሆኑ፤

ማዕድናት የማይታደሱ የተፈጥሮ ሃብቶች በመሆናቸው ጥበቃቸውና ለመላ ኢትዮጵያዊያን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጥቅም መዋላቸው በመንግሥት መረጋገጥ ያለበት ስለሆነ፤

ለአሁኑና ለወደፊቱም ትውልድ ጥቅም አካባቢን መጠበቅና ከሥነምህዳር ጋር የሚጣጣም ዘላቂነት ያለው የማዕድን ልማትን ማረጋገጥ የመንግሥት ኃላፊነት በመሆኑ፤

እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የማዕድን ሥራዎችን በተመለከተ አዲስ ሕግ ማውጣት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የማዕድን ሥራዎች አዋጅ ቁጥር 678/2002" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**[2]

   የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

   1. "መመሳጠር የሌለበት ግብይት" ማለት የሚሸጠውን የማዕድን ሃብት ጥራትና መጠን ብቻ ግምት ውስጥ በማስገባት ምንም ሽርክና ወይም የተለየ ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል በግልጽ ገበያ ላይ በነፃ ድርድር የዚህ አይነት ሃብት በተመሳሳይ በሚሸጥበት ሁኔታ ላይ ተመስርቶ የሚኖረው የገበያ ዋጋ ነው፤

---

[1] የዚህ አዋጅ አንቀጽ 32 እና 33 በ20/27 (2006) አ. 816 አንቀጽ 2(9) መሰረት አዲስ የገቡ ሲሆን ነባሮቹ አንቀጾች ከ32 እስከ 83 የነበሩት እንደቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ 34 እስከ 85 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

[2] የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2፣ 19 እና 20 በ20/27 (2006) አ. 816 አንቀጽ 2 (1)፣ (2) እና (3) የተሻሻሉ ሲሆን ከአንቀጽ 41 እስከ 44 ያሉት ድንጋጌዎች በዚሁ በአዋጅ አንቀጽ 2(4) መሰረት አዲስ የገቡ ናቸው፡፡

2. “ባህላዊ የማዕድን ማምረት ስራ” ማለት አብዛኛው ተግባር በእጅ የሚከናወን እና ተቀጣሪ ሰራተኛ የማይሳተፍበት የግለሰቦች ወይም በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚከናወን የማዕድን ማምረት ስራ ነው፤”
3. “የኮንስትራክሽን ማዕድን” ማለት ማናቸዉም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለኮንስትራክሽን በግብዓትነት የሚያገለግል አንድ ዕብነበረድ፣ ግራናይት፤ ላይምስቶን ባዛልት፣ አሸዋ፣ ጠጠር፣ ኢግኒምብራይትና የሸክላ አፈር የመሰለ ማዕድን ሲሆን፣ ሚኒስቴሩ በመመሪያ የኮንስትራክሽን ማዕድን ብሎ የሚሰይመውን ብረት ነክ ያልሆነ ሌላ ማዕድንን ይጨምራል፤
4. “አላቂ ዕቃዎች” ማለት ለማዕድን ሥራ የሚያስፈልጉና በማዕድን ሥራው ወቅት በጥቅም ላይ ውለው የሚተኩ ኬሚካሎችን ጨምሮ ሚኒስቴሩ በመመሪያ አላቂ ዕቃዎች ብሎ የሚሰይማቸው ናቸው፤
5. “ቀን” ማለት በቀን መቁጠሪያ ላይ የሰፈረ ማንኛውም ቀን ሲሆን፣ በዚህ አዋጅ፣ በደንብ ወይም በመመሪያ የተመለከተ ተግባርን ለማከናወን የተወሰኑ ቀናት ተቆርጠው ከሆነ ቀናቱ የሚወስኑት የመጀመሪያውን ቀን በመቀነስ እና እሁድና ቅዳሜ ወይም በሕዝብ በአላት ላይ እስካልዋለ ድረስ የመጨረሻውን ቀን በመጨመር ይሆናል፤
6. “መመሪያ” ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጣ መመሪያ ነው፤
7. “የአገር ውስጥ ባለሀብት” ማለት የኢንቨስትመንት ካፒታል በሥራ ላይ ያዋለ ኢትዮጵያዊ ወይም መደበኛ መኖሪያው ኢትዮጵያ ውስጥ የሆነ የውጭ አገር ዜጋ ሲሆን፣ መንግስትና የመንግስትንና የልማት ድርጅትን እንዲሁም እንደ አገር ውስጥ ባለሀብት መቆጠር የፈለገ በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆነ የውጭ አገር ዜጋን ይጨምራል፤
8. “ምርመራ” ማለት ሆን ብሎ ማዕድን ለማግኘት በማናቸውም የገፀምድር ወይም ከርሰ ምድር፣ በውሃ አካላት እንዲሁም ቀደም ሲል ተቆፍሮ በወጣና በቀረ የተቆለለ ማዕድን አዘል አፈር ወይም አለት ውስጥ በአካባቢ ላይ ለውጥ በሚያስከትል መልኩ በፎቶግራፍና ምስሎች፣ በጂኦሎጂ፣ በጂኦፊዚክስ በጂኦኬሚስትሪ፣ በተለያዩ የጉድጓድ ቁፋሮና በመሳሰሉት ዘዴዎች አማካኝነት የማዕድኑን መኖር፣ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታውን እና መጠኑን ለማወቅና እና ለማጣራት የሚደረግ ሥራ ነው፤

9. “የውጭ ባለሀብት” ማለት የውጭ ካፒታል ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት ኢንቨስት ያደረገ የውጭ ዜጋ ወይም በውጭ ዜጎች ባለቤትነት የተያዘ ድርጅት ሲሆን እንደ ውጭ ባለሀብት መቆጠር የፈለገ መደበኛ ነዋሪነቱ በውጭ አገር የሆነ ኢትዮጵያዊን ይጨምራል፤
10. “መንግሥት” ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ማለት ሲሆን እንደአግባቡ ክልሎችንም ይጨምራል፤
11. “የኢንዱስትሪ ማዕድን” ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለኢንዱስትሪ በግብዓትነት የሚያገለግል እንደ ካኦሊን፣ ቤንቶናይት፣ ኳርትዝ፣ የድንጋይ ከሰል፣ ላይምስቶን፣ ጂፕሰም፣ ፑሚስ፣ የሸክላ አፈርና ግራፋይት የመሰለ ማንኛውም ማዕድን ሲሆን፣ ብረት ነክና የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናትን ሳይጨምር ሚኒስቴሩ በመመሪያ ብሎ የሚሰይመውን ማንኛውንም ሌላ ማዕድን ይጨምራል፤
12. “ከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ” ማለት የከበሩ ወይም በከፊል የከበሩ ድንጋዮችን የማምረት ሥራን በሚመለከት ካልሆነ በቀር ከማዕድኑ ሥፍራ በዓመት የሚነሳው ማዕድን አዘል አፈርና ድንጋይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (35) ከተመለከተው መጠን በላይ የሆነ ማዕድናትን የማምረት ሥራ ነው፤
13. “ፈቃድ” ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጥ የማዕድን ቅኝት፣ ምርመራ፣ ይዞ መቆየት ወይም ማምረት ፈቃድ ነው፤
14. “የፈቃድ ክልል” ማለት ማናቸውም ፈቃድ የተሰጠበት ሥፍራ ነው፤
15. “ባለፈቃድ” ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ የቅኝት ፈቃድ፣ የምርመራ ፈቃድ፣ ይዞ የመቆየት ፈቃድ ወይም የማምረት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም ተተኪው ነው፤
16. “ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን” ማለት እንደ አግባቡ የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር[3] ወይም ማዕድን ዘርፍን በሚመለከት ኃላፊነት የተሰጠው የክልል አካል ነው፤
17. “ብረት ነክ ማዕድን” ማለት እንደ ብረት፣ መዳብ፣ ነሐስ፣ እርሳስ፣ ክሮማይት፣ ኒኬል፣ ታንታለም ማንጋኒስ የመሰለ ማዕድን ሲሆን፣ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናትን ሳይጨምር ሚኒስቴሩ በመመሪያ ብረት ነክ ማዕድን ብሎ የሚሰይመውን ማንኛውንም ሌላ ማዕድን ይጨምራል፤

[3] በ25/08 (2011) አ. 1097 አንቀጽ 9(12) የማእድናን ነዳጅ ሚንስቴር ሆኗል፡፡

18.“ማዕድን ማምረት” ማለት በማናቸውም አይነት ዘዴ በሚከናወን ሥራ ማዕድንን በገጸ ምድር፣ በከርሰ ምድር ወይም በውሃ አካላት ከሚገኝ የማዕድን ክምችት ወይም ተራፊ የማዕድን ክምችት ውስጥ ለማውጣት የሚደረግ ሥራ ሲሆን ከዚህ ጋር የተያያዘ ማከማቸትን፣ ማዘጋጀትን፣ ፕሮሰስ ማድረግን (ማቅለጥንና ማጣራትን ሳይጨምር)፣ ማጓጓዝንና መሸጥን ይጨምራል፤

19. “ማዕድን” ማለት ማናቸውም ዋጋ ያለው በጠጣር፣ በፈሳሽ ወይም በጋዝ መልክ በተፈጥሮ በመሬት ላይ ወይም ውስጥ፣ በውሃ ውስጥ ወይም ስር የሚገኝ በጂኦሎጂ ሂደት ወይም ሁኔታዎች የተፈጠረ ሲሆን ቀደም ሲል ተቆፍሮ በወጣና ተራፊ የተቆለለ ማዕድን አዘል አፈር ወይም በቀሪ የማዕድን ክምችት ውስጥ የሚገኝ ማዕድንን ይጨምራል፤ ሆኖም የሚከተሉትን አይጨምርም፡-

ሀ) ለመታጠቢያ፣ ለመዝናኛ፣ ለሕክምና ከሚውል የጂኦተርማል ውሃ እና ከውስጡ ማዕድን ለማውጣት ከሚውል እንደ ብራይን ውሃ በስተቀር ሌላውን ውሃ፤”

ለ) አግባብ ባለው የነዳጅ ሕግ ትርጓሜ የሚካተቱ የተፈጥሮ ዘይትና ጋዝን፤

ሐ) ለም አፈርን (ላይኛው አፈር) እና ነዳጅ አዘል አለትን (ነዳጅ አዘል ሼል)፤

20.“የማምረት ፈቃድ” ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጥ የከፍተኛ ደረጃ፣ የአነስተኛ ደረጃ፣ ልዩ የአነስተኛ ደረጃ ወይም የባህላዊ ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ነው፤”

21.“የማዕድን ሥራ” ማለት ከማዕድን ቅኝት፣ ምርመራ፣ ይዞ መቆየት ወይም ማምረት ጋር የተያያዘ ተግባር ነው፤

22. “የማዕድን መብት” ማለት ከቅኝት፣ ከምርመራ፣ ይዞ ከመቆየትና ከማምረት ፈቃድ ጋር የተያያዘ መብት ነው፤

23. “ሚኒስቴር” ማለት የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር[4] ወይም ተተኪው ነው፤

24. “የከበረ ማዕድን” ማለት እንደ ፕላቲነየም፣ ወርቅና ብር የመሰለ የከበረ ብረት ነክ ማዕድን ወይም እንደ አልማዝ፣ ሩቢ፣ ኢመራልድና ሳፋየር ያለ የከበረ ድንጋይ ሲሆን፣ ሚኒስቴሩ በመመሪያ የከበረ ማዕድን ብሎ የሚሰይመውን ማናቸውንም ሌላ ማዕድን ይጨምራል፤

25. “ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

[4] በ25/08 (2011) አ. 1097 አንቀጽ 9(12) የማእድናን ነዳጅ ሚንስቴር ሆኗል፡፡

26. “ፕሮሰስ ማድረግ” ማለት ማዕድንን በተለያየ ዘዴ ማውጣት፣ መቆፈር፣ ማጥለል፣ ማድረቅ፣ በዓይነት መመደብ፣ መፍጨት፣ ማበጠር፤ ማጠብ፣ ማድቀቅ ወይም ወደ ጋዝ መለወጥ ነው፤

27.“ቅኝት” ማለት ማናቸውንም ማዕድን ለማግኘት የሚካሄድ አጠቃላይ የሆነ የማዕድን ፍለጋ ሥራ ነው፤

28.“መዝገብ” ማለት በዚህ አዋጅ የተመለከተው የማዕድን መብቶች የተመዘገቡበት መዝገብ ወይም የኤሌክትሮኒክስ የማዕድን ካዳስተር ነው፤

29.“ደንብ”ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጣ ደንብ ነው፤

30. “ተራፊ ክምችት” ማለት የማዕድን ፈቃድ ሲቋረጥ፣ ሲሰረዝ ወይም ዘመኑ ሲያበቃ የነበረ ማናቸውም ተራፊ ማዕድን አዘል ቁልል ነው፤

31. “ተራፊ ማዕድን አዘል ቁልል” ማለት ከማዕድን ሥራ የተገኘ ወይም በማዕድን ሥራዉ ምክንያት የወጣና በማዕድን ባለፈቃዱ እንደገና ጥቅም ላይ ለማዋል ታስቦ ተቆልሎ፣ ተቀምጦ ወይም ተጠራቅሞ የነበረ ወይም የተተወ ማናቸዉም ፍራሽ፣ ውዳቂ፡ አሰር፡ ዝቃጭ፣ ብጣሪ፣ ቆሻሻ አዘል ድፍርስ፣ ውዳቂ ድንጋይ፣ ከብረት ማቅለጫ የሚወጣ አሸዋ፣ የማበልጸጊያ ፋብሪካ ቆሻሻ፣ አመድ ወይም ማናቸዉም ተረፈ ምርት ነዉ፤

32. “ሮያሊቲ” ማለት የማዕድን ሀብት ባለቤት ለሆነው መንግሥትና ሕዝብ ባለፈቃድ ከማዕድን ማመረቻ ቦታ ላይ ከሚያመርተው የማዕድን /ናት/ ምርት በየጊዜው በመቶኛ እየተሰላ የማምረቻና ሪስክ ወጪን ሳይጨምር የሚከፍለዉ ክፍያ ነው፤

33. “የሽያጭ ዋጋ” ማለት ከኢትዮጵያ ወደዉጭ ሀገር በሚላክበት ኬላ (ፎብ) ወይም ለሀገር ዉስጥ ፍጆታ ሲሆን አቅራቦቱ የተፈፀመበት ቦታ የማዕድኑ የገበያ ዋጋ የሚከተለው ተቀንሶሰት ነው፦

   ሀ) ማዕድኑን ከተመረተበት ቦታ ወደ ዉጭ ሀገር እስከሚላክበት ኬላ ወይም ማስረከቢያ ቦታ ድረስ የኢንሹራንስና ከማጓጓዝ ጋር የተያያዙ ልዩ ልዩ ወጪዎች ተጨምረው የወጣው የትራንስፖርት ዋጋ፤ እና

   ለ) የማበልጸጊያ ወጪዎቹ እዚሁ ኢትዮጵያ ውስጥ በማዕድኑ ሥፍራ በመደበኛነት ከሚደረጉ ሂደቶች ጋር የተያያዙ ካልሆነ በቀር ማዕድኑን ለማቅለጥና ለማጣራት የወጡ ወይም ሌሎች የማበልጸጊያ ወጪዎች፤

34.“በከፊል የከበረ ማዕድን” ማለት ለማስዋቢያነት የሚውል ወጥ ወይም በተፈጥሮአዊ አንድነት የተጣመረ እንደ ኦፓል፣ ሮዶላይት፣ ኦሊቪን፣ ጃዲይትና ላዙራይት የመሰለ ማዕድን ሲሆን፣ የከበሩ ማዕድናትን ሳይጨምር ሚኒስቴሩ በመመሪያ በከፊል የከበረ ማዕድን ብሎ የሚሰይመውን ማንኛውንም ሌላ ማዕድን ይጨምራል፤

35. “አነስተኛ የማዕድን ማምረት ሥራ” ማለት ከማዕድኑ ሥፍራ በአመት የሚመረተው የማዕድን አዘል አፈርና ድንጋይ መጠኑ ከሚከተለዉ የማይበልጥ ማዕድን የማምረት ሥራ ነው፡-

ሀ) ወርቅ፣ ፕላቲኒየም፤ ብርና ሌሎች የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናትን በሚመለከት፡-

1) በደለል ላይ ለሚካሄዱ ሥራዎች 100,000 ሜትር ኩብ፤

2) በጽንሰ ማዕድን ክምችቶች ላይ የሚካሄዱ ሥራዎች 75,000 ቶን፤

ለ) እንደ ብረት፣ እርሳስ፣ መዳብና ኒኬል የመሳሰሉ ሜታል ማዕድናትን በሚመለከት፡

1) በመሬት ላይ ለሚካሄዱ ሥራዎች 150,000 ቶን፤

2) በመሬት ዉስጥ ለሚካሄዱ ሥራዎች 75,000 ቶን፤

ሐ) እንደ ካኦሊን፣ ቤንቶናይት፣ ዲያቶማይት፣ ዶሎማይት ኳርትዝና የድንጋይ ከሰል የመሳሰሉ የኢንዱስትሪ ማዕድናትን በሚመለከት 120,000 ቶን፤

መ) የኮንስትራክሽን ማዕድናትን በሚመለከት፡-

1) አሸዋ፣ ጠጠር፣ ፑሚስ፣ ኢግኒምብራይት፣ የሸክላ አፈርና የመሳሰሉትን በሚመለከት 80,000 ሜትር ኩብ፤

2) እብነበረድ፣ ግራናይትና የመሳሰሉትን የዳይሜንሽን ድንጋዮች በሚመለከት 10,000 ሜትር ኩብ፤

ሠ) የጂኦተርማል ክምችትን በሚመለከት፡-

1) ለመታጠቢያ፣ ለመዝናኛና ለሕክምና አገልግሎት የሚዉሉትን በሚመለከት 2,000,000 ሜትር ኩብ፤

2) ለኢንዱስትሪና ለሌሎች አገልግሎቶች የሚዉሉትን በሚመለከት 25 ሜጋዋት ወይም ተመጣጣኝ የሆነ ኃይል ሊሰጥ የሚችል የጂኦተርማል እንፋሎት፤

ረ) ከድንጋይ ወይም ከብራይን የሚመረቱ የጨው ዓይነቶችን በሚመለከት 14,000 ቶን፤

36. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 47(1) የተመለከተዉ ማንኛውም ክልል ሲሆን፣ የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችንም ይጨምራል፡
37. "ስትራቴጂክ ማዕድን" ማለት ሚኒስቴሩ በመመሪያ ስትራቴጂክ ማዕድን ብሎ የሚሰይመዉ ማንኛውም ማዕድን ነው፤
38. "ማስተላለፍ" ማለት መሸጥ፣ በእዳ ማስያዝ፣ ማውረስ፣ መዳረግ ወይም በሌላ መንገድ ማስተላለፍ ነው፤
39. "የሥራ ፕሮግራም" ማለት እንደነገሩ አግባብነት ለምርመራ ወይም ለማምረት ሥራ የሚቀርብ ዝርዝር ስራውን፣ ሥራው የሚከናወንበትን ጊዜ፣ ወጪውን፣ መዋቅሩንና የሰው ኃይል ስብጥሩን የሚያመላክት ዕቅድ ነው፤
40. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸዉ አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።
41. "ፈቃድ ተፈጻሚ የሆነበት ቀን" ማለት የማዕድን ማምረት ፈቃድ ጠያቂው እና ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የማዕድን ማምረት ስምምነት የተፈራረሙበት ቀን ሲሆን ለሌሎች የማዕድን ሥራዎች ፈቃድ መሰጠቱን የሚገልጽ ደብዳቤ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የተፈረመበት ቀን ነው፤
42. "የማዕድን ኢንዱስትሪ ግልጽነት ኢኒሼቲቭ" ማለት መንግሥት ከማዕድን ማምረት ባለፈቃዶች የሰበሰበውን ገቢ እና የማዕድን አምራች ባለፈቃድ ለመንግስት የከፈለውን ማንኛውንም ክፍያዎች ለሕብረተሰቡ ማሳወቅ እንዲቻል በመንግስት፣ በማዕድን አምራች ኩባንያዎች እና በሲቪል ማህበረሰብ የጋራ ጥምረት የተቋቋመ አካል ነው፤
43. "የማዕድን ማምረት ቅድመ ዝግጅት ጊዜ" ማለት ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣንና ባለፈቃዱ የማዕድን ማምረት ውል ከተፈራረሙበት ቀን ጀምሮ የምርት ሥራው እስከሚጀመርበት ጊዜ ድረስ እንደ ማዕድኑ አይነትና ፀባይ ማዕድኑን ለማምረት አስፈላጊ የሆኑ ወደ ማዕድን ክምችቱ ለመድረስ፣ ማዕድን አዘሉን አካለ ለማወጣት፣ ለመፍጨት፣ ለማበልጸግ፣ ማዕድኑን ለማምረት እና ለማዕድን ማምረት ሥራው አገልግሎት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ግንባታዎች የሚከናወኑበት የዝግጅት ጊዜ ነው፤
44. "ልዩ የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ስራ" ማለት የባህላዊ ማዕድን ማምረት ስራ ፈቃድ ተሰጥቷቸው የጌጣጌጥ ማዕድን ወይም ከደለል ክምችት የሚገኝ የወርቅ፣ የብር፣ የፕላቲኒየም ወይም የታንታለም ማዕድን እያመረቱ ያሉና የገንዘብ አቅማቸው

ዘመናዊ የማምረቻ መሳሪያዎችን በመጠቀም ማምረት በሚያስችላቸው ግለሰቦች ወይም የአነስተኛና የጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (35) ፊደል ተራ (ሀ) መሠረት የሚከናወን የማዕድን ማምረት ሥራ ነው፡፡"

3. **<u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ግዛት ውስጥ በሚካሄዱ የማዕድን ሥራዎችና ተዛማጅ ተግባራት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>መሰረታዊ መርሆዎችና ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

4. **<u>ዓላማ</u>**

የዚህ አዋጅ አላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. መንግሥት የሀገሪቱን የማዕድን ሃብት ለመጠበቅ የተጣለበትን ኃላፊነት ተግባራዊ ማድረግ፤
2. የሀገሪቱን ኢኮኖሚያዊና ማኀበራዊ ልማት ማስፋፋት፤
3. የኢትዮጵያዊያንን የሥራ እድል ማስፋፋትና ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማሳደግ፤
4. በማዕድን ምርመራና ማምረት ሥራ የተሰማሩትን ባለሀብቶች የይዞታ ዋስትና ማረጋገጥ፤ እና
5. የሀገሪቱ የማዕድን ሀብት ሥርዓትና ዘላቂነት ባለው ሁኔታ መልማቱን ማረጋገጥ፡፡

5. **<u>ስለማዕድን ሃብት ጠባቂነት</u>**

1. በኢትዮጵያ ወሰን ውስጥ በገጸ ምድርም ሆነ በከርሰ ምድር በተፈጥሮአዊ ሁኔታዉ የሚገኝ የማዕድን ሀብት የመንግሥትና የሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሀብት ነው፡፡
2. መንግሥት የማዕድን ሀብትን በሕዝብ ስም በይዞታዉ ሥር በማድረግ ለሁሉም ኢትዮጵያዊያን የጋራ ጥቅምና ዕድገት መዋሉን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡
3. መንግሥት በፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን አማካኝነት የማዕድን ሀብትን ይቆጣጠራል፤ ያስተዳድራል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይከለክላል፤ ፈቃዶችን ያስተዳድራል።

6. **<u>መሬትን ከልሎ ስለመጠበቅ</u>**

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማናቸዉም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ መሬት ለማዕድን ሥራዎች ክፍት ይሆናል፡፡

2. ሚኒስቴሩ ለሀገሪቱ ጥቅም አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን የሕዝብ ማስታወቂያ በማውጣት ማናቸውም መሬት የማዕድን ሥራ የማይካሄድበት ነው ብሎ መከልከል ይችላል፡፡
3. ማናቸውም ሰው ቀጥሎ በተዘረዘሩት ሥፍራዎች ላይ የማዕድን ምርመራ ፈቃድ፣ ይዞ የመቆየት ፈቃድ ወይም የማምረት ፈቃድ አይሰጠውም፡-
   ሀ) ለመቃብርና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች በተከለሉ ሥፍራዎች፤
   ለ) የቅድመ ታሪክ ቅሪቶች ባሉባቸው ወይም ብሔራዊ መታሰቢያዎች በቆሙባቸው ሥፍራዎች፤
   ሐ) ለመሠረተ ልማት አውታሮች በተከለሉ ቦታዎች፤
   መ) ለተፈጥሮ አከባቢ ጥበቃ ወይም ለብሔራዊ ፓርክ በተከለሉ ሥፍራዎች፤
   ሠ) ለጉዳዩ ስልጣን የተሰጠው አካል ካልፈቀደ በቀር ከመንደሮች፣ ከከተማዎች ወይም ከውሃ ማጠራቀሚያዎች ወይም ግድቦች በ500 ሜትር ክልል ውስጥ፤ ወይም
   ረ) በሌላ ሕግ በተከለከሉ ቦታዎች፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው የሕዝብ ማስታወቂያ በሥራ ላይ በዋለበት ቀን የማዕድን መብት በጸናበት መሬት ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።
5. መንግሥት ለብሔራዊ ጥቅም ሲባል ተገቢው የማካካሻ እርምጃ ተወስዶ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ወይም (3) መሠረት የተከለለ ማንኛውም ሥፍራ ለማዕድን ሥራ ክፍት እንዲሆን ሊፈቅድ ይችላል፡፡

7. <u>የፈቃድ አስፈላጊነት</u>

1. ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሰረት ተገቢውን ፈቃድ ሳያገኝ የማዕድን ሥራዎች ማካሄድ አይችልም።
2. ማንኛውም ሰው የፀና ፈቃድ ሳይኖረው ማንኛውንም ማዕድን በተፈጥሮአዊ ሁኔታው መያዝ፣ ማዘዋወር ወይም መሸጥ አይችልም።
3. ሕጋዊ የመሬት ባለይዞታ የሆነ ሰው ሥፍራው በዚህ አዋጅ መሠረት የተያዘ ወይም የተከለከለ ካልሆነ በስተቀር የኮንስትራክሽን ማዕድናትን በይዞታው ሥር ከሚገኝ ሥፍራ ያለክፍያና ፈቃድ ሳያስፈልገው ለንግድ ላልሆነ ዓላማ አምርቶ መጠቀም ይችላል፡፡ ሆኖም የአዋሳኝ ባለይዞታዎችን መሬት ወይም ንብረት አጠቃቀም ማወክ ወይም በእነዚሁ ላይ ጉዳት ማድረስ የለበትም፡፡

4. ማንኛውም ሰው ለንግድ ላልሆነ አላማ መንገዶችን፣ ግድቦችን፣ የአውሮፕላን ማረፊያዎችን፣ ትምህርት ቤቶችን፣ ሆስፒታሎችንና ሌሎች የሕዝብ አገልግሎት ሥራዎችን ለመሥራትና ለመጠገን ፈቃድ ሰጪውን ባለሥልጣን አስቀድሞ በማስፈቀድ የኮንስትራክሽን ማዕድናትን ያለክፍያ ማምረትና መጠቀም ይችላል፡፡
5. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ፈቃድ ባይኖረውም የአንድን ባለፈቃድ ወይም የሌላ ሰው መብት ሳይነካ የማዕድን ቅኝት ማካሄድ ይችላል፡፡

8. **<u>በመንግስት ስለሚካሄዱ የማዕድን ሥራዎች</u>**

መንግስት ለጠቅላላ ኢኮኖሚ ዕድገት ወሳኝ ሚና የሚኖራቸውን የማዕድን ሥራዎች በራሱ ወይም ከግል ባለሀብቶች ጋር በቅንጅት ሊያካሂድ ይችላል፡፡

9. **<u>የፈቃዱ ዓይነቶች</u>**[5]

በዚህ አዋጅ መሰረት የሚከተሉት ፈቃዶች ሊሰጡ ይችላሉ፡-

1. የቅኝት ፈቃድ፤
2. የምርመራ ፈቃድ፤
3. ይዞ የመቆየት ፈቃድ፤
4. ባህላዊ የማዕድን የማምረት ሥራ ፈቃድ፤
5. ልዩ የአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ፤
6. የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ፤ እና
7. የከፍተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ፡፡

10. **<u>ስለምስክር ወረቀት</u>**

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት የምስክር ወረቀቶች ሲሰጡ ይችላሉ፡-

1. የግኝት ምስክር ወረቀት፤
2. የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት፡፡

11. **<u>ፈቃድ ለማግኘት ብቁ ስለመሆን</u>**

1. ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ፣ በደንብና በመመሪያ መሠረት ፈቃድ ለማግኘት የሚያስፈልጉ ሁኔታዎችን ካሟላ፡ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ንግድ ማካሄድ የሚችል ከሆነ፣ እንዲሁም የማዕድን ሥራውን ለማከናወን የሚያስፈልገው የገንዘብ

[5] የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5፣ በ20/27 (2006) አ. 816 አንቀጽ 2 (5) መሰረት አዲስ የገባ ሲሆን ነባሮቹ ንዑስ አንቀጾች 5 እና 6 እንደቅደም ተከተላቸው ንዑስ አንቀጽ 6 እና 7 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

አቅም ያለው ወይም ማግኘት የሚችልና የቴክኒክ ችሎታ ያለው ከሆነ ፈቃድ ማግኘት ይችላል።

2. ማንኛውም ሰው በባሕላዊ ማዕድን ማምረት ሥራ ላይ ለመሰማራት የገንዘብ፣ የቴክኒክና የሙያ ብቃት አያስፈልገውም።
3. የሚከተሉት ፈቃድ ማግኘት አይችሉም፡-
   ሀ) ከኪሳራ ያልወጣ ወይም ከአበዳሪዎቹ ጋር በገባዉ ሥምምነት መሥረት እዳዉን ከሥር ከሥሩ በመክፈል ላይ ያለ ሰዉ፤
   ለ) የማፍረሱ ሂደት የንግድ ማኅበሩን እንደገና ለማቋቋም ወይም ከሌላ ኩባንያ ጋር ለማዋሃድ እስካልሆነ ድረስ በመፍረስ ላይ ያለ የንግድ ማኅበር፤
   ሐ) ልዩ የአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራ ወይም የባህላዊ ማዕድን ማምረት ሥራ ሲሆን ኢትዮጵያዊ ዜግነት የሌለው ሰው ወይም አግባብ ባለው የአነስተኛ እና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ ህግ መሠረት ያልተመዘገቡ የሰዎች ስብስብ፡፡"[6]
   መ) ለኢንደስተሪ ግብዓትነት የሚውሉ ወይም ከማጋጌጫ ድንጋዮች ውጭ ያሉ እንደ አሸዋ፣ ጠጠር፣ ገረጋንቲ እና የመሳሰሉት የኮንስተራክሽን ማዕድናት ሲሆን ኢትዮጲያዊ ዜግነት የሌለው ሰው፡፡[7]
   ሠ) ቢያንስ 25 በመቶ የሚሆን የአኪሲዮን ድርሻ ከያዘ የሀገር ውስጥ ባለሀብት ጋር በጋራ በመሆን የከፍተኛ ደረጃ የደለል መዕድን ማምረት ስራ ላይ ለመሰማራት ከሚፈልግ የውጭ ባለሀብት በስተቀር በሌላ በማንኛውም የደለል መዕድን ስራ ለመሰማራት የሚፈልግ የውጭ ባለሀብት፡፡
4. በማጭበርበር ወይም የተሳሳተ መረጃ በማቅረብ ፈቃዱ የተሰረዘበት ባለፈቃድ ፈቃዱ ከተሰረዘበት ቀን አንስቶ ለአምስት አመታት ሌላ ፈቃድ ማግኘት አይችልም።

12. <u>ስለፈቃድ ማመልከቻ</u>

1. አግባብነት ባላቸው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ፈቃድ ለማግኘት፣ ለማሳደስ ወይም ለማስተላለፍ ለፈቃድ ሰጪዉ ባለሥልጣን የሚቀርብ ማመልከቻ በተወሰነው ፎርም መሰረት የተዘጋጀ ሆኖ፡-

[6] በ20/27(2006) አ.816 አንቀጽ 2(6) መሰረት ተሻሻለ፡፡

[7] በ26/63(2012) አ.1213 አንቀፅ 2(1) መሰረት ተሻሻለ፡፡

ሀ) በዚህ አዋጅ፣ በደንብና በመመሪያ የተገለጹትን ሰነዶች የያዘና ክፍያ የተፈጸመበት፣ እና

ለ) አመልካቹ የንግድ ማኅበር የሆነ እንደ ሆነ አግባብነት ባለው ሕግ መሰረት የተመዘገበ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሕጋዊ ሰነዶች የያዘ፣

መሆን አለበት፡፡

2. ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን የቀረበው ማመልከቻ በቂ መሆኑን ሲያምንበት ወዲያውኑ መዝግቦ ለአመልካቹ ደረሰኝ ይሰጣል፡፡

13.<u>ማመልከቻዎች ስለሚስተናገዱበት ቅደም ተከተል</u>

1. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የማዕድኑን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ወይም ሌሎች አግባብ ያላቸውን የኢንቨስትመንት ዓላማዎች መሠረት በማድረግ በሌላ አኳኋን ካልወሰነ በቀር፡-

ሀ) ለከፍተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ፈቃድ የቀረበ ማመልከቻ ለአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ፈቃድና ለባህላዊ የማዕድን ማምረት ፈቃድ በቀረቡ ማመልከቻዎች እንዲሁም ለአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ፈቃድ የቀረበ ማመልከቻ ለባህላዊ የማዕድን ማምረት ፈቃድ በቀረበ ማመልከቻ ላይ ቀዳሚነት ይኖራቸዋል፤

ለ) ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ለአንድ ዓይነት ማዕድን በአንድ ቦታ ላይ አንድ አይነት ደረጃ ላላቸው ፈቃዶች ከአንድ በላይ ማመልከቻዎች ከቀረቡለት ማመልከቻዎቹ በቀረቡለት ቅደም ተከተል መሰረት ማስተናገድ አለበት፤

ሐ) ሁለት ወይም ከዚያ በላይ አመልካቾች ለአንድ ዓይነት ማዕድን በአንድ ቦታ ላይ በአንድ ጊዜ አንድ አይነት ደረጃ ላላቸው ፈቃዶች ማመልከቻዎቻቸውን አቅረበው ከሆነ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ቅድሚያውን ለመወሰን ማመልከቻዎቹን የሚገመግም የቴክኒክ ቡድን ያቋቁማል፤ የቴክኒክ ሥራ ቡድኑ አመልካቾቹ ያቀረቡትን የቴክኒክ ሥራ እቅድ፣ ለሥራው ሊያወጡ ያሰቡትን የገንዘብ መጠን እና የአመልካቹን ብቃት ገምግሞ በዉጤቱ መሠረት ቀዳሚውን ይወሰናል፡፡

2. ሁለት ወይም ከዚያ በላይ አመልካቾች በአንድ ቦታ ላይ የፈቃድ ማመልከቻዎቻቸውን በአንድ ጊዜ ለሚኒስቴሩ እና ለክልል ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን አቅርበዉ ከሆነ ሚኒስቴሩና የሚመለከተዉ የክልል ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን

ማመልከቻዎቹን የሚገመግሞ የጋራ የቴክኒክ ቡድን ያቋቁማሉ፤ የቴክኒክ ቡድኑ አመልካቾቹ ያቀረቡትን የቴክኒክ ሥራ እቅድ፤ ለሥራዉ ሊያወጡ ያሰቡትን የገንዘብ መጠንና የአመልካቾቹን ብቃት ገምግሞ በዉጤቱ መሰረት ቀዳሚዉን ይወስናል፡፡

3. ሴት አመልካች ካለችና በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሠረት የተካሄደዉ የግምገማ ዉጤት እኩል ከሆነ ቅድሚያ ይኖራታል፡፡

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)፣ (2) እና (3) ድንጋጌዎች ቢኖሩም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማመልከቻ የቀረበበትን ሥፍራ ጨረታ ሊያወጣበት ይችላል፡፡

14. <u>ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ሰዎች ስለማሳወቅ</u>

1. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ መሠረት የቀረበለትን ማመልከቻ ከመዘገበ በኋላ ጥያቄ የቀረበበትን ቦታ የጂኦግራፊ ኮኦርድኔት በመጥቀስ ሰፊ ተደራሽነት ባላቸው የመገናኛ ብዙሃን አማካይነት ሦስተኛ ወገኖች እንዲያዉቁት ያደርጋል፡፡

2. ፈቃድ እንዳይሰጥ የሚቃወም ሰዉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት እንዲታወቅ በተደረገ በሰባት ቀናት ዉስጥ የቀረበ እንደሆነ ፈቃድ ሰጪዉ ባለሥልጣን ተቃዉሞዉን ለመፍታት እንዲችል ጉዳዩን በሚመለከታቸዉ ወገኖች መካከል ድርድር እንዲጀመር ያደርጋል፡፡

3. ጉዳዩ የሚመለከታቸዉ ወገኖች የቀረበዉን ተቃዉሞ በድርድር መፍታት ካልቻሉ ፈቃድ ሰጪዉ ባለሥልጣን የሁለቱንም ወገኖች ክርክር ካዳመጠ በኃላ የቀረበውን ተቃውሞ በመቀበል ወይም ባለመቀበል በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ ዉሳኔ ይሰጣል፡፡

15. <u>ስለፈቃዶቹና የመሬት ኪራይ መዝገብ</u>

1. ፈቃድ ሰጪዉ ባለሥልጣን የማዕድን ፈቃዶችና የመሬት ኪራይ መዝገብ ያቋቁማል፣ ይይዛል፡፡

2. መዝገቡ ፈቃድ እንዲሰጣቸው ያመለከቱና የተመዘገቡትን በሙሉ እና ፈቃድ ተሰጥቷቸው ወይም ተከልክለው ከሆነ ይህንኑ ዝርዝር እንዲሁም አግባብ ባላቸው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ፣ በደንብና በመመሪያ የተመለከቱ ዝርዝሮችን ይይዛል፡፡

3. ማንኛውም ፈቃድ፣ የመሬት ኪራይ ውል እና ማንኛውም እንዲህ ያለ መብት የተላለፈበት፣ የተዳረገበት፣ የተተወበት፣ የታገደበት፣ የተሰረዘበት፣ በዉርስ የተላለፈበት ወይም በሌላ ሁኔታ የተከናወነበት ሰነድ መመዝገብ አለበት፡፡ ከእንዲህ ያለ መብት

ጋር የተያያዘ ማንኛዉም ሰነድ በተዘጋጀ በ90 ቀናት ዉስጥ ቀርቦ ካልተመዘገበ በህግ ፊት ዋጋ አይኖረውም፡፡

4. መዝገብ ለመመልከት እንዲቻል ለሕዝብ ክፍት ይሆናል፡፡
5. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ዘንድ ለምዝገባ የሚቀርብ ማንኛውም ሰነድ ቅጂ የሚመለከተዉን ሥፍራ ለመለየት እንዲቻል ተያይዞ ከሚቀርብ ካርታና ሌላ ፕላን ጋር አግባብ ባለው ሕግ መሠረት መንግሥት በሚይዘው የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች መዝገብ ላይ መመዝገብ አለበት፡፡

## ክፍል ስድስት

## ስለ ፈቃድ

### 16.የቅኝት ፈቃድ ስለመስጠት

ለቅኝት ፈቃድ የቀረበው የሥራ ፕሮግራም በመሬት ገጽታ ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል የጂኦሎጂ ሥራ የሌለው ከሆነ፣ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የብቻ የሆነ መብት የማያስገኝ ፈቃድ መስጠት አለበት፡፡

### 17.የቅኝት ፈቃድ ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ

1. የቅኝት ፈቃድ በፈቃዱ ላይ ለተገለጸው ጊዜ ፀንቶ ይቆያል፤ ሆኖም ይህ ጊዜ ከአስራ ስምንት ወራት በላይ ሲሆን አይችልም።
2. የቅኝት ፈቃድ ሊታደስ አይችልም፡፡

### 18.የምርመራ ፍቃድ ስለመስጠት

1. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከተሟሉ የብቻ መብት የሚያስገኝ የማዕድን ምርመራ ፈቃድ ይሰጣል፡-
   ሀ) አመልካቹ የታሰበውን የማዕድን ምርመራ ሥራ በቀረበው የሥራ ፕሮግራም መሰረት ለማከናወን የሚያስችል የገንዘብ አቅምና አስፈላጊው የቴክኒክ ችሎታ ያለው ወይም ለማግኘት የሚችል መሆኑን ካረጋገጠ፤
   ለ) የተገመተው የማዕድን ምርመራ ሥራ ወጪ በተወሰነ ዝቅተኛ የምርመራ ወጪ እና በምርመራ ሥራ ፕሮግራሙ መሰረት ከሆነ፤
   ሐ) የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማው ተቀባይነት ካገኘ፤ እና
   መ) አመልካቹ የቅኝት ፈቃድ የነበረው ከሆነ የዚህኑ ፈቃድ ግዴታዎች ካልጣሰ፡፡
2. የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የምርመራ ፈቃድ ለአመልካቹ የማይሰጠው ከሆነ ይኸንኑ ውሳኔ በጽሑፍ ከነምክንያቱ ለአመልካቹ ያሳውቀዋል።

19.<u>የማዕድን ምርመራ ፈቃድ ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜና እድሳት</u>

1. የማዕድን ምርመራ ፈቃድ በፈቃዱ ላይ ለተገለጸው ጊዜ ፀንቶ ይቆያል፤ ሆኖም ይህ ጊዜ ከሦስት ዓመት በላይ ሊሆን አይችልም።
2. የምርመራው ፈቃድ እያንዳንዱ ከአንድ ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ ለሁለት ጊዜ ሊታደስ ይችላል። ባለፈቃዱ ቀደም ሲል ከቀረበው የስራ ፕሮግራም ተጨማሪ የምርመራ ተግባር ማከናወን እንደሚያስፈልግ ካረጋገጠ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በእያንዳንዱ ዓመት የሚታደስ ተጨማሪ ዕድሳት ሊፈቅድ ይችላል። ሆኖም ይህ ጊዜ ከአምስት ዓመት በላይ ሊሆን አይችልም።
3. ባለፈቃዱ በፈቃዱ የተመለከቱትን ግዴታዎቹን አሟልቶ ከፈፀመ፣ ለዕድሳት የሚጠየቁ ተፈላጊ ሁኔታዎችን ካሟላ እና የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በመተላለፍ ፈቃዱን ለማገድ ወይም ለመሰረዝ የሚያበቃ ጥፋት ካልፈጸመ በስተቀር ፈቃዱን የማሳደስ መብት ይኖረዋል።

20.<u>ስለማዕድን ምርመራ ባለፈቃድ መብትና ግዴታዎች</u>

1. አግባብ ያላቸው የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የማዕድን ምርመራ ባለፈቃድ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-
   ሀ) ይዞ የመቆየት ፈቃድ እንዲሰጠው የማመልከትና የማግኘት መብት፤
   ለ) በማዕድኑና ከምርመራ ፈቃዱ ክልል ጋር በተያያዘ የማምረት ፈቃድ ለማግኘት የማመልከትና ፈቃድ የማግኘት መብት፤
   ሐ) በቅድሚያ ከፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የጽሑፍ ስምምነት በማግኘት ምርመራ፣ ሙከራና ትንተና ለማድረግ አስፈላጊ በሆነው መጠን ማናቸውንም የማዕድን ናሙና ለማውጣትና ለማጓጓዝ፣ ሆኖም ማዕድናቱ የመንግሥት ንብረት ሆነው ይቆያሉ፣ ያለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ፈቃድ አይሸጡም፡፡
2. አግባብ ያላቸው የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የማዕድን ምርመራ ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-
   ሀ) የማዕድን ምርመራ ፈቃዱ ተፈፃሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በ60 ቀናት ውስጥ የምርመራ ሥራውን የመጀመር፤
   ለ) የምርመራ ፈቃዱን ስምምነቶችና ግዴታዎች የማክበር፤
   ሐ) ምርመራ፣ ሙከራና ትንተና ለማድረግ ያወጣቸውና ያጓጓዛቸው ማዕድናትን ናሙና ቅጂዎች የማስቀመጥ፡፡

21.<u>የሥራ ፕሮግራም ስለመለወጥ</u>

1. የምርመራ ባለፈቃድ ተቀባይነት አግኝቶ የነበረውን የሥራ ፕሮግራም በማናቸውም ጊዜ ለመለወጥ ማመልከት ይችላል፡፡
2. ማንኛውም የሥራ ፕሮግራም ለውጥ ለማድረግ የሚቀርብ ማመልከቻ፡-
   ሀ) ተቀባይነት አግኝቶ የነበረውን የሥራ ፕሮግራም ለመተግበር ያላስቻሉትን ሁኔታዎች ማሳየት፣ እና
   ለ) የታሰበውን የሥራ ፕሮግራም ማሻሻያ መያዝ፣
   አለበት፡፡
3. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሥራ ፕሮግራም ለውጥ ለማድረግ የቀረበለትን ጥያቄ ከመረመረ በኋላ፡-
   ሀ) ተሻሽሎ የቀረበውን የሥራ ፕሮግራም ከተቀበለ ያጸድቀዋል፤ ወይም
   ለ) ለውጥ ለማድረግ የቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ካደረገው ለውሳኔው ምክንያት የሆኑትን ጉዳዮች በመዘርዘር ለአመልካቹ በጽሑፍ ያሳውቀዋል፡፡

22.<u>ከፈቃድ ክልል ላይ የተወሰነውን ስለመልቀቅ፤</u>[8]

1. የምርመራ ፈቃድ እንዲታደስለት የሚጠይቅ ባለፈቃድ በእያንዳንዱ እድሳት ወቅት በፈቃዱ ላይ ከተመለከተው የመሬት ክልል ከሩብ እጅ የማያንሰውን ስፍራ የሚለቅ መሆኑን ማመልከት አለበት፡፡
2. የሚለቀቁ ሥፍራዎች ቅርጽ፣ አቀማመጥና ሌሎች ዝርዝር ሁኔታዎች በመመሪያ ይወሰናሉ፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ድንጋጌዎች ቢኖሩም ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ከፈቃድ ክልሉ ላይ የተወሰነው ክፍል ሳይለቀቅ በሚከተሉት ሁኔታዎች የምርመራ ፈቃድ እድሳት ሊፈቅድ ይችላል፡-
   ሀ) ማንኛውም የምርመራ ሥራ ባለፈቃድ ባከናወነው የምርመራ ሥራ የማዕድን ክምችት ማግኘቱን አረጋግጦ የምርት ሥራ ፈቃድ ጥያቄ ለማቅረብ የቅድመ አዋጭነት ወይም የአዋጭነት ጥናት ማከናወን እንደሚያስፈልገው ሲያመለክት፤ ወይም
   ለ) ማንኛውም የምርመራ ሥራ ባለፈቃድ በደንብ በሚወሰነው መሠረት ከአቅሙ በላይ በሆነ ምክንያት የምርመራ ስራውን በጸደቀው የስራ ፕሮግራም መሰረት

[8]በ20/27 (2006) አ. 816 አንቀጽ 2 (7) መሰረት አዲስ የገቡ ናቸው፡፡

ማከናወን ሳይችል ሲቀር፤ ሆኖም ባለፈቃዱ የሁኔታውን መከሰት በጽሑፍ ማሳወቅና በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ተቀባይነት ማግኘት አለበት፡፡

4. የምርመራ ፈቃድ እድሳት፡-

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ፊደል ተራ (ሀ) መሠረት ሲሆን ከሁለት ጊዜ በላይ፤ ወይም

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ፊደል ተራ (ለ) መሠረት ሲሆን ከአንድ ጊዜ በላይ፤

ሊፈቀድ አይችልም፡፡

23. <u>ይዞ የመቆየት ፈቃድ ስለመስጠት</u>

1. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚከተሉት ሁኔታዎች ከተሟሉ ለአመልካቹ የብቸኛ መብት የሚሰጥ ይዞ የመቆየት ፈቃድ ይሰጣል፡፡

ሀ) ባለፈቃዱ በምርመራ ፈቃድ ክልሉ ውስጥ አዋጪ የሆነ የማዕድን ክምችት ማግኘቱን ያስረዳ ሲሆን፣ እና

ለ) የማዕድኑ ክምችት ለጊዜው ባሉት መልካም ያልሆኑ የገበያ ሁኔታዎች ወይም ሌሎች ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ወይም ለጊዜው ማዕድኑን ለማበልጸግ የሚያስችል ቴክኖሎጂ አለመኖር ምክንያት ወዲያውኑ ሊለማ የማይችል ከሆነ ፡፡

2. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በሚከተሉት ሁኔታዎች ይዞ የመቆየት ፈቃድን ሊከለክል ይችላል፡፡

ሀ) አስፈላጊ የሆነው የማበልጸጊያ ቴክኖሎጂ ያለና የማዕድን ክምችቱ በአትራፊነት ሊመረት የሚችል ሲሆን፤

ለ) መልካም ፉክክርን የሚያግድ ሲሆን፣ ወይም

ሐ) የማዕድን ሀብት በአመልካቹ ቁጥጥር ሥር እንዲሰባሰብ የሚያደርግ ሲሆን፡፡

3. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ይዞ የመቆየት ፈቃዱን ለአመልካቹ የማይሰጠው ከሆነ ይህንኑ ውሳኔ በጽሑፍ ከነምክንያቱ ለአመልካቹ ያሳውቀዋል፡፡

24. <u>ይዞ የመቆየት ፈቃድ ዘመንና እድሳት</u>

1. ይዞ የመቆየት ፈቃድ በፈቃዱ ላይ ለተገለጸው ጊዜ ፀንቶ ይቆያል፤ ሆኖም ይህ ጊዜ ከሶስት ዓመት በላይ ሊሆን አይችልም፡፡

2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተመለከቱት ሁኔታዎች የቀጠሉ መሆናቸውን ባለፈቃዱ ካስረዳ ፈቃዱ ከሦስት አመት ለማይበልጥ ጊዜ እንዲታደሳል፡፡

## 25.ይዞ የመቆየት ባለፈቃድ መብት እና ግዴታዎች

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ይዞ የመቆየት ባለፈቃድ የፈቃድ ዘመኑ ከማለቁ በፊት በይዞ መቆየት ፈቃዱ መሠረት የተያዘውን ክልል እና ማዕድን በተመለከተ የማዕድን ማምረት ፈቃድ የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡
2. ይዞ የመቆየት ባለፈቃድ፡-

   ሀ) ያሉትን የገበያና የቴክኒክ ሁኔታዎችና ውጤታቸውን እንዲሁም በተመለከተው ማዕድንና መሬት ላይ ይዞ የመቆየት ፈቃዱ ፀንቶ እንዲቆይ የሚያስፈልግበትን ምክንያት፤ እና

   ለ) የፈቃዱ ዘመን ከመጠናቀቁ በፊት የማዕድን ማምረት ሥራውን ለመጀመር በማድረግ ላይ ያለውን ጥረት፤

   የሚያሳይ ዓመታዊ ሪፖርት ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት፡፡

## 26.የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን የማምረት ሥራ ፈቃድ ስለመስጠት

1. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚከተሉት ሁኔታዎች ከተሟሉ የብቻ የሆነ መብት የሚያስገኝ የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ፈቃድ ለአመልካቹ ይሰጣል፡፡

   ሀ) የቀረበው የሥራ እቅድ ተቀባይነት ካገኘ፤

   ለ) አመልካቹ የታሰበውን የማምረት ሥራ በላቀ ደረጃና ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ለማከናወን የሚያስችል የገንዘብ ምንጭና የቴክኒክ ችሎታ ያለው ወይም ለማግኘት የሚችል መሆኑን ካረጋገጠ፤

   ሐ) የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማው ተቀባይነት ካገኘ፤ እና

   መ) አመልካቹ የምርመራ ፈቃድ የነበረው ከሆነ የዚህኑ ግዴታ ያልጣሰ ሆኖ ከተገኘ፡፡
2. የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የማምረት ፈቃድ የማይሰጥ ከሆነ ይህንኑ በጽሑፍ ከነምክንያቱ ለአመልካቹ ያሳውቀዋል፡፡

## 27.የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ፈቃድ ጸንቶ ስለሚቆይበት ጊዜና እድሳት

1. የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ፈቃድ በፈቃዱ ላይ ለተገለጸው ጊዜ ፀንቶ ይቆያል፤ ሆኖም ይህ ጊዜ ከ20 ዓመት በላይ ሊሆን አይችልም፡፡
2. የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ፈቃድ በዚህ ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በእያንዳንዱ እድሳት ወቅት ከ10 ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ እንዲያገለግል ሊታደስ ይችላል፡፡
3. ባለፈቃዱ ክምችቱን ኢኮኖሚያዊ በሆነ ደረጃ ማምረት መቀጠል የሚችል መሆኑን ካሳየ፣ በፈቃዱ የተመለከቱትን ግዴታዎቹን አሟልቶ ከፈፀመ እና የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በመተላለፍ ፈቃዱን ለማገድ ወይም ለመሰረዝ የሚያበቃ ጥፋት ካልፈጸመ በስተቀር ፈቃዱን የማሳደስ መብት ይኖረዋል፡፡

## 28.የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ስለመስጠት

1. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚከተሉት ሁኔታዎች ከተሟሉ የብቻ የሆነ መብት የሚያስገኝ የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ፈቃድ ለአመልካቹ ይሰጣል፡፡
   ሀ) የቀረበው የሥራ እቅድ ተቀባይነት ካገኘ፤
   ለ) አመልካቹ የታሰበውን የማምረት ሥራ በላቀ ደረጃና ደህንነቱ በጠበቀ ሁኔታ ለማከናወን የሚያስችል የገንዘብ ምንጭና የቴክኒክ ችሎታ ያለው ወይም ለማግኘት የሚችል መሆኑን ካረጋገጠ፤
   ሐ) የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማው ተቀባይነት ካገኘ፤ እና
   መ) አመልካቹ የምርመራ ፈቃድ የነበረው ከሆነ የዚህኑ ግዴታ ያልጣሰ ሆኖ ከተገኘ፡፡
2. የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የማምረት ፈቃድ የማይሰጥ ከሆነ ይህንኑ በጽሑፍ ከነምክንያቱ ለአመልካቹ ያሳውቀዋል፡፡

## 29.የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ፈቃድ ጸንቶ ስለሚቆይበት ጊዜና እድሳት

1. የአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ፈቃድ በፈቃዱ ላይ ለተገለጸው ጊዜ ፀንቶ ይቆያል፤ ሆኖም ይህ ጊዜ ከ10 ዓመት በላይ ሊሆን አይችልም፡፡
2. የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማረት ፈቃድ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በእያንዳንዱ እድሳት ወቅት ከአምስት ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ እንዲያገለግል ሊታደስ ይችላል፡፡

3. ባለፈቃዱ ክምችቱን ኢኮኖሚያዊ በሆነ ደረጃ ማምረት መቀጠል የሚችል መሆኑን ካሳየ፣ በፈቃዱ የተመለከቱት ግዴታዎቹን አሟልቶ ከፈፀመ እና የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በመተላለፍ ፈቃዱን ለማገድ ወይም ለመሰረዝ የሚበቃ ጥፋት ካልፈጸመ በስተቀር ፈቃዱን የማሳደስ መብት ይኖረዋል፡፡

**30.<u>የአነስተኛና የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃዶች መብትና ግዴታዎች</u>[9]**

1. የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባፈቃድ ያመረታቸውን ማዕድናት ለገበያ የማስተዋወቅና የመሸጥ መብት ይኖረዋል፡፡
2. የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ባለፈቃድ፡-

   ሀ) ፈቃዱ ተፈፃሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በሁለት ዓመት ውስጥ የማዕድን ማምረት ሥራውን መጀመር፤ እና

   ለ) የፈቃዱን ስምምነቶችና ግዴታዎች ማክበር፤

   አለበት፡፡
3. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን እንደ ማዕድኑ አይነት፣ የማዕድኑ ክምችትና የማዕድን ሥፍራው ሁኔታ እያየ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (ሀ) የተመለከተውን ጊዜ በደንብ የሚወሰነውን መስፈርት ተከትሎ በሚደረገው የማዕድን ስምምነት ውስጥ ሊያራዝመው ወይም ሊያሳጥረው ይችላል፡፡

**31.<u>የሥራ ፕሮግራም ስለመለወጥ</u>**

1. የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃድ ተቀባይነት አግኝቶ የነበረውን የሥራ ፕግራም በማናቸውም ጊዜ ለመለወጥ ማመልከት ይችላል፡፡
2. ማንኛውም የሥራ ፕሮግራም ለውጥ ለማድረግ የሚቀርብ ማመልከቻ፡-

   ሀ) ተቀባይነት አግኝቶ የነበረውን የሥራ ፕሮግራም ለመተግበር ያላስቻሉትን ሁኔታዎች ማሳየት፣ እና

   ለ) የታሰበውን የሥራ ፕሮግራም ማሻሻያ መያዝ፣

   አለበት፡፡
3. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የሥራ ፕሮግራም ለውጥ ለማድረግ የቀረበለትን ጥያቄ ከመረመረ በኋላ፡-

---

[9] የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2፣ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ሆኖ በ20/22 (2006) አ. 816 አንቀጽ 2(8) ተሻሻለ፡

ሀ) ተሻሽሎ የቀረበውን የሥራ ፕሮግራም ከተቀበለ ያጸድቀዋል፣ ወይም

ለ) ለውጥ ለማድረግ የቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ካደረገው ለውሳኔው ምክንያት የሆኑትን ጉዳዮች በመዘርዘር ለአመልካቹ በጽሑፍ ያሳውቀዋል፡፡

## 32.ልዩ የአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ስራ ፈቃድ ስለመስጠት[10]

1. ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የሚከተሉት ሁኔታዎች ከተሟሉ የብቻ የሆነ መብት የሚያስገኝ ልዩ የአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ስራ ፈቃድ ለአመልካቹ ይሰጣል፡-
   ሀ) የቀረበው የስራ እቅድ ተቀባይነት ካገኘ፣
   ለ) አመልካቹ የታሰበውን የማምረት ስራ ለማከናወን የሚያስችል የገንዘብ አቅም ያለው መሆኑን ካረጋገጠ፣
   ሐ) የአካባቢ ተጽኖ ግምገማው ተቀባይነት ካገኘ፣ እና
   መ) አመልካቹ በጌጣጌጥ ማዕድናት ወይም ከደለል በሚገኝ የወርቅ፣ የብር፣ የፕላቲኒየም ወይም የታንታለም ባህላዊ የማዕድን ማምረት ስራ ፈቃድ የነበረውንና የዚህኑ ግዴታ ያልጣሰ ሆነ ከተገኘ፡፡
2. ልዩ አነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(3) ድንጋጌእንደተጠበቀ ሆኖ በእያንዳንዱ ዕድሳት ወቅት ከአምስት ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ እንዲያገለግል ሊታደስ ይችላል፡፡
3. ልዩ የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ስራ ባለፈቃድ በፈቃዱ የተመለከቱትን ግዴታዎች አሟልቶ ከፈፀመ እና የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችን ወይም ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በመተላለፍ ፈቃዱን ለማገድ ወይም ለመሰረዝ የሚያበቃ ጥፋት ካልፈፀመ በስተቀር ፈቃዱን የማሳደስ መብት ይኖረዋል፡፡

## 33.ልዩ የአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ስራ ፈቃድ ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜና እድሳት

1. ልዩ የአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ በፈቃዱ ላይ ለተመለከተው ጊዜ ጸንቶ ይቆያል፣ ሆኖም ይህ ጊዜ ከ10 ዓመት በላይ ሊሆን አይችልም፡፡
2. ልዩ አነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በእያንዳንዱ ዕድሳት ወቅት ከአምስት ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ እንዲያገለግል ሊታደስ ይችላል፡፡

[10] በ20/22 (2006) አ. 816 አንቀጽ 2(9) አዲስ የተጨመረ አንቀጽ ነው፡፡

3. ልዩ የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ስራ ባለፈቃድ በፈቃዱ የተመለከቱትን ግዴታዎች አሟልቶ ከፈፀመ እና የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችን ወይም ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በመተላለፍ ፈቃዱን ለማገድ ወይም ለመሰረዝ የሚያበቃ ጥፋት ካልፈፀመ በስተቀር ፈቃዱን የማሳደስ መብት ይኖረዋል፡፡

## 34.ስለባህላዊ ማዕድን ማምረት ፈቃድ[11]

1. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማመልከቻ ሲቀርብለት አመልካቹ ለፈቃድ ብቁ መሆኑን አረጋግጦ የብቻ የሆነ መብት የሚያስገኝ የባህላዊ ማዕድን ማምረት ፈቃድ ለአመልካቹ ይሰጣል፡፡
2. የባህላዊ ማዕድን ማምረት ባለፈቃድ፡-
   ሀ) ለባህላዊ ማዕድን ማምረት ሥራ በሕግ በተወሰነው የአካባቢ ጥበቃና የጤንነትና የደህንነት ደረጃዎች መሠረት የመስራት ግዴታ አለበት፤
   ለ) የፈቃዱን ስምምነቶችና ግዴታዎች ማክበር አለበት፡፡
3. የባህላዊ ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ በፈቃዱ ላይ ለተገለፀው ዘመን የፀና ይሆናል፤ ሆኖም ይህ ዘመን ከሁለት ዓመት ሊበልጥ አይችልም፡፡
4. የባህላዊ ማዕድን ሥራ ፈቃድ አይታደስም፡፡
5. የክምችቱን ኢኮኖሚያዊ አለኝታ በተሻለ ሁኔታ ለማልማት የላቁ የምርመራና የማምረት ዘዴዎችን መጠቀም እንደሚያስፈልግ ሲታመንበት ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የ90 ቀናት የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በቅድሚያ በመስጠት ባህላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድን ሊሰርዝ ይችላል፡፡
6. ባለፈቃዱ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በሚወስነው አኳኋን በላቀ የምርመራና የማምረት ተግባር ላይ ለመሰማራት የሚያስፈልገው የቴክኒክ ብቃትና የገንዘብ ምንጭ እንዳለው ለማሳየት ከቻለ የቅድሚያ መብት ይሰጠዋል፡፡
7. ባለፈቃዱ የቅድሚያ መብት የማይሰጠው ሲሆን ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን እንደ ባለፈቃዱ ምርጫ አዲስ ማዕድን ማምረቻ ፈቃድ ቦታ ወይም በፈቃዱ መሰረዝ ምክንያት ለደረሰበት ጉዳት ሊከፈለው የሚገባውን የካሣ መጠን ይወስናል፡፡ ይህም ካሣ ለባለፈቃዱ በተፋጠነ ጊዜ ውስጥ ይከፈለዋል፡፡

---

[11] የዚህ አንቀጽ (እንደተሻሻለ) ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 በ20/27 (2006) አ. 816 አንቀጽ 2(10) ተሻሻሉ፡፡

35.**ስለባለፈቃዶች አጠቃላይ መብቶች**

1. በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች የተመለከቱት መብቶች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ባለፈቃድ እንደ ነገሩ አግባብነት የሚከተሉት አጠቃላይ መብቶች ይኖሩታል፡-
   ሀ) ወደ ፈቃድ ክልል የመግባትና የማዕድን ሥራዎችን ለማካሄድ አስፈላጊ የሆኑ ፋብሪካዎችን፣ ማሽነሪዎችንና መሳሪያዎችን የማስገባት፣ ከመሬት በላይ ወይም በመሬት ሥር የሚዘሩት መሠረተ ልማቶች የመዘርጋትና የመገንባት፤
   ለ) አግባብነት ባላቸው የውሃ ሀብት ሕጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለማዕድን ሥራዎች አስፈላጊ የሆነውን ውሃ በፈቃድ ክልሉ ውስጥ ከሚገኝ ወይም አቋርጦ ከሚያልፍ ከማናቸውም የውሃ ምንጭ የመጠቀም፣ ጥልቅ ወይም ጥልቅ ያልሆነ የውሃ ጉድጓድ የመቆፈር፤
   ሐ) በፈቃድ ክልሉ ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ መሰረተ ልማቶችን ለመዘርጋት በፈቃድ ክልሉና በአዋሳኝ ከሚገኝ ቦታ የግንባታ ማዕድናትን የመጠቀም፤
   መ) ከፈቃዱ ክልል ውጭ ለሥራው የሚያስፈልገውን ሥፍራ በኪራይ እንዲሠጠው የሚመለከተውን አካል የመጠየቅ፤ ሆኖም የኪራይ ውል ግዴታዎች በሚመለከተው አካል የሚወሰኑ ሆኖ የሚጸናበትም ዘመን ከማዕድን ሥራ ፈቃዱ ዘመን የእድሳት ጊዜውን ጨምሮ ማለፍ የለበትም፤
   ሠ) የደን ውጤቶችን ስለመቁረጥና በምትካቸው ችግኞችን ስለመትከል የወጡ አግባብ ያላቸው ሕጎችን በማክበር በፈቃድ ክልሉና በተከራየው መሬት ክልል ውስጥ ለማዕድን ሥራው አስፈላጊ የሆኑ የደን ውጤቶችን የመቁረጥና የመጠቀም፤
   ረ) ሌሎች ሰዎች እንዳይገለገሉባቸው መሰናክል የማይፈጥር እስከሆነ ድረስ በነባር የመሠረተ ልማት አውታሮች የመገልገል፤
   ሰ) ወደ ፈቃድ ክልሉ ለመድረስ አስፈላጊ የሆነውን መንገድ ለማውጣት የግድ መቆረጥ ያለባቸውን ዛፎች ብቻ የመቁረጥ፤
   ሸ) በፈቃዱ መሠረት የገባቸውን ግዴታዎች ካሟላ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የፈቃድ ክልሉን በሙሉ ወይም በከፊል ወይም በፈቃዱ ላይ በተጠቀሱት ማዕድናት ላይ ያለውን መብት የመልቀቅ፣

ቀ) ፈቃዱ ሌሎች ማዕድናትን እንዲያካትት ወይም የፈቃድ ክልሉ የማዕድን ክምችቱን በሙሉ የማያካትት ከሆነ የማዕድን ክምችቱን ሙሉ እንዲሸፍን ተደርጎ እንዲሻሻልለት የመጠየቅ፡፡

2. የማጭበርበር ድርጊት ካልተፈፀመ በስተቀር ፈቃድ ለመጠየቅ የቀረበ ማመልከቻ ወይም ፈቃድ ከመስጠቱ ወይም የጊዜ ማራዘሚያ ከመደረጉ በፊት በነበረው ሂደት የተፈጸመ የፎርማሊቲ አለመሟላት የባለፈቃዱን መብት አያጓድልበትም፡፡

## 36.ስለ ባለፈቃዶች አጠቃላይ ግዴታዎች

1. አግባብ ባላቸው የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች የተለመለከቱት ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-[12]

ሀ) የማዕድን ሥራውን በጥንቃቄ፣ ትጋትና ቅልጥፍና በተሞላበት ሁኔታ ተገቢ በሆኑ ሕጎች፣ ቴክኖሎጂና ለማዕድን ኢንዱስትሪ ተቀባይነት ባገኘ የአሰራር ልምድ መሰረት የማካሄድ፤

ለ) የወኪሎቹን፣ የሠራተኞችንና የሌሎች ሰዎችን ጤንነት ደህንነት በሚያረጋግጥና በተፈጥሮ አካባቢ ላይ የሚደርስ ጉዳትን ወይም ብክላን በተቻለ መጠን መከላከል በሚያስችል ሁኔታ የማዕድን ሥራውን የማከናወን፤

ሐ) ለማዕድን ሥራው አስፈላጊ የሆነ ሥልጠናና ትምህርት ሠራተኞቹ እንዲያገኙ የማድረግ፤

መ) በፈቃዱ ክልል፣ በተከራየው መሬትና አዋሳኝ በሆነ መሬት ላይ ሕጋዊ የይዞታ መብት ያላቸውን ሰዎች ላለማወክ ተገቢውን ጥንቃቄ የመውሰድ፤

ሠ) ከሌሎች ባለፈቃዶች ወይም ከሌሎች ሰዎች ጋር በጋራ ለሚጠቀምባቸው በፈቃዱ ክልል ወይም በተከራየው መሬት ላይ ለሚዘረጉ የመሠረት ልማት አውታሮች ግንባታና ጥገና የመተባበርና ገንዘብ የማዋጣት፤

ረ) በማዕድኑ ሥራ ላይ እንቅፋት የማይፈጥረበት እስከሆነ ድረስ በነጻ ወይም ለንግድ ዓላማ ሲሆን ተገቢውን ክፍያ ለማስከፈል በዘረጋቸው የመሠረተ ልማት አውታሮች ሌሎች ሰዎች እንዲጠቀሙ የመፍቀድ፣

[12] የዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ኘ) እና (ነ) በ20/27 (2006) አ. 816 አንቀጽ 2(11) መሰረት አዲስ የገቡ ናቸው፡

ሰ) ድንገተኛ ሁኔታ ሲፈጠር ከመሠረተ ልማት አውታሮች ላይ ለሚደርሰው ብልሽት ብቻ ካሳ በማስከፈል ሌሎች ሰዎች ወይም መንግስት በጊዜያዊነት እንዲገለገሉባቸው የመፍቀድ፤

ሸ) ተፈላጊ ችሎታ ላላቸው ኢትዮጵያዊያን የቅጥር ቅድሚያ የመስጠት፤

ቀ) በዋጋቸው ተወዳዳሪና በጥራታቸው ተመጣጣኝ ደረጃ ያላቸው እንደልብ ለሚገኙ የሃገር ውስጥ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ቅድሚያ የመስጠት፤

በ) በዚህ አዋጅ፣ በደንብና በመመሪያ መሠረት የሚፈለግበትን ማናቸውንም ክፍያ በወቅቱ የመክፈል፣

ተ) መዛግብቶቹንና ሪኮርዶችን በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ወይም በሕግ ሥልጣን በተሰጣቸው ሌሎች አካላት እንዲመረመሩ የማቅረብ፣

ቸ) የፈቃድ ዘመኑ ሲያበቃ ወይም የፈቃድ ክልሉን ሲለቅ በፈቃድ ክልሉንና በተከራየው መሬት ላይ የገነባቸውን ግንባታዎች የማስወገድ፡፡

ኀ) ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር ያመረተውን የማዕድን ዓይነትና መጠን እያንዳንዱ ወር ባለቀ በ10 ቀናት ውስጥ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሪፖርት የማድረግ እና በእያንዳንዱ የበጀት ሩብ ዓመት ያመረተውን ማዕድን የበጀቱ ሩብ ዓመት ከተፈጸመ በኋላ ከ30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የመሸጥና ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የማሳወቅ፤

ነ) የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ባለፈቃድ ሲሆን የኢትዮጵያ ማዕድን ኢንዱስትሪ ግልጽነት ኢኒሼቲቭ አባል የመሆን እና ለመንግስት ገቢ ያደረገውን ገንዘብ ለሕዝቡ ግልጽ የማድረግ፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሠ) የተመለከተው የግንባታና የጥገና ወጪ ድልድል በተጠቃሚዎቹ የነፍስ ወከፍ ግልጋሎት መጠን ላይ ተመስርቶ በፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን ይወሰናል፡፡

3. ባለፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ቸ) መሠረት ያላነሳቸውን ግንባታዎች መንግሥት ያለምንም ክፍያ የራሱ ንብረት ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡

37.<u>የፈቃድ ክልል ወሰን</u>

የፈቃድ ክልል፡-

1. የማዕድን ማምረት ሥራው በደለል ወይም በጸንስ ተከማችተው የሚገኙ የማዕድን ክምችቶችን የሚመለከት ሲሆን በድንበሮቹ ውስጥ የሚገኘውን መሬትና

በድንበሮቹ ዙሪያ ባልተወሰነ ጥልቀት በሚወርድ ቀጥታ መስመር ውስጥ የሚካተተውን የከርሰ ምድር ክልል ይይዛል፡፡

2. የማዕድን ማምረት ሥራው በተራፊ ክምችት ላይ ሲሆን የተራፊ ክምችቱን ብቻ የሚያጠቃልል ይሆናል፡፡

38. <u>ስለፈቃድ መደራረብ</u>

የዚህ አዋጅ አንቀጽ 37(1) እንተጠበቀ ሆኖ፣ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በአንድ የፈቃድ ክልል ላይ ለተለያዩ ማዕድናት ፈቃዶች ሊሰጥ ይችላል፡፡ ሆኖም ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ተደራራቢው ፈቃድ ቀደም ሲል በተሰጠው ፈቃድ መሠረት በሚካሄዱ የማዕድን ሥራዎች ላይ የሚኖረውን ተጽዕኖ መገምገምና ይህንኑ ለቀድሞው ባፈቃድ ማሳወቅ አለበት፡፡

39. <u>ስለፈቃድ ቀዳሚነት</u>

1. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የማዕድኑን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ወይም ሌሎች አግባብ ያላቸውን የኢንቨስትመንት ዓላማዎች መሠረት በማድረግ በሌላ አኳኋን ካልወሰነ በቀር፡-
   ሀ) የከፍተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራዎች በአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ሥራዎች እና በባህላዊ የማዕድን ሥራዎች እንዲሁም የአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራዎች በባህላዊ የማዕድን ማምረት ሥራዎች ላይ ቀዳሚነት ይኖራቸዋል፤
   ለ) በአንድ የተወሰነ ክልል ላይ ለተለያዩ ማዕድናት ከአንድ በላይ የሆኑ ተመሳሳይ ደረጃ ያላቸው ፈቃዶች ከተሰጡ በመጀመሪያ የተሰጠ የማዕድን ሥራ ፈቃድ በሌሎች የማዕድን ሥራ ፈቃዶች ላይ ቀዳሚነት ይኖረዋል፡፡
2. ፈቃድ በተሰጠበት ክልል ላይ ለተመሳሳይ ማዕድናት በተደራቢ የተሰጠ ፈቃድ ቢኖር በክርክር ላይ ያለው ክልል በቀዳሚው ባለፈቃድ ይዞታ ሥራ እንዳለ ሆኖ ይቆጠራል፡፡

**40.ፈቃድ ስለማስተላለፍ**

1. ከቅኝትና ይዞ ከመቆየት ፈቃዶች በስተቀር ማንኛውም ፈቃድ ፈቃድ ሰጪውን ባለስልጣን በቅድሚያ በማስፈቀድ ሊተላለፍ ይችላል፤ ሆኖም የባህላዊ ወይም ልዩ የአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ በውርስ ካልሆነ በስተቀር ሊተላለፍ አይችልም፡፡[13]
2. ማንኛውም ፈቃድ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ (3) ለተመለከተ ሰው አይተላለፍም፡፡
3. ማናቸውም ፈቃድ ሲተላለፍ ለዚሁ ጉዳይ በተዘጋጀ መዝገብ ላይ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ካልተመዘገበ በቀር ሕጋዊ ውጤት አይኖረውም፡፡

**41.መብትን ስለመተው**

1. በፈቃዱ ላይ ያገባናል የሚሉ ሰዎች መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ ወይም የኪራይ ውል ባለመብት ተቃራኒ ስምምነት ካልኖረው በቀር ቢያንስ የ12 ወራት የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በጽሑፍ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በመስጠት የፈቃድ መብቱን ሊተው ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የፈቃድ ወይም የኪራይ መብቱን የተወ ማንኛውም ሰው ውሉ ጸንቶ ለቆየበት ጊዜ የሚያስከትላቸውን ግዴታዎች ከመፈጸም ነጻ አይሆንም፡፡

**42.መረጃዎችን ስለመግለጽ**

1. በዚህ አዋጅ መሠረት ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ወይም ለሌላ የመንግሥት አካል የቀረበ ማንኛውም መረጃ፣ ሰነድ ወይም ዳታ በባለፈቃዱ ስምምነት ካልሆነ በስተቀር ፈቃዱ ጸንቶ እስከሚቆይበት ጊዜ ድረስ በሚስጥር ተጠብቆ መቆየት አለበት፡፡
2. መረጃው የሚገለጸው፡-

   ሀ) በፍትህ አካላት ለተያዘ ክርክር፣ ማጣራት ወይም ምርመራ ሲሆን፣

   ለ) እንደነዚህ ያሉ መረጃዎችን እንዲቀበል በፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን ለተፈቀደለት የመንግሥት አማካሪ ወይም ሠራተኛ ሲሆን፣ ወይም

[13] እንደተሻሻለ በ20/27 (2006) አ. 816 አንቀጽ 2(12) ተሻሻለ፡፡

ሐ) ለጉዳዩ ከሚያስፈልገው በላይ ዝርዝር እስካልሆነ ድረስ ለመንግሥት ወይም መንግሥትን በመወከል የማዕድን ሥራዎች ስታስቲክስ ለማጠናቀር ሲሆን፣

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ክልከላ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## 43.<u>ስለሪኮርዶችና ሪፖርቶች</u>

1. ማንኛውም ባለፈቃድ የሚከተሉትን መረጃዎች የያዙ አግባብነት ያላቸው ሪኮርዶች በሀገር ውስጥ በመያዝ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሪፖርቶች ማቅረብ አለበት፡-
   ሀ) ከጥልቀት ጉድጓድ የወጣ ኮር እና የዚህንም ዝርዝር የተመዘገበ ዳታ ጨምሮ፣ የማዕድን ሥራውንና የተገኙ ውጤቶች የሚመለከቱ መረጃዎችን፤
   ለ) የቅጥር፣ የፋይናንስ፣ የንግድና ሌሎች አግባብ ያላቸው መረጃዎችን፡፡
2. ባለፈቃዱ ከፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በጽሁፍ የተሰጠ ፈቃድ ሳይኖረው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱትን መዝገቦች ከጥልቅ ጉድጓድ የወጣ ኮር ወይም የኮሩን የተመዘገበ ዳታ ማስወገድ ወይም ማጥፋት አይችልም፡፡

## 44.<u>ስለማዕድናት ባቤትነት፣ ስለሽያጭና ወደ ውጭ ሀገር ስለመላክ</u>

1. የምርመራ ፈቃድ ባለይዞታ የሆነ ሰው ማዕድናት ለማውጣት፣ ለማጓጓዝ ለመመርመርና ሚኒስቴሩን አስቀድሞ በማስፈቀድ ናሙናዎችን ወደ ውጪ ሀገር ለፍተሻ ለመላክ ይችላል፡፡ ሆኖም የናሙና ማዕድናት የመንግስት ንብረት ሆነው ይቆያሉ፤ ያለሚኒስቴሩም ስምምነት ባለፈቃዱ ሊሸጣቸው አይችልም፡፡
2. ማዕድን የማምረት ሥራ ባለፈቃድ በፈቃዱ ላይ የተጠቀሱትን ማዕድናት በማውጣት፣ የባለቤትነት መብት ያገኛል፡፡
3. ማንኛውም የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከቱትን ማዕድናት በአገር ውስጥ ወይም ወደውጭ አገር በመላክ መሸጥ ይችላል፤ ሆኖም በወርቅ ወይም በብር ማዕድናት ማምረት ሥራ ላይ የተሠማራ የባህላዊ ወይም ልዩ የአነስተኛ ማዕድናት ማምረት ሥራ ባለፈቃድ ምርቱን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መሸጥ አለበት፡፡[14]

[14] እንደተሸጋሸገ በ20/27 (2006) አ. 816 አንቀጽ 2(13) ተሻሻለ፡፡

## 45.ስለቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነቶች

1. ማንኛውም ባለፈቃድ ከማዕድን ሥራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነት በሚያደርግበት ጊዜ ስምምነቱን ለሚኒስቴሩ በማቅረብ ማስፈቀድና ማስመዝገብ አለበት፡፡
2. ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነት ሲቀርብለት በቴክኖሎጂ ሽግግር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 121/1983 መሠረት አስፈላጊውን ግምገማ አድርጎ ውሣኔ ይሰጣል፡፡

## 46.የማዕድን መብቶችን ስለማገድና ስለመሰረዝ

1. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) እንደተጠበቁ ሆነው ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የባለፈቃዱ ተግባር በማኅበረሰቡ በአካባቢ ወይም በሠራተኞች ላይ ከባድ አደጋ የሚያስከትል መሆኑን ሲያምንመበትና ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ማገድ ብቸኛው መፍትሔ ሆኖ ሲገኝ ፈቃዱን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ማገድ ይችላል፡፡ ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን እገዳ የሚነሳበትንና ስራ የሚጀምርበትን ቀንም ለባለፈቃዱ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ባለፈቃዱ፡-
   ሀ) በዚህ አዋጅ፣ በደንብ ወይም በመመሪያ የተጣሉበትን ገንዘብ ነክ ግዴታዎች ካልፈፀመ፤
   ለ) የማዕድን ሥራዎችን በከባድ ቸልተኝነት ወይም ሆን ብሎ አግባብ ባልሆነ መንገድ ከአካሄደ፤
   ሐ) የፈቃዱን መሠረታዊ ስምምነቶች ወይም ግዴታዎች ከጣሰ፤
   መ) በሥራ ፕሮግራሙ መሰረት የማዕድን ሥራዎችን የማያካሂድ ከሆነ፤
   ሠ) የጸደቀውን የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማና የጤንነትና ደህንነት ደረጃዎችን ጥሶ ከተገኘ፤
   ረ) በዚህ በአዋጅ፣ በደንብ ወይም በመመሪያ መሰረት ማቅረብ ከሚገባው ጉዳይ ጋር በተያያዘ ትክክለኛ ያልሆነ ወይም የተሳሳተ መረጃ አቅርቦ ከተገኘ፤
   ሰ) የተሟሉ፣ ትክክለኛ የሆኑና ወቅታዊውን ሁኔታ የሚያሳዩ መዝገቦችንና ሪኮርዶችን ካልያዘ፣ ተፈላጊ ሪፖርቶችን ወይም ሌሎች ሰነዶች በወቅቱ ካላቀረበ ወይም ተፈላጊ ማስታወቂያዎችን በወቅቱ ካልሰጠ፤ ወይም

ሸ) በአግባቡ ሥልጣን የተሰጠው የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሠራተኛ ወደ ፈቃድ ክልሉ ወይም በኪራይ ወደተያዘው ክልል እንዳይገባ ወይም የማዕድን ሥራዎች የሚካሄዱባቸውን ቦታዎች ወይም ተቋማት ወይም የባለፈቃዱን መዝገቦች፣ ሪኮርዶች ወይም ሌሎች ሰነዶች ወይም ማቴሪያሎች እንዳያይ ካደረገ ወይም በሠራተኛው የተሰጠውን ሕጋዊ ትዕዛዝ ወይም መመሪያ ካልፈጸመ፤

ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማንኛውንም ፈቃድ ሊሰረዝ ይችላል፡፡

3. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሠረት እርምጃ ከመውሰዱ በፊት የሚከተሉትን የያዘ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ለባለፈቃዱ ይሰጠዋል፡፡

ሀ) ፈቃዱን ለማገድ ወይም ለመሰረዝ ምክንያት ናቸው የሚላቸውን ነገሮች፤

ለ) ባለፈቃዱ የፈጸማቸውን መተላለፎች፣ ጥሰቶች ወይም ጉድለቶች ለማረም ሊወስዳቸው የሚገባቸውን እርምጃዎች፤ እና

ሐ) ባለፈቃዱ የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሊያይልኝ ይገባል የሚላቸውን ማናቸውም ጉዳዩች በጽሑፍ የሚያቀርብበት ከአምስት የሥራ ቀናት ያላነሰ በቂ ቀን፡፡

4. የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የእገዳ ወይም የስረዛ ማስጠንቀቂያውን የሚያነሳው፡-

ሀ) ባለፈቃዱ ለፈቃዱ መታገድ ወይም መሰረዝ ምክንያት ናቸው ተብለው የተዘረዘሩትን ነገሮች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ /ለ/ በተሰጠው ማስጠንቀቂያ በተገለጸው ጊዜ ውስጥ በበቂ ሁኔታ ካረመ፣ ካሻሻለ፣ ካስወገደ ወይም እንዳይደገሙ ከተከላከለ፤ ወይም

ለ) እገዳ ወይ ስረዛ ሊፈጽም አይገባም በማለት ባለፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/3/ /ሐ/ መሠረት ያቀረባቸውን ምክንያቶች ከተቀበለ

ነው፡፡

## ክፍል አራት

## ስለምስክር ወረቀቶች[15]

### 47.ለግኝት የምስክር ወረቀት ስለሚቀርብ ማመልከቻ

1. የማዕድን መኖር ወይም ምልክት ያገኘ ማንኛውም ሰው ያለምንም ክፍያ የተወሰነውን ፎርም በመሙላት የግኝት የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሊያመለክት ይችላል፡፡
2. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ የግኝት የምስክር ወረቀት ለማግኘት የቀረበውን ማመልከቻ ተቀብሎ ይመዘግበዋል፡፡

### 48.የግኝት የምስክር ወረቀት ስለመስጠት

ማዕድናቱ በተገኙበት ቦታ ላይ መኖራቸው ከዚያ በፊት የማይታወቅ ከሆነ፣ ማዕድናቱና የተኙበት ሥፍራ የብቻ የሆነ ፈቃድ የተሰጠባቸው ወይም ማመልከቻ የቀረበባቸው ወይም የተከለከሉ ካልሆኑ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማመልከቻውን ከተቀበለበት ጊዜ አንስቶ በ15 ቀናት ውስጥ ለአግኚው የግኝት የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

### 49.የግኝት የምስክር ወረቀት ዘመንና እድሳት

1. የግኝት የምስክር ወረቀት ለአስራ ስምንት ወራት የፀና ይሆናል፡፡
2. የግኝት የምስክር ወረቀት አይታደስም፡፡
3. የግኝት የምስክር ወረቀት የሚሰጥበት የቦታ መጠን ቢበዛ ከ10 ካሬ ኪሎ ሜትር አይበልጥም፡፡

### 50.የግኝት የምስክር ወረቀት ባለይዞታ የሆነ ሰው መብትና ግዴታ

1. የግኝት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው የምስክር ወረቀቱ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ከማለቁ በፊት አግባብ ላለው የፈቃድ ማመልከቻ የሚጠየቁትን ተፈላጊ ሁኔታዎች የሚያሟላ ከሆነ እንደአግባቡ የምርመራ ፈቃድ ወይም የማምረት ፈቃድ ማመልከቻ የማቅረብ ወይም ፈቃድ ሰጪውን ባለስልጣን በማስፈቀድ ፈቃድ የማግኘት መብቱን ለሌላ ሰው የማስተላለፍ መብት ይኖረዋል፡፡

---

[15] የዚህ ክፍል አንቀጽ 51፣ 52 እና 53 (እንደተሸጋሸጉ) በ20/27 (2006) አ. 816 አንቀጽ 2(14) ተሻሽለዋል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የግኝት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ባለፈቃድ ከሆነ የቀድሞው ፈቃድ የተገኙትን ማዕድናት ወይም አዋሳኝ የሆነውን ክልል እንዲጨምር ተደርጎ እንዲሻሻልለት በአማራጭነት የመጠየቅ መብት ይኖረዋል፡፡ ሆኖም የተሻሻለው ክልል ሊፈቀድ ከሚችለው ጣሪያ ሊያልፍ አይችልም፡፡

## 51.<u>የማማከር ወይም የቴክኒክ አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ[16]</u>

1. በማዕድን ዘርፍ የማማከር አገልግሎት ሥራ ላይ መሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ኢትዮጲያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጲያዊ ተገቢውን የማመልከቻ ክፍያ በመክፈላና የማመልከቻ ቅፅ በመሙላት ለሚኒስትሩ ማመልከት ይችላል፡፡
2. በማዕድን ዘርፍ እንደ ድሪሊንግ፣ የላብራቶሪ ወይም ማዕድናትን ከማዕድን አዘል አፈር ወይም አለት መለየት ባሉት የቴክኒክ አገልግሎት ሥራ ላይ መሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ተገቢውን የማመልከቻ ክፍያ በበመክፈልና የማመልከቻ ቅፅ በመሙላት ለሚኒስትሩ ማመልከት ይችላል
3. በማዕድን ዘርፍ የመስክ ስራ ላይ እንደ ሕክምና፣ ድንኳን መትከል ወይም ምግብ ማዘጋጀት በመሳሰሉ የቴክኒክ አገልግሎት ስራ ላይ መሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ኢትዮጲያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጲያዊ ተገቢውን የማመልከቻ ክፍያ በመክፈልና የማመልከቻ ቅፅ በመሙላት ለሚኒስትሩ ማመልከት ይችላል፡፡
4. ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1፣2 እና 3 የተመለከቱት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማመልከቻ ተቀብሎ ይመዘግበዋል፡፡

## 52.<u>የማማከር ወይም የቴክኒክ አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት</u>

1. በማማከር አገልግሎት ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚያመለክት ሰው ባመለከተበት ሙያ አስፈላጊው እውቀትና የሥራ ልምድ ያለው መሆኑን ሚኒስቴሩ ሲያረጋግጥ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

[16] በ26/63(2012) አ.1213 አንቀፅ 2(2) መሰረት ተሻሻለ፡፡

2. ማመልከቻው የቀረበው እንደ ድሪሊንግ ወይም ላብራቶሪ በመሳሰሉ የቴክኒክ አገልግሎት ላይ ለመሰማራት ሲሆን አመልካቹ ባመለከተበት የአገልግሎት ዘርፍ አስፈላጊው የባለሙያና የማቴሪያል ዝግጅት እንዳለው በሚኒስቴሩ ተረጋግጦ የጠየቀው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡
3. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ፀንቶ የሚቆይበት ዘመን፣ የሚታደስበትና የሚሰረዝበት ሁኔታ በደንብ ይወሰናል፡፡

53.<u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው መብትና ግዴታ</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 52 ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው በምስክር ወረቀቱ ላይ በተመለከተው የማዕድን ሥራ ዘርፍ የማማከር ወይም የቴክኒክ አገልግሎት መስጠት ይችላል፡፡
2. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው በማማከር ወይም በቴክኒክ አገልግሎት ሥራው ላይ ከመሰማራቱ በፊት አግባብ ካለው የመንግሥት መስሪያ ቤት የንግድ ፈቃድ ማውጣት አለበት፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ስለአስተዳደር</u>

54.<u>የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሥልጣንና ተግባር</u>[17]

1. የክልል ፍቃድ ሰጪ ባለሥልጣን፡-
   ሀ) የባህላዊ ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድና ልዩ የአነስተኛ ማዕድን ማምረት ስራ ፈቃድ መስጠት፤
   ለ) ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች፡-
      1) የኮንስትራክሽንና የኢንዱስትሪ ማዕድናትን በሚመለከት የቅኝት፣ የምርመራና ይዞ የመቆየት ፈቃዶች የመስጠት፤
      2) የአነስተኛ ደረጃ የኢንዱስትሪ ማዕድናት ማምረት ፈቃዶች እንዲሁም የአነስተኛ እና የከፍተኛ ደረጃ የኮንስትራክሽን ማዕድናት ማምረት ፈቃዶች የመስጠት፤እና
   ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (ለ) ከተመለከተው ውጪ ለሆኑት ማዕድናት

[17] የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ) እና 2 (ሀ) (እንደተሻሻለ) እንደቅደም ተከተላቸው በ20/27 (2006) አ. 816 አንቀጽ 2 (15) እና 2 (16) የተሻሻሉ ሲሆን ንዑስ አንቀጽ 4 ፊደል ተራ (ተ) በአንቀጽ 2(17) መሰረት አዲስ የገባ ነው፡፡

የግኝት የምስክር ወረቀት የመስጠት፣

ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡፡

2. ሚኒስቴሩ፡-

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) መሠረት በክልል ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን ከሚሰጡት በስተቀር የቅኝት፣ የምርመራ፣ ይዞ የመቆየትና የማዕድን ማምረት ፈቃዶች የመስጠት፤

ለ) ለስትራቴጂካዊ ማዕድናት የግኝት የምስክር ወረቀት የመስጠት፤

ሐ) በማዕድን ዘርፍ የማማከር አገልግሎት ሥራ መሰማራት ለሚፈልጉ ባለሙያዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመስጠት፤

መ) ወደ ውጭ የሚላኩ የማዕድን ናሙናዎችን የመመርመርና የመፍቀድ፤

ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡፡ ሆኖም የማዕድን ማምረት ፈቃድ የሚሰጠው በቅድሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ይሁንታ በመጠየቅ ይሆናል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) በተመለከተው መሠረት የተሰጠው ማናቸውም ፈቃድ የባለቤትነት ይዞቱ የተቀየረ እንደሆነ ፈቃዱን የሰጠው ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን ከፈቃዱ ጋር የተያያዙ ሰነዶችን ለሚመለከተው ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን ማስተላለፍ አለበት፡፡

4. ማንኛውም ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ መሠረት ለማዕድን ሥራዎች የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን መቀበል፣ ፕሮሰስ ማድረግ እና ውድቅ ማድረግ ወይም ማጽደቅ፤

ለ) ማንኛውም ባለፈቃድ በፈቃዱ የተመለከቱትን ግዴታዎች ለመወጣት አስፈላጊው የገንዘብ ምንጭና የቴክኒክ ብቃት ያለው መሆኑን የማረጋገጥ፤

ሐ) በጨረታ በማወዳደር ወይም ቀጥተኛ በሆነ ድርድር መንግስትን ወክሎ የማዕድን ስምምነቶችን የማድረግ፤

መ) በዚህ አዋጅ፣ በደንብና በመመሪያ መሠረት ፈቃድ የመስጠት፣ የማደስ የማገድና የመሰረዝ፤

ሠ) የዚህ አዋጅ አንቀጽ 40 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በአንቀጽ 41 የተመለከቱትን መረጃና ሪከርዶች የመቀበል፤

ረ) የማዕድን ሥራዎች በዚህ አዋጅ፣ በደንቦች፣ በመመሪያዎችና አግባብ ባላቸው ስምምነቶች መሠረት መካሄዳቸውን የመቆጣጠርና የማረጋገጥ፤

ሰ) ባለፈቃዱ አስቀድሞ የገባቸው ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ያመረታቸውን ማዕድናት በሙሉ ወይም በከፊል ሽያጩ በሚከናወንበት ወቅት ባለው የዓለም ገበያ ዋጋ ለመንግስት፣ ለመንግስታዊ ድርጅት ወይም ለሌላ ሰው በአገር ውስጥ እንዲሸጥ የማድረግ፤

ሸ) ባሕላዊ ማዕድን ማምረት ሥራ የሚካሄድበትን ሥፍራ እያጠና በሕግ ማስታወቂያ የመከለል፤

ቀ) በዚህ አዋጅ፣ በደንብና መመሪያ መሠረት የሚከፈሉትን ሮያሊቲ፣ የመሬት ኪራይና ሌሎች ክፍያዎች የመሰብሰብና ሂሳቡን የመመርመር፣

በ) ባለፈቃዶች የሚያካሂዷቸው የማዕድን ሥራዎች የአካባቢ ጥበቃን ያገናዘቡና ለማኅበረሰቡ የአካባቢ ልማት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ መሆኑን የማረጋገጥ፡፡

ተ) ከማዕድን ማምረት ሥራ የሚሰበሰበውን ገቢ ለሕብረተሰቡ ግልጽ የማድረግ፡፡

55.**<u>የማዕድን ሥራዎች ምክር ቤት</u>**

1. ሚኒስቴሩን የሚያማክር የማዕድን ሥራዎች ምክር ቤት ይቋቋማል፡፡
2. የማዕድን ሥራዎች ምክር ቤት አባላት ተዋጽኦ፣ ኃላፊነትና ሌሎች ዝርዝር ሁኔታዎች በደንብ ይወሰናሉ፡፡

56.**<u>ስለ ቁጥጥር</u>**

1. ማንኛውም ሥልጣን የተሰጠው የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ተቆጣጣሪ በሥራ ሰዓት ወደ ማናቸውም የፈቃድ ክልል በመግባት፡-

   ሀ) በፈቃድ ክልሉ ላይ ወይም ውስጥ በመካሄድ ላይ ያለን ማናቸውንም እንቅስቃሴ ወይም ሂደት ለመቆጣጠር፤

   ለ) ማናቸውንም መዝገብ፣ ሪኮርድ፣ መግለጫ ወይም ሰነድ ለመመርመርና የሰነዱን ወይም የሰነዱን ክፍል ቅጅ ለመውሰድ፤

   ሐ) በሥፍራው የሚገኙ ማቴሪያችንና መሣሪያዎችን ለመመርመር፤

   መ) ማናቸውንም ናሙና ለመውሰድና ለመፈተሽ፣ ለመመርመር ለመተንተንና በአይነት በአይነቱ ለመለየት፤

   ሠ) በዚህ አዋጅ፣ በደንብ ወይም በመመሪያ መጣስ ምክንያት ክስ ለመመስረት አስፈላጊ የሆኑ ማቴሪያሎችን፣ ዕቃዎችን፣ መሳሪያዎችን፣

መዝገቦች፣ መግለጫዎችን ወይም ሰነዶችን ለመያዝና በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ጥበቃ ሥር ለማቆየት፤ እና

ረ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ የተመለከቱትን ተግባራት ለመፈጸም እንዲችል የሚያስፈልጉት ድጋፎች እንዲሰጠው ትዕዛዝ ለመስጠት፤

ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሠ) መሠረት ማናቸውም ማቴሪያል፣ መሳሪያ፣ መዝገብ፣ መግለጫ ወይም ሰነድ በፈቃድ ሰጪው ጥበቃ ሥር እንዲቆይ ሲደረግ፡-

ሀ) በይዞታው ወይም በቁጥጥሩ ሥራ የነበረ ሰነድ የተያዘበት ሰው ተቆጣጣሪው እየተከታተለው የሰነዱ ወይም የሰነዱን ክፍል ቅጅዎች እንዲወስድ ማድረግ ይቻላል፣

ለ) ከተያዘው ማቴሪያል፣ መሳሪያ፣ መዝገብ፣ መግለጫ ወይም ሰነድ ጋር በተያያዘ ክስ ካልተመሰረተ ወይም በማናቸውም ክርክር ወቅት እንደማስረጃ ሊያገለግል መቻሉ አጠራጣሪ ሆኖ ሲገኝ ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ለተያዘበት ሰው ወዲያወኑ ይመለሳል፡፡

3. ተቆጣጣሪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ምርመራውን እንዲያካሄድ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የተሰጠውን ደብዳቤ አግባብ ላለው የባለፈቃዱ ሠራተኛ የማሳየት ግዴታ አለበት፡፡

57.**<u>በሰራተኞች ላይ ጎጂ ተጽዕኖ የሚያስከትሉ እርምጃዎች መውሰድ ስለሚከለከሉባቸው ሁኔታዎች</u>**

ማንኛውም ባለፈቃድ ይህን አዋጅ፣ ደንብን፣ መመሪያን ወይም የፈቃድ ግዴታዎቹን አለማክበሩን በሥሩ የሚገኝ ሠራተኛ ለፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን በማሳወቁ ምክንያት በሠራተኛው የሥራ ሁኔታ ላይ ጎጂ ተጽዕኖ የሚያደርስ እርምጃ ሊወሰድ አይችልም፡

58.**<u>የትርፋማነት ማነስ የማዕድን ማምረት ሥራ መቀነስ</u>**

1. የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲከሰቱ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ያሳውቃል፡-

ሀ) የወቅቱ የኢኮኖሚ ሁኔታ የማዕድን ሥራው ትርፍ ከገቢው ጋር ያለውን ንጽጽር ለ12 ተከታታይ ወራት በአማካይ ከስድስት በመቶ ያነሰ አድርጎት ከሆነ፤ ወይም

ለ) ማናቸውም የማዕድን ሥራ በማናቸውም የአስራ ሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ከአሥር በመቶ በላይ የሆነ ሠራተኛ ሊያስቀንስ በሚችል ደረጃ የሚቀንስ ወይም የሚቆም ሲሆን፡፡

2. የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርን ካማከረ በኋላ ጉዳዩ የሚመለከተው የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ የእርምት እርምጃዎች እንዲወስድ በጽሁፍ መመሪያ ሊሰጠው ይችላል፡፡

3. የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃዱ በተሰጠው መመሪያ መሰረት መፈጸምና የእርምት እርምጃዎቹ መወሰዳቸውን በጽሑፍ ማረጋገጥ አለበት፡፡

## ክፍል ስድስት

## ስለካሣ ክፍያ

### 59.ስለካሳ መርሆዎች

1. የዚህን አዋጅ አላማ ለማስፈጸም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማናቸውንም የማይቀሳቀስ ንብረት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ለሕጋዊ ባለንብረቱ ተገቢውን ካሣ እንዲከፈል በማድረግ መውረስ ይችላል፡፡ ለዚህም ጉዳይ አፈጻጸም ሲባል የማዕድን ሥራ በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1460 መሠረት የሕዝብ አገልግሎት ሥራ ሆኖ ይቆጠራል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ባለፈቃድ ከማዕድን ሥራው ጋር በተያያዘ ማናቸውም ንብረት ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት አለበት፡፡

### 60.ስለ ካሳ ስምምነቶች

1. ማንኛውም ባለፈቃድ ለሚያካሂደው የማዕድን ሥራ መሬት እንዲለቀቅለት የሚያስፈልግ ከሆነ ለሚለቀቀው መሬት ወይም ለንብረቱ የሚከፍለው ካሳ ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ ስለሚለቀቅበትና ለንብረት ካሳ ስለሚከፈልበት ሁኔታ ለመወሰን በወጣ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ይሆናል፡፡[18]

[18] በ20/27 (2006) አ. 816 አንቀጽ 2 (18) ተሻሻለ፡፡

2. በባለፈቃዱና ባለንብረቱ መካከል በካሣ ስምምነቱ ሁኔታዎችና ግዴታዎች ላይ ስምምነት እንደተደረሰ ባለፈቃዱ ወዲያውኑ የስምምነቱን ቅጅ ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ማቅረብ አለበት፡፡
3. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የተደረገው የካሳ ስምምነት ቅጂ እንደደረሰው ወዲያውኑ ይመዘግበዋል፡፡

61.ካሳን አስመልክቶ ስለሚቀርብ አቤቱታና ይግባኝ[19]

1. ካሳን አስመልክቶ የሚቀርብ አቤቱታ ወይም ይግባኝ የመሬት ይዞታን ለህዝብ ጥቅም ሲባል ለማስለቀቅና ለንብረት ካሳ ስለሚከፈልበት ሁኔታ ለመወሰን በወጣ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ይፈጸማል፡፡
2. ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ከማዕድን ሥራ ጋር በተያያዘ መሬትን ካሣ በመክፈል ማስለቀቅ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ መሬትን ለሕዝብ ጥቅም ካሳ ተከፍሎ እንዲለቀቅ የማድረግ ሥልጣን ከተሰጠው መሥሪያ ቤት ጋር በመመካከር ሥራው በአፋጣኝ የሚፈፀምበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

## ክፍል ሰባት

## ስለአካባቢ

62.የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማና የመልሶ ማቋቋሚያ ፈንድ

1. ከቅኝት፣ ከይዞ መቆየት ወይም ከባህላዊ የማዕድን ማምረት ፈቃድ በስተቀር ማንኛውም ፈቃድ እንዲሰጠው የሚጠይቅ አመልካች የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማውን አግባብ ላለው መሥሪያ ቤት በማቅረብ ማጸደቅ አለበት፡፡
2. ከቅኝት፣ ከይዞ መቆየት ወይም ከባህላዊ የማዕድን ማምረት ባለፈቃድ በስተቀር ማንኛውም ባለፈቃድ ለአካባቢ ተፅዕኖ መልሶ ማቋቋሚያ ወጪ መሸፈኛ የሚውል ፈንድ ይመድባል፡፡
3. ከባህላዊ ማዕድናት ማምረት ባለፈቃድ በስተቀር ማንኛዉም የማዕድን ማምረት ባለፈቃድና እንደአግባቡ የማዕድን ምርመራ ባለፈቃድ በፈቃድ ክልሉ እና በስምምነት በሚወሰን በፈቃድ ክልሉ አካባቢ ለሚኖሩ ነዋሪዎች የማህበረሰብ ልማት እቅድ መሳተፍና ለዚህ የሚያስፈልግ ወጪ መመደብ አለበት፡፡[20]
4. ይህንን አንቀጽ ለማስፈፀም ዝርዝር ጉዳይ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

---

[19] እንደተሻሻለ በ20/27 (2006) አ. 816 አንቀጽ 2 (19) ተሻሻለ፡፡
[20]በ20/27 (2006) አ. 816 አንቀጽ 2 (20) ተሻሻለ፡፡

## 63.ስለማዕድን ሥራ መዘጋት

1. ልዩ የአነስተኛ፣ የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ስራ ባለፈቃድ በሚከተሉት ሁኔታዎች የማዕድን ሥራ መዝጋት የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ፈቃድ ሰጪውን ባለስልጣን ሊጠይቅ ይችላል፡-

   ሀ) ፈቃዱ ሲሰረዝ፤

   ለ) የማዕድን ስራው ሲቋረጥ፤

   ሐ) የማዕድን ስራውን ክልል በከፊል ወይም በሙሉ ሲለቅ፤ ወይም

   መ) የማዕድኑን ስራ ሲተው፡፡[21]

2. ማመልከቻው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱት ሁኔታዎች በተከሰቱ በ180 ቀን ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

3. የጤና፣ የደህንነትና የአካባቢ ጥበቃን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች መፍትሔ የተሰጣቸው መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር የማዕድን መዘጋት የምስክር ወረቀት አይሰጥም፡፡

4. የማዕድን መዝጋት የምስክር ወረቀት መሰጠቱ፣ ባለፈቃዱን የማዕድኑ ሥራ ከተዘጋ በኋላ በአካባቢው ላይ ሊደርስ ስለሚችለው ተጽእኖ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማው በሚጠይቀው መሠረት ክትትል የማድረግ ኃላፊነቱን በማናቸውም መንገድ አያስቀረውም፤ ውሉ ጸንቶ ለቆየበት ጊዜ የሚያስከትላቸውን ግዴታዎች ከመፈጸምም ነጻ አያደርገውም፡፡

## 64.የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን መፍትሄ የመስጠት ሥልጣን

1. ባለፈቃዱ የሞተ እንደሆነ ወይም ሊገኝ ካልቻለ ወይም ኩባንያ ሲሆን ህልውናው ካከተመ ወይም በኪሳራ ከተዘጋ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ተጨማሪ ብክለት እንዳይደርስ ለማድረግ አላስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎች ይወስዳል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን ሥራ ለመስራት የሚያስፈልገው ገንዘብ ባለፈቃዱ ለዚህ ተግባር ብሎ ካኖረው ወይም ለዚህ ጉዳይ የተቀመጠ ገንዘብ ከሌለ ወይም በቂ ካልሆነ ለዚሁ ጉዳይ ከመንግስት ግምጃ ቤት ከተመደበ ገንዘብ ላይ ወጪ ተደርጎ ይሠራል፡፡

---

[21]በ20/27 (2006) አ. 816 አንቀጽ 2 (21) ተሻሻለ፡፡

## ክፍል ስምንት

## ስለ ሮያልቲ፣ የገቢ ግብርና ሌሎች ገንዘብ ነክ ጉዳዮች

### 65.ሮያልቲ[22]

1. የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ የተመረተውን ማዕድን በንግድ ልውውጥ በሸጠበት ዋጋ ላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) መሠረት ሮያልቲ ይከፍላል፡፡
2. በከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃዶች የሚከፈለው ሮያልቲ በሚከተለው መጠን ይሆናል፡-

   ሀ) ለከበሩ ማዕድናት 8 በመቶ፤

   ለ) በከፊል ለከበሩ ማዕድናት 6 ›› ፤

   ሐ) ለብረት ነክ ማዕድናት 5 ›› ፤

   መ) ለኢንዱስትሪ ማዕድናት 4 ›› ፤

   ሠ) ለኮንስትራክሽን ማዕድናት 3 ›› ፤

   ረ) ለጨው 4 ››፤

   ሰ) ለጂኦተርማል 2 ››፡፡
3. በባህላዊ፣ በልዩ የአነስተኛ እና በአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ስራ ባለፈቃዶች የሚከፈለው የሮያሊቲ መጠን በክልል ህጎች ይወሰናል፡፡

### 66.ለጊዜው ስለሚተመን የሮያልቲ መጠን[23]

1. መከፈል የሚገባውን የሮያልቲ መጠን ለመተመን በማይቻልበት ጊዜ ባለፈቃዱ ጊዜያዊ የሮያልቲ ክፍያ ይከፍላል፡፡
2. መከፈል ያለበት የሮያልቲ መጠን ሲረጋገጥ ባለፈቃዱ ልዩነቱን ይከፍላል ወይም የከፈለው እላፊ ተመላሽ ይሆንለታል፡፡
3. ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ማንኛውም ማዕድን ማምረት የጀመረ ባለፈቃድ ሊከፍለው የሚገባውን የሮያሊቲ ክፍያ ለመቀነስ፣ ለጊዜው ለማንሳት ወይም ለማስቀረት እንደአግባቡ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ወይም ለሚመለከተው የክልል የበላይ ባለስልጣን ሀሳብ በማቅረብ ሊያስወስን ይችላል፡፡

---

[22] የዚህ አንቀጽ (እንደተሸጋሸገ) ንዑስ አንቀጽ 2 (ሀ) እና 3 እንደቅደም ተከተላቸው በ20/27 (2006) አ. 816 አንቀጽ 2 (22) እና 2 (23) ተሻሽለዋል፡፡

[23] የዚህ አንቀጽ (እንደተሸጋሸገ) ንዑስ አንቀጽ 3 በ20/27 (2006) አ. 816 አንቀጽ 2 (24) ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 ሆኖ ተሻሻለ፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት የሮያሊቲ ክፍያ ለመቀነስ፣ ለጊዜው ለማንሳት ወይም ለማስቀረት የሚያስችሉ ዝርዝር መስፈርቶች በደንብ ይወሰናሉ፡ ፡

67.የገቢ ግብር

1. ማንኛውም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃድ ከማዕድን ሥራ ከሚያገኘው ገቢ በማዕድን ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 53/1985 (እንደተሻሻለ) መሠረት የገቢ ግብር ይከፍላል፡፡
2. የባህላዊ፣ ልዩ የአነስተኛ እና የአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ስራ ባለፈቃዶች ከማዕድን ሥራ ከሚያገኙት ገቢ የሚከፍሉት የገቢ ግብር በክልል ህጎች ይወሰናል፡፡[24]

68.መረጃ ስለመሰብሰብ

1. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማንኛውም ባለፈቃድ ከሮያልቲው ክፍያ ጋር በተያያዘ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ማክበሩን ለማረጋገጥ ማናቸውም የቃል፣ የጽሑፍ ወይም የኤሌክትሮኒክስ መረጃ እንዲያቀርብ ወይም እንዲያሳይ በጽሁፍ ማዘዝ ይችላል፡፡
2. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚያስፈልጉ መረጃዎች እንዳይቀርቡ ወይም እንዲጠፉ ተደርገዋል ብሎ ሲያምን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 54 መሠረት ምርመራ እንዲካሄድ ሊያዝ ይችላል፡፡

69.ሮያልቲና የገቢ ግብር ስላለመክፈል

ባለፈቃዱ መክፈል ባለበት ጊዜ ውስጥ ሮያሊቲ፣ የገቢ ግብር ወይም ማናቸውንም ሌላ ክፍያ ሳይከፍል ከቀረ፣ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ያልተከፈሉ ክፍያዎች ተጠናቀው እስኪከፈሉ ወይም ክፍያውን ለመፈጸም የሚያስችል በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ተቀባይነት ያለው ዘዴ እስኪመቻች ድረስ ጉዳዩ ከሚመለከተው ማንኛውም የማዕድን ማምረቻ ቦታ ወይም በባለፈቃዱ ከተያዘ ሌላ የማዕድን ማምረቻ ቦታ ምንም አይነት ማዕድን እንዳይነሳና እንዳይሸጥ በመከልከል ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

[24]በ20/27 (2006) አ. 816 አንቀጽ 2 (25) ተሻሻለ፡፡

**70.<u>የመሬት ኪራይ</u>**

1. ማንኛውም ባለፈቃድ በፈቃዱ ላይ ለተመለከተው ክልል የመሬት ኪራይ በየዓመቱ በቅድሚያ ይከፍላል፡፡ የኪራዩ መጠን ክልሎች የሚያወጧቸው ሕጎች የሚወሰን ሆኖ ማናቸውም የኪራዩን መጠን የሚለውጥ የሕግ ማሻሻያ ተፈጻሚ የሚሆነው ማሻሻያው ከወጣበት ቀን በኋላ በሚሰጡ ፈቃዶች ላይ ብቻ ይሆናል፡፡
2. ማንኛውም ባለፈቃድ ከፈቃድ ክልል ውጪ በኪራይ ለያዘው መሬት በየዓመቱ በቅድሚያ ኪራይ ይከፍላል፡፡ የኪራዩ መጠን የኪራዩ መብት በተመሠረተበት ሰነድ የሚወሰን ሆኖ በሰነዱ ውስጥ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር እስከ ኪራዩ ዘመን መጨረሻ የጸና ይሆናል፡፡

**71.<u>ስለፈቃድ ክፍያ</u>**

በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚሰጡ ፈቃዶችና ፈቃዶቹን ለማሳደስ የፈቃድ ክፍያ ይከፈላል፡፡ የክፍያው መጠንና የአከፋፈሉ ሁኔታ እንደአግባቡ በደንብና በክልል ህጎች ይወሰናል፡፡

**72.<u>በመንግስት ስለሚያዝ አክሲዮን</u>[25]**

1. መንግስት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 መሰረት የማዕድን ስራዎች የማካሄድ መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛዉም ባለፈቃድ ከሚካሄድ የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ስራዎች ኢንቨስትመንት አምስት በመቶ አክሲዮን ያለምንም ክፍያ ይይዛል፡፡ እንዲሁም ስለድርሻው መቶኛ፣ ስለአከፋፈሉ፣ ከተሳትፎ ስለሚመነጬት መብትና ግዴታዎች እና ሌሎች የተሳትፎ ዝርዝር ሁኔታዎች ከባለፈቃዱ ጋር በሚደረግ ስምምነት በሚወሰነው መሰረት መንግስት ተጨማሪ አክሲዮኖችን መያዝ ይችላል፡፡
2. ከአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራዎች ኢንቨስትመንት መንግስት ያለምንም ክፍያ ሊይዝ የሚችለው የአክሲዮን መጠን እና የተጨማሪ አክሲዮኖች ሁኔታ በክልል ህጎች ይወሰናል፡፡

[25] እንደተሸጋሸገ በ20/27 (2006) አ. 816 አንቀጽ 2 (26) ተሻሻለ፡፡

**73.ስለዋስትና**

ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ፈቃድ እንዲሰጠው ወይም እንዲታደስለት ወይም ፈቃድ ለማስተላለፍ፣ ለመዳረግ ወይም በዕዳ ለማስያዝ የሚጠይቅ አመልካች ለግዴታዎቹ መፈጸም ማረጋገጫ የሚሆን የገንዘብ፣ የባንክ ወይም ሌላ ዋስትና እንዲያቀርብ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ዋስትና የሚጠየቅበት ሁኔታ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

**74.ስለ ውጭ ምንዛሪ**

1. ወደ ውጭ የሚላኩ ማዕድናት የሚያመርት የከፍተኛ ወይም የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ በውጭ ምንዛሪ ካገኘው የሽያጭ ገቢ ውስጥ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ የሚወሰን ድርሻ በመያዝ በውጭ ምንዛሬ ለሚፈጸሙ ክፍያዎች ሊጠቀምበት ይቻላል፡፡
2. የውጭ ባለሀብት የሆነ የከፍተኛ ወይም የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ የሚከተሉት ክፍያዎች ወደ ኢትዮጵያ ባስገባበት የውጭ ምንዛሬ ዓይነት ወይም በሌላ በተፈቀደ የውጭ ምንዛሪ ዝውውሩ በሚፈጸምበት ቀን ባለው የምንዛሪ ተመን መሠረት ከኢትዮጵያ ውጭ ለማዛወር ይችላል፡-
   ሀ) ከማዕድን ሥራ ኢንቨስትመንት ካፒታል የተገኘ ትርፍና የትርፍ ድርሻ፤
   ለ) ከውጭ አገር በብድር የሚገኝ ዋና ገንዘብና ወለድ፤
   ሐ) ከማዕድን ሥራው ጋር ግንኙነት ባለው የቴክኖሎጂ ወይም የሥራ አመራር ስምምነት ምክንያት የሚከፈሉ ገንዘቦች፣ ጥቅሞች ወይም ሌሎች ክፍያዎች
   መ) የማዕድን ሥራ ድርጅት ፈርሶ ሂሳቡ ሲጣራ የሚገኝ ገቢ፤
   ሠ) አክሲዮን ለሀገር ውስጥ ባለሀብት ሲዛወር ወይም ሲሸጥ ወይም የማዕድን ሰራው በከፊል ወይም በሙሉ በሀገር ውስጥ ባለሀብት ባለቤትነት ሥር ሲደርግ የተገኘ ገንዘብ፡፡
3. በማዕድን ሥራው ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ የውጭ ሀገር ዜጎች ያገኙትን ደመወዝና ሌሎች ክፍያዎች አግባብ ባለው የውጭ ምንዛሪ ደንብ በሚፈቅደው መሠረት ወደ ውጭ አገር ለመላክ ይችላሉ፡፡

75.ከግምሩክ ቀረጥና  ታክስ ነጻ ስለመሆን[26]

1. ማንኛውም የምርመራ ባለፈቃድ ወይም የእርሱ ተቋራጭ ለስራው የሚያስፈልጉና በፀደቀው የሥራ ፕሮግራም መሠረት ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገቧቸው አላቂ ዕቃዎች፣ መሣሪያዎች፣ ማሽነሪዎች እና ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነጻ ይሆናሉ፡፡
2. ማንኛውም የልዩ አነስተኛ፣ የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃድ ወይም የእርሱ ተቋራጭ ለሥራው የሚያስፈልጉ እና በማዕድን ማምረት ስምምነቱና በጸደቀው የሥራ ፕሮግራም መሠረት በምርት ቅድመዝግጅት ጊዜ ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባቸው መሳሪያዎች፣ ማሽነሪዎች፣ ተሽከርካሪዎችና አላቂ ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነጻ ይሆናሉ፡፡ ሆኖም መሳሪያዎችን፣ ማሽነሪዎችንና ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ነፃ የማስገባት መብት ማምረት ከተጀመረበት ቀን አንስቶ ከአምስት ዓመት በኋላ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡
3. የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃድ ለንግድ በሆነ መጠን ማዕድን ማምረት ከጀመረበት ቀን አንስቶ ለመጀመሪያዎቹ ሶስት ወራት ሊያሰራው የሚችል ማናቸውንም አላቂ ዕቃዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ (2) (ሀ) በተገለጸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ማስገባት ይችላል፡፡
4. የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃድ የምርት ሥራውን በላቀ ደረጃ ለማስፋፋት ሲፈለግና የማስፋፊያው እቅድ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሲፀድቅ ለማስፋፊያ ሥራው የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችና ማሽነሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነጻ ማስገባት ይችላል፡፡
5. ወርቅ ወይም ብር ከሚያመርት የባህላዊ ወይም ልዩ የአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ በስተቀር ማንኛውም የማዕድን ማምረት ስራ ባለፈቃድ በፈቃዱ መሠረት ያመረታቸውን ማዕድናት ወደ ውጭ አገር ሲልክ አስፈላጊውን የጉምሩክ እና የባንክ ፎርማሊቲ ማሟላት እንደተጠበቀ ሆኖ ከማናቸውም የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነጻ ይሆናል፡፡

[26] የዚህ አንቀጽ (እንደተሻሻለ) ንዑስ አንቀጽ 2፣ 3 እና 5በ20/27 (2006) አ. 816 አንቀጽ 2 (27) ተሻሽለዋል፡፡

6. የባህላዊ ማዕድን ማምረት ባለፈቃድ ወይም አሸዋ ወይም ገረጋንቲ ለማምረት የሚያስችል ፈቃድ ያለው ማንኛውም የኮንስትራክሽን ማዕድን ማምረት ባለፈቃድ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (4) የተመለከቱት የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነጻ መብት ተጠቃሚ አይሆንም፡፡
7. ማናቸውም በዚህ አንቀጽ መሠረት ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነጻ ሆኖ የገባ ዕቃ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በቅድሚያ ሳይፈቀድና ተገቢው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት አይሸጥም፡፡ ሆኖም ዕቃው ተመልሶ ከሀገር የሚወጣ ከሆነ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነጻ ይሆናል፡፡

76.<u>ስለባለፈቃዶች ምዝገባና ስለውክልና</u>

1. ማንኛውም ባለፈቃድ አግባብ ባለው ባለሥልጣን ዘንድ በንግድ መዝገብ ላይ የመመዝገብና ለፈቃዱ ዘመን በኢትዮጵያ ውስጥ ጽ/ቤት የማቋቋም ግዴታ አለበት፡፡
2. ባለፈቃዱ በፈቃዱ ላይ የተመለከቱትን ማዕድናት ለማምረት፣ ለመሸጥ ወይም ወደውጭ አገር ለመላክ ወይም ለሥራዎቹ አስፈላጊ የሆኑ ዕቃዎችን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት ወይም የአእምሮ ሥራዎችን በውል ለማግኘት ከሌላ የመንግስት መሥሪያ ቤት ፈቃድ አያስፈልገውም፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ የባለፈቃዱን የጉምሩክና የባንክ ፎርማሊቲዎች የማሟላት ግዴታ አያስቀርም፡፡

77.<u>ስለመንግሥት ድጋፍ</u>

1. መንግሥት፡-
   ሀ) የሀገሪቱን ወቅታዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመፍታት እገዛ ለሚደርጉ የማዕድን ሥራዎች፣
   ለ) ማዕድናትን በማበልጸግ በሀገር ውስጥ ተጠቃሚነትን ለሚያስፋፉ የማዕድን ሥራዎች፤ እና
   ሐ) በኅብረት ሥራ ማህበራት ለሚከናወኑ ባህላዊ የማዕድን ሥራዎች፤
   ማበረታቻና ድጋፍ ሊያደርግ ይችላል፡፡
2. የማበረታቻውና የድጋፉ ዓይነትና ሁኔታ የማዕድን ሥራውን መሠረት ያደረገ ሆኖ በደንብ ይወሰናል፡፡

**78.አለመግባባቶችን ስለመፍታት**

1. የማዕድን ቅኘት፣ ምርመራ፣ ይዞ መቆየት ወይም ማምረትን ከተመለከተ ስምምነት በመነጨ፣ በስምምነቱ አተረጓጎም፣ መጣስ ወይም መቋረጥ ምክንያት ወይም ከእነዚሁ ጋረ በተያያዙ ምክንያቶች በመንግስትና በባለፈቃድ መካከል የሚፈጠር ማንኛውም ክርክር፣ አለመግባባት ወይም የይገባኛል ጥያቄ በተቻለ መጠን በጋራ ውይይት ይፈታል፡፡
2. ጉዳዩ በጋራ ውይይት ሊፈታ ካልቻለ በስምምነቱ ውስጥ በተመለከተው ስነስርዓት መሰረት በግልግል ዳኝነት ታይቶ ይወሰናል፡፡ በግልግል ዳኝነት የሚሰጠው ውሳኔ በተዋዋይ ወገኖች ላይ የፀና ይሆናል፡፡[27]
3. በግልግል ዳኝነት በሚሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ወገን ቅሬታውን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ይግባኝ እንዲታይለት ማቅረብ ይቻላል፡፡

**79.ስለፈቃድ መብት መቋረጥ**

1. የፈቃድ መብት፡-

   ሀ) ባለፈቃዱ የፈቃዱን ክልል በሙሉ ሲለቅ ወይም የፈቃድ መብቱን ሲተው፤

   ለ) በዚህ አዋጅ፣ በደንቦችና በመመሪያዎች መሠረት ፈቃዱ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሲሰረዝ፤

   ሐ) የፈቃዱ ዘመን ከተፈጸመ በኋላ ሳይታደስ ሲቀር፣ ወይም

   መ) የወራሾች መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ባለፈቃዱ ሲሞት ወይም ባለፈቃዱ የንግድ ድርጅቱ ከሆነ ሲፈርስ ወይም የመክሰር ውሳኔ ሲሰጥበት፤

   ይቋረጣል፡፡
2. በስምምነት በሌላ ሁኔታ ካልተገለጸ በቀር የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ሲቋረጥ ለማዕድን ሥራዎች ጥቅም ላይ ውለው የእርጅና ቅናሻቸው ሙሉ በሙሉ ያልተፈጸመውን የማይንቀሳቀሱና ተንቀሳቃሽ ንብረቶች በባለፈቃዱ የሂሣብ መዝገብ ላይ በሚታየው ዋጋቸው መንግስት ሊወስዳቸው ይችላል፡፡ መንግስት በዚህ መብቱ ካልተጠቀመ ባለፈቃዱ አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠረት ንብረቶቹን ለሌላ ሰው ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡ ይህ የማይሆን ከሆነ ስለአካባቢው ጥበቃ በገባቸው ግዴታዎች መሠረት እንዲያስወግዳቸው ይገደዳል፡፡

[27]በ20/27 (2006) አ. 816 አንቀጽ 2 (28) ተሻሻለ፡፡

3. የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ የማዕድን መብት ሲቋረጥ በፈቃድና በኪራይ ተይዞ በነበረዉ ቦታ የሚገኙ ጉድጓዶችና ሌሎች ስራዎች በሰዎች ጤንነት፣ ሕይወትና ንብረት ላይ አደጋ እንዳያስከትሉ ፈቃድ ሰጪዉ ባለሥልጣን አጥጋቢ ነዉ ብሎ በሚቀበለዉ አኳኋን ባለፈቃዱ እንዲያጥራቸዉና መከላከያ እንዲያበጅላቸዉ ይገደዳል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 80.ቅጣት

ማንኛዉም ሰዉ፡-

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 67 መሠረት የተሰጠን ትዕዛዝ ከጣሰ ወይም ካላከበረ ወይም እንዲህ ያለ ትዕዛዝ መስጠቱንና በትዕዛዙም መሰረት ማዕድኑን መሸጥ የተከለከለ መሆኑን እያወቀ ማዕድን ከተቀበለ፤
2. ይህን አዋጅ፣ ደንብን፣ መመሪያን ወይም የፈቃድ ግዴታዎችን ከጣሰ ወይም ካላከበረ፤ ወይም
3. በዚህ አዋጅ፣ በደንብ ወይም በመመሪያ መሰረት መቅረብ ካለባቸዉ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ትክክል ያልሆነ ወይም የሚያሳስት መረጃ አቅርቦ ከተገኘ፤

እስከ ብር 200,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም እስከ አምስት አመት በሚደርስ እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

4. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (3) ድንጋጌ ቢኖርም ስለጥፋት ደረጃና ለእያንዳንዱ ደረጃ የሚገባዉ ቅጣት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

### 81.ስለቅሬታ አቀራረብ

1. በዚህ አዋጅ መሰረት በተሰጠ አስተዳደራዊ ዉሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛዉም ሰዉ ቅሬታዉን በየደረጃዉ ለሚገኙ የፈቃድ ሰጪዉ ባለስልጣን ኃላፊዎች ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ማንኛዉም ሰዉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት በተሰጠ አስተዳደራዊ ዉሳኔ ላይ ይግባኝ እንዲታይለት ለፍርድ ቤት ማቅረብ የሚችለዉ በፈቃድ ሰጪዉ ባለስልጣን ያሉ አስተዳደራዊ መፍትሔዎች በሙሉ ተሟጠዉ ካለቁ በኋላ ነዉ፡፡

82.**ስለአዋጁ አፈጻጸም**

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊይወጣ ይችላል፡፡
2. ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የወጡ ደንቦችን በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
3. ፈቃድ ሰጪዉ ባለሥልጣን ለድርድር መነሻ የሚሆን ሞዴል የማዕድን ስምምነት ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡
4. ይህ አዋጅ በስራ ላይ ከመዋሉ በፊት ለኢንደስተሪ ግብዓትነት የሚውሉ ወይም ከማጋጌጫ ድንጋዮች ውጪ ያሉ እንደ አሸዋ ፣ ጠጠር፣ ገረጋንቲ እና የመሳሰሉት የኮንስትራክሽን ማዕድናት እንዲሁም የደልል መዕድን ስራን በሚመለከት ለውጪ ባለሀብት የተሰጠ ፈቃድ ወይም ከውጪ ባለሀብት ጋር የተደረገ የማዕድን ማምረት ስምምነት ፀንቶ ለሚቆይበት ቀሪ ዘመን የፀና ይሆናል፡፡ ሆኖም የፈቃዱ ወይም የስምምነቱ ዘመን አብቅቶ ሲታደስ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሰረት ይፈፀማል፡፡[28]

83.**የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

1. ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተሰጠ ወይም የተደረገ ማንኛውም የማዕድን ማምረት ፈቃድ ወይም የማዕድን ማምረት ስምምነት ፀንቶ ለሚቆይበት ቀሪ ዘመን ፈቃዱ በተሰጠበት ወይም ስምምነቱ በተደረገበት ወቅት ተፈፃሚ በነበረው ህግ መሠረት ባለበት ይቀጥላል፡፡ ሆኖም የፈቃዱ ወይም የስምምነቱ ዘመን አብቅቶ ሲታደስ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ይፈፀማል፡፡[29]
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ ቢኖርም አንደኛዉ ወገን አግባብ ባለዉ ስምምነት ከሚያካሔደዉ የማዕድን ስራ በሚገኘዉ ጥቅም ላይ በዚህ አዋጅ ምክንያት ጉዳት የደረሰ እንደሆነ ጉዳት የደረሰበት ወገን ሲጠይቅ ሁለቱም ወገኖች በቅን ልቦና ተወያይተዉ አስፈላጊዉን ማስተካከያ ለማድረግ ሊስማሙ ይችላሉ፡፡

---

[28] በ26/63(2012) አ.1213 አንቀፅ 2(2) መሰረት ተሻሻለ፡፡
[29] በ20/27 (2006) አ. 816 አንቀጽ 2 (29) ተሻሻለ፡፡

3. ይህ አዋጅ በስራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተፈጠረ ለክስ መነሻ የሚሆን ጉዳይ ወይም የተጀመረ የክርክር ወይም የአፈጻጸም ሂደት ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ጸንተዉ በነበሩ ህጎች መሰረት ፍጻሜ ያገኛል፡፡

84.<u>የተሻሩና ጸንተዉ የሚቆዮ ህጎች</u>

1. የማዕድን አዋጅ ቁጥር 52/1985 /እንደሻሻለ/ በዚህ አዋጅ ተሸሯል፡፡
2. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማንኛዉም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተሸፈኑትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረዉም፡፡
3. የማዕድን ሥራዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 182/1985 ድንጋጌዎች የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እስካልተቃረኑ ድረስ በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣ ደንብ እስከሚተኩ ድረስ ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል፡፡

85.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ 28 ቀን 2002 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## ደንብ ቁጥር 182/1986 ዓ.ም

## ስለ ማዕድን ሥራዎች የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የጠቅላይ ሚኒስትርንና የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 2/1983 አንቀጽ 4 (2) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የማዕድን ሥራዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 182/1986" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ፣**[30]

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በቀር በዚህ ደንብ ውስጥ

   1. በማዕድን አዋጅ ቁጥር 52/1985[31] ለተዘረዘሩት ቃላት የተሰጡት ትርጓሜዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡
   2. "አነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ" ማለት ማንኛቸውንም ማዕድናትን በሚመለከት ከማዕድኑ ሥፍራ በአመት የሚመረተው ማዕድን አዘል አፈርና ድንጋይ መጠኑ ከሚከተለው የማይበልጥ ማዕድን የማምረት ሥራ ነው፡፡

      ሀ) እንደ ወርቅ፣ ፕላቲንየም፣ ብር እና ሌሎችም የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናትን በሚመለከት፣

      1) በደለል ላይ ለሚካሄዱ ሥራዎች እስከ 100,000 ሜትር ኩብ

      2) በጽንሰ ማዕድን ክምችቶች ላይ የሚካሄዱ ሥራዎች እስከ 75,000 ሺህ ቶን፣

      ለ) እንደ ብረት፣ እርሳስ፣ መዳብና ኒኬል የመሳሰሉ ሜታል ማዕድናትን በሚመለከት፡-

      1) በመሬት ላይ ለሚካሄዱ ሥራዎች እስከ 150,000 ቶን፤

---

[30] የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (5) እና (6) በማሻሻያ ደንብ ቁጥር 12/24 (1998) አ. 124 አንቀፅ 2(1) መሰረት የተጨመሩ ናቸው፡፡

[31] ይህ አዋጅ በ16/45 (2002) አ. 678 ተሽሯል በዚህ አዋጅ የተዘረዘሩ ትርጓሜዎች በሙሉ በሻሪው አዋጅ ላይ ተዘርዝረዋል፡፡

2) በመሬት ውስጥ ለሚካሄዱ ሥራዎች እስከ 75,000 ቶን

ሐ) እንደ ካኦሊን፣ ቤንቶናይት፣ ዳያቶማይት፣ ዶሎማይት፣ ኳርትዝ እና የድንጋይ ከሰል የመሳሰሉ የኢንዱስትሪ ማዕድናትን በሚመለከት እስከ 120,000 ቶን፣

መ) የኮንስትራክሽን ማዕድናትን በሚመለከት፣

1) አሸዋ፣ ጠጠር፣ ፑሚስ ድንጋይ፣ የሸክላ አፈርና የመሳሰሉትን በሚመለከት 80,000 ሜትር ኩብ፣

2) እብነበረድ ግራናይትና የመሳሰሉትን የዳይሜንሽን ድንጋዮች በሚመለከት እስከ 10,000 ሜትር ኩብ፣

ሠ) የማዕድን ውሃን በሚመለከት እስከ 20,000 ሜትር ኩብ፣

ረ) የጂኦተርማል ክምችትን በሚመለከት፣

1) ለመታጠቢያ፣ ለመዝናኛና ለሕክምና አገልግሎት እስከ 2 ሚሊዮን ሜትር ኩብ፣

2) ለኢንዱስትሪና ለሌሎች አገልግሎቶች እስከ 25 ሜጋዋት ወይም ተመጣጣኝ የሆነ ኃይል ሊሰጥ የሚችል የጂኦተርማል እንፋሎት፣

ሰ) ከድንጋይ ወይም ከብራይን ለሚመረቱ የጨው ዓይነቶች እስከ 14,000 ቶን፣

3. "ከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ" ማለት የከበሩ ወይም በከፊል የከበሩ ድንጋዮችን የማምረት ሥራን በሚመለከት ካልሆነ በቀር ከማዕድኑ ሥፍራ በዓመት የሚነሣው ማዕድን አዘል አፈርና ድንጋይ መጠን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ከተመለከተው መጠን በላይ የሆነ ማዕድናትን የማምረት ሥራ ነው፡፡

4. "አዋጅ" ማለት የማዕድን አዋጅ ቁጥር 52/1985 ነው፡፡[32]

5. "የኢንዱስትሪ ማዕድናት" ማለት በፋብሪካ ሥራ ሂደት አልፈው ጠርሙስ፣ ወረቀት፣ ሲሚንቶ፣ ማዳበሪያና ለምግብነት ወይም ለሌላ ዓላማ የሚውል ጨው የመሳሰሉ የፍጆታ ዕቃዎችን ለመፈብረክ በጥሬ ግብዓትነት ጥቅም ላይ የሚውሉና ለኃይል ማመንጫነት የሚያገለግሉ በተፈጥሮ የሚገኙ ጠጣር ማዕድናትን ሁሉ ያጠቃልላል፤

[32] ይህ አዋጅ በአዋጅ ቁጥር 678/2002 ተሽሯል፡፡

6. “በከፊል የከበሩ ማዕድናት” ማለት በአዋጁ አንቀጽ 2(18) የተመለከቱትን ሳይጨምር ሌሎች ማናቸውም በተፈጥሮአዊ ግኝታቸው ለማስዋቢያነት የሚውሉ ወጥ ወይም በተፈጥሮአዊ አንድነት የተጣመሩ እንደ ኦፓል፣ ሮዶላይት፣ ጋርኔትና ኦሊቪን የመሳሰሉ እንዲሁም ሚኒስቴሩ በመመሪያ በከፊል የከበሩ ማዕድናት ብሎ የሚሰይማቸው ሌሎች ተመሳሳይ ማዕድናት ናቸው፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለማዕድን ሥራ ፈቃዶች

### ምዕራፍ አንድ

### ስለፈቃድ ማመልከቻዎች

3. ለፍለጋ ፈቃድ ስለሚቀርብ ማመልከቻ

የፍለጋ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን ዝርዝሮች መያዝ አለበት፡፡

1. አመልካቹ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ፣
   ሀ) ሙሉ ስሙን ዜግነቱን የተወለደበት ጊዜና ቦታ፣
   ለ) ሙያውን፣
   ሐ) የመኖሪያ ቦታውንና አድራሻውን፣
2. አመልካቹ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ከሆነ፣
   ሀ) ስሙን ዜግነቱን የሕግ አቋሙንና ካፒታሉን፣
   ለ) የዋና መሥሪያ ቤቱን አድራሻ እና በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ወኪሉን ስምና አድራሻ፣
   ሐ) ትክክለኛነታቸው አግባብ ባለው የድርጅቱ ሹም ተረጋግጦ የሚቀርብ የሚከተሉት ሰነዶች፣
      1) ድርጅቱ የተቋቋመበት የመመሥረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ቅጂ፣
      2) የዲሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ሪፖርት ካለ የመጨረሻውን ሪፖርት ቅጂ፣
      3) ያለፉት ሶስት ዓመታት የሂሣብ ሚዛን፣ የትርፍና ኪሣራ መግለጫዎች እንዲሁም የኦዲተሮች ሪፖርቶች ካሉ የነዚህኑ ቅጂዎች፣
      4) የዲሬክተሮች ቦርድ ካለ የአባላቱን ስም፣ አድራሻና ዜግነት እንዲሁም በአመልካቹ ድርጅት ስም ለመፈረም ሥልጣን የተሰጠውን ሰው ስም፣

5) ፈቃድ የተጠየቀበትን የማዕድን ዓይነት እና ፍለጋው ሊካሄድ የታሰበበትን ሥፍራ የሚያሳይ በመመሪያ በሚወሰነው መሠረት የተዘጋጀ ካርታ፣
6) አመልካቹ ቀደም ሲል በኢትዮጵያ ውስጥ ተሰጥቶት የነበረ ፈቃድ ወይም የማዕድን መብት ካለ፣
7) የአመልካቹን የፋይናንስ ሁኔታ የቴክኒክ ብቃትና ልምድ የሚያሳይ መግለጫ፣
8) ፈቃዱ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ አመልካቹ ሊያከናውን ያሰበውን የሥራ ፕሮግራምና ሊያወጣ ያቀደውን የወጪ መጠን፣ እና
9) ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በአግባቡ ያስፈልጋሉ ብሎ የሚጠይቃቸውን ሌሎች መረጃዎች፡፡

4. <u>ለምርመራ ፈቃድ ስለሚቀርብ ማመልከቻ፣</u>

የምርመራ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፣

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 3 የተዘረዘሩትን መረጃዎች፣
2. አመልካቹ የምርመራ ፈቃድ ለመጠየቅ መሠረት ያደረገው የፍለጋ ፈቃድ ካለው የፈቃዱን መለያ፣
3. ፈቃድ ስለተጠየቀባቸው ማዕድናትና ሥፍራ በአመልካቹ የሚታወቅ የጂኦሎጂ መረጃ አጭር ዘገባ፣

5. <u>ለማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>

1. የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፣
   ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ 3 የዘረዘሩትን መረጃዎች፣
   ለ) አመልካቹ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ለመጠየቅ መሠረት ያደረገው የምርመራ ፈቃድ ካለው የፈቃዱን መለያ፣
   ሐ) ፈቃዱ ጸንቶ እንዲቆይ የሚፈለግበትን ጊዜ፣
   መ) የተረጋገጠውንና የሚገመተውን የክምችት መጠንና የማዕድናቱን ፊዚካል፣ ኬሚካል፣ ሚኖሮሎጂካል፣ ቴክኒካል ባሕርይ ጨምሮ የክምችቱን ዝርዝር ሁኔታ የሚገልጽ ጥናት፣

ሠ) ኦፊሴላዊ በሆነ የወሰን ቅየሳ ላይ ተመሥርቶ ፈቃዱ የተጠየቀበትን ሥፍራ ወሰኖች መታጠፊያ ጂኦግራፊያዊ ከኦርዲኔቶችና በእነሱም መካከል ያለውን ርቀት የሚያመለክትና ሥፍራውን ለመለየት የሚያስችሉ አቢይ ምልክቶችን ሕንፃዎች የመሬት አቀማመጥና ሌሎች ገጽታዎችን የሚያሳይ አግባብ ባለው መስፈርት የተሠራ ካርታ፣

ረ) ሊከናወን ስለታሰበው የልማትና ምርት ዕቅድ እና ሌሎችም ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ባግባቡ ያስፈልጋሉ ብሎ የሚጠይቃቸው መረጃዎች፡፡

2. የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተገለጹት በተጨማሪ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡፡

ሀ) የሽያጭ ገቢን የካፒታልና የሥራ ማስኬጃ ወጪን የእርጅናና ሌሎች ተቀናሾችን እንዲሁም የሚገመተውን ትርፍና የጥሬ ገንዘብ ፍሰት የሚያሳይ የተሟላ የፊዚቢሊቲ ጥናት፣

ለ) የቅጥርና የሥልጠና ፕሮግራም አጭር መግለጫ፣

ሐ) የሚያስፈልጉ የመሠረተ ልማት አውታሮች ዝርዝር፣

መ) ሥራው በተፈጥሮ አካባቢ ላይ ስለሚያስከትለው ተጽዕኖ የተደረገ ግምገማ ሪፖርት፣

3. ባሕላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፣

ሀ) የአመልካቹን ሙሉ ስም አድራሻ የተወለደበትን ጊዜና ቦታ፣

ለ) ፈቃድ የተጠየቀባቸው ማዕድናትና ሥፍራው፣

ሐ) ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በአግባቡ ያስፈልጋሉ ብሎ የሚጠይቃቸውን ሌሎች መረጃዎች፣

## ምዕራፍ ሁለት

## ስለፈቃድ አሰጣጥ

**6. ማመልከቻን ስለመመዝገብ ስለማስታወቅና ስለማጣራት፣[33]**

1. እያንዳንዱ የፈቃድ ማመልከቻ በትክክለኛው ፎርም ተሟልቶ ሲቀርብ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ለዚሁ ተግባር ባዘጋጀው መዝገብ ላይ እንደአቀራረቡ ቅደም ተከተል ወዲያውኑ ይመዘግባል፤ እያንዳንዱ አመልካችም የምዝገባ ቀንና ቁጥሩን የሚገልጽ ደረሰኝ ይሰጠዋል፡፡
2. ፈቃድ ሰጭው ባለስልጣን ፈቃድ ለማግኘት የቀረበውን ማመልከቻ ከመዘገበ በኋላ ወዲያውኑ በአመልካቹ የቀረቡትን መረጃዎች በሙሉ አጣርቶ ትክክለኛነታቸውን ያረጋግጣል፡፡
3. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የፈቃድ ማመልከቻዎችንና የተሰጡ ፈቃዶችን የሚያሳይ መዝገብ አዘጋጅቶ ለሕዝብ ክፍት ያደርጋል፡፡

**7. መቃወሚያዎችን ስለማቅረብ፣[34]**

1. ማናቸውም ሰው የተጠየቀው ፈቃድ እንዳይሰጥ ወይም የተሰጠ ፈቃድ እንዲታገድ ወይም እንዲሰረዝ መቃወሚያውን ከነምክንያቶቹ በጽሁፍ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን መቃወሚያው እንደደረሰው ወዲያውኑ መርምሮ ይወስናል፡፡

**8. ፈቃድን ስለመስጠትና ስለመመዝገብ፣**

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 (4) በተጠቀሰው የሠላሳ ቀን ጊዜ ውስጥ በማመልከቻው ላይ ምንም ዓይነት መቃወሚያ ካልቀረበ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በማመልከቻው የቀረቡለትን መረጃዎች ካጣራና አመልካቹ የተወሰነውን የፈቃድ ክፍያና የመሬት ኪራይ ከከፈለ በኋላ ማመልከቻው የቀረበበትን ሥፍራና ማዕድናት በተመለከተ ወይም ማመልከቻው ከቀረበበት ሥፍራና ማዕድናት ውስጥ በአዋጁ አንቀጽ 6 እና በዚህ ደንብ አንቀጽ 11 መሠረት ያልተያዘውን ወይም ያልተከለከለውን እና ቀደም

---

[33] የዚህ አንቀፅ ቀድሞ ንዑስ አንቀፅ (2)፣ (3) እና (4) ነበሩት በማሻሻያ በ12/24 (1998) ደ. 124 አንቀፅ 2(2) መሰረት ተሰርዘው አዲስ ንኡስ አንቀጾች (2) እና (3) ተጨምረዋል፡፡

[34] የዚህ አንቀፅ ቀድሞ ንዑስ አንቀፅ (2) እና (3) ነበሩት በ12/24 (1998) ደ. 124 አንቀፅ 2(3) መሰረት ተሰርዘው በአዲስ ተተክተዋል፡፡

ሲል ብቸኛ የሆነ መብት የሚያስገኝ ፈቃድ ያልተሰጠበትን ወይም ማመልከቻ ያልቀረበበትን ክፍል በሚመለከት ፈቃድ ይሰጣል፤ ሆኖም አመልካቹ፣

ሀ) የተጠየቀው ፈቃድ የሚያስከትላቸውን ግዴታዎች ለመወጣት የሚያስችል የፋይናንስ ምንጭ የቴክኒክ ችሎታና ልምድ እንዳለው ለፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ካላረጋገጠ፤ እና

ለ) እንደነገሩ ሁኔታ በፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ተቀባይነት ያገኘ የሥራ ፕሮግራምና የወጭ ወይም የልማትና የምርት ፕሮግራም ግዴታዎች አቅርቦ ወይም ስምምነት አድርጐ ካልሆነ በቀር፤ የፍለጋ፣ የምርመራ ወይም የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ አይሰጥም፡፡

2. በዚህ ደንብ አንቀጽ 7 መሠረት በማመልከቻው ላይ ተቃውሞ ከቀረበ ፈቃድ የመስጠቱ ሂደት ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ማመልከቻው ከተመዘገበ ከአንድ መቶ ሃያ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በተቃውሞው ላይ ውሳኔ እስከሚሰጥበት ድረስ ይዘገያል፡፡ የተሰጠው ውሳኔ ተቃውሞውን ውድቅ የሚያደርግ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካቹ ወዲያውኑ ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

3. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የፈቃድ ማመልከቻውን ከተቀበለውና ካጸደቀው ውሳኔውን ለዚሁ ጉዳይ በተዘጋጀው መዝገብ ላይ ያሰፍራል፡፡ አመልካቹም በመዝገቡ ላይ ይፈርማል፡፡

4. በአዋጁ አንቀጽ 46 (1) እንደተደነገገው የብሄራዊ ክልላዊ መስተዳድር የማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ ለባሕላዊ የማዕድን ማምረት ሥራዎች እና በሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ለሚካሄዱ ኮንስትራክሽን ማዕድናት ፈቃድ የመስጠት ሥልጣን የተሰጠው ሲሆን ሌሎች ማናቸውንም የማዕድን ሥራዎችን በተመለከተ ፈቃድ የሚሰጠው የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር ነው፡፡

9. <u>**ፈቃድን ስለመከልከል፣**</u>

1. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የቀረበው ማመልከቻ ወይም ተያይዞ የቀረበው መረጃ በቂ አይደለም ብሎ ከወሰነ ይህንኑ ከነምክንያቱ ለአመልካቹ ማሳወቅ አለበት፣

2. አመልካቹ የሚደግፉትን ማስረጃዎች ለማቅረብ እንዲችል ፈቃድ ሰጭውን ባለሥልጣን የማማከር ዕድልና የቀረበበትን ተቃውሞ ለመቋቋም ከሠላሳ ቀን ያላነሰ ጊዜ ይሰጠዋል እንዲሁም ማመልከቻውን የማረም ወይም የማሟላት መብት ይኖረዋል፡፡
3. አመልካቹ የፈቃድ ሰጭውን ባለሥልጣን ምክር ካገኘና የተሰጠው ጊዜ ካለፈም በኋላ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ማመልከቻው ወይም የቀረበው መረጃ ወይም የአመልካቹ ችሎታ የጠየቀውን ፈቃድ ለመስጠት የማያበቃ መሆኑን ሲያምንበት ይህንኑ ለአመልካቹ ያሳውቀዋል፡፡
4. አመልካቹ ፈቃዱን በመከልከሉ ምክንያት የሚያነሳው ክርክር በዚህ ደንብ አንቀጽ 44 (2)መሠረት እንዲታይለት የማድረግ መብት ይኖረዋል፡፡

10.<u>ስለፈቃድ ክልሎች ስፋት፣</u>

1. በአንድ ፈቃድ ሊያዝ የሚችለው ክልል ስፋት ጣሪያ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡
   ሀ) ለፍለጋ ፈቃድ 50 ካሬ ኪሎ ሜትር
   ለ) ለምርመራ ፈቃድ 20 ካሬ ኪሎ ሜትር
   ሐ) ለባሕላዊ የማዕድን ሥራ ፈቃዶች 5000 ካሬ ሜትር
   መ) ለአነስተኛ ደረጃ የኢንዱስትሪያልና የኮንስትራክሽን ማዕድናት ማምረት ሥራ ፈቃድ 20,000 ካሬ ሜትር፣
   ሠ) ለከፍተኛ ደረጃ የኢንዱስትሪያልና ኮንስትራክሽን ማዕድናት ማምረት ሥራ ፈቃድ 200,000 ካሬ ሜትር፣
   ረ) ለሌሎች ማዕድናት ማምረት ሥራ ፈቃዶች 10 ካሬ ኪሎ ሜትር፣
2. የባሕላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ በአንድ ጊዜ በጠቅላላ ስፋቱ ከ10,000 ካሬ ሜትር የበለጠ ከሁለት በላይ ፈቃድ ሊይዝ አይችልም፡፡
3. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ በዚህ አንቀጽ የተመለከተውን የፈቃድ ክልል ስፋት ሊያሻሽለውና በአንድ ፈቃድ ሊያዝ የሚችለውንም የክልል ስፋት ጣሪያና ዝቅተኛ መጠን ሊወስን ይችላል፡፡

11.<u>ስለተከለከሉ ሥፍራዎች፣</u>

1. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በሌላ አኳኋን ካልፈቀደ በስተቀር በአርኪዎሎጂ ሥፍራዎች የባሕል ወይም የኃይማኖት መንፈሳዊ ክብር በተሰጣቸው ሥፍራዎች በሕዝብ አገልግሎት ሕንጻዎች፣ በባቡር ሃዲዶች፣ በአውራ ጐዳናዎች፣ አውሮፕላን

ማረፊያዎች፣ በግድቦች፣ በውሃ ማጠራቀሚያዎች፣ በቧንቧ መስመሮች፣ በፋብሪካዎች ወይም ሌሎች መንግሥታዊ ተቋሞች አካባቢ በ100 ሜትር ክልል ውስጥ ፈቃድ አይሰጥም፡፡

2. በፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በተለይ ካልተፈቀደ በቀር ማንኛውም ሰው በከተማ ክልል በገጠር መንደሮች፣ በመቃብር ሥፍራ ወይም በወቅቱ ሰብል ባለበት የእርሻ ቦታ በ100 ሜትር ክልል ውስጥ የማዕድን ፍለጋ ማካሄድ አይችልም፡፡

3. በማናቸውም ሌላ ሕግ በተከለከሉ ሥፍራዎች የማዕድን ሥራዎትን ማካሄድ አይቻልም፡፡

12. <u>ስለተጣመረ ፈቃድ፣</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 34 መሠረት የተጣመረ ፈቃድ እንዲሰጠው የሚጠይቅ አመልካች ለእያንዳንዱ ፈቃድ አስፈላጊ የሆኑትን የማመልከቻ ግዴታዎች ማሟላትና የተጣመረ ፈቃድ እንዲሰጠው የጠየቀበትን ምክንያት ማስረዳት አለበት፡፡

2. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን አመልካቹ ለእያንዳንዱ ፈቃድ መሟላት ያለበትን ግዴታ ማሟላቱን የተጣመረ ፈቃድ እንዲሰጠው ያቀረበው ምክንያት አጥጋቢ መሆኑን እና የማዕድኑን ክምችት ለማልማትና ለማምረት ችግር የማይፈጥር መሆኑን ሲያምንበት የተጣመረውን ፈቃድ ይሰጣል፡፡

13. <u>የፈቃድ ቅጂ ስለመስጠትና ስለመተካት፣</u>

1. ባለፈቃዱ የፈቃዱን አንድ ወይም ተጨማሪ ቅጂ እንዲሰጠው ፈቃድ ሰጭውን ባለሥልጣን ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣንም ጥያቄው ሲደርሰው የፈቃዱን የተረጋገጠ ቅጂ አዘጋጅቶ ይሰጠዋል፡፡

2. ፈቃድ የጠፋበት ወይም የተበላሸበት ባለፈቃድ ፈቃዱ እንዲተካለት ለፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ሊያመለክት ይችላል፡፡ ጥያቄው የቀረበለት ፈቃድ ሰጭ ባለሥልጣንም ምትክ ፈቃድ አዘጋጅቶ ለባለፈቃዱ ይሰጠዋል፡፡

<u>ምዕራፍ ሶስት</u>

<u>ፈቃዶችን ስለማደስ፣ ስለማስተላለፍና ስለመሰረዝ</u>

14. <u>ስለ ምርመራ ፈቃድ ዕድሳት</u>

1. የምርመራ ፈቃድን ለማሳደስ የሚቀርብ ማመልከቻ የፈቃዱ ዘመን ከመፈጸሙ ከዘጠና ቀናት በፊት መቅረብና የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡፡

ሀ) ፈቃዱ መጀመሪያ ሲሰጥ ወይም ባለፈው ዕድሳት ወቅት በቀረቡ መረጃዎች ላይ የተደረጉ ለውጦች፣

ለ) በመመሪያ የሚወሰኑ መረጃዎችን ያካተተ ዓመታዊ ሪፖርት፣

ሐ) አመልካቹ በዕደሳው ዘመን ሊያከናውን ያሰበውን የሥራ ፕሮግራምና ያቀደውን ወጭ የሚያሳይ ዝርዝር፣

መ) በአዋጁ አንቀጽ 11 መሠረት ከፈቃዱ ክልል ላይ የሚለቀውን ሥፍራ፣

ሠ) ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በአግባቡ ያስፈልጋሉ ብሎ የሚጠይቃቸውን ሌሎች መረጃዎች፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(መ) የተጠቀሰው የሚለቀቅ ሥፍራ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በሌላ አኳኋን ካልተስማማ በቀር በመመሪያ በሚገለፀው መሠረት በብሎክ በብሎክ ሆኖ እያንዳንዱ ብሎክ ከአንድ እስኩዌር ኪሎ ሜትር ያላነሰና ቀላል ጂኦሜትራዊ ቅርፅ ያለው መሆን አለበት፡፡

3. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በማመልከቻው የቀረቡለትን መረጃዎች ካጣራና አመልካቹ የተወሰነውን የፈቃድ ማሳደሻ ክፍያና የመሬት ኪራይ ከከፈለ በኋላ በአዋጁ አንቀጽ 10 (1) እና (2) መሠረት ፈቃዱን ያድስለታል፡፡

## 15.ስለባህላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ዕድሳት፣

1. ባህላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድን ለማሳደስ የሚቀርብ ማመልከቻ የፈቃዱ ዘመን ከመፈጸሙ ከሠላሳ ቀናት በፊት መቅረብና የሚከተሉትን መያዝ አለበት፣

ሀ) ፈቃዱ መጀመሪያ ሲሰጥ ወይም ባለፈው ዕድሳት ወቅት በቀረቡ መረጃዎች ላይ የተደረጉ ለውጦች፣

ለ) ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በአግባቡ ያስፈልጋሉ ብሎ የሚጠይቃቸውን ሌሎች መረጃዎች፣

2. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በማመልከቻው የቀረቡለትን መረጃዎች ካጣራና አመልካቹ የተወሰነውን የፈቃድ ማሳደሻ ክፍያና የመሬት ኪራይ ከከፈለ በኋላ በአዋጁ አንቀጽ 15 (1) መሠረት ፈቃዱን ያድስለታል፡፡

## 16.ስለአነስተኛና ከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃዶች ዕድሳት

1. የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድን ለማሳደስ የሚቀርብ ማመልከቻ የፈቃዱ ዘመን ከመፈጸሙ ከመቶ ሰማንያ ቀናት በፊት መቅረብና የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡፡

ሀ) ፈቃዱ መጀመሪያ ሲሰጥ ወይም ባለፈው ዕድሳት ወቅት በቀረቡ መረጃዎች ላይ የተደረጉ ለውጦች፤

ለ) ዕቅዱን ጨምሮ የተረጋገጠውንና ይኖራል ተብሎ የሚገመተውን ቀሪውን የማዕድን ክምችት ዝርዝር ሁኔታ የሚያሳይ ሪፖርት፤

ሐ) ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በአግባቡ ያስፈልጋሉ ብሎ የሚጠይቃቸውን ሌሎች መረጃዎች፡፡

2. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ከማመልከቻው ጋር ተያይዘው የቀረቡትን መረጃዎች ካጣራና አመልካቹ የተወሰነውን የፈቃድ ማሳደሻ ክፍያና የመሬት ኪራይ ከከፈለ በኋላ እንደሁኔታው በአዋጁ አንቀጽ 17 ወይም 19 መሠረት ፈቃዱን ያድስለታል፡፡

17.<u>ስለፈቃድ ማስተላለፍ፣ መዳረግ፣ በዕዳ ማስያዝና ስለውርስ፤</u>

1. የምርመራ ፈቃድንና የባለፈቃዱን የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ የማግኘት መብት በአዋጁ አንቀጽ 9 (3) መሠረት ለማስተላለፍ ወይም ለመዳረግ የሚቀርብ ማመልከቻ እንዲሁም የአነስተኛ ደረጃ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድን በአዋጁ አንቀጽ 16 (2) ወይም 18(2) መሠረት ለማስተላለፍ ወይም ለመዳረግ የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡፡

ሀ) ፈቃዱ ሊተላለፍለት ወይም ሊደረግለት የተፈለገውን ሰው በተመለከተ በዚህ ደንብ አንቀጽ 3 የተዘረዘሩትን መረጃዎች፤

ለ) ፈቃዱ ሊተላለፍለት ወይም ሊዳረግለት የተፈለገው ሰው የፈቃዱን ስምምነቶችና ግዴታዎች እንዲሁም አግባብ ያለው የሥራ ፕሮግራምና ወጭ ወይም የልማትና የምርት ፕሮግራምና የባለፈቃዱን ሌሎች ግዴታዎችን አክብሮ ለመፈጸም ግዴታ መግባቱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ፣

ሐ) የታሰበውን ማስተላለፍ ወይም መዳረግ የሚመለከቱ የውል፣ የኢኮኖሚና የፋይናንስ ነክ ስምምነቶችና ግዴታዎች ዝርዝር፣

2. የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድን በአዋጁ አንቀጽ 16(2) ወይም 18(2) መሠረት በዕዳ ለማስያዝ የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፣

ሀ) የመያዣው ተጠቃሚ እንዲሆን የተፈለገውን ሰው በተመለከተ በዚህ ደንብ አንቀጽ 3 የተዘረዘሩትን መረጃዎች፤

ለ) ሊሰጥ የታሰበው የዋስትና ዓይነትና የዋስትናው ስምምነቶችና ግዴታዎች፤

ሐ) ፈቃዱን በመጨረሻ የሚረከበውን ሰው የፋይናንስና የቴክኒክ ችሎታ እንዲሁም የፈቃዱን ስምምነቶችና ግዴታዎች፣ የልማትና የምርት ፕሮግራምና የባለፈቃዱን ሌሎች ግዴታዎችን አክብሮ ለመፈጸም የገባውን ግዴታ ለማረጋገጥ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የሚጠይቃቸውን መተማመኛዎች ጨምሮ ሊሰጥ የታሰበው ዋስትና ተግባራዊ ሊደረግ የሚችልባቸውን ሁኔታዎች፡፡

3. የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድን በአዋጁ አንቀጽ 16 (2) ወይም 18 (2) መሠረት በውርስ ለማስተላለፍ የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡፡

ሀ) የባለፈቃዱ ወራሽ መሆንን ለማረጋገጥ የተሰጠ የፍርድ ቤት ማስረጃና ወራሾችን በተመለከተ በዚህ ደንብ አንቀጽ 3 የተዘረዘሩትን መረጃዎች፣

ለ) የአመልካቹን የፋይናንስ አቋም፣ የቴክኒክ ችሎታና ልምድ በዝርዝር የያዘ መግለጫ፣

ሐ) ወራሾች የፈቃዱን ስምምነቶችና ግዴታዎች፣ የልማትና የምርት ፕሮግራምና የባለፈቃዱን ሌሎች ግዴታዎችን አክብረው ለመፈጸም የገቡትን ግዴታ፡፡

4. በአዋጁ አንቀጽ 14 (2) መሠረት፣

ሀ) ባህላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድን ለማስተላለፍ፣ ለመዳረግ ወይም በዕዳ ለማስያዝ የሚቀርብ ማመልከቻ ፈቃዱ ሊተላለፍለት፣ ሊዳረግለት ወይም የመያዣው ተጠቃሚ እንዲሆን የተፈለገውን ሰው በተመለከተ በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 (3) የተዘረዘሩትን መረጃዎች መያዝ አለበት፣

ለ) ባህላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድን በውርስ ለማስተላለፍ የሚቀርብ ማመልከቻ የባለፈቃዱ ወራሽ መሆንን ለማረጋገጥ የተሰጠ የፍርድ ቤት ማስረጃና ወራሾችን በተመለከተ በዚህ ደንብ አንቀጽ 5(3) የተዘረዘሩትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡፡

18. <u>ፈቃድን ስለመዘረዝና ስለማገድ፣</u>

1. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ባለፈቃዱ ጥፋት በመፈጸሙ ምክንያት በዚህ ደንብ አንቀጽ 40 በተደነገገው መሠረት ማንኛውንም ፈቃድ ሊሠርዝ ወይም ሊያግድ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተመለከተው በተጨማሪ ባህላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ በአዋጁ አንቀጽ 15 (2) መሠረት ሊሠረዝ ይችላል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለ ግኝት

### 19.ግኝትን ስለማስታወቅ፣

1. ማንኛውም ማዕድን ወይም የማዕድን ክምችት ያገኘ ሰው ወዲያውኑ እንደ ሁኔታው በግኝቱ ቦታ ላይ ምልክት ማኖር ወይም ክምችቱ ቦታ ላይ ምልክት ማኖር ወይም ክምችቱ ይገኝበታል ተብሎ የሚገመተውን ሥፍራ ምልክት በማድረግ መከለል አለበት፡፡ እያንዳንዱ ምልክት ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በሚወስነው ዓይነትና ቅርጽ ሆኖ የአግኝውን ስም መያዝ አለበት፡፡
2. ማዕድናትን ወይም የማዕድናትን ክምችት ያገኘ ማንኛውም ሰው የግኝቱን ቦታና ባህርይ የሚያሳይ የግኝት ማስታወቂያና የተገኘውን ማዕድን ናሙና ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት፡፡
3. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የግኝት ማስታወቂያ ላቀረበው ሰው እንዳግባቡ ሽልማት እንዲሰጠው ሊያደርግ ይችላል፡፡

### 20.ስለማጣራትና ስለምስክር ወረቀት፣

1. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የግኝት ማስታወቂያው እንደደረሰው የቀረቡለትን የማዕድን ናሙናዎች ባህርይና አግኝው ምልክት ያደረገበትን ሥፍራ ማጣራት እና ሥፍራውና ማዕድናቱ ብቸኛ የሆነ መብት የሚያስገኝ ፈቃድ ቀደም ሲል ያልተሰጠባቸው ወይም የፈቃድ ማመልከቻ ያልቀረበባቸው መሆኑን ወይም የግኝቱ ሥፍራ ያልተያዘ ወይም ያልተከለከለ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡
2. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ግኝቱን ካጣራና የግኝቱ ሥፍራና ማዕድናቱ የፈቃድ ማመልከቻ ሊቀርብባቸው የሚችሉ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለ12 ወራት ጸንቶ የሚቆይ የግኝት የምስክር ወረቀት ለአግኝው ይሰጣል፡፡

### 21.የግኝት የምስክር ወረቀት ባለይዞታ መብት እና ግዴታ

1. የግኝት የምስክር ወረቀት ባለይዞታ የሆነ ሰው፣ የምስክር ወረቀቱ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ፈቃድ እንዲሰጠው ካመለከተና ለፈቃድ ማመልከቻ የሚጠየቁ ሁኔታዎችን ካሟላ እንደሁኔታው የምርመራ እና ወይም የማምረት ሥራዎችን

ለማከናወን የሚያስችል የፋይናንስና የቴክኒክ ችሎታ ያለው ከሆነ ምርመራ ወይም የማምረት ወይም ምርመራና ማምረትን ያጣመረ ፈቃድ የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡

2. አግኚው የግኝት የምስክር ወረቀቱ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ የተገኘውን ማዕድን ወይም ክምችት በተመለከተ የፍለጋ ሥራ ማከናወን ይችላል፣ ሆኖም በዚህ ጊዜ ውስጥ የምርመራ ተግባር ማከናወንም ሆነ ማዕድኑን ማውጣት ወይም ማስተላለፍ አይችልም፡፡

## ክፍል አራት

## የባለፈቃዶች መብትና ግዴታ

## ምዕራፍ አንድ

## መብቶች

### 22.ስለ መሠረተ ልማት አውታሮችና ስለሌሎች ግንባታዎች

1. በባለፈቃዱ የሚሠሩ የመሠረተ ልማት አውታሮችና ሌሎች ግንባታዎች ተገቢ የሆነ ዲዛይንና የቴክኒክ አሠራር መከተልና አግባብ ባለሙ መመሪያ መሠረት ደኅንነቱ የተጠበቀና ቀልጣፋ አገልግለት ሊሰጡ በሚችሉበት አኳኋን መገንባት መጠገንና በጥቅም ላይ መዋል አለባቸው፡፡
2. ባለፈቃዱ የሠራቸው የመሠረተ ልማት አውታሮች ለንግድ ዓላማ ለሌሎች ባለፈቃዶችም አገልግሎት የሚሰጡ ከሆነ የመሠረተ ልማት አውታሮቹን ለመገንባትና ለማካሄድ የሚወጣው ወጭ በተጠቃሚዎች መካከል እንዲከፋፈል ባለፈቃዱ ፈቃድ ሰጭውን ባለሥልጣን ሊጠይቅ ይችላል፡፡
3. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የእያንዳንዱን ተጠቃሚ የግልጋሎት ድርሻ መሠረት በማድረግ ወጭውን ያከፋፍላል፡፡ በተጠቃሚዎች መካከል የሚከፋፈለው ወጭም የመሠረተ ልማት አውታሮቹ ዓመታዊ የእርጅና ቅናሽ የሥራ ማስኬጃና የጥገና ወጭዎች ጠቅላላ ድምር ይሆናል፡፡ ዓመታዊ የእርጅና ቅናሽ የሚሰላው ገና ተቀናሽ ያልሆነውን የመሠረተ ልማት አውታሮቹ የካፒታል ወጭ ለባለፈቃዱ ቀሪ የፈቃድ ዘመን ዓመታት በማካፈል ይሆናል፡፡

23.<u>በፍለጋና በምርመራ ወቅት በተገኙ ማዕድናት ላይ ስለማዘዝ</u>

1. የፍለጋ ወይም የምርመራ ፈቃድ ባለይዞታ በፍለጋው ወይም በምርመራው ወቅት ያገናቸውን ማዕድናት ይዞ ለመቆየት ወይም ሊያዝባቸው ከፈለገ ይህንኑ ለፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ማመልከት ይችላል፡፡
2. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን አስፈላጊ በመሰለው ሁኔታ ማዕድናቱ ከፈቃዱ ቦታ እንዲነሱና አመልካቹ የተወሰነውን ክፍያ ወይም ሮያልቲ ከፍሎ ይዟቸው እንዲቆይ ወይም እንዲያዝባቸው ሊፈቅድ ይችላል፡፡

24.<u>ስለአየር ላይ ፎቶግራፎችና መረጃዎች፣</u>

1. ማንኛውም ባለፈቃድ በቅድሚያ ፈቃድ ሰጭውን ባለሥልጣንና ከፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በሚያገኘው መረጃ መሠረት የሚመለከተውን መንግሥታዊ አካል በማስፈቀድ ከአየር ላይ ፎቶግራፎችን ማንሳት ይችላል፡፡
2. ባለፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ያነሳቸውን የአየር ላይ ፎቶግራፎች ቅጂ ለፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን መስጠት አለበት፡፡
3. ማንኛውም ባለፈቃድ በፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ዘንድ የሚገኙ ምስጢር ያልሆኑ ካርታዎችንና መረጃዎችን የማየት መብት ይኖረዋል፡፡

<u>ምዕራፍ ሁለት</u>

<u>ግዴታዎች</u>

25.<u>ወሰን ስለመከለል፣</u>

1. የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ማመልከቻ ያቀረበ አመልካች ፈቃድ የተጠየቀበትን ሥፍራ በቅድሚያ መከለል አለበት፡፡ የመከለሉ ተግባር በእያንዳንዱ የወሰኑ መታጠፊያና የቀጥታ መስመር ክፍልፋይ ላይ ምልክት በማድረግ ይከናወናል፡፡
2. በወሰኑ መታጠፊያዎች ላይ የሚደረጉ ምልክቶች ዲያሜትራቸው ከ25 ሴንቲ ሜትር የማያንስ የተጠረቡ ድንጋዮች፣ ብረቶች ወይም የመሳሰሉት መሆን አለባቸው፡፡ በወሰኑ ቀጥታ መስመር ክፍልፋዮች ላይ የሚደረጉ ምልክቶች ዲያሜትራቸው ከ10 ሴንቲ ሜትር የማያንስ የተጠረቡ ድንጋዮች፣ ብረቶች ወይም የመሳሰሉት መሆን አለባቸው፡፡ ማንኛውም ምልክት ከፍታው ቢያንስ ከመሬት አንድ ሜትር ሆኖ መሬት ላይ በደንብ መቸከል አለበት፡፡

3. በእያንዳንዱ ምልክት ላይ የአመልካቹ ስምና በኋላም የፈቃድ ቁጥሩን የሚገልጽ ምልክት መለጠፍ አለበት፡፡
4. ባለፈቃዱ የፈቃድ ክልሉ ወሰን በአዋጁ አንቀጽ 11 ወይም 31 መሠት የሚደረጉ ለውጦችን እንዲያንጸባርቅ አድርጐ መከለልና ምልክቶቹ ለውጡን እንዲያሳዩ አድርጐ ማስተካከል አለበት፡፡
5. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የፈቃድ ማመልከቻ የቀረበበትን ወይም ፈቃድ የተሰጠበትን ሥፍራ ወሰን አከላለል ለዚሁ ተግባር በተመደበ የፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ሠራተኛ እንዲመረመርና ወሰኑም በመንግሥት ቀያሽ እንዲረጋገጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡
6. እንደነገሩ ሁኔታ አመልካቹ ወይም ባለፈቃዱ የክልሉን ወሰን በማረጋገጥ ረገድ ለፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ሠራተኛ ወይም ለቀያሹ ድጋፍ መስጠት አለበት፡፡
7. ቀያሹ የተከለለው ወሰን በቀረበው ማመልከቻ ወይም በፈቃዱ ላይ የተገለጸውን ሥፍራ በትክክል የማያሳይ መሆኑን ሲያረጋግጥ ወሰኑ በዚሁ መሠት መስተካከልና ለቅየሳው የወጣው ወጭ በአመልካቹ ወይም በባለ ፈቃዱ መከፈል አለበት፡፡

26.<u>ስለሥራ ፕሮግራምና ስለወጭዎች፣</u>

1. ለፍለጋ ወይም ለምርመራ ፈቃድ ያመለከተ ሰው የሚያቀርበው የሥራ ፕሮግራምና የወጭ ዝርዝር ማመልከቻ የቀረበበትን ሥፍራ፣ የማዕድናቱን ዓይነት፣ ሊከናወን የሚችለውን ሥራ ባህርይና ሊኖር የሚችለውን ክምችት በማገናዘብ ተገቢ ከሚሆነው የሥራ መጠን ጋር ተመጣጣኝ መሆንና በመመሪያ የሚወሰነውን ዝቅተኛ የሥራ ፕሮግራምና የወጭ ግዴታ የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡
2. የቀረበው የሥራ ፕሮግራምና የወጭ ዝርዝር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጹትን ሁኔታዎች የሚያሟላ ከሆነ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ያፀድቀዋል፡፡ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የነበረው የሥራ ፕሮግራምና የወጭ ዝርዝር በቂ ሆኖ ካላገኘው ለአስተያየቱ መሠረት የሆኑትን ምክንያቶች በመግለጽ አመልካቹ ፕሮግራሙንና የወጭ ዘርዝሩን እንዲያስተካክል ያስታውቀዋል፡፡
3. ባለፈቃዱ በማንኛውም ዓመት የሚፈለግበትን ዝቅተኛ የሥራ ፕሮግራምና የወጪ ግዴታ ካላሟላ ከጉድለቱ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ገንዘብ ወዲያውኑ ለመንግሥት ተከፋይ ያደርጋል፡፡ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣንም ይህንኑ ገንዘብ ባለፈቃዱ ካቀረበው ዋስትና ላይ ሊወስድ ይችላል፡፡

4. ባለፈቃዱ በማንኛውም ዓመት ሊያከናውን ግዴታ ከገባው ሥራ በላይ ካከናወነ ወይም ወጪ ካወጣ ከግዴታው በላይ የፈጸመው ሥራ ወይም ያወጣው ወጪ በሚቀጥለው ዓመት በስምምነት የተወሰነውን ዝቅተኛ የሥራ ፕሮግራምና የወጪ ግዴታ ከፈጸመና አግባብነት ሲኖረው በዚሁ በሚቀጥለው ዓመት ግዴታው ላይ ታሳቢ ይደረግለታል፡፡

27.<u>ስለልማትና ምርት ፕሮግራም</u>

1. የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ እንዲሰጠው ባመለከተ ሰው የሚቀርብ የልማትና የምርት ፕሮግራም አመልካቹ ሥራውን እንዴት እንደሚያደራጅና ክምችቱን እንደሚያወጣ በዝርዝር መግለጽ አለበት፡፡
2. ሥራው በተለየ መንገድ እንዲካሄድ የሚያደርግ ምክንያት ኖሮ በቅድሚያ በፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ካልተፈቀደ በስተቀር የልማትና የምርት ፕሮግራሙ በአዋጁ አንቀጽ 26 ከተገለጹት ዓላማዎች ጋር የሚጣጣም መሆን፣ እንዲሁም ከክምችቱ ባህርይና ሁኔታ ከታቀዱ የገበያ ሁኔታዎችና ከሌሎች ኢኮኖሚያዊና ቴክኒካዊ ሁኔታዎች በተጣጣመ መንገድ ማዕድናቱን በከፍተኛ ደረጃ ለማልማትና ለማምረት የሚያስችል መሆን አለበት፡፡
3. የልማትና የምርት ፕሮግራሙ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተገለጸውን የሚያሟላ ከሆነ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ያጸድቀዋል፡፡ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ከጉዳዩ ጋር አግባብ ያላቸውን ሁኔታዎች በሙሉ ግምት ውስጥ በማስገባት ፕሮግራሙ አጥጋቢ አይደለም ብሎ ሲያምን ለአስተያየቱ መሠረት የሆኑትን ምክንያቶች በመግለጽ አመልካቹ ፕሮግራሙን እንዲያስተካክል ያስታውቀዋል፡፡

28.<u>ስለቅጥርና ሥልጠና፣</u>

1. ባለፈቃዱ ቅጥርን በተመለተ በአዋጁ አንቀጽ 27(1) እንደተደነገገው ለኢትዮጵያ ዜጎች ቅድሚያ መስጠት አለበት፡፡ አንድን የሥራ ቦታ ለመሙላት ብቁ የሆነ ኢትዮጵያዊ ካልተገኘ ብቁ የሆነ የውጭ አገር ዜጋ ሊቀጥር ይችላል፡፡ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የሚቀጠሩት የውጭ አገር ዜጎችና ቤተሰቦቻቸው ወደ አገር ውስጥ የመግቢያና የመኖሪያ ፈቃድ ከመንግሥት የሚያገኙበትን ሁኔታ በማመቻቸት ረገድ ባለፈቃዱን ይረዳል፡፡
2. የሠራተኛ ቅጥርና ሥልጠና ከሥራው ባህርይና ደረጃ ጋር የተጣጣመ እንዲሁም ሥራው በተቀላጠፈና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ እንዳይካሄድ የማያደናቅፍ መሆን አለበት፡፡

3. የምርመራ ፈቃድ ባለይዞታ የሆነ ሰው በየዓመቱ እያንዳንዱ ዘመን ከማለቁ ከሠላሳ ቀናት በፊት የሚቀጥለውን ዓመት የቅጥርና የሥልጠና ፕሮግራም ለፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት፡፡ የቅጥርና የሥልጠና ፕሮግራሙ በስምምነት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር በመሠረቱ ስፋት ያለው አይሆንም፡፡
4. የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ባለይዞታ የሆነ ሰው በየዓመቱ ዘመኑ ከማለቁ ከስልሳ ቀናት በፊት የሚቀጥለውን ዓመት የቅጥርና የሥልጠና ፕሮግራም ለፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ያቀርባል፡፡
5. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት የቀረበው ፕሮግራም በቂ አይደለም ብሎ ሲያምን፣ ባለፈቃዱ ፕሮግራሙን እንዲያስተካክል ለአስተያየቱ መሠረት የሆኑትን ምክንያቶች በመግለጽ ፕሮግራሙ በደረሰው በሠላሳ ቀናት ውስጥ ለባለፈቃዱ ያስታውቀዋል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚቀርብ የቅጥርና የሥልጠና ፕሮግራም ሠራተኞችን ያልሰለጠኑ፣ የሰለጠኑ የጽሕፈት፣ የቴክኒክና የአስተዳደር ሠራተኞች በሚል ምድብ ከፋፍሎ በዝርዝር ማሳየት አለበት፡፡

29.<u>ስለጤንነት፣ ደኅንነትና የተፈጥሮ አካባቢ ጥበቃ</u>

1. ማንኛውም ባለፈቃድ ለወኪሎቹና ለሠራተኞቹ ተገቢ የሆኑ የሥራ ልብሶችንና የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎችን ማቅረብ እንዲሁም ተገቢውን ሥልጠና ያገኙ መሆናቸውን ወይም በሌላ አኳኋን ለሥራው ብቁ ሆነው መገኘታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡
2. ባለፈቃዱ ከሥራው ባህርይና ደረጃ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የጤናና የሕክምና አገልግሎት ማቅረብና ለሥራው የሚያስፈልጉ ፈንጂዎችና ኬሚካሎች አደጋ በማያደርሱና ጥንቃቄ በተሞላበት አኳኋን እንዲጓዙ፣ እንዲከማቹ፣ እንዲያዙና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሥነ ሥርዓቶችን መከተል አለበት፡፡
3. ባለፈቃዱ በማንኛውም ሰው ላይ የሞት ወይም ከባድ የአካል ጉዳት ያደረሰ ወይም በማናቸውም ንብረት፣ በተፈጥሮ አካባቢ ወይም በማዕድን ሥራው ላይ ጉዳት የሚያስከትል ድርጊት ወይም ሁኔታ ሲከሰት ወዲያውኑ ለፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ማሳወቅና ሁኔታው የሚያስከትለውን ተጽዕኖ ለመቀነስ የሚያስፈልጉትን እርምጃዎች መውሰድ አለበት፡፡

4. የፈቃድ ዘመን ከመፈጸሙ ወይም ከመቋረጡ በፊት ባለፈቃዱ ጉድጓዶችን፣ ቦዮችንና ሌሎች አደጋ ሊያደርሱ የሚችሉ ሥራዎችን መሙላት፣ መዝጋት ማጠር ወይም በሌላ በማናቸውም ዘዴ አደጋ ሊያደርሱ እንዳይችሉ ማድረግ አለበት፡፡
5. የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ፣ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በሌላ አኳኋን ካልፈቀደ በስተቀር፣ በፈቃዱና አግባብ ሆኖ ሲገኝም በኪራይ የተያዘው ክልል የፈቃድ ዘመኑ ከመቋረጡ በፊት ወደ ነበረበት ሁኔታ እንዲመለስ ወይም ለሌላ የወደፊት ጠቀሜታ እንዲውል ለማስቻል በየደረጃው እንደነበረ የመመለስ፣ መልሶ የማቅናት ወይም የማስተካከል እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡
6. ባሕላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ ከሥራው ጋር ተመጣጣኝ የሆኑ ጉድጓዶችን እንደ መድፈን ዛፎችን እንደመትከል ያሉ የአካባቢ ጥበቃዎችን ማድረግ ግዴታው ሲሆን በሥራውም ላይ እንደ ሜርኩሪ ያሉ ንጥረ ነገሮችን መጠቀም አይፈቀድለትም፡፡

30.<u>ስለመዛግብትና ሪኮርድ እና ሪፖርት</u>

1. ማንኛውም ባለፈቃድ ፈቃዱ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ የሚከተሉትን በኢትዮጵያ ውስጥ መያዝ አለበት፤
   ሀ) የሚከተሉትን የያዘና በነዚሁ ላይ በየሳምንቱ የሚደረጉ ለውጦችን የሚያሳይ መዝገብ፤
      1) የተከናወኑ የማዕድን ሥራዎች፤
      2) በጠቅላላ ሠራተኞችን (በየሥራ መደባቸው በመለየት)፣ የሥራ ሁኔታዎችንና አደጋዎችን፤
      3) የተመረቱትን፣ የተከማቹትን፣ የተዘጋጁትን የተጓጓዙትን፣ ወደ ውጭ የተላኩትን እና የተሸጡትን ማዕድናት ዝርዝር፤
      4) የዕቃዎች፣ መሣሪያዎችና ሌሎች ንብረቶች ዝርዝር፣
   ለ) ከፈቃዱ ሥፍራ የተወሰዱ ማዕድናትን ናሙናዎች እና ከፈቃዱ ሥፍራ ጋር የተያያዙ የምርመራ እንዲሁም የቴክኒክና ሌሎች ሪፖርቶች ቅጂዎችን፡፡

2. የፍለጋ ፈቃድ ባለይዞታ በመመሪያ የሚገለጹ መረጃዎችን ያካተተ የዓመቱን አጠቃላይ ሪፖርት አመቱ ባለፈ በሠላሳ ቀን ውስጥ ለፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት፡፡
3. የምርመራ ፈቃድ ባለይዞታ በመመሪያ የሚገለጹ መረጃዎች ያካተተ ዓመታዊ ሪፖርት ዓመቱ ባለፈ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ለፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት፡፡
4. የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ባለይዞታ እያንዳንዱ ሩብ ዓመት ባለቀ በሠላሳ ቀናት ውስጥ የሚከተሉትን አጠቃልሎ የያዘ የሩብ ዓመት ሪፖርት ለፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት፤
   ሀ) በየደረጃው የተሠሩ የጂኦሎጂካል ሥራዎችን ዓይነትና የተገኙ ውጤቶችን ጨምሮ የተከናወኑ የማዕድን ሥራዎችን በአጠቃላይ፤ እንዲሁም የማዕድናቱን ምርት ሁኔታና በቀሪው ክምችት ላይ ያለውን ለውጥ፤
   ለ) በዚህ ደንብ አንቀጽ 28(6) በተገለጸው መሠረት በየሥራ ምድቡ የተሠማሩትን ሠራተኞች ጠቅላላ የሥራ ቀናት ብዛት፣ እንዲሁም የሥራ ሁኔታዎችንና አደጋዎችን፤
   ሐ) የተመረቱትን፣ የተከማቹትን፣ የተዘጋጁትን፣ የተጓጓዙትን፣ የተሸጡትንና ወደውጭ የተላኩትን (የተገኘውን ኤፍ.ኦ.ቢ. ወይም ሌላ ዋጋ ጨምሮ) ማዕድናት ዝርዝር፣ ወደ ውጭ የተላኩትን ማዕድናት መድረሻ ሥፍራና የገዢዎችን ዜግነት፣ እንዲሁም ከጠቅላላው ሽያጭ የተገኘውን ገቢ፤
   መ) የዕቃዎች፣ የመሣሪያዎችና የሌሎች ንብረቶችን ዝርዝርና በነዚሁ ላይ የተደረጉ ለውጦችን፤
   ሠ) ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በአግባቡ ያስፈልጋሉ ብሎ የሚጠይቃቸውን ሌሎች መረጃዎች፡፡
5. ባለፈቃዱ በየዓመቱ መጨረሻ ፈቃዱን የሚመለከተው ዘመን ባለቀ በሠላሳ ቀን ውስጥ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተዘረዘሩትን መረጃዎች የያዘ አጠቃላይ ሪፖርት ለፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት፡፡

31.**ፈቃድን ስለማሳየት፣**

ባለፈቃዱ ወይም ወኪሉ ወይም ሠራተኛው፣ አግባብ ያለው የመንግሥት ባለሥልጣን፣ በፈቃዱ ክልል ወይም በኪራይ በተያዘው መሬት ላይ ሕጋዊ ባለይዞታ የሆነ ሰው ወይም ጉዳዩ የሚመለከተው ሌላ ሰው ፈቃዱን ለማየት ሲጠይቅ ዋናውን ፈቃድ ወይም በፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ትክክለኛነቱ የተረጋገጠውን የፈቃዱን ኮፒ ማቅረብና ማሳየት አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## ስለፈቃድ ክፍያዎች፣ ስለመሬት ኪራይ፣ ስለሮያልቲና ሌሎች ክፍያዎች

32.**ስለፈቃድ ክፍያዎች**

1. ፈቃድ ለማውጣት የሚጠይቅ አመልካች በአዋጁ አንቀጽ 39 መሠረት የሚከፍለው የፈቃድ ክፍያ እንደሚከተለው ይሆናል፤
   ሀ) ለፍለጋ ፈቃድ ብር 100
   ለ) ለምርመራ ፈቃድ ብር 200
   ሐ) ለባሕላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ብር 10
   መ) ለአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ስራ ፈቃድ፤
      1) ለከበሩ ማዕድናት ብር 300
      2) ለሌሎች ማዕድናት ብር 200
   ሠ) ለከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ስራ ፈቃድ ብር 5000
2. ፈቃድ ለማሳደስ የሚጠይቅ አመልካች በአዋጁ አንቀጽ 39 መሠረት የሚከፍለው የፈቃድ ማሳደሻ ክፍያ እንደሚከተለው ይሆናል፣
   ሀ) ለምርመራ ፈቃድ ብር 100
   ለ) ለባሕላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ብር 10
   ሐ) ለአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ፤
      1) ለከበሩ ማዕድናት ብር 200
      2) ለሌሎች ማዕድናት ብር 100
   መ) ለከፍተኛ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ብር 3,000

**33.ስለሮያልቲ፣[35]**

1. ማንኛውም ባለፈቃድ በአዋጁ አንቀጽ 37(1) መሠረት የሚከፍለው ሮያልቲ እንደሚከተለው ይሆናል፤
   ሀ) ለከበሩ ማዕድናት 5 በመቶ
   ለ) ለሜታል እና ሜታል ላልሆኑ ማዕድናት፣ የኮንስትራክሽን ማዕድናትን ጨምሮ 3 በመቶ
   ሐ) ለጂኦተርማል ክምችትና ለማዕድን ውኃ 2 በመቶ
   መ) በከፊል ለከበሩ ማዕድናት 4 በመቶ[36]
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የሚከፈለው ሮያልቲ የሚሰላው ማዕድናቱ በተመረቱበት ሥፍራ በሚኖራቸው ዋጋ ላይ ተመስርቶ ነው፡፡ ክፍያው የሚፈጸመውም በየሩብ ዓመቱ ሆኖ እያንዳንዱ ሩብ ዓመት በተፈጸመ በሠላሳ ቀናት ውስጥ ይሆናል፡፡
3. ቅድሚያ ትኩረት በሚሰጣቸው የልማት ክልሎች የሚካሄዱ የማዕድን ሥራዎችን ማበረታታት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ከተመለከተው ያነሰ የሮያልቲ ክፍያ በስምምነት ሊወሰን ይችላል፡፡
4. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ማንኛውም ባለፈቃድ የሚጠየቀውን የሮያልቲ ክፍያ ለመቀነስ ለጊዜው ለማንሳት ወይም ለማስቀረት አግባብ ላለው የመንግሥት አካል ሃሳብ በማቅረብ ሊያስወስን ይችላል፡፡

**34.ሌሎች ክፍያዎች፣[37]**

1. በአዋጁ አንቀጽ 49 መሠረት ለምዝገባ ለሚቀርብ ሰነድ ብር 50 ይከፈላል፡፡
2. የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ብር 25ይከፈላል።
3. በአዋጁ አንቀጽ 51 መሠረት ለታዩ ጉዳዮች የውሳኔ ቅጂ ለማግኘት ብር 25 ይከፈላል፡፡

   የፈቃድ ቅጂ ወይም የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ምትክ ለማውጣት ብር 15 ይከፈላል፡፡

---

[35] በ 4/14 (1990) ደ. 27 መሰረት ተሰርዞ ቀድሞ ከአንቀፅ 34 እስከ 45 የነበሩት ከአንቀፅ 33 እስከ 44 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

[36] በ12/24 (1998) ደ. 124 አንቀፅ 2(4) መሰረት የተጨመረ ነው፡፡

[37]በ12/24 (1998) ደ. 124 አንቀፅ 2(5) መሰረት ተሻሻለ፡፡

4. ወደ ውጭ ሀገር የሚላኩ ማዕድናትን ለማስመርመርና ሠርተፊኬት ለማውጣት በማዕድናቱ ክብደት መሠረት የሚከተለው ክፍያ ይከፈላል፤

ሀ) እስከ 50 ኪሎ ግራም............................ ብር 20

ለ) ከ50 በላይ እስከ 200 ኪሎ ገራም ........ብር 30

ሐ) ከ200 ኪሎ ግራም በላይ ...................... ብር 40

35. **ክፍያን ስለማዘግየት፣**

ማንኛውም በዚህ ደንብ አንቀጽ 33 ወይም 34 መሠረት መፈጸም ያለበት ክፍያ በወቅቱ ካልተፈጸመ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ክፍያው በመዘግየቱ ወይም ባለመፈጸሙ በዚህ ደንብ ክፍል ስድስት ድንጋጌዎች መሠረት ሊወስድ የሚችለው የቅጣት እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ ያልተከፈለው ገንዘብ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ወር ወይም ከወር ላነሰ ጊዜ 2 በመቶ መቀጫ ተጨምሮበት ይከፍላል፡

## ክፍል ስድስት

## ስለጥፋቶችና ስለቅጣት

36. **አንደኛ ደረጃ ጥፋቶች**

1. ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) በቅድሚያ ተገቢውን ፈቃድ ሳይዝ በማዕድን ሥራ ላይ ከተሠማራ፤

ለ) ከፈቃድ ማመልከቻ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ሀሰተኛ መረጃ ከሰጠ ወይም ካጭበረበረ ወይም በአዋጁ አንቀጽ 12 እና በዚህ ደንብ አንቀጽ 19 (2) መሠረት የግኝት ማስታወቂያ ካልሰ፤

2. ማንኛውም ባለፈቃድ፡-

ሀ) የማዕድን ሥራዎችን በግዴለሽነት፣ በከባድ ቸልተኛነት ወይም ሆነ ብሎ አግባብ ባልሆነ መንገድ ከአካሄደ፤

ለ) የተፈጥሮ አካባቢን፣ ጤንነትን፣ ደኅንነትን፣ ወይም ሌሎች የማዕድን ሥራዎችን የሚመለከቱ ግዴታዎችን በተደጋጋሚ ከጣሰ፤ወይም

ሐ) በተደጋጋሚና በተጨባጭ ሁኔታ የማዕድን ሥራዎችን የሚመለከቱ አስተዳደራዊና የፋይናንስ ግዴታዎችን ካላሟላ፤

አንደኛ ደረጃ በሆነ ጥፋት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

37.<u>ሁለተኛ ደረጃ ጥፋቶች</u>

ማንኛውም ባለፈቃድ፡-

1. ተፈላጊ መዝገቦችንና ሪኮርዶችን ወይም ሌሎች ሰነዶችን ወይም ማቴሪያሎችን ካልያዘ ወይም መሠረታዊ በሆኑ ነጥቦች ላይ ትክክለኛ ያልሆኑ ወይም ያልተሟሉ መዝገቦችንና ሪኮርዶችን ከያዘ ወይም ተፈላጊ ሪፖርቶችን ወይም ሌሎች ሠነዶችን ካላቀረበ ወይም ተፈላጊ ማስታወቂያዎችን ካልሰጠ፤
2. የማዕድን ሥራዎችን በቸልተኛነት ወይም የማንኛውንም ሰው ጤንነት ወይም ደኅንነት፣ የተፈጥሮ አካባቢን ወይም የማዕድኑን ክምችት አደጋ ላይ በሚጥል አኳኋን ከአካሄደ፣ በአጠቃላይ ተገቢ የማዕድን አሠራር ልምዶችን ካልተከተለ ወይም ፈቃዱ የሚያስከትልበትን ግዴታ ካላከበረ፤
3. ለመንግሥት ገቢ መደረግ ያለበት ማንኛውንም ክፍያ በወቅቱ ካልከፈለ ወይም
4. በአግባቡ ሥልጣን የተሰጠው የፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ሠራተኛ ወደፈቃዱ ክልል ወይም በኪራይ ወደተያዘው ክልል እንዳይገባ ወይም የማዕድን ሥራዎች የሚካሄዱባቸውን ቦታዎች ወይም ተቋሞች ወይም የባለፈቃዱን መዝገቦች፣ ሪኮርዶች ወይም ሌሎች ሰነዶች ወይም ማቴሪያሎች እንዳያይ ካደረገ ወይም በሠራተኛው የተሰጠውን ሕጋዊ ትዕዛዝ ወይም መመሪያ ካልፈጸመ፣ ሁለተኛ ደረጃ በሆነ ጥፋት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

38. <u>አስተዳደራዊ ጥፋቶች</u>

ማንኛውም ባለፈቃድ፡-

1. መሠረታዊ በሆኑ ነጥቦች ላይ ትክክለኛ ያልሆኑ ወይም ያልተሟሉ መዝገቦችንና ሪኮርዶችን የመያዝ ጉድለቶችን ሳይጨምር፣ የተሟሉ፣ ትክክለኛ የሆኑና ወቅታዊውን ሁኔታ የሚያሳይ መዝገቦችንና ሪኮርዶችን ካልያዘ፤
2. ተፈላጊ ሪፖርቶችንና ሌሎች ሰነዶችን በወቅቱ ካላቀረበ ወይም ተፈላጊ ማስታወቂያዎችን በወቅቱ ካልሰጠ፤ወይም
3. ጥፋቱ የማንኛውም ሰው ጤንነት ወይም ደኅንነት የተፈጥሮ አካባቢን ወይም የማዕድኑን ክምችት አደጋ ላይ የማይጥል ቢሆንም፤ የማዕድን ሥራዎቹ ተገቢ በሆነ መንግድና በጥንቃቄ ካላካሄደ ወይም ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን ካላከበረ፣
አስተዳደሪዊ በሆነ ጥፋት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

39.<u>ስለቅጣቶች</u>

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 37 በተመለከተው አንደኛ ደረጃ በሆነ ጥፋት ሥር የሚወድቅ በማድረግ ወይም ባለማድረግ የሚፈጸም የጥፋት ድርጊት የሚያስከትለው ቅጣት ፈቃድን ወዲያውኑ መሠረዝንና ከብር 5000 የማይበልጥ የገንዘብ ቅጣትን ሊጨምር ይችላል፤ እንዲሁም አጥፊው ያንኑ ጥፋት ደግሞ ከፈጸመ የገንዘብ ቅጣቱ በእጥፍ ሊጨምር ይችላል፡፡
2. በዚህ ደንብ አንቀጽ 38 የተመለከተውን ሁለተኛ ደረጃ በሆነ ጥፋት ሥር የሚወድቅ ድርጊት ስለመፈጸሙ ማስጠንቀቂያ የደረሰው ባለፈቃድ በማድረግ ወይም ባለማድረግ የፈጸመውን የጥፋት ድርጊት ለማረም ወዲያውኑ እርምጃ ከወሰደ ጥፋቱ የሚያስከትልበት ቅጣት ከብር 2000 የማይበልጥ የገንዘብ ቅጣት ይሆናል፡፡ አጥፊው የእርምት እርምጃ መውሰድ ካልቻለ ወይም ካልወሰደ የገንዘብ ቅጣቱ መጠን በእጥፍ ሊጨምር ይችላል፡፡ በተጨማሪም ለፈቃዱ የእርምት እርምጃ ካልወሰደ ወይም ጥፋቱ በማንኛውም ሰው ጤንነት ወይም ደኅንነት፣ በተፈጥሮ አካባቢ ወይም በማዕድን ክምችት ላይ ሊደርስ የተቃረበ ወይም ቀጣይነት ያለው ጉዳት ካስከተለ፣ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ባለፈቃዱ ጥፋቱን እስከሚያስተካክል ድረስ የማዕድን ሥራዎቹን ወዲያውኑ እንዲያቆም ሊያዘው ይችላል፡፡ የጥፋቱ ድርጊት ወይም ሁኔታ እስኪስተካከልም ፈቃዱ ታግዶ ይቆያል፡፡
3. ማንኛውም ባለፈቃድ በዚህ ደንብ አንቀጽ 39 በተመለከተው አስተዳደራዊ ጥፋት ሥር የሚወድቅ ወይም በማድረግና ባለማድረግ የተፈጸመ ጥፋት ስለመፈጸሙ ማስጠንቀቂያ ከደረሰው በኋላ ወዲያውኑ የእርምት እርምጃ ካልወሰደ ወይም የጥፋት ድርጊቱ ሊታረም የማይችል ከሆነ ብር 500 በማይበልጥ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል፡፡
4. ማንኛውም በማድረግ ወይም ባለማድረግ የተፈጸመ ሁለተኛ ደረጃ ወይም አስተዳደራዊ ጥፋት የቀጣይነት ወይም የተደጋጋሚነት ባህርይ ያለው ሆኖ ሲገኝ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ጥፋቱን እንደቅደም ተከተሉ አንደኛ ደረጃ ወይም ሁለተኛ ደረጃ ጥፋት አድርጎ ሊቆጥረውና ባለፈቃዱም በዚሁ መሠረት ሊቀጣ ይችላል፡፡
5. የዚህን ደንብ ሌሎች ድንጋጌዎች የተላለፈ ማንኛውም ሰው በአዋጁ አንቀጽ 53 (5) መሠረት ይቀጣል፡፡

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 40. ስለክርክሮች አወሳሰን ሥርዓት

1. በአዋጁ አንቀጽ 51/1/ መሠረት በፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የስልጣን ክልል የሚነሱ ክርክሮች የሚታዩበትና የሚወሰኑበት ሥርዓት እንደሚተለው ይሆናል፤
   ሀ) አቤት ባዩ የክርክሩን ፍሬ ሃሣብና ማስረጃውን በማመልከቻ ለፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ያቀርባል፡፡ ማመልከቻው የአቤት ባዩን ቅሬታና እንዲሰጥለት የሚፈልገውን ውሳኔ መግለጽ አለበት፡፡
   ለ) ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ማመልከቻውን እንደተቀበለ ተከሳሹ መጥሪያና የማመልከቻ ቅጂ እንዲደርሰው ያደርጋል፡፡ ክርክሩ የሚሰማበትን ጊዜና ቦታም ለሁለቱም ወገኖች ያሳውቃል፡፡
   ሐ) ባለጉዳዮቹ በቀጠሮው ሰዓትና ቦታ ተገኝተው ጉዳያቸውን ለፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ያስረዳሉ፣ ማስረጃዎቻቸውንም ያቀርባሉ፡፡ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የቀረቡለትን ማስረጃዎች ይመዘግባል፡፡ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ጉዳዩ በሌላ ጊዜና ቦታ እንዲታይ በቀጠሮ ሊያስተላልፍ እንዲሁም በመጀመሪያውም ሆነ ከዚያ በኋላ በተያዘው ቀጠሮ ከባለጉዳዮቹ አንዱ በሌለበት ጉዳዩን ማየት ሊቀጥል ይችላል፡፡
   መ) ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የክስ ማመልከቻ ከቀረበለት በኋላና ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በማናቸውም ጊዜ ክርክር የተነሳበት ማዕድን ወይም ሌላ ንብረት እንዲያዝ፣ ተከብሮ እንዲጠበቅ ወይም ባለጉዳዩ በንብረቱ ዋጋ መጠን ዋስትና እንዲያቀርብ ሊያደርግ ይችላል፡፡
   ሠ) ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በጉዳዩ የሰጠውን ውሳኔ ባለጉዳዮቹ እንዲያውቁት ማድረግና ለእያንዳንዱ ባለጉዳይ የውሳኔውን መዝገብ ግልባጭ መስጠት አለበት፡፡
   ረ) ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ውሳኔውንና የውሳኔውን መዝገብ ግልባጭ በጉዳዩ ላይ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱም በሕግ በተፈቀደው መሠረት ውሳኔውን ያስፈጽማል፡፡
   ሰ) በክርክሩ የተረታው ወገን የአገልግሎት ክፍያዎችንና ወጭዎችን እንዲከፍል ሊደረግ ይችላል፡፡

ሸ) የዚህ ንዑስ አንቀጽ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ጉዳዮችን በመጀመሪያ ደረጃ የማየት ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት በሚታዩ የፍትሐ ብሔር ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች በፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ዘንድ በሚታዩ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

2. ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የቀረቡለትን ክሶች፣ የክርክሩን ሂደትና የሰጣቸውን ውሳኔዎች መዝግቦ ይይዛል፡፡

## 41.ጊዜን ስለማሳጠር ወይም ስለማራዘም

አንድ ድርጊት በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መፈጸም እንዳለበት የሚወስኑ የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች ቢኖሩም ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በበቂ ምክንያት ጊዜው እንዲያጥር ወይም እንዲራዘም ሊወስን ይችላል፡፡ ሆኖም የጊዜው ማጠር ወይም መርዘም የባለፈቃዱን መብት የሚጐዳ ወይም በፈቃዱ ወይም በአዋጁ የተመለከቱትን ተግባሮቹንና ግዴታዎቹን በመፈጸም አቅሙ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር መሆን የለበትም፡፡

## 42.ለባለፈቃዶች ስለሚሰጥ የመንግሥት ድጋፍ

ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ለባሕላዊና ለአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃዶች በሚመለከተው አኳኋን ድጋፍና ዕርዳታ ሊሰጣቸው ይችላል፡፡

1. የማዕድን ክምችት ያለበትን ሥፍራ ለይቶ በመከለልና የባሕላዊና የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃዶች ብቻ እንዲሠማሩበት ማድረግ፤
2. የቴክኒክና የአስተዳደር ድጋፍ፣ ዕርዳታና ሥልጠና መስጠት፤
3. ለሥራቸው የሚሆን የገንዘብ ድጋፍ እንዲያገኙ መርዳት፤
4. በፈቃደኛነት የሚመሠረቱ የማዕድን አምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት እንዲቋቋሙና ሥራቸውን እንዲያካሂዱ መርዳት፤
5. የተመረቱ ማዕድናትን በማዘጋጀት፣ በማጓጓዝ፣ በማከማቸትና ለገበያ በማቅረብ ረገድ ምክር መስጠት፡፡

## 43.ስለኮንትሮለሩ ሥልጣንና ተግባር

1. ኮንትሮለሩ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በሚጠው መመሪያ መሠረት የማዕድን ሥራዎችን ቴክኒካዊና አስተደደራዊ እንቅስቃሴዎች መቆጣጠርና በአዋጁ የተሰጡትን ተግባሮች በማከናወን ረገድ ተቀዳሚ ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡
2. ለፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ሌሎች ኃላፊዎች በተለይ የሚሰጥ ውክልና እንዲሁም የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እንደተጠበቀ ሆኖ ኮንትሮለሩ የፈቃድ ሰጭው

ባለሥልጣን በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች በሥራ ላይ ለማዋል አስፈላጊው ሥልጣን ሁሉ ተሰጥቶታል፡፡ ሆኖ በኮንትሮለሩ ውሳኔዎች ላይ ቅር በመሰኘት የሚቀርቡ አቤቱታዎች ለፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የበላይ ኃላፊ ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡

3. ለኮንትሮለሩ ወይም ለፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ሌሎች ኃላፊዎች በተለይ ውክልና ካልተሰጠ በስተቀር በዚህ ደንብ አንቀጽ 41 መሠረት የሚቀርቡ ክርክሮች በፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የበላይ ኃላፊ ታይተው ይወሰናሉ፡፡

44. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሚያዚያ 12 ቀን 1986 ዓ.ም**

**ታምራት ላይኔ**

**የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር**

ለ/ <u>ኢነርጂ</u>

**አዋጅ ቁጥር 295/1978**

**የነዳጅ ሥራዎችን ለማስተዳደር የወጣ አዋጅ**

**"ኢትዮጵያ ትቅደም"**

የሀገሪቱ የነዳጅ ሀብት ተፈልጐ በጥቅም ላይ እንዲውል መደረጉ ለሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የኢኮኖሚ ዕድገትና ብልጽግና ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክት በመሆኑ፤

የነዳጅ ሥራዎች ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀምና ሀብትን በአግባብ በመጠበቅ መርህ መሠረት የሚከናወኑ እና የሀገሪቱን የነዳጅ ሀብት አለኝታ በይበልጥ ለማወቅ የሚያስችሉ መሆን ስላለባቸው፤

የነዳጅ ቴክኖሎጂ ዕውቀት የሚቀሰምበትን ሁኔታ በማመቻቸት በመስኩ የሀገር ውስጥ የሰው ኃይልና መሠረተ ልማት ማደራጀት ስለሚያስፈልግ፤

እንዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የነዳጅ ሥራዎችን በሚመለከት የተለየ ሕግ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግንና የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ሥልጣንና ኃላፊነት እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 110/1969 ዓ.ም አንቀጽ 5 (6) መሠረት የሚከተለው ታውጅዋል፡፡

1. <u>**አጭር ርዕስ**</u>

   ይህ አዋጅ "የነዳጅ ሥራዎች አዋጅ ቁጥር 295/1978" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>**ትርጓሜ**</u>

   በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

   1. "ኮንትራክተር" ማለት ከመንግሥት ጋር የነዳጅ ስምምነት የሚያደርግ ማንኛውም ሰው ነው፤
   2. "የነዳጅ ዘይት ድፍድፍ" ማለት ስበቱ (ስፔስፊክ ግራቪቲ) ከግምት ሳይገባ፣ ነዳጁ ከሚወጣበት ጉድጓድ አፍ ላይ በፈሳሽ መልክ የሚመረተው ሃይድሮካርቦን፣ አስፋልት፣ ኦዞክራይት እና ከተፈጥሮ ጋዝ "በኮንደንሴሽን" ወይም በ"ኤክስትራክሽን" የሚገኘው "ዲስትሌት" ወይም "ኮንደንሴት" በመባል የሚታወቀው ፈሳሽ ሃይድሮካርቦን በሙሉ ነው፤

3. “መንግሥት” ማለት የኀብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ መንግሥት ነው፤[38]
4. “ሚኒስትር” ወይም “ሚኒስቴር” ማለት የማዕድንና የኃይል ምንጭ ሚኒስትር[39] ወይም ሚንስቴር ሲሆን፣ እንደሁኔታው የነዚህኑ ተተኪ ይጨምራል፤
5. “የተፈጥሮ ጋዝ” ማለት በአካባቢ የአየር ሙቀትና ግፊት ሁኔታ በጋዝነት ደረጃ የሚገኝ ሃይድሮካርቦን ሲሆን፣ እርጥበት ያለውን የማዕድን ጋዝ፣ ደረቅ የማዕድን ጋዝን፣ ፈሳሽ ሃይድሮካርቦን እርጥበት ካለው ጋዝ ከወጣ ወይም ከተለየ በኋላ የሚቀረውን ኬዚንግሄድ ጋዝና ዝቃጭ ጋዝ፣ እና ከፈሳሽ ወይም በጋዝነት መልክ ካለ ሃይድሮካርቦን ጋር የሚመረተውን ሃይድሮካርቦን ያልሆነ ጋዝ ይጨምራል፤
6. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
7. “ነዳጅ” ማለት ከዘይት ሼል ወይም ከታር ሳንድ የተገኘ ሃይድሮካርቦንን ጨምሮ የነዳጅ ዘይት ድፍድፍና የተፈጥሮ ጋዝ ነው፤
8. “የነዳጅ ስምምነት” ማለት የነዳጅ ሥራዎች ለማካሄድ በመንግሥትና በኮንትራክተር መካከል የሚደረግ ውል ወይም ሌላ ዓይነት ስምምነት ነው፤
9. “የነዳጅ ሥራዎች” ማለት የነዳጅ ዘይት ድፍድፍ ማጣራትን ሳይጨምር፣ ነዳጅ መፈለግ፣ ማልማት፣ ማውጣት፣ ማምረት፣ በመስክ መለያየት፣ ማዘጋጀት (ማጣራትን ሳይጨምር)፣ ማከማቸት፣ ወደ ውጭ ሀገር እስከሚላክበት ወይም ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ወደሚሰራጭበት ሥፍራ ማጓጓዝ እና ለገበያ ማቅረብ ሲሆን፣ ከተፈጥሮ ጋዝ የተለያዩ ምርቶች ማውጣትን ይጨምራል፤
10. “ሰብኮንትራክተር” ማለት በነዳጅ ስምምነት መሠረት ለነዳጅ ሥራዎች አፈጻጸም አስፈላጊ የሆነውን አገልግሎት ለማቅረብ ከኮንትራክተሩ ጋር ውል ያደረገ ማንኛውም ሰው ነው፤
11. “የኢትዮጵያ ክልል” ማለት የመሬት ክልሉ፣ በመሬት ክልሉ ውስጥ የሚገኙ ውሀዎች፣ ደሴቶች፣ በደሴቶቹ ዙሪያ የሚገኙ ውሀዎች፣ የባሕር ክልሉና የዚሁ የባሕር ክልል ወለልና ከርሰ ምድር፣ ኤክስክሉዚፍ ኢኮኖሚክ ዞን እና ኮንቲኔንታል ሼልፍ ነው፡፡

[38] በኢ.ፌድ.ሪ ህገ መንግስት(1/1 (1987) አ.1 አንቀጽ 1) መሰረት መንግስት ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ሆኗል፡፡

[39] በአዋጅ ቁጥር 25/08 (2011) አ. 1097 አንቀጽ 9 (12) መሰረት የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

3. **የአፈጻጸም ወሰን**
   1. ማንኛውም ኮንትራክተር በኢትዮጵያ ክልል የሚያካሂዳቸው የነዳጅ ሥራዎች ሁሉ በዚህ አዋጅ መሠረት ይተዳደራሉ፡፡
   2. ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን በፊት የነዳጅ ሥራዎችን በሚመለከት የተደረገ ማናቸውም ስምምነት፣ ተዋዋዮቹ ወገኖች በሌላ አኳኋን ካልተስማሙ በስተቀር፣ ስምምነቱ ተፈጻሚ በሆነበት ቀን በሥራ ላይ በነበረው ሕግ መሠረት ይተዳደራል፡፡
4. **የነዳጅ ባለቤትነት**
   1. በኢትዮጵያ ክልል ላይ ውስጥም ሆነ በታች በተፈጥሮ መልኩ የሚገኝ ነዳጅ ባለቤትነቱ የመንግሥት ነው፡፡
   2. ነዳጁ ከተመረተ በኋላ የሚኖረው የባለቤትነት መብት አግባብ ባለው የነዳጅ ስምምነት መሠረት ይሆናል፡፡
5. **የነዳጅ ሥራዎች ስለሚካሄዱበት ሁኔታ**

   መንግሥት የነዳጅ ሥራዎችን በነዳጅ ስምምነት መሠረት በኮንትራክተሮች ሊያካሂድ ይችላል፡፡
6. **ሚኒስትሩ መንግሥትን የሚወክል ስለመሆኑ**
   1. ይህን አዋጅ በሚመለከት ከኮንትራክተሩ ጋር ለሚኖር ግንኙነት ሚኒስትር መንግሥትን ይወክላል፤ ይህን አዋጅ በሚገባ ለማስፈጸምም ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡
   2. ይህን አዋጅ በሚመለከት ደንብ ለማውጣትና የነዳጅ ስምምነት ለመፈራረም ወይም ለመሰረዝ ከተሰጠው ሥልጣን በስተቀር፤ ሚኒስትሩ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ማናቸውንም ሌላ ሥልጣን አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በጽሑፍ ውክልና መስጠት ይችላል፡፡
7. **የሚኒስትሩ ሥልጣን**[40]

   ሚኒስትሩ የሚከተሉት ሥልጣኖች ይኖሩታል፤
   1. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን የማውጣት፤

---

[40] በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ላይ ሚኒስቴሩ ደንብ የማውጣት ሰልጣን የተሰጠው ሲሆን ይህ ስልጣን አሁን ባለው ስርዓት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት የተሰጠ ነው፡፡ ስለሆነም ሚኒስቴሩ ደንብ የማውጣት ስልጣን የሌለው መሆኑ ታሳቢ ተደርጎ ይነበብ፡፡

2. ማንኛውም ኮንትራክተር አግባብ ባለው የነዳጅ ስምምነት መሠረት ግዴታውን ለመወጣት አስፈላጊው የገንዘብ አቅም፣ የቴክኒክ ብቃትና የሙያ ችሎታ እንዳለው የማረጋገጥ፤
3. የፕሮዳክሺን ሼሪንግና የሞደርን ኮንሴሽን የስምምነት ዓይነቶችን ጨምሮ የነዳጅ ስምምነት መደራደሪያ ሞዴሎችን የማዘጋጀት፤
4. በጨረታ በማወዳደር ወይም የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚሰጠው መመሪያ መሠረት በቀጥታ በመደራደር፡-
   ሀ) ኮንትራክተሩን በተወሰነ ክልል የነዳጅ ሥራዎች ለማከናወን የሚያስችለውን ብቸኛ የሆነ የነዳጅ ስምምነት የመዋዋል፤ ወይም
   ለ) ኮንትራክተሩን በተወሰነ ክልል ጂኦሎጂካዊ እና ጂኦፊዚካዊ ጥናት ለማካሄድ የሚያስችለውን ብቸኛ ያልሆነ የነዳጅ ስምምነት የመዋዋል፤
5. ኮንትራክተሩ የሚያካሂዳቸው ሥራዎች በነዳጅ ስምምነቱ መሠረት የሚከናወኑ መሆኑን የመከታተልና የማረጋገጥ፤
6. የነዳጅ ስምምነቱ በሚሸፍነው ክልል ውስጥ፣ ኮንትራክተሩ የሚያካሂዳቸውን የነዳጅ ሥራዎች አላግባብ በማያሰናክል መልክ፣ ከነዳጅ በስተቀር ሌሎች ማዕድናትን ወይም የተፈጥሮ ሀብቶችን ለመፈለግ ወይም ለማምረት የሚያስችል ፈቃድ ለሶስተኛ ወገኖች የመስጠት፤
7. በዚህ አዋጅ በሚወጣ ደንብ ወይም በነዳጅ ስምምነቱ መሠረት በኮንትራክተሩ የሚከፈለውን ወይም እንዲከፈል የሚወሰነውን፤
   ሀ) ሮያልቲ፤
   ለ) የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ፤
   ሐ) ቦነስ፤
   መ) ኪራይ፤ ወይም
   ሠ) ማናቸውንም ሌላ ክፍያ፤

   በሚመለከት ስሌት የማውጣት፣ ክፍያውን የመሰብሰብና ሂሳቡን የመመርመር፡፡
8. **<u>በመመሪያ ስለሚወሰኑ ጉዳዮች</u>**

   ሚኒስትሩ፡-
   1. የነዳጅ ሥምምነት ጨረታ የሚወጣበትንና የሚገመገምበትን መንገድና ሥነ ሥርዓት፤

2. የነዳጅ ሥራዎች ለማካሄድ የሚቀርበውን ማመልከቻ ፎርምና ይዘት፤
3. የነዳጅ ሥራዎች ለማካሄድ የሚያመለክት ሰው ማሟላት ያለበትን ተፈላጊ የሙያ ብቃትና የሥራ ልምድ፤ እና
4. ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮችን፤

በመመሪያ ሊወሰን ይችላል፡፡

9. **<u>የነዳጅ ስምምነት ስለሚይዛቸው ጉዳዮች</u>**

ማናቸውም የነዳጅ ስምምነት ከሌሎች ጉዳዮች በተጨማሪ፤ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መያዝ ይኖርበታል፤

1. በኢትዮጵያ የገቢ ግብር ሕግ መሠረት የሚከፈሉትን ታክሶች ሳይጨምር፣ ስለሮያልቲ፣ ስለመሬት መጠቀሚያ ክፍያ፣ ስለቦነስ፣ ስለኪራይ፣ ወይም ለመንግሥት መደረግ ስላለባቸው ሌሎች ክፍያዎች፤
2. ለአደጋ መከላከያ ሊወሰዱ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎችና ፕሮግራሞች፣ እንዲሁም በነዳጅ ሥራዎች ላይ ከተሰማሩ ሠራተኞች የሥራ ሁኔታ ጋር ስለተያያዙ ሌሎች ጉዳዮች፤
3. በነዳጅ ስምምነት መሠረት መከናወን ስላለበት አነስተኛ (ሚኒመም) የስራ መጠንና መደረግ ስላለበት አነስተኛ ወጪ እንዲሁም በየጊዜው መለቀቅ ስላለበት ክልል፤
4. ስለኮንትራክተሩ መብትና ግዴታ፤
5. በነዳጅ ሥራዎች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ ሚኒስትሩ ስለሚኖረው ሥልጣን፤
6. ስለሪፖርቶችና መረጃዎች ይዘት እና ለሚኒስትሩ ስለሚቀርቡበት ጊዜና ሁኔታ፤
7. ከነዳጅ ስምምነት የሚመነጭ የኮንትራክተሩ መብት ወይም ግዴታ ስለሚተላለፍበት ወይም ስለሚዛወርበት ሥነ ሥርዓት፤
8. የነዳጅ ስምምነት ስለሚሠረዝበት ወይም ስለሚቋረጥበት ሁኔታ እና ክርክሮች ስለሚፈቱበት ሥነ ሥርዐት፤
9. መንግሥት በተወሰኑ ወይም በሁሉም የነዳጅ ሥራ መስኮች ተሳትፎ ስለሚያደርግበት ሁኔታ፤

10. የተዋዋይ ወገኖች መብትና ግዴታ ሚዛን ተጠብቆ ስለሚቆይበት ሁኔታ (ስታቢላይዜሽን ክሎውዝ)፤
11. የአካባቢን ደህንነት ለመጠበቅ መሟላት ስላለባቸው ሁኔታዎች፤
12. ስለሂሳብ አያያዝ ሥነ ሥርዓት፤
13. ኮንትራክተሩ በነዳጅ ስምምነቱ መሠረት ግዴታዎቹን ሳይፈጽም ቢቀር ስለሚወሰዱ እርምጃዎች፤
14. ስለኢትዮጵያውያን ሠራተኞች አቀጣጠር፣ መብትና ግዴታ በተለይም ሥልጠና፤ እና
15. የነዳጅ ሥራዎችን በትክክል ለማካሄድ አስፈላጊ ስለሆኑ ሌሎች ጉዳዮች፡፡

10.**<u>የነዳጅ ሥራዎች የማይካሄዱባቸው ቦታዎች</u>**

1. ሚኒስትሩ፣ አግባብ ካላቸው ሌሎች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር፣ ከሀገር ጥቅምና ደህንነት ጋር በተያያዘ ምክንያት የነዳጅ ሥራዎች ለማካሄድ የማይፈቀድባቸውን ቦታዎች ይወስናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ሚኒስትሩ የሚያደርገው ውሳኔ ቀደም ሲል በተደረገ የነዳጅ ስምምነት መሠረት ለነዳጅ ሥራዎች በተወሰነ ክልል ውስጥ የተገኘን መብት የሚነካ አይሆንም፡፡

11.**<u>የነዳጅ ስምምነት የጊዜ ገደብ</u>**

1. የነዳጅ ስምምነት የጊዜ ገደብ እንደሚከተለው ይሆናል፤
   ሀ) ብቸኛ ባልሆነ የነዳጅ ስምምነት መሠረት ለሚከናወኑ ሥራዎች እስከ ሁለት ዓመት፤
   ለ) ብቸኛ በሆነ የነዳጅ ስምምነት መሠረት ለሚካሄድ የነዳጅ ፍለጋ ሥራ እስከ አራት ዓመት፤
   ሐ) ብቸኛ በሆነ የነዳጅ ስምምነት መሠረት ለሚካሄድ ነዳጅ የማልማትና የማምረት ሥራ እስከ ሃያ አምስት ዓመት፡፡
2. ሚኒስትሩ ተገቢ ሆኖ ሲገኝ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተመለከተው ገደብ ላይ የሚከተለውን የጊዜ ማራዘሚያ ለመፍቀድ ይችላል፡-
   ሀ) ብቸኛ ባልሆነ የነዳጅ ስምምነት መሠረት ለሚከናወኑ ሥራዎች እስከ ሁለት ዓመት፤

ለ) ብቸኛ በሆነ የነዳጅ ስምምነት መሠረት ለሚካሄድ የነዳጅ ፍለጋ ሥራ እስከ አራት ዓመት፤

ሐ) ብቸኛ በሆነ የነዳጅ ስምምነት መሠረት ለሚካሄድ ነዳጅ የማልማትና የማምረት ሥራ እስከ አሥር ዓመት፡፡

3. ሚኒስትሩ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ማብቂያ ላይ ኮንትራክተሩ እያካሄደ ያለውን የቁፋሮ፣ የሎጊንግ፣ የሙከራ ወይም ጉድጓድ የመድፈን ሥራ ወይም የነዳጅ ግኝት ግምገማ እንዲያጠናቅቅ ለማስቻል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ከተመለከተው በተጨማሪ የጊዜ ገደብ ማራዘሚያ ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል፡፡

4. ከዚህ በላይ ከተመለከቱት ማራዘሚያዎች ሌላ ሚኒስትሩ ለተፈጥሮ ጋዝ ግኝት ግምገማ ተግባር እንዳስፈላጊነቱ ተጨማሪ የጊዜ ገደብ ማራዘሚያ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

12.**ቅድሚያ ስለመስጠትና ስለሥልጠና**

ማንኛውም ኮንትራክተር፡-

1. ተፈላጊው ችሎታና የሥራ ልምድ ላላቸው ኢትዮጵያውያን በተቻለ መጠን የቅጥር ቅድሚያ ይሰጣል፤
2. የሀገር ውስጥ ማቴሪያል፣ የምርት ውጤትና አገልግሎት በሚፈለገው ጊዜ፣ በተመጣጣኝ ዋጋና ጥራት ሊገኝ እስከቻለ ድረስ በነዚሁ ለመጠቀም ቅድሚያ ይሰጣል፤
3. በነዳጅ ስምምነቱ መሠረት ኢትዮጵያውያንን በነዳጅ ሥራዎች ያሠለጥናል፡፡

13.**ስለማስተላለፍና ስለመተካት**

1. ሚኒስትሩ በቅድሚያ መፍቀዱን በጽሑፍ ሲገልጽ፣ ኮንትራክተሩ ከነዳጅ ስምምነቱ የተገኙ መብቶቹን፣ ግዴታዎቹንና ጥቅሞቹን በከፊል ወይም በሙሉ ማስተላለፍ፣ ሌሎች እንዲተኩባቸው ማድረግ ወይም በሌላ መንገድ ማዛወር ይችላል፤ ሚኒስትሩም ለዚሁ የሚያስፈልገውን ፈቃድ ያለበቂ ምክንያት ሊከለክል አይችልም፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ የማስተላለፉ፣ ሌሎችን የመተካቱ ወይም በሌላ መንገድ የማዛወሩ ዝርዝር ሁኔታ አግባብ ባለው የነዳጅ ስምምነት መሠረት ይወሰናል፡፡

14.**<u>የአሠራር ደረጃ</u>**

ኮንትራክተሮች የነዳጅ ሥራዎች የሚያካሂዱት በዓለም አቀፍ ደረጃ አጠቃላይ ተቀባይነት ያለውን የነዳጅ ኢንዱስትሪ የአሠራር ደረጃና ልምድ በመከተል እንዲሁም ነዳጅና ሌሎች ሀብቶች በማይባክኑበትና የሰው ሕይወት፣ ንብረትና የአካባቢ ደህንነት በሚጠበቅበት አኳኋን ይሆናል፡፡

15.**<u>ንብረት ስለማስተላለፍ</u>**

1. በነዳጅ ስምምነት መሠረት በተለቀቀ ወይም የውል ዘመኑ በተቋረጠ ክልል ላይ የሚገኙ ድርጅቶችን፣ መሣሪያዎችንና ተቋሞችን ኮንትራክተሩ ያለክፍያ ለመንግሥት ያስተላልፋል፤ ሆኖም የተጠቀሰው ክልል ወይም ከፊሉ፡-
   ሀ) አግባብ ባለው የነዳጅ ስምምነት በተገለጸው ሁኔታ ለንግድ በሚውል ደረጃ ነዳጅ ለማምረት የሚያስችል መሆኑ የተረጋገጠ፤ ወይም
   ለ) ለንግድ በሚውል ደረጃ ነዳጅ በማምረት ላይ የሚገኝ ወይም ቀደም ሲል በዚሁ ሁኔታ ሲያመርት የቆየ፤

   መሆን አለበት፡፡
2. ሚኒስትሩ የማስተላለፉን ሁኔታ ላለመቀበልና ኮንትራክተሩ በመንግሥት ላይ ወጪ ሳያስከትል ድርጅቱን፣ መሣሪያዎቹንና ተቋሞቹን በከፊል ወይም በሙሉ እንዲያነሳ ለማስገደድ ይችላል፡፡

16.**<u>በሌሎች ንብረት ስለመጠቀም</u>**

ኮንትራክተሩ ከሚያካሂዳቸው የነዳጅ ሥራዎች ጋር በተያያዘ ሁኔታ በማናቸውም ንብረት መጠቀም ሲያስፈልገው፣ መንግሥት ለነዳጅ ሥራዎች አስፈላጊ የሆነውን መብት ወይም ጥቅም ሊወስድ ይችላል፤ ሆኖም ኮንትራክተሩ ባለመብት ወይም ባለጥቅም ለሆነው ሰው ተገቢ ኪሣራ ይከፍላል፡፡

17.**<u>ለታሪካዊ ሥፍራዎችና ለሌሎች ማዕድናት ስለሚደረግ ጥንቃቄ</u>**

ማንኛውም ኮንትራክተር፡-

1. የነዳጅ ሥራዎች የሚያካሂደው የአንትሮፖሎጂ፣ የአርኪዮሎጂና የታሪክ ቅርሶችንና ሥፍራዎችን ደኅንነት በማያናጋ ሁኔታ ይሆናል፤
2. የአንትሮፖሎጂ፣ የአርኪዮሎጂ፣ የታሪክ ቅርሶችንና ሥፍራዎችን ወይም ሌሎች ማዕድናትን ሲያገኝ በተቻለ መጠን ወዲያውኑ ሁኔታውን ለሚኒስትሩ ያሳውቃል፤

3. እነዚህን የአንትሮፖሎጂ፣ የአርኪዮሎጂ፣ የታሪክ ቅርስ ወይም ሌሎች ማዕድናትን ሚኒስትሩ በቅድሚያ ሳይፈቅድ ካሉበት ቦታ ማንቀሳቀስ አይችልም፡፡

18. <u>ስለሂሳብ አያያዝና ስለመዛግብት</u>

1. ማንኛውም ኮንትራክተር፡-

ሀ) ስለሚያካሂዳቸው የነዳጅ ሥራዎች የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት በኢትዮጵያ ውስጥ ይይዛል፤

ለ) በሚኒስትሩ ተቀባይነት ባለውና በታወቀ ገለልተኛ ኦዲተር የተመረመረ የሂሳብ መግለጫ፣ የሂሳብ ሚዛን መግለጫ እና የገቢና የወጪ ሂሳብ መግለጫን ጨምሮ፣ ለሚኒስትሩና አግባብ ላላቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በየዓመቱ ያቀርባል፡፡

2. ማንኛውም ኮንትራክተር ሚኒስትሩ በሚያወጣው ደንብ ውስጥ በሚገለጸው ሥርዓት ወይም የዚህ ዓይነቱ ደንብ በማይኖርበት ጊዜ አግባብ ባለው የነዳጅ ስምምነት መሠረት፣ የቁፋሮ፣ የጂኦፊዚካል እና የጂኦሎጂካል መረጃዎችን ጨምሮ የነዳጅ ሥራዎቹን ክንዋኔ የሚያሳዩ መዛግብት ይይዛል፤ እንዲሁም እነዚህኑ መረጃዎች፣ ሪፖርቶችንና መግለጫዎችን ለሚኒስትሩ ያቀርባል፡፡

19. <u>ስለመድንና ከተጠያቂነት ስለመጠበቅ</u>

1. ኮንትራክተሩ የነዳጅ ሥራዎች ማካሄድ ከመጀመሩ በፊት ሚኒስትሩ በጽሑፍ ያጸደቀው በቂ የሆነ ገንዘብና ሽፋን የሚሰጥ የሠራተኞች የጉዳት ካሣ፣ የንብረትና የሦስተኛ ወገን ኢንሹራንስ ይገባል፤ ጸንቶ እንዲቆይም ያደርጋል፡

2. በንብረት ላይ በደረሰ ጥፋት ወይም ብልሽት ወይም በሰዎች ላይ በደረሰ የሞት አደጋ ወይም የአካል ጉዳት ምክንያት ሊቀርቡ የሚችሉትን ጨምሮና በነዚህ ብቻ ሳይወሰን፣ ኮንትራክተሩ አግባብ ባለው የነዳጅ ስምምነት ውስጥ በተገለጸው መሠረት ራሱ በሚያካሂደው ወይም በስሙ በሚካሄድለት የነዳጅ ሥራ ወይም ከሥራው በመነጨ ምክንያት በሚቀርቡ ማናቸውም ዓይነት የዕዳ ጥያቄዎች፣ ኪሳራና ጉዳቶች ሁሉ መንግሥት እንዳይጠየቅ የማድረግ፣ የመከላከልና ከኃላፊነት የማዳን ግዴታ አለበት፡፡

## 20.ለአገር ውስጥ ገበያ ስለማቅረብ

1. ኮንትራክተሩ ከነዳጅ ዘይት ድፍድፍ ድርሻው ውስጥ ለአገር ውስጥ ፍጆታ የሚውለውን ለመንግሥት እንዲያቀርብ ሚኒስትሩ በጽሑፍ ሊያዘው ይችላል፡፡
2. ኮንትራክተሩ እንዲያቀርብ የተጠየቀው የነዳጅ ዘይት ድፍድፍ ዋጋ፣ መጠንና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎች ሁለቱ ወገኖች በሚስማሙበት አኳኋን ይፈጸማል፡፡

## 21.ከቀረጦችና ታክሶች ነፃ ስለመሆን

1. ማንኛውም ኮንትራክተርና ሰብኮንትራክተር ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባቸው የቁፋሮ፣ የጂኦሎጂካል፣ የጂኦፊዚካል፣ የማምረቻ፣ የማዘጋጃ፣ የማጣሪያ፣ የማጓጓዣና ሌሎች ለነዳጅ ሥራዎች አስፈላጊ የሆኑ መሣሪያዎችና ዕቃዎች፣ የአየር፣ የባሕርና የየብስ ማጓጓዣዎችን፣ ሌሎች የማጓጓዣ መሣሪያዎችንና መለዋወጫቸውን ጨምሮ (የግል አቶሞቢሎችንና ለነዚሁ የሚያስፈልገውን ነዳጅ ሳይጨምር)፤ ነዳጅ፣ ኬሚካሎች፣ ዘይትና ቅባቶች፣ ፊልሞች፣ ሴስሚክቴፖች፣ ተንቀሳቃሽ ቤቶች፣ ተንቀሳቃሽ ቢሮዎችና የተገጣጣሚ ስትራክቸሮች የተፈታቱ ክፍሎች እና ለነዳጅ ሥራዎች አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ማቴሪያሎች ከገቢ ዕቃ የጉምሩክ ቀረጥ፣ ከታክስ እና ከማናቸውም ዓይነት ተመሣሣይ ክፍያዎች ነፃ ይሆናሉ፡፡
2. የውጭ ሀገር ዜጋ የሆኑ የኮንትራክተሩና የሰብኮንትራክተሩ ተቀጣሪ ሠራተኞች ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገቧቸው የቤት ዕቃዎችና የግል መገልገያዎች፣ አንድ የቤት መኪና ጨምሮ፣ በጊዜው በሚሠራበት ደንብ መሠረት ከገቢ ዕቃ የጉምሩክ ቀረጦች፣ ከታክሶችና ከማናቸውም ዓይነት ተመሳሳይ ክፍያዎች ነፃ ይሆናሉ፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ዕቃዎች ተመልሰው ሲወጡ የወጭ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥና ሌሎች በወጭ ዕቃዎች ላይ የሚጣሉ ታክሶች አይከፈሉባቸውም፤ ሆኖም እነዚህ ዕቃዎች በኢትዮጵያ ውሰጥ ለሌላ ሰው ከተላለፉ እንደነገሩ ሁኔታ ኮንትራክተሩ፣ ሰብኮንትራክተሩ ወይም የውጭ ሀገር ዜጋ የሆኑ ሠራተኞቻቸው አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የጉምሩክ ቀረጥና ሌሎች ክፍያዎችን ይፈጽማሉ፡፡

4. ኮንትራክተሩ የተመረተ ነዳጅ ከአገር ውጪ ሲያወጣ ከወጪ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥ፣ ከታክስ ወይም ከማናቸውም ዓይነት ተመሣሣይ ክፍያዎች ነፃ ይሆናል፡፡

22.**ሮያልቲ**

1. ማንኛውም ኮንትራክተር ለተመረተ ነዳጅ ሮያልቲ ይከፍላል፡፡
2. የሮያልቲው መጠንና የአከፋፈሉ ሁኔታ በነዳጅ ስምምነቱ ይወሰናል፡፡

23.**ስለገቢ ግብርና ሌሎች ክፍያዎች**

1. ማንኛውም ኮንትራክተርና ሰብኮንትራክተር አግባብ ባለው የኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የገቢ ግብር ይከፍላል፡፡
2. የውጭ ዜጋ የሆኑ የማንኛውም ኮንትራክተርና ሰብኮንትራክተር ተቀጣሪዎች በነዳጅ ስምምነቱ መሠረት መሠራት ያለበትን ተግባር ሲያከናውኑ የሚከፈላቸው ደመወዝና በጥሬ ገንዘብም ሆነ በዓይነት የሚሰጣቸው ሌላ ጥቅም የገቢ ግብር አይከፈልበትም፡፡
3. ማንኛውም ኮንትራክተር አግባብ ባለው የነዳጅ ስምምነት የተወሰነውን በታክስ ስም የሚጠራ ወይም የማይጠራ ማናቸውንም ተጨማሪ ክፍያ ይከፍላል፡፡

24.**ስለውጭ ምንዛሪ ደንቦች፤**

1. በኢትዮጵያ ውስጥ በየጊዜው የሚወጡት የውጭ ምንዛሪ ሕጎችና መመሪያዎች በኮንትራክተሮችና ሰብኮንትራክተሮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፤ ሆኖም አግባብ ባለው የነዳጅ ስምምነትና በገቢ ግብር ሕጎች መሠረት ኮንትራክተሮችና ሰብኮንትራክተሮች የሚፈለግባቸውን ክፍያና ግብር ካሟሉ በኋላ የሚከተሉት መብቶች ይኖሯቸዋል፤

   ሀ) ከነዳጅ ሥራዎች የሚገኘውን ጨምሮ ማናቸውንም ገንዘብ ከኢትዮጱያ ውጭ የማኖር ወይም በገንዘቡ የመጠቀም፤

   ለ) የውጪ ሰብኮንትራክተሮችንና ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ የኮንትራክተሩ ተቀጣሪዎችን ከኢትዮጵያ ውጪ የመክፈል፤ ሆኖም የውጪ ሰብኮንትራክተሮችና ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ የኮንትራክተሩ ሠራተኞች በኢትዮጵያ ሊከፍሉ የሚገባቸውን ታክሶችና ለኑሮ የሚያስፈልጋቸውን ወጪ ለመሸፈን የሚያስችላቸውን ገንዘብ በውጪ ምንዛሪ ወደ አገር ውስጥ እንዲያስገቡ ይገደዳሉ፡፡

ሐ) ወደ አገር ውስጥ ያስገቡትን ወይም ከነዳጅ ሥራዎች፣ ከዕቃ ሽያጭ ወይም ኪራይ የተገኘውን ወይም በነዳጅ ስምምነት መሠረት ከአገልግሎት የተገኘውን ገንዘብ ወደ ውጭ የመላክ፡፡

2. ኮንትራክተሮችና ሰብኮንትራክተሮች የተቀበሉትን፣ ያስገቡትን፣ የላኩትንና በውጭ አገር ያኖሩትን ገንዘብ በሚመለከት ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በየወቅቱ ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡ የሪፖርቱ አቀራረብ አግባብ ባለው የነዳጅ ስምምነት ይወሰናል፡፡

25.<u>ስለግልግል</u>

1. በመንግሥትና በኮንትራክተሩ መካከል በነዳጅ ስምምነቱ፣ በስምምነቱ አተረጓጐም፣ በስምምነቱ መጣስ ወይም መቋረጥ ምክንያት ወይም ከእነዚሁ ጋር በተያያዙ ምክንያቶች የሚፈጠር ማናቸውም ክርክር፣ አለመግባባት ወይም ክስ በተቻለ መጠን በጋራ ውይይት ይፈታል፡፡

2. ጉዳዩ በጋራ ውይይት ሊፈታ ካልቻለ በነዳጅ ስምምነቱ ውስጥ በተመለከተው ሥነ ሥርዓት መሠረት በግልግል ዳኝነት ታይቶ ይወሰናል፡፡

26.<u>ተፈጻሚ ስለሚሆነው ሕግ</u>

የዚህ አዋጅ አንቀጽ 25 እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በነዳጅ ስምምነቶችና በነዳጅ ሥራዎች ላይ ሁሉ ተፈጻሚ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕግ ነው፡፡

27.<u>ከሌሎች ሕጎች ጋር ስላለው ቅራኔ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ በግልጽ የተጠቀሱ ጉዳዮችን በሚመለከት በጽሑፍ ያሉም ሆነ በልማድ ሲሰራባቸው የቆዩ ሕጎች ወይም መመሪያዎች፣ በተለይም የነዳጅ ሥራዎችን በሚመለከት የሚከተሉት ሕጎች፣ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፤

ሀ) የማዕድን አዋጅ ቁጥር 282/63

ለ) የማዕድን ደንብ ቁጥር 396/63

ሐ) የጋራ ልማት ማኅበር አዋጅ ቁጥር 235/75

28. **<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ፣</u>**

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ፣ መጋቢት 17 ቀን 1978 ዓ.ም**

**ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ**

**ደንብ ቁጥር 49/1991 ዓ.ም**

**የኤሌክትሪክ ሥራዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 4/1987 አንቀጽ 5 እና በኤሌክትሪክ አዋጅ ቁጥር 86/1989 አንቀጽ 28 (1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

1. **አጭርርዕስ**

   ይህ ደንብ "የኤሌክትሪክ ሥራዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 49/1991" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. "አዋጅ" ማለት የኤሌክትሪክ አዋጅ ቁጥር 86/1989[41] ሲሆን በአዋጁ ለተዘረዘሩት ቃላት የተሰጡት ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈፃሚ ይሆናሉ፤
   2. "ኤጀንሲ" ማለት የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኤጀንሲ ነው፤[42]
   3. "የማመንጫ ተቋም" ማለት ኤሌክትሪክ ለማመንጨት የሚያገለግል የቴክኖሎጂ ስብስብ ነው፤
   4. "ከፍተኛ የኃይል ፍላጎት" ማለት በኤሌክትሪክ ተጠቃሚዎች በተወሰነ የጊዜ ክልል ውስጥ የሚከሰት ከፍተኛው የፍጆታ መጠን ነው፤
   5. "ቋሚ የሲስተም ጭነት" ማለት በኃይል አቅርቦት ተቋም ላይ በተከታታይነት የሚታይ የፍጆታ መጠን ነው፤
   6. "ማርጅናል የማመንጫ አቅም ዋጋ" ማለት በኪሎዋት የሚተመን አንድ ተጨማሪ ኃይል ለማመንጨት የሚያስፈልግ ወጪ ነው፤

---

[41] በ20/12 (2006) አ. 810 ተሽሯል፡፡

[42] ይህ ኤጀንሲ የተቋቋመበት አዋጅ ቁጥር 86/1989 ከላይ እንደተገለፀው የተሻረ እና ኤጀንሲውም በደንብ ቁጥር 20/36 (2006) አ. 308 በተቋቋመው የኢትዮጵያ የኢነርጂ ባለስልጣን የተተካ እና መብት እና ግዴታውም የተላለፈ በመሆኑ ኤጀንሲው የሚለው ባለስልጣኑ በሚል እና መስሪያ ቤቱም የኢትዮጵያ የኢነርጂ ባለስልጣን በሚል ተተክቶ የሚነበብ ይሆናል፡፡ ውስጥ ደንቡ ዝርዝር ላይ ኤጀንሲው የሚለው ባለስልጣኑ በሚል ተተክቶ የሚነበብ ይሆናል፡፡

7. “ማርጅናል የኢነርጂ ዋጋ” ማለት በኪሎዋት ሰዓት የሚተመን አንድ ተጨማሪ ኢነርጂ ለማምረት የሚያስፈልግ ወጪ ነው፤
8. “የሲስተም ማመንጫ ዋጋ” ማለት በኃይል አቅርቦት ተቋም ውስጥ የተለያየ የማመንጫ ዋጋ ሊኖራቸው በሚችል የኤሌክትሪክ ማመንጫ ቴክኖሎጂዎች የሚመነጨውን ኢነርጂ የሚወክል አንድ የኢነርጂ ዋጋ ነው፤
9. “የሲስተም ማርጅናል ማስተላለፊያ አቅም ዋጋ” ማለት በኪሎዋት የሚለካ አንድ ተጨማሪ የኤሌክትሪክ ኃይል ለማስተላለፍና ትራንስፎርም ለማድረግ የሚያስፈልግ ወጪ ነው፤
10. “የሲስተም ማርጅናል የማከፋፈያ አቅም ዋጋ” ማለት በኪሎዋት የሚለካ አንድ ተጨማሪ የኤሌክትሪክ ኃይል ለማከፋፈልና ትራንስፎርም ለማድረግ የሚያስፈልግ ወጪ ነው፤
11. “ከፍተኛ ቮልቴጅ”ማለት ከ60,000 ቮልት በላይ የሆነ የቮልቴጅ መጠን ነው፤
12. “መካከለኛ ቮልቴጅ” ማለት ከ1000 በላይ እስከ 60,000 ቮልት የሆነ የቮልቴጅ መጠን ነው፤
13. “ዝቅተኛ ቮልቴጅ” ማለት እስከ 1000 ቮልት የሆነ የቮልቴጅ መጠን ነው፤
14. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

## ክፍል ሁለት

## ስለኤሌክትሪክ ሥራ ፈቃዶች

## ምዕራፍ አንድ

## ስለፈቃድ ማመልከቻዎች

3. ጠቅላላ

1. የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት፣ ለማስተላለፍ፣ ለማከፋፈልና ለመሸጥ፣ እንዲሁም ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ወይም ወደ ውጭ ለመላክ የሚያስችል ፈቃድ ለማግኘት ለኤጀንሲው የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡-

   ሀ) የአመልካቹን ማንነትና አድራሻ፤

   ለ) የፕሮጀክቱን የፊዚቢሊቲ ጥናት፤

   ሐ) የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት፤

መ) የአመልካቹን የፋይናንስ ሁኔታ፣ የቴክኒክ ብቃትና ልምድ የሚያሳዩ ሠነዶች፤

ሰ) የግንባታና ኢንስታሌሽን ዲዛይን፤ እና

ረ) ኤጀንሲው ያስፈልጋሉ ብሎ በመመሪያ የሚወስናቸው ሌሎች መረጃዎች።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ) የተመለከተው የፊዚቢሊቲ ጥናት የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፤

ሀ) የማህበራዊና ኢኮኖሚ ተፅዕኖ ጥናት፤

ለ) የፕሮጀክቱን ወጪና ገቢ ግምት፤

ሐ) ፕሮጀክቱ የሚቆይበትን ጊዜ፤

መ) የግንባታና የኢንስታሌሽን ፕሮግራምና አገልግሎት መስጠት የሚጀምርበትን ቀን።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሐ) የተመለከተው የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፤

ሀ) በአካባቢ ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ማናቸውንም ጉዳዮች እና እነዚህኑ ለማቃለል የሚያስችል እንዲሁም አካባቢውን ወደ ቀድሞው ሁኔታ ለመመለስ ወይም ለሌላ ጥቅም ለማዋል የሚያስችል ዕቅድና የሚፈናቀሉ ሰዎችን መልሶ የማቋቋሚያ ፕሮግራም፤

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ (ሀ) የተመለከቱትን ዕቅዶችና ፕሮግራሞች ለመተግበር የሚያስፈልገውን ወጪግምት፡፡

4. የዚህ ደንብ አንቀጽ 9 እና 10 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም አመልካች ለኤጀንሲው የሚያቀርባቸው መረጃዎች በምስጢር መጠበቅ አለባቸው፡፡

4. <u>ለኤሌክትሪክ ማመንጨት ፈቃድ ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>

የኤሌክትሪክ ማመንጨት ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማናቸውም ማመልከቻ በዚህ ደንብ አንቀጽ 3 ከተመለከቱት አጠቃላይ ሁኔታዎች በተጨማሪ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፤

1. የኤሌክትሪክ መገኛውን ምንጭ፤

2. ኤጀንሲው በሚወስነው ስኬል መሠረት የተዘጋጀ የፕሮጀክቱን ቦታ የሚያሳይ ካርታ፤

3. የኤሌክትሪክ ፕሮጀክቱ አጠቃላይ የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት አቅም፤
4. እንደአግባቡ የኤሌክትሪክ ኃይል ግዢ ውል፡፡

5. <u>**የኤሌክትሪክ ማስተላለፍ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ**</u>

የኤሌክትሪክ ማስተላለፍ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ በዚህ ደንብ አንቀጽ 3 ከተመለከቱት አጠቃላይ ሁኔታዎች በተጨማሪ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፤

1. ዋናና አማራጭ የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ መስመሮች አቋርጠው ሚያልፉባቸውን ሥፍራዎች የሚጠቁም ካርታ፤
2. የማስተላለፊያ መስመሮች ጠቅላላ ርዝመትና የሚያስተላልፉት ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል ጭነት መጠን፤
3. የቮልቴጁን ደረጃና ፍሪኩዌንሲ፡፡

6. <u>**ኤሌክትሪክ ለማከፋፈልና ለመሸጥ ፈቃድ ስለሚቀርብ ማመልከቻ**</u>

የኤሌክትሪክ ማከፋፈልና መሸጥ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ በዚህ ደንብ አንቀጽ 3 ከተመለከቱት አጠቃላይ ሁኔታዎች በተጨማሪ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፤

1. የማከፋፈያ ጣቢያው ኤሌክትሪክ የሚያገኝበትን ምንጭ፤
2. ከፕሮጀክቱ ተጠቃሚ ይሆናሉ ተብለው የሚገመቱ ደንበኞችን ብዛትና የኤሌክትሪክ ኃይል መሸጫ ዋጋ፤
3. እንደአግባቡ የኤሌክትሪክ ኃይል ግዥ ውል፡፡

7. <u>**ለኤሌክትሪክ አስመጭነት ወይም ላኪነት ፈቃድ ስለሚቀርብ ማመልከቻ**</u>

ኤሌክትሪክ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ወይም ወደ ውጭ ሀገር ለመላክ የሚያስችል ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ በዚህ ደንብ አንቀጽ 3 ከተመለከቱ አግባብ ካላቸው አጠቃላይ ሁኔታዎች በተጨማሪ የሚከተሉትንመያዝ አለበት፤

1. ኤሌክትሪክ ከሚያስመጣበት ወይም ከሚልክበት ሀገር ጉዳዩ ከሚመለከተው ባለሥልጣን ጋር የተደረገስምምነት፤
2. የቮልቴጁንና የፍሪኩዌንሲውን ደረጃ፤
3. እንደአግባቡ የኤሌክትሪክ ኃይል ግዢ ውል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## ስለማመልከቻ ምዝገባና ማስታወቂያ

8. ***ማመልከቻን ስለመመዝገብ***

እያንዳንዱ ማመልከቻ በዚህ ደንብ ምዕራፍ አንድ መሠረት በትክክለኛው ፎርም ተሟልቶ ሲቀርብ ኤጀንሲው ለዚሁ ተግባር ባዘጋጀው መዝገብ ላይ እንደአቀራረቡ ቅደም ተከተል ወዲያውኑ ይመዘግበዋል፤ እያንዳንዱ አመልካችም የምዝገባውን ቀንና ቁጥሩን የሚገልጽ ደረሰኝ ይሰጠዋል፡፡

9. ***ማመልከቻን ስለማስታወቅ***

1. ፈቃድ ለማግኘት የቀረበው ማመልከቻ ማስታወቂያ በሀገሪቱ ውስጥ ሰፊ ስርጭት ባላቸው ጋዜጦች በሁለት ተከታታይ እትሞች እንዲወጣ ኤጀንሲው ማመልከቻው በተመዘገበ በሦስት የሥራ ቀናት ውስጥ ማስታቂያውን ለሚመለከተው አሳታሚ ይልካል፡፡
2. ማስታወቂያው የፈቃዱን ዓይነት፣ ዓላማና የፈቃዱን ሥፍራ የሚገልጽና የካርታ ቅጅዎች የሚታዩበትን ወይም የሚገዙበትን አድራሻና ጉዳዩ ይመለከተኛል የሚል ማናቸውም ሰው ያለውን ተቃውሞ ወይም አስተያየት የሚያቀርብበትን የኤጀንሲውን አድራሻ የሚገልጽ መሆን አለበት።
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማስታወቂያው ለሦስት ተከታታይ ቀናት በሬዲዮና በቴሌቪዥን መነገር አለበት፡፡
4. አመልካቹ ለማስታወቂያው የሚያስፈልጉትን ወጪዎች በሙሉ ይሸፍናል፡፡

10. ***የካርታዎችን ቅጅዎች በይፋ እንዲታዩ ስለማድረግ***

አመልካቹ የፈቃዱን ሥፍራ የሚያሳዩት የካርታ ቅጅዎች በይፋ እንዲታዩ በኤጀንሲው ቢሮና ፈቃዱ በተጠየቀበት አካባቢ ባለ የከተማ መስተዳደር ጽ/ቤት ማስቀመጥ አለበት።

11. ***መቃወሚያዎችን ስለማቅረብ***

1. ማንኛውም ጉዳዩ ይመለከተኛል የሚል ሰው ማስታወቂያው በጋዜጣ ለመጨረሻ ጊዜ ከወጣበት ቀን ጀምሮባሉት 60 ቀናት ውስጥ በተጠየቀው ፈቃድ ላይ ያለውን ተቃውሞ ወይም አስተያየት ከነምክንያቶቹ በጽሁፍ ለኤጀንሲው ሊያቀርብ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የቀረበ መቃወሚያ ውድቅ ከተደረገ ኤጀንሲው ውሳኔውን ከነምክንያቱ በጽሑፍ ገልጾ ለተቃዋሚው እንዲደርሰው ያደርጋል፡፡

12. **ማመልከቻን ስለማሻሻል**

ማመልከቻውን ለማሻሻል የሚፈልግ ማናቸውም አመልካች ማሻሻያውን ለኤጀንሲው በጽሁፍ ማቅረብ አለበት፡፡ የዚህ ምዕራፍ ድንጋጌዎች በቀረበው ማሻሻያ ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## ፈቃድ ስለመስጠትና ስለመከልከል

13. **ፈቃድ ስለመስጠት**

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 11 በተጠቀሰው የ60 ቀናት ጊዜ ውስጥ ከማመልከቻው ላይ ምንም ዓይነት መቃወሚያ ካልቀረበና ኤጀንሲው በአመልካቹ የተጠየቀው ፈቃድ የሚያስከትላቸውን ግዴታዎች ለመወጣት የሚያስችል የፋይናንስ ምንጭ፣ የቴክኒክ ችሎታና ልምድ አመልካቹ ያለው መሆኑን ሲያምንበት የተወሰነውን ክፍያ በማስከፈል በ30 ቀናት ውስጥ ፈቃዱን ይሰጠዋል፡፡
2. በዚህ ደንብ አንቀጽ 11 መሠረት በማመልከቻው ላይ ተቀውሞ ከቀረበ ፈቃድ የመስጠቱ ሂደት ማመልከቻው በኤጀንሲው ከተመዘገበ ከ120 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በተቃውሞው ላይ ውሳኔ እስከሚሰጥበትድረስ ይዘገያል፡፡ የተሰጠው ውሳኔ ተቃውሞውን ውድቅ የሚያደርግ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካቹ ወዲያውኑ ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡
3. አመልካቹ አግባብ ባለው የኢንቨስትመንት ሕግ መሠረት ኢንቨስት ለማድረግ የሚፈቀድለት ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ መሠረት ፈቃድ አይሰጠውም፡፡

14. **ፈቃድን ስለመከልከል**

1. ኤጀንሲው የቀረበው ማመልከቻ ወይም ተያይዞ የቀረበው መረጃ ወይም የአመልካቹ የፋይናንስ አቅም የቴክኒክ ችሎታና ልምድ በቂ አይደለም ብሎ ከወሰነ ይህንኑ ከነምክንያቱ ለአመልካቹ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡
2. አመልካቹ የሚደግፉትን መረጃዎች ለማቅረብ እንዲችል ኤጀንሲውን የማማከር ዕድልና የቀረበበትን ተቃውሞ ለመቋቋም ከ30 ቀናት ያላነሰ ጊዜ ይሰጠዋል፤ እንዲሁም ማመልከቻውን የማረም ወይም የማሟላት መብት ይኖረዋል።

3. አመልካቹ የኤጀንሲውን ምክር ካገኘና የተሰጠው ጊዜ ካለፈም በኋላ ኤጀንሲው ማመልከቻው ወይም የቀረበው መረጃ ወይም የአመልካቹ ችሎታ የጠየቀውን ፈቃድ ለመስጠት የማያበቃ መሆኑን ሲያምንበት ይህንኑ ለአመልካቹ በጽሁፍ ያሳውቀዋል፡፡

15.**የፈቃድ ቅጅ ስለመስጠትና ስለመተካት**

1. ባለፈቃዱ የተወሰነውን ክፍያ በመክፈል አንድ ወይም ተጨማሪ የፈቃዱን ቅጂዎች እንዲሰጠው ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ኤጀንሲውም ጥያቄው እንደደረሰው የፈቃዱን የተረጋገጠ ቅጂ አዘጋጅቶ መስጠት አለበት፡፡
2. ባለፈቃዱ የተወሰነውን ክፍያ ከፍሎ የጠፋበትን ወይም የተበላሸበትን ፈቃድ ምትክ እንዲሰጠው ኤጀንሲውን ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ኤጀንሲውም ጥያቄው እንደደረሰው የጠፋውን ወይም የተበላሸውን ፈቃድ ምትክ አዘጋጅቶ መስጠት አለበት፡፡

16.**ፈቃድ ስለማስተላለፍ**

ማንኛውም ባለፈቃድ በአዋጁ አንቀጽ 12 ድንጋጌዎች መሠረት ፈቃዱን ሊያስተላልፍ ይችላል፤ ሆኖም ፈቃዱ የሚተላለፍለት ሰው በፈቃዱ የተመለከቱትን ግዴታዎች ለመወጣት የሚያስችል ብቃት ያለው መሆን አለበት፡፡

17.**ፈቃድ ስለማሻሻል**

ማንኛውም ባለፈቃድ ፈቃዱን ለማሻሻል ከፈለገ ለኤጀንሲው በጽሁፍ ያመለክታል፡፡ በማመልከቻው ላይም የዚህ ክፍል ምዕራፍ ሁለት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

18.**ስለፈቃድ ዘመንና እድሳት**

1. በአዋጁናበዚህ ደንብ መሰረት የሚሰጥፈቃድጸንቶ የሚቆይበት ዘመን በፕሮጀክቱ ዕድሜ ላይ የተመሠረተሆኖ ጣሪያው እንደሚከተለውይሆናል፤
   ሀ) ለኃይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ፈቃድ ...................... 40 ዓመት
   ለ) ለኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ፈቃድ ............................... 50 ዓመት
   ሐ) ለኤሌክትሪክ ኃይል ማከፋፈልና መሸጥ ፈቃድ ...................... 50 ዓመት
   መ) ለኤሌክትሪክ አስመጭነት ወይም ላኪነት ፈቃድ ................... 10 ዓመት
2. ከኃይድሮ ውጭ ለሌሎች ኃይል ማመንጫዎች የፈቃድ ዘመን ጣሪያ በሚኒስቴሩ በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

3. ማናቸውም ባለፈቃድ፦
   ሀ) የፈቃዱ ዘመን ከማለቁ ሁለት ዓመት በፊት ፈቃዱ እንዲታደስለት ከጠየቀ፤
   ለ) የአዋጁን፣ የዚህን ደንብና በእነዚሁ መሠረት የሚወጡ መመሪያዎችን በመተላለፍ ፈቃዱን ለመሰረዝ የሚያበቃ ጥፋት ካልፈጸመ፤ እና
   ሐ) የሥራውን ደረጃ የኤሌክትሪክ ኢንዱስትሪ በወቅቱ በደረሰበት ዘመናዊ ቴክኖሎጂና አጠቃላይ ተቀባይነት ባለው የአሠራር ልምድ ለማሳደግ ከተስማማ፤

   ፈቃዱ በተከታታይ ሊታደስለት ይችላል፤ ሆኖም እያንዳንዱ የእድሳት ዘመን ከፈቃዱ የመጀመሪያ ዘመን ግማሽ በላይ ሊሆን አይችልም።
4. የዚህ ክፍል ምዕራፍ ሁለት ድንጋጌዎች በፈቃድ እድሣት ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

19. <u>ፈቃድን ስለመሰረዝ</u>

የአዋጁ አንቀጽ 14 (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ባለፈቃዱ ከሚከተሉት ጥፋቶች አንዱን ከፈጸመ ፈቃዱ ሊሰረዝበት ይችላል፤

1. የቴክኒክ ደረጃዎችን ካልጠበቀ፣ የደኅንነት መመሪያዎችንና የአካባቢ ጥበቃ ሕጎችን ካላከበረ፤
2. የታሪፍ ደንቦችን ካላከበረ፤
3. ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ የኤሌክትሪክ አቅርቦትን በተደጋጋሚ ካቋረጠ፣ ከቀነሰ ወይም ካቆመ።

20. <u>ስለፈቃድ መቋረጥ</u>

1. ፈቃድ በሚከተሉት ሁኔታዎች ይቋረጣል፤
   ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ 18 መሠረት ሳይታደስ ከቀረ፤
   ለ) በዚህ ደንብ አንቀጽ 19 ድንጋጌዎች መሠረት በኤጀንሲው ከተሰረዘ፤
   ሐ) የወራሾች መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ባለፈቃዱ ከሞተ ወይም ባለፈቃዱ የንግድ ድርጅት ሲሆን ከፈረሰ ወይም የመክሰር ውሳኔ ከተሰጠበት፡፡
2. ፈቃዱ ሲቋረጥ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦቱ ሳይቋረጥ እንዲቀጥል ለማድረግ የግድ አስፈላጊ የሆኑ የባለፈቃዱን የኤሌክትሪክ ተቋሞች መንግሥት ከመጽሐፍ ወይምከመተኪያ ዋጋቸው አነስተኛ በሆነው ስሌት ላይ የተመሠረተ የካሣ ክፍያ በማሳብ ሊወስድ ይችላል፡፡

3. ተቋሞቹ ከአገልግሎት ውጭ በመሆናቸው መንግሥት ሊወስዳቸው ካልፈለገ ባለፈቃዱ በራሱ ወጭ ተቋሞቹን ማስወገደ አለበት፡፡

21.**ስለፈቃድ ክፍያዎች**

1. የኤሌክትሪክ ሥራ ፈቃድ ለማውጣት የሚጠይቅ ማንኛውም አመልካች የፈቃድ ማመልከቻው ሲመዘገብ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚጠየቀውን የፈቃድ ክፍያ 20 ፐርሰንት በቅድሚያ ይከፍላል፤ ሆኖም አመልካቹ በዚህ ደንብ አንቀጽ 14 መሠረት ፈቃድ የሚከለከል ከሆነ ክፍያው አይመለስለትም፡፡
2. ለኤሌክትሪክ ማመንጨት ፈቃድ የሚጠየቀው ክፍያ በእያንዳንዱ ኪሎ ዋት ብር 1 ይሆናል፤ ሆኖም ዝቅተኛው ክፍያ ብር 1,000 ይሆናል፡፡
3. ለኤሌክትሪክ ማስተላለፍ ፈቃድ የሚጠየቀው ክፍያ በእያንዳንዱ ሰርኪዩት ኪሎ ሜትር ብር 20 ይሆናል፤ ሆኖም ዝቅተኛው ክፍያ ብር 2,000 ይሆናል፡፡
4. ለኤሌክትሪክ ማከፋፈልና መሸጥ ፈቃድ የሚጠየቀው ክፍያ በእያንዳንዱ ኪሎ ቮልት አምፒር የትራንስፎርመር አቅም ብር 2 ይሆናል፤ ሆኖም ዝቅተኛው ክፍያ ብር 1,000 ይሆናል፡፡
5. ለኤሌክትሪክ አስመጭነት ወይም ላኪነት ፈቃድ የሚጠየቅ ክፍያ በሜጋዋት ሰዓት ብር 1 ይሆናል፤ ሆኖም ዝቅተኛው ክፍያ ብር 2,000 ይሆናል፡፡
6. ፈቃድን ለማሻሻል ወይም ለማሳደስ የሚጠየቀው ክፍያ ለፈቃዱ ማውጫ የሚጠየቀው ክፍያ 50 ፐርሰንት ይሆናል።
7. ፈቃድ ለማስተላለፍ የሚጠየቀው ክፍያ ለፈቃዱ ማውጫ የሚጠየቀው ክፍያ 20 ፐርሰንት ይሆናል፡፡
8. የፈቃድ ቅጅ ወይም ምትክ ለመስጠት የሚጠየቀው ክፍያ ብር 150 ይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የባለፈቃዶች እና የደንበኞች ግዴታዎች

22.**የባለፈቃዶች መብት**

ባለፈቃዶች የሚከተሉት መብቶች ይኖሯቸዋል፤

1. የኤሌክትሪክ ሥራዎችን ለማካሄድ በፈቃዱ ወደተሸፈነው ክልል የመግባት፤
2. የዚህን ደንብ ድንጋጌዎችና በዚህ ደንብ መሠረት የወጡ መመሪያዎችን ለሚጥሱ ደንበኞች ማስጠንቀቂያ በመስጠት የኤሌክትሪክ አቅርቦትን የማቋረጥ፤
3. የደንበኞችን የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን የመመርመር፡፡

## 23.የባለፈቃዶች ግዴታ

ባለፈቃዶች የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሯቸዋል፤

1. በአዋጁ፣ በዚህ ደንብና በነዚሁ መሠረት በሚመጡ መመሪያዎች እና በፈቃዱ በተመለከቱት ግዴታዎች መሠረት የኤሌክትሪክ ሥራዎችን ማካሄድ፤
2. የሰውን ሕይወት፣ የንብረትና የአካባቢን ደኅንነት ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ የጥንቃቄ እርምጃዎችን የመወሰድ፤
3. ለደንበኞች የማያቋርጥ የኤሌክትሪክ አገልግሎት የመስጠት፤
4. በፈቃዱ ክልል የሚገኙ አዲስ ደንበኞች የሚያቀርቡትን የአገልግሎት መስመር የማስቀጠል ጥያቄ በፍጥነት የማስተናገድ፤
5. ኤሌክትሪክ ከመቋረጡ በፊት ለደንበኞች የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ የመስጠት፤
6. በአዋጁ አንቀጽ 16 የተመለከቱት ኤሌክትሪክ ለማቋረጥ የሚያስችሉ ምክንያቶች እንደተወገዱ የኤሌክትሪክ አገልግሎቱን ወዲያውኑ የመጀመር፤
7. ስለ ኤሌክትሪክ አጠቃቀም ለደንበኞች አስፈላጊውን መመሪያ የመስጠት፤
8. ደንበኞች ለሚያቀርቡት አቤቱታ ወዲያውኑ ምላሽ የመስጠት፤
9. የቅጥር፣ የገንዘብ፣ የንግድና ሌሎች የሂሣብ መዛግብትና ስለኤሌክትሪክ ሥራዎች ሪኮርዶች የመያዝና በመመሪያ በሚወሰነው መሠረት በየወቅቱ ሪፖርት የማቅረብ፤
10. ማንኛውንም መዛግብትና ሪከርዶችን ለኤጀንው ምርመራ የማቅረብ፤
11. ለኤሌክትሪክ ሥራ አስፈላጊ የሆነውን ሥልጠናና ትምህርት ለሠራተኞቻቸው የመስጠት፤
12. በዋጋቸው ተወዳዳሪና በጥራታቸው ተመጣጣኝ ደረጃ ላላቸው፤ በሚፈለገውም መጠን ለሚገኙ የሀገር ውስጥ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ቅድሚያ የመስጠት።

## 24.የደንበኞች መብት

ደንበኞች የሚከተሉት መብቶች ይኖሯቸዋል፡-

1. ከባለፈቃዶች ያልተቋረጠ፣ ከአደጋ የተጠበቀና ጥራት ያለው የኤሌክትሪክ አቅርቦት የማግኘት፤
2. የኤሌክትሪክ አገልግሎትን የሚመለከቱ አቤቱታዎችን እንደ ነገሩ አግባብነት ለባለፈቃዱ ወይም ለኤጀንሲው የማቅረብ፡፡

25.**የደንበኞች ግዴታ**

ደንበኞች የሚከተለው ግዴታዎች ይኖሯቸዋል፡-

1. ስለኤሌክትሪክ አጠቃቀም የሚሰጡ ማስታወቂያዎችንና መመሪያዎችን የማክበር፤
2. የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን፣ ጥገና፣ ምርመራና የቆጣሪ ንባብ ሥራዎች ሲካሄዱ አስፈላጊውን ትብብር የማድረግ፤
3. ማናቸውም የኤሌክትሪክ ብልሽት ሲያጋጥም ወዲያውኑ ለባለፈቃዱ የማሳወቅ፡፡

## ክፍል አራት

## ስለ ኤሌክትሪክ ዋጋና ታሪፍ

26.**አጠቃላይ መርህ**

1. የኤሌክትሪክ ዋጋ አተማመን ሀብትን በብቃት በመጠቀም መርህ ላይ ተመስርቶ ተጠቃሚዎችና አምራቾች ተጨማሪ የኢነርጂ ምርትና ፍጆታ የሚያስከትለውን ትክክለኛውን የፍጆታና የማምረቻ ዋጋ በሚያገኙበት መልክ ይከናወናል፡፡
2. በደንበኞች ላይ የሚጣለው የአቅርቦት ዋጋ በሲስተሙ ላይ ከሚያስከትለው የወጪ ተጽዕኖ አንፃር ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ሆኖ የኢነርጂ አጠቃቀሙን በተቻለ መጠን ምርቱን ለማስገኘት ከሚወጣው ወጪ አንፃር ሚዛናዊ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ ይሆናል፡፡
3. የዋጋ ተመኑ በቂና ቀጣይነት ያለው የመዋዕለ ንዋይ ምንጭ ለማስገኘትና አስተማማኝ አገልግሎት ለማቅረብ የሚያስችል ሆኖ፤ የአገልግሎት ብቃትን ለማሻሻል የሚያስችል የዋጋ አተማመን ሥርዓት መያዝ አለበት፡፡
4. ዝርዝር የታሪፍ መደቦች አወጣጥ የአፈጻጸም ችግሮችን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ እንዲያስችል በተቻለ መጠን ያልተወሳሰበ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

27.**የዋጋ አተማመን አጠቃላይ ስልቶች**

1. ለጅምላም ሆነ ለችርቻሮ ተጠቃሚዎች የኢነርጂና የኃይል አቅርቦት ዋጋ የሚተመነው፡-
   ሀ) በሲስተሙ ላይ የተወሰነ ተጨማሪ ኃይል ወይም ኢነርጂ ለማመንጨት በሚደረገው ወጪ፤ እና
   ለ) በሲስተሙ የከፍተኛ ውጤታማነት ዕቅድ ላይ የተመሰረተ ሆኖ አስፈላጊ ነው ተብሎ በሚወሰነው ገደብ የፋይናንስ ፍላጎትን ሊያሟላ በሚችል መልኩ ሊስተካከል ይችላል፡፡

2. ከብሔራዊ ግሪድ ውጭ ለሚደረግ የዋጋ አተማመን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ስልት በቴክኒካዊ ምክንያት ተግባራዊ ሊሆን የማይችል ሲሆን የአቅርቦት ዋጋ አተማመኑ፤
   ሀ) በአማካይ የአቅርቦት ዋጋ፤ እና
   ለ) ተቀባይነት ባለው የትርፍ መጠን፤
   ላይ ይመሠረታል፡፡

28.<u>የማመንጫ ዋጋ አተማመን</u>

1. በብሔራዊ ግሪድ ሲስተም ውስጥ የኃይል ማመንጫ ዋጋ አተማመንን በሚመለከት፡-
   ሀ) ማርጅናል የኃይል ማመንጫ ዋጋ የሚተመነው የሲስተሙን ከፍተኛ የኃይል ፍላጎት ለመሸፈን ይችላል ተብሎ በሚገመት ከፍተኛ ብቃት ባለው የማመንጫ ተቋም ዋጋ ላይ ተመስርቶ ይሆናል፤
   ለ) የኢነርጂ ዋጋ የሚተመነው ቋሚ የሲስተም ጭነትን ለመሸፈን ይችላል ተብሎ በሚገመተው ከፍተኛ ብቃት ባለው የማመንጫ ተቋም ዋጋ ላይ ተመስርቶ ይሆናል፣
   ሐ) ለውኃ ኃይል ማመንጫ ማርጅናል የኢነርጂ ዋጋ የሚተመነው ከአጠቃላይ ወጪው ላይ የኃይል አቅርቦት ዋጋ ተቀንሶ በሚቀረው ዋጋ ላይ በመመስረት ይሆናል፡፡
   መ) በነዳጅ የሚንቀሳቀስ የኃይል ማመንጫ ወጪ እንዲሁም በጅምላ ግዥ የሚገኝ የኃይልና የኢነርጂ ዋጋ በማመንጨት ዕቅድ ላይ በመመስረት ተተምኖ በሲስተሙ የማመንጨት ዋጋ ላይ ይከፋፈላል፡፡
2. ከብሔራዊ ግሪድ ሲስተም ውጭ የማመንጫ ዋጋ አተማመንን በሚመለከት፡-
   ሀ) ማርጅናል የማመንጫ አቅም ዋጋ የሚተመነው የገበያውን ፍላጎት ሊሸፍን በሚችል ከፍተኛ ብቃት ባለው የማመንጫ ተቋም ዋጋ ላይ ተመስርቶ ይሆናል፤
   ለ) ለእያንዳንዱ የማመንጫ ተቋም ማርጅናል የኢነርጂ ዋጋ ይተመናል፤
   ሐ) ለአነስተኛ የውኃ ኃይል ማመንጫ ተቋማት እንደ አግባብነቱ በብሔራዊ ግሪድ ሲስተም ውስጥ ላሉት የውኃ ኃይል ማመንጫ ተቋማት የሚሠራበት የዋጋ አተማመን ሊወሰድ ይችላል፤

መ) ለየማመንጫው የተተመነው ዋጋ በአቅርቦት ክልል ውስጥ ለማመንጨት በታቀደው የኢነርጂ መጠን አኳያ በአቅርቦቱ አጠቃላይ ዋጋ ላይ እንዲበተን ይደረጋል፤ ይህ ዋጋ እንደአስፈላጊነቱ በየጊዜው በኤጀንሲው ይገመገማል፤

ሠ) በነጻጅ ኃይል የሚሠሩ የኃይል ማመንጫዎች በበቂ ደረጃ የሚገኙበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የሚያስችል ተገቢ የማበረታቻና የመቅጫ ስልቶች በዋጋ አተማመኑ እንዲካተቱ ይደረጋል።

3. ከግል አምራቾች በጅምላ የሚገዛ ኃይልና ኢነርጂ ዋጋ ኤጀንሲው በሚያጸድቀው የግዢ ውል መሠረት የሚተመን ሆኖ ወደ ተጠቃሚ ደንበኞች በቀጥታ የሚተላለፍ ይሆናል፡፡

29. <u>የኃይል ማስተላለፊያ ዋጋ አተማመን</u>

1. በብሔሪዊ ግሪድ ሲስተም ውስጥ የኃይል ማስተላለፊያ ዋጋ አተማመንን በሚመለከት የሲስተም ማርጅናል ማስተላለፊያ አቅም ዋጋ ለማስተላለፊያ ዋጋ አተማመን መሠረት ይሆናል፡፡

2. ከብሔራዊ ግሪድ ሲስተም ውጭ የኃይል ማስተላለፊያ ዋጋ አተማመንን በሚመለከት፤ የሲስተሙ የኃይል ማስተላለፊያ ዋጋ የሚተመነው በሂሣብ አያያዝ በተደረሰበት ግምታዊ ወይም የተረጋገጠ ወጪ እና ተቀባይነት ባለው የትርፍ መጠን ላይ ተመስርቶ ይሆናል፡፡

30. <u>የኃይል ማከፋፈያ ዋጋ አተማመን</u>

1. በብሔራዊ ግሪድ ሲስተም ውስጥ የኃይል ማከፋፈያ ዋጋ አተማመንን በሚመለከት የሲስተም ማርጅናል የማከፋፈል አቅም ዋጋ ለማከፋፈያ ዋጋ አተማመን መሠረት ይሆናል፡፡

2. ከብሔራዊ ግሪድ ሲስተም ውጭ የኃይል ማከፋፈያ ዋጋ አተማመንን በሚመለከት የሲስተሙ የኃይል ማከፋፈያ ዋጋ የሚተመነው በሂሣብ አያያዝ በተደረሰበት ግምታዊ ወይም የተረጋገጠ ወጭ እና ተቀባይነት ባለው የኢንቨስትመንት ምላሽ መጠን ላይ ተመስርቶ ይሆናል፡፡

3. በደንበኞች ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው ታሪፍ የሚወሰነው በሚጠቀሙበት ቮልቴጅ ደረጃ ተሰልቶ በሚገኘው የማከፋፈያ ወጪ ላይ የማመንጫና የማስተላለፊያ ወጪዎች ተደምረውበት ይሆናል፡፡

## 31.ሌሎች ክፍያዎች

1. የኃያልና ኢነርጂ ቆጣሪ ወጪዎችና የኤሌክትሪክ ፍጆታ ክፍያን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ወጪዎች ለደንበኞች አገልግሎት ዋጋ አተማመን መሠረት ይሆናሉ፡፡
2. የማስቀጠያ ክፍያ አዲስ የኃይል ጥያቄን ለደንበኛ ለማቅረብ በሚያስፈልገው ተጨማሪ ወጪ ላይ የሚመሠረት ይሆናል፡፡
3. የሪአክቲቭ ፍጆታ ክፍያ ፍጆታው በሚፈጸምበት ቮልቴጅ ደረጃ የእያንዳንዱ የሪአክቲቭ ፍጆታ ከሚፈጥረው የተጨማሪ አቅም ዋጋ ጋር እንዲገናዘብ ይደረጋል፡፡
4. ሌሎች እንደአስፈላጊነቱ የሚፈጸሙ ክፍያዎች በባለፈቃዶችና በደንበኞች መካከል የሚደረጉ ስምምነቶችን መሠረት በማድረግ ይፈጸማሉ።

## 32.ስለ አሠራር ብቃት መለኪያዎችና ስለዋጋ ትመና ሥርዓት

1. የኤሌክትሪክ አቅርቦትን የማሻሻል ዕድሎችን ለመጠቆሚያነት የሚያገለግሉና በአቅርቦት ዋጋዎች ላይ ተጽዕኖ ሊያስከትሉ የሚችሉ የማመንጫ፣ የማስተላለፊያና የማከፋፈያ የአሠራር ብቃት መለኪያዎችን ኤጀንሲው ከባለፈቃዶች ጋር በመመካከር ይወስናል፡፡
2. አግባብነት ያላቸውን የዋጋ መተመኛ መስፈርቶች ሁሉ አቀናጅቶ በመጠቀም የዚህን ክፍል ደንጋጌዎች ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ዝርዝር የዋጋ ትመና ሥርዓት በኤጀንሲው ይወሰናል፡፡

## 33.ስለዋጋ ወቅታዊ ማስተካከያዎችና ታሪፍ ክለሳ ጥናቶች

1. የማመንጫ፣ የማስተላለፊያና የማከፋፈያ ዋጋ ወቅታዊ ማስተካከያዎች ከሚመለከታቸው የምርት ግብአቶች ዋጋ ለውጥና ከአሠራር ብቃት መለኪያዎች አኳያ ይደረጋሉ፡፡
2. የዋጋ ወቅታዊ ማስተካከያ የሚደረግበት የጊዜ ገደብ በኤጀንሲው ይወሰናል፡፡
3. አጠቃላይ የታሪፍ ክለሳ ጥናት በየአራት ዓመቱ ይካሄዳል።

## 34.ስለሂሣብ መዝገብ አያያዝ

1. ተቀባይነት ካላቸው የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት አጠቃላይ መርሆች ጋር የተጣጣመና የዋጋ ቁጥጥር ሥርዓቱን ለመደገፍ የሚችል ሆኖ በባለፈቃዶች ሥራ ላይ የሚውል አንድ ወጥ የሆነ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት በኤጀንሲው ይወሰናል፡፡

2. ማንኛውም ባለፈቃድ የመንግሥት የበጀት ዓመት ባለቀ በስድስት ወራት ውስጥ በኦዲተር የተመረመረ የሂሳብ ሪፖርት ለኤጀንሲው ያቀርባል፡፡

## ክፍል አምስት

## የደኅንነት፣ የቴክኒክና የአገልግሎት ጥራት ደረጃዎች

## ምዕራፍ አንድ

## አጠቃላይ የደኅንነት መመሪያዎች

### 35.ስለኤሌክትሪክ አቅርቦት መስመሮችና መሣሪያዎች ደኅንነት

የኤሌክትሪክ አቅርቦት መስመሮችና መሣሪያዎች፤

1. በተዘረጉበት የአካባቢ ሁኔታዎች የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ በቂ ኃይል የመሸከምና የኢንሱሌሽን ብቃት እንዲሁም በብልሽት ወቅት ሊከሰት የሚችለውን የኤሌክትሪክ መጠን የመቋቋም ችሎታና በቂ የሜካኒካል ጥንካሬ ደረጃ ሊኖራቸው፤ እና
2. በሰው፣ በእንስሳትና በንብረት ላይ ጉዳት በማያስከትል ሁኔታ ሊገነቡ፣ ሊገጣጠሙ፣ ሊጠበቁና ሊጠገኑ ይገባል፡፡

### 36.ከተጠቃሚዎች ጋር ስለሚገናኙ የአገልግሎት መስመሮችና መሣሪያዎች

1. ማንኛውም ባለፈቃድ በደንበኛ ግቢ ውስጥ የሚገኙና የራሱ ንብረት የሆኑ ወይም በእርሱ ኃላፊነት ሥር የሆኑ የኤሌክትሪክ አቅርቦት መስመሮች ተገጣጣሚዎችና መሣሪያዎች አደጋ በማያስከትል ሁኔታ ለአገልግሎት ብቁ ሆነው መገኘታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡
2. ማንኛውም ደንበኛ በግቢው ውስጥ የሚገኙ የባለፈቃዱን መሣሪያዎች በተቻለው መጠን አደጋ በማያስከትሉ ሁኔታ በጥንቃቄ መጠበቅ አለበት፡፡

### 37.ታወሮችንና ምሰሶዎችን ግራውንድ ስለማድረግ

1. የኤሌክትሪክ መስመር ተሸካሚ ባለብረት ታወሮችና ምሰሶዎች ሁሉ ከእግሮቻቸው በአንዱ ላይ ግራውንድ የማድረግ ሥራ 20 ሚ.ሜ ስፋት ባለው የብረት ዘንግ መከናወን አለበት ፡፡
2. የታወሮች ማቆሚያ የሬዚስታንስ መጠንን ወደ 10 ኦምስ ዝቅ ማድረግ ካስፈለገ በእግሮቻቸው ላይ ተጨማሪ ግራውንድ የማድረግ ሥራ መከናወን አለበት፡፡
3. ከፍተኛ ሬዚስታንስ ባላቸው ልዩ በሆኑ ድንጋያማ አካባቢዎች የታወሮች ማቆሚያ ሬዚስታንስ እስከ 20 ኦምስ ሊደርስ ይችላል፡፡

4. ከመሬት በላይ የሚዘረጉ የኤሌክትሪክ መስመሮችን የሚሸከሙ የብረት ምሰሶዎች ወይም በብረት ዘንግ የተጠናከሩ የሲሚንቶ አርማታ ምሰሶዎች እንዲሁም ከመስመሩ ጋር ግንኙነት ያላቸው የብረታ ብረት ተገጣጣሚዎች፣ የትራንስፎርመር ኒውትራል እና የደንበኞች መቆጣጠሪያ ፓነሎች በሚያስተማምን ሁኔታ ግራውንድ መደረግ አለባቸው፡፡

38.**<u>የስዊቾችና የማቋረጫ መሣሪያዎች አቀማመጥ</u>**

ከመሬት ከተገናኘ ወይም ኒውትራል ሽቦና ኤሌክትሪክ የሚተላለፍባቸውን ሽቦዎች በአንድ ላይ ለማገናኘት ወይም ለማቋረጥ ተብሎ ከተዘጋጀ የማገናኛ ስዊች በስተቀር፣ ማንኛውም ሰርኪዩት ብሬከር፣ ማገናኛ ወይም ስዊች ለትራንፎርመርና ጀኔሬተር ሙከራ ተግባር ለማገናኘት ወይም ጀኔሬተር ወይም ትራንስፎርመርን ለመቆጣጠር ለሚደረግ ጥናት ካልሆነ በስተቀር በማናቸውም ዓይነት ሁኔታ ከባለሁለት ሽቦ መስመሮች ወይም ከባለበርካታ ሽቦ መስመሮች ኒውትራል ወይም ከመሬት ጋር ከተገናኘ ሽቦ ጋር መገጠም የለበትም፡፡

39.**<u>ስለ መከላከያ ሽቦዎች</u>**

1. ማንኛውም የመከላከያ ሽቦ፡-
   ሀ) የመበጠስ ጥንካሬ ከ635 ኪሎ ግራም ማነስ የለበትም፤
   ለ) ኤሌክትሪክ መተላለፍ በሚቋረጥባቸው ቦታዎች ላይ ከመሬት ጋር መያያዝ አለበት፤
   ሐ) ብረት ወይም ስቲል ከሆነ ጋልቫናይዝድ መሆን አለበት፡፡
2. ማናቸውም የመከላከያ ሽቦ ወይም ተጠላልፈው የተሠሩ የመከላከያ ሽቦዎች በአደጋ ወቅት ከሽቦዎች ጋር የተገናኘው የኤሌክትሪክ መሥመር እስኪወገድ ድረስ እንዳይቀልጡ በቂ ኤሌክትሪክ የመሸከም ችሎታ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

40.**<u>የቀለም ምልክቶች</u>**

ባለፈቃዱ ኤጀንሲው በሚያጠጣው መመሪያ መሠረት በማከፋፈያ ጣቢያዎች፣ በኔት ስቴሽኖችና በደንበኛው የማሠራጫ ባዝ ባሮች ላይ ከመሬት የተገናኙ ኒውትራል ሽቦዎችን ወይም ኃይል ከሚተላለፍባቸው መስመሮች ጋር የተያያዙ ሌሎች መስመሮችን መለየት በሚያስችል ሁኔታ ቋሚ የቀለም ምልክቶች ማድረግ ይኖርበታል፡፡

41.<u>ስለአደጋ መከላከያ መሣሪያዎችና መግልገያዎች</u>

1. በማንኛውም የመንገድ አካል ወይም ሕዝብ በብዛት ሊገኝ በሚችልበት ሌላ ሥፍራ፣ በፋብሪካ፣ በማዕድን ሥፍራ ወይም በማናቸውም ደንበኛ ግቢ ውስጥ ከምድር በላይ የሚዘረጋ የኤሌክትሪክ መስመር ኤጀንሲው ተቀባይነት ይኖራቸዋል ብሎ ያጸደቃቸው የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎች ሊገጠሙለት ይገባል፡፡
2. በደረቅና በንጹህ አሸዋ የተሞሉ የእሳት ማጥፊያ ባሊዎች፣ የእሳት ማጥፊያ መሣሪያዎችና የመጀመሪ ያዕርዳታ መስጫ ሣጥኖች ወይም መደርደሪያዎች በግልጽ ተጽፎባቸው በኤሌክትሪክ ማመንጫ ጣቢያዎች ውስጥ መቀመጥ አለባቸው፡፡
3. አምስትና ከዚያ በላይ ሜጋዋት የማመንጨት ችሎታ ባላቸው የኤሌክትሪክ ማመንጫ ጣቢያዎች እንዲሁም አምስትና ከዚያ በላይ ሜጋቮልት አምፒር አቅም ያላቸው ትራንስፎርመሮች ባሉባቸው የቤት ውስጥ ማከፋፈያ ጣቢያዎች ውስጥ እሳት ወይም ጢስ በሚያስከትል አደጋ ወቅት መጠቀም እንዲቻል በቂ ብዛት ያላቸው ጭንብሎች ግልጽ በሆነና በቀላሉ ሊደረስበት በሚችል ቦታ መቀመጥ አለባቸው፡፡

42.<u>ስለመብረቅ መከላከያ</u>

ለመብረቅ የተጋለጡ ከምድር በላይ የተዘረጉ የኤሌክትሪክ መስመሮች፣ የማከፋፈያ ጣቢያዎች ወይም የማመንጫ ጣቢያዎች ያሉት ማንኛውም ባለፈቃድ የመብረቅ ኤሌክትሪክን ፍሰት አቅጣጫ ወደ መሬት የሚመሩ ብቃት ያላቸው አስተማማኝ ዘዴዎችን በጥቅም ላይ ማዋል አለበት፡፡

43.<u>ስለአደጋ ማስጠንቀቂያ</u>

የከፍተኛ ቮልቴጅ ኢንስታሌሽን ያለው ባለፈቃድ በአማርኛ፣ በእንግሊዝኛና በአካባቢው ቋንቋ የተጻፈበትና የሰው የራስ ቅልና አጥንቶች አጽም ቅርጽ ያለበት የአደጋ ምልክት በጀኔሬተሮች፣ በትራንስፎርመሮች፣ በቀላሉ መወጣጣት በሚቻልባቸው ከምድር በላይ የተዘረጉ ምሰሶዎች እና በኤጀንሲው መመሪያ በሚወሰኑ ሌሎች ኢንስታሌሽኖች ላይ በግልጽ በሚታይና በዘላቂነት ሊቆይ በሚችልበት ሁኔታ መለጠፍ አለበት፡፡

**44.ስለኤሌክትሪክ ጉዳት ማስወገጃ መመሪያ**

1. ባለፈቃዱ በኤሌክትሪክ ንዝረት ለሚጎዱ ሰዎች አስቸኳይ ዕርዳታ ለመስጠት የሚረዳ በአማርኛ፣ በእንግሊዝኛና በአካባቢው ቋንቋ የተጻፈ መመሪያ በኤሌክትሪክ ማመንጫ ጣቢያዎች፣ በቤት ውስጥ የማከፋፈያና የመቆጣጠሪያ ጣቢያዎች እና በፋብሪካዎች ውስጥ ግልጽ በሆነ ቦታ ማስቀመጥ አለበት፡፡
2. ባለፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው መመሪያ ቅጂ እንዲሰጠው ለሚጠይቅ ማንኛውም ሰው በኤጀንሲው መመሪያ የተወሰነውን ክፍያ አስከፍሎ ይሰጠዋል።
3. በሰዎች በሚጠበቁ ባለከፍተኛ ቮልቴጅ ማመንጫ ጣቢያዎች፣ በማከፋፈያ ጣቢያዎችና በመቆጣጠሪያ ጣቢያዎች ውስጥ በጥሩ ሁኔታ የሚሠሩ የሰው ሠራሽ የመተንፈሻ መሣሪያዎች ሊኖሩ ይገባል፡፡

**45.ስለአደጋ ሪፖርት**

ከኤሌክትሪክ ማመንጨት፣ ማስተላለፍ፣ ማከፋፈል ወይም መጠቀም ጋር በተያያዘ ምክንያት በተከሰተ አደጋ በሰውና በእንስሳት ላይ የደረሰን ጉዳት ወይም የሕይወት መጥፋት ወይም የንብረት ጥፋት ባለፈቃዱ ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ 24 ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ለኤጀንሲው ሪፖርት ማድረግ አለበት።

**46.አገልግሎት ስላቋረጡ የኤሌክትሪክ መስመሮች**

የኤሌክትሪክ መስመሮች አገልግሎት መስጠታቸውን ካቋረጡ በኋላ ባለፈቃዱ አደጋ በማያስከትል ሁኔታ ተጠብቀው እንዲቆዩ ወይም እንዲወገዱ ማድረግ አለበት፡፡

**47.ክልከላዎች**

1. አምፖሎችን፣ ፋኖችን፣ ፊውዞችን፣ ማብሪያ ማጥፊያዎችን፣ የዝቅተኛ ቮልት የቤት ውስጥ የኤሌክትሪክ ቁሳቁሶችንና ተገጣጣሚዎችን ከመለወጥ በስተቀር በማገልገል ላይ ባለ የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ላይ በመጨመር፣ በመቀየር፣ በመጠገን ወይም በማስተካከል የኃይል ብቃቱን ወይም ባህሪውን የሚቀይሩ ሥራዎችን ከባለፈቃዱ ውጭ ወይም በባለፈቃዱ ስምምነትና በኤሌክትሪክ ሥራ ተቋራጭ ከሚሠራ ውውጭ በደንበኞቹ ግቢ ውስጥ ማከናወን የተከለከለ ነው፡፡
2. ከመሬት በላይ በተዘረጋ የኃይል መስመር ሥር ወይም መጠበቅ በሚገባው የጐን ርቀት ክልል ውስጥ ግንባታ ማከናወን ወይም ዛፎችን ማሳደግ የተከለከለ ነው፡፡

48.<u>የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽኖችን ስለመመርመርና ስለመፈተሽ</u>

ኤጀንሲው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የኤሌክትሪክ ማመንጫ ጣቢያዎችን፣ የማከፋፈያ ጣቢያዎችን፣ የማስተላለፊያ መስመሮችን፣ የመቆጣጠሪያ ጣቢያዎችንና ሌሎች የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽኖችን በማናቸውም ጊዜ ሊመረምርና ሊፈትሽ ይችላል፡፡

<u>ምዕራፍ ሁለት</u>

<u>ስለማስተላለፊያ መስመሮችና ማከፋፈያ ጣቢያዎች</u>

49.<u>የኤሌክትሪክ መስመር አቋርጦ ስለሚያልፍባቸው ሥፍራዎች</u>

የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ መስመር አቋርጦ የሚያልፍባቸው ሥፍራዎች በሚመረጡበት ወቅት የሚተላለፈው የኤሌክትሪክ ጭነት መጠንና ባህርይ፣ የኃይል ምንጩ አስተማማኝነት፣ የማከፋፈያ ጣቢያዎች አቀማመጥ፣ የአቅርቦቱ የወደፊት መስፋፋት ዕድል፣ የደኅንነትና የአካባቢ ተጽዕኖዎች እንዲሁም የግንባታና የሥራ ማስኬጃ ወጪዎች ከግምት ውስጥ መግባት አለባቸው፡፡

50.<u>ስለማስተላለፊያና የመከላከያ ሽቦዎች</u>

1. የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ሽቦዎች የሚጠበቅባቸውን የኤሌክትሪካል፣ መካኒካልና ኢኮኖሚያዊ መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው፡፡
2. የሽቦዎቹ መጠን የሚመረጠው በብሔራዊ ደረጃዎች ወይም ብሔራዊ ደረጃዎች ከሌሉ በኢንተርናሽናል ኤሌክትሮ ቴክኒካል ኮሚሽን ደረጃዎች ተስማሚነት ካላቸውና በደረጃዎቹ መስፈርቶች ከሚታቀፉት መካከል ይሆናል፡፡
3. የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) በመከተል የሚደረገው ምርጫ የኤጀንሲውን አጠቃላይ መመሪያ መሠረት አድርጎ መፈጸምና የተመረጡትን ሽቦዎች ኤሌክትሪክ የመሸከም ችሎታ፣ የኮሮናንና የሬዲዮ ጫጫታ የማስወገድ ብቃት፣ ቮልቴጅ የመቀነስ ሁኔታና ለሌሎች ቴክኒካዊ ጠባዮች በመፈተሽ መታገዝ አለበት፡፡

51.<u>ስለኢንሱሌተሮች</u>

1. ለተለያዩ መሣሪያዎች፣ ዕቃዎች፣ ስትራክቸሮች የሚያስፈልገው የኢንሱሌሽን ደረጃ የሚመረጠውና ሥራ ላይ የሚውለው የኢንሱሌተሮች ብልሽትና የአገልግሎት መቋረጥ ብዛት በኢኮኖሚያዊ መመዘኛ የተቀባይነትን ደረጃ ማሟላት እንዲችል ለማድረግ የኦቨር ቮልቴጅ መጠንና መስመሩን ከአደጋ

ለመከላከል የተገጠሙትን ልዩ ልዩ መሣሪያዎች ጠባያት ከግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚደረገው ምርጫ በብሔራዊ ደረጃዎች ወይም ብሔራዊ ደረጃዎች ከሌሉ በኢንተርናሽናል ኤሌክትሮ ቴክኒካል ኮሚሽን ደረጃዎች መሠረት ይፈጸማል፡፡

52.<u>ስለተገጣጣሚዎች</u>

ቦል አይና ሶኬት ካፕሊንግ፣ የኮኝክልስ፣ ክላምፕስ፣ አርኪንግ ሆርን፣ ቫይብሬሽን ዳምፐርና አርመር ሮድን የሚያካትቱ የቅጥልጥል ስኒዎች ተገጣጣሚዎች እንደ ቮልቴጅ መጠናቸው የብሔራዊ ደረጃዎችን ወይም ብሔራዊ ደረጃዎች ከሌሉ የኢንተርናሽናል ኤሌክትሮ ቴክኒካል ኮሚሽን ደረጃዎችን በጠበቀ ሁኔታ መመረጥ አለባቸው፡፡

53.<u>የፌዝ ሽቦዎችን ቦታ ስለመቀያየር</u>

የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ የፌዝ ሽቦዎችን ቦታ የመቀያየር ተግባር ለአጫጭር ርዝመት መስመሮች ከሆነ በየመካከሉ በሚገኙ የማከፋፈያ ጣቢያዎች ለባለ 132 ኪሎ ቮልትና ከዚያ በላይ ለሆኑ ረጃጅም መስመሮች ከሆነ እንደ ፌዞቹ አቀማመጥ አመቺ በሆነ ቦታ ላይ መከናወን ይኖርበታል፡፡

54.<u>ስለታወሮች ዲዛይን</u>

1. የከፍተኛ ቮልቴጅ ማስተላለፊያ ታወሮች የኤሌክትሪክ መስመሩ ይኖረዋል ተብሎ በሚገመተው ዕድሜ ወቅት ሊከሰቱ የሚችሉትን የሚከተሉትን ሸክሞች መቋቋም በሚችሉበት ሁኔታ ዲዛይን መደረግ አለባቸው፡-

   ሀ) የነፋስን ግፊት፣ የማስተላለፊያና የመከላከያ ሽቦዎችንና የቅጥልጥል ሲኒዎችን ክብደትና የሽቦዎችን ውጥረት፤

   ለ) በማስተላለፊያና መከላከያ ሽቦዎች መበጠስ ሳቢያ የሚከሰቱ የመዝመምና የመጠምዘዝ እንቅስቃሴዎች የሚያስከትሉትን ጭነት፤

   ሐ) በግንባታና በጥገና ሥራ ወቅት ሊከሰቱ የሚችሉ ጭነቶችን፡፡

2. የሽቦዎች ጥንካሬ የሚሰላው በማንኛውም ጊዜ ሊከሰት የሚችለውን የአየር ሙቀትና ቅዝቃዜ መጠንና የንፋስ ፍጥነት ከግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል፡፡

3. የታወር መጠን በሚተመንበት ጊዜ በፌዞች መካከል፣ በፌዞችና በሌሎች አካሎች መካከልና ከመሬት የሚኖረው የኤሌክትሪክ መስመር ርቀት፣ የቅጥልጥል

ስኒዎች ርዝመት እና የርግበትና የሺልድ መከላከያ ሽቦ አንግል ከግምት ውስጥ መግባት አለባቸው፡፡

4. የታወር መሠረት ዲዛይኖች በመደበኛ አገልግሎት ወቅት ከሚኖረው ጭነትና ከሽቦዎች መበጠስ ሁኔታ በእያንዳንዱ እግር የሚከሰተውን የአፐሊፍትና ኮምፕሬሽን ኃይል ከመቋቋምና አግባብነት ካላቸው የደኅንነት መስፈርቶች አንጻር መታየት ይኖርባቸዋል፡፡
5. የታወር ዲዛይን እንደአግባቡ የወደፊት ኃይል የማስተላለፍ ፍላጎት ዕድገትን በማገናዘብ መሠራት አለበት፡፡

55.<u>ኃይል በሚተላለፍባቸውና በማይተላለፍባው አካላት መካከል መጠበቅ ስለሚገባው ርቀት</u>

የኤሌክትሪክ ኃይል በሚተላለፍባቸውና ከመሬት ጋር በተገናኙ ኃይል በማይተላለፍባቸው አካላት መካከል መኖር የሚገባው ዝቅተኛ ርቀት በኤጀንሲው መመሪያ መሠረት ይወሰናል፡፡

56.<u>በፌዞች መካከል መጠበቅ ስለሚገባው ርቀት</u>

በኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ወይም በመከላከያ ሽቦዎች መካከል መጠበቅ የሚገባው ርቀት የሚወሰነው በከፍተኛ ሙቀት ወቅት ሽቦዎች የሚኖራቸውን የርግበት መጠን የቅጥልጥል ሲኒዎችን ርዝመት ከግምት ውስጥ በማስገባትና ኤጀንሲው የወሰነውን ስታንዳርድ በመከተል ይሆናል፡፡

57.<u>ከምድር፣ ከመንገዶችና ለመጓጓዣነት ከሚያገለግሉ የውኃ አካላት መጠበቅ ስለሚገባው ርቀት</u>

1. የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ሽቦዎች፣ በሚተላለፍባቸውና በማይተላለፍባቸው አካላት መካከል ሊኖር ከሚገባው ዝቅተኛ ርቀት በተጨማሪ በከፍተኛ የአየር ሙቀት ወቅት ከምድር ወይም ከውኃ ወለል በላይ ቢያንስ የ5 ሜትር ከፍታ ሊኖራቸው ይገባል፡፡
2. የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ሽቦዎች ከመንገድ ወለል በላይ ሊኖራቸው የሚገባው ከፍታ፡-
   ሀ) በከፍተኛ የአየር ሙቀት ወቅት ከ8 ሜትር፤ እና
   ለ) በአጎራባች ታወሮች ላይ የተወጠሩ ሽቦዎች በሚበጠሱበት አጋጣሚ መጠበቅ የሚገባው ርቀት ከ7 ሜትር ማነስ የለበትም፡፡

3. በካናሎችና በሌሎች ለመጓጓዣነት ከሚያገለግሉ የውሃ አካሎች በላይ የሚዘረጉ የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ሽቦዎች ኃይል በሚተላለፍባቸውና በማይተላለፍባቸው አካላት መካከል ሊኖር ከሚገባው ዝቅተኛ ርቀት በተጨማሪ፤ በከፍተኛ የአየር ሙቀት ወቅት በከፍተኛው የውኃው አካል ላይ ከሚንቀሳቀሰው ማጓጓዣ ከፍተኛ ምሰሶ ጫፍ በላይ ቢያንስ የ1.5 ሜትር ከፍታ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

## 58.<u>ከሕንጻዎችና ግንባታዎች መጠበቅ ስለሚገባው ርቀት</u>

1. የኤሌክትሪክ ኃያል ማስተላለፊያ ሽቦዎች በከፍተኛ ንፋስ ወቅት ከማንኛውም የሕንጻ ወይም የግንባታ አካል ቢያንስ 4.5 ሜትር የጎን ርቀት ሊኖራቸው ይገባል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገውን ሁኔታ ማሟላት የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ የኃይል ማስተላለፊያ ሽቦዎቹ ከሕንጻው ወይም ከግንባታው ጫፍ በላይ የሚኖራቸው ከፍታ በከፍተኛ የአየር ሙቀት ወቅት እንዲሁም በአጎራባች ታወሮች ላይ የተወጠሩ ሽቦዎች በሚበጠሱበት አጋጣሚ መጠበቅ የሚገባው ርቀት ቢያንስ 5.5 ሜትር መሆን አለበት፡፡

## 59.<u>ከዛፎች መጠበቅ ስለሚገባው ርቀት</u>

1. የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ሽቦዎች ኃይል በሚተላለፍባቸውና በማይተላለፍባቸው አካላት መካከል ሊኖር ከሚገባው ዝቅተኛ ርቀት በተጨማሪ በከፍተኛ የአየር ሙቀትና በከፍተኛ ንፋስ ወቅት ከዛፎች ሊኖራቸው የሚገባው የከፍታና የጎን ርቀት ቢያንስ 1.5 ሜትር መሆን አለበት፡፡
2. የፍራፍሬ ዛፎች ሲሆኑ፤ ኃይል በሚተላለፍባቸውና በማይተላለፍባቸው አካላት መካከል ሊኖር ከሚገባው ዝቅተኛ ርቀት በተጨማሪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሠረት መኖር ያለበት ርቀት 4 ሜትር ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተመለከቱት ርቀቶች የሚወሰኑት ዛፎቹ ይኖራቸዋል ተብሎ የሚገመተውን የእድገት መጠን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ይሆናል፡፡

60.<u>ከሌሎች መስመሮች መጠበቅ ስለሚገባው ርቀት</u>

1. ጎን ለጎን የተዘረጉ መስመሮችን በሚመለከት በኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ሽቦዎችና በሌሎች የማስተላለፊያ መስመሮች ወይም የቴሌኮሚኒኬሽን መስመሮች መካከል በከፍተኛ ንፋስ ወቅት ሊኖር የሚገባው ርቀት፣ ኃይል በሚተላለፍባቸውና በማይተላለፍባቸው አካላት መካከል ሊኖር ከሚገባው ዝቅተኛ ርቀት በተጨማሪቢያንስ 2.5 ሜትር መሆን አለበት፡፡
2. መስመሮቹ አንዱ ሌላውን በማቋረጥ የተዘረጉ ሲሆን ኃይል በሚተላለፍባቸውና በማይተላለፍባቸው አካላት መካከል ሊኖር ከሚገባው ዝቅተኛ ርቀት በተጨማሪ በከፍተኛ የአየር ሙቀት ወቅትና በአጎራባች ታወሮች ላይ የተወጠሩ ሽቦዎች በሚበጠሱበት አጋጣሚ መጠበቀ የሚገባው የከፍታ ርቀት ቢያንስ 1.5 ሜትር መሆን አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተጠቀሱት መስመሮች የተለያየ ቮልቴጅ የሚኖራቸው ሲሆን ርቀቱ የሚወሰነው ከፍተኛውን ቮልቴጅ መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡

61.<u>ስለማከፋፈያ ጣቢያዎች</u>

1. የማንኛውም የማከፋፈያ ጣቢያ ዲዛይን የአቅርቦት አስተማማኝነትን፣ የመስፋፋትና የመታደስ ብቃትንና ከአደጋ ሁኔታዎች መጠበቅን እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ አሠራርን ለማረጋገጥ በሚያስችል አኳኋን መከናወን አለበት፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የማከፋፈያ ጣቢያ ቢያንስ አንድ የዝቅተኛ ቮልቴጅ መጋቢ መስመር እንዲኖረውና የወደፊቱን የኤሌክትሪክ ጭነት ዕድገት ምጣኔ መሠረት ያደረገና ቢያንስ የአምስት ዓመትየአቅርቦት ዋስትና የሚሰጥ ሆኖ ዲዛይን መደረግ አለበት፡፡
3. የመሣሪያዎች መረጣ በብሔራዊ ደረጃዎች ወይም ብሔራዊ ደረጃዎች ከሌሉ በኢንተርናሽናል ኤሌክትሮ ቴክኒካል ኮሚሽን ደረጃዎች ላይ መመሥረትና ወቅታዊና የወደፊት ፍላጎቶችን እንዲሁም ኤጀንሲው በሥራ ላይ እንዲውል ያጸደቀውን የመሣሪያዎች አቀማመጥና ቅንጅት ያገናዘበ መሆን አለበት፡፡

4. የማከፋፈያ ጣቢያ የኤሌክትሪክ ዕቃዎች የማምረት ሥራ ሊጀመር የሚችለው የጣቢያው ንድፍ በኤጀንሲው ከጸደቀ በኋላ ብቻ ይሆናል፤ እንዲሁም በኤጀንሲው ያልጸደቀ ማንኛውንም ለውጥ በንድፉ ላይ ማድረግ አይቻልም፡፡
5. የማከፋፈያ ጣቢያ የሚገነባበትን ቦታ በመምረጥ ረገድ የወጭ ቅነሳና እንደ መንገድ መኖር፣ የመስፋፋት ችሎታ፣ ለጭነት ማዕከላት ቅርበት፣ ከብክለት ነጻ መሆንና የሠራተኞች ማኅበራዊና ባህላዊ ፍላጐቶችን ማሟላት የመሳሰሉ የጣቢያውን ሥራ ለማካሄድ የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

**ምዕራፍ ሦስት**

**ኤሌክትሪክ ስለማከፋፈል**

## 62.ስለማከፋፈያ መስመር ዲዛይን አጠቃላይ መስፈርቶች

1. የማከፋፈያ ኔትወርክ ዲዛይን፤
   ሀ) የወደፊቱን የመስፋፋት ዕቅድ ያገናዘበ፤ እና
   ለ) በማከፋፈሉ ፈቃድ ዘመን ውስጥ ሊያጋጥሙ የሚችሉትን የአካባቢው የኤሌክትሪክ ጭነት ጠባያትን ከግምት ውስጥ ያስገባ፣
   
   መሆን አለበት፡፡
2. የማከፋፈያ ኔትወርክ ዲዛይን የኤሌክትሪክ ብክነትን፣ መቋረጥንና የሥራ ማስኬጃና የጥገና ወጪዎችን በመቀነስ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ሊያስገኝ በሚችል ሁኔታ መሠራት አለበት፡፡
3. የማከፋፈያ ኔትወርክ አዘረጋግ ዲዛይን በአካባቢው ማስተር ፕላን ወይም ማስተር ፕላን ከሌለ በኤጀንሲው በጸደቀ ፕላን ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት፡፡
4. የማከፋፈያ ኔትወርክ ዕቃዎች መጠንና የግንባታ ዓይነት የብሔራዊ ደረጃዎችን ወይም ብሔራዊ ደረጃዎች ከሌሉ የኢንተርናሽናል ኤሌክትሮ ቴክኒካል ኮሚሽን ደረጃዎችን መስፈርቶች የተከተለ መሆን አለበት፡፡

## 63.ስለትራንስፎርመሮች

ለማከፋፈያ ኔትወርክ አገልግሎት የሚውሉ ትራንስፎርመሮች የአገልግሎትና የብቃት ደረጃ እንዲሁም የግንባታ ዓይነት በኤጀንሲው መመሪያ መሠረት ይወሰናል፡፡

64.**<u>ስለምሰሶዎች አተካከል</u>**

1. የኤሌክትሪክ ምሰሶዎች አተካከል ማስተር ፕላንን ወይም ማስተር ፕላን ከሌለ በኤጀንሲው የጸደቀ ፕላንን የተከተለ መሆን አለበት፡፡
2. የኤሌክትሪክ ምሰሶዎች ርዝመትና በመካከላቸው የሚኖረው ርቀት የሚወሰነው በኤጀንሲው መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡

65.**<u>የአገልግሎት መስመር</u>**

ማንኛውንም ወደ ደንበኞች የሚዘረጋ የኤሌክትሪክ መስመር ከምሰሶዎች ላይ ካልሆነ በስተቀር በመጥለፍ መገናኘት አይቻልም፡፡

66.**<u>የኤሌክትሪክ ኃይል ማከፋፈያና የመከላከያ ሽቦዎች</u>**

1. የኤሌክትሪክ ኃይል ማከፋፈያና የመከላከያ ሽቦዎች በቴክኒካዊና ኢኮኖሚያዊ መስፈርቶች ተቀባይነት ያላቸው መሆን አለባቸው፡፡
2. የሽቦዎቹ መጠን የሚመረጠው በብሔራዊ ደረጃዎች ወይም ብሔራዊ ደረጃዎች ከሌሉ በኢንተርናሽናል ኤሌክትሮ ቴክኒካል ኮሚሽን ደረጃዎች መሠረት ይሆናል፡፡

67.**<u>መጠበቅ ስለሚገባቸው ርቀቶች</u>**

የመካከለኛና ዝቅተኛ ቮልቴጅ ሽቦዎች ከሕንጻና ግንባታዎች ከአይሮፕላን መንደርደሪያ መንገዶች፣ ከባቡር ሀዲዶች፣ ከውኃ ላይ መንገዶች፣ ከተለያዩ የመሬት አካላት፣ ከኮሙኒኬሽን ሰርኪዩት፣ በአየር ላይ ከተዘረጋ የማከፋፈያ ኬብልና ከመብረቅ መከላከያ ሽቦዎች የሚኖራቸው ርቀት እንዲሁም በፌዞች መካከልና ከመሬት በተገናኙና ኃይል በሚተላለፍባቸው አካላት መካከል መጠበቅ የሚገባው ርቀት በኤጀንሲው መመሪያ መሠረት ይወሰናል፡፡

68.**<u>ስለኤሌክትሪክ ፍጆታ ቆጣሪዎች</u>**

1. የኤሌክትሪክ ፍጆታ ቆጣሪ ልዩ ልዩ ክፍሎች የአገልግሎትና የብቃት ደረጃ የብሔራዊ ደረጃዎችን ወይም ብሔራዊ ደረጃዎች ከሌሉ የኢንተርናሽናል ኤሌክትሮ ቴክኒካል ኮሚሽን ደረጃዎችን መስፈርት የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡
2. የኤሌክትሪክ ፍጆታ ቆጣሪዎች ለደንበኞች ከመገጠማቸው በፊት በተገቢው የጭነት ደረጃ ካሊብሬት መደረግ አለባቸው፡፡

**69.ኤሌክትሪክ ስለማከፋፈል አገልግሎት ጥራት**

1. የኤሌክትሪክ ማከፋፈል አገልግሎት ጥራት የሚለካው በቀጣዮቹ አንቀጾችና በኤጀንሲው መመሪያ በተመለከተው አኳኋን የሚከተሉትን መስፈርቶች መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡
   ሀ) የቮልቴጅ ደረጃ፤
   ለ) የፌዞች መመጣጠን፤
   ሐ) ህውከት የሚያስከትሉ ችግሮች፣ ፈጣንየቮልቴጅ መርገብገብና ሀርሞኒክ ዲስቶርሽን አለመኖር፤
   መ) በኮሙኒኬሽን ሥርዓት ውስጥ ጣልቃ አለመግባት፤
   ሠ) አማካይ የኃይል መቋረጥ ድግግሞሽ አነስተኛነት፤
   ረ) አጠቃላይ የኃይል መቋረጥ የጊዜ መጠን አነስተኛነት፤
   ሰ) የፍጆታ ክፍያ አሰባሰብ፡፡
2. ባለፈቃዱ የአገልግሎት ጥራትን ለመለካት የሚያስፈልጉ መረጃዎችን የመሰብሰብ ግዴታ ይኖርበታል፡፡

**70.ስለቮልቴጅ ደረጃ**

ባለፈቃዱ የሚያሰራጨው የቮልቴጅ መጠን ከደንበኞች በሚያገናኙ ልዩ ልዩ መድረሻ ጫፎች ላይ እንደሚከተለው መሆን አለበት፡-

1. የመካከለኛ ቮልቴጅ ፕራይመሪ ማከፋፈያ ሲሆን፤
   ሀ) መነሻው 15,000 ቮልት ሆኖ በ10 ፐርሰንት ሊጨምር ወይም ሊቀንስ የሚችል፤ እና
   ለ) መነሻው 33,000 ቮልት ሆኖ በ10 ፐርስንት ሊጨምር ወይም ሊቀንስ የሚችል፡፡
2. የዝቅተኛቮልቴጅ ማከፋፈያ ሲሆን፡-
   ሀ) መነሻው 220 ቮልት ሆኖ በ5 ፐርሰንት ሊጨምር ወይም ሊቀንስ የሚችል፤ እና
   ለ) መነሻው 380 ቮልት ሆኖ በ 5 ፐርሰንት ሊጨምር ወይም ሊቀንስ የሚችል፡፡

**71.ስለ ፍሪኩዌንሲና ፓወር ፋክተር**

1. የሥርዓቱ ፍሪኩዌንሲ 50 ኸርዝ ሆኖ በ1 ፐርሰንት ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል፡፡
2. የኤሌክትሪክን ኃይል ለንግድ ወይም ለኢንዱስትሪ የሚጠቀሙ ደንበኞች የሚገጥሟቸው ማሽኖችና መሣሪያዎች ፓወር ፋክተር ከ0.9 ማነስ የለበትም፡፡

**72.የፌዞች መመጣጠን**

1. የኤሌክትሪክ ጭነቶች በባለፈቃዱ የሥርጭት ሥርዓት ውስጥ በየፌዞቹ መከፋፈል ይገባቸዋል።
2. የአንድ ፌዝ ጭነት ከሌላ ፌዝ ጭነት ሲነጻጸር ከ10 ፐርሰንት በላይ መብለጥ አይኖርበትም፡፡

**73.ስለዋጋ ማስከፈያ ኢንቮይሶች**

1. ባለፈቃዱ በፍጆታ ንባብ መሠረት ትክክለኛና ግልጽ የሆኑ የኤሌክትሪክ ፍጆታ ዋጋ ማስከፈያ ኢንቮይሶች ማቅረብ አለበት፡፡
2. በኢንቮይሶች ላይ የሚከተሉት መረጃዎች ለደንበኞች መገለጽ አለባቸው፡-
   ሀ) የመክፈያ ቦታ፤
   ለ) ደንበኞች የሚሰተናገዱበት ቦታና ጊዜ፤
   ሐ) የአገልግሎት እጦት ቅሬታና የአደጋ ወይም የማንኛውም ሌላ ብልሽት ሪፖርት መቀበያ የስልክ ቁጥሮች፡፡

**74.የአቅርቦት አገልግሎትን ስለመቀጠል**

ባለፈቃዱ በክፍያ መስተጓጎል ምክንያት አቋርጦት የነበረን የኤሌክትሪክ አቅርቦት አገልግሎት ደንበኛው የፍጆታንና የሚፈለግበትን ተጨማሪ ክፍያ በፈጸመ በ24 ሰዓት ጊዜ ውስጥ መልሶ መቀጠል አለበት፡፡

**75.ስለደንበኞች ቅሬታ መዝገብ**

1. ባለፈቃዱ በሚሰጠው አገልግሎት አለመሟላት ወይም ከአገልግሎቱ ጋር በተያያዘ ማናቸውም ምክንያት በደንበኞች የሚቀርብለትን እያንዳንዱን ቅሬታ በመቀበል የቅሬታ አቅራቢውን የውል ቁጥርና ስም፣ ቅሬታው የቀረበበትን ቀንና ሰዓት ከነምክንያቱ መመዝገብ አለበት፡፡

2. ባለፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለሚደረግ የቅሬታ ምዝገባ የሚያገለግል የደንበኞች ቅሬታ መዝገብ በየንግድ አገልግሎት ጣቢያዎቹ ማኖር አለበት፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 76.ስለሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

1. የኤሌክትሪክ ሥራ ተቋራጭነት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት በኤጀንሲው የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡-
   ሀ) የአመልካቹን ማንነትና አድራሻ፤
   ለ) አመልካቹ ያገኘው ዲግሪ ዲፕሎማ ወይም የምስክር ወረቀት ካለው ይህንኑ፤
   ሐ) አመልካቹ የሥራ ልምድ ካለው ይህንኑ፤
   መ) ኤጀንሲው ያስፈልጋሉ ብሎ በመመሪያ የሚወስናቸውን ሌሎች መረጃዎች፡፡
2. ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የቀረቡለትን መረጃዎች ካጣራ በኋላ የአመልካቹን የሙያ ብቃትና ልምድ ለመገምገምና የምስክር ወረቀቱን ደረጃ ለመወሰን እንዳስፈላጊነቱ የጽሑፍና የተግባር ፈተና ሊሰጥ ይችላል፡፡
3. ኤጀንሲው አመልካቹ የተወሰነውን ክፍያ ከከፈለ በኋላ በ30 ቀናት ውስጥ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡
4. ለሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚጠየቀው ክፍያ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡
   ሀ) ለደረጃ አንድ .................................. ብር 500
   ለ) ለደረጃ ሁለት .................................. ብር 400
   ሐ) ለደረጃ ሦስት .................................. ብር 300
   መ) እስከ ደረጃ አራት ለሚሆኑ ዝቅተኛ ደረጃዎች ........................ ብር 100
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ስለሚሰጥ ፈተናና ስለሙያ ብቃት የምስክር ወረቀት ደረጃዎች ሚኒስቴሩ ዝርዝር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

### 77.መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

አግባብ ባላቸው የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች ለኤጀንሲው የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ለዚህ ደንብ አፈጻጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሚኒስቴሩ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 78.<u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

1. ይህ ደንብ ከመጽናቱ በፊት የኤሌክትሪክ ኃይል በማመንጨት፣ በማስተላለፍ ወይም በማከፋፈል ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ኤጀንሲው በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ በዚህ ደንብ መሠረት ፈቃድ ማውጣት አለበት፡፡
2. ይህ ደንብ ከመጽናቱ በፊት የኤሌክትሪክ ኃይል ለንግድ ላልሆነ አላማ በማመንጨት፣ በማስተላለፍ ወይም በማከፋፈል ተግባር ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ኤጀንሲው በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የአዋጁን አንቀጽ 10 (2) ድንጋጌ ማሟላት አለበት፡፡
3. ከአዋጁ መውጣት በፊት በቀድሞው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ መብራትና ኃይል ባለሥልጣን ተሰጥቶ የነበረ ማንኛውም የኤሌክትሪክ ተቋራጮች የሙያ ብቃት ምስክር ወረቀት ኤጄንሲው በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ በዚህ ደንብ መሠረት በሚሰጥ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እስከሚተካ ድረስ ጸንቶ ይቆያል፡፡

## 79.<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንበ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 12 ቀን 1991**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## አዋጅ ቁጥር 247/1993 ዓ.ም

## የነዳጅ ዋጋ ማረጋጊያ ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ

የነዳጅ ምርቶች ከማንኛውም ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እንቅስቃሴ ጋር ያላቸውን ከፍተኛ ትስስር እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በመገንዘብ፤

የነዳጅ ዋጋን ማረጋጋት የሚያስችል ፈንድ ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የነዳጅ ዋጋ ማረጋጊያ ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 247/1993" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   የነዳጅ ዋጋ ማረጋጊያ ፈንድ (ከዚህ በኋላ "ፈንዱ" እየተባለ የሚጠራ) የገንዘብ ሚኒስቴር በሚከፍተው ልዩ የባንክ ሂሣብ ውስጥ ተቀማጭ እንዲሆን በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

3. **የፈንዱ ዓላማ**[43]

   የፈንዱ ዓላማ፦

   1. በዓለም ገበያ በሚከሰተው የነዳጅ ዋጋ ማደግ ምክንያት የሚያስፈልገውን ተጨማሪ ወጪ በመደጎም የነዳጅን ዋጋ ማረጋጋት፤
   2. ነዳጅ ዋጋ ማረጋጊያ ፈንድ አላማን ሳያደናቅፍ መንግስት ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ሥራዎች ወጪ መሸፈን፤ ይሆናል፡፡

4. **ፈንዱ ምንጮች**

   ፈንዱ ከሚከተሉት ምንጮች የሚሰበሰብ ይሆናል፤

   1. በዓለም ገበያ የነዳጅ ዋጋ በመቀነሱ ምክንያት ከሚገኝ ተራፊ ሂሣብ፤
   2. ለነዳጅ ዋጋ ማረጋጊያ እንዲውል ከሚገኝ የውጭ ዕርዳታ፤ ይሆናል፡፡

[43] በ9/62 (1995) 342 አንቀፅ 2 መሰረት የቀድሞ ተሰርዞ ተተክቷል፡፡

5. **የፈንዱ ተሰብሳቢ ገንዘብ**

1. የኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት የአገር ውስጥ የነዳጅ መሸጫ ዋጋ በሚወሰንበት ጊዜ ለነዳጅ መግዣና ለሌሎችም ጉዳዮች ታሳቢ ተደርገው በነበሩ ወጪዎች እና በትክክል በተደረገው ወጪ መካከል የሚኖረውን ልዩነት ለፈንዱ ሂሣብ ገቢ ያደርጋል፡፡
2. የኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለፀውን ሂሣብ ለፈንዱ ገቢ የሚያደርገው በየሦስት ወሩ የሚደረገው የነዳጅ ምርቶች ዋጋ ማስተካከያ ተግባራዊ ከተደረገበት ወር እ.ኤ.አ. በሚቀጥለው ወር[44] አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ይሆናል፡፡

6. **ስለክፍያዎች**

ከፈንዱ ሂሣብ ገንዘብ ወጪ ሆኖ የሚከፈለው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሲፈቅድ ይሆናል፡፡

7. **የገንዘብ ሚኒስትሩ ሥልጣን**

የገንዘብ ሚኒስትሩ፡-

1. ፈንዱ የሚቀመጥበትን ልዩ የባንክ ሂሣብ ይከፍታል፤
2. የፈንዱን ሂሣብ ይይዛል፤ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፡፡

8. **የሂሳብ መዛግብት**

የፈንዱ የመዝገብና የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት የፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን የሚከተል ይሆናል፡፡

9. **ኦዲት**

የፈንዱ ሂሣብና መዛግብት በዋናው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

10. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከሰኔ 26 ቀን 1993 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ 26 ቀን 1993 ዓ.ም**

**ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

---

[44] በ8/3 (1994) ማ. 1 ታረመ፡፡

## አዋጅ ቁጥር 317/1995

## የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ

የገጠሩን አካባቢ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማሻሻል የኤሌክትሪክ አገልግሎት ማቅረብ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በብድር ላይ የተመሠረተ የቴክኒክ አገልግሎትና የፋይናንስ ድጋፍ በመሥጠት በገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ተግባር የሚሠማሩ የግል ባለሀብቶችን እና የኅብረት ሥራ ማህበራትን ማበረታታት አስፈላጊ በመሆኑ፤

ለዚህ ተግባራዊነት የፋይናንስ ምንጭ ሆኖ የሚያገለግል ፈንድ ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55 (1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 317/1995" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**[45]

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

   1. "ኤጀንሲ" ማለት የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኤጀንሲ ነው፣[46]
   2. "ማዕከል" ማለት በአዋጅ ቁጥር 269/1994 የተቋቋመው የኢትዮጵያ የገጠር ኢነርጂ ልማትና ማስፋፊያ ማዕከል ነው፣
   3. "ኮርፖሬሽን" ማለት የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ነው፣

---

[45]አንቀፅ 2/2 ላይ ማዕከል፣ 2/3 የማዕከሉ ዳይሬክተር እና አንቀፅ 2/5 ላይ አስፈፃሚ ሴክሬተሪያት ለሚሉ ቃላት የተሰጠው ትርጓሜ ላይ መሰረት የተደረገው በአዋጅ ቁጥር 269/1994 መሰረት የተቋቋመው የኢትዮጵያ የገጠር ኢነርጂ ልማት እና ማስፋፋያ ማዕከል በአዋጅ ቁጥር 691/2003 መሰረት ማቋቋሚያ አዋጁ የፈረሰ እና የማዕከሉ መብት እና ግዴታ በወቅቱ ለነበረው የውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር ለአሁኑ የውሃ፣ መስኖ እና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር የተላለፈ በመሆኑ እነዚህ ቃላት አስፈላጊ አይደለም፡፡

[46] ይህ ኤጀንሲ የተቋቋመበት አዋጅ ቁጥር 3/50 (1989) አ. 86 ከላይ እንደተገለፀው የተሻረ እና ኤጀንሲውም በደንብ ቁጥር 308/2006 በተቋቋመው የኢትዮጵያ የኢነርጂ ባለስልጣን የተተካ እና መብት እና ግዴታውም የተላለፈ በመሆኑ ኤጀንሲው የሚለው ባለስልጣኑ በሚል እና መስሪያ ቤቱም የኢትዮጵያ የኢነርጂ ባለስልጣን በሚል ተተክቶ የሚነበብ ይሆናል፡፡ ውስጥ ደንቡ ዝርዝር ላይ ኤጀንሲው የሚለው ባለስልጣኑ በሚል ተተክቶ የሚነበብ ይሆናል፡፡

4. “ዳይሬክተር” ማለት የኢትዮጵያ የገጠር ኢነርጂ ልማትና ማስፋፊያ ማዕከል ዋና ዳይሬክተር ነው፣
5. “አስፈጻሚ ሴክሬታሪያት” ማለት የኢትዮጵያ የገጠር ኢነርጂ ልማትና ማስፋፊያ ማዕከል ነው፣
6. “ከግሪድ ውጭ” ማለት በኮርፖሬሽን ያልተሸፈነ የኤሌክትሪክ አቅርቦት ነው፣
7. “የገጠር አካባቢ” ማለት ከግሪድ ውጭ ያለ አካባቢ ነው፤
8. “መንግሥት” ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ነው፣
9. “ሚኒስቴር” እና “ሚኒስትር” ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው የገጠር ልማት ሚኒስቴር እና ሚኒስትር[47] ነው፣
10. “ኦፕሬተር” ማለት ከግሪድ ውጭ ለንግድ ዓላማ ኤሌክትሪክ የማመንጨት፣ የማከፋፈልና የመሸጥ ሥራ የሚሠራ ሰው ነው፣
11. “ኦፕሬሽን” ማለት ከግሪድ ውጭ ለንግድ ዓላማ ኤሌክትሪክ የማመንጨት፣ የማከፋፈልና የመሸጥ ሥራ ነው፣
12. “የገንዘብ ባለአደራ ተቋም” ማለት ከፈንዱ ልዩ ልዩ ምንጮች የሚሰበሰበውን ገንዘብ የሚያስቀምጥና በቦርዱ ትዕዛዝ ብድር የሚሰጥና ብድሩንም ተቀብሎ በፈንዱ የባንክ ሂሳብ የሚያስቀምጥ ማንኛውም የፋይናንስ ተቋም ነው፤
13. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47(1) የተገለጸ ክልል ሲሆን፤ ለዚህ አዋጅ ዓላማ አፈጻጸም አዲስ አበባና ድሬዳዋን ይጨምራል፤
14. “ታዳሽ የኃይል ምንጭ” ማለት ከተፈጥሮ የሚገኝ በራሱ ወይም በሰው አማካይነት በማያቋርጥ ዑደት ሂደቱን ጠብቆና እንደአስፈላጊነቱ ተተኪም በመሆን ለሰዎች አገልግሎት ጥቅም ላይ የሚውል እንደ የፀሐይ፣ የነፋስ፣ የውሃ፤ የባዮማስና የመሳሰሉት የኃይል ምንጭ ነው፤
15. “የገጠር ኢሌክትሪፊኬሽን” ማለት ከግሪድ ውጭ ኤሌክትሪክ ማመንጨት፣ ማስተላለፍ፣ ማከፋፈል፣ መሸጥና እነዚህን ለማስፈጸምና ለማስፋፋት የሚከናወኑ ተጓዳኝ ተግባሮች ናቸው፤

[47] 25/08 (2011) አ.1097 አንቀጽ 9(6) የግብርና ሚንስቴር ሆኗል።

16.“የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን መርሐ ግብር” ማለት በገጠር አካባቢ ለፈንዱ ከተቀመጡት ዓላማዎች አንፃር በፈንዱ እየታገዘ የኤሌክትሪክ አቅርቦትን ለማስፋፋት በቦርዱ የሚጸድቅ የእንቅስቃሴ አቅጣጫ ነው፤

17.“የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮጀክት” ማለት ከግሪድ ውጭ የኤሌክትሪክ አገልግሎትን ለማዳረስ የሚከናወን የዲዛይን፣ የግንባታ፣ የማመንጨት፣ የማስተላለፍና ሌሎች ተጓዳኝ ሥራዎች ናቸው፤

18.“ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

19.“የአሠራር ወጥነት መመሪያ” ማለት በፈንዱ ልዩ ልዩ አካላትና ፈንዱን በሚያስፈጽሙ የክልል አስፈጻሚ ጽሕፈት ቤቶች የሚከናወኑ የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ተግባራት ወጥነትና ቅንጅት ባለው አኳኋን እንዲሠሩ የሚመራ መመሪያ ነው።

3. <u>**መቋቋም**</u>

የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፈንድ (ከዚህ በኋላ “ፈንዱ” እየተባለ የሚጠራ) ቋሚ የፋይናንስ ምንጭ ሆኖ የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር[48] በሚከፍተው ልዩ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ተቀማጭ እንዲሆን በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

4. <u>**የፈንዱ ዓላማዎች**</u>

ፈንዱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፤

1. በግል፣ በህብረት ሥራ ማህበራትና በአካባቢ ኅብረተሰብ ለሚካሄዱና በተለይም በዋነኝነት ታዳሽ የኃይል ምንጮችን ለሚጠቀሙ የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮጀክቶች የብድርና የቴክኒክ አገልግሎት መስጠት፤
2. በገጠሩ አካባቢ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለምርትና ለማህበራዊ አገልግሎት እንዲውል ማበረታታት።

5. <u>**የፈንዱ ምንጮች**</u>

የፈንዱ ምንጮች የሚከተሉት ይሆናሉ፤

1. ከመንግሥት የሚመደብ በጀት፤
2. ከሌሎች መንግሥታት የሚገኝ ብድርና ዕርዳታ፤
3. ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች የሚገኝ ብድርና ዕርዳታ፤
4. መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ከሚገኝ ዕርዳታ፤

[48] በ25/08 (2011) አ. 1097 አንቀጽ 9(4) መሰረት የገንዘብ ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

5. ከሌሎች ልዩ ልዩ ምንጮች የሚገኝ ገቢ፡፡

## ክፍል ሁለት

## የፌዴራል የፈንዱ አካላት

6. **የፈንዱ አካላት**
   1. ፈንዱ በፌዴራል ደረጃ፤

      ሀ) በገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርዱ" እየተባለ የሚጠራ)፤

      ለ) አስፈጻሚ ሴክሬታሪያት፤

      ይኖረዋል
   2. ቦርዱ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሩ ይሆናል፤
   3. ክልሎች የራሳቸውን የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን አስፈጻሚ ሴክሬታሪያት ሊያቋቁሙ ይችላሉ፣
   4. የክልል የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ሴክሬታሪያት ጽሕፈት ቤቶች፤ የየክልሎቻቸው የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮጀክቶች በዚህ ሕግና ቦርዱ በሚያወጣቸው ልዩ ልዩ መርሐ ግብሮችና መመሪያዎች መሠረት መከናወናቸውን ይከታተላሉ፡፡
7. **የቦርዱ አባላት**
   1. ቦርዱ በመንግሥት የሚሰየሙ ይኖሩታል።
   2. የቦርዱ አባላት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፡፡ ሆኖም ማንኛውም አባል ለተጨማሪ የሥራ ዘመናት እንደገና ሊመደብ ይችላል፡፡
   3. አንድን የቦርድ አባል መንግሥት በማናቸውም ጊዜ እና ምክንያት ሊያነሳው እና በሌላ ሊተካው ይችላል፡፡
   4. የቦርዱ አባላት ቁጥር በሞት፣ ሥራን በፈቃድ በመልቀቅ ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት ቢቀንስ፤ ክፍት ቦታው በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ይሞላል፡፡
   5. ማንኛውም የቦርድ አባል በቦርዱ ውስጥ ካለው ሥራ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በጥቅም የሚጋጭ ማንኛውንም ተግባር ማከናወን የለበትም፡፡ በቦርዱ ውስጥ ካለ ሥራ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የጥቅም ግጭት ሲያጋጥመው ይህንኑ ለቦርዱ በማሳወቅ ጉዳዩ ከሚታይባቸው የቦርዱ ስብሰባዎች እራሱን ማግለል አለበት፡፡

8. **የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር**

ቦርዱ የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፤

1. ሚኒስቴሩን በፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ያማክራል፣
2. የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን መርሐ ግብርን ሥራ ላይ ለማዋል የሚያገለግሉ የአሠራር ሥርዓቶችን መመሪያዎችን፤ ደረጃዎችንና የፕሮጀክት አፈጻጸም መመሪያዎችን ያፀድቃል። እነዚህኑ በየጊዜው እየመረመረ ተገቢውን ማስተካከያ ያደርጋል፤
3. ብድር ለመስጠት የሚያስችሉ ግልፅ መመሪያዎችን፣ መስፈርቶችንና አግባብ ያላቸውን የአሠራር ሥርዓቶች ያፀድቃል፤
4. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ኦፕሬሽናቸውን በኮርፖሬሽኑ አማካይነት ለለቀቁ ኦፕሬተሮች ካሳ የሚከፈልበትን መስፈርት አውጥቶ በሚኒስቴሩ ያስፀድቃል፤
5. ሪፖርቶችን ይቀበላል፣ ይመረምራል፣ እንደ አስፈላጊነታቸው ያፀድቃል፤
6. ፈንዱን ያስተዳድራል፤
7. ከልዩ ልዩ የፈንዱ ምንጮች ገቢ የሚደረገውን ገንዘብ በኃላፊነት የሚያስቀምጥ የገንዘብ ባለአደራ ተቋም በሴክሬታሪያቱ ሲቀርብለት ያጸድቃል፤
8. ስለ ገንዘብ ባለአደራ ተቋሙ ዝርዝር አሠራር መመሪያ ያወጣል፤
9. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሥልጣንና ተግባሩን ለክልል የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ሴክሬታሪያት ጽሕፈት ቤቶች በውክልና ሊሠጥ ይችላል፤
10. የገጠር ኢሌክትሪፊኬሽንን የሚያጠናክሩ ሌሎች ሥራዎች ያከናውናል፤
11. የቦርዱ ውሳኔዎች፣ መርሐ ግብሮች እና አመራሮች ለሕዝብ ግልፅ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
12. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ከተጠቀሱት የፈንዱ ምንጮች የሚገኘው ገቢ በሚመለከተው አካል በጊዜው መሰብሰቡን ያረጋግጣል፡፡

9. **የቦርዱ ስብሰባዎች**

1. ቦርዱ በየሦስት ወሩ ይሰበሰባል፡፡ ሊቀመንበሩ ሲጠራ በማናቸውም ጊዜ ሌሎች አስቸኳይ ስብሰባዎችን ያደርጋል፡፡
2. ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

3. የቦርዱ ውሳኔ ሆኖ የሚፀናው በስብሰባው ከተገኙት ከግማሽ በላይ ድምፅ የሰጡበት ውሳኔ ነው። እኩሌታ ድምፅ ሲገኝ ሊቀመንበሩ ድምፁን የሰጠበት ወገን አብላጫ ድምፅ ይሆናል፡፡
4. ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

10.<u>የአስፈጻሚ ሴክሬታሪያቱ ሥልጣንና ተግባር</u>

አስፈጻሚ ሴክሬታሪያቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡-

1. ዓመታዊና አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሪፖርትን በማዘጋጀት በቦርዱ ያስፀድቃል፤
2. የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮጀክት ኦፕሬተሮችን ማመልከቻ ይመረምራል፤ ቦርዱ ባፀደቃቸው መስፈርቶች መሠረት ይወስናል፤
3. መስፈርቶችን አውጥቶ በውድድር ላይ በተመሠረተ አሠራር ባለአደራ የፋይናንስ ተቋምን ይመርጣል፤ ይህንኑ እንዲያፀድቀው ለቦርዱ ያቀርባል፤
4. ብድር የሚሰጥባቸውን ግልፅ መመሪያዎችና አግባብ ያለውን የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮጀክት ለመምረጥ የሚያስችሉ የምርጫ መስፈርቶችና ሥርዓቶችን አዘጋጅቶ ለቦርዱ በማቅረብ ያስፀድቃል፤
5. የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን መርሐ ግብር ከሌሎች የገጠር ልማት ተግባራት ጋር እንዲቀናጅ የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል፣
6. በገጠር ውስጥ የኤሌክትሪክ አገልግሎት እንዲስፋፉ ለምርትና ማህበራዊ ጥቅም እንዲውል ያደርጋል፤
7. የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ጣቢያዎችን ለመትከል፣ ለማንቀሳቀስና ለማስተዳደር በሚያስችሉ የአቅም ግንባታ ተግባሮች ላይ ከሚመለከታቸው ጋር ይተባበራል፤
8. ተቀባይነት ያላቸውንና የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን የደህንነት ደረጃና ኢኮኖሚያዊ አቅም ያገናዘቡ ቁሳቁሶችን፣ መሣሪያዎችንና ቴክኖሎጂን ዝርዝር ያዘጋጃል ይይዛል፤ እንዲሁም በመረጃነት እንዲሠራጩ ያደርጋል፤
9. ለፈንዱ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ ሊሆኑ የሚችሉ ሁኔታዎችን ያጠናል፤
10. የቦርዱን የሥራ መዛግብት፣ ዘገባዎችና የስብሰባ ቃለ ጉባኤዎች ይይዛል፣ እንዲሁም የቦርዱ ውሳኔዎችና መመሪያዎች በትክክል መፈጸማቸውን ተከታትሎ ያረጋግጣል፤
11. በዚህ አዋጅ ከተጠቀሱት የፈንዱ ምንጮች የሚገኘው ገንዘብ በጊዜው መሰብሰቡንና በፈንዱ ሂሳብ ገቢ መደረጉን ያረጋግጣል፤

12.ሌሎች ከተግባርና ኃላፊነቱ ጋር የሚገናኙ ሥራዎችን ይሠራል፤

13.ፈንዱ በየጊዜው ለሚወጥነው የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮግራም የበለጠ ውጤታማ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ የሚውልበትን እያጠና ለቦርዱ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል።

11.<u>**የዳሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**</u>

ዳሬክተሩ ፈንዱን በሚመለከቱ ጉዳዮች ተጠሪነቱ ለቦርዱ ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 የተመለከቱትን የአስፈጻሚ ሴክሬታሪያቱን ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ ያወጣል።

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

12.<u>**የአሠራር ወጥነት**</u>

1. የአሠራር ወጥነት እንዲኖር ሁሉም የፈንዱ አሠራሮችና ተግባሮች በአሠራር መመሪያ ይመራሉ፡፡
2. ቦርዱ የአሠራር መመሪያ ያወጣል።

13.<u>**የገንዘብ ባለአደራው ተቋም ኃላፊነት**</u>

1. የገንዘብ ባለአደራው ተቋም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ከተጠቀሱት የፈንዱ ምንጮች የሚገኘውን ገንዘብ በኃላፊነት ይይዛል፡፡
2. በቦርዱ ትዕዛዝ ለገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮጀክቶች የሚሰጠውን ብድር ይሰጣል፡ በብድር የተሰጠ ገንዘብ ሲመለስ ይቀበላል፡፡
3. ተበዳሪዎች የወሰዱት ገንዘብ በጊዜው መመለሱን ይከታተላል፡፡
4. የፈንዱን ገቢና ወጪ የሚያሳይ የሂሳብ መዝገብ ያዘጋጃል፡፡ ይህንኑ ቦርዱ በመመሪያ በሚወስነው ጊዜ ለቦርዱ ያቀርባል፡፡
5. ሌሎች ከኃላፊነቱ ጋር አግባብ ያላቸውን ሥራዎች ይሠራል፡፡

14.<u>**ለገጠር ኢሌክትሪፊኬሽን ፕሮጀክቶች ፈቃድ ስለመስጠት**</u>

ኤጀንሲው አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ለገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮጀክቶች ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያቋርጣል፣ ይሰርዛል፡፡

15.<u>**ለብድር ብቁ ስለመሆን**</u>

ከፈንዱ ለመበደር የሚፈልግ ሰው በገጠር ኤሌክትሪክሽን ሥራ ለመሠማራት ብቁ መሆንና ብድር ለማግኘት የሚያስችሉ መስፈርቶችን ማሟላት አለበት፡፡

16.**<u>የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን አልሚዎች ዋስትና</u>**

1. የኮርፖሬሽኑ የኤሌክትሪክ አቅርቦት በየ10 ዓመት ምን ያህል የአገሪቱን ክፍል እንደሚሸፍን የሚያሳይ ጠቋሚ የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ማስተር ፕላን ማውጣት አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ማስተር ፕላን ለሕዝብ ግልፅና የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽንን ፕሮግራም በማስፈጸም ረገድ ተገቢ ትኩረት የሚሰጠው መሆን አለበት፡፡
3. ኮርፖሬሽኑና ሴክሬታሪያቱ በየዓመቱ እየተገናኙ ለሚኒስቴሩና ለኤጀንሲው ከሚያቀርቡት ዓመታዊ የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ጠቋሚ ዕቅድ አኳያ ዕቅዳቸውን ያቀናጃሉ፡፡
4. የኮርፖሬሽኑ ኤሌክትሪክ አቅርቦት ሂደት በገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ተግባር የተሠማራውን ባለሀብት፣ የኅብረት ሥራ ማህበር ወይም የአካባቢ ኅብረተሰብ ያስለቀቀ እንደሆነ ለአልሚው ፈጣንና ትክክለኛ ካሣ ይከፈለዋል፡፡

17.**<u>የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ደንበኞች መብት</u>**

1. ኦፕሬተሩ ኤጀንሲው በሕግ በተሰጠው ሥልጣን አማካይነት ከሚወስነው ኤሌክትሪክ ታሪፍ በላይ አያስከፍልም፡፡
2. የኤሌክትሪክ አገልግሎቱን ከማቋረጡ በፊት ኦፕሬተሩ አግባብ ባለው መንገድ ለደንበኛው ማሳወቅ አለበት፡፡
3. ኦፕሬተሩ የኤሌክትሪክ አገልግሎቱን ከማቆሙ ከ3 ወር በፊት ለኤጀንሲው ማሳወቅ አለበት፡፡
4. አግባብ ባለው ሕግ ስለ ኤሌክትሪክ ደንበኞች መብት የተደነገጉት ድንጋጌዎች፣ ለገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ደንበኞችም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

18.**<u>ከብሔራዊ ግሪድ ጋር መያያዝ</u>**

አስፈጻሚ ሴክሬታሪያቱ የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮጀክቶች ወደፊት ከብሔራዊ ግሪድ ጋር በሚገናኙበት አቅጣጫ እንዲንቀሳቀሱ ፕላን ያወጣል፤ ይህንኑ ይመከራል፡፡

19.**<u>የፀደቁ ፕሮጀክቶች ቁጥጥርና ክትትል</u>**

የአስፈጻሚ ሴክሬታሪያቱ እንደአስፈላጊነቱ የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽኖች ፕሮጀክቶች ለፕሮጀክቶቹ ክንዋኔ በፀደቀው መርሐ ግብር መሠረት መከናወናቸውን ይቆጣጠራል

ያረጋግጣል፤ ለፕሮጀክቱ በተገባው ውል መሠረትም አስፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

20. **የመንገድና የመሬት አጠቃቀም**

የኤሌክትሪክ አዋጅ ቁጥር 86/1989[49] ስለ መንገድና መሬት አጠቃቀም የሚደነግገው ለገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮጀክቶችም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

21. **የአካባቢ ጥበቃ**

የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮጀክቶች ዕቅድ፣ ግንባታ፣ ሥራና ጥገና የአካባቢ ጥበቃ ሕጎችን ያከበሩ መሆን አለባቸው።

22. **ደህንነት**

1. ኦፕሬተሮች ሠራተኞቻቸውን፣ ሕዝቡንና ንብረቱን ከአደጋ ለመጠበቅ ተገቢ የሆነውን ቅድመ ደህንነት እርምጃ ይወስዳሉ፡፡
2. የኤሌክትሪክ አዋጅ ቁጥር 86/1989[50]፣ ደንብ ቁጥር 49/1991 እና የደህንነት መመሪያዎች በገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

23. **የሂሣብ መዛግብት**

አስፈጻሚ ሴክሬታሪያቱ የፈንዱን ትክክለኛና የተሟሉ የሂሣብ መዛግብትና አስረጅ ሰነዶችን ይይዛል፡፡

24. **ኦዲት**

1. ለዋናው ኦዲተር በሕግ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የፈንዱ ሂሣብ ቦርዱ በሚሰይመው የውጭ ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል፡፡
2. ሂሣቡ የሚመረመረው በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ባለው የሂሣብ ምርመራ መርሆዎችና ሥርዓት መሠረት ሆኖ የኦዲት ሪፖርቱ ቦርዱና የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር አስተያየት እንዲሰጡበት ይቀርብላቸዋል፡፡
3. የቴክኒክ ምርመራ በተመረጡት ተግባራት ላይ በየዓመቱ ይከናወናል፡፡

25. **የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

---

[49] በ20/12 (2006) አ. 810 ተሽሯል፡፡

[50] በ20/12 (2006) አ. 810 ተሽሯል፡፡

26.**<u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

1. ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን በደንቡ በሚወሰነው መሠረት ሚኒስቴሩ ወይም ቦርዱ ሊያወጡ ይችላሉ፡፡

27.**<u>ተፈጻሚ የማይሆኑ ሕጐች</u>**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ በዚህ አዋጅ በተደነገጉት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

28.**<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ ከጥር 29 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር 29 ቀን 1995 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 810/2006

## የኢነርጂ አዋጅ

ለአገሪቱ የተፋጠነ የኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገት ዋነኛ ከሆኑ ግብዓቶች ውስጥ ኢነርጂ አንዱ በመሆኑ፤

በሥራ ላይ ያለውን የኤሌክትሪክ አዋጅ ከወቅቱ ብሔራዊ እና አካባቢያዊ የኢነርጂ ቁጥጥር አሰራር እድገት አንጻር ማሻሻልና የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ቁጥጥርን በማካተት በአዲስ የኢነርጂ አዋጅ መተካት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የኢነርጂ አዋጅ ቁጥር 810/2006 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

   1. "ኢነርጂ" ማለት ከውሃ ኃይል፣ ከፀሐይ፣ ከነፋስ፣ ከከርሰ ምድር እንፋሎት ወይም ከሌላ ምንጭ የሚገኝ የኤሌክትሪክ ኃይል ነው፤
   2. "ማመንጨት" ማለት ኤሌክትሪክ ማምረት ነው፤
   3. "ማስተላለፍ" ማለት በከፍተኛ ቮልቴጅ የኤሌክትሪክ ኃይል ማጓጓዝ ነው፤
   4. "ማከፋፈል" ማለት በመካከለኛና በአነስተኛ ቮልቴጅ መስመሮች አማካይነት ለደንበኞች የሚቀርብ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ነው፤
   5. "ግሪድ" ማለት የኤሌክትሪክ ኃይል ከማመንጫ ጣቢያ ተነስቶ ለደንበኞች የሚቀርብበት የማገናኛ ቦታዎችን ጨምሮ የተያያዘው የማስተላለፊያና ማከፋፈያ ሥርዓት ነው፤
   6. "ዝቅተኛ ቮልቴጅ" ማለት እስከ 400 ቮልት የሚደርስ የቮልቴጅ መጠን ነው፤
   7. "መካከለኛ ቮልቴጅ" ማለት ከ400 በላይ እስከ 33,000 ቮልት የሆነ የቮልቴጅ መጠን ነው፤
   8. "ከፍተኛ ቮልቴጅ" ማለት ከ33,000 ቮልት በላይ የሆነ የቮልቴጅ መጠን ነው፤

9. “የኤሌክትሪክ ሥራ” ማለት የኤሌክትሪክ ዲዛይን፣ ኢንስታሌሽን፣ ጥገና፣ ፍተሻ፣ መቆጣጠር፣ ተቋራጭነት፣ ወይም ማማከር፣ የኤሌክትሮ መካኒካል ሥራ ወይም ማንኛውም ሌላ የኤሌክትሪክ ነክ ሥራ ነው፤[51]
10. “ኢንስታሌሽን” ማለት ኢሌክትሪክን ከአቅርቦቱ አንስቶ ጥቅም ላይ እስከሚውልበት ቦታ ለማድረስ ጥቅም ላይ የዋሉ ወይም እንዲውሉ የተገጠሙ ሽቦዎችን፣ እቃዎችን፣ አያያዦችን እና ሌሎች ቁሳቁሶችን ያጠቃልላል፤
11. “ደንበኛ” ማለት ከባለፈቃድ የኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚያገኝ ሰው ነው፤
12. “ኮድ” ማለት በባለሥልጣኑ መመሪያ የተደነገጉ የኤሌክትሪክ ሥራዎችን ወይም የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃዎችን የሚመለከቱ የሥርዓቶችና የአሠራሮች ስብስብ ነው፤
13. “የኢነርጂ ኦዲት” ማለት
    ሀ) የአንድን ደንበኛ የኢነርጂ ፍጆታ አጠቃቀም በቂ እውቀት ለማግኘት፤
    ለ) አዋጭ የሆኑ የኢነርጂ ቁጠባ እድሎችን ለመለየትና መጠናቸውን ለመለካት፤ እና
    ሐ) ግኝቶቹን ሪፖርት ለማድረግ፤

    የሚያስችል የተቀናጀ ሥርዓት ነው፤
14. “የኢነርጂ ቁጠባ” ማለት በአንድ ሂደት ወይም ሥርዓት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውለውን የኢነርጂ መጠን ብክነትን በማስወገድ እና ኢኮኖሚያዊና አግባብ በሆነ አጠቃቀም መቀነስ ነው፤
15. “የኢነርጂ ብቃት” ማለት በዝቅተኛ የኢነርጂ ፍጆታ ተመሳሳይ ወይም ከፍ ያለ ምርት ወይም አገልግሎት ማቅረብ መቻል ነው፤
16. “የኢነርጂ ብቃት ተለጣፊ ምልክት” ማለት ተጠቃሚዎች ግዢ በሚፈጽሙበት ወቅት ስለንብረቱ የኢነርጂ አጠቃቀም ብቃት እንዲያውቁ አስፈላጊውን ግንዛቤ ለመስጠት የሚያስችል መረጃን የያዘ በንብረቱ ላይ የሚለጠፍ ምልክት ነው፤
17. “የኢነርጂ አገልግሎት ኩባንያ” ማለት የደንበኛን መገልገያ ወይም ይዞታ በሚመለከት የኢነርጂ ብቃት ማሻሻያ አገልግሎት የሚሰጥና ለሰጠው አገልግሎትም ክፍያውን በሙሉ ወይም በከፊል በተገኘው የኃይል ብቃት መሻሻል ላይ ተመሥርቶ የሚቀበል ኩባንያ ነው፤

[51] በ24/42(2010) አ.1085 አንቀፅ 2(1) ተሻሻለ፡፡

18.“የፈቃደኝነት ስምምነት” ማለት የኢነርጂ ብቃትን ለማሻሻል በሁሉም ተሳታፊ ወገኖች ስምምነት የተደረሰባቸው ኢላማዎች በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እንዲያከናውኑ ለማስቻል ግዴታዎችን የሚጥል ባለሥልጣኑ ከማንኛውም ሰው ጋር የሚያደርገው ውል ነው፤

19.“ፈንድ” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 23 መሠረት የተቋቋመው የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ፈንድ ነው፤

20.“ባለአደራ ወኪል” ማለት ከፈንዱ ልዩ ልዩ ምንጮች የሚሰበሰበውን ገንዘብ እንዲያስቀምጥ፣ በቦርዱም ትዕዛዝ ብድር እንዲሰጥና ተከፋይ ገንዘቡንም እንዲቀበል የተወከለ ማንኛውም የፋይናንስ ተቋም ነው፤

21.“ፈቃድ” ማለት ለንግድ ዓላማ ኤሌክትሪክ ለማመንጨት፣ ለማስተላለፍ፣ ለማሰራጨትና ለመሸጥ፣ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ወይም ወደ ውጭ አገር ለመላክ፣ ወይም የኢነርጂ ኦዲት፣ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ተቋራጭ ወይም የማማከር አገልግሎቶችን ለማከናወን በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

22.“ባለፈቃድ” ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤

23.“የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት” ማለት የኤሌክትሪክ ስራዎች የማከናወን ብቃትን በማረጋገጥ ለማንኛውም ሰው በባለስልጣኑ የሚሰጥ ሰነድ ነው፤

24.“ታሪፍ” ማለት ለኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚከፈል የዋጋ ተመን ዝርዝር ነው፤

25.“ባለስልጣን” ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የሚቋቋም የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን ነው፤[52]

26.“ቦርድ” ማለት የባለሥልጣኑ ቦርድ ነው፤

27.“ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47(1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤

28.“ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

29.ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል።

[52] በ20/36 (2006) ደ.308 መሰረት የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን ተቋቁሟል፡፡

## ክፍል ሁለት
## የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን

3. **መቋቋም**

የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይቋቋማል፡፡

4. **የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር**

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በዚህ አዋጅ እና በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦችና መመሪያች መሠረት ፈቃድና የብቃት ማረጋገሪጫ የምስክር ወረቀት መስጠትና ማደስ፤
2. ማንኛውም ባለፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እና በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችንና መመሪያችን አክብሮ እየሠራ መሆኑን መቆጣጠር፤ ይህ አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ተጥሰው ሲገኙም እንደጥፋቱ ክብደት ባለፈቃዱን ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠውን ሰው በገንዘብ መቅጣት ወይም ፈቃዱን ማገድ ወይም መሠረዝ፤
3. በባለፈቃድ የሚቀርብለትን ከብሔራዊ ግሪዱ ጋር የተያያዘ ታሪፍ መገምገምና እንዲጸድቅ ለመንግስት የውሳኔ ሀሳብ ማቅረብ፤ ሲጸድቅም አፈጻጸሙን መቆጣጠር፣ ከብሔራዊ ግሪዱ ውጭ የሆኑ ታሪፎችን አወሳሰን መመሪያ ማውጣትና አፈጸጸሙን መቆጣጠር፤
4. የረጅም፣ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ስትራቴጂና ፕሮግራም በአገር አቀፍ እንዲሁም በዘርፍ ደረጃ ማዘጋጀት እና አፈጸጸማቸውን በየወቅቱ በሚቀርቡለት ሪፖርቶች መሠረት መገምገም፤
5. የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባን በብሔራዊ እና በዘርፍ ደረጃ ማስፋፋት፤
6. የኢነርጂ ኦዲት ኮድ፣ የኢነርጂ ብቃት ደረጃዎች ኮድ፣ የኢነርጂ ብቃት ማረጋገረጫ ተለጣፊ ምልክት ኮድ፣ የግሪድ ኮድ፣ የደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ ኮድ፣ የኢንስፔክሽን ኮድ፣ የአገልግሎት ጥራት ደረጃ ኮድ፣ የሕንፃ ኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ ኮድ፣ የቴክኒካል ስታንዳርድ ኮድ እና ሌሎች ኮዶችን ማውጣት እና አፈጻጸማቸውንም መቆጣጠር፤
7. የኤሌክትሪክ ኃይል ግዢ እና የኔትወርክ አገልግሎት ስምምነቶችን ማጽደቅ፤

8. የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባን፣ የኢነርጂ ልማትን እና የኤሌክትሪክ ኃይል ንግድን ለማስፋፋት ከሥልጠና ተቋማት እና ከአህጉራዊና ከዓለም አቀፍ መድረኮች ጋር መተባበር፤
9. የኢነርጂ ብቃት መፈተሻ ላብራቶሪዎችን ማቋቋም እና የፍተሻ ሥርዓቶችን ማውጣትና መተግበር፤
10. የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ጥናትን፣ ልማትንና ሠርቶ ማሳያን እንዲሁም የቴክኖሎጂ ዝውውር ተግባራትን ማስፋፋትና ማስተባበር፤
11. ከኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ጋር የተዛመዱ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መተንተን፣ ማደራጀትና ማሰራጨት፤
12. በዚህ አዋጅ መሠረት ቁጥጥር ሊደረግበት በሚገባ በማናቸውም ጉዳይ ላይ በሚመለከታቸው ወገኖች መካከል አለመግባባት በመከሰቱ የቀረበ አቤቱታን መስማት፣ ማጣራት እና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም ማስማማት ወይም በግልግል መጨረስ፤
13. በአዋጁ መሠረት በሚወጣ ደንብ የሚወሰኑ ፈቃድና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለመስጠትና ለማደስ እና ለሚሰጣቸው ሌሎች አገልግሎቶች የሚጠየቁ ክፍያዎችን እና የፈንዱን ገቢዎች መሰብሰብ፤
14. እንደአስፈላጊነቱ ሥልጣንና ተግባሩን አግባብ ላላቸው የክልል አስፈጻሚ አካላት በውክልና ማስተላለፍና የአቅም ግንባታ ድጋፍ መስጠት፡፡

5. <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>

የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. ከብሔራዊ ግሪድ ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ የታሪፍ የውሳኔ ሃሳቦችን መርምሮ እንዲጸድቁ ለመንግሥት ያቀርባል፤
2. ከብሔራዊ ግሪዱ ውጭ የሆኑ ታሪፎች አወሳሰን መመሪያን፣ ብሔራዊ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ስትራቴጂንና ፕሮግራምን እና የኤሌክትሪክ ኃይል ግዢና የኔትወርክ አገልግሎት ስምምነቶችን ያጸድቃል፤
3. በዚህ አዋጅ መሠረት ባለሥልጣኑ የሚያወጣቸውን መመሪያዎች ያጸድቃል፤
4. ፈንዱ በወቅቱ መሰብሰቡንና በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፤
5. የባለአደራ ወኪል ምርጫን እንደሁም ከፈንዱ የሚሰጡ ብድሮችን ያጸድቃል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለፈቃድ እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

6. **የፈቃድ አስፈላጊነት**
    1. ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ መሰረት ፈቃድ ሳይኖረው ለንግድ ዓላማ ኤሌክትሪክ ማመንጨት፣ ማስተላለፍ፣ ማከፋፈልና መሸጥ፣ ወደ ውጭ አገር መላክ ወይም ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ወይም የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ማማከር፣ የኢነርጂ አገልግሎት ተቋራጭነት፣ የኢነርጂ ኦዲት ወይም ከእነዚህ ሥራዎች ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን መስራት አይችልም።
    2. ለንግድ ላልሆነ ዓላማ ኤሌክትሪክ ለማመንጨት፣ ለማስተላለፍ ወይም ለማከፋፈል ፍላጎት ያለው ማንኛውም ሰው በቅድሚያ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ እና የአካባቢ ጥበቃና የአደጋ መከላከያ ሁኔታዎችን ማሟላቱን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ መረጃዎችን ማቅረብ አለበት፡፡
    3. ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ኤሌክትሪክ በማመንጨት፣ በማስተሳለፍ፣ በማከፋፈልና መሸጥ፣ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባን በማማከር፣ የኢነርጂ አገልግሎት ተቋራጭነት፣ የኢነርጂ ኦዲት ወይም ሌሎች ከዚህ አዋጅ ጋር የተያያዙ ተግባራትን ሲያከናውን የነበረ ማንኛውም ሰው አስፈላጊ የሆኑ ዝርዝር መረጃዎችን የያዘ ማመልከቻ ለባለሥልጣኑ በማቅረብ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፡፡
7. **ፈቃድ ለማግኘት ብቁ ስለመሆን**

    ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ እና በአዋጁ መሰረት በሚወጣ ደንብ፣ በኢንቨስትመንት እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተገለጹትን ፈቃድ ለማግኘት ብቁ የሚያደረጉ መስፈርቶችን ካሟላ፣ በንግድ ሕግ መሠረት የንግድ ሥራ ማካሄድ የሚችል እንዲሁም የፈቃድ ግዴታዎችን ለመወጣት የሚያስችል የገንዘብ ምንጭ፣ የቴክኒክ ችሎታ፣ ሙያ እና ልምድ ያለው መሆኑ በባለሥልጣኑ ሲረጋገጥ ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

8. ***ፈቃድን ስለማደስ፣ ስለማገድ እና ስለመሰረዝ***

1. *ፈቃድ እንዲታደስለት የሚያመለክት ማንኛውም ባለፈቃድ በዚህ አዋጅና በአዋጁ መሰረት በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተመለከቱትን መስፈርቶች አሟልቶ መቅረብ አለበት፡፡*
2. *ባለፈቃዱ በዚህ አዋጅ፣ በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ወይም በፈቃዱ ላይ የተጠቀሱትን ግዴታዎች ካላከበረ ባለሥልጣኑ በገንዘብ ሊቀጣው ወይም ፈቃዱን ለያግድ ወይም ሊሰርዝ ይችላል፡፡*
3. *ባለሥልጣኑ ፈቃድ ከመሰረዙ በፊት ባለፈቃዱ ስህተቱን እንዲያርም በቂ ይሆናል ብሎ የሚገምተውን ጊዜ ይሰጠዋል።*
4. *የወራሾች መብት እንደተጠበቀ ሆኖ እንደአግባብነቱ ባለፈቃዱ ሲሞት ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ከሆነ ሲፈርስ ወይም አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የመክሰር ውሳኔ ሲሰጥበት ፈቃዱ ሊሰረዝ ይችላል፡፡*
5. *በዚህ አዋጅ አንቀጽ* 10 *ንዑስ አንቀጽ* (*ሀ*) *ወይም* (*ለ*) *መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ባለፈቃድ ሥራ ያልጀመረው ከአቅም በላይ በሆነ አስገዳጅ ምክንያት መሆኑን ማመልከቻ አቅርቦ ባለስልጣኑም ይህንኑ ካረጋገጠ ፈቃዱን ለሁለት ጊዜ ብቻ በየዓመቱ ሊያድስ ይችላል፡፡*[53]
6. *የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ* (5) *ድንጋጌ ቢኖርም ማንኛውም ባለፈቃድ ፈቃድ ከወሰደበት ጊዜ ጀምሮ በሁለት ዓመት ውስጥ ሥራውን ሳይጀምር ከቀረ ወይም በዚህ አዋጅ በአንቀጽ* 10 *ንዑስ አንቀጽ* (*ሀ*) *ወይም* (*ለ*) *የተደነገገውን ሁኔታ ያላከበረ እንደሆነ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡*
7. *ባለፈቃዱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ* 10 *ንዑስ አንቀጽ* (*ሀ*) *ወይም* (*ለ*) *መሠረት በፈቃዱ ላይ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሥራ መጀመሩን ለባለስልጣኑ በሪፖርት ካሳወቀ እንደሁኔታው ባለሥልጣኑ ክትትል አድርጎ ማረጋገጡ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የፈቃድ ዘመኑ ባለፈቃዱ ሥራ ስለመጀመሩ ሪፖርት ካደረገበት ጊዜ ጀምሮ የሚቆጠር ይሆናል፡፡*

[53] *ንዑስ አንቀፅ* (5)፣ (6) *እና* (7) *በ*24/42(2010) *አ.*1085 *አንቀፅ* 2(2) *መሰረት አዲስ የገቡ ናቸው፡፡*

9. **ፈቃድን ስለማስተላለፍና ምትክ ፈቃድ ስለመስጠት**

1. በባለሥልጣኑ የተሰጠ ማናቸውም ፈቃድ በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም በወጣ ደንብ መሠረት በባለሥልጣኑ የጽሑፍ ስምምነት ለሌላ ሰው ሊያስተላለፍ ይችላል፡፡
2. የማመንጨት፣ የማስተላለፍ፣ የማከፋፈልና የመሸጥ፣ ወደ አገር ውስጥ የማስገባት ወይም ወደ ውጭ አገር የመላክ ባለፈቃድ የንግድ ሥራው በዋስትና በመያዙ፣ በመተላለፉ ወይም ከሌላ ጋር በመቀላቀሉ ምክንያት በመቆጣጠር ወይም በባለቤትነት መብቱ ላይ ለውጥ ሲደረግ በባለሥልጣኑ መጽደቅ ይኖርበታል፡፡
3. ማናቸውንም የባለፈቃዱን የማይንቀሳቀስ ንብረት ወይም ከሃያ አምስት በመቶ በላይ የሆነን የአክስዮን ድርሻ የሚመለከት ሽያጭ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተገለጸው መሠረት በመቆጣጠር ወይም በባለቤትነት መብት ላይ ለውጥ እንደተደረገ ያስቆጥራል፡፡
4. ፈቃዱ የጠፋበት ወይም የተበላሸበት ባለፈቃድ ምትክ ፈቃድ እንዲሰጠው ሲያመለከት በዚህ አዋጅ መሠረት በወጣ ደንብ የተወሰነውን ክፍያ በማስከፈል ምትክ ፈቃዱ ሊሰጠው ይችላል፡፡

10.**የባለፈቃድ ግዴታዎች**

1. ማንኛውም ባለፈቃድ፦
   ሀ) በዚህ አዋጅ መስረት በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት ስለ ሥራው አግባብነት ያላቸውን ሪከርዶች ይይዛል፤ እንዲሁም እቅዶችን፣ ሪፖርቶችን፣ መረጃዎችንና ደጋፊ ማስረጃዎችን ለባለሥልጣኑ ያቀርባል፤
   ለ) መዛግብቱና ሪከርዶቹ በአግባቡ ሥልጣን በተሰጣቸው የባለሥልጣኑ ሃላፊዎች እንዲመረመሩ ሲጠየቅ ለምርመራ ያቀርባል፡፡
2. ማንኛውም ባለፈቃድ ሥራዎቹን ሲያከናውን ይህን አዋጅ፣ በአዋጁ መሰረት የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን እና አግባብነት ያላቸውን የአካባቢ ጥበቃ ሕጎችን እንዲሁም በባለሥልጣኑ የተወሰኑትን የጥንቃቄ፣ የጥራትና የአተገባበር ደረጃዎችን ማክበር አለበት፡፡

3. [54]ሀ) ከጂኦተርማል ወይም ከውሃ ኃይል ኤሌክትሪክ ለማመንጨት ፈቃድ የወሰደ
   ማንኛውም ሰው ፈቃዱን ከወሰደበት ጊዜ ጀምሮ በአምስት ዓመት የጊዜ ገደብ ውስጥ ሥራ መጀመርና ሥራውን ስለመጀመሩም ለባለሥልጣኑ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡
   ለ) ከፀሐይ ኃይል፣ ከንፋስ፣ ከባዮማስ፣ ከድንጋይ ከሰል፣ ከተፈጥሮ ጋዝ ወ.ዘ.ተ. ኤሌክትሪክ ለማመንጨት ፈቃድ የወሰደ ማንኛውም ሰው ፈቃዱን ከወሰደበት ጊዜ ጀምሮ በሶስት ዓመት የጊዜ ገደብ ውስጥ ሥራውን መጀመርና ሥራውን ስለመጀመሩም ለባለሥልጣኑ ሪፖርት ማቅረብ አለበት።
   ሐ) ኤሌክትሪክ ኃይልን ከውጪ ማስመጣት ወይም ወደ ውጭ ሀገር መላክ ለመንግስት ብቻ የተከለለ ሥራ ነው።

11.<u>ስለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት</u>

1. የኤሌክትሪክ ሥራ ተግባራትን ማከናወን የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ መሠረት በባለሥልጣኑ የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ከባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የወሰደ ማንኛውም ሰው ሥራ ከመጀመሩ በፊት እንደአግባብነቱ ከፌዴራል ንግድ ሚኒስቴር[55] ወይም ከክልል ንግድ ቢሮ ተገቢውን የንግድ ፈቃድ ማውጣት ይኖርበታል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ከባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የወሰደ ማንኛውም ግለሰብ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ለማሳደስ ሲፈልግ በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣ ደንብ የሚገለጸውን አግባብነት ያለውን የሥራ ልምድ ወይም የተከታታይ ትምህርት ፕሮግራም ተሳትፎ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

[54]በ24/42(2010) አ.1085 አንቀፅ 2(3) መሰረት ተሻሻለ፡፡
[55] 25/08 (2011) አ. 1097 አንቀጽ 9(7) የንግድና ኢንዱስትሪ ሚንስቴር

4. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለመስጠት፣ ለማደስ፣ ለማገድ፣ ለመሰረዝ ወይም ምትክ ለመስጠት መሟላት የሚኖርባቸው መስፈርቶችና ሁኔታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ ይወሰናሉ፡፡

## ክፍል አራት

## የኤሌክትሪክ አቅርቦት ተግባራትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች

### 12. ባለፈቃዱ የኤሌክትሪክ አገልግሎቶችን የሚያቋርጥባቸው ሁኔታዎች

1. ባለፈቃዱ በሚከተሉት ምክንያቶች ካልሆነ በስተቀር የኤሌክትሪክ አገልግሎቶችን ሊያቋርጥ አይችልም፦
   ሀ) የኤሌክትሪክ እቃዎችን ወይም መስመሮችን ለመፈተሽ፣ ለመጠገን፣ ለማደስ፣ ለማስተካከል ወይም ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች አስፈላጊ ሥራዎችን ለማከናወን፤
   ለ) እንደ ውሃ ሙላት፣ የመሬት መናድና መንቀጥቀጥ ያሉ ወይም ከባለፈቃዱ አቅም በላይ የሆኑ ሌሎች የተፈጥሮ አደጋዎች ሲከሰቱ፤
   ሐ) ደንበኛው ክፍያ ሳይፈጽም ሲቀር፤
   መ) ደንበኛው ስምምነት ካደረገበት ግዴታዎች እና ሁኔታዎች ውጪ ያልተፈቀደለትን ኤሌክትሪክ ሲጠቀም ወይም የገባለትን የኤሌክትሪክ ቆጣሪ ሲያሰናክል፡፡
2. ባለፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) በተደነገገው መሰረት የኤሌክትሪክ አገልግሎቱን ከማቋረጡ አስቀድሞ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው ደንብ በተገለጸው ጊዜ ውስጥ ለህብረተሰቡ ማስታወቅ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ)፣ (ሐ) እና (መ) የተመለከቱት ሁኔታዎች እንደተስተካከሉ ባለፈቃዱ የኤሌክትሪክ አገልግሎቱን ወዲያውኑ መቀጠል አለበት፡፡

### 13. ብሔራዊ ግሪድ

1. መንግስት ማንኛውንም የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ መስመር በማስታወቂያ ብሔራዊ ግሪድ ብሎ ለመሰየም ይችላል፡፡
2. በብሔራዊ ግሪዱ መጠቀም የሚቻልበት አግባብ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ መሰረት ይሆናል፡፡

14.<u>የኤሌክትሪክ ኃይል ንግድ</u>

1. የኤሌክትሪክ ኃይል ወደ አገር ውስጥ የሚገባበት ወይም ወደ ውጭ አገር የሚላክበት ሁኔታ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡
2. የኃይል ግዢ ስምምነት ሳይኖር የኤሌክትሪክ ኃይል ንግድ የሚከናወንበት አግባብ በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

15.<u>ስለመቆጣጠር</u>

1. በባለሥልጣኑ የተወከለ ሃላፊ ለህሊና ግምት ተገቢ በሆነ በማናቸውም ሰዓት የኤሌክትሪክ ማመንጫት፣ ማስተላለፉ፣ ማከፋፈልና መሸጥ ወይም የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽ ስራዎችን ሳያግድ ወይም ሳያደናቅፍ በቦታው ውስጥ በመግባት መመርመር ወይም መቆጣጠር ይችላል፡፡
2. ማናቸውም የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን የደህንነት መስፈርትን ስለማሟላቱ ፈቃድ ባለው የኤሌክትሪክ ተቆጣጣሪ ሳይረጋገጥ ከባለፈቃዱ የኤሌክትሪክ አቅርቦት መስመር ጋር ማገናኘት አይቻልም፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ለኤሌክትሪክ አቅርቦት ሥራዎች በመሬት ስለመጠቀም</u>

16.<u>በመሬት ስለመጠቀም</u>

ማንኛውም የማመንጨት፣ የማስተላለፍ፣ የማከፋፈል፣ የመሸጥ፣ ወደ አገር ውስጥ የማስገባት ወይም ወደ ውጭ አገር የመላክ ባለፈቃድ፡-

1. በማንኛውም ሰው ይዞታ ሥር ወደ ሆነ መሬት ወይም ቅጥር ግቢ በመግባት አዲስ የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን መዘርጋት የሚችለው በቅድሚያ ከባለይዞታው ፈቃድ በማግኘት ነው፤
2. በማንኛውም ሰው ይዞታ ሥር ወደ ሆነ መሬት ወይም ቅጥር ግቢ በመግባት የኤሌክትሪክ መስመር ለማገናኘት፣ ለመጠገን፣ ለማሻሻል፣ ለመመርመር ወይም መስመሩን ለማንሳት የሚያስፈልጉ ተግባራትን ለማከናወን የሚችለው በቅድሚያ ባለይዞታውን በማሳወቅ ነው፤
3. የኤሌክትሪክ ግንባታ ሥራዎችን ለማካሄድ መሰናከል የሚሆኑ ወይም በኤሌክትሪክ መስመር ላይ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ዛፎችን የመቁረጥ ወይም የመመልመል ወይም ሰብሎችን አትክልቶችን ወይም ሌሎች ነገሮችን የማስወገድ መብት አለው፡፡

17.**ካሣ ስለመክፈል**

ባለፈቃዱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16 የተደነገጉትን ተግባራት ሲያከናውን በባለይዞታው ንብረት ላይ ላደረሰው ጉዳት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ካሣ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

18.**መሬትን ስለመውሰድ**

ማንኛውም የማመንጨት፣ የማስተላለፍ፣ የማከፋፈል እና የመሸጥ፣ ወደ አገር ውስጥ የማስገባት ወይም ወደ ውጭ አገር የመላክ ባለፈቃድ መንግሥት ለሕዝብ ጥቅም ሲባል አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ከግል ባለይዞታ የወሰደው መሬት ተጠቃሚ ሊደረግ ይችላል፡፡

## ክፍል ስድስት

## የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች

19.**የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ተግባራትን መቆጣጠር**

1. የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ቁጥጥር ተግባራት በኢንዱስትሪና በሕንጻ ዘርፎች እና በኤሌክትሪክ እቃዎችና መገልገያ ቴክኖሎጂዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
2. የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ተግባራት ቁጥጥር እንደአስፈላጊነቱ ከሚከተሉት አንዱን ወይም ከዚያ በላይ የሆኑትን ተግባራዊ በማድረግ ሊፈጸም ይችላል፦
   ሀ) ዝቅተኛ የኢነርጂ ብቃት ደረጃን፤
   ለ) የኢነርጂ ብቃት ተለጣፊ ምልክት ኮዶችን፤
   ሐ) አስገዳጅ የኢነርጂ ኦዲትን፤
   መ) የፈቃደኝነት ስምምነትን፤
   ሠ) አስገዳጅ የኢነርጂ ቁጠባን፤ ወይም
   ረ) አስገዳጅ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ እቃ ማስገጠምን፡፡
3. ባለሥልጣኑ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ተግባራት ቁጥጥርን በራሱ ወይም ፈቃድ ባለው የኢነርጂ አገልግሎት ድርጅት አማካይነት ሊያከናውን ይችላል፡፡
4. ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው ደንብ መሰረት ከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚዎች የራሳቸውን የኢነርጂ አስተዳደር ክፍል እንዲያቋቁሙና በየወቅቱም ሪፖርት እንዲያቀርቡ ሊያስገድዳቸው ይችላል፡፡

5. ባለሥልጣኑ በኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ከፍተኛ የአፈጻጸም ደረጃ ለማግኘት እንዲያስችለው ከኢነርጂ መገልገያ እቃ አምራቾች፣ አስመጪዎች ወይም ከከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚዎች ጋር ውጤቱ የሚለካና አስገዳጅነት ያለው የፈቃደኝነት ስምምነት መግባት ይችላል፡፡

20.<u>ብሔራዊ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች</u>

1. ባለሥልጣኑ ብሔራዊ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ስትራቴጂዎችንና ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
2. ብሔራዊ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች በዝርዝር ኢኮኖሚያዊ የግምገማ ዓላማዎችና በሚለኩ ግቦች የተደገፉ መሆን አለባቸው፡፡
3. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሱትን ብሔራዊ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ስትራቴጂዎችንና ፕሮግራሞችን በየወቅቱ ይገመግማል፡፡

21.<u>ስለሪፖርት አቀራረብ</u>

1. ማንኛውም የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ አፈጻጸም ሪፖርት አስፈላጊ የሆኑ ስታንዳርዶችን መከተል እና የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ተግባሩ ሊፈጽመው የታሰበውን ሁሉንም ጉዳዮችን መያዝ እንዲሁም በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ የተመለከቱትን የሪፖርት አቀራረብ ሥርዓቶችን መከተል ይኖርበታል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚቀርበው ሪፖርት ባለሥልጣኑ ስለኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ አሰራር ተገቢ ግንዛቤ እንዲያገኝ የሚያስችለው መሆን አለበት፡፡

22.<u>የፈቃደኝነት ስምምነት</u>

1. የፈቃደኝነት ስምምነቶች ግልጽና የማያሻማ ዓላማዎች እንዲሁም ዓላማዎቹም የማይፈጸሙ ወይም ሊፈጸሙ የማይችሉ በሚሆንበት ጊዜ ወደ ተሻሻሉ ወይም ወደ ተጨማሪ እርምጃዎች ሊመሩ የሚያስችሉ ከክትትልና ከሪፖርት አቀራረብ መስፈርቶች ጋር የተያያዙ ሥርዓቶች ሊኖሩዋቸው ይገባል፡፡
2. ግልጽነትን ከማረጋገጥ አንጻር የፈቃደኝነት ስምምነቶች ተግባራዊ ከመሆናቸው በፊት ሚስጥራዊ ድንጋጌዎች እስከፈቀዱ ድረስ ለህብረተሰቡ ሊደርሱ እና ሊታተሙ እንዲሁም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላትም አስተያየት እንዲሰጡባቸው የሚጋብዙ መሆን አለባቸው፡፡

3. ባለሥልጣኑ በብሔራዊ ደረጃ የኢነርጂ ብቃትን የሚያበረታታ የፈቃደኝነት ስምምነት ተግባራዊ እንዲሆን የሚያስችል ፕሮግራም ቀርጾ ሊተገብር ይችላል፡፡
4. የፈቃደኝነት ስምምነት ለመግባትና የኢነርጂ ብክነቱን በተቀመጠው ግዴታና የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ለመቀነስ ፈቃደኛ ያልሆነ ማንኛውም የከፍተኛ ኢነርጂ ተጠቃሚ ደንበኛ ለሚያስከትለው የኢነርጂ ብክነት በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣ ደንብ የሚወሰነውን ክፍያ እንዲፈጽም ይደረጋል፡፡

23.<u>የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ፈንድ</u>

1. የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ፈንድ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡
2. ፈንዱ በኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ተግባር ላይ ለተሠማሩ ሰዎች ብድርና ድጋፍ ለመስጠት ዓላማ ይውላል፡፡
3. ፈንዱ የሚከተሉት የገንዘብ ምንጮች ይኖሩታል፡-
   ሀ) በመንግሥት የሚመደብ በጀት፤
   ለ) ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት የሚገኝ ብድር እና ስጦታ፤
   ሐ) መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የሚገኝ ስጦታ፤
   መ) የኢነርጂ ብቃት ከሌላቸው የኤሌክትሪክ እቃዎችና መገልገያዎች፣ ሕንጻዎች እና ኢንዱስትሪዎች ከሚሰበሰብ መቀጮ፤ እና
   ሠ) ከሌሎች ምንጮች የሚገኙ ገቢዎች፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) (መ) መሠረት የሚሰበሰበው የፈንዱ ገቢ በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

<u>**ክፍል ሰባት**</u>

<u>**የወንጀል ጥፋቶች እና ቅጣቶች**</u>

24.<u>ፈቃድ ሳይኖር ስለመስራት</u>

በሌላ ሕግ ለህብረት ሥራ ማህበራት የተሰጠው መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ፈቃድ ሳይኖረው ለንግድ ዓላማ ኤሌክትሪክ ያመነጨ፣ ያስተላለፈ፣ ያከፋፈለና የሸጠ፣ ወደ አገር ውስጥ ያስገባ ወይም ወደ ውጭ አገር የላከ ወይም የኤሌክትሪክ ሥራን፣ ኢነርጂ ኦዲትን፣ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ የተቋራጭነት ወይም የማማከር አገልግሎትን ያከናወነ ማንኛውም ሰው እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ወይም እስከ ብር 50,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፤ አገልግሎት ሲሰጥባቸው የተገኙ ዕቃችና መገልገያዎችም በመንግስት ይወረሳሉ፡፡

25.<u>ከብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ጋር የተያያዙ ወንጀሎች</u>

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ ወይም በአዋጁ መሰረት በወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች የተመለከቱትን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስፈርቶች፣ ሁኔታዎች ወይም ግዴታዎች ያልፈጸመ እንደሆነ እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ወይም እስከ ብር 15,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

26.<u>በኤሌክትሪክ ተቋማት ላይ ጉዳት ስለማድረስ</u>

በማመንጫ፣ ማስተላለፊያ ወይም ማከፋፈያ ተቋማት ላይ ጉዳት ያደረሰ ማንኛውም ሰው ከአምስት እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ወይም እስከ ብር 50,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

27.<u>የባለሥልጣኑን ሥራ ስለማሰናከል</u>

ማንኛውም የባለሥልጣኑ ተቆጣጣሪ በዚህ አዋጅ መሰረት ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ የተቃወመ፣ ያደናቀፈ፣ ችግር የፈጠረ ወይም በኢንስፔክተሩ በአግባቡ የተሰጠውን መመሪያ ሆነ ብሎ ተላልፎ የተገኘ ማንኛውም ሰው ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም እስከ ብር 25,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

28.<u>የኤሌክትሪክ ኃይል ስለመስረቅ</u>

ማንኛውም ሰው፡-

1. ማናቸውንም የኤሌክትሪክ ኃይል የሰረቀ፣ በሕገ-ወጥ መንገድ ከሌላ መስመር ጋር ያገናኘ፣ መስመሩን ያሰናከለ ወይም የኤሌክትሪክ ኃይል እንዲሰረቅ ከሌላ መስመር ጋር እንዲገናኝ ወይም መስመሩ እንዲሰናከል ያደረገ፤ ወይም
2. መስመሩ የተሰረቀ፣ በሕገወጥ መንገድ ከሌላ መስመር ጋር የተገናኘ ወይም የተሰናከለ መሆኑን እያወቀ ከዚሁ መስመር ማናቸውንም የኤሌክትሪክ ኃይል ለፍጆታ ያዋለ ወይም የተገለገለ እንደሆነ፤

እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ወይም እስከ ብር 20,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

29.**<u>በኢነርጂ ላይ የሚፈጸሙ ሌሎች የወንጀል ጥፋቶች</u>**

ማንኛውም ሰው፡-

1. በዚህ አዋጅ መሰረት በተሰጠ ፈቃድ ውስጥ የተመለከቱትን ማናቸውንም ሁኔታዎች የተላለፈ እንደሆነ፤
2. ከባለፈቃዱ ስምምነት ውጪ ባለፈቃዱ የኤሌክትሪክ ኃይል በሚያቀርብበት በማናቸውም የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት መስመር ላይ ማናቸውንም የኤሌክትሪክ አስተላላፊ ነገር ወይም የኤሌክትሪክ ዕቃ ያስቀመጠ፣ የተከለ ወይም የዘረጋ ወይም እንዲቀመጥ፣ እንዲተከል ወይም እንዲዘረጋ የፈቀደ እና ከዚሁ ጋር ያገናኘ ወይም እንዲገናኝ የፈቀደ እንደሆነ፤
3. በተከለለው የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ይዞታ ውስጥ የገነባ፣ ያረሰ ወይም የቆፈረ ወይም ሰብሎችን፣ አትክልቶችን ወይም ዛፎችን ያበቀለ ወይም የኤሌክትሪክ ግንባታ ወይም ሥራዎችን የሚያውኩ ወይም በኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽኖች ላይ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ግንባታዎችን አላፈርስም፣ ዛፎችን አልቆርጥም ወይም አልመለምልም ወይም ሰብሎችን፣ አትክልቶችን ወይም ሌሎች ነገሮችን አላስወግድም ያለ እንደሆነ፤
4. በባለፈቃዱ የተገጠመለትን የኤሌክትሪክ ቆጣሪ ያሰናከለ ወይም እንዲሰናከል የፈቀደ ወይም የኤሌክትሪክ ፍጆታን እንዳይመዘግብ ያደረገ ወይም የተባበረ እንደሆነ፤
5. ከባለፈቃዱ ስምምነት ውጪ ማናቸውንም ዓይነት የኤሌክትሪክ አስተላለፊ ነገሮችን ወይም የኤሌክትሪክ ዕቃዎችን የባለፈቃዱ ከሆኑት የኤሌክትሪክ አቅርቦት መስመሮች ላይ ያለያየ ወይም እንዲለያዩ የፈቀደ ወይም የተባበረ እንደሆነ፤
6. ከባለፈቃዱ በቅድሚያ የይሁንታ ማረጋገጫ ሳያገኝ በቋሚነት በተዘረጋለት የኤሌክትሪክ መስመር ላይ ማናቸውንም ለውጥ ያደረገ ወይም ለውጥ እንዲደረግበት የፈቀደ እንደሆነ፤
7. በማናቸውም መንገድ የኤሌክትሪክ ኃይል የአቅርቦት መጠኑ በሜትር ተለክቶ ሳይረጋገጥ ወይም ሊከፍልበት ከተዋዋለው ማናቸውም የኤሌክትሪክ እቃዎች ወይም መሣሪያዎች ውጪ የተጠቀመ ወይም እነዚህኑ የኤሌክትሪክ እቃዎች

ወይም መሳሪያዎች ከተወሰነው ጊዜ እና ሊከፍልባቸው ከተዋዋለው ውጪ የተጠቀመባቸው እንደሆነ፣

8. የቀረበለትን የኤሌክትሪክ ኃይል ከቀረበበት ተግባር ውጪ ለሌላ ተግባር የተጠቀመ እንደሆነ፣
9. ከባለፈቃዱ ስምምነት ውጪ በባለፈቃዱ የተሰጠውን ማናቸውንም የኤሌክትሪክ ኃይል ለማንኛውም ሌላ ሰው የሰጠ እንደሆነ፣
10. ማናቸውንም የኤሌክትሪክ መስመር ተሸካሚ ምሰሶዎችን ወይም የተሸካሚ አካላትን ያለያየ ወይም የሰረቀ ወይም በመለያየቱ ወይም በስርቆቱ የተባበረ እንደሆነ፣ ወይም
11. በባለፈቃዱ ቁጥጥር ስር ባለ ማናቸውም ከኤሌክትሪክ ጋር ተያያዥነት ባለው ሥራ ላይ ሆነ ብሎ ወይም በግድየለሽነት ጉዳት ያደረሰ ወይም ይህንኑ ያቋረጠ እንደሆነ፣

እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ወይም ከብር 25,000 ባልበለጠ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

30. <u>የኢነርጂ ብቃትን የሚመለከቱ ወንጀሎች</u>

1. በዚህ አዋጅ ወይም በአዋጁ መሠረት በሚወጣው ደንብ መሠረት በተቀመጡት የኢነርጂ ብቃት አስገዳጅ ደረጃዎች የተመለከቱትን መስፈርቶች ያላሟላ ማናቸውንም ምርት ያመረተ፣ ወደ አገር ውስጥ ያስገባ፣ የተገበያየ፣ ያከፋፈለ ወይም የተጠቀመ ማንኛውም ሰው እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ እስራት ወይም እስከ ብር 25,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡
2. ወንጀለኛው ደጋጋሚ ጥፋተኛ ሲሆን ወይም የተፈጸመው ወንጀል የአገርን ብሔራዊ ኢኮኖሚ በከፍተኛ ደረጃ የሚጎዳ ሲሆን ቅጣቱ እስከ አስር ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት ወይም እስከ ብር 100,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይምበሁለቱም ሊሆን ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ጥፋት ተፈጽሞባቸው የተገኙ የኢነርጂ ብቃት የሌላቸው ምርቶች በመንግስት ይወረሳሉ፡፡

31.<u>ሪፖርት ማድረግንና ሪከርድ መያዝን ስለመተላለፍ</u>

ማንኛውም ሰው፡-

1. በዚህ አዋጅ ወይም በአዋጁ መሰረት በወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች መሠረት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ የሚገባውን ሪፖርት ሳያቀርብ ከቀረ ወይም የተሳሳተ ሪፖርት ካቀረበ፤ ወይም
2. ባለሥልጣኑ በወሰነው ወይም ባጸደቀው ቅጽ እና አቀራረብ መሠረት መያዝ የሚገባውን ሪከርድ ሳይዝ ከቀረ፤

እስከ ሁለት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ወይም እስከ ብር 15,000 በሚደርስ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

32.<u>ሃሰተኛ ወይም አሳሳች መግለጫ ስለማቅረብ</u>

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት መቅረብ የሚገባውን መረጃ በሚመለከት ሃሰተኛ ወይም አሳሳች መግለጫ ለባለሥልጣኑ ያቀረበ እንደሆነ እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ወይም እስከ ብር 25,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

33.<u>ሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው አካል ላይ ስለሚጣል ቅጣት</u>

በዚህ አዋጅ የተመለከቱት ወንጀሎች በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው ሰው በተፈጸመ ጊዜ ቅጣቱ አግባብ ያላቸውን የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች ተከትሎ ይወሰናል፡፡

## <u>ክፍል ስምንት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

34.<u>ክፍያዎች</u>

ማንኛውም ባለፍቃድ በዚህ አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ መሰረት ከተወሰነው ታሪፍ በላይ ክፍያ ሊጠይቅ አይችልም፡፡

35.<u>ስለከተማ ፕላን</u>

1. ማንኛውም የከተማ ፕላን የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ ሥርዓቱን በግልጽ መለየት እና ማሳየት ይኖርበታል።
2. ማንኛውም ባለፈቃድ የኤሌክትሪክ መስመር ሲዘረጋ የከተማውን ማስተር ፕላን ተከትሎ መሆን አለበት፡፡

## 36. ስለሌሎች ግንባታዎች እና ሥራዎች

ከኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ እና ማከፋፈያ ጣቢያዎች ወይም መስመሮች ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ወይም መመሪያ በሚወሰን የርቀት ክልል ውስጥ ማናቸውንም ዓይነት ግንባታዎች፣ እርሻዎች፣ ተክሎች ወይም ሌሎች የቋሚነት ጸባይ ያላቸውን ሥራዎች ማከናወን አይቻልም፡፡

## 37. በነባር የማስተላለፊያ እና የማከፋፈያ መስመሮች ስለመጠቀም

በባለፈቃዱ የማስተላለፊያ እና የማከፋፈያ መስመሮች ሌሎች ባለፈቃዶች የባለፈቃዱን ሥራዎች በማያደናቅፍ ሁኔታና ባለሥልጣኑ የሚወስነውን ታሪፍ በመክፈል እንዲገለገሉበት ሲጠይቁ መፍቀድ አለበት፡፡

## 38. ስለክርክሮች አፈታት

1. ባለሥልጣኑ፦
   ሀ) ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ በሚደነገገው መሰረት ባለፈቃዱ ባላከበራቸው ከኤሌክትሪክ አገልግሎቶች ወይም ከኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ተግባራት ጋር በተገናኘ ደንበኛው በባለፈቃዱ የተመቻቸውን አቤቱታ የመስማት ሂደቶች በሙሉ ከፈፀመ በኋላ የሚቀርብለትን የደንበኛውን አቤቱታ መስማት አለበት፤
   ለ) ከኤሌክትሪክ አቅርቦት ሁኔታዎች፣ ከታሪፍ ወይም ከአቅርቦት ወይም ከአገልግሎት ጥራት ጋር በተገናኘ በባለፈቃዶች መካከል ወይም በባለፈቃድና በደንበኛ መካከል አለመግባባት ሲከሰት እና ጉዳዩን ለባለሥልጣኑ ለማቅረብ ሲስማሙ ባለሥልጣኑ አለመግባባቱን በማስማማት ሊፈታው ወይም በግልግል ሊዳኘው ይችላል፡፡
2. ባለስሥልጣኑ አለመግባባቱን በማስማማት ለመፍታት ቅድሚያ ይሰጣል፤ ሆኖም አለመግባባቱን በማስማማት ለመፍታት የማይቻል ከሆነ የመጨረሻና አስገዳጅነት ያለው ዳኝነት በመስጠት አለመግባባቱን በግልግል ይፈታል፡፡
3. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ) እና (2) መሰረት አለመግባባቶችን በግልግል ለመፍታት እንዲችል የግልግል ፓናል ያቋቁማል፡፡

4. የግልግል ፓናሉ አባላት እና በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚቀርቡ አለመግባባቶች እና አቤቱታዎች የሚፈቱበት ሥነ ሥርዓት በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

## 39.ስለመክሰር

1. አግባብ ባላቸው የንግድ ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት በባለፈቃዱ ላይ የመክሰር ውሳኔ ከተሰጠና አዲስ ባለፈቃድ ሥራውን ለመቀጠል ፍላጎቱን ካሳየ የደንበኞችን ፍላጎት ከመጠበቅ አኳያ ባለሥልጣኑ የቀድሞውን ፈቃድ በመሰረዝ እና ማናቸውንም በቁጥጥሩ ስር ያሉ ተግባራትን ሁሉ በመፈጸም ሥራውን ወደ አዲሱ ባለፈቃድ ማስተላለፍ አለበት፡፡
2. የቀድሞው ባለፈቃድ ሥራዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለአዲስ ባለፈቃድ ሊተላለፉ የቀድሞው ባለፈቃድ ንብረቶች በሙሉ ወይም በከፊል ወደ አዲሱ ባለፈቃድ እንዲተላለፉለት ባለሥልጣኑ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር መተባበር አለበት፡፡

## 40.ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ባለሥልጣኑ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 41.የመመሪያዎች አወጣጥና ሕትመት

1. ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 40 (2) መሰረት ማንኛውንም መመሪያ ከማውጣቱ በፊት፦

    ሀ) ባለፈቃዶችን፤

    ለ) ከፍተኛ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን፤

    ሐ) የኢነርጂ ብቃትን የሚተገብሩ ተቋማትን፤ እና

    መ) ሌሎች ባለድርሻዎችን፤

    ሊወክሉ ይችላሉ ብሎ የሚገምታቸውን ሰዎች ማማከር አለበት፡፡
2. ባለሥልጣኑ የሚያወጣቸውን መመሪያዎች የማሳተም ሃላፊነት አለበት፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ማናቸውም መመሪያ ስለሚታተምበት አግባብ በባለሥልጣኑ ይወሰናል፡፡

42. <u>የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸዉ ሕጎች</u>

1. የኤሌክትሪክ አዋጅ ቁጥር 86/1989 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

43. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>

1. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 42 (1) ድንጋጌ ቢኖርም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 መሠረት የሚወጣው ደንብ እስከሚጸናበት ቀን ድረስ በኤሌክትሪክ አዋጅ ቁጥር 86/1989 ተቋቁሞ የነበረው የኤሌክትሪክ ኤጀንሲ ሕጋዊ ሰውነቱን እንደያዘ በመቀጠል በዚህ አዋጅ የተደነገገውን የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፡፡
2. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 42 (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በኤሌክትሪክ አዋጅ ቁጥር 86/1989 መሰረት ወጥተው የነበሩ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ስታንዳርዶች በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጡ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ስታንዳርዶች እስከሚተኩ ድረስ ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል።
3. በኤሌክትሪክ አዋጅ ቁጥር 86/1989 እና በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት ተሰጥተው የነበሩ ፈቃዶችና የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቶች በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት እንደተሰጡ ይቆጠራል።

44. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር 19 ቀን 2006 ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## ደንብ ቁጥር 447/2011

## የኢነርጂ ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀጽ 5 እና በኢነርጂ አዋጅ ቁጥር 810/2006 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ (40) (1) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢነርጂ ደንብ ቁጥር 447/2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ:-

   1. "አዋጅ" ማለት የኢነርጂ አዋጅ ቁጥር 810/ 2006 (በአዋጅ ቁጥር 1085/2010 እንደተሻሻለ) ነው፤
   2. በአዋጁ የተመለከቱት ትርጓሜዎች በዚህ ደንብ ላይ ተፈጻሚ ናቸው፤
   3. "የኢነርጂ ብቃት ውጤታማነት እርምጃ" ማለት የኢነርጂ ብቃትን ለማሻሻል የተወሰደ የአደረጃጀት፣ የቅርጽ፣ የቴክኒክ፣ የአፈጻጸም፣ የቴክኖሎጂ፣ የተቋም ወይም የቁጥጥር ለውጥ ነው፤
   4. "የኢነርጂ ብቃት አገልግሎት" ማለት የኢነርጂ አገልግሎቱ ባለበት እንዲቀጥል ወይም እንዲጨምር ሆኖ የኢነርጂ ፍጆታ እንዲቀንስ የሚያስችሉ የምርመራ፣ የምክር፣ የጥናት፣ የንድፍ፣ የግንባታ፣ የኢንስታሌሽን፣ የማሻሻል፣ የመጠገን፣ የማስተዳደር እና የመቆጣጠር ተግባራትን በማሸን፣ በዕቃዎችና በሕንጻዎች ላይ ማከናወን ነው፤
   5. "የአጭር ጊዜ ፕሮግራም" ማለት ከአንድ ዓመት እስከ ሦስት ዓመት ድረስ የሚሸፍን ፕሮግራም ነው፤
   6. "የመካከለኛ ጊዜ ፕሮግራም" ማለት ከአራት ዓመት እስከ ስድስት ዓመት ድረስ የሚሸፍን ፕሮግራም ነው፤

7. “የረጅም ጊዜ ፕሮግራም” ማለት ከሰባት ዓመት እስከ አስር ዓመት ድረስ የሚሸፍን ፕሮግራም ነው፤
8. “ፋሲሊቲ” ማለት ለሥራቸው ኢነርጂ የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪን፣ ሕንጻን፣ ይዞታን እና ተያያዥ ኢንስታሌሽን እና መሣሪያዎችን ይጨምራል፤
9. “ኢንዱስትሪ” ማለት ለንግድ ዓላማ ዕቃዎችን በማምረት ተግባር የተሰማራ እና ለዚሁ ተግባር ኤሌክትሪክ የሚጠቀም ፋብሪካ ነው፤
10. “የተመረጠ ፋሲሊቲ” ማለት የኢነርጂ አጠቃቀምን መሠረት በማድረግ በባለሥልጣኑ በሚወጣ መመሪያ መሠረት የተመረጠ ኢንዱስትሪ ወይም ሕንጻ ነው፤
11. “የማመንጫ ፋሲሊቲ” ማለት ኤሌክትሪክን የሚያመነጭ የቴክኖሎጂ ስብስብ ነው፤
12. “ግሪድ ኮድ” ማለት የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት፣ የማስተላለፍ እና የማከፋፈል ሥርዓትን በሚመለከት አስፈላጊ የቴክኒክ አፈጻጸም መመዘኛዎችን የያዘ በባለስልጣኑ የሚወጣ ኮድ ነው፤
13. “ይዞታ” ማለት ከማናቸውም መሬት፣ ሕንጻ ወይም ግንባታ ጋር በተያያዘ የሚኖር እንደአግባቡ የመጠቀም ወይም የይዞታ መብት ነው፤
14. “የኔትወርክ አገልግሎት” ማለት የኤሌክትሪክ ኃይል የማስተላለፍ ወይም የማከፋፈል አገልግሎት ሲሆን የቮልቴጅ እና ፍሪኩዌንሲ መጠኑን ስምምነት ከተደረሰበት መጠን እንዳያልፍ ለመጠበቅ የሚያስችሉ ተጨማሪ አገልግሎቶችንም ያጠቃልላል፤
15. “ቆጣሪ” ማለት ማናቸውንም ተያያዥ እቃዎችን ጨምሮ የኤሌክትሪክ ፍጆታን የሚለካ መሣሪያ ነው፤
16. “ድጋፍ ሰጪ አገልግሎት” ማለት ኤሌክትሪክ ከማመንጨት እና ከማቅረብ ውጭ የሚሰጡ አገልግሎቶች ሲሆኑ የፍሪኩዌንሲ ቁጥጥርን፣ የመጠባበቂያ አቅም መጠን፣ የቮልቴጅ እና አፋጣኝ የኃይል ድጋፍ፣ ኤሌክትሪክ ከተቋረጠ በኋላ እንደገና የማስጀመር እና የኃይል ጭነት መጠን መቀነስን ወይም ማቋረጥን ያጠቃልላል፤
17. “ብቃቱ የተረጋገጠ ሰው” ማለት በዚህ ደንብ መሠረት ለኤሌክትሪክ ሥራ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ነው፤

18.“የብቻ ፈቃድ” ማለት ባለሥልጣኑ ለብቻ ፈቃድ በሰጠበት መልክዓ ምድራዊ አካባቢ ለተመሳሳይ ተግባር ሌላ ፈቃድ የማይሰጥበት ፈቃድ ዓይነት ነው፤

19.“የብቻ ያልሆነ ፈቃድ” ማለት በተመሳሳይ መልክዓ ምድራዊ አካባቢ ለተመሳሳይ ዓይነት ተግባራት እንዲያገለግል በተጨማሪ ፈቃድ ሊሰጥበት የሚችል የፈቃድ ዓይነት ነው፤

20.“አግባብ ያለው ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን” ማለት እንደየአግባቡ ባለሥልጣኑ ወይም ንግድ ሚኒስቴር[56] ወይም ማናቸውም የክልል የንግድ፣ የኢንዱስትሪ ወይም የግንባታ ቢሮ ነው፤

21.“ወቅታዊ ገበያ” ማለት ገዥዎች የኤሌክትሪክ ዋጋውን ለመክፈል የተዘጋጁበት እና ሻጮችም የኤሌክትሪክ ኃይሉን ለማስረከብ የተዘጋጁበት የኤሌክትሪክ የገበያ ሥርዓት ነው፤

22.“የግል ኃይል አመንጪ” ማለት በኃይል ግዥ ስምምነት ለብሔራዊ ግሪዱ ኤሌክትሪክ በጅምላ የሚሸጥ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ተቋም ባለቤት የሆነ ማናቸውም ሰው ነው፤

23.“ታዳሽ የኃይል ምንጭ” ማለት ኢነርጂ ለማመንጨት ጥቅም ላይ የሚውል እንደ ፀሀይ ብርሃን፣ ነፋስ፣ ውኃ እና የከርሰምድር እንፋሎት ያለ ታዳሽና የማያልቅ የተፈጥሮ ሀብት ነው፤

24.“ቁጥጥር የሚደረግበት መሠረታዊ ንብረት” ማለት በባለሥልጣኑ የእርጅና ቅናሽ ላይና የንብረት ተመላሽ ላይ በመመስረት ባለፈቃዱ ከሽያጭ ሊያገኝ የሚገባውን ገቢ የሚያሰላበት በባለሥልጣኑ የተፈቀደ የባለፈቃዱ ንብረት ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## ፈቃድ እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

### 3. ስለማመልከቻ አቀራረብና ፈቃድ አሰጣጥ ጠቅላላ መስፈርቶች

1. ማናቸውንም ፈቃድ ለማግኘት ለባለሥልጣኑ የሚቀርብ ማመልከቻ ባለሥልጣኑ ለዚህ ዓላማ ያዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ከሚከተሉት የአመልካቹ መረጃዎች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት:-

ሀ) የአመልካቹን ማንነት እና አድራሻ፤

ለ) የአመልካቹን የፋይናንስ አቅምና ሁኔታ፤

[56] 25/08 (2011) አ.1097 አንቀጽ9(7) የንግድና ኢንድስትሪ ሚንስቴር ሆኗል፡፡

ሐ) የአመልካቹን የቴክኒክ ብቃት እና ልምድ፤

መ) የማመልከቻ መመርመሪያ ክፍያ ደረሰኝ፡፡

2. ባለሥልጣኑ ለአመልካቹ ፈቃዱን መስጠት የሚችለው አመልካቹ ፈቃድ እንዲሰጠው በማመልከቻ የጠየቀውን የኤሌክትሪክ ተቋም ገንብቶ አገልግሎት ላይ የማዋል ብቃት ያለው መሆኑን በማረጋገጥ ይሆናል፡፡

3. ባለሥልጣኑ አመልካቹ ብቁ መሆኑን አረጋግጦ ፈቃድ ለመስጠት የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ሊያስገባ ይችላል፡-

ሀ) አመልካቹ የቀድሞ እና የወቅቱ የንግድ ሥራዎቹንና እና ተያያዥ ሕጋዊ ግዴታዎቹን መፈጸሙንና ካልፈጸመም ምክንያቱን፤ እና

ለ) በአዋጁ መሠረት ፈቃድ በተሰጣቸው የንግድ ዘርፎች ላይ በማጭበርበር ወይም በተመሳሳይ ጥፋት በወንጀል ተከሶ አለመቀጣቱን፡፡

4. አመልካቹ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ሰው ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከቱት ጉዳዮች ተፈጻሚነት የሚኖራቸው እንደየአግባቡ በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል የሥራ ኃላፊዎች ላይም ይሆናል፡፡

5. በዚህ ደንብ መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ተቋሙን ለማልማት፣ ለመገንባት፣ ለማሠራት ወይም ለመጠገን ተግባራዊ የሚሆኑ አግባብነት ያላቸውን ሌሎች ሕጎችን የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

6. ባለሥልጣኑ አመልካቹ የጠየቀውን ፈቃድ የከለከለ እንደሆነ ፈቃዱን የከለከለበትን ምክንያት ለአመልካቹ በጽሁፍ መግለጽ እና ቅሬታ ካለው እንደገና እንዲታይለት ለመጠየቅ መብት እንዳለው ማሳወቅ አለበት፡፡

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) መሠረት የውሳኔው ማስታወቂያ የደረሰው አመልካች ቅሬታውን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለባለሥልጣኑ ቅሬታ ሰሚ አካል ማቅረብ ይችላል፡፡

8. ባለሥልጣኑ ከብሔራዊ ግሪድ ውጭ ስለሚሰሩ አነስተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት፣ የማከፋፈልና እና የመሸጥ ፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓትን በተመለከተ መመሪያ ያወጣል፡፡

9. የአዋጁ አንቀጽ 6 (2) እንደተጠበቀ ሆኖ ለንግድ ላልሆነ ዓላማ ኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት፣ ለማስተላለፍ ወይም ለማከፋፈል ፍላጎት ያለው ማንኛውም ሰው

ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ መሠረት መረጃዎችን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

4. **<u>የፈቃድ ማመልከቻን ስለመመዝገብ</u>**

1. ባለሥልጣኑ የፈቃድ ማመልከቻ በዚህ ደንብ አንቀጽ 3 በተመለከተው መሠረት ተሟልቶ መቅረቡን በማረጋገጥ ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀው የምዝገባ ማመልከቻ መዝገብ ላይ እንደ ማመልከቻው ቅደም ተከተል በመመዝገብ ለአመልካቹ የምዝገባ ቀኑንና ቁጥሩን የሚገልጽ ደረሰኝ ይሰጣል፡፡
2. ባለሥልጣኑ የሚሰጠውን እያንዳንዱን ፈቃድ እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መዝግቦ መያዝ እና መዝገቡንም ለሕዝብ ክፍት ማድረግ አለበት፡፡

5. **<u>የፈቃድ ማመልከቻን ይፋ ስለማድረግ</u>**

1. ባለሥልጣኑ ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት በአመልካቹ ወጪ የፈቃድ ጥያቄውን ሰፊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ ወይም በሌሎች የመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች አማካኝነት የሚከተሉትን መረጃዎች ይፋ ማድረግ አለበት:-
   ሀ) ለፈቃድ ጥያቄ የቀረበውን ማመልከቻ እና የአመልካቹን ስም፤
   ለ) ሚስጥራዊ ከሆኑ የንግድ መረጃዎች በስተቀር ኅብረተሰቡ ማመልከቻውን ከባለሥልጣኑ ቢሮ ቀርቦ ሊመለከት የሚችል መሆኑን፤
   ሐ) የተጠየቀው ፈቃድ ቢሰጥ ጉዳት ይደርስብኛል የሚል ካለ በጋዜጣ ወይም በሌላ መገናኛ ብዙሃን ላይ በተገለጸ በ30 ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን በጽሁፍ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ የሚችል መሆኑን፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በወጣ ማስታወቂያ ላይ ተቃውሞ የቀረበ እንደሆነ ባለሥልጣኑ የሚመለከታቸው ወገኖች በስምምነት ለመጨረስ ድርድር እንዲያካሂዱ ያደርጋል፡፡
3. የቀረበውን ተቃውሞ አስመልክቶ ድርድር እንዲያካሂዱ ከተወሰነበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች መስማማት ካልቻሉ፤ ባለሥልጣኑ የሁለቱንም ወገኖች ክርክር በመስማት የቀረበውን ተቃውሞ በመቀበል ወይም ውድቅ በማድረግ በ30 ቀናት ውስጥ ውሣኔ ይሰጣል፡፡

6. **<u>ማመልከቻን ስለማሻሻል</u>**

1. አመልካቹ በማመልከቻው ላይ ማናቸውንም ማሻሻያ ለማድረግ የፈለገ እንደሆነ ለባለሥልጣኑ በጽሁፍ ማመልከት አለበት፡፡

2. ተሻሽሎ በቀረበው ማመልከቻ ላይ የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

7. **የማመንጨት ፈቃድ ማመልከቻ**

ማንኛውም ኤሌክትሪክ የማመንጨት ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ በዚህ ደንብ አንቀጽ 3 ከተመለከቱት ጠቅላላ መስፈርቶች በተጨማሪ የሚከተሉትን መያዝ አለበት:-

1. በቅድሚያ የፈቃድ ማመልከቻ ጥያቄ ሲቀርብ:-
   ሀ) የኤሌክትሪክ መገኛ ምንጩን፤
   ለ) የፕሮጀክቱን ቦታ የሚያሳይ ካርታ፤
   ሐ) የፕሮጀክቱን አጠቃላይ የማመንጨት አቅም በመለኪያ፤
   መ) የሚገናኘውን የማስተላለፊያ ግሪድ ወይም የተያያዘ የአቅርቦት ኔትወርክ ወይም ከግሪድ ውጭ የሚሰራ ስለመሆኑ፤
   ሠ) ቢያንስ የፕሮጀክት ቅድመ አዋጪነት ጥናት፤
   ረ) የታቀደ የገንዘብ ምንጭ እና የብድር እና የመዋጮ ተነጻጻሪነት በመቶኛ፤
   ሰ) ፈቃዱ ፀንቶ እንዲቆይ የሚፈለግበት ጊዜ፤ እና
   ሸ) ፈቃድ ሰጪው አስፈላጊ ናቸው ብሎ ያመነባቸውን ሌሎች ተያያዥ ማስረጃዎች፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የቀረበ የፈቃድ ማመልከቻ ጥያቄ መሠረት ፈቃድ ሲሰጥ በፈቃዱ ላይ የተመለከተውን የንግድ ሥራ ከመጀመሩ በፊት:-
   ሀ) እንደአግባቡ የፀደቀ የኃይል ግዥ ስምምነት፤
   ለ) እንደአግባቡ የፕሮጀክት ፋይናንስ ስምምነት፤
   ሐ) ከሚመለከተው አካል የአካባቢ ተጽዕኖ ሁኔታ ግምገማ ይሁንታ የምስክር ወረቀት፤
   መ) እንደአግባቡ፤ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፤ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፤ የመሬት አጠቃቀም የምስክር ወረቀት፤ የውሃ መጠቀሚያ ፈቃድ፤ የከርሰምድር እንፋሎት ኃይል የማልማት ፈቃድ፣ ሌሎች ቀዳማይ የኢነርጂ ምንጮችን የማልማት ፈቃድ፤ እና የግንባታ ፈቃድ፤ ተሟልተው መቅረብ አለባቸው፡፡

8. **<u>የኤሌክትሪክ ማስተላለፍ ፈቃድ ማመልከቻ</u>**

ከብሔራዊ ግሪዱ ጋር በተያያዘ ኤሌክትሪክ የማስተላለፍ ፈቃድ ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው መንግሥታዊ ተቋም ብቻ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የማስተላለፍ ፈቃድ ጥያቄ ማመልከቻው በዚህ ደንብ አንቀጽ 3 ከተመለከቱት አጠቃላይ መስፈርቶች በተጨማሪ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል:-

1. የማስተላለፊያ ግሪዱ የሚያልፍበት መስመር ካርታና የሥራ ቦታ፤
2. የፕሮጀክት አዋጪነት ጥናት፤
3. የማስተላለፊያ ግሪዱ ከሌላ ግሪድ ጋር የሚገናኝ ከሆነ የሚገናኘው ሌላኛው የማስተላለፊያ ግሪድ፤
4. ትክክለኛ የማስተላለፊያ ግሪዱ ወሰን፤
5. ሊገናኝ የሚችልበትን የአቅርቦት ኔትወርክ፤
6. ከሚመለከተው አካል የአካባቢ ተጽዕኖ ሁኔታ ግምገማ ይሁንታ የምስክር ወረቀት፤ እና
7. ፈቃዱ ፀንቶ እንዲቆይ የሚፈለግበት ጊዜ፡፡

9. **<u>ለኤሌክትሪክ ማከፋፈል እና መሸጥ ፈቃድ ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>**

በብሔራዊ ግሪዱ ውስጥ ኤሌክትሪክ የማከፋፈልና የመሸጥ ሥራ ለመሥራት ብቸኛ መብት ባለው የመንግሥት ተቋም ኤሌክትሪክ የማከፋፈል እና የመሸጥ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ በዚህ ደንብ አንቀጽ 3 ከተመለከቱት አጠቃላይ መስፈርቶች በተጨማሪ የሚከተሉትን መያዝ አለበት:-

1. የማከፋፈል ኔትወርክ የሚያልፍበት መስመር ካርታና እና የሥራ ቦታ፤
2. የፕሮጀክት አዋጪነት ጥናት፤
3. የማከፋፈል ሥራው ከሌላ የማከፋፈል እና የመሸጥ ኔትወርክ ጋር የሚገናኝ ከሆነ ሊገናኝ የሚችልበት የሌላኛው የማከፋፈል እና የመሸጥ ኔትወርክ ዋና ዋና መረጃዎች፤
4. ትክክለኛ የማከፋፈል እና የመሸጥ ኔትወርክ ወሰን፤
5. ሊገናኝ የሚችልበት የማስተላለፊያ ኔትወርክ ወይም የኤሌክትሪክ ምንጭ፤
6. እንደአግባቡ የኃይል ግዥ ስምምነት
7. ከሚመለከተው አካል የአካባቢ ተጽዕኖ ሁኔታ ግምገማ ይሁንታ የምስክር ወረቀት፤ እና

8. ፈቃዱ ፀንቶ እንዲቆይ የሚፈለግበት ጊዜ፡፡

10. **<u>ለኤሌክትሪክ አስመጪነት ወይም ላኪነት ፈቃድ ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>**

ኤሌክትሪክ ወደውጭ ሃገር ለመላክ ወይንም ከውጭ ሃገር ለማስገባት የሚቀርብ ማመልከቻ በዚህ ደንብ አንቀጽ 3 ከተመለከቱት አግባብ ካላቸው መስፈርቶች በተጨማሪ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡-

1. ከብሔራዊ ግሪድ ኮድ ጋር የተጣጣመ መሆኑን የሚያረጋግጥ የቴክኒክ ደረጃ፤
2. እንደአግባቡ የኃይል ግዥ ስምምነት ወይንም የኃይል ማስተላለፍ አገልግሎት ስምምነት፤
3. እንደአግባቡ በወቅታዊ ገበያ ለመሳተፍ የሚያስችለው ተቀባይነት ያለው አግባብ ካለው ተቋም የተሰጠ ፈቃድ ወይንም የሰነድ ማስረጃ፤
4. ከሃገር ውስጥ ወደውጭ ሃገር እንዲላክ ወይንም ከውጭ ሃገር ወደሃገር ውስጥ እንዲገባ የሚፈለግ የኃይልና የኢነርጂ መጠንና ምንጩ፤
5. ወደውጭ ሃገር የሚላከው ወይንም ከውጭ ወደሃገር ውስጥ እንዲገባ የሚፈለገው የኃይል መጠን በተገልጋዮችና በኢኮኖሚው ላይ ሊያሳድር የሚችለው አንደምታ፤ እና
6. እንደአግባቡ ኤሌክትሪክ ከሚያስመጣበት ወይንም ከሚልክበት ሃገር ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የተደረገ ስምምነት፡፡

11. **<u>ስለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ</u>**

1. ማንኛውም ሰው ከባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይሰጠው የኤሌክትሪክ ሥራ ተግባራትን ማከናወን አይችልም፡፡
2. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት በባለሙያ የሚቀርብ ማናቸውም ማመልከቻ ከዝርዝር የቴክኒክ መስፈርቶችና መረጃዎች በተጨማሪ የሚከተሉትን መያዝ አለበት:-

    ሀ) የአመልካቹን ማንነት እና አድራሻ፤

    ለ) የትምህርት ደረጃ፤ እና

    ሐ) እንደአስፈላጊነቱ የሥራ ልምድ፡፡
3. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት በድርጅት የሚቀርብ ማናቸውም ማመልከቻ ከዝርዝር የቴክኒክ መስፈርቶችና መረጃዎች በተጨማሪ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡-

ሀ) የአመልካቹን አድራሻ፣

ለ) በቋሚነት ስለተቀጠሩ ብቁ ባለሙያዎች፣

ሐ) እንደአግባቡ የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ፡፡

4. አመልካች ማመልከቻውን በዚህ ደንብ በሰንጠረዥ 1 ከተገለፀው የማመልከቻ መመርመሪያና የምዝገባ ክፍያ ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡
5. ባለሥልጣኑ አመልካች ከማመልከቻው ጋር አያይዞ ያቀረባቸውን መረጃዎች ትክክለኛነት መርምሮ ካረጋገጠ በኋላ አመልካቹ ላመለከተበት የምስክር ወረቀት ደረጃ ብቁ ስለመሆኑ ለመወሰን እንደአግባቡ የጽሁፍ እና የተግባር ፈተና ሊሰጥ ይችላል፡፡
6. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ የተደነገገው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስፈርቶች መሟላታቸውን ያረጋገጠ እንደሆነ በዚህ ደንብ በሰንጠረዥ 1 የተገለፀውን የምስክር ወረቀት ክፍያ በማስከፈል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ለአመልካቹ መስጠት አለበት፡፡
7. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለመስጠት የሚያስፈልጉ ዝርዝር የቴክኒክ መስፈርቶችና መረጃዎች ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡
8. ባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ እንዲሰጠው የጠየቀው ሰው ያቀረበው መረጃ በቂ አይደለም ብሎ ከወሰነ ይህንኑ ውሳኔ ለአመልካቹ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

12. <u>ፈቃዱ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ እና እድሳት</u>

1. በአዋጁ እና በዚህ ደንብ መሠረት የሚሰጥ ፈቃድ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ እንደሚከተለው ይሆናል:-

   ሀ) ለውኃ እና ለጂኦተርማል ኃይል ማመንጫ ፈቃድ እስከ 25 ዓመት፣

   ለ) ለነፋስ፣ ለፀሀይ፣ ለባዮማስ፣ ለከተማ ቆሻሻ፣ ለተርማል እና ለባዮጋዝ ኃይል ማመንጫ ፈቃድ እስከ 20 ዓመት፣

   ሐ) ለማስተላለፍ ፈቃድ እስከ 30 ዓመት፣ እና

   መ) ለማከፋፈል እና ለመሸጥ ፈቃድ እስከ 20 ዓመት፡፡
2. በሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ፈቃድ ሊታደስ የሚችለው ባለፈቃዱ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ሲያሟላ ብቻ ይሆናል:-

ሀ) የፈቃድ ጊዜው ከማብቃቱ ከአንድ ዓመት በፊት ሲያመለክት እና ፋሲሊቲዎች በጥሩ የሥራ ሁኔታ ላይ ስለመሆናቸው በባለሥልጣኑ ሲረጋገጥ፤

ለ) ባለፈቃዱ ለፈቃድ መሠረዝ ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ማናቸውንም የአዋጁን፣ የዚህን ደንብ እና ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚወጣ መመሪያ ድንጋጌዎችን ያልጣሰ ከሆነ፤ እና

ሐ) በኃይል ኢንደስትሪ ውስጥ በአጠቃላይ ተቀባይነት ባገኘ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ መሠረት ሥራዎችን ለማሳደግ የተስማማ ከሆነ፡፡

3. እያንዳንዱ የፈቃድ እድሳት ጊዜ ፈቃዱ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሰጥ ጸንቶ እንዲቆይ የተደረገበት ዓመታት ካበቃ በኋላ እንደሚከተለው ይሆናል:-

ሀ) ለውኃ ኃይል ማመንጫ ፈቃድ እስከ 12 ዓመት ከ6 ወር፤

ለ) ለነፋስ፣ ለፀሀይ፣ ለባዮማስ፣ ለከተማ ቆሻሻ፣ ለተርማል እና ለባዮጋዝ ኃይል ማመንጫ ፈቃድ እስከ 10 ዓመት፤

ሐ) ለማስተላለፍ ፈቃድ እስከ 15 ዓመት፤

መ) ለማከፋፈል እና ለመሸጥ ፈቃድ እስከ 10 ዓመት፡፡

4. የኤሌክትሪክ ኃይልን ወደውጭ ሃገር ለመላክ ወይንም ከውጭ ሃገር ለማስመጣት የሚሰጥ ፈቃድ ዘመን እና የእድሳት ጊዜ በዚህ አንቀጽ ለማስተላለፊያና እንደአግባቡም ለማከፋፈልና ለመሸጥ ከተቀመጠው ፈቃድ ዘመን ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

13. <u>ፈቃድን ስለማሻሻል</u>

1. ፈቃዱን ለማሻሻል የሚፈልግ ማንኛውም ባለፈቃድ የጽሁፍ ማመልከቻ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የቀረበ ማመልከቻ ላይ የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ ቅጽ ተሞልቶ ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር ለባለሥልጣኑ መቅረብ አለበት፡-

ሀ) የነባሩ ፈቃድ ቅጂ፤

ለ) ማመልከቻው የቀረበው በወኪል ከሆነ የውክልና ማስረጃ ቅጂ፤

ሐ) ኢንቨስትመንቱ የሚፈጸመው በንግድ ማኅበር ሲሆን የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ቅጂ፤ እና

መ) ሌሎች በባለሥልጣኑ መመሪያ የተወሰኑ ሰነዶች፡፡

4. ማንኛውም ሰው በተመሳሳይ ሥራ በተለያየ ቦታ ለመሰማራት ወይም ሥራውን ለብቻ ፈቃድ ካልሆነ አካባቢ ውጭ ለማስፋፋት ሲወስን አዲስ ፈቃድ ማውጣት አለበት፡፡

14.<u>ፈቃድን ስለማስተላለፍ</u>

ማንኛውም ባለፈቃድ ፈቃዱን ሊያስተላልፍ የሚችለው ፈቃዱ የሚተላለፍለት ሰው በፈቃዱ የተመለከቱትን ግዴታዎች ለመወጣት የሚያስችል ብቃት ያለው ስለመሆኑ በባለሥልጣኑ ሲረጋገጥ ይሆናል፡፡

15.<u>የፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን ስለማገድ ወይም ስለመሰረዝ</u>

1. ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ፈቃድ ሊታገድ ይችላል፡-

ሀ) በባለስልጣኑ ከተሰጠው ደረጃ ውጭ መሠረታዊ የአገልግሎት አቅርቦት ጥራት ጉድለት ወይም የደህንነት ጉድለት ሲፈጠርና በተሰጠው የማስተካከያ ጊዜ ውስጥ የእርምት እርምጃ ያልወሰደ እንደሆነ፤

ለ) በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት ማቅረብ የሚገባውን ሪፖርት አሟልቶ ያላቀረበ ወይም የተሳሳተ ሪፖርት ያቀረበ እንደሆነ ወይም አስፈላጊ ሰነዶችን ሳይዝ የቀረ እንደሆነ፤

ሐ) የባለሥልጣኑ የቁጥጥር ሥራ እንዳይከናወን ሆነ ብሎ ያሰናከለ ወይም ያወከ እንደሆነ፤

መ) ከባለሥልጣኑ እውቅና ውጭ ለሦስተኛ ወገን ፈቃዱን አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፤ ወይም

ሠ) የማመንጫ ባለፈቃድ ሲሆን፣ የፈቃድ ስምምነቱ በሚጠይቀው መሠረት የታደሰ የኃይል ግዥ ስምምነት ያላቀረበ እንደሆነ፡፡

2. ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሊታገድ ይችላል፡-

ሀ) በብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ላይ ከተፈቀደው ሥራ ውጭ መሰማራት ወይም ደረጃውን ያልጠበቀ ሥራ መስራት፤

ለ) የሰራው ሥራ መሠረታዊ በሆነ የደህንነትና የጥራት ችግር ምክንያት በተገልጋዩ ላይ የህይወት ወይም የንብረት አደጋ መፍጠር፤

ሐ) በዚህ ደንብ መሠረት መቅረብ የሚገባውን ሪፖርት ሳያሟላ ማቅረብ ወይም የተሳሳተ ሪፖርት ማቅረብ ወይም አስፈላጊ ሰነዶችን አለመያዝ፤

መ) የባለስልጣኑ የቁጥጥር ሥራ እንዳይከናወን ሆነ ብሎ ማሰናከል ወይም ማወክ፣ እና

ሠ) በባለሥልጣኑ የተሰጠውን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት፡፡

3. ባለሥልጣኑ ፈቃድን ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን ከማገዱ በፊት ለማገጃ ምክንያት የሆኑ ጉዳዮችን በመግለጽ ቢያንስ ከ45 (አርባ አምስት) ቀናት በፊት ለባፈቃዱ ወይም ለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለቤቱ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት አለበት፡፡

4. ፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የታገደበት ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (3) መሠረት በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የማስተካከያ እርምጃ ያልወሰደ እንደሆነ ወይም በሁለት ዓመት ውስጥ እገዳን ሊያስከትል የሚችል ሌላ ጥፋት ደግሞ የመፈጸመ እንደሆነ ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡

5. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት በሚሰጠው የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ውስጥ ባለፈቃዱ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ባለቤቱ የሚወስደውን እርምጃ ወይም የመፍትሔ ሀሳብን ለባለሥልጣኑ በጽሁፍ እንዲያቀርብ ማሳወቅ አለበት፡፡

6. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (8) የተመለከተው ጊዜ እንዳበቃ፡-

ሀ) ማናቸውንም ፈቃድ በሙሉ ወይም በከፊል ሲያግድ ወይም ሲሰርዝ ስለእገዳው ወይም ስለስረዛው ሰፊ ስርጭት ባለው መገናኛ ብዙሃን ለሕዝብ ይፋ ማድረግ አለበት፡፡

ለ) ማናቸውንም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በሙሉ ወይም በከፊል ሲያግድ ወይም ሲሰርዝ ስለእገዳው ወይም ስለስረዛው ሰፊ ስርጭት ባለው መገናኛ ብዙሃን ለሕዝብ ይፋ ሊያደርግ ይችላል፡፡

7. ባለሥልጣኑ ፈቃዱን ወይንም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ለማገድ ሲወስን ፈቃዱ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ በመታገዱ ወይም በመሰረዙ ምክንያት በማንኛውም ሰው ላይ ሊደርስ የሚችለውን የጉዳት መጠን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

8. ፈቃዱ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ማንኛውም ሰው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ውሳኔው እንደገና እንዲታይለት በጽሁፍ ለባለስልጣኑ ማመልከት ይችላል፡፡

16.<u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ጸንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ እና እድሳት</u>

1. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለሁለት ዓመታት ጸንቶ ይቆያል፡፡
2. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ ከማብቃቱ ቢያንስ ከ15 (ከአስራ አምስት) ቀናት በፊት ከማመልከቻ ጋር ቀርቦ መታደስ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው ጊዜ ገደብ ውስጥ የምስክር ወረቀቱ ሳይታደስ ጊዜው ያለፈበት ማንኛውም ሰው የእድሳት ዘመኑ ካበቃ በኋላ ቀጥሎ ባሉት 90 (ዘጠና) ቀናት ውስጥ የምስክር ወረቀቱ እንዲታደስለት ለባለሥልጣኑ ሊያመለክት የሚችል ሲሆን፣ ባለሥልጣኑም በመመሪያ በሚወሰን መሠረት ቅጣት አስከፍሎ፣ ሊያድስ ይችላል፡፡
4. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም ባለሙያ የምስክር ወረቀቱን ለማሳደስ ሲቀርብ የምስክር ወረቀቱ ጸንቶ በቆየበት ጊዜ ውስጥ ቢያንስ ለሦስት ወራት ያህል የሥራ ልምድ ያገኘበትን የሚገልጽ ማስረጃ ወይም ከብቃት ማስረጃው ጋር ግንኙነት ባለው ተከታታይ የስልጠና ፕሮግራም ለ16 ሰዓታት ሥልጠና መካፈሉን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡
5. ማንኛውም ብቃቱ የተረጋገጠ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ለማሳደስ ሲቀርብ የድርጅቱን ባለሙያዎች የትምህርት ማስረጃ ከነብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ እና አስፈላጊ ከሆኑ ሌሎች ሰነዶች ጋር በማያያዝ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

17.<u>ፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለመተካት</u>

1. ማንኛውም ባለፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው በዚህ ደንብ በሰንጠረዥ 1 የተወሰነውን የማመልከቻና የምዝገባ ክፍያ በመክፈል የጠፋበትን ወይም የተበላሸበትን ፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ምትክ እንዲሰጠው ለባለሥልጣኑ ሊያመለክት ይችላል፡፡

2. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማመልከቻውን ከተቀበለ በኋላ አግባብ ያለውን ማጣራት አካሂዶ ምትክ ፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

18.**<u>ቁጥጥር ስለማካሄድ</u>**

1. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው በምስክር ወረቀቱ መሠረት ሥራውን እያከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ ባለሥልጣኑ ተቆጣጣሪ ሠራተኛ ይመድባል፡፡
2. በባለሥልጣኑ የተመደበ ተቆጣጣሪ ሠራተኛ የቁጥጥር ተግባሩን በሚያከናውንበት ጊዜ ከባለሥልጣኑ የተሰጠውን መታወቂያ በማሳየት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያለውን ሰው እንደአግባቡ ሰነዶችን፣ መዝገቦችን፣ ማሽኖችን፣ የመገልገያ መሣሪያዎችን እና ሌሎች በእጁ ያሉ መረጃዎችን ሊጠይቅ እና ሊመረምር ይችላል፡፡
3. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው በብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ ስለተከናወኑ ተግባራት ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ መሠረት ባለሥልጣኑ ያዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት የማጠናቀቂያ ሪፖርት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

19.**<u>ስለፈቃድ እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መሰረዝ</u>**

ፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በሚከተሉት ሁኔታዎች ይሰረዛል፣

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 12 እና አንቀጽ 16 መሠረት ያልታደሰ እንደሆነ፣ ወይም
2. በዚህ ደንብ አንቀጽ 15 መሠረት በባለሥልጣኑ የተሰረዘ እንደሆነ፣ ወይም
3. የወራሾች መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ባለፈቃዱ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያገኙ ግለሰብ የሞተ እንደሆነ ወይም የንግድ ድርጅት ሲሆን የፈረሰ ወይም የመክሰር ውሳኔ የተሰጠበት እንደሆነ፡፡

20.**<u>ስለፈቃድ እና ስለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ክፍያ</u>**

ፈቃድ መስጠትን፣ ማስተዳደርን እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን በተመለከተ ባለሥልጣኑ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚፈጸሙ ክፍያዎች የአገልግሎት ክፍያን በተመለከተ በዚህ ደንብ በሰንጠረዥ 1 መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## መብትና ግዴታ

### 21.የባለፈቃዱ መብቶች

ማንኛውም ባለፈቃድ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 22 (9) ላይ ከተደነገገው መጠን በታች የሆነ መዋዕለ ነዋይ እንዲጸድቅለት በራሱ ፍላጎት ለባለሥልጣኑ የማቅረብ፤
2. በፀደቀው ታሪፍ መሠረት ገቢውን የመሰብሰብ፤
3. በአዋጁ አንቀጽ 16 መሠረት የኤሌክትሪክ አቅርቦት ሥራዎችን ለማካሄድ በደንበኛው ይዞታ ውስጥ የመግባት፤
4. በአዋጁ አንቀጽ 12 መሠረት የደንበኞችን የኤሌክትሪክ አገልግሎት የማቋረጥ፤ እና
5. የደንበኞችን የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽኖችን የመመርመር፡፡

### 22.የባለፈቃዱ ግዴታዎች

ማንኛውም ባለፈቃድ በአዋጁ አንቀጽ 10 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ግዴታዎች አሉበት፡-

1. በአዋጁ፣ በዚህ ደንብ እና ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጡ መመሪያዎች እና የፈቃድ ሁኔታዎች መሠረት የኤሌክትሪክ አቅርቦት ሥራዎችን የማካሄድ፤
2. የፈቃዱን ተግባራት ለመጀመር የሚያስፈልጉትን ፋሲሊቲዎች ባለሥልጣኑ በሚያወጣው የግሪድ ኮድና ሌሎች አሠራሮች መሠረት የማሟላት፤
3. ሁሉንም የቅጥር፣ የገንዘብ፣ የንግድና ሌሎች መዛግብትን እና ሪከርዶችን እንዲሁም የኤሌክትሪክ ሥራዎችን መዛግብቶች ቢያንስ ለ10 ዓመታት የመያዝ፤
4. ዕቅድን፣ መረጃን እና ሪፖርቶችን በዚህ ደንብ እና ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ የአሠራር ሥርዓት በተወሰነው መሠረት የማቅረብ፤
5. የግንባታ ፕላንና ሪፖርት የማቅረብ፤
6. የንግድ ሥራውን በብቃት ለመምራት የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን፣ ሥርዓቶችን እና የአስተዳደር ዘዴዎችን ተግባራዊ ማድረግ እና ይህም አግባብነት ካላቸው ከሠራተኞች ጤና እና ደህንነት፤ ከሕዝብ፣ ከአካባቢ እና ከተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሕጎች ጋር የተጣጣመ ስለመሆኑ ለባለሥልጣኑ መረጃ የማቅረብ፤

7. የሰውን ህይወት፣ ንብረት፣ የአካባቢ እና የተፈጥሮ ሀብት ደህንነትን ለመጠበቅ የጥንቃቄ እርምጃ የመውሰድ፤
8. በኤሌክትሪክ አቅርቦት የያዘውን የብቸኛነት ቦታ ከፍተኛ ታሪፍ ለማስከፈል ወይም የወጪ ቅነሳ ብቃት እርምጃዎች እንዳይካተቱ ለማድረግ አለመጠቀም፤
9. ባለሥልጣኑ ባፀደቀው የኃይል ግዥ ስምምነት ወይም በባለሥልጣኑ በተፈረመ ሌላ ስምምነት ላይ ካልተመለከተ በስተቀር በፈቃዱ ከተሸፈነውና ቁጥጥር ከሚደረግበት ሀብት ከ10 በመቶ (ከአስር በመቶ) ዋጋ በላይ ለሚያደርገው የመዋዕለ ነዋይ ኢንቨስትመንት በቅድሚያ በባለሥልጣኑ እንዲፀድቅ የማድረግ፤
10. ለሠራተኞቹ አግባብ ያለው ሥልጠና የመስጠት፤
11. አግባብ ባለው አካል በፀደቀ ታሪፍና የኃይል ግዥ ስምምነት መሠረት ብቻ ክፍያ የመሰብሰብ፤
12. በባለሥልጣኑ የሚሰጡ ሁሉንም ማስታወቂያዎች ተግባራዊ የማድረግ፤ እና
13. የተሰረዘበትን ፈቃድ ለባለስልጣኑ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የመመለስ፡፡

23. <u>የማመንጨት ባለፈቃድ መብቶች እና ግዴታዎች</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 10 (3) (ሀ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኤሌክትሪክ የማመንጨት ባለፈቃድ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-
   ሀ) በፈቃዱ ውስጥ የተገለጸውን የማመንጫ ተቋም በፈቃዱ ውስጥ ከተገለጸው ማስተላለፊያ ወይም የአቅርቦት ኔትወርክ ጋር በማገናኘት ኤሌክትሪክ የመሸጥ፤
   ለ) በፈቃዱ ውስጥ በተመለከተው መሠረት በዚህ ደንብ እና ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ መሠረት በአካባቢ ወይንም በዓለም አቀፍ የገበያ ትስስር በወቅታዊ የገበያ ዋጋ ኤሌክትሪክ የመሸጥ፤
   ሐ) ባለስልጣኑ ባፀደቀው የኃይል ግዥ ስምምነት ላይ የተመለከተውን ክፍያ የማስከፈል፤
   መ) በኢንቨስትመንት አዋጁና ሌሎች አግባብነት ባላቸው የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ከማናቸውም የኢነርጂ ምንጮች ኤሌክትሪክ የማመንጨት፤ እና
   ሠ) አግባብ ባለው አካል በፀደቀ ታሪፍ ወይም ባለስልጣኑ በቅድሚያ ባፀደቀው የኃይል ግዥ ስምምነት መሠረት ለማስተላለፍ ወይም ለማከፋፈል እና ለመሸጥ ባለፈቃዱ ኤሌክትሪክ የማቅረብና ክፍያ የመሰብሰብ፡፡

2. የማመንጨት ባለፈቃዱ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል:-
   ሀ) በፈቃዱ ውስጥ በተገለጸው ጊዜ እና ቅድመ ሁኔታዎች መሠረት ሥራ የመጀመር፤
   ለ) ለማስተላለፊያ ግሪዱ ወይም በፈቃዱ ውስጥ ለተገለጸው የአቅርቦት ኔትወርክ ጥራቱን የጠበቀ ኤሌክትሪክ የማቅረብ፤
   ሐ) በፈቃዱ ላይ ለተገለጸው አካል ብቻ ኤሌክትሪክ የመሸጥ፤
   መ) ከማስተላለፊያ ግሪድ ጋር የማገናኘት ቴክኒካል ሁኔታዎችን ወይም በፈቃዱ ውስጥ የተገለጸውን የአቅርቦት ኔትወርክ ወይም በዚህ ደንብ እና ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ የተገለጹትን ሁኔታዎች የማክበር፤
   ሠ) በፈቃዱ መሠረት የሚያከናውናቸው ተግባራት በአካባቢው ላይ ስላላቸው ተጽዕኖ ተገቢውን ጥንቃቄ የመውሰድ፤
   ረ) በአገልግሎት ክፍያ ደንቡ መሠረት ፈቃዱን ለማስተዳደር የተወሰነውን ክፍያ የመክፈል፤
   ሰ) ባለሥልጣኑ በፈቃዱ ላይ የሚያካትታቸውን ሌሎች ግዴታዎች የመፈጸም፤
   ሸ) በማስተላለፍ ወይም በማከፋፈል እና በመሸጥ በባለፈቃዱ ጥያቄ መሠረት ኤሌክትሪክ የማመንጨትና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ተጨማሪ አገልግሎቶችን የማቅረብ፤
   ቀ) የማመንጫ ተቋሙን ብቃትና አስተማማኝነት ማረጋገጥና የሕዝቡን እና የሠራተኞቹን ደህንነት የመጠበቅ፤ እና
   በ) አግባብነት ያላቸውን የግሪድ እና የአፈጻጸም ኮዶችን የማክበርና ከባለሥልጣኑ ጋር ስምምነት በተገባው መሠረት ተገቢ በሆነ ጊዜ ውስጥ በግሪድ እና በአፈጻጸም ኮዶች የተቀመጡትን ግቦች የማሳካት፡፡

24.<u>የማስተላለፍ ባለፈቃድ መብቶች እና ግዴታዎች</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 10 (3) (ሀ) የተደነገገው እንደ ተጠበቀ ሆኖ፤ የማስተላለፍ ባለፈቃድ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-
   ሀ) በፈቃዱ ውስጥ የተገለጸውን የማስተላለፍ ግሪድ የመስራት፣ በፈቃዱ ውስጥ ተገልጾ ከሆነም የማስተላለፊያ ግሪዱን ከሌላ የማስተላለፊያ ግሪድ፣ የማከፋፈያ ኔትወርክ ወይም በፈቃዱ ውስጥ ከተገለጸ ማናቸውም የማስተላለፍ ቮልቴጅ ሽያጭ ቦታ ጋር የማገናኘት፤

ለ) በፈቃድ ክልሉ ውስጥ ኤሌክትሪክ የማስተላለፍ፤

ሐ) አግባብ ባለው አካል በፀደቀ የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ ታሪፍ መሠረት ለማከፋፈል እና ለመሸጥ ባለፈቃዱ ኤሌክትሪክ የማስተላለፍ፤

መ) አዋጪና የሃገር ውስጥ አቅርቦቱን የማያሰናክል ሆኖ ሲገኝ በአዋጁ አንቀጽ 14 (2) መሠረት ወጪና ገቢ የኃይል ሽያጭና ግዥ ሥራ ላይ አስቀድሞ በሚፈረም የኃይል ግዥ ስምምነት መሠረት ወይም በወቅታዊ የኃይል ገበያ የመሳተፍ፤

ሠ) የተገናኘውን የኤሌክትሪክ ሥርዓት ዘላቂነት፣ ደህንነት እና አስተማማኝነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ ተጨማሪ አገልግሎቶችን እንዲያቀርብለት የማመንጫ ባለፈቃዱን የመጠየቅ እና ግዥ የመፈጸም፡፡

2. የማስተላለፍ ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

ሀ) በቂ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ አስተማማኝ እና ደህንነቱ የተጠበቀ ኤሌክትሪክ ማስተላለፉን ለማረጋገጥ የማስተላለፊያ ግሪዱን የማሰራት፣ የመንከባከብ፣ የመጠገን እና የመጠበቅ፤.

ለ) ቴክኒካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች እስከፈቀዱ ድረስ ግሪዱ የኔትወርክ አገልግሎት ለመስጠት በበቂ አቅሙ የሚሠራ መሆኑን የማረጋገጥ፤

ሐ) በዚህ ደንብ እና ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ መሠረት ተግባራዊ የሚሆኑ ደረጃዎችን፣ ሁኔታዎችን እና ኮዶችን የማክበር፤

መ) እንደአግባቡ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ከተገናኘው የሌሎች ሀገራት የማስተላለፊያ ግሪድ ጋር በመተባበር የብሔራዊ ግሪዱን ሥራ ማከናወን፤

ሠ) የማስተላለፍ ኔትወርኩ ኢኮኖሚያዊ ሆኖ ብቃት፣ አስተማማኝነት እና ዘላቂነት ኖሮት የሕዝብን እና የሠራተኞቹን ምቾት እንዲያረጋግጥ የመጠገን እና የማልማት፤

ረ) የኤሌክትሪክ ፍላጎትን አስተማማኝ እና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መልክ ለማሟላት የሚያስችል የኃይል ማመንጫ ተቋማት ጠቋሚ እቅድ የማዘጋጀት፤

ሰ) በዕቅድ ላይ ተመስርቶ የማስተላለፊያ ኔትወርኩን አቅም ከፍላጎት ጋር በማጣጣም ለአስተማማኝ አገልግሎት ዝግጁ የማድረግ፤

ሸ) አግባብነት ያላቸውን የግሪድ እና የአፈጻጸም ኮዶችን የማክበርና ከባለሥልጣኑ ጋር በስምምነት በተወሰነው ተገቢ በሆነ ጊዜ ውስጥ ግቦችን የማሳካት፤ እና

ቀ) በዕቅድ ላይ ተመሥርቶ አዲስ የኃይል ማመንጫ ተቋማትን እና ወጣ ያለ የማከፋፈያ ኔትወርክን ለማገናኘት በወቅቱ ያለውን ኔትወርክ የማጠናከር ወይም ሽፋኑን የማስፋት፡፡

25.<u>የማከፋፈል እና የመሸጥ ባለፈቃድ መብቶችና ግዴታዎች</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 10 (3) (ሀ) የተደነገገው እንደ ተጠበቀ ሆኖ የማከፋፈል እና የመሸጥ ባለፈቃዱ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-

   ሀ) በብሔራዊ ግሪድ ውስጥ በተሰጠ የፈቃድ ክልል ኤሌክትሪክ የማከፋፈል እና የመሸጥ የብቻ ፈቃድ መብት፤

   ለ) ከብሔራዊ ግሪድና ከየብቻ የፈቃድ ክልል ውጭ ላሉ አገልግሎት ፈላጊዎች ኤሌክትሪክ የማከፋፈልና የመሸጥ የብቻ ያልሆነ ፈቃድ መብት፤

   ሐ) ከኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ደንበኞች የኤሌክትሪክ አቅርቦትና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን የአገልግሎት ክፍያዎች አግባብ ባለው አካል በፀደቀ ታሪፍ መሠረት የመሰብሰብ፤

   መ) በዚህ ደንብ እና ይህን ደንብ ለማስፈፀም በሚወጡ መመሪያዎች መሠረት ከማመንጨት ወይም ከማስተላለፍ ባለፈቃድ ኤሌክትሪክ የመግዛት፤

   ሠ) ደንበኛው በአዋጁና በውለታው መሠረት ኃይል ለማቋረጥ የሚያበቁ ግዴታዎቹን ሲጥስና/ወይንም ከውል ውጭ አገልግሎቱን ሲጠቀም ኃይል የማቋረጥ፤

   ረ) አዋጪና የሃገር ውስጥ አቅርቦቱን የማያሰናክል ሆኖ ሲያገኘው አግባብ ባለው ፈቃድ ወጪና ገቢ የኃይል ግዥና ሽያጭ ሥራ ላይ የመሳተፍ፤ እና

   ሰ) የማከፋፈል እና የመሸጥ የብቻ ፈቃድ ሲሆን በፈቃድ ክልሉ ውስጥ የአቅርቦት ኔትወርኩን ተጠቅሞ ኤሌክትሪክ የማቅረብ፡፡

2. የአገልግሎት ጠያቂው ይዞታ ከባለፈቃዱ የማከፋፈል እና የመሸጥ ፈቃድ ክልል ውጭ ከሆነ ባለፈቃዱ የአቅርቦት ኔትወርኩን ለብቻ እስካልሆነው ፈቃድ ክልል ድረስ በመውሰድ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለጠያቂው መስጠት ይችላል፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው የሚከተሉት ሁኔታዎች እስከተሟሉ ድረስ ብቻ ነው፡-

   ሀ) የአገልግሎት ጠያቂው ይዞታ በሌላ የማከፋፈል እና የመሸጥ ባለፈቃድ የማከፋፈል እና የመሸጥ ክልል ውስጥ ካልሆነ፤

ለ) በሌላ የማከፋፈል እና የመሸጥ ባለፈቃድ ክልል ከሆኑ ቴክኒካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች አንጻር ተግባራዊ ለማድረግ ለሌላኛው ማከፋፈል እና መሸጥ ባለፈቃዱ ስለማይቻል ለጠያቂው ኤሌክትሪክ ለማቅረብ የማይችል መሆኑ ከታወቀ፣ ወይም የማከፋፈል እና የመሸጥ ባለፈቃዱን ለማገናኘት እና ለማቅረብ የሚስማማ ከሆነ፣ እና

ሐ) ኃይል የማቅረብ ባለፈቃዱ በራሱ የማከፋፈል እና የመሸጥ ክልል ውስጥ ያሉበትን ግዴታዎቹን ለማሟላት የማይጎዳው እስከሆነ ድረስ ብቻ ነው፡፡

4. የማከፋፈል እና የመሸጥ ባለፈቃዱ የአዋጁ አንቀጽ 10 እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ግዴታዎች አሉበት:-

ሀ) በውሉ መሠረት ለደንበኞች ኤሌክትሪክ የማቅረብ፣

ለ) በፈቃዱ ክልል ውስጥ ለአዲስ ኃይል የማገናኘት ጥያቄ ፈጣን ምላሽ የመስጠት፣

ሐ) የታቀደ የኤሌክትሪክ ማቋረጥን ከ72 (ከሰባ ሁለት) ሰዓታት በፊት ለደንበኞች የማሳወቅ፣

መ) ለደንበኞች ስለኤሌክትሪክ አጠቃቀም አስፈላጊ የሆነ መመሪያ የመስጠት፣

ሠ) ብቁ፣ አስተማማኝ እንዲሁም የኅብረተሰቡን፣ የሠራተኞችን እና የደንበኞችን ደህንነት በሚያረጋግጥ ሁኔታ የማከፋፈያ ሥርዓቱን የማልማት እና የመንከባከብ፣

ረ) አግባብነት ያላቸውን የግሪድ እና የአፈጻጸም ኮዶችን የማክበርና ከባለሥልጣኑ ጋር በተደረሰው ስምምነት መሠረት ተገቢ በሆነ ጊዜ ውስጥ በኮዶችና በአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃዎች ላይ የተቀመጡትን ግቦችን የማሳካት፣

ሰ) ለደንበኞች አቤቱታ አፋጣኝ ምላሽ የመስጠት፣

ሸ) የደንበኞችን አቤቱታዎች መዝግቦ የመያዝ እና በሦስተኛ አካል ሊደረግ ለሚችል ምርመራ ዝግጁ የማድረግ፣

ቀ) የደንበኞች አቤቱታ የሚሰማበትንና የሚፈታበትን መድረክ የማቋቋም፣

በ) በእቅድ ላይ ተመስርቶ የማከፋፈያ ኔትወርኩን አቅም ከፍላጎት ጋር በማጣጣም ለአስተማማኝ አገልግሎት ዝግጁ የማድረግ፣

ተ) በዕቅድ ላይ ተመሥርቶ አዲስ የኃይል ማመንጫ ተቋማትን ለማገናኘት በወቅቱ ያለውን ኔትወርክ የማጠናከር ወይም ሽፋኑን የማስፋት፣

ቸ) ኢኮኖሚያዊ ብቃት እንደሚያመጡ የታመነባቸውን የደንበኞች የኃይል አጠቃቀም ማሻሻያ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ፕሮግራሞች እንዲተገበሩ የማድረግ እና ለፕሮግራሞቹ አግባብ የሆነ የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት በቅድሚያ በባለሥልጣኑ ተቀባይነት የማግኘት፣

ነ) በትክክለኛ የኤሌክትሪክ ፍጆታ ንባቦች በመመስረት ግልጽ እና ትክክለኛ ደረሰኝ የመስጠት፣ እና

ኘ) ለደንበኞች አመቺ የሆነ የቅድመ ክፍያ ቆጣሪ አስተዳደርንና የክፍያ ዘዴን የመተግበር፡፡

5. ቦታው በባለፈቃዱ የማከፋፈል እና የመሸጥ ክልል ውስጥ ከሆነና የቦታው ባለይዞታ ለቦታው የኤሌክሪትክ አገልግሎት እንዲሰጠው ከጠየቀ ባለፈቃዱ አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡
6. ባለፈቃዱ የደንበኛውን ማመልከቻ በተቀበለ በ2 (በሁለት) ወር ውስጥ የኤሌክትሪክ አገልግሎት መስጠት አለበት፣ ሆኖም በወቅቱ አገልግሎቱን ለመስጠት የማያስችለው አሳማኝ ሁኔታ ካለ ለደንበኛው በጽሁፍ መግለጽ ይኖርበታል፡፡
7. ባለፈቃዱ ለአገልግሎት ጠያቂው የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለማቅረብ ሲወስን ከአገልግሎት ጠያቂው ጋር ውል መፈጸም አለበት፡፡
8. ባለፈቃዱ ለደንበኞቹ በቂ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ አስተማማኝ እና ደህንነቱ የተጠበቀ ኤሌክትሪክ ማገናኘት እና ማቅረብ በሚያስችል ሁኔታ የአቅርቦት ኔትወርኩን መገንባት፣ ሥራውን ማካሄድ፣ መጠገን እና መጠበቅ አለበት፡፡
9. ብቃት ያለው የኤሌክትሪክ አቅርቦትን ለማረጋገጥ እንዲቻል ባለፈቃዱ ቴክኒካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች እስከፈቀዱ ድረስ የፍላጎት እና የአቅርቦት አማራጮችን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡
10. ባለፈቃዱ ለዚህ ደንብ ተፈጻሚ የሚሆኑ ደረጃዎች፣ ፕሮቶኮሎች፣ ኮዶች እና ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚወጣ መመሪያን የማክበር እና በራሱ ኔትወርክ ሥር ያለውን የአቅርቦት ኔትወርክ የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት፡፡

26. <u>የአስመጪና ላኪ ባለፈቃድ መብቶችና ግዴታዎች</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 10 (3) (ሐ) የተደነገገው እንደ ተጠበቀ ሆኖ አስመጪ እና ላኪ ባለፈቃዱ የሚከተሉት መብቶች አሉት፡-

ሀ) በፈቃዱ ላይ በተገለጸው የፈቃድ አግባብና ሁኔታ መሠረት እንዲሁም እንደአግባቡ በሚደረስ የማስተላለፊያ ስምምነት መሠረት የኤሌክትሪክ ኃይልን ወደሃገር ውስጥ ለማስገባት ወይንም ወደውጭ ሃገር ለመላክ ብሔራዊ ግሪዱን በመጠቀም የማስተላለፍ፤

ለ) በፈቃዱ ላይ በተገለጸው የፈቃድ አግባብና እንደአግባቡ በሚደረስ የማስተላለፍ ስምምነት መሠረት በብሔራዊ ግሪዱ ውስጥ ያለአድልኦ የመገልገል፡፡

2. አስመጪ እና ላኪ ባለፈቃዱ የሚከተሉት ግዴታዎች አሉበት:-

ሀ) እንደአግባብነቱ አሰራሩን ከብሔራዊ የማከፋፈያና የማስተላለፊያ ግሪድ ኮድ ጋር የተጣጣመ የማድረግ፤

ለ) የፀደቀ ሪጅናል ግሪድ ኮድ ባለበት ሁኔታ አሰራሩን ከሪጅናል ግሪድ ኮድ ጋር የማጣጣም፡፡

27.<u>የደንበኛ መብቶችና እና ግዴታዎች</u>

1. ደንበኛ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) ከባለፈቃዱ አስተማማኝ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የኤሌክትሪክ አገልግሎት የማግኘት፤

ለ) እንደየአግባቡ ከኤሌክትሪክ አገልግሎት ጋር በተያያዘ ማናቸውም አቤቱታ በባለሥልጣኑ በሚወጣ የአሰራር ሥርዓት መሠረት ለባለፈቃዱ ወይም ለባለሥልጣኑ የማቅረብ፤ እና

ሐ) ደረጃውን ባልጠበቀ የኤሌክትሪክ አቅርቦት ምክንያት በዕቃዎች እና መገልገያዎች ላይ ለሚደርስ ማናቸውም ጉዳት ተመጣጣኝ ካሣ በወቅቱ የማግኘት፡፡

2. ደንበኛ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖርበታል:-

ሀ) ስለኤሌክትሪክ አጠቃቀም የወጡ ማስታወቂያዎችንና ትዕዛዞችን የማክበር፤

ለ) በደንበኛው ይዞታ ውስጥ የኤሌክትሪክ ሥራዎች ሲከናወኑ የመተባበር፤

ሐ) ኤሌክትሪክን በውሉ ውስጥ ከተገለጸው አገልግሎት ውጭ ያለመጠቀም፤

መ) ለተጠቀመበት ኤሌክትሪክ ክፍያ የመፈጸም፤

ሠ) ከኤሌክትሪክ አቅርቦት ጋር በተያያዘ ማናቸውም ያልተለመደ ሁኔታ ሲያጋጥም ለባለፈቃዱ በፍጥነት የማሳወቅ፤ እና

ረ) በባለሥልጣኑ የፀደቀውንና በባለፈቃዱ የወጣውን አግባብነት ያለውን የደንበኞች ቻርተር ድንጋጌ የማክበር፡፡

28.<u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው መብቶች እና ግዴታዎች</u>

1. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-

   ሀ) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተሰጠበት አግባብ የተፈቀዱ የኤሌክትሪክ ሥራዎችን በሀገሪቱ ውስጥ የማከናወን፤

   ለ) በዚህ ደንብ በተገለጸው ሁኔታ ካመለከተ እና አስፈላጊ መስፈርቶችን ካሟላ በ15 (በአሥራ አምስት) ቀናት ውስጥ እንደአግባቡ፤ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እድሳት ወይም፤ ምትክ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የማግኘት፡፡

2. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም ሰው የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

   ሀ) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያገኘበትን ተግባር በከፍተኛ ጥንቃቄና ደረጃውን በጠበቀ የሥራ አፈጻጸም የማከናወን፤

   ለ) በባለሥልጣኑ የወጣ የሥነ ምግባር ኮድን የማክበር፤

   ሐ) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ለሌላ ማንኛውም ሰው በማንኛውም መልኩ አሳልፎ ያለመስጠት፤

   መ) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ ከተሰረዘ ወዲያውኑ ለባለስልጣኑ የመመለስ፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ስለኤሌክትሪክ ታሪፍ እና ስለግሪድ አጠቃቀም</u>

### <u>ንኡስ ክፍል አንድ</u>

### <u>ስለኤሌክትሪክ ታሪፍ</u>

29.<u>አጠቃላይ መርሆዎች</u>

ባለሥልጣኑ የግሪድና ተያያዥነት ያለውን ታሪፍ ለመገምገም እና የውሳኔ ሀሳብ ለማቅረብ ወይም ከግሪድ ውጭ ያለውን ታሪፍ ለማፅደቅ በሚከተሉት መርሆዎች ይመራል፡-

1. ኤሌክትሪክ የማመንጨት፣ የማስተላለፍ፣ የማከፋፈል እና የመሸጥ ተግባራት በዘርፉ የንግድ መርሆዎች እና የላቀ አሰራር መሠረት መመራታቸውን፤
2. እንደአግባቡ ውድድር ማበረታታቱን፣ የሀብት አጠቃቀሙ ኢኮኖሚያዊ መሆኑን፣ የአፈጻጸም ብቃቱ፣ ግልጽነቱ፣ የኃይል አቅርቦት ሥርዓቱ የተቀናጀ መሆኑን እና የኤሌክትሪክ ዘርፉ መዋዕለ ነዋይ መሳብ መቻሉን፤
3. የደንበኞችን ፍላጎት ማሟላቱን እና አግባብነት ባለው ደንብ መሠረት የኤሌክትሪክ ወጪው መሸፈኑን፤
4. አንድ ዓመት በላይ ጸንቶ የሚቆይ ታሪፍ መሆኑን፤
5. ከታዳሽ የኃይል ምንጮች እና የሚባክን የሙቀት ኃይልን ተጠቅሞ ኤሌክትሪክ ማመንጨትን ማበረታታቱን፤
6. በድጎማ፣ በጎንዮሽ ድጎማ ወይም በስጦታ የተሸፈነ ወጪን በንግድ ሥራው ወጪ ውስጥ ያለመካተታቸውን፤ እና
7. በተቻለ መጠን የታሪፍ ክለሳው የዋጋ መረጋጋትን የሚያረጋግጥና ለመተግበር የሚያመች መሆኑን፡፡

30. <u>ስለታሪፍ ግምገማ፣ የውሳኔ ሀሳብ እና ማፀደቅ</u>

1. ኤሌክትሪክ ከማመንጨት፣ ከማስተላለፍ፣ ከማከፋፈል እና ከመሸጥ ጋር በተያያዘ የግሪድ ታሪፍ ሲገመገም እና የውሳኔ ሀሳብ ሲቀርብ ወይም ከግሪድ ውጭ ያለ ታሪፍ ሲፀድቅ የሚከተሉትን እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሁኔታዎች ከግንዛቤ ሊያስገባ ይችላል፡-
   
   ሀ) የነዳጅ ወጪን፤
   
   ለ) የኃይል ግዥ ወጪን፤
   
   ሐ) የዋጋ ግሽበት ምጣኔን፤ እና
   
   መ) የውጭ ምንዛሪ መዋዠቅን፡፡
2. ባለሥልጣኑ ከግሪዱ ጋር ተያያዥነት ያለውን ታሪፍ ሲገመግም እና የውሳኔ ሀሳብ ሲያቀርብ ወይም ከግሪድ ውጭ ያለውን ታሪፍ ሲያፀድቅ በታሪፍ መመሪያው በተገለጸው መሠረት አስፈላጊ ናቸው ብሎ የሚያምንባቸውን መረጃዎች እንዲያቀርብ ባለፈቃዱን ሊጠይቅ ይችላል፡፡

3. ባለሥልጣኑ ከግሪዱ ጋር ተያያዥነት ያለውን ታሪፍ ሲገመግም እና የውሳኔ ሀሳብ ሲያቀርብ ወይም ከግሪድ ውጭ ያለን ታሪፍ ሲያፀድቅ ለማንኛውም የኤሌክትሪክ ደንበኛ ከዚህ ቀጥሎ ከተመለከቱት ውጭ አላስፈላጊ ልዩነት ማድረግ የለበትም:-
   ሀ) የደንበኞች ሎድ ፋክተር፣ ፓወር ፋክተር፣ ቮልቴጅ፤
   ለ) በማንኛውም የተወሰነ ጊዜ ውስጥ ያለን የኤሌክትሪክ ፍጆታ፤
   ሐ) የማናቸውም ስፍራ መልክዓ ምድራዊ የቦታ አቀማመጥ፣ የአቅርቦቱን ባህሪ እና የተፈለገበት ተግባር፡፡

31.<u>ስለታሪፍ ግምገማ፣ የውሳኔ ሀሳብ እና የማፀደቅ ሥነ-ሥርዓት</u>

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 29 መሠረት ከግሪዱ ጋር ተያያዥነት ያለውን ታሪፍ ለግምገማ እና ለውሳኔ ሀሳብ ወይም ከግሪድ ውጭ የሆነን ታሪፍ ለማፀደቅ ባለፈቃዱ ማመልከቻውን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ባለሥልጣኑ ማመልከቻውን በተቀበለ በ120 (በአንድ መቶ ሃያ) ቀናት ውስጥ እና ከሕዝብ የተቀበለውን አስተያየት እና ተቃውሞ ከግምት ውስጥ በማስገባት አስፈላጊ ማስተካከያዎችን በማድረግ ከግሪድ ውጭ ታሪፍን ያፀድቃል ወይም ምክንያቱን በመመዝገብ ማመልከቻውን ውድቅ ያደርጋል፤ ሆኖም ማመልከቻውን ውድቅ ከማድረጉ በፊት የባለፈቃዱ ሀሳብ እንዲሰማ እድል መሰጠት አለበት፡፡
3. ባለሥልጣኑ ከግሪዱ ጋር ተያያዥነት ያለውን ታሪፍ የውሳኔ ሀሳብ ለማፀደቅ አግባብነት ላለው የመንግሥት አካል ማቅረብ አለበት፡፡
4. ባለሥልጣኑ ከግሪዱ ጋር ተያያዥነት ያለውን ታሪፍ ወይም ከግሪድ ውጭ ያለው ታሪፍ በፀደቀ በ7 (በሰባት) ቀናት ውስጥ የፀደቀውን ታሪፍ ቅጅ ለሚመለከተው ባለፈቃድ መላክ አለበት፡፡
5. ባለፈቃዱ የፀደቀውን ታሪፍ በኅብረተሰቡ ዘንድ በቂ ግንዛቤ እንዲፈጠር ሰፊ ተደራሽነት ባለው መገናኛ ብዙሃንና ሌሎች የመገናኛ መንገዶችን በመጠቀም ለሕዝብ ማስታወቅ አለበት፡፡
6. ባለሥልጣኑ ሁሉም ባለፈቃዶች ሊከተሉት የሚገባ የሚከተሉትን ክፍሎች ያካተተ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡-
   ሀ) ቁጥጥር የሚደረግበት መሠረታዊ ንብረት፤
   ለ) የእርጅና ቅናሽ፤

ሐ) የሥራ ካፒታል፣

መ) የካፒታል ወጪ፣

ሠ) ከኢንቨስትመንት የሚገኝ ትርፍ፣

ረ) የደንበኛ ማገናኛን ጨምሮ የሥራ ማስኬጃና የጥገና ወጪ፣ እና

ሰ) ሌሎች ግንኙነት ያላቸውን ወጪዎች፡፡

7. ባለፈቃዱ ባለስልጣኑ በሚያወጣው የታሪፍ ስሌት ሥርዓት መሠረት የታሪፍ ክለሳ ጥናት በየአራት ዓመቱ ማካሄድ እና የጥናት ሪፖርቱንም ለባለስልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

8. ባለፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (7) ከተቀመጠው የታሪፍ ማስተካከያ የጊዜ ገደብ ውጭ ባለፈቃዱ የታሪፍ ክለሳ ጥያቄ ስለሚያቀርብበት አግባብ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል፡፡

32.<u>ወጥ ስለሆነ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓትና የኦዲት ሪፖርት</u>

1. ባለሥልጣኑ በሁሉም ባለፈቃዶች ላይ ተፈጻሚነት የሚኖረው የታሪፍ ሥርዓትን የሚደግፍ፣ የሂሳብ አያያዝ መርሆዎችን መሠረት ያደረገ ወጥ የሆነ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ ያወጣል፡፡

2. ማንኛውም ባለፈቃድ የሂሳቡን ኦዲት ሪፖርት የመንግሥት በጀት ዓመት ባለቀ በ6 (በስድስት) ወራት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

## <u>ንኡስ ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለግሪድ አጠቃቀም</u>

33.<u>መርሆዎች</u>

1. በፈቃዱ ላይ በተገለጸው የፈቃድ ሁኔታዎች መሠረት የብሔራዊ ማስተላለፊያ ግሪዱ ለዓለም አቀፋዊ የኃይል ትስስር ክፍት ይሆናል፣ አጠቃቀሙም ግልጽና ወጪን ያገናዘበና በሚፀድቅ የማስተላለፍ ስምምነት መሠረት መሆን አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ በተደነገገው መሠረት የብሔራዊው የማስተላለፊያ መስመር አጠቃቀም በነባር ተገልጋይ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሣድር መሆን የለበትም፡፡

34.<u>አጠቃቀምን ስለመከልከል</u>

1. ባለፈቃዱ የብሔራዊ የማስተላለፊያ ግሪዱ ትስስር ወይም አጠቃቀም በዚህ ደንብ አንቀጽ 33 ላይ ከተደነገገው የግሪድ አጠቃቀም መርህ ጋር የሚጋጭ ከሆነ ሁኔታው እስከሚሻሻል ድረስ ትስስሩን ወይም አጠቃቀሙን መገደብ ወይም መከልከል ይችላል፡፡
2. ባለሥልጣኑም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በባለፈቃዱ የተወሰደው እርምጃ አግባብ መሆን አለመሆኑን በማጣራት ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## ክፍል አምስት

## ስለኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ

## ምዕራፍ አንድ

## ስለኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ኦዲት፣ ተቋራጭነት ወይም የማማከር አገልግሎት ፈቃድ እና ስለ ፈንድ

### 35.ስለፈቃድ ማመልከቻ አቀራረብ

1. ማንኛውም ሰው ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ሳያገኝ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ኦዲት፣ ተቋራጭነት ወይም የማማከር አገልግሎቶችን ማከናወን አይችልም፡፡
2. ማንኛውም የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ኦዲት፤ የተቋራጭነት ወይም የማማከር ፈቃድ ማመልከቻ ለባለሥልጣኑ ሲቀርብ የሚከተሉትን መያዝ አለበት:-
   ሀ) የአመልካቹን አድራሻ፤ የመታወቂያውን ኮፒ፤
   ለ) እንደየአግባቡ የተቀጣሪ ሠራተኞችን የብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ፤
   ሐ) እንደየአግባቡ ዲግሪ፣ ዲፕሎማ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና ቀጥታ ግንኙነት ያለው የሥራ ልምድ፤ እና
   መ) ባለሥልጣኑ በመመሪያ የሚወስናቸው ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች፡፡
3. አመልካቹ የጠየቀው ፈቃድ ሊሰጥ የሚችል መሆን አለመሆኑን ለመመዘን እና የፈቃዱን ደረጃ ለመወሰን በአገልግሎት ክፍያ ደንቡ መሠረት የማይመለስ የማመልከቻ መመርመሪያ ክፍያ ከፈቃድ ማመልከቻ ጋር መቅረብ አለበት፡፡
4. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የቀረቡትን መረጃዎች ትክክለኛነት ካረጋገጠ በኋላ የአመልካቹን ብቃት ለመመዘን እና የፈቃዱን ደረጃ ለመወሰን እንደየአግባቡ የጽሁፍ ወይም የተግባር ፈተና ሊሰጥ ይችላል፡፡

5. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተጠቀሱትን የፈቃድ ምዘና እና የደረጃ መስፈርቶችን በተመለከተ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡
6. ባለሥልጣኑ አመልካቹ የፈቃድ መስፈርቶችን ማሟላቱን ካረጋገጠ በኋላ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ፈቃዱን መስጠት አለበት፡፡
7. ባለሥልጣኑ በአመልካቹ የቀረበው መረጃ በቂ አይደለም ብሎ ከወሰነ ውሳኔውን ለአመልካቹ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

36.<u>ስለፈቃድ ማመልከቻ ምዝገባ የቀረበው የፈቃድ ማመልከቻ ጥያቄ</u>

በዚህ ደንብ አንቀጽ 35 መሠረት ተሟልቶ የቀረበ እንደሆነ ለዚሁ ተግባር በባለሥልጣኑ ቢሮ ውስጥ በተዘጋጀ የማመልከቻ መመዝገቢያ መዝገብ ላይ ወዲያውኑ እንደቅደም ተከተሉ እንዲመዝገብ ተደርጎ ለእያንዳንዱ አመልካች የምዝገባ ቀኑን እና ቁጥሩን የሚያመለክት ደረሰኝ መሰጠት አለበት፡፡

37.<u>ፈቃድ ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ እና እድሳት</u>

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 35 መሠረት የተሰጠ ፈቃድ:-
   ሀ) ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለ2 (ለሁለት) ዓመታት ፀንቶ ይቆያል፤
   ለ) በየሁለት ዓመቱ መታደስ አለበት፤
   ሐ) ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ ከማብቃቱ ከ15 (ከአሥራ አምስት) ቀናት በፊት ለእድሣት መቅረብ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሐ) መሠረት ለእድሳት ሳያቀርብ የፈቃዱ ዘመን ያበቃበት ማንኛውም ሰው የእድሳት ዘመኑ ካበቃበት በኋላ ባሉት 90 (ዘጠና) ቀናት ውስጥ ፈቃዱ እንዲታደስለት ሊያመለክት የሚችል ሲሆን፣ ባለሥልጣኑም ፈቃዱ ካበቃበት በኋላ ላለው ለእያንዳንዱ ቀን በአገልግሎት ክፍያ ደንቡ የተመለከተውን የዘገየ እድሳት ክፍያ በማስከፈል ፈቃዱን ያድስለታል፡፡
3. ፈቃድ ለማሳደስ የሚፈልግ ማንኛውም ባለፈቃድ ፈቃዱ ጸንቶ በቆየበት ጊዜ ውስጥ በፈቃዱ ስላከናወነው ተግባር የተሟላ ሪፖርት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡
4. ማንኛውም ፈቃድ የተሰጠው የሕግ ሰውነት ያለው ድርጅት ፈቃዱን ለማሳደስ ሲቀርብ የተቀጣሪ ባለሙያዎቹን የታደሰ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

38.<u>ስለምትክ ፈቃድ</u>

1. ማንኛውም ባለፈቃድ የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል ለጠፋበት ወይም ለተበላሸበት ፈቃድ ምትክ እንዲሰጠው ለባለሥልጣኑ ሊያመለክት ይችላል፡፡
2. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማመልከቻውን ከተቀበለ በኋላ መርምሮ በአገልግሎት ክፍያ ደንቡ የተወሰነውን በማስከፈል ምትክ ፈቃዱን መስጠት አለበት፡፡

39.**<u>ፈቃድን ስለማገድ ወይም ስለመሰረዝ</u>**

1. ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ የኢነርጂ ኦዲት፣ የማማከር ወይም የተቋራጭነት ፈቃድ ሊታገድ ይችላል፡-
   ሀ) በፈቃዱ ላይ ከተጠቀሰው ገደብ ውጭ በሥራ ላይ መሰማራት ወይም ደረጃውን ያልጠበቀ ሥራ መሥራት፣
   ለ) የሰራው ሥራ መሠረታዊ የሆነ የደህንነትና የጥራት ችግር ያለበት በመሆኑ ምክንያት በተገልጋዩ ህይወት ወይም ንብረት ላይ አደጋ መፍጠር፣
   ሐ) በዚህ ደንብ መሠረት ማቅረብ የሚጠበቅበትን ሪፖርት አሟልቶ አለማቅረብ ወይም የተሳሳተ ሪፖርት ማቅረብ ወይም አስፈላጊ ሰነዶችን በአግባቡ አለመያዝ፣
   መ) የባለሥልጣኑ የቁጥጥር ሥራ እንዳይከናወን ሆነ ብሎ እክል መፍጠር ወይም ማወክ፣ ወይም
   ሠ) በባለስልጣኑ የተሰጠውን ፈቃድ ያለባለሥልጣኑ ስምምነት ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት፡፡
2. ፈቃድ የታገደበት ማንኛውም ሰው በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የማስተካከያ እርምጃ ያልወሰደ እንደሆነ ወይም በሁለት ዓመት ውስጥ እገዳን ሊያስከትል የሚችል ሌላ ጥፋት ደግሞ የፈጸመ እንደሆነ ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡
3. ባለፈቃዱ ግለሰብ ሲሆን የሞተ እንደሆነ ወይም የንግድ ድርጅት ሲሆን በፍርድ ቤት የመክሰር ውሳኔ የተሰጠበት ወይም የፈረሰ እንደሆነ የወራሾች መብት እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ምዕራፍ መሠረት የተሰጠ ፈቃድ ይሰረዛል፡፡
4. ባለሥልጣኑ ፈቃዱን ከማገዱ ወይም ከመሰረዙ በፊት ፈቃዱ የሚታገድበትን ወይም የሚሠረዝበትን ምክንያት በመግለጽ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ለባለፈቃዱ መስጠት አለበት፡፡

5. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ማስጠንቀቂያ የደረሰው ባለፈቃድ የተሰጠው ፈቃድ ሊሰረዝበት ወይንም ሊታገድበት እንደማይገባ የሚያነሳውን ተቃውሞ ወይም መከላከያ ግልጽ አድርጎ በ15 (በአሥራ አምስት) ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ በጽሁፍ ማቅረብ አለበት፡፡
6. ባለሥልጣኑ የባለፈቃዱ መከላከያ ወይም ተቃውሞ በቂና አሳማኝ ሆኖ ያላገኘው እንደሆነ ወይም ባለፈቃዱ በ15 (በአሥራ አምስት) ቀናት ውስጥ ምንም መከላከያ ወይም ተቃውሞ ያላቀረበ እንደሆነ ፈቃዱን በሙሉ ወይም በከፊል አግዶ ወይም ሰርዞ በ15 (በአሥራ አምስት) ቀናት ውስጥ ስለእገዳው ወይም ስለስረዛው ለባለፈቃዱ በጽሁፍ ያሳውቃል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም የተወሰደውን እርምጃ ለህዝብ ማስታወቅ ይችላል፡፡

40.<u>ስለአገልግሎት ክፍያ</u>

የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ፣ ኦዲት ተቋራጭነት ወይም የማማከር አገልግሎቶች ፈቃድ ማመልከቻ መመርመሪያ፤ ለጽሁፍና ለተግባር ፈተና ማካሔጃ፤ ፈቃድ ለመስጠት፣ ለማደስ እና ለመተካት በባለስልጣኑ የሚፈጸመው የአገልግሎት ክፍያ መጠን ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው በሰንጠረዥ 1 መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

41.<u>የባለፈቃዱ መብቶችና ግዴታዎች</u>

1. በዚህ ደንብ ክፍል አምስት መሠረት የተሰጠን ፈቃድ የያዘ ማንኛውም ባለፈቃድ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል:-
   ሀ) በመላው ሀገሪቱ ውስጥ በፈቃዱ የተመለከቱ ተግባራትን የማከናወን፤
   ለ) በፈቃዱ የተጠቀሰውን አገልግሎት ለመስጠት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን የመጠየቅና የማግኘት፤ እና
   ሐ) በፈቃዱ መሠረት በቂ አገልግሎት ለሰጠበት ተገቢውን ክፍያ የማግኘት፡፡
2. በዚህ ደንብ ክፍል አምስት መሠረት የተሰጠን ፈቃድ የያዘ ማንኛውም ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል:-
   ሀ) በአዋጁ፣ በዚህ ደንብ፣ ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ እና በፈቃድ ሁኔታዎች መሠረት የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ተግባራትን የማከናወን፤
   ለ) ከደንበኛው ጋር በተደረሰው ስምምነት መሠረት አገልግሎት የመስጠት፤
   ሐ) ከመጨረሻ ውይይት በኋላ የክንውን ኦዲት ሪፖርቱን ኦዲት ለተደረገው አካል በአንድ ወር ውስጥ የማቅረብ፤

መ) ለደንበኞች አቤቱታ ወዲያውኑ ምላሽ የመስጠት፤

ሠ) በኢነርጂ ብቃት አጠቃቀም ላይ አስፈላጊ መመሪያዎችን ለደንበኞች የመስጠት፤

ረ) የሠራተኛ፣ የገንዘብ፣ የንግድ እና ሌሎች መዝገቦችን እና ሬከርዶችን ቢያንስ ለ5 (ለአምስት) ዓመታት የመያዝ፤

ሰ) በባለሥልጣኑ ሲጠየቅ መዛግብትን ለቁጥጥር ሥራ የማቅረብ፤

ሸ) ለሠራተኞቹ አግባብ የሆነ ሥልጠና የመስጠት፤ እና

ቀ) የተሰረዘ ፈቃድ ለባለስልጣኑ የመመለስ፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባን ስለማስተዋወቅ እና መቆጣጠር

### 42.አጠቃላይ መርሆዎች

1. ባለሥልጣኑ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ የቁጥጥር እርምጃዎችን ለመተግበር በእርምጃዎቹ ጥቅሞች ላይ ትኩረት በማድረግ ለግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ቅድሚያ ይሰጣል፡፡
2. ባለሥልጣኑ የእርምጃዎችን ባህሪ እና የሚያመጡትን ጥቅም መሠረት በማድረግ የኢነርጂ ቁጠባ የቁጥጥር እርምጃዎችን ደረጃ በደረጃ መፈጸም አለበት፡፡

### 43.የባለፈቃዶችን የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ሥራዎች ስለመቆጣጠር

1. ባለሥልጣኑ የኢነርጂ ኦዲት፣ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ተቋራጭነት ወይም የማማከር አገልግሎት ተግባራትን ለማከናወን ፈቃድ በተሰጣቸው ሰዎች ላይ የቁጥጥር ተግባር የሚያካሂድ ተቆጣጣሪ ሠራተኛ ይመድባል፡፡
2. በባለሥልጣኑ የተመደበ ተቆጣጣሪ ሠራተኛ በማንኛውም የሥራ ሰዓት ከባለሥልጣኑ የተሰጠውን መታወቂያ በማሳየት የባለፈቃዱን የኢነርጂ ኦዲት፣ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ተቋራጭነት ወይም የማማከር አገልግሎትን መቆጣጠር ይችላል፡፡
3. ተቆጣጣሪ ሠራተኛው ቁጥጥር በሚያካሂድበት ወቅት ማናቸውንም የባለፈቃዱን የኢነርጂ ኦዲት፣ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ተቋራጭነት ወይም የማማከር አገልግሎት ሰነዶች፣ ሪከርዶች፤ መገልገያዎች እና ሌሎች ማናቸውም ለቁጥጥሩ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች እንዲቀርቡ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

4. ተቆጣጣሪ ሠራተኛው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) መሠረት ስላካሄደው የቁጥጥር ተግባር ለባለሥልጣኑ የጽሁፍ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡
5. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) መሠረት በተካሄደው የቁጥጥር ተግባር ባለፈቃዱ የኢነርጂ ኦዲት፣ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ተቋራጭነት ወይም የማማከር አገልግሎት ተግባራትን ሲያከናውን ይህን ደንብ እና ደንቡን ለማስፈጸም በወጣው መመሪያ የተመለከቱትን ማናቸውንም ግዴታዎች ጥሶ የተገኘ እንደሆነ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ ባለሥልጣኑ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት አለበት፡፡
6. ባለፈቃዱ በጽሁፍ ማስጠንቀቂያው ውስጥ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ የማስተካከያ እርምጃ ያልወሰደ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ፈቃዱን እንደሁኔታው ሊያግድ ወይም ሊሰርዝ ይችላል፡፡

44.<u>ሪፖርት ስለማድረግ</u>

1. የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ተግባራትን ለማከናወን ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው ስለሥራውና ስለክንውኑ በየዓመቱ ለባለሥልጣኑ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡
2. ባለስልጣኑ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ሪፖርት የሚቀርብበትን ቅጽ በመመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## <u>ምዕራፍ ሦስት</u>

## <u>ስለኤሌክትሪክ ዕቃዎች እና መገልገያዎች</u>

45.<u>ስለኢነርጂ ብቃት አፈጻጸም ደረጃ</u>

ባለሥልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 4(6) መሠረት የኤሌክትሪክ ዕቃዎችን እና መገልገያዎችን ዝቅተኛ እና ከፍተኛ የኢነርጂ ብቃት የአፈጻጸም ደረጃ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡

46.<u>ስለኤሌክትሪክ ዕቃዎች እና መገልገያዎች</u>

1. ማንኛውም የኤሌክትሪክ ዕቃ እና መገልገያ አምራች፣ አስመጪ፣ አከፋፋይ ወይም ቸርቻሪ አስገዳጅ የብሔራዊ የኢነርጂ ብቃት ደረጃዎችን ያላሟላ እና የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያልተሰጠውን የኤሌክትሪክ ዕቃ እና መገልገያ

ማምረት፣ ማስመጣት፣ በጅምላም ሆነ በችርቻሮ መሸጥ፣ ማከራየት ወይም በማናቸውም መልኩ በኢትዮጵያ ገበያ ውስጥ ገብቶ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ አይችልም፡፡

2. ማናኛቸውም የኤሌክትሪክ ዕቃዎች እና መገልገያዎች አምራች ወይም አስመጪ ብሔራዊ የኢነርጂ ብቃት ደረጃ የወጣላቸውን የኤሌክትሪክ ዕቃዎች እና መገልገያዎች ከማምረቱ ወይም ከማስመጣቱ በፊት በዚህ ደንብ መሠረት በሚወጣ መመሪያ ከባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፡፡
3. የኤሌክትሪክ ዕቃዎችና መገልገያዎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሥርዓት ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡
4. ባለሥልጣኑ የሚጠበቀውን የኢነርጂ ብቃት ተለጣፊ ምልክት እና ዝቅተኛ የኢነርጂ ብቃት አፈጻጸም ደረጃዎችን ባላከበሩ አምራቾች፣ አስመጪዎች፣ ጅምላ ሻጮች ወይም ቸርቻሪዎች ላይ አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስድ አግባብነት ላለው ፈቃድ ሰጪ አካል ሊያሳውቅ ይችላል፡፡

47.<u>ስለኤሌክትሪክ ዕቃዎች እና መገልገያዎች ተለጣፊ ምልክት</u>

1. ማንኛውም ሰው አስገዳጅ የተለጣፊ ምልክት የሚጠይቅን ማናቸውንም የኤሌክትሪክ እቃ እና መገልገያ ተለጣፊ ምልክት ሳያደርግ ማምረት፣ ማስመጣት፣ በጅምላ ወይም በችርቻሮ መሸጥ አይችልም፡፡
2. ተለጣፊ ምልክቱ የኤሌክትሪክ ዕቃውን እና የመገልገያውን የኢነርጂ ብቃትና ሌሎች ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ የሚወሰኑ አስፈላጊ መረጃዎችን መያዝ አለበት፡፡
3. ተለጣፊ ምልክቱ በእያንዳንዱ የኤሌክትሪክ እቃ መገልገያ እና ማሸጊያ ላይ በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ መጻፍ እና ግልጽ ቦታ ላይ መለጠፍ አለበት፡፡
4. ማንኛውም ሰው በዚህ ደንብ መሠረት ተለጣፊ ምልክት የተደረገበትን የኤሌክትሪክ እቃ ወይም መገልገያ ለመጀመሪያ ቸርቻሪ ከመሸጡ ወይም ለመጀመሪያ ተከራይ ከማከራየቱ በፊት በምርቱ ወይም በማሸጊያው ላይ የተለጠፈውን ማናቸውንም የኢነርጂ ብቃት ተለጣፊ ምልክት ማስወገድ፣ ማበላሸት፣ መደበቅ ወይም መለወጥ የለበትም፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ማንኛውም ሰው በተለጣፊ ምልክቱ ላይ ስላለው መረጃ ትክክለኛነት ኃላፊነት አለበት፡፡
6. ባለሥልጣኑ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ዕቃዎች እና መገልገያዎች ወይም የማሽኒያቸውን ተለጣፊ ምልክት ቅርጽ፣ ይዘት፣ ዓይነት፣ ምልክት እና ዝርዝር ሥርዓቶችን አስመልክቶ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 48.ስለኤሌክትሪክ ዕቃዎች እና መገልገያዎች የኢነርጂ ብቃት ፍተሻ

1. ባለሥልጣኑ እንደአስፈላጊነቱ ማንኛውም አምራች ወይም አስመጪ የኤሌክትሪክ ዕቃውን እና መገልገያውን የኢነርጂ ብቃት እንዲያስፈትሽ ባለሥልጣኑ በሚገልጸው ቦታ እና በባለሥልጣኑ የተመረጡ ናሙናዎችን እንዲያቀርብ ሊጠየቅ ይችላል፤ አምራቹ ወይም አስመጪውም በጥያቄው መሠረት የኤሌክትሪክ ዕቃውን እና መገልገያውን የማቅረብ እና የማስፈተሽ ግዴታ አለበት፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ ናሙናዎችን በመምረጥ ከገበያ ላይ በመግዛት መፈተሽ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የፍተሻ ሥራው ናሙናውን መፈታታትንና መክፈትን ግድ የማይል ከሆነና ንብረቱ ላይ ምንም ዓይነት ጉዳት የማያስከትል ሲሆን ፍተሻውን ያለፉት ናሙናዎች ለአስመጪው ወይንም ለአምራቹ ይመለሳሉ፡፡
4. ለፍተሻ ሥራው የቀረቡ ናሙናዎች ተመልሰው አገልግሎት ሊሰጡ በማይችሉበት ሁኔታ መፈታታትን ግድ የሚሉ ከሆነ ፍተሻውን ቢያልፉም ናሙናዎቹ እስካልተጠየቁ ድረስ ለአስመጪው ወይም ለአምራቹ ላይመለሱ ይችላሉ፡፡
5. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የቀረበለትን ማናቸውንም የኤሌክትሪክ ዕቃ እና መገልገያ ናሙና በትኖ ሊመረምር እንዲሁም የኢነርጂ ብቃቱን በአግባቡ ለመወሰን አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን ሌሎች የፍተሻ ዘዴዎችንም ሊጠቀም ይችላል፤ ሆኖም የፍተሻውን ዘዴ እንደየአግባቡ ለአምራቹ ወይም ለአስመጪው በቅድሚያ ማሳወቅ አለበት፡፡
6. ባለሥልጣኑ የኤሌክትሪክ ዕቃዎችን እና መገልገያዎችን የኢነርጂ ብቃት ለማስፈተሽ አግባብነት ካለው አካል ጋር ስምምነት ሊገባ ይችላል፡፡

## ምዕራፍ አራት

## ስለኢንዱስትሪዎች የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ

## 49.ጠቅላላ መርሆዎች

1. በኢንዱስትሪዎች ውስጥ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ተግባራት የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ:-
   ሀ) የኢነርጂ ብክነት መከላከልን፤
   ለ) የቀዳሚ ኢነርጂ ምንጭ መቀጣጠል መሻሻልን፤
   ሐ) የኢነርጂ ተረፈ ምርትን መልሶ መጠቀምን፤
   መ) አንድን የኢነርጂ ዓይነት በሌላ መተካትን፤
   ሠ) ፓወር ፋክተርን በማሻሻል የኤሌክትሪክ አጠቃቀምን የበለጠ ብቁ ማድረግን፤
   ረ) በሲስተሙ ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ፍላጎት በሚኖርበት ጊዜ ከፍተኛ የኃይል ፍላጎትን መቀነስን፤
   ሰ) ደረጃቸውን የጠበቁ ዕቃዎች መጠቀምን፤ እና
   ሸ) የኢነርጂ ብቃት ያለው መሣሪያ ወይም ዕቃ እንዲሁም ለኢነርጂ ቁጠባ አስተዋጽዖ የሚያደርጉ የኦፕሬሽን መቆጣጠሪያ ሲስተሞችን መጠቀምን፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለስልጣኑ ተጨማሪ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ዘዴዎችን ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

## 50.ስለተመረጡ ኢንዱስትሪዎች

1. ባለሥልጣኑ ይህን ደንብ ለማስፈፀም በሚወጣ መመሪያ መሠረት ኢንዱስትሪዎችን በዓይነት፣ በኢነርጂ ፍጆታ ወይም በኢነርጂ አጠቃቀም ዘዴ መምረጥ ይችላል፡፡
2. የተመረጠው የኢንዱስትሪ ባለቤት ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ፣ ደረጃ፣ ቅድመ ሁኔታዎችና ሥርዓቶች መሠረት:-
   ሀ) የኢንዱስትሪውን የኢነርጂን ፍጆታ መቆጠብ፣
   ለ) በተወሰነ ጊዜ ገደብ የኢንዱስትሪውን የኢነርጂ አጠቃቀም ኦዲት ማስደረግ እና መተንተን፣
   ሐ) የኢንዱስትሪውን የኢነርጂ አጠቃቀም መረጃ ዎችን ለባለሥልጣኑ ሪፖርት ማድረግ፣ እና
   መ) የፈቃደኝነት ስምምነት መግባት፣ አለበት፡፡

3. ባለስልጣኑ የተመረጡ ኢንዱስትሪዎች ተግባራዊ ማድረግ ያለባቸውን የኢነርጂ አጠቃቀምን ለማሻሻል የሚያስችሉ እርምጃዎችን በተመለከተ ትዕዛዝ መስጠት ይችላል፡፡

51.<u>ስለተመረጠ ኢንዱስትሪ ባለቤት ግዴታዎች</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 19 (4) እና (5) እንዲሁም አንቀጽ 22 (4) መሠረት ማንኛውም የተመረጠ የኢንዱስትሪ ባለቤት የሚከተሉት ግዴታዎች አሉበት፡-
   ሀ) በኢንዱስትሪው ውስጥ ለኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ እርምጃዎች ሙሉ ኃላፊነት እና ብቃት ያለው ቢያንስ አንድ ባለሙያ የመመደብ፤
   ለ) የኢነርጂ ፍጆታ፣ የምርት እና የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ እርምጃዎችን በተመለከተ ለባለሥልጣኑ ሪፖርት የማቅረብ፤
   ሐ) ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ ከሚደነገጉት ቅድመ ሁኔታዎች እና ሥርዓቶች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በኢነርጂ ፍጆታ እና በኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ላይ ተጽዕኖ የሚያሣድሩ የኢንስታሌሽን፣ የማሽን ለውጥ ወይም የኤሌክትሪክ ዕቃዎችን እና መገልገያዎችን መዝግቦ የመያዝ፤
   መ) ከኢነርጂ ጋር የተያያዙ መዝገቦችን ቢያንስ ለ5 (ለአምስት) ዓመታት የማቆየት፤
   ሠ) ከመመዘኛዎች፣ ሥርዓቶች እና የጊዜ ሰሌዳዎች ጋር በማጣጣም ለኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ለማሳካት ግብ እና ዕቅድ በማውጣት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ እና የተመረጠ ኢንዱስትሪ ሥራን ኦዲት እና ትንተና የማድረግ፤ እና
   ረ) በተመረጡ በ180 (በአንድ መቶ ሰማንያ) ቀናት ውስጥ ስለኢንዱስትሪው ለባለሥልጣኑ ሪፖርት የማድረግ፡፡
2. የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ)፣ (መ) እና (ሠ) በአግባቡ ለማስፈጸም የሚያግዙ ቅጾች፣ መመዘኛዎች፣ ሥርዓቶች እና የጊዜ ሰሌዳዎች ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ ይወሰናሉ፡፡

52.<u>ስለፈቃደኝነት ስምምነት</u>

1. ቀጣይነት ላለው የኢነርጂ ብቃት መሻሻል በአዋጁ አንቀጽ 22 መሠረት ባለሥልጣኑ ከእያንዳንዱ አግባብ ካለው ከተመረጡ ከፍተኛ ኢነርጂ ተጠቃሚ ኢንደስትሪዎች፤ እንደ የአግባቡም ከኢነርጂ መሣሪያዎች እና መገልገያዎች

አምራቾች ወይም አስመጪዎች ጋር የፈቃደኝነት ስምምነት መደራደር፣ መፈራረምና መፈጸም ይችላል፡፡

2. የፈቃደኝነት ስምምነቱ ተመሳሳይነት ካላቸውና ከተመረጡ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ በተግባር የዋሉ የኢነርጂ ብቃት ማሻሻያ እርምጃዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት እና ብቃትን ደረጃ በደረጃ ሊያሻሽሉ የሚችሉ የተረጋገጡና ከሁኔታዎች ጋር የተጣጣሙ እርምጃዎችንም ሊያካትት ይገባል፡፡
3. የፈቃደኝነት ስምምነቱ የኢነርጂ ብቃት መሻሻልን በተመለከተ ከእያንዳንዱ የማሻሻያ እርምጃ በዓመት ውስጥ የሚጠበቀውን ውጤት በመቶኛ የሚያመላክት መሆን አለበት፡፡
4. ማንኛውም የተመረጠ ኢንዱስትሪ ባለቤት የፈቃደኝነት ስምምነቱ በአግባቡ ስለመፈጸሙ፣ የኢነርጂ ብቃት ስኬቱን በመቶኛ እንዲሁም ያጋጠመውን ማናቸውንም ሌላ መሰናክል በመግለጽ በስምምነቱ ላይ በሚገለጸው የአቀራረብ አግባብ ወቅታዊ ሪፖርት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡
5. ባለሥልጣኑ የሪፖርቱን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ተጨማሪ መረጃዎችን በመጠየቅ ወይም በአካል በመገኘት በሪፖርቱ የተጠቀሱትን ጉዳዮች ትክክለኛነት ሊያጣራ ይችላል፡፡
6. በአዋጁ አንቀጽ 22 (4) መሠረት የፈቃደኝነት ስምምነቱ በተገባው ውል መሠረት ያለበቂ ምክንያት ያልተፈጸመ እንደሆነ ባለስልጣኑ አስተዳደራዊ መቀጫ ሊወስን ይችላል፡፡

53.<u>ስለኢነርጂ አስተዳደር ክፍል</u>

1. የተመረጠው ኢንዱስትሪ ባለቤት በተመረጠው ኢንዱስትሪ ውስጥ ሙሉ ኃላፊነትን ወስዶ ከኢነርጂ ፕሮግራም አንጻር የሚሰራ የኢነርጂ አስተዳደር ክፍል ማቋቋም እና ባለሙያዎችን መመደብ አለበት፡፡
2. የኢነርጂ አስተዳደር ክፍል ሠራተኞች በኤሌክትሪካል ወይም ኤሌክትሮ-መካኒካል ወይም በሌላ አግባብ በሆነ የምህንድስና መስክ የተማሩ እና የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ኃላፊነትን ለመወጣት ብቁ መሆን አለባቸው፡፡
3. የኢነርጂ አስተዳደር ክፍል የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል:-
   ሀ) ኢነርጂ የሚጠቀም ማሽንን እና ዕቃን በየወቅቱ የመጠገን እና ብቃቱን የመፈተሽ፣

ለ) የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ መርህን ተከትሎ የኢነርጂ ፍጆታን የማሻሻል፤

ሐ) በባለሥልጣኑ ለተመደበ ተቆጣጣሪ ወይም ባለፈቃድ የመዛግብቱን ትክክለኛነት ለመፈተሽ እና ለማረጋገጥ እንዲችል መረጃ መያዙን የማረጋገጥ፤

መ) የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ግቦች እና ዕቅዶች ዝግጅትን የማገዝ፤ እና

ሠ) የምርመራ እና የግምገማ ውጤቶችን ትክክለኛነት የማረጋገጥ፡፡

54.<u>ስለመረጃ ስርጭት</u>

ባለሥልጣኑ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ መረጃን እና አግባብነት ያለውን ማናቸውንም ሌላ መረጃ ለማሰራጨት የትምህርት ተቋማትን፣ የፌደራል እና የክልል መንግሥታት ተቋማትን፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን፣ አገልግሎት አቅራቢዎችን፣ የንግድ ድርጅቶችን፣ የሙያ እና የኅብረት ሥራ ማህበራትን እና የመሳሰሉትን ሊጠቀም ይችላል፡፡

<u>ምዕራፍ አምስት</u>

<u>ስለሕንጻዎች ኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ</u>

55.<u>ስለሕንጻዎች የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ የቁጥጥር ተግባራት</u>

1. የሕንጻ ኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ቁጥጥር በኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ኮዶች፣ ደረጃዎች ወይም ተለጣፊ ምልክቶች መካከል በአንዱ ወይም በሁሉም ሊካሄድ ይችላል፡፡
2. በግንባታ ወይም በጥገና ወቅት የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ እርምጃዎች ታሣቢ እንዲደረጉ በሕንጻ ኮዶች ውስጥ መካተት አለበት፡፡

56.<u>ስለሕንጻ ኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ዘዴዎች</u>

1. የሕንጻ ኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ከሚከተሉት ዘዴዎች ውስጥ አንዱን ወይም ከዚያ በላይ ሊያካትት ይችላል:-

ሀ) ወደ ሕንጻው የሚገባውን የፀሐይ ብርሃን ሙቀት መቀነስ፤

ለ) ክፍሉን በአስፈላጊው የሙቀት ደረጃ የሚጠብቅ ብቁ የአየር ሙቀት መቆጣጠሪያ መሣሪያዎችን መጠቀም፤

ሐ) ኢነርጂ ቆጣቢ የሆኑ የሕንጻ ግንባታ ዕቃዎችን መጠቀም፤

መ) በቂ የተፈጥሮ ብርሃንን በሕንጻው ውስጥ መጠቀም፤ ወይም

ሠ) በሕንጻው ውስጥ ለኃይል ቁጠባ አስተዋጽዖ የሚያደርጉ ዕቃዎችን እና መሣሪያዎችን መትከልና መጠቀም፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ቢኖርም ስለሕንጻው የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ተጨማሪ ዘዴዎች ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ ሊወሰን ይችላል፡፡

57.<u>ስለተመረጡ ሕንጻዎች</u>

1. ባለሥልጣኑ ይህን ደንብ ለማስፈፀም በሚወጣ መመሪያ ሕንጻዎችን በዓይነት፣ በስፋት፣ በኢነርጂ ፍጆታ መጠን ወይም በኢነርጂ አጠቃቀም ዘዴ ሊመርጥ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በባለሥልጣኑ የሚወጣ መመሪያ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

ሀ) የሕንጻውን አጠቃላይ ሙቀት የማስተላለፍ አቅም እና የኢነርጂ ፍጆታ፤

ለ) የሕንጻውን ሙቀት የማስተላለፍ አቅም መገመገሚያ መመዘኛዎች፣ ሥርዓቶች እና ሁኔታዎች፣ የግንባታ መሣሪያዎች አጠቃላይ ሙቀት የማስተላለፍ አቅም እንዲሁም የኢነርጂ አጠቃቀም፤ እና

ሐ) የሕንጻውን የአየር ሁኔታ መቆጣጠሪያ ዘዴውን፣ የሚጠቀመውን ውሃና አካባቢን የማሞቂያ ቴክኖሎጂ፡፡

3. የተመረጠው ሕንጻ ባለቤት የሕንጻውን ኢነርጂ ፍጆታ ለመቆጠብ አግባብነት ያለውን እርምጃ መውሰድና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት በሚወጣ መመሪያ በተመለከቱ መስፈርቶችና አሰራሮች መሠረት የሕንጻውን ኢነርጂ ፍጆታ ማስተንተን አለበት፡፡
4. ማንኛውም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተመረጠ ሕንጻ ፈቃድ ባለው ኢነርጂ ኦዲተር፣ ተቋራጭ ወይም አማካሪ በየሦስት ዓመቱ ኦዲት መደረግ አለበት፡፡

## <u>ምዕራፍ ስድስት</u>

## <u>ስለኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ፈንድ</u>

58.<u>ፈንዱ ለሚከተሉት ዓላማዎች ይውላል</u>

1. ቦርዱ ኢንዱስትሪዎች፣ ሕንጻዎች እና ሌሎች የንግድ ድርጅቶች አስቀድሞ በተካሄደ የኢነርጂ ኦዲት ሪፖርትና መነሻ ጥናትን መሠረት በማድረግ ቀጥሎ

የተዘረዘሩትን ከኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ጋር የተገናኙ ሥራዎችን ለመተግበር ከፈንዱ በመንግሥት የንግድ ባንክ ወለድ ምጣኔ ወይም በአነስተኛ ወለድ ምጣኔ ወይም ከወለድ ነጻ በሆነ ሙሉ ወይም ከፊል ብድር ወይም ሙሉ ወይም ከፊል የብድር ዋስትና ወይም ወጪ በመጋራት መልክ፡-

ሀ) ለአጭር፣ ለመካከለኛ እና ለረጅም ጊዜ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ማስፈጸሚያ ፕሮጀክቶች፤

ለ) የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ለምርምር እና ለልማት፣ ለማማከር አገልግሎት፣ ለኢነርጂ ኦዲት፣ ለሰርቶ ማሳያ ፕሮጀክቶችና ለአቅም ግንባታ ሥራዎች፤

ሐ) የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ለመረጃ ስርጭት እና ተያያዥ ለሆኑ የሕዝብ ግንኙነት ተግባራት፤ ለመሳሰሉት እንዲጠቀሙበት ሊፈቅድ ይችላል፡፡

2. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ፈንዱን ለመጠቀም የሚያስችል ዝርዝር መስፈርት በመመሪያ ይወስናል፡፡

59. <u>ስለቦርዱ ሥልጣንና ተግባራት</u>

1. ቦርዱ በአዋጁ አንቀጽ 5 የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው ፈንዱን በተመለከተ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

ሀ) ለፈንዱ የገንዘብ ማግኛ ፖሊሲዎችን የመቅረጽ፤

ለ) ዓላማዎቹን መሠረት በማድረግ የፈንዱን ድልድል የመወሰን፤

ሐ) የፈንዱን ዓመታዊ ግብ የመወሰን፤

መ) በብድር የተሰጠውን ፈንድ በመሰብሰብ ለተመሣሣይ ዓላማ በተዘዋዋሪ ብድርነት ሥራ ላይ እንዲውል የመወሰን፤ እና

ሠ) ከፈንዱ ብድር እና ድጎማ ለማግኘት የጥያቄ አቀራረብ ሥርዓትና የድልደላ መመዘኛ መመሪያ የማዘጋጀት፡፡

2. ባለሥልጣኑ ከፈንዱ አስተዳደር ጋር የተያያዙ የዕለት ተዕለት ተግባራትን ያከናውናል፡፡

3. ቦርዱ ፈንዱ በአዋጁ አንቀጽ 23 (2) ለተገለጸው ዓላማ ስለመዋሉ በየጊዜው ክትትል ማድረግ አለበት፡፡

60. <u>ስለፈንዱ አስተዳደር</u>

1. የኢነርጂ ቦርድ ስለ ፈንዱ አስተዳደር መመሪያ ያወጣል፡፡

2. የኢነርጂ ቦርድ ከተለያየ ምንጭ የሚሰበሰበውን ፈንድ የሚያስተዳድር የገንዘብ ባለአደራ ተቋም በመምረጥ ማፅደቅ አለበት፡፡
3. ለፈንዱ የሚደረግ መዋጮ በቅድሚያ ለኢነርጂ ቦርድ በማስታወቅ በባለአደራ ወኪል ዘንድ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡

61.<u>**ስለፈንዱ አሰባሰብ**</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 23 (3) ላይ ከተገለጹት ምንጮች የሚሰበሰበው ገንዘብ በየዓመቱ ተሰብስቦ ለተመረጠው የገንዘብ ባለአደራ ተቋም ገቢ መደረግ አለበት፡፡
2. ቦርዱ ፈንዱ በየጊዜው መሰብሰቡን እና በገንዘብ ባለአደራ ተቋሙ ዘንድ መቀመጡን ማረጋገጥ አለበት፡፡

62.<u>**ስለፈንዱ አጠቃቀም ሪፖርት**</u>

በዚህ ደንብ ለተመለከቱት ዓላማዎች ከፈንዱ ብድር ወይም ድጋፍ ያገኙ ተጠቃሚዎች በባለሥልጣኑ በሚዘጋጁ ቅጾች መሠረት የሩብ፣ የግማሽ እና ዓመታዊ ሪፖርት ለቦርዱ ማቅረብ አለባቸው፡፡

63.<u>**የገንዘብ ባለአደራ ተቋሙ ኃላፊነት**</u>

ባለአደራ ወኪሉ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤

1. በአዋጁ አንቀጽ 23 (3) ድንጋጌ መሠረት ባለአደራ ወኪሉ ከተለያዩ የፈንዱ ምንጮች የተገኘውን ገቢ የመቀበል እና የማስቀመጥ፤
2. ባለአደራ ወኪሉ በቦርዱ ትዕዛዝ ለኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ተግባራት እንዲውል የተወሰነን ብድር ለተበዳሪው መስጠት እና ከተበዳሪው መልሶ የመሰብሰብ፤
3. ባለአደራ ወኪሉ በውሉ መሠረት የፈንዱን ገቢ እና ወጪ የሚያሳይ የሩብ፣ የግማሽ እና ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫ ማዘጋጀት እና ለቦርዱ የማቅረብ፤
4. ከፈንዱ ጋር በተያያዘ በቦርዱ በውል የሚሰጡትን ሌሎች ተጨማሪ ተግባራት የማከናወን፡፡

<u>**ክፍል ስድስት**</u>

<u>**አለመግባባትን ስለ መፍታት**</u>

<u>**ምዕራፍ አንድ**</u>

<u>**ጠቅላላ**</u>

64.<u>**አጠቃላይ መርሆዎች**</u>

1. ማናቸውም አለመግባባቶች እና አቤቱታዎች በቅድሚያ በተከራካሪ ወገኖች መካከል በሚደረግ የጋራ ስምምነት ሊፈቱ ይችላሉ፡፡
2. ተከራካሪ ወገኖች አለመግባባታቸውን በጋራ ስምምነት መፍታት ካልቻሉ አለመግባባታቸው እንዲፈታላቸው አቤቱታቸውን ለባለስልጣኑ ወይም ለአስማሚው ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት አለመግባባቱ በአስማሚው ካልተፈታ በግልግል ዳኝነት እንዲፈታ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የግልግል ዳኝነቱን ውሣኔ የሰጠው ባለስልጣኑ ከሆነ ውሳኔው በተከራካሪዎች ላይ አስገዳጅና የመጨረሻ ይሆናል፡፡

## 65.<u>ከደንበኞች የሚቀርብ አቤቱታን ስለመስማት</u>

1. ደንበኛው ባለፈቃዱ ያዘጋጀውን ሁሉንም አቤቱታ የመስማት ሥርዓቶች አሟጦ ከጨረሰ እና በባለፈቃዱ ውሳኔ ያልረካ ከሆነ ወይም ባለፈቃዱ አቤቱታው በደረሰው በአንድ ወር ውስጥ ውሳኔ ካልተሰጠ አቤቱታውን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ባለፈቃዱ ውሳኔ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ በ15 (በአሥራ አምስት) ቀናት ውስጥ ደንበኛው አቤቱታውን በጽሁፍ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ያለበት ሲሆን ባለሥልጣኑም አቤቱታውን በተቀበለ በ15 (በአሥራ አምስት) ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ባለሥልጣኑ በቀረበለት አቤቱታ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ አስገዳጅና የመጨረሻ ይሆናል፡፡

## <u>ምዕራፍ ሁለት</u>

## <u>አለመግባባትን በማስማማት ስለመፍታት</u>

## 66.<u>አስማሚ ስለመሰየም</u>

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 64 (1) መሠረት ተከራካሪ ወገኖች አለመግባባታቸውን በስምምነት መፍታት ካልቻሉ አንዱ ወይም ሁሉም ወገኖች ባለሥልጣኑ አስማሚ እንዲሰይም ጥያቄ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት አስማሚ እንዲሰየም የሚቀርብ ጥያቄ፡-

ሀ) የተከራካሪ ወገኖችን ስም እና አድራሻን፤

ለ) የአለመግባባቱን መነሻ እና ከማስማማት ሂደቱ የሚፈለግ መፍትሄን፤ እና ሐ) በአስማሚነት እንዲሰየም የታጨውን ሰው ስምና አድራሻ መያዝ አለበት፡፡

3. ባለሥልጣኑ የአስማሚ ይሰየምልን ጥያቄን በተቀበለ በ10 (በአስር) ቀናት ውስጥ መሰየም አለበት፡፡

67.<u>የአስማሚ መሰየምን ስለመቃወም</u>

1. ማንኛውም ተከራካሪ ወገን በዚህ ደንብ አንቀጽ 66 (3) መሠረት በተሰጠ መሰየም ካልተስማማ አስማሚው በተሰየመ በ5 (በአምስት) ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ከነምክንያቱ በጽሁፍ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ባለሥልጣኑ ስያሜውን በመቃወም የቀረበው ምክንያት አሳማኝ ሆኖ ካገኘው ተከራካሪ ወገኖች በስምምነት ሌላ ተተኪ ተሰያሚ ዕጩ እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ ይሠጣል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) መሠረት አስማሚ ምርጫ ሲያካሂዱ ተከራካሪ ወገኖች ሳይስማሙ ቀርተው ባለሥልጣኑ አስማሚ እንዲሰየምላቸው ከጠየቁ ባለሥልጣኑ ጥያቄው በቀረበ በ5 (በአምስት) ቀናት ውስጥ ተተኪ አስማሚ በመመደብ ለተከራካሪ ወገኖች በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

68.<u>ማስማማትን ስለመጀመር</u>

1. አስማሚው በተሾመ በ10 (በአስር) ቀናት ውስጥ ማስማማቱን መጀመር አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት አስማሚው ሥራውን መጀመር እንዲችል ተከራካሪ ወገኖች ከአስማሚው ጋር የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

69.<u>ከአስማሚነት ስለመልቀቅ ወይም ስለመነሳት</u>

1. አስማሚው እንደተመደበ በሥራው ላይ አድልኦ ወይም ወገንተኛነት ሊፈጥሩ የሚችሉ ማናቸውም ምክንያቶች መኖራቸውን ከተረዳ ወዲያውኑ ሥራውን በመልቀቅ ለተከራካሪ ወገኖች እና ለባለሥልጣኑ ካሳወቀ በሌላ መተካት አለበት፡፡
2. አስማሚው በማናቸውም ጊዜ ነጻ ሆኖ ወይም ያለ ወገንተኛነት የመሥራት ችሎታውን ሊጎዱ የሚችሉ ወይም አግባብነት ባለው መንገድ ይጎዳሉ ተብለው

የሚታሰቡ ማናቸውም ዓይነት ጥቅም ግጭት እንዳለው በተከራካሪ ወገኖች ተቃውሞ ሲቀርብና በባለሥልጣኑ ሲረጋገጥ ተነስቶ በሌላ መተካት አለበት፡፡

70.<u>ማስማማት ስለሚቋረጥበት ሁኔታ</u>

1. የማስማማት ሂደት ከሚከተሉት ሁኔታዎች በአንዱ ሊቋረጥ ይችላል፡-
   ሀ) ተከራካሪዎቹ አለመግባባታቸውን በስምምነት ከፈቱ ወይም ሊፈቱ ካልቻሉ፣
   ለ) አስማሚው ከተከራካሪዎች ጋር ከተመካከረ በኋላ የማስማማት ሂደቱ ቢቀጥል ማስማማት የማይቻል መሆኑን ለተከራካሪዎች እና ለባለሥልጣኑ በጽሁፍ ካሳወቀ፤ ወይም
   ሐ) ከተከራካሪዎች አንዱ ወይም ሁሉም ምክንያት መግለጽ ሳያስፈልግ በራሳቸው ፍላጎት ማስማማቱ እንዲቋረጥ የወሰኑ መሆኑን ለአስማሚው እና ለባለሥልጣኑ በጽሁፍ ካሳወቁ፡፡
2. አስማሚው በማስማማቱ የተደረሰበትን የመጨረሻ ውጤት ለባለሥልጣኑ በጽሁፍ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

<u>ምዕራፍ ሦስት</u>

<u>አለመግባባትን በግልግል ዳኝነት ስለመፍታት</u>

71.<u>ስለግልግል ዳኝነት</u>

በዚህ ደንብ መሠረት አለመግባባቱ በማስማማት ካልተፈታ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸው በባለስልጣኑ የግልግል ዳኝነት እንዲታይ ሊስማሙ ይችላሉ፡፡

72.<u>ስለግልግል ዳኝነት ፓናል መቋቋም</u>

1. ባለሥልጣኑ በዚህ ደንብ አንቀጽ 71 መሠረት የሚቀርብ አለመግባባትን ለመፍታት የግልግል ዳኝነት ፓናል ያቋቁማል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቋቋመው የግልግል ዳኝነት ፓናል የዳኞች ብዛት ሰብሳቢውን ጨምሮ ከሦስት መብለጥ የለበትም፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም እንደ አለመግባባቱ የውስብስብነት ደረጃ ባለስልጣኑ በአንድ ዳኛ ብቻ እንዲዳኝ ሊወስን ይችላል፡፡
4. ባለሥልጣኑ ስለግልግል ዳኝነት ፓናል አባላት ብቃት፣ ሹመት፣ ሽረት እና መተካት በመመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

73.<u>ስለግልግል ፓናል የዳኝነት ሥልጣን</u>

የግልግል ዳኝነት ፓናል በአዋጁ፣ በዚህ ደንብ እና ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ በሚሸፈኑ ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ሥልጣን አለው፡፡

74.<u>ስለግልግል ዳኝነት ፓናል ሥነ-ሥርዓት</u>

በዚህ ደንብ አንቀጽ 72 መሠረት በሚቋቋመው የግልግል ዳኝነት ፓናል በሚካሄድ ክርክር ላይ የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

75.<u>ስለግልግል ዳኝነት የአገልግሎት ክፍያ</u>

ባለሥልጣኑ የግልግል ዳኞች አገልግሎት ክፍያን በተመለከተ በቀጥታ ጉዳዩ የሚመለከታቸውና ወጪውን በሚሸፍኑት አካላት ፈቃደኝነት ላይ ተመሰርቶ በድርድር ይወስናል፡፡

## <u>ክፍል ሰባት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

76.<u>ስለ ጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እና የገንዘብ ቅጣት</u>

1. በኤሌክትሪክ አቅርቦት ላይ የተሰማራ የማመንጨት፣ የማስተላለፍ ወይም የማከፋፈልና እና የመሸጥ ባለፈቃድ አገልግሎት የሚሰጠው በተቀመጠለት ደረጃ መሠረት ያለመሆኑ ሲረጋገጥ ባለስልጣኑ ለባለፈቃዱ ከበቂ የማስተካከያ ጊዜ ጋር የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፡፡
2. በኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ አስገዳጅ አሠራሮች ላይ የአፈጻጸም ክፍተት ሲኖር፤ የብቃት ምስክር ወረቀት የተሰጣቸው ሙያተኞች፣ ፈቃድ ያላቸው የኢነርጂ ኦዲተሮች ወይም አማካሪዎች ወይም ኮንትራክተሮች አገልግሎት አሰጣጣቸው በተቀመጠለት ደረጃ ወይም ተቀባይነት ባለው አሠራር መሠረት ያለመሆኑ ሲረጋገጥ ባለሥልጣኑ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ከበቂ የማስተካከያ ጊዜ ጋር ይሰጣል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በተሰጠ በቂ የማስተካከያ ጊዜ ውስጥ ባለፈቃዱ አገልግሎቱን በተፈለገው ደረጃ ባለማሻሻሉ በተገልጋዩ እና በኅብረተሰቡ ላይ ችግር ከተፈጠረ በአዋጁ አንቀጽ 4 (2) እና አንቀጽ 8 (2) መሠረት ባለስልጣኑ:-
   ሀ) እንደጥፋቱ ክብደት እስከ 10 ሚሊዮን (አስር ሚሊዮን) ብር የሚደርስ አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣት ይወስናል፤

ለ) በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በአንድ ባለፈቃድ ላይ በዚህ ንዑስ አንቀጽ (ሀ) መሠረት የሚጣለው ጠቅላላ የቅጣት መጠን ከብር 20 ሚሊዮን (ሃያ ሚሊዮን) መብለጥ የለበትም፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት በተሰጠ በቂ የማስተካከያ ጊዜ ውስጥ የሙያ ብቃት የተረጋገጠላቸው ፈቃድ ያላቸው የኢነርጂ ኦዲተሮች ወይም አማካሪዎች ወይም ኮንትራክተሮች የአገልግሎት ደረጃቸው በተቀመጠው ደረጃ ወይም በአዋጁ አንቀጽ 4 (6) እንደተደነገገው በባለስልጣኑ በሚወጣ ኮድ መሠረት ያለመሆኑ ሲረጋገጥና ማስጠንቀቂያውን ተመስርቶ የማስተካከያ ወይም የእርምት እርምጃ ካልተወሰደ ባለሥልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 4 (2) መሠረት እስከ ብር 200ሺ (ሁለት መቶ ሺ) የሚደርስ አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣት ይወስናል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ መሠረት ባለሥልጣኑ የገንዘብ ቅጣት እርምጃ በሚወስድ ጊዜ በጥፋቱ ምክንያት የደረሰውን ጉዳት ከግምት ያስገባ መሆን አለበት፡፡

6. ባለስልጣኑ ቅጣቱን ከመወሰኑ በፊት ሊወሰን ያለውን ቅጣት አስመልክቶ ለባለጉዳዩ በመግለጽ መከላከያ ሀሳብ ካለው እንዲያቀርብ ወይም የማቅለያ ሀሳብ እንዲያቀርብ በቂ ጊዜ መስጠት አለበት፡፡

7. ዝርዝር የቅጣት እርከንና ዋስትና ሊሰጥባቸው የሚገቡ ዝቅተኛ የአገልግሎት ደረጃዎች ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ ይወስናል፡፡

77.<u>ስለጅምላ የኤሌክትሪክ ኃይል የግዥ ሥነ-ሥርዓት</u>

1. የጅምላ ኤሌክትሪክ ኃይል የሚገዛበት ሥነ- ሥርዓት አግባብ ባለው የሀገሪቱ ሕግ መሠረት በተቻለ መጠን ፍትሐዊ፣ ግልጽ እና ውድድርን የሚያበረታታ መሆን አለበት፡፡

2. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የጅምላ ኤሌክትሪክ ኃይል ግዥ አሠራር ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

3. ለባለስልጣኑ ረቂቅ የጅምላ ኃይል ግዥ እና ረቂቅ የኔትወርክ አጠቃቀም ስምምነት በአዋጁ አንቀጽ 4 (7) መሠረት ሲቀርብለት መርምሮ ያፀድቃል፡፡

78.<u>ስለ ደህንነት፣ ቴክኒክ እና የአገልግሎት ጥራት ደረጃዎች</u>

ባለሥልጣኑ ስለ ደህንነት፣ ቴክኒክና የአገልግሎት ጥራት ደረጃዎች መመሪያ ያወጣል፡፡

79.**አደጋን ስለማሳወቅ**

1. የኤሌክትሪክ ኃይል ከማመንጨት፣ ከማስተላለፍ፣ ከማከፋፈል ወይም ከመጠቀም ጋር በተገናኘ ለሰው ሕይወት ማለፍ ምክንያት የሆነ ወይም ከባድ የአካል ጉዳት ያደረሰ ወይም በንብረት ላይ ከባድ ውድመት ያደረሰን ማናቸውንም አደጋ ባለፈቃዱ ባወቀ በ24 ሰዓት ውስጥ ለባለሥልጣኑ እና አግባብ ላለው የመንግሥት አካል ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሠረት ከባድ የአካል ጉዳት ማለት ተጎጂው በሆስፒታል ተኝቶ የሚታከም ሲሆን እንዲሁም ከባድ የንብረት ጉዳት ማለት አብዛኛው የንብረቱ ክፍል የተበላሸ ወይም የወደመ እንደሆነ ነው፡፡

80.**በባለሥልጣኑ ስለሚደረግ ምርመራ**

1. ማንኛውም በባለሥልጣኑ የተወከለ ተቆጣጣሪ በባለፈቃዱ ይዞታ በሆነ በማንኛውም ቦታ ውስጥ የመግባት እና በማናቸውም ጊዜ የመቆጣጠር፣ የመመርመር እንዲሁም መረጃ የመውሰድ መብት አለው፡፡
2. ባለፈቃዱ በቁጥጥር እና በምርመራ ወቅት በባለሥልጣኑ ከተወከለው ተቆጣጣሪ ጋር መተባበር እና ድጋፍ ማድረግ አለበት፡፡
3. በባለሥልጣኑ የተወከለ ተቆጣጣሪ የቁጥጥር ተግባሩን ከመጀመሩ በፊት ከባለሥልጣኑ የተሰጠውን የተቆጣጣሪነት መታወቂያ ካርድ ወይንም አግባብነት ያለውን ፈቃድ ማሳየት አለበት፡፡

81.**ከግሪድ ውጭ የማከፋፈል፣ የመሸጥ እና የማመንጨት ባለፈቃድ ስለሚደረግ ጥበቃ**

1. ብሔራዊ ግሪዱ ከግሪድ ውጭ ከሚሰራ የማመንጨት፣ የማስተላለፍ ወይም የማከፋፈል እና የመሸጥ የብቻ የሆነ ባለፈቃድ ኔትወርክ ዞንድ በሚደርስበት ወቅት የብሔራዊ ግሪዱ ባለፈቃድ በስምምነት አግባብነት ያለው ካሳ ለባለፈቃዱ በመክፈል የማከፋፈል እና የመሸጥ የብቻ ፈቃድ ኔትወርኩንና እና ተያይዞ ያለውን የማመንጫ ፋሲሊቲ ከብሔራዊ ግሪዱ ጋር እንዲጠቃለል ሊያደርግ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተጠቀሰው መሠረት የአቅርቦት ፋሲሊቲው ወደ ብሔራዊ ግሪዱ የሚካተተው ደረጃውን ጠብቆ የተሰራ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡ ፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚከፈለውን የካሳ መጠን አስመልክቶ ስምምነት ላይ ካልተደረሰ ባለሥልጣኑ በግልግል ዳኝነት አይቶ ይወስናል፡፡
4. ከግሪድ ውጭ ያለ የማከፋፈል እና የመሸጥ ባለፈቃድ በመፍረሱ ወይም በመክሰሩ ምክንያት የኤሌክትሪክ አገልግሎት መስጠት ያልቻለ እንደሆነ የነባር ደንበኞች አገልግሎት እንዳይቋረጥ ለማድረግ የብሔራዊ ግሪዱ እንዳስፈላጊነቱ የማስተላለፍ ወይም የማከፋፈልና የመሸጥ ባለፈቃድ ከግሪድ ውጭ ያለውን የማመንጫና የማከፋፈያ ፋሲሊቲ እንዲያገናኝ ባለሥልጣኑ ውሣኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

82.<u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

ባለሥልጣኑ ይህን ደንብ በአግባቡ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

83.<u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>

1. ይህ ደንብ ከመጽናቱ በፊት ለንግድ ዓላማ የተሰጠ ኤሌክትሪክ የማመንጨት፣ የማስተላለፍ ወይም የማከፋፈልና የመሸጥ ወይም የአስመጪነት እና የላኪነት ፈቃድ በባለሥልጣኑ በማስታወቂያ በሚገለጸው የጊዜ ገደብ ውስጥ በዚህ ደንብ መሠረት በሚሰጥ አዲስ ፈቃድ መተካት አለበት፡፡
2. ይህ ደንብ ከመጽናቱ በፊት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በዚህ ደንብ መሠረት በባለሥልጣኑ ማስታወቂያ በሚገለጽ የጊዜ ገደብ ውስጥ በአዲስ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እስኪተካ ድረስ ጸንቶ ይቆያል፡፡

84.<u>የተሻሩ እና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>

1. የኤሌክትሪክ ሥራዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 49/1991 ተሽሯል፡ ፡
2. ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

85.<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር 20 ቀን 2011 ዓ.ም**

**ዶ/ር አብይ አህመድ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ሠንጠረዥ 1

## ለፈቃድ እና ለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ የክፍያ ዝርዝር

| | | |
|---|---|---|
| 1. ለቁጥጥር/ ለሪጉሌሽን የአገልግሎት ክፍያ | | |
| ተ.ቁ | የአገልግሎት ዓይነት | ለአገልግሎቱ የሚከፍለው ክፍያ መጠን በብር |
| 1. | የኤሌክትሪክ ዘርፍ ቁጥጥር አገልግሎት | 0.117 ብር/ በተሸጠ ሜጋ ዋት ሰዓት በዓመት |
| 2. የኤሌክትሪክ ሥራ ፍቃድ ክፍያ | | |
| ተ.ቁ | የአገልግሎት ዓይነት | ለአገልግሎቱ የሚከፍለው ክፍያ መጠን በብር |
| 1 | የኤሌክትሪክ ማመንጨት /ማሰተላለፍ/ ማከፋፈልና መሸጥ ፈቃድ ማመልከቻ | 496 |
| 2 | የኤሌክትሪክ ማመንጨት/ማሰተላለፍ/ ማከፋፈልና መሸጥ ፈቃድ መስጠት | |
| | እስከ 10 ሜጋዋት | 2500 |
| | ከ10 ሜጋዋት በላይ | 6883 |
| 3 | የማመንጫ/ማስተላለፊያ/ማከፋፈያና መሸጥ ፈቃድ ዕድሳት/ማሻሻል/ ማስተላለፍ | |
| | እስከ 10 ሜጋዋት | 1668 |
| | ከ10 ሜጋዋት በላይ | 4595 |

| 3. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የአገልግሎት ክፍያ | | |
|---|---|---|
| 3.1. በባለሙያ የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ | | |
| የሙያ ደረጃ | የአገልግሎት ዓይነት | ለአገልግሎቱ የሚከፍለው ክፍያ መጠን በብር |
| ደረጃ 1 | ምዝገባ | 51.56 |
| | የጽሁፍ ፈተና | 212.32 |
| | የተግባር ፈተና | 272.98 |
| | ሰርተፍኬት | 69.76 |
| | እድሳት | 121.33 |
| ደረጃ 2 | ምዝገባ | 41.25 |
| | የጽሁፍ ፈተና | 169.85 |
| | የተግባር ፈተና | 218.39 |
| | ሰርተፍኬት | 55.81 |
| | እድሳት | 97.06 |
| ደረጃ 3 | ምዝገባ | 30.95 |
| | የጽሁፍ ፈተና | 127.39 |
| | የተግባር ፈተና | 163.79 |
| | ሰርተፍኬት | 41.85 |
| | እድሳት | 72.80 |
| ደረጃ 4 | ምዝገባ | 20.63 |
| | የጽሁፍ ፈተና | 84.93 |
| | የተግባር ፈተና | 109.20 |
| | ሰርተፍኬት | 27.90 |
| | እድሳት | 48.53 |
| ደረጃ 5 | ምዝገባ | 10.30 |
| | የጽሁፍ ፈተና | 42.46 |
| | የተግባር ፈተና | 54.60 |

| | | |
|---|---|---|
| | ሰርተፍኬት | 13.95 |
| | እድሳት | 24.27 |
| 3.2. በድርጅቶች ለብቃት ማረጋገጫ የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ | | |
| ደረጃ | የአገልግሎት ዓይነት | ለአገልግሎቱ የሚከፍለው ክፍያ መጠን በብር |
| ደረጃ 1 | የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት | 606.64 |
| | የብቃት ማረጋገጫ ለማደስ | 121.33 |
| ደረጃ 2 | የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት | 400.38 |
| | የብቃት ማረጋገጫ ለማደስ | 80.08 |
| ደረጃ 3 | የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት | 200.19 |
| | የብቃት ማረጋገጫ ለማደስ | 40.04 |
| 4. የኢነርጂ ኦዲተሮችና ለኢነርጂ አገልግሎት ሰጪ ኩባንያዎች ፈቃድ የአገልግሎት ክፍያ | | |
| | የአገልግሎት ዓይነት | ለአገልግሎቱ የሚከፍለው ክፍያ መጠን በብር |
| ለኢነርጂ ኦዲተሮች | ለፍቃድ ማመልከቻ | 321.5 |
| | ፍቃድ ለመስጠት | 402 |
| | ፍቃድ ለማደስ | 143 |
| ለኢነርጂ አገልግሎት ሰጪ ኩባንያዎች (ESCOs) ፈቃድ | ለፍቃድ ማመልከቻ | 68 |
| | ፍቃድ ለመስጠት | 163 |
| | ፍቃድ ለማደስ | 40.75 |

## አዋጅ ቁጥር 838/2006

## የነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች አቅርቦት ሥራ መቆጣጠሪያ አዋጅ

በሀገሪቱ ውስጥ የሚካሄደው የነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች አቅርቦት ሥራ ዓለም አቀፍ ደረጃውንና ጥራቱን በጠበቀ ሁኔታና በሰው ጤና፣ በንብረትና በአካባቢ ላይ ጉዳት በማያደርስ መልኩ መከናወኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስም ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶችን በማጣራት፣ በማከማቸት፣ በማጓጓዝ፣ በማከፋፈልና በመቸርቸር እና ከእነዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሥራዎች የሚሠሩ ተቋማትና ባለሙያዎች ዓለም አቀፍ ልምድ በሚጠይቀው መሠረት በሚፈለገው የብቃት ደረጃ ላይ የሚገኙ መሆኑን መከታተልና መቆጣጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55 (1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች አቅርቦት ሥራ መቆጣጠሪያ አዋጅ ቁጥር 838/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

   1. "ነዳጅ" ማለት ድፍድፍ ነዳጅ እና ከድፍድፍ ነዳጅ፣ ከከሰል ድንጋይ፣ ከሺስት፣ ከቅርፊት፣ ከፒት የሚሠራ ማናቸውንም ፈሳሽ ወይም ጋዝ ወይም ማናቸውንም የድፍድፍ ነዳጅ ምርት እና ኮንደንሴትን ያካትታል፤
   2. "የነዳጅ ውጤት" ማለት የተፈጥሮ ድፍድፍ ነዳጅን፣ ባዮ-ፊውልን ወይም ሲንተቲክ ነዳጅን ከማጣራት ወይም ከማቀነባበር የተገኘ ንፁህ ወይም የተቀላቀለ ውጤት ሲሆን የሚከተሉትን ያካትታል፡-

      ሀ) ሬንጅ፣ ቢትመን፣ የፔትሮሊየም ኮክ እና ሌሎች ዝቃጭ ምርቶችን፤

      ለ) ለሞተሮች ማንቀሳቀሻ ወይም ለቦይለሮች ማሞቂያ ወይም ለማሞቂያ ፈርነሶች የሚውሉ ባንከሮች ወይም ከባድ ዝቃጭ የነዳጅ ዘይቶችን፤

ሐ) ለንግድ የሚውሉ ጋዞች ማለትም ሚቴን፣ ኢቴን፣ ፕሮፔን፣ ቡቴን እና ሌሎች መሰል የፔትሮሊዬም ጋዞች፣ የተፈጥሮ ጋዝ ወይም በጋዝነትም ሆነ በፈሳሽ መልክ የእነዚህ ጋዞች ድብልቅን፤

መ) ቤንዚን ወይም ናፍጣ፣ ባዮ-ዲዝል፣ ኢንዱስትሪያዊ የማሪን ወይም ሲንተቲክ ናፍጣዎችን፤

ሠ) የባዮ-ኤታኖል ምርቶችን፤

ረ) ለኢሉሚኔሽን ወይም ኮምባስችን የሚሆኑ ነጭ ላምባ ወይም ሌሎች መሰል ዘይቶችን፤

ሰ) የተሽከርካሪ ቅባት ዘይቶች፣ የቤዝ ዘይቶች ወይም የተጣሩና የተቀላቀሉ ያለቀላቸው ነዳጅ ዘይቶችን፤

ሸ) ለአውሮፕላን የሚያገለግሉ ነዳጆችን፤

ቀ) በፔንሲኪ-ማርተንስ ዝግ የመሞከሪያ አፓራተስ በተወሰነው መሠረት ከ120 ዲግሪ ሴልሺየስ ያነሰ ፍሳሽ ፖይንት ያላቸው ሌሎች የድፍድፍ ነዳጅ ምርቶች ወይም ተረፈ ምርቶችን፤

3. “የነዳጅ አቅርቦት ሥራ” ማለት ነዳጅና የነዳጅ ውጤት ወደ ሀገር ውስጥ የማስገባት፣ ወደ ውጭ የመላክ፣ የማጣራት፣ የማደባለቅ፣ የማጓጓዝ፣ የማከማቸት፣ የማከፋፈል፣ የመቸርቸር ወይም ከእነዚህ ጋር ተያያዥነት ያለው ማናቸውም ሥራ ሲሆን የነዳጅ ምርትን ለራሳቸው በግብአትነት በቀጥታ ከአከፋፋይ የሚገዙ ተቋማት ተግባራትን ይጨምራል፤

4. “የአቅርቦት ሠንሰለት” ማለት ከነዳጅ አቅርቦት ሥራ ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ግንኙነት ያላቸውን ተግባሮች፣ ሥራዎች፣ ተቋሞችና መሣሪያዎች ያካትታል፤

5. “የነዳጅ ተቋም” ማለት ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶችን ለማጣራት፣ ለመደባለቅ፣ ለማከማቸት፣ ለማጓጓዝ፣ ወደውጭ ለመላክ፣ ወደሀገር ውስጥ ለማስገባት፣ ለማከፋፈል ወይም ለመቸርቸር እና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን ሥራዎች ለመሥራት በጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም ተቋም ነው፤

6. “ማጣሪያ” ማለት ከድፍድፍ ነዳጅ የነዳጅ ምርቶችንና ፈሳሽ ፔትሮሊየም ጋዝ ለማምረት የሚያገለግል የነዳጅ ማጣሪያ ፋብሪካ ነው፤

7. “የቧንቧ መስመር” ማለት ነዳጅ ወይም የነዳጅ ውጤቶችን ለማጓጓዝ ጥቅም ላይ የሚውል ቧንቧ ወይም የቧንቧዎች ኔትወርክ ሲሆን ተያያዥ ሥራዎችንና መሣሪያዎችን ያካትታል፤
8. “ግንባታ” ማለት የተያያዥ ህንፃዎችን ግንባታ ሳይጨምር የነዳጅ ተቋም ግንባታ ነው፤
9. “መደባለቅ” ማለት የተሻለ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ጠቀሜታ ለማግኘት የነዳጅ ውጤትን ከባዮ-ፊውል ወይም ከሌላ የቴክኖሎጂ ውጤት ጋር በተወሰነና በተመጣጠነ መጠን የማቀላቀል ተግባር ነው፤
10. “ብክለት” ማለት የዚህን አዋጅ ወይም አግባብ ያለውን ሕግ ድንጋጌ በመጣስ ከፍ ያለ የጥራት ደረጃ ያለውን የነዳጅ ውጤት ዝቅተኛ የጥራት ደረጃ ካለው የነዳጅ ውጤት ጋር በመደባለቅ የተከሰተ ለሰው፣ ለሌሎች ሕያዋን ለሆኑ ነገሮች፣ ለአካባቢ፣ ለመሣሪያዎች ወይም ለማሽነሪዎች አደገኛ ሊሆን የሚችል ሁኔታ ነው፤
11. “ማከማቸት” ማለት ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች ወደ ማከማቻ ወይም ወደ ማከፋፈያዎች እስከሚሠራጩ ድረስ ለተወሰነ ጊዜ ይዞ ማቆየት ነው፤
12. “ማጓጓዝ” ማለት የተለያዩ የማጓጓዣ ዘዴዎችን በመጠቀም የነዳጅ ውጤቶችን ከኢትዮጵያ ውጭ ከሚገኝ የማከማቻ ተቋም ሀገር ውስጥ ወደሚገኝ ማከማቻ ተቋም ወይም ሀገር ውስጥ ከሚገኝ የማከማቻ ተቋም ወደ ሌላ ማከማቻ ተቋም ወይም በቀጥታ ለተጠቃሚው ወደ ሚከፋፈልበት ተቋም ማጓጓዝ ነው፤
13. “ማከፋፈል” ማለት የነዳጅ ውጤቶችን ለነዳጅ ማደያዎች ወይም በቀጥታ ተጠቃሚ ለሆኑ አካላት በጅምላ ማቅረብ ነው፤
14. “ጅምላ ሻጭ” ማለት በሌላ ሕግ ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች ወደ አገር ውስጥ ማስገባትን በተመለከተ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶችን ከአምራች ወይም ከአስመጪ ገዝቶ ለቸርቻሪ የሚሸጥ ማንኛውም ሰው ሲሆን አምራች ወይም አስመጪ ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶችን ለቸርቻሪ ወይም ለጅምላ ሻጭ ሲሸጥ በጅምላ ንግድ እንደተሳተፈ ይቆጠራል፤
15. “ቸርቻሪ” ማለት ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶችን ከጅምላ ሻጭ፣ ከአስመጪ ወይም ከአምራች ገዝቶ ለተጠቃሚ የሚሸጥ ማንኛውም ሰው ሲሆን ጅምላ ሻጭ፣ አስመጪ ወይም አምራች ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶችን በቀጥታ ለተጠቃሚ ሲሸጥ በችርቻሮ ንግድ ውስጥ እንደተሳተፈ ይቆጠራል፤

16.“የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት” ማለት ለንግድ ዓላማ ቢሆንም ባይሆንም ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶችን የማጣራት፣ የመደባለቅ፣ ወደአገር ውስጥ የማስገባት፣ ወደውጭ የመላክ፣ የማከማቸት፣ የማጓጓዝ፣ የማከፋፈል፣ የመቸርቸር ወይም የመደባለቅና ከእነዚሁ ጋር ተያይዘው የሚከናወኑ ሌሎች ሥራዎች የመሥራትን ብቃት ለማረጋገጥ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፤

17.“ክትትል” ማለት የነዳጅ ተቋማት በተሰጣቸው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መሠረት መሥራታቸውን የማረጋገጥ ሂደት ነው፤

18.“ባለፈቃድ” ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት እንደ አግባቡ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም የግንባታ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤

19.“ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የውሃ፣ የመስኖና ኢነርጅ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

20.“ክልል”ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 (1) የተመተለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

21.“ኮሚቴ” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 26 የተመለከተው ኮሚቴ ነው፡፡

22.“ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

23.ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ያካትታል፡፡

3. <u>**የተፈፃሚነት ወሰን**</u>

1. ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚካሄድ ማናቸውም ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች አቅርቦት ሥራ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ በሚካሄድ የነዳጅ ፍለጋ፣ ማልማትና ማውጣት ሥራ እና ልማቱ በሚካሄድበት አካባቢ በሚከናወን ነዳጅ የማጓጓዝና የማከማቸት ተግባር እንዲሁም ለወታደራዊ አገልግሎት በሚውል የነዳጅ አቅርቦት ሥራ ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና ስለግንባታ ፈቃድ</u>

4. <u>**የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት**</u>

ማናቸውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖረው በነዳጅ አቅርቦት ሥራ ላይ መሠማራት አይችልም።

5. <u>**ማመልከቻ ስለማቅረብ**</u>

1. በነዳጅ አቅርቦት ሥራ መሠማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ለሚኒስቴሩ ማመልከት አለበት፡፡
2. ማመልከቻ የሚቀርብበት፣ የሚገመገምበትና የሚፀድቅበት ሥርዓት እንዲሁም መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎችና መቅረብ የሚገባቸው መረጃዎችና ማስረጃዎች ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ መመሪያ የሚወሰኑ ይሆናል፡፡

6. <u>**የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት**</u>

1. ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 መሠረት የቀረበን ማመልከቻ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ሥር ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች አንፃር በመገምገም የተጠየቀውን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል ወይም ይከለክላል።
2. ሚኒስቴሩ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከመስጠቱ በፊት የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡-
   - ሀ) የተጠቃሚዎችን የወደፊት የነዳጅ ውጤቶች ፍላጎትን ከማሟላት አንፃር የሚያበረክተውን አስተዋጽዖ፤
   - ለ) ከሀገሪቱ የኢነርጂ ዕቅድና ስትራቴጂዎች ጋር የሚጣጣም መሆኑን፤
   - ሐ) በነዳጅና በነዳጅ ውጤቶች አቅርቦት ኢንዱስትሪ ውስጥ የውድድር ሁኔታ ለመፍጠር የሚኖረውን አስተዋጽዖ፤
   - መ/ ከማኅበራዊና አካባቢ ጥበቃ አንፃር ሊያስከትል የሚችለውን ተጽዕኖ፤
   - ሠ) በሕዝብ ጤና እና ደህንነት እንዲሁም በድርጅቱ ሠራተኞች ላይ ሊያሳድር የሚችለውን ተጽዕኖ፤
   - ረ) አመልካቹ ከሕግ፣ ከቴክኒክና ከፋይናንስ አንፃር ያለውን ችሎታና ብቃት፤
   - ሰ) ሊሠራ የታሰበውን ሥራ አስመልክቶ በአካባቢው ህብረተሰብ የቀረበ ጥያቄ ወይም አስተያየት፤ እና
   - ሸ) ሊሠራ በታሰበው ሥራ ምክንያት ሊጎዱ የሚችሉ ሌሎች ሕዝባዊ ጥቅሞች፡፡
3. በዚህ አንቀጽ መሠረት ሚኒስቴሩ የተጠየቀውን ፈቃድ የከለከለ ከሆነ ምክንያቱን ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለአመልካቹ በጽሑፍ መግለጽ አለበት፡፡

7. <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜና እድሳት</u>

   1. በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ እና የሚታደስበት የጊዜ ገደብ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ በሚወሰነው መሠረት ይሆናል፡፡
   2. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ እና መመሪያ ውስጥ የተመለከቱትን አስፈላጊ ሁኔታዎች ማክበሩን ሚኒስቴሩ ሲያረጋግጥ የምስክር ወረቀቱን ያድሳል፡፡
   3. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሳይታደስ ከቀረ እንደተሠረዘ ይቆጠራል።

8. <u>የአገልግሎት ክፍያ</u>

   የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በሚሰጥበትና በሚታደስበት ጊዜ በአመልካቾች ሊከፈል የሚገባው የአገልግሎት ክፍያ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

9. <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን ስለማስተላለፍ</u>

   ሚኒስቴሩ በጽሑፍ ካልፈቀደ በስተቀር የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን ለሌላ ሰው ማስተላለፍ አይቻልም።

10. <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን ስለማገድ ወይም ስለመሰረዝ</u>

    በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፣ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው፡-

    1. የአካባቢ ጥበቃን፣ የማኅበረሰብ ደህንነትን፣ አነስተኛ የአከፋፋይ የነዳጅ ውጤቶች የማከማቸት አቅምንና በሥሩ የሚተዳደሩ የችርቻሮ ተቋማት ቁጥርን፣ የነዳጅ ውጤቶች ጥራት ደረጃን፣ የነዳጅ ውጤቶች ብክለትን፣ የነዳጅ ውጤቶች ሕገ ወጥ ንግድን ወይም ታክስ ማጭበርበርን አስመልክቶ በዚህ አዋጅም ሆነ በሌላ ሕግ የወጡ ድንጋጌዎችን ካላከበረ፤
    2. ማሟላት ያለበትን የነዳጅ ተቋም ደረጃዎችና መሥፈርቶች አስመልክቶ እንዲያርም በጽሑፍ ተገልጾለት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላረመ፣

    ሊታገድ ወይም ሊሠረዝ ይችላል፡፡

11. <u>የነዳጅ ተቋት ግንባት</u>

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ የነዳጅ ተቋም ግንባታ ፈቃድ ሳይኖረው የነዳጅ ተቋም ግንባታ ማካሄድ አይችልም። ሆኖም በአንድ ነባር የነዳጅ ተቋም ውስጥ ለሚካሄድ መደበኛ የጥገና ሥራዎች እና የቧንቧ መስመር ዝርጋታ አዲስ የግንባታ ፈቃድ ማውጣት አያስፈልግም።

12.**ስለግንባት ፈቃድ ማመልከቻ**

የግንባታ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን መረጃዎች ማካተት አለበት፡-

1. የአመልካቹን ስምና አድራሻ፤
2. ሊገነባ የታቀደውን የሥራ ዓይነት፤
3. ሊገነባ የታቀደው ሥራ ጠቀሜታና ኢኮኖሚያዊ አዋጭነት፤
4. ሊገነባ ለታቀደው ሥራ የተፈቀደ ፕላንና ዝርዝር መሥፈርት ከሦስት ቅጂዎች ጋር፤
5. ሊገነባ የታቀደው የነዳጅ ቧንቧ መሥመር ዝርጋታ ሥራ ከሆነ መነሻውና መድረሻውን እንዲሁም የቧንቧ መሥመሩ የሚያልፍበት መሬትን የመጠቀም ፈቃድ አግባብ ካለው አካል የተሰጠው ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የጽሑፍ ማስረጃ፤
6. ሌሎች ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተገለፁ ዝርዝር መረጃዎች፡፡

13.**የግንባታ ፈቃድ የሚያበቃበት ግዜ**

የነዳጅ ተቋም ግንባታ ፈቃድ በተሰጠ በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ የተፈቀደው የግንባታ ሥራ ካልተጀመረ የተሰጠው ፈቃድ እንደተሠረዘ ይቆጠራል፡፡

14.**የግንባታ ፈቃድ  መታገድ ወይም መሠረዝ**

1. ሚኒስቴሩ በሰጠው የግንባታ ፈቃድ የተካተቱ ገደቦች ወይም ሁኔታዎች ካልተሟሉ የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ በመስጠት በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ ፈቃድን ማገድ ይችላል።
2. ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በሰጠው የአንድ ወር ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ጊዜ ውስጥ ባለፈቃዱ ፈቃዱ የታገደበትን ምክንያት ካረመ ሚኒስቴሩ እገዳውን ያነሳል።
3. ባለፈቃዱ በተሰጠው የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ጊዜ ውስጥ ፈቃዱ የታገደበትን ምክንያት ካለረመ ሚኒስቴሩ ፈቃዱን ይሠርዛል።

15.**<u>የተፈቀደ ግንባታም ስራ ላይ ስለማዋል</u>**

በዚህ አዋጅ መሠረት በተሰጠ የግንባታ ፈቃድ የተሠራ ማናቸውም የነዳጅ ተቋም ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በወጣ መመሪያ እንዲሟሉ የተዘረዘሩ ቅድመ ሁኔታዎች ስለመሟላታቸው በሚኒስቴሩ የጽሑፍ ማረጋገጫ ሳይሰጥ ሥራ ላይ ሊውል አይችልም።

16.**<u>ሕጎችን ስለማክበር</u>**

1. ማንኛውም ባለፈቃድ ከነዳጅ ተቋም ጋር በተያያዘ የሠራተኞች ጤና አጠባበቅን፣ የሕዝብ ደህንነትን እና የአካባቢ ጥበቃን የሚመለከቱ አግባብነት ያላቸውን ሕጎች የማክበርና ደረጃዎችንና የቴክኒክ ዝርዝር መሥፈርቶችን የማሟላት ግዴታ አለበት፡፡
2. ማንኛውም ባለፈቃድ የሥራውን እንቅስቃሴ የሚመለከቱ መዝገቦችንና ሪኮርዶችን የመያዝና በሚኒስቴሩ ሲጠየቅ ሪፖርቶችን የማቅረብ ግዴታ አለበት።
3. ማንኛውም ባለፈቃድ በሚኒስቴሩ የተመደበ ተቆጣጣሪ በማንኛውም የነዳጅ ተቋም ወይም የነዳጅ ተቋም ግንባታ ቦታ ተገኝቶ የቁጥጥርና ክትትል ሥራ ማካሄድ ሲፈልግ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>የሕዝብ ጤናና ደህንነት እና አካባቢ ጥበቃ</u>

17.**<u>ስለደረጃዎችና ዝርዝር መስፈርቶች</u>**

ሚኒስቴሩ በነዳጅ ውጤቶች የአቅርቦት ሠንሰለት መሠረተ ልማት እና በነዳጅ ምርቶችና አገልግሎቶች የጥራት ደረጃዎችና መሥፈርቶች እንዲሁም በሥነ-ምግባር ደንቦች ዝግጅት ረገድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሠራል።

18.**<u>የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ</u>**

ሚኒስቴሩ አግባብ ካለው አካል ጋር በመመካከር በዚህ አዋጅ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለመስጠት በቅድመ ሁኔታነት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የሚያስፈልጋቸውን የነዳጅ አቅርቦት ሥራዎች ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

19.**<u>የነዳጅ እና የነዳጅ ውጤቶች ፍተሻ</u>**

1. ከ500 ሊትር በላይ ነዳጅ ወይም የነዳጅ ውጤት በፈሰሰ ጊዜ ንብረቱን በኃላፊነት የያዘው አካል ምርቶቹ በፈሰሱ በ24 ሰዓታት ውስጥ ስለ ሁኔታው ለሚኒስቴሩ ወይም ሚኒስቴሩ ለወከለው አካል ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡
2. የፈሰሰው ነዳጅ ወይም የነዳጅ ውጤት በይዞታው ሥር የነበረ ሰው ወይም ባለቤት ፍሳሹ በአካባቢ ላይ ጉዳት እንዳያስከትል ተገቢነት ያላቸውን እርምጃዎች ወዲያውኑ መውሰድ ይኖርበታል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) የተመለከተው ሰው ግዴታውን ሳይወጣ ቀርቶ ሚኒስቴሩ ወይም በሚኒስቴሩ የተወከለ አካል ችግሩን ለማስወገድ ተገቢ እርምጃዎችን በመውሰዱ የወጣ ወጪ ቢኖር የመተካት ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል አራት

## የነዳጅ ወይም የነዳጅ ውጤቶች አቅርቦት ስራ

20.ደረጃዎችን ስለማሟላት

ለተጠቃሚዎች የሚከፋፈል ነዳጅ ወይም የነዳጅ ውጤት የአገሪቱን ደረጃዎችና መሥፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

21.ስለነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች ማጓጓዝ

ማንኛውም ነዳጅ ወይም የነዳጅ ውጤቶችን በማጓጓዝ ሥራ ላይ የሚውል ቦቴ ወይም የነዳጅ ማጓጓዣ ቧንቧ መሥመር ይህንኑ በሚመለከት የወጡ ደረጃዎችንና መሥፈርቶችን ማሟላት አለበት፡፡

22.የነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች አጠባበቅ

ማንኛውም ነዳጅ ወይም የነዳጅ ውጤት ለታሰበለት አገልግሎት ብቻ መዋል አለበት፡፡

23.የነዳጅ ውጤቶችን ከባዮ-ፊውል ስለመደባለቅ

የነዳጅ ውጤት ከባዮ-ፊውል እና ከሌላ የቴክኖሎጂ ውጤት ጋር ስለሚደባለቅበት ሁኔታ ሚኒስቴሩ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

24.መጠባበቂያ የነዳጅ ውጤቶች ስለመያዝ

በሀገር ውስጥ በበቂ ሁኔታ የነዳጅ ውጤቶች አቅርቦት አስተማማኝነትን ለማረጋገጥ ማንኛውም አከፋፋይ ከ500 ሜትር ኩብ ያላነሰ የመጠባበቂያ ክምችት መያዝ አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## ስለሚኒስቴሩ ስልጣንና ተግባር እና ስለቴክኒክ አማካሪ ኮሚቴ መቋቋም

### 25.የሚኒስቴሩ ስልጣንና ተግባር

ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በነዳጅና በነዳጅ ውጤቶች አቅርቦት ፖሊሲና ስትራቴጂ ነክ ጉዳይ ላይ መንግሥትን ያማክራል፤
2. ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች አቅርቦት ሰንሰለት ሥራዎችን በሚመለከት የሚቀርቡ የሕግና የቁጥጥር የውሳኔ ሃሳቦቸን ያስተባብራል፤
3. አግባብ ካለው አካል ጋር በመመካከር ከውጭ ወደሀገር ውስጥ የሚገቡ ወይም በሀገር ውስጥ የሚመረቱ ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶቹን የሚመለከት ዝርዝር የቴክኒክ መሥፈርትና የጥራት ቁጥጥር አሠራር እንዲወጣ በማድረግ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
4. የኅብረተሰቡን ጤንነትና ደህንነት ለመጠበቅና የአካባቢ ጥበቃን ለማረጋገጥ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር እየመረመረ ይፈቅዳል፤ በአቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ የሚከናወኑ ሥራዎችን የደህንነት ጥንቃቄ ያረጋግጣል፤
5. ለአስቸኳይ ጊዜ አቅርቦት የሚውል የነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች በቂ ክምችት በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል መያዙን እና በገበያ ውስጥ የነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች አቅርቦት በበቂ መጠን መኖሩን ያረጋግጣል፤
6. ከነዳጅና ከነዳጅ ውጤቶች አቅርቦት ጋር በተያያዘ ለአስተዳደራዊና ቁጥጥር ተግባራት አስፈላጊ የሆኑ ጥናቶችን ያካሂዳል ወይም እንዲካሄዱ ያደርጋል፤
7. በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦች መሠረት የኮንስትራክሽን ፈቃድ እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል ወይም ይሠርዛል፤
8. የነዳጅ አቅርቦት ሥራዎች ከቴክኒካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ አካባቢያዊና ደህንነት ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የሚያስከትሉትን ተፅእኖ በሚመለክት አስፈላጊ ቁጥጥርና ምርመራዎችን ያካሂዳል፤
9. ለሚሰጣቸው ፈቃዶችና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቶች ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ በሚወሰነው መሠረት የአገልግሎት ክፍያ ያስከፍላል፤

10. በዚሁ አዋጅ መሠረት አገልግሎቶችን ከሚሰጡ ሰዎች ጋር በተያያዘ የሥነ-ምግባር መመሪያ ያወጣል፣ መከበሩን ያረጋግጣል፤
11. ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ተግባራትን ያከናውናል፤
12. እንዳስፈላጊነቱ አግባብነት ላላቸው የክልል አካላት የሥልጣን ውክልና ይሰጣል፡፡

## 26. ስለ ቴክኒክ አማካሪ ኮሚቴ መቋቋም

1. ከነዳጅ አቅርቦት ሥራዎች ጋር በተያያዘ የሚያማክር የቴክኒክ ኮሚቴ (ከዚህ በኋላ "ኮሚቴ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. የኮሚቴው ተጠሪነት ለሚኒስትሩ ይሆናል፡፡

## 27. የኮሚቴው አባላት

የኮሚቴው አባላት ሰብሳቢውን ጨምሮ ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላትና የግሉ ዘርፍ ተውጣጥተው በመንግሥት ይሰየማሉ፤ ቁጥራቸውም እንዳስፈላጊነቱ ይወሰናል፡፡

## 28. የኮሚቴው ተግባር

ኮሚቴው፡-

1. ከነዳጅ አቅርቦት ሥራዎች እና ተያያዥ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ በሚኒስቴሩ ተጠንተውና ተዘጋጅተው የሚቀርቡለትን ፖሊሲዎች፣ ረቂቅ ሕጎችና የአፈፃፀም ሥልቶች ይመረምራል፣ በውይይት አዳብሮ የውሳኔ ሃሳቡን ለሚኒስትሩ ያቀርባል፤
2. ከነዳጅ አቅርቦት ሥራዎችና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ መወሰድ አለባቸው የሚላቸውን አዎንታዊ እርምጃዎች በሚመለከት ሚኒስትሩን ያማክራል፡

## 29. ስለኮሚቴው ስብሰባ

1. ኮሚቴው በዓመት ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፡፡ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።
2. በኮሚቴው ስብሰባ ላይ አብላጫ ቁጥር ያላቸው አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።
3. የኮሚቴው ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ኮሚቴው የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

30.**ቅጣት**

ማንኛውም በነዳጅ አቅርቦት ሠንሰለት ሥራ ውስጥ የተሠማራ ሰው ሕገወጥ ጥቅም ለማግኘት በይዞታው ሥር የሚገኝ የነዳጅ ውጤትን ከማንኛውም ሌላ ዝቅተኛ የጥራት ደረጃ ካለው የነዳጅ ውጤት ወይም ጠጣርም ሆነ ፈሳሽ ነገር ጋር ቀላቅሎ ቢገኝ በንግድ ውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 አግባብ ባላቸው ድንጋጌዎች መሠረት ይቀጣል፡፡

31.**ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።
2. ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

32.**ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

33.**የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

ይህ አዋጅ ከመፅናቱ በፊት በነዳጅ ውጤቶች አቅርቦት ሠንሰለት ውስጥ ተሠማርቶ የሚገኝ ማንኛውም ሰው የነዳጅ ተቋሙንና አሠራሩን ሚኒስቴሩ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና አዋጁን ለማስፈፀም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ማስተካከል አለበት፡፡

34.**አዋጁ የሚፀናበት ግዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ 9 ቀን 2006 ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## **አዋጅ ቁጥር 981/2008 ዓ.ም**

## **የጂኦተርማል ሀብት ልማት አዋጅ**

የጂኦተርማል ሀብት ተጠብቆና ለምቶ ለአገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጥቅም እንዲሁም ዕድገት መዋሉን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የጂኦተርማል ሀብት ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨትን ጨምሮ ለአገሪቱ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ላላቸው አገልግሎቶች መዋሉን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ የሚካሄዱ የጂኦተርማል ኃይል ማመንጨት ተግባራትን የሚደግፍ የሕግ እና የቁጥጥር ማዕቀፍ መኖር ለውጤታማ የጂኦተርማል ሀብት ልማትና ጥቅም ላይ መዋል አስፈላጊ በመሆኑ፤

የጂኦተርማል ሀብት ልማት እና ተግባራት ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ የሚመራ አዲስ ሕግ ማውጣት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት 55 (2) (ሀ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## **ክፍል አንድ**

## **ጠቅላላ**

1. **አጭር ርእስ**

   ይህ አዋጅ "የጂኦተርማል ሀብት ልማት አዋጅ ቁጥር 981/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

   1. "የጂኦተርማል ሥራ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጥ ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው ተግባራት ናቸው፤
   2. "የጂኦተርማል ሀብት" ማለት የማዕድንም ሆነ የውሃ ሀብት ወይም ቁሳዊ ንብረት ያልሆነ ነገር ግን ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የጂኦተርማል ኢነርጂ፣ የጂኦተርማል ተረፈ ምርትን እና የጂኦተርማል ፈሳሽን የሚያካትት ተፈጥሯዊ የመሬት ሙቀት ነው፤

3. “የጂኦተርማል ኢነርጂ” ማለት በማንኛውም ሁኔታ ከመሬት ገፀ-ምድር በታች የሚገኝ ሆኖ ከተፈጥሮአዊ የመሬት ሙቀት የተገኘ ወይም የተፈጠረ ወይም ከዚሁ የተፈጥሮ ሙቀት ውስጥ የወጣ ኢነርጂ ነው፤
4. “የጂኦተርማል ተረፈ-ምርት” ማለት ዘይት፣ የሃይድሮ ካርቦን ጋዝና ሂሊየምን ሳይጨምር በመጠን፣ በጥራት ወይም በቴክኒክ ረገድ ለማውጣት ወይም ለማምረት አስቸጋሪ በመሆኑ ምክንያት ራሳቸውን ችለው እንዳይወጡ ወይም እንዳይመረቱ በቂ ጠቀሜታ የሌላቸው ሆኖም ውህድ ሆኖ ወይም በጂኦተርማል እንፋሎት ውስጥ የሚገኙ ማንኛውም ማዕድን ነው፤
5. “የጂኦተርማል ፈሳሽ” ማለት ውሃ፣ ብራይንና እንፋሎትን አካቶ በሚገኝበት ከፍታ ወይም ጥልቀት ሙቀቱ ውሃ የሚፈላበት ደረጃ የደረሰም ይሁን ከዛ በላይ እንዲሁም ሙቀቱ የተገኘው በተፈጥሮም ይሁን በሪኢንጄክሽን ከጅኦተርማል ሀብት ጋር የተያያዘ ፈሳሽ ነው፤
6. “የጂኦተርማል ሀብት ክልል” ማለት ማንኛውም የጂኦተርማል ሀብት የተገኘበት ወይም የሀብቱ መገኛ እንደሆነ ታምኖ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በሕዝብ ማስታወቂያ የተሰየመ ማንኛውም መሬት ነው፤
7. “የንግድ ማህበር” ማለት በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፤
8. “ደረጃ I የጂኦተርማል ሀብት” ማለት የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት ብቃት ያለውና በዚያው አካባቢ እንደማሞቂያና የተቀናጀ ሙቀትና ኃይል የመሣሠሉ አገልግሎቶች መስጠት የሚችል ጂኦተርማል ሀብት ነው፤
9. “ደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት” ማለት የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨትን ሣይጨምር የሙቀት ኃይሉን በቀጥታ ጥቅም ላይ ለሚያውሉ አገልግሎቶች፣ ለግብርና እና ለኢንዱስትሪ፣ ለመዝናኛ ገላ መታጠቢያ እንዲሁም ለህክምናና ለመሣሠሉ ሌሎች አገልግሎቶች የሚውል የጂኦተርማል ሀብት ነው፤
10. “አግባብ ያለው አካል” ማለት ሐረጉ የተጠቀሰበት ድንጋጌ በሚመለከተው ጉዳይ ላይ በሕግ ኃላፊነት እና ሥልጣን የተሰጠው መንግሥታዊ አካል ነው፤
11. “አላቂ ዕቃዎች” ማለት ለጂኦተርማል ስራ የሚያስፈልጉና በጂኦተርማል ሥራው ወቅት በጥቅም ላይ የሚውሉ ወይም የሚተኩ ኬሚካሎች፣ ሲሚንቶን ጨምሮ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በመመሪያ አላቂ ዕቃዎች ብሎ የሚሰይማቸው ናቸው፤

12.“ሰነድ” ወይም “ሪከርድ” ማለት የኤሌክትሮኒክስ ጽሑፎችን ወይም ሪከርዶችን ጨምሮ ማንኛውም ጽሑፍ ወይም ሪከርድ ነው፤

13.“መቆፈር” ማለት ለጂኦተርማል ሥራ የሚደረግ የጉድጓድ ቁፋሮ ነው፤

14.“የምርመራ ፈቃድ” ማለት የጂኦተርማል ሀብት መኖሩንና የሀብቱን መጠንና የኢኮኖሚ ጥቅም ለማረጋገጥ ሲባል ጉድጓዶችን መቆፈርን እንዲሁም ለጉድጓድ ፍተሻ ሲባል የጂኦተርማል ፈሣሾችን መልቀቅን ጨምሮ ዝርዝር የጂኦሎጂ፣ የጂኦኬሚስትሪና የጂኦፊዚክስ ጥናቶችን በማከናወን የጂኦተርማል ሀብትን መጠን፣ አቀማመጥ፣ ባሕርያትና ወሰን ለማረጋገጥ የሚረዱ ሥራዎችን ለማካሄድ መብት የሚሠጥ ፈቃድ ሲሆን የአካባቢና ማህበረሰብ ተጽዕኖ፣ የሀብት መጠንና የአዋጭነት ጥናቶችን ማጥናትና ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን ማካሄድንም ይጨምራል፤

15.“ኮር” ማለት በቁፋሮ ከጉድጓድ የሚወሰድ ጠጣር የአለት ናሙና ነው፤

16.“ማመንጨት” ማለት በኢነርጂ አዋጅ የተሰጠው ትርጓሜ ይኖረዋል፤

17.“መንግሥት” ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ሲሆን እንደ አግባቡ ክልል መንግሥታትንም ይጨምራል፤

18.“የታወቀ የጂኦተርማል ሀብት ክልል” ማለት የታወቀ የጂኦተርማል ሀብት ክልል ተብሎ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በሕዝብ ማስታወቂያ የተሰየመ አካባቢ ነው፤

19. “መሬት” ማለት ከመሬት በታችም ይሁን በላይ የንብረት አገልግሎት መብት ወይም ጥቅም የተገኘበት በማንኛውም ዓይነት ይዞታ ሥር የሚገኝ መሬት ሲሆን በውሃ የተሸፈነ መሬትንም ያካትታል፤

20.“ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን” ማለት የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን ነው፤

21.“የሕዝብ ማስታወቂያ” ማለት ሰፊ ተደራሽነት ባለው መገናኛ ብዙሀን ወይም የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ዘዴ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተካተቱ መሠረታዊ ጉዳዮችን ይፋ ማድረግ ነው፤

22.“የቅኝት ፈቃድ” ማለት አንድ ቦታ የጂኦተርማል ሀብት ሊኖረው እንደሚችል ለማረጋገጥ ሲባል የጂኦሎጂ፣ የጂኦኬሚስትሪና የጂኦፊዚክስ ባሕርያቱን ለማጥናት የሚያስችሉና በአካባቢው ተፈጥሮ ላይ ተጽዕኖ የሌላቸውን የመሬት ላይ የምርመራ ሥራዎችን ለማካሄድ መብት የሚሠጥ ፈቃድ ሲሆን ጉድጓድ መቆፈርን አያካትትም፤

23.“ሪኢንጄክሽን” ማለት የጂኦተርማል ፈሳሽን በጉድጓድ አማካኝነት ከመሬት በታች መልሶ መጨመር ነው፤

24.“መሠረዝ” ማለት ባለፈቃዱ ፈቃዱን በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን አስገዳጅነት እንዲመልስ ማድረግ ነው፤

25.“መመለስ” ማለት በባለፈቃዱ በፈቃደኝነት ፈቃዱን ወይም ከፈቃዱ ክልል ውስጥ የተወሰነን ቦታ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን መመለስ ነው፤

26.“የሙቀት መለኪያ ጉድጓድ” ማለት የጂኦሳይንትፊክ ወይም ከሙቀት ጋር የተያያዘ መረጃ ለማግኘት ሲባል የሚቆፈር ማንኛውም ጉድጓድ ነው፤

27.“መቋረጥ” ማለት ከፈቃድ መሠረዝ፣ መነጠቅ ወይም መመለስ ጋር በተያያዙ ምክንያቶች ባለፈቃዱ የነበረው መብት ሲያበቃ ነው፤

28.“ማስተላለፍ” ማለት የጂኦተርማል ፈቃድ ወይም ከፈቃዱ ጋር ተያያዥ ሀብትን መሸጥ፣ በዕዳ ማስያዝ፣ ማውረስ፣ መዳረግ ወይም በሌላ መንገድ ባለቤትነትን ማስተላለፍ ነው፤

29.“ጉድጓድ” ማለት የጂኦተርማል ሀብት ለመፈለግ ወይም ለማምረት ወይም የጂኦተርማል ሀብቱን ሪኢንጀክት ለማድረግ ወይም ለመከታተል በማንኛውም መሬት ላይ ተቆፍሮ የተጠናቀቀ ጉድጓድ ነው፤

30.“የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድ” ማለት የጂኦተርማል የሀብት መጠንና የአዋጭነት ጥናቶችን ለማጥናት፣ ከፍተኛ ደረጃ የጂአሎጂ፣ የጂኦኬሚስትሪና የጂኦፊዚክስ ጥናቶችን ለማካሄድ፣ የምርት፣ የሪኢንጄክሽንና የክትትል ጉድጓዶችን ለመቆፈር፣ የእንፋሎት መስክን ለማልማት፣ የጂኦተርማል ሀብትን ከመሬት ሥር ለማውጣትና ለመጠቀም መብት የሚሠጥ ፈቃድ ነው፤

31.“የሥራ ፕሮግራም” ማለት ዝርዝሩ በዚህ አዋጅ እና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብና መመሪያ የሚወሰን ሆኖ የጂኦተርማል ቅኝት ፈቃድ እና የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድ ለመስጠት እንዲሁም የጀኦተርማል ምርመራ ፈቃድ ለመስጠት ወይም ለማደስ እንደቅድመ ሁኔታ መቅረብ ያለበት የሥራ ዝርዝር እና የወጪ ዕቅድ ነው፤

32.“ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ 47 (1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን፣ የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤

33.“ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

34.ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል ፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ግዛት ውስጥ በሚካሄዱ የጂኦተርማል ሀብት ልማት ሥራዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

4. <u>ዓላማ</u>

ይህ አዋጅ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1. የሀገሪቱ የጂኦተርማል ሀብት ሥርዐትና ዘላቂነት እንዲሁም የአካባቢ ጥበቃን ግምት ውስጥ ባስገባ ሁኔታ መልማቱን ማረጋገጥ፤
2. ከጂኦተርማል ኃይል ለአገር ውስጥ እና ለውጭ አገር ፍጆታ የሚውል ኤሌክትሪክ ማመንጨትንና ማቅረብን መደገፍ፤
3. የደረጃ II ጂኦተርማል ሀብትን ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች የሚውልበትን ሁኔታ ማራመድ፤
4. በጂኦተርማል ሀብት ልማት ሥራ ላይ የተሠማሩ ባለሀብቶች መብቶችን የማረጋገጥ፤ እና
5. በኢትዮጵያ ቀጣይነት ያለው ከካርቦን ነፃ የሆነ ኢኮኖሚን ማበረታታት፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለጂኦተርማል ሀብት ልማት ጠቅላላ ድንጋጌዎች

5. <u>ውጤታማ የመሬትና ሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም</u>

1. አዋጭና ከዚህ አዋጅ ጋር የሚስማማ እስከሆነ ድረስ ለጂኦተርማል ሀብት ልማት በሚሰጥ የፈቃድ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ከጂኦተርማል ፈቃዱ ጎን ለጎን ጥቅም ላይ እንዲዉሉ አግባብ ባለው አካል ሊወሰን ይችላል።

2. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የጂኦተርማል ሥራ በሚካሄድበት የፈቃድ ክልል ውስጥ ጂኦተርማልን የማይመለከቱ ሌሎች የልማት ሥራዎች ጎን ለጎን የሚካሄዱበትን አሠራር በተቻለ መጠን መደገፍ አለበት።

6. <u>የሀብት ጥበቃና ዘለቄታዊነት</u>

የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድ ያለው ባለፈቃድ ተገቢነት ያለውና ከአካባቢ ብክለት የጸዳ አሠራር የመከተል ግዴታ ያለበት ሲሆን የጂኦተርማል ሀብቱ ዘለቄታዊነት መጠበቁን ለማረጋገጥ ሲባል ከጂኦተርማል ኢንዱስትሪ ምርጥ አሠራርና ከጂኦተርማል ሀብቱ ባሕርያት ጋር የተጣጣመ መሆኑን በማረጋገጥ የጂኦተርማል ፈሣሾች ሪኢንጄክሽንን መተግበር አለበት።

7. <u>መሬትን ለጆኦተርማል ስራዎች ስለመከለል</u>

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማናቸውም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ መሬት ለጂኦተርማል ሥራዎች ክፍት ይሆናል፡፡
2. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን የሕዝብ ማስታወቂያ በማውጣት ማናቸውም መሬት የታወቀ የጂኦተርማል ክልል ነው ብሎ ሊሰይም ይችላል፡፡ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የታወቀ የጂአተርማል ክልልን መጠን እና ቅርጽን ለመወሰን ከሌሎች ሁኔታዎች በተጨማሪ፡-

   ሀ) እንዲከለል ሀሣብ የቀረበበትን አካባቢ የታወቀ የጂኦሎጂካል፣ ጂኦኬሚካል እና ጂኦፊዚካል ባህርያትን፤ እና

   ለ) የጂኦተርማል ሀብቱ የሚገኝበት መሬት በወቅቱ እየሰጠ ያለውንና ወደፊት ሊሰጥ የሚችለውን ሌላ ጠቀሜታ፣ ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

3. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን የሕዝብ ማስታወቂያ በማውጣት ማናቸውም መሬት የጂኦተርማል ስራ የማይካሄድበት ነው ብሎ መከለል ይችላል፡፡ ሆኖም ይህን የመሰለው ክልከላ በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ በተሰጠው ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰ ከሆነ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የመካስ መብት ይኖረዋል።
4. ማንኛውም ሰው ቀጥሎ በተዘረዘሩት ሥፍራዎች ላይ የጂኦተርማል ሥራዎች ፈቃድ አይሰጠውም፡-

   ሀ) ለመቃብርና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች በተከለሉ ሥፍራዎች፤

ለ) የቅድመ ታሪክ ቅሪቶች ባሉባቸው ወይም ብሔራዊ መታሰቢያዎች በቆሙባቸው ሥፍራዎች፤

ሐ) ለመሠረተ ልማት አውታሮች በተከለሉ ቦታዎች፤

መ) ለተፈጥሮ አካባቢ ጥበቃ ወይም ለብሔራዊ ፓርክ በተከለሉ ሥፍራዎች፤

ሠ) አግባብ ያለው አካል ካልፈቀደ በቀር ከመንደሮች፣ ከከተማዎች ወይም ከውኃ ማጠራቀሚያዎች ወይም ግድቦች በአምስት መቶ (500) ሜትር ክልል ውስጥ፤ እና

ረ) በሌላ ሕግ በተከለከሉ ቦታዎች፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው የሕዝብ ማስታወቂያ በሥራ ላይ በዋለበት ቀን ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ፈቃድ በተሰጠበት እና የፀና የኃይል ግዥ ስምምነት ባለው መሬት መጠንና ቅርጽ ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

6. መንግሥት ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ተገቢው የማካካሻ እርምጃ ተወስዶ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ወይም (4) መሠረት የተከለለ ማንኛውም ሥፍራ ለጂኦተርማል ሥራ ክፍት እንዲሆን ሊፈቅድ ይችላል፡፡

8. <u>በመንግስት ስለሚካሄድ የጂኦተርማል ስራ</u>

1. መንግሥት ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ እና ማኅበራዊ ዕድገት ወሳኝ ሚና የሚኖራቸውን የጂኦተርማል ሥራዎች በራሱ ወይም ከሌሎች ባለሀብቶች ጋር በቅንጅት ሊያካሂድ ይችላል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድን አወዳድሮ ለመስጠት የሚያስችለው በቂ መረጃ እንዲኖረው ለማስቻል መንግሥት የጂኦተርማል ሀብት ፍለጋ እና ልማት ሥራዎች ያካሂዳል።

9. <u>ስለ ጂኦተርማል ሀብት መዝገብ</u>

1. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የጂኦተርማል ሀብት መዝገብ አደራጅቶ ይይዛል፡፡

2. በጂኦተርማል ሀብት መዝገብ ውስጥ የፈቃድ ማመልከቻዎችና ፈቃድን ለመስጠት፣ ለመከልከል ወይም ለመሠረዝ የተሰጡ ውሳኔዎች፣ የይግባኝ ሪከርዶችና በዚህ አዋጅ፣ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብና መመሪያ የሚወሰኑ የጽሑፍ ሰነዶች ይመዘገባሉ፡፡

3. ከፈቃድ ጋር የተገናኙና በግል የተካሄዱ ግብይቶችን፣ ማስተላለፍን፣ በዕዳ መያዝን፣ በውርስ ማስተላለፍን የሚመለከቱ ሰነዶች ስምምነቱ ከተከናወነ ወይም ህጋዊነትን ካገኘ በኋላ ባሉት በዘጠና (90) ቀናት ውስጥ መብቱን ባገኘው ሰው አማካይነት ቀርበው መመዝገብ አለባቸው። ለምዝገባ በወቅቱ ያልቀረቡ ስምምነቶች በሕግ ፊት ዋጋ አይኖራቸውም።
4. የጂኦተርማል ሀብት መዝገብ ለሕዝብ ክፍት ይሆናል።

10.**ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ሰዎች ስለማሳወቅ**

1. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ መሠረት የቀረበለትን ማመልከቻ በጂኦተርማል ሀብት መዝገብ ከመዘገበ በኋላ ጥያቄ የቀረበበትን ቦታ የጂኦግራፊ ኮኦርድኔት በመጥቀስ ሰፊ ተደራሽነት ባለው የመገናኛ ብዙሃን አማካይነት ሦስተኛ ወገኖች እንዲያውቁት ያደርጋል፡፡
2. ፈቃድ እንዳይሠጥ ተቃውሞ የሚያቀርብ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ጥያቄ የቀረበበት ቦታ በመገናኛ ብዙሃን እንዲታወቅ በተደረገ በአሥራ አምስት (15) ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ያቀረበ እንደሆነ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በጉዳዩ ላይ በሚመለከታቸው ወገኖች መካከል ድርድር እንዲጀመር ያደርጋል።
3. ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች የቀረበውን ተቃውሞ አስመልክቶ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ድርድሩ እንዲጀመር ከወሰነበት ቀን ጀምሮ በስልሣ (60) ቀናት ውስጥ መስማማት ካልቻሉ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሁለቱንም ወገኖች ክርክር ካዳመጠ በኋላ በአሥራ አምስት (15) የሥራ ቀናት ውስጥ የቀረበውን ተቃውሞ የመቀበል ወይም ያለመቀበል ውሣኔ ይሰጣል፡፡

**ክፍል ሦስት**

**ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን**

11.**የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ስልጣንና ተግባር**

ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የጂኦተርማል ሀብት ልማት ኢንቨስትመንትን ለማሣደግ የሚረዱ ሁኔታዎችን የማመቻቸት፤

2. የጂኦተርማል ሀብት ልማትን የሚመለከቱ ተግባራት በዚህ አዋጅ፣ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መከናወናቸውን የማረጋገጥ፤
3. የጂኦተርማል ሀብት ልማትን በማሳደግ እና ባለፈቃዶች ኃላፊነቶቻቸውን እንዲወጡ በማድረግ መካከል የሚኖርን ወይም ሊከሰት የሚችል የጥቅም ግጭትን ለማስወገድ ተገቢ እርምጃ የመውሰድ፤
4. በደረጃ I እና ደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ላይ የጂኦተርማል ሥራ ፈቃዶችን የመስጠት ወይም የመከልከል የተሰጡ ፈቃዶችን የማደስ፣ የማገድ፣ የማራዘም እና የመሠረዝ፤
5. ለጂኦተርማል ዘርፍ የማማከር አገልግሎት ሥራ እና ለጂኦተርማል ቴክኒክ ነክ ሥራ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመስጠት፤
6. የጂኦተርማል ፈሳሽና ተያያዥ ውጤቶች ወደ ውጪ እንዲላኩ ፈቃድ የመስጠት ወይም የመከልከል፤
7. አግባብ ካለው አካል ጋር በመመካከር የጂኦተርማል ተረፈ ምርት ጥቅም ላይ እንዲውል ወይም እንዲሸጥ የመፍቀድ፤
8. የፈቃድ ክልል በጨረታ ወይም በማመልከቻ የሚሰጥበትን ሁኔታ የመወሰን፤
9. በዚህ አዋጅ መሠረት ማንኛውም ባለፈቃድ በፈቃዱ የተመለከቱ ግዴታዎችን ለመወጣት አስፈላጊው የገንዘብ ምንጭ፣ የቴክኒክ ብቃትና ልምድ ያለው መሆኑን የማረጋገጥ፤
10. አንድን አካባቢ የታወቀ የጂኦተርማል ሀብት መገኛ ክልል ብሎ የመሰየም፤
11. በዚህ አዋጅ እና በዚህ አዋጅ መሠረት በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተመለከቱ መረጃዎችን እና ሪከርዶችን የመቀበል፤
12. የጂኦተርማል ሥራዎች በዚህ አዋጅ፣ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ፣ መመሪያና አግባብ ባላቸው ስምምነቶች መሠረት መካሄዳቸውን የመቆጣጠርና የማረጋገጥ፤
13. በመንግሥት በሚወጣ ተመን መሠረት የፈቃድና ሌሎች ክፍያዎችን የመሰብሰብ፤

14. አግባብ ካለው አካል ጋር በመተባበር የጂኦተርማል ሥራዎች ከኢትዮጵያ የአካባቢ፣ የጤና እና የደህንነት ሕግጋት ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን የማረጋገጥ፤
15. ከጂኦተርማል ሥራ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የጤናና የደህንነት ደረጃዎችን፣ የጉድጓድ ቁፋሮ ኮዶችን፣ የቁጥጥር መመሪያዎችንና ሌሎች መሰል ኮዶችን የማውጣትና አፈፃፀማቸውንም የመቆጣጠር፤
16. ይህን አዋጅ ለማስፈፀም አግባብ ካላቸው አካላት ጋር የመተባበር፡፡

## ክፍል አራት

## ስለፈቃዶች እና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቶች

### 12. የፈቃድ አስፈላጊነት

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ተገቢውን ፈቃድ ከፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሳያገኝ የጂኦተርማል ሥራ ማካሄድ አይችልም።

### 13. የፈቃድ ዓይነቶች

1. ማንኛውም አመልካች በዚህ አዋጅ፣ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብና መመሪያ መሠረት ፈቃድ ለማግኘት የሚያስፈልጉ ሁኔታዎችን ካሟላ የሚከተሉት የጂኦተርማል ሥራ ማካሄድ የሚያስችሉ ፈቃዶችን በደረጃ I የጂኦተርማል ሀብት ላይ ሊሰጡት ይችላሉ፦

   ሀ) የቅኝት ፈቃድ፤

   ለ) የምርመራ ፈቃድ፤ እና

   ሐ) የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድ፡፡
2. በደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ላይ የጂኦተርማል ሥራ ፈቃድ የሚሰጥበት ሁኔታ እና ዝርዝር ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብና መመሪያ ይወሰናል፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ክልሎች ሙቀቱ ከአንድ መቶ ሀያ (120) ዲግሪ ሴንቲግሬድ በማይበልጥ እና መጠኑ በዓመት ከሁለት ሚሊዮን (2 ሚሊዮን) ሜትር ኪዩብ በማይበልጥ የደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ላይ የጂኦተርማል ሥራ ፈቃድ ይሰጣሉ።

### 14. የቅኝት ፈቃድ

1. የቅኝት ፈቃድ የብቻ የሆነ መብት የማያስገኝና ያለውድድር የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡

2. የቅኝት ፈቃድ በፈቃዱ ላይ ለተገለፀው ጊዜ ፀንቶ ይቆያል፣ ሆኖም ይህ ጊዜ ከሃያ አራት (24) ወር በላይ ሊሆን አይችልም።
3. የቅኝት ፈቃድ አይታደስም፡፡
4. የቅኝት ፈቃድ ያዥ የቅኝት ክልል በምርመራና በጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድ ሥር ያልተያዘ ከሆነ እና በዚህ አዋጅ፣ ይህን እዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብና መመሪያ የተገለፁ አስፈላጊ መስፈርቶችን የሚያሟላ ከሆነ የምርመራ ፈቃድ እንዲሰጠው ሊያመለከት ይችላል፡፡
5. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የቅኝት ፈቃድ ሥር የነበረን ክልል በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ለሌላ ሰው የምርመራ ወይም የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድ የሰጠ ከሆነ ይህንኑ ለቅኝት ፈቃድ ያገኙ ማስታወቅ አለበት፡፡

15.<u>**የምርመራ ፍቃድ**</u>

1. የብቻ የሆነ መብት የሚያስገኝ የምርመራ ፈቃድ የሚሰጠው፡-
   ሀ) በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ተቀባይነት ያገኘ የሥራ ዕቅድ አና የአካባቢና የማኅበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት ላቀረበ፤
   ለ) የታሰበውን የምርመራ ሥራ በቀረበው የሥራ ፕሮግራም መሠረት ለማከናወን የሚያስችል የገንዘብ አቅም ያለው ወይም ለማግኘት የሚችል መሆኑን እና አስፈላጊው የቴክኒክ ችሎታ ያለው መሆኑን ላረጋገጠ፤
   ሐ) ከዚህ በፊት የጂኦተርማል ሥራ ፈቃድ የነበረው ከሆነ የዚህኑ ፈቃድ ግዴታዎች ላልጣሰ አመልካች ይሆናል፡፡
2. የምርመራ ፈቃድ በፈቃዱ ላይ ለተገለፀው ጊዜ ፀንቶ ይቆያል፤ ሆኖም ይህ ጊዜ ከአምስት (5) ዓመት በላይ ሊሆን አይችልም።
3. የምርመራ ፈቃድ እያንዳንዱ ከአንድ (1) ዓመት ለማይበልጥ ለሁለት ጊዜ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ተቀባይነት ሲያገኝ ሊታደስ ይችላል፤ ሆኖም ለሁለተኛ ጊዜ የታደሰ የምርመራ ፈቃድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ እንዳበቃ ይሠረዛል፡፡
4. ባለፈቃዱ በፈቃዱ የተመለከቱትን ግዴታዎች አሟልቶ ከፈፀመ፣ ለዕድሳት የሚጠየቁ ተፈላጊ ሁኔታዎችን ካሟላና ይህን አዋጅ፣ አዋጁን ተከትለው የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን ድንጋጌዎች በመተላለፍ ፈቃዱን ለማገድ ወይም

ለመሠረዝ የሚያበቃ ጥፋት ካልፈፀመ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት መንግሥት ፈቃዱን ሊያድስለት ይችላል፡፡

16.<u>የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድ</u>

1. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የብቻ የሆነ መብት የሚያስገኝ የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድ የሚሰጠው የሚከተሉትን ሁኔታዎች ለሚያሟላ አመልካች ይሆናል፦
   ሀ) በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ተቀባይነት ያገኘ የሥራ ዕቅድ፣ የአዋጭነት ጥናትና የአካባቢ እና የማኅበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት ላቀረበ፤
   ለ) ሕጋዊ የኃይል ግዥ ስምምነት ላለው፤
   ሐ) የታሰበውን ሥራ በቀረበው የሥራ ፕሮግራም መሠረት ለማከናወን የሚያስችል የገንዘብ አቅምና አስፈላጊው የቴክኒክ ችሎታ ያለው ወይም ለማግኘት የሚችል መሆኑን ላረጋገጠ፤
   መ) ከዚህ በፊት የጂኦተርማል ሥራ ፈቃድ የነበረው ከሆነ የዚህኑ ፈቃድ ግዴታዎች ላልጣሰ፡፡
2. የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድ በፈቃዱ ላይ ለተገለፀው ጊዜ ፀንቶ ይቆያል፤ ሆኖም ይህ ጊዜ ከሃያ አምስት (25) ዓመት በላይ ሊሆን አይችልም።
3. የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ ሲያበቃ መንግሥት በሚመቸው መንገድ የጂኦተርማል ሀብት ልማቱን ሊያስቀጥል ይችላል፡፡
4. የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ባለፈቃድ በደረጃ I ጂኦተርማል ሀብት ላይ የኃይል ማመንጨት ተግባርን ብቻ የማካሄድ ወይም በተጓዳኝ ጥቅም ላይ የዋለ የጂኦተርማል ሀብትን ለራሱ የመጠቀም ወይም በሽያጭ መንግስት እንዲጠቀምበት የማድረግ መብት አለው፡፡
5. አግባብነት ያላቸውን የኢነርጂ ሕግ ድንጋጌዎች የሚያሟላና በደረጃ I ጂአተርማል ሀብት ላይ የኃይል ማመንጨት ተግባር ለማካሄድ ብቁ የሆነ የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ባለፈቃድ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማመልከቻ ሲያቀርብ ኤሌክትሪክ ለማመንጨት ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

6. በደረጃ I የጂኦተርማል ሀብት ላይ የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ባለፈቃድ በሀገሪቱ የኢነርጂ እና የኢንቬስትመንት ሕግ መሠረት ከጂኦተርማል ሀብት ኤሌክትሪክ የማመንጨት እና ያመነጨውን ኤሌክትሪክ አግባብ ላለው አካል የመሸጥ ግዴታ አለበት፡፡

17. <u>ፈቃድን በውድድር ስለመስጠት</u>

1. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሙከራ ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራዎች ተከናውነውና የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድ ለመስጠት በሚያስችል ደረጃ የጂኦተርማል ሀብት መኖሩ የተረጋገጠ የታወቀ የጂኦተርማል ሀብት ክልልን በማወዳደር የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡
2. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የተወሰነን ክልል የሚመለከት የምርመራ ፈቃድ ማመልከቻ የቀረበለት እንደሆነ የሕዝብ ማስታወቂያ በማውጣት ፍላጎት የላቸው ሌሎች ሰዎች የሕዝብ ማስታወቂያው በወጣ በሠላሳ (30) ቀን ውስጥ ማመልከቻ ለቀረበበት ቦታ የቴክኒክ ብቃትንና የገንዘብ አቅምን በመመዘኛነት በመጠ ቀም እንዲወዳደሩ መጋበዝ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማመልከቻ ያልቀረበለት እንደሆነ በቅድሚያ የተቀበለውን ማመልከቻ ያስተናግዳል።

18. <u>ስለማመልከቻ ሥነ-ሥርዓት</u>

ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርቡ ማመልከቻዎች በፍጥነትና በብቃት የሚስተናገዱበትን ሁኔታ ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሥነ-ሥርዓቶች፣ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎችና የጊዜ ገደቦች ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ይወሰናሉ።

19. <u>ፈቃድ ለማግኘት ብቁ ስላለመሆን</u>

1. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 13 (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ፈቃድ ማግኘት አይችሉም፦
   ሀ) ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት መክሠሩ የተረጋገጠ ማንኛውም ሰው፤
   ለ) የማፍረሱ ሂደት የንግድ ማኅበሩን እንደገና ለማቋቋም ወይም ከሌላ ኩባንያ ጋር ለማዋሃድ እስካልሆነ ድረስ በመፍረስ ላይ ያለ የንግድ ማኅበር፤

ሐ) ከማመልከቻው ጋር የተሳሳተ መረጃ ሆን ብሎ ያቀረበ ወይም ማመልከቻውን አስመልክቶ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ለሚሰጠው ውሣኔ አስፈላጊ የሆነ መረጃ ሆን ብሎ ያላቀረበ ሰው፤

መ) ቀድሞ ፈቃድ የነበረው ከሆነ የተሳሳተ መረጃ ሆን ብሎ ያቀረበ ወይም ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ለሚያካሂደው የሪፖርት ግምገማ አስፈላጊ የሆነ መረጃ ሆን ብሎ ያላቀረበ ሰው።

2. በማጭበርበር ወይም ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን አስፈላጊ የሆነ መረጃን ሆን ብሎ ባለማቅረብ ፈቃዱ የተሠረዘበት ባለፈቃድ ፈቃዱ ከተሠረዘበት ቀን አንስቶ ለአሥር (10) ዓመታት ማንኛውንም ዓይነት ፈቃድ ማግኘት አይችልም።

20.<u>ስለስራ ፕሮግራም</u>

1. ማንኛውም ዓይነት ፈቃድ እንዲሰጠው የሚያመለከት ሰው ከማመልከቻው ጋር የሥራ ፕሮግራሙን፣ በጀቱን እና በፈቃዱ የተሸፈኑ ተግባራትን የሚመለከቱ ዝርዝር ሥራዎችን የያዘ የሥራ ፕሮግራም ማቅረብ አለበት፡፡

2. ባለፈቃዱ በጀትን ጨምሮ ተቀባይነት አግኝቶ የነበረውን የሥራ ፕሮግራም በማንኛውም ጊዜ ለመለወጥ ለፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን ማመልከት ይችላል፡፡

3. በማንኛውም የሥራ ፕሮግራም ላይ ለውጥ ለማድረግ የሚቀርብ ማመልከቻ፡-

ሀ) ተቀባይነት አግኝቶ የነበረውን የሥራ ፕሮግራም ለመተግበር ያላስቻሉትን ክስተቶች ወይም የባለፈቃዱን የቀድሞ ሥራ ፕሮግራም መሠረት በማድረግ ለውጡ ያስፈለገበትን የቴክኒክና የፋይናንስ ምክንያቶችን ለይቶ ማሳየት እና መሠረታዊ ለውጥ የሚደረግ ከሆነም አሳማኝ ምክንያቶችን ማቅረብ፤ እና

ለ) የታሰበውን የሥራ ፕሮግራም ማሻሻያና በጀት መያዝና የሚከፈል ክፍያ ካለ መከፈል አለበት፡፡

4. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሥራ ፕሮግራም ለውጥ ለማድረግ ማመልከቻ በቀረበ በአሥር (10) ቀን ውስጥ፦

ሀ) ተሻሽሎ የቀረበው የሥራ ፕሮግራም አሳማኝ ሆኖ ከተገኘ ተቀብሎ ያፀድቀዋል፤ ወይም

ለ) የሥራ ፕሮግራም ለውጥ ለማድረግ የቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ካደረገው ለውሣኔው ምክንያት የሆኑትን ጉዳዮች በመዘርዘር ለአመልካቹ በጽሑፍ ያሳውቃል።

## 21.ስለባለፈቃዶች አጠቃላይ መብቶች

በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች የተመለከቱት መብቶች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ አዋጅ የተመለከቱ ተግባራትን ለማከናወን አስፈላጊ እስከሆኑና በፈቃዱ ላይ የተደረጉ ማናቸውም ገደቦች እንደተጠበቁ ሆኖ የፈቃዱ ጊዜ እስከሚያበቃ ድረስና ተፈጻሚነት ያላቸው ሌሎች ሕጎችን መሠረት በማድረግ ባለፈቃዱ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-

1. በጀትን ጨምሮ ተቀባይነትን ባገኘ የሥራ ዕቅድ መሠረት በፈቃዱ የተዘረዘሩ የጂኦተርማል ሥራዎችንና እነዚህኑ ሥራዎች ለመሥራት አስፈላጊ የሆኑ ማናቸውንም ተግባራት ለማከናወን ወደ ፈቃድ ክልል የመግባት፤
2. በሥራ ዕቅዱ መሠረት ወደ ፈቃድ ክልሉ ሠራተኞችንና ሥራዎቹን ለማካሄድ አስፈላጊ የሆኑ ፋብሪካዎችን፣ ማሽነሪዎችንና መሣሪያዎችን የማስገባት፤
3. አግባብነት ያላቸው የውሃ ሀብት ሕጎችና የተፋሰስ ዕቅዶችን በማክበር፣ የተሻሉ የአሠራር ልምዶች፣ የጤናና ደህንነት ደንቦችና መመሪያዎች በማክበር ለሥራው አስፈላጊ የሆነ ውሃን በፈቃድ ክልሉ ውስጥ ከሚገኝ የገፀ-ምድር፣ የከርሠ-ምድር ወይም አቋርጦ ከሚያልፍ ከማንኛውም የውሃ አካል የመጠቀም ወይም የውሃ ጉድጓድ የመቆፈር፤
4. የጂኦተርማል ሥራ ለማካሄድ አስፈላጊ የሆኑ ከመሬት በላይ ወይም በመሬት ሥር የሚዘረጉ መሠረተ ልማቶችን የመዘርጋትና የመገንባት እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ ፋብሪካዎችንና ማሽነሪዎችን መትከል ሕንፃዎችንና ሌሎች ግንባታዎችን የማካሄድ እና የማደስ፤
5. በፈቃድ ክልሉ ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ መሠረተ ልማቶችን ለመዘርጋት በፍቃድ ክልሉ በሚገኙ የግንባታ ማዕድናት የመጠቀም፤
6. ማንኛውንም የጂኦተርማል ፈሳሽ የመያዝና የመጠቀም፤
7. አግባብነት ያላቸው የውሀ ሀብት ሕጎችን፣ የተፋሰስ ዕቅዶችንና ተያያዥነት ያላቸውን የአካባቢ ጥበቃ ሕጎችን በማክበር ጥቅም ላይ የዋለ ውሃን የማስወገድ፤
8. የደን ውጤቶችን ስለመቁረጥና በምትካቸው ችግኞችን ስለመትከል የወጡ አግባብ ያላቸው ሕጎችን በማክበር በፈቃድ ክልሉ ውስጥ ለጂአተርማል ሥራው ብቻ አስፈላጊ የሆኑ የደን ውጤቶችን የመቁረጥና የመጠቀም፤

9. ሌሎች ሰዎች እንዳይገለገሉባቸው መሰናክል በማይፈጥር ሁኔታ በነባር መንገዶች፣ ድልድዮችና የመሠረተ ልማት አውታሮች የመገልገል፤
10. በፈቃዱ መሠረት መሬቱን ጥቅም ላይ ለማዋልና ወደ ፈቃድ ክልሉ ለመግባት የሚያስፈልጉ መጋቢ መንገዶችን፣ ድልድዮችንና ሌሎች የመገናኛ ዘዴዎችን የአካባቢ ዕቅድንና የግንባታ ደረጃን ጠብቆ የመገንባትና የማደስ፤
11. አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎችና መመሪያዎች በማክበር ለጂኦተርማል ሥራው አስፈላጊ የሆኑ ጉድጓዶችን የመቆፈርና የመገንባት፤
12. ለራሱና ለሠራተኞቹ መኖሪያ የሚያገለግሉ ጊዜያዊ ቤቶች ግንባታዎችን የማካሄድ፣ የመገንባትና የመጠገን እና እነዚህን ቤቶችና ግንባታዎች የመተው፤
13. ጂኦተርማል ፈቃድ ለመስጠት መሟላት ካለባቸው ሁኔታዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ በደረጃ I የጂኦተርማል ሀብት ላይ ከማመንጫ ተቋም የሚወጣ የጂኦተርማል ፍሳሽን ለኤሌክትሪክ አገልግሎት ላልሆነ ተግባር በፈቃድ ክልሉ ውስጥ ወይም በፈቃዱ ክልል አካባቢ የመጠቀም ወይም የመሸጥ፤
14. ባለፈቃዱ የውጭ ባለሀብት ሲሆን በኢትዮጵያ ተቀባይነት ባለው የሂሣብ አሠራር መሠረት እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ መሠረት የውጭ ምንዛሪ የባንክ ሂሣብ የመያዝ።

22. <u>ስለባለፈቃዶች አጠቃላይ ግዴታዎች</u>

1. በዚህ አዋጅ እና አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተመለከተ ሌሎች ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ባለፈቃዱ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-
   ሀ) የጂኦተርማል ሥራውን ተገቢ በሆኑ ሕጎች፣ ቴክኖሎጂና ለጂኦተርማል ሥራ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ባገኘ የአሠራር ልምድ መሠረት የማካሄድ፤
   ለ) የወኪሎቹን፣ የሠራተኞቹንና የሌሎች ሰዎችን ጤንነትና ደህንነት በሚያረጋግጥና በተፈጥሮ አካባቢ ላይ የሚደርስ ጉዳትን ወይም ብክላን መከላከል በሚያስችል ሁኔታ ሥራውን የማከናወን፤
   ሐ) ለጂኦተርማል ሥራው አስፈላጊ የሆነና በጂኦተርማል ኢንዱስትሪ ተቀባይነት ባገኘ የአሠራር ልምድ መሠረት ሁሉም ሠራተኞች ትምህርትና ሥልጠና ያገኙ መሆናቸውን የማረጋገጥ፤
   መ) በፈቃዱ ክልልና አዋሳኝ በሆነ መሬት ላይ ሕጋዊ የይዞታ መብት ያላቸውን ሰዎች ላለማወክ ተገቢውን ጥንቃቄ የመውሰድ፤

ሠ) በፈቃድ ክልሉ ከሌሎች ሰዎች ጋር በጋራ ለሚጠቀምባቸው እንደ መንገድ የመሳሰሉ ልማቶች ግንባታና ጥገናን በሚመለከት በተጠቃሚዎቹ የነፍስ ወከፍ የአገልግሎት መጠን ላይ ተመሥርቶ በሚደርስ ስምምነት መሠረት ገንዘብ የማዋጣት፤

ረ) በጂኦተርማል ሥራው ላይ እንቅፋት የማይፈጥርበት እስከሆነ ድረስ በዘረጋቸው የመንገዶችና የድልድዮች መሠረተ ልማቶች ሌሎች ሰዎች በነፃ እንዲጠቀሙ የመፍቀድ፤

ሰ) ድንገተኛ ሁኔታ ሲፈጠር፣ ለሚደርሰው ብልሽት ብቻ ካሣ በማስከፈል መንግሥት ወይም ሌሎች ሰዎች በመንገዱ በሕንጻው፣ በመገናኛ መሳሪያዎቹ በመሳሰሉ መሠረተ ልማቶች በጊዜያዊነት እንዲገለገሉ የመፍቀድ፤

ሸ) ተፈላጊው ችሎታ ላላቸው ኢትዮጵያውያን የቅጥር ቅድሚያ የመስጠት፤

ቀ) በዋጋቸው ተወዳዳሪና በጥራታቸው ተመጣጣኝ ደረጃ ያላቸው እንደልብ ለሚገኙ የሀገር ውስጥ ዕቃዎች ግዥና አገልግሎቶች ቅድሚያ የመስጠት፤

በ) በዚህ አዋጅ፣ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብና መመሪያ መሠረት የሚፈለግበትን ማናቸውንም ክፍያ በወቅቱ የመክፈል፤

ተ) ፈቃዱንና የሥራ ፕሮግራሙን የሚመለከቱ ማናቸውንም ሁኔታዎች የማክበር፤

ቸ) መዛግብቶችንና ሪከርዶችን ጨምሮ አግባብነት ያላቸውን ሰነዶች በሙሉ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ወይም በሌላ ሕግ ሥልጣን በተሰጣቸው እንዲመረመሩ የማቅረብ፤

ኀ) የሰውን ጤና እና ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ድንገተኛ ሁኔታ ሲፈጠር መንግሥት ወደ ቦታው ገብቶ አስፈላጊውን እንዲፈጽም የመፍቀድ፤

ነ) በአካባቢና በኅብረተሰቡ ላይ የሚደርስ ተፅዕኖን የመቀነስና እንዲሁም ተገቢ ሆኖ ሲገኝ ተቀባይነት ባገኘው የአካባቢና የኅብረተሰብ ላይ የሚደርስ ተፅዕኖ መቀነሻ ዕቅድ መሠረት እርምጃ የመውሰድ፤

ኘ) የጂኦተርማል ሥራ ፈቃድ ሲያበቃ፣ ሲቋረጥ ወይም የፈቃድ ክልሉን በራሱ ፈቃድ ሲለቅ በፈቃድና በኪራይ ተይዞ በነበረው ቦታ የሚገኙ ጉድጓዶችና ሌሎች ሥራዎች በሰዎች ጤንነት፣ ሕይወትና ንብረት ላይ አደጋ እንዳያስከትሉ ተቀባይነት ባገኘው የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ግምገማ መሠረት

ማጠር፣ ግንባታዎች ማንሳት፣ የቆፈራቸውን ጉድጓዶች በአግባቡ በመድፈን የመተው እና መከላከያ የማበጀት፤

አ) አግባብ ባለው አካል ዘንድ በንግድ መዝገብ ላይ የመመዝገብና ለፈቃዱ ዘመን በኢትዮጵያ ውስጥ ጽሕፈት ቤት የማቋቋም፤

ከ) በሚመለከተው ክልል ህግ መሠረት ለፈቃድ ክልሉና በኪራይ ለያዘው መሬት በየዓመቱ በቅድሚያ ክፍያ መክፈል።

2. ባለፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ኘ) መሠረት ያላነሳቸውን ግንባታዎች መንግሥት ያለምንም ክፍያ የራሱ ንብረት ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡

23.<u>የፈቃድ ክልል ወሰን</u>

1. የታወቀ የጂኦተርማል ክልል መጠንና ድንበር በፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ይወሰናል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና የዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ከታወቀ የጂኦተርማል ክልል ውጭ የሚገኝ የጂኦተርማል ክልልን የሚመለከት ፈቃድ ለመስጠት በግሎባል ፖዚሽንንግ ሲስተም (በጂ.ፒ.ኤስ) ኮኦርድኔት የሚገለጹ የማዕዘን ነጥብ ባሉት አንድ የጂኦሜትሪ ቅርጽ የወሰን መስመሮች ውስጥ የተወሰነ የቦታ መጠን የሚኖረው ሆኖ፡-

ሀ) ለቅኝት ፈቃድ ሲሆን ከሁለት ሺህ (2000) ስኩዌር ኪሎ ሜትር የማይበልጥ፤

ለ) ለምርመራ ፈቃድ ሲሆን ከሁለት መቶ (200) ስኩዌር ኪሎ ሜትር የማይበልጥ ሆኖ፣ አንድ ሰው እስከ ሁለት ፈቃድ ብቻ፤ ወይም

ሐ) ለጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድ ሲሆን ከሃምሳ (50) ስኩዌር ኪሎ ሜትር የማይበልጥ የጂኦተርማል ሀብት ክልል ሊፈቀድ ይችላል፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ዝርዝር አፈፃፀም አዋጁን ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

24.<u>የሌሎች አገልግሎቶች ፈቃድ ስለመደረብ</u>

አግባብነት ያለው አካል ከፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ጋር በመመካከርና ለአገሪቱ የሚያስገኘውን የኢኮኖሚ ጥቅምና በነባር ባለፈቃድ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ተፅዕኖ በተመለከተ አመልካቹ ያካሄደውን ጥናት ግምት ውስጥ በማስገባት፣

እንዲሁም ነባሩን ባለፈቃድ በቅድሚያ በማሳወቅና በሥራዎቹና በአፈጻጸሙ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አለማሣረፋቸውን አረጋግጦ በተመሳሳይ የፈቃድ ክልል ውስጥ ለሌሎች አገልግሎቶች ፈቃድ ደርቦ ሊሰጥ ይችላል፡፡

25.<u>ስለፈቃድ ቀዳሚነት</u>

1. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የጂኦተርማል ሀብቱን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ወይም ሌሎች አግባብ ያላቸውን የኢንቨስትመንት ዓላማዎች መሠረት በማድረግ በሌላ አኳኋን ካልወሰነ በቀር ፈቃድ በመስጠት ሂደት በደረጃ I የጂኦተርማል ሀብት ላይ የጂኦተርማል ሥራ ፈቃድ መሰጠት በደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ላይ በሚሰጥ የጂኦተርማል ሥራ ፈቃድ ላይ ቀዳሚነት ይኖረዋል።
2. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የጂኦተርማል ሀብቱን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ወይም ሌሎች አግባብ ያላቸውን የኢንቨስትመንት ዓላማዎች መሠረት በማድረግ በሌላ አኳኋን ካልወሰነ በቀር ፈቃድ በመስጠት ሂደት የምርመራ ፈቃድ በቅኝት ፈቃድ ላይ እና የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድ በምርመራና በቅኝት ፈቃድ ላይ ቀዳሚነት ይኖረዋል።
3. ፈቃድ በተሰጠበት ክልል በተደራቢ የተሰጠ ፈቃድ ቢኖር በክርክር ላይ ያለው የጂኦተርማል ሀብት ፈቃድ ክልል በቀዳሚው ባለፈቃድ ይዞታ ሥር እንዳለ ሆኖ ይቆጠራል።

26.<u>ፈቃድ ስለማስተላፍ</u>

1. ከቅኝት ፈቃድ በስተቀር ማንኛውም ፈቃድ የያዘ ባለፈቃድ በቅድሚያ የፈቃድ ሰጪውን ባለሥልጣን የጽሑፍ ስምምነት በማግኘትና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ የተመለከተ የፈቃድ ማስተላለፍ ክፍያ በመፈፀም ፈቃዱን ለሌላ ሰው ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡
2. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማንኛውንም ፈቃድ እንዲተላለፍ ከመፈቀዱ በፊት ፈቃድ እንዲተላለፍለት የሚፈልገው ሰው አስፈላጊው የገንዘብ አቅም፣ የቴክኒክ ችሎታና ልምድ ያለውና በማንኛውም ፈቃድ ሥር ያሉ ግዴታዎችንና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ በደንብና በመመሪያ የተዘረዘሩ ሌሎች መሥፈርቶችን የሚያሟላ ስለመሆኑ ማረጋገጥ አለበት፡፡

3. ከፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በቅድሚያ ስምምነት ካልተገኘ በስተቀር ፈቃዱ የሚተላለፍባቸው ሰነዶች የሚከተሉትን የስምምነት ድንጋጌዎች ማካተት አለባቸው፡-
   ሀ) ያለምንም ልዩነት ፈቃዱ የሚመለከተው ክልልና የፈቃዱ ሁኔታዎች በአጠቃላይ የሚተላለፉ መሆኑን፣ እና
   ለ) ፈቃዱ የሚተላለፍለት ሰው ተቀባይነት ባገኘው የሥራ ፕሮግራም መሠረት ለመፈፀም የተስማማ መሆኑን።
4. በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 19 (1) እና (2) ለተመለከተ ሰው ማንኛውም ዓይነት ፈቃድ አይተላለፍም፡፡
5. በሚተላለፍ ፈቃድ ሥር ያለ ማንኛውም መብት በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ተቀባይነት አግኝቶ ካልተመዘገበ በቀር ፈቃዱ ተላልፏል ለተባለለት ሰው የሚያስገኘው ሕጋዊ ውጤት አይኖረውም፡፡

27.<u>መብትን ስለመተው</u>

1. ባለፈቃዱ ፈቃዱን ወይም የፈቃድ ክልሉን የትኛውንም ክፍል በቅድሚያ ፈቃድ ሰጪውን ባለሥልጣን በጽሑፍ በማሳወቅ መተው ይችላል፡፡ ሆኖም መብቱን በራሱ ፍላጎት ከተወ በኋላም የለቀቀውን ቦታ ቀድሞ ወደነበረበት ሁኔታ የመመለስ ወይም በራሱ ተግባራት ምክንያት የተከሰቱ ብክለቶችን የማስወገድ ወይም ለዚህ ተግባር የሚውል ዋስትና ወይም ገንዘብ የማስያዝ የመሟሠሉት ግዴታዎች አሉበት።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የፈቃድ ወይም የኪራይ መብቱን የተወ ማንኛውም ሰው ፈቃዱ ወይም የኪራይ ውሉ ፀንቶ ለቆየበት ጊዜ የሚያስከትላቸውን ግዴታዎች ከመፈፀም ነፃ አይሆንም።

28.<u>መረጃዎችን ስለመግለጽ</u>

1. የአዕምሯዊ ንብረት ባለቤትነት መብት እንዳለው ወይም ሚስጥር መሆኑ በባለፈቃዱ ምልክት ተደርጎበት በዚህ አዋጅ መሠረት የቀረበ ማንኛውም መረጃ፣ ሪፖርት፣ ሰነድ ወይም ዳታ በባለፈቃዱ ስምምነት ካልሆነ በስተቀር ፈቃዱ ፀንቶ እስከሚቆይበት ጊዜ ድረስ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ወይም በሌላ የመንግሥት አካል ለሌላ ሦስተኛ ወገን መገለጽ የለበትም፡፡ ሆኖም ባለፈቃዱ

በፈቃዱ ሥር የነበረ ክልልን ከተወ ወይም ፈቃዱ ከተሠረዘ በኋላ ማናቸውም የጂኦተርማል ሀብቱን የሚመለከቱ መረጃዎች ለሕዝብ ክፍት ይሆናሉ።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ክልከላ፡-

   ሀ) በፍትሕ አካላት ዘንድ ለተያዘ ክርክር፣ ማጣራት ወይም ምርመራ ሲሆን፤

   ለ) እንደዚህ ያሉ መረጃዎችን እንዲቀበል በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የተፈቀደለት ከመንግሥት ጋር ውለታ ያለው አማካሪ ሲሆንና ይኸው አማካሪ በዚህ አንቀጽ መሠረት መንግሥት ሚስጥር ለመጠበቅ እንደገባው በተመሳሳይ ግዴታ ያለበት ሲሆን፤ ወይም

   ሐ) ለጉዳዩ ከሚያስፈልገው በላይ ዝርዝር እስካልሆነ ድረስ ለመንግሥት ወይም መንግሥትን በመወከል የልማት ሥራዎችን ስታትስቲክስ ለማጠናቀር ሲሆን፣ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 29.ስለሪከርዶችና ሪፖርቶች

1. ማናቸውም ባለፈቃድ በፈቃዱ በግልጽ እንደሚያስፈልጉ ከተጠቀሱ ዝርዝር ሪከርዶችና ሪፖርቶች በተጨማሪ የሚከተሉትን መረጃዎች የያዙ ሰነዶችን በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ መያዝ እና እነዚህኑ ሪፖርቶች ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት፡-

   ሀ) ስለጉድጓድና ከጉድጓድ ስለወጣ ኮር የተመዘገበ ዝርዝር ዳታ፤ ጉድጓዱም ስለሚሰጠው ምርት፣ ስለ ሪኢንጄክሽን ተግባራትና በጉድጓዶች መካከል ሊኖር የሚችል ተጽዕኖን ለመፈተሽ የተደረጉ ሙከራዎችን ጨምሮ የጂኦተርማል ሥራውንና የተገኙ ውጤቶችን የሚመለከቱ መረጃዎችን፤

   ለ) የቅጥር፣ የፋይናንስ፣ የንግድና ሌሎች በፈቃድ፣ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ በደንብና በመመሪያ የተመለከቱ አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን፡፡

2. ባለፈቃዱ የፈቃድ ሰጪውን ባለሥልጣን በጽሑፍ የተሰጠ ይሁንታን ሳያገኝ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) የተመለከቱትን ማናቸውንም ከጉድጓድ ጋር የተያያዘ ወይም ከጉድጓድ የወጣ ኮር ወይም የኮሩን የተመዘገበ ዳታ ማስወገድ ወይም ማጥፋት አይችልም።

## 30.ከጂኦተርማል ጋር የተያያዙ ናሙናዎችን ወደ ውጭ ስለመላክ

1. ባለፈቃዱ ከፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በቅድሚያ በጽሑፍ በተሰጠ ፈቃድ መሠረት የጂኦተርማል ፈሳሾችን፣ ብራይንና ሌሎች የጂኦሎጂካል ናሙናዎችን ወደ ውጭ ሀገር ለፍተሻ የመላክ መብት አለው፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የጂኦተርማል ናሙናዎች መጠን፣ አያያዝ፣ ምርመራና ቁጥጥር አፈጻጸም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብና መመሪያ ይወሰናል፡፡

31.<u>ስለቴክኖሎጂ ሽግግር</u>

1. ማንኛውም ባለፈቃድ ከጂኦተርማል ሥራው ጋር በተያያዘ ሁኔታ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነት በሚያደርግበት ጊዜ ሰምምነቱን ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በማቅረብ ማስፈቀድና ማስመዝገብ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን መቅረብ የሚገባቸው መረጃዎች እና መቅረብ የማይገባቸው የአዕምሯዊ ንብረት መረጃዎች በደንብና በመመሪያ ይወስናሉ።
3. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 ድንጋጌዎች ባለፈቃዱ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በሚሰጣቸው መሰል የቴክኖሎጂና የአዕምሮአዊ ንብረት ባለቤትነት መብቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።
4. ከባለፈቃዱ ጋር የሚደረጉ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነቶች ከአገሪቱ የቴክኖሎጂ ሽግግር ሕጎች ጋር የሚጣጣም መሆኑን ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማረጋገጥ አለበት፡፡

32.<u>ፈቃድ ስለማገድ</u>

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ወደ ፈቃድ ክልሉ በመግባት ቁጥጥር በማድረግ የባለፈቃዱ ተግባር በማኅበረሰቡ፣ በሠራተኞቹ ወይም በአካባቢ ላይ ከባድ አደጋ የሚያስከትል መሆኑን ሲያምንበትና ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ማገድ ብቸኛው መፍትሄ ሆኖ ሲያገኘው ፈቃዱን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ማገድ ይችላል፡፡
2. የሕዝብን ጤና፣ ደህንነት ወይም አካባቢን ለመታደግ ፈጣን ምላሽ የሚያስፈልገው ድንገተኛ ሁኔታ ካልተፈጠረ በስተቀር ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ፈቃዱን ከማገዱ በፊት፦

ሀ) ፈቃዱን ለማገድ ምክንያት ናቸው የሚላቸውን ነገሮች፣ ባለፈቃዱ የፈፀማቸውን የዚህን አዋጅ፣ ሌሎች ሕጎችንና ደንቦችን ጥሰቶች ለማረም ሊወስዳቸው የሚገባቸውን በጊዜ የተገደቡ እርምጃዎች፤ እና

ለ) ባለፈቃዱ የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን እገዳ ሊፈጸም አይገባም የሚላቸውን ማናቸውም ጉዳዮች በጽሑፍ የሚያቀርብበት ከሃያ (20) ያልበለጠ በቂ የሥራ ቀን የያዘ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት አለበት፡፡

3. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የእገዳ ማስጠንቀቂያውን በማንሳት ባለፈቃዱ ወደነበረበት ሁኔታ ሥራዉን እንዲቀጥል የሚፈቅደው፦

ሀ) ባለፈቃዱ ለፈቃዱ መታገድ ምክንያት ናቸው ተብለው የተዘረዘሩትን ነገሮች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (ሀ) በተሰጠው ማስጠንቀቂያ በተገለፀው የጊዜ ገደብ ውስጥ በበቂ ሁኔታ ካረመ፣ በበቂ ሁኔታ ካሻሻለ፣ ካስወገደ ወይም እንዳይደገሙ ከተከላከለ፣ ወይም

ለ) እገዳ ሊፈፀም አይገባም በማለት ባለፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (ለ) መሠረት ያቀረባቸውን ምክንያቶች ከተቀበለ፣ ይሆናል፡፡

33.<u>ስለፈቃድ መሠረዝና መቋረጥ</u>

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ ፈቃድ የሚሰረዘው፡-

ሀ) ባለፈቃዱ የፈቃዱን ክልል በሙሉ ሲለቅ ወይም የፈቃድ መብቱን ሲተው፤

ለ) በዚህ አዋጅ፣ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብና መመሪያ መሠረት ፈቃዱ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሲሠረዝ፤

ሐ) የፈቃዱ ዘመን ከተፈፀመ በኋላ ሳይታደስ ሲቀር፤

መ) የወራሾች መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ባለፈቃዱ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ ሲሞት ወይም ባለፈቃዱ የሕግ ሰውነት መብት ያለው የንግድ ማህበር ከሆነ መፍረሱ ሲረጋገጥ ወይም የመክሰር ውሣኔ ሲሰጥበት፤ ይሆናል፡፡

2. በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ ፈቃድ ሊቋረጥ የሚችለው ባለፈቃዱ፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ፣ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብና መመሪያ የተመለከቱ የፋይናንስ ግዴታዎችን ካላከበረ፤

ለ) የጂኦተርማል ሥራዎችን በከባድ ቸልተኝነት ወይም ሆን ብሎ አግባብ ባልሆነ መንገድ ካካሄደ፤

ሐ) የፈቃዱን መሠረታዊ ስምምነቶች ወይም ግዴታዎች ከጣሰ፤

መ) በሥራ ፕሮግራሙ መሠረት የጂኦተርማል ሥራዎችን የማያካሂድ ከሆነ፤

ሠ) የተፈቀደ የአካባቢና ማህበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት ተግባራዊ ያላደረገ ወይም የደህንነትና የጤና ደረጃዎችን ያላከበረ ከሆነ፤

ረ) በዚህ አዋጅ፣ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብና መመሪያ መሠረት ማቅረብ ከሚገባው ጉዳይ ጋር በተያያዘ ትክክለኛ ያልሆነ ወይም የተሳሳተ መረጃ አቅርቦ ከተገኘ፤

ሰ) በማናቸውም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብና መመሪያ መሠረት የተሟሉ፣ ትክክለኛ የሆኑና ወቅታዊውን ሁኔታ የሚያሳዩ መዝገቦችንና ሪከርዶችን ካልያዘ ወይም በፈቃዱ መሠረት መቅረብ የሚገባቸውን ሪፖርቶች ወይም ሌሎች መዝገቦችን ካላቀረበ፤

ሸ) በአግባቡ ሥልጣን የተሰጠው የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሠራተኛ ወደ ፈቃድ ክልሉ ወይም በኪራይ ወደተያዘው ክልል እንዳይገባ ወይም የጂኦተርማል ሥራዎች የሚካሄድባቸውን ቦታዎች ወይም ተቋማት ወይም የባለፈቃዱን መዝገቦች፣ ሪከርዶች ወይም ሌሎች ሰነዶች ወይም ማቴሪያሎች እንዳያይ ካደረገ ወይም በሠራተኛው የተሰጠውን ሕጋዊ ትዕዛዝ ወይም መመሪያ ካልፈፀመ፤

ቀ) በፈቃዱ ውስጥ በተቀመጠው መሠረት ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማቅረብ ያለበትን አስፈላጊ መሠረታዊ መረጃ ያላቀረበ ከሆነ፡፡

3. በፈቃዱ ወይም በሌላ ስምምነት፣ በሌላ ሁኔታ ካልተገለፀ በቀር በደረጃ I ወይም በደረጃ II የጂኦተርማል ሀብት ላይ የሚሰጥ የጂኦተርማል ሥራ ፈቃድ ሲቋረጥ ለጂኦተርማል ሥራዎች ጥቅም ላይ ውለው የእርጅና ቅናሻቸው ሙሉ በሙሉ ያልተጠናቀቁ ጉድጓዶችን ሳይጨምር የማይንቀሳቀሱና ተንቀሳቃሽ ንብረቶች በባለፈቃዱ የሂሣብ መዝገብ ላይ በሚታየው ዋጋቸው መንግሥት ሊገዛቸው ይችላል፡፡

4. መንግሥት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወይም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ በሚወሰን የጊዜ ገደብ ውስጥ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከቱ ንብረቶችን ሊያነሳቸው ካልቻለ፣ ባለፈቃዱ አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠረት ንብረቶቹን ለሌላ ሰው ሊያስተላልፍ ይችላል፣ ንብረቱ ሊተላለፍ የማይችል ከሆነ ስለአካባቢ ጥበቃ በገባቸው ግዴታዎች መሠረት ያስወግዳቸዋል።

34.**የጂኦተርማል የማማከር አገልግሎት ወይም የቴክኒክ ነክ ስራ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት**

1. ማንኛውም በጂኦተርማል የማማከር አገልግሎት ላይ መሠማራት የሚፈልግና ከጂኦተርማል ጋር የተያያዘ ሙያ ያለው ግለሰብ በዚህ አዋጅ እና ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ መሰረት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት እንዲሰጠው ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሊያመለከት ይችላል፡፡
2. ማንኛውም በጂኦተርማል የማማከር አገልግሎት ወይም ቴክኒክ ነክ ሥራ ላይ መሰማራት የሚፈልግ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው የንግድ ማህበር በዚህ አዋጅ እና ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ ወረቀት እንዲሰጠው ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ሊያመለከት ይችላል፡

**ክፍል አምስት**

**ስለ አስተዳደር፣ ስለካሳ ክፍያ፣ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ክፍያ ነጻ ስለመሆን፣ ስለ ገቢ ግብር፣ ስለፈቃድ ክፍያ እና ስለአካባቢ ደህንነት**[57]

35.**ስለ ቁጥጥር**

1. ማንኛውም ሥልጣን የተሰጠው የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ተቆጣጣሪ ሠራተኛ ተገቢ በሆነ የሥራ ሰዓት ከባለሥልጣኑ የተሰጠውን የጸና መታወቂያ ካርድ በማሳየት ወደማንኛውም የፈቃድ ክልል በመግባት፡-
   ሀ) የፈቃድ ክልሉንና በፈቃድ ክልሉ ውስጥ በመካሄድ ላይ ያለን ማናቸውንም እንቅስቃሴ ወይም ሂደት ለመቆጣጠር፤
   ለ) ማንኛውንም ሪከርድ፣ መግለጫ ወይም ሌላ ሰነድ ለመመርመርና የሰነዱን ወይም የሰነዱን ክፍል ቅጅ ለመውሰድ፤
   ሐ) ማንኛውንም ናሙና ለመውሰድና ለመፈተሽ፣ ለመመርመር፣ ለመተንተንና በዓይነት በዓይነቱ ለመለየት፤ ይችላል፡፡
2. ባለፈቃዱ ሥልጣን ለተሰጠው ተቆጣጣሪ ድጋፍ የሚሰጥ አግባብ ያለው ሰራተኛ መመደብና በፈቃዱ ክልል ውስጥ ባለ ጊዜ ሁሉ ደህንነቱን የማረጋገጥና በፈቃድ ክልሉ ውስጥ ለሚገኙ ሌሎች ሠራተኞች የታደለውን የደህንነት መጠበቂያ መሳያ መስጠት አለበት፡፡

[57] በ26/52(2012) አ.1204 አንቀፅ 2(1) መሰረት ተሻሻለ፡፡

3. ሥልጣን የተሰጠው ተቆጣጣሪ በማስረጃዎችና በአካባቢ ሁኔታዎች ላይ በመመስረት የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መጣሳቸውን፣ እየተጣሱ ወይም ሊጣሱ መሆኑን ካመነ የፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን በጽሑፍ በሚሰጠው ይሁንታ መሰረት አስተዳደራዊ ወይም ህጋዊ ክስ ለመመስረት አስፈላጊ የሆኑ መዝገቦችን፣ ሪከርዶችን፣ መግለጫዎችን ወይም ሌሎች ሰነዶችን ደረሰኝ በመስጠት ለመያዝና በፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ጥበቃ ስር ለማቆየት
ይችላል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሐ) መሰረት ናሙና ሲወሰድ ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት ማንኛውም ሰነድ ሲያዝና በፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ጥበቃ ስር እንዲቆይ ሲደረግ፡-
   ሀ) በይዞታው ወይም በቁጥጥሩ ሥር የነበረ ሰነድ የተያዘበት ሰው እነዚሁ ሰነዶች ከመወሰዳቸው በፊት ተቆጣጣሪው እየተከታተለው የሰነዱን ወይም የሰነዱን ክፍል ቅጅዎች እንዲወስድ ማድረግ ይቻላል፤ ወይም
   ለ) ከተያዘው የትኛውም ነገር ጋር በተያያዘ ክስ ካልተመሠረተ ወይም በማናቸውም ክርክር ወቅት እንደማስረጃ ሊያገለግል መቻሉ አጠራጣሪ ሆኖ ሲገኝ ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ለተያዘበት ሰው ወዲያውኑ ይመለሳል፡፡

36. <u>የሠራተኞች ጥበቃ</u>

ማንኛውም ባለፈቃድ የፈቃድ ግዴታዎቹን ወይም ይህን አዋጅ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚወጣ ደንብና መመሪያን አለማክበሩን በሥሩ የሚገኝ ሠራተኛ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ወይም ለሌላ ለማንኛውም ሥልጣን ለተሰጠው ሰው በማሳወቁ ምክንያት በሠራተኛው የሥራ ሁኔታ ላይ ጎጅ ተጽዕኖ የሚያደርስ እርምጃ ሊወሰድ አይችልም።

37. <u>ስለ ካሳ</u>

ማንኛውም የጂኦተርማል ሥራ ለማከናወን መሬትን ማስለቀቅ የሚጠይቅ ባለፈቃድ ለሚለቀቀው የመሬትን ንብረት ባለይዞታ ለሕዝብ ጥቅም መሬት የሚለቀቅበትንና ለንብረት ካሣ የሚከፈልበትን ሁኔታዎች ለመወሰን በወጣ አዋጅ መሰረት ካሣ መክፈል አለበት፡፡

38. <u>የአካባቢና የማህበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ</u>

1. የጂኦተርማል ሥራ ለማከናወን ፈቃድ ለማግኘት ማመልከቻ የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው፣ ከቅኝት ፈቃድ በስተቀር የአካባቢና የማኅበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ አግባብ ላለው አካል አቅርቦ ማፀደቅ አለበት፡፡
2. ከቅኝት ባለፈቃድ በስተቀር ማንኛውም ባለፈቃድ የፈቃድ ክልሉን ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት ከነበረበት ሁኔታ በተሻለ ወይም በነበረበት ሁኔታ ለመመለስ የሚውል ፈንድ ይመድባል።

39.<u>ተፈጥሮአዊና ባህላዊ ሀብቶችን ስለመንከባከብና መጠበቅ</u>

ባለፈቃዱ የጂኦተርማል ሥራውን በጂኦተርማል ወይም በሌላ የኃይል ወይም የማዕድን ሀብት ላይ አስፈላጊ ያልሆነ ብክነት ወይም ጉዳት በማያደርስ ሁኔታ፤ በገፀ-ምድርና በከርሠ-ምድር ውሃ ሀብቶች ጥራት ላይ እንዲሁም በአየርና በሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶች፣ የዱር እንስሳትን፣ አፈርና እጽዋትን ጨምሮ በባህላዊ ሀብቶችና በአርኪዎሎጂ ቅርሶች፣ የተፈጥሮ መስህቦችና ለመዝናኛ የሚውሉ ሀብቶች ላይ ጉዳት በማያደርስ ሁኔታ ማካሄድ አለበት፡፡

40.<u>ስለሰዎችና ንብረት ደህንነት</u>

1. ባለፈቃዱ የጂኦተርማል ሥራው የሰውን ጤናና ደህንነት በጠበቀና በንብረት ላይ ጉዳት በማያደርስ ሁኔታ ማካሄድ አለበት፡፡
2. ባለፈቃዱ በሥራው ምክንያት ሆን ተብሎም ይሁን በቸልተኝነት በሌላ በማንኛውም ሰው ወይም ንብረት ላይ ለሚደርስ ማናቸውም ጥፋት፣ ጉዳት ወይም አደጋ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

41.<u>ስለማህበረሰብ ልማት ፈንድ</u>

የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድ ለማግኘት ያመለከተ ሰው ባመለከተበት የፈቃድ ክልል ውስጥ ወይም አካባቢ ከሚኖሩ ነዋሪዎች ጋር በመመካከር በጽሑፍ የተዘጋጀ የኅብረተሰብ ልማት ዕቅድ ማካተት አለበት፡፡ ዕቅዱ የነዋሪዎቹን ማኀበራዊ ተቋማት ለማሻሻል የሚመደበውን ፈንድ ጨምሮ የዕቅዱን ማስፈፀሚያ መርሃግብር መያዝ አለበት፡፡

42.<u>ስለጂኦተርማል ስራዎች መዘጋት የምስክር ወረቀት</u>

ባለፈቃዱ ፈቃዱ ሲሠረዝ፣ ሲቋረጥ ወይም ሥራውን ሲተው ይህን አዋጅ ተከትሎ በወጣ ደንብና መመሪያ መሠረት የጂኦተርማል ሥራዎቹን በአካባቢና ማህበረሰብ

ተጽዕኖ ዕቅድ በሚያዘው መሠረት መዝጋቱን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፡፡

43.የፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን መፍትሔ የመስጠት ሥልጣን

1. ባለፈቃዱ የሞተ እንደሆነ ወይም ሊገኝ ካልቻለ ወይም የሕግ ሰውነት ያለው የንግድ ማህበር ሲሆን ህልውናው ካከተመ ወይም በኪሣራ ከተዘጋ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የአካባቢ ተጽዕኖን ለመከላከልና የኅብረተሰቡን ጤና፣ ደህንነትና ማኅበራዊ ተቋማት ለመጠበቅ አስፈላጊውን እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን ሥራ ለመሥራት የሚያስፈልገው ገንዘብ ባለፈቃዱ ለዚህ ተግባር ብሎ ካስቀመጠው የአካባቢ ፈንድ ወጪ ይሆናል፡ ፡

44.ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነጻ ስለመሆንና በባለፈቃድ ስለሚከፈል የገቢ ግብር[58]

1. ማንኛውም የጂኦተርማል ሥራ ባለፈቃድ ለሥራው የሚያስፈልጉና በፀደቀው የሥራ ፕሮግራም መሠረት ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባቸው አላቂ ዕቃዎች፣ መሣሪያዎች፣ ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች ተጨማሪ ዕሴት ታክስን ጨምሮ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ይሆናሉ፡፡
2. ማናቸውም በዚህ አንቀጽ መሠረት ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ የገባ ዕቃ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በቅድሚያ በጽሑፍ ሳይፈቅድና ተገቢው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት በማንኛውም ሁኔታ በአገር ውስጥ ለሌላ ሰው አይተላለፍም፤ ሆኖም ዕቃው ተመልሶ ከሀገር የሚወጣ ከሆነ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ይሆናል፡፡
3. የጂኦተርማል ኃይል አልምቶ በመሸጥ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ድርጅት ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑት የግብር ምጣኔዎች በፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 ምዕራፍ 4 ላይ ለማዕድንና ነዳጅ ሥራዎች የተመለከቱት ምጣኔዎች ይሆናሉ፤[59]

45.ስለፈቃድ ክፍያ

1. በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ ሲሰጥ የፈቃድ ማውጫ ክፍያ ይፈፀማል፡፡

[58] በ26/52(2012) አ.1204 አንቀፅ 2(2) መሰረት ተሻሻለ፡፡
[59] በ26/52(2012) አ.1204 አንቀፅ 2(3) መሰረት ተሻሻለ፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተሰጠ ፈቃድ በየዓመቱ የፈቃድ ማሳደሻ ክፍያ ሲፈጸም የሚታደስ ይሆናል፡፡
3. የፈቃድ ማውጫ እና የፈቃድ ማሳደሻ ክፍያ የአከፋፈል ሁኔታና የገንዘቡ መጠን ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 46.አለመግባባቶችን ስለመፍታት

1. በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣንና በባለፈቃድ መካከል ከውል በመነጨ ወይም ከፈቃድ ጋር በተያያዘ የሚፈጠር ማንኛውም ክርክር፣ አለመግባባት ወይም የይገባኛል ጥያቄ በተቻለ መጠን በጋራ ውይይት ይፈታል፡፡
2. በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣንና በባለፍቃዱ መካከል የሚፈጠር አለመግባባት በዘጠና (90) ቀናት ውስጥ ሊፈታ ካልተቻለ በግልግል ዳኝነት ሥርዓት ታይቶ የመጨረሻና አስገዳጅ ውሳኔ ያገኛል፤[60]

### 47.ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

### 48.የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

1. ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በማዕድን ሥራዎች አዋጅ ቁጥር 678/2002 (እንደተሻሻለ) መሠረት ከጂኦተርማል ሥራ ጋር በተያያዘ የተሰጠ ፈቃድና ስምምነት ፀንቶ ለሚቆይበት ቀሪ ዘመን ተፈፃሚነቱ ይቀጥላል፡፡
2. ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በማዕድን ሥራዎች አዋጅ ቁጥር 678/2002 (እንደተሻሻለ) መሠረት ከጂኦተርማል ሥራ ጋር በተያያዘ ፈቃድና ስምምነት ያለው ባለፈቃድ በማንኛውም ጊዜ በዚህ አዋጅ፣ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብና መመሪያ የተመለከተ ፈቃድ እንዲሰጠው ሊያመለከት ይችላል፡፡

---

[60] በ26/52(2012) አ.1204 አንቀፅ 2(5)(6) መሰረት ተሻሻለ ንዑስ አንቀፅ 3 ተሰረዘ፡፡

3. ይህ አዋጅ በስራ ላይ ከመዋሉ በፊት በማዕድን ሥራዎች አዋጅ ቁጥር 678/2002 (እንደተሻሻለ) መሰረት የጂኦተርማል ሀብት ምርመራ ፈቃድ ተሰጥቶባቸው የጂኦተርማል ሀብት ስራዎች ለመስራት በድርድር ሂደት ላይ ከነበሩ ስምምነቶች ጋር የሚቃረኑ የአዋጁ ድንጋጌዎች በስምምነቶች (በተዋዋይ ወገኖች እንደተሻሻሉ) ላይ ተፈፃሚ አይሆኑም፤[61]

49. **ተፈጻሚ ስለማይሆኑ ህጎች**

1. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ የተሸፈኑትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡
2. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 48 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የማዕድን ሥራዎች አዋጅ ቁጥር 678/2002 (እንደተሻሻለ) ጂኦተርማል ሀብትን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

50. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መስከረም 6 ቀን 2009 ዓ.ም.**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

[61] በ26/52(2012) አ.1204 አንቀፅ 2(6) መሰረት ተሻሻለ ንዑስ አንቀፅ 3 ተሰረዘ፡፡

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 453/2011

## ስለ ጂኦተርማል ሀብት ልማት የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀጽ 5 እና በጂኦተርማል ሀብት ልማት አዋጅ ቁጥር 981/2010 አንቀጽ 47 (1) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የሚኒስትሮች ምክር ቤት የጂኦተርማል ሀብት ልማት ደንብ ቁጥር 453/2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር፦

   1. "አዋጅ" ማለት የጂኦተርማል ሀብት ልማት አዋጅ ቁጥር 981/2010 ነው፤
   2. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተሰጡት ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈፃሚ ይሆናሉ፣
   3. የማመንጨት ፈቃድ" ማለት የጂኦተርማል ሀብትን በመጠቀም ኤሌክትሪክ ለማምረት የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤
   4. "ፍሉው ቴስት" ማለት በጂኦተርማል ምርመራ ሥራ ወቅት የቁፋሮ ሥራ ከተከናወነ በኋላ የጂኦተርማል ፈሳሽ ማከማቻው ሁኔታና የጂኦተርማል ፈሳሽ የማውጣት አቅም ለመገመት የሚከናወን የአሰራር ሂደት ነው፤
   5. "የቁፋሮ እቅድ" ማለት ፕሮጀክቱን ለማልማት የሚዘረጋ አጠቃላይ የመሠረተ ልማት አውታሮች እና ሕንጻን፣ ይዞታን፣ ተያያዥ ኢንስታሌሽንና መሣሪያዎችን ጨምሮ መንገዶችን፣ ፓይፕላይን፣ ጉድጓዶችን እና የውሃ መገኛና ማከማቻዎችን የሚያብራራ ዕቅድ ፕሮግራም ነው፤
   6. "የቁፋሮ ፕሮግራም" ማለት ባለፈቃዱ በፈቃድ ይዞታው ባለው የጂኦተርማል ክምችት የሚያከናውነውን የቁፋሮ ሥራን እና ሙከራን በተመለከተ የሚያብራራ ፕሮግራም ሲሆን በፈቃድ ቦታው ከአንድ በላይ የሆኑ የቁፋሮ ሥራ የሚከናውንባቸው እና የጉድጓድ መደቦችና ለማልማት የሚጠበቁ ጉድጓዶችን ዕቅድ አካቶ የያዘ ፕሮግራም ነው፤

7. “የጉድጓድ ንድፍ ዕቅድ” ማለት በባለፈቃዱ አጠቃላይ የጉድጓድ ቁፋሮ አሰራር ላይ የታቀደውን ንድፍ የሚያብራራ ሲሆን በተጨማሪም ቁፋሮን፣ ሎጊንግ፣ የሙከራ ሥራ እና የእያንዳንዱ ጉድጓድ የቁፋሮ ሥራ ማጠቃለያን ያካትታል፤
8. “የቁፋሮ ይሁንታ ፈቃድ” ማለት በቁፋሮ ፕሮግራሙ መሠረት ለእያንዳንዱ ጉድጓድ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤
9. “ኮንሴፕሽዋል ሞዴል” ማለት በጂኦሎጂ፣ ጂኦኬሚስትሪና ጂኦፊዚክስ በተገኙ ጥናቶች መሠረት የሪዘርኮሩ ሙቀትና ግፊት፣ ሪቻርጅ ዞን፣ የሪዘርኮር ጸባይና የሪዘርኮር ፈሳሹ የኬሚካል ይዘቱ መረጃ በመጠቀም የሙቀቱን ምንጭ፣ የሪዘርኮሩ ሙቀትና ግፊት እና በውስጡ የሚደረገው እንቅስቃሴ እንዲሁም የተገመተው ሪዘርኮሩ መጠንን የሚያሳይ ሞዴል ነው፤
10. “ሎግኢንግ” ማለት በሥነምድር ጥናት ጊዜ በጉድጓድ ቁፋሮ ወቅት በጂኦፊዚክስ ሥራ ወይም ከጉድጓድ የወጣ የኮር ናሙና ተፈጥሮዊ አቀማመጡን የመርመርና የማጤን ሂደት ነው፤
11. “ግሉባል ፖሲሽኒንግ ሲስተም" ማለት ቢያንስ ሃያ አራት) ሳተላይቶችን በመጠቀም ያለንበትን ቦታ ለማወቅ የሚረዳን መሳሪያ ነው፤
12. “ሪዘርኮር” ማለት በመሬት ውስጥ የሚገኝ የጂኦተርማል ፈሳሽ መያዝ የሚችለው የድንጋይ ስብስብ ነው፤
13. “ኤዚንግ” ማለት የጉድጓድ ቁፋሮ ከተከናወነ በኋላ ተደርምሶ ጉድጓዱ እንዳይደፍነው የሚከናወን ሥራ ነው፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለ ፈቃድ</u>

### <u>ምዕራፍ አንድ</u>

### <u>የደረጃ 1 የጂኦተርማል ሀብት ፈቃድ</u>

3. <u>ለቅኝት ፈቃድ ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>
   1. የቅኝት ፈቃድ ለማግኘት ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚቀርብ ማመልከቻ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት እና ተገቢውን ክፍያ በመፈጸም ከሚከተሉት መረጃዎች ጋር መቅረብ ይኖርበታል፦

      ሀ) አመልካቹ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ፦

         1) ሙሉ ስሙን፣ ጾታውን፣ እድሜውን፣ ዜግነቱን፣ የትውልድ ቀንና ቦታ፣

2) ሙያውን፤
3) የመኖሪያ ቦታውንና አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የኢሜይል አድራሻ፣
4) የውጪ ዜጋ ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ እንዲሰራ መብት የሚሰጥ ፈቃድ፣
5) ፍቃድ የተጠየቀበትን ቦታና የግሎባል ፖሲሽኒንግ ሲስተም ኮርዲኔት የያዘ አካባቢያዊ ገፅፀታውንና ስነ-ምድራዊ ተፈጥሮ አቀማመጡን፣ በመሬት ላይ የሚታዩ ቅሪቶችና ስነ-ምድራዊ ለውጦች የሚያሳይ የተቀናጀ ካርታ፤
6) በፍቃድ ዘመኑ ወቅት አመልካቹ ሊያከናውን ያቀደው የሥራ ፕሮግራም፣፤
7) በፈቃድ ክልል ውስጥ ያሉ ነዋሪዎች፣ አርብቶአደር ማህበረሰቦችን ጨምሮ የሚኖሩትን በመለየት በፈቃድ ቦታው አካባቢ ለመከናወን የታቀዱ ሥራዎች ላይ በማተኮር: በአካባቢ ማህበረሰቦች ላይ የሚያስከትሏቸው ተፅእኖዎች እና ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ የቀረበ እቅድ፣
8) ማንኛውም በመሬት ላይ ለሚደርስ ተፅዕኖዎች የሚደረግ የማስተካከያ እቅድ፣ እና
9) በሥራ ፕሮግራሙ ውስጥ የተገለፀውን ሥራ ለማከናወን የሚያስችል ከቴክኒክና የገንዘብ አቅም ጋር የተያያዘ መረጃ፡፡

ለ) አመልካቹ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ከሆነ፡-

1) ስሙ፣ዜግነቱን፣የሕግ አቋሙን፣ የንግድ ሁኔታ እና ዋና የንግድ ቦታ፣
2) የዋና ቢሮውን አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የኢሜይል አድራሻ፤
3) አግባብ ባለው መሥሪያ ቤት የተረጋገጠ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ የአመልካቹ ወኪል ስም፣ አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የኢሜይል አድራሻ፣
4) አግባብ ባለው መስሪያ ቤት የተረጋገጠ ድርጅቱ የተቋቋመበት የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ቅጂዎች፣ እና
5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ(ሀ) ስር ከንዑስ አንቀጽ (4 እስከ ንዑስ አንቀጽ (9) የተጠቀሱትን ዝርዝር መረጃዎች፡፡

2. አመልካቹ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ከተጠቀሱ መረጃዎች በተጨማሪ ፈቃድ በተጠየቀበት ቦታ ውስጥ የተካተተውን አካባቢ ለመለየት፤ ስለ ቦታው በማጣራትና አሳማኝ የትንታኔ መረጃዎችን ያካተተ የሚከተሉትን የያዘ ዕቅድ ሊያቀርብ ይችላል፡-

   ሀ) የቦታውን አቀማመጥ፤ ስነ ምድራዊ ገጽታ፤ በመሬት ላይ የሚታዩ ዋና ዋና ክስተቶች የሚገልፅ ጂኦሎጂካል ካርታ፤

   ለ) ከውሀ እና ከጋዝ ናሙና የተገኘ የሙቀት መጠን የሚገልፅ መረጃ፤ ማንኛውም ከጂኦፊዚክስ ስራ የተገኘ የጥናት ውጤትና

   መ) ወደ ፍቃድ ቦታው ለመድረስ የሚጠቀምበት መንገድ፣ እና

   ሠ) አመልካቹ በኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ጊዜ የያዘው ወይም ከዚህ በፊት ይዞ ሲንቀሳቀስበት የነበረ የጂኦተርማል ፍቃድ ካለ፡፡

3. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ከተጠቀሱት መረጃዎች በተጨማሪ ሊቀርቡ የሚገባቸው ሌሎች መረጃዎች በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

4.<u>በዚህ አንቀፅ ለምርመራ ፈቃድ ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>

1. የምርመራ ፈቃድ ለማግኘት ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚቀርብ ማመልከቻ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት እና ተገቢውን ክፍያ በመፈጸም ከሚከተሉት መረጃዎች ጋር መቅረብ ይኖርበታል፡፡

   ሀ) አመልካቹ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ፥-

   1. ሙሉ ስሙን ፣ ያታውን ፣እድሜውን፣ ዜግነቱን፣የትውልድ ቀንና ቦታ፤
   2. ሙያውን፤
   3. የመኖሪያ ቦታውንና አድራዛየ፣ የስልክ ቁጥር እና የኢሜይል አድራሻ፣
   4. የውጪ ዜጋ ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ እንዲሰራ መብት የሚሰጥ ፈቃድ፣፤
   5. ፈቃድ የተጠየቀበትን ቦታና የግሎባል ፖሲሽኒንግ ሲስተም ኮርዲኔት የያዘ አካባቢያዊ ገፅታውንና ስነምድራዊ ተፈጥሮ አቀማመጡን፣ በመሬት ላይ የሚታዩ ቅሪቶችና ስነ-ምድራዊ ለውጦች የሚያሳይ የተቀናጀ ካርታ፤
   6. አመልካቹ አካባቢው እንዴት እና ለምን ለጂኦተርማል ልማትና ጥቅም አቅም እንዳለው ሊያሳምነው የቻለውን አጠቃላይ መረጃ፤

7. የጤንነት፣ የደህንነት፣ የአካባቢ እና የማህበረሰብ ልማት ተገዢነትን የማረጋገጥ ሀላፊነት ያለባቸው ሰራተኞች ስም እና የሚገኙበት መረጃ፣
8. ለታቀደው የምርመራ ሥራ የመነሻ ሁኔታዎችን የሚያሳይ የፀደቀ የአካባቢ እና ማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ፣
9. አመልካቹ ፕሮጀክቱን ለማከናወን የቴክኒክ፣ የገንዘብ አቅም እና ልምድ እንዳለው የሚያሳዩ መረጃዎች፡፡

ለ)አመልካቹ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ከሆነ፡-

1. ስሙ፣ ዜግነቱን፣ የሕግ አቋሙን፣ የንግድ ሁኔታ እና ዋና የንግድ ቦታ፣
2. የዋና ቢሮውን አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የኢሜይል አድራሻ፣
3. የአመልካቹ በኢትዮጵያ ተወካይ ስም፣ አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የተወካይ ኢሜይል አድራሻ፣
4. አግባብ ባለው መስሪያ ቤት የተረጋገጠ ድርጅቱ የተቋቋመበት የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ቅጂዎች፣
5. የድርጅቱ ዋና ኃላፊዎች ስም፣ ዜግነት፣ የሥራ ልምድ፣ በተጨማሪም ዳይሬክተሮችና ኃላፊዎች እና የሕግ ሰውነት ያለው አካል ካፒታል ድርሻ ካለው ከ5% በላይ ድርሻ ማንኛውም ሰው፣ ያለው
6. የዳይሬክቶሮች ቦርድ ስም ዝርዝር አድራሻና ዜግነት፣
7. በአመልካቹ ስም ለመፈረም ስልጣን የተሰጠው ሰው ስም እና የሥራ ድርሻ፣ እና
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ(ሀ) ስር ከንዑስ ንዑስ አንቀፅ (4) እስከ (9) የተጠቀሱትን ዝርዝር መረጃዎች፡፡

2. የምርመራ ፍቃድ ለማግኘት የሚቀርበው የሥራ ፕሮግራም የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡-

ሀ) በመጀመሪያ ዓመት የሚከናወኑ የምርመራ ሥራዎች ዝርዝር ማብራሪያ፣ በተጨማሪ የሚካሄዱ የቅኝት ሥራዎች ካሉ እንዲሁም የመነሻ ምርመራ ጉድጓድ ለመቆፈር የተለዩ ቦታዎች ካሉ፣

ለ) ቢበዛ በሶስተኛ ዓመት መጨረሻ ድረስ የሚጠናቀቅ የጉድጓድ ቁፋሮ ዕቅድና በአራተኛ ዓመት የጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ መጀመርን ያካተተ የረዥም ጊዜ የምርመራ ሥራዎች ዕቅድ፤

ሐ) የነባር መንገዶች የሚገኙበትን ቦታ እና አስፈላጊ የሆኑ መንገዶች ለመገንባት የተያዘ ዕቅድ፣

መ) ቁልፍ ለሆኑ ሥራዎች ወጪዎችን ለማሳየት የሚረዳ የፍቃድ ዘመኑ የሥራ

ፕሮግራም እና ተያያዥ በጀት፣

ሠ) የጤና እና የደህንነት ዕቅድ፤ እና

ረ) ከአፍሪካ ህብረት የጂኦተርማል ቁፋሮ የትግበራ ኮድ ጋር የሚጣጣም በመመሪያ በሚወሰነው መሠረት የጉድጓድ ቁፋሮ፣ ሙከራ እና ሪፖርት ማድረጊያ ዕቅድ፡፡

3. አመልካቹ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ከተገለፁ መረጃዎች በተጨማሪ ፈቃድ በተጠየቀበት ቦታ ውስጥ የተካተተውን አካባቢ ለመለየት፤ ስለ ቦታው በማጣራትና አሳማኝ የትንታኄ መረጃዎችን ያካተተ የሚከተሉትን መረጃዎች የያዘ ዕቅድ ሊያቀርብ ይችላል፡-

ሀ) ዋና ዋና የጂኦሎጂ እና ስትራክቸራል ባህርያት፤ በመሬት ላይ የሚታዩ ለውጦችን የሚያሳይ የፍቃድ ቦታውንና አካባቢውን የሚገልፅ የጂኦሎጂ ካርታ፤ ለ) በቦታው የተከናወኑ የጂኦኬሚካል ሰርቬይ ጥናቶችና ትንታኔዎችን የሚያሳይ እና የጂኦተርማል ፈሳሽ ማከማቻው ባህርያትና ሊኖር የሚችለው ሀብት ሙቀት መጠን መግለጫ፤

ሐ) ማንኛውም ከጂኦፊዚክስ ሥራ የተገኘ የጥናት ውጤት፣ ጂኦፊዚካል ክሮስሴክሽንና ካርታ፣

መ) ወደ ፍቃድ ቦታው ለመድረስ የሚጠቀምበት መንገድ፤

ሠ) የፍተሻ ጉድጓዶች ሊቆፈሩ የሚችሉባቸው ቦታዎችን የሚሳይ ካርታ፤

ረ) በእያንዳንዱ የጥናት ደረጃ ሳላይ የተሳተፉ ሰዎች ስም፣ የጂኦተርማል ምርመራ ሥራ ላይ ያላቸው ብቃትና ልምድ የሚገልፅ ማብራሪያ፤

ሰ) የዳይሬክተሮች ቦርድ የቅርብ ጊዜ ዓመታዊ ሪፓርት፤ እና

ሸ) የትርፍና ኪሳራ መግለጫዎች ሰነድ እና የባለፉት 3 (ሦስት) ዓመታት የኦዲተሮች ሪፖርቶች ቅጂ፡፡

4. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በዚህ አንቀፅ ከተጠቀሱት መረጃዎች በተጨማሪ ሊቀርቡ የሚገባቸው ሌሎች መረጃዎች በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

5. <u>የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማት እና የመጠቀም ፍቃድ ማመልከቻ</u>

1. የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማት እና የመጠቀም ፈቃድ ለማግኘት ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚቀርብ ማመልከቻ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት እና ተገቢውን ክፍያ በመፈጸም ከሚከተሉት መረጃዎች ጋር መቅረብ ይኖርበታል፡፡

ሀ) አመልካቹ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ፡-

1. ሙሉ ስሙን፣ ፆታውን፣ እድሜውን፣ ዜግነቱን፣ የትውልድ ቀንና ቦታ፣
2. ሙያውን፤
3. የመኖሪያ ቦታውንና አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የኢሜይል አድራሻ፤
4. የውጪ ዜጋ ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ እንዲሰራ መብት የሚሰጥ ፈቃድ፣፤
5. ፈቃዱ ለምን ያህል ጊዜ እንደተፈለገ፣
6. የጂኦተርማል ሀብቱ ሙቀት፣ ፈሳሽ የማሳለፍና የመያዝ እና የጂኦተርማል የግፊት መጠን አቅሙ፣ እንዲሁም ከጉድጓድ የተገኘ የውሃ ኬሚስትሪ መረጃ፤
7. ፈቃዱ የተጠየቀበትና ሥራው ሊካሄድ የታሰበበት ቦታድንበር መታጠፊያዎችን ጭምር የሚያሳይ ጂኦሜትሪያዊ ቅርፅ ያለው የግሎባል ፖሲሽኒንግ ሲስተም፣ ጂኦግራፊክ ኮርዲኔት እና አመላካች የሆነ የመሬት ላይ ምልክቶች፣ መልካ ምድራዊ እና አካላዊ ገፅታ የሚያሳይ ካርታ፤
8. የጂኦተርማል ክምችቱ ምን ያህል ጥልቀት እና ስፋት እንዳለው የሚያሳይ የመነሻ ፅንሰ-ሃሳብ ሞዴልና ሊኖር የሚችል የክምችት መጠን፣ የጂኦተርማል ክምችቱ ፀባይ፣ ስፋቱንና መጠኑን በተሻለ ለማረጋገጥና የበለጠ ለማብራራት የሚጠቀምበትን መንገድ የሚያሳይ የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማት ፕሮግራም ሪፖርት፣

9. በፈቃድ ቦታው ያሉና የታቀዱ ጉድጓዶች፣ እንፋሎቱን ማሰባሰቢያ ዘዴዎች፣ የጂኦተርማል ሀብቱን ለማልማት እና ለመጠቀም የሚያስችሉ ህንፃዎችና ንብረቶች፣ በቀጣይ ቁፋሮና ልማት ወቅት ዕቅዱ ሊሻሻል እንደሚችል ታውቆ በቦታው ያሉና የሚገነቡ አገልግሎት መስጫዎች ዕቅድ ጨምሮ በቦታውና ከቦታው ውጭ የሚደረግ ማሻሻያዎች ዝርዝር፣
10. ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን በሚያወጣው መመሪያ በሚጠይቀው መሠረት የሚጠበቀው ዲስቻርጅና ኢንጀክሽን፣ የጂኦተርማል ፈሳሽ ማከማቻ ሪዘርኮር ፀባይ፣ የጂኦተርማል ሀብት ምርት እና ትንተና፣
11. ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት (11)ጨምሮ በፈቃድ ዘመኑ የመጀመሪያ ሁለት ዓመታት የሚከናወኑ ዝርዝር የሥራ ፕሮግራምና በጀት እና ለቀሪው የፈቃድ ዘመን የበጀት ዕቅድ፤
12. በአመልካቹ ለህብረተሰቡ የተደረገ የአገልግሎት፣ የእርዳታና የማስተባበር ሥራ ካለ እንዲሁም ከአከባቢው ህብረተሰብ ጋር በመተባበር የሚመጣውን ተፅእኖ ለመለየትና ለመፍታት የታቀደ ዕቅድ፣
13. አግባብ ባላቸው የክልል ባለስልጣናት የፀደቁ የማህበረሰብ ልማት እቅዶች፤
14. የካፒታል እና የሥራ ማስፈጸሚያ ወጪዎች ትንበያና እንዲሁም የፕሮጀክቱን የፋይናንስ አዋጭነት የሚያሳይ የበጀት ምንጭ እና የፋይናንስ እቅድ፤
15. የኢትዮጵያ ዜጎችን ቅጥርና ሥልጠና በተመለከተ የቅጥር እና የሥልጠና ፕሮግራሞች፤
16. በሚመለከታቸው ሕጎች መሠረት የፀደቀ የአካባቢ እና ማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ ሪፖርት፤
17. ለጂኦተርማል ሥራ የሚያስፈልጉ በኢትዮጵያ ውስጥ ሊገኙ የሚችሉ እቃዎችና አገልግሎቶች፣ ከሥራው ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ከውጪ የሚገቡ እቃዎችና አገልግሎቶች እና እነዚህ እቃዎችና አገልግሎቶች በሥራ ላይ እንዴት እንደሚውሉ የሚያሳዩ ዕቅዶች፤
18. የጂኦተርማል ሥራው በሚዘጋበት ጊዜ የጉድጓዶችን መድፈንና መተው እንዲሁም ህንጻዎችንና መገልገያዎችን የማጠር ወይም የማንሳት ዕቅድ፤ እና
19. የጂኦተርማል ሀብት ጥቅም እንዲውል የታቀደው ለተቀናጀ ሙቀትና ኃይል ከሆነ፣ በዚህ ደንብ አንቀጽ 24 መሠረት የሚፈለግ መረጃ፡፡

ለ) አመልካቹ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ከሆነ፡-

1. ስሙ፣ ዜግነቱን፣ የሕግ አቋሙን፣ የንግድ ሁኔታ እና ዋና የንግድ ቦታ፤
2. የዋና ቢሮውን አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የኢሜይል አድራሻ፣
3. የአመልካቹ በኢትዮጵያ ተወካይ ስም፣ አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር፣ እና የተወካይ ኢሜይል አድራሻ፤
4. አግባብ ባለው መስሪያ ቤት የተረጋገጠ ድርጅቱ የተቋቋመበት የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ቅጂዎች፤
5. የድርጅቱ ዋና ኃላፊዎች ስም፣ ዜግነት፣ የሥራ ልምድ፣ በተጨማሪም ዳይሬይክተሮችና ኃላፊዎች እና የሕግ ሰውነት ያለው አካል ካፒታል ድርሻ ካለው 5% በላይ ድርሻ ያለው ማንኛቸውም ሰው፤
6. የዳይሬክተሮች ቦርድ ስም ዝርዝር፣
7. አድራሻና ዜግነት፤ በአመልካቹ ስም ለመፈረም ስልጣን የተሰጠው/የተሰጣቸው ሰዎች ስም/ ስሞች እና የሥራ ድርሻቸው፣ እና
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ(ሀ) ስር ከንዑስ ንዑስ (4) እስከ (19) የተገለጹት ዝርዝር መረጃዎች፡፡

2. አመልካቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተገለጹት መረጃዎች በተጨማሪ የሚከተሉትን መረጃዎች ሊያቀርብ ይችላል፡-

ሀ) አመልካቹ ፈቃድ ለመጠየቅ መሠረት ያደረገውን የምርመራ ፈቃድ የፈቃድ ቁጥር፣

ለ) በሚሰጠው የፈቃድ ቦታ በአመልካቹ የተካሄደ የምርመራ ሥራ ካለ የማጠቃለያ ሪፖርት፤

ሐ) የዳይሬክተሮች ቦርድ የቅርብ ጊዜ ዓመታዊ ሪፓርት ቅጂ፣ እና

መ) የትርፍና ኪሳራ መግለጫዎች ሰነድ፣ እና የባለፉት ሦስት ዓመታት የኦዲተሮች ሪፖርቶች ቅጂዎች፡፡

3. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ከተጠቀሱት መረጃዎች በተጨማሪ ሊቀርቡ የሚገባቸው ሌሎች ዝርዝር መረጃዎችን በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## የደረጃ 2 የጂኦተርማል ሀብት ፈቃድ

6. **የደረጃ 2 የጂኦተርማል ሀብት ፈቃድ የመስጠት ስልጣን**

   1. በአዋጁ አንቀጽ 13(3) መሠረት ለሚመለከተው የክልል መንግሥት የቀረበ የደረጃ 2 የጂኦተርማል ሀብት ፈቃድ ማመልከቻን ፈቃድ ሰጪው የክልል መንግሥት ምዝገባ እና የመጀመሪያ ምልከታ ያደርጋል፡፡
   2. ለሚመለከተው የክልል መንግሥት የቀረበ የደረጃ 2 የጂኦተርማል ሀብት ፍቃድ ማመልከቻ ፕሮጀክቱ በየዓመቱ ከሁለት ሚሊዮን (2 ሚሊዮን) ኪዩቢክ ሜትርና ከዚያ ያነሰ የጂኦተርማል ሀብት እና አማካይ የሙቀት መጠን ከመቶ ሃያ (120) ዲግሪ ሴልሺየስ ወይም ከዚያ በታች ከሆነ የክልሉ መንግሥት በሚደነግገው አሠራር መሠረት ማመልከቻው የሚስተናገድ ሲሆን ለመረጃ አያያዝና ለቅንጅታዊ አሰራር ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ከፍቃድ ጥያቄው ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ለፈቃድ ሰጪው ያጋራል፡፡

7. **ለደረጃ 2 የጂኦቷርማል ሀብት ፍቃድ ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የሚቀርብ ማመልከቻ**

   ለደረጃ 2 የጂኦተርማል ሀብት ፍቃድ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚቀርብ ማመልከቻ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት እና ተገቢውን ክፍያ በመፈጸም ከሚከተሉት መረጃዎች ጋር መቅረብ ይኖርበታል፡፡

   1. አመልካቹ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ፡-

      ሀ ሙሉ ስሙን፣ ዖታውን፣ እድሜውን፣ ዜግነቱን፣ የትውልድ ቀንና ቦታ፤

      ለ)ሙያውን፤

      ሐ) የመኖሪያ ቦታውንና አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የኢሜይል አድራሻ፣

      መ) የውጪ ዜጋ ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ እንዲሰራ መብት የሚሰጥ ፈቃድ

      ሠ) ፈቃድ የተጠየቀበት ቦታ ይሸፍነዋል ተብሎ የታሰበበትን ሥፍራ የሚያሳይ ካርታ እና የግሎባል ፖሲሽኒንግ ሲስተም ኮርዲኔት እና የቦታውን አስፈላጊነት የሚያሳይ የመጀመሪያ ደረጃ ቅድመ ጥናት፤

      ረ) አመልካቹ አካባቢው እንዴት እና ለምን ለጂኦተርማል ልማትና ጥቅም አቅም እንዳለው ሊያሳምነው የቻለውን አጠቃላይ መረጃ፤

ሰ) በፈቃድ ክልል ውስጥ ያሉ ነዋሪዎች፣ አርብቶ አደር ማህበረሰቦችን ጨምሮ የሚኖሩትን በመለየት በፈቃድ ቦታው አካባቢ ለመከናወን የታቀዱ ሥራዎች ላይ በማተኮር፤ በአካባቢ ማህበረሰቦች ላይ የሚያስከትሏቸው ተፅዕኖዎች እና ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ የቀረበ እቅድ፣

ሸ) በፍቃድ ጊዜ ውስጥ የሚመረቱ ምርቶች፣ የገቢ እና ወጪዎች፣ እንዲሁም የአካባቢውን ማህበረሰብ የሥራ እና የሥልጠና ተጠቃሚነትን የሚጨምር የሽያጭ ዕቅድ፣

ቀ) በመርሃ ግብሩ ውስጥ የተገለጸውን ሥራ ለመፈጸም የሚያስችል ከቴክኒክ እና የገንዘብ አቅም ጋር የተያያዘ መረጃ፣

በ) ፈሳሽ ሙቀት ለመለካት የሚያስችል በቂ የሆነ የሙከራ እና የክትትል እቅድ፤

ተ) የሚገመተው ደረጃ 2 የጂኦተርማል ሀብት ምርት፣ ፍሰትና ሪኢንጄክሽን እና የጂኦተርማል ሀብቱ ጥቅም ላይ መዋል የሚጀምርበት የጊዜ ሰሌዳ ማብራሪያ፤

ቸ) ተፅዕኖን መከላከል ወይም መቀነስን ያካተተ የአካባቢ እና ማህበራዊ ተጽእኖ ግምገማ ጥናት፣፤

ኀ) የኢትዮጵያ ዜጐችን ቅጥርና ሥልጠና በተመለከተ የቅጥርና የሥልጠና ፕሮግራሞች፤ እና

ነ) ለጂኦተርማል ሥራ የሚያስፈልጉ በኢትዮጵያ ውስጥ ሊገኙ የሚችሉ እቃዎችና አገልግሎቶች እና ከሥራው ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ከውጪ የሚገቡ እቃዎችና አገልግሎቶች ዕቅዶች፡፡

2. አመልካቹ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ከሆነ፡-

ሀ) ስሙ፤ዜግነቱን፡›የሕግ አቋሙን፣ የንግድ ሁኔታ፤

ለ) የዋና ቢሮው አድራሻ፣

ሐ) የአመልካቹ በኢትዮጵያ ተወካይ ስም፣ አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የተወካይ ኢሜይል አድራሻ፤

መ) አግባብ ባለው የመንግስት መስሪያ ቤት የተረጋገጠ ድርጅቱ የተቋቋመበት የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ቅጂዎች፣

ሠ) የድርጅቱ ዋና ኃላፊዎች ስም፣ ዜግነት፣ የሥራልምድ፣ በተጨማሪም ዳይሬክተሮችና ኃላፊዎች እና የሕግ ሰውነት ያለው አካል ካፒታል ድርሻ ካለው ከአምስት በመቶ (5%) በላይ ድርሻ ያለው ማንኛውም ሰው፤

ረ) የዳይሬክተሮች ቦርድ ስም ዝርዝር አድራሻና ዜግነት፤

ሰ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከፊደል ተራ (መ) እስከ (ነ) ስር የተጠቀሱትን ዝርዝር ማስረጃዎች፤

ሸ) በአመልካቹ ስም ለመፈረም የተሰጠው ሰው ስም እና ሥልጣን፡፡

3. አመልካቹ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (6) ከተገለፁ መረጃዎች በተጨማሪ የሚገኝ ከሆነ ፈቃድ በተጠየቀበት ቦታ ውስጥ የተካተተውን አካባቢ ለመለየት፣ ስለ ቦታው በማጣራትና አሳማኝ የትንታኔ መረጃዎችን ያካተተ ዕቅድና የሚከተሉትን ሊያቀርብ ይችላል፡-

ሀ) የቦታውን አቀማመጥ፣ ስነ ምድራዊ ገጽታ፣ በመሬት ላይ የሚታዩ ዋና ዋና ክስተቶች የሚገልፅ ጂኦሎጂካልና ስትራክቸራል ካርታ፡-

1) ከውሀ እና ከጋዝ ናሙና የተገኘ የሙቀት መጠን ውጤት መግለጫ፤

2) ማንኛውም ከጂኦፊዚክስ ስራ የተገኘ የጥናት ውጤትና ካርታዎች፡፡

ለ) የታቀዱ ማሻሻያዎችን የሚያሳይ የቅየሳ ቦታውን የሚያሳይ ዕቅድ፤

ሐ) የዳይሬክተሮች ቦርድ የቅርብ ጊዜ ዓመታዊ ሪፖርት፤

መ) የትርፍና ኪሳራ መግለጫዎች ሰነድ እና የባለፉት ሦስት ዓመታት ኦዲተሮች ሪፖርቶች ቅጂ ካለ፤

ሠ) ወደ ፍቃድ ቦታው ለመድረስ የሚጠቀምበት መንገድ፤

ረ) አመልካቹ በኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ጊዜ የያዘው ወይም ከዚህ በፊት ይዞ ሲንቀሳቀስበት የነበረ የጂኦተርማል ፍቃድ ካለ ስለፈቃዱ መረጃ፤

ሰ) በአመልካቹ ለአከባቢው ህብረተሰብ የተሰጠ አገልግሎት ወይም የትብብር ሥራ ካለናነእንዲሁም ከአከባቢው ህብረተሰብ ጋር በመተባበር ችግሮችን ለመለየትና ለማስወገድ የታቀደ ዕቅድ፡፡

4. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ምክንያታዊ የሆነ ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎችን በሚወጣ መመሪያ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

8. <u>የማመልከቻዎች ማስታወቂያ ምዝገባ እና ህትመት</u>

1. ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን እና ለሚመለከተው የክልል መንግሥት ለደረጃ 2 የጂኦተርማል ሀብት ፍቃድ የቀረበ ማንኛውም ማመልከቻ፣ ፍቃድ፣ ዕድሳት፣ ጊዜ ማራዘሚያ፣ ፍቃድ መመለስ፣ መዳረግ ወይም ማንኛውም ዓይነት በዕዳ ማስያዝ ጥያቄ ማመልከቻ በጂኦተርማል መዝገብ መመዝገብ አለበት፡፡
2. ለማንኛውም ማመልከቻ ጥያቄ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን፡-

ሀ) የደረጃ 2 የጂኦተርማል ሀብት ፍቃድ ማመልከቻ ስለታቀደው ፕሮጀክት፣ አካባቢ እና በመመሪያ በሚወጣው መሠረት ሌሎች አስፈላጊ ጉዳዮችን አካቶ ሰፊ ተደራሽነት ባለው ጋዜጣ ላይ ያሳውቃል፤

ለ) ማስታወቂያው በጋዜጣ ላይ በወጣ በአስራ አምስት (15) ቀናት ውስጥ ተቃውሞ ካልቀረበ በሚቀጥሉት አስር (10) የሥራ ቀናት ውስጥ በቴክኒክና ፋይናንስ መስፈርት መሠረት ይገመግማል፤

ሐ) የቴክኒክና ፋይናንስ መስፈርት ደንብ መሠረት በመመሪያ ይወጣል፡፡

3. አመልካቹ ሁሉንም የምዝገባ እና የህትመት ወጪዎች ይሸፍናል፡፡

9. <u>የደረጃ 2 የጂኦተርማል ሀብት ፍቃድ ስለመስጠት</u>

1. በመመሪያ በሚወሰነው ቅጽና መስፈርት መሠረት የብቻ የሆነ መብት የሚያስገኝ የደረጃ 2 የጂኦተርማል ሀብት ፍቃድ ለጂኦተርማል ሀብት ቀጥተኛ ጥቅም የሚውል ያለ ውድድር ይሰጣል፡፡
2. እንደአግባቡ የደረጃ 2 የጂኦተርማል ሀብት ፍቃድ አመልካቹ ከዚህ በፊት የቅኝት ወይም የምርመራ ፈቃድ ሳይኖረው ሊሰጠው ይችላል፡፡
3. የደረጃ 2 የጂኦተርማል ሀብት ባለፈቃድ ማሟላት ያለበት ዓመታዊ የመለኪያ እና ሪፖርት ማድረጊያ መስፈርቶች፡-

ሀ) የእንፋሎት እና/ወይም የሞቀ ውሃ ፍሰት፤

ለ) በተቋሙ ውስጥ ያለው ሙቀት፤

ሐ) ከተቋሙ ውጭ ያለው ሙቀት፤ እና

መ) በፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የሚያስፈልጉ ተጨማሪ መለኪያዎች እንደ ተቋሙ ዓይነት፣ የጂኦተርማል ሀብቱ ሁኔታና ጥራት እና የማንኛውም የሽያጭ ውሎች፡፡

10. **<u>በባለፈቃድ የሚያዝ የፈቃድ ቦታ ስፋት ወሰንና መያዝ የሚቻለው የፈቃድ ቁጥር ብዛት</u>**

1. በደረጃ 11 የጂኦተርማል ሀብት ፈቃድ መያዝ የሚገባው የቦታ ስፋትና ወሰን የሚወሰነው ለደረጃ 2 የጂኦተርማል ስራ የሚያስፈልግ ቦታ እና በባለፈቃዱ ፕሮጀክት በሚቀርበው ዕቅድ አቅምና ማረጋገጫ ማስረጃ መሠረት ይሆናል፡፡
2. ባለፈቃዱ ለማመልከት እና ፈቃድ ለማግኘት አስፈላጊውን መስፈርት አሟልቶ ከተገኘ ለደረጃ 2 የጂኦተርማል ሀብት ፈቃድ የቁጥር ወሰን የለውም፡፡

11. **<u>ስለመዛግብት እና ሪፖርቶች</u>**

የደረጃ 2 የጂኦተርማል ሀብት ባለፈቃድ ፍቃድ የወሰደው ከፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣንም ይሁን ከሚመለከተው የክልል ባለሥልጣን የሚከተሉትን ለፍቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ወይም ለሚመለከተው የክልል ባለሥልጣን ማሳወቅ ይኖርበታል፡-

1. በአደጋ ሳቢያ በሰው ላይ የአካል ጉዳት ወይም ሞት የሚያስከትል አደጋ ከደረሰ ወይም በውሃ ወይም በአየር ጥራት ላይ ጎጂ ውጤት ከተከሰተ ወዲያውኑ ማሳወቅ፣
2. ባለፈቃዱ በየዓመቱ ፈቃዱን ከተሰጠበት ቀን በኋላ ባሉት ስልሳ (30) ቀናት ውስጥ ያለፈውን ዓመት ዓመታዊ ሪፖርት የሚከተሉትን በማጣቀስ ማቅረብ አለበት፡-

ሀ) በክትትል እቅድ እንደተቀመጠው የጂኦተርማል ሀብቱን ክትትል ውጤት፣

ለ) የወጣውንና ጥቅም ላይ የዋለውን ጂኦተርማል ፈሳሽ መጠን፤

ሐ) ከጂኦተርማል ፈሳሹ የወጣ ተረፈ-ምርት ካለ መጠኑን ወይም ከሽያጭ ሥራው የተገኘ ውጤት፤

መ) በየመደቡ የተከፋፈሉ የተቀጠሩ

## ክፍል ሶስት

## ፈቃዶችን ስለማደስ፣ ስለመተካት ፣ ስለማስተላለፍ እና ስለመሰረዝ

### 12.ስለምርመራ ፈቃድ ዕድሳት

1. የምርመራ ፈቃድን ለማደስ የሚቀርብ ማመልከቻ የፈቃዱ ዘመን ከመፈፀሙ ከስልሳ (60) ቀናት በፊት የሚከተሉትን በማሟላት መቅረብ አለበት፡-

   ሀ) በፍቃድ ዘመኑ ጊዜ የሚጠበቁበትን ሁሉንም መስፈርቶች ስለማሟላቱ ማስረጃ፣

   ለ) ፈቃዱ በመጀመሪያ ሲሰጥ ወይም ዕድሳት ከመከናወኑ በፊት የተደረጉ ለውጦች ካሉ በወቅቱ የቀረቡ መረጃዎች፤

   ሐ) በመመሪያ የሚወሰኑ መረጃዎችን ያካተተ ዓመታዊ ሪፖርት፣

   መ) በቅርብ ጊዜ ላከናወናቸው የምርመራ ሥራዎች ለሚቀርበው ሪፖርት የሥራ ፕሮግራም እና ለሥራው የወጣ ወጪ፤

   ሠ) አመልካቹ በዕድሳት ጊዜው ለመስራት ያቀደው የሥራ ፕሮግራም እና ወጪዎች ዕቅድ፣

   ረ) በአዋጁ አንቀጽ 27 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በፈቃደኝነት ከፈቃድ ቦታው ከየትኛው አካባቢ በከፊል የሚለቀው ቦታ ካለ ዝርዝር፣

   ሰ) ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሊቀርቡ የሚገባቸውን ሌሎች መረጃዎች በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

2. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የቀረበውን የዕድሳት ጥያቄ እና ሰነዶች ከመረመረ በኋላ ተገቢው የዕድሳት ክፍያ ሲፈጸምና የዕድሳት ጥያቄው ሲጸድቅ በአዋጁ አንቀጽ መሠረት በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የምርመራ ፈቃዱ ይታደስለታል፡፡

3. በመጀመሪያው የምርመራ ፈቃድ ዘመን የጂኦተርማል ፈሳሽ ማከማቻ ማረጋገጫ ጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮ ካልተጠናቀቀ የምርመራ ፈቃድ ዕድሳቱ አይከናወንም፡፡

13.**<u>የደረጃ 2 የጂኦተርማል ሀብት ፈቃድ ዕድሳት</u>**

የደረጃ 2 የጂኦተርማል ሀብት ፈቃድ የሚሰጠው ከሀያ አምስት ዓመታት ላልበለጠ ጊዜ ሆኖ በሚቀርበው የፕሮጀክቱ ጥናት ላይ በመመርኮዝ እና የፕሮጀክቱ የፈቃድ ጊዜ ሲያበቃ በመመሪያው እንደሚገለጸው እንደ መጀመሪያው ፈቃድ ተመሳሳይ ጊዜና ሁኔታ መሥረት ሊታደስ ይችላል፡፡

14.**<u> ፈቃድ ስለማስተላለፍ</u>**

1. የምርመራ ፈቃድ ወይም በደረጃ 2 የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ ለማስተላለፍ በአዋጁ አንቀጽ 26 በተደነገገው መሠረት በጽሁፍ በመመሪያ በሚወጣው የማመልከቻ ቅፅ በመሙላትና በማያያዝ ተገቢውን ክፍያ በመፈጸም የሚከተሉትን በማካተት መቅረብ አለበት፡-

   ሀ) ፈቃዱ ሊተላለፍለት የተፈለገውን ሰው ማንነት፣ የቴክኒክ እና የገንዘብ አቅም የሚያሳይ መረጃ፤

   ለ) ባለፈቃዱ የፍቃድ ቦታውን ሙሉ ለሙሉ ወይም ከአንድ ብሎክ በላይ ከሆነ በከፊል ለማስተላለፍ ስለፈለጋቸው ብሎኮች ማረጋገጫ፤

   ሐ) ፈቃዱ ሊተላለፍለት የተፈለገው ሰው ከር የፈቃዱን ስምምነቶችና ግዴታዎች እንዲሁም አግባብ ያለው የሥራ ፕሮግራምና ወጪ የባለ ፈቃዱን ሌሎች ግዴታዎች አክብሮ ለመፈጸም ግዴታ መግባቱን የሚያረጋግጥ የተፈረመበት ማስረጃ፣

   መ) የታሰበውን ማስተላለፍ የሚመለከቱ የውል፣ የኢኮኖሚና ገንዘብ ነክ ስምምነቶችና ግዴታዎች ዝርዝር፡፡

2. የምርመራ ፈቃድ ወይም በደረጃ 2 የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ በአዳ ለማስያዝ በጽሁፍ በመመሪያ በሚጸድቀው የማመልከቻ ቅፅ በመሙላትና በማያያዝ ተገቢውን ክፍያ በመፈጸም የሚከተሉትን በማካተት መቅረብ አለበት፡-

   ሀ) በዕዳ ያዥነት የሚተላለፍለት ሰው ማንነት፣

   ለ) ሊሰጥ ስለታቀደው የደህንነት ጥበቃ ሁኔታና አኳኋን፤ እና

   ሐ) ፈቃዱን የሚቀበለው የፈቃድ ሰጪ ባለስልጣን የሚጠይቀውን መሟላት የሚገባቸውን ለሟሟላት እና የፍቃዱን ውሎችና ግዴታዎች ለማክበር የሚያስፈልጉትን የገንዘብ እና የቴክኒካል መስፈርቶች ማረጋገጥ፤ የሚገባውን

የደህንነት ጥንቃቄ፣ የሥራ ፕሮግራም እና ሌሎች የባለፈቃዱ ግዴታዎች ማሟላት፡፡

3. ለደረጃ 2 ጂኦተርማል ሀብት ፈቃድ የማስተላለፍ ወይም በዕዳ የማስያዝ ማመልከቻ የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ከተቀበለ በዚህ ደንብ በአንቀጽ 7 መሠረት የተቀመጡትን አስፈላጊ መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡፡
4. ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን እነዚህን 4/ ማመልከቻዎች መገምገምና በሚወጡ መመሪያዎች መሥረት ውሳኔዎችን መስጠት አለበት፡፡

15.<u>ስለማገድና ስለመሰረዝ</u>

ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን በአዋጁ አንቀጽ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ውስጥ በአንዱ ማንኛውንም ፈቃድ ሊሰርዝ ይችላል፡-

1. አስቀድሞ በማሳወቅ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን አስተዳደሪያዊ ትእዛዞችን በመስጠት ቅጣቶችን ሊወስን ይችሳላል፣
2. የፈቃድ ሰጭው ባለስልጣን በኢትዮጵያ ሕጎች መሠረት ማንኛውንም ተጨማሪ ቅጣቶች ወይም መፍትሄዎችን ሊሰጥ ይችላል፣
3. ከፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ውጪ በሆነ በሌላ ባለሥልጣን የተሰጡ ፈቃዶች ሊታገዱ የሚችሉት ተፈጻሚነት ባላቸው ሕጎችና ደንቦች መሠረት ይሆናል፡፡

16.<u>ያፈቃድ ወረቀት ስለመተካት</u>

ባለፈቃዱ ለጠፋበት ወይም ለተበላሸበት የፈቃድ ወረቀት የፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን እንዲተካለት መጠየቅ ይችላል፣ ከሚመለከተው የመንግሥት መስሪያ ቤት ማረጋገጫ ተያይዞ ጥያቄ እንደቀረበና ተገቢው ክፍያ በዚህ ደንብ በአንቀጽ 62 መሠረት ሲፈጸም የፈቃዱ የምስክር ወረቀት ምትክ ይሰጠዋል፡፡

<u>ክፍል አራት</u>

<u>መረጃ ስለመያዝ ፣የፈቃድ አሰጣጥ እና የፈቃዱ አፈፃፀም ሁኔታ</u>

17.<u>ያመረጃ አደረጃጀት ስርዓት ዝርጋታ</u>

1. የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የጂኦሎጂካል ሀብት መረጃ የመሰብሰብ እና የማደራጀት ሥርዓት ከኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ወይም በእርሱ ምትክ የእርሱን ተግባር እንዲሰራ ከተቋቋመ ተቋም ጋር በመተባበር ይዘረጋል፡፡

2. የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን እና የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ወይም በእርሱ ምትክ የእርሱን ተግባር እንዲሰራ የተቋቋመ ተቋም ትብብር በሚከተሉት ተግባራትና መርሆዎች ይመራሉ፡-

ሀ) ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን እና የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ወይም በእርሱ ምትክ የእርሱን ተግባር እንዲሰራ ከተቋቋመ ተቋም መረጃ ማግኛ፣ ተደራሽነት እና ኃላፊነቶች ጋር የተያያዙ የመግባቢያ ስምምነት ይፈጽማሉ፤

ለ) ከኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ወይም በእርሱ ምትክ የእርሱን ተግባር እንዲሰራ ከተቋቋመ ተቋም ደረጃውን የጠበቀና ወጥ የሆነ የዳታ ምዝገባ፣ የሪፖርት ፕሮቶኮሎችን የትግበራ መለኪያ እና ለመቆጣጠር ኃላፊነት ያለበትን ሰው በመሾም የዳታ ተዓማኒነትን እንዲረጋገጥ ያደርጋሊ፣

ሐ) ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን መረጃዎች በሚጠየቁበት ጊዜ ተፈጻሚነት ባላቸው ሕግና በሚወጡ መመሪያዎች መሠረት ይሰጣል፤ እንደአግባቡ ተገቢ ክፍያዎችን ሊያስከፍል ይችላል፤

መ) በኢትዮጵያ የጂኦተርማል ሀብት መረጃ የማደራጀት ሥርዓት ከተዘረጋ የመረጃ ቋት በማቋቋም የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ክፍል በመመስረት የኢትዮጵያን የጂኦተርማል ሀብት መረጃ ወደ ቋቱ በማስገባት ለጠቅላላው ሕብረተሰብ ተደራሽ ማድረግ፤

ሠ) የረጅም ጊዜ ግቡ በነባር ወይም በአዲስ የመንግስት አካል የሰው ኃይል እና በመሳሪያ አቅምን በመገንባት፣ የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ሥርዓት በመዘርጋትና በማስተዳደር. ሃላፊነትና ተጠያቂነት ባለው ሁኔታ የመረጃውን ምንጭና መረጃውን በተመለከተ መረጃ የሚሰጥ ለህዝብ እና የግል ጠያቂዎች ምላሽ ለመስጠትና መረጃን ለማሰራጨት ማስቻል ነው፡፡

18. <u>ስለ ጂኦተርማል ሀብት መዝገብ</u>

ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በአዋጁ አንቀጽ 9 መሠረት ከተገለፁ የሚመዘገቡ የጽሑፍ ሰነዶች በተጨማሪ የሚከተሉትን መረጃዎች የያዘ የጽሑፍ ሰነዶች በጂኦተርማል ሀብት መዝገብ ይመዘግባል፡-

ሀ) የመጀመሪያ ደረጃ ትንበያዎችን የሚያመለክቱ የጂኦተርማል ሀብት ሊገኙባቸው ይችላሉ ተብሎ የሚታመንባቸውን ሆኖም ያልተረጋገጠባቸውን ቦታዎች የሚያሳይ ካርታ እና ጂኦግራፊክ ኮርዲኔት፤

ለ) በአዋጁ መሠረት ፈቃድ የተሰጠባቸው ቦታዎች የሚያሳይ ካርታ፤

ሐ) በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት የታደሱ ፈቃዶች ፣ የፈቃድ ቁጥሩንና የቦታውን ስም፣

መ) ፈቃድን፣ የፈቃድ መብትን፣ የፈቃድ ቦታን ወይንም የተወሰነውን የፈቃድ ቦታ የማስተላለፍን፣ የጊዜ ማራዘምን፣ የመተውን፣ የመሰረዝን ወይም የማቋረጥን፣ማስታወቂያዎችን እና/ወይም ትዕዛዞችን፤ እና

ሠ) በመመሪያ በሚወሰነው መሠረት የታወቀ የጂኦተርማል ሀብት ቦታዎችን የሚያሳይ ካርታና ጂኦግራፊክ ኮርዲኔቶችን፡፡

2. እያንዳንዱ ማመልከቻ ለፈቃድ ጥያቄ በሚቀርብበት ጊዜ፣ በተጨማሪም በጨረታ ጊዜ ስኬታማ ተጫራች አመልካች በሚሜሚፈርምበት ጊዜ መዝግቦ መያዝ አለበት፡፡

19.<u>የጂኦተርማል ስራ ፈቃድ ማመልከቻዎችን ስለማረጋገጥ እና ምዝገባ</u>

1. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በዚህ ደንብ መሠረት የጂኦተርማል ሥራ ፈቃድ ጥያቄ ማመልከቻው በደረሰው (3) በሶስት የሥራ ቀናት ውስጥ መስፈርቱን የሚያሟላ መሆን እና አለመሆኑን በማጣራት ይወስናል፤ ማመልከቻው መስፈርቶቹን አሟልቶ ካልተገኘ ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ ለአመልካቹ ማመልከቻው ተቀባይነት አለማግኘቱን ከነምክንያቱ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

2. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማመልከቻው ሁሉንም መስፈርቶች እንዳሟላ ካረጋገጠ ወዲያውኑ በመመዝገብ ለአመልካቹ ስለምዝገባው በጽሁፍ የምዝገባውን ቀን በመጥቀስ ማሳወቅ አለበት፡፡

20. <u>የጂኦተርማል ስራ ፈቃድ ማመልከቻዎችን ስለማስታወቅ</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 17 (2) መሠረት የሕዝብ ማስታወቂያው ወጥቶ ሰላሳ ቀናቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የምርመራ ፈቃዱን ለመስጠት ማመልከቻ ያቀረቡ አመልካቾችን ሰነዶች በአስራ አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ የቴክኒካልና የገንዘብ አቅም መስፈርት መሠረት በመገምገም ከሁሉም አመልካቾች የሚበልጠውን ይወስናል::

2. የሕዝብ ማስታወቂያው በወጣበት ሰላሳ ቀናት ውስጥ ሌሳ ማመልከቻ ካልቀረበ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ለአመልካቹ የምርመራ ፈቃዱን ለመስጠት የቴክኒክና የገንዘብ አቅም መስፈርቱን ያሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ ሰነዶቹን በአስር የሥራ ቀናት ውስጥ ይገመግማል::
3. የቴክኒካልና የገንዘብ አቅም መስፈርት በዚህ ደንብ መሠረት በሚወጣ መመሪያ ይወጣል፡፡
4. ከምርመራ ፈቃዱ ግምገማ እና የቅኝት፣ ደረጃ ǀ የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ወይም ደረጃ 2 ጂኦተርማል ሀብት የሥራ ፈቃድ ማመልከቻ ከተመዘገበ በኋላ በአዋጁ አንቀጽ 10 መሠረት ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ፍቃዱ የሚገኝበትን ቦታ እና ስለ ፕሮጀክቱ ማብራሪያ በመመሪያ በሚወሰነው መሠረት ማስታወቂያ በማዘጋጀት ለፈቃድ ጠያቂው በመስጠት በአገሪቱ ሰፊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ እንዲወጣ በማድረግ ለአስራ አምስት ቀናት እንዲቆይ ማድረግ አለበት፡፡
5. አመልካቹ በዚህ ደንብ በሚወጣ መመሪያ መሠረት ሁሉንም ለምዝገባውና ለህትመት የሚወጣውን ወጪዎች መሸፈን አለበት፡፡

21.<u>የፍቃድ መስፈርቶች እና ግዴታዎች</u>

የፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የቀረበውን ማመልከቻ በመገምገም በአዋጁ፣ በዚህ ደንብና በሚወሰን መመሪያ መሠረት ተሟልተው ሲገኙ በሚከተሉት መጠይቆች እና መስፈርቶች መሠረት ፈቃድ መስጠት አለበት፡-

1. ለምርመራ ፈቃድ፡-

ሀ) በአዋጁ አንቀጽ 15 እና አንቀጽ 17(2) በተደነገገው መሠረት የብቻ የሆነ መብት የሚያስገኝ ፈቃድ በውድድር በመመሪያ በሚወሰነው ቅጽና መስፈርት መሠረት ይሰጣል፤

ለ) ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በምርመራ ፈቃድ መሥፈርት መሠረት ፈቃድ ሲሰጥ ባለፈቃዱ የደረጃ 1 የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ የእያንዳንዱ ፈቃድ ቦታ ከሃምሳ (50) ካሬ ኪሎ ሜትር ያልበለጠ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የምርመራ ፈቃድ ቦታውን በአጠቃላይ ወይም በከፊል በሚሸፍን ቦታ ለማግኘት መብት ይኖረዋል፣ ሆኖም የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ ለማግኘት

በአዋጁ፣ በዚህ ደንብ እና በሚወጣ መመሪያ መሠረት መስፈርቶችና ግዴታዎች የምርመራ ፈቃድ ዘመኑ ከመጠናቀቁ በፊት አሟልቶ መገኘት ይኖርበታል፡፡

2. ለምርመራ ፈቃድ ወይም የደረጃ 1 የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ፡-

ሀ) አግድም የሚቆፈሩ ጉድጓዶችን ጨምሮ በፈቃድ ክልሉ ውስጥ የሚካሄዱ ማናቸውም የጂኦተርማል ሥራዎች አዋሳኝ የሌሎች የጂኦተርማል ፈቃዶች ክልል ውስጥ ጣልቃ መግባት የለባቸውም፤

ለ) ለእያንዳንዱ ጉድጓድ ወይም አንድ የጉድጓድ አፍ ለሚሜሚጋሩ ጉድጓዶች የጂኦተርማል ፈሳሹን ፍሰት፣ ሙቀትና የግፊት ልኬት መጠን በአፍሪካ ህብረት የጂኦተርማል ቁፋሮ የአሰራር ኮድ መሠረት በሚወጣ መመሪያ ባገናዘበ መልኩ መለካትና ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ሪፖርት ማድረግ፣

ሐ) የኤሌክትሪክ ማመንጪያ መሣሪያዎች የሚከተሉትን ጨምሮ መለካትና በየሩብ ዓመቱ ሪፖርት መደረግ አለበት፡-

1) ወደ ማመንጫ ተቋሙ የሚገባው የእንፋሎት ወይም/እና ሙቅ ውሃ መጠን፤
2) የእንፋሎት ኬሚስትሪ እንደ ክሎራይድ ፣ ፒ.ኤች፣ እርጥበት ወይም የውሃ ኬሚስትሪ፣
3) ወደ ማመንጫ ተቋሙ የሚገባው የውሃ እና/ወይም እንፋሎት ሙቀት መጠን፣
4) ወደ ማመንጫ ተቋሙ የሚገባው የውሃ እና/ወይም እንፋሎት ግፊት መጠን፣
5) አጠቃላይ የሚመነጨው የኤሌክትሪክ ኃይል
6) ማመንጫ ተቋሙ የሚያወጣው የተጣራ ኤሌክትሪክ ኃይል፤
7) በመሸጫ ቦታ ላይ የሚቀርብ ኤሌክትሪክ ኃይል፣
8) በየዓመቱ ከማመንጫ ተቋሙ የሚወጣው የማይዘቅጥ እንደ ካርቦን ዳዮክሳይድ፣ ሃይድሮጅን ሰልፋይድ፣ ሜቴንና የመሳሰሉ ግምታዊ የጋዝ መጠን፤

9) ከማመንጫ ተቋሙ የሚወጣው የእንፋሎት እና/ወይም ሙቅ ውሃ ሙቀት መጠን፡፡

3. ለደረጃ 1 የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃድ የሚሰጠው፡-

ሀ) የብቻ የሆነ መብት ያለው፣ የምርመራ ፈቃድ በውድድር አሸንፎ ፈቃድ የተሰጠውና የደረጃ 1 የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ ለማግኘት የተቀመጡትን ሁኔታዎች ያሟላ፣ ወይንም በአዋጁ አንቀጽ 17(1) እና በዚህ ደንብ የተደነገገውን በውድድር ፈቃድ የማግኘት መብት አሟልቶ ሲገኝ፤

ለ) የፀደቀ የኃይል ግዢ ስምምነት ተያይዞ ከቀረበ፤

ሐ) በአዋጁ አንቀጽ 20 መሠረት የሚከተሉትን ጨምሮ የያዘ የጸደቀ የሥራ ፕሮግራም ሲቀርብ፡-

1) የኃይል ማመንጨት አቅሙ ጋር የአመልካቹን ፍላጎት ታሳቢ ያደረገ የቴክኒክ ሪፖርት፤
2) የሚጠበቅ የኃይል ማመንጨት አቅም እና ሌሎች ውጤቶች ወይም ተረፈ
ምርቶች፤
3) በፈቃዱ ጊዜ የሚጠናቀቅ ሥራዎችን ያካተተ የሥራ አተገባበር ዕቅድ፤
4) የጤና እና የደህንነት ዕቅድ፤
5) ኃይል ለማመንጨት ወይንም የመነጨውን ኃይል ግዢ አስመልክቶ ከመንግሥት ጋር የተደረጉ ውለታዎችና ስምምነቶች በሙሉ፤
6) በባለፈቃዱ የጂኦተርማል ፈሳሹን ለሌላ ጥቅም ለማዋል የተያዘ ዕቅድ ወይንም የጂኦተርማል ፈሳሹን ለሶስተኛ ወገን እንዲጠቀም የተደረገ ስምምነት ዕቅድ ዝርዝር ማብራሪያ፤
7) የመረጃ አሰባሰብና አጠባበቅ ዕቅድና ሪፖርት አደራረግን አስመልክቶ ከአፍሪካ ህብረት የጂኦተርማል ቁፋሮ የትግበራ ኮድ ጋር የሚጣጣም በመመሪያ በሚወሰነው መሠረት የሚወጣ ዝቅተኛ መስፈርት እና ሪፖርት አደራረግ የተመለከተ የጊዜ ሰሌዳ ዕቅድ፤

8) በፈቃድ ቦታው አካባቢ ከሚገኙ ማህበረሰቦች ጋር በጋራ ተባብሮ ለመስራት የተቀረፀ ዕቅድ፤
9) ፕሮጀክቱ ተፅዕኖ ሊያደርስ በሚችልባቸው ማህበረሰቦች ላይ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ ለመቀነስ ወይም ለማቃለል ያለው ዕቅድ፤
10) በተሰጠው ፈቃድ ሥራ ላይ በከፍተኛ ደረጃ በአካባቢው ላይ ሊያደርስ የሚችለው ጥፋት ማብራሪያ እና ጥፋቱን ለመቆጣጠር ወይም ለመቀነስ የሚወሰደው እርምጃ ዕቅድ፤
11) ለአካባቢ ጥበቃ የሚውል ፈንድ ስለማቋቋምና ስለመጠቀም የተዘጋጀ ዕቅድ፤
12) በፈቃድ ዘመኑ የሚያስፈልግ የካፒታል ኢንቨስትመንት፣ የመደበኛ ሥራ ወጪ እና የገንዘብ ምንጭ የሚያሳይ በጀትና ዕቅድ፤
13) የጂኦተርማል ሥራውን በሚያከናውን- በት ወቅት ለመቅጠርና ለማሰልጠን የያዘው ዕቅድ፤
14) የጂኦተርማል ሥራው ሲዘጋ የሚዘጋበት እቅድና በተጨማሪም የማይሰሩ ጉድጓዶችን የመተውና መዝጋት፣ የሚሰሩ ጉድጓዶችን የመክደን እና ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በሚፈቅደው መሥረት ይዞ የማቆየትና የማዘግየት እና የፕሮጀክቱ መሠረተ ልማትና አገልግሎት መስጫ ዕቃዎችን የማስወገድ ሥራ፤
15) በፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን እንደአስፈላጊነቱ በሚያወጣቸው መመሪያዎች የሚወሰኑ ሌሎች ድንጋጌዎች፡፡

መ) ባለፈቃዶች በታቀደው የሥራ ፕሮግራም መሠረት ስለተከናወኑ ሥራዎች ዓመታዊ ሪፖርት ማቅረብ እና የሚቀጥለው ዓመት የሥራ ዕቅድ እና ወጪ በመመሪያ በሚደነገገው መሠረት ማቅረብ አለባቸው፡፡

22. <u>የደረጃ 1 የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ እና የማመንጨት ፈቃድ ግንኙነት</u>

በመጀመሪያ ለሚገነባው የኃይል ማመንጫ ተቋም እና በመቀጠል በፈቃድ ቦታው በተጨማሪ ለሚገነቡት ለእያንዳንዱ የኃይል ማመንጫ ተቋሞች የማመንጨት ፈቃድ ለደረጃ 1 የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ ያህል ጊዜ ይሰጣል፤ የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጫ ፈቃድ ሲፈቀድ እንዲህ

ዓይነቱን ፈቃድ ከሚመለከተው የደረጃ 1 የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ ጋር በማጣቀሻነት በማያያዝ ይካተታል፡፡

23.<u>በባለፈቃዶች መያዝ የሚቻለው የፈቃድ ቁጥር ብዛት እና የፈቃድ ቦታ ስፋት ወሰን</u>

የአዋጁ አንቀጽ 23 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፡-

1. የቅኝት ባለፈቃድ በአንድ ጊዜ ከአንድ በላይ ፈቃዶችን መያዝ ቢችልም የእነዚህ ፈቃዶች ጠቅላላ ስፋታቸው ከሁለት ሺህ (2000) ካሬ ኪሎ ሜትር መብለጥ አይችልም::
2. ለደረጃ 1 የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ በፈቃዱ የተቀመጡትን ግዴታዎች ከተገበረ እና በሥራ ፕሮግራሙ የተቀመጡትን ካከበረ፣ ለደረጃ 1 የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ የፈቃድ ብዛት ቁጥር ወሰን የለውም፡፡

24.<u>የደረጃ 1 የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ እና በተጨማሪ የተጣመረ የኃይልና ሙቀት በጋራ ስለመጠቀም</u>

1. የደረጃ 1 የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ አመልካች ወይም ባለፈቃድ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የጂኦተርማል ተረፈ-ምርት ፍሳሹን በምን መልኩ ለመጠቀም እንዳቀደ የሚያሳይ የሥራ ፕሮግራም ማቅረብ ይችላል፤ በተጨማሪም፡-

   ሀ) ለታቀደው ጥቅም ማብራሪያ ዕቅድ፤

   ለ) ኤሌክትሪክ ከማመንጨት በተጨማሪነት ከጂኦተርማል ፈሳሽ ማከማቻ ምንጩ፡ ለመጠቀም የታቀዱት ሥራዎችና በምንጩ ላይ ሊኖረው ይችላል ተብሎ የሚታሰበው ተጽእኖ፤ እና

   ሐ) የጥምር ሥራው በሠራተኞች፣ በጤናና በደህንነት ጥበቃ፣፥ የማህበረሰብ ልማትና የባለፈቃዱ የፋይናንስና ቴክኒካል አቅም፣ የበጀት፣የአካባቢ ጥበቃ፣ ኢኮኖሚ እና ሌሎች አስፈላጊ ናቸው ተብለው በመመሪያ የሚወሰኑ ሁኔታዎችላይ ያለው ተፅዕኖ፡፡
2. ለአዲስ የደረጃ 1 የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ አመልካች፣ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በመስፈርቱ መሠረት ተሟልቷል ብሎ ሲያምን እና የአመልካቹ የኃይልና የሙቀት የጋራ የመጠቀም ጥያቄ ዕቅድ

እንዲሁም በጀት በህዝቡ ደህንነትና በጂኦተርማል ሀብቱ ላይ ተፅዕኖ እንደሌለው ሲያምን የደረጃ 1 የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ እና የጂኦተርማል ፈሳሽን ለኃይልና ለሙቀት የመጠቀም ፈቃድ ይሰጣል፡፡

3. ቀደም ሲል የደረጃ 1 የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ የጂኦተርማል ፈሳሹን ለተጨማሪ ጥቅም ለማዋል የቀረበው ዕቅድ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ተቀባይነት ሲያገኝና ተገቢው ክፍያ ሲፈጸም እንዲሁም ባለው ፈቃድ ኃይል በማመንጨት ላይ ምንም ተፅዕኖ ከሊለው፣ ባለፈቃዱ በግልጽ የቴክኒክ ወይም የገንዘብ ችግር እንዳለበት ካልታየ በስተቀር ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የተሻሻለ የደረጃ 1 የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ እና የጂኦተርማል ፈሳሽ ኃይልና ሙቀት በጋራ የመጠቀም ፈቃድ ላለው ፈቃድ ዘመን ሊሰጥ ይችላል፡

25.<u>ዝቅተኛ የሥራ እና የማሻሻያ መስፈርቶች</u>

1. ለቅኝት ፈቃድ በፈቃዱ ዘመን መጨረሻ የተጠናቀቁ ሥራዎች የማጠቃለያ ሪፖርት እና ያልተጠናቀረ ጥሬ መረጃ እና የተጠናቀረ መረጃ መቅረብ አለበት፡፡

2. ለምርመራ ፈቃድ፡-

ሀ) ባለፈቃዱ በየዓመቱ የተከናወኑ ሥራዎች ማጠቃለያ ሪፖርት እና የተሰበሰበ ያልተጠናቀረ ጥሬ መረጃ እና የተጠናቀረ መረጃ፣ የሥራ ፕሮግራም ማሻሻያ ዕቅድ እንዲሁም ወጪና በቂ ምክንያት የያዘ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፤

ለ) ባለፈቃዱ በሶስተኛ ዓመት መጨረሻ ወይም ከዚያ በፊት ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የመጀመሪያ የቅድመ ፅንሰ ሃሳብ ሞዴልና ማብራሪያ፣ ስለ ጂኦተርማል ሀብት ከመሬት ገጽታ ምርመራ ሥራና ከጉድጓድ ቁፋሮ ምርመራ ዕቅድ በመነሳት ማቅረብ አለበት፤

ሐ) ባለፈቃዱ በአራት ዓመት መጨረሻ ወይም ከዚያ በፊት የጂኦተርማል ምርት

ማረጋገጫ የጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ መጀመር አለበት፡፡

3. ለደረጃ 1 የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ፡-

ሀ) የደረጃ 1 የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ በተሰጠ በአራት ዓመት ውስጥ ባለፈቃዱ ኤሌክትሪክ የማመንጨት ፈቃድ የመጠየቅ መብትና ኃላፊነት አለበት፤

ለ) የደረጃ 1 የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ ከተጀመረ በአራት ዓመት ውስጥ ባለፈቃዱ ከጂኦተርማል ፈሳሽ ማከማቻ ልማት ሥራ ጋር በተያያዘ እንደ ምርት እና ሪኢንጀክሽን ጉድጓድ ቁፋሮ እና ሌሎች ሥራዎች ማከናወን ይገባዋል፤ የተሻሻለ የፅንሰ ሃሳብ ሞዴልና ማከማቻ ሪፖርት፣ የምርት እና የሪኢንጀክሽን ጉድጓድ ቁፋሮ ሊያከናውን የሚችልባቸው ቦታዎች የሚያሳይ ካርታ ዕቅድ እና በቀሪው ፈቃድ ዘመን የሚገነቡ አገልግሎት መስጫዎች ዕቅድ ማቅረብ አለበት፤

ሐ) ባለፈቃዱ በየዓመቱ መጨረሻ ባሉ ስልሳ ቀናት ውስጥ የሚፈለግበትን ዝቅተኛውን መረጃ ማስረከቢያ መስፈርቶች እንደ የምርት እና ሪኢንጀክሽን መረጃዎች በመመሪያ በሚወጣው መሠረት እና ማሻሻያ የሥራ ፕሮግራምና በጀት ማቅረብ አለበት፡፡

26.<u>ስለመዛግብት እና ሪፖርት</u>

1. ማንኛውም ባለፈቃድ ፈቃዱ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ የሚከተሉትን የያዘና በእነዚህ ላይ የሚደረጉ ወቅታዊ ለውጦችን የሚያሳይ መዝገብ በኢትዮጵያ ውስጥ መያዝ አለበት::

ሀ) መደበኛ መዛግብት፡-

1) የሰውን ጤንነት ወይም አካባቢን የሚጎዱ ወይም ጉዳት የሚያደርሱ አደጋዎች ወይም ግጭቶችን መመዝገብና በተፈጸሙ በ24 ሰዓት ውስጥ ሪፖርት ማድረግ፤

2) በሥራ እና በአገልግሎት ላይ የተደረገ ለውጥ ካለ፤

3) በየመደቡ የተከፋፈሉ የተቀጠሩ ሠራተኞች መረጃዎች፤

4) የሁሉም መሳሪያዎች፣ ማሽኖች እና ሌሎች ቁሳዊ ንብረቶች ዝርዝር፡፡

ለ) ሁሉንም የቴክኒካል ሪፖርት ትንተና፣ ከአካባቢ ጥበቃ እና ከፍቃድ ቦታው የጂኦተርማል ሀብት ጋር የተያያዙ ሪፖርቶች ቅጂዎች፡፡

ሐ) በሥራ ፕሮግራሙ በታቀደው መሠረት እና ለቁፋሮ ሥራ በአፍሪካ ህብረት የጂኦተርማል ቁፋሮ ትግበራ ኮድ መሠረት በሚወጡ መመሪያዎች ባከበረ መልኩ በተሰጠው የፈቃድ ቦታ ላይ የተሰበሰበ መረጃ፡፡

2. የምርመራ ባለፈቃዱ የሚከተሉትን መዛግብት መያዝ ይኖርበታል፡-

ሀ) በጉድጓድ ቁፋሮ ላይ የተሟላ መረጃና የጉድጓዱ ሎግ መረጃ፤

ለ) የጉድጓዶች በምርት እና በሪኢንጄክሽን ጊዜ የየቀኑን የሙቀት፣ ግፊት እና የጂኦተርማል ፍሰት ሙሉ መረጃ፤እና

ሐ)በፈቃዱ ላይ የተገለጹ ሌሎች መረጃዎች፡፡

3. የምርመራ ባለፈቃድ የሚከተሉትን መረጃዎች በመመዝገብ ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ማስረከብ ይኖርበታል፡-

ሀ) ለእያንዳንዱ ጉደጓድ እና የፍተሻ ሥራዎች ለሁሉም ጉድጓዶች ወርሃዊ ሪፖርቶች፣ ከሎግ ጋር የተያያዘ መረጃ እና ከጉድጓዱ ጋር የተያያዙ የምዝገባ ማስታወሻዎች፣ የቁፋሮና የሙከራ ስራ ውጤቶችን እንዲሁም የጉድጓዱን ማጠናቀቂያ ሪፖርት ያካተተ፤

ለ) የምርመራ ባለፈቃድ በየዓመቱ ፈቃዱ ከተሰጠበት ቀን በኋላ ባሉት ስልሳ ቀናት ውስጥ ያለፈውን ዓመት ማጠቃለያ ሪፖርት የሚከተሉትን የያዘ በዓመቱ ያቀርባል፡-

1) በሥራው መርሃ ግብር መሠረት የተከናወነውን ሥራ፤፣
2) የተገኙ ውጤቶች፤
3) አደጋዎች ወይም ፍሳሾችን ያካተተ ዋና ዋና የሆኑ ክስተቶች፤
4) በየመደቡ የተከፋፈሉ የተቀጠሩ ሠራተኞች ብዛት፤
5) ወጪዎች በየመደብ ዓይነት፡፡

4. የደረጃ 1 የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማት እና የመጠቀም ባለፈቃድ ፈቃዱን ከወሰደበት ማብቂያ በኋላ ባሉት ስልሳ (60) ቀናት ውስጥ ያለፈውን ዓመት በየወሩ የተከናወኑትን የሚከተሉትን የያዘ ሪፖርት ያቀርባል፡-

ሀ) አጠቃላይ የወጣው ጂኦተርማል ፍሰት መጠን እና ማንኛውም ከዚያ በኋላ የተከሰተውን ፊዚካላዊ እና ኬሚካላዊ ባህሪያት ያካተተ፤

ለ) ወደ አገልግሎት መስጫው የገባውን የጂኦተርማል ፈሳሽ መጠን፤

ሐ)ከጂኦተርማል ፍሳሽ የወጡ ተረፈ ምርቶች ካሉ መጠናቸው፤

መ) ከፍተኛ ጉዳት ወይንም ሞት ያደረሱ ሁሉንም ክስተቶች እና አደጋዎች ወይንም በማህበረሰቡና በአካባቢው ላይ የደረሱ ተፅዕኖዎች እንዲሁም ተፅዕኖውን ለመቀነስ የተወሰዱ እርምጃዎች፤

ሠ) በየመደቡ የተከፋፈሉ የተቀጠሩ ሠራተኞች ብዛት፡፡

5. የኤሌክትሪክ የመጨረሻ ማስተላለፊያ ቦታ ወይም ባስ ባር ወይም ስምምነት ከተደረገበት ማስተላለፊያ ቦታ ወደ ማስተላለፊያ ግሪድ የተላለፈው የኤሌክትሪክ ኃይል መጠን፡፡
6. የደረጃ 1 የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ባለፈቃድ ቢያንስ በየአምስት ዓመት ውስጥ በፍቃድ ሰጪው ባለስልጣን ተቀባይነት ያለው የአሃዝ ሪዘርኮር ሞዴል ጨምሮ ወቅታዊ የጂኦተርማል ፈሳሽ ክምችት ሪፖርት ለፍቃድ ሰጪው ባለስልጣን ማቅረብ አለበት፡፡
7. የደረጃ 1 የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ ወይም የደረጃ 2 የጂኦተርማል ሀብት ፍቃድ በሕግ ሰውነት ያገኘ ባለፈቃድ፣ ባለፈቃዱ ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔውን ባደረገ በዛው ወር ውስጥ የቦርዱን ሪፖርት እና የሂሳብ ተቆጣጣሪዎች ከባለፈው የበጀት ዓመት ጋር የተያያዙ የሒሳብ መግለጫዎች እና በስብሰባው ተቀባይነት ያገኙ ካሉ የጂኦተርማል ልማት ሥራዎች ጋር የተያያዙ ቅጂዎች ለፍቃድ ሰጪው ባለስልጣን ማቅረብ አለበት፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ጨረታ</u>

### 27.<u>ስለ ጨረታ ውድድር</u>

ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን በአዋጁ አንቀጽ 17 እና በዚህ ደንብ መሠረት የምርመራ ፈቃድ እና የደረጃ 1 የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፈቃዶችን በጨረታ አወዳድሮ ሊሰጥ ይችላል፡፡

### 28.<u>የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ኃላፊነት እና ስልጣን</u>

ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን አንድን የፍቃድ ቦታ በጨረታ በሚያወዳድርበት ጊዜ የሚከተሉትን መስፈርቶች መከተል ይኖርበታል፡-

1. ለጨረታ ማስታወቂያና ለምርጫ ሂደት የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀት፤
2. ለጨረታ የሚቀርበውን ቦታ መወሰን፤

3. በጨረታ ሰነድ ውስጥ ሊጠቃለሉ የሚችሉ ዝቅተኛ የቴክኒክ ብቃትን እና. የገንዘብ አቅምን መወሰን፤
4. የጨረታውን ምዘና ሂደት ማለትም የኃይል ማመንጫ ተቋማትን ማቋቋም የኤሌክትሪክ ማመንጫ እና የሀይል ፍጆታ ታሪፍን በተመለከተ በኢነርጂ አዋጅ ቁጥር 810/2006 አንቀጽ 4(3) መሠረት ከብሔራዊ ግሪዱ ጋር በተያያዘ የሚቀርብለትን ታሪፍ መገምገምና ለመንግሥት ለውሳኔ ማቅረብ፤
5. ለደረጃ 1 የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማትና የመጠቀም ፍቃድ ሀይል ግዥ ስምምነቶችንና ሌሎች የፕሮጀክት ስምምነቶችን ጨምሮ የጨረታ ሰነዶችን ማዘጋጀት፤
6. ለእያንዳንዱ ጨረታ ማስታወቂያ ዝቅተኛ የጨረታ ዋጋ እና ተቀባይነት ያለው የጥሬ ገንዘብ ክፍያዎች ወይም ሌላ የክፍያ አማራጭን ማዘጋጀት፤
7. ለጨረታ ማስከበሪያና ይፋ ላልሆነ ስምምነት ማስፈፀሚያ ክፍያ ለከፈሉ በጨረታ መወዳደር ለሚችሉ ተጫራቾች በቀላሉ ሊያገኙት የሚችሉትን መረጃዎች በኤሌክትሮኒክስ ማዘጋጀት፤
8. ስለጨረታው በተገቢው መንገድ ይፋ ማድረግ፤
9. የቀረቡ ጨረታዎችን መገምገም፤
10. አሸናፊውን ተወዳዳሪ መለየት፤
11. ለአሸናፊ ተጫራች ስለሚሰጠው የፈቃድ ጊዜ ድርድር ማድረግና ማጠናቀቅ ወይም ምንም አሸናፊ ተጫራች ከሌለ የታቀደውን የፈቃድ ክልል በውድድር ከሚሰጥ ጨረታ ማውጣት ወይም ለምርመራ ፈቃድ ከጨረታው ማስታወቂያ በፊት አንድ አመልካች ካመለከተ የጨረታው ሂደት እንዳለቀ አመልካቹን መግለፅ እና አመልካቹ የዚህን ደንብ አንቀፅ 11 ቅድመ ሁኔታ ካሟላ ፈቃዱን መስጠት፤
12. ክፍያዎች መሰብሰብና የጨረታ ማስያዣውን እንዳስፈላጊነቱ ማረጋገጥ፤ እና
13. ውጤቱን ለተጫራቾች ማሳወቅ እና ከውጤቱ በኋላ ባሉት ሰላሳ (30) ቀናት ውስጥ ተጫራቾች ለሚያቀርቡት ጥያቄ ስለ ጨረታው ግምገማ ተገቢውን ማብራሪያ መስጠት፡፡

29.**የጨረታ ሰነድ**

የጨረታ ሰነድ በፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ወይም ጨረታውን ለመመዘን ብቃት ያላቸው ቴክኒካል ባለሙያዎችን በማካተት በሚቋቋም የጨረታ ኮሚቴ ይዘጋጃል፤ የጨረታ ሰነዱን ተወዳዳሪዎች በሚጠይቁበት ጊዜ እና አስፈላጊውን ክፍያ ከፈጸሙ በኋላ ይቀርብላቸዋል፣ የጨረታ ሰነዱ ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀ የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ክፍል የሚገኝ ሲሆን የሚከተሉትን መረጃዎች ሊይዝ ይችላል:-

1. የጨረታ ማመልከቻ ማስገቢያ እና መክፈቻ የጊዜ ገደብ፣
2. አሸናፊውን ተጫራች መለያ የመመዘኛ እና የመምረጫ መስፈርቶች እና ሂደት፣
3. ለደረጃ 1 ጉድጓድ ማልማት እና መጠቀም ፈቃድ የሚቀርብ ጨረታ የደረጃ ጉድጓድ ማልማት፣ መጠቀም እና የሃይል ማመንጨት ረቂቅ ሞዴል የያዘ ሰነድ፤
4. አነስተኛ የጨረታ ዋጋው፤
5. በጨረታው አሸናፊ የሆነው የአከፋፈሉ ሁኔታ የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

   ሀ) የጨረታው አሸናፊ በሜገለጽበት ጊዜ የሚከፈል ከአጠቃላይ የጨረታ ዋጋው ቢያንስ ሃያ በመቶ (5%)፤ እና

   ለ) ቀሪው የጨረታ ዋጋ ክፍያ የባለፈቃዱ የረጅም ጊዜ የፕሮጀክት ሂሳብ መዝጊያ ጊዜ ወይም በሀይል ማመንጫ ጣቢያው ሥራ ማስጀመሪያ አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወይም ከሁለቱ በቀደመው ሊሆን ይችላል፡፡6
6. አሸናፊው ተጫራች ካቀረበው - የገንዘብ ማስያዥያ በመነሳት፣ የሚጠበቅበት ክፍያ ወይንም የዋስትና ቦንድ ወይንም ማስያዥያ::
7. ለደረጃ 1 የጉተድጓድ ማልማት እና መጠቀም ፈቃድ ረቂቅ የሀይል ግዥ ሰነድ እና ሌሎች የፕሮጀክት ሰነዶች፤ እና
8. በፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የተረጋገጡ እና የዚህን ደንብ ተፈፃሚነት የሚያረጋግጡ ሌሎች አጠቃላይ መረጃዎች ወይም ማስረጃዎች::

## 30.ስለ ጨረታ ውድድር ለህዝብ የማስተዋወቅ ሂደት

1. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ጨረታውን ለማስጀመር የሚያደርገውን የማስታዎቂያ ጥሪ በኢትዮጵያ ውስጥ በስፋት ተደራሽነት ባለው ጋዜጣ እና/ወይም በፍቃድ ሰጪው ባለስልጣን ድረ- ገፅና በሌሎች የመገናኛ ዘዴዎች የመወዳደሪያ የጨረታ ማስታዎቂያውን ያቀርባል፡፡
2. ጨረታውን ለማስጀመር የሚደረገው ጥሪ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡-

   ሀ) የጨረታ ውድድር ይሸፍነዋል ተብሎ የሚታሰበው የፍቃድ ቦታ ስም ወይም የስያሜ ቁጥር፤

   ለ) ሥፍራውን የሚያሳይ ካርታ፣ የታቀደውን ፍቃድ ወሰን የሚገልጽ የግሎባል ፖሲሽኒንግ ሲስተም ኮኦርዲኔት እና ማግኘት ከተቻለ የሳተላይት ምስል፤

   ሐ) ተጫራቹ ከኤሌክትሮኒክስ የጨረታ መረጃ ክፍል መረጃ ማግኘት የሚሜችልበት መንገድ፣ ለጨረታ ሰነዱ የሚያስፈልግ ክፍያ፣ ይፋዊ ያልሆነ ስምምነትን የሚገልጽ መረጃ፣፤ እንዲሁም ለተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና፤

   መ) የጨረታው መቀበያ እና የጨረታው መክፈቻ ቦታ፣ ቀን እና ሰዓት ፤ የጨረታ ማስከበሪያ ቦንድ ማስያዣ መጠንና ክፍያ፤ እና

   ሠ) በፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን በሚወሰን ተሳታፊነትን የሚያበረታታ ሌላ መረጃ፡፡

## 31.ስለጨረታ አቀራረብ

ተጫራቾች በጨረታ ሰነዱ ውስጥ በተመለከቱት መስፈርቶች መሠረት አስፈላጊ ሰነድ ማቅረብ እንዲሁም፦

1. የጨረታውን ሰነድ በተወሰነለት የጊዜ ገደብ ማቅርብ፤
2. የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ባዘጋጀው ፎርም አሰራር መሠረት የጨረታውን ሰነድ ማቅረብ፤
3. በፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የተረጋገጠ የጨረታ ማስከበሪያ በእያንዳንዱ ጨረታ ማካተት፤

4. በጨረታ ሰነዱ ላይ በተጠየቀው መሠረት የቴክኒክ አቅም፣ የሥራ ፕሮግራም፣ ተያያዥነት ያለው የበጀት መጠን፣ በሥራ ፕሮግራሙ መሥረት የጊዜ ሰሌዳ እና ጨረታው ካለፈ ለፕሮጀክቱ ማስፈፀሚያ ከአበዳሪ ድርጅቶች ጋር የተፈፀሙ ስምምነቶችን የሚያሳይ ደብዳቤ አያይዞ ማቅረብ፤
5. በጨረታ ሰነዱ ውስጥ በተጠቀሰው መሠረት የቀረበ የፋይናንስ እቅድ ማቅረብ፤
6. የተሟላ የፍቃድ ማመልከቻ ማቅረብ፤
7. በመጫረቻ ፖስታው ላይ የፍቃድ ቦታው ስምና የስያሜ ቁጥር እና "በጨረታው ማስታዎቂያ ላይ ከተገለፀው ቀን በፊት እንዳይከፈት" በመጻፍ ከጨረታ ማስከበሪያ ቦንድ ጋር በማያያዝ ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን በጨረታ ሰነዱ በተገለፀው አድራሻ በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት ሁለት (2) ኤሌክትሮኒክ ኮፒ በማያያዝ ማስገባት፤
8. በተጫራቾች መካከል ግጭት ወይንም ማስፈራራት የተከለከለ መሆኑን ማስገንዘብ፡፡

32.<u>በጨረታ ዉድድር ለመሳተፍ የሚያስፈልጉ ዝቅተኛ መመዘኛዎች</u>

1. በጨረታ አማካኝነት ፈቃዶች ተጫራቹ በአዋጁ እና በዚህ ደንብ ላይ የተቀመጡ መስፈርቶችን ማሟላት አለበት፡፡
2. ተጫራቾች እንደ አስፈላጊነቱ ቦንድ ያስይዛሉ፡፡
3. ተጨራቾች ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የሚያቀርበውን የቴክኒክና የፋይናንስ መመዘኛዎች ማሟላት አለባቸው፡፡
4. አንድ ተጫራች የጨረታው መቀበያ ጊዜ ካበቃ በኋላ ጨረታውን ማቋረጥ አይችልም፤ ጨረታውን መላክ በጨረታው ለመወዳደር ሕጋዊ ግዴታ ሆኖ ያገለግላል፡፡

33. <u>ጨረታን ውድቅ ስለማድረግ</u>

ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ጨረታን ውድቅ ሊያደርግ የሚችለው፡-

1. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ካስቀመጠው ዝቅተኛ የጨረታ ዋጋ በላይ የሆነ ጨረታ ከሌለ፤ እና

2. የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በጨረታ ሰነዱ ውስጥ ያስቀመጠውን የቴክኒክ እና የገንዘብ አቅም መስፈርትን የሚያሟላ ተጫራች እንደሌለ ካረጋገጠ፡፡

34.**<u>ስለጨረታ ሂደት እና አሸናፊነት</u>**

1. ጨረታዎች ማስታዎቂያ ከወጣበት ጊዜ አንስቶ ባሉት ዘጠና ቀናት ውስጥ ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡
2. የጨረታው ማስታዎቂያ በጋዜጣ ከወጣ ከዘጠና ቀናት በኋላ በማስታዎቂያው ላይ በተገለፀው ጊዜ ለህዝብ ክፍት ሆኖ በፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ይከፈታል፡-

   ሀ) ጨረታው የሚከፈተው የቀረቡትን ጨረታዎች ለህዝብ ለማሳወቅ እና ለመመዝገብ ነው፤

   ለ) በዚህ ጊዜ ማንኛውንም ዓይነት ጨረታ መቀበልም ሆነ ውድቅ ማድረግ አይቻልም፡፡
3. ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የተጫራቾችን ሰነድ ለጨረታ ገምጋሚ ኮሚቴ ያቀርባል፤የጨረታ ኮሚቴው ሚስጥራዊነቱን ጠብቆ የቴክኒካል እና ፋይናንስ ሁኔታ በመገምገም አሸናፊውን ይገልጻል፡፡
4. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን አሸናፊውን ተጫራች ለመምረጥ ጨረታ ገምጋሚ ኮሚቴው ያቀረበውን የግምገማ ውጤት ከግምት ውስጥ በማስገባት ያጸድቃል፡፡ ነገር ግን በጨረታ ገምጋሚ ኮሚቴው ውጤት የማይስማማ ከሆነ ጉዳዩን ከቀረበው ምክንያት ጋር ይመልሰዋል፡፡
5. ጨረታው ከተከፈተ በኋላ ባሉት ሃያ (20) ቀናት ውስጥ ፈቃድ ሰጭው ባለስልጣን በጨረታ ሰነዱ ላይ በተገለጸው መሠረት የጨረታ ማስከበሪያ ላስያዙ ተጫራቾች ውሳኔውን በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡
6. ጨረታው ላሸናፊው ከተገለጸና ከተላለፈ በስልሳ ቀናት ውስጥ በፍቃድ ሰጪው የተዘጋጁ ሁለት ኦሪጅናል የፍቃድ ሰነዶች እንዲሁም ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚነት ያለው የሀይል ግዥ ስምምነት እና ሌሎች የፕሮጀክት ሰነዶች ከአሸናፊነት ማስታዎቂያ ጋር ለጨረታው አሸናፊ ይላካል፡፡

7. ተጫራቹ ፈቃዱ ከተላለፈለት በኋላ ከአስራ አምስት ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ፍቃዱን አሸናፊ ስለመሆኑ እውቅና እና ተያያዥ ዶክመንቶችን ጨምሮ የፍቃድ ውሎችን መቀበሉን ለማረጋገጥ በሁለቱም ዋና የፍቃድ ሰነዶች ላይ ይፈርማል፡፡ የተፈረመበትን እያንዳንዱን የፍቃድ ዶክመንት ለፍቃድ ሰጪው ባለስልጣን ይመልሳል፡፡ በመመሪያው እንደተቀመጠው ለክልሎች የአንድ ዓመት የመሬት ኪራይ ክፍያ እና ሌሎች በጨረታው ላይ የተቀመጡትን ክፍያዎች ይከፍላል፡፡
8. የጨረታው አሸናፊ ፈቃዱን እንደወሰደ ለተቀሩት ተወዳዳሪዎች ለጨረታ ማስከበሪያ ያስያዙት ገንዘብ ይመለስላቸዋል፡፡
9. አንድ አሸናፊ ተጫራች በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ የፈቃድ ውሉን ካልፈፀመ ለጨረታ ያስያዘው ገንዘብ ተወርሶ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ፈንድ ውስጥ ይቀመጣል፡፡
10. የፍቃድ አሸናፊው የተፈፀመው በህጋዊ ወኪል በኩል ከሆነ፣ ህጋዊ ወኪሉ ጉዳዩን ማስፈፀም እንደሚችል የሚገልጽ የቦታውን ስም ወይንም መለያ ቁጥር የያዘ ህጋዊ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡
11. በአዋጁ አንቀጽ 9 የጂኦተርማል ሃብት ምዝገባ እንዲሁም በዚህ ደንብ መሠረት ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ስለ መረጃው መመዝገብ በጽሁፍ ለባለፍቃዱ ማሳወቅ አለበት፡፡
12. ፈፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ለውድድር የታቀዱ ቦታዎች ላይ ለመወዳደር የቀረቡ ጨረታዎችን በከፊል ወይም ሙሉ ለሙሉ ሊሰርዝ ይችላል፣ ነገር ግን ከጨረታ መወዳደሪያው ዝቅተኛ ዋጋ በላይ የሚቀርቡ ጨረታዎችን ላይሰርዝ ይችላል፡፡

35. <u>የጨረታ አሸናፊው የአከፋፈል ሁኔታ</u>

1. የተመረጠው ተጫራች በፈቃድ ሰጪዉ ባለሥልጣን ተቀባይነት ባለዉ መልኩ ክፍያዎችን መፈጸም አለበት፡፡
2. የጨረታው አሸናፊ በሚገለጽበት ቀን የሥራ ሰዓት ሳይጠናቀቅ ወይም የፍቃድ ሰጪው ባለስልጣን በሚወስነው ሌላ ጊዜ አሸናፊው ተጫራች ለእያንዳንዱ የፍቃድ ቦታ የሚከተሉትን ማስገባት ይኖርበታል፡-

ሀ) በጨረታ ሰነዱ ውስጥ እንደተመለከተው በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ተቀባይነት ያለው የክፍያ ሁኔታ እና ወይም የውል ስምምነት፤

ለ) ለመጀመሪያው ዓመት የመሬት ኪራይ ክፍያ፤ እና

ሐ) መፈፀም ያለባቸው የፈቃድ ክፍያዎች፡፡

3. የጨረታው አሸናፊ በሚኖረው የፋይናንስ ውል እና የጊዜ ገደብ መሠረት ተጨማሪ ክፍያዎችን ሊፈፅም ይችላል፡፡

4. የጨረታው አሸናፊ የሚጠበቅበትን ክፍያ መፈፀም ካልቻለ ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የጨረታውን ተቀባይነት ማገድ እና የተላከውን ማንኛውም ገንዘብ መያዝ ይችላል፣ እንዲሁም ተጫራቹ ያስያዘውን የጨረታ ማስከበሪያ ገንዘብ ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን በቅጣት መልክ ይከፍላል፡፡

36. <u>ስለተቃውሞ አቀራረብ</u>

1. ተጫራቾች የጨረታው ውጤት ከተገለጸ በኋላ ባሉት አስር የሥራ ቀናት ውስጥ የቅሬታቸውን አሳማኝ ምክንያት እና መረጃ በጽሁፍ በመግለጽ ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ሊያቀርቡ ይችሳላሉ፡፡

2. ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ተቃውሞውን ከተቀበለ በኋላ ተቃውሞው ውሳኔ እስኪያገኝ የጨረታና የፈቃድ ሂደቱን እና ከጨረታው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ክንውኖች በማቆም በሚቀጥሉት አስር የሥራ ቀናት ውስጥ መርምሮ ውሳኔውን ማሳወቅ አለበት፡፡

3. በጨረታው ተሳታፊ የቀረበ ተቃውሞ የቀረበው ምክንያት አሳማኝ ከሆነ ጨረታው በድጋሚ ሊታይ ወይም ደግሞ በፍቃድ ሰጪው ውሳኔ መሠረት ጨረታው ሊደገም ይችላል፡፡

37. <u>ስለይሁንታ ፈቃዶች እና ማረጋገጫዎች</u>

ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ከታክስ አተገባበር እና ከጉምሩክና ቀረጥ ነፃ ከመሳሰሉ ለባለፈቃዱ ከሚያስፈልጉት የተለያዩ የይሁንታ ፈቃዶችና ማረጋገጫዎች ኃላፊነቱን በአግባቡ በመወጣት እና በመተግበር በሚመለከተው የኢትዮጵያ ሕጎችና ደንቦች መሠረት ከሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ስለደረጃ 1 የጂኦተርማል ቁፋሮ ሥራዎች

### 38. ለቁፋሮ ሥራዎች አግባብነት ያላቸው አጠቃላይ መስፈርቶች

1. ለደረጃ 1 የጂኦተርማል ሀብት ልማት ቁፋሮ ሥራዎች የቁፋሮ ፈቃድና ለሥራዎቹ የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን በተመለከተ በዚህ ደንብ በሌላ አኳኋን ካልተገለጸ በስተቀር ሁሉም ከጉድጓድ ቁፋሮ በፊት የሚከናወኑ አስፈላጊ የመሠረተልማት ዝርጋታ እቅድና ልማት እና ለተመሳሳይ ሥራዎች የሚከናወኑ የፍሎው ቴስት፣ ጂኦተርማል ፈሳሾችን የማውጣት፣ ፈሳሾችን መልሶ ወደ ጂኦተርማል ሪዘርቫየሩ ሪኢንጄክት ማድረግ ወይንም ጉድጓዶችን መዝጋትና መተው በዚህ ክፍል መሠረት መተግበር አለባቸው፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ የቁፋሮ ሥራዎች የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርባቸዋል፡-

   ሀ) ሁሉንም የአካባቢ ደህንነት መስፈርቶችን አሟልቶ መገኘት፤

   ለ) የጂኦተርማል ሀብቱን መጠበቅ እና ብክነትን መቀነስ፤

   ሐ) በመሬት ላይ እና በከርሰ ምድር በሚገኙ እና በሌሎች ሀብቶች ላይ አላስፈላጊ ተፅዕኖዎችን እንዳያደርሱ መከላከል፤

   መ) የህዝብን እና የሠራተኛን ጤንነትና ደህንነት አግባብነት ያላቸውን ሕጎች በመከተል መጠበቅ፤

   ሠ) በዓለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎች ላይ በመመርኮዝ የሚወጡ መመሪያዎችን መከተል፤

   ረ) በአዋጁ እና በዚህ ደንብ የተቀመጡ ሁሉንም መስፈርቶችን ማሟላት፡፡

### 39. በፈቃድ ሰጪ ባለስልጣን የሚፀድቁ እና የሚሰጡ የይሁንታ ፈቃዶች

1. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን አግባብ ባለው ሁኔታ የሚከተሉትን ሊያፀድቅ ወይም የይሁንታ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡-

   ሀ) የቁፋሮ ዕቅድና ፕሮግራም፤

   ለ) ለአንድ ወይም ከአንድ በላይ ለሆኑ ጉድጓዶች የጉድጓድ ንድፍ ዕቅድ እና የቁፋሮ የይሁንታ ፈቃድ፤

2. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የቁፋሮ ፕሮግራሙን ሳያጸድቅለት ባለፈቃዱ በቁፋሮ ፕሮግራሙ የታቀዱ ምንም አይነት ሥራዎችን መጀመር አይችልም፡፡
3. በባለፈቃዱ በፀደቀ የቁፋሮ ዕቅድ፣ የቁፋሮ ፕሮግራም እና የጉድጓድ ንድፍ ዕቅድ ላይ የሚደረግ ማንኛውም ለውጥ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በጽሁፍ የተደረገውን ለውጥና ለለውጡ ምክንያት የሆኑትን ጉዳዮች በማብራራት የግምገማ ሪፖርት መቅረብ አለበት፡፡

40.<u>የቁፋሮ ዕቅድ ስለማፅደቅ</u>

1. ባለፈቃዱ የቁፋሮ ዕቅዱን ለማፅደቅ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚከተሉትን ማቅረብ ይኖርበታል፡-

   ሀ) የቁፋሮ ፕሮጀክቱን የተሟላ የልማት

   ለ) የጤንነትና ደህንነት ዕቅድ፤ እና

   ሐ) የመጀመሪያ ደረጃ የማመሳከሪያ የአካባቢ እና ማህበረሰብ ዳሰሳ ጥናት፡
2. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የቁፋሮ ዕቅዱ ሁሉንም የሕግ እና የቴክኒካል መስፈርቶችን አሟልቶ ሲገኝ ማመልከቻ በተቀበለ አስራ አምስት (15) የሥራ ቀናት ውስጥ ሊያፀድቀው ይችላል፡፡
3. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የቁፋሮ ዕቅዱን ካላፀደቀ ባለፈቃዱ በተሰጠው አስተያየት መሠረት የተሻሻለ ፕሮግራም እንዲያቀርብ ለማስቻል ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ያላፀደቀበትን ምክንያት በጽሁፍ መግለጽ ይኖርበታል፡፡
4. ባለፈቃዱ የቁፋሮ ዕቅዱ ከፀደቀለት በኋላ የሥራ ቦታ ማሻሻያን የመጀመር እና በተጨማሪም የአካባቢ ጥናት እና ማህበረሰብ አጠባበቅ ሥራ ሊያከናወን ቢችልም ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ለአንድ ወይንም ከአንድ በላይ ለሆኑ ጉድጓዶች የቁፋሮ ፕሮግራም እና የጉድጓድ ንድፍ ዕቅድ እስኪያጸድቅና የቁፋሮ ፈቃድ እስኪያገኝ ድረስ የቁፋሮ ሥራ መጀመር አይችልም፡፡

41. **<u>የቁፋሮ ፕሮግራም ስለማፅደቅ</u>**

1. የቁፋሮ ፕሮግራም ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ለዚሁ ተግባር በሚያዘጋጀው ቅጽ ላይ ተሞልቶ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

2. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የቁፋሮ ፕሮግራሙ ሁሉንም የሕግ እና የቴክኒካል መስፈርቶችን አሟልቶ ሲገኝ ማመልከቻ በተቀበለ አስራ አምስት (15) የሥራ ቀናት ውስጥ ሊያፀድቀው ይችላል፡፡

3. የቁፋሮ ኘሮግራሙ ለእያንዳንዱ ጉድጓድ የአካባቢያዊ እና ማህበራዊ ተፅዕኖዎችን ለመገምገም በቂ መረጃ መስጠት የሚኖርበት ሲሆን በተጨማሪም የሚከተሉትን ማቅረብ ይኖርበታል፡-

ሀ) የጉድጓድ መቆፈሪያ መደብ አቀማመጥ፤

ለ) የነባርና አዲስ ለታቀዱ የመዳረሻ መንገዶች ሁኔታ ማብራሪያ፤

ሐ) ማናቸውም አስፈላጊ የድጋፍ አገልግሎት መስጫና የመሠረተ ልማት አውታሮች ማብራሪያ፤

መ) ለጉድጓድ መቆፈሪያ መደብ እና ለመንገድ መገንቢያ የሚሆኑ ግብዓቶች መገኛ፤

ሠ) የውሃ መገኛዎች፣ ጥቅም ላይ የሚውሉበት ዓላማ፣ መጠን እና የመጠቀም ፈቃድ፤

ረ) የቁፋሮ ቦታውን ገፀ-ምድር ወደነበረበት ይዞታ የመመለስ ዕቅድ፤

ሰ) አካባቢን እና ሌሎች ሀብቶችን ለመጠበቅ የሚከናወኑ ተግባራት ማብራሪያ፤

ሸ) የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት፤

ቀ) የማህበራዊና ማህበረሰብ ጥናት ግምገማና አደጋ መከላከያ እርምጃዎች፣ እና

በ) ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ምክንያታዊ የሆኑ ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎችን በሚወጣ መመሪያ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

4. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የቁፋሮ ፕሮግራሙን ካላፀደቀ ባለፈቃዱ በተሰጠው አስተያየት መሠረት የተሻሻለ ፕሮግራም እንዲያቀርብ ለማስቻል ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ያላፀደቀበትን ምክንያት በጽሁፍ መግለጽ ይኖርበታል፡፡

42. <u>**የጉድጓድ ንድፍ ዕቅድ እና ጉድጓድ ቁፋሮ የይሁንታ ፈቃድ ማመልከቻ**</u>

1. ባለፈቃዱ የጉድጓድ ንድፍ ዕቅድ እና የቁፋሮ የይሁንታ ፈቃድ ማመልከቻ ከቁፋሮ ፕሮግራም ጋር በአንድ ላይ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. የጉድጓድ ንድፍ ዕቅድ ለእያንዳንዱ ጉድጓድ መቅረብ ያለበት ሲሆን ንድፉ አመቺ መሆኑን ምክንያታዊ በሆነ በግልጽ ለመወሰንና ለመረዳት የሚያስችል በቂ መረጃ መያዝ ይኖርበታል፤በተጨማሪም የጂኦሎጂካል ኢላማ ቦታዎችን፣ ማናቸውም የታቀደ አግድማዊ ቁፋሮ እና ዝርዝር የጉድጓድ ኬዚንግ ፕሮግራምና የሚጠቀሙበት ቁሳቁስ መረጃዎች ማብራሪያ ማካተት ይኖርበታል፡፡
3. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የጉድጓድ ንድፍ ዕቅድ እና የቁፋሮ የይሁንታ ፈቃድ ሁሉንም የሕግ እና የቴክኒካል መስፈርቶችን አሟልቶ ሲገኝ ማመልከቻውን በተቀበለ አስር የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት የሚኖርበት ሲሆን በነዚህ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ካልተሰጠ የጉድጓድ ንድፍ ዕቅዱ እና የቁፋሮ የይሁንታ ፈቃድ ጥያቄው እንደፀደቀ ይቆጠራል፡፡

43. <u>**ከአንድ ጉድጓድ በላይ ለመቆፈር ስለሚቀርብ ጥያቄ**</u>

1. የባለፈቃዱ የቁፋሮ ፕሮግራም ከአንድ በላይ ለሆኑ ጉድጓዶች ሊተገበር የሚችል ቢሆንም የጉድጓድ ቁፋሮ ሥራው በተመሳሳይ ሁኔታ የሚካሄድ ከሆነና እና ቀድሞ ከተደረገ ሳይንሳዊ የስነምድር ጥናት ውጤት በመነሳት ተመሳሳይ የጂኦሎጂና የጂኦተርማል ፈሳሽ ክምችት ሁኔታ እንደሚጠብቀው ካመነ መሆን አለበት፡፡
2. ባለፈቃዱ የጉድጓድ ንድፍ ዕቅድ እና የቁፋሮ የይሁንታ ፈቃድ ለእያንዳንዱ ለሚቆፈረው ጉድጓድ ማቅረብ የሚኖርበት ሲሆን እንዲሁም ከአንድ በላይ ለሆኑ ጉድጓዶች በተመሳሳይ ጊዜ ማቅረብ ይችላል፡፡

44. <u>**የቁፋሮ ሥራዎችን ስለማካሄድ**</u>

የጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ ለማካሄድ ቁፋሮ ከመጀመሩ በፊትና በቁፋሮ ጊዜ ባለፈቃዱ የሚከተሉትን መፈርቶች ማሟላት ይጠበቅበታል፡-

1. የጂኦተርማል ጉድጓድ ቁፋሮውን በቁፋሮ ፕሮግራሙ መሠረት እና ለባለፈቃዱ ከፀደቀው የጉድጓድ ንድፍ ዕቅድና የቁፋሮ የይሁንታ ፈቃድ ጋር በሚጣጣም መልኩ ለመቆጣጠር የሚችል በጂኦተርማል ጉድጓድ ቁፋሮ ብቁ የሆነ ባለሙያ ያለው፤
2. ተገቢውን የደህንነት ጥበቃ አሰራር በመቅረጽና በመተግበር ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የደህንነት ጥበቃውን በሚመለከተው የሕግ ማዕቀፍ መሠረት መከናወኑን የሚያረጋግጥ ወይንም የሕግ ማዕቀፉ በሌለበት ሁኔታ በአፍሪካ ህብረት የጂኦተርማል ቁፋሮ የአሰራር ኮድ መሠረት በሚወጣ መመሪያ ባገናዘበ መልኩ የሚያረጋግጥ ባለሙያ ያለው፤
3. ለባለሙያዎቹ በመደበኛ እና በአደጋ ጊዜ አሰራሮችን ፈጣን እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ማከናወን የሚያስችላቸው ስልጠና መስጠት፣
4. በአግባቡ ለሥራ ብቁ የሆኑ መሳሪያዎችን የሚጠቀም፤
5. ፈጣን እና ውጤታማ የሆነ የአስቸኳይ አደጋ ምላሽ የሚሰጡ የአፈፃፀም አሰራሮችን ተግባራዊ ማድረግ፤
6. በጉድጓድ ቁፋሮ ወቅት ሁሉንም ሥራዎች መቆጣጠር፣ የእያንዳንዱን ጉድጓድ ቁፋሮ ከመነሻ እስከ ማጠናቀቂያው በመከታተል በየቀኑ የሚከናወኑ ሥራዎችን ሪፖርት ለማድረግ የሚያስችል አሰራር መዘርጋትና ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን እነዚህን ሪፖርቶች እንደአስፈላጊነቱ በሚጠየቅበት ጊዜ ማቅረብ፤
7. ጉድጓዶቹ ሁልጊዜ በቁጥጥር ሥር መሆናቸውን ማረጋገጥ፤ እና
8. የደህንነት ጥበቃን በተመለከተ ውይይቶችን በመደበኛነት ማድረግ፡፡

## 45. <u>ለቁፋሮ ሥራዎች የአካባቢ፣ የጤንነት እና የደህንነት መስፈርቶች</u>

1. ባለፈቃዱ የቁፋሮ ሥራዎቹን መልኩ ማከናወን አለበት፡-

   ሀ) ከመሬት ላይ ወይም ከከርሰምድር የሚገኝ በሚከተለው ውሃ፣ አየር፣ የተፈጥሮ ሀብቶች፣ የዱር አራዊት፣ አፈር፣ ዕጽዋት እና ታሪካዊ ቦታዎችን የመጠበቅ፤

   ለ) ባህላዊ እሴቶችን፣ ውብ ተፈጥሯዊ ቦታዎችን እና የመዝናኛ ሀብቶችን መጠበቅ፤

   ሐ) ከሥራው ጋር የተያያዙ የድምፅ ሁከትን መቀነስ፤

መ) የንብረት ማጥፋትን እና አስፈላጊ ያልሆነ የመሬት ጉዳትን መከላከል፡፡

2. ባለፈቃዱ በሥራ ላይ የማይገኙ መሳሪያዎችንና ቁሳቁሶችን ማስወገድ ወይንም በተገቢው ሁኔታ ማስቀመጥ አለበት፡፡
3. ባለፈቃዱ ከቁፋሮ እና ከጉድጓዶች ፍተሻ የሚወጡ ፈሳሾችን በተገቢ ሁኔታ በተዘጋጁ በማቆሪያ ጉድጓዶች ወይም ታንከሮች ማስቀመጥ አለበት፡፡
4. ባለፈቃዱ የማቆሪያ ጉድጓዶቹ የማያስፈልጉትመ ከሆነ ቦታውን ፈቃዱን በወሰደበት ጊዜ ወደነበረበት ወይም ወደ ተሻለ ሁኔታ መመለስ አለበት፡፡
5. ባለፈቃዱ በአካባቢ ጥበቃ መስፈርቶች መሠረት ችግር ሲያጋጥም በአካባቢው ላይ የሚከሰተውን ማንኛውንም ተፅዕኖ ለመቀነስ ወዲያውኑ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት፡፡
6. ባለፈቃዱ ለሥራው የሚጠቀምባቸውን አደገኛ የሆኑ ኬሚካሎች እና ፈንጂዎች ለሥራው በሚያስፈልገው መጠን ብቻ መጠቀም ሲኖርበት በሚያጓጉዝበት እና በሚያከማችበት ጊዜ የዓለም አቀፍ መርሆዎችና ምርጥ ተሞክሮዎችን እና የኢትዮጵያን የሕግ ማዕቀፎች መከተል ይጠበቅበታል፡፡
7. ባለፈቃዱ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲከሰቱ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን እና ለአከባቢው መስተዳድር አካላት ወድያውኑ ማሳወቅ አለበት፡-

   ሀ) ጉድጓዱ ከቁጥጥር ውጪ ከሆነ፤

   ለ) በፈቃድ ቦታው እና በአካባቢው በሰው ላይ የሚደርሱ የአካል ጉዳት ወይም ሞት ጨምሮ በሰው እና በማህበረሰቡ ላይ አደጋ ያስከተሉ ወይም ሊያስከትሉ የሚችሉ አጋጣሚሚዎችን፤

   ሐ) ወደ አካባቢ የሚለቀቁ በዓይነት ወይም በመጠን ለአካባቢው ጎጂ የሆኑ ንጥረ ነገሮች፡፡
8. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የደህንነት ቁጥጥር ፕሮግራም ሊያወጣ የሚችል ሲሆን ይህም የደህንነት  ተቆጣጣሪን በመሰየም በጤናና ደህንነት መስፈርት መሠረት መከናወኑን ሊያረጋግጥ ይችላል፡፡

9. ፈቃዱን ለማፅደቅ ከቀረበው የጤናና ደህንነት ዕቅድ በተጨማሪ ባለፈቃዱ የህዝቡን ጤንነትና ደህንነት፣ የሰራተኛውን ደህንነት ወይንም አካባቢ ላይ ለሚደርስ አደጋ ፈጣን እና ውጤታማ የአስቸኳይ አደጋ ምላሽ የሚሰጡ የአስቸኳይ ጊዜ አፈጻጸም አሰራሮችን እንዲያቀርብ ፈቃድ ሰጭው ባለስልጣን ሊጠይቅ ይችላል፡፡

46. **ያአካባቢ ፈንድ ስለመመደብ**

1. በአዋጁ አንቀጽ 38(2) መሠረት ባለፈቃዱ ለዚህ ዓላማ በተከፈተ ዝግ የባንክ ሂሳብ ውስጥ የአካባቢ ፈንድ ማስቀመጥ አለበት፡፡
2. በባለፈቃዱ የሚቀመጠው የገንዘብ መጠን የሚወሰነው በፀደቀው የአካባቢያዊ እና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት መሠረት ሲሆን ለምርመራና የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማት እና የመጠቀም ፈቃድ ለየፕሮጀክቱ ጠቅላላ ሥራ ከሚወጣው ወጪ ከ0.1 በመቶ (0.1%) ያነሰ መሆን አይችልም፡፡
3. ባለፈቃዱ ለፈቃድ ሰጭው ባለስልጣን ፈንዱን ስለማስቀመጡ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

47. **የአካባቢ ፈንድ ስለመልቀቅ**

ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ባለፈቃዱ የአካባቢ ፈንዱ እንዲለቀቅለት በሚጠይቅበት ጊዜ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን ሲያረጋግጥ ይለቅለታል፡-

1. ከተቋረጠ ወይም ከተሰረዘ እና ባለፈቃዱ የፍቃድ ቦታውን ፈቃዱ ከመሰጠቱ በፊት ወደነበረበት ወይም ወደተሻለ ሁኔታ መልሶ ካስተካከለ፤ ወይም
2. ፈቃዱ ወደ ሌላ ሰው ከተላለፈ እና ተመሳሳይ መጠን ያለው ፈንድ በአዲሱ ባለፈቃድ ከተተካ፡፡

48. **ማስረጃ ስለማረጋገጥ**

1. ሁሉም የቁፋሮ ሰራተኞች የቁፋሮ ሥራ ከመጀመራቸው በፊት በዓለም አቀፍ ደረጃ በተገቢው ሁኔታ የተረጋገጠ የትምህርት ማስረጃ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ማስረጃው በ የሁለት ዓመቱ መታደስ ይኖርበታል፡፡

2. የጉድጓድ መዝገያውን ማገናኛ መበየድ የሚገባው የበያጅነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው በያጅ መሆን የሚገባው ሲሆን የሚበየድበት ዕቃዎችም ለዚሁ ተግባር በተወሰነው መመሪያ መሠረት መሆን ይገባዋል፡፡

49. **<u>የደረጃ 2 የጂኦተርማል ሀብት ጉድጓድ ቁፋሮ ወደ ደረጃ 1 የሚተላለፍበት ሁኔታ</u>**

1. በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ወይም በሚመለከተው የክልል ባለሥልጣን የተሰጠ የደረጃ 2 የጂኦተርማል ሀብት ፈቃድ በሚከተሉት ሁኔታ በቁፋሮ ጊዜ ያለውን ሙቀት ከሚፈለግበት ነጥብ ጥልቀት በአስር ዲግሪ ሴልሺየስ ሊደርስ እንደሚችል ወይም ከደረሰና ከአካባቢው ውሃ ልክ ጋር ሲታይ ወዲያውኑ የቁፋሮ ሥራውን በማቆም ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በማሳወቅ ለደረጃ 1 የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማት እና የመጠቀም ፈቃድ በሚካሄድበት ሂደት መከናወን ይገባዋል፡፡
2. አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጹት ክስተቶች ሲኖሩ ባለፈቃዱ ፕሮጀክቱን የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ባስቀመጠው መስፈርት ሊቀጥል ይችላል ወይም ለደረጃ 1 የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማት እና የመጠቀም ፈቃድ በአዋጁና ደንቡ መሠረት ማልማት ይችላል፤ ካልሆነም የደረጃ 2 የጂኦተርማል ሀብት ፈቃዱንና ይዞታውን መመለስ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሚመለከተው የክልል መንግሥት የደረጃ 2 የጂኦተርማል ሀብት ፈቃድ ላይ የሚከናወኑ የቁፋሮ ሥራዎች የምስክር ወረቀትን ጨምሮ የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ አሰራር ሂደትን ተከትሎ ይከናወናል፡፡

## <u>ክፍል ሰባት</u>

## <u>ስለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቶች</u>

50. **<u>ለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>**

1. በአዋጁ አንቀጽ 34 መሠረት በጂኦተርማል አማካሪነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ማመልከቻ ያቀረበ ማንኛውም አመልካች የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል:-

ሀ) አመልካቹ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ፡-

1) ሙሉ ስሙን፣ጾታውን፣ እድሜውን፣ ዜግነቱን፣የትውልድ ቀንና ቦታ፤
2) የመታወቂያ ቅጂ፤
3) የመኖሪያ ቦታውንና አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የኢሜይል አድራሻ፤
4) ሙያውን፤
5) የትምህርት ማስረጃ ቅጂ እና በመመሪያ በሚገለጸው መሠረት አግባብ ያለው የሥራ ልምድ ማስረጃ፤
6) የማማከር ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የጠየቀበትን የሙያ ዘርፍ፣
7) ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በመመሪያ የሚወስናቸው ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎች፡፡

ለ) አመልካቹ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ከሆነ፡-

1) ስሙን ፣ ዜግነቱን ፣ የሕግ አቋሙንና የንግድ ሁኔታ፤
2) የዋና ቢሮውን አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የኢሜይል አድራሻ፤
3) በድርጅቱ የተቀጣሪ ባለሙያዎች የትምህርት፣ የሥራ ውል እና በመመሪያ በሚገለጸው መሠረት አግባብ ያለው የሥራ ልምድ ማስረጃ፤
4) አግባብ ባለው የመንግስት መስሪያ ቤት የተረጋገጠ ድርጅቱ የተቋቋመበት የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ቅጂዎች፤
5) በአመልካቹ ድርጅት ስም ለመፈረም ስልጣን የተሰጠውን ኃላፊ ስም እና ማንነት የሚገልጽ ማስረጃ፣ አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የኢሜይል አድራሻ፤
6) የውጪ ዜጋ ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ እንዲሰራ መብት የሚሰጥ ፈቃድ፤
7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ (ሀ) ስር ከ(6) እስከ (7) የተጠቀሱትን መረጃዎች፡፡

2. በጂኦተርማል ለቴክኒክ ነክ ሥራዎች ለሚሰጡት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማመልከቻ ያቀረበ ማንኛውም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አመልካች የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡-

ሀ) ስሙን ፣ ዜግነቱን ፣ የሕግ አቋሙን የንግድ ሁኔታ፤

ለ) የዋና ቢሮውን አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የኢሜይል አድራሻ፤

ሐ) በድርጅቱ የተቀጣሪ ባለሙያዎችን የትምህርት፣ የሥራ ውል እና በመመሪያ በሚገለጸው መሠረት አግባብ ያለው የሥራ ልምድ ማስረጃ፤

መ) አግባብ ባለው መስሪያ ቤት የተረጋገጠ ድርጅቱ የተቋቋመበት የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ቅጂዎች፤

ሠ) በአመልካቹ ድርጅት ስም ለመፈረም ስልጣን የተሰጠውን ኃላፊ ስም እና ማንነት የሚገልጽ  ማስረጃ፣ አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና የኢሜይል አድራሻ፤

ረ) የውጭ ዜጋ ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ እንዲሰራ መብት የሚሰጥ ፈቃድ፤

ሰ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በፊደል ተራ (ሀ) ስር ከ(6) እስከ (7) የተጠቀሱትን መረጃዎች፤

ሸ) የጂኦተርማል የቴክኒክ ነክ ሥራዎች ወይም ለጂኦተርማል ምክር አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የጠየቀበትን ዘርፍ፤

ቀ) የተገለጸውን ሥራ ለመፈፀም የሚያስችል ቴክኒካዊ እና የገንዘብ አቅም ጋር የተያያዘ መረጃ፡፡

3. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የጂኦተርማል የቴክኒክ ነክ ሥራዎች ብቃት እና የጂኦተርማል የማማከር የምስክር ወረቀት በየሙያው ዘርፉ ሊለያይ ይችላል፡፡

51. <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት</u>

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 50 (1) እና (2) መሠረት ተሟልቶ የቀረበ ማመልከቻ ተገቢው የማመልከቻ ክፍያ እንደተፈፀመ ይመዘገባል፤
2. ከማመልከቻው ጋር ተያይዘው የቀረቡ ሰነዶችን ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ማመልከቻውን ከተቀበለ በኋላ ባሉት አስር (10) የሥራ ቀናት ውስጥ በመመሪያው በሚወሰነው መስፈርት መሠረት የሚያሟላ መሆኑን በማጣራትና በመገምገም የምስክር ወረቀት ይሰጣል ወይንም የማያሟላበትን ምክንያት በጽሁፍ በመግለጽ ሊከለክል ይችላል፡፡

52. <u>***የብቃት ማረጋገጫ ፀንቶ የሚሚቆይበት ጊዜና ዕድሳት***</u>

1. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለሁለት ዓመት የፀና ይሆናል፡፡
2. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ፀንቶ የቆየበት ጊዜ ካለቀ በኋላ በየዓመቱ መታደስ አለበት፡፡
3. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ዕድሳቱን የሚፈጽመው ባለፈቃዱ በገባው ግዴታና መለኪያ መሠረት ማከናወኑን ካረጋገጠ በኋላ ይሆናል፡፡
4. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለቤት በተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መሠረት የሙያው ሥነ-ምግባርና የቴክኒክ ብቃቱ የሚጠይቀውን ግዴታ ያልተወጣ መሆኑ ከተረጋገጠ የምስክር ወረቀቱ አይታደስም፡፡
5. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የዕድሳት ማመልከቻውን ካልተቀበለ በአስር የሥራ ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

53. <u>***የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለመሰረዝ***</u>

1. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በሚከተሉት ምክንያቶች የብቃት ማረጋገጫውን ሊሰርዝ ይችላል፡-

   ሀ) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ የተሳሳተ ማስረጃ በማስገባት የተገኘ መሆኑ ከተረጋገጠ፤

   ለ) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለቤት የጂኦተርማል ዘርፉ የሚጠይቀውን ወቅታዊ ብቃትና ቴክኖሎጂ ያገናዘበ እንዲሁም ሙያዊ ሥነ-ምግባርን ያሟላ አገልግሎት መስጠት አለመቻሉ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ከተረጋገጠ የምስክር ወረቀቱ ጸንቶ የሚቆይበት ዘመን ከማለቁ በፊት ሊሰረዝ ይችላል፤

   ሐ) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የያዘ ሰው የዚህን ደንብ ወይም ደንቡን ለማስፈፀም የወጡትን መመሪያዎች ድንጋጌዎች ወይም መመሪያዎች ካላከበረ ወይም የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ከተቀበለ በኋላ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የማስተካከያ እርምጃዎችን ካልወሰደ ሊሰረዝ ይችላል፡፡

2. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ከተሰረዘበት ከአንድ ዓመት በኋላ አዲስ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሊጠይቅ ይችላል፡ ፡ሆኖም አመልካቹ ፈቃዱ ለመሰረዙ ምክንያት የነበሩትን ቀደምት ስህተቶች ማስተካከል እና በፈቃድ ሰጭ ባለስልጣን የተቀመጠውን ሁሉንም መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡፡
3. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰረዘበት ወይም ሥራውን ያቆመ ማንኛውም ሰው የብቃት ማረጋገጫውን ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን መመለስ አለበት፡፡

## ክፍል ስምንት
## ጥፋቶችና አስተዳደራዊ ቅጣቶች

### 54. አንደኛ ደረጃ ጥፋቶችና አስተዳደራዊ ቅጣቶች፡-

1. ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) በቅድሚያ ተገቢውን ፈቃድ ሳይዝ በጂኦተርማል ሥራ ላይ ከተሰማራ፤

ለ) ከፈቃድ ማመልከቻ ወይም ፈቃድ ወይም ከብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ጥያቄና እድሳት ጋር በተያያዘ ሁኔታ ሀሰተኛ መረጃ ከሰጠ ወይም ካጭበረበረ፤

ከሁለት መቶ ሺ.ህ (200,000) ብር እስከ ሶስት መቶ ሺ.ህ (300,000) ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

2. ማንኛውም ባለፈቃድ፡-

ሀ) የጂኦተርማል ሥራውን በአዋጁ፣ በዚህ ደንብና ይህን ደንብ ለማስፈፀም በሚወጡ መመሪያዎች መሰረት ቴክኖሎጂውና የጂኦተርማል ኢንደስትሪው ተቀባይነት ባገኘ አሰራር ልምድ ካላከናወነ፤

ለ) ዘላቂነት በሌለው መልኩ እና ከሪዘርቫየር ኢንጅነሪንግ ሪፖርት ጋር ወጥነት የሌለው የጂኦተርማል ሥራ ካከናወነ፤

ሐ) ከፈቃድ መብቱ ጋር በተያያዘ ማንኛውንም የማጭበርበር ድርጊት ከፈጸመ፣ ወይም ከጂኦተርማል ሥራው ጋር በተያያዘ ሀሰተኛ መረጃ ከሰጠ፤

መ) የተፈጥሮ አካባቢን፣ ጤንነትን፤ ደህንነትን፣ ወይም ሌሎች የጂኦተርማል ሥራዎችን የሚመለከቱ ግዴታዎችን ከጣሰ፤ ወይም

ሠ) በተጨባጭ ሁኔታ የጂኦተርማል ሥራዎችን የሚመለከቱ አስተዳደራዊና የገንዘብ ግዴታዎችን ካላሟላ፤

ከአንድ መቶ ሺህ (100,000)ብር እስከ አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ (150,000) ብር በማሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡ እንዲሁም አጥፊው ያንኑ ጥፋት ደግሞ ከፈጸመ የገንዘብ ቅጣቱ በእጥፍ ሊጨምር ይችላል፡፡

55. <u>ሁለተኛ ደረጃ ጥፋቶች እና ቅጣቶች፡-</u>

ማንኛውም ባለፈቃድ፡-

1. እንደአግባቡ በዚህ ደንብ አንቀጽ ድንጋጌዎች የተመለከቱትን ተፈላጊ መዝገቦችና ሪከርዶችን ወይም ሌሎች ሰነዶችን በተገቢው መልኩ ካልያዘ ወይም መሠረታዊ በሆኑ ነጥቦች ላይ ትክክለኛ ያልሆኑ ወይም ያልተሟሉ መዝገቦችንና ሪከርዶችን ከያዘ ወይም ተፈላጊ ሪፖርቶችን ወይም ሌሎች ሰነዶችን ካላቀረበ ወይም ተፈላጊ ማስታወቂያዎችን ካልሰጠ፤
2. በአግባቡ ስልጣን የተሰጠው የፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ሠራተኛን ወደ ፈቃዱ ክልል ወይም የጂኦተርማል ሥራዎች የሚካሄዱባቸው ቦታዎች ወይም ተቋሞች እንዳይገባ ከከለከለ ወይም የባለፈቃዱን መዝገቦች፣ ሪከርዶች ወይም ሌሎች ሰነዶች እንዳያይ ካደረገ ወይም በሠራተኛው የተሰጠውን ሕጋዊ ትዕዛዝ ወይም መመሪያ ካልፈጸመ፤
3. የማማከር እና የቴክኒክ አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለቤት የጂኦተርማል ዘርፉ የሚጠይቀውን ወቅታዊ የሙያ ብቃትና ቴክኖሎጂ ያገናዘበ እንዲሁም ሙያዊ ሥነ ምግባርን ያሟላ አገልግሎት መስጠት ካልቻለ፤ የፈጸመውን የጥፋት ድርጊት ለማረም ወዲያውኑ እርምጃ ከወሰደ ከሃምሳ ሺህ (50,000) ብር እስከ ሰማንያ ሺህ (80,000) ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤ ጥፋቱን ለማረም ወዲያውኑ የእርምት እርምጃ ካልወሰደ የገንዘብ ቅጣቱ እጥፍ ይሆናል፤ ጥፋቱ በማንኛውም ሰው ጤንነት ወይም ደህንነት፣ በተፈጥሮ አካባቢ ወይም በጂኦተርማል ሀብቱ ላይ ሊደርስ የተቃረበ ወይም ቀጣይነት ያለው ጉዳት ካስከተለ፣ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ባለፈቃዱ ጥፋቱን እስከሚያስተካክል ድረስ የጂኦተርማል ሥራዎቹን ወዲያውኑ እንዲያቆም ያደርጋል፤ የጥፋቱ ድርጊት ወይም ሁኔታ እስኪስተካከል ፈቃዱ ታግዶ ይቆያል፡፡

56. **ሶስተኛ ደረጃ ጥፋቶች እና ቅጣቶች፡-**

ማንኛውም ባለፈቃድ፡-

1. መሠረታዊ በሆኑ ነጥቦች ላይ ትክክለኛ ያልሆኑ ወይም ያልተሟሉ መዝገቦችንና ሪኮርዶችን የመያዝ ጉድለቶችን ሳይጨምር የተሟሉ ትክክለኛ የሆኑና ወቅታዊውን ሁኔታን የሚያሳዩ መዝገቦችንና ሪከርዶችን ካልያዘ፤
2. ተፈላጊ ሪፖርቶችንና ሌሎች ሰነዶችን በወቅቱ ካላቀረበ ወይም ተፈላጊ መግለጫዎችን በወቅቱ ካልሰጠ፤ ወይም
3. ጥፋቱ የማንኛውንም ሰው ጤንነት ወይም ደህንነት፣ የተፈጥሮ አካባቢን ወይም የጂኦተርማል ፈሳሽ ክምችቱን አደጋ ላይ የማይጥል ቢሆንም የጂኦተርማል ሥራዎቹን ተገቢ በሆነ መንገድና በጥንቃቄ ካላካሄደ ወይም ደንቦችንና መመሪያዎችን ካላከበረ፤

   ማስጠንቀቂያ እንደደረሰው ወዲያውኑ የእርምት እርምጃ ካልወሰደ ወይም የጥፋት ድርጊቱ ሊታረም የማይችል ከሆነ ከሰላሳ ሺህ (30,000)ብር እስከ ሃምሳ ሺህ (50,000) ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡
4. ማንኛውም ባለፈቃድ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2 እና 3) የተፈፀመ ጥፋት የቀጣይነት ወይም  የተደጋጋሚነት ባህርይ ያለው ሆኖ ሲገኝ ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ጥፋቱን እንደቅደም ተከተሉ አንደኛ ደረጃ ወይም ሁለተኛ ደረጃ ጥፋት አድርጎ ሊቆጥረውና ባለፈቃዱም በዚሁ ሊቀጣ ይችላል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

57. **ከጂኦተርማል ጋር የተያያዙ ናሙናዎችን ወደ ውጪ ስለመላክ**

1. በአዋጁ አንቀጽ 30 መሠረት ማንኛውም የጂኦተርማል ሥራ ባለፈቃድ የጂኦተርማል ናሙናዎች ለላቦራቶሪ ምርመራ ወደ ውጪ አገር መላክ የሚችለው ፈቃድ ሰጪውን ባለስልጣን በማስፈቀድ እና ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በመፈፀም ይሆናል፡፡

2. አመልካቹ በምርምር ተቋማት የሚሠራ ወይም በውጪ አገር ከፍተኛ ትምህርት በመከታተል ላይ የሚገኝ ሰው ከሆነ የጄኦተርማል ናሙናዎቹ ለትምህርታዊ ምርምር አስፈላጊ መሆናቸውን የሚገልጽ አግባብ ካለው ተቋም የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
3. በአዋጁ አንቀፅ 30 (2) መሠረት የጄኦተርማል ናሙና ለመላክ ለሚፈልግ የጄኦተርማል ሥራ ባለፈቃድ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡-
   ሀ) ከፍተኛ ሙቀት ካላቸው ጉድጓዶች፣ ሞቃታማ ምንጮች እና የሞቀ ውኃ ጉድጓዶች በአንድ ነጠላ ናሙና ከፍተኛው አምስት (5) ሊትር ፈሳሽ፤
   ለ) በአንድ ጉድጓድ እስከ ሁለት ነጥብ አምስት(2.5) ቶን ኮር ወይም የድንጋይ ናሙና፡፡
4. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በዚህ ደንብ እና በሚወጣው መመሪያ መሠረት ከጂኦተርማል ጋር ተያያዥነት ያላቸው ናሙናዎችን ለመላክ ሊወስን ይችላል፡፡

58.<u>ስለቅጥርና ሥልጠና</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 22 (1) ፊደል ተራ (ሸ) ስለቅጥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ባለፈቃድ አንድን የሥራ መደብ ለመሙላት ብቁ የሆነ ኢትዮጵያዊ ማግኘት አለመቻሉን የሚያስረዳ ማስረጃ ሲያቀርብና ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን አረጋግጦ ፈቃድ ሲሰጥ ብቁ የሆነ የውጭ አገር ዜጋ ሊቀጥር ይችላል፡፡
2. ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚቀጠሩት የውጭ አገር ዜጐችና ቤተሰቦቻቸው ወደ አገር ውስጥ የመግቢያና የመኖሪያ ፈቃድ ከሚመለከተው የመንግሥት መስሪያ ቤት እንዲያገኙ ድጋፍ ያደርጋል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የውጪ አገር ዜጋ እንዲቀጥር የተፈቀደለት ባለፈቃድ አግባብ ያለው ክህሎትና ዕውቀት የሚተላለፍለት ተተኪ ኢትዮጵያዊ ሠራተኛ አብሮ የሚሠራበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርበታል፡፡

4. የውሙመራ አገር ዜግነት ያለው ባለሙያዕውቀቱንና ክህሎቱን ለኢትዮጵያዊ ሠራተኛ በበቂ ሁኔታ ለማስተላለፍ የሠራበት ጊዜ በቂ መሆኑን ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በክትትል ሂደት ሲያረጋግጥ ባለፈቃዱ የውጪ አገር ዜጋውን በኢትዮጵያዊ ባለሙያ መተካት አለበት፡፡
5. የሠራተኛ ቅጥር ሁኔታና ሥልጠና አሠጣጥ ከሥራው ባህርይና ደረጃ ጋር የተጣጣመ እንዲሁም ሥራውን በተቀላጠፈና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ ማካሄድ የሚያስችል መሆን ይኖርበታል፡፡

59.**<u>የፈቃድ ክፍያዎች</u>**

ፈቃድ ለማውጣት የሚጠይቅ አመልካች በአዋጁ አንቀጽ 45 መሠረት የሚከፍለው የፈቃድ ክፍያ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

1. የቅኝት የማመልከቻ ክፍያ..........500 ብር
2. የምርመራ የማመልከቻ ክፍያ ............ 500 ብር
3. ለደረጃ 1 የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማት እና የመጠቀም ፈቃድ የማመልከቻ ክፍያ.......500ብር
4. የደረጃ 11 የጂኦተርማል ሀብት ማመልከቻ ክፍያ ..............500 ብር
5. የቅኝት ፈቃድ ክፍያ ..........4000 ብር
6. የምርመራ ፈቃድ ክፍያ.......5050
7. ለደረጃ 1 የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማት የመጠቀም ፈቃድ ክፍያ .....9560 ብር
8. የደረጃ 11 የጂኦተርማል ሀብት ፈቃድ ክፍያ.....5050 ብር

60.**<u>የፈቃድ እድሳት ክፍያ</u>**

ፈቃድ ለማደስ የሚጠይቅ አመልካች በአዋጁ አንቀጽ 45 መሰረት የሚከፍለው የፈቃድ ክፍያ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

1. የምርመራ ፈቃድ እድሳት ክፍያ .......3320 ብር
2. ለደረጃ 1 የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማት ሺ ብበ እና የመጠቀም ፈቃድ የእድሳት ክፍያ......7000 ብር
3. የደረጃ 11 የጂኦተርማል ሀብት ፈቃድ እድሳት ክፍያ......... 3320 ብር

61.<u>የምትክ ወይም ተጨማሪ የፈቃድ ቅጂ ክፍያ</u>

በባለ ፈቃዱ ለጠፋ፣ የተቃጠለ፣ የተበላሸ፣ የተሰረቀ ወይም ተጨማሪ የፈቃድ ወይም የምስክር ወረቀት ቅጂ የሚከፈለው ክፍያ የሚከተሉት ናቸው፡

1. የቅኝት ፈቃድ የምስክር ወረቀት .......300 ብር
2. የምርመራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት......300 ብር
3. ለደረጃ 1 የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማት እና የመጠቀም ፈቃድ የምስክር ወረቀት..... 300 ብር
4. የደረጃ 11 የጂኦተርማል ሀብት ፈቃድ የምስክር ወረቀት .......300 ብር
5. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት........300 ብር
6. ሌላ ሰነድ በገጽ ............................ 50 ብር

62.<u>ፈቃድ የማስተላለፊያ ክፍያ</u>

በባለ ፈቃዱ የሚከፈል የፈቃድ ለውጥ ክፍያ የሚከተሉት ናቸው:-

1. የምርመራ ፈቃድ ምስክር ወረቀት.... 1010 ብር
2. ለደረጃ 1 የጂኦተርማል ጉድጓድ መስክ የማልማት እና የመጠቀም ፈቃድ..............1010ብር
3. የደረጃ 11 የጂኦተርማል ሀብት ፈቃድ የምስክር ወረቀት.......... 1010 ብር

63.<u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አገልግሎት ክፍያ</u>

1. የማማከር አገልግሎት የምዝገባ ክፍያ......100 ብር
2. የቴክኒክ የቴክኒክ ነክ አገልግሎት የምዝገባ ክፍያ .......1010 ብር
3. የማማከር አገልግሎት የፈቃድ ክፍያ 4000 ብር
4. የቴክኒክ የቴክኒክ ነክ አገልግሎት ፈቃድ ክፍያ .....2650 ብር
5. የማማከር አገልግሎት እድሳት ክፍያ...... 200 ብር
6. የቴክኒክ ነክ አገልግሎት የእድሳት ክፍያ ......200 ብር

64.<u>ልዩ ልዩ የአገልግሎት ክፍያዎች</u>

በባለ ፈቃዱ የሚከፈል ልዩ ልዩ የአገልግሎት ክፍያዎች የሚከተሉት ናቸው:

1. የናሙና መላኪያ

   ከ10 ኪሎ በታች በጥቅል ............... 50 ብር

   ከ20 ኪሎ በታች በጥቅል..............100 ብር

   ከ20 ኪሎ እና ከዚያ በላይ በጥቅል......200 ብር

2. የጉድጓድ ቁፋሮ የይሁንታ ፈቃድ በጉድጓድ.......1050 ብር

65. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ 15 ቀን 2011 ዓ.ም**

**ዶ/ር አብይ አህመድ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ክፍል 20

## ትራንስፖርትና መገናኛ

### ሀ/ የመንገድ ትራንስፖርት

### የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 261/1955

### የተሽከርካሪ መኪናዎች ክብደትና ልክ መወሰኛ ደንብ

### ስለ ትራንስፖርት በ1935 ዓ.ም በወጣው አዋጅ መሠረት የወጣ ደንብ

1. የሥራና መገናኛ ሚኒስትር፣ ስለ ትራንስፖርት በ1935 ዓ.ም በቁጥር 35 በወጣው አዋጅ (በዚህ ደንብ ውስጥ "አዋጅ" ተብሎ በሚጠቀሰው) በ59ኛው አንቀጽ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡
2. ይህ ደንብ የ1955 ዓ.ም "የተሽከርካሪ መኪናዎች ክብደትና ልክ መወሰኛ ደንብ" ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል፡፡

**ትርጓሜ**

3. በዚህ ደንብ ውስጥ በቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም እንዲሰጠው ካላስፈለገ በቀር፣
   ሀ) የተፈቀደለት ሹም" ማለት ይህን ደንብና ወደፊትም እንዳስፈላጊነታቸው ተለይተው በሚነገሩ መንገዶች ላይ ስለሚካሄደው የትራንስፖርት ሥራ የሚወጡትን ሌሎች ደንቦች ለማስፈጸም ከመገናኛ ክፍል ዋና መሥሪያ ቤት[62] በሚገባ የተፈቀደለት ሰው ነው፡፡
   ለ) "የአክስ ጭነት" ማለት አንድ ተሽከርካሪ መኪና በርዝመቱ አቅጣጫ በሚገኙት አማካይ ሥፍራዎች አንድ ሜትር ወይም ከዚህ ባነሰ ርቀት በተደረጉት እግሮቹ ለሚጓዙበት አውራ ጐዳና የሚያስተላልፈው ጠቅላላ ክብደት ነው፡፡
   ሐ) "የንግድ ተሽከርካሪ መኪና" ትርጉሙ በአዋጁ ውስጥ እንደተመለከተው ነው፡፡
   መ) "የመንገድ ትራንስፖርት መቆጣጠር ሥራ ዲሬክተር" ማለት ይህ ደንብ ጸንቶ እንዲሠራበት ለማድረግና አፈጻጸሙንም ለመጠባበቅ ከሥራና መገናኛ ሚኒስትር[63] የተሾመ ሰው ነው፡፡
   ሠ) "አውራ ጐዳና" ማለት ከግል መንገዶች በቀር በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛት ውስጥ የሚገኙት ማናቸውም ዓይነት መንገዶች ናቸው፡፡

[62] የመገናኛ ክፍል ዋና መስሪያ ቤት ተብሎ የተገለፀው የትራንስፖርት ሚኒስቴር ወይም የትራንስፖርት ባለስልጣን ሆኗል፡፡

[63] በ22/12 (2008) አ. 916 አንቀጽ 9 (12) መሰረት የትራንስፖርት ሚኒስቴር ወይም የትራንስፖርት ባለስልጣን ሆኗል፡፡

ረ) “ባለሞተር ተሽከርካሪ መኪና” ትርጉሙ በአዋጁ ውሰጥ እንደተመለከተው ነው፡፡

ሰ) “ኦምኒበስ አውቶመቢል” ትርጉሙ በአዋጁ ውስጥ እንደተመለተው ነው፡፡

ሸ) “ያደባባይ የኪራይ ተሽከርካሪ መኪና” ትርጉሙ በአዋጁ ውስጥ እንደተመለከተው ነው፡፡

ቀ) “ግማሽ ተሳቢ” ማለት ለመንገደኞች ወይም ለጭነት ማጓጓዣ የሚያገለግልና ሞተር ባለው በሌላ መኪና የሚሳብ ሆኖ ነጠላ ክብደቱና የተሸከመውም የጭነቱ ክብደት ጭምር በከፊል በሌላው መኪና ላይ እንዲያርፍ ወይም በሌላው መኪና እንዲሳብ ተደርጎ የተሠራ ማናቸውም ተሽከርካሪ ነው፡፡

በ) “ተሳቢ” ማለት ለራሱ የተለየ የሞተር ኃይል የሌለውና ጐታች በሆነ በሌላ ተሽከርካሪ መኪና ላይ ሊቀጠልና ሊጐተት የሚችል ጠቅላላ ክብደቱ በጐታቹ መኪና ላይ እንደሚያርፍ ተደርጎ የተሠራ ማናቸውም ተሽከርካሪ ነው፡፡

ተ) “ጐታች መኪና” ማለት በተለይ ሌሎች ተሽከርካሪዎችን ለመጐተቻ የሚያገለግል ሆኖ የተጐታቹ ተሽከርካሪ ነጠላ ክብደቱና ጭነቱም ጭምር በሱ ላይ እንደሚያርፍ ተደርጎ የተሠራ ማናቸውም ተሽከርካሪ ነው፡፡

**<u>ተሽከርካሪ መኪናን ማንቀሳቀስና መንዳት ስለ መከልከል</u>**

4. ከዚህ ቀጥሎ በተመለከተው አኳኋን ካልሆነ በቀር ማንም ሰው በማናቸውም መንገድ ላይ ልኩና ክብደቱ ከዚህ ደንብ ውስጥ ከተወሰነው በላይ የሆነ ማናቸውም ተሽከርካሪ መኪና እንዳይነዳ ወይም እንዳያንቀሳቅስ ወይም ማንኛውም የተሽከርካሪ ባለቤት እያወቀ ተሽከርካሪው እንዲንቀሳቀስ ወይም ተነድቶ እንዲሄድ እንዳያደርግ ወይም እንዳይፈቅድ ተከልክሏል፡፡

**<u>የተሽከርካሪዎችን የትልቅነት ልክ ስለ መወሰን</u>**

5. ሀ) ማናቸውም ባለሞተር ተሽከርካሪ መኪና ወይም ተሳቢ ወይም ግማሽ ተሳቢ፣ ጭነት ቢኖረውም ባይኖረውም ጠቅላላ የጐኑ ስፋት ከውጭ በኩል እየተለካ ከ2 ሜትር ከ50[64] መብለጥ የለበትም፡፡

ለ) ማናቸውም ባለሞተር ተሽከርካሪ መኪና ወይም ተሳቢ ወይም ግማሽ ተሳቢ ጭነት ቢኖረውም ባይኖረውም ቁመቱ ወደ ላይ ከ3 ሜትር ከ80 መብለጥ የለበትም፡፡

64 በህግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 23/23 (1956) ህ. 292 አንቀጽ 3 መሰረት ተሻሻለ፡፡

ሐ) ተሳቢ የሌለው አንድ ባለሞተር ተሽከርካሪ ጭነት ቢኖረውም ባይኖረውም ከፊትና ከኋላ፣ መገፊያዎቹ ጭምር ተለክቶ ጠቅላላ ርዝመቱ ከ11 ሜትር መብለጥ የለበትም፡፡ እንዲሁም መንገደኞችን የጫነ ማናቸውም አውቶቡስ ከማናቸውም ዓይነት ተሽከርካሪ መኪና ወይም ተሳቢ ወይም ግማሽ ተሳቢ ጋር ተቀጥሎ እንዳይጓዝ ተከልክሏል፡፡

መ) ጐታች ካሚዮንና ግማሽ ተሳቢ ተብለው የሚጠሩት ከሌላ ጋር የሚቀጠሉ ተሽከርካሪዎች ጭነት ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም ከፊትና ከኋላ መገፊያቸው ጭምር ተለክቶ ጠቅላላ ርዝመታቸው ከ14 ሜትር ማለፍ የለበትም፡፡

ሠ) ማናቸውም ዓይነት ተቀጣጣይ የሆኑ ተሽከርካሪዎች ተሳቢዎች ወይም ግማሽ ተሳቢዎች ባንድ ጊዜ ተቀጣጥለው የሚጓዙ ከሁለት ተሽከርካሪዎች እንዳይበልጡ ክልክል ነው፣ እንዲሁም እነዚህ ተቀጣጥለው የሚጓዙት ተሽከርካሪዎች ጭነት ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም ጠቅላላ ርዝመታቸው ከፊትና ከኋላ መገፊያቸው ጭምር ተለክቶ ከ18 ሜትር መብለጥ የለበትም፡፡

<u>**የተሽከርካሪዎች የክብደት ወሰን**</u>

6. ሀ) ማናቸውም ያንድ ተሽከርካሪ መኪና አንድ አክስ ከ8 ሜትሪክ ቶንስ የበለጠ ጭነት እንዲሸከም አይፈቀድም፣

ለ) ከፊት በኩል ከሚገኘው የመሪው አክስ ከሚባለው በቀር አንድ የተሽከርካሪ መኪና እስከ ከ6 ሜትሪክ ቶንስ የበለጠ ጭነት የሚሸከም በሆነ ጊዜ በእግሩ ላይ ጥንድ ላስቲክ እንዲኖረው ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መሠረት ለሁለቱ አክሶች አንድ ዓይነት የሆኑ 4 ላስቲኮች እንዲደረጉላቸው ይህ ደንብ ያስገድዳል፡፡

ሐ) አፈጻጸሙ በዚህ በ6ኛው አንቀጽ "ሀ" እንደ ተነገረው ሆኖ፣ በማናቸውም ያንድ ተሽከርካሪ ወይም ተቀጣጥለው በሚጓዙ ተሽከርካሪዎች አንድ አክስ ወይም ሁለት ወይም ሶስት አክሶች አማካይነት በአውራ ጐዳናው ላይ የሚያርፈው ጠቅላላ ክብደት የዚህ ደንብ አባሪ በሆነው ሠንጠረዥ ላይ ከተመለከተው ማለፍ የለበትም፡፡

መ) በዚህ ደንብ ሠንጠረዥ ውስጥ በተመለከተው መሠረት በጠቅላላው የሚፈቀደው ክብደት መከበሩን ለመቆጣጠር በአክሶቹ መካከል ያለው ርቀት የሚለካው በተሽከርካሪው በርዝመቱ አቅጣጫ ሆኖ በአክሶቹ ውስጥ በመጀመሪያውና በመጨረሻው መካከል ያለውን ርቀት በመውሰድ ነው፡፡

**ስለ ልዩ ልዩ ፈቃድ አሰጣል**

7. ዲሬክተሩ ወይም እሱ በሚገባ በጽሕፈት ሥልጣን የሰጠው ወኪሉ በዚህ ደንብ ከተወሰነው በላይ የሆነ ክብደት ወይም ትልቅነት ላለው አንድ ተሽከርካሪ መኪና ወይም የተቀጣጠሉ ተሽከርካሪዎች ወይም ተሳቢ ወይም ግማሽ ተሳቢ ላንድ ጊዜ ባንድ የመንገድ መሥመር ላይ ለመጓዝ ብቻ ዲሬክተሩ ወይም ወኪሉ አስፈላጊና ትክክል መስሎ በሚታየው አኳኋን ልዩ ፈቃድ ለመስጠት ይችላል፡፡

**ክብደትን ለመቀነስ ለዲሬክተሩ የተሰጠ ሥልጣን**

8. ሀ) በዚሁ ደንብ የተፈቀዱት የጭነት ክብደቶች ለመንገዶች ወይም ለመንገድ ክፍሎች ጉዳት የሚያወጡ ሆነው በተገኙ ጊዜ ዲሬክተሩ ተለይተው በተነገሩት መንገዶች ወይም የመንገድ ክፍሎች ላይ ተገቢ ሲሆን ለተወሰነ ጊዜያት ላንድ አክስ ወይም ለብዙ አክሶች የሚፈቀደውን የክብደት መጠን አስፈላጊ መስሎ እንደታየው ለመቀነስ ሥልጣን አለው፡፡

   ለ) ዲሬክተሩ ወይም በራሱ ፊርማ በሚገባ በጽሕፈት ሥልጣን የሰጠው ወኪሉ በማናቸውም ድልድይ፣ የቦይ መሻገሪያ ወይም የመንገድ ሕንፃ ላይ ለማስተላለፍ የሚፈቀደውን ጠቅላላ ክብደት ልክ ለመወሰን ይችላል፡፡

   ሐ) በዚህ በ8ኛው አንቀጽ "ሀ" እና "ለ" በተመለከተው መሠረት ማናቸውም የክብደትመቀነስ ወይም መወሰን በተደረገ ጊዜ ውሳኔው በሚነካቸው ድልድዮች፣ የቦይ መሻገሪያዎችና የመንገድ ሕንፃዎች ወይም የነዚሁ ክፍሎች ላይ ማስታወቂያ ይለጠፋል፡፡ ከዚህም በቀር ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሰዎች ውሳኔውን ያውቁት ዘንድ ዲሬክተሩ የተሻለ መስሎ በሚታየው ሌላ መንገድ አስፈላጊዎቹን ጥንቃቄዎች ያደርጋል፡፡

9. እያንዳንዱ የንግድ ተሽከርካሪ መኪና ወይም ተሳቢ ወይ ግማሽ ተሳቢ የራሱ ነጠላ ክብደትና እንዲሁም ፈቃድ ሲቀበል በተመዘገበበት ሰነድ ላይ የተወሰነለት ጠቅላላ ክብደት ጭምር በግልጽ በሚነበቡ ቢያንስ 5 ሳንቲ ሜትር ቁመት ባላቸው ቁጥሮችና ፊደሎች ከሁለት ፊት እንዲጻፍበት ያስፈልጋል፡፡

**ከተሽከርካሪው ርዝመት ተርፎ ውጭ የሚውለውን ጭነት**

**ስለ መወሰን**

10. በማናቸውም ተሽከርካሪ ወይም ተሳቢ ወይም ግማሽ ተሳቢ የሚገኘው ጭነት ከተሽከርካሪው ከፊቱ ጫፍ ከአንድ ሜትር በላይ፣ እንዲሁም ከኋላ በኩል ከዕቃ

መሸከሚያው አልጋ ጫፍ ከሁለት ሜትር በላይ ተርፎ ውጭ እንዳይውል ክልክል ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ አንቀጽ ውስጥ ስለ ርዝመት የተመለከተው ደንብ በግንዲላዎች፣ ቧንቧዎች፣ ለሕንፃ ሥራ የሚያገለግሉ ዕቃዎች ወይም በማይነጣጠሉ ዕቃዎች ላይ አይጸናም፡፡ ይህም ቢባል ደግሞ ርዝመታቸው ከ18ሜትር በላይ የሆኑ ግንዲላዎች፣ ቧምቧዎች፣ ሌሎችም ለሕንፃ ሥራ የሚያገለግሉ ዕቃዎችን ያለ ዲሬክተሩ ልዩ ፈቃድ በመንገድ ላይ ለማጓጓዝ የተከለከለ ነው፡፡

**<u>የምልክት መብራትና መለያ</u>**

11.በተሽከርካሪው ላይ የሚገኘው ጭነት የኋለኛውን ቀይ መብራት እንዳይሸፍን ተደርጎ መስተካከል አለበት፡፡ መብራቱ ከኋላ ለሚከተሉት ተሽከርካሪዎች በግልጽ የማይታይ በሆነ ጊዜ፣ በሌሊት ሲጓዝም ሆነ ቆሞ የተሽከርካሪው ወይም የተሳቢው ወይም የግማሽ ተሳቢው ጭነት ከኋላ በኩል ከጭነቱ ወለል ተርፎ ውጭ የዋለ እንደ ሆነ ስፋቱ ቢያንስ 30 ሳንቲ ሜትር ሆኖ በአራት ማዕዘን ቅርጽ የተሠራ ቀይ ጨርቅ በስተኋላ ከጭነቱ ጫፍ ላይ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**<u>ጭነትን አደላድሎና አጥብቆ ስለ ማሰር</u>**

12.ማንም ሰው ጭነቱ ወይም የጭነቱ ልባስ ተደልድሎና በመንገድ ላይ እንዳይላላ ወይም እንዳይፈታ ተደርጎ በጥብቅ ያልታሰረ አንድ ተሽከርካሪ መኪና ወይም ተሳቢ ወይም ግማሽ ተሳቢ በማናቸውም መንገድ ላይ ይዞ እንዳይጓዝ ክልክል ነው፡፡

**<u>የመንገደኞች ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ስለሚጭኑት ጭነት</u>**

13. ሀ) ማናቸውም ያደባባይ የኪራይ ተሽከርካሪ መኪና ከፊትና ኋላ መግፊያዎቹ ተርፎ ውጭ የሚውል ማናቸውም ዓይነት ጭነት ይዞ በማናቸውም መንገድ ላይ እንዳይጓዝ ተከልክሏል፡፡

ለ) ማናቸውም የመንገደኞች ማመላለሻ ተሽከርካሪ ከተሽከርካሪው ውጭ የተንጠለጠለ ወይም ያፈነገጠ ከፊትም ሆነ ከኋላ በኩል ከተሽከርካሪው ተርፎ ውጭ የዋለ ማናቸውም ዓይነት ዕቃ ይዞ እንዳይጓዝ ክልክል ነው፡፡

**<u>ይህ ደንብ የማይጸናባቸው፣</u>**

14.የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪያዎች ወይም ለጊዜው በመንገዶች ላይ የሚዘዋወሩ የመንገድ ሥራ መኪናዎችና ልዩ ፈቃድ ተሰጥቶዋቸው የሚመላለሱ ተሽከርካሪዎች በዚህ ደንብ ውስጥ በቁጥር 4፣ 5፣ 8ና 9 የተነገሩት አይጸናባቸውም፡፡

**የማቆም የመመርመር የመለካት ወይም የመመዘን ሥልጣን**

15.ሀ) ሙሉ የደንብ ትጥቁን የለበሰ ማናቸውም ለዚህ የተመደበ ፖሊስ ወይም የተፈቀደለት ሹም አንድ የተጫነ ወይም ያልተጫነ ተሽከርካሪ መኪና ወይም ተቀጣጥለው የሚጓዙ ተሽከርካሪዎች ወይም ተሳቢ ወይም ግማሽ ተሳቢ የዚህን ደንብ ቃል ያልፈጸመ ሆኖ ሲገኝ የነጂውን የመንጃ ፈቃድ ለመጠየቅ፤ ተሽከርካሪውን ለማቆመና መጠኑ እንዲለካ፤ እንዲመረመርና ክብደቱ እንዲመዘን ለማዘዝ ይችላል፡፡

ለ) የተሽከርካሪው ወይም ተቀጣጥለው የሚጓዙት ተሽከርካሪዎች በተዘዋዋሪ ወይም አንድ ቦታ ቀዋሚ በሆነ ሚዛን እዚያው እየተያዙበት ቦታ ላይ እንዲመዘኑ ለማድረግ ይችላል፡፡

ሐ) አንድ የተፈቀደለት ሹም ወይም ለዚሁ የተመደበ ፖሊስ አንዱን ተሽከርካሪና ጭነቱን በሚያስመዝንበት ጊዜ ክብደቱ በዚህ ደንብ ከተፈቀደው በልጦ ቢያገኘው ትርፉን ጭነት ተሽከርካሪው በሚያልፍበት በመጀመሪያው ከተማ አራግፎ ክብደቱን በዚህ ደንብ ከተወሰነው ጋር እንዲያስተካክል ነጂዉን ለማስገደድ ሥልጣን አለው፡፡

መ) ማናቸውም የተፈቀደለት ሹም ለዚሁ የተመደበ ፖሊስ እንዲራገፍ ስላደረገው ጭነት ጥበቃ ምንም ዓይነት ኃላፊነት አይነካውም፡፡

ሠ) አንድ ተሽከርካሪ ወይም ተቀጣጥለው የሚጓዙት ተሽከርካሪዎች ይህንን ደንብ ተላልፈው በተገኙበት ቦታ የተፈቀደለት ሹም ወይም ለዚሁ የተመደበ ፖሊስ ለተሽከርካሪው ነጂ በሕግ ተላላፊነት የሚከሰስ መሆኑን ወዲያውኑ ካስታወቀው በኋላ፤ ተሽከርካሪው ወይም ተቀጣጥለው የሚጓዙት ተሽከርካሪዎች መንገዳቸውን እንዲቀጥሉ ከመፈቀዱ በፊት ከምርመራው ያገኘውን የመመዘን ወይም የመለካት ውጤት፤ እንዲሁም የተሽከርካሪውን ወይም ተቀጣጥለው የሚጓዙትን ተሽከርከሪዎች የሠሌዳ ቁጥር፤ የባለቤትነቱንና የነጂውን ስም ጭምር የሚገልጽ ሙሉ ማስታወሻ መያዝ አለበት፡፡

**ስለ መቀጫ**

16.ይህን ደንብ የተላለፈ ወይም በዚህ ደንብ መሠረት የተሰጠውን የማናቸውንም ፈቃድ ግዳጆች ሳይፈጽም የቀረ ማናቸውም ሰው ከጥፋተኛ ተቆጥሮ በፍርድ ቤት

ተመስክሮበት ሲፈረድበት በ1949 ዓ.ም በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ[65] በተመለከተው መሠረት ይቀጣል፡፡

17. ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**ሠንጠረዥ**

| በተሽከርካሪውበመጀመሪያውና በመጨረሻው አክስ መካከል መኖር የሚገባው ርቀት ልክ | ለተሽከርካሪ መኪና አክሶች የሚፈቀድ የማይታለፍ ጭነት ልክ |
|---|---|
| በሳንቲ ሜትር | በኪሎ ግራም |
| 120 | 14,515 |
| 150 | 14,515 |
| 185 | 14,515 |
| 215 | 14,515 |
| 245 | 14,790 |
| 275 | 15,230 |
| 305 | 15,670 |
| 335 | 16,105 |
| 365 | 16,545 |
| 395 | 16,975 |
| 425 | 17,400 |
| 455 | 17,875 |

[65] በ1949 ዓ.ም በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በሚል የተገለጸው በ1996 ዓ/ም በወጣው የኢ.ፌዴሪ ወንጀል ህግ ተተክቷል፡፡

| የፍትህ ሚኒስቴር | |
|---|---|
| 485 | 18,250 |
| 520 | 18,670 |
| 550 | 19,085 |
| 580 | 19,500 |
| 610 | 19,915 |
| 640 | 20,320 |
| 670 | 20,730 |
| 700 | 21,135 |
| 730 | 21,530 |
| 760 | 21,930 |
| 790 | 22,325 |
| 820 | 22,720 |
| 855 | 23,110 |
| 885 | 23,495 |
| 915 | 23,880 |
| 945 | 24,265 |
| 975 | 24,645 |
| 1005 | 25,020 |
| 1035 | 25,395 |
| 1065 | 25,765 |

| | |
|---|---|
| 1095 | 26,130 |
| 1130 | 26,500 |
| 1160 | 26,860 |
| 1190 | 27,220 |
| 1220 | 27,580 |
| 1250 | 27,930 |
| 1280 | 28,285 |
| 1310 | 28,635 |
| 1340 | 28,980 |
| 1370 | 29,325 |
| 1400 | 29,665 |
| 1450 | 30,175 |
| 1500 | 30,675 |

**አዲስ አበባ ጥቅምት 21 ቀን 1955 ዓ.ም**

**ባላምባራስ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል**

**የሥራና የመገናኛ ሚኒስትር**

## የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 361/1961

## የ1961 ዓ.ም የባለሞተር ተሽከርካሪዎች ፍጥነት ወሰን ደንብ

## በ1960 ዓ.ም በመንገዶች ላይ ጉዞንና ማመላለሻን (ትራንስፖርትን) ለመቆጣጠር በተደነገገው አዋጅ መሠረት የወጣ ደንብ

1. **አውጪው ባለሥልጣን**

   ይህን ደንብ የመገናኛ ሚኒስትሩ ያወጣው በ1960 ዓ.ም፣ በመንገዶች ላይ ጉዞንና ማመላለሻን ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 256/1960 ዓ.ም) አንቀጽ 5/2(ሠ) እና (በ) ከዚህ በታች "ዋናው አዋጅ" እየተባለ የሚጠቀሰው በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ነው፡፡

2. **አጭር አርእስት**

   ይህ ደንብ "የ1961 ዓ.ም የባለሞተር ተሽከርካሪዎች ፍጥነት ወሰን ደንብ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

3. **ስለ መሻር**

   የ1956 ዓ.ም የትራንስፖርት ማሻሻያ ደንብ፣ የሕግ ማስታወቂያ ቁጥር 279/1956 ዓ.ም አንቀጽ 17 እና አንቀጽ 18 በ1960 ዓ.ም በወጣው በሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 335 እንደገና እንዲጸና ተደርጎ የነበረው ተሽሮ በዚህ የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ተተክቷል፡፡

4. **ትርጉም**

   የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም እንዲሰጥ ካላስፈለገ በስተቀር፣ በዋናው አዋጅ በአንቀጽ 3 ውስጥ ያሉት ቃላት ትርጉም በዚህ ደንብ ውስጥ ተፈጻሚ ይሆናል፣ የሚከተሉት ተጨማሪ ቃላትም ከታች የተዘረዘረ ትርጉም ይኖራቸዋል፡፡

   1. "የፍጥነት ወሰን" ማለት በማንኛውም ሁኔታ አንድ ባለሞተር ተሽከርካሪ ሊነዳ የሚቻልበት ከፍተኛው ፍጥነት ማለት ነው፡፡
   2. "የእርሻ መሣሪያ" ማለት ለእርሻ፣ ለአትክልት ወይም ለከብት እርባት ሥራ እንዲውል የተሠራ ወይም የተደረገ ማንኛውም ተሽከርካሪ ወይም እንደዚህ ያለውን ተሽከርካሪ ለማንሣት፣ ለመሸከም ወይም ለመሳብ የተሠራ ወይም የተደረገ ተሽከርካሪ ማለት ነው፡፡
   3. "የአንደኛ ደረጃ አውራ ጐዳና"፣

ሀ/ ከጐረቤት አገሮች የንግድና የገበያ ጣቢያዎች ጋር ኢትዮጵያን የሚያገናኝ፣

ለ) ታላላቅ ከተሞችን፣ የጠቅላይ ግዛትና ዋና ከተሞችን፣ የባሕር ወደቦችንና የጠረፍ ዋና ጣቢያዎችን ከንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት፣ መናገሻ ከተማ ጋር የሚያገናኝ፣

ሐ) ሕዝብ የሚበዛባቸው ዋና ዋና ሥፍራዎችን እርስ በርሳቸው የሚያገናኝ እና/ወይም

መ) የገበያ፣ የልማት ሥራና የኢኮኖሚ እድገት ዋና ዋና ጣቢያዎችን የሚያገናኝ ማንኛውም ብሔራዊ መንገድ ነው፡፡

4. "የሁለተኛ ደረጃ አውራ ጐዳና" የአንደኛ ደረጃ አውራ ጐዳና ያልሆነ፣ ማንኛውም ብሔራዊ መንገድ ሆኖ፣

ሀ) በየጠቅላይ ግዛቱ በእርሻ፣ በከብት እርባታ፣ በእንዱስትሪና በገበያ ወረዳዎች የሚገኙ ዋና ከተማዎችን እና/ወይም መንደሮችን እርስ በርሳቸው የሚያገናኝ፣ እና/ወይም

ለ) የአውራጃ አስተዳደር መቀመጫ የሆኑ ከተማዎችን ከአንደኛ ደረጃ አውራ ጐዳናዎች ጋር የሚያገናኝ ማንኛውም ብሔራዊ መንገድ ነው፡፡

5. "የመጋቢ መንገድ" የአንደኛ ደረጃና የሁለተኛ ደረጃ አውራ ጐዳና ያልሆነ ማንኛውም ብሔራዊ ጐዳና ሆኖ፣

ሀ) የእርሻ ወረዳዎችን ከገበያ ሥፍራዎች ጋር የሚያገናኝ፣

ለ) ትንንሽ ከተማዎችንና መንደሮችን እርስ በርሳቸው የሚያገናኝ እና/ወይም፣

ሐ) የእርሻ፣ የማዕድንና የሌላ የልማት ሥራ ወረዳዎችን ከአንደኛ ደረጃ አውራ ጐዳናዎችና ከሁለተኛ ደረጃ አውራ ጐዳናዎች ጋር የሚያገናኝ ነው፡፡

6. "የቀበሌ መጋቢ መንገድ" ማለት በንጉሠ ነገሥቱ መንግስት የአውራ ጐዳና ባለሥልጣን መሪነትና ተቆጣጣሪነት ያልታቀደ፣ ያልተሠራ ወይም ያልተጠበቀ፣ በጠቅላላው ለሕዝብ አገልግሎት ክፍት የሆነና ተሽከርካሪዎች ሊመላለሱበት የሚችሉ ማንኛውም መንገድ ነው፡፡

5. <u>ጠቅላላ መሠረታውያን አሳቦች</u>

1. ማናቸውም ሰው፣ ተሽከርካሪው አደጋን ሳያስከትል ሊነዳ የሚችልበትን ሁናቴ ሁሉ በሚገባ አመዛዝኖ ካልሆነ በቀር፣ በማንኛውም በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ግዛት መንገድ ላይ ከፍ ባለ ፍጥነት ተሽከርካሪ መንዳት የለበትም፡፡ የተባለው ሁናቴም በዚህ ብቻ ሳይወሰን የሚከተለውን ይጠቀልላል፡፡
   ሀ) የመንገዱን ንጣፍ፣ ስፋትና ጠቅላላ ሁኔታ፤
   ለ) መንገዱ የሚያልፍበትን መሬት ሁኔታና በዚህ ምክንያት የሚገጥመውን የመንገድ መጠምዘዝና የመንገዱ ስፋት መጠን፤
   ሐ) የዝናም፣ የጭጋግ ወይም የሌላ የተፈጥሮ ሁኔታ መኖርና ይህ ማየትንና መንዳትን እንዴት እንደሚነካ፤
   መ) የዝናም፣ የጭጋግ ወይም የሌላ የተፈጥሮ ሁኔታ መኖርና ይህ ማየትንና መንዳትን እንዴት እንደሚነካ፤
   መ) በአካባቢው ያለው የነዋሪው ሕዝብ መጠን፤
   ሠ) ያለው ወይም ይኖራል ተብሎ የሚገመተው የትራፊክ ብዛት መጠን፤
   ረ) መዞሪያዎች፣ የተዘጉ መተላለፊያዎች፣ የተሰናከሉ ተሽከርካሪዎች፣ የወደቀ አለትና ሌላም መተላለፍን የሚያውክ መሰናክል መኖርንና፤
   ሰ) ነጂው በማንኛውም ጊዜ ተሽከርካሪውን በሙሉ እንዳይቆጣጠርና አደጋን በማያደርስ አኳኋን እንዳይነዳ የሚያውክ ማንኛውም ሁኔታ፡፡
2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የአነዳድ ሁናቴ ቢዘረዘርም፣ ማናቸውም ሰው፣ በዚህ ደንብ በአንቀጽ 6 እና 7 ወይም በአንቀጽ 8 የተመደበውን የፍጥነት ወሰን በመተላለፍ ባለሞተር ተሽከርካሪን በማንኛውም በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ግዛት መንገድ ላይ መንዳት የለበትም፡፡
3. ማናቸውም ሰው በማንኛውም በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ግዛት መንገድ ላይ ባለሞተር ተሽከርካሪውን በሚነዳበት ጊዜ፤ ከአደጋ ለመዳን በዝግታ እንዲያሽከረክር አስፈላጊ ካልሆነ በቀር የትራፊክን መንቀሳቀስ በማይገባ በሚያግድ ዝቅተኛ ፍጥነት መንዳት የለበትም፡፡

4. አደጋ እንዳይደርስ በዝግታ መንዳት አስፈላጊ ሲሆን ወይም በዚህ ደንብ በአንቀጽ 6 እና 7 ወይም በአንቀጽ 8 መሠረት በዝግታ መንዳት የተመደበ ሲሆን በአጠገቡ ከሚንቀሳቀስ ትራፊክ ሲነፃፀር በዝግታ የሚነዳና በዚያው አቅጣጫ የሚጓዝ ማንኛውም ባለሞተር ተሽከርካሪ የመንገዱን የቀኝ ጠርዝ ይዞ መሄድ አለበት፡፡

6. <u>ከከተማ ክልል ውጪ በጠቅላላ የሚፈቀድ የፍጥነት ወሰን[66]</u>

ማናቸውም ሰው ከከተማ ክልል ውጪ፣

1. የግል አቶሞቢል ወይም ሞተር ሳይክል ቀጥሎ ከተመለከተው የፍጥነት መጠን በላይ መንዳት የለበትም፤
   ሀ) በአንደኛ ደረጃ አውራ ጐዳና በሰዓት መቶ (100) ኪሎ ሜትር፤
   ለ) በሁለተኛ ደረጃ አውራ ጐዳና ላይ በሰዓት ሰባ (70) ኪሎ ሜትር፤
   ሐ) በመጋቢ መንገድና በቀበሌ መጋቢ መንገድ ላይ በሰዓት ስልሳ (60) ኪሎ ሜትር፤
2. የንግድ ወይም የኪራይ ተሽከርካሪ ቀጥሎ ከተመለከተው የፍጥነት መጠን በላይ መንዳት የለበትም፤
   ሀ) በአንደኛ ደረጃ አውራ ጐዳና ላይ በሰዓት ሰማንያ (80) ኪሎ ሜትር፤
   ለ) በሁለተኛ ደረጃ አውራ ጐዳና ላይ በሰዓት ስልሳ (60) ኪሎ ሜትር፤
   ሐ) በመጋቢ መንገድና በቀበሌ መጋቢ መንገድ ላይ በሰዓት ሃምሳ (50) ኪሎ ሜትር፤
3. ባለሞተር ተሽከርካሪና ተሳቢ፣ ከባድ ካምዮንና ግማሽ ተሳቢ፣ የእርሻ መሣሪያ ወይም ማንኛውንም ባለሞተር ተሽከርካሪ ከሚከተለው የፍጥነት መጠን በላይ መንዳት የለበትም፤
   ሀ) በአንደኛ አውራ ጐዳና ላይ በሰዓት ሰባ (70) ኪሎ ሜትር፤
   ለ) በሁለተኛ ደረጃ አውራ ጐዳና ላይ በሰዓት ሃምሳ (50) ኪሎ ሜትር፤
   ሐ) በመጋቢ መንገድና በቀበሌ መጋቢ መንገድ ላይ በሰዓት አርባ (40) ኪሎ ሜትር፤

[66]የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ በደንብ ቁጥር 17/89 (2003) ደ. 208 ከአንቀፅ 11 እስከ 13 በተጠቀሱት ድንጋጌዎች የተሸፈነ በመሆኑ በግልጽ ሳይነገር ተሽሯል፡፡

7. **<u>በከተማ ክልል ውስጥ በጠቅላላ የሚፈቀድ የፍጥነት ወሰን፣</u>**[67]

ማናቸውም ሰው በከተማ ክልል ውስጥ፣

1. የግል ኦቶሞቢል ወይም ሞተር ሳይክል በማንኛውም መንገድ ላይ በሰዓት ከስድሳ (60) ኪሎ ሜትር በላይ መንዳት የለበትም፤
2. ከነጭነቱ በሕግ የተፈቀደው ጠቅላላ ክብደቱ ከሶስት ሺ አምስት መቶ (3500) ኪሎ ግራም የማይበልጥ የንግድ ተሽከርካሪ ወይም የኪራይ ተሽከርካሪ በሰዓት ከአርባ (40) ኪሎ ሜትር በላይ መንዳት የለበትም፡፡
3. ከነጭነቱ በሕግ የተፈቀደ ጠቅላላ ክብደቱ ከሶሰት ሺ አምስት መቶ (3500) ኪሎ ግራም የሚበልጥ የንግድ ተሽከርካሪ፣ ባለሞተር ተሽከርካሪና ተሳቢ፣ ከባድ ካምዮንና ግማሽ ተሳቢ፣ የእርሻ መሣሪያ ወይም ሌላ ባለሞተር ተሽከርካሪ በሰዓት ከሠላሳ (30) ኪሎ ሜትር በላይ መንዳት የለበትም፡፡

8. **<u>ልዩ የፍጥነት ወሰን፤</u>**

1. በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ፣ ለሕዝብ ደኅንነት አስፈላጊ ሲሆን፣ በማንኛውም መንገድ ወይም በከፊሉ ወይም በማንኛውም ድልድይ ላይ የሚሽከረከር ማንኛውም ዓይነት ባለሞተር ተሽከርካሪ ከላይ በአንቀጽ 6 እና 7 የተመደበውን የፍጥነት መጠን መቀነስ አለበት፡፡
2. ሀ) ከከተማ ክልል ውጪ ከላይ በአንቀጽ 6 ከተመደበው የተለየ የፍጥነት ወሰን የመመደብ አላፊነት ለአውራ ጐዳና ባለሥልጣን በውክልና ተሰጥቶአል፣

   ለ) በከተማ ክልል ውስጥም፣ ከላይ በአንቀጽ 7 ከተመደበው የተለየ የፍጥነት ወሰን የመመደብ አላፊነት፣ በየከተማቸው እንዲሠሩበት፣ ለከተማ ባለሥልጣኖች በውክልና ተሰጥቷል፡፡

   ስለሆነም፤ በተለይ የሚመደበው የፍጥነት ወሰን ማስታወቂያ የመንገድ ምልክት አልፎ አልፎ በግልጽ በሚታይ ሥፍራ በመንገዶቹ ወይም በድልድዮቹ ላይ መደረግ አለበት፡፡

---

[67] የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ በደንብ ቁጥር 17/89 (2003) ደ. 208 ከአንቀፅ 11 እስከ 13 በተጠቀሱት ድንጋጌዎች የተሸፈነ በመሆኑ በግልጽ ሳይነገር ተሽሯል፡፡

9. <u>**ይህን ደንብ ስለ መተላለፍ**</u>

**በዚህ ደንብ ውስጥ ወይም በዚህ ደንብ መሠረት ከተመደበው የፍጥነት ወሰን በላይ ማንኛውንም ዓይነት ባለሞተር ተሽከርካሪ የሚነዳ ማናቸውም ሰው፣ በዋናው አዋጅ አንቀጽ 24 መሠረት፣ እንደ ጥፋተኛ ተቆጥሮ በተፈረደበት ጊዜ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ[68] ይቀጣል፡፡**

10. <u>**ይህ ደንብ ስለሚጸናበት ጊዜ**</u>

**ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡**

**አዲስ አበባ የካቲት 15 ቀን 1961 ዓ.ም**

**አማኑኤል አብርሃም**

**የመገናኛ ሚኒስትር**

---

[68] በ1949 ዓ.ም በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በሚል የተገለጸው በ1996 ዓ/ም በወጣው የኢፌዴሪ ወንጀል ህግ ተተክቷል፡፡

## አዋጅ ቁጥር 468/1997

## ትራንስፖርትን ስለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ

ለአገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ዕድገት የትራንስፖርት አገልግሎት የበለጠ ተወዳዳሪ፣ ደህንነቱ የተጠበቀና ብቃት ያለው ሆኖ እንዲራመድ ክትትል ስለሚያስፈልገው፣ የትራንስፖርት አደረጃጀት የመንግሥት ፖሊሲን በአግባቡ ለመተግበር አመቺ ሁኔታ በሚፈጥር መልኩ እንደገና መዋቀር ስለሚገባው፣

ትራንስፖርትን አስመልክቶ የፌዴራልና የክልል አስፈጻሚ አካላት የተሰጣቸውን ሥልጣንና ተግባር በማያሻማ ሁኔታ ማስቀመጥ አስፈላጊ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55/1/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/1997" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

   1. "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የመሠረተ ልማት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፣[69]
   2. "ማህበር" ማለት የህዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ ለተሰማሩ ሰዎችና ድርጅቶች የተቋቋመና በዚህ አዋጅ መሰረት የተመዘገበ ማህበር ነው፣
   3. "የንግድ የመንገድ ማመላለሻ" ማለት በግለሰብ ወይም በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው አካል በሚካሄድ ድርጅት መንገደኞችን ወይም ዕቃዎችን ለኪራይ፣ ለጥቅም ወይም ለትርፍ የማመላለስ ሥራ ሆኖ እንደሚከተለው የግል ወይም የህዝብ ተብሎ ይከፈላል፣

      ሀ) "የግል የንግድ የመንገድ ማመላለሻ" ማለት መንገደኞችን ወይም ዕቃዎችን የሚያመላልስ ሰው ተሽከርካሪ ንብረትነቱ የድርጅቱ ሆኖ፣

[69]በአዋጅ ቁጥር በ22/12(2008) አ.916 አንቀጽ 9 (12) አማካኝነት የትራንስፖርት ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

i. የሚመላለሱት ዕቃዎች የዚያው የድርጅት ንብረት የሆኑ ወይም ለጥገና ወይም ለማደስ በአደራ የተሰጡት የሆኑ እንደሆኑና ዕቃዎቹን ማመላለስ ለድርጅቱ ዓይነተኛ የንግድ ሥራ አስፈላጊና ማሟያ የሆነ እንደሆነ፣ ወይም

ii. የሚመላለሱት መንገደኞች የዚያው ድርጅት ሠራተኞች ሆነው የሚመላለሱትም ወደ ሥራ ቦታቸውና ከሥራ ቦታቸው የሆነ ወይም የድርጅቱን ሥራ ለማከናወን የሆነ እንደሆነ ነው፤

ለ) "የህዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ" ማለት የግል ተብሎ ያልተመደበ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሁሉ ነው፤

4. "የዲሲፕሊን መምሪያ" ማለት በሚኒስትሩ የወጣ የዲሲፕሊን እርምጃ አወሳሰንና አፈጻጸም መምሪያ ነዉ፤

5. "አውራ ጎዳና" ማለት የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የሚያስተዳድረውና አውራ ጎዳና ብሎ የሚሰይመው መንገድ ነው፤

6. "የስምሪት ፕሮግራም" ማለት የህዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን የዓመት፣ የወር፣ የሣምንት ወይም የቀን እንቅስቃሴ የሚወስን ድልድል ነው፤

7. "የስምሪት መስመር" ማለት በባለሥልጣኑ የሚወሰን የህዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የስምሪት መነሻና መድረሻ ነው፤

8. "የመንጃ ፍቃድ" ማለት ባለሞተር ተሽከርካሪዎችን ለመንዳት የሚያስችል በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብና መመሪያ መሠረት የሚሰጥ የመንጃ ፈቃድ ነው፤

9. "የፌዴራል የመንጃ ፈቃድ" ማለት በጋራ ጥቅም መርሕ /ሪስፕሮሲቲ/ መሠረት ለውጭ አገር ዜጎች ወይም ለጉብኝት፣ ለንግድ ሥራ ወይም ለመንግሥት ሥራ ወደ ውጭ አገር ለሚሄዱ ኢትዮጵያዉያን ባለሞተር ተሽከርካሪ ለማሽከርከር የሚያስችል በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብና መመሪያ መሠረት የሚሰጥ የመንጃ ፈቃድ ነው፤

10. "መንገደኛ" ማለት በተሽከርካሪ ተሣፍሮ የሚሄድ ማንኛውም ሰው ሲሆን ነጂውን፣ ገንዘብ ተቀባዩንና በተሽከርካሪው ላይ የተመደበ ማንኛውንም ሌላ ሠራተኛ አይጨምርም፤

11. "ክትትል" ማለት የትራንስፖርት አዋጅ፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ደረጃዎችና ውሳኔዎች በትክክል በሥራ ላይ መዋላቸውን የማረጋገጥ ተግባር ነው፤

12.“መንገድ” ማለት ለማናቸውም ተላላፊ ክፍት ካልሆነ የግል መንገድ በስተቀር ተሽከርካሪዎች በተለምዶ የሚጠቀሙበት ማናቸውም ጎዳና፣ የከተማ መንገድ፣ አውራ ጎዳና ወይም መተላለፊያ ነው፤

13.“ተሽከርካሪ” ማለት ልዩ ወታደራዊ ተሽከርካሪዎችን ሳይጨምር በመንገድ ላይ በመንኮራኩር የሚሄድ ማንኛውም ዓይነት ተሽከርካሪ ሆኖ ሠረገላ፣ ብስክሌት፣ ባለሞተር ተሽከርካሪ፣ ግማሽ ተሣቢ እና ተሣቢ ተብሎ ይከፈላል፤

14.“ሠረገላ” ማለት ከብስክሌት፣ ከባለሞተር ተሽከርካሪ፣ ከግማሽ ተሣቢ እና ከተሣቢ በስተቀር ማናቸውም ተሽከርካሪ ነው፤

15.“ብስክሌት” ማለት በሚነዳው ሰው ኃይል እየተንቀሳቀሰ የሚሄድ ተሽከርካሪ ነው፤

16.“ባለሞተር” ተሽከርካሪ ማለት በመካኒካል ወይም በኤሌክትሪክ ኃይል እየተንቀሣቀሰ የሚሄድ ተሽከርካሪ ሆኖ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ፣ ባለሞተር ብስክሌት፣ የግል አውቶሞቢል፤ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ፣ ጎታች መኪና እና ልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያ ተብሎ ይከፈላል፤

17.“የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ” ማለት ማናቸውንም ዓይነት ዕቃ እንዲያመላልስ ተብሎ የተሰራና ለዚሁ አገልግሎት እንዲውል የተደረገ ባለሞተር ተሽከርካሪ ሲሆን ጎታች መኪናን ይጨምራል፤

18.“ባለሞተር ብስክሌት ማለት” የጎን ተሽከርካሪውን ሳይጨምር ክብደቱ ከ400 ኪሎ ግራም የማይበልጥ ከአራት መንኮራኩር በታች ያለው ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፤

19.“የግል ተሽከርካሪ” ማለት ከጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ፣ ከባለሞተር ብስክሌት፣ ከሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ፣ ከጎታች መኪና እና ከልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያ የተለየ ለግል መጠቀሚያ የሚውል ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፤

20.“የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ” ማለት መንገደኞችን ለማመላለስ የሚያገለግል ባለሞተር ተሽከርካሪ ሲሆን የንግድ አውቶሞቢልና አውቶቡስ ተብሎ ይከፈላል፤

21.“የንግድ አውቶሞቢል” ማለት ከአሥራ ሁለት የማይበልጡ መንገደኞችን የሚያሳፍር የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ነው፤

22.“አውቶቡስ” ማለት ከአሥራ ሁለት መንገደኞች በላይ ለማሳፈር የሚችል የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ነው፤

23.“ጎታች መኪና” ማለት በተለይ ሌሎች ተሽከርካሪዎችን ለመጎተት የሚያገለግል ሆኖ የሌላ ጭነትን ሳይሆን የሚጎትተውን ተሽከርካሪና በርሱ ላይ ያለውን ጭነት ክብደት ብቻ በከፊል ለመሸከም የተሰራ ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፤

24.“ልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያ” ማለት ሰውን ወይም ዕቃን በመንገድ ላይ እንዲያመላልስ ሆኖ የተሰራ ተሽከርካሪ ሳይሆን ለእርሻ፣ ለአትክልት፣ ለከብት እርባታ፣ ለመንገድ፣ ለሕንፃ፣ ለቁፋሮ ወይም ለማናቸውም ተመሳሳይ ሌላ ሥራ የተሰራ ወይም ለዚሁ ጉዳይ እንዲውል የተደረገ ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፤

25.“ግማሽ ተሳቢ” ማለት ለመንገደኞች ወይም ለጭነት ማመላለሻ የሚያገለግልና በሌላ ባለሞተር ተሽከርካሪ የሚሳብ ሆኖ የተሽከርካሪውም ጭነቱም ክብደት በከፊል በሌላ ተሽከርካሪ ላይ እንዲያርፍ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ እንዲሳብ ተደርጎ የተሰራ ተሽከርካሪ ነው፤

26.“ተሳቢ” ማለት ለራሱ የተለየ የሞተር ኃይል የሌለው ሆኖ ጎታች በሆነ በሌላ ባለሞተር ተሽከርካሪ ላይ ሊቀጠልና ሊጎተት የሚችልና ክብደቱ ጎታች በሆነው ባለሞተር ተሽከርካሪ ላይ እንደማያርፍ ሆኖ የተሰራ ተሽከርካሪ ነው፤ ሆኖም ከባለሞተር ብስክሌት ጋር ተያይዞ የሚሳበውን የጎን ተሽከርካሪ አይጨምርም፤

27.“ክልል” ማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 47 የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ያካትታል፤

28.“አገር አቋራጭ የመንገድ ትራንስፖርት” አገልግሎት ማለት ሁለት ወይም ከሁለት በላይ ክልሎችን በሚያገናኝ መንገድ ላይ የሚካሄድ ማናቸውም የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ነዉ፤

29.“ዓለም አቀፍ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት” ማለት የኢትዮጵያ ድንበሮችን አቋርጦ የሚካሄድ ማንኛውም የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ወይም እንቅስቃሴ ነው፤

30.“ትራንስፖርት” ማለት በመንገድ፣ በሀዲድና በውሃ ላይ በሞተር ኃይል በሚንቀሳቀሱ አጓጓዦች የሚደረግ የትራንስፖርት አገልግሎት ነው፤

31.“መርከብ” ማለት በሞተር ኃይል የሚንቀሳቀስ የውሃ ማጓጓዣ ነው፤

32.“ቢሮ” ማለት የትራንስፖርት ሕጎችን የሚያስፈጽም የክልል አስፈጻሚ አካል ነው፤

33.[70]

34.“ሐዲድ” ማለት ለባቡር መሄጃ ተብሎ የተሰራ መተላለፊያ ነው፤

35.“ባሕረኛ” ማለት በኢትዮጵያ መርከብ ወይም በአገር አቋራጭ የውሃ ላይ ማጓጓዣ ላይ ተቀጥሮ ወይም ተመድቦ እንዲሰራ የተደረገ ማንኛውም ሰው ሲሆን አዛዡን፣ ነጅውንና ለማጁን ያጠቃልላል፡፡

## 3. የአፈጻጸም ወሰን

ለክልል ቢሮዎች በሕግ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ አዋጅ

1. በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ መንገዶች አጠቃቀም፣ በመንገዶች በሚገለገሉ ተሸከርካሪዎችና አሽከርካሪዎች፣
2. [71]
3. በኢትዮጵያ መርከቦችና ባህረኞች፣

እንዲሁም በጠቅላላ የየብስና የውሃ ትራንስፖርት ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## የትራንስፖርት ባለሥልጣን

## 4. መቋቋም

1. የትራንስፖርት ባለሥልጣን ከዚህ በኋላ ባለሥልጣን እየተባለ የሚጠራ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቃቁሟል፡፡
2. ባለሥልጣኑ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

## 5. ዋና መሥርያ ቤት

የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ውስጥ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማንኛቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሊያቋቁም ይችላል።

## 6. የባለስልጣኑ ዓላማዎች

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. ቀልጣፋ፣ ብቁ፣ ኢኮኖሚያዊ እና የተመጣጠነ የትራንስፖርት ሲስተም እንዲስፋፋ ማድረግ፤
2. የትራንስፖርት አገልግሎት ደህንነቱ የተጠበቀና ምቾት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ፤

---

[70] በ23/73 (2009) አ.1048 አንቀፅ 51(1) ተሻረ፡፡

[71] በ23/73 (2009) አ.1048 አንቀፅ 51(1) ተሻረ፡፡

3. ብሔራዊና ዓለም አቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎት መሥመሮች እንዲዘረጉና እንዲደራጁ ማድረግ፤ እና
4. ትራንስፖርት በማንኛውም ረገድ እንዲያድግ ማበረታታት፡፡

7. <u>የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር</u>

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

1. ትራንስፖርትን በአጠቃላይ በተመለከተ፤

ሀ) ትራንስፖርትን የሚመለከቱ የፖሊሲ ሃሳቦችን አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ ሲፈቀዱም ተግባራዊ ማድረግ፤

ለ) ደህንነቱ የተረጋገጠ፣ ቀልጣፋ፣ የተሟላና የተመጣጠነ የትራንስፖርት አገልግሎት መኖሩን መከታተል፤

ሐ) ትራንስፖርትን የሚመለከቱ የመንግስት ፖሊሲዎችና ሕጎችን እንዲሁም ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ሥራ ላይ ማዋልና ማስፈጸም፤

መ) በአገር ደረጃና ዓለም አቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎት መስመሮች እንዲዘረጉ ማድረግ፤

ሠ) የተቀናጀ የሕዝብና የዕቃ ትራንስፖርት ሥርዓት እንዲስፋፋ ማድረግ፤

ረ) መንገደኞች፣ ዕቃዎችና ፖስታዎች በንግድ ትራንስፖርት ስለሚጓዙበት ሁኔታ መመሪያ ማውጣትና አፈፃፀሙን መከታተል፤

ሰ) ትራንስፖርትን የሚመለከቱ ማናቸውም መረጃዎችንና ስታትስቲኮችን በቋሚ ሁኔታ መሰብሰብና ማጠናቀር፤

ሸ) ስለትራንስፖርት አገልግሎት እንደ አግባቡ የሥልጠናና የምክር አገልግሎት መስጠት፣ እንደአስፈላጊነቱም የማሰልጠኛ ተቋሞችን ማቋቋምና ማካሄድ፤

ቀ) ትራንስፖርትን በማንኛውም ረገድ ስለሚያድግበት ሁኔታ ጥናቶችን ማካሄድ፣ እንዲካሄድ ማበረታታት እንዲሁም ፕላንና ፕሮግራም ማዘጋጀት፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ማድረግ፤

በ) ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር የአካባቢ መበከልን ለመከላከል ከተሽከርካሪዎችና ባቡሮች ስለሚወጣው ጪስ፣ ጋዝ፣ ተንና ስለመሳሰሉት ከአገሪቱ አቅምና ከዓለም አቀፍ መመዘኛዎች ጋር የተገናዘበ ደረጃ አዘጋጅቶ ማቅረብ፤ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን መከታተል፤

ተ) ለሚሰጠው አገልግሎት ዋጋ ማስወሰንና መሰብሰብ፤

ቸ) በህዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ በተሰማሩት ግለሰቦች ድርጅቶችና ማህበራት የገበያ እጦት ሲያጋጥም ወይም በተገልጋይ ህብረተሰብ የትራንስፖርት አገልግሎት እጥረት ሲከሰት ክትትል ማድረግ፣ እንዲሁም የትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦትና ፍላጎት መጣጣሙን ማረጋገጥና ስምሪቱ ፍትሃዊ እንዲሆን ማድረግ፤

ኀ) የቢሮዎችን አቅም ለማጎልበት አመች ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤

2. የመንገድ ትራንስፖርትን በተመለከተ፤

ሀ) በመንገዶች የሚጠቀሙ ባለሞተር ተሽከርካሪዎች ከሚሰጡት አገልግሎት ዓይነት ሊኖራቸው የሚገባውን የደህንነት መሳሪያዎች ክብደትና መጠናቸውን እንዲሁም የተሳፋሪን ብዛትና የጭነት ክብደት መወሰን፤ በዚሁም መሠረት ምዝገባ እንዲካሄድ የማረጋገጫ ሰርትፊኬት መስጠት፤

ለ) በአገር አቋራጭና በዓለም የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ ለሚሰማሩ ሰዎችና ድርጅቶች የሙያ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠትና መከታተል፤

ሐ) ከውጭ ሀገር የሚመጡትንና በአገር ውስጥም የሚሰሩትን፣ የሚገጣጠሙትን ወይም በከፊል የሚሰሩትን ማናቸውንም ባለሞተር ተሽከርካሪዎች መከታተል፤ ለዚሁም መመዘኛ /ስፔሲፊኬሽን/ ማውጣት፤

መ) በአገር አቋራጭና በዓለም አቀፍ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ የሚሰማሩ ወይም ንብረትነታቸው የዲፕሎማቲክ፣ የዓለም  አቀፍ ድርጅቶች፣ ከአንድ ክልል በላይ የሚንቀሳቀሱ የተራድኦ ድርጅቶች ወይም የፌዴራል መንግሥት የሆኑ ባለሞተር ተሽከርካሪዎችን መመዝገብና የቴክኒክ ምርመራ ማካሄድ እንዲሁም መከታተል፤

ሠ) መንጃ ፈቃድን የሚመለከት መመሪያ ማውጣትና ተግባራዊነቱን መከታተል፤ የፌዴራል የመንጃ ፈቃድ መስጠትና ማደስ፤

ረ) በባለሥልጣኑ ወይም በክልል ቢሮዎች በሚመዘገቡ ባለሞተር ተሽከርካሪዎች ላይ የሚለጠፉ ሠሌዳዎች ማምረት፤

ሰ) በአገር አቋራጭና በዓለም አቀፍ የህዝብ ማመላለሻ ሥራ ላይ የተሰማሩት ሰዎች፣ ድርጅቶች ወይም ማህበራት የሚያስከፍሉትን ታሪፍ ለሚሰጡት አገልግሎት ማግኘት ስለሚገባቸው ጥቅምና የተጠቃሚውን የመክፈል አቅም ግምት ውስጥ በማስገባት ማጽደቅ፤

ሸ/ በዓለም አቀፍ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ወይም በተመሳሳይነት ሥራ ላይ ለተሰማሩ ተሽከርካሪዎችና አሽከርካሪዎች የትራንዚት ፈቃድ መስጠትና መከታተል፤

ቀ) ስለተሽከርካሪዎች አመዘጋገብና የቴክኒክ ምርመራ መመሪያ ማውጣትና መከታተል፤

በ) ባለሞተር ተሽከርካሪ መንዳት ለሚያስተምሩ ሰዎችና ትምህርት ቤቶች የሥራ ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ማውጣትና ተግባራዊነቱን መከታተል፤

ተ) ማናቸውንም የተሽከርካሪ መጠገኛና ማደሻ ጋራዥ የቴክኒክ ብቃት ስለማረጋገጥ፣ የሥራ ፈቃድ አሰጣጥና ስለደረጃው አወሳሰን መመሪያ ማውጣትና ተግባራዊነቱን መከታተል፤

ቸ) ለሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት የሚውሉ መናኸሪያዎች ደረጃና መመዘኛ /ስፔስፍኬሽን/ ማውጣትና መከታተል፤

ኀ) በአገር አቋራጭና በዓለም አቀፍ የሕዝብ ማመላለሻ ሥራ ለሚሰማሩ ተሽከርካሪዎች ማኅበራት የሚያቀርቡለትን የስምሪት ፕሮግራም ማጽደቅ ካልቀረበለትም ራሱ ማዘጋጀትና ለዚሁ የወጣውን የዲሲፕሊን መመሪያ ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በገበያ ሥርዓት አገልግሎት እንዲሰጡ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤

ነ) የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም ጊዜያዊ የኢኮኖሚ ወይም የማህበራዊ ችግሮች ሲከሰቱ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን ሚኒስቴሩ በሚያፀድቀው መመሪያ መሠረት በአስፈላጊው ቦታና መስመር ደልድሎ ማሰራትና መከታተል

ኘ) በአገር አቋራጭና በዓለም የንግድ የመንገድ ማመላለስ ሥራ ላይ የተሰማሩት ሰዎችና ድርጅቶች የሚያቋቁሙአቸውን ማህበራት መመዝገብ፤ ስለ አሠራራቸው መመሪያ ማውጣትና መከታተል፤

ኦ) ባለሞተር ተሽከርካሪዎች በሦስተኛ ወገን ላይ ለሚያደርሱት አደጋ የመድን ዋስትና ሽፋን እንደሚኖራቸው ማረጋገጥ፤ እንዲሁም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር በሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ለሚጓጓዙ መንገደኞችና ዕቃዎች ሊኖር ስለሚገባው የመድን ዋስትና ሽፋን መመሪያ ማውጣትና ማስፈፀም፤

ከ) ተሽከርካሪዎች እንደገና ስለሚሰሩበት፣ ስለሚፈታቱበት ወይም ከጥቅም ውጭ ስለሚደረጉበት ሁኔታ መመሪያ ማውጣትና መከታተል፤

ኸ) በአውራ ጎዳናዎች ላይ የመንገድ ትራንስፖርት አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መከበራቸውን መከታተል፤

ወ) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በአገር አቋራጭ እና በዓለም አቀፍ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ የሚሰማሩ ተሽከርካሪዎችን የቀለም ዓይነትና ዓርማ መወሰን፤

ዐ) በሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎችና ድርጅቶች፣ ማኅበራት፣ የሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ተጠቃሚዎች የሚወከሉበት አማካሪ ኮሚቴ ማቋቋም፤

ዘ) የተሽከርካሪ ዋጋ ግምት የመተመን አገልግሎት መስጠት፤

ዠ) የመካከለኛ የትራንስፖርት መገልገያ መሣሪያዎች በአገሪቷ የቦታ አቀማመጥ በሚያመች መልኩ እንዲስፋፉ ማበረታታት ፡፡

3. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 ድንጋጌ ቢኖርም ለፌዴራል መንግሥት ተጠሪ የሆኑ ከተሞችን የመንገድ ትራንስፖርት በተመለከተ፤

ሀ) የትራንስፖርት አገልግሎቱ እንዲስፋፋ ማድረግ፤ የአውቶቡስና የታክሲ ፌርማታዎች፣ መናኸሪያዎችና መድረሻዎች እንዲሰሩ ማድረግና ማስተዳደር፤

ለ) ተሽከርካሪዎችን መመዝገብ፤ ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ማካሄድና መከታተል፤

ሐ) በትራንስፖርት ሥራ የተሰማሩ ግለሰቦችንና ድርጅቶችን ማደራጀት፤ የትራፊክ አመራር ውጤታማ የሚሆንበትን ስልት በመቀየስ ተግባራዊ ማድረግ፤ የአቅም ግንባታ ድጋፍ መስጠት፤

መ) በትራንስፖርትና በጋራዥ አገልግሎት ለሚሰማሩ ግለሰቦችና ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ መስጠት፤

ሠ) ባለሞተር ተሽከርካሪ መንዳት ለሚያስተምሩ ሰዎችና ትምህርት ቤቶች የሥራ ፈቃድ መስጠት፤ የመንጃ ፈቃድ መስጠት፤

ረ) የሕዝብን ደኅንነት የሚጎዱ ተሽከርካሪዎችን እንቅስቃሴ በመከታተል ማገድ፤

ሰ) ከከተሞቹ ትራንስፖርት አገልግሎት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች ተግባራት ማከናወን፤

4. [72]

5. [73]

6. የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ መክሰስና መከሰስ፤ እና

7. ሌሎች ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሕጋዊ ተግባሮችን ማከናወን፤

8. <u>የባለሥልጣኑ አመራር</u>

ባለሥልጣኑ፣

1. በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግሥት የሚሾም አንድ ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ እና
2. አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች፣ ይኖሩታል።

9. <u>የዋና ሥራ አስኪያጁ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ዋና ሥራ አስኪያጅ ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የባለሥልጣኑን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ዋናው ሥራ አስኪያጅ፣

ሀ) በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ ያዉላል፤

ለ) በፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች ሕግ መሠረት የባለሥልጣኑን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የባለሥልጣኑን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

መ) ለባለሥልጣኑ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ባለሥልጣኑን ይወክላል፤

---

[72] በ23/73 (2009) አ.1048 አንቀፅ 51(1) ተሻረ፡፡

[73] በ13/60 (1999) አ. 549 አንቀጽ 17(2) ሀ መሰረት ተሰርዟል፡፡

ረ) የባለሥልጣኑን ዓመታዊ የሥራ የሂሣብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

3. ዋናው ሥራ አስኪያጅ ለባለሥልጣኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለባለሥልጣኑ ኃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፤ ሆኖም እርሱን ተከቶ የሚሠራው ኃላፊ ከ30 ቀናት ለሚበልጥ ጊዜ የሚሠራ ከሆነ ውክልናው አስቀድሞ ለሚኒስትሩ ቀርቦ መጽደቅ አለበት፡፡

10.<u>በጀት</u>

የባለሥልጣኑ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፤

1. ባለሥልጣኑ ለሚሰጠው ፈቃድና አገልግሎት ከሚያስከፍለው ክፍያ፤
2. በመንግሥት ከሚሰጥ የበጀት ድጋፍ፤ እና
3. ከማናቸውም ሌላ ምንጭ፡፡

11.<u>ስለሂሳብ መዛግብት</u>

1. ባለሥልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፡፡
2. የባለሥልጣኑ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል።

<u>ክፍል ሦስት</u>

<u>የሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ስለማካሄድና</u>

<u>ስለ ሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ማኅበራት</u>

12.<u>የሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ስለማካሄድ</u>

1. ማንኛውም ግለሰብ ወይም በሕግ መሠረት የተቋቋመ ድርጅት በሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ሊሠማራ ይችላል፡፡
2. በሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ ለመሠማራት ፈቃድ የተሰጣቸው ሰዎችና ድርጅቶች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13 መሠረት የሚቋቋም ማኅበር አባል በመሆን ሥራቸውን ሊያካሂዱ ወይም የማኅበር አባል ሳይሆኑ ሥራቸውን በግላቸው ሊያካሂዱ ይችላሉ፡፡

13.<u>ስለማኅበራት መቋቋም</u>

1. በሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ የተሠማሩ ሰዎችና ድርጅቶች የሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ማኅበር ሊያቋቁሙና አባል ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

2. በመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ውድድር መኖሩን ለማረጋገጥ በአንድ ማህበር የሚታቀፉ የአባላት ብዛት ባለሥልጣኑ ይወሰናል፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛዉም በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ የተመለከቱትን ሁኔታዎች የሚያሟላ ሆኖ የተገኘዉን ማንኛዉንም በሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ የተሠማራ ሰው ወይም ድርጅት በአባልነት የመቀበል ግዴታ አለበት።
4. በሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ የተሠማራ ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት በአንድ ጊዜ በአንድ የሥምሪት መስመር ውስጥ ከአንድ በላይ በሆኑ ማኅበራት ውስጥ አባል ሊሆን አይችልም።
5. ባለሥልጣኑ የማኅበራትን ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል።

14.**ተፈፃሚነት የሚኖረዉ ህግ**

በፍትሐብሔር ሕግ ከአንቀጽ 404-482 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ በሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ማኅበሮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፤ ሆኖም በነዚሁ ድንጋጌዎች ለፍትሕ ሚኒስቴርና[74] ለማኅበሮች ጽሕፈት ቤት የተሰጠው ኃላፊነት ማኅበራቱን በሚመለከት በዚህ አዋጅ ለባለሥልጣኑ ተላልፎአል፡፡

15.**ስለማህበራት ምዝገባ**

1. ማናቸውም ማኅበር እንደተቋቋመ ወዲያውኑ የምዝገባ ማመልከቻውን ከማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ ጋር አያይዞ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት።
2. ለባለሥልጣኑ የምዝገባ ማመልከቻ ሲቀርብለት፤
   ሀ) የማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ ሕግንና ባለሥልጣኑ ያወጣዉን ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ የተከተለ መሆኑን፣
   ለ) አግባብነት ያለው ማንኛቸውም ሕግ የሚጠይቀው ሁኔታ መሟላቱን በማረጋገጥ፣ እና የተወሰነውን የመመዝገቢያ ክፍያ በማስከፈል ማኅበሩን ይመዘግበዋል፡፡
3. ባለሥልጣኑ የማኅበሩን የመመዝገቢያ ጥያቄ የማይቀበለው ከሆነ ያልተቀበለበትን ምክንያት በመግለጽ በ7 ቀናት ውስጥ ለማኅበሩ ማስታወቅ አለበት፡፡ ባለሥልጣኑ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ በማመልከቻው ላይ አንዳችም ውሳኔ ካልሰጠ ማኅበሩ እንደተመዘገበ ይቆጠራል።
4. ማኅበሩ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ በሕግ የሰውነት መብት ያገኛል፡፡

---

[74] በአዋጅ ቁጥር 22/62 (2008) አ. 943 አንቀጽ 3(1) መሰረት የፌደራል ጠቅላይ ዐ/ህግ ሆኗል፡፡

16.**<u>የምዝገባ ዕድሳት</u>**

1. ማንኛውም ማህበር በየዓመቱ ከመስከረም 1 ቀን እስከ የካቲት 30 ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን ክፍያ በመፈፀም ምዝገባዉን ማሳደስ አለበት፡፡
2. ምዝገባው በየዓመቱ ካልታደሰ ማህበሩ ሥራውን አይቀጥልም፡፡

17.**<u>የማኅበራት ዓላማና ተግባር</u>**

ማኅበራት የሚከተሉት ዓላማዎችና ተግባሮች ይኖራቸዋል፤

1. ለአባላት የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የስምሪት ፕሮግራም ማዘጋጀትና እንደ አግባቡ በባለሥልጣኑ ሲጸድቅ ማስፈጸም፤
2. ለአባላት የጋራ ጥቅም የሚያገለግሉትን የሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች መናኸሪያዎችን፣ የመንገድ ጣቢያዎችን፣ የጭነት ማከፋፈያ ጽ/ቤቶችን፤ የጥገና ተቋሞችን፣ የነዳጅ ማደያ ጣቢያዎችን፣ የመለዋወጫ ዕቃ መደብሮችንና የመሳሰሉትን ማቋቋምና ማካሄድ፤
3. ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችንና ሰነዶችን በሚገባ መያዝና በባለሥልጣኑ ሲጠየቁም ማቅረብ፤
4. ስለመንገድ ትራንስፖርት የወጡትን ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች አባላት እንዲያውቁና እንዲያከብሩ ማድረግ፤
5. የአባላቱ ተሽከርካሪዎች የሚያደርሱትን የትራፊክ አደጋ ለመቀነስ የሚያስችል የግንዛቤ ማዳበሪያና ስልጠና ስርዓት ማመቻቸት፤ እና
6. ከሥራቸው ጋር በተገናኙ ሌሎች ሕጋዊ ተግባሮችን ማከናወን።

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

18.**<u>የመረጃ ማዕከል ስለማቋቋም</u>**

1. ባለሥልጣኑ ትራንስፖርትን የሚመለከቱ መረጃዎችን ለማሰባሰብና ለማጠናቀር የመረጃ ማዕከል ያቋቁማል፡፡

2. የክልል ቢሮዎች የፌዴራልና የክልል ፖሊስ ኮሚሽኖች፣ የህዝብ የንግድ የመንገድ ማህበራት፣ ግለሰቦች እና ሌሎች ድርጅቶች ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ከትራንስፖርት ጋር የተያያዘ አስፈላጊውን መረጃ በወቅቱ ማቅረብ ወይም ማስተላለፍ አለባቸዉ።
3. አስፈላጊውን መረጃ ለማስተላለፍ የሚረዳ የናሙና ቅጽ ባለሥልጣኑ ያዘጋጃል፡፡

19.<u>በሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ የተሠማሩ ሰዎችና ድርጅቶች ግዴታ</u>

በሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ የተሠማሩ ሰዎችና ድርጅቶች ስለመንገድ ትራንስፖርት የወጡትን አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ማክበር አለባቸው።

20.<u>ስለብቸኛ መብቶችና ዉሎች</u>

1. ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ በዓለም አቀፍና በአገር አቋራጭ የሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ ለተሠማሩ ሰዎች፣ ድርጅቶች ወይም ማህበራት የተረጋገጠ ገቢ የሚያገኙበትን ሁኔታ በመፍጠር የሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ አገልግሎት በማያገኙ ወይም በቂ ባልሆነባቸዉ መስመሮች እንዲሰሩ ለማበረታታት ብቸኛ ወይም የተወሰኑ መብቶች ለመስጠት የሚያስችል መመሪያ ያወጣል።
2. የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ማንኛዉም አስጫኝ የሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ የሚሠሩ ሰዎች ወይም ድርጅቶች ጋር ብቸኛ የማጓጓዣ ዉል የማድረግ መብቱን የማገድ ወይም የመገደብ ዉጤት አይኖራቸዉም።

21.<u>ተሽከርካሪዎችን የማስመዝገብ ግዴታ</u>

1. የፍጥነት ወሰኑ በሰዓት ከ20 ኪሎ ሜትር ከማይበልጥ ልዩ ተንቀሣቃሽ መሳሪያ በስተቀር፣
   ሀ) በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብና መመሪያ መሠረት ያልተመዘገበ፣ እና
   ለ) ተገቢዉን የመኪና ሰሌዳ ወይም ሌላ የመለያ ምልክት የሌለዉን፣ ተሽከርካሪ በማናቸዉም መንገድ ላይ መንዳት ክልክል ነው።
2. ተገቢዉን የመኪና ሠሌዳ ወይም ሌል የመለያ ምልክት አለመኖር ተሽከርካሪዉን እንዳልተመዘገበ ስለሚያስቆጥረዉ ተገቢዉ ምርመራ እስከሚፈፀም ድረስ ፖሊስ እንዲህ ያለውን ተሽከርካሪ ለማቆየት ይችላል፡፡

22.**የመንጃ ፈቃድ አስፈላጊነት**

1. ማንኛውም ሰው ዓይነቱ ተለይቶ የተገለጸን ባለሞተር ተሽከርካሪ ለመንዳት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብና መመሪያ መሠረት የተሰጠው የጸና የመንጃ ፈቃድ ከሌለው በስተቀር በማናቸውም መንገድ ላይ ማናቸውንም ዓይነት ባለሞተር ተሽከርካሪ መንዳት አይችልም።
2. ማናቸውም የባለሞተር ተሽከርካሪ ባለቤት የጸና የመንጃ ፈቃድ የሌለው ሰው ተሽከርካሪውን እንዲነዳ መፍቀድ የለበትም፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ እና /2/ ድንጋጌ ቢኖርም፣ የመንጃ ፈቃድ የሌላቸው ሰዎች የባለሞተር ተሽከርካሪ አነዳድ ለመማር መንዳት የሚችሉበት ሁኔታ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

23.**የባህሪኛና የባቡር ነጅነት ፈቃዶች**

1. [75]
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተው ቢኖርም ከዚህ አዋጅ መጽናት በፊት በሚመለከተው አካል የተሰጠ ፈቃድ በፈቃዱ እስከተመለከተው ጊዜ የጸና ይሆናል፡፡

24.**ስለሥልጣን ዉክልና**

1. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባለሥልጣኑ ከስልጣንና ተግባሩ በከፊል አንደ አግባቡ ለክልል ቢሮዎች፣ ለማዘጋጃ ቤቶችና ለሌሎች መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ላልሆኑ አካላት በውክልና መስጠት ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ውክልና የተሰጣቸው አካላት በውክልና የተቀበሉትን ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ ሊያውሉ ስለትራንስፖርት የወጡ አዋጆችን፣ ደንቦችን፣ መመሪያዎችንና በባለሥልጣኑ የሚወጡ ደረጃዎችን መከተልና መጠበቅ ይገባቸዋል፡፡

25.**የተሻሩና ጸንተው የሚቆዩ ሕጎች**

1. የመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 14/1984 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

[75] በ13/60 (1999) አ. 549 አንቀጽ 17(2) (ለ) እንዲሁም በ23/73 (2009) አ.1048 አንቀፅ 51(1) ተሻረ፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ /1/ ድንጋጌ ቢኖርም በአዋጅ ቁጥር 14/1984 ወጥተዉ ወይም ጸንተው የነበሩ ደንቦች ሁሉ ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ በዚህ አዋጅ መሠረት እንደወጡ ተቆጠረው የፀኑ ይሆናሉ፡
3. ይህን አዋጅ የሚቃረን ሌላ ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

26.**ስለመብትና ግዴታዎች መተላለፍ**

1. በአዋጅ ቁጥር 14/1984 ተቋቁሞ የነበረው የመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለባለሥልጣኑ ተላልፈዋል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ የትራንስፖርት ባለሥልጣንና የድሬዳዋ ከተማ የትራንስፖርት ኤጀንሲ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለባለሥልጣኑ ተላልፈዋል፤ የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሆነዉ ይደራጃሉ፡፡

27.**የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

1. በአዋጅ ቁጥር 14/1984 መሠረት የተቋቋሙ ማህበራት በዚህ አዋጅ እንደተቋቋሙ ተቆጥረው ሥራቸውን ይቀጥላሉ።
2. ክልሎች የራሳቸውን እስኪያወጡ ድረስ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ትራንስፖርት ነክ በሆኑት ጉዳዮች ላይ በክልሎች ውስጥ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

28.**ደንብ የማዉጣት ስልጣን**

ይህን አዋጅ በአግባቡ ሥራ ላይ ለማዋል የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የማውጣት ሥልጣን ይኖረዋል።

29.**ቅጣት**

ይህን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችን የተላለፈ ማንኛውም ሰው በወንጀል ሕግ መሠረት ይቀጣል፡፡

30.**አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከሐምሌ 6 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ቀን 1997 1ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 547/1999

## በየብስ የዕቃ ማጓጓዝ ሥራን ለመደንገግ ተሻሽሎ የወጣ አዋጅ

የትራንስፖርት አገለግሎት የአገራችንን ልማት ለማሳካት፣ ለአጠቃላይ የንግዱ ክፍለ ኢኮኖሚ ዕድገትና ለሕዝቦች መቀራረብ ወሳኝ ሚና የሚጫወት የአገልግሎት ዘርፍ በመሆኑ፤

በማናቸውም የማጓጓዣ ዓይነት ዕቃ ማጓጓዝን የሚመለከቱ የአገራችን የትራንስፖርት ሕጎች አንዱ ከሌላው ጋር መጣጣምና ተቀናጅቶ አገልግሎት በመስጠት ለአገራችን የኢኮኖሚ ዕድገት የበኩሉን ድርሻ መወጣት የሚጠበቅበት በመሆኑ፤

ከዚህ አንፃር በ1952 ዓ.ም በንግድ ሕግ አማካኝነት ወጥቶ በሥራ ላይ ያለውን ሕግ በተለይም የአጓጓዦችን የኃላፊነት መሠረት፣ የኃላፊነት መጠን ወሰንና ሌሎች መብቶችና ግዴታዎችን አስመልክቶ ዓለም ዓቀፍ ይዘት ካለውና በአዋጅ ከወጣው የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አሠራር ጋር በማቀናጀት ወጥ የሆነና የተቀላጠፈ አግልግሎት መስጠት በሚያስችል መልኩ አሻሽሎ መደንገግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55 /1/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "በየብስ የዕቃ ማጓጓዝ ሥራን ለመደንገግ ተሻሽሎ የወጣ አዋጅ ቁጥር 547/1999" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "ዕቃን በየብስ የማጓጓዝ ውል" ማለት አጓጓዡ የጭነት ክፍያ ወይም ዋጋ በማስከፈል ዕቃን የአገር ውስጥ ውኃን ጨምሮ በየብስ ላይ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በተሽከርካሪ ለማጓጓዝ ግዴታ የገባበት ማንኛውም ውል ማለት ነው፤
2. "ዕቃ" ማለት የቁም እንስሳትን ጨምሮ ኮንቴነሮችን፣ የዕቃ ማሸጊያዎችን ወይም ተመሳሳይ የዕቃ ማሸጊያ ቁሶችን ወይም በዕቃ ላኪው ወይም በዕቃ አስረካቢ በጥቅል መልክ ለጭነት የሚቀርብ ማንኛውም ንብረት ነው፣

3. “አጓጓዥ” ማለት ዕቃን በተሽከርካሪ አማካኝነት በየብስ ወይም በአገር ውስጥ ውኃ የሚያጓጉዝ ሰው ማለት ነው፤
4. “ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
5. “ላኪ” ማለት ለራሱ ወይም ለሦስተኛ ወገኖች ሲል ዕቃውን እንዲያጓጉዝ ለአጓጓዡ የሚያስረክብ ሰው ማለት ነው፤
6. “ተረካቢ” ማለት ዕቃውን ለመቀበል ሕጋዊ መብት ያለው ሰው ማለት ነው፤
7. “አደገኛ ዕቃዎች” ማለት በባህሪያቸው አደጋ የሚያመጡ ዕቃዎች ወይም አደጋ ሊያስከትሉ ይችላሉ ተብለው የተመደቡ፣ ተቀጣጣይ፣ የሬድዮ ሞገድ የማመንጨትና የመርጨት ባህሪ ያላቸው፣ በጤንነት ላይ አደጋ ማስከተል የሚችሉ አደገኛ የንጥረ ነገር ወይም የጋዝ ወይም የፈሳሽ ባህሪ ያላቸው፤ በአጠቃላይ በሰዉ ልጆችና በአካባቢ ላይ ጥፋት ማስከተል የሚችሉትን ሁሉ የሚያጠቃልል ሆኖ ዝርዝሩ አግባብ ባለው አካል ይወሰናል፤
8. “ተሽከርካሪ” ማለት ማንኛውንም ዓይነት ዕቃ ወይም ጭነት እንዲያመላልስ ተብሎ የተሠራና ለዚሁ አገልግሎት እንዲውል የተደረገ ባለሞተር ሲሆን ባቡርን፣ ግማሽ ተሣቢንና ተሣቢን ይጨምራል፣
9. “ጭነት ማስተላለፍ” ማለት ዕቃን ለማጓጓዝ የማጓጓዣ ውል ከፈፀመው ተሽከርካሪ ባለቤት ወደ ሌላ ተሽከርካሪ ባለቤት ወይም ወደ ሌላ የትራንስፖርት ዓይነት ማስተላለፍ ማለት ነው ፣
10. “ተጨማሪ ክፍያ ” ማለት በገበያ ዋጋ መሠረት መከፈል ከሚገባው መደበኛ የጭነት ክፍያ ተመን በላይ ክፍያ ማስከፈል ማለት ነው፡፡
11. “እስፒሻል ድሮዊንግ ራይት” ማለት በጥቅል ወይም በኪሎ ግራም የተጠቀሰዉ የአጓጓዡ የኃላፊነት መጠን የዓለም አቀፍ የገንዘብ ፈንድ አሠራርን መሠረት በማድረግ ገንዘቡ ከሚከፈልበት አገር ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የምንዛሪ ተመን ማለት ነው፣

12.“ዕቃ አስተላላፊ” ማለት በአገር ውስጥ ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕቃ ተቀባይን ወይም ዕቃ ላኪን በመወከል የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት፣ የወደብ ሥነ-ሥርዓት እና ሌሎች ሥነ-ሥርዓቶችን አስፈፅሞ የገቢ ወይም የወጪ ዕቃዎች በወደብ እንዲገቡ ወይም እንዲወጡ ማድረግ ሲሆን ዕቃን የማጓጓዝንና የማስረከብን ሥራ ይጨምራል፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

1. የዚህ አዋጅ ድንጋጌ በተሽከርካሪ አማካኝነት ዕቃን በክፍያ በየብስ ላይ እና በአገር ውስጥ ውሃ ላይ ለማጓጓዝ በሚደረግ ማናቸዉም ዉል ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
2. የዚህ አዋጅ ድንጋጌ የማጓጓዙ ሥራ በዚህ አዋጅ ተፈጻሚነት ወሰን ክልል ውስጥ በሆነ ጊዜ በመንግሥት ወይም በመንግሥት ተቋማት በሚከናወን የማጓጓዝ ሥራ ላይም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
3. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ እና /2/ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የዚህ አዋጅ ድንጋጌ በሚከተሉት ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።
   ሀ) በፖስታ አገልግሎት ሕግ መሠረት በሚከናወን የማጓጓዝ ስራ፣
   ለ) የቤት ዕቃን ከቤት ቤት የማጓጓዝ ሥራ፡፡
4. ለዚህ አዋጅ ዓላማዎች ሲባል የአጓጓዡ ወኪሎች፣ ሰራተኞችና የማጓጓዝ ሥራውን ለማከናወን የሚጠቀምበት ሌላ ማናቸውም ሰው ለሚፈጽሙት ድርጊትና መፈፀም ሲገባቸው ሣይፈፀሙ ለቀሩት ተግባር አጓጓዡ ኃላፊ የሚሆን ሲሆን፤ እነዚሁ ወኪሎች፣ ሠራተኞችና ሌሎች ሰዎች የፈፀሙት ተግባር በቅጥር ውላቸው መሠረት ከሆነ ስራውን መፈፀማቸው ወይም አለመፈፀማቸው የአጓገፉ ኃላፊነት ብቻ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የማጓጓዝ ውል ስለመመስረት</u>

4. <u>የማጓጓዣ ሰነድ</u>

1. ዕቃ የማጓጓዝ ውል በማጓጓዣ ሰነድ መረጋገጥ አለበት፡፡
2. የዕቃ ማጓጓዝ ሰነድ አለመኖር፣ ያልተሟላ መሆን ወይም መጥፋት፣ በዚህ አዋጅ የተመለከተውን ድንጋጌና ዕቃዎቹን ስለማጓጓዝ የተደረገውን ውል ዋጋ ያለውና ተፈጻሚ መሆኑን ሊያስቀረው አይችልም።

5. <u>**የማጓጓዣ ሰነድ ቅጅዎች**</u>

1. የዕቃ ማጓዣው ሰነድ በሦስት ዋና ቅጅዎች ዕቃውን በሚልከዉ ሰው ይዘጋጃል፡፡

ሀ) የመጀመሪያ ቅጅ በላኪው ተፈርሞበት ለአጓጓዡ ይሰጣል፡፡

ለ) ሁለተኛዉ ቅጅ ላኪዉና አጓጓዡ ፈርመዉበት ከዕቃዉ ጋር ይሆናል፡፡

ሐ) ሦስተኛው ቅጅ አጓጓዡ ፈርሞበት ዕቃውን ከተቀበለ በኋላ አጓጓዡ ለላኪው ይሰጠዋል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 1/ሐ/ የተጠቀሰዉ ፊርማ የታተመ ወይም በላኪዉና በአጓጓዡ ማኅተም የሚተካ ሊሆን ይችላል፡፡

3. የሚጓጓዙት ዕቃዎች በተለያዩ ተሽከርካሪዎች፣ የባቡር ፉርጎዎች ወይም በተለያዩ ዓይነት ማጓጓዣዎች ወይም በተለያዩ ጭነቶች የተከፋፈሉ ሲሆኑ፣ ላኪዉ ወይም አጓጓዡ ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ ወይም የባቡር ፉርጎ ወይም ለእያንዳንዱ ማጓጓዣ ዓይነት ወይም የዕቃዎች ጭነት የተለያየ የማጓጓዣ ሰነድ የመጠየቅ መብት ይኖረዋል።

6. <u>**የዕቃ ማጓጓዣ ሰነድ የሚይዛቸው ዝርዝሮች**</u>

1. የዕቃ ማጓጓዣዉ ሰነድ የሚከተሉትን ዝርዝሮች መያዝ ይኖርታል፡፡

ሀ) የዕቃ ማጓጓዣ ሰነዱ የተሰጠበትን ቀንና ቦታ፤

ለ) የላኪውን ስምና አድራሻ፣

ሐ) የአጓጓዡን ስምና አደራሻ፣

መ) ዕቃዎቹን ለማጓጓዝ ርክክብ የተደረገበት ቀንና ቦታ፣ መድረሻ ላይ የማስረከቢያ ቦታ፤

ሠ) የተረካቢዉ ስምና አድራሻ፣

ረ) ስለ ዕቃዎቹ ዝርዝር መግለጫ፣ የዕቃውን ባህሪ እና የአስተሻሸግ ዘዴ፣ እንዲሁም አደገኛ ዕቃዎች በሆኑ ጊዜ የታወቀው አጠቃላይ ባህሪያቸው መግለጫ፣

ሰ) የጥቅሎቹ ብዛት ልዩ ምልክትና ቁጥራቸዉ፣

ሸ) የዕቃዎቹ ጠቅላላ ክብደት ወይም ይህ ካልተገለፀ ብዛታቸዉ፤

ቀ) ከማጓጓዙ ጋር የተያያዙ የማጓጓዣ ክፍያዎች፣ ተጨማሪ ክፍያዎችና ሌሎች ውሉ ከተደረገበት ጊዜ እስከ ማስረከቢያው ጊዜ ድረስ የሚወጡ ወጪዎች

በ) በዚህ አዋጅ አንቀፅ 13 ድንጋጌ መሠረት ለጉምሩክ መብት ማስፈፀም እና ለሌሎች ስነ-ሥርዓቶች የሚጠየቁ ሰነዶች አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ በአባሪነት መያያዛቸዉን፡፡

2. አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ የማጓጓዣው ሰነድ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ዝርዝሮችም መያዝ አለበት፤

ሀ) ጭነት ማስተላለፍ የማይፈቀድ መሆኑን የሚያመለክት ፅሁፍ፤

ለ) ላኪው ለመክፈል ግዴታ የገባባቸዉ ክፍያዎች፣

ሐ) የዕቃዎቹ ዋጋ መግለጫ፣

መ) የዕቃዎቹን የመድን ዋስትና በተመለከተ፤ ላኪዉ ለአጓጓዡ የሚሰጣቸዉን መመሪያዎች፣

ሠ) ዕቃዉን ለማጓጓዝ ስምምነት የተደረሰበት የጊዜ ገደብና የሚጓጓዝበት የጉዞ መስመር፤

ረ) ለአጓጓዡ የተሰጡ ሰነዶች ዝርዝር፤

3. ተዋዋይ ወገኖች ጠቃሚ ናቸው ብለው ካመኑ በዚህ አንቀጽ ያልተጠቀሱ ሌሎች ዝርዝሮችን በማጓጓዣ ሰነዱ ላይ ሊያስገቡ ይችላሉ፡፡

7. <u>ለታዘዘለት የሚል የዕቃ ማጓጓዣ ሰነድ</u>

ላኪውና አጓጓዡ ከተስማሙ የማጓጓዣው ሰነድ ተቀባዩ ሰው ላዘዘው በሚል ሊዘጋጅ ይችላል፡፡

8. <u>ሌላ የማጓጓዣ ሰነድ</u>

1. ላኪውና አጓጓዡ ከተስማሙ የማጓጓዣዉ ሰነድ አጓጓዡ በሚሰጠዉና ላኪዉ ተገቢ የሆኑትን ጽሑፎች በሚያሰፍርበት እንደ ደረሰኝ ባሉ ሌሎች ሰነዶች ሊተካ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተጠቀሰው ደረሰኝ ወይም ሰነድ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚቃረን የዉል ቃል ይዞ ቢገኝ የማጓጓዣ ዉሉ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ተፈፃሚነት ያገኛል።

9. <u>ስለላኪዉ ጽሑፍ</u>

1. የሚከተሉትን አስመልክቶ፡

ሀ) በአንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 (ለ)፣ (መ)፣ (ሠ)፣ (ረ)፣ (ሰ)፣ (ሸ)፣ (ቀ) እና (በ) የተጠቀሱትን በመሙላት ረገድ፣

ለ) በአንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሱትን በመሙላት ረገድ እና

ሐ) የማጓጓዣ ሰነዱ እንዲዘጋጅለት ወይም በሰነዱ ላይ እንዲገባ በተሰጡ ሌሎች መመሪያዎች ወይም ትዕዛዞች በአግባቡ ባለመፈፀማቸው ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ወይም ያልተሟላ መግለጫ በመስጠቱ ምክንያት አጓጓዡ ለወጪ ቢዳረግ ወይም ኪሣራና እና ጉዳት ቢደርስበት ላኪው በሙሉ ኃላፊነት አለበት፡፡

2. በላኪው ጠያቂነት አጓጓዡ በአንቀጽ 6 (1) ላይ የተጠቀሱትን ዝርዝሮች በዕቃ ማጓጓዣ ሰነዱ ላይ አስገብቶ ከሆነ ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በስተቀር አጓጓዡ በላኪዉ ስም እንዳደረገው ይቆጠራል፡፡

3. አስፈላጊ በሆነ ጊዜ የዕቃ ማጓጓዣው ሰነድ በአንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 (በ) የተጠቀሱትን ሰነዶች በአባሪነት ካልያዘ፣ ወይም የዕቃ ማጓጓዣው ሰነድ በአንቀጽ 6 የተጠቀሱትን ዝርዝሮች ባልያዘ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 8 ድንጋጌ መሠረት እንደ ደረሰኝ ባሉ ሌሎች ሰነዶች ከተተካ አጓጓዡ ይህን ሣያረጋግጥ ዕቃ በመቀበሉ ምክንያት ለደረሱ ወጭዎች፣ ኪሣራ እና ጉዳት በዕቃዎቹ ላይ የማዘዝ መብት ላለው ሰው ኃላፊነት አለበት፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>የዕቃ ማጓጓዣ ዉል አፈፃፀም</u>

### 10.<u>መጠቅለል</u>

1. ከዕቃዎቹ ባህሪ አንፃር መጠቅለል የሚያስፈልጋቸዉ ሆኖ ሲገኝ፤ ዕቃዎቹ እንዳይጠፉና እንዳይጎዱ ላኪዉ መጠቅለል ወይም ማሸግ ይኖርበታል።
2. ከአጠቃላለል ጉድለት የተነሳ በዕቃዉ ላይ ለሚደርስ ማናቸውም ጉዳት ላኪዉ ኃላፊ ይሆናል።
3. እንዲሁም ዕቃዎቹ ያልታሸጉ መሆኑን ወይም አስተሻሸጉ ጉድለት የነበረበት መሆኑን አጓጓዡ እያወቀ ዕቃዎቹን ተቀብሎ ያጓጓዘ እንደሆነ ለሚደርሰው ጉዳት ራሱ ኃላፊ ይሆናል፡፡

11.<u>አለመስማማትን ስለመግለፅ</u>

1. አጓጓዡ ዕቃዎቹን ሲረከብ፣
   ሀ) በማጓጓዣ ሰነዱ ላይ የሰፈሩትን የዕቃዎች ብዛት ወይም የጥቅሎችን ቁጥር፣ በጥቅሎች ላይ ያለውን ልዩ ምልክቶችንና መግለጫዎችን ትክክለኛነት እና እንዲሁም የዕቃዎቹን ክብደት፣
   ለ) የዕቃዎቹን ውጭያዊ ሁኔታና አስተሻሸጋቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡
2. አጓጓዡ ከዚህ በላይ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀጽ /1/ የተጠቀሱትን ዝርዝሮች ለማረጋገጥ የሚችልበት ተቀባይነት ያለው መንገድ የሌለው ከሆነ ምክንያቱን መሠረት ያደረገበትን ከመግለጽ ጋር አለመስማማቱን በማጓጓዣ ሰነዱ ላይ ማስፈር ይኖርበታል፡፡ የዕቃዉን ግልፅ ሁኔታና አስተሻሸጋቸዉን በተመለከተም በተመሳሳይ ሁኔታ ማንኛዉንም አለመስማማት መግለፅ አለበት፡፡
3. በማጓጓዣ ሰነዱ ላይ በቀረቡት ያለመስማማት መግለጫዎች እንደሚገደድ በግልፅ ካልተስማማ በስተቀር ላኪው በእነዚህ መግለጫዎች ውጤት አይገደድም፡፡
4. ላኪው ለጭነት ያቀረበውን የዕቃዉን ጠቅላላ ክብደት፤ ወይም መጠን፣ ጥቅል ከሆነ ጥቅሉ በውስጡ የያዘውን አጓጓዡ እንዲያረጋግጥ ሊጠይቅ ይችላል፡፡
5. የማረጋገጡም ውጤት በዕቃ ማጓጓዣው ሠነድ ላይ መገለፅ አለበት፡፡ አጓጓዡ ዕቃዎቹን በተገለፀው ሁኔታ ለማረጋገጥ ያወጣው ወጪ ካለ ይህን ወጪ ላኪው እንዲከፍለው መጠየቅ ይችላል፡፡

12.<u>የማጓጓዣ ሰነድ የሚሰጠው ውጤት</u>

1. ተቃራኒ ማስረጃ ቀርቦ ማስተባበል ካልተቻለ በስተቀር የማጓጓዣ ሰነድ ወይም ከአንቀጽ 4 - 8 ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት የተዘጋጀ ሌላ ሰነድ የማጓጓዣ ውል ስለመደረጉ፣ የውሉን ሁኔታዎችና ዕቃዎቹን አጓጓዡ ስለ መቀበሉ፣ ስለ ዕቃዎቹ ዓይነት፣ ብዛት፣ መጠንና ክብደት ማስረጃ ነው።
2. ተቃራኒ ማስረጃ ቀርቦ ማስተባበል እስካልተቻለ ድረስ በዚሁ አዋጅ አንቀፅ 11 (2) ድንጋጌ መሠረት በአጓጓዡ በግልጽ ተለይቶ የሰፈረዉን የአለመስማማት መግለጫ ያልያዘ የማጓጓዣ ሰነድ፤ አጓጓዡ በተረከባቸዉ ጊዜ ዕቃዎቹና አስተሻሸጋቸዉ በጥሩ ሁኔታ ለአጓጓዡ እንደተሰጡና የጥቅሎቹ ብዛት፣ ክብደት

ምልክቶቻቸዉና ቁጥሮቹ በማጓጓዣ ሰነዱ ላይ ከተጠቀሱት ጽሑፎች ጋር የተጣጣሙ እንደሆኑ ይገመታል።

13.**<u>የጉምሩክና ሌሎች ሥነ-ሥርዓቶች</u>**

1. ላኪው የጉምሩክን ወይም ሌሎች ሥነ-ሥርዓቶችን ለማስፈፀም ሲባል አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን ከማጓጓዣ ሰነድ ጋር በማያያዝ ለአጓጓዡ መስጠት ይኖርበታል፡፡
2. አጓጓዡ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተጠቀሱትን ሰነዶችና መረጃዎች ትክክለኛነትም ሆነ የተሟሉ ስለመሆናቸው ለመመርመር ምንም አይነት ግዴታ የለበትም፡፡
3. ላኪው በእነዚህ ሰነዶችና መረጃዎች አለመኖር፣ ያለመሟላት ወይም ግድፈት የተነሳ ለሚደርሰው ጉዳት በአጓጓዡ ጥፋት ወይም ቸልተኝነት ካልሆነ በስተቀር ለአጓጓዡ ኃላፊ ይሆናል፡፡
4. አጓጓዡ የተጠቀሱትን ሰነዶችና ከማጓጓዣ ሰነዱ ጋር ተያያዥ የሆኑትን ሰነዶች የሚረከበዉ በወኪልነት ሲሆን የሰነዶች መጥፋት፣ ወይም ተገቢ ያልሆነ አጠቃቀም ለሚያስከትለው ውጤት ኃላፊነት አለበት፡፡
5. ይህም ኃላፊነት አጓጓዡ ዕቃዉ በጠፋ ጊዜ ከሚከፍለው ካሣ ሊበልጥ አይችልም፡፡

14.**<u>ላኪው በዕቃዉ ለማዘዝ ስላለው መብት፣</u>**

1. ላኪው በማጓጓዣ ዉሉ መሠረት ግዴታዎችን በሙሉ ከፈፀመ ዕቃውን ከአጓጓዡ መልሶ በመዉሰድ ወይም ዕቃዉ በጉዞ ላይ እያለ በማስቆም ወይም የዕቃዉን የማስረከቢያ ቦታ በመለወጥ ወይም በጉዞ ላይ እየለ ዕቃዉ ሊራገፍበት የሚገባው ቦታ ከመድረሱ በፊት በማጓጓዣ ሰነዱ ላይ ከተመለከተዉ ተረካቢ ዉጪ ለሌላ ሰዉ እንዲሰጥ በማድረግ ዕቃዉን የማስተላለፍ መብት አለው፡፡
2. የማጓጓዣ ሰነዱ ለላኪው ተሰጥቶ ከሆነ ላኪው ይህንን የማጓጓዣ ሰነድ ለአጓጓዡ ሳያቀርብ በዕቃዉ ላይ ያለውን መብት ማስተላለፍ አይችልም።
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ የተጠቀሰዉ የዕቃ ላኪው በዕቃዉ ላይ የማዘዝ መብት የሚቋረጠዉ የማጓጓዣ ሰነድ ለዕቃ ተረካቢዉ ሰው ከተሰጠ በኋላ ወይም ዕቃው መድረሻ ሥፍራው ደርሶ ተቀባዩ አጓጓዡ ዕቃውን እንዲያስረክበው ከጠየቀ በኋላ ነው።

4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /3/ የተጠቀሰው ቢኖርም ላኪው በማጓጓዣ ሰነዱ ላይ ዕቃ ተቀባዩ እቃውን የማስተላለፍ መብት ይኖረዋል የሚል አካቶ ከሆነ ተረካቢዉ የማጓጓዣ ሰነዱ ከተፃፈበት ጊዜ ጀምሮ ዕቃውን የማስተላለፍ መብት አለው፡፡
5. ተቀባዩ ዕቃውን የማስተላለፍ መብቱን በሚገለገልበት ጊዜ ዕቃዎቹ ለሌላ ሰው እንዲሰጡ አዞ ከሆነ ይሄዉ የታዘዘለት ሦስተኛ ሰዉ ሌሎች ተረካቢዎችን ለመሰየም መብት አይኖረዉም፡፡
6. በዕቃዉ ላይ ያለውን መብት ለሌላ የማስተላለፍ መብት በሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ ይመሰረታል
   ሀ) ላኪው ወይም እንደነገሩ ሁኔታ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 በተጠቀሰዉ መሠረት ተቀባዩ አዲስ መመሪያዎች ያሉበትን የማጓጓዣ ሰነዱን አንደኛ ቅጅ ለአጓጓዡ በማቅረብ መብቱን የማስተላለፉ ትዕዛዝ አፈፃፀም ያስከተለውን ወጪ፣ ኪሣራና ጉዳት አስመልክቶ አጓጓዡን በመካሥ፣
   ለ) እንደዚህ ዓይነቶቹ ትዕዛዞች ፈፃሚዉ ሰዉ ዘንድ በደረሱ ጊዜ ሊፈፀሙ የሚችሉና ትዕዛዞቹ ከአጓጓዡ መደበኛ አሰራር ጋር የማይጋጩ የሆነ እንደሆነ ወይም የላኪዉንና የተቀባዩን ሌሎች ዕቃዎችን ከማጓጓዝ ሥራ ጋር የማይጋጩ ሆነው ሲገኙ እና፣
   ሐ) ትዕዛዞቹ በማጓጓዣ ውሉ ላይ የተመለከተውን ጭነት የመከፋፈል ውጤት የማይኖራቸው ሲሆን ነው።
7. አጓጓዡ በንዑስ አንቀጽ 6 (ለ) በተጠቀሰዉ ምክንያት የተቀበላቸዉን ትዕዛዞች መፈፀም ባልቻለ ጊዜ ትዕዛዙን ለሰጠው ሰዉ ወዲያውኑ ማሳወቅ ይኖርበታል።
8. አጓጓዡ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ እስከ /7/ በተጠቀሱት ሁኔታዎች የተቀበላቸውን ትዕዛዞች ያልፈፀመ እንደሆነ ወይም የዕቃ ማጓጓዣ ሰነዱን አንደኛ ቅጂ ሣይጠይቅ ትዕዛዞቹን ተቀብሎ የፈፀመ እንደሆነ ለሚደርሰው ጥፋት ወይም ጉዳት የመብት ጥያቄ ለማቅረብ መብት ላለው ሰው ተጠያቂ ይሆናል፡፡

15.<u>የማጓጓዝ ዉልን መፈፀም የማያስችል ሁኔታ</u>

1. የማጓጓዝ ዉልን በማጓጓዣ ሰነድ ላይ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት ለመፈፀም የማያስችል ምክንያት ካለ አጓጓዡ በዕቃዎቹ ላይ የማዘዝ መብት ካለው ሰው፣ በአንቀጽ 14 ንዑስ አንቀፆች 1 እስከ 8 ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት ምን መደረግ እንዳለበት ትዕዛዝ እንዲሰጠዉ መጠየቅ አለበት፡፡

2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ /1/ ቢኖርም በተፈጠረዉ ሁኔታ በማጓጓዣ ሰነዱ ከተመለከቱት ሁኔታዎች በተለየ መልኩ ዕቃውን ለማጓጓዝ የሚያስችሉ ከሆነና አጓጓዡ በቂ ነው ተብሎ በሚገመት ጊዜ ውስጥ በአንቀጽ 14 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 8 ድረስ ባሉት ሁኔታዎች መሠረት በዕቃዎቹ ላይ ለማዘዝ መብት ካለው ሰው ላይ ትዕዛዝ ማግኘት ካልቻለ በዕቃዎቹ ላይ ለማዘዝ መብት ያለውን ሰው ተገቢ ጥቅም ለማስጠበቅ አስፈላጊ የመሰለውን እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

16.<u>የተረካቢዉ መብት</u>

1. ተቀባዩ ዕቃዎቹ መድረስ ካለባቸው ቦታ ከደረሱ በኋላ ዕቃውን የሚያመለክት ሰነድ ወይም የማጓጓዣ ሰነዱ ሁለተኛ ቅጂ አባሪ ካለዉ ከእነአባሪዉ ዕቃዎቹን እንዲሰጠዉ አጓጓዡን ለመጠየቅ ይችላል፡፡
2. የዕቃዎቹ መጥፋት ታውቆ ከሆነ ወይም በአንቀጽ 25 የተጠቀሰዉ ጊዜ ካበቃ በኋላ ዕቃዎቹ ካልደረሱ፣ ተቀባዩ ከማጓጓዣ ውሉ የሚመነጩ ማናቸውም መብቶች እንዲፈፀምለት በራሱ ስም አጓጓዡን ለማስገደድ መብት አለው፡፡
3. ተረካቢዉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ በተሰጡት መብቶች የሚጠቀም ከሆነ፣ በማጓጓዣ ሰነዱ የተመለከቱትን ክፍያዎች መክፈል አለበት፡፡ ሆኖም በዚህ ጉዳይ ላይ አለመግባባት በተከሰተ ጊዜ አጓጓዡ ከተቀባዩ ዋስትና እስካልተሰጠዉ ድረስ እቃዎችን እንዲያስረከብ አይገደድም፡፡

17.<u>ማስረከብ ስላልተቻለ ዕቃ</u>

1. ዕቃዎቹ መረከብ ካለባቸው ቦታ ከደረሱ በኋላ ለማስረከብ ሁኔታዎች በከለከሉ ጊዜ፣ አጓጓዡ ላኪዉ ምን ማድረግ እንዳለበት ትዕዛዝ እንዲሰጠዉ መጠየቅ አለበት፡፡ ተቀባዩ ዕቃውን አልቀበልም ያለ እንደሆነ ላኪዉ የማጓጓዣ ሰነዱን አንደኛ ቅጅ ለማቅረብ ሳይገደድ ዕቃውን ለሌላ ሰው የማስተላለፍ መብት ይኖረዋል።
2. ተቀባዩ ዕቃውን ለመረከብ ፈቃደኛ ባይሆንም፣ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት አጓጓዡ ላቀረበው የመመሪያ ጥያቄ ከላኪዉ ተቃራኒ የሆነ መመሪያ እስካልደረሰዉ ድረስ ተቀባዩ ሃሳቡን በመቀየር አጓጓዡ ዕቃዉን እንዲያስረክበዉ ለመጠየቅ ይችላል፡፡

3. አንንገፑ ለማስረከብ ያልተቻለዉ ዕቃ የሚበላሽ የሆነ እንደሆነና ከላኪው በቂ ነው ተብሎ በሚገመት ጊዜ ውስጥ ትዕዛዝ ያልደረሰዉ እንደሆነ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 20 ድንጋጌ መሠረት ዕቃዉ እንዲሸጥ ማድረግ አለበት፡፡
4. አንንገፑ ዕቃውን ለማስረከብ ያልቻለበት ሁኔታ የተፈጠረው ዕቃው ደርሶ ተረካቢው መብቱን በመጠቀም ዕቃዉ ለሦስተኛ ሰዉ እንዲሰጥ ካዘዘ በኋላ ከሆነ ዕቃ ተረካቢው እንደ ላኪ፣ ይህ የታዘዘለት ሦስተኛ ሰዉ ደግሞ እንደ ዕቃ ተረካቢ ተቀጥረው የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ተፈጻሚ ይሆናሉ።

18. <u>ወጭዎች</u>

አንንገፑ መፈፀም ሲገባው ባለመፈፀሙ ወይም መፈፀም የማይገባውን በመፈፀሙ ምክንያት የደረሰ ወጪ ካልሆነ በስተቀር አንንገፑ ላኪዉ ትዕዛዝ እንዲሰጠው፤ እነዚህን ትዕዛዞች ለማከናወን ያወጣቸውን ማናቸውንም ወጭዎች እንዲተካለት የመጠየቅ መብት አለው፡፡

19. <u>ዕቃን ማራገፍና ማስቀመጥ</u>

በአንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ /1/ እና በአንቀጽ 17 ድንጋጌዎች የተጠቀሰው ሁኔታ በተፈጠረ ጊዜ አንገፑ ዕቃውን እንዲያዝባቸው መብት ባለው ሰዉ በሚታሰብ ወጪ ዕቃውን ወዲያውኑ አውርዶ ያራግፋል፡፡ ይህም በሆነ ጊዜ የማጓጓዝ ሥራዉ እንደተጠናቀቀ ይቆጠራል። ከዚህ በኋላ አንንገፑ ዕቃውን መብት ባለው ሰዉ ስም ያስቀምጣል። በማጓጓዣ ሰነዱ የተጠቀሱት ክፍያዎችና ሌሎች ወጭዎች በጠቅላላ በእቃዎቹ ላይ የሚታሰቡ ይሆናሉ።

20. <u>ዕቃዎችን አንንገፑ ስለሚሸጥበት ሁኔታ</u>

1. አንንገፑ በዚህ አንቀፅ 17 ድንጋጌ መሠረት ዕቃውን አንንገፑ ማስረከብ ሳይችል ሲቀርና ዕቃዎቹ የሚባላሹ የሆነ እንደሆነ ወይም የዕቃው ሁኔታ ወደ መበላሸት ማምራቱ ዕርግጠኛ በሆነ ጊዜ ወይም የማስቀመጫዉ ወጭ ከዕቃው ዋጋ በላይ የሆነ እንደሆነ ዕቃዎቹን የሚያዝባቸው ሰው የሚሰጠውን ትዕዛዝ ሳይጠብቅ ሊሸጣቸው ይችላል፡፡
2. በሌሎች ሁኔታዎች አንንገፑ ዕቃውን መሸጥ የሚችለው በእቃዉ ላይ ለማዘዝ መብት ያለው ሰው ተቃራኒ የሆነ ትዕዛዝ ጥያቄው በአንንገፑ በቀረበ 30 ቀን ጊዜ ውስጥ መልስ ሣይሰጥ ሲቀር ነው።

3. ሽያጩ ተካሂዶ ለዕቃዎቹ መከፈል ያለበት ወጭ ከተቀነሰ በኋላ፣ ቀሪ ካለ ዕቃዎቹን ለማስተላለፍ መብት ላለው ሰው ይሰጣል፡፡ እነዚህ ክፍያዎች በሽያጭ ከተገኘው በላይ ከሆኑ አጓጓዡ ልዩነቱን የማግኘት መብት አለው፡፡
4. ሽያጩም አግባብ ባለዉ ሕግ መሠረት በጨረታ ይፈጸማል፡፡

## ክፍል አራት
## የአጓጓዡ ኃላፊነት

**21.የኃላፊነት መሠረትና የጊዜ ገደብ**

አጓጓዡ ዕቃውን በተረከበበት እና በሚያስረክብበት ጊዜ መካከል፤ የማስረከቢያ ጊዜው በማለፉና በመዘግየቱ ምክንያት፤ ዕቃዉ በከፊልም ሆነ በሙሉ ቢጠፋ ወይም ጉዳት ቢደርስበት ኃላፊ ይሆናል፡፡

**22.የአጓጓዡ ከኃላፊነት ነፃ መሆን**

በአንቀጽ 21 የተደነገገዉ ቢኖርም አጓጓዡ ከኃላፊነት ነፃ የሚሆነው ዕቃ የጠፋዉ ወይም ጉዳት የደረሰበት ወይም የዘገየዉ ከዐቅም በላይ በሆነ ምክንያት ወይም በዕቃዉ ዉስጣዊ ይዘት ጉድለት ምክንያት ወይም በላኪዉ ወይም በተቀባዩ ጥፋት ምክንያት መሆኑን ያስረዳ እንደሆነ ነው።

**23.ስለተሽከርካሪ ሁኔታ፡**

አጓጓዡ ዕቃውን ለማጓጓዝ በተጠቀመባቸው ተሽከርካሪ ብልሽት ወይም ጉድለት ምክንያት ወይም ተሽከርካሪዉን በአከራየዉ ሰው ጥፋት ወይም ቸልተኝነት ምክንያት ወይም በወኪሉ ወይም በአከራዩ ሰራተኛ የጥፋት ድርጊት ወይም ቸልተኝነት ምክንያት ዕቃ ቢጠፋ ወይም ጉዳት ቢደርስበት ወይም ርክክቡ ቢዘገይ ከሃላፊነት ለመዳን አይችልም፡

**24.ከማስረከቢያ ጊዜ ስለመዘግየት**

የማስረከቢያ ጊዜ ዘገየ ሚባለዉ፡-

1. በማጓጓዣ ዉል ላይ በተጠቀሰዉ ጊዜ ሳይፈፀም ሲቀር፤

2. የማስረከቢያ ጊዜ ስምምነት በማጓጓዣ ዉሉ ላይ ባልተጠቀሰ ጊዜ ሁኔታዎችን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ጉዞው በእርግጥ የወሰደውን ጊዜ፣ በተለይም ከፊል ጭነት በሆነ ጊዜ በመደበኛዉ ሁኔታ ጭነቱን ለመጨረስ የሚወስደውን ጊዜ ከግምት ውስጥ በማስገባት፤ የሚወሰድ ሆኖ አንድ ጠንቃቃ አጓጓዥ ከሚወስድበት ጊዜ በልጦ ሲገኝ።

## 25.ዕቃን አለማስረከብ

1. አንድ አጓጓዥ በማጓጓዣ ሰነዱ ላይ የተጠቀሰዉ ጊዜ ካበቃ በኋላ በሰላሣ ቀናት ጊዜ ውስጥ ዕቃውን ሳያስረክብ የቀረ እንደሆነ፣ ወይም በማጓጓዣ ውሉ መሠረት ስምምነት የተደረሰበት ጊዜ ከሌለ ዕቃዎቹን አጓጓዡ ለማጓጓዝ ከተረከበበት ጊዜ ጀምሮ በስልሣ ቀናት ውስጥ ማስረከብ ካልቻለ ዕቃዎቹ የጠፉ ለመሆናቸው ሊስተባበል የማይችል ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ የጠቀሰዉ ጊዜ ካለፈ በኋላ ዕቃዎቹን ለመጠየቅ መብት ያለዉ ሰዉ እቃዎቹ እንደጠፉ ቆጥሮ መብቱን ከአጓጓዡ ሊጠይቅ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት በዕቃው ላይ መብት ያለው ሰው ለጠፉት ዕቃዎች ካሣ ከተቀበለ ካሣዉ ከተከፈለበት ቀን በኋላ ባለው አንድ አመት ጊዜ ውስጥ እቃዎቹ ከተገኙ አጓጓዡ ስለ ዕቃው መገኘት በፅሁፍ እንዲያሣውቀው ወዲያውኑ ለመጠየቅ ይችላል፤ አጓጓዡም በጽሑፍ ዕውቅና ሊሰጥ ይገባል፡፡
4. በዕቃው ላይ የማዘዝ መብት ያለው ሰው የፅሁፍ ማረጋገጫ በተሰጠው 30 ቀናት ጊዜ ውስጥ በአንቀፅ 29 እና 30 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በማጓጓዣ ሰነዱ ያለውን ክፍያ ከፍሎ፣ እንዲሁም ካሣ ክፍያው ካሳ ክፍያ ዉስጥ የተጨመሩ ሌሎች ክፍያዎች ከተቀነሱ በኋላ የወሰደውን ካሣ በመመለስ አጓጓዡ ዕቃውን እንዲያስረክበው መጠየቅ ይችላል፡፡

## 26.አደገኛ ዕቃዎች

1. ላኪው አደገኛነት ያላቸውን ዕቃዎች ለአጓጓዡ ባስረከበ ጊዜ ለአጓጓዡ የዕቃዎቹን የአደገኝነት ባህሪ እና አስፈላጊ በሆነም ጊዜ ሊወሰድ የሚገባውን የጥንቃቄ እርምጃ በትክክል ማላወቅና ማመልከት አለበት፡፡

2. ይህ መረጃ በማጓጓዣ ሰነዱ ውስጥ ያልተካተተ ከሆነ አጓጓዡ ለማጓጓዝ ሲረከብ የዕቃዎቹን የአደገኛነት ባህሪ ያወቅ የነበረ መሆኑን የማስረዳት ኃላፊነት የላኪዉ ወይም የተረካቢው ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ በተጠቀሰዉ ሁኔታ አጓጓዡ ዕቃዎቹ አደገኛ መሆናቸዉን የማያዉቅ ከሆነ ካሣ ለባለዕቃው መክፈል ሣይኖርበት በማናቸዉም ጊዜ ወይም ቦታ ይህን አደገኛ ዕቃ ማራገፍ ወይም ከጥቅም ዉጪ ማድረግ፣ ወይም ጉዳት እንዳያደርስ ሊያመክነው ይችላል፡፡

27.<u>የኃላፊነት መጠን ወሰን</u>

1. ዕቃ በመጥፋቱ ወይም በመጐዳቱ ምክንያት አጓጓዡ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ተጠያቂና ኃላፊ በሚሆንበት ጊዜ ለጠፋው ወይም ለተጐዳው ዕቃ ካሣ የመክፈል ኃላፊነቱ ዕቃውን ማስረከብ በሚገባው ቦታ ዕቃው በሚያወጣው የገበያ ዋጋ ልክ ይሆናል፡፡ የዕቃዉ የገበያ ዋጋ የማይታወቅ ከሆነ ተመሣሣይ ዕቃ በሚኖረው የገበያ ዋጋ መሠረት ይሆናል፡፡
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አጓጓዡ የሚከፍለው የካሣ መጠን በጥቅል ከኤስ.ዲ.አር 835 ወይም ሌላ የጭነት መለኪያ ወይም በኪሎ ግራም ከኤስ.ዲ.አር 2.5 ከሁለቱ ከፍተኛ ከሆነው መብለጥ የለበትም፡፡
3. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀፅ /1/ እና /2/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማጓጓዣ ውል በሚመሠረትበት ጊዜ የዕቃዎቹን ዋጋ የሚገልፅ ሰነድ የማጓጓዣ ውሉ አካል ከተደረገ ዕቃው ቢጠፋ ወይም ጉዳት ቢደርስበት አጓጓዡ የሚከፍለው የካሣ መጠን በሰነዱ ላይ የተገለፀው የዕቃ ዋጋ ላይ ዕቃውን ማስረከብ በሚገባው ቦታና ቀን ዕቃው የሚኖረው የገበያ ዋጋ መሠረት ልዩነቱን ጨምሮ ይሆናል፡፡
4. አጓጓዡ ዕቃውን በወቅቱ ሳያደርስ ያዘገየ እንደሆነ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 21 እና 24 መሠረት አጓጓዡ ርክክባቸው የዘገየውን ዕቃዎች አስመልክቶ ከዕቃ ላኪው ወይም አስጫኝ ወይም ተቀባይ የሚከፈለውን የጭነት ማጓጓዣ ዋጋ ሁለት ተኩል ($2^{1/2}$) ጊዜ አጥፎ ለዕቃ ተቀባይ ወይም በዕቃው ላይ የማዘዝ መብት ላለው ሰው የመክፈል ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡ ነገር ግን ይህ ክፍያ በማጓጓዣ ዉሉ ላይ ከተጠቀሰው ጠቅላላ የጭነት አገልግሎት ክፍያ ዋጋ ሊበልጥ አይችልም፡፡

28.**<u>የካሣ መጠን አወሣሰን</u>**

በአንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ /1/ እና /2/ መሠረት ከፍተኛውን መጠን ለማስላት ሲባል ከዚህ በታች የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚዎች ይሆናሉ፣

1. ዕቃውን አቀናጅቶ ለመጫን ጥቅም ላይ የዋለው ኮንቴይነር፣ የዕቃ ማሸጊያ ሣጥን /ፖሌት/ ወይም ዕቃን ለማቀናጀት ጥቅም ላይ የሚዉሉ ተመሣሣይ የዕቃ ማሸጊያዎች ወይም በማጓጓዣ ሰነዱ የተጠቀሰው የጭነት መለኪያ በውስጡ የያዛቸው ጥቅሎች ተገልፀው ማጓጓዣ ሰነዱ ላይ ካልሰፈሩ በቀር ኮንቴይነሩ፣ የዕቃ ማሸጊያ ሣጥኑ ወይም ተመሣሣይ የሆነው የዕቃ መጠቅለያ ወይም ማሸጊያ ብቻ እንደ አንድ ጥቅል ይቆጠራል፡፡
2. የዕቃ ማሸጊያ ኮንቴይነር ራሱ በጠፋ፣ ጉዳት በደረሰበት ጊዜ ኮንቴይነሩ የአጓጓዡ ንብረት ወይም በአጓጓዡ የቀረበ ካልሆነ በቀር እንደ አንድ መጠቅለያ ሆኖ ይቆጠራል፡፡
3. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅን /1/ እና /2/ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነዉ ጆንያ ከረጢትና የመሣሠሉት እንደ ዕቃ መጠቅለያ አይቆጠሩም፡፡ ዕቃ የያዘ ጆንያ ወይም ከረጢት ወይም ተመሣሣይ የሆነ የዕቃ መቋጠሪያ ከነዕቃዉ ቢጠፋ ወይም ቢጐዳ ካሣ የሚከፈለው የዚህ ዓይነቱ ዕቃ ባለዉ የገበያ ዋጋ መሠረት ብቻ ይሆናል።

29.**<u>ስለከፍተኛ ካሣ</u>**

ዕቃ በአጓጓዢ ቁጥጥር ሥር ባለ ጊዜ በሙሉ ወይም በከፊል ቢጠፋ ወይም ጉዳት ቢደርስበት በአንቀጽ 27 ንዑስ አንቀፅ /1/ ወይም ንዑስ አንቀፅ /2/ ከተጠቀሰው በላይ ካሣ መጠየቅ የሚቻለው በንዑስ አንቀፅ (3) መሠረት የዕቃው ዋጋ ተገልጾ ከሆነ ወይም ዕቃውን በጊዜ ማስረከቡን አስመልክቶ ልዩ ጥቅም ያለው መሆኑን ዕቃ ላኪው ገልጾ የማጓጓዣ ውሉ አካል ባደረገው ጊዜ ነው፡፡

30.**<u>አጠቃላይ ሃላፊነት</u>**

የአጓጓዡ ጠቅላላ የኃላፊነት መጠን ዕቃዎቹ ጠቅላላ ቢጠፉ በአንቀፅ 21 እና 27 መሠረት ከሚኖርበት ኃላፊነት መጠን መብለጥ አይኖርበትም፡፡

## 31.ስለ ተጨማሪ ሃላፊነት

1. ላኪዉ ከመደበኛ ክፍያ በላይ ተጨማሪ ክፍያ እንዲደረግ ስምምነት በማድረግ የዕቃዉ ዋጋ በአንቀፅ 27 ንዑስ አንቀፅ /3/ መሠረት የገለፀ እንደሆነ ዕቃ በጠፋ ወይም ጉዳት በደረሰበት ጊዜ የአጓጓዡ ካሣ የመክፈል ኃላፊነት በቀረበዉ የዋጋ ሰነድ ሆኖ፣ የካሣ ክፍያው በአንቀፅ 29 በተደነገገው መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡
2. ዕቃ አስረካቢው አጓጓዡ ዕቃውን በተወሰነ ጊዜ ማስረከቡ ልዩ ጥቅም እንደሚያስገኝለት አስቀድሞ የማጓጓዝ ውሉ በሚመሠረትበት ጊዜ ገልጾ ከሆነ፣ አጓገፁ በውሉ መሠረት ርክክቡን ባለመፈፀሙ ለደረሰዉ ተጨማሪ ጥፋት ወይም ጉዳት ከአንቀጽ 27 - 30 ከተመለከተዉ ካሣ ውጪ በተገለፀው ልዩ ጥቅም መጠን ከአጓጓዡ ካሣ መጠየቅ ይችላል፡፡

## 32.ሆን ተብሎ ስለሚፈፀም ጥፋት ድርጊት

1. አጓጓዡ በእቃዉ ላይ የደረሰዉ ጉዳት ሆነ ተብሎ በተፈፀመ የጥፋት ድርጊት መሆኑ በማስረጃ ሲረጋገጥ፣ በዚህ አዋጅ ድንጋጌ መሠረት ከኃላፊነት ነፃ ለመሆን ወይም ኃላፊነቱን መጠን የመወሰን መብቱን ሊጠቀምበት አይችልም፡፡
2. ሆን ተብሎ የተፈፀመው ድርጊት ወይም ጥፋት በአጓጓዡ ወኪል ወይም ሠራተኛ ወይም የማጓጓዙን ሥራ ለማከናወን በተጠቀመባቸው ሌላ ማናቸውም ሰው የተፈፀመ እንደሆን እነዚህ ወኪሎች፣ ሠራተኞች ወይም ሌሎች ሰዎች ያከናወኑት ተግባር በቅጥር ውላቸው መሠረት ከሆነ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌዎች ተፈጻሚዎች ይሆናሉ፡፡
3. በተጨማሪም በዚህ ሁኔታ ወኪሎቹ ወይም ሰራተኞቹ በዚህ አዋጅ ድንጋጌ መሠረት የግል ኃላፊነታቸዉን መሠረት በማድረግ ለመከራከር አይችሉም፡፡

## ክፍል አምስት

## መብት እንዲከበር ስለመጠየቅና ክስ ስለማቅረብ

## 33.ርክክብ ጊዜ ቅሬታ ስለማቅረብ

1. ዕቃ ተረካቢው በአጓጓዡ በኩል የማታለል ነገር ካልተሠራ በቀር በግልጽ የሚታዩ የዕቃ ጉድለቶች ወይም ጉዳቶች መኖራቸውን ሳያረጋግጥ ከአጓጓዡ ዝም ብሎ ከተቀበለ ወይም ዕቃዎቹ መጥፋታቸውን ወይም መጎዳታቸውን ወዲያውኑ እንደተረከበ ቅሬታውን በፅሁፍ ካላቀረበ በስተቀር ክስ ማቅረብ አይችልም፡፡

2. ዕቃ ተረካቢው በዕቃው ላይ የደረሰው ጉድለት ወይም ጉዳት በግልፅ የማይታይ በሆነ ጊዜ በሰባት ቀን ጊዜ ውስጥ የዕቃዎቹን መጥፋት ወይም መጎዳት አስመልክቶ ስለተረከበው ዕቃ ዝርዝር ሁኔታ ቅሬታውን ለአጓጓዡ ካልገለፀ ዕቃዎቹን በማጓጓዣ ሰነዱ ላይ በተመለከተው መሰረት በጥሩ ሁኔታ እንደተቀበለ ይቆጠራል፡፡
3. የደረሰው ጥፋት ወይም ጉዳት በማጓጓዣ ሰነዱ ላይ ስለዕቃው ከተሰጠ መግለጫ ጋር የማይጣጣም መሆኑ በዕቃ ተረካቢው በፅሑፍ ከተገለፀ አጓጓዡ በኃላፊነት ይጠየቃል፡፡
4. የዕቃዎቹ ሁኔታ በርክክብ ጊዜ በአጓጓዡና በተረካቢ በአንድነት በሚገባ ተረጋግጠዉ ከሆነ፣ ይህን የሚያፋልስ ተቃራኒ ማስረጃ ተቀባይነት የሚኖረው የጠፋዉ ዕቃ ወይም የደረሰዉ ጉዳት ርክክቡ በተፈፀመበት ጊዜ በግልፅ ሊታይ የማይቻል ሲሆንና ተቀባዩ እሁድና የበዓል ቀናትን ሳይጨምር የማረጋገጥ ፍተሻዉ ከተካሄደበት ቀን ጀምሮ በሰባት ቀናት ውስጥ ቅሬታዉን በፅሑፍ ማስታወሻ ለአጓጓዡ ሰጥቶ ሲገኝ ነው፡፡
5. ተቀባዩ ዕቃዎቹን ከተረከባቸዉ ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ለአጓጓዡ የዕቃዉን መዘግየት አስመልክቶ ያለውን ቅሬታ በፅሁፍ ማስታወሻ ለአጓጓዥ ካልላከ በስተቀር አጓጓዥ ዕቃዉን ለማስረክብ ለዘገየበት ጊዜ ካሣ አይከፈለዉም፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ /1/ እስከ /5/ የተጠቀሱት ጊዜያት ሲሰሉ አጓጓዡ ዕቃውን የሚያስረክብበት ቀን ወይም ተረካቢው መረከብ ይችል ዘንድ ለማረጋገጥ ፍተሻ የተደረገበት ቀን ወይም ዕቃዎቹ ለተረካቢው የተሰጠበት ቀንን አይጨምርም፡፡
7. አጓጓዡና ተረካቢው በዕቃዎቹ ላይ የሚያስፈልጉ ምርመራዎችንና ማረጋገጫዎችን ለማድረግ የሚያስችል አንዱ ለአንዱ አስፈላጊ አቅርቦቶችን መስጠት ይኖርበታል፡፡

34.<u>የዳኝነት ስልጣን</u>

በዚህ አዋጅ መሠረት ማጓጓዝን አስመልክቶ ክርክር የተነሣ እንደሆነ ከሣሽ የሆነ ወገን ሥልጣን ላለዉ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማቅረብ መብት አለው፡፡ ክሱን ለማቅርብ የሚችልበት ሥልጣን ያለዉ ፍርድ ቤትም፡-

ሀ) በተከሳሽ መደበኛ መኖሪያ ወይም ዋና መ/ቤት ወይም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ወይም ውሉን እንዲዋዋሉ ያደረገው ወኪል ባለበት፤ ወይም

ለ) ዕቃዉን ለማጓጓዝ የማጓጓዣ ውል የተፈፀመበት ቦታ ወይም በውሉ መሠረት የዕቃው ማስረከቢያ ቦታ ባለ ፍ/ቤት እንጂ በሌላ ፍርድ ቤት ሊያቀርብ አይችልም፡፡

35. <u>ይርጋ</u>

1. በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ድንጋጌዎች መሠረት በማጓጓዣ ዉል ምክንያት ክስ ለማቅረብ የሚቻለው በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ የይርጋዉ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረዉ፡-

   ሀ) በከፊል ለጠፋ፣ ለተጎዳ ወይም ከማስረከቢያ ጊዜ ለዘገየ፣ ከማስረከቢያ ቀን ጀምሮ፤

   ለ) ሙሉ በሙሉ ለጠፋ፣ የዉሉ ጊዜ ከአለቀ በኋላ ከሰላሳ ቀን ጀምሮ፣ ስምምነት በሌለ ጊዜ ዕቃዎቹ በአጓጓዡ ከተጫኑበተ ቀን ጀምሮ ስልሣ ቀን ካለፈ በኋላ፤

   ሐ) በሌሎች በማናቸዉም ሁኔታዎች የማጓጓዣ ውል የተደረገበት ጊዜ ካለቀ ሦስት ወራት በኋላ፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ አጓጓዡ የጠፋዉን ወይም ጉዳት የደረሰበትን ወይም ርክክቡ የዘገየውን ዕቃ አስመልክቶ በዕቃ ተረካቢው በፅሁፍ ከተገቢው ሰነድ ጋር የቀረበለትን የካሣ ክፍያ ጥያቄ አለመቀበሉን ከአጓጓዡ ወይም ከተቀባይ የተላከለትን ሰነድ መልስ በማያያዝ በፅሁፍ እስከሚገልፅ ጊዜው ይራዘማል፡፡

3. የጽሁፍ ጥያቄው ስለመድረሱ ወይም ስለምላሹና ሰነዶች ስለመመለሳቸው የማስረዳት ሸክሙ በእነዚህ መረጃዎች ለመጠቀም በሚያስፈልገው ወገን ላይ ይወድቃል፡፡

## ክፍል ስድስት

## በመቀባበል ስለሚፈፀም ማጓጓዝ

### 36.አንድ ውል ስለመሆኑ

የማጓጓዙ ሥራ በአንድ ውል የሚገዛ ሆኖ፣ በተለያዩ አጓጓዦች በመቀባበል የሚፈፀም ከሆነ የመጀመሪያው አጓጓዥ በገባዉ የማጓጓዣ ዉል መሠረት፤ ሁለተኛው አጓጓዥና ተከታዮቹ አጓጓዦች የማጓጓዣ ሰነዱንና ውሉ የሚያስከትለውን ግዴታ በመቀበላቸዉ የተነሣ የማጓጓዣ ውሉ ተዋዋይ ወገን ተደርገው በመቆጠር እያንዳንዱ አጓጓዥ በተናጠል ስለ አጠቃላዩ የማጓጓዙ ሥራ ኃላፊነት ይኖርበታል።

### 37.በቅብብሎሽ የማጓጓዝ ሥራ ጋር የተያያዙ ሌሎች ነዶች

1. ዕቃዎችን አስቀድሞ ካለው አጓጓዥ የተቀበለ አጓጓዥ ስለተረከበዉ ዕቃ ቀኑ ተጽፎበት የተፈረመ ደረሰኝ መስጠት ይገባዋል፡፡ ይኸው ተቀባይ አጓጓዥ በማጓጓዣ ሰነዱ ሁለተኛዉ ቅጂ ላይ ስሙንና አድራሻዉን ማስገባት አለበት፡፡
2. እንዲሁም አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ተቀባይ አጓጓዥ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ /2/ የተመለከቱትን አይነት ዕቃውን አስመልክቶ በማጓጓዣ ሰነዱ ላይ የሠፈረው መግለጫ ወይም የዕቃውን ሁኔታ አስመልክቶ ቅሬታ ካለው በማጓጓዣ ሰነዱ ሁለተኛው ቅጅ ላይና በደረሰኙ ላይ ማመልከት አለበት፡፡
3. አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጾች /1/ እና /2/ ድንጋጌዎች በተቀባይ አጓጓዦች መካከል ባለ ግንኙነትም ላይ ተፈፃሚዎች ይሆናሉ፡፡

### 38.ኃላፊነት ያለበት አጓጓዥ

1. በዕቃዉ ላይ መብት ያለው ሰው የዕቃዎች መጥፋት፣ መጎዳት፣ ወይም መዘግየት የሚያስከትሉትን ኃላፊነት በተመለከተ፤ በመጀመሪያ አጓጓዥ፣ በመጨረሻ አጓጓዥ ወይም የዕቃ መጥፋት፣ መጎዳት፣ ወይም መዘግየት ድርጊት በተፈጠረ ጊዜ የማጓጓዝ ሥራውን ሲያከናውን በነበረው አጓጓዥ ላይ ክስ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ክስ አቅራቢዉ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 36 በተጠቀሱት አጓጓዦች ላይ በአንድነትና በነጠላ ክስ ማቅረብ ይችላል፡፡

39.<u>በአጓጓዦች መካከል ስለሚኖር ግንኙነት</u>

ከዚህ በታች የተመለከቱት ድንጌጋዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ለማክበር ሲል ወይም በፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረት ካሣ የከፈለ አጓጓዥ፣ የከፈለዉን ክፍያና ያወጣቸዉን ወጭዎች ከእነወለዱ በማጓጓዙ ሥራ ላይ የተካፈሉ ሌሎች አጓጓዦች በሚከተለው አኳኋን እንዲተኩለት መጠይቅ ይችላል፡፡

ሀ) በዕቃዎቹ መጥፋት ወይም መጎዳት የተነሣ ካሣ ለመክፈል ኃላፊ የሆነ አጓጓዥ ካሣዉን ራሱም ሆነ ሌላ አጓጓዥ ቢከፍለዉ ለካሣዉ ብቸኛ ወሳኝና ተጠያቂ አጓጓዥ ይሆናል፡፡

ለ) የደረሰው የዕቃ መጥፋት ወይም መጎዳት በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ አጓጓዦች ምክንያት የሆነ እንደሆነ እያንዳንዳቸው ባለባቸው የኃላፊነት መጠን ካሣ መክፈል አለባቸው፡፡ የኃላፊነት መጠን ማከፋፈል የማይቻል በሆነ ጊዜ እያንዳንዱ አጓጓዥ ከማጓጓዙ ሥራ የሚያገኘው የማጓጓዣ ክፍያ መሠረት በማድረግ የሚደርስበትን የካሣ መጠን መክፈል ይኖርበታል፡፡

40.<u>በአጓጓዦች መካከል ስለሚኖርመዋጮ</u>

1. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 34 ድንጋጌ በአጓጓዦች መካከል ከማጓጓዣ ውል የመነጨ የዕዳ ወይም የመብት ጥያቄ ጉዳይ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
2. በአጓጓዦች መካከል የሚኖረው የዕዳ ክፍያ የይርጋ ጊዜው የሚጀምረው በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የሚከፈለው የካሣ መጠን የመጨረሻ ውሣኔ ካገኘበት ቀን ጀምሮ፣ ወይም የዚህ ዓይነት ውሣኔ በሌለበት ጊዜ ክፍያው ከተፈፀመበት ቀን ጀምሮ ነው፡፡

## <u>ክፍል ሰባት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

41.<u>በዕቃ አስተላላፊ የሚደረግ የማጓጓዣ ውል</u>

1. ዕቃ አስተላላፊ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2251 ድንጋጌዎች መሠረት ዕቃን የማጓጓዝ ሥራ በራሱ ስም ወይም በራሱ ትራንስፖርት ያጓዘ እንደሆነ ወይም ለዕቃ አስተላላፊው የተሰጠዉ የዕቃ ማስተላለፍ የውክልና ሥራ ትዕዛዝ ዕቃ አስተላላፊው የዚህ አይነት ግዴታዎች እንዳሉበት ባመለከተ ጊዜ ዕቃ አስተላላፊው እንደ ዕቃ አጓጓዥ ተቆጥሮ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በዕቃ አስተላላፊው ላይ ተፈፃሚዎች ይሆናሉ፡፡

2. ስለሆነም ዕቃ አስተላላፊ በዚህ አዋጅ ለአጓጓዡ በተሰጡት መብቶች የመጠቀም፣ እንደዚሁም ግዴታዎችን የመወጣትኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

42.<u>የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ስለመቃረን</u>

1. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚቃረኑ የውል ቃሎች ተፈጻሚነት አይኖራቸዉም፡፡ የእነዚህ የውል ቃሎች ተፈፃሚ አለመሆን የሌሎቹን የውል ቃሎች ፈራሽ አያደርገውም።
2. በተለይ የአጓጓዡን የመድህን ዋስትና ጥቅሞች ለአጓጓዡ አሳልፎ መስጠትን ወይም የማስረዳት ሸክምን የሚጥሱ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

43.<u>የተሻሩ ሕጎች</u>

1. ስለ ሰው ማጓጓዝ ውል የተደነገጉት አንቀፆች እንዳሉ ወይም እንደተጠበቁ ሆነው፣ ዕቃ ማጓጓዝን በተመለከተ የተደነገጉት የንግድ ሕግ ሦስተኛ መጽሐፍ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች በሙሉ በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡፡
2. ይህንን አዋጅ የሚቃረኑ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ውሣኔዎች ይህንን አዋጅ በሚመለከት ተፈፃሚ አይሆኑም፡፡

44.<u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>

1. ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የተፈጠሩ ህጋዊ ሁኔታዎች የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ቢያሻሽሏቸዉ ቀደም ሲል የተፈጠረው ሁኔታ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡
2. ይህ አዋጅ ከዚህ አዋጅ መውጣት በፊት ውጤት ያገኙ ሕጋዊ ሁኔታዎችን ተፈፃሚነት አያግድም፡፡
3. ይህ አዋጅ ከመዉጣቱ በፊት የተደረገ የማጓጓዣ ስራ ዉሎች በንግድ ህግ ድንጋጌዎች መሠረት የሚገዙ ይሆናሉ፡፡

45.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጳጉሜ 1 ቀን 1999 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 548/1999

## የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አዋጅ

የኢትዮጵያ ህዝብና መንግሥት ዋነኛ ዓላማ የሆነውን ጠንካራ የኢኮኖሚ ግንባታና ሁለንተናዊ ዕድገት ዕውን ለማድረግ ንግድና ትራንስፖርት ሊነጣጠሉ በማይችሉበት ሁኔታ ተሣሥረው የሚገኙ ከመሆኑም በላይ ትራንስፖርት ለዓለም ዓቀፍ ንግድ፣ ለክልላዊ ዓለም ዓቀፍ ውህደት እና የተመጣጠነ ብሔራዊ ዕድገት ለማረጋገጥ ቁልፍ ሚና የሚጫወት የኢኮኖሚ ዘርፍ በመሆኑ፤

ወጪና ገቢ ዕቃዎችን ከማስተናገድ በተያያዘ ሁኔታ የወደብ ላይ ዕቃ አያያዝ፣ ዕቃን ወደብ ላይ መጋዘን ውስጥ ማቆየት፤ የጉምሩክና የወደብ መብት የማስፈጸምና ከሰነድ ጋር በተያያዘ መልኩ ሌሎች ሥነ-ሥርዓቶችን ማስፈጸሙ ጊዜ ወሳጅ ብቻ ሣይሆን ከፍተኛ ወጪ የሚያስከትል በመሆኑ መልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አሠራርን በመተግበር የተፋጠነ የትራንዚት ሎጂስቲክስ አገልግሎት መስጠት የተጠቀሱትን ችግሮች በማቃለል ረገድ ከፍተኛ ጠቀሜታ የሚያስገኝ በመሆኑ፤ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 55/1/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 548/1999" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ አዋጅ ውስጥ:-

   1. "ዓለም አቀፍ መልቲ ሞዳል ትራንስፖርት" ማለት ቢያንስ በሁለት የተለያዩ የማጓጓዣ ዓይነቶች፣ ወጥ በሆነ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ውል መሠረት መልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ከአንድ የተወሰነ ቦታ ተረክቦ በማጓጓዝ ሌላ አገር ውስጥ የሚገኝ የማስረከቢያ ቦታ ለማስረከብ የሚደረግ የማጓጓዝ ሥራ ነው፡፡ በአንድ አይነት ማጓጓዣ ተጓጉዞ የመጣን ዕቃ ተቀብሎ ማድረስ እንደ መልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አይቆጠርም፤

2. “መልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ” ማለት ማንኛውም ሰዉ በራሱ ወይም በሱ ስም በሚሰራ ሌላ ሰው አማካይነት የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ውል የተዋዋለ እና ዋና ሆኖ የሚሰራ ወይም በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ክንውን የሚሳተፍ እና ስለ ውሉ አፈፃፀም ኃላፊ የሆነ ሰው ማለት ነው፣
3. “የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ዉል” ማለት ዓለም አቀፍ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ የመጫኛ ዋጋ ተከፍሎት የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርትን ለመፈፀም ወይም እንዲፈፀም ለማድረግ የተደረገ ውል ነው፣
4. “የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነድ” ማለት የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ውል መኖሩን፣ እቃዉ በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ኃላፊነት ስር ያለ መሆኑን እና አከናዋኙም በውሉ ድንጋጌ መሠረት እቃውን ለማስረከብ ግዴታ ያለበት መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ ነው፡
5. “ዕቃ ላኪ” ማለት ማንኛውም ከመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ጋር የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ዉል የፈፀመ ወይም ማንኛዉም በላኪዉ ስም ወይም ላኪዉን ወክሎ በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ዉሉ መሠረት ዕቃ ለመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ያስረከበ ሰው ማለት ነው፣
6. “ዕቃ ተረካቢ” ማለት እቃውን ለመረከብ መብት ያለው ሰው ማለት ነው፡፡
7. “ዕቃ” ማለት ማንኛውም ንብረት ሆኖ የቁም ከብቶችን፣ እንዲሁም ኮንቴይነሮችን፣ የዕቃ ማሸጊያ ሣጥን (ፖሌትስ) ወይም ተመሳሳይ ዕቃ የሚታሸግበት ወይም በዕቃ አስረካቢው የሚሸጡ ማናቸውም የዕቃ ማሸጊያዎችን ይጨምራል፣
8. “ሰው” ማለት በተፈጥሮ ወይም በሕግ ሕጋዊ ሰውነት የተሰጠው ማለት ነው፣
9. “ማስረከብ” ማለት፡-
    i. ሊተላለፍ የሚችል የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነድ በሚሆንበት ጊዜ ዕቃውን ለተረካቢው ወይም ለመረከብ መብት ላለው ማናቸውም ሰው ማስረከብ ወይም በቁጥጥር ስር እንዲሆን ማድረግ ማለት ነው፡፡
    ii. ተላላፊ ያልሆነ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነድ በሚሆንበት ጊዜ ዕቃውን ለተረካቢው ወይም በተረካቢዉ ስም እንደተረካቢው ሆኖ ለመረከብ ስልጣን ለተሰጠው ማናቸውም ሰው ማስረከብ ወይም በቁጥጥሩ ሥር እንዲሆን ማድረግ ማለት ፡፡

10. “የተላለፈለት” ማለት ለእሱ ጥቅም ሲባል በዕቃዉ ላይ ያለ መብት የተላለፈለት ሰው ሲሆን፣ ተከታታይ የማስተላለፍ ተግባር ከተደረገ በመጨረሻ የተላለፈለት ሰው ማለት ነው፤
11. “ማስተላለፍ” ማለት ሊተላለፍ በሚችል የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነድ ላይ ዕቃ ተቀባዩ ወይም ሰነዱ የተላለፈለት ሰው ሰነዱ ላይ ፊርማውን በመጨመር ከመመሪያ ጋር በሰነዱ ላይ የተመለከተው ንብረት ባለቤትነት ተለይቶ ለታወቀ ሰዉ እንዲተላለፍ ማድረግ ነው፣
12. “ስፔሻል ድሮዊንግ ራይት /ኤስዲአር/” ማለት በጥቅል ወይም በኪሎ ግራም የተጠቀሰው የአጓጓዡ የኃላፊነት መጠን የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት አሰራርን መሠረት በማድረግ ገንዘቡ ከሚከፈልበት አገር ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የምንዛሪ ተመን ማለት ነው፤
13. “ኃላፊነት መውሰድ” ማለት ዕቃ ለመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ መሰጠቱንና እርሱም ዕቃውን ለማጓጓዝ መቀበሉን ማረጋገጥ ማለት ነው፤
14. “የትራንስፖርት አይነት” ማለት እቃዎችን በመንገድ፣ በአየር፣ በባቡር፤ ወይም በባህር የማጓጓዝ ዘዴ ነው፤
15. “አደገኛ ዕቃ” ማለት በባህሪያቸው አደጋ የሚያመጡ ዕቃዎች ወይም አደጋ ሊያስከተሉ ይችላሉ ተብለው የተመደቡ ተቀጣጣይ፣ የሬዲዮ ሞገድ ማመንጨት የሚችሉ፣ በጤንነት ላይ አደጋ ማስከተል የሚችሉ፣ የንጥረ ነገር ወይም የጋዝ ባህሪ ያላቸው ወይም የሰው ልጅ ጤንነትና አካባቢ ላይ ጥፋት ማስከተል የሚችሉ ዕቃዎች ማለት ነው፡፡

3. <u>**የተፈፃሚነት ወሰን**</u>

1. ይህ አዋጅ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ዕቃውን ለማጓጓዝ የተረከበበት ቦታ ወይም አጓጉዞ የሚያስረክብበት ቦታ ኢትዮጵያ ውስጥ የሆነና፤ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነድ በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ 4 እስከ 10 ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት በተሰጠባቸው ማናቸውም የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ውል ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረተ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ውል ሲመሰረት የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በዉሉ ላይ ግዴታ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች መኖር ዕቃ ላኪዉ ዕቃውን በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ወይም በተናጠል የማጓጓዝ ዘዴ ለመላክ ከፈለገ የመምረጥ መብቱን አይነኩም፡፡

## ክፍል ሁለት

## የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ስነድ

### 4. የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ስነድ ስለመስጠት

1. መልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ዕቃውን ሲረከብ መልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ስነድ ይሰጣል፣ ስነዱም እንደ ዕቃ ላኪ ምርጫ ሊተላለፍ በሚችል ወይም ሊተላለፍ በማይችል አይነት ይሆናል፡፡
2. መልቲ ሞዳል ትንስፖርት ሰነድ በመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ወይም በእሱ የውክልና ስልጣን በተሰጠው ሰው መፈረም አለበት፡፡
3. በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነዱ ላይ የሚኖረው ፊርማ በእጅ የተፈረመ፣ በፋክስ መልዕክትነት የታተመ፣ በማኅተም የተመታ፣ በምልክት፣ ወይም በሌላ በመካኒካልና በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የተደረገ ሊሆን ይችላል፡፡
4. የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1727 (2) ለዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

### 5. ሊተላለፍ የማይችል የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነድ

1. ዕቃ ላኪዉ ከተስማማ መካኒካል እና ኤሌክትሮኒክስ በሆነ ዘዴ ወይም በአንቀጽ 8 ላይ በተመለከተው መሠረት በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነዱ ላይ የሚጠቀሱ ዝርዝር ጽሑፎችን ጠብቆ ሊያቆይ በሚችል ሌላ ዘዴ በመጠቀም ሊተላለፍ የማይችል የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነድ መስጠት ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ በተመለከተው ሁኔታ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ዕቃውን ተረክቦ ለዕቃ ላኪዉ ሊነበብ የሚችል ሁሉንም ዝርዝሮች የያዘ ሰነድ ያስረክበዋል፡፡ ይህም ሰነድ ለዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች አፈፃፀም ሲባል እንደ መልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነድ ይቆጠራል፡፡
3. የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነድ በማይተላለፍ አይነት ሲዘጋጅ የተረካቢዉን ስም ማመልከተ ይገባዋል፡፡

4. የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ እቃውን ከማስረከብ ግዴታው ነፃ የሚሆነው ዕቃውን ሊተላለፍ በማይችለዉ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነድ ላይ በስም ለተጠቀሰዉ ተረካቢ ወይም ይህ በስም የተጠቀሰው ተረካቢ በደንቡ መሠረት በፅሑፍ ላዘዘዉ ሰው ሲያስረክብ ብቻ ነው፡፡

## 6. ሊተላለፍ የሚችል የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነድ

የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነድ ሊተላለፍ በሚችል መልኩ ሲዘጋጅ፡-

1. ለአምጪዉ ወይም ለታዘዘለት በሚል ይዘጋጃል፣
2. ለታዘዘለት በሚል ከተዘጋጀ በሰነዱ ላይ በመፈረም ለሌላ ሰዉ የሚተላለፍ እንዲሆን ይደረጋል፡፡
3. ለአምጪዉ በሚል የተዘጋጀ ከሆነ በላዩ ላይ መፈረም ሣያስፈልግ የሚተላለፍ ይሆናል፣
4. ከአንድ በላይ በሆነ ቅጅ ዋና ሰነዶች የተዘጋጀ ከሆነ የእያንዳንዱን ዋና ቅጅ ሰነድ ቁጥር ማመልከት ይኖርበታል፡፡
5. ኮፒ ሰነዶች የሚሰጡ ከሆነ እያንዳንዱ ኮፒ የማይተላለፍ ኮፒ ተብሎ ምልክት ሊደረግበት ይገባል፡፡

## 7. የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነድ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ ሆኖ ለመቆጠሩ

1. ሊተላለፍ በሚችል ወይም ሊተላለፍ በማይችል የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነድ ላይ ስሙ የተጠቀሰ ዕቃ ተቀባይ እና እንደየሁኔታው ሰነዱ የተላለፈለት ሰው ሁሉ በሰነዱ ላይ የተጠቀሰው የንብረት ባለቤትነት ሰነድ ላይ በመፈረም የተላለፈለት ሰውም ሆነ መብት የተሰጠው ሰው ሰነድ ወይም መብቱ በመተላለፉ ምክንያት የዕቃ ላኪውን መብትና ግዴታ ይወስዳል፡፡
2. ነገር ግን በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተዉ በማናቸውም መልክ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ከዕቃ ላኪዉ አስረካቢው የጭነት ዋጋ ለመጠየቅ ወይም በተረካቢነት ወይም የተላለፈለት በመሆኑ ምክንያት በተረካቢውና በተላለፈለት ሰው ላይ ማናቸውንም ኃላፊነት እንዲወጡ ለማስገደድ ያለውን መብት የሚነካ አይደለም፡፡

8. **የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነድ ይዘት**

የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነድ የሚከተሉትን ዝርዝሮች ያካትታል፡፡

ሀ) የዕቃዉን አጠቃላይ ሁኔታ፣ እቃውን ለመለየት አስፈላጊ የሆኑ መሪ ምልክቶችን፣ እንደየአስፈላጊነቱ የዕቃዉን አደገኛነት የሚገልፁ ጽሑፎችን፣ የእሽጎቹን ወይም የነጠላ ዕቃዉን ቁጥርና አጠቃላይ ክብደት ወይም በመጠን የተገለፀ ከሆነ ይህንኑና በዕቃ ላኪዉ የሚሰጡ ዝርዝሮችን፤

ለ) የዕቃው ውጭያዊ ሁኔታ መግለጫ፣

ሐ) የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ስምና መደበኛ የንግድ ሥራ ማከናወኛ ቦታ፤

መ) የዕቃ ላኪዉ ስም፤

ሠ) በላኪዉ የተጠቀሰ የተረካቢዉ ስም፤

ረ) መልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ዕቃውን የተረከበበተ ቀንና ቦታ፤

ሰ) ዕቃውን አጓጉዞ የማስረከቢያ ቦታ፣፤

ሸ) በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት የተደረገበት ከሆነ፣ የማስረከቢያ ቦታ የዕቃዉ ማስረከቢያ ቀን ወይም ጊዜ፤

ቀ) የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነዱ ተላላፊ ወይም የማይተላለፍ መሆኑን የሚገልፅ ጽሑፍ፤

በ) የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ወይም የዉክልና ስልጣን ያለዉ ሰዉ ፊርማ፤

ተ) ተዋዋይ ወገኖች በግልጽ የተስማሙ ከሆነ ለእያንዳንዱ የትራንስፖርት አይነት የመጫኛ ወይም የመጫኛ ዋጋ ተከፋይ በሚሆንበት የገንዘብ አይነት፣ በተረካቢው የሚከፈል ከሆነ ምን ያህሉ እንደሚከፈል ወይም የመጫኛ ዋጋዉ በእርሱ ሊከፈል መሆኑን ሌላ አመላካች የሆነ መግለጫ፤

ቸ) ሰነዱ በሚዘጋጅበት ጊዜ የሚታወቅ ከሆነ የታሰበዉን የጉዞ መስመር የትራንስፖርቱን አይነት እና ዕቃው ከአንዱ የማጓጓዣ ዓይነት ወደ ሌላዉ የማጓጓዣ ዓይነት የሚተላለፍበትን ቦታ፤

ኀ) በአንቀጽ 44 የተጠቀሰውን ቃል ያጠቃልላል፤

ነ) በኢትዮጵያ ተፈፃሚነት ካላቸው ሕጎችና ደንቦች ጋር የሚቃረኑ ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም ተዋዋይ ወገኖቹ በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነዱ እንዲካተት የተስማሙበትን ዝርዝር የሚጨምር ይሆናል፤

ኘ) የአንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 4 መመዘኛዎችን እስካሟላ ድረስ፣ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነዱ በአንቀጽ 8 ላይ ከተዘረዘሩት አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑትን ሳያሟላ መቅረቱ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነድነት ያለውን ሕጋዊ ባህሪ አያሳጣውም፤

## 9. <u>በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነድ ላይ ስለሚሠፍር ቅሬታ</u>

1. የመልቲ ምዳል ትራንስፖርት ሰነዱ የዕቃውን አጠቃላይ ሁኔታ፣ መለያ ምልክቶች፣ የዕሽጎች ወይም የነጠላ ዕቃዎች ቁጥር፣ ክብደት ወይም ብዛት የያዘ ከሆነና ይህም በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ወይም እርሱ በወከለው ሰዉ የሚታወቅ ከሆነ ወይም ስለተረከበው ዕቃ የተሰጡት ዝርዝር መግለጫዎች ዕቃውን በትክክል የማይወክሉ መሆኑን በበቂ ምክንያት ከተጠራጠረ ወይም የተሰጠውን መገለጫ ትክክለኛነት የሚያረጋግጥበት መንገድ የሌለው ከሆነ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ወይም እርሱን ወክሎ የሚሰራው ሰው በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነድ ላይ ትክክለኛ ያልሆኑትን መግለጫዎች፣ ለጥርጣሬው መንስኤ የሆነውን ምክንያት ወይም የተሰጠውን መግለጫ ትክክለኛነት ማረጋገጫ መንገድ ያልነበረው መሆኑን ገልጾ ቅሬታውን ማስፈር አለበት፡፡
2. የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ወይም ወኪሉ በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነዱ ላይ እቃዉ ያለበትን ውጭያዊ ሁኔታ ያልገለፀ ከሆነ መልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ መልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነዱ ላይ እቃዉ በጥሩ ሁኔታ የነበረ መሆኑን እንደጠቀሰ ወይም በጥሩ ሁኔታ እንደተረከበ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

## 10. <u>የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነድ የማስረጃነት ውጤት</u>

በአንቀጽ 9 መሠረት ሰነዱ ላይ የሚሰፍሩትን ዝርዝር አስመልክቶ የቅሬታ ማስታወሻ ሊቀርብባቸዉ ይችላል ተብለዉ ከተፈቀዱት ዉጪ፡-

1. የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነድ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ዕቃዉን በሰነዱ ላይ በተጠቀሰዉ ዝርዝር መሠረት የተረከበ ለመሆኑ ግምት የሚወስድበት በቂ ማስረጃ ነው፡፡

2. የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነዱ የተዘጋጀው ሊተላለፍ በሚችል አይነት ከሆነና ሰነዱ ላይ ዕቃውን አስመልክቶ የተጠቀሰውን ዝርዝር መግለጫ በቅን ልቦና በመቀበሉ ዕቃ ተቀባዩን ጨምሮ ሰነዱ የተላለፈለትን ሦስተኛ ወገን አስመልክቶ በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ የሚቀርብ ማናቸውም ተቃራኒ ማስረጃ ተቀባይነት የለውም።

11. <u>ሆን ተብሎ የሰፈረ የተሳሳተ ወይም ሳይሰፍር የቀረ ቃል</u>

መልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ሆነ ብሎ ለማታለል በማሰብ በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነዱ ላይ ዕቃዉን በተመለከተ ሀሰተኛ መረጃ የሰጠ ወይም በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (ሀ) ወይም (ለ) ወይም አንቀጽ 9 (1) (2) መሠረት እንዲካተቱ የሚፈለጉ መረጃዎችን ያስቀረ ከሆነ፣ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የኃላፊነት ጣሪያ ወሰን ተጠቃሚነት መብት ከማጣቱም በላይ በሰነዱ ላይ ዕቃዉን አስመልክቶ በሰፈረዉ መረጃ በመተማመን ዕቃ ተቀባዩን ጨምሮ ሰነዱ የተላለፈለት ሦስተኛ ወገን ለሚደርስበት ኪሣራ፣ ጉዳት ወይም ወጪ መልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

12. <u>ዕቃ ላኪዉ ስለሚሰጠዉ ዋስትና</u>

1. የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አክናዋኙ እቃውን በሚረክብበት ጊዜ ስለእቃዉ አጠቃላይ ሁኔታ ያለውን ዝርዝር በተመለከተ ምልክቱን፣ ቁጥሩን፣ ክብደቱንና መጠኑን እና እንደ ሁኔታው የዕቃዉን የአደገኛነት ባህሪ መግለጫ በተመለከተ በቂነትና ትክክለኛነት ዕቃ ላኪዉ በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነዱ ውስጥ እንዲካተት በሚል በሰጠው መረጃ መጠን መሠረት ለመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ዋስትና እንደሰጠ ተደርጎ የቆጠራል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከተውን ዝርዝር አስመልክቶ ትክክለኛ መረጃ ባለመስጠቱ የተነሣ ወይም ከዝርዝሮቹ አለመሟላት የተነሣ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ የሚደርስበትን ኪሣራ ዕቃ ላኪዉ ይተካል፡፡ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነዱ ለሌላ የተላለፈ ቢሆንም እንኳን ዕቃ ላኪዉ ኃላፊ ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰዉ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ያወጣውን ወጪ እንዲተካለት የማድረግ መብት በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ውሉ መሠረት ዕቃ ተረካቢዉን አስመልክቶ ካልሆነ በስተቀር የኃላፊነት ጣሪያ ወሰን አይኖረውም፡፡

## 13.ሌሎች ሰነዶች

የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነድ መስጠት አስፈላጊ ከሆነ ሌሎች ከትራንስፖርት ጋር የተገናኙ ሰነዶችን ወይም መልቲ ሞዳል ትራንስፖርት የሚያካትቱ ሌሎች አገልግሎቶች ተፈጻሚነት ያላቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ወይም ብሔራዊ ሕጎችን መሠረት በማድረግ ሰነድ መስጠትን አይከለክልም፡፡ ነገር ግን የእነዚህ ሌሎች ሰነዶች መሰጠት የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነዱን ሕጋዊ ባህሪ የሚቃረን አይሆንም።

## ክፍል ሦስት

## የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ኃላፊነትና ተጠያቂነት

## 14.ዕቃ ማስረከብ

1. ዕቃውን ከመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ወይም ከወኪሉ ለመረክብ መጠየቅ የሚቻለው አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሊተላለፍ የሚችል መልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነድ እንደ ሰነዱ ዓይነት በአግባቡ ለዕቃ ተቀባዩ በፊርማ የተላለፈ፣ የማይተላለፍ ከሆነ ይህንኑ ሰነድ በማስረከብ ብቻ ነው፡፡
2. መልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነዱ የተሰጠው ከአንድ በላይ በሆነ ዋና የሰነድ ቅጅ ከሆነ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ዕቃውን የማስረከብ ኃላፊነቱን ማውረድ የሚችለው ራሱ ወይም ወኪሉ በቅን ልቦና ከዋናዎቹ ሰነዶች አንዱን ብቻ በመቀበል ዕቃውን የለቀቀ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡

## 15.የኃላፊነት ጊዜ ወሰን

1. በዚህ አዋጅ መሠረት መልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ለእቃዉ ያለበት ኃላፊነት የሚሸፍነው ጊዜ ዕቃውን ከተረከበበት እስከ አስረከበበት ያለውን ጊዜ ነው፤
2. ለአንቀጽ 14 ድንጋጌዎች አፈፃፀም ሲባል፣ መልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ለተረከበዉ ዕቃ ኃላፊነት እንዳለበት የሚቆጠረዉ፡-
   ሀ) እቃውን ለማጓጓዝ በኃላፊነት ከሚከተሉት ከተረከበበት ጊዜ አንስቶ ነው፡-
      i. ከዕቃ ላኪው ወይም ከወኪሉ፣
      ii. በማስረከቢያ ቦታ ተፈፃሚ በሚሆነው ሕግና ደንብ መሠረት ዕቃው ሊጓጓዝ ይችል ዘንድ እንዲቀበል ከተፈቀደለት ባለስልጣን ወይም ሌላ ሦስተኛ ወገን፣
   ለ) ዕቃውን በሚከተለው አኳኋን እስከ ሚያስረክብበት ጊዜ፡-

i. ለተረካቢው በማስረከብ ወይም

ii. ተረካቢው ዕቃውን ከመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ በማይረከብበት ጊዜ፣ በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ውሉ መሠረት ወይም በሕግ ወይም በማስረከቢያ ቦታ ተፈፃሚ በሆነው ልዩ የአሰራር ልማድ መሠረት ዕቃን ተረካቢው ሊረከብ በሚችል ሁኔታ በማስቀመጥ ወይም

iii. እቃውን በማስረከቢያ ቦታ ተፈፃሚነት ባለው ሕግና ደንብ መሠረት ዕቃውን ለባለዕቃዉ መልሶ ለማስረከብና መረከብ እንዲችል ለተፈቀደለት ባለስልጣን ወይም ሦስተኛ ወገን፣

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ በሚል የተጠቀሰው የአከናዋኙን ሰራተኞች ወይም ወኪሎች ወይም ለመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ውል አፈፃፀም ሲባል በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ የተቀጠሩ አገልግሎት ሰጪዎችን እና ሌሎችን ይጨምራል። አስረካቢ ወይም ተረካቢ በሚል የተጠቀሰውም አገልግሎት የሚሰጡትንና ወኪሎቻቸዉን ይጨምራል፡፡

16.<u>የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ለሠራተኞቹ፣ ለወኪሎቹና ለሌሎች ሰዎች ያለበት ኃላፊነት</u>

የዚህ አዋጅ አንቀጽ 25 ድንጋጌ ተፈፃሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ሠራተኞቹ ወይም ወኪሎቹ ተግባራቸውን በተሰጣቸዉን ስልጣን ወሰን ውስጥ ሆነዉ በሚያከናዉኑበት ወይም ለመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ውሉ መፈፀም አገልግሎታቸውን የተጠቀሙባቸው ማናቸዉም ሰዎች በዉሉ አፈፃፀም ጊዜ ላከናወኑት ድርጊት ወይም ማከናወን ሲገባቸዉ ሳያከናዉኑ ለቀሩት ድርጊት የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ እነዚህ ድርጊቶች እንደራሱ ድርጊት ወይም ድርጊቱን ሣይፈፅም እንደቀረ ተቀጥሮ ኃላፊ ይሆናል፡፡

17.<u>የኃላፊነት መሰረት</u>

1. የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ሠራተኞቹ ወይም ወኪሎቹ ወይም በአንቀጽ 16 የተጠቀሰው ማናቸውም ሰው የተከሰተውን ሁኔታ እና የተከተለውን ውጤት ለማስቀረት ሊወሰዱ የሚገባቸውን ማናቸውንም ተገቢ እርምጃ ሁሉ የፈፀመ መሆኑን ካላስረዳ ድረስ መልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ዕቃው በአንቀጽ 15 (1) በተደነገገው መሠረት በኃላፊነቱ ሥር እያለ በመጥፋታቸዉ ወይም ጉዳት

የደረሰባቸው ወይም ርክክቡን በማዘግየት ምክንያት ለሚደርሰው ጉዳት ኃላፊ ይሆናል፡፡

2. ዕቃን ማስረከብ ዘገየ የሚባለው በዉሉ ላይ በግልፅ በተጠቀሰዉ ጊዜ እቃዎቹን ባለማስረከብ ወይም ይህ አይነት ስምምነት ከሌለ እንደየሁኔታዉ አንድ ኃላፊነቱን በትጋት የሚወጣ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ሊወስድበት ይችላል ተብሎ የሚገመተውን በቂ ጊዜ መሠረት በማድረግ ነው፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ ከተወሰኑት የማስረከቢያ ቀን ጀምሮ ባሉት 90 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ዕቃዎቹን ካላስረከበ ባለመብቱ ዕቃዎቹ እንደጠፉ ሊቆጥር ይችላል፡፡

18. <u>ከኃላፊነት ነፃ ስለመሆን</u>

የዕቃዉ መጥፋት ወይም መጎዳት፤ ወይም መዘግየት የተከሰተው በባለመብቱ ጥፋት ወይም ቸልተኝነት ከሆነ፣ በአጓጓዡ ጥፋት ወይም ቸልተኝነት ሳይሆን በባለመብቱ በተሰጡ መመሪያዎች፣ እቃዉ ከራሱ ውስጣዊ ይዘት ግድፈት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ኃይል ከሆነ አጓጓዡ ከኃላፊነት ነፃ ይሆናል፡፡

19. <u>ተደራራቢ ምክንያቶች</u>

በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ በኩል በሠራተኞቹ ወይም ወኪሎቹ ወይም በአንቀጽ 16 ላይ በተጠቀሱ በማናቸውም ሰዎች የተፈፀመው ጥፋት ወይም ቸልተኝነት ከሌላ ምክንያት ጋር ተዳምሮ ጥፋቱን፣ ጉዳቱን ወይም መዘግየት ካስከተለ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ የዕቃ መጥፋት ወይም መጎዳት ወይም መዘግየት በዚህ ምክንያት የደረሰ ለመሆኑ ካላስረዳ በስተቀር በተባለዉ ጥፋት ወይም ቸልተኝነት ምክንያት ለተከሰተዉ የዕቃ መጥፋት ወይም መጎዳት ወይም መዘግየት የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ባደረገዉ ጥፋት ወይም ቸልተኝነት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

20. የ<u>ኃላፊነት ወሰን</u>

1. መልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ዕቃዉ ለማጓጓዝ ከመረከቡ በፊት በላኪዉ ዓይነታቸዉና ዋጋቸዉ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነዱ ላይ ያልተገለፁ ማናቸውም ዕቃዎች ቢጠፉ፣ ጉዳት ቢደርስባቸዉ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ካሣ የመክፈል ኃላፊነት ከስፔሻል ድሮዊንግ ራይት /ኤስ.ዲ.አር/ 835 በጥቅል ወይም ሌላ የጭነት መለኪያ ወይም ከጠፋት ወይም ጉዳት ከደረሰባቸዉ

ዕቃዎች ዋጋ ስፔሻል ድሮዊንግ ራይት /ኤስ.ዲ.አር/ በ2.5 በኪሎ ግራም ሆኖ ከሁለቱ ከፍተኛውን ካሣ ይከፍላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ከፍተኛዉን መጠን ለማስላት ሲባል ከዚህ በታች የተመለከቱት ደንቦች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

ሀ) ዕቃውን አጠቃሎ ለመጫን ጥቅም ላይ የዋለው ኮንቴይነር የዕቃ ማሸጊያ ሳጥን ወይም ዕቃን አጠቃሎ ለማሸግ ጥቅም ላይ የዋሉ ሌላ በማጓጓዣ ሰነዱ የተጠቀሱ ጥቅል ይይዛል ተብሎ የተጠቀሰዉ ወይም ሌላ የጭነት መላኪያ፡፡ በዕሽጉ ዉስጥ የሚገኙ ዕቃዎች ዝርዝር በሰነዱ ላይ ካልተገለፀ በስተቀር ዕቃዎችን አቀናጅቶ ለመያዝ የሚጠቅም ጥቅል ወይም የጭነት መላኪያ እንደ አንድ ጥቅል ብቻ ይቆጠራል፡፡

ለ) የዕቃ ማሸጊያዉ ራሱ በጠፋ ወይም ጉዳት በደረሰበት ጊዜ ይህ የዕቃ ማሸጊያ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ንብረት ወይም በእርሱ የቀረበ ካልሆነ በቀር እንደ አንድ የተለየ የጭነት መለኪያ ይቆጠራል።

3. የዕቃዉ መጥፋት ወይም መጎዳት በተከሰተበት ወቅት ትራንስፖርቱ የተከናወነዉ በአንድ የትራንስፖርት አይነት በሚከናወንበት የማጓጓዣ ሥራዉ ክፍል ከሆነና ለዚህም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ ከተመለከተዉ የኃላፊነት መጠን በላይ ከፍተኛ ኃላፊነት መጠን ተፈፃሚ እንዲሆን የሚደነግግ ሕግ ካለ፣ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ለጠፋዉ ወይም ጉዳት ለደረሰበት ዕቃ የሚኖርበት ኃላፊነት የሚወሰነው የዕቃዉ መጥፋት ይም መጎዳት በደረሰ ጊዜ የማጓጓዝ ሥራውን ያከናወነዉ አጓጓዥን አስመልክቶ ለተከናወነበት ተፈፃሚ የሚሆነዉ አግባብነት ያለዉ ሕግ መሠረት ይሆናል፡፡

21. <u>በዕቃዉ መዘግየት ሳቢያ የኃላፊነት ወሰን</u>

መልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ዕቃውን በወቅቱ ሳያደርስ በመዘግየቱ ሳቢያ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16 እና 17 መሠረት አጓጓዡ የዘገዩትን ዕቃዎች ለማጓጓዝ የተቀበለውን ወይም ባለዕቃዉ መክፈል ያለበትን የጭነት አገልግሎት ዋጋ በሁለት ተኩል ($2^{1/2}$) ተባዝቶ ለባለዕቃዉ የመክፈል ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡ ነገር ግን ይህ ክፍያ በማጓጓዣ ውሉ ላይ ከተጠቀሰዉ የጭነት አገልግሎት ጠቅላላ ዋጋ ሊበልጥ አይችልም፡፡

22.**<u>አጠቃላይ ኃላፊነት</u>**

በአንቀጽ 20 እና 21 ወይም በአንቀጽ 15 እና 17 መሠረት የአጓጓዡ ጠቅላላ የኃላፊነት መጠን ዕቃዉ ጠቅላላ ቢጠፋ በአንቀጽ 20 ወይም አንቀጽ 23 መሠረት ከተወሰነው የኃላፊነት መጠን ሊበልጥ አይችልም፡፡

23.**<u>ስለተጨማሪ ኃላፊነት</u>**

በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ እና በዕቃ ላኪ መካከል በሚፈፀም ስምምነት መሠረት በአንቀጽ 20 እና 21 ከተመለከቱት የኃላፊነት ወሰን በላይ ከፍ በማድረግ በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነዱ ውስጥ በመጥቀስ መወሰን ይችላል፡፡

24.**<u>ከዉል ዉጪ የሚደርስ ኃላፊነት</u>**

የእቃውን መጥፋት ወይም መጐዳት ወይም መዘግየት በተመለከተ ዉልን፣ ከዉል ዉጪ ኃላፊነትን ወይም ሌላ የኃላፊነት ምንጭን መሠረት በማድረግ በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ላይ ለሚመሰረት ክስ በዚህ አዋጅ ላይ የተመለከቱት መከላከያዎችና የኃላፊነት መጠን ወሰኖች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

25.**<u>የሠራተኞችና ወኪሎች መከላከያ</u>**

እቃዎቹ በመጥፋታቸዉ፣ ወይም ጉዳት ስለደረሰባቸዉ ወይም በመዘግየት ምክንያት በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ሰራተኛው ወይም ወኪል ላይ ክስ ከተመሰረተ እና ይኸዉ ሠራተኛ ወይም ወኪል ተግባሩን ያከናወነዉ በሥራ ውሉ መሠረት መሆኑን ያስረዳ እንደሆነ ወይም የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ዉሉን ለመፈፀም ሲል አገልግሎታቸውን በተጠቀመባቸዉ በሌሎች ማናቸዉም ሰዎች ከሆነና ይኸዉ ሌላኛ ሰዉ ደግሞ ድርጊቱን የፈፀመዉ ዉሉን በአግባቡ ለመፈፀም መሆኑን ያስረዳ እንደሆነ ሠራተኛዉ ወይም ወኪሉ ወይም ሌላኛዉ ሰዉ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት አንስቶ ሊከራከርባቸዉ የሚችላቸዉን መከላከያዎችና የኃላፊነት መጠን ወሰን ክርክሮችን ጠቅሰዉ የመከራከር መብት ይኖራቸዋል፡፡

26.**<u>ከፍተኛዉ የካሳ መጠን</u>**

በአንቀጽ 27 እና 28 ላይ ከተመለከተው በስተቀር ከመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ እና ከሠራተኛዉ ወይም ወኪሉ ወይም ለመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ውሉ አፈፃፀም አገልግሎታቸውን ከተጠቀመባቸው በማናቸውም ሌሎች ሰዎች በጠቅላላ ሊከፈል የሚችለው የካሣ መጠን በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ከተመለከተው ኃላፊነት ወሰን ሊበልጥ አይችልም።

27.<u>የኃላፊነትን መጠንን ለመወሰን መብት ስለማጣት</u>

1. የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ የዕቃዉ መጥፋት፣ መጐዳት ወይም መዘግየት እንዲከሰት ያደረገዉ ሆነ ብሎ ወይም በከፍተኛ ቸልተኝነትና ዕቃዉ ሊጠፋ ወይም ሊጎዳ ወይም ሊዘገይ እንደሚችል እያወቀ በፈፀመዉ ድርጊት ወይም መፈፀም ሲገባዉ ባለመፈፀሙ ምክንያት መሆኑ ከተረጋገጠ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ በዚህ አዋጅ ላይ የተመለከተዉን ኃላፊነት መጠን ወሰን ተጠቃሚ የመሆን መብት ያጣል፡፡
2. የአንቀጽ 25 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ሠራተኛ ወይም ወኪሉ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ለዉሉ አፈፃፀም አገልግሎታቸውን የተጠቀሙባቸው ማናቸውም ሰው የፈፀሙት ድርጊት ወይም መፈፀም ሲገባው ሣይፈጽመው የቀረው ድርጊት ለዕቃው መጥፋት ወይም መጎዳት ወይም መዘግየት ምክንያት ከሆነ ወይም የፈፀሙት ሆነ ብለው ይህንኑ የዕቃ መጥፋት ወይም መጐዳት ወይም መዘግየት ለማስከተል ከሆነ ወይም በከፍተኛ ቸልተኝነት ይኸው የዕቃ መጥፋት ወይም መጐዳት ወይም መዘግየት ሊከሰት እንደሚችል ያውቁ የነበረ መሆኑ ከተረጋገጠ በዚህ አዋጅ ድንጋጌ የተመለከተው የሃላፊነት መጠን ወሰን ተጠቃሚ አይሆኑም፡፡

<u>ክፍል አራት</u>

<u>የእቃ ላኪዉ ኃላፊነት</u>

28.<u>አጠቃላይ ድንጋጌ</u>

የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ በዕቃ ላኪዉ ወይም በሠራተኞቹ ወይም በወኪሎቹ ጥፋት ወይም ቸልተኝነት ምክንያት ጉዳት የደረሰበት በሆነ ጊዜና እነዚህም ሠራተኞች ወይም ወኪሎች ተግባራቸውን ያከናወኑት በሥራ ውላቸዉ መሠረት ከሆነ ዕቃ አስረካቢው የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ በዚህ ምክንያት ለደረሰበት ኪሣራ ኃላፊ ይሆናል፡፡ ማንኛውም የዕቃ አስረካቢዉ ሠራተኛ ወይም ወኪል በራሱ በኩል በተፈፀመ ጥፋት ወይም ቸልተኝነት ለደረሰ ኪሣራ ኃላፊ ነዉ፡፡

29.<u>በአደገኛ እቃዎች ላይ ተፈፃሚ ስለሚሆን ልዩ ደንብ</u>

1. ዕቃ አስረካቢዉ በተገቢ ሁኔታ አደገኛ እቃዉን አደገኛ በማለት ማመልከት ወይም በሚለጠፍ ነገር ማሣየት አለበት፡፡

2. መልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ አደገኛነት ያላቸውን ዕቃዎች ለአጓጓዡ ወይም በእሱ ስም የማጓጓዝ ስራውን ለሚሰራ ማንኛውም ሰው ባስረከበ ጊዜ ለአጓጓዡ የዕቃውን የአደገኝነት ባህሪ እና አስፈላጊ በሆነም ጊዜ ሊወሰድ የሚገባውን የጥንቃቄ እርምጃ በትክክል ማሳወቅና ማመልከት አለበት፡፡

30. **<u>የአደገኛ እቃው ምልክት</u>**

ዕቃ አስረካቢው በአንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት ለመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ሳያሳውቀው ከቀረ እና የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ በበኩሉ የአደገኛነት ባህሪያቸውን የማያውቅ ከሆነ፡-

1. የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ እነዚህን አደገኛ ዕቃዎች በመጫኑና በማጓጓዙ ምክንያት ለሚደርስበት ኪሣራ ዕቃ አስረካቢዉ ኃላፊ ይሆናል፡፡
2. ያለምንም ካሣ ክፍያ እንደየሁኔታው አስፈላጊነት እቃዎቹ ጉዳት እንዳያደርሱ በማናቸውም ጊዜ እንዲራገፉ፣ እንዲወደሙ፣ እንዲወገዱ ሊያደርግ ይችላል፡፡

31. **<u>የአጓጓዡ ስለዕቃው ባህሪ ማወቅ</u>**

1. በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ውል መሠረት እቃዎቹ በኃላፊነት ተወስደው የተጓጓዙት የአደገኛነት ባህሪያቸው እየታወቀ ከሆነ በአንቀጽ 30 የተመለከቱት ድንጋጌዎች በማናቸውም ሰው በመከላከያነት ሊጠቀሱ አይችሉም፡፡
2. የአንቀጽ 30 (2) ድንጋጌ ተፈፃሚ በማይሆንበት ወይም በመከላከያነት ሊጠቀስ በማይችልበት ጊዜ አደገኛ ዕቃዉ ለህይወት ወይም ለንብረት በእርግጥም አደገኛ እንደሆኑ ስለሚቆጠር እንዲራገፉ፣ እንዲወድሙ ወይም ጉዳት እንዳያደርሱ እንዲወገዱ ሊደረግ ይችላል፡፡ በዚህም ጊዜ በአንቀጽ 16 እና 17 በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ኃላፊ ካልሆነ ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 38 ድንጋጌ መሠረት ጉዳትን የመጋራት ግዴታ ከሌለ በስተቀር ካሣ አይከፈልም፡፡

## ክፍል አምስት

## ማስታወቂያ ስለመስጠትና በፍርድ ቤት ክስ ስለመመስረት

32.<u>በግልጽ ሊታወቅ የሚችል የዕቃ መጥፋት ወይም መጎዳት ሲፈጠር የሚሰጥ ማስታወቂያ</u>

እቃው ለተረካቢው ከተሰጠበት ቀን በኋላ ያለው የሥራ ቀን ሳያልፍ አጠቃላይ የደረሰው የዕቃ መጥፋት ወይም መጎዳት በግልፅ ሊታወቅ የሚችል ከሆነ የጠፉ ወይም ጉዳት የደረሰባቸዉ ለመሆኑ ዕቃ ተረካቢው ለመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ በጽሑፍ ማስታወቂያ እስካልሰተጠዉ ድረስ መልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ውል በተገለፀው መሠረት እቃውን በአግባቡ እንዳስረከበ ይገመታል፡፡

33.<u>በግልጽ ሊታይ የማይችል የዕቃ መጥፋት ወይም መጎዳት ሲከሰት የሚሰጥ ማስታወቂያ</u>

1. የጠፋዉን ወይም ጉዳት የደረሰበትን ዕቃ በርክክብ ወቅት በግልፅ አይቶ ማወቅ የማይቻል ከሆነ የዕቃዉ ርክክብ ከተፈፀመበት ቀን በኃላ ባሉት ሰባት ተከታታይ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ካልተሰጠ የአንቀጽ 32 ድንጋጌዎች ለዚህ ሁኔታም ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡
2. እቃውን ተረካቢዉ ሲረከብ የዕቃዉ ሁኔታ በተዋዋዮቹ ወይም በሕጋዊ ወኪሎቻቸዉ በጋራ የተመረመሩ ወይም ቁጥጥር የተደረገባቸው ከሆነ በዚህ ቁጥጥር ወይም ምርመራ አማካኝነት የተረጋገጠውን ዕቃ መጥፋት ወይም መጎዳት በተመለከተ የፅሑፍ ማስታወቂያ መስጠት አያስፈልግም፡፡
3. የእቃዎቹ መጥፋት ወይም መጉዳት እርግጠኛ ሲሆን ወይም ወዲያው የተረጋገጠ ሲሆን የጠፋዉን ዕቃ ወይም ጉዳት የደረሰበትን ለመመርመርና ለመለየት ይቻል ዘንድ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ እና ዕቃ ተረካቢዉ አንዱ ለሌላዉ ምርመራዉን ለማካሄድ የሚያስችል ተገቢ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ ማሟላት ይኖርባቸዋል፡፡

34.<u>የዕቃ ርክክብ በመዘግየቱ ምክንያት ስለሚሰጥ ማስታወቂያ</u>

እቃዎቹ ለተረካቢዉ ከተሰጡበት ቀን በኋላ ባሉት ስልሣ ተከታታይ ቀናት ውስጥ ለመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ የፅሑፍ ማስታወቂያ ካልተሰጠዉ በስተቀር ወይም ለዕቃ ተረካቢዉ በአንቀጽ 15 (2) (ለ) (¡) እና (¡¡) መሠረት ርክክቡ የተፈፀመ

ለመሆኑ ማስታወቂያ የተሰጠው ከሆነ ለዕቃ ማስረከቡ በመዘግየቱ ምክንያት በመልቲ ሞዳል አከናዋኙ የሚከፈል ካሣ አይኖርም፡፡

35. **<u>የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ለሚደርስበት ኪሣራ ወይም ጉዳት የሚሰጠዉ ማስታወቂያ</u>**

ኪሣራ ወይም ጉዳት ከደረሰ በኋላ ባሉት 90 ተከታታይ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ወይም በአንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) መሠረት ርክክብ ከተደረገ በኋላ ከሁለቱ ዘግይቶ የተፈፀመዉን ድርጊት መሰረት በማድረግ መልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ስለደረሰበት ኪሣራ ወይም ጉዳት አጠቃላይ ሁኔታ ጠቅሶ ለዕቃ አስረካቢዉ ማስታወቂያ ካልሰጠ ዕቃ አስረካቢው ወይም ሠራተኞቹ ወይም ወኪሎቹ በፈፀሙት ጥፋት ወይም ቸልተኝነት የተነሣ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ምንም ዓይነት ኪሣራ ወይም ጉዳት እንዳልደረሰበት በቂ ማስረጃ ነው፡፡

36. **<u>የሥራ ቀን ባልሆነ ጊዜ ማስታወቂያ የሚቋረጥ ስለመሆኑ</u>**

ከአንቀፅ 32 እስከ 35 ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት የሚሰጥ ማስታወቂያ የሚያበቃበት ጊዜ ዕቃዎቹ በሚራገፉበት ቦታ በሥራ ቀን ላይ ካልዋለ ማስታወቂያው የሚያበቃበት ጊዜ እስከሚቀጥለው የስራ ቀን ድረስ ይራዘማል፡፡

37. **<u>በሌሎች የሚሰጥ ማስታወቂያ</u>**

መልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ አገልግሎቱን የሚጠቀምበትን ሌላ ሰው ጨምሮ ለመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አክናዋኙ ወኪል ሆኖ በስራ ቦታ ላይ ለሚሰራ ሰዉ ወይም የዕቃ አስረካቢዉ ወኪል ሆኖ ለሚሰራ ሰዉ ቢሰጥ ከአንቀጽ 32 - 36 ላሉት ድንጋጌዎች አፈፃፀም ሲባል ለመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አክናዋኙ ወይም ለዕቃ ላኪዉ እንደተሰጠ ይቆጠራል።

38. **<u>በባሕር ማጓጓዝ ወቅት በአደጋ ምክንደት የደረስ የጋራ ጉዳት</u>**

የዚህ አዋጅ ማናቸዉም ድንጋጌዎች የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ውሉ ድንጋጌዎች ወይም የባህር ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ዕቃ በባህር ሲጓጓዝ በአደጋ ምክንያት በአጓጓዡና በባለዕቃዉ ላይ ለደረሰ የጋራ ጉዳት ክፍያ ማስተካከያ ደንቦች የሚኖራቸውን ተፈፃሚነትና የተፈፃሚነት ወሰን በተመለከተ ክልከላ አያደርግም፡፡

39.**መልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ እቃዎችንና ሰነዶችን በመያዣነት ለመያዝ ያለው መብት**

መልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ውሉ መሠረት ሊከፈለው የሚገባውን ማናቸውንም ክፍያ እና የመጋዘን ኪራይን ጨምሮ እነዚህን አጠቃላይ ክፍያዎች ለማስከፈል የሚያወጣቸዉን ወጪዎች ጭምር ለማስከፈል እቃዎቹንና ሰነዶቹን በመያዣነት የመያዝ መብት አለው፡፡

40.**ስለ ክስ ይርጋ**

1. በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ከመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አፈፃፀም ጋር በተገናኘ በፍ/ቤት የሚቀርቡ ክርክሮች በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ለፍ/ቤት ካልቀረቡ በይርጋ ቀሪ ይሆናሉ።
2. ይሁን እንጂ ርክክቡ ከተፈፀመበት ቀን በኋላ ባሉት 6 ወራት ውስጥ የክሱን አጠቃላይ ይዘትና ዋና ዋና ዝርዝሮች የሚገልፁ፣ የጽሑፍ ማስታወቂያ ወይም የዕቃዎቹ ርክክብ ያልተደረገ ከሆነ ደግሞ የእቃዎቹ ርክክብ መደረግ ከነበረበት ቀን ቀጥሎ ባለዉ ቀን ጀምሮ ክስ ካልተመሰረተ ይህ ጊዜ እንዳበቃ በይርጋ ይቋረጣል፤
3. የይርጋ ጊዜው መታሰብ የሚጀምርው ዕቃዎቹን በሙሉ ወይም በከፊል ካስረከበበት ቀን ቀጥሎ ካለው ቀን፣ ወይም ርክክብ ያልተደረገ ከሆነ ርክክቡ መደረግ ከነበረበት የመጨረሻ ቀን ቀጥሎ ካለው ቀን ጀምሮ ነው፡፡
4. ይርጋ በሚታሰብበት በማናቸውም ጊዜ ውስጥ ግዴታ እንዲፈጽምለት የተጠየቀው ሰው ለባለመብቱ ተገቢውን መግለጫ በመስጠት የይርጋ ጊዜውን ለማራዘም ይችላል፡ ፡ ይህ ጊዜ ሌላ መግለጫ በመስጠት በተጨማሪ ሊራዘም ይችላል፡፡
5. አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ኃላፊ የተባለዉ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ቢያልፍም በበኩሉ ለመጠየቅ የሚችለው የካሣ ጥያቄ ካሣውን ለጠየቀው ሰው የካሣ ክፍያውን ከፈፀመበት ቀን ወይም ካሣ የቀረበበት በመሆኑ የፍርድ ቤት መጥሪያ ከደረሰው ቀን በኃላ ባሉት 90 ቀናት ውስጥ ክሱን ከመሠረተ ነዉ፡፡

41.**የዳኝነት ስልጣን**

ከመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ጋር በተገናኘ የሚኖረው የፍ/ቤት ክርክር ከሣሽ በመሰለው ሃሣብ መሠረት ስልጣን ያለው ፍ/ቤት በሚገኝበት ቀጥሎ ከተመለከቱት ቦታዎች በአንዱ ክስ ሊመሰርት ይችላል፡፡

ሀ) በተከማሸ መደበኛ የንግድ ሥራ ማከናወኛ ቦታ፣ ይህ በሌለ ጊዜ አዘወትሮ በሚኖርበት ቦታ፣

ለ) ተከሣሹ የንግድ ቦታ ወይም ቅርንጫፍ ወይም ዉሉ እንዲፈፀም የተደረገበት ወኪል የሚኖርበት ከሆነ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ዉሉ በተፈፀመበት ቦታ፣

ሐ) ዕቃዎቹን በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ለማጓጓዝ በኃላፊነት የተሰጠበት ወይም የማስረከቢያ ቦታ፣

መ) በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ውሉ መሠረት ለዚሁ ዓላማ በሚል በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ውሉ ላይ በተጠቀሰ ማናቸዉም ቦታ፡፡

## ክፍል ስድስት

## ተጨማሪ ድንጋጌዎች

### 42. ፈራሽ የዉል ቃሎች

1. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚቃረኑ የውል ቃሎች ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡ የእነዚህ የውል ቃሎች ተፈፃሚ አለመሆን የሌሎቹን የውል ድንጋጌዎች ፈራሽ አያደርግም፡፡
2. ለእቃዎቹ የሚገባውን የመድን ውል ለመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ጥቅም እንዲሆን መብት የሚያስተላልፍ ወይም ሌላ ማናቸውም የውል ድንጋጌ በሕግ ፊት ውጤት አይኖረዉም፡፡

### 43. ኃላፊነትን ወይም ግዴታን ስለመጨመር

የአንቀጽ 44 ድንጋጌዎች ቢኖሩም መልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ከዕቃ አስረካቢው ጋር በመስማማት በዚህ አዋጅ የተጣሉበትን ኃላፊነቶችና ግዴታዎች ሊጨምር ይችላል፡፡

### 44. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በአስገዳጅ ሁኔታ ተፈፃሚ ስለማድረግ

የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሰነዱ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ላይ የተመሰረተና አዋጁንም የሚቃረን የውል ቃል ካለ ዋጋ እንደማይኖረው፤ ይህም የዕቃ አስረካቢውን ወይም የተረካቢውን መብትና ጥቅም በእጅጉ የሚጎዳ እንደሚሆን የሚገልጽ ጽሑፍ መያዝ አለበት፡፡

45.<u>የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች  አለማክበር ስለሚያስከትለዉ ቅጣት</u>

ባለመብቱ እቃዎቹን በአንቀጽ 42 መሠረት ፈራሽ እንዲሆን በተደረገ የውል ቃል የተነሣ ወይም በአንቀጽ 44 ላይ በተጠቀሰዉ መሠረት ማስገባት ያለበትን ጽሑፍ ቀሪ በማድረጉ የተነሣ ኪሣራ ቢደርስበት ባለመብቱ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ለጠፉ ወይም ለተጎዱ ወይም ለዘገዩ እቃዎች ሊከፈለዉ እስከሚገባዉ የካሣ መጠን ድረስ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ካሣ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

46.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡ ፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ 29 ቀን 1999 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ፕሬዝደንት**

# አዋጅ ቁጥር 589/2000

## የመንገድ ልማት ፕሮጀክቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ

የመንገድ ልማት ፕሮጀክቶችን በገንዘብ የሚደግፉ ለጋሽ ወይም አበዳሪ ድርጅቶች ለነዚህ ፕሮጀክቶች ዕቃ ለሚያቀርቡ ወይም የሥራ ተቋራጭነት ወይም የማማከር አገልግሎት ለሚሰጡ ሰዎች ወይም ድርጅቶች መክፈል ያለበትን ገንዘብ ለመልቀቅ በመዘግየታቸው ምክንያት የተፈጠሩ ችግሮች ወደፊት እንዳያጋጥሙ ለመከላከል ለመንገድ ልማት ፕሮጀክቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የመንገድ ልማት ፕሮጀክቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 589/2000" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**

   የመንገድ ልማት ፕሮጀክቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ከዚህ በኋላ "ፈንዱ" በመባል የሚጠራ እና የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር[76] በሚከፍተው ልዩ የባንክ ሂሣብ ውስጥ ተቀማጭ የሚሆን ፈንድ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

3. **የፈንዱ ዓላማዎች**

   ፈንዱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል።

   1. የመንገድ ልማት ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ማፋጠን፤
   2. የመንገድ ልማት ፕሮጀክቶችን በገንዘብ የሚደግፉ ለጋሽ ወይም አበዳሪ ድርጅቶች ገንዘብ በተገቢው ጊዜ ባለመልቀቃቸው ዕቃ አቅራቢዎች፣ ሥራ ተቋራጮች ወይም አማካሪዎች ለዘገየባቸው ክፍያ በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ላይ በሚያቀርቡት የወለድና የካሣ ጥያቄ ምክንያት በመንግሥት ላይ የሚደርሰውን የገንዘብ ኪሣራ መከላከል ነው።

4. **የፈንዱ ምንጭ**

   የፈንዱ ምንጭ አንድ ጊዜ ከመንግሥት የሚመደብ ብር 75,000,000 /ሰባ አምስት ሚሊዮን ብር/ በጀት ይሆናል።

---

[76] በ25/08 (2011) አ. 1097 አንቀጽ 9(4) መሰረት የገንዘብ ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

5. **የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን**

ሚኒስቴሩ፡-

1. የፈንዱ ገንዘብ የሚቀመጥበትን ልዩ የባንክ ሂሣብ ይከፍታል፤
2. የፈንዱን ሂሣብ ይይዛል፤ ያስተዳድራል፡፡

6. **ስለ ክፍያና ማስተካት**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር፡-

1. የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ከሥራ ተቋራጮች፣ ከአማካሪዎች ወይም ከዕቃ አቅራቢዎች ጋር በተፈራረመው ውል መሠረት በየጊዜው ሊከፈል ስለሚገባው ሂሣብ በሰነድ የተደገፈ የክፍያ ጥያቄ ሲያቀርብ ከፈንዱ ወጪ በማድረግ ለባለመብቶቹ ይከፍላል፤
2. በየጊዜው ከፈንዱ ወጪ ሆኖ ለሥራ ተቋራጮች፤ ለአማካሪዎች ወይም ለዕቃ አቅራቢዎች የተከፈለውን ገንዘብ ፕሮጀክቱን በገንዘብ ለሚደግፈው ለጋሽ ወይም አበዳሪ ድርጅት በሰነድ የተደገፈ ጥያቄ በማቅረብ እንዲተካ ያደርጋል፡፡

7. **የሂሣብ መዛግብት**

የፈንዱ የመዝገብና የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት የፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን የሚከተል ይሆናል።

8. **ኦዲት**

የፈንዱ ሂሣብና መዛግብት በዋናዉ ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

9. **አዋጁ የሚፀና በት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ 7 ቀን 2000 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 681/2002

## ስለተሽከርካሪ መለያ፣ መመርመሪያና መመዝገቢያ አዋጅ

በሰው ህይወትና ንብረት ላይ በመድረስ ላይ ላለው የመንገድ ትራፊክ አደጋ አንዱ መንስኤ የተሽከርካሪ ምዝገባና ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ስርዓት ችግር ያለው ሆኖ በመገኘቱ በመሆኑ፤

የተሽከርካሪ ምዝገባና ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ በአገር አቀፍ ደረጃ ወጥነት ባለው ሁኔታ እንዲፈጸም የሚያስችል ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ መመዘኛ ማውጣት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 55/1/ መሠረት የሚከተለዉ ታዉጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የተሽከርካሪ መለያ፣ መመርመሪያና መመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር 681/2002" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

   1. "ተሽከርካሪ" ማለት ልዩ ወታደራዊ ተሽከርካሪዎችን ሳይጨምር በመንገድ ላይ በመንኮራኩር የሚሄድ ማንኛውም ዓይነት ተሽከርካሪ ሆኖ ሠረገላ፣ ብስክሌት፣ ባለሞተር ተሽከርካሪ፣ ግማሽ ተሣቢ እና ተሳቢ ተብሎ ይከፈላል፤
   2. "ሠረገላ" ማለት ከብስክሌት፣ ከባለሞተር ተሽከርካሪ፣ ከግማሽ ተሣቢና ከተሳቢ በስተቀር ማናቸውም ተሽከርካሪ ነው፤
   3. "ብስክሌት" ማለት በሚነዳው ሰው ኃይል እየተንቀሳቀሰ የሚሄድ ተሽከርካሪ ነው፤
   4. "ባለሞተር ተሽከርካሪ" ማለት በመካኒካል ወይም በኤሌክትሪክ ኃይል በመንገድ ላይ እየተንቀሳቀሰ የሚሄድ ተሽከርካሪ ነው፤

5. “ተሳቢ ወይም ግማሽ ተሳቢ” ማለት ለራሱ የተለየ የሞተር ሃይል የሌለው ጎታች በሆነ በሌላ ባለሞተር ተሽከርካሪ ላይ ሊቀጠልና ሊጎተት የሚችል ተሽከርካሪ ነው፤
6. “ልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያ” ማለት ሰዉን ወይም እቃን በመንገድ ላይ እንዲያመላልስ ሆኖ የተሰራ ተሽከርካሪ ሳይሆን ለእርሻ፣ ለአትክልት፣ ለከብት እርባታ፣ ለመንገድ፣ ለሕንፃ፣ ለቁፋሮ ወይም ለማናቸዉም ተመሳሳይ ሌላ ስራ የተሰራ ወይም ለዚህ ጉዳይ እንዲውል የተደረገ ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፤
7. “ምዝገባ የተደረገለት ተሽከርካሪ” ማለት ተፈላጊ ሰነዶች መሟላታቸው ተረጋግጠ በባለንብረቱ ስም ምዝገባ የተደረገለት ተሽከርካሪ ነው፤
8. “መለያ ቁጥር” ማለት አንድ ተሽከርካሪ ደህንነቱና ምቹቱ በምርመራ ተረጋግጠ አግባብነት ባለው አካል ሲመዘገብ የሚሰጠው የቁጥሮች፣ የፊደሎችና የምልክቶች ጣምራ ነው፤
9. “ዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት” ማለት አንድ ተሽከርካሪ በመንገድ ላይ ለመንቀሳቀስ የቴክኒክ ብቃትና ምቾት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ የሚሰጥና ለአንድ ዓመት የሚፀና ተለጣፊ ምልክት ነው፤
10. “የመለያ ቁጥር ሠሌዳ” ማለት ተሽከርካሪውን በመንገድ ላይ በቀላሉ ለመለየት እንዲያስችል በተሽከርካሪው ላይ የሚደረግ መለያ ቁጥሮች የተጻፈበት ሠሌዳ ነው፤
11. “የኢንተርናሽናል ትራፊክ” ማለት በውጭ አገር የተመዘገበና በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንገዶች ላይ ለተወሰነ ጊዜ ለመሽከርከር እውቅና የተሰጠው ተሽከርካሪ ነው፤ ሆኖም የዚህ ዓይነቱ እውቅና የሚሰጠው ተሽከርካሪዉ የተመዘገበበት አገር በተመሳሳይ ሁኔታ በኢትዮጵያ የተመዘገበ ተሽከርካሪ በመንገዶቹ ላይ እንዲሽከረከር የሚፈቅድ ከሆነ ነው፤
12. “የአካል ጉዳተኛ ጋሪ” ማለት ባለመንኮራኩር ወንበርና ባለሦስት እግር ብስክሌት የመሳሰለ አካል ጉዳተኛ የሆኑ ሰዎችን ለማጓጓዣ ብቻ የተሰራና ለዚህ ሥራ ብቻ የሚውል ተሽከርካሪ ነው፤
13. “በመዝገብ የተያዘ ተሽከርካሪ” ማለት በባለፋብሪካ፣ በነጋዴ፣ በዳግም ሰሪ ወይም ከጥቅም ውጭ የሆኑ ተሽከርካሪዎችን በሚሰበስብ ሰው መዝገብ ለሽያጭ የተያዘ ማንኛውም ተሽከርካሪ ነው፤

14. “ባለፋብሪካ” ማለት ተሽከርካሪዎችን ሠርቶ ወይም ገጣጥሞ በማቅረብ የንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ነው፤
15. “የመከላከያ ኃይል ተሽከርካሪ” ማለት የአገር መከላከያ ሚኒስቴር ንብረት ሆኖ ለወታደራዊ ተግባር ብቻ እንዲውል የተመደበ ማንኛውም ተሽከርካሪ ነው፤
16. “ኦፊሲዬል ሰነዶች” ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ባለንብረትነትን በሚገባ ለማሳወቅና የቴክኒክ ምርመራ ለማካሄድ የሚቀርቡ ማመልከቻዎች፣ የጉምሩክ ሰነዶች፣ የቴክኒክ ምርመራ ቅጾች፣ ደብዳቤዎችና ሌሎች ጽሁፎች ናቸው፤
17. “ኦፊሲዬል መዝገብ” ማለት የተሽከርካሪ ባለንብረትነትንና ዓመታዊ ምርመራን የሚመለከቱ መግለጫዎች የሚጻፉበት መዝገብ ነው፤
18. “ባለይዞታ” ማለት የባለንብረት መብት ባይኖረውም አንድ ተሽከርካሪ ይዞ ለመጠቀም ሕጋዊ መብት ያለው ማናቸውም ሰው ነው፤
19. “ዳግም ሰሪ” ማለት ማንኛውንም አሮጌ ወይም አዲስ ተሽከርካሪ ዋና ዋና ዕቃዎቹን በማውለቅ፣ በመለወጥ ወይም በመጨመር በመጀመሪያ አሰራሩ ላይ ዓይነተኛ ለውጥ አድርጎ የማቅረብ የንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው ነው፤
20. “የመመርመሪያ ጊዜ” ማለት ዓመታዊ የተሽከርካሪ ምርመራ የሚከናወንበት ጊዜ ነው፤
21. “ሬከር” ማለት ከጥቅም ውጭ የሆኑ ተሽከርካሪዎችን በመፈታታት ጠቃሚ ክፍሎቻቸውን ለዳግም አገልግሎት የማቅረብ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው ነው፤
22. “የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር” ማለት አግባብነት ባለው አካል ለአንድ ተሽከርካሪ ባለንብረት የሚሰጥ የባለሀብትነት ማረጋገጫ ሰነድ ነው፤
23. “ጊዜያዊ የመንቀሳቀሻ ፈቃድ” ማለት አንድ ተሽከርካሪ ምዝገባን እስከሚያካሂድ ድረስ ለቅድመ ምዝገባ ዝግጅት አግባብነት ባለው አካል የሚሰጥ ጊዜያዊ የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ነው፤
24. “ነጋዴ” ማለት ተሽከርካሪ በመግዛትና በመሸጥ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው ነው፤
25. “የተሽከርካሪ ምርመራ” ማለት አንድ ተሽከርካሪ በመንገድ ላይ የቴክኒክ ብቃትና ምቾት ያለው መሆኑንና መንቀሳቀስ የመቻል ብቃቱን ለማረጋገጥ የሚደረግ የቴክኒክ ምርመራ ነው፤

26. “ባለሥልጣን” ማለት በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/1997 የተቋቋመው የትራንስፖርት ባለሥልጣን ነው፤
27. “አግባብነት ያለው አካል” ማለት ባለሥልጣኑ ወይም ተሽከርካሪ ለመመዝገብና ለመመርመር ሥልጣን የተሰጠው የክልል መንግሥት አካል ነው፤
28. “ሰዉ” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
29. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በኢትዮጵያ መንገዶች ላይ በሚሽከረከሩ ተሽከርካሪዎች ላይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለ ምዝገባና የባለንብረት መታወቂያ ደብተር</u>

4. <u>ምዝገባና የባለንብረት መታወቂያ ደብተር ስለማስፈለጉ</u>

የማንኛዉም ተሽከርካሪ ባለንብረት ተሽከርካሪዉን በማንኛዉም መንገድ ላይ ለማንቀሳቀስ ምዝገባ በማካሄድ አግባብነት ካለዉ አካል የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር መቀበል አለበት፡፡

5. <u>ምዝገባና የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር የሚያስፈልጋቸው ተሽከርካሪዎች</u>

የሚከተሉት ተሽከርካሪዎች የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተርና ምዝገባ አያስፈልጋቸዉም፡-

1. በመዝገብ የተያዙ ተሽከርካሪዎች፤
2. በኢንተርናሽናል ትራፊክ ሥራ ላይ የተሰማሩ ተሽከርካሪዎች፤
3. ከፍተኛ ፍጥነታቸው በሰዓት ከ20 ኪሎ ሜትር የማይበልጥ ልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያዎች፤
4. የአካል ጉዳተኛ ጋሪዎች፡፡

6. <u>ለምዝገባና ለባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>

1. ከውጭ ወደ አገር ውስጥ የገባ ተሽከርካሪን በሚመለከት አግባብነት ላለው አካል የሚቀርብ የምዝገባና የባለንብረት መታውቂያ ደብተር ማመልከቻ ከተሽከርካሪው የጉምሩክ ዲክላራሲዮንና ከሌሎች አስፈላጊ ሰነዶች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

2. በአገር ውስጥ የተሰራ አዲስ ተሽከርካሪን በሚመለከት አግባብነት ላለው አካል የሚቀርብ የምዝገባና የባለንብረት መታወቂያ ደብተር ማመልከቻ ተሽከርካሪው ከተገዛበት ኢንቮይስና ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡
3. ተሽከርካሪ በግዥ፣ በስጦታ፣ በውርስ ወይም በማናቸውም ሁኔታ የተላለፈለት ማንኛውም ሰው የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተሩ በስሙ እንዲዛወርለት በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ አግባብነት ላለው አካል ማመልከት አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ መሠረት የሚቀርበው ማመልከቻ ተሽከርካሪውን በሚመለክት ቀደም ሲል ተሰጥቶ ከነበረው የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተርና የዝውውሩን ሕጋዊነት ለማስረዳት በሚመለከተው አካል ከተሰጠ ወይም ከተረጋገጠ ሰነድ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

7. <u>ተሽከርካሪን ስለመመዝገብና የባለንብረትነት ደብተር ስለመስጠት</u>

1. አግባብነት ያለው አካል በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 መሠረት የቀረበለትን ማመልከቻ ትክክለኛነትና የተሽከርካሪውን የቴክኒክ ብቃትና ለተመዘገበበት አገልግሎት ምቹ መሆኑን ካረጋገጠና የተወሰነው የአገልግሎት ክፍያ ከተፈጸመ በኋላ፣ የሚከተሉትን የተሽከርካሪውን ዝርዝር መግለጫ በኦፊስዩል መዝገብ ውስጥ አስፍሮ የቀረቡለትን ሰነዶች ሁሉ አያይዞ ያስቀምጣል፡-
   ሀ) የባለንብረቱን ስምና አድራሻ፤
   ለ) የሻንሲ ቁጥሩንና የምርቱን ዘመን፤
   ሐ) የሞተሩን ቁጥርና የምርቱን ዘመን፤
   መ) የወንበሩን ብዛት ወይም የመጫን አቅሙን፣ ቁመቱንና ርዝመቱን፤
   ሠ) ቀለሙን፤
   ረ) ቀረጥ መከፈሉን ወይም አለመከፈሉን፤ እና
   ሰ) ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን።
2. አግባብነት ያለው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ተሽከርካሪን እንደመዘገበ ለአመልካቹ የባለንብረት መታወቂያ ደብተር ይሰጠዋል፡፡

8. <u>ስለምዝገባ ለውጥና የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተርን ስለማሳረምና ስለመተካት</u>

1. በኦፊስዮል መዝገብ ውስጥ ወይም በባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር ላይ ከሰፈሩት መግለጫዎች መካከል የተሳሳተ ነገር መኖሩን ባለቤቱ ሰነዱ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በሠላሳ ቀናት ውስጥ ስህተቱን አግባብነት ላለው አካል ማሳወቅና

ደብተሩን ለእርምት ማቅረብ አለበት፡፡ ይህም ሲሆን ስህተቱ ያጋጠመው አግባብነት ባለው አካል ጥፋት ብቻ ካልሆነ በስተቀር ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ ባለንብረቱ ይፈጽማል፡፡

2. በኦፊስዮል መዝገቡ ውስጥና በባለንብረትነት መታወቂያ ደብተሩ ላይ በሰፈሩት መግለጫዎች ላይ ለውጥ ሲያጋጥም ምዝገባው እንዲስተካከልና ደብተሩ በዚሁ መሠረት እንዲሻሻል ባለቤቱ በሠላሳ ቀናት ውስጥ ደብተሩን ማቅረብ አለበት፡፡ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያም ይፈጽማል፡፡
3. የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር የጠፋ፣ የተበላሸ ወይም የማይነበብ የሆነ እንደሆነ ባለቤቱ ምትክ ደብተር እንዲሰጠው ወዲያው አግባብነት ላለው አካል ማመልከት አለበት፡፡
4. አግባብነት ያለው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ መሠረት ማመልከቻ ሲቀርብለት አመልካቹ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ እንዲፈጽም በማድረግ በጠፋው ምትክ ደብተር ይሰጠዋል።
5. ጠፍቶ የነበረና ምትክ የተሰጠበትን የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር መልሶ ያገኘ ሰው ተጨማሪ የሆነው የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር እንዲሰረዝና እንዲወገድ ወዲያው አግባብነት ላለው አካል ማስረከብ አለበት፡፡

9. <u>የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተርን ስለመመለስ</u>

ማንኛውም ተሽከርካሪ ከአገር እንዲወጣ ወይም እንዲወላልቅ ወይም ጨርሶ በመንገድ ላይ እንዳይንቀሳቀስ በተደረገ በ30 ቀናት ውስጥ ባለንብረቱ ወይም ባለይዞታው የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተሩ እንዲሰረዝ አግባብነት ላለው አካል መልሶ ማስረከብ አለበት፡፡

## ክፍልሦስት

## ስለመለያ ቁጥር ሰሌዳዎች

## ንዑስ ክፍል አንድ

## የወል ድንጋጌዎች

10. <u>የመለያ ቁጥር ሰሌዳ አስፈላጊነት</u>

ማናቸውም ተሽከርካሪ አግባብነት ባለው አካል የተሰጠ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ካልተለጠፈለት በስተቀር በማንኛውም መንገድ ላይ እንዲንቀሳቀስ ሊደረግ አይችልም፡፡

11.**<u>የመለያ ቁጥር ሰሌዳ የማያስፈልጋቸው ተሽከርካሪዎች</u>**

የሚከተሉትን ተሽከርካሪዎች በሚመለከት የዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 ድንጋጌ ተፈጻሚ አይሆንም፡-

1. በኢንተርናሽናል ትራፊክ ሥራ ላይ የተሰማሩ ተሽከርካሪዎች፤
2. ከፍተኛ ፍጥነታቸው በሰዓት ከ20 ኪሎ ሜትር የማይበልጥ ልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያዎች፤
3. የአካል ጉዳተኛ ጋሪዎች፡፡

12.**<u>የመለያ ቁጥር ሰሌዳ እንዲታይ ስለማድረግ</u>**

1. የመለያ ቁጥር ሰሌዳ በሚከተለው አኳኋን ተለጥፎ እንዲታይ መደረግ አለበት፡
   ሀ) ለሞተር ብስክሌት ሲሆን፤ በሞተር ብስክሌቱ የኋላ አግዳሚ ዘንግ ላይ በዘጠና ዲግሪ ማዕዘን፤
   ለ) ለባለሞተር ተሽከርካሪ ሲሆን በተሽከርካሪው የፊትና የኋላ አግዳሚ ዘንግ ላይ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው ቦታ በዘጠና ዲግሪ ማዕዘን፤
   ሐ) ለተሣቢ ሲሆን በተሳቢው የኋላ አግዳሚ ዘንግ ላይ ለዚሁ ተብሎ በተዘ ጋጀው ቦታ በዘጠና ዲግሪ ማዕዘን።
2. የማንኛውም ተሽከርካሪ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ጎልቶ እንዲታይና ከዕይታ እንዳይከለል መደረግ አለበት፡፡

13.**<u>የመለያ ቁጥር ሰሌዳን ስለመለወጥና ስለመተካት</u>**

1. የመለያ ቁጥር ሰሌዳን የቀለም ኅብር፣ የፊደል ጥምረት ወይም ማናቸውም ሌላ ምልክት በተመለከተ ግድፈት መኖሩን የተሽከርካሪው ባለቤት ወይም ባለይዞታ ሠሌዳው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በአሥር ቀናት ውስጥ የመለያ ቁጥር ሰሌዳው በትክክለኛው ሰሌዳ እንዲለወጥ አግባብነት ላለው አካል ማቅረብ አለበት፡፡ ይህም ሲሆን ግድፈቱ ያጋጠመው አግባብነት ባለው አካል ጥፋት ምክንያትነት ብቻ ካልሆነ በስተቀር ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ ባለንብረቱ ወይም ባለይዞታው ይፈጽማል፡፡
2. የመለያ ቁጥር ሰሌዳ የጠፋ፣ የተበላሸ ወይም የማይነበብ የሆነ እንደሆነ የተሽከርካሪው ባለቤት ወይም ባለይዞታ ምትክ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ እንዲሰጠው ወዲያው አግባብነት ላለው አካል ማመልከት አለበት፡፡

3. አግባብነት ያለው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት ማመልከቻ ሲቀርብለት አመልካቹ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ እንዲፈጽም በማድረግ ምትክ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ይሰጠዋል፡፡
4. ጠፍቶ የነበረና ምትክ የተሰጠበትን የመለያ ቁጥር ሰሌዳ መልሶ ያገኘ ሰው ተጨማሪ የሆነው ሰሌዳ እንዲወገድ አግባብነት ላለው አካል ማስረከብ አለበት፡፡

14.<u>ስለመለያ ቁጥር ሰሌዳ አለመኖር</u>

1. የተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሰሌዳ አለመኖር የተሽከርካሪው ባለንብረትነት በሚገባ ያልተረጋገጠ ለመሆኑ መነሻ ግምት ያስወስዳል። የተሽከርካሪውን ባለንብረትነት በሚገባ የማረጋገጥ ተግባርም የተሽከርካሪው ባለይዞታ ይሆናል።
2. ማንኛውም ተሽከርካሪ ትክክለኛ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ሳይደረግበት በማንኛውም መንገድ ላይ የተንቀሳቀሰ እንደሆነ የባለንብረትነቱ ሁኔታ በሚገባ እስኪጣራ ድረስ አግባብ ያለው ሕግ የማስከበር ሥልጣን የተሰጠው አካል ተሽከርካሪውን ይዞ ማቆየት ይችላል።

15.<u>የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ዓይነቶችና ምልክቶች</u>

1. አግባብነት ባለው አካል የሚሰጡ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ዓይነቶችና ምልክቶች ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ በተመለከተው መሠረት ይሆናል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ይዘት፣ ቅርጽ እና ሚስጥራዊ ምልክቶች በባለሥልጣኑ ይወሰናሉ፡፡

## <u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለቋሚ የመለያ ቁጥር ሰሌዳዎች</u>

16.<u>ቋሚ የመለያ ቁጥር ሰሌዳዎች ስለመስጠት</u>

አግባብነት ያለው አካል በዚህ አዋጅ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/፣ /2/ ወይም /3/ መሠረት በቀረበ ማመልከቻ ላይ ተመሥርቶ የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር በሚሰጥበት ወቅት ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ለተሽከርካሪው የሚያስፈልገውን ያህል ቋሚ የመለያ ቁጥር ሰሌዳዎች መስጠት አለበት፡፡

17.**ቋሚ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ**

ማንኛውም ቋሚ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13 መሠረት እንዲለወጥ ወይም እንዲተካ ካልተደረገ በስተቀር ተሽከርካሪው እንዲወላልቅ ወይም ጨርሶ በመንገድ ላይ እንዳይንቀሳቀስ እስከሚደረግበት ጊዜ ድረስ ጸንቶ ይቆያል፡፡

18.**ቋሚ የመለያ ቁጥር ሰሌዳዎችን ስለመመለስ**

ማንኛውም ቋሚ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 የተመለከተው ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ ሲያበቃ ወይም የተሽከርካሪው ምዝገባ ሲሰረዝ የተሽከርካሪው ባለቤት ወይም ባለይዞታ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 መሠረት ከሚመለሰው የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር ጋር አግባብነት ላለው አካል ማስረከብ አለበት፡

**ንዑስ ክፍል ሦስት**

**ዕለታዊ የመለያ ቁጥር ሰሌዳዎች**

19.**ዕለታዊ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ስለመስጠት**

ቋሚ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16 መሠረት ከባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር ጋር መሰጠት የማይቻልበት ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር ከመሰጠቱ በፊት ተሽከርካሪውን በማንኛውም መንገድ ላይ ለማንቀሳቀስ የሚያስገድድ ምክንያት ሲኖር አግባብነት ያለው አካል ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ለተሽከርካሪው የሚያስፈልገውን ያህል ዕለታዊ የመለያ ቁጥር ሰሌዳዎች ከጊዜያዊ ማንቀሳቀሻ ፈቃድ ጋር መስጠት ይችላል፡፡

20.**ዕለታዊ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ**

1. ዕለታዊ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ጸንቶ የሚቆየው ከተሰጠበት ቀን አንስቶ ለ15 ቀናት ይሆናል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ ቢኖርም የተወሰነው የአገልግሎት ክፍያ ተከፍሎ ለ15 ቀናት ሁለት ጊዜ እንዲራዘም አግባብነት ያለው አካል ሊፈቅድ ይችላል።
3. የዕለት መለያ ቁጥር ሰሌዳ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ እንዳበቃ ወይም ጊዜው ከማብቃቱ በፊት ለተሽከርካሪው ቋሚ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ከተሰጠ የተሽከርካሪው ባለንብረት ወይም ባለይዞታ ሰሌዳውን አግባብነት ላለው አካል ወዲያውኑ ማስረከብ አለበት፡፡

## ንዑስ ክፍል አራት

## ተላላፊ የመለያ ቁጥር ሰሌዳዎች

### 21.የተላላፊ መለያ ቁጥር ሰሌዳ አጠቃቀም

1. ተላላፊ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ የሚያገለግለው በተሽከርካሪ ባለፋብሪካ፣ ነጋዴ ወይም ዳግም ሠሪ መዝገብ ለተያዙ ተሽከርካሪዎች ብቻ በማለዋወጥ እንዲሰራበት ነው፡፡
2. ተላላፊ ሰሌዳ የተደረገበት ተሽከርካሪ በማንኛውም መንገድ ላይ ሊንቀሳቀስ የሚችለው ለሚከተሉት ጉዳዮች ብቻ ነው፦
   ሀ) ከገባበት ወደብ ወይም ከተገዛበት ሥፍራ ወደ ንግድ ሥፍራ ለማዛወር፤
   ለ) አልፎ አልፎ ከመጋዘን ወደ ማሳያ ክፍል ወይም ለሽያጭ ወደ ሚቀርብበት ሥፍራ ለመውሰድና ወደ መጋዘን ለመመለስ፤
   ሐ) ለፍተሻ ወይም ለማሳያ ከሃያ አምስት ኪሎ ሜትር ለማይበልጥ የደርሶ መልስ ርቀት ለሚደረግ መንዳት፤
   መ) ከንግድ ሥፍራ ለገዥ ወይም ለተላለፈለት ሌላ ሰው ወደማስረከቢያ ስፍራ ለማድረስ፤ ወይም
   ሠ) ወደ ምርመራና ምዝገባ ቦታ ለማድረስ፡፡
3. የተሽከርካሪ ባለፋብሪካ ነጋዴ ወይም ዳግም ሰሪ መገልገያ በሆኑ ተሽከርካሪዎች ላይ ምንጊዜም ቢሆን ተላላፊ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ አይደረግም፡፡

### 22.ተላላፊ የመለያ ቁጥር ሰሌዳዎች ስለመስጠት

1. ማናቸውም የተሽከርካሪ ባለፋብሪካ፣ ነጋዴ ወይም ዳግም ሰሪ ተላላፊ የመለያ ቁጥር ሰሌዳዎች እንዲሰጡት ሲፈልግ ማመልከቻውን በተባለው ሥራ ላይ እንዲሰማራ ከተሰጠው ፈቃድ ቅጅ ጋር አያይዞ አግባብነት ላለው አካል ማቅረብ አለበት፡፡
2. አግባብነት ያለው አካል የቀረበለት ማመልከቻና የተያያዘው የፈቃድ ቅጅ እውነተኛና ትክክለኛ መሆኑን ሲያረጋግጥ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ አስከፍሎ የተጠየቁትን ተላላፊ የመለያ ቁጥር ሰሌዳዎች ለአመልካቹ ይሰጠዋል፡፡

23.**ተላላፊ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ**

1. ተላላፊ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ጸንቶ የሚቆየው ከተሰጠበት ቀን አንስቶ ለአንድ ዓመት ብቻ ነው፡፡
2. ተላላፊ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ እንዲራዘም ሲጠየቅ አግባብነት ያለው አካል በእያንዳንዱ የዕድሳት ዘመን ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ እያስከፈለ ለአንድ ዓመት ሊያራዝመው ይችላል።

24.**ስለተላላፊ የመለያ ቁጥር ሰሌዳዎች አጠቃቀም መዝገብ**

1. ተላላፊ የመለያ ቁጥር ሰሌዳዎች የተሰጡት ማንኛውም የተሽከርካሪ ባለፋብሪካ ነጋዴ ወይም ዳግም ሰሪ ሰሌዳዎቹ በጥቅም ላይ የዋሉባቸውን ተሽከርካሪዎች በሚመለከት አግባብነት ባለው አካል በተወሰነው አኳኋን መዝግቦ መያዝና በየወሩ አግባብነት ላለው አካል ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተውን መዝገብ ማንኛውም የተፈቀደለት አግባብነት ያለው አካል ሰራተኛ ወይም የትራፊክ ፖሊስ ለምርመራ ሊያየው ይችላል፡፡

**ክፍል አራት**

**ዓመታዊ የተሽከርካሪ ምርመራ**

25.**ዓመታዊ ምርመራ ስለማስፈለጉ**

ማናቸውም ተሽከርካሪ የቴክኒክ ምርመራ አድርጎ ዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት ካልተደረገበት በስተቀር በማንኛውም መንገድ ላይ ሊንቀሳቀስ አይችልም፡፡

26.**ዓመታዊ ምርመራ ስለማያስፈልጋቸው ተሽከርካሪዎች**

የሚከተሉት ተሽከርካሪዎች ዓመታዊ ምርመራ አያስፈልጋቸውም፡-

1. በኢንተርናሽናል ትራፊክ የተሰማሩ ተሽከርካሪዎች፤
2. በመዝገብ የተያዙ ተሽከርካሪዎች፤
3. ከፍተኛ ፍጥነታቸው በሰዓት ከ20 ኪሎ ሜትር የማይበልጥ ልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያዎች፤ እና
4. የአካል ጉዳተኛ ጋሪዎች፡፡

27.**ተሽከርካሪዎችን ለምርመራ ስለማቅረብ**

1. የተሽከርካሪ ባለንብረት ወይም ባለይዞታ ተሽከርካሪውን በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ለዓመታዊ የተሽከርካሪ ምርመራ ማቅረብ አለበት፡፡

2. ማንኛውም አመልካች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ተሽከርካሪውን በመመርመሪያ ጊዜ ለምርመራ ማቅረብ የማያስችለው በቂ ምክንያት ሲያጋጥመው አግባብነት ያለው አካል ለምርመራ የማቅረቢያ ጊዜውን ከሁለት ወር ላልበለጠ ጊዜ ሊያራዝምለት ይችላል፡፡

28.<u>የምርመራ ጣቢያዎች</u>

1. አግባብነት ባለው አካል የተቋቋመ የምርመራ ጣቢያ ወይም አግባብነት ባለው አካል ውክልና የተሰጠው ድርጅት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 29 በተደነገገው የምርመራ መሥፈርቶች መሠረት የተሽከርካሪ ዓመታዊ ምርመራ ማካሄድ አለበት።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ውክልና የተሰጠው ድርጅት የምርመራ መሥፈርቶችን በሚገባ ተከትሎ ዓመታዊ የተሽከርካሪ ምርመራ እንዲካሄድ ካላደረገ አግባብነት ካለው አካል ጋር በገባው የውክልና ስምምነት መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

29.<u>ስለምርመራ መሥፈርቶች</u>

1. በምርመራ ጣቢያዎች ምርመራ ለማካሄድ ሥልጣን የተሰጠው መርማሪ የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላታቸውን ለማረጋገጥ እያንዳንዱን ተሽከርካሪ መመርመር አለበት፡-
   ሀ) ተሽከርካሪውን ለመለየት በአካሉ፣ በሻንሲው ወይም በሞተሩ ላይ በፋብሪካው የተጻፉትና በባለንብረትነት መታወቂያ ደብተሩ መግለጫዎች ወይም በመዝገብ ላይ የተጠቀሱት ቁጥሮችና ፊደሎች ትክክለኛ መሆናቸውን፤
   ለ) ተሽከርካሪው ለተመዘገበበት ዓላማ አደጋን በማያስከትል አኳኋን በመንገድ ላይ ሊንቀሳቀስ የሚችል መሆኑን፤
   ሐ) ተሽከርካሪው በሕግ መሠረት የተወሰኑትን የተሽከርካሪ አሰራር፣ መሣሪያዎች፣ መጠንና ክብደትን የሚያሟላና ለተመዘገበበት አገልግሎት ምቹ መሆኑን፤ እና
   መ) አግባብ ባለው ህግ መሠረት ስለአካባቢ ብክለት መከላከል የወጣውን መስፈርት ያሟላ መሆኑን፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ ተጨማሪ የምርመራ መስፈርቶችንና የዚህን አንቀጽ አፈጻጸም በሚመለከት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

30.**<u>የምርመራ ምስክር ወረቀት</u>**

ሥልጣን የተሰጠው መርማሪ የሚፈልግበትን የምርመራ መስፈርት በሙሉ ማሟላቱን ካረጋገጠ በኋላ የምርመራ ምስክር ወረቀት ወዲያውኑ ይሰጣል።

31.**<u>የምርመራ ምስክር ወረቀት ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ</u>**

1. የምርመራ የምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለአንድ ዓመት ጸንቶ ይቆያል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ ቢኖርም የመመዝገቢያ ጊዜውን አሳልፎ የቀረበ ተሽከርካሪን በሚመለከት የሚሰጥ የምርመራ የምስክር ወረቀት ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ከመደበኛው የመመርመሪያ የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ይሆናል።

32.**<u>ዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት ስለመስጠት</u>**

1. አግባብነት ያለው አካል ለዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት ማመልከቻ ሲቀርብለት፡-
   ሀ) ማመልከቻውን ከኦፊሲዬል መዝገቡና ከሰነዶቹ ጋር ያመሳክራል፤
   ለ) በማመልከቻው ላይ የተመለከቱትን የመለያ ቁጥሮች በተሰረቁና በተለወጡ ተሽከርካሪዎች ዝርዝር ውስጥ ካሉ ቁጥሮች ጋር ያስተያያል፤
   ሐ) አመልካቹ የተሽከርካሪው እውነተኛ ባለንብረት ወይም ባለይዞታ መሆኑን ወይም የዚህ ዓይነቱ ሰው ሕጋዊ ወኪል መሆኑን ያረጋግጣል፡፡
2. አግባብነት ያለው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ በተመለከተው ምርመራ ውጤትና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 30 መሠረት የተሰጠን የተሽከርካሪ ምርመራ የምስክር ወረቀት መሠረት በማድረግ እና ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ተሽከርካሪውን በሚመለከት ዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት ለአመልካቹ ይሰጣል፡፡

## 33.ዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት እንዲታይ ስለማድረግ

1. ለባለሞተር ተሽከርካሪ የተሰጠ ዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት በተሽከርካሪው የፊት መስታወት በታችኛው የቀኝ ማዕዘን ላይ ተለጥፎ መታየት አለበት፡፡
2. የፊት መስተዋት ለሌለው ባለሞተር ተሽከርካሪ የተሰጠ ዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት ተሽከርካሪው በማንኛውም መንገድ ላይ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ በተሽከርካሪው ውስጥ መቀመጥና በትራፊክ ፖሊስ ሲጠየቅ እንዲታይ መደረግ አለበት፡፡
3. ለተሳቢ የተሰጠ ዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት ተሳቢውን ለሚጎትተው ባለሞተር ተሽከርካሪ ከተሰጠው ዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት ጎን ለጎን ተለጥፎ መታየት አለበት፡፡

## 34.ዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክትን ስለማሳረም እና ስለመተካት

1. በዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት ላይ ከሰፈሩት መግለጫዎች መካከል የተሳሳተ ነገር መኖሩን የተሽከርካሪው ባለቤት ወይም ባለይዞታ ተለጣፊው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በአስር ቀናት ውስጥ ተለጣፊ ምልክቱን ለእርምት አግባብ ላለው አካል ማቅረብ አለበት፡፡ ይህም ሲሆን ስህተቱ ያጋጠመው አግባብ ባለው አካል ጥፋት ምክንያትነት ብቻ ካልሆነ በስተቀር ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ ባለንብረቱ ወይም ባለይዞታው ይፈጽማል፡፡
2. በዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት ላይ በሰፈሩት መግለጫዎች ላይ ለውጥ ሲያጋጥም ተለጣፊ ምልክቱ በዚሁ መሠረት እንዲሻሻል የተሽከርካሪው ባለቤት ወይም ባለይዞታ በአስር ቀናት ውስጥ ተለጣፊ ምልክቱን አግባብ ላለው አካል ማቅረብ አለበት፡፡ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያም ባለንብረቱ ወይም ባለይዞታው ይፈጽማል፡፡
3. ዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት የጠፋ፣ የተበላሸ ወይም የማይነበብ የሆነ እንደሆነ የተሽከርካሪው ባለቤት ወይም ባለይዞታ ምትክ ተለጣፊ ምልክት እንዲሰጠው ወዲያውኑ አግባብ ላለው አካል ማመልከት አለበት፡፡
4. አግባብ ያለው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ መሠረት ማመልከቻ ሲቀርብለት አመልካቹ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ እንዲፈጽም ካደረገ በኋላ ምትክ ዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት ይሰጠዋል፡፡

5. ጠፍቶ የነበረና ምትክ የተሰጠበትን ዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት መልሶ ያገኘ ሰው ተጨማሪ የሆነው ዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት እንዲሰረዝና እንዲወገድ ወዲያውኑ አግባብ ላለው አካል ማስረከብ አለበት፡፡

35.<u>ዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ ለተለጣፊ ምልክቱ መሰጠት መሠረት የሆነው የምርመራ ምስክር ወረቀት ጸንቶ ከሚቆይበት ጊዜ ጋር ተመሳሳይ ይሆናል፡፡

36.<u>ዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት አለመኖር</u>

1. ዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት አለመኖር ተሽከርካሪው ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ አለማድረጉን መነሻ ግምት ያስወስዳል፡፡ ተሽከርካሪው መመርመሩን የማስረዳቱ ተግባርም የተሽከርካሪው ባለንብረት ወይም የባለይዞታ ይሆናል፡፡
2. ማንኛውም ተሽከርካሪ የዚህን አዋጅ አንቀጽ 33 በመተላለፍ በማንኛውም መንገድ ላይ እንዲንቀሳቀስ ከተደረገ የመመርመሩ ሁኔታ በሚገባ እስኪጣራ ድረስ አግባብ ያለው ሕግ የማስከበር ሥልጣን የተሰጠው አካል ተሽከርካሪውን ይዞ ማቆየት ይችላል፡፡

37.<u>ስለልዩ ምርመራ</u>

1. ማንኛውም ተሽከርካሪ የዚህን አዋጅ አንቀጽ 30 ድንጋጌ የሚያሟላ ቢሆንም አግባብነት ያለው አካል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ልዩ ምርመራ ሊያደርግበት ይችላል፡፡
2. ማንኛውም ተሽከርካሪ፡-

   ሀ) በመንገድ ላይ ለማገልገል ብቁ አለመሆኑ፤

   ለ) አሰራሩ፣ መሣሪያዎቹ፣ መጠኑ ወይም ክብደቱ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የተወሰኑትን ደረጃዎች የማያሟላ መሆኑ፤ ወይም

   ሐ) በአደጋ ምክንያት ከባድ ጉዳት የደረሰበት መሆኑ፤

   በግልጽ የሚታይ ሲሆን አግባብ ያለው ሕግ የማስከበር ሥልጣን የተሰጠው አካል ተሽከርካሪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ለሚደረግ ልዩ ምርመራ እንዲቀርብ ሊያስገድድ ይችላል።
3. በዚህ አንቀጽ መሠረት ለሚደረግ የተሽከርካሪ ልዩ ምርመራ የአገልግሎት ክፍያ አይጠየቅም፡፡

## ክፍል አምስት

## ስለተሽከርካሪዎች ኦፊሲዬል መዝገብና ሰነዶች

### 38. ኦፊሲዬል መዝገብና ሰነዶች ስለመያዝ

አግባብነት ያለው አካል ባለንብረትነታቸው የታወቀና የተመዘገቡ ተሽከርካሪዎችን በሚመለከት ኦፊሲዬል መዝገብና ሰነዶች እንዲሁም የዓመቱን የተጠቃለለ የተሽከርካሪዎች ዝርዝር አደራጅቶ በሚገባ ይይዛል።

### 39. የተሰረቁ ወይም የተለወጡ ተሽከርካሪዎች ዝርዝር

1. አግባብነት ያለው አካል የተሰረቁ፣ የተለወጡ፣ ጠፍተው የተገኙና ባለንብረቱ ያልተገኘ ተሽከርካሪዎችን የተጠቃለለ ዝርዝር አደራጅቶ በሚገባ ይይዛል፤ ሲጠየቅም ለሚመለከተው አካል ይሰጣል፡፡
2. አግባብነት ያለው አካል አስፈላጊና ተገቢ መስሎ ሲያገኘው በማናቸውም ጋዜጣ ዝርዝሩን ሊያሳትም ይችላል።

### 40. በኦፊሲዬል መዝገብና ሰነዶች የተያዘን መረጃ ስለማግኘት መብት

1. ማንኛውም ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው በኦፊሲዬል መዝገብና ሰነዶች ውስጥ ያለን መረጃ ለማየት ወይም የተረጋገጠ ቅጅው እንዲሰጠው ሲጠይቅ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ አስከፍሎ መረጃውን እንዲያይ ወይም ቅጅው እንዲሰጠዉ ያደርጋል፡፡
2. ማንኛውም የሕግ አስፈጻሚ አካል ለሥራው አፈጻጸም የሚያስፈልገውን መረጃ ለማየት ወይም ቅጅው እንዲሰጠው ሲጠይቅ የአገልግሎት ክፍያ አይጠየቅም፡፡

### 41. ቀደምትነት ስለሚኖረው ማስረጃ

1. በኦፊሲዬል ሰነድነት የተያዙ ማመልከቻዎች፣ ደብዳቤዎችና ቅጾች እንዲሁም በኦፊሲዬል መዝገብ ላይ የሰፈሩ መግለጫዎች ለተመዘገቡት ጉዳዮች መነሻ ማስረጃ ይሆናሉ፡፡
2. የባለንብረትነት መብት በተላለፈላቸው ሰዎች መካከል ክርክር በሚነሳበት ጊዜ ቀደምትነት ያለው ማስረጃ የሚወሰነው የባለንብረትነት መታወቂያ ደብተር በተሰጠበት ቀን ቅደም ተከተል ላይ ተመሥርቶ ይሆናል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 42.የተከለከሉ ተግባሮች

ማንኛውም ሰው፦

1. አግባብነት ካለው አካል የጽሑፍ ፈቃድ ሳይኖረው ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ከተመለከቱት ሌላ የቀለም ኅብር፣ የፊደል ጣምራ ወይም ምልክቶች ለተሽከርካሪው መለያ ቁጥር ሰሌዳ መጠቀም፤
2. በተሽከርካሪው መለያ ቁጥር ሰሌዳና አካባቢው ማስታወቂያዎችን ወይም ሌሎች ምልክቶችን መለጠፍ፤
3. ለተሽከርካሪው በፋብሪካው ከተገጠመለት መደበኛ መብራት ተጨማሪ መብራት ማስገባት፤
4. የነጂውን የማየት ችሎታ በሚያውክ ሁኔታ አሻንጉሊቶችን ወይም ሌሎች ጌጣጌጦችን ማስቀመጥ፤ ወይም
5. አግባብነት ካለው አካል አስቀድሞ ሳያስፈቅድ በባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ላይ የሰፈሩ መረጃዎችን በተሽከርካሪው አካላት ላይ መቀየር ወይም ተሽከርካሪውን መበተን፤ አይችልም፡፡

### 43.የማስጠንቀቂያ ምልክቶች

አግባብነት ያለው አካል እንደአስፈላጊነቱ በማንኛውም ተሽከርካሪ ላይ አንፀባራቂ የሆኑ ማስጠንቀቂያ ምልክቶች እንዲደረጉ ሊያዝ ይችላል፡፡

### 44.ስለሰሌዳ ሥራ እና ቁጥር አፃፃፍ

ባለሥልጣኑ ሰሌዳ አምርቶ የማሰራጨት ተግባሩ እንደተጠበቀ ሆኖ ተፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተጨማሪ ፊደላትና ቁጥሮች ያለው ሰሌዳ በሥራ ላይ ማዋል ይችላል።

### 45.ስለመከላከያ ኃይል ተሽከርካሪዎች

1. ለመከላከያ ኃይል ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር፣ የመለያ ቁጥር ሰሌዳዎችና ዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት የሚሰጠው በአገር መከላከያ ሚኒስቴር ይሆናል።
2. ለመከላከያ ኃይል ተሽከርካሪዎች የሚሰጠው የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ከተመለከቱት የቀለም ሕብር፣ የፊደል ጣምራና ምልክቶች የተለየ መሆን አለበት።

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ እና /2/ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ይህ አዋጅ እንደአግባብነቱ ለመከላከያ ኃይል ተሽከርካሪዎች ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

46.<u>በኢንተርናሽናል ትራፊክ ስለተሰማራ ተሽከርካሪ</u>

በአገሮች መካከል የሚደረግ የጋራ መጠቃቀም መርህ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከባለሥልጣኑ የተሰጠ ጊዜያዊ የማንቀሳቀሻ ፈቃድ ካልኖረ በስተቀር ማንኛውንም በኢንተርናሽናል ትራፊክ የተሰማራ ተሽከርካሪን በኢትዮጵያ መንገዶች ላይ ማንቀሳቀስ የሚቻለው አገር ውስጥ ከገባበት ቀን ጀምሮ ከአንድ ወር ላልበለጠ ጊዜ ብቻ ነው፡፡

47.<u>የተሽከርካሪ መመርመሪያና መመዝገቢያ ክፍያ</u>

ለተሽከርካሪ መመርመሪያ፣ መመዝገቢያና ተያያዥነት ላላቸው አገልግሎቶች የሚጠየቀው ክፍያ፡-

1. ባለሥልጣኑ የሚመዘግባቸውን ተሽከርካሪዎች በሚመለከት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ፤
2. በክልል አካላት የሚመዘገቡ ተሽከርካሪዎችን በሚመለከት በየክልሉ በሚወጣ ሕግ፤ ይወሰናል፡፡

48.<u>ቅጣት</u>

1. ማንኛውም ሰው፡-
   ሀ) ዓመታዊ ምርመራ ወቅቱን አሳልፎ ተሽከርካሪውን ለምርመራ ካቀረበ ለእያንዳንዱ ለዘገየበት 15 ቀን ብር 100 ይቀጣል፤
   ለ) ዓመታዊ የተሽከርካሪ ምርመራ አድርጎ ምልክቱን ሳይለጥፍ በመንገድ ላይ እንዲሽከረከር ያደረገ ወይም በአንቀጽ 42 /2/፣ /3/ እና /4/ የተጠቀሱትን ክልከላዎች የተላለፈ ብር 200 /ሁለት መቶ ብር/ እንዲሁም የተበላሸ ወይም በሚገባ ሊታይ የማይችል የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ለጥፎ በመንገድ ላይ እንዲሽከረከር ያደረገ ከሆነ ብር 500 /አምስት መቶ ብር/ ይቀጣል፤
   ሐ) ለተሽከርካሪው ዓመታዊ ምርመራ ሳያካሂድ በመንገድ ላይ እንዲሽከረከር ያደረገ ከሆነ ወይም የተሽከርካሪውን ስም ንብረትነቱን በስሙ ማዛወር ሲገባው በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ሳያዛውር የቀረ እንደሆነ ብር 700 /ሰባት መቶ ብር/ ይቀጣል፤

መ/ የተሽከርካሪው አካል ጉድለት ኖሮት እንዲያስተካክል አግባብነት ባለው አካል በጽሑፍ ተገልፆለት እስከ አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ሳያስተካክል እንዲሽከረከር ካደረገ ብር 1,000 /አንድ ሺ ብር/ ይቀጣል።

2. ማንኛውም ሰው፦

ሀ) አንድን ተሽከርካሪ የራሱ ያልሆነ ወይም በማስመሰል የተዘጋጀ ዓመታዊ የምርመራ ምልክት በመለጠፍ በመንገድ ላይ እንዲሽከረከር ያደረገ ከሆነ፤

ለ) አንድን ተሽከርካሪ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ሳይለጠፍበት በመንገድ ላይ እንዲሽከረከር ያደረገ ወይም የራሱ ያልሆነ ወይም በማስመሰል የተዘጋጀ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ለጥፎበት ከተገኘ ወይም በመንገድ ላይ እንዲሽከረከር ያደረገ ከሆነ፤

ሐ) የተሽከርካሪን የሻንሲ ቁጥር፣ የሞተር ቁጥር ወይም የምርት ዘመን ወይም በአንቀፅ 42 /5/ የተክለከሉትን ተግባሮች አግባብነት ላለው አካል ሳያሳውቅ የለወጠ ከሆነ፤ ወይም

መ) በመጥፋቱ ወይም በሌላ ምክንያት በምትክነት የተሰጠ እያለ የቀድሞውን የተሽከርካሪ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር፣ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ወይም ዓመታዊ ተለጣፊ ምልክት መልሶ የተጠቀመ ከሆነ፤

ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ፣ በወንጀል ህግ በተደነገገው መሠረት የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር ከብር 2500 እስከ ብር 5000 በሚደርስ መቀጮ ወይም ከሁለት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

3. የሚፈለግበትን የምርመራ መስፈርት ሙሉ በሙሉ ለማያሟላ ተሽከርካሪ የምርመራ ምስክር ወረቀት የሰጠ ወይም እንዲሰጥ ያደረገ አግባብነት ያለው አካል ወይም ውክልና የተሰጠው ድርጅት ሠራተኛ ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ፣ በወንጀል ህግ በተደነገገው መሠረት የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር እስከ ብር 3,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጮና ከስድስት ወር እስከ ሁለት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ይቀጣል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት አግባብነት ባለው አካል በተጣለበት የገንዘብ መቀጮ ቅር የተሰኘ ሰው በ30 ቀናት ውስጥ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል።

5. መቀጮው የተጣለበት ሰው አግባብነት ያለው አካል ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /4/ መሠረት ይግባኝ አቅርቦ ከሆነ ይግባኙ ውድቅ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ገቢ ሳያደርግ ቢቀር ክፍያው መፈጸሙን የሚያሳይ ደረሰኝ እስኪያቀርብ ድረስ የሚመለከተው ፖሊስ ጥፋቱ የተፈጸመበትን ተሽከርካሪ ይዞ የማቆየት ሥልጣን ይኖረዋል።

**49.ደንብ የማውጣት ሥልጣን**

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።
2. የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር[77] ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**50.ስለ አዋጁ አፈጻጸም**

ባለሥልጣኑ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች በአገር አቀፍ ደረጃ ወጥ በሆነ መንገድ በሥራ ላይ መዋላቸውን ለማረጋገጥ ክትትል ያደርጋል፣ የመመዝገብና የመመርመር ኃላፊነት ለተሰጣቸው የክልል አካላት አስፈላጊውን የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

**51.የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

1. የባለሞተር ተሽከርካሪና የተሣቢ መለያ፣ መመርመሪያና መመዝገቢያ ደንብ ቁጥር 360/1961 /እንደተሻሻለ/ በዚህ አዋጅ ተሽሯል።
2. የዚህን አዋጅ ድንጋጌ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

**52.አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ነሐሴ 5 ቀን 2002 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

---

[77] 25/08 (2011) አ. 1097 አንቀጽ 9(9) የትራንስፖርት ሚንስቴር ሆኗል፡፡

## ደንብ ቁጥር 205/2003

## ብሔራዊ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ምክር ቤትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/1997 አንቀጽ 28 መሠረት ይህን ደንብ አዉጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ በብሔራዊ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ምክር ቤት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 205/2003 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

   1. በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/1997 አንቀጽ 2 የተመለከተው ትርጓሜ ተፈጻሚ ይሆናል፤
   2. “የመንገድ ትራፊክ ደህንነት” ማለት የመንገድ ተጠቃሚዎችና ማናቸውም ሀብት ከትራፊክ አደጋ የሚጠበቁበት ሁኔታ ነው፤
   3. “ሚኒስቴር” ማለት የትራንስፖርት ሚኒስቴር ነዉ፡፡

3. **መቋቋም**

   1. ብሔራዊ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ “ምክር ቤት” እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
   2. ምክር ቤቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

4. **ዓላማ**

   የምክር ቤቱ ዓላማ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ስልቶችን በመቀየስ ለተግባራዊነቱ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላትን ማስተባበር ይሆናል፡፡

5. **የምክር ቤቱ ስልጣንና ተግባር**

   ምክር ቤቱ በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 የተመለከተውን ዓላማ እውን ለማድረግ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

   1. ብሔራዊ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ዕቅዶችንና ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት፤

2. የመንገድ ትራፊክ ደህንነትን ለማሻሻል የሚመለከታቸው አካላትን ተሳትፎ ማጠናከር፣ የመንገድ ትራፊክ አደጋን ለመቀነስ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ተቀናጅቶና የበለጠ ውጤታማ ሆኖ እንዲከናወን ማስተባበርና ድጋፍ መስጠት፣
3. መንገድን፣ተሽከርካሪንና የመንገድ ተጠቃሚን የሚመለከቱ በሥራ ላይ ያሉ ህጎች፣ ስታንዳርዶችና መመሪያዎች የመንገድ ትራፊክ አደጋን ከመግታት አኳያ ውጤታማነታቸውን በመገምገም የማሻሻያ ሀሳብ ማቅረብ፣
4. የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ትምህርት በመደበኛና በተጓዳኝ ትምህርት ውስጥ እንዲጠናከር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር መተባበርና እንደአስፈላጊነቱ ድጋፍ መስጠት፣
5. የመንገድ ትራፊክ አደጋን ለመግታት የሚያስችሉ መድረኮች እንዲካሄዱ ሁኔታዎችን ማመቻቸትና ማካሄድ፣
6. የመንገድ ትራፊክ ደህንነትን ለማስፈን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ህብረተሰቡ የሚሳተፍበትን ሁኔታ ማመቻቸትና የብዙሃን መገናኛ ተሳትፎን ማጠናከርና እገዛ ማድረግ፣
7. በልዩ ልዩ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት እንቅስቃሴዎች ውስጥ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ እንዲጠናከር ማድረግ፣
8. የሚመለከታቸው አካላት የመንገድ ትራፊክ ደህንነትን ለማረጋገጥ የነደፉትን ስትራቴጂና ፕሮግራም ውጤታማነት በየጊዜው በመከታተልና በመገምገም ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ማቅረብ፣
9. የመንገድ ትራፊክ ደኅንነትን ለማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሚመለከታቸው አካላት የተውጣጡ አባላትን የያዙ የቴክኒክ ኮሚቴዎችን ማቋቋምና እንቅስቃሴዎቻቸውን ማስተባበር፣
10. ዓላማዎቹን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ማከናወን፡፡

6. <u>**የምክር ቤቱ አባላት**</u>

የምክር ቤቱ አባላት ሰብሳቢውን ጨምሮ በመንግስት ይሰየማሉ። ቁጥራቸውም እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል፡፡

7. <u>**የምክር ቤቱ ስብሰባዎች**</u>

1. የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በየስድስት ወሩ ይካሄዳል፣ ሆኖም በሰብሳቢው ጥሪ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል፡፡

2. የምክር ቤቱ አብላጫው አባላት በስብሰባ ሲገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡
3. የምክር ቤቱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

8. **<u>የምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት</u>**

1. ምክር ቤቱ በሚኒስቴሩ ውስጥ የተደራጀ ጽሕፈት ቤት ይኖረዋል፤
2. ጽሕፈት ቤቱ ፡-

ሀ) የምክር ቤቱ ሴክሬታርያት ሆኖ ያገለግላል፤

ለ) የምክር ቤቱን ጉዳዮችና ስብሰባዎች ሪከርድ ይይዛል፤

ሐ) የምክር ቤቱ ውሳኔዎች በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤

መ) በመንገድ ትራፊክ ደህንነት ጥናት በማካሄድ የረጅም ጊዜ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ማሻሻያ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤

ሠ) የፕሮግራሙን አፈጻጸም በመከታተልና በመመዘን የማሻሻያ ሃሳብ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣

ረ) በሚመለከታቸው አካላት የሚቀርቡ የፕሮግራምና ስትራቴጂ አተገባበር ሪፖርቶችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፤

ሰ) የመንገድ ትራፊክ አደጋ መረጃዎችን ይተነትናል፤ የምክር ቤቱን ሥራዎች ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ ሕትመቶችን ያዘጋጃል፤

ሸ) በምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ይፈጽማል።

9. **<u>የመተባበር ግዴታ</u>**

የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና ዕቅዶችን በመተግበር ረገድ ከምክር ቤቱ ጋር የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

10. **<u>መመሪያ የማዉጣት ስልጣን</u>**

ይህንን ደንብ በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሚኒስቴሩ ሊያወጣ ይችላል፡፡

11.<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት 21 ቀን 2003 ዓ.ም.**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ደንብ ቁጥር 206/2003

## የተሽከርካሪ መለያ፣ መመርመሪያና መመዝገቢያ ክፍያ ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በተሽከርካሪ መለያ፣ መመዝገቢያና መመርመሪያ አዋጅ ቁጥር 681/2002 አንቀጽ 47(1) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የተሽከርካሪ መለያ፣ መመርመሪያና መመዝገቢያ ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 206/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በተሽከርካሪ መለያ፣ መመርመሪያና መመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር 681/2002 አንቀጽ 2 የተሠጡ ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

3. **የተፈፃሚነት ወሰን**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን በሚመዘገቡ ተሽከርካሪዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4. **የአገልግሎት ክፍያዎች**

   ለተሽከርካሪ መለያ፣ መመርመሪያ፣ መመዝገቢያና ተያያዥነት ላላቸው አገልግሎቶች የሚጠየቀው ክፍያ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ በተመለከተው መሠረት ይሆናል፡፡

5. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሚያዝያ 6 ቀን 2003 ዓ.ም.**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## ¾›ÑMÓKAƒ ¡õÁ-‹ c”Ö[»

| }.l | ¾›ÑMÓKAƒ ¯A’ƒ | | ¡õÁ (w`) | |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ¾vK"w[ƒ Sታ·¨mÁ Åw}` | | | |
| | 1.1 | KV}` dA¡KA‹ | 8 | 00 |
| | 1.2 | KK?KA‹ }iŸ`"]-‹ | 15 | 00 |
| | 1.3 | ˆ`ˆ Ñ<ÇÄ‹” KTeK¨Ø uእÁ”Ç”Æ Ñ<ÇA | 5 | 00 |
| | 1.4 | uUƒ¡’ƒ c=cØ Ÿª“ ¡õÁ u}ÚT] | 5 | 00 |
| 2 | ¾SKÁ lØ` WK?Ç | | | |
| | 2.1 | ¾°Kƒ cK?Ç (K›”É ¨") | 250 | 00 |
| | 2.2 | sT> WK?Ç KV}` dA¡M c=cØ ¨AU c=}" | 10 | 00 |
| | 2.3 | sT> WK?Ç KK?KA‹ }iŸ`"]-‹ c=cØ ¨AU c=}" | 15 | 00 |
| | 2.4 | }LLò WK?Ç c=cØ ¨AU c=ታÅe (K›”É ¯Sƒ) | 250 | 00 |
| 3 | ¯Sታ© ¾}iŸ`"] U`S^ ¾Ue¡` ¨[kƒ“ ¾U´Ñv }K×ò UM¡ƒ | | | |

| }.l | ¾›ÑMÓKAƒ ¯A’ƒ | | | ¡õÁ (w`) | |
|---|---|---|---|---|---|
| | 3.1 | KV}` dA¡M | | 20 | 00 |
| | 3.2 | KÓM ›¨<„Vu=KA‹“ ¾Q´w TSLKh }iŸ`"]-‹ ¾’Í=¨<” SkSÝ ÚUa& | | | |
| | | G | Ÿ›Ueƒ ¾TAuMØ SkSÝ LL†¨< | 50 | 00 |
| | | G | u}ÚT] uSkSÝ | 3 | ® ® |
| | | K | Ÿ6 እስከ 44 SkSÝ LL†¨< | 65 | 00 |
| | | K | u}ÚT] uSkSÝ | 4 | 00 |
| | | N | Ÿ45 እስከ 64 SkSÝ LL†¨< | 70 | 00 |
| | | N | u}ÚT] uSkSÝ | 4 | 00 |
| | | S | 65 SkSÝ LL†¨< | 80 | 00 |
| | | S | u}ÚT] uSkSÝ | 4 | 00 |
| | 3.3 | ¾ß’ƒ }iŸ`"]-‹ | | | |
| | | G | Ÿ5 እስከ 70 Ÿ<ንታM KT>ß’< | 55 | ® ® |
| | | G | u}ÚT] uŸ<”ታM | 4 | ® ® |
| | | K | Ÿ71 እስከ 12 ኩንታM KT>ß’< | 140 | ® ® |

| }.l | ¾›ÑMÓKAƒ ¯A’ƒ | | | ¡õÁ (w`) | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | u}ÚT] uŸ<”ታM | 3 | ® ® |
| | | N | Ÿ120 Ÿ<”ታM uLA KT>ß’< | 22® | ® ® |
| | | | u}ÚT] uŸ<”ታM | 2 | 0® |
| | | S | T”–¨<U }du= | 55 | ® ® |
| | | | u}ÚT] uŸ<”ታM | 1 | 00 |
| | 3. 4 | KM¿ }”kdni SX]Á | | 23® | ® ® |
| | 3. 5 | ^^ Ñ<ÇÄ‹” KTeK¨Ø uእÁ”Ç”Æ Ñ<ÇA | | 4 | ® ® |
| | 3. 6 | K}K×ò ¾U`S^ UM¡ƒ ÓMvß | | 8 | ® ® |
| | 3. 7 | K¯Sታ© ¾U´Ñv "`É ÓMvß | | 10 | ® ® |
| 4 | S´Ñw"’ W’Ê‹”“ S²`´a‹” KT¾ƒ | | | | |
| | 4. 1 | S´Ñw"’ W’Ê‹”“ S`´a‹” KSSMŸƒ | | 5 | ® ® |
| | 4. 2 | uS´Ñw ¨AU uW’Ê‹ ¨<eØ ¾T>Ñ˜ S[Í” pÏ KS¨<cÉ uÑê | | 8 | ® ® |

| }.l | ¾›ÑMÓKA ƒ ¯A’ƒ | | ¡õÁ (w`) | |
|---|---|---|---|---|
| | 4. 3 | ¾S´`´ pÏ KS¨<cÉ uÑê | 5 | ® ® |

## ደንብ ቁጥር 208/2003

## የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/1997 አንቀጽ 28 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 208/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር፡-

   1. "ተሽከርካሪ"፣ "ሠረገላ"፣ "ብስክሌት"፣ "ባለሞተር ተሽከርካሪ" እና "ልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያ" በተሽከርካሪ መለያ፣ መመርመሪያና መመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር 681/2002 በአንቀጽ 2 ንዑስ አንቀፅ (1)፣ (2)፣ (3)፣ (4) እና (6) የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፤
   2. "የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ" ማለት ማናቸውንም ዓይነት ዕቃ እንዲያመላልስ ተብሎ የተሰራና ለዚሁ አገልግሎት እንዲውል የተደረገ ባለሞተር ተሽከርካሪ ሲሆን ጎታች መኪናን ይጨምራል፤
   3. "ባለሞተር ብስክሌት" ማለት የጎን ተሽከርካሪውን ሳይጨምር ክብደቱ ከ400 ኪሎ ግራም የማይበልጥ ከአራት መንኮራኩር በታች ያለው ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፤
   4. "የግል ተሽከርካሪ" ማለት ከጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ፣ ከባለሞተር ብስክሌት፣ ከሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ፣ ከጎታች መኪና እና ከልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያ የተለየ ለግል መጠቀሚያ የሚውል ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፤
   5. "የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ" ማለት መንገደኞችን ለማመላለስ የሚያገለግል ባለሞተር ተሽከርካሪ ሲሆን የንግድ አውቶሞቢልና አውቶቡስ ተብሎ ይከፈላል፤
   6. "አዉቶቡስ" ማለት ከአሥራ ሁለት መንገደኞች በላይ ለማሳፈር የሚችል የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ነው፤

7. “ጎታች መኪና” ማለት በተለይ ሌሎች ተሽከርካሪዎችን ለመጎተት የሚያገለገል ሆኖ የሌላ ጭነትን ሳይሆን የሚጎተተውን ተሽከርካሪና በርሱ ላይ ያለውን ጭነት ክብደት ብቻ በከፊል ለመሸከም የተሰራ ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፤
8. “ግማሽ ተሣቢ” ማለት ለመንገደኞች ወይም ለጭነት ማመላለሻ የሚያገለግልና በሌላ ባለሞተር ተሽከርካሪ የሚሳብ ሆኖ የተሽከርካሪው ጭነትና ክብደት በከፊል በሌላ ተሽከርካሪ ላይ እንዲያርፍ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ እንዲሳብ ተደርጎ የተሰራ ተሽከርካሪ ነው፤
9. “ተሳቢ” ማለት ለራሱ የተለየ የሞተር ኃይል የሌለው ሆኖ ጎታች በሆነ በሌላ ባለሞተር ተሽከርካሪ ላይ ሊቀጠልና ሊጎተት የሚችልና ክብደቱ ጎታች በሆነው ባለሞተር ተሽከርካሪ ላይ እንደማያርፍ ሆኖ የተሰራ ተሽከርካሪ ነው፣ ሆኖም ከባለሞተር ብስክሌት ጋር ተያይዞ የሚሳበዉን የጎን ተሽከርካሪ አይጨምርም፤
10. “መንገድ” ማለት ለማናቸውም ተላላፊ ክፍት ካልሆነ የግል መንገድ በስተቀር ተሽከርካሪዎች በተለምዶ የሚጠቀሙበት ማናቸውም የከተማ መንገድ፥ የገጠር መንገድ፣ አውራ ጎዳና ወይም መተላለፊያ ነው፤
11. “ትራፊክ” ማለት በማንኛውም መንገድ አንድ ወይም ብዙ ሆነው የሚተላለፉ እግረኞች ወይም ሰው ተቀምጦባቸው ወይም እየተነዱ ወይም እየተጠበቁ የሚሄዱ እንስሶችና ተሽከርካሪዎች ናቸዉ፤
12. “ትራፊክ ተቆጣጣሪ” ማለት የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መከበራቸውን ለመቆጣጠር እና የትራፊክ ፍሰትን ለማስተናበር አግባብነት ባለው ሕግ ሥልጣን የተሰጠው ሰው ሲሆን ትራፊክ ተቆጣጣሪ ፖሊስ ወይም የትራንስፖርት ተቆጣጣሪ በሚል ይታወቃል፤[78]
13. “ትራፊክ ተቆጣጣሪ ፖሊስ” ማለት የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መከበራቸውን ለመቆጣጠር እና የትራፊክ ፍሰትን ለማስተናበር አግባብነት ባለው ሕግ ሥልጣን የተሰጠው የፖሊስ አባል ነው፤[79]

---

[78] በ23/8(2009) ደ.395 አንቀፅ 2(1) ተሻሻለ፡፡

[79] የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጾች (13) እና (14) በ23/8(2009) ደ.395 አንቀፅ 2(1) መሰረት አዲስ ተጨመሩ ሲሆን ነባሮቹ ንዑስ አንቀጾች እንደቅደም ተከተላቸው ከንዑስ አንቀጽ (15) እስከ (35) ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

14. “ትራንስፖርት ተቆጣጣሪ” ማለት የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መከበራቸውን ለመቆጣጠር በተለይም በመንገድ ላይ የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎችን የቴክኒክ ብቃት እንዲያረጋግጥና ከትራንስፖርት አስተዳደር ጋር በተያያዘ የወጡ መመሪያዎችን አፈፃፀም ለመቆጣጠር አግባብ ባለው አካል ሥልጣን የተሰጠው ሰው ነው፤”
15. “እንስሳ” ማለት ከውሻና ከድመት በቀር ማናቸውም የቤት እንስሳ ነው፡
16. “የአደጋ አገልግሎት ተሽከርካሪ” ማለት የአደጋ አገልግሎት ተግባሩን ለመፈጸም በሚዘዋወርበት ወቅት በግንባሩ አቅጣጫ ሳያቋርጥ ብልጭ ብልጭ የሚል ቀይ ወይም ሰማያዊ የመብራት ምልክት የሚያሳይ ወይም ለማስጠንቀቂያ ተስማሚ የሆነ የድምፅ ምልክት ወይም ደወል የሚያሰማ አምቡላንስ፣ የመከላከያ ወይም የፖሊስ ኃይል ወይም የእሳት አደጋ መከላከያ ተሽከርካሪ ነው፣
17. “መስቀለኛ መንገድ” ማለት ሁለት ወይም ከሁለት የበለጡ መንገዶች በመስቀለኛ መልክ የሚገናኙበት ሥፍራ ነዉ፤
18. “ነጠላ መንገድ” ማለት በአንድ ረድፍ የሚጓዙ ተሽከርካሪዎችን የሚያስኬድ በቂ ስፋት ያለው የመንገድ ክፍል ነዉ፤
19. “የማብሪያ ጊዜ” ማለት ከፀሐይ መጥለቂያ እስከ ፀሐይ መዉጫ ድረስ ያለው ጊዜና እንዲሁ በአየር ሁኔታ ምክንያት የማይቻልበት ወቅት ነው፤
20. “የከተማ ክልል” ማለት የከተማ ምክር ቤት በቀጥታ የሚያስተዳድረው ቀበሌ ወይም ከተማ ክልል ነው፤
21. “የከተማ መንገድ” ማለት በከተማ ክልል ዉስጥ የሚገኝ ማናቸውም መንገድ ነው፤
22. “ባለአንድ አቅጣጫ መንገድ” ማለት ተሽከርካሪዎች በአንድ አቅጣጫ ብቻ እንዲሄዱበት የተፈቀደ መንገድ ነዉ፤
23. “ተሽከርካሪን በመዘግየት ማቆም” ማለት ተሳፋሪዎችን ለማሳፈር ወይም ለማዉረድ ወይም የንግድ ዕቃዎችን ለመጫን ወይም ለማራገፍ ከሚያስፈልገዉ ጊዜ በላይ ተሳፋሪ ወይም የንግድ ዕቃ በዉስጡ ቢኖርም ባይኖርም የተሽከርካሪ መቆም ነው፤
24. “እግረኛ ማቋረጫ” ማለት እግረኞች አቋርጠው እንዲያልፉበት ተብሎ በመንገዱ ላይ የመንገድ ምልክት የተደረገለት የመንገድ ክፍል ወይም ድልድይ ነዉ፤
25. “የሐዲድ መንገድ ማቋረጫ” ማለት መንገድና የሐዲድ መንገድ የሚገናኙበት መስቀለኛ መንገድ ነው፤

26.“የመንገድ ምልክት” ማለት ተሽከርካሪዎች የሚተላለፉበትን አቅጣጫ ለመወሰንና እንዲሁም ለተላላፊዎችን የሚያስጠነቅቅ፣ የሚከለክል፣ የሚያስገድድ፣ ቅድሚያ የሚያሰጥ እና መረጃ ለመስጠት የሚያገለገል ማንኛውም የመንገድ ምልክት ነው፤

27.“ተሽከርካሪን ለጥቂት ጊዜ ማቆም” ማለት ተሳፋሪዎችን ለማሳፈር ወይም ለማውረድ የንግድ ዕቃዎችን ለመጫን ወይም ለማራገፍ ሲባል በመጫኑ ወይም በማውረዱ ጊዜ ብቻ ተሽከርካሪ ለጥቂት ጊዜ ሲቆም ነው፤

28.“ተሽከርካሪን ለጊዜው ማቆም” ማለት በውስጡ ተሳፋሪን ወይም የንግድ ዕቃ ቢኖርም ባይኖርም ተሽከርካሪን ለጊዜውም ቢሆን ማቆም ነው፤

29.“የማቆሚያ መስመር” ማለት የትራፊክ መቆጣጠሪያ ምልክት ወይም የቁም ምልክት ወይም የትራፊክ ተቆጣጣሪ እንዲቆም ምልክት ሲሰጥ ትራፊክ እንዲቆምበት ተብሎ በመንገድ ላይ የሚደረግ የመስመር ምልክት ነው፤

30.የመንገድ ማመላከቻ' ማለት ተላላፊዎችን ለማቆምና ለማስተላለፍ የሚያገለግል በእጅ፣ በመካኒክ፣ ወይም በኤሌክትሪክ ሀይል አማካኝነት በመለዋወጥ የሚሰጥ ምልክት ነው፤[80]

31.“በመነተት ያለ ተሽከርካሪ” ማለት ተሣቢ ወይም ግማሽ ተሣቢ ያልሆነ በሌላ ተሽከርካሪ የሚሣብ ማንኛውም ተሽከርካሪ ነው፡

32.“አሽከርካሪ” ማለት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ያለው ሰው ነው፣

33.“ባስሥልጣን” ማለት በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/1997 የተቋቋመው የትራንስፖርት ባለሥልጣን ነው፤

34.“አግባብነት ያለው አካል” ማለት የትራንስፖርት ባለሥልጣን የመንገድ ትራንስፖርትን ለመምራት ስልጣን የተሰጠው የክልል ወይም የከተማ ትራንስፖርት ቢሮ ነው፤

35.ማንኛዉም በወንድ ፆታ የተገለፀዉ የሴትንም ይጨምራል።

3. <u>ዓላማ</u>

የዚህ ደንብ ዓላማ በመንገድ ላይ ደህንነቱ የተጠበቀና ቀልጣፋ የትራፊክ እንቅስቃሴ መኖሩን ለማረጋገጥ ነው።

[80] በ23/8(2009) ደ.395 አንቀፅ 2(2) ተሻሻለ፡፡

4. **<u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ ደንብ ማንኛውም ትራፊክ በኢትዮጵያ መንገዶች ላይ በሚያደርገው እንቅስቃሴ ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

5. **<u>ጠቅላላ የጥንቃቄ መርሆዎች</u>**

1. በቸልታ ያለበቂ ጥንቃቄ ስለመንዳት

ማንኛውም አሽከርካሪ፡-

ሀ) የጊዜውንና የአየሩን ሁኔታ እንዲሁም የመንገዱን ዓይነትና በመንገዱ ላይ የሚተላለፈውን ተመላላሽ ሁኔታና ብዛት ሳይገምት እንዲሁም በትምህርት ቤት፣ በጤና ተቋም እና በመሳሰሉት ያለ ጥንቃቄ ወይም በሕዝብ ላይ ጉዳት ሊያስከትል በሚችል ፍጥነት፤ ወይም

ለ) በመንገዱ በሚተላለፉ ለሌሎች ደኅንነት ሳያስብና በሚገባ ሳይጠነቀቅ፤

በቸልታ ተሽከርካሪ ማሽከርከር የለበትም፡፡

2. ስለተንቀሳቃሽ ስልክ እና ምስሎች

ሀ) ከአደጋ አገልግሎት ተሽከርካሪ አሽከርካሪ በስተቀር ማንኛውም አሽከርካሪ ተንቀሳቃሽ ስልክን ወይም ሬዲዮ በእጁ ይዞ እየተነጋገረ፣ አጭር መልዕክት እየፃፈ፣ እየላከ፣ ወይም እያነበበ ማንኛውንም ተሽከርካሪ ማሽከርከር የለበትም፡፡[81]

ለ) ማንኛዉም አሽከርካሪ ቴሌቪዥን ወይም ሌሎች ተንቀሳቃሽ ምስሎችን በተሽከርካሪ ውስጥ እያየ ማንኛውንም ተሽከርካሪ ማሽከርከር የለበትም፡፡

ሐ) የዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ድንጋጌ በአደጋ አገልግሎት ተሽከርካሪ አሽከርካሪዎች ላይ አይጸናም፡፡

መ) የዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) ድንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆኖ በተሽከርካሪ ውስጥ ስለ ሬዲዮ መገናኛ አጠቃቀም ባለሥልጣኑ መመሪያ ያወጣል፡፡

3. ስለደኅንነት ቀበቶ

ሀ) ማንኛውም አሽከርካሪ ከሞተር ብስክሌት በስተቀር የደኅንነት ቀበቶ ሳያስር በመንገድ ላይ ማንኛውንም ተሽከርካሪ ማሽከርከር የለበትም፡፡

---

[81] በ23/8(2009) ደ.395 አንቀፅ 2(3) ተሻሻለ፡፡

ለ) ማንኛውም አሽከርካሪ ከሞተር ብስክሌት በስተቀር ሌላ ተሽከርካሪን በሚያሽከረክርበት ወቅት በተሽከርካሪዉ ውስጥ የተሳፈረዉ ሰው የደኅንነት ቀበቶ ማሰሩን ማረጋገጥ አለበት፡፡

ሐ) የዚህ ንዑስ አንቀፅ ፊደል ተራ (ለ) ድንጋጌ ተፈፃሚ የማይሆንባቸው ተሽከር ካሪዎችን በሚመለከት ባለሥልጣኑ ይወስናል፡፡

4. ስለመንገድ አጠቃቀም

በመንገድ የሚጠቀም ማንኛዉም ሰው፡-

ሀ) በሕይወትም ሆነ በንብረት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ጥንቃቄ ማድረግ፤

ለ) ለትራፊክ እንቅፋት አለመሆን፤ እና

ሐ) አግባብነት ያለው አካል ካልፈቀደ በስተቀር በተሽከርካሪ ወይም በእግረኞች መንገድ ላይ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ሌሎች ተግባራትን አለማከናወን፤

ይጠበቅበታል፡፡

5. የመንገድ ምልክቶች፣ ማመላከቻዎች፣ እና በትራፊክ ተቆጣጣሪ ስለሚሰጡ ምልክቶች፡-[82]

ሀ) በመንገድ የሚጠቀም ማንኛውም ሰው በመንገድ ምልክቶች፣ በማመላከቻዎች እና በትራፊክ ተቆጣጣሪ አማካኝነት የሚሰጠውን ትዕዛዝ መፈጸም አለበት፡፡

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ (ሀ) የተደነገገው ቢኖርም በመንገድ የሚጠቀም ሁሉ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ይህንን ደንብ የሚቃረን ቢሆንም እንኳ የትራፊክ ተቆጣጣሪ የሚያሳየውን ምልክትና የሚሰጠውን ትእዛዝ ወዲያዉኑ መፈጸም አለበት፡፡

6. ፈቃድ ስለማስፈለጉ

የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሣይኖሪው ማንኛውም ሰው ማንኛውንም ባለሞተር ተሽከርካሪ እንዲያሽከረክር አይፈቀድም፡፡

7. ስለ አሽከርካሪ

ሀ) ማንኛውም አሽከርካሪ፡-

(1) ጫት ቅሞ ወይም እየቃመ፣ በመድኃኒት ተመርዞ፣ አደንዛዥ ዕጽ ወስዶ ወይም አልኮል ጠጥቶ በመስከር፤

(2) በሰውነቱ ጤናማ ያለመሆን የተነሳ ወይም በድካም መንፈስ፣ ወይም

---

[82] በ23/8(2009) ደ.395 አንቀፅ 2(4) ተሻሻለ፡፡

(3) ከአዕምሮ ጉድለት የተነሣ አደጋ በማያስከትል አኳኋን ለመንዳት በማይችልበት ጊዜ፤

ማናቸውንም ተሽከርካሪ ማሽከርከር የለበትም፡፡

ለ) ማንኛውም አሽከርካሪ በተገቢ አካል በመስከር ሲጠረጠርና ሲጠየቅ የአልኮል መጠኑን መመርመር አለበት፡፡ አሽከርካሪዉ በመጠጥ ሰክሯል ማለት የሚቻለው ለዚሁ ተግባር በተሠራው መሣሪያ ሲመረመር ከፍተኛ የአልኮል መጠን ደም ውስጥ ዜሮ ነጥብ ስምንት ግራም በሊትር ወይም ከትንፋሹ በሚያስወጣው አየር ውስጥ ዜሮ ነጥብ አራት ሚሊግራም በሊትር ንጹህ አልኮል በልጦ ሲገኝ ነው፡፡

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ለ) መሠረት አሽከርካሪው ለመመርመር ፈቃደኛ ካልሆነ በመጠጥ እንደሰከረ ይቆጠራል፡፡

መ) አደንዛዥ ዕፅ ወስዶ ወይም በአልኮል መጠጥ ሰክሮ የተገኘ አሽከርካሪ ሌላ ሰው ተሽከርካሪውን እንዲያሽከረከርለት ካላደረገ በስተቀር ትራፊክ ተቆጣጣሪው ተሽከርካሪውን ለ12 ሰዓታት ይዞ ማቆየት ይችላል፡፡

8. ተሽከርካሪ ማሽከርከር የሚከለከልበት ሁኔታ

ማንኛውም አሽከርካሪ፡-

ሀ) አሠራሩ፣ ዕቃዎቹና ሁኔታው በተሽከርካሪ አሠራር ሕግ ከተወሰነው ውጭ የሆነ፤

ለ) ዓመታዊ ምርመራ ተደርጎለት የቴክኒክ ብቃቱ ያልተረጋገጠ፤

ሐ) ከኋላ አንፀባራቂ ምልክት ያልተለጠፈበት፣

መ) ማንኛውም አሽከርካሪ የፊትና የኋላ ሠሌዳ የሌለውን፣[83]

ተሽከርካሪ ማሽከርከር የለበትም፡፡

9. የተሽከርካሪንና የእንሰሳን እንቅስቃሴ መቆጣጠር

ሀ) ማንኛውም አሽከርካሪ ተሽከርካሪውን በሚያንቀሳቅስበት ጊዜ በተሽከርካሪው እንቅስቃሴ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር መሪውን በሁለት እጆቹ መያዝ አለበት፡፡

ለ) ማንኛውም ሰው በእንስሳ ላይ ተቀምጦ ሲሄድ፣ ወይም እንሰሳን እየነዳ ወይም እየጎተተ ሲሄድ፣ ወይም በእንሰሳ የሚንቀሳቀስ ጋሪን ወይም ሰረገላን እየነዳ በመንገድ ላይ በሚሄድበት ጊዜ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፡፡[84]

10. የመንገዱን ቀኝ ጠርዝ ይዞ ማሽከርከር

[83] በ23/8(2009) ደ.395 አንቀፅ 2(5) መሰረት አዲስ ገባ ነው፡፡

[84] በ23/8(2009) ደ.395 አንቀፅ 2(6) ተሻሻለ፡፡

በዚህ ደንብ ውስጥ በሌላ አኳኋን ካልታዘዘ በቀር ማንኛውም አሽከርካሪ የመንገዱን ቀኝ ጠርዝ ይዞ ማሽከርከር አለበት፡፡

11.በዝግታ ስለሚጓዙ ተሽከርካሪዎች

ከሚከተሉትና በአጠገቡ ከሚተላለፉት ተሽከርካሪዎች ባነሰ ፍጥነት የሚሄድ ተሽከርካሪ ከቀኝ በኩል የሚገኘውን የመንገዱን ጠርዝ ተጠግቶ መሄድ አለበት፡፡

12.ማየት ባልተቻለበት ጊዜ

ማንኛውም የተሽከርካሪ አሽከርካሪ ዕይታውን የሚያውክ ወይም በተወሰነ ርቀት ለማየት ባልቻለበት ጊዜ የሚሄድበትን ነጠላ መሥመር ለውጦ ወደ ሌላው መሥመር ለመሻገር አይፈቀድለትም፡፡

13.በመንገዶች ስለመጠቀም

ሀ) ማንኛውም የተሽከርካሪ አሽከርካሪ መንገድ ባለበት ሥፍራ በመንገዱ ላይ ብቻ ማሽከርከር አለበት።

ለ) ለአንድ ዓይነት ተሽከርካሪ ተብሎ የተዘጋጀ የተለየ ነጠላ መንገድ ሲኖር ማንኛውም የዚህ ዓይነት ተሽከርካሪ አሽከርካሪ በዚሁ ነጠላ መንገድ ብቻ ማሽከርከር አለበት፤ የሌላ ዓይነት ተሽከርካሪ አሽከርካሪዎች በዚሁ ነጠላ መንገድ እንዲተላለፉ አይፈቀድም፡፡

14.የተከፋፈሉ መንገዶች

ሀ) መንገዱ በድንጋይ ምልክት፣ በአትክልት፣ በትራፊክ ደሴትና ይህን በመሳሰለ የተከፋፈለ እንደሆነ እያንዳንዱ የመንገዱ አጋማሽ ባለአንድ አቅጣጫ መንገድ ሆኖ ይቆጠራል፡፡

ለ) በማያቋርጥ የቀለም መሥመር በተከፈለ መንገድ ላይ የሚጓዙ ተሽከርካሪዎች ቀኙን ረድፍ ይዘው መሄድ አለባቸው፡፡ የቀለሙ መሥመር በሚቆራረጥበት ቦታ ላይ ካልሆነ ተሽከርካሪዎች ከቀኝ ወደ ግራ እንዲሻገሩ አይፈቀድም፡፡

6. <u>“እለፍ”፣ “ቁም” እና “የማስጠንቀቂያ” ትራፊክ ምልክቶች</u>

1. "እለፍ" የሚል ምልክት

ሀ/ የምልክቱ አሠጣጥ፡-

(1) በትራፊክ መቆጣጠሪያ መብራት ሲሆን አረንጓዴ ቀለም ወይም አረንጓዴ መብራት ይታያል፣

(2) በትራፊክ ተቆጣጣሪ ሲሆን ተሽከርካሪው እንዲያልፍ ወደሚፈቅድበት አቅጣጫ በትራፊክ ተቆጣጣሪው አንድ ወይም ሁለት ክንዶቹን ዘርግቶ መዳፋን በመክፈት ያመለክታል።

ለ) የምልክቱ ትርጉም፡-

(1) በትራፊክ መቆጣጠሪያ መብራት ወይም በትራፊክ ተቆጣጣሪ ሲሰጥ፡-

ሀ) ተሽከርካሪው ጉዞውን በቀጥታ ወደፊት ለመቀጠል፣ ወደቀኝና ወደግራ ለመታጠፍ፣ እና

ለ) እግረኞች ሌላ ትራፊክ በሚሄድበት አቅጣጫ መንገዱን ለማቋረጥ ይችላሉ፣

ሐ) አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) (ለ) (1) (ለ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ መንገዱን የሚያቋርጡ እግረኞች ለእነርሱ ተብሎ የተሰራውን የእግረኞች የትራፊክ መቆጣጠሪያ ምልክት ወይም የትራፊክ ተቆጣጣሪውን ትዕዛዝ ማክበር አለባቸው፤

መ) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) (ለ) (1) (ሐ) ምልክት ወይም ትዕዛዝ በማይኖርበት ጊዜ የይለፍ ምልክት የተሰጣቸው ተሽከርካሪዎች እስከሚያልፉ ጠብቀው ወይም ተሽከርካሪ አለመኖሩን በማረጋገጥ መንገዱን ማቋረጥ አለባቸው፡፡

(2) በትራፊክ መቆጣጠሪያ መብራት ሲሰጥ፡-

(ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ) (1) (ሀ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከፊት ለፊት በኩል የተቃረበ ተሽከርካሪ ካለ ወደ ግራ መጠምዘዝ ክልክል በመሆኑ "ማስጠንቀቂያ" ምልክት እስኪሰጥ ቆሞ መጠበቅ፣ እና

(ለ) የትራፊክ መቆጣጠሪያ መብራት አረንጓዴ ቀለም ያሳየ እንደሆነ ትራፊክ ቀስቱ በሚያሳየው አቅጣጫ መንገዱን መቀጠል ይችላል፡፡

(3) በትራፊክ ተቆጣጣሪ ሲሰጥ፡-

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ) (1) (ሀ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አሽከርካሪዉ ወደ ግራ ለመጠምዘዝ የሚችለው ትራፊክ ተቆጣጣሪ ምልክት ሲሰጠው ነዉ፡፡

2. "ቁም" የሚል ምልክት

ሀ) የምልክቱ አሠጣጥ፡-

(1) በትራፊክ መቆጣጠሪያ መብራት ሲሆን ቀይ ቀለም ወይም ቀይ መብራት ይታያል፤

(2) በትራፊክ ተቆጣጣሪ ሲሆን ተሽከርካሪው ወደሚቆምበት መሥመር ትራፊክ ተቆጣጣሪው አንድ ወይም ሁለት ክንዶቹን ዘርግቶ የእጁን መዳፍ ከፍቶ ያመለክታል።

ለ) የምልክቱ ትርጉም፡-

(1) የሚተላለፉት ተሽከርካሪዎች ሁሉ ለመቆሚያ በተወሰነው መስመር ላይ ወይም ከእግረኞች ማቋረጫ አጠገብ ይቆማሉ፤ በመንገድ ላይ የማቆሚያ መስመር ወይም የእግረኛ ማቋረጫ መስመር ምልክት ባይኖር ተሽከርካሪዎች ለሌሎች ተሽከርካሪዎችና እግረኞች እንቅፋት በማይሆኑበት ቦታ ላይ መቆም፣ እና

(2) ቁም በሚል ምልክት ምክንያት የቆሙት ተሽከርካሪዎች በሚሄዱበት አቅጣጫ የሚሄዱ እግረኞች መንገዱን ማቋረጥ አይችሉም፡፡

3. “የማስጠንቀቂያ” ምልክት

ሀ) የምልክቱ አሠጣጥ፡-

(1) በትራፊክ መቆጣጠሪያ መብራት ሲሆን ቢጫ መብራት ይታያል ወይም ቢጫና ቀይ መብራት በመፈራረቅ ይታያል፤

(2) በትራፊክ ተቆጣጣሪው ሲሆን ትራፊክ ተቆጣጣሪው አንድ ክንዱን ከራሱ በላይ በቀጥታ ዘርግቶ ያመለክታል።

ለ) የምልክቱ ትርጉም፡-

(1) “እለፍ” ከሚለው ምልክት በኋላ የማስጠንቀቂያ ምልክት ሲሰጥ ከመስቀለኛው መንገድ ውስጥ ገና ያልገቡ ተሽከርካሪዎች በመቆሚያው መሥመር ላይ መቆም አለባቸው፤ ከመስቀለኛዉ መንገድ ውስጥ የገቡ ተሽከርካሪዎች ግን ፈጥነው ማለፍ አለባቸዉ፤

(2) "ቁም" ከሚለው ምልክት በኋላ የማስጠንቀቂያ ምልክት ሲሰጥ "እለፍ" የሚል ምልክት እስኪሰጥ ድረስ ተሽከርካሪዎች ተዘጋጅተው መጠበቅ እንጂ ማለፍ የለባቸውም፡

(3) እግረኞች መንገዱን ማቋረጥ ክልክል ነው፤ እና

(4) ወደ ግራ ለመጠምዘዝ የሚጠባበቁ ተሽከርካሪዎች ሌሎች ተላላፊ ተሽከርካሪዎች ሁሉ ከመስቀለኛው መንገድ ወዲያው እንደወጡ ወደ ግራ ለመጠምዘዝ ይችላሉ፡፡

4. የሚያቋርጥ ቀይ ወይም ቢጫ መብራት ስለማሳየት፡-

ሀ) በማንኛውም መስቀለኛ መንገድ ላይ የትራፊኩ መቆጣጠሪያ ምልክት ሳያቋርጥ ብልጭ ጥፍት የሚል ቀይ ምልክት ሲያሳይ ማናቸውም ባለተሽከርካሪ በማቆሚያው መስመር ላይ መቆም አለበት፤ የማቆሚያ መስመር ምልክት ባልተደረገበት መንገድ ላይ ግን ከመስቀለኛው መንገድ ሳይገባ ቆሞ መጠበቅና በራሱና በሌሎች ተላላፊዎች ላይ ጉዳት የሚያደርስ መሆኑን አረጋግጦ ማለፍ ይችላል።

ለ) በማንኛውም መስቀለኛ መንገድ ላይ የትራፊኩ መቆጣጠሪያ ምልክት የማያቋርጥ ቢጫ መብራት ሲያሳይ ባለተሽከርካሪ ሁሉ ፍጥነታቸውን ቀንሰው በጥንቃቄ መንዳት አለባቸዉ፡፡

5. በትራፊክ ተቆጣጣሪው የሚሰጥ ትዕዛዝ አስገዳጅ ስለመሆኑ፡-

ሀ) በትራፊክ ተቆጣጣሪው የምልክት አሰጣጥ በእርግጥ የሚያጠራጥር ካልሆነ በስተቀር የምልክቱ አሰጣጥ በዚህ ደንብ በተወሰነው አኳኋን ባይሆንም ትራፊክ ተቆጣጣሪዉ የሚሰጠው ትእዛዝ የግድ መፈጸም አለበት፡፡

ለ) አግባብነት ያለው አካል በዚህ ደንብ የተመለከቱትን የመንገድ ምልክቶች በከፊል ወይም በሙሉ ለሁልጊዜ ወይም ለአጭር ጊዜ እንዳይፈፀሙበት በጽሁፍ አንድን ሰዉ ነፃ ለማድረግና እንደዚህ ያለውን ነፃነት ለማስቀረት ወይም ለመሰረዝ ይችላል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>በመንገድ ስለመጠቀምና ፍጥነት</u>

7. <u>የተላላፊዎችን እንቅስቃሴ ስለማሰናከል</u>

1. ማንኛዉም ሰው ሥልጣን ሳይኖረው ወይም ሳያስፈቅድ ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት፡-

ሀ/ በመንገድ እንዳያስተላልፍ የሚያደርግ ወይም የጉዞን ፍጥነት የሚያስቀንስ ወይም እንደ ልብ ለመንቀሳቀስ የማያስችል ማናቸውንም ነገር፤

ለ/ በመንገዱ የሚጠቀሙበትን የሚያደናቅፍ ወይም ጉዳት ሊያደርስባቸው የሚችል ወይም ተላላፊዎችን የሚያውክ ወይም ሰዎችንና ተሽከርካሪዎችን በማንኛውም አኳኋን ሊጎዳ የሚችል ነገር፤

በማንኛውም መንገድ ላይ ማስቀመጥ፣ ማድረግ ወይም ማንቀሳቀስ የለበትም፡፡

2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብነት ያለው አካል በሕዝብ ማስታወቂያ ወይም የመንገድ ምልክት በማድረግ ተሽከርካሪዎች ሁሉ ወይም የተወሰኑ ተሽከርካሪዎች፣ እግረኞች ወይም እንስሶች የተወሰነ የመንገድ ክፍል እንዳይገቡ ወይም እንዳይወጡ መከልከል ይችላል፡፡

## 8. መንገዶችን ስለማበላሸት

ማንኛውም ሰው፡-

1. ከአሰራሩ፣ ከአያያዙ ወይም ከአቀማመጡ ገድለት የተነሣ ጎማዎቹ ወይም ጎማዎቹን በሚያሽከረከሩ ክብ ነገሮች፣ ኩሽኔታዎች ወይም በሌላው የአካላቱ ክፍል መንገዱን ለማበላሸት የሚችል ተሽከርካሪ ወይም መጎተት የለበትም፤
2. ዘይት ወይም ማንኛውንም መንገድን ሊያበላሹ የሚችሉ ነገሮችን መንገድ ላይ ማፍሰስ የለበትም፤
3. ለተለያዩ ሥራዎች ሲባል መንገድን የሚቆፍር ማንኛውም አካል መንገዱን ከመቆፈሩ በፊት የሚመለከተውን አካል አስቀድሞ ማስፈቀድና ሥራው እንዳለቀ ወዲያውኑ በነበረበት ሁኔታ እንዲስተካከል ማድረግ አለበት፡፡
4. በተሽከርካሪ ወይም በእግረኛ መንገድ ላይ ወይም ፍሳሹ ወደ እግረኛ ወይም ወደ ተሽከርካሪ መንገድ በሚገባበት ስፍራ ላይ ተሽከርካሪውን ማጠብ ወይም ማሳጠብ የለበትም፡፡[85]

## 9. በመንገድ ላይ ተሽከርካሪዎችን ስለመጠገን

1. ማንኛዉም ሰው በመንገድ ላይ ተሽከርካሪን መጠገን የለበትም፡፡
2. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገዉ ቢኖርም የተሽከርካሪዉን ጉዞ ያቋረጠው አነስተኛ ብልሽት ከሆነና የጥገና ሥራው በመንገዱ ለሚጠቀሙት ሌሎች ተላላፊዎች እንቅፋት ካልሆነ ተሽከርካሪዉን ለማንቀሳቀስ ወይም ካለበት ቦታ ለማንሣት ያህል የሚያስፈልገዉን የመጠገን ሥራ የመንገዱን ጠርዝ በመያዝ ለመሥራት ይችላል፤ ይሁን እንጂ ተሽከርካሪዉ በማናቸዉም አኳኋን በመንገድ ላይ ያለማቋረጥ፡-

---

[85] በ23/8(2009) ደ.395 አንቀፅ 2(7) መሰረት አዲስ ገባ ነው፡፡

ሀ) ከከተማ ክልል ውጭ ሲሆን ከሃያ አራት (24) ሰዓት በላይ፤ እና

ለ) በከተማ ክልል ወስጥ ሲሆን ለከባድ ተሽከርካሪ ከሦስት (3) ሰዓት በላይ እና ለቀላልና መካከለኛ ተሽከርካሪ ከሁለት (2) ሰዓት በላይ፤

በመንገድ ላይ መቆየት የለበትም፡፡

3. አንድ ተሽከርካሪ ባለማቋረጥ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ከተወሰነው በላይ በአንድ ቦታ ላይ ቢቆይ በአንቀጽ 33 የተደነገገው ይፈፀምበታል፡፡

4. ማንኛዉም ሰዉ የተጎዳ ወይም የተበላሸ ተሽከርካሪ ከመንገድ ላይ በሚያነሳበት ጊዜ በመንገዱ ላይ የወዳደቁ ስብርባሪ ነገሮች ሁሉ ከመንገዱ ላይ ማስወገድ አለበት፡፡

5. ማንኛውም ተሽከርካሪ በመንገድ ላይ ቢበላሽ አሽከርካሪው ከተሽከርካሪው ፊትና ኋላ ባለው መንገድ በ30 ሜትር ርቀት ላይ ለሌላ ትራፊክ በግልፅ በሚታይ መልኩ ድንጋይ፣ እንጨት እና የመሳሰሉትን ሳይሆን ባለሦስት ማዕዘን አንፀባራቂ ሠሌዳ ማስቀመጥ አለበት።

10. <u>ጢስ፣ ነዳጅ፣ ዘይትና ድምፅ ቁጥጥር</u>

1. ማንኛውም አሽከርካሪ፡-

ሀ) ከሚገባው መጠን በላይ ጢስ፣ እንፋሎቶት፣ ዘይት ወይም ነዳጅ የሚተፋ በሌሎች ተላላፊዎች ላይና በአካባቢው ላይ ጉዳት የሚያመጣ ወይም የሚያውክና በደንብ ያልተጠገነ ተሽከርካሪ፤

ለ) በሚገባ ባለመታደሱ ወይም የቴክኒኩ ሁኔታ በሚገባ ለመጠበቁ ወይም ከአጫጫኑ ጉድለት የተነሣ ከመጠን በላይ ድምፅ የሚያሰማ ተሽከርካሪ፤ እና

ሐ) ተሽከርካሪ ውስጥ ከመጠን በላይ ማንኛውንም ድምጽ እያሰማ ወይም በጆሮ እያዳመጠ፤

ማሽከርከር የለበትም፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) የተመለከተው መጠን በትራንስፖርት ባለሥልጣን ይወሰናል፡፡

11.<u>የፍጥነት ወሰን</u>

1. ማንኛዉም አሽከርካሪ በፍጥነት ወሰን ህግ ዉስጥ የተመለከተዉን መጠን አክብሮ ማሽከርከር አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው የፍጥነት ወሰን እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛዉም ሰዉ በማናቸውም መንገድ ላይ ሲያሽከረክር የመንገዱን ሁኔታ፣

የትራፊኩን ብዛት፣ ተላላፊን ለማየትና ተሽከርካሪውን ለመቆጣጠር ያለው ችሎታ ከሚፈቅድለት ፍጥነት በላይ ማሽከርከር የለበትም፡፡

12.<u>ልዩ ሁኔታ</u>

1. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የመንገድ ምልክቶችን ለመትከል ሥልጣን የተሰጠው አካል በማናቸውም የመንገድ ክፍል ውስጥ ተገቢውን የመንገድ ምልክት በማድረግ በዚህ ደንብ በአንቀጽ 11 በተወሰነው ፍጥነት ልክ ለጊዜው ወይም በቋሚነት ለማሳነስ ይችላል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ በተሽከርካሪዎች ላይ የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ ስለሚገጠምበት ሁኔታ በመመሪያ ይወስናል።

13.<u>በዝግታ ስለማሽከርከር</u>

ማንኛዉም አሽከርካሪ ከመስቀለኛ፣ ከጉብታማ፣ በእግረኛ ማቋረጫ፣ ከመታጠፊያ፣ ከጠባብ ድልድይ፣ ከኮረብታ ጫፍ፣ ወይም ቁልቁለት መንገድ ሲቃረብ፣ በጠባብ ወይም በጠመዝማዛ መንገድ ላይ በሚነዳበት ጊዜ፣ የማየት ኃይል በተቀነሰበት ወቅትና አደጋ ሊያስከትል የሚያሠጋበት ጊዜ ሁሉ የተሽከርካሪውን ፍጥነት በመቀነስ በዝግታ ማሽከርከር አለበት፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>ስለትራፊክ ድንጋጌዎች</u>

14.<u>ተከትሎ እና ተከታትሎ ስለማሽከርከር</u>

1. ማንኛውም አሽከርካሪ ሌላ ተሽከርካሪ ተከትሎ ሲያሽከረከር በማናቸውም ጊዜ ያለአንዳች አደጋ ማቆም እንዲችል የራሱንና ከፊቱ የሚሄደውን ተሽከርካሪ ፍጥነት፣ የመንገዱን ሁኔታ፣ እይታንና የትራፊኩን ብዛት በማመዛዘን በቂ ርቀት ጠብቆ ማሽከርከር አለበት፡፡
2. ቁጥራቸው አራት ወይም ከአራት በላይ ሆነዉ ከከተማ ክልል ውጭ ተከታትለው የሚሄዱ ተሽከርካሪዎችን የሚያሽከረክር ማንኛዉም አሽከርካሪ ሌላው ተሽከርካሪ ያለአንዳች አደጋ ከመካከል ለመግባት እንዲችል በተሽከርካሪው መካከል ሰፋ ያለ ርቀት ጠብቆ ማሽከርከር አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) የተደነገገዉ አስከሬን አጅበው ወይም በሌላ ልዩ አጋጣሚ ምክንያት አጅበው በሚሄዱ አሽከርካሪዎች ላይ አይጸናም፡፡

15.<u>ፊት ለፊት ስለመገናኘትና ቀድሞ ስለማለፍ</u>

1. በተቃራኒ አቅጣጫ የሚተላለፉ ሁለት ተሽከርካሪዎች ከሚጓዙበት መስመር ሳይዛነፉ ያለአንዳች አደጋ ለመተላለፍ በማያስችል ጠባብ መንገድ ላይ ፊት ለፊት የተገናኙ እንደሆነ ፍጥነታቸዉን ቀንሰው በተቻለ መጠን የመንገዱን ቀኝ ጠርዝ ይዘዉ መተላላፍ አለባቸው።
2. ለአዉቶብስ በማንኛዉም ጊዜ የማለፍ ትድሚያ መስጠቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ተሽከርካሪዎች በአቀበት ወይም በቁልቁለት ላይ ሲገናኙ ቁልቁል የሚሄደው አሽከርካሪ ወደ አቀበት ለሚወጣዉ አሽከርካሪ የማለፍ ቅድሚያ መስጠት አለበት፡፡
3. ማንኛውም አሽከርካሪ ሌላውን ተሽከርካሪ ቀድሞ ለማለፍ ሲፈልግ በግራዉ በኩል ብቻ ማለፍ አለበት።
4. ማንኛውም አሽከርካሪ ከፊት ለፊት ለሚመጣ ተሽከርካሪ ወይም ለሚቀድመው ተሽከርካሪ አደጋ ወይም እንቅፋት ሳያስከትል መቅደም እንዲያስችል በርቀት ከፊት ለፊት የሚመጣ ተላላፊ ተሽከርካሪ አለመኖሩን ሳያረጋግጥ ቀድሞ ማለፍ የለበትም፡፡
5. ማንኛዉም አሽከርካሪ፡-

   ሀ) አርቆ ወይም አሻግሮ ለማየት ባልቻለበት ጊዜ፤

   ለ) ከኮረብታ ጫፍ፣ ከቁልቁለት፣ ከድልድይ፡ ተነጥሎ ከተሰራ መሿለኪያ ወይም ከኅባጣ መንገድ ለመድረስ በተቃረበ ጊዜ፤ ወይም

   ሐ) ከመስቀለኛ ወይም ከሀዲድ መንገድ በሀምሳ ሜትር ርቀት ውስጥ፤

   ሌላውን ተሽከርካሪ መቅደም አይፈቀድለትም፡፡
6. በሌላ ተሽከርካሪ የሚቀደም አሽከርካሪ ከመንገዱ ወደ ቀኝ በመጠጋት የሚቀድመው ተሽከርካሪ ጨርሶ አልፎት ከመሄዱና አደጋ በማያስከትል ርቀት ከመንገዱ ወደ ቀኝ ጥግ ከመመለሱ በፊት የጉዞውን ፍጥነት መጨመር የለበትም።

16.<u>አቅጣጫ ስለመለወጥ</u>

1. ማንኛውም አሽከርካሪ፡-

   ሀ) አርቆ ወይም አሻግሮ ለማየት ባልቻለበት ጊዜ፡

   ለ) ከኮረብታ ጫፍ፣ ቁልቁበት፣ ከድልድይ፣ ተነጥሎ ከተሠራ መሿለኪያ ወይም ከኅባጣ መንገድ ሲደርስ፤

ሐ) ከመስቀለኛ ወይም በሐዲድ መንገድ ማቋረጫ ሃምሳ ሜትር ርቀት ውስጥ፤ ወይም

መ) የማያቋርጥ የቀለም መሥመር በተደረገበት መንገድ ላይ፡

ወደ ግራ መጠምዘዝ የለበትም፡፡

2. በትራፊክ ደሴት ዙሪያ የሚያሽከረክር ማንኛዉም አሽከርካሪ የትራፊክ ደሴት ቀኙን አቅጣጫ ተከትሎ መንዳት አለበት፡፡

3. በነጠላ መንገዶች በተከፋፈለ መንገድ የሚያሽከረክር ማንኛዉም አሽከርካሪ፡-

ሀ) በሌላዉ ተላላፊ ወይም በሚከተለው ተሽከርካሪ ላይ አደጋ የሚያስከትል መሆኑን ካላረጋገጠ በቀር ከአንዱ ነጠላ መንገድ ወደ ሌላዉ ለመሻገር አይፈቀድለትም፤

ለ) አንድ መንገድ በሦስት ወይም በአምስት እና በላይ ነጠላ መንገዶች ተከፋፍሎ ሲገኝ ማንኛዉም አሽከርካሪ፡-

(1) ወደ ግራ ለመጠምዘዝ ካልሆነ፤

(2) ሌላ ተሽከርካሪ ለመቅደም ካልሆነ፤ወይም

(3) ነጠላዉ መንገድ ተሽከርካሪው በሚሄድበት አቅጣሜ በአንድ አቅጣጫ ትራፊክ ብቻ የተመደበ ካልሆነ፤

በስተቀር ከመካከለኛው ነጠላ መንገድ ውስጥ ገብቶ እንዲያሽከርክር አይፈቀድለትም፡፡

17.<u>ስለመጠምዘዝና ወደ ኋላ ስለማሽከርከር</u>

1. ማንኛውም አሽከርካሪ በሌላ ተላላፊና ተከትለዉት በሚመጡ ተሽከርካሪዎች ላይ አደጋ የማያስከትል መሆኑን ሳያረጋግጥ አቅጣጫዉን ወደ ሌላ መንገድ መጠምዘዝ ወይም መለወጥ ወይም የቆመ ተሽከርካሪውን ሲያስነሳ የነበረበትን አቅጣጫ መለወጥ የለበትም፡፡

2. ወደ ቀኝ ለመጠምዘዝ የሚፈልግ አሽከርካሪ በቀኝ በኩል የሚጓዝ ሌላ ተሽከርካሪ አለመኖሩን አረጋግጦና በተቻለ መጠን የመንገዱን ቀኝ ተጠግቶ መጠምዘዝ አለበት፡ ፡

3. ወደ ግራ የሚጠመዘዝ ማንኛውም አሽከርካሪ በ15 ሜትር ርቀት በፊት ራሱን በማዘጋጀት፡-

ሀ) ከባለሁለት አቅጣጫ መንገድ ወደ ባለሁለት አቅጣጫ መንገድ ለመጠምዘዝ፣ የመስቀለኛ መሀል አካፋዩን መስመር ወደ ግራ በመተው መስቀለኛ መንገድ መግባትና ወደ ግራ በሚጠመዘዝበት አቅጣጫ ባለው መንገድ ያለውን የመሀል አካፋይ መስመር ወደ ግራ በመተዉ መስቀለኛውን መንገድ መዉጣት፤

ለ) ከባለሁለት አቅጣጫ መንገድ ወደ ባለአንድ አቅጣጫ መንገድ ለመጠምዘዝ፣ የመሀል አካፋዩን መስመር ወደ ግራ በመተው መስቀለኛ መንገድ መግባትና ወደ ግራ በሚጠመዘዝበት አቅጣጫ ያለውን ባለአንድ አቅጣጫ መንገድ የግራ ጠርዝ ይዞ ከመስቀለኛው መንገድ መዉጣት፤

ሐ) ከባለአንድ አቅጣጫ መንገድ ወደ ባለ ሁለት አቅጣጫ መንገድ ለመጠምዘዝ፣ የባለአንድ አቅጣጫ መንገድ የግራ ጠርዝ በመያዝ ወደ ግራ በሚጠመዘዝበት አቅጣጫ ያለውን ባለሁለት አቅጣጫ መንገድ የመሀል አካፋይ መስመር ወደ ግራ በመተዉ መስቀለኛዉን መንገድ መዉጣት፤

መ) ከባለአንድ አቅጣጫ መንገድ ወደ ሌላ ባለአንድ አቅጣጫ መንገድ ለመጠምዘዝ፤ የባለአንድ አቅጣጫ መንገድ የግራ ጠርዝ በመያዝ ወደ ግራ በሚጠመዘዝበት አቅጣጫ ያለውን ባለአንድ አቅጣጫ መንገድ የግራ ጠርዝ ይዞ ከመስቀለኛ መንገድ መዉጣት፤

ሠ) የመስቀለኛ መንገድን አቋርጦ ወደግራ የሚታጠፍ አሽከርካሪ በዚህ ንዑስ አንቀፅ ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (መ) በተመለከተው አኳኋን መጠምዘዝ፤

አለበት፡፡

4. ማንኛውም አሽከርካሪ ወደ ኋላ ማሽከርከር አስፈላጊ ከሆነበት አደጋ እንዳይደርስ ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጎ በማንኛውም መንገድ ላይ አስፈላጊ በሆነ መጠን ወደ ኋላ ማሽከርከር ይችላል፡፡

18. <u>የባቡር ሐዲድ ማቋረጥ</u>

1. ማንኛውም አሽከርካሪ በሐዲድ ማቋረጫ ሲደርስ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለማቆም እንዲችል ተሽከርካሪውን በዝግታ መንዳትና አስፈላጊዉን ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፡፡

2. ማንኛውም አሽከርካሪ፡-

ሀ) ከባቡር ሐዲድ ማቋረጫ ሲደርስ፣ ባቡር የተቃረበ መሆኑን ለማስጠንቀቅ በጥበቃ ክፍል ወይም በመካኒክ ወይም በኤሌትሪክ ኃይል ምልክት በሚሰጥበት ጊዜ፤

ለ) በማቋረጫው ላይ ያለው በር በሚከፈትበት ወይም በሚዘጋበት ጊዜ፣ ወይም

ሐ) መጪ ባቡር በሚታይበት፣ ድምፅ በሚሰማበት ወይም በማንኛዉም አኳኋን መቃረቡ በሚታወቅበት ጊዜ፣

ከሚቀርበው ሐዲድ ከስድስት (6) ሜትር በማያንስ ርቀት ተሽከርካሪዉን አቁሞ የሐዲድ በሮች እስከሚከፈቱ ወይም በር የሌለ እንደሆነ ባቡሩ እስከሚያልፍ ጉዞውን መቀጠል የለበትም፡፡

3. ማንኛዉም ሰዉ በሐዲድ ማቋረጫ ላይ ወይም ያለው በር በመዘጋት ወይም በመከፈት ላይ ሳለ ወይም ከተዘጋ በኋላ በበሩ ላይ ወይም በሥሩ ወይም በሩን ዞሮ እንዲያልፍ አይፈቀድለትም፡፡

4. ፈንጂ ወይም ተቀጣጣይ ነገሮችን የጫነ ተሽከርካሪ ወይም አውቶቡስ ወይም ከስምንት መንገደኞች በላይ የጫነ የተሽከርካሪ አሽከርካሪ ከባቡሩ ሐዲድ ማቋረጫ ሲቃረብ ከሚቀርበው ሐዲድ ከስድስት ሜትር በማያንስ ርቀት ተሽከርካሪውን አቁም መጪው ባቡር አለመቃረቡን የሚያስጠነቅቅ ምልክት አለመሰጠቱን ለማረጋገጥ የሐዲዱን ግራና ቀኝ አቅጣጫ ከተመለከተና ካዳመጠ በኋላ አደጋ የማያስከትል መሆኑን አረጋገጦ ጉዞውን መቀጠል አለበት፡፡

5. ማንኛዉም አሽከርከሪ ከባቡር ሐዲድ ማቋረጫ በደረሰ ጊዜ ከቅርቡ ሐዲድ ለመድረስ በሚቀረው ስድስት ሜትር ርቀትና የሐዲዱን ማቋረጫ ተሻግሮ ባለው ስድስት ሜትር ርቀት መካከል ማርሽ መቀያየር የለበትም፡፡

19. <u>ምልክት ስለመስጠት</u>

1. ማንኛውም አሽከርካሪ ከመጠምዘዙ፣ አቅጣጫ ከመለወጡ፣ ፍጥነት ከመቀነሱ ወይም ከማቆሙ አስቀድሞ በከተማ ክልል ውስጥ በ 25 ሜትር እና ከከተማ ክልል ውጪ በ50 ሜትር ርቀት ላይ ለሌሎች የመንገድ ተጠቃሚዎች ጉልህ ሆኖ ሊታይ የሚችል የማስጠንቀቂያ ምልክት መስጠት አለበት፡፡[86]

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚሰጡት የማስጠንቀቂያ ምልክቶች በመካኒክ ወይም በኤሌክትሪክ ኃይል በሚንቀሳቀሱ መሣሪያዎች መሆን አለበት፡፡ በመካኒክ ወይም በኤሌክትሪክ መሣሪያዎች ማስጠንቀቂያ ምልክት ሲሰጥ፡-

ሀ) ወደቀኝ ለመጠምዘዝ ወይም አቅጣጫ ለመለወጥ አሽከርካሪዉ በተሽከርካሪው ቀኝ ብርሃን ያለዉ ቀስት ወይም አመልካች ያሳያል ወይም ከተሽከርካሪው ኋላ

86 በ23/8(2009) ደ.395 አንቀፅ 2(8) ተሻሻለ፡፡

ቀኝ ብልጭ ድርግም የሚል ቀይ ወይም ቢጫ መብራትና በተሽከርካሪው ግንባር ቀኝ ብልጭ ድርግም የሚል ነጭ ወይም ቢጫ መብራት፤

ለ) ወደ ግራ ለመጠምዘዝ ወይም አቅጣጫ ለመለወጥ አሽከርካሪው በተሽከርካሪው ግራ ብርሃን ያለው ቀስት ወይም አመልካች ወይም በተሽከርካሪው ኋላ ግራ ብልጭ ድርገም የሚል ቀይ ወይም ቢጫ መብራትና በተሽከርካሪው ግንባር ግራ ብልጭ ድርግም የሚል ነጭ ወይም ቢጫ መብራት፤

ሐ) የተሽከርካሪውን ፍጥነት ለመቀነስ ወይም ለማቆም አሽከርካሪው ከተሽከርካሪው ኋላ ካሉት መብራቶች ቢያንስ አንዱን ቀይ መብራት፤

ማሳየት አለበት፡፡

3. የመካኒክ ወይም የኤሌክትሪክ መሣሪያዎች የተበላሹ ወይም በመካኒክ ጉድለት ምክንያት ለመሥራት ባልቻሉ ጊዜ አሽከርካሪው የማስጠንቀቂያ ምልክት በእጅ መስጠት አለበት። በእጅ የማስጠንቀቂያ ምልክት ሲስጥ፡-

ሀ) ወደ ቀኝ ለመጠምዘዝ ወይም አቅጣጫ ለመለወጥ በፈለገ ጊዜ አሽከርካሪው የግራ ክንዱን ከግራ ወደ ቀኝ በማዞር፤

ለ) ወደ ግራ ለመጠምዘዝ በፈለገ ጊዜ አሽከርካሪዉ የግራ ክንዱን ወደ ውጭ አግድሞሽ በመዘርጋት መዳፉን ወደታች በማድረግ፤

ሐ) በዝግታ ለመንዳት ወይም ለማቆም በሚፈልግበት ጊዜ አሽከርካሪዉ የግራ ክንዱን ከፍና ዝቅ እያደረገ መዳፉን ወደታች በማድረግ፤

ማሳየት አለበት፡፡

4. የመካኒክ ወይም የኤሌክትሪክ መሣሪያዎች በሚገባ መሥራታቸውን መቆጣጠር የአሽከርካሪው ኃላፊነት ሲሆን በእነዚህ መሣሪያዎች የመካኒክ ጉድለት አሽከርካሪው ተገቢውን የማስጠንቀቂያ ምልክት ባለመስጠቱ ለሚያደርሰው ጥፋት ተጠያቂ ነው፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) እንደተደነገገው ከፊት ለፊት በሚሔድ አሽከርካሪ ምልክት የተሰጠው ማንኛውም አሽከርካሪ የተሽከርካሪውን ፍጥነት መቀነስ ወይም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ማቆምና ምልክት ሰጪው አሽከርካሪ ያለአንዳች እንቅፋት ለመጠምዘዝ፣ አቅጣጫውን ለመለወጥ፣ ፍጥነትን ለመቀነስ ወይም እንደነገሩ ሁኔታ ተሽከርካሪውን ለማቆም እንዲቻል አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሁሉ መፈጸም አለበት፡፡

## 20. የማስጠንቀቅያ ድምፅ መሣሪያዎች

በዚህ ደንብ ውስጥ በሌላ አኳኋን በተለይ ካልታዘዘና ጉዳዩ በሚመለከተው ባለሥልጣን በሕግ ካልተፈቀደ በስተቀር ማንኛውም አሽከርካሪ በፊሽካ፣ በደዉል ወይም ከጭስ ማዉጫ ጋር በተያያዘ መሣሪያ ወይም በሕግ ባልተፈቀደ በሌላ በማንኛውም መሣሪያ የማስጠንቀቂያ ድምፅ ማሰማት ክልክል ነው።

21.<u>የማስጠንቀቂያ ድምፅ ስለመጠቀም</u>

ማንኛውም አሽከርካሪ የሚገጥመውን አደጋ ለመከላከል የግድ አስፈላጊ ካልሆነ አደጋውን የሚከላከልበት ሌላ መንገድ ከሌለውና የሚያሰማውም የማስጠንቀቂያ ድምፅ በተቻለ መጠን አጭር ካልሆነ በስተቀር በከተማ መንገድ ውስጥ የማስጠንቀቂያ ድምፅ ማሰማት አይፈቀድለትም፡፡ ተሽከርካሪው በቆመበት ጊዜ በማናቸውም አኳኋን የማስጠንቀቂያ ድምፅ ማሰማት ክልክል ነው፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ቅድሚያ ስለመስጠት</u>

22.<u>ከመስቀለኛ መንገዶች ስለመድረስና ስለመግባት</u>

1. ማንኛውም አሽከርካሪ ከአንድ መስቀለኛ መንገድ በደረሰ ጊዜ መስቀለኛውን መንገድ ለማለፍ አስቀድሞ ከመስቀስኛው መንገድ ውስጥ ለገባ ተሽከርካሪ ቅድሚያ መስጠት አለበት፡፡
2. ከተለያየ አቅጣጫ ሁለት ወይም ከሁለት የሚበዙ ተሽከርካሪዎች በአንድ ጊዜ ከመስቀስኛው መንገድ የደረሱ እንደሆነ ማንኛውም አሽከርካሪ ከቀኝ በኩል ለተቃረበው ተሽከርካሪ ቅድሚያ መስጠት አለበት፡፡
3. በአንድ መስቀለኛ መንገድ ላይ የትራፊክ ክብ ተሠርቶ እንደሆነ ወደ ክቡ የተቃረበው አሽከርካሪ አስቀድሞ ክቡን በመዞር ላይ ላሉት ተሽከርካሪዎች ሁሉም ቅድሚያ መስጠት አለበት፡፡

23.<u>በመስቀለኛ መንገድ ላይ ወደ ግራ ስለመጠምዘዝ</u>

ማንኛውም አሽከርካሪ ከመስቀለኛ መንገድ ውስጥ ከገባ በኋላ ወደ ግራ ለመጠምዘዝ ቢፈልግ አደጋ እንዳያስከትል በቂ በሆነ ርቀት ላይ አቁም ከፊት ለፊቱ ለተቃረበው ተሽከርካሪ ቅድሚያ መስጠት አለበት።

24.<u>ቅድሚያ ወደሚሰጥበት መንገድ ስለመግባት</u>

1. ማንኛውም አሽከርካሪ ቅድሚያ የሚሰጥበት መንገድ ጋር ከተያያዘ መስቀለኛ መንገድ በተቃረበ ጊዜ የማለፍ ቅድሚያ ምልክት ከተደረገበት መንገድ ማንኛውም አቅጣጫ ወደ መስቀለኛው መንገድ ለተቃረበ ተሽከርካሪ ቅድሚያ መስጠት አለበት፡፡
2. ማንኛውም አሽከርካሪ ከፊት ለፊቱ ቁም የሚል ምልክት ከተደረገበት መስቀለኛ መንገድ በደረሰ ጊዜ ተሽከርካሪውን በማቆሚያዉ መሥመር ወይም በእግረኞች ማቋረጫ አጠገብ ወይም አቋራጩን መንገድ አሻግሮ ለማየት በሚያስችለው ቅርብ ቦታ ላይ አቁሞ ከአቋራጩ መንገድ ለተቃረበዉ ማንኛውም ተሽከርካሪ ቅድሚያ መስጠት አለበት፡፡
3. ማንኛውም አሽከርካሪ ባለ አራት ጎን ቢጫ የትራፊክ መስመር በተቀባ መስቀለኛ መንገድ ላይ በተቃረበ ጊዜ ወደተቀባው የትራፊክ መስመር ቀድሞ ለገባው አሽከርካሪ ቅድሚያ መስጠት አለበት፡፡[87]

25. **ወደ ዋና መንገድ ስለመግባት**

ማንኛውም አሽከርከሪ ከግል መንገድ፣ ከአጥር ግቢ፣ ከቤት መውጫ ወይም ከሌላ መንገድ ወጥቶ ወደ ዋና መንገድ ለመግባት በፈለገ ጊዜ የእግረኞችን መሔጃ ወይም የመንገዱን ጠርዝ ከመሻገሩ በፊት ለእግረኞችና በዋናው መንገድ ለማለፍ ለተቃረቡት ተሽከርካሪዎች ሁሉ ቅድሚያ መስጠት አለበት፡፡

26. **ከእግረኞች ማቋረጫ መንገድ ላይ ስለመቃረብ**

ማንኛውም አሽከርካሪ ከእግረኞች ማቋረጫ መንገድ ላይ ወይም የእግረኛ መንገድ በሌለበት ተሽከርካሪዉ በሚሔድበት አቅጣጫ ለትራፊክ የተመደበ የመንገድ ክፍል በተቃረበ ጊዜ የተሽከርካሪውን ፍጥነት መቀነስና እግረኞቹ ካሉ መንገዱን ጨርሰው እስኪሻገሩ ድረስ ተሽከርካሪውን ማቆም አለበት፡፡

27. **ለአደጋ አገልግሎት ተሽከርካሪዎች**

1. የአደጋ አገልግሎት ተሽከርካሪ በተቃረበ ጊዜ ከፊት ለፊት መንገድ ላይ የሚገኙ ትራፊኮች ሁሉ የሚከተለውን መፈጸም አለባቸው፡-
   ሀ) አሽከርካሪዎች ተሽከርካሪዎቻቸዉን በፍጥነት ከመንገዱ ወደ ቀኝ ጠርዝ መንዳትና አደጋ በማያደርስ ርቀት ላይ የአደጋ አገልግሎት ተሽከርካሪው እስኪያልፍ ድረስ ማቆም አለባቸዉ፤

[87] በ23/8(2009) ደ.395 አንቀፅ 2(9) መሰረት አዲስ የገባ ነው፡፡

ለ) በመንገዱ ላይ የሚገኙ እግረኞች ወይም እንስሳትን የሚጠብቁ ወይም የሚነዱ ሁሉ እንስሳትን ይዘው መንገዱን በፍጥነት መልቀቅ አለባቸው፡፡

2. ተሽከርካሪዉ የአደጋ አገልግሎት ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም የተሽከርካሪ አሽከርካሪ ወይም ተሳፋሪው ከተሽከርካሪው ላይ ቀይ ወይም ሰማያዊ ብርሃን እንዲያሳይ ወይም በፉጨትም ሆነ ወይም በደወል የማስጠንቀቂያ ምልክት እንዲሰጥ አይፈቀድለትም፡፡

28.<u>ስለአደጋ አገልግሎት ተሽከርካሪዎች ልዩ ሁኔታዎች</u>

1. ማንኛውም የአደጋ አገልግሎት አሽከርካሪ ተግባሩን በሚያከናዉንበት ጊዜ በተቻለ ሁኔታ ተግባሩ በሚፈልገዉ መጠን፡-

ሀ) በዚህ ደንብ ወይም በሌላ ህግ የተደነገገውን ግዴታ ሳይጠብቅ ተሽከርካሪውን ለማቆም፤

ለ) አደጋ እንዳይደርስ በሚበቃ አኳኋን የተሽከርካሪዉን ፍጥነት ቀንሶ ቁም በሚል ምልክት ላይ ሳይቆም ለማለፍ፤

ሐ) ከተወሰነዉ ፍጥነት በላይ ለመንዳት፤ እና

መ) ተግባሩን ለመፈጸም በሚያስፈልገዉ መጠን ስለትራፊክ የወጡትን ድንጋጌዎችና የመንገድ ምልክቶች ሳይመለከት በፈቀደዉ አቅጣጫ ለመጠምዘዝ፤

ተፈቅዶለታል፡፡

2. ማንኛውም የአደጋ አገልግሎት አሽከርካሪ ከተፈቀደለት ተግባር ውጭ ለሆኑ ለሌሎች ጉዳዮች ተሽከርካሪውን መጠቀም የለበትም፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የአደጋ አገልግሎት አሽከርካሪ በዚህ ደንብ በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (4) (ሀ) እና (ለ) የተደነገገውን ግዴታ ማክበር አለበት፡፡

4. ቀድሞ የሚሔደዉ የአደጋ አገልግሎት ተሽከርካሪ በሚፈጽመው ተግባር ተካፋይ ለመሆን የሚከተል የሌላ የአደጋ አገልግሎት አሽከርካሪ ካልሆነ በቀር ማንኛውም አሽከርካሪ ከአንድ መቶ ሜትር ባነሰ ርቀት ከአንድ የአደጋ አገልግሎት ተሽከርካሪ ኋላ ተጠግቶ መንዳት የለበትም፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ተሽከርካሪን ስለማቆም</u>

29.<u>ተሽከርካሪን እንዳይቆም ስለሚከለከልበት ሁኔታ</u>

የዚህ ደንብ አንቀጽ 9 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1. ከከተማ ክልል ውጭ በሆነ በማንኛውም መንገድ ላይ ተሽከርካሪ የሚያሽከረክር ማን ኛውም አሽከርካሪ ከመንገድ ላይ ለተሽከርካሪዉ ማቆሚያ ቦታ ከሌለ በስተቀር ከተሽከርካሪው ቢወርድም ባይወርድም ትራፊክ በብዛት በሚተላለፍበት መንገድ ላይ ለጊዜው ወይም ለረጅም ጊዜ፤
2. ማንኛውም አሽከርካሪ የመንገዱ ስፋት ከ12 ሜትር በላይ ካልሆነ በቀር ተሽከርካሪውን ከሌላ ተሽከርካሪ ተቃራኒ አንጻር ከመንገድ ላይ ለጊዜው ወይም ለረጅም ጊዜ፤
3. ማንኛውም አሽከርካሪ በዚያው መንገድ የሚነዳ የሌላ ተሽከርካሪ አሽከርካሪ ከሁለቱም አቅጣጫ ከ50 ሜትር ርቀት ላይ ለማየት በማይቻልበት ሁኔታ በመንገድ ላይ፤

ተሽከርካሪውን ማቆም የለበትም፡፡

30.**ስለማሰናከል**

ማንኛውም አሽከርካሪ ሌላውን ተላላፊ በሚያሰናክል ወይም በሚከለክል ወይም ሌሎች የመንገዱ ተጠቃሚዎች የመንገዱን ምልክት በግልፅና በነፃነት ለማየት በማያስችላቸው ሁኔታ ተሽከርካሪውን ለጊዜው ወይም ለረጅም ጊዜ ማቆም የለበትም፡፡

31.**ተሽከርካሪን ለጊዜዉ ወይም ለረጅም ጊዜ ማቆም የተከለከለባቸዉ ሥፍራዎች**

ማንኛውም አሽከርካሪ ከሌላ ትራፊክ ጋር እንዳይጋጭ ለመከላከል ወይም ማናቸውንም ሌላ ህግ ለመፈጸም ካልሆነ በስተቀር፤

1. መንገዱ ባለአንድ አቅጣጫ ሆኖ አግባብነት ያለው አካል ካልፈቀደ በስተቀር በማናቸውም መንገድ በስተግራ፤
2. በእግረኛ መሂጃ ላይ፤
3. በመስቀለኛ መንገድ ውስጥ ወይም ከመስቀለኛ መንገድ በ12 ሜትር ውስጥ፤
4. በግል መንገድ፣ ተሽከርካሪዎች በሚተላለፉበት የቤት መዉጫ ወይም መግቢያ ወይም የመንገዱ ስፋት ከ12 ሜትር ያነሰ ሆኖ ሲገኝ፤
5. የጎርፍ ማስተላለፊያ ፉካ ካለበት በ5 ሜትር ውስጥ፤
6. በእግረኛ ማቋረጫ ውስጥ ወይም ከእግረኛ ማቋረጫ በ12 ሜትር ውስጥ፤
7. ቁም የሚል ምልክት ወይም የመንገድ ምልክት ካለበት ሥፍራ በ12 ሜትር ውስጥ፤
8. በሐዲድ መንገድ ማቋረጫ ከሚቀርበው ሐዲድ በ12 ሜትር ውስጥ፤
9. ከእሳት አደጋ ጣቢያ ወይም የመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ ከሚሰጥበት ጣቢያ ወይም ሆስፒታል መግቢያ በ12 ሜትር ውስጥ ወይም ከመግቢያው መካከል ጀምሮ

ከመንገዱ ግራና ቀኝ በ25 ሜትር ውስጥ፤ ይሁን እንጂ በሽተኛ ወይም የተጎዳ ሰው ወይም የአደጋ መከላከያ መሣሪያ ይዘው ከዚሁ ከተጠቀሱት ጣቢያዎች የሚወጡ ወይም የሚገቡ ተሽከርካሪዎች በእነዚህ ሥፍራዎች ሊቆሙ ይችላሉ፤

10.በመንገድ ጥግ ቆሞ ከሚገኝ ሌላ ተሽከርካሪ ጋር ተደርቦ፤

11.በድልድይ ወይም በመሿለኪያ ላይ፤

12.ከአውቶቡስ ማቆሚያ በስተኋላና በስተፊት በ15 ሜትር ውስጥና የመንገዱ ስፋት ከ12 ሜትር በላይ ካልሆነ በቀር በመንገዱ አንጻር ከአውቶቡስ ማቆሚያ በ30 ሜትር ውስጥ፤ ወይም

13.በእያንዳንዱ አቅጣጫ ለትራፊክ አንድ ነጠላ መንገድ ብቻ ባለበትና መንገዱ በነጭ ቀለም በተከፋፈለበት ሥፍራ፤

ተሽከርካሪውን ለአጭር ወይም ለረጅም ጊዜ ማቆም የለበትም፡፡

32.<u>ተሽከርካሪን ስለማቆም</u>

1. ማንኛውም አሽከርካሪ እርሱ በሌለበት ጊዜ ተሽከርካሪው ከቆመበት ሥፍራ እንዳይነሳ ወይም እንዳይንቀሣቀስ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ከላደረገ በቀር ተሽከርካሪውን በማንኛውም መንገድ ላይ አቁሞ መሄድ የተከለከለ ነው፡፡
2. ማንኛውም አሽከርካሪ ሞተሩን ሳያጠፋና ማስነሻውን ሳይቆልፍ፣ የማንሻውን ቁልፍ ሳያነሳና እጅ ፍሬን ወይም ተሽከርካሪው ከቆመበት ሥፍራ እንዳይንቀሳቀስ የሚያደርገውን ሌላውንም መሣሪያ ሳያጠብቅና በሮቹን ሳይዘጋ ተሽከርካሪዉን ትቶ መሄድ የተከለከለ ነው፡፡
3. ማንኛውም አሽከርካሪ ተሽከርካሪዉን ከቁልቁለት መንገድ ላይ ባቆመ ጊዜ የተሽከርካሪዉን የፊት እግሮች ከመንገዱ በጣም ወደሚቀርበው ጠርዝ መመለስ አለበት፡፡
4. የድንጋይ ጠርዝ ባለበት መንገድ ላይ ተሽከርካሪውን ለአጭር ወይም ለረጅም ጊዜ የሚያቆም ማንኛውም ሰው ከድንጋይ ጠርዝ በጣም የሚቀርበውን የተሽከርካሪው እግር ከ40 ሜትር እንዳይርቅ አድርጎ ከድንጋይ ጠርዝ በትይዩ መስመር ማቆም አለበት፡፡ ሆኖም ሥራው የሚመለከተው ባለሥልጣን ተሽከርካሪው በማዕዘናዊ አቅዋም እንዲቆም ፈቅዶ ምልክት ባደረገበት መንገድ ላይ ይህ ድንጋጌ አይፀናም፡፡

5. ማንኛውም አሽከርካሪ በማብሪያ ጊዜ ተሽከርካሪውን በመንገድ ላይ ሲያቆም የማቆሚያ መብራት ማብራት አለበት፡፡

## 33.የትራፊክ ተቆጣጣሪ ሥልጣን

1. የዚህ ደንብ አንቀጽ 9 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ትራፊክ ተቆጣጣሪ፡-
   ሀ) ተሽከርካሪ እንዳይቆም ከተከለከለበት መንገድ ላይ ቆሞ ባገኘ ጊዜ ተሽከርካሪውን ወዲያው እንዲያነሣ አሽከርካሪውን ወይም ተሽከርካሪውን በኃላፊነት የተረከበውን ሰው ማዘዝ፤
   ለ) ተላላፊዎችን የሚያሰናክሉ ነገሮችን ለማስቀረት አስፈላጊ መስሎ ሲታየው ተሽከርካሪውን በማንኛውም ሥፍራ እንዲያቆም ወይም ተሽከርካሪውን ከቆመበት ሥፍራ ወደ ሌላ እንዲያዛውር ማንኛዉም የተሽከርካሪ አሽከርካሪ ወይም ተሽከርካሪውን በኃላፊነት የተረከበውን ሰው ማዘዝ፤
   ሐ) አንድ ተሽከርካሪ በግጭት ወይም በመገልበጥ ምክንያት መንገድ ዘግቶ ቢገኝ የተሽከርካሪው ባለንብረት ወይም አሽከርካሪዉ ተሽከርካሪውን በአስቸኳይ እንዲያስነሳ ለማድረግ፤
   መ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ) እና (ሐ) በተደነገገው መሠረት አሽከርካሪው ወይም ተሽከርካሪውን በኃላፊነት የተረከበው ሰው ከትራፊክ ተቆጣጣሪዉ የተሰጠውን ትእዛዝ ሳይፈጽም ቢቀር ወይም በዚያን ጊዜ ከሥፍራው ባይገኝ ተሽከርካሪውን ለማንሳት ወይም እንዲነሣ በማድረግ፤

   ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት አንድ ተሽከርካሪ ከቆመበት ሥፍራ እንዲነሣ በፈለገ ጊዜ የተባለውን ተሽከርካሪ ወደ ጋራዥ ወይም አደጋ ወደማያሠጋበት ሌላ ሥፍራ ለማዛወር ይችላል፡፡ ይህንን በሚያደርግበት ጊዜ ስለተሽከርካሪው ደኅንነት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፡፡ ትራፊክ ተቆጣጣሪው ይህንን ለመፈፀም ያወጣውን ወጪ የተሽከርካሪው ባለቤት ይሸፍናል፡፡

## 34. ስለተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ

1. ማናቸውም መንገድ በከተማ ክልል ውስጥ በተቻለ መጠን ለተሽከርካሪ መቆሚያነት ሳይሆን ለትራፊክ እንቅስቃሴ ክፍት መሆን አለበት፡፡
2. የከተማ አስተዳደር በከተማው ክልል ውስጥ ከመንገድ ውጭ በቂ የሆነ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ እንዲዘጋጅ ማድረግ አለበት፡፡

## ክፍል ስድስት

## የመንገደኛ ማመላለሻ

### 35. ስለመሳፈርና መዉረድ

1. ማንኛዉም ሰው ተሽከርካሪው ጨርሶ ሳይቆም ከተሽከርካሪ ላይ መውጣት ወይም መዉረድ የለበትም፡፡
2. ከአሽከርካሪዉ በስተቀር ማንኛዉም ሰዉ ከተሽከርካሪ ላይ መውጣት ወይም መዉረድ የሚፈቀድለት ተሽከርካሪዉ የቆመዉ ከመንገዱ በስተቀኝ እንደሆነ በስተቀኝ በኩል ወይም ተሽከርካሪዉ የቆመዉ ከመንገዱ በስተግራ እንደሆነ በግራ በኩል ብቻ ነዉ፤
3. ተሽከርካሪ ላይ ለመዉጣት ወይም ከተሽከርካሪ ለመውረድ የተለየ ቦታ፣ መዝጊያ ወይም ሌላ መግቢያ ያለ እንደሆነ ማንኛዉም ሰዉ በዚያው መግቢያ ካልሆነ በቀር ተሽከርካሪው ላይ መውጣት ወይም መውረድ የለበትም፡፡

### 36. መንገደኞችን ስለማጓጓዝ

1. ማንኛውም አሽከርካሪ ተሽከርካሪው የሞተር ብስክሌት ወይም ብስክሌት ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ሰው ከተሽከርካሪው አካል በስተውጭ እንዲሳፈር መፍቀድ የለበትም፡፡ አሽከርካሪውም ለተሳፋሪዎች ደህንነትና ምቾት በሚስማማ አኳሃን ማጓጓዝ አለበት፡፡
2. ማንኛውም አሽከርካሪ የተሽከርካሪው በሮች ካልተዘጉ፣ እንዳይከፈቱ ሆነዉ ካልተጠበቁና ወደ ተሽከርካሪው በሚወጡበት ወይም ከተሽከርካሪዉ በሚወርዱበት ወይም በተሽከርካሪው ዉስጥ ባለዉ ወይም ወደ ተሽከርካሪው በተቃረበዉ ማንኛውም ሰዉ ላይ አደጋ እንዳይደርስ ለማረጋገጥ ተገቢዉን ጥንቃቄ ካልወሰደ በቀር ተሽከርካሪውን ማንቀሳቀስ ወይም ማሽከርከር የለበትም፡፡
3. ማንኛውም ሰው ማንኛውም ተሽከርካሪ በመንቀሳቀስ ላይ ባለበት ጊዜ ወይም በሌሎች ተላላፊዎች ላይ አደጋ እንዳይደርስ ተገቢውን ጥንቃቄ ካላደረገ በስተቀር የማንኛዉንም ተሽከርካሪ በር መክፈት የለበትም፡፡
4. ማንኛውም አሽከርካሪ በተጓዦች ጤንነት ላይ ጉዳት የሚያደርስ ወይም ሊያደርስ የሚችል መርዝን፣ በሽታን፣ መጥፎ ሽታን፣ ጨረርን፣ ድምጽን፣ ንዝረትን፣ ሙቀትን ወይም ሌላ ክስተትን የሚያመነጭ ማንኛውንም ነገር ወይም ሌላ ቁሳቁስ ከተሳፋሪዎች ጋር አብሮ መጫን የለበትም፡፡

5. ተሳፋሪዎችን በመቀመጫ ልክ የሚያሳፍር አሽከርካሪ ተሳፋሪዎች መቀመጣቸውን ሳያረጋግጥ ተሽከርካሪውን ማንቀሳቀስ የለበትም፡፡

**37.<u>አሽከርካሪዉ አጠገብ ስለሚቀመጡ መንገደኞች</u>**

ማንኛዉም አሽከርካሪ ከግንባር በቀኝ በኩል ባለዉ መቀመጫ ከአንድ መንገደኛ በላይ ማስቀመጥ አይችልም፤ ይሁን እንጂ የተሽከርካሪዉ የፊት ለፊት መቀመጫ ስፋት በቂ መሆኑ በባለሥልጣኑ ሲፈቅድ ሁለት መንገደኞች ለማስቀመጥ ይቻላል።

**38.<u>መንገደኛን ስለማሳፍር</u>**

1. የጭነት ተሽከርካሪ የሚያሽከረክር ማንኛውም አሽከርካሪ በአሽከርካሪዉ መቀመጫ ክፍል ካልሆነ በስተቀር እንደዚህ ባለው ተሽከርካሪ ላይ ማንኛውንም ሰዉ ማሳፈር የለበትም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የጭነት ተሽከርካሪው፡-
   ሀ) መንገደኞችን ያለ አንዳች አደጋ በማሳፈር ተሽከርካሪው ተስማሚና በቂ ዝግጅት ካለዉ፤
   ለ) አደጋ የማያስከትል መቀመጫ ካለዉ፤ እና
   ሐ) መንገደኞች በዚሁ መቀመጫ ላይ ብቻ የሚቀመጡ መሆኑን፤
   
   በማረጋገጥ አግባብነት ባለው አካል ሕዝብ ለማመላለስ ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) የተደነገገው በማንኛውም መከላከያ ኃይል ወይም በፖሊስ ሠራዊት ተሽከርካሪዎች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**39.<u>ትርፍ ሰዉ ስለማሳፈር</u>**

1. ማንኛውም አሽከርካሪ ተሽከርካሪው በህግ ከተፈቀደለት የማሣፈር አቅም በላይ ማሳፈር የለበትም፡፡
2. ማንኛውም የሕዝብ የመንገድ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ትርፍ ሰው አሣፍሮ ሲጓዝ ቢገኝ የትራፊክ ተቆጣጣሪው ወዲያውኑ ትርፉን ተሣፋሪ እንዲወርድ በማድረግ አሽከርካሪውን ይከሳል፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ ቢኖርም ከአካባቢው ርቆ እና ለደህንነት አስጊ ከሆነ የዚህ አሽከርካሪ በተቻለ መጠን ቀርብ ወደሆነው ከተማ ተሣፋሪውን በትራፊክ ተቆጣጣሪው አጀቢነት ፍጥነቱን በመቀነስ እንዲጓዝ በማድረግ ማውረድ አለበት፡፡ በመሆኑም ለዚህ የወጣውን ወጪ አሽከርካሪው ወይም ባለንብረቱ ይከፍላል፡፡

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ከተሽከርካሪው የመጫን አቅም በላይ የሆነ መቀመጫ ወይም ማንኛውንም እንደመቀመጫ የሚያገለግልን ነገር በተሽከርካሪው ላይ ተገጥሞ ወይም ተቀምጦ ሲያገኝ የትራንስፖርት ተቆጣጣሪው ይኸው እንዲነሳ ወይም ከተሽከርካሪው ላይ እንዲያወርድ አሽከርካሪውን ለማዘዝና ይኸው እስኪፈፀም ድረስም ተሽከርካሪው እንዲቆም ለማድረግ ይችላል፡፡[88]

40.**ሕፃናትን ስለማሳፈር**

1. ማንኛውም አሽከርካሪ በተሽከርካሪው ላይ ከሰባት ዓመት በታች የሆነ ህፃን በሚያሣፍርበት ጊዜ አደጋ እንዳይደርስበት ከአዋቂ ጋር መሆኑን ወይም ለደህንነት ሲባል በተሠራ መሣሪያ መታቀፉን ማረጋገጥ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዕድሜያቸው ከ 13 ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናትን በአሽከርካሪው ጎን በሚገኘው የመኪናው የፊተኛው ክፍል ማስቀመጥ የለባቸውም፡፡[89]

**ክፍል ሰባት**

**ዕቃዎችን ስለማመላለስ**

41.**የንግድ ሸቀጦች አጫጫን**

1. ማንኛውም አሽከርካሪ፡-
   ሀ) የተሽከርካሪው አሠራር ዕቃዎችን ያለአደጋ ለመጫን ወይም ፈሳሽን ለማጓጓዝ ተስማሚና በቂ ዝግጅት ከሌለዉ፤
   ለ) ጭነቱ ከተሽከርካሪ ጎን ተርፎ የሚወጣ ከሆነ፤
   ሐ) ጭነቱ ከተሽከርካሪው በስተፊት ባለው ጫፍ ከአንድ ሜትር በስተኋላ ከተሽከረካሪው፣ ከተሳቢው ወይም ከግማሽ ተሳቢዉ አካል ከሁለት ሜትር በላይ ተርፎ የሚወጣ ከሆነ፤
   መ) ጭነቱ አሽከርካሪው ወደፊት ወይም ወደ ጎን እንዳያይ የሚከለከል፣ በሚያሽከረክርበት ጊዜ የአሽከርካሪውን እንቅስቃሴ የሚያሰናክል ወይም ወደ አሽከርካሪው መቀመጫ እንደልብ ለመግባት ወይም ለመውጣት የሚከለክል ከሆነ፤ እና

[88] በ23/8(2009) ደ.395 አንቀፅ 2(10) መሰረት አዲስ የገባ ነው፡፡
[89] በ23/8(2009) ደ.395 አንቀፅ 2(11) ተሻሻለ፡፡

ሠ) የሚጓጓዙ ዕቃዎችን ጥራት የሚያበላሽ ወይም ጥራታቸውን የሚቀንስ ከሆነ፤ በማንኛውም ተሽከርካሪ ውስጥ ወይም በላዩ ላይ ማንኛውንም ዓይነት ዕቃ፣ ፈሳሽ ወይም ሽቀጥ መጫን ወይም እንዲጫን ማድረግ የለበትም፡፡

2. ማንኛውም አሽከርካሪ ከሚጭናቸው ዕቃዎች ባህሪ አንጻር ተገቢውን ተሽከርካሪ መጠቀም አለበት፡፡

3. ሁለት ተሽከርካሪዎች ተቀጣጥለዉ በርዝመቱ ምክንያት በአንድ ተሽከርካሪ ብቻ ሊጫን የማይቻል ጭነት በአንድነት የሚጭኑ ሲሆን ሁለቱ ተሽከርካሪዎች በዚህ አንቀጽ ለተመለከተዉ ዓላማ እንደ አንድ ተሽከርካሪ ይቆጠራሉ።

4. ባለሥልጣኑ ዕቃዎችና እንስሳት ስለሚጫኑበት ወይም ስለሚጓጓዙበት ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 42.<u>ተራፊ ጭነት ላይ ምልክት ስለማድረግ</u>

1. በዚህ ደንብ በአንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ) የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የአንድ ተሽከርካሪ ጭነት ከተሽከርካሪው ግንባር ወይም ከኋላ ትርፍ ሆኖ ሲገኝ አሽከርካሪው በተራፊዉ ጭነት ላይ፤

   ሀ) መብራት በሚበራበት ጊዜ ከፊት ተርፎ በሚገኘው ጭነት ጫፍ ነጭ ወይም ቢጫ፤ ከኋላ ተርፎ በሚገኘው ጭነት ላይ ቀይ መብራት፤

   ለ) መብራት በማያስፈልግበት ጊዜ በተራፊዉ ጭነት ላይ በኋላ ጫፍ ቢያንስ ሠላሳ ሳንቲ ሜትር ካሬ የሆነ ቀይ ጨርቅ ወይም ቀይ ቀለም የተቀባ ጠፍጣፋ ሠሌዳ፤

   ማድረግ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) እና (ለ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተራፊ ጭነት ላይ ምልክት ስለማድረግ በሚመለከት ባለሥልጣኑ መመሪያ ያወጣል፡፡

## 43.<u>ጭነትን ስለማሰር</u>

ማንኛውም አሽከርካሪ ጭነቱና የጭነቱ መሸፈኛ እንዳይወድቅ ወይም እንዳይፈታ አድርጎ በጥብቅ ሳያስር በማናቸውም መንገድ ላይ ተሽከርካሪን ማሽከርከር የለበትም፡፡

## 44.<u>በህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ላይ የሚደረግ ልዩ ክልከላ</u>

1. ማንኛውም አሽከርካሪ በማንኛውም የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ዕቃ መጫኛ አቃፊ ጎን በላይ የሆነ ጭነት ጭኖ ማሽከርከር የለበትም፡፡

2. ማንኛውም አሽከርካሪ ከህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪው አካል ውጭ ወደ ፊት ወይም ወደ ኋላ የሚተርፍ ዕቃ ጭኖ በማንኛውም መንገድ ላይ ማሽከርከር የለበትም፡፡

45. **የሚበኑ ወይም የሚበተኑ ነገሮችን ስለመጫን**

ማንኛውም አሽከርካሪ በተሽከርካሪው መንቀሳቀስ ወይም በንፋስ ኃይል ምክንያት እንዳይቦን ለመከላከል ጭነቱን በሚገባ ሳይሸፍን አሸዋ፣ አፈር ወይም ሌሎች የሚበኑ ወይም የሚበተኑ ተመሳሳይ ነገሮች መጫን የለበትም፡፡

46. **በመንገድ ላይ የፈሰሱትን ነገሮች መጥረግ ግዴታ ስለመሆኑ**

የተሽከርካሪው ጭነት በመንገድ ላይ የሚፈስ ሲሆን ወይም ፈሶ ቢገኝ አሽከርካሪው ተሽከርካሪውን አቁሞ ጭነቱ መፍሰሱን እንዳይቀጥል አስፈላጊውን ጥንቃቄ ካላደረገና አስቀድሞ መንገድ ላይ የፈሰሰውን ካልጠረገ ወይም እንዲጠረግ ካላደረገ በቀር ጉዞውን መቀጠል የለበትም፡፡

47. **የትራፊክ ተቆጣጣሪ ሥልጣን**

ማንኛውም የትራፊክ ተቆጣጣሪ በዚህ ክፍል የተደነገገውን በመተላለፍ ዕቃ የጫነ ተሽከርካሪ ሲያገኝ የተጣሰው ድንጋጌ እስኪከበር ድረስ ተሽከርካሪውን እንዲያቆምና ጉዞውን እንዳይቀጥል አሽካርካሪውን ማዘዝ አለበት፡፡

## ክፍል ስምንት

## ስለሚጎተት ተሽከርካሪ፤ ስለመጫወቻ ተሽከርካሪ፤ ስለሞተር ብስክሌት እና ብስክሌት

48. **ተሽከርካሪን ስለመጎተት**

1. አንድ ተሽከርካሪ በሌላ የሞተር ተሽከርካሪ በሚጎተትበት ጊዜ በመካከላቸው ያለው ርቀት ከሦስት ሜትር የማይበልጥ ሆኖ ሁለቱ ተሽከርካሪዎች በሽቦ ገመድ ወይም በጠንካራ የመሳቢያ የብረት ዘንግ በጥብቅ አለባቸው፡፡
2. በሽቦ ገመድ ወይም በመሳቢያው የብረት ዘንግ ላይ በጉልህ ሊታይ የሚችል ቀይ ቀለም የተቀባ ጨርቅ ወይም ሠሌዳ መደረግ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሠረት አንድ ተሽከርካሪ በሚጎተትበት ጊዜ ለሚከተለው አሽከርካሪ ግልጽ ሆኖ ሊታይ በሚቻልበት ሥፍራ ላይ በሚጎተተው ተሽከርካሪ ኋላ ቀይ ቀለም የተቀባ ጨርቅ ወይም ሠሌዳ ማድረግ አለበት፡፡

4. ማንኛውም የሞተር ተሽከርካሪ በአንድ ጊዜ ከአንድ ተሽከርካሪ በላይ እንዲጎትት አይፈቀድም፡፡

49.**የመጫወቻ ተሽከርካሪዎች**

ማንኛውም ሰው ለመጫወቻና ለጊዜ ማሳለፊያ ተብሎ የተሠራ ብስክሌት ወይም በጫማ መልክ የሚጠለቅ ተንሸራታችና ሌሎች መጫዎቻዎችን ለሌሎች ተሽከርካሪዎች ክፍት በሆነ በማንኛውም መንገድ ላይ ማሽከርከር የተከለከለ ነው፡፡

50.**ሞተር ብስክሌት ስለመንዳት**

1. ማንኛውም የሞተር ብስክሌት አሽከርካሪ በተዘጋጀዉ ኮርቻ ተመቻችቶ ሳይቀመጥና ለአሽከርካሪዉ ተብሎ የተሰራውን ምቹ ቆብ (ሄልሜትን) እና ሌሎች አልባሳት በአግባቡ ሳያደርግ በማንኛውም መንገድ ላይ ሞተር ብስክሌት መንዳት የተከለከለ ነው፡፡
2. ማንኛውም አሽከርካሪ ግራና ቀኝ እግሮቹን ከሞተር ብስክሌቱ በሁለቱም ጎን ላይ ሳያደርግ ሞተር ብስክሌት መንዳት የተከለከለ ነው፡፡
3. ማንኛውም አሽከርካሪ ከአሽከርካሪው መቀመጫ ኋላ ለመፈናጠጫ በተዘጋጀው መቀመጫ ወይም በስተጎን ባለው ተቀጣይ ተሽከርካሪ ካልሆነ በስተቀር እንዲሁም ተሣፋሪው ምቹ የሆነ ቆብ (ሄልሜትን) በአግባቡ ሳያደርግ በሞተር ብስክሌቱ ላይ ማንኛዉም ሰው ማሳፈር የተከለከለ ነው፡፡
4. ማንኛውም የሞተር ብስክሌት አሽከርካሪ በሞተር ብስክሌቱ ላይ ዕቃን ለመጫን ተብሎ ከተሰራለት የዕቃ መጫኛ ሳጥን ውጪ ማናቸውንም ዓይነት ጭነት መጫን ወይም ከአንድ ሰው በላይ ማሳፈር የለበትም፡፡[90]
5. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው አገልግሎት እንዲሰጥ ታስቦ ሽፋን በተገጠመላቸዉ ሞተር ብስክሌትቶች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

51.**ብስክሌት ስለመንዳት**

1. ማንኛውም ሰዉ ብስክሌቱ በመልካም ሁኔታና አሠራሩም ለመንገድ ተስማሚ ካልሆነ በስተቀር መንዳት የተከለከለ ነው፡፡
2. ማንኛውም ሰው ለአሽከርካሪው ተብሎ በብስክሌቱ ላይ በተዘጋጀው መቀመጫ ላይ ተመቻችቶ ሳይቀመጥ ማንኛውንም ብስክሌት መንዳት የተከለከለ ነው፡፡

[90] በ23/8(2009) ደ.395 አንቀፅ 2(12) ተሻሻለ፡፡

3. ማንኛውም ብስክሌት አሽከርካሪ ብስክሌቱን በሚነዳበት ጊዜ የብስክሌቱን መሪ በእጆቹ ሳይዝ በእግሮቹም የብስክሌቱን ማሽከርከሪያ ሳይቆነጥጥ መንዳት የተከለከለ ነው፡፡
4. ማንኛውም ሰው ብስክሌት ሲነዳ ብስክሌቱን ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር የሚከለክል ማንኛዉንም ጥቅል፣ ጭነት ወይም ዕቃ መጫን የለበትም፡፡ ቢጭንም የዕቃዉን ርዝመት ወይም ስፋት በማናቸውም አኳኋን ከ70 ሳንቲ ሜትር መብለጥ የለበትም።
5. ማንኛውም ሰው ብስክሌት በሚነዳበት ጊዜ በማንኛውም አኳኋን በመንዝ ላይ ያለ ሌላ ተሽከርካሪ መያዝ ወይም ራሱ ወይም ብስክሌቱ በሌላ ተሽከርካሪ እንዲጎተት ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡
6. ማንኛውም ብስክሌት አሽከርከሪ ቀድሞ ለመሄድ ካልሆነ በቀር በመንዝ ላይ ካለ ተሽከርካሪ በግራ በኩል እየነዳ መሄድ የተከለከለ ነው፡፡
7. ብስክሌት አሽከርካሪዎች ቅደም ተከተል መሥመርን ይዘው መንዳት አለባቸው፡፡ ሆኖም ለሌላ ትራፊክ እንቅፋት የማይሆኑ ከሆነ ሁለት ብስክሌት አሽከርካሪዎች ብቻ ጎን ለጎን ሆነው ለመንዳት ይችላሉ።
8. ማንኛውም ሰው የማስጠንቀቂያ ደዉልና የተሟላ ፍሬን የሌለው ብስክሌት መንዳት የተከለከለ ነው፡፡
9. ማንኛውም የብስክሌት አሽከርካሪ ብስክሌቱ የተሳፋሪ መቀመጫ ያለው ካልሆነ በስተቀር ሰው አሣፍሮ መንዳት የተከለከለ ነው፡፡
10. ማንኛውም የብስክሌት አሽከርካሪ ባለስልጣኑ በሚያወጣዉ መመሪያ መሠረት የአደጋ መከላከያ ቆብ (ሔልሜት) ማድረግ አለበት፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## ስለ እንስሳት

### 52.እንስሳትን በመንገድ ላይ ስለመንዳት

1. ማንኛውም ሰው በሌላ ሥፍራ መንዳት ሲችል እንስሳትን በማንኛውም መንገድ ላይ መንዳት የለበትም፡፡ ሌላ ሥፍራ ሳይኖር ቀርቶ በመንገድ ላይ መንዳት ግድ ቢሆንበትም ለትራፊክና በመንገድ ለሚጠቀሙት ሁሉ እንቅፋት እንዳይሆንባቸው አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፡፡
2. ማንኛውም ሰው እንስሳትን በመንገድ ላይ ሲነዳ የመንገዱን ቀኝ ጠርዝ ዳር ተከትሎ መንዳት አለበት፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም ሰው በመሀል መንገድ ላይ እንስሳትን መንዳት የተከለከለ ነው፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ የከተማ መስተዳድሮች እንስሳትን በተመለከተ በመንገድ ላይ ስለሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ መመሪያ ሊያወጡ ይችላሉ፡፡

53.<u>እንስሳ ጠባቂ መውሰድ ስለሚገባው ጥንቃቄ</u>

የእንስሳት ጠባቂ በመንገድ ላይ ተሽከርካሪ በሚገጥምበት ወቅት ለተሽከርካሪ መንገድ ለመልቀቅ የሚቻለውን ሁሉ መፈጸም አለበት፡፡

54.<u>የእንስሳ ጠባቂ መብራት መያዝ ስለሚገባው</u>

በማብሪያ ጊዜ እንስሳትን በመንገድ ላይ የሚነዳ ማንኛውም ሰው በጉልህ የሚታይ መብራት ለሚጓዘው ተሽከርካሪ አቅራቢያ በሆነው ጎን መያዝና ማሳየት አለበት፡፡

<u>ክፍል አስር</u>

<u>ስለእግረኞች</u>

55.<u>ተሽከርካሪ በሚሄድበት መንገድ ላይ ስለመሄድ</u>

1. ማንኛውም ሰው፡-

   ሀ) የእግረኛ መሄጃ ከሌለ በስተቀር፤ ወይም

   ለ) መንገድ ለማቋጥ ካልሆነ በስተቀር፤

   ተሽከርካሪ በሚተላለፍበት በማንኛውም መንገድ ላይ መሄድ የለበትም፡፡
2. ማንኛውም ሰው መንገዱን ተከትሎ በሚሄድበት ጊዜ ከፊቱ የሚመጣውን ትራፊክ እየተመለከተ የመንገዱን ግራ ጠርዝ ይዞ መሄድ አለበት፡፡

56.<u>መንገድ ስለማቋረጥ</u>

1. ማንኛውም ሰው የትራፊኩን ብዛትና ሁኔታ አጣርቶ ሳይመረምር በራሱና በሌሎች ተላላፊዎች ጉዳት ሳይደርስ መንገዱን ለማቋረጥ የሚችል መሆኑን ሳያረጋግጥ መንገድ ማቋረጥ የለበትም፡፡
2. ማንኛውም ሰው መንገዱ ለማቋረጥ በፈለገ ጊዜ ተገቢውን ጥንቃቄና ፍጥነት በማድረግ እንዲሁም ያለ በቂ ምክንያት በመንገዱ ላይ ሳይቆም ወይም ሳይዘገይ ቀጥተኛና አጭር በሆነ መስመር ማቋረጥ አለበት፡፡
3. ማንኛውም ሰው መንገድ ለማቋረጥ በፈለገ ጊዜ ከአንድ መጪ ተሽከርካሪ ኋላ ወይም የአንድ መጪ ተሽከርካሪ ኋላ ወይም የአንድ መጪ ተሽከርካሪ አሽከርካሪ ሊያየው ከማይችለበት ከማንኛውም ሥፍራ ላይ መንገድ ማቋረጥ የለበትም፡፡

4. ማንኛውም ሰው በከተማ ክልል መንገድ ለማቋረጥ ምልክት የተደረገበት የእግረኛ ማቋረጫ ወይም ለእግረኛ መሸጋገሪያ የተሠራ ድልድይ ያለ ከሆነ የእግረኛ ማቋረጫውን ወይም መሸጋገሪያ ድልድዩን ብቻ መጠቀም አለበት፡፡
5. ማንኛውም ሰው መስቀለኛን መንገድ በሰያፍ ማቋረጥ የለበትም፡፡

57.<u>ስለአካል ጉዳተኞች</u>

ማንኛውም አሽከርካሪ አካል ጉዳተኛ በሚሳፈሩበት እና መንገዱን በሚጠቀሙበት ጊዜ ጉዳት እንዳይደርስባቸው ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፡፡

58.<u>በመንገድ ውስጥ ስለመቆም</u>

ማንኛውም ሰው ሕጋዊ ተግባሩን ለመፈጸም ካልሆነ በስተቀር ተሽከርካሪ እንዲቆም ለማድረግ፣ ለመሳፈርም ሆነ ለሌላ ጉዳት በማንኛዉም መንገድ ውስጥ መቆም የተከለከለ ነው፡፡

59.<u>በአጥር ስለተከለሉ የእግረኛ መሄጃዎች</u>

የእግረኛ መሄጃ በአጥር የተከለከለ ሆኖ ሲገኝ ማንኛዉም እግረኛ በአጥር ላይ መቀመጥ፣ መደገፍ፣ ከአጥሩ በመንገዱ በኩል መቆም ወይም መዘዋወር የተከለከለ
ነው፡፡

60.<u>በእግረኛ መሄጃ ላይ ስለመቆምና ቁሳቁሶችን ስለማስቀመጥ</u>

1. ማንኛውም ሰው በእግረኛ መሄጃ ላይ ከመቆሙ ወይም ከመዘዋወሩ የተነሳ ተላላፊውን እግረኛ የሚያደናቅፍ የሚሆን ከሆነ በማንኛውም የእግረኛ መሄጃ ላይ መቆም ወይም መዘዋወር የተከለከለ ነው፡፡
2. ማንኛውም ሰው በእግረኛ መሄጃ ላይ የእግረኞች እንቅስቃሴ የሚያውክ ማንኛውንም ቁሳቁስ ወይም ሸቀጥ ማስቀመጥ፣ መነገድ፣ መቆፈር፣ ማበላሸት ወይም በሀዘን ምክንያት ከአቅም በላይ ካልሆነ በስተቀር የተለያዩ ነገሮችን መትከል ወይም ተመሳሳይ ነገሮች ማከናወን የተከለከለ ነው፡፡

61.<u>በእጅ እየተደገፉ ስለሚሽከረከሩ ጋሪዎች</u>

በእጅ እየተገፉ የሚሽከረከሩ የህጻናት፣ የጥቃቅን እቃ መያዣዎች፣ አካል ጉዳተኞች የሚጠቀሙባቸው በእጅ የሚገፉ በሞተር ከሚነዱ ባለመንኮራኩር ወንበሮች በስተቀር ከመንገዱ የሚርቀውን የእግረኛ መሄጃ ክፍል ይዘው መሄድ አለባቸው፡፡

62.<u>ልዩ ሁኔታዎች</u>

በዚህ ደንብ በአንቀጽ 55 እና በአንቀጽ 56 የተደነገገው በሰልፍ ወይም በአስክሬን አጀብ ወይም ይህን በመሳሰለው ተካፋይ በሆኑ ሰዎች ላይ አይጸናም፡፡

## ክፍል አሥራ አንድ

## የመንገድ ምልክቶች እና ማመላከቻዎች[91]

### 63.በአንድ ዓይነት የመንገድ ምልክትና ማመላከቻ ስለመጠቀም[92]

ትራፊክን ለመቆጣጠር ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዘው በሚገኙት እና ወደፊት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ሥራ ላይ እንዲውሉ በሚደረጉ የመንገድ ምልክቶች እና ማመላከቻዎች ካልሆነ በስተቀር በሌላ የመንገድ ምልክት ወይም ማመላከቻ መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡

### 64.የመንገድ ምልክትና ማመላከቻ መትከልና ማንሳት

ባለስልጣኑ የመንገድ ምልክቶችና ማመላከቻዎች እንዲተከሉ፣ እንዲታደሱ፣ እንዲጠገኑ፣ እንዲለወጡ ወይም እንዲነሱ የማድረግ ስልጣን ይኖረዋል፡፡[93]

### 65. የመንገድ ምልክቶችንና ማመላከቻዎችን ማኖር ክልክል ስለመሆኑ[94]

1. በዚህ ደንብ የተፈቀደላቸው ወይም ወኪሎቻቸው ካልሆኑ በስተቀር ማንኛውም ሰው በማንኛውም መንገድ ላይ ወይም በማንኛውም መንገድ አጠገብ የመንገድ ምልክት ወይም ማመላከቻ ወይም እንደ መንገድ ምልክትና ማመላከቻ ያለ ወይም የመንገድ ምልክት ወይም ማመላከቻ መስሎ የሚያሳስት ማናቸውንም ምልክት ወይም ማመላከቻ ማድረግ፣ ማቆም፣ ወይም መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡
2. ማንኛውንም የመንገድ ምልክትና ማመላከቻ ማንሳት፣ ማበላሸት፣ ከቆመበት ማዛወር፣ መለወጥ፣ ወይም በማናቸውም አኳኋን በግልፅ እንዳይታይ ወይም እንዳይነበብ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

## ክፍል አስራ ሁለት

## ስለመብራት

### 66.ስለተሽከርካሪ መብራት ቀለም

---

[91] በ 23/8(2009) ደ.395 አንቀፅ 2(13) ተሻሻለ፡፡
[92] በ 23/8(2009) ደ.395 አንቀፅ 2(14) ተሻሻለ፡፡
[93] በ 23/8(2009) ደ.395 አንቀፅ 2(14) ተሻሻለ፡፡
[94] በ 23/8(2009) ደ.395 አንቀፅ 2(14) ተሻሻለ፡፡

ማንኛውም አሽከርካሪ በስተፊት ቀይ ወይም ሰማያዊ መብራት ወይም ተሽከርካሪዉ በኋላ በሚነዳበት ጊዜ ካልሆነ በስተቀር በኋላው ነጭ መብራት የሚያሳይ የአደጋ አገልግሎት ያልሆነ ተሽከርካሪ ማሽከርከር የለበትም፡፡

67.<u>ስለተሽከርካሪዎች መብራት</u>

1. ማንኛውም አሽከርካሪ የተሽከርካሪውን ሁለቱ የግንባር መብራቶችና የግራና የቀኝ ቀይ የኋላ መብራት ሳይበራና የተሽከርካሪው የኋላ የሰሌዳዉ ቁጥር በቂ ብርሃን እንዲኖረው ሳያደርግ በማብሪያ ጊዜ ተሽከርካሪ ማሽከርከር የለበትም፡፡
2. ማንኛውም አሽከርካሪ፡-
   ሀ) ከሞተር ብስክሌት በስተቀር የተሽከርካሪው ሁለቱ የግምባር የማቆሚያ መብራቶችና ቀይ የኋላ መብራት ካልበራ ወይም የተለየ የማቆሚያ መብራት ተዘጋጅቶ እንደሆነ ተሽከርካሪዉ ከቆመበት መንገድ ወገን ራቅ ብሎ የሚገኘው የማቆሚያ መብራት ካልበራ በስተቀር ፣
   ለ) ሌሎች ተሽከርካሪዎች ሲሆን የማያቋርጥ ነጭ መብራት ካልበራ በስተቀር፤ በማብሪያ ጊዜ ተሽከርካሪውን መንገድ ላይ ማቆም የለበትም፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ በራሳቸው መብራት ሳይሆን ከሌላ የብርሃን ምንጭ በሚያገኙት ብርሃን በግልጽ በሚታዩ ተሽከርካሪዎች ላይ አይጸናም፡፡
4. ማንኛውም አሽከርካሪ ከተሽከርካሪው ስሪት ውጪ የሆኑ ሌሎች ከፍተኛ ኃይል ያላቸው የግንባር መብቶች መግጠምና መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡

68.<u>ስለተሳቢዎች መብራት</u>

1. ከተሳቢው ግንባር በስተግራ ባለው ጫፍ ላይ ነጭ መብራት ካልታየና ከተሳቢው በስተኋላ ቀይ መብራት ካልታየ በስተቀር ማንኛውም አሽከርካሪ በማብሪያ ጊዜ ተሳቢ ያለው የሞተር ተሽከርካሪ ማሽከርከር ተከለከለ ነው፡፡
2. በዚህ ደንብ ለዚህ ክፍል ዓላማ ሲባል ከተሽከርካሪ ጋር ያልተያያዘ ተሳቢ እንደ ሞተር ተሽከርካሪ ሆኖ ይቆጠራል፡፡
3. በዚህ ደንብ ለዚህ ክፍል ዓላማ ሲባል ግማሽ ተሳቢ እሱን የሚስበው የሞተር ተሽከርካሪ አንድ ክፍል ሆኖ ይቆጠራል፡፡ ከሞተር ተሽከርካሪ ጋር ያልተያያዘ ግማሽ ተሳቢ እንደ አንድ የሞተር ተሽከርካሪ ሆኖ ይቆጠራል፡፡

69.<u>ስለማሽኖች</u>

ማንኛውም አሽከርካሪ ከማሽኑ ኋላ ቀይ መብራት ሳይበራ ወይም የቀይ አንጸባራቂ ምልክት ሳያስቀምጥ በማብሪያ ጊዜ ማንኛውንም ምልክት ማሽን በመንገድ ላይ እንዲያሽከረክር ወይም እንዲጎትት አይፈቀድም፡፡

70.<u>ስለሞተር ብስክለቶች መብራት</u>

1. በስተግንባር በኩል አንድ ማብራት በቂ ከመሆኑ በስተቀር ከዚህ ደንብ በአቀጽ 67 ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው በሞተር ብስክሌቶች ላይም የፀና ይሆናል፡፡
2. ከሞተር ብስክሌቱ ጋር የተያያዘ የጎን ተሽከርካሪ ያለ እንደሆነ በዚሁ ተሽከርካሪ በስተግንባር ነጭ፣ በስተኋላ ቀይ መብራቶች ከሞተር ብስክሌቱ ጋር ተያይዞ በሚገኘው የጎን ተሽከርካሪ ላይ ከሞተር ብስክሌቱ በተቃኒ የሚገኘው በኩል ካልበሩ በስተቀር ማንኛውም አሽከርካሪ እንደዚህ ያለውን ሞተር ብስክሌት በማብሪያ ጊዜ ማሽከርከር የለበትም፡፡

71.<u>ስለባለሦስት እግር ሞተር ብስክሌቶች</u>

ከአንድ ባለሦስት እግር ሞተር ብስክሌት የፊት አንድ እግሩ የኋለ ሁለቱን እግሮች በያዘው አክስል በስተግንባር ሲሆን ለዚሁ ክፍል ዓላማ ሲባል እንደዚህ ያለው ባለሦስት እግር ሞተር ብስክሌት እንደ ሞተር ብስክሌት ሆኖ ይቆጠራል፡፡

72.<u>ስለብስክሌቶች መብራት</u>

ከአንድ መቶ ሜትር በማያንስ ርቀት ጉልህ ሆኖ የሚታይ ነጭ መብራት በስተግንባር፣ በስተኋላ ደግሞ ቀይ መብራት ካላበራ በስተቀር ማንኛውም ሰው በማብሪያ ጊዜ ብስክሌት ማሽከርከር የለበትም፡፡

73.<u>ስለመፈተሻ መብራቶች</u>

የአደጋ አገልግሎት ተሽከርካሪዎች ካልሆኑ በስተቀር ማንኛውም አሽከርካሪ ወይም ተሳፋሪ ተሽከርካሪው በመንቀሳቀስ ላይ ሳለ በተሽከርካሪዉ ላይ ያለውን የመፈተሻ መብራት ማብራት የለበትም፡፡

74.<u>የግንባር መብራቶችን ሃይል ስለመቀነስ</u>

ማንኛዉም አሽከርካሪ፡-

1. ያለ አደጋ ለማሽከርከር የመንገዱ መብራት በቂ ካልሆነ በስተቀር በከተማ ውስጥ ሲነዳ፣
2. ከፊት ለፊቱ ሌላ ተሽከርካሪ ሲቃረብና ተሽከርካሪውም እስኪያልፍ ድረስ፣

3. ከሃምሳ ሜትር በሚያንስ ርቀት ሌላውን ተሽከርካሪ ተከትሎ በሚያሽከረክርበት ጊዜ፣ እና
4. ተሽከርካሪን ባቆመበት ጊዜ፣

የተሽከርካሪውን ትልቁን የግንባር መብራት ኃይል ወደ አነስተኛ መብራት ኃይል መቀነስ አለበት፡፡

## ክፍል አስራ ሦስት

## ከአደጋ ስለመጠበቅ

### 75.በቁልቁለት መንገድ ላይ ስለመንዳት

1. ማንኛውም አሽከርካሪ ሞተሩን እንዲሠራ ሳይደርግና ማርሽ ሳያገባ በማንኛዉም መንገድ ላይ የሞተር ተሽከርካሪ ማሽከርከር የለበትም፡፡
2. በቁልቁለት መንገድ የባለሞተር ተሽከርካሪ የሚያሽከረክር ማንኛዉም አሽከርካሪ በቁልቁለቱ ለተሽከርካሪው ዓይነት፣ አሰራርና ክብደት በሚስማማ አነስተኛ ማርሽ መጠቀም አለበት፡፡
3. ማንኛውም አሽከርካሪ ወደ ቁልቁለት መንገድ ከመግባቱ በፊት የተሽከርካሪው መሪ፣ ፍሬንና የተለያዩ የመቆጣጠሪያ መሣሪዎች በአግባቡ የሚሠሩ ለመሆኑ መፈተሻ አለበት፡፡

### 76.መንገድ ላይ ተሽከርካሪን ስለመጠገን

በመንገድ ላይ ተሽከርካሪ የሚጠግን ማንኛውም ሰው የመጠገኑን ሥራ የሚያከናወንበት ሌላ ዘዴ ከሌለ በስተቀር ተሽከርካሪው ካለበት ዙሪያ መሥመር ሰውነቱን ወደ መንገድ አውጥቶና አንጸባራቂ ምልክት ሳያደርግ መጠገን የለበትም፡፡

### 77.ከዕይታ ስለመጋረድ

ማንኛውም አሽከርካሪ፡-

1. በተሽከርካሪው የንፋስ መከለያ፣ የብርሃን ማስተላፊያና የኋላ ትዕይንት ማሳያ መስታወቶች ላይ የሚጋረድ ጭቃ፣ ጤዛ ወይም እንፋሎት እያለ ማሽከርከር የለበትም፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም አሽከርካሪ የተሽከርካሪ ፊት በመሸፈን ወይም በማናቸውም ሁኔታ የአሽከርካሪውን ዕይታ በሚከልል ማንኛውም ነገር ተሽከርካሪውን መጋረድ ወይም መሸፈን የለበትም፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ለህዝብ ማመላለሻና ለተወሰኑ ተሽከርካሪዎች ለፀሐይ መከላከያ ወይም ለሌሎች ሁኔታዎች ሲባል የተሽከርካሪውን አካል መጋረድ ወይም መሸፈን የሚቻልበትን ሁኔታ ባለስልጣኑ ይወስናል፡፡

78.<u>በጠምዛዛ መንገድ ላይ ስለሚደረግ ጥንቃቄ</u>

1. ማንኛውም አሽከርካሪ በጠምዛዛ መንገድ ላይ ሲያሽከረክር፡-
   ሀ) ፍጥነቱን መቀነስ፤ እና
   ለ) ከፊት ለፊቱ ለሚመጣ ተሽከርካሪ የጡሩምባ ድምጽ ማሰማት፤
   አለበት፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ እንደ መንገዱ ሁኔታ የቀኝ ረድፉን ይዞ መጓዝ አለበት፡፡

79.<u>ነዳጅ ስለመሙላት</u>

1. ማንኛውም አሽከርካሪው ተሽከርካሪዉ ሞተር እየሠራ ተሽከርካሪዉ የሕዝብ መመላለሻ ከሆነ በተሽከርካሪው ውስጥ መንገደኞች እያሉ ማንኛውንም ዓይነት ነዳጅ መሙላት ወይም ማስሞላት የለበትም፡፡
2. በተሽከርካሪው አጠገብ እሳት ወይም ሲጋራ የሚያጨስ ሰው ባለበት ማንኛውም ሰው በሞተር ተሽከርካሪዉ ነዳጅ እንዲሞላ ወይም የነዳጁ ጋን መክደኛ እንዲከፈት ወይም ሌላው ሰው ይህን እንዲያደርግ መፍቀድ የለበትም፡፡
3. ማንኛውም ሰው ተሽከረካሪ ነዳጅ ሲሞላ በነዳጅ ማደያው ክልል በ12 ሜትር ክልል ውስጥ በተንቀሳቃሽ ስልክ መነጋገር፣ በሌሎች ኤሌክትሮኒክስ ነክ መሣሪያዎች መጠቀም ወይም ሲጃራ ማጨስ ክልክል ነው፡፡

## <u>ክፍል አስራ አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

80.<u>ከአደጋ ክስተት በኋላ የሚኖር ግዴታ</u>

የመንገድ ትራፊክ አደጋ ሲከሰት በአደጋው ምክንያት ሰው የሞተ ወይም የተጎዳ እንደሆነ ወይም በንብረት ላይ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ግዴታዎች መፈጸም አለባቸው፡-

1. አደጋውን ያደረሰው አሽከርካሪ አደጋው በተከሰተበት ሥፍራ ወይም በተቻለው ፍጥነት በአቅራቢያው ወዲያውኑ ተሽከርካሪውን አቁሞ በዚህ ንዑስ አንቀጽ (2)

በተመለከተው ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር በዚህ አንቀጽ የተወሰነውን ግዴታ ሳይፈጽም ተሽከርካሪውን ከአደጋው ቦታ ማንቀሳቀስ የለበትም፤

2. አደጋ ያደረሰ ማንኛውም አሽከርካሪ በዚሁ አደጋ የተጎዳውን ሰው በአቅራቢያ ወደ ሚገኝ የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ መስጫ ወይም ሆስፒታል በማድረስ ዕርዳታ እንዲሰጠው ማድረግን ጨምሮ የተቻለውን ሁሉ ማድረግ አለበት፤
3. አደጋ ያደረሰ ማንኛውም አሽከርካሪ ለማናቸውም ፖሊስ ወይም ለተጎዳው ሰው ወይም አደጋዉ ለሚመለከተው ለማንኛውም የሌላ ተሽከርካሪ አሽከርካሪ ወይም አደጋው በሚመለከተው ማንኛውም ተሽከርካሪ ለተሳፈረ ማንኛውም ሰው ስሙንና አድራሻን፤ የሚያሽከረክረውን ተሽከርካሪ ባለቤት ስም፣ አድራሻና ተሽከርካሪው ኢንሹራንስ የገባበትን ኩባንያ ስምና አድራሻ ከዚህ በላይ ለተጠቀሱት ለማንኛውም ሰው መስጠትና እንዲሁም የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱንም ማሳየት አለበት፡ ፡

## 81.ስለማስታወቅ

1. የመንገድ ትራፊክ አደጋ ያደረሰ ማንኛውም አሽከርካሪ፡-
   ሀ) በአደጋው ሰው የሞተ ወይም የተጎዳ እንደሆነ ወዲያውኑ ወይም በተቻለ ፍጥነት፤ ወይም
   ለ) ጉዳት የደረሰው በንብረት ላይ እንደሆነ አደጋው ከደረሰ በኋላ ከሃያ አራ ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ፤

   አደጋው በደረሰበት ሥፍራ ለሚገኘው የትራፊክ ተቆጣጣሪ ወይም የትራፊክ ተቆጣጣሪ የሌለ እንደሆነ ለአደጋው ስፍራ ለሚቀርበው የፖሊስ ጽህፈት ቤት መረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት ፡፡
2. በዚህ ደንብ አንቀጽ 80 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በመንገድ ላይ ብቻውን በቆመ ተሽከርካሪ ላይ አደጋ ያደረሰ ማንኛዉም የተሽከርካሪ አሽከረካሪዉን ወዲያውኑ አቁሞ፡-
   ሀ) የሌላውን ተሽከርካሪ አሽከርካሪ መፈለግና የራሱን ስምና አድራሻ መስጠት ወይም
   ለ) የተጎጂው ተሽከርካሪ አሽከርካሪ ወይም የተሽከርካሪው ባለቤት ያለበትን ለማግኘት ባይችል አደጋው በደረሰበት ስፍራ ለሚገኘው የትራፊክ ተቆጣጣሪ ወይም ለሚቀርበው የፖሊስ ጣቢያ ማሣወቅ አለበት፡፡ እንዲሁም ስሙንና አድራሻውን የሚያሽከርክረውን ተሽከርካሪ የሰሌዳ ቁጥርና የአደጋውን አጭር

መግለጫ በጽሑፍ አድርጎ በተሽከርካሪው ላይ ሊታይ በሚችልበት ስፍራ አስቀምጦ መሄድ፤

አለበት፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የትራፊክ አደጋ አድርሰው ሳያስታውቁ በሚያመልጡ አሽከርካሪዎች ላይ የትራፊክ ተቆጣጣሪ አስሮ ምርመራ ሊያደርግ ይችላል፡፡

82.<u>የሌሎች አካላት ተግባር</u>

1. አግባብነት ያለዉ አካል ወይም የትራፊክ ተቆጣጣሪ የዚህ ደንብ ድንጋጌዎችን በአግባቡ ስራ ላይ ለማዋል ለተማሪ ትራፊክ፣ ለደንብ አስከባባሪ እና ፍቃደኛ የትራፊክ ተባባሪ አባላት የትራፊክ ደንብ ሥልጠና በመስጠት የማስተባበርና መረጃ የመስጠት ስራ እንዲያካሂዱ ሊወክል ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የዉክልና ስልጣን ለተሰጣቸዉ ዓላማ ሲባል፡-
   ሀ) "የተማሪ ትራፊክ" ማለት ከተለያዩ ትምህርት ቤቶች የተመለመሉ ተማሪዎች የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ስልጠና ወስደዉ በትምህርት ቤታቸዉ አካባቢ ፍሰቱን የሚያስተባብሩና የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ግንዛቤ የሚሰጡ፤
   ለ) "የመንገድ ደንብ አስከባሪ" ማለት የመንገድ ትራፊክ ፍሰት ላይ መሰናክል እና ችግሮች ሲፈጠሩ መሰናክሉን የሚያስነሱ እና መረጃ የሚሰጡ፤
   ሐ) "ፍቃደኛ የትራፊክ ተባባሪ አባላት" ማለት መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የተዉጣጡ አባላት ሆነዉ መሰረታዊ የትራፊክ ደንብ መተላለፍ ሁኔታ ለትራፊክ ተቆጣጣሪና አግባብነት ላለዉ አካል መረጃ በመስጠት ቁጥጥሩን የሚያግዙ፤

   አካላት ናቸዉ፡፡
3. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (2) ከተራ ፊደል (ሀ) እስከ (ሐ) የተመለከቱት ሥራቸዉን ሲያካሂዱ የፀና የመታወቂያ ወረቀት መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

83.<u>ተሽከርካሪ ባለቤቶች የሚፈጽሙት ግዴታ</u>

1. አደጋ ያደረሰ ወይም ይህን ደንብ ወይም ማንኛዉንም ሌላ ህግ ተላልፏል የተባለ የተሽከርካሪ ባለቤት አደጋዉ ወይም ጥፋቱ በተፈፀመበት ወቅት በሚያዉቀዉ መጠን ተሽከርካሪዉን ያሽከርክር የነበረዉን ሰዉ ስምና አድራሻ ለሚጠይቀዉ ለማንኛውም ፖሊስ መስጠት አለበት፡፡

2. ያለበቂ ምክንያት የተጠየቀዉን መረጃ አልሰጥም የሚል ማንኛዉም የተሽከርካሪ ባለቤት ለፍትህ ባለመተባበሩ ምክንያት በወንጀል ህጉ አንቀፅ 448 መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

84.<u>የተሻረ ህግ</u>

1. የትራንስፖርት ደንብ ቁጥር 279/1956 እንደተሻሻለ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡
2. ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛዉም ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ ደንብ ዉስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረዉም፡፡

85.<u>በደንብ ተላላፊዎች ላይ ስለሚጣል ቅጣት[95]</u>

1. የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች የተላለፈ ማንኛውም አሽከርካሪ ወይም እግረኛ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው "ሠንጠረዥ ለ" መሰረት ይቀጣል፡፡
2. የትራፊክ ተቆጣጣሪ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎችን የተላለፈን አሽከርካሪ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድን ጠይቆ በመቀበል ላጠፋው ጥፋት የሚገባውን ቅጣት እንዲፈፅም የሚያዝ የቅጣት ወረቀት ይሰጠዋል፡፡
3. የትራፊክ ተቆጣጣሪ ወይም በሕግ ሥልጣን የተሰጠው ሌላ ሰው የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች የተላለፈን እግረኛ ወይም ሌላ ማናቸውም ሰው ላጠፋው ጥፋት የሚገባውን ቅጣት እንዲፈፅም የቅጣት ወረቀት ይሰጠዋል፤ ዝርዝር አፈፃፀሙ ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) መሰረት የቅጣት ወረቀት የተሰጠውና በተሰጠው የቅጣት ወረቀት ተገቢነት ላይ ቅሬታ ያደረበት ማንኛውም ሰው፡-

   ሀ) በሁለት የሥራ ቀናት ውስጥ የቅጣት ወረቀቱን ለሰጠው የትራፊክ ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤት ቅሬታውን ለማቅረብ ይችላል፤

   ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) መሰረት ባቀረበው ቅሬታ ላይ በተሰጠው ምላሽ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው አግባብነት ላለው አካል ውሳኔውን ባወቀ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለማቅረብ ይችላል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) እና (3) መሰረት እንደቅደም ተከተሉ ቅጣት የተጣለበት አሽከርካሪ ወይም ማንኛውም ሰው በንዑስ አንቀጽ (4) በተደነገገው መሰረት ቅሬታውን አቅርቦ ቅጣቱን ካላሻረ በስተቀር የተጣለበትን ቅጣት በአስር የሥራ ቀናት ውስጥ መክፈል አለበት፡፡

[95] በ23/8(2009) ደ.395 አንቀፅ 2(16) ተሻሻለ፡፡

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሰረት በአስር የሥራ ቀናት ውስጥ የተጣለበትን ቅጣት ያልከፈለ አሽከርካሪ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው "ሠንጠረዥ ለ" ተራ ቁጥር (2) (ሐ) መሰረት ተጨማሪ ቅጣትና የጥፋት ሪከርድ ይያዝበታል፤ ከአሽከርካሪ ውጪ ቅጣት የተጣለባቸውን ሰዎችን የሚመለከተው ተመሳሳይ አፈፃፀም ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) የተደነገገው ቢኖርም የተጣለበት ቅጣት የከፈለ ማንኛውም አሽከርካሪ ቅጣቱን በከፈለ በሰላሳ ቀናት ውስጥ የተጣለበት ቅጣት እንዲሰረዝለት ቅሬታውን ለትራንስፖርት ሚኒስቴር ለማቅረብ ይችላል፤ በሚኒስቴሩ የሚሰጠውም ውሳኔ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሆናል፡፡
8. የትራፊክ ተቆጣጣሪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ከአሽከርካሪው ላይ የተቀበለውን የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሽከርካሪው ከየት መቀበል እንደሚችል ማስረዳት እና በሁለት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ በአቅራቢያው ለሚገኘው አግባብነት ላለው አካል ማስረከብ አለበት፡፡
9. በዚህ አንቀጽ መሰረት በሚጣል ቅጣት የሚመዘገብ የጥፋት ነጥብ በሪከርድነት ተመዝግቦ የሚቆየው ለአንድ ዓመት ብቻ ይሆናል፡፡

## 86. የትራፊክ ተቆጣጠሪዎች ስለሚፈፅሙት ጥፋት[96]

1. ማንኛውም የትራፊክ ተቆጣጣሪ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ሲያስፈፅም ከአድሎ በፀዳ እና ሰብዓዊ መብቶችን ባከበረ ሁኔታ መሆን ይኖርበታል፡፡
2. ማንኛውም የትራፊክ ተቆጣጠሪ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ሲያስፈፅም ጥፋት የፈፀመ ስለመሆኑ የትራፊክ ተቆጣጣሪው መሥሪያ ቤት እምነት ያደረበት እንደሆነ በሌላ አግባብነት ባለው ሕግ የሚጠየቅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 'ሐ' መሰረት ከትራፊክ ተቆጣጣሪነት ሥራ እንዲነሳ ይደረጋል፡፡

## 87. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ሚኒስቴሩ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ለማስፈፀም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

---

[96] በ23/8(2009) ደ.395 አንቀፅ 2(17) መሰረት አዲስ አንቀጾች አንቀጽ 86 እና 87 ተጨምረው ነባሩ አንቀጽ 86 አንቀጽ 88 ሆኖ ተሸጋሽጓል፡፡




88.<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>



ይህ ደንብ በፌዴራል ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።



**አዲስ አበባ ነሐሴ 20 ቀን 2003 ዓ/ም**





**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**



| W”Ö[» ’G’ | | SCHEDULE ‘A’ |
|---|---|---|
| ¾S”ÑÉ UM¡„‹ | | ROAD SIGNS |
| 1. ¾TeÖ”kmÁ UM¡ƒ | | 1. WARRNING SIGNS |
| ¾}uLg S”ÑÉ |  | Road in bad condition |
| ¨Å Ó^ ¾T>ơÖõ S”ÑÉ |  | Road turns to the left |
| ¨Å k˜ ¾T>ơÖõ S”ÑÉ |  | Road turns to the right |
| SËS]Á ¨Å Ó^ kØKA ¨Å k˜ ¾T>ơÖõ S”ÑÉ |  | Road turns first to the left and then to the right |

| | | |
|---|---|---|
| SËS]Á ¨Å k˜ kØKA ¨Å Ó^ ¾T>ሰÖõ S”ÑÉ |  | Road turns first to the right and then to the left |
| •¾Öuu ¾T>H@É S”ÑÉ |  | Road narrows |
| Övw ÉMÉA |  | Narrow bridge |
| uS”ÑÆ LA W^}™‹ ›K< |  | Men at work on road |
| vK ›^ƒ ›p×Ý SekK– S”ÑÉ |  | Intersection in four directions |
| SÑ“– S”ÑÉ ukØ ¨Å Ó^ |  | Intersection straight ahead and to the left |




| | | |
|---|---|---|
| SÑ“– S”ÑÉ ukØቃ“ ¨Å k˜ |  | Intersection straight ahead and to the right |
| SÑ“– S”ÑÉ ¨Å Ó^“ ¨Å k˜’ ¨Å òƒ kØቃ• S”ÑÉ ¾KU |  | Intersection to the left and to the right, no road straight ahead |
| S´Ñ>Á ÁK¨< ¾vu<` NÇ=É Ts[Ý |  | Railway crossing with gate |
| S´Ñ>Á ¾K?K¨< ¾vu<` NÇ=É Ts[Ý |  | Railway crossing without gate |
| ¨Åòƒ ¾ƒ^ò¡ Sw^ƒ ›K |  | Traffic light ahead |
| ¨Å Ó^ ¾T>ቃÖõ ›ÅÑ– Ÿ<`v (UM¡~ c=µ` ¨Å k˜ ¾T>ቃÖõ›ÅÑ– Ÿ<`v) |  | Sharp deviation of route to left (to right if chevrons reversed) |

| | | |
|---|---|---|
| uSÑ“– Yõ^ LA K}LLò-‹ pÉT>Á eØ |  | Cede priority to traffic on the crossing road |
| uS”ÑÉ ›ÓÉU ¾T>’õe •GAK– ”óe ›K |  | Strong cross wind |
| ¨Åòƒ ¡w ›ÅvvA ›K |  | Round about ahead |
| G<Kƒ ’ÖL S”ÑÉ ¨Å ›”É ’ÖL S”ÑÉ AK¨×M |  | Dual carriage way ends |
| S”ÑÆ ue}k˜ uŸ<M AÖvM (UM¡~ Ÿµ[ uÓ^ uŸ<M) |  | Road narrows to right (left if symbol reversed) |
| }ÅÒÒT> ¾TeÖ”kmÁ ¨AU ¾}ÅÒÒT> ¾vu<` NÇ=É Ts[Ý TeÖ”kmÁ’<br>G. ¨Åòƒ 250 T@ƒ` `q ¾vu<` NÇ=É Ts[Ý S•\” ¾T>ÁSK¡ƒ’<br>K. ¨Åòƒ 170 T@ƒ` `q ¾vu<` NÇ=É Ts[Ý S•\” ¾T>ÁSK¡ƒ’<br>N. ¨Åòƒ 100 T@ƒ` `q ¾vu<` NÇ=É Ts[Ý |  | Repeated warning or railway crossing:<br>a. Railway crossing 250 meters ahead<br>b. Railway crossing 170 meters ahead |



| | | |
|---|---|---|
| S•\" ¾T>ÁSK¡ƒ | | c. Railway crossing 100 meters ahead |





| | | |
|---|---|---|
| vK›”É ›p×Ý S”ÑÉ” vKG<Kƒ ›p×Ý S”ÑÉ Ás`ÖªM |  | To way traffic crosses one way road |
| uS”ÑÉ LA ¾T>ð“Ö` É”ÒA ›K |  | Loose stones on road |
| ¾vu<` NÇ=É Ts[Ý |  | Railway crossing |
| ›ÅÑ– lMlKƒ |  | Dangerous slope |
| ¾ኣÓ[™‹ Ts[Ý |  | Pedestrian's crossing |


| | | |
|---|---|---|
| TeÖ”kmÁ’ eKQí“ƒ |  | Attention children |
| u›”É ›p×Ý S”ÑÉ LA KÑ>²?¨< ƒ^ò¡ uG<Kƒ ›p×Ý ••ኢ”Ç=H@Éuƒ ¾}ðkÅ |  | Temporary two-way traffic on one-way road |
| ¾T>Á”g^ƒƒ S”ÑÉ |  | Slippery road |
| ›ÅÒ |  | General danger |
| ¨Åòƒ ¾ƒ^ò¡ SÚ“”p ›K |  | Traffic congestion ahead |

| | | |
|---|---|---|
| |  | take care of, wild animals may cross the road |
| ¨Åò ƒ ¾u? ƒ• ‹”ed ƒ›K< (S”ÑÆ” Ás`×K<) |  | Cattle ahead crossing road |
| TeÖ”kmÁ eK›"M Ñ<Ç}™‹ |  | Attention disabled persons |
| ¨Åò ƒ ¾‹`h SX]Á-‹ ›K< (S”ÑÆ” Ás`×K<) |  | Farm machinery ahead/crossing |
| ÖS´T³ S”ÑÉ |  | Winding road |
| ¨Åò ƒ ¾‹d ƒ ›ÅÒ SŸLŸÁ |  | Fire station ahead/fire |



| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ×u=Á ›K’ (¾ኧdƒ›ÅÒ SŸLŸÁ }iŸ`"] Ás`×M) | | fighting vehicle crossing | | |
| ¨Åòƒ ¾ß’ƒ }iŸ`"]-‹ ›K<’ (S”ÑÆ” Ás`×K<) |  | Trucks ahead/crossing | | |
| ¨Åòƒ ¾lí“ƒ SÝ¨Ý x;ታ•• ›K |  | Play ground | | |
| S”ÑÉ KG<Kƒ SŸðM ¾T>ËU`uƒ |  | Divided road begins | | |
| KG<Kƒ }ŸõKA ¾’u[ S”ÑÉ TwmÁ |  | Divided road ends | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| lU ¾T>M UM¡ƒ ¨Åòƒ ›K |  | Stop sign ahead | | |
| pÉT>Á eØ ¾T>M UM¡ƒ ¨Åòƒ ›K |  | Yield sign ahead | | |
| uÔ” uŸ<M T°²“© p`î c`„ ¾T>Ñ“˜ S”ÑÉ ›K |  | Side road (angled) | | |
| " Y" p`î ÁK¨< SÑ“– S”ÑÉ |  | "Y" intersection | | |
| uv”Ç=^ ƒ^òŸ<” ¾T>Áe}“ÓÉ c¨< ›K |  | Flagger | | |
| |  | | | |





| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| S”ÑÉ kÁi ›K | | Survey crew | | |
| ŸvK ›^ƒ ›p×Ý S”ÑÉ ƒA¿¾vu<` GÇ=É Ts[Ý ›K |  | Parallel rail road crossing (cross road) | | |
| uÔ” uŸ<M Ÿ}Ñ“—¨< S”ÑÉ ƒA¿ ¾vu<` GÇ=É Ts[Ý S”ÑÉ ›K |  | Parallel rail road crossing (side road) | | |
| "T" p`î "K¨< S”ÑÉ ƒA¿ ¾vu<` GÇ=É Ts[Ý S”ÑÉ ›K |  | Parallel rail road crossing (T intersection) | | |
| ¾›eóMƒ S”ÑÉ |  | Pavement | | |




| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| SËS]Á | | begins | | |
| ¾›eóMƒ S"ÑÉ SÚ[h |  | Pavement ends | | |
| "Ç ›K |  | Falling rocks | | |
| }"kdni (}'g=) ÉMÉA |  | Swing bridge | | |
| ¨Å ¨"›' Ç`‰ ¾T>¨eÉ S"ÑÉ |  | Road leads to quay or river bank | | |
| ¾S"ÑÆ Ç` ›ÅÑ– ’¨< |  | Dangerous shoulders | | |


S"ÑÆ" ¾T>Ás`Ö< ¾Æ` •ኣ"edƒ eKT>•\ Ø"no ›É`Ó


| 2. ¾T>q×Ö\ UM¡„‹ | | 2. REGULATORY SIGNS |
|---|---|---|
| ke~ uT>ÁSK¡}¨< ›p×Ý }¡Ÿ`"]- -‹ TKõ A‹LK< |  | Vehicles may pass either side |
| ke~ uT>ÁSK¡}¨< ¾TqT>Á Yõ^ LA w‰ ›lU |  | Park right only (left if symbol reversed) |
| UM¡~ ÁKuƒ” x;ታ· k—<” •ኢKõ |  | Pass the place so marked on its right side |
| UM¡~ ÁKuƒ x;ታ· Ó^¨<” ••ኢKõ |  | Pass the place so marked on its left side |
| kY~ uT>ÁSK¡}¨< ›p×Ý•ኢKõ |  | Proceed in direction by arrow mark on sign |





| | | |
|---|---|---|
| ¾ƒ^òŸ<” ¡w ›ekÉV uSµ` LA LK }iŸ`"] pÉT>Á cØ}I kY~ •ኧ”ÅT>ÁSK¡}¨< ¾ƒ^òŸ<” ¡w ²<` |  | Cede priority to traffic already circling traffic circle, then circle traffic circle as indications by arrow |
| uüÇM ¾T>”kdkc< dA¡KA‹ w‰ ¾T>ÁMñuƒ S”ÑÉ |  | Road to be used by pedal cyclists only |
| uS”ÑÆ LA ¾TiŸ`Ÿ]Á ›’e}– õØ’ƒ |  | Minimum speed |
| ¾›’e}– õØ’ƒ SÚ[h |  | End of minimum speed |
| ue}Ó^ µa SSKe ¡M¡M ”¨< |  | No U turns |




| | | |
|---|---|---|
| ÖpLL ``´S~ uUM¡~ LA<br>Ÿ}Ökc¨< T@ƒ uLA KJ'<<br>}iŸ`"] ¨AU ¾}k×ÖK< }iŸ`"]-‹<br>¾}ŸKŸK |  | No vehicle or<br>combination of vehicles<br>over shown length |
| ÖpLL ¡wÅ~ uUM¡~ LA<br>Ÿ}SKŸ}¨< uLA KJ' ¾ß'ƒ<br>}iŸ`"] ¾}ŸKŸK |  | Closed to truck of total<br>weight above the weight<br>indicated on the sign |
| ÖpLL ¡wÅ~ uUM¡~ LA<br>Ÿ}SKŸ}¨< uLA KJ' }iŸ`"]<br>¾}ŸKŸK |  | Closed to vehicle a<br>total weight above the<br>weight indicated on the<br>sign |
| Kwe¡K?ƒ ¾}ŸKŸK |  | Closed to bicycles |
| uእÏ KT>Ññ ƒU ßU` KT"–¨<U<br>}iŸ`"] Ÿ›"É ›p×Ý ¾}²Ò S"ÑÉ |  | Closed to all vehicles<br>including handcarts (one |




| | | |
|---|---|---|
| | | way road) |
| ¨Å Ó^ SሰÖõ ¡M¡M ’¨< |  | No left turn |
| ŸG<Kƒ •ኢÓ` uLA ÁL†¨<” ¾V}` }iŸ`"]-‹ SpÅU ¾}ŸKŸK |  | No overtaking of motor vehicles on move than two wheels |
| ŸG<Kƒ•ኢÓ`uLA LL†¨< ¾V}` }iŸ`"]-‹ ¾}ŸKŸK |  | Closed to motor vehicles on more than two wheels |
| KV}` we¡K?ƒ ¾}ŸKŸK |  | Closed to motor cycles |
| KvK V}` }iŸ`"]-‹ ¾}ŸKŸK |  | Closed to motor vehicles |
| |  | |




| | | |
|---|---|---|
| ¾Ÿ}T ¡MM | | Municipal area |
| õØ’ƒ ¾}¨c’uƒ ¡MM SÚ[h ¨AU ¾Ÿ}T ¡MM SÚ[h |  | End of area of restricted speed or end of municipal area |
| UM¡~ •ኢ”ÅT>ÁSK¡}¨< •ኢÓÉ ¾}Å[Ñuƒ ¡MM SÚ[h |  | End of area of restriction as indicated on sign |
| ¾Ø\Uv ÉUê TcTƒ ¾}ŸKŸKuƒ |  | Prohibition of use of audible warning appliances |
| lU’ Al UM¡ƒ vKuƒ T”–¨<U }iŸ`"] ŸSekM– S”ÑÉ ŸSÓv~ uòƒ SqU ›Kuƒ |  | Stop! All vehicle will be brought to a complete Standstill before entering intersection |



| | | |
|---|---|---|
| uእ"eXƒ KT>Xu< }iŸ`"]-‹" Kእ"ef‹ ¾}ŸKŸK |  | Closed to animal-drawn vehicles and to animals |
| uእÏ KT>Ññ }iŸ`"]-‹ ¾}ŸKŸK |  | Closed to handcarts |
| KእÓ[™‹ ¾}ŸKŸK |  | pedestrians |
| ¾›¡eK< ß'ƒ uUM¡~ LA Ÿ}SKŸ}¨< ß'ƒ uLA KJ' }iŸ`"] ¾}ŸKŸK |  | Closed to vehicles where the load on any one axle exceeds the load indicated on the sign |
| õØ'ƒ ¾}¨c'uƒ ¡MM'uŸ=KA T@ƒ uUM¡~ LA Ÿ}SKŸ}¨< õØ'ƒ uLA ¾}ŸKŸK |  | Area of restricted speed: speeds exceeding that indicated on the sign in |


| | | |
|---|---|---|
| | | kilometers |
| ÖpLL eó~ uT@ƒ` uUM¡~ LA Ÿ}SKŸ}¨< uLA KJ’ }iŸ`"] ¾}ŸKŸK |   | Closed to vehicle of a total width exceeding that indicated in meters on the sign |
| ÖpLL Ÿõታ†¨< uT@ƒ` uUM¡~ LA Ÿ}SKŸ}¨< uLA KJ’<}iŸ`"]-‹ ¾}ŸKŸK |   | Closed to vehicles of a total height exceeding that indicated in meter on the sign |
| pÉT>Á ÁK¨< S”ÑÉ |  | Priority road |
| "pÉT>Á ÁK¨< S”ÑÉ" ¾T>K¨< UM¡ƒ ƒ°³´ SÚ[h |  | End of priority road |
| ¨Å k˜ መለጠፍ ¡M¡M ”¨< |  | No right turn |


| | | |
|---|---|---|
| uUM¡~ LA ŸT>ያ¾¨< v'c `kƒ }ÖÓ„ TiŸ`Ÿ` ¡M¡M ”¨< |  | Driving of vehicles less than over shown length apart prohibited |
| uእÏ KT>Ññ ƒU ßU` KT”–¨<U }iŸ`"] ŸG<K~U ›p×Ý ¾}²Ò S”ÑÉ |  | Closed to all vehicles including handcarts |
| AI UM¡ƒ "Kuƒ ËUa •እeŸT>kØK¨< SekK– S”ÑÉ' ¨AU "SÚ[h" ŸT>M nM Ò` kØKA ¾T>Ñ˜ ¾²=I ¯A'ƒ UM¡ƒ •እeŸ›Kuƒ É[e K›ß`U J' K[ÏU Ñ>²? KTqU ¾}ŸKŸK |  | No stopping and parking from this sign to the next intersection, or to the next sign of this kind with the inscription " End" |
| AI UM¡ƒ "Kuƒ ËUa •እeŸT>kØK¨< SekK– S”ÑÉ' ¨AU "SÚ[h" ŸT>M nM Ò` kØKA ¾T>Ñ˜ ¾²=I ¯A'ƒ UM¡ƒ •እeŸ›Kuƒ É[e uS²Ó¾ƒ KTqU ÁM}ðkÅ |  | No parking from this sign to the next intersection, or to the next sign of this kind with the inscription "End" |

| | | |
|---|---|---|
| Ÿ¨Åòƒ KT>S× }iŸ`"] pÉT>Á eØ |  | Cede priority to oncoming vehicles |
| lU’ ¾Ñ<U\¡ SY]Á u?ƒ |  | Stop! Customs office |
| ›ÅÑ– õ”Ç;ት ¾T>ÁeŸƒM ß’ƒ KÝ’ }iŸ`"] ¾}ðkÅuƒ S”ÑÉ |  | Hazardous cargo road |
| ›ÅÑ– õ”Ç;ት ¾T>ÁeŸƒM ß’ƒ KÝ’ }iŸ`"] ¾}ŸKŸK |  | Closed to hazardous cargo |
| ¾ß’ƒ }iŸ`"] S}LKòÁ |  | Truck’s road |




| | | |
|---|---|---|
| Kß’ƒ }iŸ`"] ¾}ŸKŸK |  | closed to truck |
| ¾}iŸ`"] SÔ}‰ ¡MM |  | Tow away zone plaque |
| ¾Åc?~” k˜ Á´ |  | keep right |
| ¾Åc?~” Ó^ Á´ |  | keep left |
| K›”É [Éõ Ÿ}kSÖ¨< ›’e}– õØ’ƒ uLA TiŸ`Ÿ” ¾T>ÁeÑÉÉ |  | compulsory minimum speed to one lane |
| u}KÁ¾ [Éõ ¨<eØ }ðíT>•ƛ”Ç=J” ¾}kSÖ ¾õØ’ƒ ¨c” |  | Speed limits applying to different lanes |
| u}KÁ¾ [Éõ ¨<eØ }ðíT>•ƛ”Ç=J” ¾}kSÖ ›’e}– õØ’ƒ ¨c” |  | Compulsory minimum speed applying to different lanes |

| 3. S[Í cÜ UM¡„‹ | | 3. INFORMATIVE SIGNS |
|---|---|---|
| ¾ØÑ“ ›ÑMÓKAƒ |  | Break dawn service |
| S´“– (u<“ u?ƒ) |  | Refreshments or cafeteria |
| UÓw u?ƒ |  | Restaurant |
| ¨Å òƒ ¾ƛÓ[– Ts[Ý ›K |  | Pedestrian crossing ahead |
| ‚K?ö” (eM¡) |  | Telephone |
| ¾’ÇÏ TÅÁ ×u=Á |  | Fuel |
| vK›”É ›p×Ý S”ÑÉ |  | One way street |

| | | |
|---|---|---|
| ¨Å Ó^ ¾T>ÁeÏ?É S"ÑÉ ¾KU |  | No through road on left |
| òƒ Kòƒ ¾T>ÁeÏ?É S"ÑÉ ¾KU |  | No through road on right |
| òƒ Kòƒ ¾T>ÁeÏ?É S"ÑÉ ¾KU |  | No through road ahead |
| u}KÁ¾ `kƒ LA uSJ" ¾vu<` NÇ=É Ts[Ý •ኧ"ÅT>ÁÒØU S[Í ¾T>cØ |  | Count down markers to railway crossing |
| TqT>Á xታ• |  | Parking |
| ¾SËS]Á °`Çታ SeÝ xታ |  | First aid station |

| | | |
|---|---|---|
| J,M (V,M) |  | Hotel or Motel |
| **4. ¾S"ÑÉ LA px‹ (SeSa‹)** | | **4. ROAD MARKINIGS** |
| ¾SqT>Á SeS` |  | Stop line |
| pÉT>Á eØ ¾T>M SeS` |  | Give way line |
| S"ÑÉ" u[Éõ ¾T>ŸóõM ¾}q^[Ö SeS` |  | Broken lane line |
| ¾}q^[Ö ¾S"ÑÉ ›"óA SeS` |  | Broken center line |
| ÁM}q^[Ö ¾S"ÑÉ ›"óA SeS` |  | Solid center line |

| | | |
|---|---|---|
| ÁM}q^[Ö“ ¾}q^[Ö ¾S”ÑÉ ›"óA SeS` |  | Solid and broken center line |
| ¾ኦÓ[™‹ Ts[Ý SeS` |  | Pedestrian’s crossing |

| | | |
|---|---|---|
| ›p×Ý” ¾T>ÁeS`Ö< px‹’›iŸ`"]-‹ ŸSekM– S”ÑÉ **ከመግባታቸው** uòƒ ¾T>H@Æuƒ” ›p×Ý ¾T>ÁdA ¾kYƒ UM¡ƒ vKuƒ ’ÖL S”ÑÉ LA ÁqTK< |  | Preelection markings; before reaching an intersection drivers will place their vehicles by an arrow pointing in the lended direction |
| ¾TqT>Á UM¡„‹’ ŸUM¡~ ¨<eØ dA}LKñ TqU AðkÇM |  | Parking marks; parking permitted within the limits of the markings |
| ¾SekM–S”ÑÉ Te}LKòÁ UM¡„‹ ’ ¨Åk˜ ¾T>•Öñ }iŸ`"]-‹ ¾SYS\” k˜ AA³K<’ **በቀጥታ** ¨Åòƒ ¨AU ¨Å Ó^ ¾T>ÁMõ }iŸ`"] ¾}s[Ö<ƒ” SYSa‹ Ts[Ø A‹LM:: ÁM}s[Ö<ƒ” SYSa‹ Ts[Ø ›A‰MU |  | Channelising markings of intersection traffic turning to the right shall remain on the right of the line; traffic proceeding straight ahead or turning left may cross interrupted line; no crossing of uninterrupted lines |
| T}LKòÁ UM¡„‹’ ¾kKU ’Öw×w vKv†¨< ¡MKA‹ LA S”Çƒ ›A‰MU |  | Channelising markings; no vehicle may be drive on stripe-painted areas |

| | |
|---|---|
| | W”Ö[» ’K’ |
| | 1. ¾Øóƒ እርከን |
| **1– የእርከን ¾Øóƒ ^^** | |
| 1 | }iŸ`"] ያለአግባብ ¾Ô}} |
| 2 | ¾}TEL ß’ƒ TkòÁ /eþ”Ç / ¾K?K¨< ß’ƒ ß• }iŸ`"] ¾’Ç |
| 3 | ¾Ø\Uv ÉUê ÁK›Ñvw /uTAÑv ቦታ/ ÁcT |
| 4 | }Ñu= vMJ’ የጥሩምባ ÉUê ¾}ÖkS |
| 5 | uƒ`õ ß’ƒ LA UM¡ƒ ÁLÅ[Ñ |
| 6 | uS”ÑÉ LA }ሽከርካሪ ÁXÖu |
| 7 | ¾ß”pLƒ SŸLŸÁ /H@MT@ƒ/ dÁÅ`Ó ወይም አብሮት የጫነውን ሰው ማድረጉን ሳያረጋግጥ V}` dA¡M ÁiŸ[Ÿ[ |
| 8 | Ÿ}ðkÅ¨< õØ’ƒ በታች }iŸ`"] ÁiŸ[Ÿ[ |
| 9 | የጭንቅላት መከላከያ ሄልሜት ሳያደርግ ብስክሌት ያሽከረከረ |
| **2– የእርከን ¾Øóƒ ^^** | |
| 1 | በተሽከርካሪ SÓu=Á /S¨<ÜÁ/ u` LA ÁqS |
| 2 | ŸSÖ” uLA ÉUê •ÁcT ÁiŸ[Ÿ[ |
| 3 | ¾k—<” Ö`´ dA´ በዝግታ Áiከረከ[ |
| 4 | u}ŸKŸK ቦታ LA ተሽከርካሪ ÁqS |
| 5 | Ÿ}ðkÅKƒ Ñ>²? uLA }iŸ`"] S”ÑÉ LA ÁqS |
| 6 | ለተሽከርካሪ¨< እንቅስቃሴ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ሁለት እጁን መሪ ላይ ሳያደርግ ያሽከረከረ |
| **3– የእርከን ¾Øóƒ ^^** | |

| | |
|---|---|
| 1 | u25 T@ƒ` `kƒ UM¡ƒ dÁXA ›p×Ý ¾k¾[ |
| 2 | uÖvw S”ÑÉ LA SŸ=“ ÁqS |
| 3 | um `k~” Öwq ÁLiŸ[Ÿ[ |
| 4 | ¾S”ÑÉ ›ŸóóA Åc?ƒ /SeS`/ Ás[Ö |
| 5 | ¾SkSÝ ku„ dÁe` ወይም ተሳፋሪዎች የመቀመጫ ቀበቶ ማሰራቸውን ሳያረጋግጥ }iŸ`"] ÁiŸ[Ÿ[ |
| 6 | ከተፈቀደለት ጊዜ በላይ ¾}uLg” }gŸ`"]” S”ÑÉ LA ¾ÖÑ’ |
| 7 | u}gŸ`"]¨< LA ¾}Ý’¨<” ß’ƒ uT>Ñv ÁLc[ ¨AU ÁLKuc |
| 8 | ›ð`’ ›gª’ É”ÒA“ ¾SdcK<ƒ” vM}ðkÅ ቦታ• Á^Ñð ¨AU እንዲራገፍ ÁÅ[Ñ |
| 9 | K?KA‹ ¾ƒ^ò¡ õcƒ” ¾T>Ác“¡K< É`Ñ>„‹” ¾ðçS |
| 10 | ÁM}ðkÅ ß’ƒ ŸQ´w Ò` ¾Ý’ |
| 11 | ŸT>Ñv¨< uLA ße ’ እንፋሎጽ ²Aƒ ¨AU ’ÇÏ •ÁÚc“ እየተፈፈ ¾T>H@É }iŸ`"] ÁiŸ[Ÿ[ |
| 12 | uƒ^ò¡ Åc?ƒ LA ÁiŸ[Ÿ[ |
| 13 | }dó] ß• ’ÇÏ TÅÁ Ñw„ ¾kÇ ¾Q´w ƒ^”eþ`ƒ ተሽከርካሪ |
| 14 | uTw]Á Ñ>²? መብራት እያለውdÁu^ ÁiŸ[Ÿ[ |
| 15 | ¨ÅTAH@Éuƒ ›p×Ý UM¡ƒ Ád¾ |
| 16 | }gŸ`"] Å`x ÁqS |
| 17 | ከ7 ዓመት በታች የሆነ ህፃንን ከአዋቂ ጋር ሳያስቀምጥ ወይም ለደህንነት ሲባል በተሰራ ማቀፊያ ውስጥ ሳያስቀምጥ Áሽከረከረ |
| 18 | የጉዞ ረድፍ ጠብቆ ያላሽከረከረ |
| 19 | በመታጠፊያ መንገድ ላይ ተሽከርካሪ ያቆመ |

| | |
|---|---|
| 20 | የትራፊክ ምልክት ወደቀኝ ብቻ መታጠፍ በሚፈቅድ መንገድ ላይ መንገድ የዘጋ |

| 4– •`Ÿ” ¾Øóƒ ^^ | |
|---|---|
| 1 | pÉT>Á SeÖƒ c=Ñv¨< ¾ŸKŸK |
| 2 | vM}TEL Sw^ƒ ÁiŸ[Ÿ[ |
| 3 | ¾T>ታÖõuƒ” ›p×Ý dA´ ÁiŸ[Ÿ[ |
| 4 | ÁKT”çv[mÁ UM¡ƒ ¾}uLg” }gŸ`"] S”ÑÉ LA ÁqS |
| 5 | uc”cKƒ ¾T>iŸ[Ÿ` uc¯ƒ Ÿ10 Ÿ.T@. uታ‹ ¾T>Õ´ M¿ }gŸ`"] uS”ÑÉ LA ÁiŸ[Ÿ[ |
| 6 | u›¨<„u<e TqT>Á eõ^ }gŸ`"] ÁqS |
| 7 | ¾ኧdƒ ›ÅÒ }gŸ`"] ¨<H SS<Á x• LA ወይም በእሳት አደጋ መከላከያና ሆስፒታል በር ላይ ተሽከርካሪ ያቆመ |
| 8 | u}ŸKŸK xታ• LA ¾Ý’ ¨AU Á¨[Å |
| 9 | uvu<` GÇ=É ›ÖÑw }Ñu=¨<” Ø”no ÁLÅ[Ñ |
| 10 | K›Lò }gŸ`"] pÉT>Á ¾ŸKŸK |
| 11 | Ÿ}ðkÅ¨< ¾Ó”v` Sw^ƒ GAM ¨<Ü ¾J’< Sw^„‹” (û¨<³-‹”) ¾}ÖkS |
| 12 | UM¡ƒ dÁdA }gŸ`"] ŸqSuƒ x•• Á”kdkc ¨AU ÁqS |
| 13 | እግረ– Ts[Ý S”ÑÉ LA }iŸ`"] ÁqS |
| 14 | ¾T>ŸK¡M UM¡ƒ ¾×c |
| 15 | uƒ^ò¡ Åc?ƒ LA }gŸ`"] ÁqS |
| 16 | u}gŸ`"]¨< ¾¨<ß ›"M LA c¨< ¾Ý’ |
| 17 | ¾keƒ ›p×Ý ¾Kkk |
| 18 | Ÿ}¨c'Kƒ SkSÝ ¨AU ¾ß’ƒ M¡uLA ¾Ý’ |
| 19 | ¾›iŸ`"]¨<” °Aታ•• ¾T>ŸልK< SÒ[Í-‹”፣ }K×ò Le+¡ ወይም ሌሎች |

| | |
|---|---|
| | ተመሳሳይ ነገሮችን ያስቀመጠ ወይም የለጠፈ |
| 20 | ከ13 ዓመት በታች የሆነ ማንኛውንም ልጅ ፊት ላይ አስቀምጦ ያሽከረከረ |
| 21 | K›ÅÒ ›ÑMÓKA ƒ }gŸ`"] pÉT>Á ÁMcÖ |
| 22 | ተንቀሳቃሽ eM¡ •Á'ÒÑ[ ወይም መልዕክት እየላከ ወይም እየተቀበለ ወይም ማንኛውንም ነገር በጆሮ ማዳመጫ እያዳመጠ }iŸ`"] ÁiŸ[Ÿ[ |
| 23 | ቴሌቪዥን ወይም ሌሎች ተንቀሳቃሽ ምስሎችን ተሽከርካሪ ውስጥ እየተመለከተ ያሽከረከረ |
| 24 | ተሽከርካሪ ላይ ከኋላ አንፀባራዊ ምልክት ሳይለጥፍ ያሽከረከረ |
| 25 | የትራፊክ ተቆጣጣሪ ትዕዛዝ ያልፈፀመ |
| 26 | ተሽከርካሪው ውስጥ ሬዲዮ፣ ቴፕ፣ ሲዲ ወይም ተመሣሣይ ነገሮችን በከፍተኛ ድምጽ የከፈተ |

| | |
|---|---|
| 5– እ`Ÿ” ¾Øóƒ ^^ | |
| 1 | SekK– S”ÑÉ LA pÉT>Á ÁMcÖ }gŸ`"] |
| 2 | }gŸ`"] uእ”penc? LA •ÁK }dó] ¾Ý’ ¨AU Á¨[Å |
| 3 | ›K›Óvw }gŸ`"]” ¾kÅS |
| 4 | ¾}gŸ`"]” u` Ÿõ„ ÁiŸ[Ÿ[ |
| 5 | uQÓ Ÿ}¨c’¨< Ÿõ•’ `´Sƒ“ eóƒ ¨<ß ß’ƒ ¾Ý’ |
| 6 | Ÿ}ðkÅKƒ ¨”u` M¡ ¨<ß ¾ÚS[ |
| 7 | QÒ© YM×” dA•[¨< ¾ƒ^ò¡ õcƒ” Á¨Ÿ ÁÅ“kð |
| 8 | uእÓ[– S”ÑÉ LA }gŸ`"] ÁqS |
| 9 | ህዝብ በሚበዛበት፣ ሆስፒታሎችና ትምህርት ቤቶች በሚገኙበት አካባቢ መስቀለኛና እግረኛ ማቋረጫ ላይ እንዲሁም የአሽከርካሪውን እይታ የሚከልል የአየር ሁኔታና ሌሎች ሁኔታዎች በሚኖሩበት ጊዜ ፍጥነት ሳይቀንስ ያሽከረከረ |
| 10 | በመንገድ ላይ ያፈሰሰውን ወይም የጣለውን ፈሳሽ ወይም ጠጣር ነገሮችን ያላፀዳ |
| 11 | በተሽከርካሪው ላይ ተገቢ ያልሆነ አካል የጨመረ |
| 6– እ`Ÿ” ¾Øóƒ ^^ | |
| 1 | KእÓ[– pÉT>Á ÁMcÖ |
| 2 | kA ¾ƒ^ò¡ Sw^ƒ ¾×c |
| 3 | uQÓ Ÿ}¨c’¨< õØ’ƒ uLA ÁiŸ[Ÿ[ |
| 4 | uTw]Á Ñ>²? U”U Sw^ƒ XA•[¨< ÁiŸ[Ÿ[ |

| | |
|---|---|
| 5 | u}ŸKŸK S”ÑÉ ¨AU ›p×Ý ÁiŸ[Ÿ[ |
| 6 | SNM S”ÑÉ LA }dó] ¨AU ẞ’ƒ ¾Ý’ ¨AU Á¨[Å |
| 7 | ¾ƒ^ò¡ ›ÅÒ ðêV x;ታ¨< LA ÁMqS |
| 8 | ¾›ÅÒ ›ÑMÓKAƒ }iŸ`"] Ÿ}ðkÅKƒ ÉUê“ ¾›ÅÒ UM¡ƒ Sw^ƒ ŸT>ðêS¨< }Óv` ¨<Ü ›K›Óvw ¾}ÖkS |
| 9 | በጭነት ተሽከርካሪ በሕግ ከተፈቀደለት ውጭ ሰውን ያሳፈረ |
| 10 | uÉMÉA LA }iŸ`"] ÁqS |
| 11 | ¾T>ÁeÑÉÉ UM¡ƒ ¾×c ¨AU ÁK›Óvw ¨Å%EL ÁiŸ[Ÿ[ |
| 12 | Ÿ}T ¨<cØ ŸvÉ Sw^ƒ /v¨<³/ ¾}ÖkS |
| 13 | c¡a’ ›Å”³» °ê ¨eÊ ወይም ጫት ቅሞ ወይም እየቃመ ያሽከረከረ |
| 14 | የትራፊክ አደጋ አድርሶ የተጎዳውንና ሕክምና የሚያስፈልገውን ሰው ህክምና ወደ ሚሰጥበት ተቋም ወስዶ ያላሳከመ |
| 15 | ተንቀሳቃሽ eM¡ •Á’ÒÑ[ ወይም መልዕክት እየላከ ወይም እየተቀበለ ወይም ማንኛውንም ነገር በጆሮ ማዳመጫ እያዳመጠ የህዝብ ማመላለሻ }iŸ`"] ÁiŸ[Ÿ[ |
| **2.eKp×ƒ ’Øw ›c×Ø“ ¾p×ƒ SÖ”** | |
| **G. KSËS]Á Ñ>²? Øóƒ c=ðçU** | |

| }.l | ¾Øóƒ •ኢ`Ÿ” | KØó~ ¾T>S²Ñu¨< ’Øw | ¾T>¨cÅ¨<•`UÍ /¾Ñ”²w p×ƒ SÖ” በብር/ |
|---|---|---|---|
| 1 | 1– ¾Øóƒ •ኢ`Ÿ” | 2 | 80.00 |
| 2 | 2– ¾Øóƒ ኢ`Ÿ” | 3 | 100.00 |
| 3 | 3– ¾Øóƒ •ኢ`Ÿ” | 4 | 120.00 |
| 4 | 4– ¾Øóƒ ኢ`Ÿ” | 5 | 140.00 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 5 | 5– ¾Øóƒ እ`Ÿ” | 6 | 160.00 |
| 6 | 6– ¾Øóƒ እ`Ÿ” | 7 | 180.00 |

K. K2– Ñ>²? •“ Ÿ²=Á uLA Øóƒ c=ðçU

| }.l | ከቀድሞው ጥፋት ጋር ተደምሮ የሚመዘገብ የጥፋት ነጥብ | ¾T>¨cÅ¨< እ`UÍ /¾Ñ”²w p×ƒ በብር/ |
|---|---|---|
| 1 | 4-9 | 200.00 |
| 2 | 10-11 | 220.00 |
| 3 | 12-13 | 240.00 |
| 4 | 14-16 | K6/eÉeƒ/ ¨` ¾›iŸ`"] wnƒ T[ÒÑÝ õnÉ ኢÑÇ“ የ}GÉf YMÖ“ እ”Ç=¨eÉ TÉ[Ó |
| 5 | 17-19 | K1 /›”É/ ¯Sƒ ¾›iŸ`"] wnƒ T[ÒÑÝ õnÉ •ÑÇ“ ¾}GÉf YMÖ“ |
| 6 | 20-21 | ¾›iŸ`"] wnƒ T[ÒÑÝ õnÉ AW[³M:: õnÆ ¾}W[²uƒ vKõnÉ ከ2 ዓመት በኋላ እንደ ›Ç=e K=Á¨× A‹LM:: |

ሐ.<u>eKp×ƒ ›KSðçU</u>

p×~” dAðêU ¾k[ ›iŸ`"] kÉV u}S²Ñuuƒ ’Øw LA Ÿ²=l በታች vK¨< W”Ö[» ¾}SKŸ}¨< ’Øw }ÅUauƒ uÉU\ SW[ƒ Ak×M::

| }.l | ÁM}ðçSuƒ Ñ>²? | ¾T>S²Ñu¨< ’Øw |
|---|---|---|
| 1 | Ÿ31-60/ŸWLd ›”É እስከ eÉX / k“ƒ ¨<eØ p×~” ÁMðçS | 4 |

| | | |
|---|---|---|
| 2 | Ÿ60/ eÉX/ k“ƒ uLA p×~” ÁMðçS | 6 |

S.K?KA‹ ¾Å”w S}LKõ Øó„‹

| }.l | ¾Øó„‹ ^^ | p×ƒ (w`) |
|---|---|---|
| 1 | uS”ÑÉ LA አላግባብ እንስሳት ¾’Ç ¨AU Aµ ¾}Ñ— | 80 |
| | | |
| 2 | ulÓ dÁeðpÉ uƒ^ò¡ ¾S”ÑÉ UM¡ƒ ¾}ÖkS | 150 |
| 3 | የተሽከርካሪ ወይም የእግረኛ መሄጃ መንገድን የቆፈረ፣ ያበላሸ ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ነገሮችን ያከናወነ | 1000 |
| 4 | በተሽከርካሪ ወይም በእግረኛ መሄጃ መንገድ ላይ የተሽከርካሪዎችን ወይም የእግረኞችን እንቅስቃሴ የሚያውክ ቁሳቁስ ወይም ሸቀጥ ያስቀመጠ፣ የነገደ ወይም በሐዘን ምክንያት ከአቅም በላይ ካልሆነ በስተቀር ያለፈቃድ የተለያዩ ነገሮችን የተከለ ወይም ተመሳሳይ ነገሮችን ያከናወነ | 300 |
| 5 | በማብሪያ ጊዜ በጉልህ የሚታይ መብራት ሳይዝና ለተሽከርካሪው አቅራቢያ በሆነው ጎን መብራቱን ሳያሳይ እንስሳትን የነዳ ማናቸውም ነጋዴ | 100 |
| 6 | በማብሪያ ጊዜ በጉልህ የሚታይ መብራት ሳይዝና ለተሽከርካሪው አቅራቢያ በሆነው ጎን መብራቱን ሳያሳይ እንስሳትን የነዳ ማናቸውም የእንስሳ ጠባቂ | 40 |

| | | |
|---|---|---|
| 7 | በተሽከርካሪ መንገድ ላይ በእጅ የሚገፋ ባለመንኮራኩር ወንበርን ወይም የሚሳብ ጋሪን የገፋ ወይም የሳበ | 80 |
| 8 | ለመጫወቻና ለጊዜ ማሳለፊያ ተብሎ የተሰራ ብስክሌት ወይም በጫማ መልክ የሚጠለቅ ተንሸራታች ወይም ሌሎች መጫዎቻዎች በተሽከርካሪ መንገድ ላይ ያሽከረከረ ወይም የተጠቀመ | 80 |

ሠ. <u>•እግረኞች ስለሚቀጡበት ሁኔታ</u>

| }.l. | ¾Øó„‹ ^^ | p×ƒ (w`) |
|---|---|---|
| 1 | }Ñu=¨<” Ø”no dÁÅ`Ó S”ÑÉ Ás[Ö | 40 |
| 2 | ለተሽከርካሪ u}ðkÅKƒ S”ÑÉ LA ÁKum U¡”Áƒ ¾qS ¨AU ¾}Õ² | 40 |
| 3 | ¾•ኣÓ[– S”ÑÉ uK?Kuƒ S”ÑÉ LA k˜ Ö`²<” Aµ ¾}Õ² | 40 |
| 4 | KኣÓ[– S”ÑÉ }wKA Ÿ}ŸKK S”ÑÉ ¨<ß ¾}Õ² | 40 |
| 5 | uw[ƒU J’ uÓ”w }KA}¨< የታጠሩ S”ÑÊ‹ ²KA S”ÑÉ Ás[Ö | 40 |

## አዋጅ ቁጥር 811/2006

## የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የዲመሬጅ ክፍያ ለመደንገግ የወጣ አዋጅ

የወጪና ገቢ ምርቶችን በተመጣጣኝ የትራንስፖርት ዋጋ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጓጉዘው ወደ ወደብ እንዲደርሱ ወይም ከወደብ ወደተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ተሰራጭተዉ ለተጠቃሚው እንዲቀርቡ ማስቻል አስፈላጊ በመሆኑ፤

በጭነት ላኪዎችና ተረካቢዎች፣ የመጫኛና የማራገፊያ አገልግሎት በሚሰጡ መጋዘኖች እና ቁጥጥር በሚያከናውኑ አካላት የአሰራር ቅልጥፍና መጓደል ምክንያት የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የሥራ ጊዜ ከፍተኛ ብክነት የሚታይበት በመሆኑ፤

ይህን የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የሥራ ጊዜ ብክነት በማስቀረትና ምልልስን በማፋጠን ጭነት የማንሳት አቅምን ለማሳደግ እንዲሁም የዕቃዎችን የወደብ ቆይታ ጊዜ በማሳጠር አላስፈላጊ ወጪን ለመቀነስና ተያያዥ ችግሮችን ለማስወገድ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የዲመራጅ ክፍያን የሚደነግግ ህግ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የዲመሬጅ ክፍያ አዋጅ ቁጥር 811/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፤-

   1. "የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ" ማለት ማንኛውንም ዕቃ እንዲያመላልስ ተብሎ የተሰራና ለዚሁ አገልግሎት እንዲውል የተደረገ ባለሞተር ተሽከርካሪ ሲሆን ጐታች መኪናን ይጨምራል፤
   2. "ዕቃ" ማለት የቁም እንስሳትን ጨምሮ ኮንቴነሮችን፣ የዕቃ ማሸጊያዎችን ወይም ተመሳሳይ የዕቃ ማሸጊያ ቁሶችን ወይም በዕቃ ላኪው ወይም በዕቃ አስረካቢ በጥቅል መልክ ለጭነት የሚቀርብ ማንኛውም ንብረት ነው፤
   3. "አጓጓዥ" ማለት ዕቃን በተሽከርካሪ አማካኝነት በየብስ ወይም በአገር ውስጥ ውሃ የሚያጓጉዝ ሰው ነው፤

4. “ላኪ” ማለት ለራሱ ወይም ለሦስተኛ ወገኖች ሲል ዕቃውን እንዲያጓጉዝ ለአጓጓዥ የሚያስረክብ ሰው ነው፤
5. “ተረካቢ” ማለት ዕቃውን ለመቀበል ህጋዊ መብት ያለው ሰው ነው፤
6. “መጋዘን” ማለት ማንኛውም ብትንም ሆነ ጥቅል ዕቃዎችን በኮንቴነር ጭምር የመጫኛና የማራገፊያ አገልግሎት የሚሰጥ ማንኛውም ቦታ ሆኖ ወደብንና የጉምሩክ መጋዘንን ይጨምራል፤
7. “አሽከርካሪ” ማለት የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ለመንዳት የሚያስችለው ህጋዊ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ያለው ሰው ነው፤
8. “ዲመሬጅ” ማለት የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪን፡-
   ሀ) በላኪ፣ በተረካቢ ወይም በመጋዘን ለመጫኛ ወይም ለማራገፊያ ከተወሰነው የጊዜ ገደብ በላይ፤ ወይም
   ለ) በመንግሥት ተቆጣጣሪ አካል ለማካሄድ የቁጥጥር ሥራ ከተወሰነው የጊዜ ገደብ በላይ፤

   እንዲቆይ በመደረጉ ለባከነው ጊዜ ማካካሻ የሚፈጸም ክፍያ ነዉ፤
9. “የመጫኛ ወይም የማራገፊያ ጊዜ” ማለት የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ለመጫን ወይም ለማራገፍ የተወሰነለት ቦታ ከደረሰ በኋላ ጭነቱን ለመጫን ወይም ለማራገፍ የሚወስደው ጊዜ ሲሆን ተፈላጊ ሰነዶች ተጠናቀዉና ተፈርመው አሽከርካሪው የሚረከብበትን ጊዜ ያጠቃልላል፤
10. “ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት እንደቅደምተከተሉ የትራንስፖርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤
11. “ባለስልጣን” ማለት በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/2005 የተቋቋመው የትራንስፖርት ባለሥልጣን ነው፤
12. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
13. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በጭነት ላኪዎች፣ ተረካቢዎች፣ የመጫኛና የማራገፊያ አገልግሎት በሚሰጡ መጋዘኖች፣ የፍተሻና የቁጥጥር ስራ በሚያከናውኑ አካላት፣ የጭነት ትራንስፖርት አገልገሎት በሚሰጡ ትራንስፖርተሮች እና የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የመጫኛ፣ የማራገፊያና የቁጥጥር ጊዜ ገደብ እና የዲመሬጅ ክፍያ

4. **የመጫኛ፣ የማራገፊያና የቁጥጥር ጊዜ ገደብ**

   1. ማንኛዉም ላኪ፣ ተረካቢ ወይም የመጋዘን አገልግሎት የሚሰጥ አካል፡-

      ሀ) የመጫን አቅሙ 20 ቶን ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪን በ8 ሰዓት ውስጥ የመጫን ወይም 6 ሰዓት ውስጥ የማራገፍ፤ ወይም

      ለ) የመጫን አቅሙ ከ20 ቶን በታች የሆነ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪን በ5 ሰዓት ውስጥ የመጫን ወይም በ4 ሰዓት ውስጥ የማራገፍ ግዴታ አለበት፡፡

   2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው የጊዜ ገደብ መቆጠር የሚጀምረዉ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዉ የመጫኛ ወይም የማራገፊያ ቦታው እንደደረሰ ይሆናል፡፡

   3. የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪው የመጫኛ ወይም የማራገፊያ ቦታው ከደረሰ በኋላ ከአጓጓዡ ጋር ባልተያያዘ ምክንያት የመጫኛ ወይም የማራገፊያ ቦታ ለውጥ ከተደረገ በለውጡ ምክንያት የባከነው ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተካቶ ይታሰባል።

5. **የቁጥጥር ጊዜ ገደብ**

   1. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ የጫነዉን ዕቃ በመግቢያ ወይም በመውጫ በር ወይም በመተላለፊያ መንገድ ላይ የሚያደርገውን ቁጥጥር በአንድ ሰዓት ውስጥ እንዲሁም በመዳረሻ የጉምሩክ ጣቢያ የሚያደርገዉን ከአራት ሰዓት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅ አለበት፡፡

   2. የግብርና ሚኒስቴር የእንስሳት ኳራንቲን ጣቢያ፡-

      ሀ) የአንድ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪን ንጽህና እና ምቹነት የማረጋገጥ ስራ በ30 ደቂቃ ዉስጥ፤

      ለ) በአንድ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ የተጫኑ እንስሳትን የጤና ማረጋገጫ ሰርተፍኬት መስራትና መስጠት በሦስት ሰዓት ውስጥ፤

      ሐ) የአንድ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪን የመኖ የይለፍ ሰርተፍኬት መስራትና መስጠት በ30 ደቂቃ ውስጥ፤

      ማጠናቀቅ አለበት፡፡

3. የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የአንድ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪን የክብደት ሚዛን ቁጥጥር በ20 ደቂቃ ውስጥ ማጠናቀቅ አለበት፡፡
4. በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ በግብርና ሚኒስቴር፣ በንግድ ሚኒስቴር ወይም የተቆጣጣሪነት ሥልጣን ባለው የሚመለከተው ሌላ መንግሥታዊ አካል የሚካሄድ አንድ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ የጫነውን ዕቃ የመቆጣጥር ሥራ በሦስት ሰዓት ውስጥ መጠናቀቅ አለበት፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)፤ (2)፤ (3) እና (4) የተመለከተው የጊዜ ገደብ መቆጠር የሚጀምረው የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪው ቁጥጥር ወደሚደረግበት ጣቢያ እንደደረሰ ይሆናል፡፡

6. <u>**የመጫኛ፣ የማራገፊያና የቁጥጥር የሥራ ሰዓት**</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 መሠረት የመጫንና የማራገፍ አገልግሎት የሚሰጥ መጋዘን ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 መሠረት ቁጥጥር የሚያካሂድ ማንኛውም ተቆጣጣሪ አካል ከሰኞ እስከ እሁድ 24 ሰዓት ሙሉ ይህንኑ አገልግሎት መስጠት አለበት፡፡

7. <u>**የዲመሬጅ ክፍያ**</u>

1. ማንኛውም ላኪ፣ ተረካቢ ወይም የመጋዘን አገልግሎት የሚሰጥ አካል በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 በተደነገገው መሠረት ግዴታውን ካልተወጣ፡-
   - ሀ) የመጫን አቅሙ 20 ቶን ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪን በሚመለከት፡-
     1) ለመጀመሪያ ሁለት ሰዓት የባከነ ጊዜ በሰዓት ብር 100 ሂሳብ፤
     2) ከሁለት ሰዓት በላይ እስከ አራት ሰዓት ለባከነ ጊዜ በሰዓት ብር 150 ሂሳብ፤
     3) ከአራት ሰዓት በላይ ለባከነ ጊዜ በሰዓት ብር 200 ሂሳብ፤ ወይም
   - ለ) የመጫን አቅሙ ከ20 ቶን በታች የሆነ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪን በሚመለከት፡-
     1) ለመጀመሪያ ሁለት ሰዓት የባከነ ጊዜ በሰዓት ብር 75 ሂሳብ፤
     2) ከሁለት ሰዓት በላይ እስከ አራት ሰዓት ለባከነ ጊዜ በሰዓት ብር 100 ሂሳብ፤
     3) ከአራት ሰዓት በላይ ለባከነ ጊዜ በሰዓት ብር 150 ሂሳብ፤

የዲመሬጅ ክፍያ ለአጓጓዡ መክፈል አለበት፡

2. ማንኛውም ቁጥጥር የሚያካሂድ አካል በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 በተደነገገው መሠረት ግዴታውን ካልተወጣ፡-
   ሀ) የመጫን አቅሙ 20 ቶን ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪን በሚመለከት ለባከነ ጊዜ በሰዓት ብር 100 ወይም
   ለ) የመጫን አቅሙ ከ20 ቶን በታች የሆነ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪን በሚመለከት ለባከነ ጊዜ በሰዓት ብር 75 ሂሳብ፣

   የዲመሬጅ ክፍያ ለአጓጓዡ መክፈል አለበት፣ ሆኖም የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪው ከተወሰነው የጊዜ ገደብ በላይ እንዲቆይ ሊደረግ የቻለው መቅረብ የሚገባው የጭነት ማጓጓዣ ሰነድ በአጓጓዡ ባለመቅረቡ ምክንያት ከሆነ የዲመሬጅ ክፍያ ሊጠየቅ አይችልም።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት የዲመሬጅ ክፍያ ተግባራዊ የሚሆነው በቀን ለ10 ሰዓት ብቻ ይሆናል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ከሚወሰነው የዲመሬጅ ክፍያ በላይ የሆነ ጉዳት የደረሰበት አጓጓዥ በማጓጓዣ ውሉና አግባብ ባለው ህግ መሰረት ተጨማሪ የጉዳት ካሣ የመጠየቅ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
5. የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪን ለመጫን ወይም በማራገፍ ወይም ለቁጥጥር ከተወሰነው የጊዜ ገደብ በላይ ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት እንዲቆይ ያደረገ የመንግሥት መጋዘን ወይም የተቆጣጣሪ አካል ሠራተኛ ወይም ኃላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሠረት በአሠሪው የተፈጸመን የዲመሬጅ ክፍያ የመተካት ኃላፊነት አለበት።

8. <u>**የመጫኛ፣ የማራገፊያና የቁጥጥር ጊዜ ማረጋገጫ ሰነድ**</u>

1. ማንኛውም ላኪ፣ ተረካቢ፣ መጋዘን ወይም ተቆጣጣሪ አካል የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ በመጫኛ፣ በማራገፊያ ወይም በመቆጣጠሪያ ቦታ የደረሰበትንና አጠናቆ የወጣበትን ቀንና ሰዓት ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀ ቅጽ ላይ መዝግቦ ከአሽከርካሪው ጋር መፈራረም አለበት፣
2. አሽከርካሪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በተመዘገበው ቀንና ሰዓት የማይስማማ ከሆነ ልዩነቱን አስፍሮ ሰነዱን መፈረምና በአቅራቢያው ለሚገኝ

የባለሥልጣኑ የትራንስፖርት ኢንስፔክተር ወይም በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/2005 አንቀጽ 24 መሠረት በባለሥልጣኑ ውክልና ለተሰጠው አካል ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ሪፖርት የደረሰው የትራንስፖርት ኢንስፔክተር ወይም ውክልና የተሰጠው አካል ጉዳዩን አጣርቶ የምርመራ ውጤቱን የያዘ ማስረጃ ለሚመለከታቸው ወገኖች ይሰጣል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

9. **የባለስልጣኑ ሥልጣንና ተግባር**

ባለስልጣኑ፡-

1. ይህ አዋጅ በሚገባ በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
2. እንደአስፈላጊነቱ በጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የመጫኛ፣ የማራገፊያና የመቆጣጠሪያ ቦታዎች የትራንስፖርት ኢንስፔክተሮች ይመድባል፤
3. ሞዴል የጭነት ማመላለሻ ውልና የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ እንቅስቃሴ መቆጣጠሪያ ቅጾችን ያዘጋጃል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፤
4. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን የጭነት ማጓጓዣ ታሪፍ በማጥናት የውሳኔ ሃሣብ ያቀርባል፤ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሲጸድቅም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፡፡

10. **ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛዉም ህግ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

11. **ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ በሚገባ ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።
2. ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

12.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ 9 ቀን 2006 ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**<u>አዋጅ ቁጥር 843/2006</u>**

**<u>የክፍያ መንገዶች አዋጅ</u>**

የመንገድ ዘርፍ ልማት በአገሪቱ የሚካሄደውን ሁሉን አቀፍ ልማት ለማፋጠንና ድህነትን ለማስወገድ ቁልፍ ሚና ያለው በመሆኑ፤

በአገሪቱ በክፍያ አገልግሎት የሚሰጡ ዘመናዊና የተሻሻሉ መንገዶች መገንባት በመጀመራቸውና እነዚህ መንገዶች ካላቸው ልዩ ባህሪ አኳያ የተለየ የመንገድ አስተዳደርን የሚሹ በመሆኑ፤

ከዚህም በመነሳት በክፍያ አገልግሎት የሚሰጡ መንገዶች የሚተዳደሩበት ሕግ ማውጣት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግስት አንቀጽ 55 (1) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**<u>ክፍል አንድ</u>**

**<u>ጠቅላላ</u>**

1. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

   ይህ አዋጅ "የክፍያ መንገዶች አዋጅ ቁጥር 843/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **<u>ትርጓሜ</u>**

   በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

   1. "ሚኒስቴር" ማለት የትራንስፖርት ሚኒስቴር ነው፤
   2. "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ነው፤
   3. "ኢንተርፕራይዝ" ማለት በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የሚቋቋም የኢትዮጵያ የክፍያ መንገዶች ኢንተርፕራይዝ ነው፤
   4. "የክፍያ መንገድ" ማለት የመንገድ ተጠቃሚዎች ክፍያ እየከፈሉ የሚጠቀሙበት መንገድ ነው፤
   5. "የአገልግሎት ክፍያ" ማለት ማንኛውም ተሽከርካሪ የክፍያ መንገድን ለመጠቀም የሚከፍለው ክፍያ ነው፤
   6. "ተሽከርካሪ" ማለት ብስክሌትን፤ ሞተር ብስክሌትን፤ ባለሶስት እግር ተንቀሳቃሽን፤ የኮንስትራክሽን ልዩ ተንቀሳቃሽ መሳሪያንና ልዩ ወታደራዊ

ተሽከርካሪን ሳይጨምር በመንገድ ላይ በሜካኒካልና በኤሌክትሮኒክ ሃይል እየተንቀሳቀሰ የሚሄድ ማንኛውን ተሽከርካሪ ነው፤

7. “ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
8. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል፡፡

3. <u>**የተፈጻሚነት ወሰን**</u>

ይህ አዋጅ የፌደራል መንግሥት በሚያስተዳድራቸው የክፍያ መንገዶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለክፍያ መንገድና የአገልግሎት ክፍያ</u>

4. <u>**የባለሥልጣኑ ኃላፊነት**</u>
   1. ባለሥልጣኑ የክፍያ መንገዶች የሚለሙበትን ዕቅድ ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
   2. ባለሥልጣኑ የክፍያ መንገዶች የሚገነቡበትን ውሎች ይዋዋላል፤ ያስፈጽማል፤
   3. ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የክፍያ መንገድን በነጻ እንዲያገለግል ያደርጋል፤ መንገዱንም ያስተዳድራል፡፡

5. <u>**የአገልግሎት ክፍያ አፈጻጸም**</u>
   1. የክፍያ መንገድን የሚጠቀም ተሽከርካሪን በሚመለከት የአገልግሎት ክፍያውን ለሚሰበስበው አካል የመክፈል ኃላፊነት ያለበት አሽከርካሪው ነው፡፡
   2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የአገልግሎት ክፍያን በኤሌክትሮኒክ ዘዴ፤ በቅድመ ክፍያና በዱቤ ሥርዓት መፈጸም ይቻላል፡ ፡

6. <u>**ከአገልግሎት ክፍያ ነጻ ስለመሆን**</u>
   1. ከድንገተኛ አደጋ ጋር በተያያዘ የሚጓዙ የእሳት አደጋ ተሽከርካሪዎች፣ አምቡላንሶች እና በአስቸኳይ ሥራ ጉዳይ የሚጓዙ የመከላከያ፣ የፖሊስና የደህንነት ኃይሎች ተሽከርካሪዎች ከአገልግሎት ክፍያ ነጻ ይሆናሉ፡፡
   2. ሚኒስቴሩ ከላይ በንዑስ አንቀጽ (1) በተገለጹት እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሌሎች ሁኔታዎች ከአገልግሎት ክፍያ ነፃ የመሆን መብት ስለሚሰጥበት አግባብ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

7. **የአገልግሎት ክፍያ የመክፈል ግዴታ**

ከአገልግሎት ክፍያ ነጻ እንዲሆኑ ከተፈቀደላቸው ተሽከርካሪዎች በስተቀር ማንኛውም ሰው የአገልግሎት ክፍያ ሳይከፍል በክፍያ መንገድ ላይ ተሽከርካሪን ማሽከርከር አይችልም፡፡

8. **የአገልግሎት ክፍያ ታሪፍ**

   1. ኢንተርፕራይዙ ከሚያስተዳድራቸው የክፍያ መንገዶች ከተጠቃሚዎች የሚሰበሰብ የአገልግሎት ክፍያን ታሪፍ ይወሰናል፡፡
   2. ሚኒስቴሩ የታሪፉን አግባብነትና አፈጻጸም ያረጋግጣል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

9. **ቅጣት**

   1. የአገልግሎት ክፍያ ትኬት ሳይዝ በክፍያ መንገድ ላይ ሲያሽከረክር የተገኘ አሽከርካሪ ከመንገዱ መነሻ እስከ መድረሻ ላለው ርቀት የተቀመጠውን የአገልግሎት ክፍያ ታሪፍ ሦስት እጥፍ ይከፍላል።
   2. የተጭበረበረ የአገልግሎት ክፍያ ትኬት ይዞ በክፍያ መንገድ ላይ ሲያሽከረክር የተገኘ አሽከርካሪ በወንጀል ሕግ መሠረት የሚጠየቅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከመንገዱ መነሻ እስከ መድረሻ ላለው ርቀት የተቀመጠውን የአገልግሎት ክፍያ ታሪፍ አምስት እጥፍ ይከፍላል።
   3. በክፍያ መንገድ ላይ ተሽከርካሪው በብልሽትም ሆነ በሌላ ምክንያት መቆሙን በ30 ደቂቃ ውስጥ ለመንገዱ አስተዳዳሪ ያላሳወቀ አሽከርካሪ ብር 100 ይቀጣል፡፡
   4. በማንኛውም ምክንያት ከአንድ ሰዓት በላይ በክፍያ መንገድ ላይ ተሽከርካሪ ከቆመ የመንገዱ አስተዳዳሪ ተሽከርካሪውን የሚያነሳው ሲሆን ለተሽከርካሪው ማንሻና ማቆያ እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለመንገዱ ጥገና የሚወጣውን ወጪ አሽከርካሪው ወይም ባለቤቱ ይከፍላል፡፡
   5. በሕግ ከተፈቀደው ክብደት በላይ የጫነ ተሽከርካሪን በክፍያ መንገድ ላይ ያሽከረከረ አሽከርካሪ አግባብ ባለው ህግ ለትርፍ ጭነት የተጣለውን ቅጣት ይከፍላል፡፡
   6. በክፍያ መንገድ አጥር ክልል ውስጥ ገብቶ መንገዱን የሚያቋርጥ እግረኛ ብር 50 ይቀጣል፡፡

7. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (5) በተደነገጉት መሰረት ቅጣት የተጣለበት አሽከርካሪ ቅጣቱን እስከሚከፍል ድረስ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱ ተይዞ ይቆያል፡፡
8. ኢንተርፕራይዙ ራሱ የሚያስተዳድራቸው የክፍያ መንገዶችን በሚመለከት በዚህ አንቀጽ የተጣሉ ቅጣቶችን ያስፈጽማል፡፡
9. በዚህ አዋጅ ያልተሸፈኑ የትራፊክ ደንብ መተላለፍ ጉዳዮች በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ይታያሉ።
10. ሚኒስቴሩ መመሪያ በማውጣት በዚህ አንቀጽ የተጣሉትን ቅጣቶች መጠን የማሻሻል ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

10. <u>**ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች**</u>

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም

11. <u>**ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን**</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ሚኒስቴሩ ይህንን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

12. <u>**የመተባበር ግዴታ**</u>

ማንኛውም ሰው ይህንን አዋጅ ለሚያስፈጽሙ አካላት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

13. <u>**አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዘደንት**

## ደንብ ቁጥር 340/2007

## በክብደት ላይ የተመሠረተ ዓመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በመንገድ ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 66/1989 አንቀጽ 6 (1) (ሐ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

1. **አጭር ርእስ**

   ይህ ደንብ "በክብደት ላይ የተመሠረተ ዓመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 340/2007" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፤

   1. "አዋጅ" ማለት የመንገድ ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 66/1989 ነው፤
   2. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተሰጡ ትርጓሜዎች በዚህ ደንብም ተፈጻሚ ይሆናሉ፤
   3. "በክብደት ላይ የተመሠረተ ዓመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ" ማለት ለማናቸውም ተሽከርካሪ በሚኖረው የመጫን አቅም ወይም የመቀመጫ ብዛት እና የአክስል መጠን ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ መሠረት የሚፈፀም ክፍያ ነው፤
   4. "ተለጣፊ ምልክት" ማለት የተሽከርካሪ ባለንብረት ወይም ባለይዞታ በዚህ ደንብ መሠረት ዓመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ መፈፀሙን ለማረጋገጥ የሚሰጥ ተለጣፊ ምልክት ነው፤
   5. "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትራንስፖርት ባለሥልጣን ነው፤
   6. "ቢሮ" ማለት በተሽከርካሪዎች ላይ ዓመታዊ ምዝገባና የቴክኒክ ምርመራ ለማካሄድ በሕግ ሥልጣን የተሰጠው የክልል አካል ነው፤
   7. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 (1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

8. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
9. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ጾታ ይጨምራል፡፡

3. **የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ ደንብ በሕግ በግልፅ ተለይተው ተፈጻሚ እንዳይሆንባቸው ከተደረጉት ተሽከርካሪዎች በስተቀር በማንኛውም የኢትዮጵያ መንገዶች ላይ በሚንቀሳቀሱ ማናቸውም ተሽከርካሪዎች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

4. **ስለክፍያ**

1. የማናቸውም ተሽከርካሪ ባለንብረት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ በተመለከተው ታሪፍ መሠረት ዓመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ መክፈል አለበት፤
2. በዚህ ደንብ መሠረት መከፈል ያለበት ክፍያ ያልተፈፀመለትን ተሽከርካሪ ይዞ የተገኘ ማንኛውም ባለይዞታ ወይም አሽከርካሪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር (1) የተመለከተውን ክፍያ መክፈል አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሠረት ክፍያ ከተፈጸመ በኋላ ባለሥልጣኑ ወይም ቢሮው ለባለንብረቱ፣ ባለይዞታው ወይም አሽከርካሪው ክፍያ በተፈፀመለት ተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሰሌዳ አንድ ተለጣፊ ምልክት ይሰጠዋል።

5. **ተለጣፊ ምልክትን ስለመያዝና ስለማሳየት**

1. ከፊት የንፋስ መከላከያ መስታወት ላላቸው ባለሞተር ተሽከርካሪዎች የተሰጠው ተለጣፊ ምልክት ከመስታወቱ ላይ በታችኛው የቀኝ ማዕዘን ተለጥፎ መታየት አለበት፡፡
2. ከፊት የንፋስ መከላከያ መስታወት ለሌላቸው ባለሞተር ተሽከርካሪዎች የተሰጠው ተለጣፊ ምልክት በማንኛውም ተሽከርካሪውን በሚነዳው፣ በሚያንቀሳቅሰው ወይም በሚያስጠግነው ሰው እጅ መቀመጥ አለበት፡፡
3. ለተሳቢ ወይም ግማሽ ተሳቢ የሚሰጥ ተለጣፊ ምልክት በጎታቹ ባለሞተር ተሽከርካሪ መስታወት ላይ በታችኛው የቀኝ ማዕዘን ይህንኑ ተሳቢ ወይም ግማሽ ተሳቢ ከሚጎትተው ባለሞተር ተሽከርካሪ ከተሰጠው ተለጣፊ ምልክት ጎን ተለጥፎ መታየት አለበት፡፡

6. **ስለክፍያ አሰባሰብ**

   1. በአዋጁ አንቀጽ 6(4) በተደነገገው መሠረት ባለሥልጣኑ ወይም ቢሮው ወይም እነርሱ ውክልና የሚሰጡት አካል ማናቸውም ተሽከርካሪ ለዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራና ምዝገባ ሲቀርብለት ከዚሁ ተሽከርካሪ ሊሰበሰብ የሚገባውን ዓመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ መሰብሰብ አለበት፡፡
   2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተሰበሰበ ክፍያ በአንድ ወር ውስጥ ወደ መንገድ ፈንድ የባንክ ሂሣብ ገቢ መደረግ አለበት፡፡

7. **ተለጣፊ ምልክት ስለማዘጋጀት እና የአገልግሎት ዘመን**

   1. በባለሥልጣኑ፣ በቢሮው ወይም እነርሱ በሚወክሉት አካል በኩል አገልግሎት ላይ የሚውሉትን ተለጣፊ ምልክቶች እና የክፍያ መሰብሰቢያ ደረሰኞች አዘጋጅቶ የሚያሠራጨው የመንገድ ፈንድ ጽህፈት ቤት ነው፡፡
   2. የተለጣፊ ምልክት ከተሠጠበት ቀን አንስቶ ለአንድ አመት ብቻ የሚያገለግል ይሆናል፡፡

8. **ተለጣፊ ምልክት አለመኖር**

   1. ተሽከርካሪን የሚነዳ፣ የሚያንቀሳቅስ ወይም የሚያሠራ ሰው የተሽከርካሪውን ተለጣፊ ምልክት እንዲያሳይ በትራፊክ ፖሊስ ወይም በሌላ ሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ሲጠየቅ ወዲያውኑ ማሳየት አለበት፡፡
   2. የተሽከርካሪው ባለቤት ወይም ባለይዞታ ክፍያ መፈጸሙን እስኪያረጋግጥ ድረስ ትራፊክ ፖሊስ ተሽከርካሪውን በቁጥጥር ሥር አውሎ በሥራ ሰዓት የተያዘ ከሆነ ከስድስት ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ፣ ከሥራ ሰዓት ውጪ የተያዘ ከሆነ እንደሁኔታው ከአስራ ሁለት ወይም ከሃያ አራት ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ተሽከርካሪው በተገኘበት ክልል ለሚገኘው ክፍያ ሰብሳቢ ባለስልጣን ወይም ቢሮ ያቀርበዋል፡፡
   3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት በቁጥጥር ሥር የዋለው ተሽከርካሪ የሚለቀቀው በዚህ ደንብ የተወሰነውን ክፍያ ተፈጽሞ ተለጣፊ ምልክት ሲሰጠው ወይም ክፍያውን የፈጸመ ለመሆኑ የሚያስረዳ ማስረጃ ሲያቀርብ ይሆናል፡፡

9. <u>ምትክ ተለጣፊ ምልክት ስለመስጠት</u>

ተለጣፊ ምልክት የጠፋ፣ የተሰረቀ የተቀደደ፣ የተበላሸ ወይም የማይነበብ የሆነ እንደሆነ፣ የተሽከርካሪው ባለንብረት ወይም ባለይዞታ ምትክ ተለጣፊ ምልክት እንዲሰጠው ለባለሥልጣኑ ወይም ለቢሮው ወይም በእነርሱ ለተወከለው አካል ሲያመለክት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያው ሠንጠረዥ የተመለከተውን ክፍያ ሲፈጽም ምትክ ተለጣፊ ምልክት ይሰጠዋል።

10. <u>ደንብ መተላለፍ</u>

ይህን ደንብ ተላልፎ የተገኘ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው የደንብ መተላለፍ ድንጋጌ መሠረት ይቀጣል፡፡

11. <u>ደንቡ ስለሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት 16 ቀን 2007 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስቴር**

## ክብደት ላይ የመሠረት ዓመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ ታሪፍ

| ተ.ቁ | የተሽከርካሪ ዓይነት ወይም የመጫን አቅም | የአመታዊ ክፍያ መጠን/በብር/ |
|---|---|---|
| 1 | **አውቶሞቢሎችና የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች** | |
| 1.1 | እስከ 5 መቀመጫ ያላቸው | 125 |
| 1.2 | ከ 6 እስከ 12 መቀመጫ ያላቸው | 150 |
| 1.3 | ከ13 እስከ 29 መቀመጫ ያላቸው | 200 |
| 1.4 | ከ30 እስከ 41 መቀመጫ ያላቸው | 250 |
| 1.5 | ከ 41 በላይ መቀመጫ ያላቸው | 800 |
| 2 | **የደረቅ ጭነት ማመላለሻዎች** | |
| 2.1 | እስከ 15 ኩንታል | 300 |
| 2.2 | 16 እስከ 35 ኩንታል የሚጭኑ | 550 |
| 2.3 | 36 እስከ 70 ኩንታል የሚጭኑ | 1000 |
| 2.4 | 71 እስከ 120 ኩንታል የሚጭኑ | 1500 |
| 2.5 | 121 እስከ 180 ኩንታል የሚጭኑ | 2000 |
| 2.6 | ከ180 ኩንታል በላይ የሚጭኑ | 2500 |
| 3 | **የፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ** | |
| 3.1 | እስከ 1000 ሊትር የሚጭኑ | 750 |
| 3.2 | ከ 1001 እስከ 13,000 ሊትር የሚጭኑ | 1250 |

| | | |
|---|---|---|
| 3.3 | ከ 13001 እስከ 14,000 ሊትር የሚጭኑ | 1500 |
| 3.4 | ከ 14,001 ሊትር በላይ የሚጭኑ | 2000 |
| 4 | **ሌሎች** | |
| 4.1 | ሞተር ሳይክሎች | 50 |
| 4.2 | ልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያዎች ወይም ከመንገድ ውጪ የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች | 300 |
| 5 | **ምትክ ተለጣፊ ሲሰጥ** | 100 |

## አዋጅ ቁጥር 1048/2009

## የባቡር ትራንስፖርት አስተዳደር አዋጅ

የባቡር ትራንስፖርት ተስፋፍቶ የሀገሪቱን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የሚደግፍ አማራጭ የትራንስፖርት ንዑስ ዘርፍ ለማድረግ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር የሚገባ በመሆኑ፤

የባቡር መሰረተ-ልማቶች የሚገነቡበትና አገልግሎት ላይ የሚውሉበት ሀገር አቀፍ ደረጃ የሚወሰንበት ሥርዓት መዘርጋት የሚያስፈልግ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 55(2) (ሐ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡-

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የባቡር ትራንስፖርት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1048/2009" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

   1. "የእውቅና የምስክር ወረቀት" ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት የተወሰነ አገልግሎት እንዲሰጥ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል እውቅና ለተሰጠው ተቋም የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፤
   2. "እውቅና የተሰጠው ተቋም" ማለት የጥገና ተቋም፣ የሥልጠና ማዕከል፣ ወይም የምዘና ተቋም ነው፤
   3. "ምዘና" ማለት የባቡር ሥራ ባለሙያን ሙያዊ ብቃት ወይም የባቡርንና የባቡር መሠረተ-ልማት ክፍሎችን የቴክኒክና የደህንነት ብቃትን ለማረጋገጥ ሲባል የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ወይም በምዘና ተቋም የሚከናወን ተግባር ነው፤
   4. "የምዘና ባለሙያ" ማለት የባቡር ሥራ ባለሞያዎችን፣ ባቡሮችን፣ ወይም የባቡር መሠረተ-ልማት ክፍልን የቴክኒክና የደህንነት ብቃት ለመመዘን ወይም ለመፈተሸና የሙያ ምስክርነት ለመስጠት እንዲችል የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር

በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጠው የተፈጥሮ ሰው ነው፤

5. “የምዘና ተቋም” ማለት ምዘናን በማከናወን ሙያዊ ምስክርነት እንዲሰጥ በዚህ አዋጅ መሠረት የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የእውቅና ምስክር ወረቀት የተሰጠው ተቋም ነው፤
6. “ኦዲት” ማለት የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የፀደቀ የደህንነት አስተዳዳር ሥርዓት በመሠረተ-ልማት አስተዳዳሪው ወይም በአገልግሎት ሰጪው ተቋም በአግባቡ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ተብሎ የሚከናወን ተግባር ነው፤
7. “የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ” ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ለባቡር ሥራ ባለሙያዎች የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤
8. “የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ሥርዓት” ማለት የኤሌክትሪክ ኃይልን በመጠቀም ለሚጓዝ ባቡር የኤሌክትሪክ ኃይል የሚቀርብበት ጠቅላላ ሥርዓት ሲሆን ኤሌክትሪክ የተሸከመ ገመድን፣ የኤሌክትሪክ ኃይል መቀየሪያን ወይም መመጠኛ መሣሪያን፣ የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ ንዑስ ጣቢያን፣ በንዑስ ጣቢያዎች መካከል የተዘረጋ የኤሌክትሪክ መስመርን እና ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መሣሪያዎች ያጠቃልላል፤
9. “ፈታኝ” ማለት አሰልጣኝ መሆን አለመሆኑ ከግምት ሳይገባ ሥልጠና ላጠናቀቁ የባቡር ሥራ ባለሙያዎች የንድፈ-ሀሳብና የተግባር ፈተና የሚያዘጋጅ፣ የሚፈትን እና ውጤት የሚሰጥ የተፈጥሮ ሰው ነው፤
10. “የፌደራል ፀጥታ አካላት” ማለት የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን እና የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ነው፤
11. “የመሠረተ ልማት አስተዳዳሪ” ማለት የባቡር መሠረተ ልማትን የማስተዳደር በተለይም የመሠረተ-ልማትን የመጠገን፣ በመሠረተ-ልማት ላይ የሚደረግ የባቡር ትራፊክን የመምራት፣ የመቆጣጠርና ተገቢ ምልክቶችንና ማመልከቻዎች የመትከል ኃላፊነት ያለበት ተቋም ነው፤

12.“ኢንስፔክሽን” ማለት የዚህን አዋጅ እና አዋጁን መሠረት አድርገው የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ለማረጋገጥ ሲባል የሚከናወን ተግባር ነው፤

13.“ሎኮሞቲቭ” ማለት ከተገጠመለት ሞተር የሚያገኘውን ኃይል በመጠቀም በሀዲድ ላይ የሚጓዝ ማንኛውም ባቡር ነው፤

14.“የጥገና ኃላፊ” ማለት ማንኛውም ጥገና የተደረገለት ባቡር ወይም የመሠረተ-ልማት ክፍል ወይም የእነዚህ አካል የሆነ ማናቸውም መሣሪያ የደህንነት ሥጋት ሳይፈጥር ተመልሶ አገልግሎት ላይ ለመዋል እንደሚችል ማረጋገጫ የሚሰጥ የተፈጥሮ ሰው ነው፤

15.“የጥገና ተቋም” ማለት እንደ አግባብነቱ ባቡርን ወይም የባቡር መሠረተ ልማትን ወይም ሁለቱንም የመጠገን ሥራ እንዲሰራ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የእውቅና የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም ተቋም ሲሆን በባቡር መሠረተ-ልማት አስተዳዳሪ ወይም በአገልግሎት ሰጪ ተቋም ለተመሳሳይ ተግባር የተደራጀ የሥራ ክፍልን ይጨምራል፤

16.“ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የትራንስፖርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

17.“ኔትወርክ” ማለት በአንድ የመሠረተ ልማት አስተዳዳሪ ሀላፊነት ሥር የሚተዳዳር የባቡር መሠረተ-ልማት ነው፤

18.“ሀዲድ” ማለት ባቡር እንዲሔድበት ተብሎ በባቡር መስመር ላይ የተዘረጋ ብረት ነው፤

19.“የባቡር መሠረተ ልማት” ማለት የባቡር መስመር፣ የደህንነትና የመገናኛ መሣሪያዎች፣ የጥገና ተቋም፣ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ሥርዓት፣ እና የባቡር ጣቢያዎችን የያዘ መሠረተ ልማት ሲሆን ባቡርን አይጨምርም፤

20.“የባቡር መስመር” ማለት ባቡር እንዲሄድበት ተብሎ የተዘረጋን ሀዲድ፣ ሀዲድ የተዘረጋበትን የመሬት ወይም የድልድይ ክፍል፣ ሀዲድን ከሌላ የመንገድ ተጠቃሚ ለመለየት የተሰራ አጥርን ወይም መከለያን እና ከእነዚህ ጋር የተያያዘ መሠረተ-ልማትን አጠቃሎ የሚይዝ የባቡር መሠረተ-ልማት ክፍል ነው፤

21.“የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት” ማለት ባቡርን በመጠቀም በባቡር መሠረተ ልማት ላይ መንገደኞችን ወይም ዕቃዎችን ከቦታ ወደ ቦታ የማጓጓዝ ተግባር ነው፤

22.“አገልግሎት ሰጪ” ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት አግባብነት ያለው ፈቃድ የተሰጠውና ዋነኛ ተግባሩ የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት የሆነ የመንግስት ወይም የግል ተቋም ነው፤

23.“የባቡር ሥራ” ማለት በባቡር ማስተርነት፣ በጥገና ኃላፊነት፣ በአሰልጣኝነት፣ በፈታኝነት፣ በባቡር ፍሰት ተቆጣጣሪነት፣ በምዘና ባለሙያነት፣ በደህንነት አስተዳደር ሥርዓት ኃላፊነት የሚከናወን ተግባር ነው፤

24.“የደህንነትና የመገናኛ መሣሪያዎች” ማለት ደህንነቱ የተጠበቀ የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ተብሎ ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም መሣሪያ ማለት ሲሆን የሬዲዮና የምስል መልዕክት መቀበያና ማስተላለፊያ መሣሪያን፣ ከባቡር ውጪ በመሆን የባቡርን እንቅስቃሴ ለማወቅ፣ ለመምራትና ለመቆጣጠር የሚያገለግል የግንኙነትና የመቆጣጠሪያ መሣሪያን፣ በባቡር መሠረተ-ልማት ውስጥና አቅራቢያ የተተከለ ምልክትና ማመላከቻን ይጨምራል፤

25.“የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ” ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ለመሠረተ-ልማት አስተዳዳሪ ደህንነቱ የተረጋገጠ የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ዝግጅትና አቅም ያለው መሆኑን ሲረጋገጥ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

26.“የደህንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት” ማለት አገልግሎት ሰጪ ተቋም ደህንነቱ የተረጋገጠ የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ዝግጅትና አቅም ያለው መሆኑን ሲረጋገጥ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የሚሰጥ ምስክር ወረቀት ነው፤

27.“የደህንነት አስተዳደር ሥርዓት” ማለት የመሰረተ ልማት አስተዳዳሪ ወይም የአገልግሎት ሰጪ ተቋም የሚያከናውናቸው ተግባራት ደህንነቱ የተጠበቀ የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚዘረጉት ድርጅታዊ መዋቅርና የአሠራር ሥርዓት ነው፤

28.“የደህንነት አስተዳደር ሥርዓት ኃላፊ” ማለት የደህንነት አስተዳደር ሥርዓት በአግባቡ ስለመተገበሩ ኃላፊነት ያለበት የተፈጥሮ ሰው ነው፤

29.“የደህነት ሥጋት ክስተት” ማለት በባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ላይ የደህንነት ሥጋት የፈጠረ ነገር ግን የባቡር አደጋ ያላስከተለ ማንኛውም ክስተት ወይም ድርጊት ነው፤

30.“ተጨማሪ የባቡር ማስተርነት የምስክር ወረቀት” ማለት የባቡር ማስተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ያለው ሰው አንድን የባቡር ዓይነት በአንድ የባቡር መስመር ላይ ለመንዳት እንዲችል በዚህ አዋጅ መሰረት በአገልግሎት ሰጪ ተቋም የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፤

31.“ባቡር” ማለት የራሱን የሞተር ኃይል በመጠቀም ወይም በሌላ የሞተር ኃይል በተገጠመለት ተሽከርካሪ በመሳብ ወይም በመገፋት በሀዲድ ላይ የሚጓዝ ተሽከርካሪ ሲሆን ሎኮሞቲቭ ወይም ፉርጎ በመባል ይከፈላል፤

32.“የባቡር አደጋ” ማለት ከባቡር ትራንስፖርት ጋር በተያያዘ መነሻው ከባቡር መሰረተ ልማት ወይም ከባቡር ውስጥ ሆኖ በባቡር መሰረተ ልማት ውስጥ፣ በባቡር ውስጥ እና ከባቡር መሰረተ ልማት ውጪ ወይም ከባቡር ውጪ በሰው ህይወት ወይም ንብረት ላይ ጉዳት ያስከተለ ድርጊት ወይም አጋጣሚ እና መነሻው ከባቡር መሰረተ ልማት ወይም ከባቡር ውጪ ሆኖ በባቡር እና በባቡር መሰረተ ልማት ውስጥ በሰው ህይወት፣ አካል እና ንብረት ላይ ጉዳትን ያስከተለ ያልተፈለገ ወይም ያልታሰበና ድንገተኛ የሆነ አንድ ክስተት ወይም ተከታታይነት ያላቸው ክስተቶች ነው፡፡

33.“አሰልጣኝ” ማለት ለባቡር ሥራ ባለሙያዎች የንድፈ-ሀሳብ እና የተግባር ትምህርት የሚሰጥ ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ነው፤

34.“የባቡር ፍሰት ተቆጣጣሪ” ማለት በባቡር መሰረተ-ልማት ላይ ባቡሮች የሚያደርጉትን ትራፊክ የሚመራና የሚቆጣጠር የመሰረተ-ልማት አስተዳዳሪ ሠራተኛ የሆነ የተፈጥሮ ሰው ነው፤

35.“የሥልጠና ማዕከል” ማለት የባቡር ሥራ ባለሙያዎችን እንዲያሰለጥን የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል እውቅና የተሰጠው ማንኛውም ተቋም ሲሆን በባቡር መሠረተ-ልማት አስተዳዳሪ ወይም በአገልግሎት ሰጪ ተቋም ሥር ለተመሳሳይ ተግባር የተደራጀ የሥራ ክፍልን ይጨምራል፤

36.“የባቡር ማስተርነት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ” ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት መሰረታዊ መስፈርቶችን ላሟላና የብቃት ማረጋገጫ ምዘና ፈተና ላለፈ ሰው የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የሚሰጥ ባቡርን ለመንዳት የሚያስችል ፈቃድ ነው፤

37.“የባቡር ማስተር” ማለት በባቡር ውስጥ ሆኖ የባቡሩን እንቅስቃሴ በመምራትና በመቆጣጠር ባቡሩን በሀዲዱ ላይ እንዲንቀሳቀስ የሚያደርግ የተፈጥሮ ሰው ነው፤

38.“የባቡር ጣቢያ” ማለት ባቡር መንገደኛን ወይም ዕቃን እንዲጭንበትና እንዲያወርድበት ተብሎ በተለይ የተዘጋጀ ስፍራ ሲሆን፤ ተሳፋሪዎች ደህንነታቸው ተጠብቆ ወደ ባቡሩ እንዲገቡና እንዲወጡ ለማድረግ ተብሎ የተዘጋጀ የመሠረተ ልማት ክፍልን፣ የጭነት መጫኛና ማራገፊያ ተርሚናሎችን እና እንደ አግባብነቱ የባቡር እንቅስቃሴ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎችን ይጨምራል፤

39.“አገልግሎት ላይ የማዋል ፈቃድ” ማለት የባቡር መሠረተ-ልማት ክፍል፣ ሎኮሞቲቭ፣ ወይም ፉርጎ የተሰራበት ዲዛይን፤ አሰራሩና የቴክኒክ ብቃቱ ደህንነቱ የተረጋገጠ የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል መሆኑ ሲረጋገጥ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

40.“ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

41.“ፉርጎ” ማለት መንገደኞችን፣ ዕቃዎችን ወይም እንሰሳትን ለማሳፈር ወይም ለመጫን ተብሎ የተዘጋጀ ሆኖ የራሱ ኃይል የሌለው ባቡር ነው፤

42.“የፀና” ማለት የታደሰና ያልታገደ ወይም ያልተሰረዘ ማለት ነው፤

43.“የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል” ማለት የትራንስፖርት ሚኒስቴር ወይም በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ የሚወሰን የመንግስት አስፈፃሚ መስሪያ ቤት ነው፡፡

44. በዚህ አዋጅ በወንድ ፆታ የተገለፀው ሴትንም ያጠቃልላል፤

3. <u>**የተፈፃሚነት ወሰን**</u>

1. ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ የባቡር መሠረተ ልማት፣ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚከናወን የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት እና በኢትዮጵያ ውስጥ በሚከናወን የባቡር ሥራ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በሚከተሉት ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፤

   ሀ) በግል ይዞታነት የተያዘ ሆኖ የመሰረተ ልማት ባለቤቱ የራሱን ጭነት ብቻ ለማጓጓዝ በሚጠቀምበት የባቡር መሠረተ ልማት ላይ፤

   ለ) በመዝናኛ ፓርክ ወስጥ ለጨዋታ ወይም ለመዝናኛነት በተገነባ የባቡር መሠረተ ልማት ላይ፤

ሐ) የሀዲድ ስፋቱ ከ 1,435 (አንድ ሺ አራት መቶ ሰላሳ አምስት) ሚሊሜትር በታች በሆነ የባቡር ሥራ ወይም የባቡር መሠረተ ልማት ላይ፡፡

3. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) (ሀ)፣ (ለ)፣ እና (ሐ) የተጠቀሱትን ተግባር ለመቆጣጠር ደንብ ሊወጣ ይችላል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለባቡር እና የባቡር መሠረተ ልማቶች

4. **ሎኮሞቲቭ እና ፉርጎዎችን ስለመመዝገብ**

   1. ማናቸውም በኢትዮጵያ ውስጥ አገልግሎት ላይ የሚውሉ ሎኮሞቲቮች እና ፉርጎዎች የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል መመዝገብ እና የምዝገባ ምስክር ወረቀት ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡
   2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተመዘገቡ ሎኮሞቲቮች እና ፉርጎዎች የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የሚሰጥ መለያ ቁጥር ይኖራቸዋል፣ መለያ ቁጥሩም በጉልህ ሊታይ የሚችል ሆኖ በሎኮሞቲቮች እና ፉርጎዎች የፊትና የኋላ እንዲሁም የግራና የቀኝ አካላት ላይ መፃፍ አለበት፡፡
   3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተመዘገበ ሎኮሞቲቭ ወይም ፉርጎ አገልግሎት መስጠት ሲያቆም ምዝገባው ይሰረዛል፡፡
   4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተመዘገበ ሎኮሞቲቭ ወይም ፉርጎ ባለቤትነት ለሌላ ሰው የተላለፈ እንደሆነ ምዝገባው እንደገና መከናወን አለበት፡፡
   5. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተከናወነ የሎኮሞቲቭ ወይም የፉርጎ ምዝገባ መታደስ የማያስፈልገው ነው።

5. **ምዝገባን ስለሚያስከለክሉ ሁኔታዎች**

   የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል የኢትዮጵያ ደረጃዎችንና የደህንነት ደንቦችን የማያሟሉ ሎኮሞቲቮች እና ፉርጎዎች እንዳይመዘገቡ ወይም ወደሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ለመከልከል ይችላል።

6. **ያለፈቃድ ባቡርን እና የባቡር መሠረተ-ልማቶችን አገልግሎት ላይ ማዋል ስለመከልከሉ**
   1. ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠና የፀና አገልግሎት ላይ የማዋል ፈቃድ ያልተሰጣቸውን ሎኮሞቲቮች፣ ፉርጎዎች ወይም የባቡር መሠረተ-ልማት ክፍሎችን ተጠቅሞ የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት አይችልም፡፡
   2. ማንኛውም ሰው አገልግሎት ላይ ለማዋል ፈቃድ ያገኘባቸውን ሎኮሞቲቮችን፣ ፉርጎዎችን ወይም የባቡር መሠረተ-ልማቶችን ፈቃድ ከተሰጠበት የአገልግሎት ዓይነት ውጪ ሊጠቀምባቸው አይችልም፡፡
7. **ሎኮሞቲቮችን እና ፉርጎዎችን አገልግሎት ላይ ስለማዋል**
   1. ማንኛውም ሎኮሞቲቭ ወይም የመንገደኛ ማመላለሻ ፉርጎ ለምዝገባ ሲቀርብ፤ ቀጥሎም በየሁለት ዓመቱ የኢትዮጵያን ደረጃዎችንና የደህንነት ደንቦችን የሚያሟላ ስለመሆኑ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የቴክኒክ ፍተሻ እየተደረገበት አገልግሎት ላይ የማዋል ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡
   2. ማንኛውም የእቃ ማጓጓዣ ፉርጎ ለምዝገባ ሲቀርብ፤ ቀጥሎም በየሶስት ዓመቱ የኢትዮጵያን ደረጃዎችንና የደህንነት ደንቦችን የሚያሟላ ስለመሆኑ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የቴክኒክ ፍተሻ እየተደረገበት አገልግሎት ላይ የማዋል ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡
8. **የባቡር መሠረተ-ልማቶችን አገልግሎት ላይ ስለማዋል**
   1. የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል የባቡር መሠረተ-ልማት ክፍሎች የኢትዮጵያን ደረጃዎችንና የደህንነት ደንቦችን የሚያሟሉ መሆናቸውን ሲያረጋግጥ ለእያንዳንዱ የመሠረተ-ልማት ክፍል በተናጥል አገልግሎት ላይ የማዋል ፈቃድ ይሰጣል፡፡
   2. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚሰጥ የባቡር መሠረተ-ልማቶችን አገልግሎት ላይ የማዋል ፈቃድ ለሙሉ ኔትወርክ ወይም ለኔትወርኩ የተወሰነ ክፍል ሊሰጥ ይችላል፡፡
   3. የባቡር መሠረተ-ልማቶችን አገልግሎት ላይ የማዋል ፈቃድ በየሶስት ዓመቱ መታደስ ይኖርበታል፡፡

9. **ባቡር እና የባቡር መሠረተ-ልማት ግብዓትን**

ስለማምረትና ወደ ሀገር ውስጥ ስለማስገባት ማንኛውም ሰው በውጪ ሀገር የተመረተ ባቡር እና የባቡር መሠረተ-ልማት ግብዓት ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት፤ ወይም እነዚህኑ በኢትዮጵያ ውስጥ ለማምረት የሚችለው ሎኮሞቲቮቹ፣ ፉርጎዎቹ ወይም የባቡር መሠረተ-ልማት ማምረቻ ግብአቶቹ አሰራርና ቴክኒክ የኢትዮጵያን የጥራት እና የደህንነት ደረጃ የሚያሟሉ መሆናቸው የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

**ክፍል ሦስት**

**ስለባቡር ሥራ ባለሙያዎች**

10. **የባቡር ሥራ ባለሙያዎችን ስለመመዝገብ**

1. የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል በባቡር ሥራዎች ላይ የተሰማራን ማንኛውም ሰው የሚመዘገብበት ሀገር አቀፍ የባቡር ሥራ ባለሙያዎች መዝገብ አደራጅቶ ይይዛል፡፡
2. ማንኛውም ሰው የባቡር ሥራዎችን ለመስራት የሚችለው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የባቡር ሥራ ባለሙያዎች መዝገብ ላይ የተመዘገበ እንደሆነና እንደ አግባብነቱ በባለሥልጣኑ የተሰጠ የፀና የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ያለው እንደሆነ ብቻ ነው፡፡
3. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚደረግ ምዝገባ ለአምስት ዓመታት ፀንቶ ይቆያል፤ ሆኖም ተመዝጋቢው በአምስት ዓመቱ መጨረሻ ምዝገባውን በማሳደስ ለማራዘም ከፈለገ በ30 ቀናት ውስጥ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ማመልከት ይችላል፡፡

11. **የባቡር ሥራዎች ለመስራት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የሚያስፈልግ ስለመሆኑ**

1. ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የተሰጠው የጸና የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ከሌለው በስተቀር የባቡር ሥራዎችን ለመስራት አይችልም፡፡
2. ማንኛውም የባቡር ሥራን የሚሰራ ሰው የተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በደረጃ ወይም በዓይነት ተለይቶ የተሰጠው እንደሆነ እንደ አግባብነቱ ከተሰጠው ደረጃ ወይም ዓይነት ውጪ የሆኑ የባቡር ሥራዎችን ለመስራት አይችልም፡፡

3. ማንኛውም በሕግ ያልተከለከለ ሰው የባቡር ሥራዎችን ለመስራት የሚያስችለው የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እንዲሰጠው የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠውን አካል በጽሁፍ ለመጠየቅ ይችላል፡፡
4. ተጨማሪ መስፈርቶች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 51 (2) ድንጋጌ መሰረት በመመሪያ የሚወጡ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለባቡር ሥራዎች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመስጠት የሚቻለው አመልካቹ የሚከተሉትን መሠረታዊ መስፈርቶች አሟልቶ የሚገኝ ሲሆን ነው፤
   ሀ) የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለጠየቀበት የባቡር ሥራ በታወቀ ተቋም ተገቢውን ሥልጠና ወስዶ በብቃት ያጠናቀቀ ስለመሆኑ ማስረጃ ካቀረበ፤
   ለ) አግባብነት ያለውን የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ ምዘና ፈተናን ያለፈ እንደሆነ፤
   ሐ) ዕድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ ከሆነ፤
   መ) የባቡር ሥራውን ለመስራት የሚያስችል የተሟላ የአካልና የአዕምሮ ጤንነት ያለው ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የሀኪም ማስረጃ ካቀረበ፤
   ሰ) ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ ከሆነ የባቡር ሥራን እንዲሰራ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተሰጠ ማስረጃ ካቀረበ፤
   ረ) ኢትዮጵያዊ ዜግነት የሌለው ከሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ እንዲሰራ ከሚመለከተው አካል የሥራ ፈቃድ የተሰጠው እና የባቡር ሥራን በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሰራ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የተሰጠ ማስረጃ ካቀረበ፤
5. ማንኛውም የባቡር ሥራ ባለሙያነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለሦስት ዓመታት ጸንቶ የሚቆይ ይሆናል፤ ሦስተኛው ዓመት እንደተጠናቀቀ ቀጥሎ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ መታደስ አለበት፡፡
6. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) ድንጋጌ ቢኖርም የባቡር ማስተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው ዕድሜው ሀምሳ ዓመትና በላይ ከሆነ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱ በየዓመቱ መታደስ አለበት፡፡

12.<u>ባቡርን ስለመንዳት</u>

ማንኛውም ሰው ባቡርን ለመንዳት የሚችለው፤

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 መሠረት የተሰጠና የፀና የባቡር ማስተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ያለው የሆነ እንደሆነ፤ እና
2. አግባብነት ያለው ተጨማሪ የባቡር ማስተርነት ምስክር ወረቀት ያለው እንደሆነ፣

ብቻ ነው፡፡

13.<u>ስለ ተጨማሪ የባቡር ማስተርነት ምስክር ወረቀት</u>

1. ማንኛውም አገልግሎት ሰጪ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የባቡር ማስተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጠውን ሰው ማንኛውንም ዓይነት ባቡር እንዲነዳ ከማድረጉ በፊት የባቡሩን ዓይነት እና ባቡሩ የሚነዳበትን መስመር የተመለከተ ተጨማሪ ሥልጠና እንዲወስድና ብቃቱ እንዲረጋገጥ ማድረግ አለበት፡፡
2. አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰውን ሥልጠና የሚሰጥበትንና ምዘና የሚከናወንበትን ሥርዓት በደህንነት አስተዳደር ሥርዓቱ ውስጥ በማካተት የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ማቅረብና ማፀደቅ አለበት፡፡
3. አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ብቃቱን ላረጋገጠው የባቡር ማስተር ተጨማሪ የባቡር ማስተርነት የምስክር ወረቀት መስጠት አለበት፤ የምስክር ወረቀቱ የባቡር ማስተሩ ለመንዳት የሚችለውን የባቡር ዓይነትና ባቡሩን ሊነዳበት የሚችልበትን የባቡር መስመር የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

<u>**ክፍል አራት**</u>

<u>**ስለደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ፤ ምስክር ወረቀት፣ እና ስለታሪፍ**</u>

14.<u>ለባቡር መሠረተ-ልማት አስተዳዳሪ ስለሚሰጥ የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ</u>

1. ማንኛውም ሰው የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የተሰጠና የፀና የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ሳይኖረው የራሱን ወይም በይዞታው ያለን ማንኛውንም የባቡር መሠረተ ልማት አገልግሎት ላይ እንዲውል ለማድረግ አይችልም፡፡

2. ማንኛውም በሕግ ያልተከለከለ ሰው የራሱ ወይም በሕግ መሰረት በይዞታው ያደረገውን የባቡር መሠረተ ልማት አገልግሎት ላይ ለማዋል የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ እንዲሰጠው የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ማመልከት ይችላል፡፡
3. የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተዘጋጀውን ፎርም በመሙላት ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፤
   ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥ በባቡር መሠረተ-ልማት አስተዳዳሪነት ለመስራት እንዲችል በሚኒስቴሩ የተመዘገበበትን የምዝገባ የምስክር ወረቀት፤
   ለ) የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የጸደቀ የባቡር መሠረተ-ልማት የደህንነት አስተዳደር ሥርዓት ሰነድ፤
   ሐ) ለቀጠራቸው የባቡር ሥራ ባለሙያዎች የፀና የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድና የቅጥር ማስረጃዎች፤
   መ) የባቡር መሠረተ ልማቱን ለመጠገን ላደራጀው የሥራ ክፍል የተሰጠውን የዕውቅና ምስክር ወረቀት፤
   ሰ) ለባቡር መሠረተ ልማት ክፍሎች የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተሰጠ አገልግሎት ላይ የማዋል ፈቃድ፤
   ረ) የባቡር መሠረተ ልማቱ ለአገልግሎት የሚውልበትን ዝርዝር መረጃ የያዘ ሰነድ፤
   ሠ) በባቡር መሠረተ-ልማቱ አማካኝነት ሊደርስ ለሚችል ጉዳት የሶስተኛ ወገን ኢንሹራንስ የገባ መሆኑን የሚሳይ ማስረጃ፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ፊደል ተራ (መ) የተደነገገው ቢኖርም የባቡር መሠረተ-ልማቶቹ የሚጠገኑት የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የእውቅና የምስክር ወረቀት በተሰጠው ሌላ የጥገና ተቋም አማካኝነት የሆነ እንደሆነ የመሠረተ-ልማት አስተዳዳሪው ለጥገና የሥራ ክፍሉ የዕውቅና የምስክር ወረቀት ማቅረብ አያስፈልገውም፡፡
5. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚሰጠው የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ የመሠረተ-ልማት አስተዳዳሪው ለሚያስተዳደረው ኔትዎርክ በሙሉ ወይም ለኔትዎርኩ ከፊል ክፍል ብቻ ሊሆን ይችላል፡፡
6. የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ በየሁለት ዓመቱ መታደስ አለበት፡፡

## 15. ለአገልግሎት ሰጪ ተቋም ስለሚሰጥ የደህንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት

1. ማንኛውም ሰው የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የተሰጠ የፀና የደህንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳይኖረው የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት አይችልም፡፡
2. በሌላ ሕግ የተከለከለ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ሰው የራሱን ወይም የሌላን ሰው የባቡር መሠረተ-ልማት ተጠቅሞ የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪነት ሥራን ለመስራት እንዲችል የደህንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠውን አካል ለመጠየቅ ይችላል፡፡
3. የደህንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተዘጋጀውን ፎርም በመሙላት ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፤

   ሀ) በዚህ አዋጅ መሠረት በኢትዮጵያ ውስጥ በአገልግሎት ሰጭነት ለመስራት በሚኒስቴሩ የተመዘገበበት የምዝገባ ምስክር ወረቀት፤

   ለ) የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የጸደቀ የአገልግሎት ሰጪ ተቋም የደህንነት አስተዳደር ሥርዓት ሰነድ፤

   ሐ) በዚህ አዋጅ መሠረት ለፉርጎዎቹ፣ ለሎኮሞቲቮቹ፣ እና ለባቡር ጥገና የሥራ ክፍል የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የተሰጠ የፀና አገልግሎት ላይ የማዋል ፈቃድ፤

   መ) ባቡሮችን ለመጠገን ተግባር ላደራጀው የሥራ ክፍል የተሰጠውን የዕውቅና ምስክር ወረቀት፤

   ሠ) ለቀጠራቸው የባቡር ሥራ ባለሙያዎች በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠና የፀና የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድና የቅጥር ማስረጃ፤

   ረ) በባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ለሚደርስ ጉዳት የሶስተኛ ወገን ኢንሹራንስ የተገባበት ማስረጃ፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ፊደል ተራ (መ) የተደነገገው ቢኖርም ባቡሮቹ የሚጠገኑት የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የእውቅና ምስክር ወረቀት በተሰጠው የጥገና ተቋም አማካኝነት የሆነ እንደሆነ አገልግሎት ሰጭ ተቋሙ ለራሱ የጥገና ሥራ ክፍል የዕውቅና ምስክር ወረቀት ማቅረብ አያስፈልገውም፡፡
5. የደህንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በየዓመቱ መታደስ አለበት፡፡

16. <u>ስለታሪፍ</u>

1. ማንኛውም የመሠረተ ልማት አስተዳዳሪ ለሚሰጠው የባቡር መሠረተ ልማት የመጠቀም አገልግሎት የሚያስከፍለውን የክፍያ መጠንና አገልግሎቱ የሚሰጥባቸውን ሁኔታዎች ለሚኒስቴሩ አቅርቦ ሳያጸድቅ ተግባራዊ ማድረግ አይችልም፡፡
2. ማንኛውም አገልግሎት ሰጪ ተቋም ለሚሰጠው የመንገደኛና የዕቃ ማጓጓዝ አገልግሎት የሚያስከፍለውን የክፍያ መጠንና አገልግሎቱ የሚሰጥባቸውን ሁኔታዎች የያዘ በሚኒስቴሩ የፀደቀ ወቅታዊ ታሪፍ ከሌለው በስተቀር የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎትን በክፍያ ለመስጠት አይችልም፡፡
3. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) አፈፃፀም ማንኛውም የመሠረተ-ልማት አስተዳዳሪና አገልግሎት ሰጭ ተቋም ለሚሰጠው አገልግሎት ሊያስከፍል የሚፈልገውን የታሪፍ መጠን ለመወሰን የተጠቀመባቸውን ዝርዝር መረጃዎች በማያያዝ ሚኒስቴሩ በሚወስነው ፎርም መሠረት ለሚኒስቴሩ ማቅረብ አለበት፡፡
4. ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ታሪፍ እንዲፀድቅ ጥያቄ ሲቀርብለት፣ ታሪፉን ለመወሰን ጥቅም ላይ የዋሉትን መረጃዎች እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች በመመርመር ለማጽደቅ ወይም አሻሽሎ ለመወሰን ይችላል፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ስለሥልጠና፣ ጥገና፣ እና ምዘና</u>

17. <u>የእውቅና ምስክር ወረቀት አስፈላጊነት</u>

የሚከተሉትን ተግባራት ለማከናወን የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የተሰጠና የፀና የእውቅና ምስክር ወረቀት መኖር አለበት፣

1. የባቡር ሥራ ባለሙያዎችን ለማሠልጠን፣
2. ባቡርን እና የባቡር መሠረተ-ልማት ክፍሎችን ለመጠገን፣

3. የባቡር ሥራ ባለሙያዎችን የብቃት ደረጃ ለመመዘን እና የባቡርንና የባቡር መሠረተ-ልማት ክፍሎችን የቴክኒክና የደህንነት ብቃት በመፈተሽ የሙያ ምስክርነት ለመስጠት፡፡

18. <u>የባቡር ሥራ ባለሙያዎችን ስለማሰልጠን</u>

1. ማንኛውም ተቋም፣ የመሠረተ-ልማት አስተዳዳሪ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም የባቡር ሥራ ባለሙያዎችን ለማሰልጠን የሚችለው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 (1) መሰረት የተሰጠ የፀና የእውቅና ምስክር ወረቀት ያለው እንደሆነ ብቻ ነው፡፡
2. የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የሚሰጥ የእውቅና ምስክር ወረቀት የሥልጠና ማዕከሉ ሥልጠና እንዲሰጥ የተፈቀደለትን የባቡር ሥራ ዓይነቶችንና የሚሰጠውን የሥልጠና ደረጃ የሚገልፅ መሆን አለበት፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ቢኖሩም አግባብነት ባለው ሕግ መሰረት እውቅና የተሰጣቸው ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የባቡር ሥራ ባለሞያዎችን በመጀመሪያ ድግሪና ከዚያ በላይ በሆነ ደረጃ ለማስተማር የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የእውቅና ምስክር ወረቀት ማግኘት አያስፈልጋቸውም፡፡

19. <u>ስለሥልጠና ማስረጃ እና የብቃት ማረጋገጫ ምዘና</u>

1. የማንኛውም የባቡር ሥራ ባለሞያ የሚያቀርበው የሥልጠና ማስረጃ ተቀባይነት የሚኖረው ሥልጠናውን የወሰደው የእውቅና ምስክር ወረቀት በተሰጠው የሥልጠና ማዕከል ከሆነ ብቻ ነው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ተቀባይነት ያለው የስልጠና ማስረጃ ማቅረብ የቻለ ማንኛውም ሰው ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት በሚወጣ መመሪያ በውጪ ሀገር ከሚገኝ የስልጠና ማዕከል ያገኘው የስልጠና ማስረጃ ተቀባይነት ያገኘለት ማንኛውም ሰው በባቡር ሥራ ባለሙያነት የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ከመመዝገቡ በፊት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 4 ፊደል ተራ (ለ) መሰረት የብቃት ማረጋገጫ ምዘና መውሰድና የማለፊያ ነጥብ ማምጣት አለበት።

## 20. ባቡርን እና የባቡር መሠረተ-ልማት ክፍሎችን ስለመጠገን

1. ማንኛውም ተቋም፣ የመሠረተ-ልማት አስተዳዳሪ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም ባቡርን ወይም የባቡር መሠረተ-ልማት ክፍሎችን ለመጠገን የሚችለው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 (2) መሠረት የተሰጠና የፀና የእውቅና ምስክር ወረቀት ያለው እንደሆነ ብቻ ነው፡፡
2. ማንኛውም የመሠረተ-ልማት አስተዳዳሪ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የተሰጠ አግባብነት ያለው የእውቅና ምስክር ወረቀት ባለው የጥገና ተቋም ካልሆነ በስተቀር በሌላ በማናቸውም ተቋም ወይም ሰው የባቡር መሠረተ-ልማት ክፍልን ወይም ባቡርን እንዲጠገን ለማድረግ አይችልም፡፡
3. የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የሚሰጠው የእውቅና ምስክር ወረቀት የጥገና ተቋሙ ሊጠግናቸው የሚችላቸውን የባቡር ዓይነቶች፣ የባቡር መሠረተ-ልማት ክፍሎችን እና ሊያከናውነው የሚችለውን የጥገና ደረጃ የሚገልፅ መሆን አለበት፡፡

## 21. የባቡር ሥራ ባለሙያዎችን ስለመመዘን

1. የባቡር ሥራ ባለሙያዎች የብቃት ደረጃ ምዘና የሚከናወነው የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ነው፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል የብቃት ማረጋገጫ ምዘናው በሌላ የትምህርትና ስልጠና ተቋም፣ የስልጠና ማዕከል ወይም በሌላ ማናቸውም ተቋም እንዲያከናወን ለማድረግ ይችላል፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በሕግ አግባብ የተቋቋመ የትምህርት ወይም የስልጠና ማዕከል ወይም ሌላ ማናቸውም ተቋም አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የባቡር ሥራዎችን ለመመዘን እንዲችል እውቅና እንዲሰጠው የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠውን አካል ለመጠየቅ ይችላል፤ ሆኖም ማንኛውም የሥልጠና ማዕከል ራሱ ያሰለጠናቸውን የባቡር ሥራ ባለሙያዎች መመዘን የተከለከለ ሲሆን፣ ለሌላ ፈቃድ የተሰጠው አካል በማቅረብ እና ማስመዘን አለበት፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ምዘናውን በአግባቡ አላከናወነም ለማለት የሚያበቃ ምክንያት ሲኖረው የባቡር ሥራ ባለሙያውን በራሱ ባለሙያዎች ሊመዝነው ወይም በሌላ የምዘና ተቋም በድጋሚ እንዲመዘን ለማድረግ ይችላል፡፡

22.<u>ባቡርን እና የባቡር መሠረተ-ልማት ክፍሎችን የደህንነት ብቃት ስለመመዘን</u>

1. የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ባቡርን ወይም አንድ ወይም ከአንድ በላይ የባቡር መሠረተ-ልማት ክፍልን የቴክኒክና የደህንነት ብቃት ደረጃ ላይ ፍተሻ በማድረግ ሙያዊ ምስክርነት ለሚሰጡ የምዘና ተቋማት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት የእውቅና ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡
2. ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም፣ የመሠረተ-ልማት አስተዳዳሪ፣ አገልግሎት ሰጪ ተቋም፣ የባቡር ወይም የባቡር መሠረተ-ልማት ክፍሎች አምራች ተቋም፣ ወይም ሌላ ማናቸውም ተቋም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) የተገለፀውን ተግባር ለመፈፀም የእውቅና ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ማመልከት ይችላል፡፡

23. <u>የእውቅና ምስክር ወረቀትን ስለማደስ፣ ስለማገድና ስለመሰረዝ</u>

1. በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሠረት የሚሰጥ የእውቅና ምስክር ወረቀት በየሶስት ዓመቱ መታደስ አለበት፡፡
2. ማንኛውም የእውቅና ምስክር ወረቀት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰኑት ምክንያቶች ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል፡፡

24.<u>የመሠረተ-ልማት አስተዳዳሪን እና አገልግሎት ሰጪ ተቋምን ስለመመዘን</u>

1. የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድን ወይም የደህንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትን ከመስጠቱ ወይም የሰጠውን ከማደሱ በፊት በዚህ አዋጅና አዋጁን ተከትለው በወጡት ደንቦችና መመሪያዎች የተደነገጉ መስፈርቶችና ቅድመ-ሁኔታዎች የተሟሉ ስለመሆናቸው በመረጠው ሌላ ተቋም አስመዝነው የፍተሻውን ሪፖርት እንዲያቀርቡለት የመሰረተ ልማት አስተዳደሪን ወይም አገልግሎት ሰጪን ለማዘዝ ይችላል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል በማናቸውም ጊዜ በራሱ ባለሙያዎች ወይም በመረጠው ሌላ ማናቸውም ሰው አማካኝነት የባቡር መሰረተ ልማት አስተዳደሪ ወይም አገልግሎት ሰጪ ላይ የራሱን ምዘና ከማድረግ አይከለክለውም፡፡

## ክፍል ስድስት

## የደህንነት አስተዳደር ሥርዓት፣ የደህንነት ደረጃዎች እና ሥርዓቶች

### 25.የደህንነት አስተዳደር ሥርዓት አስፈላጊነት

1. ማንኛውም የባቡር መሠረተ-ልማት አስተዳዳሪ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም በየጊዜው ወቅታዊ የሚደረግ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የጸደቀ የደህንነት አስተዳደር ሥርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡
2. ማንኛውም የባቡር መሠረተ-ልማት አስተዳዳሪ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም እንደአግባብነቱ የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ወይም የደህንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ወይም እንዲታደስለት በሚጠይቅበት ጊዜ ሁሉ የደህንነት አስተዳደር ሥርዓቱን የሚያሳይ ሰነድ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

### 26.የደህንነት አስተዳደር ሥርዓት ይዘትና ፎርም

1. ተጨማሪ መስፈርቶች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 51 (2) ድንጋጌ መሰረት በመመሪያ የሚወጡ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በባቡር መሠረተ-ልማት አስተዳዳሪ ወይም በአገልግሎት ሰጪ ተቋም ተዘጋጅቶ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል የሚቀርብ የደህንነት አስተዳደር ሥርዓት የሚከተሉትን ዝርዝሮች መያዝ አለበት፤
   ሀ) የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎትን አደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉ ሁኔታዎችን የተመለከተ የደህንነት ሥጋት ትንተና፤
   ለ) የደህንነት ሥጋቶችን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚከናወኑ ተግባራት፣ የአሰራር ደንቦች፣ ቅደም ተከተሎች እና ተግባራቱን የማከናወን ሥልጣንና ኃላፊነት፤
   ሐ) የደህንነት ሥጋት ክስተት ሲከሰት ወይም የባቡር አደጋ ሲያጋጥም ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች፤

መ) የደህንነት ሥጋት ክስተት ሲፈጠር ወይም የባቡር አደጋ በደረሰ ጊዜ የሚሰጠውን ምላሽ፣ የሚከናወኑ ተግባራትንና አፈፃፀሙ የሚመራበት የአሰራር ሥርዓት፤

ሰ) የባቡር ሥራ ባለሙያዎች የደህንነት ሥጋትን ወይም የባቡር አደጋን አስቀድሞ ለመከላከል ሊፈጽሟቸው የሚገቡ የጥንቃቄ ተግባራትና ኃላፊነቶች፤ እንዲሁም የደህንነት ሥጋት ወይም የባቡር አደጋ በደረሰ ጊዜ ሊፈጽሟቸው የሚገቡ ተግባራትና የሚኖርባቸውን ኃላፊነቶች፤

ረ) የደህንነት ግቦችን፣ ስታንዳርዶችን እና የአፈጻጸም ዒላማዎችን፤

ሠ) ክትትልና ምዘና የሚከናወንበት አግባብና የአሰራር ሂደት፤

ሸ) የባቡር ሥራ ባለሙያዎች ብቃት የሚረጋገጥበት የአሰራር ሥርዓት፤

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የባቡር መሠረተ-ልማት አስተዳዳሪ ወይም አገልግሎት ሰጪ በሕግ ሥልጣን ከተሰጣቸው የሕግ አስከባሪና የፀጥታ አካላት የሚሰጡትን የደህንነት ሥጋትን እና የባቡር አደጋን ለመከላከል የሚያስችሉ ምክሮችን ተቀብሎ በደህንነት አስተዳደር ሥርዓቱ ውስጥ ማካተትና መተግበር አለበት፡፡

27. <u>የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎትን ደህንነት ስጋት ላይ የሚጥሉ ስራዎች</u>

የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ደህንነትን ስጋት ላይ ሊጥሉ የሚችሉ በባቡር መሰረተ-ልማቶች አቅራቢያ የሚከናወኑ ማናቸውም የልማትና የግንባታ ስራዎች አስቀድመው የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ፈቃድ ማግኘት አለባቸው፡፡

## ክፍል ሰባት

## ስለኦዲትና ኢንስፔክሽን

28. <u>ኦዲትና ኢንስፔክሽን የሚከናወንበት ዓላማ</u>

የባቡር ትራንስፖርት ኦዲትና ኢንስፔክሽን የሚደረግበት ዓላማ በሥራ ላይ የሚገኙ ሎኮሞቲቮች፣ ፉርጎዎች፣ የባቡር መሠረተ ልማቶች፣ የደህንነት አስተዳደር ሥርዓቶች፤ እንዲሁም በባቡር ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች በሕግ የተደነገገውን የደህንነት መስፈርቶች እና ሌሎች ግዴታዎች ያሟሉና የብቃት ደረጃቸው የተረጋገጠ መሆኑን ለማረጋገጥና ለመቆጣጠር፤ ጉድለት ሲገኝም ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ ይሆናል፡፡

29. <u>የኦዲትና ኢንስፔክሽን መኮንን</u>

1. የኦዲትና ኢንስፔክሽን መኮንን የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ዋና ዳይሬክተር የሚመደብ ይሆናል፡፡
2. የኦዲትና ኢንስፔክሽን መኮንን ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ሁሉ በዋና ዳይሬክተሩ የተፈረመ የመታወቂያ ወረቀት መያዝና አግባብነት ባለው ሰው ሲጠየቅ ማሳየት አለበት፡፡

30. <u>የኦዲትና ኢንስፔክሽን መኮንን ሥልጣንና ኃላፊነት</u>

1. ማንኛውም የኦዲትና ኢንስፔክሽን መኮንን አስቀድሞ ማሳወቅ ሳያስፈልገው በማንኛውም ጊዜ ወደ ባቡር መሠረተ ልማቶች፣ ባቡሮች፣ እና እውቅና የተሰጣቸው ተቋማት ውስጥ በመግባት ይህ አዋጅና አዋጁን መሠረት አድርገው የወጡት ደንቦችና መመሪያዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የኦዲትና ኢንስፔክሽን ሥራ ለማከናወን ይችላል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የኦዲትና ኢንስፔክሽን መኮንን አስቀድሞ ማሳወቅ ሳያስፈልገው ወደማንኛውም ባቡርና የባቡር መሰረተ-ልማት ክፍል በመግባት፤

   ሀ) የመሰረተ-ልማት አስተዳዳሪው የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት ያቀረበው መረጃ ትክክለኛ ስለመሆኑ እና ይህንኑ ፈቃድ ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች ተሟልተው የቀጠሉ መሆናቸውን ለመመርምር፤

   ለ) አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ የደህንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ያቀረበው መረጃ ትክክለኛ ስለመሆኑ እና ይህንኑ የምስክር ወረቀት ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች ተሟልተው የቀጠሉ መሆናቸውን ለመመርምር፤

   ሐ) ባቡሮችና የባቡር መሰረተ-ልማቶች ከባለሥልጣኑ የተሰጠና የፀና አገልግሎት ላይ የማዋል ፈቃድ ያላቸው መሆኑን እንዲሁም ይህንኑ ፈቃድ ሲያገኙ የነበራቸው ይዞትና የደህንነት ብቃት ያልተቀየረ መሆኑ ለማረጋገጥ የሚያስችል ምርመራ ለማድረግ፤

መ) ማንኛውም የባቡር ሥራ ባለሞያ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት ያቀረበው መረጃ ትክክለኛ ስለመሆኑ እና ይህንኑ ፈቃድ ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች ተሟልተው የቀጠሉ መሆናቸውን ለመመርምር፤

ይችላል፡፡

3. እውቅና በተሰጣቸው ተቋማት ላይ ለሚደረግ የኦዲትና ኢንስፔክሽን ተግባር የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው በተመሳሳይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፤ ሆኖም በእነዚህ ተቋማት ላይ የኦዲትና ኢንስፔክሽን ተግባራቱ ሊከናወኑ የሚችሉት በመደበኛ የሥራ ቀንና የሥራ ሰዓት ብቻ ይሆናል፡፡

31.<u>ጉድለት በተገኘ ጊዜ የኦዲትና ኢንስፔክሽን መኮንን ሥልጣንና</u>

ኃላፊነት የኦዲትና ኢንስፔክሽን መኮንን የዚህን አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ድንጋጌዎችን የሚቃረኑ ሁኔታዎች ወይም የባቡር ትራንስፖርት ደህንነትን አደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉ ሁኔታዎች ባጋጠሙት ጊዜ እንደ አግባብነቱ፤

1. ጉድለቱ አነስተኛ እና ከፍተኛ የደህንነት ስጋትን የማይፈጥር ሆኖ ባገኘው ጊዜ እንደ አግባብነቱ የመሰረተ ልማት አስተዳዳሪው፣ አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ፣ ወይም እውቅና የተሰጠው ተቋም ተገቢውን የእርምት እርምጃ ወዲያውኑ እንዲወስድ ለማዘዝ፤ ወይም
2. ጉድለቱ ከባድ የሆነ እንደሆነ እና ከፍተኛ የደህንነት ስጋትን የሚፈጥር የሆነ እንደሆነ ጉድለቱ እስኪስተካከል ድረስ ወይም ተጨማሪ የማጣራት ስራዎች እስኪሰሩ ድረስ እንደአግባብነቱ፤

ሀ) አንድ ወይም ከአንድ በላይ ሎኮሞቲቮች፣ ፉርጎዎች ወይም የባቡር ስራ ባለሙያዎች ሥራ እንዲያቆሙ ለማዘዝ፤

ለ) አንድ የባቡር መስመርን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል አገልግሎት መስጠት እንዲያቆም ለማዘዝ፤ ወይም

ሐ) የመሠረተ-ልማት አስተዳዳሪው፣ አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ፣ ወይም እውቅና የተሰጠው ተቋም ተግባሩን ሙሉ በሙሉ እንዲያቆም ለማዘዝ፤

ይችላል፡፡

32. <u>ከኦዲትና ኢንስፔክሽን መኮንን ጋር የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም የመሠረተ-ልማት አስተዳዳሪ፣ አገልግሎት ሰጪ፣ እውቅና የተሰጠው ተቋም ወይም የባቡር ሥራ ባለሙያ የኦዲትና ኢንስፔክሽን መኮንን በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር በሚያከናውንበት ወቅት፡-

1. እንደ አግባብነቱ ወደ ባቡር መሠረተ-ልማቶች፣ ባቡሮች፣ እና ተቋማቱ እንዲገባና ምርመራ እንዲያደርግ የመፍቀድ፤
2. ተቀጣሪ ሠራተኞችን የሚመለከቱ መረጃዎችን ጨምሮ ሌሎች አግባብነት ያላቸውን መረጃዎችና ሰነዶችን እንዲመለከት የመፍቀድ፤
3. ከሥልጣንና ኃላፊነቱ ጋር በተያያዘ ለሚያቀርበው ጥያቄ በሚያውቀው መጠን ተገቢውንና እውነተኛ ምላሽ የመስጠት፤
4. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 31 መሰረት በኦዲትና ኢንስፔክሽን መኮንኑ የሚሰጥ ሕጋዊ ትዕዛዝን የመፈፀም፤

ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል ስምንት

## ስለባቡር የደህንነት ስጋት ክስተትና አደጋ ምርመራ

### 33.ምርመራ የማድረግ ዓላማ

1. በዚህ አዋጅ መሠረት በመሠረተ-ልማት አስተዳዳሪ፣ በአገልግሎት ሰጪ ተቋም ወይም የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የሚከናወነው የባቡር የደህንነት ሥጋት ክስተት እና የባቡር አደጋ ምርመራ ዓላማዎች የሚከተሉት ይሆናሉ፤
   ሀ) የተከሰተን የደህንነት ሥጋት ክስተት ለማስወገድ የሚያስችል እርምጃ ለመውሰድ፤
   ለ) ተመሳሳይ የደህንነት ሥጋት ክስተት እና የባቡር አደጋ እንዳይከሰቱ ለማድረግ የሚያስችሉ ተግባራትን ለማከናወን፤ እና
   ሐ) ለደህንነት ሥጋት ክስተት ወይም ለባቡር አደጋ መከሰት መንስዔ የሆኑ ምክንያቶችን በማወቅ ተመሳሳይ የባቡር አደጋና የደህንነት ስጋት ክስተትን ለማስቀረት የሚያስችሉ እርምጃዎች ለመወሰድ፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለፁትን ዓላማዎች ለማሳካት የሚደረገው ምርመራ በሕግ በተሰጠ ሥልጣን መሰረት በሌላ አካል የሚደረግ ምርመራን ሳይጠብቅ እና ሳይከተል ይከናወናል፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ ቢኖርም የባቡር ደህንነት ስጋት ክስተት እና የባቡር አደጋን በተመለከተ የሚደረግ ምርመራ በሕግ ለሌላ አካል በተሰጠ ሥልጣን መሰረት የሚከናወን ምርመራን በማያደናቅፍ ሁኔታ መፈፀም ይኖርበታል፡፡

34.<u>የመሠረተ-ልማት አስተዳዳሪ እና አገልግሎት ሰጪ ተቋም ኃላፊነት</u>

1. ማንኛውም የመሠረተ ልማት አስተዳዳሪ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም በባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ላይ የደህንነት ስጋት ክስተት ወይም የባቡር አደጋ ሲያጋጥም ወዲያውኑ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል እና በአቅራቢያው ለሚገኝ የጸጥታ አካል ማሳወቅ አለበት፡፡
2. ማንኛውም የመሠረተ ልማት አስተዳዳሪ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም የደህንነት ሥጋትን ለማስወገድ ወይም ሕይወትን ለማዳን ካልሆነ በስተቀር የፀጥታ ኃይሎች በቦታው እስኪደርሱ ድረስ ማስረጃዎች ሊያጠፉ የሚችሉ ተግባራትን መፈፀም የለበትም፡፡
3. ማንኛውም የመሠረተ ልማት አስተዳዳሪ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም በሌላ ሕግ ሥልጣን የተሰጣቸው የፀጥታ አካላት የደህንነት ሥጋትንና የባቡር አደጋን በተመለከተ ምርመራ ሲያደርጉ በይዞታው የሚገኙትን መረጃዎች የመስጠትና ለሚቀርቡለት ጥያቄዎችም ትክክለኛ ምላሽ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የመሠረተ ልማት አስተዳዳሪ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም የደህንነት ሥጋት ወይም የባቡር አደጋ ሲያጋጥም ተገቢውን ምርመራ የማድረግ፣ እንደ አግባብነቱ ክስተቱ ወይም አደጋው መፈጠሩን ባወቀ በ24 ሰዓት ጊዜ ውስጥ ዝርዝር መረጃዎችን የያዘ ሪፖርት የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል በጽሁፍ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሰረት የሚቀርብ ሪፖርት እንደ አግባብነቱ የደህንነት ሥጋቱን ወይም የባቡር አደጋውን ዝርዝር ሁኔታ፣ የተወሰደውን የመፍትሔ እርምጃና የተገኘውን ውጤት የሚገልጽ መሆን ይኖርበታል፡፡
6. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ድንጋጌ ቢኖርም የደህንነት ስጋቱን ወይም የባቡር አደጋውን ዝርዝር መረጃና የተወሰደውን የመፍትሔ እርምጃ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ለማሳወቅ ተጨማሪ ጊዜ የሚያስፈልግ በሚሆንበት ጊዜ የክስተቱን ወይም የአደጋውን መድረስ ብቻ የሚገልጽ መረጃ በማቅረብ ዝርዝር መረጃዎችንና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎችን የያዘ ሪፖርት የማጣራቱና እርምጃ የመውሰዱ ተግባር እንደተጠናቀቀ ለማቅረብ ይቻላል፣ ሆኖም አደጋው ከተከሰተ ከሰባት ቀን በላይ መብለጥ

የለበትም፡፡

7. የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፣ (4) እና (6) መሠረት ሪፖርት ሲደርሰው ወዲያውኑን ለሚኒስቴሩ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

35.<u>የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ስለሚደረግ ምርመራ</u>

1. የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል በዚህ አዋጅ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ (1) ፣ (4) እና (6) መሰረት ሪፖርት ሲደርሰው ሪፖርቱን በመመርመር፤

ሀ) የቀረበለትን ሪፖርትና የተወሰደውን የመፍትሔ እርምጃ ተቀብሎ ያፀደቀው እንደሆነ ይህንኑ ለባቡር መሠረተ ልማት አስተዳዳሪው ወይም ለአገልግሎት ሰጪ ተቋሙ ማሳወቅ አለበት፤

ለ) በሪፖርቱና በተወሰደው የመፍትሔ እርምጃ ተገቢነት ላይ ጥርጣሬ ያደረበት እንደሆነ እንደ አግባብነቱ፣

(1) ተጨማሪ መረጃዎች እንዲቀርቡለት፣ ተገቢ የሆነው የመፍትሔ እርምጃ እንዲወሰድ፣ ወይም ሌላ አግባብነት ያለውን ትዕዛዝ ለመስጠት፤ ወይም

(2) በራሱ ሠራተኞች ወይም በሚወክለው ሌላ ባለሙያ የራሱን ምርመራ ለማድረግ፣

ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ማንኛውም ሞት ወይም አምስት እና ከአምስት በላይ በሆኑ ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት ወይም ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ የንብረት ጉዳት ያስከተለ አደጋ መከሰቱን ባወቀ ጊዜ ምርመራ በማድረግ የራሱን ሪፖርት ማዘጋጀት አለበት፡፡

3. ማንኛውም የመሠረተ ልማት አስተዳዳሪ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ) (2) እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል የራሱን ምርመራ ሲያደርግ በይዞታው የሚገኙትን መረጃዎች የመስጠትና ለሚቀርቡለት ጥያቄዎችም ተገቢውን ምላሽ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር እና ስለቅሬታና አቤቱታ አቀራረብ

### 36. የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር

ሚኒስቴሩ የዚህን አዋጅ አፈፃፀም በተመለከተ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. የባቡር ትራንስፖርትን የሚመለከቱ የፖሊሲ ሀሳቦችን፣ ስትራቴጂዎችን እና ሕጎችን ማመንጨት፤ ከሌሎች የትራንስፖርት ዓይነቶች ጋር የተቀናጀ ሀገር አቀፍ የባቡር መሰረተ-ልማት ማስተር ፕላንን ማዘጋጀት፤ በመንግስት ሲፀድቁም ተፈፃሚነታቸውን ማረጋገጥ፤
2. አግባብነት ባለው ህግ በሚወሰነው መሰረት በባቡር መሰረተ ልማት ግንባታና በባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ማሳደግ፤ በግሉ ዘርፍ ለሚከናወን የባቡር መሰረተ-ልማት ግንባታና ማስፋፊያ ፈቃድ መስጠት፤
3. የመሰረተ ልማት አስተዳዳሪዎችንና አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን መመዝገብ፤
4. ከጎረቤትና ሌሎች አገራት ጋር የባቡር ትራንስፖርትን በተመለከተ ከመንግስት በሚሰጥ አቅጣጫ መሰረት የመደራደር፤ የባቡር ትራንስፖርትን በተመለከተ ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች አፈፃፀም መከታተል፤
5. መንገደኞችና ዕቃዎች የሚጓጓዙበት ታሪፍ በውድድር ላይ የተመሰረተ እና ፍትሐዊ መሆኑን ማረጋገጥ እና ማጽደቅ፤
6. ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር ከባቡር ትራንስፖርት ጋር የተያያዙ ትምህርትና ሥልጠናዎች እንዲሁም ጥናትና ምርምሮችና ቴክኖሎጂዎች የሚስፋፉበትን የሚያድጉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤
7. ስለባቡር ደህንነት ለኅብረተሰቡ ሥልጠና መስጠትና ግንዛቤያቸውን ማሳደግ፤
8. በዚህ አዋጅ መሠረት የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠውን አካል የበላይ ኃላፊ በወሰናቸው ውሳኔዎች ላይ የቀረቡለትን አቤቱታዎችና ቅሬታዎች መመርመርና ውሳኔ መስጠት፤
9. የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነቶችን በአግባቡ እየተወጣ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

37.<u>ስለቅሬታ አቀራረብ</u>

1. በኦዲትና ኢንስፔክሽን መኮንን ወይም በሌላ የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠውን አካል የሥራ ኃላፊ በዚህ አዋጅና አዋጁን መሠረት አድርገው በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት በተሰጡ ውሳኔዎች ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው የተሰጠውን ውሣኔ በመቃወም የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል የበላይ ኃላፊ ቅሬታ ለማቅረብ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርብ ቅሬታ ቅሬታው የሚቀርብበት ውሳኔ በተሰጠ ወይም ቅሬታ አቅራቢው የውሳኔውን መሰጠት ባወቀ በ15 ቀናት ውስጥ የቅሬታውን ምክንያት በመግለጽ በጽሁፍ መቅረብ አለበት፡፡
3. የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠውን አካል የበላይ ኃላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ቅሬታ ሲቀርብለት ተጨማሪ ዝርዝር ማጣራቶችን ማድረግ የሚያስፈልግ ካልሆነ በስተቀር ቅሬታው በቀረበለት በ15 የስራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠትና ለቅሬታ አቅራቢው በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፤ ተጨማሪና ዝርዝር ማጣራቶች ማድረግ የሚያስፈልግ ከሆነ በ45 ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት እና ለቅሬታ አቅራቢው ማሳወቅ አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት በተሰጠ ውሳኔ ያልረካ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 38 መሰረት ለሚኒስትሩ አቤቱታን ማቅረብ ይችላል፡፡

38.<u>ለሚኒስትሩ ስለሚቀርብ አቤቱታ</u>

1. የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠውን አካል በላይ ኃላፊ በዚህ አዋጅ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ባከናወነው ተግባር ወይም በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው አቤቱታውን ለሚኒስትሩ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚቀርብ አቤቱታ ምክንያቶቹ ተገልፀውና በጽሁፍ ተዘጋጅተው የአቤቱታው ምክንያት የሆነው ተግባር በተፈፀመ ወይም ውሳኔ በተሰጠ ወይም የውሳኔው መሰጠት በታወቀ በ30 ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

3. ሚኒስትሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት አቤቱታ ሲቀርብለት ተጨማሪ ዝርዝር ማጣራቶችን ማድረግ የማያስፈልግ ከሆነ አቤቱታው በቀረበለት በ20 የሥራ ቀናት ውስጥ፤ ተጨማሪ ዝርዝር ማጣራቶችን ማድረግ የሚያስፈልግ የሆነ እንደሆነ ደግሞ በ60 ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት እና ለአቤት ባዩ ውሳኔውን ማሳወቅ አለበት፡፡
4. ሚኒስትሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የይግባኙን ምክንያቶች እና የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን የተሰጠውን አካል ውሳኔ መርምሮ ውሣኔውን በማጽደቅ፣ በመሻር ወይም በማሻሻል ለይግባኝ ባዩ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሰረት የተሰጠ ውሳኔ የመጨረሻው አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሆናል፡፡

## ክፍል አስር

## የወንጀል ጥፋቶችና ቅጣቶች

### 39. የፈቃድ አለመኖር

1. ማንኛውም ሰው
   ሀ) የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ያልተመዘገቡ እና አገልግሎት ላይ የማዋል የፀና ፈቃድ ያልተሰጣቸው ሎኮሞቲቮች፣ ፉርጎዎች ወይም የባቡር መሰረተ ልማቶችን ለባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ያዋለ ወይም እንዲውሉ ያደረገ እንደሆነ፤ ወይም
   ለ) በዚህ አዋጅ መሰረት የተሰጠው የፀና የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ ወይም የደህንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳይኖረው የመሠረተ ልማት አስተዳዳሪነት ወይም የአገልግሎት ሰጪነት ተግባርን ያከናወነ እንደሆነ

   ከአስር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከሀያ ሺ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለፀው ጥፋት የሰው ህይወት መጥፋትን ወይም አካል መጉደልን ወይም ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ የሆነ የንብረት ጉዳትን ያስከተለ እንደሆነ ቅጣቱ ከሀያ ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከሁለት መቶ ሺ ብር በማያንስ ከአምስት መቶ ሺ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይሆናል፡፡

40.<u>የሀሰት ማስረጃ ስለማቅረብ</u>

1. ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሰረት ምዝገባ ለማከናወን ወይም የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ፣ የደህንነት ማረጋገጫ ፈቃድ፣ አገልግሎት ላይ የማዋል ፈቃድ፣ የደህንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት፣ ወይም የእውቅና ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሀሰት ሰነዶችን ያቀረበ ወይም የተጠቀመ እንደሆነ ከሦስት ዓመት በማያንስ እና ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡
2. ማንኛውም የመሰረተ ልማት አስተዳዳሪ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም የደህንነት አስተዳደር ሥርዓቱን በተመለከተ ሀሰተኛ መረጃ ወይም ሪፖርት የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ያቀረበ እንደሆነ ከሦስት ዓመት በማያንስ እና ከአሥር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

41.<u>የባቡር ትራንስፖርት ደህንነትን አደጋ ላይ ስለመጣል</u>

1. ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ መሰረት በማድረግ በወጡት ደንቦችና መመሪያዎች ላይ የተደነገጉትን የጥንቃቄ ደንቦችን በመተላለፍ በተለይም በባቡር መሰረት ልማቶች አቅራቢያ የሚከናወኑ የግንባታ፣ የቁፋሮ ወይም ተመሳሳይ ሥራዎችን፣ ወይም የባቡር መሰረተ-ልማቶችን ከላይ ወይም ከስር አቋርጠው ወይም በትይዩ የሚከናወኑ መሰረተ-ልማቶችን በተመለከተ የወጡ ሕጎችን በመተላለፍ በባቡር ትራንስፖርት ላይ የደህንነት ስጋት እንዲፈጠር ያደረገ እንደሆነ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከአንድ መቶ ሺ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተፈፀመው የወንጀል ድርጊት የባቡር አደጋ እንዲደርስ በማድረግ ሞትን ወይም ከባድ የአካል ጉዳትን አስከትሎ እንደሆነ ወይም ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት የንብረት ጉዳትን አስከትሎ እንደሆነ የእስራት ቅጣቱ እስከ ሀያ ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት ይሆናል፡፡

42.<u>ከኦዲትና ኢንስፔክሽን መኮንን ጋር አለመተባበር</u>

ማንኛውም ሰው የኦዲትና ኢንስፔክሽን መኮንን በዚህ አዋጅና አዋጁን መሰረት አድርገው በወጡት ደንቦችና መመሪያዎች የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት ለማከናወን ወደ ሎኮሞቲቭ፣ ፉርጎ፣ የባቡር መሠረተ ልማት ወይም ዕውቅና ወደ ተሰጠው ተቋም እንዳይገባ የከለከለ እንደሆነ ወይም የኦዲትና ኢንስፔክሽን መኮንኑ ለሚያቀርበው ጥያቄ በሚያውቀው መጠን ተገቢውንና እውነተኛ ምላሽ ያልሰጠ ወይም አግባብነት ያለውን መረጃ ለማሳየት ፈቃደኛ ያልሆነ እንደሆነ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከሀያ ሺ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

43.<u>የባቡር የደህንነት ስጋት ክስተትንና የባቡር አደጋን አለማሳወቅ</u>

1. ማንኛውም የመሰረተ ልማት አስተዳዳሪ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሰረት የባቡር ደህንነት ስጋት ወይም የባቡር አደጋ መከሰቱን የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ያላሳወቀ እንደሆነ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከሀያ ሺ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡
2. የደህንነት ስጋት ክስተቱ ወይም የባቡር አደጋው ሪፖርት ያልተደረገው የባቡር መሰረተ ልማት አስተዳደሪውን ወይም የአገልግሎት ሰጭውን ወይም የሌላ ማናቸውንም ሰው ጥፋት ወይም ጉድለት እንዳይታወቅ ለመደበቅ በማሰብ የሆነ እንደሆነ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከአንድ መቶ ሺ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል፡፡

44.<u>ተገቢ ምርመራ አለማድረግ ወይም ሀሰተኛ የምርመራ ሪፖርት ማቅረብ</u>

ማንኛውም የመሰረተ ልማት አስተዳዳሪ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም የባቡር ደህንነት ስጋት ክስተት ሲፈጠር ወይም የባቡር አደጋ ሲከሰት በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሰረት ተገቢውን ምርመራ ያላደረገ እንደሆነ ወይም ሀሰተኛ የምርመራ ሪፖርት ያቀረበ እንደሆነ ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከአንድ መቶ ሺ ብር የማይበልጥ መቀጮ ይሆናል፡፡

45.<u>ሌሎች የወንጀል ጥፋቶች</u>

ማንኛውም ሰው የዚህን አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎችን ወይም ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የወጡ ደንብና መመሪያዎችን የተላለፈ ወይም አፈጻጸማቸውን ያሰናከለ እንደሆነ በቀላል እስራት ወይም በገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

46.**የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በወንጀል የሚቀጣበት ሁኔታ**

የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የዚህን አዋጅ ከአንቀጽ 39 እስከ አንቀጽ 45 ከተጠቀሱት ወንጀሎች አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑቱን የፈፀመ እንደሆነ ወይም ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የወጡ ደንብና መመሪያዎችን የተላለፈ እንደሆነ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 42 በተደነገገው መሰረት ይቀጣል፡፡

**ክፍል አስራ አንድ**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

47.**ወንጀልን መከላከልና ምርመራ**

በባቡር መሠረተ-ልማቶችና አገልግሎቶች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችንና የወንጀል ስጋቶችን ህብረተሰቡንና የሚመለከታቸውን የፌደራልና የክልል ተቋማትን በማስተባበር የመከላከልና ተፈጽመው ሲገኙም የመመርመር ሥልጣን የፌደራል የፀጥታ አካላት ነው፡፡

48.**የመተባበር ግዴታ**

ይህን አዋጅ ለማስፈፀም ማንኛውም ሰው የባቡር ትራንስፖርትን እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ከተሰጠውን አካል ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

49.**የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

1. ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በነበረ ሕግ ወይም አሰራር መሰረት ፈቃድ አግኝቶ ይህ አዋጅ ተፈፃሚ የሚሆንባቸውን ተግባራት በማከናወን ላይ የሚገኝ ማናቸውም ሰው ሚኒስቴሩ በሚወስነው ጊዜ ውስጥ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሰረት እንደገና መመዝገብና አግባብነት ያላቸውን ፈቃድና የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት በሚኒስቴሩ የሚወሰነው ጊዜ እስከሚያበቃ ድረስ ቀደም ሲል በነበረው ሕግ ወይም አሰራር መሰረት ተሰጥተው የነበሩ አግባብነት ያላቸው ፈቃዶች ፀንተው ይቆያሉ፡፡

50.**የተሻሩ ድንጋጌዎችና አሰራሮች**

1. የትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/1997 የአንቀጽ 2 (33)፣ የአንቀጽ 3 (2)፣ የአንቀጽ 7 (4) ድንጋጌዎች እና የአንቀጽ 23 (1) "በኢትዮጵያ ሀዲዶች ላይ ባቡርን ማሽከርከር" የሚለው ሀረግ በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡፡

2. የባቡር ትራንስፖርት ትራፊክ እና ደህንነት መቆጣጠሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 348/2008 አንቀጽ 24፣25፣26፣27፣ 28 እና 29 ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡፡
3. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

51.<u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን ያወጣል።
2. ሚኒስቴሩ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የወጡትን ደንቦች ለማስፈጸም መመሪያ ያወጣል፡፡

52.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ 19 ቀን 2009 ዓ.ም**

**ሙላቱ ተሾመ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## ደንብ ቁጥር 348/2008

## የባቡር ትራንስፖርት ትራፊክ እና ደህንነት መቆጣጠርያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣን እና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/1997 አንቀጽ 28 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርእስ**

   ይህ ደንብ "የባቡር ትራንስፖርት ትራፊክ እና ደህንነት መቆጣጠሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 348/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፤

   1. "የባቡር መሰረተ ልማት" ማለት የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎትን ለመስጠት የሚያስፈልግ ሐዲድ፣ የደህንነትና የመገናኛ መሣሪያዎች፣ መጠገኛ ጋራዦች እና የባቡር ጣቢያዎችን የሚያካትት መሠረተ ልማት ሲሆን በሀዲዱ ላይ የሚሄደውን ባቡር አይጨምርም፤
   2. "ኦፕሬተር" ማለት የባቡር መሠረተ ልማት ኦፕሬተር ወይም የባቡር ኦፕሬተር ነው፤
   3. "የባቡር መሠረተ ልማት ኦፕሬተር" ማለት የባቡር መሠረተ-ልማትን የሚያስተዳድር የባቡር መሠረተ ልማት ባለቤት ነው፤
   4. "የባቡር ኦፕሬተር" ማለት የራሱን ወይም የሌላን ሰው ባቡር በመጠቀም በራሱ ወይም በሌላ ሰው ባለቤትነት በተያዘ የባቡር መሠረተ ልማት ላይ የባቡር የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ነው፤
   5. "የባቡር ማስተር" ማለት በባቡር ውስጥ ሆኖ የባቡሩን እንቅስቃሴ በመምራትና በመቆጣጠር ባቡሩን በሀዲዱ ላይ እንዲንቀሳቀስ የሚያደርግ የተፈጥሮ ሰው ነው፤
   6. "የባቡር ማስተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ" ማለት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በባለሥልጣኑ የተሰጠ በኢትዮጵያ ውስጥ ባቡር ለመንዳት የሚያስችል ፍቃድ ነው፤

7. “ባቡር” ማለት ለባቡር ተብሎ በተገነባ ሀዲድ ላይ የሚንቀሳቀስ ባለሞተር ተሽከርካሪ ሲሆን በራሱ የተለየ ሞተር የሌለውን በባቡሩ ላይ ተቀጥሎ በመጎተት ወይም በመገፋት በሀዲድ ላይ የሚንቀሳቀስ ፉርጎን ይጨምራል፤
8. “ሀዲድ” በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/97 የተሰጠውን ትርጉም ይኖረዋል፤
9. “የባቡር ጣቢያ” ማለት ባቡር ተሳፋሪዎችን እንዲያሳፍርበት እና ጭነትን እንዲጭንበት ወይም ተሳፋሪዎችን እንዲያወርድበት እና ጭነትን እንዲያራግፍበት ተብሎ የተዘጋጀ ሥፍራ ነው፤
10. “መጠገኛ ጋራዥ” ማለት ባቡርን፣ ሐዲድን፣ የደህንነትና መገናኛ መሣሪያዎችን፣ እና የባቡር ጣቢያዎችን መጠገን ዋነኛ ሥራው ሆኖ የተቋቋመ የባቡር መሠረተ-ልማት አካል ሲሆን የባቡር መሰረተ-ልማቱና ባቡሮች በየዕለቱ አገልግሎት ከመስጠታትው በፊት ቴክኒካዊ ጉድለቶች የሌለባቸው መሆኑን የማረጋገጥ ሀላፊነት ያለበት ጋራዥ ነው፤
11. “ዲፖ” ማለት የባቡር እንቅስቃሴ መቆጣጠሪያ፣ የባቡር ስምሪት ማዘዣ እና የፉርጎ መቀጠያና መለያያ ቦታ ነው፤
12. “የባቡር ደህንነት አስተዳደር ሥርዓት” ማለት የባቡር የየዕለት የትራንስፖርት አገልግሎት በተቀናጀ ሁኔታ ደህንነቱ ተጠብቆ እንዲከናወን ተብሎ የተዘረጋ መደበኛ ስርአት ሲሆን የደህንነት ግቦችን፣ የአፈጻጸም መለኪያዎችን የደህንነት ሥጋት ትንተና ኃላፊነትና ሥልጣንን፣ የአሠራር ደንቦችንና ቅደም ተከተሎችን፣ የክትትል ምዘና ሥርዓትን እና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮችን የሚያካትት ሥርዓት ነው፤
13. “የደህንነትና የመገናኛ መሣሪያዎች” ማለት ባቡር ደህንነቱ ተጠብቆ አገልግሎት ለመስጠት እንዲችል ጥቅም ላይ የሚውሉ መሣሪያዎች ሲሆኑ ኤሌክትሮ መካኒካል መሣሪያዎችን፣ የትራፊክ ምልክቶችን እና ማመላከቻዎችን ይጨምራል፤
14. “የባቡር ፍሰት ተቆጣጣሪ” ማለት በዲፖ እና በባቡር ጣቢያዎች ውስጥ ሆኖ የባቡርን እንቅስቃሴ የሚመራ እና የሚቆጣጠር የኦፕሬተሩ ሠራተኛ ነው፤
15. “የባቡር አደጋ” ማለት መነሻው ከባቡር መሠረተ ልማት ወይም ከባቡር ውስጥ ሆኖ በባቡር መሠረተ ልማት ወይም በባቡር ውስጥ ወይም ከባቡር መሠረተ ልማት እና ከባቡር ውጭ በሰው ህይወት ወይም ንብረት ላይ ጉዳት ያስከተለ

አደጋ፤ ወይም መነሻው ከባቡር መሠረተ ልማት ወይም ከባቡር ውጪ ሆኖ በባቡር መሠረተ ልማት ውስጥ ወይም በባቡር ውስጥ በሰው ህይወት ወይም ንብረት ላይ ጉዳት ያስከተለ አደጋ ወይም የአደጋ አጋጣሚ ነው፤

16. “የደህንነት ሥጋት ክስተት” ማለት በሰውና በንብረት ላይ ጉዳትን ያላስከተለ ነገር ግን ጉዳት ሊያስከትል ይችል የነበረ ወይም የሚችል ማናቸውም ክስተት ነው፤
17. “የምዝገባ ምስክር ወረቀት” ማለት ባለሥልጣኑ የባቡር መሰረተ ልማት ኦፐሬተርን፣ የባቡር ኦፐሬተርን እና ባቡርን ከመዘገበ በኋላ የሚሰጠው የምዝገባ ማረጋገጫ ማስረጃ ነው፤
18. “የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት” ማለት ለባቡር መሠረተ-ልማቶች አፐሬተሮች እና ለባቡር ኦፐሬተሮች በባለሥልጣኑ የሚሰጥ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ነው፤
19. “ኦዲት እና ኢንስፔክሽን መኮንን” ማለት የባቡር መሠረተ ልማትን፣ አፐሬተርን እና ሙያተኞቹን የሚቆጣጠር እና ብቃታቸውን ኦዲት እና ኢንስፔክት የሚያደርግ በባለሥልጣኑ የሚመደብ ባለሙያ ነው፤
20. “ባለሥልጣን” እና “ዋና ዳይሬክተር” ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/1997 የተቋቋመው የትራንስፖርት ባለስልጣን እና የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ነው፤
21. “ሚኒስቴር” እና “ሚኒስትር” ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የትራንስፖርት ሚኒስቴርና ሚኒስትር ነው፤
22. “ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
23. በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ያጠቃልላል፡፡

3. **ዓላማ**

የዚህ ደንብ ዓላማ ደህንነቱ የተጠበቀ ቀልጣፋ የባቡር መሠረተ ልማት እና የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት እንዲኖር ማድረግ ነው፡፡

4. **የተፈጻሚነት ወሰን**

1. ይህ ደንብ በኢትዮጵያ ውስጥ በተዘረጋ የባቡር መሠረተ ልማት፣ ኦፐሬተር፣ ባቡር እና የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት እንቅስቃሴ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ይህ ደንብ ተፈጻሚ የማይሆንባቸው የባቡር መሠረተ ልማት፣ ኦፕሬተር እና የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎቶች ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናሉ።

## ክፍል ሁለት

## ስለ ኦፕሬተር እና ባቡር ማስተር

## ንዑስ ክፍል አንድ

## ስለባቡር መሰረተ ልማት ኦፕሬተር

### 5. ስለ ባቡር መሰረት ልማት ደህንነት እና የጥንቃቄ ስራዎች

ማንኛውም የባቡር መሠረተ ልማት ኦፕሬተር፣

1. ደህንነቱ የተጠበቀ የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የደህንነት አመራር ሥርዓት የመዘርጋት፣
2. ስራ ከመጀመሩ በፊት የባቡር ሀዲዱ፣ የግንኙነትና የደህንነት መሳሪያዎች እና የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ለደህንነት ስጋት የማይፈጥር እና ለአደጋ የማያጋልጥ መሆኑን የማረጋገጥ፣
3. ድንገተኛ አደጋ እና የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ሲያጋጥም ችግሩን ለመፍታት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የመዘርጋት፣
4. ለፍተሻ እና ለጥገና የሚገለገልባቸውን መሣሪያዎች ወቅታዊ ብቃታቸውን በየጊዜው የማረጋገጥ፣
5. የባቡር መሰረተ-ልማት አደጋ ሲያጋጥም እና የደህንነት ስጋት ክስተት ሲፈጠር ለባለስልጣኑ ወዲያውኑ የማሳወቅ፣
6. በባለስልጣኑ የቴክኒክ ምርመራ ተደርጎለት ብቃቱ የተረጋገጠ የባቡር መሰረተ-ልማትን ለአገልግሎት የማዋል፣
7. የባቡር መሰረተ ልማት መከለያ አጥሮችን እና የድልድይ ምሶሶዎችን ከተሽከርካሪ ግጭት ለማዳን የሚያስችል ምልክቶችን የመለጠፍ፣
8. ለባቡር እንቅስቃሴ አስፈላጊ የሆነ መረጃ ለባቡር ፍሰት ተቆጣጣሪ እና ለባቡር ማስተር በወቅቱ የማስተላለፍ፣
9. የደህንነት እና የግንኙነት መሳሪያዎች ተበላሽተው አገልግሎት የማይሰጡበት ወቅት መሳሪያዎቹን በመተካት አገልግሎቱ በተገቢው ሁኔታ እንዲሰጥ የሚያደርግ

የባቡር መሰረተ ልማት ኦፕሬተር ባለሙያ መመደብ እና መሳሪያዎቹ በአስቸኳይ አገልግሎት መስጠት መጀመራቸውን የማረጋገጥ፣

ግዴታ አለበት፡፡

6. **ስለ አገልግሎት አሰጣጥ**

ማንኛውም የባቡር መሠረተ ልማት ኦፕሬተር፣

1. የሚሰጠው አገልግሎት ለተገልጋዮች ምቹ እና ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡
2. የባቡር መሠረተ-ልማቱ ለአቅመ ደካማ ሰዎች፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአረጋዊያን እና ነፍሰ ጡር ሴቶች ተደራሽ እና ምቹ ማድረግ አለበት፡፡

7. **ስለ ባቡር መሰረተ ልማት ባለሙያ**

ማንኛውም የባቡር መሠረተ ልማት ኦፕሬተር የሚቀጥረው የባቡር መሠረተ ልማት ባለሙያ ተገቢው ሙያ ያለው መሆኑን አረጋግጦ የመቅጠር እና ቀጣይ ብቃቱም ወቅቱ የሚጠይቀውን የሙያ መስፈርት የተከተለ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

8. **ምልክት ስለመትከል**

ማንኛውም የባቡር መሰረተ-ልማት ኦፕሬተር፤

1. ተሽከርካሪዎች በባቡር ድልድይ ሥር በሚያልፉበት ቦታ የድልድዩን ከፍታ የሚገልጽ ምልክት በግልጽ በሚታይ ሥፍራ መትከል፤
2. የተሽከርካሪ መንገድ የባቡር ሀዲድን አቋርጦ በሚያልፍበት ቦታ ላይ ለባቡር የኃይል አቅርቦት የተዘረጋውን የኤሌክትሪክ መስመር ከፍታ የሚገልጽ ምልክት በግልጽ በሚታይ ሥፍራ መትከል፤
3. ደህንነቱ የተጠበቀ የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልጉ ምልክቶችና አመላካቾችን በባቡር መሠረት ልማት ላይ በተገቢው ቦታ መትከል፤
4. የተሽከርካሪ መንገዱን አቋርጠው ወደ ባቡር ጣቢያው የሚገቡ እና ከባቡር ጣቢያ የሚወጡ ተሳፋሪዎችን ደህንነት ለመጠበቅ ተሽከርካሪዎች ቆመው እግረኞች መንገዱን እንዲያቋርጡ የሚያስገድድ ምልክትና ማመላከቻዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር በባቡር ጣቢያዎች አካባቢ መተከላቸውን ማረጋገጥ፤

5. የባቡር መሠረተ ልማት ደህንነትን እና የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ደህንነት ለመጠበቅ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች የመንገድ ላይ ምልክቶችንና ማመላከቻዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር በተገቢው ቦታ መተከላቸውን ማረጋገጥ፣

አለበት፡፡

**ንዑስ ክፍል ሁለት**

**ስለ ባቡር ኦፕሬተር**

9. **ስለ ባቡር ደህንነት እና የጥንቃቄ ስራዎች**

1. ማንኛውም የባቡር አፕሬተር፡-

ሀ) ደህንነቱ የተጠበቀ የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የደህንነት አመራር ሥርአት መዘርጋት፤

ለ) ድንገተኛ አደጋ እና የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ሲያጋጥም ችግሩን ለመፍታት የሚያስችል የአሠራር ሥርአት መዘርጋት፤

ሐ) ወደ ሥራ የሚሰማሩ ባቡሮች ከመሰማራታቸው በፊት ለአገልግሎት ብቁ መሆናቸውንና የሚሰሩ የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎች በአግባቡ የተገጠመላቸው መሆኑን በየዕለቱ ማረጋገጥ፤

መ) ለአገልግሎት የሚያሰማራቸው ባቡሮች ከተዘረጋው መሠረተ ልማት ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

ሠ) በባቡሩ የውጭ አካል ላይ ሰዎች እንዳይንጠላጠሉ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ፤

ረ) የባቡር አደጋ ሲያጋጥም እና የደህንነት ሥጋት ክስተት ሲፈጠር ለባለሥልጣኑ፣ ለባቡር መሠረተ ልማት አፕሬተሩ እና አደጋው በደረሰበት ስፍራ ለሚገኘው ትራፊክ ፖሊስ ወይም ለሚቀርበው የፖሊስ ጽህፈት ቤት ወዲያውኑ ማሳወቅ፣

አለበት፡፡

2. ማንኛውም የባቡር አፕሬተር፡-

ሀ) ከባለሥልጣኑ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ሳይሰጠው የባቡር ኦፕሬተርነት አገልግሎት መስጠት፣

ለ) በባለሥልጣኑ ዘንድ ተመዝግቦ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ያልተሰጠውን ባቡር ለአገልግሎት ማዋል፣

ሐ) ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የቴክኒክ ምርመራ ተደርጎለት ብቃቱ ያልተረጋገጠ ባቡር ለአገልግሎት ማሰማራት፣

መ) የባቡር ማስተርነት የብቃት ማረጋገጫ የሌለው ማንኛውም ሰው ባቡሩን እንዲያንቀሳቅስ ማድረግ፣

ሠ) በተሳፋሪዎች ደህንነት እና ጤንነት ላይ ጉዳት የሚያደርስ ወይም ሊያደርስ የሚችል መርዝን፣ ጨረርን፣ መጥፎ ሽታን፣ ድምጽን፣ ንዝረትን፣ ሙቀትን ወይም ሌላ ጎጂ ክስተትን ሊያመነጭ የሚችል ነገር ወይም ፈንጅ እና ተቀጣጣይ ነገሮችን መጫን፣

የለበትም፡፡

10.<u>**ስለብቃት ማረጋገጫ**</u>

ማንኛውም የባቡር ኦፕሬተር ከባለሥልጣኑ የባቡር ኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ ሳይሰጠው የባቡር ኦፕሬተርነት አገልግሎት መስጠት የለበትም፡፡

11.<u>**ስለባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ**</u>

1. ማንኛውም የባቡር ኦፕሬተር፡-

ሀ) በሕግ ከተፈቀደለት የተሳፋሪ ቁጥር እና የጭነት መጠን በላይ ማጓጓዝ፣

ለ) ለመንገደኞች ከተፈቀደው ባቡር ወይም ፉርጎ ውጭ በጭነት ባቡር ወይም ፉርጎ ላይ መንገደኞችን ማጓጓዝ፣

ሐ) እድሜያቸው ከ10 ዓመት በታች የሆኑ ሕጻናትን እና የአዕምሮ ህሙማንን ያለአጋዥ ማሳፈር፣

መ) በዚህ ደንብ አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በከተማ ቀላል ባቡር ከ10 ኪ.ግ. በታች፣ በአገር አቋራጭ የመንገደኞች ማጓጓዣ ባቡር ከ40 ኪ.ግ. በታች የሚመዝን ዕቃ ከያዘ ተሳፋሪ ለዕቃ ማጓጓዣ ክፍያ መጠየቅ የለበትም፡፡

2. ማንኛውም የባቡር ኦፕሬተር፡-

ሀ) የትራንስፖርት አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ አካል ጉዳተኞችን፣ አረጋዊያንን፣ አቅመ ደካሞችን እና ነፍሰ ጡር ሴቶችን በመጫንና በማውረድ ረገድ ድጋፍ ማድረግ፣

ለ) ለሚያጓጉዘው ጭነት ተስማሚ የባቡር ፉርጎ ማቅረብ፤

ሐ) የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥበትን የጊዜ ሰሌዳ ማውጣትና በተገልጋዮች እንዲታወቅ ማድረግ፤

መ) የሚሰጠው የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት የመድህን ዋስትና ሽፋን እንዲኖረው ማድረግ፤

ሠ) ባለሥልጣኑ የሚያወጣውን ሌሎች የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዶችን ማሟላት፤

አለበት፡፡

12.<u>ልዩ ሁኔታ</u>

የባቡር መሠረተ ልማት ኦፕሬተርን እና የባቡር ኦፕሬተርን ተግባር የሚያከናውነው አንድ ሰው በሆነ ጊዜ በዚህ ክፍል ንዑስ ክፍል አንድ እና ሁለት የተደነገጉት ድንጋጌዎች በጣምራ ተፈጻሚ ይሆኑበታል፡፡

## <u>ንዑስ ክፍል ሶስት</u>

## <u>ስለ ባቡር ማስተር</u>

13.<u>ስለ ባቡር ማስተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ</u>

1. ማንኛውም የባቡር ማስተር ባቡር በሚነዳበት ጊዜ ሁሉ የጸና የባቡር ማስተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መያዝ እና ሥልጣን ባለው አካል እንዲያሳይ ሲጠየቅ ማሳየት አለበት፡፡
2. ማንኛውም ሰው የባቡር ማስተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሳይኖረው ባቡር መንዳት የተከለከለ ነው።

14.<u>በጥንቃቄ ስለመንዳት</u>

ማንኛውም የባቡር ማስተር፡-

1. የአካባቢ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት እና ከመቆጣጠሪያ ማዕከል በሚደርሰው መረጃ በመታገዝ በጥንቃቄ የመንዳት እና፤
2. በባቡር ትራንስፖርት ፍሰት ተቆጣጣሪ የሚሰጠውን ትእዛዝ የማክበር፣

ግዴታ አለበት።

15.<u>ስለ አልኮልና አደንዛዥ ዕጽ</u>

1. ማንኛውም የባቡር ማስተር ጫት ቅሞ ወይም እየቃመ፣ ንቃትን የሚገድብ መድሃኒት ወስዶ፣ አደንዛዥ ዕጽ ወስዶ፣ አልኮል ጠጥቶ፣ ሰክሮ፣ በሰውነቱ ጤናማ

ያለመሆን የተነሳ ወይም በድካም መንፈስ ውስጥ ሆኖ፣ ወይም ከአእምሮ ጉድለት የተነሳ አደጋ በማያስከትል አኳኋን ለመንዳት በማይችልበት ጊዜ ሁሉ ባቡር መንዳት የለበትም።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት "አልኮል ጠጥቶ ሰክሯል" የሚባለው በደሙ ውስጥ ያለው የአልኮል መጠን 0.8 ግራም በሊትር በልጦ ሲገኝ ወይም በትንፋሽ በሚያስወጣው አየር ውስጥ የአልኮል መጠኑ 0.4 ሚ.ግ. በሊትር በልጦ ሲገኝ ነው፡፡
3. ማንኛውም የባቡር ማስተር በስካር ተጠርጥሮ ተገቢው አካል የአልኮል መጠኑን እንዲመረመር ሲጠይቅ ፈቃደኛ ሆኖ መቅረብና መመርመር አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው መሠረት የባቡር ማስተሩ ለመመርመር ፈቃደኛ ካልሆነ በመጠጥ እንደሰከረ ይቆጠራል፡፡

16.<u>**የደህንነት እና የጥንቃቄ እርምጃዎች**</u>

ማንኛውም የባቡር ማስተር፡-

1. ባቡሩ ከመንቀሳቀሱ በፊት የባቡሩ በሮች መዘጋታቸውን ማረጋገጥ፤
2. ከባቡር ዲፖ፣ ጣቢያ እና ዋሻ ሲወጣ እና ሲገባ፣ እግረኛና መኪና የባቡር ሀዲዱን በሚያቋርጡባቸው ቦታዎች ሲቃረብ ሁሉ የጡሩንባ ድምጽ ማሰማት፤
3. ለእይታ አስቸጋሪ በሆነበት ጊዜ እና ቦታ ሁሉ የባቡር መብራት መጠቀም፤
4. ምንም አይነት አደጋ በሌለበት ሁኔታ የድንገተኛ አደጋ መሣሪያዎችን ከመጠቀም መቆጠብ፤ እና
5. ባቡር በሚነዳበት ጊዜ በጆሮ ማዳመጫ መሣሪያ ከመቆጣጠሪያ ማዕከል ከሚላኩ መልዕክቶች ውጭ የሆኑ ሌሎች ድምጾችን እና ተንቀሳቃሽ ስልክ ከመጠቀም መቆጠብ፤ አለበት፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>ስለአሽከርካሪ፣ ተሳፋሪ እና እግረኛ</u>

### <u>ንዑስ ክፍል አንድ</u>

### <u>ስለ አሽከርካሪ</u>

17.<u>**ተሽከርካሪ ስለማቆም**</u>

ማንኛውም አሽከርካሪ፡-

1. ከባቡር ጣቢያ ፊት እና ኋላ በ20 ሜትር ርቀት ውስጥ፤

2. እግረኞች እና ተሽከርካሪዎች የባቡር ሀዲዱን ከሚያቋርጡበት መንገድ ላይ በማንኛውም አቅጣጫ በ20 ሜትር ክልል ውስጥ፤
ተሽከርካሪ ማቆም የለበትም፡፡

18.<u>የደህንነት እና የጥንቃቄ እርምጃዎች</u>

1. ማንኛውም አሽከርካሪ፡-
   ሀ) የተሽከርካሪ መንገድ በባቡር ድልድይ ሥር በሚያልፍበተ ቦታ ሲደርስ የተተከለውን የከፍታ ምልክት አክብሮ በጥንቃቄ ማለፍ፣
   ለ) የተሽከርካሪ መንገድ ሀዲድን አቋርጦ በሚያልፍበት ቦታ ላይ ሲደርስ ለባቡሩ የኃይል አቅርቦት የተዘረጋውን የኤሌክትሪክ መሥመር ከፍታ የሚገልጸውን ምልክት አይቶ ተገቢውን የጥንቃቄ እርምጃ መውሰድ፣
   ሐ) ሀዲድን በሚያቋርጥበት ጊዜ አግባብነት ያላቸው የባቡር ኦፕሬተር ሰራተኞች የሚሰጡትን ትዕዛዝ እና የትራፊክ ምልክቶችና ማመላከቻዎችን ማክበር፣
   መ) ከባቡር ጣቢያ የሚወጡ እና ወደ ባቡር ጣቢያ የሚገቡ እግረኞች እና ተሽከርካሪዎች ወደ መንገድ ሲገቡ ወይም መንገዱን ሲያቋርጡ ቅድሚያ ሰጥቶ በጥንቃቄ ማሳለፍ፣
   ሠ) የሀዲድን አዋሳኝ መንገዶች ሲጠቀም በመንገድ ምልክቶችና ማመላከቻዎች የሚሰጡ ትዕዛዞችን ማክበር፣ እንዲሁም በሌሎች የትራንስፖርት ሕጎች የተደነገጉትን የጥንቃቄ እርምጃዎች ሁሉ መውሰድ፣
   ረ) የባቡር ሀዲድን በሚያቋርጥበት ጊዜ ተሽከርካሪው ብልሽት ቢገጥመው ወዲያውኑ ማንሳት፣
   ሰ) የባቡር መሠረተ ልማትን እንዳይጎዳ ተጠንቅቆ ማሽከርከር፣

   አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ረ) መሠረት አሽከርካሪው መኪናውን ማንሳት ካልቻለ ኦፕሬተሩ የተበላሸውን ተሽከርካሪ የማስነሳትና ወጪውን ከባለንብረቱ የመጠየቅ መብት አለው፡፡

19.<u>ስለማሳወቅ</u>

ማንኛውም ሰው በባቡር መሠረተ ልማት ላይ ጉዳት ካደረሰ ያደረሰውን ጉዳት ለባቡር መሠረተ ልማት ኦፕሬተሩ፣ ለትራፊክ ተቆጣጣሪ ፖሊስ ወይም ጉዳቱ በተከሰተበት አካባቢ ለሚገኘው የፖሊስ ጽሕፈት ቤት ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት።

20.<u>የባቡር ሀዲድን ስለማቋረጥ</u>

አሽከርካሪዎች የባቡር ሀዲድን የሚያቋርጡበትን ሁኔታ በተመለከተ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 208/2003 አንቀጽ 18 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## <u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለ ተሳፋሪ፣ እግረኛ እና ሌሎች ሰዎች</u>

21.<u>የባቡር ኦፐሬተር ሠራተኞችን ትእዛዝ ስለማክበር</u>

ማንኛውም ተሳፋሪ፣ እግረኛ ወይም ሌላ ሰው፡-

1. አግባብ ባላቸው የባቡር ኦፕሬተር ሠራተኞች እና ትራፊክ ፖሊስ የሚሰጡ ትዕዛዞችን የማክበር፤
2. ወደ ባቡር ጣቢያው ሲገባም ሆነ ከባቡር ጣቢያው ሲወጣ ለእግረኞች ተብሎ በተፈቀደው ቦታ ብቻ የመጠቀም፤
3. በባቡር ኦፕሬተሩ የተከለከሉ ተግባራትን ከመፈጸም የመቆጠብ፤

ግዴታ አለበት።

22.<u>ለተሳፋሪዎች ስለተከለከሉ ነገሮች</u>

ማንኛውም ተሳፋሪ የሚከተሉትን መፈጸም የተከለከለ ነው፤

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 9 ንኡስ አንቀጽ (11) የተመለከቱትን፣ እንስሳትን እና ሌሎች በባለሥልጣኑ የተከለከሉ ነገሮችን ይዞ ወደ ባቡር ጣቢያ መግባትም ሆነ ባቡር ላይ መሳፈር፤
2. ምንም ዓይነት አደጋ በሌለበት የአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ መሣሪያዎችን መነካካት፤
3. የባቡርንም ሆነ የባቡር መሠረተ ልማትን ንጽህና የሚያጓድል እና የሚጎዳ ማንኛውም ተግባር መፈጸም፤
4. የተሳፋሪዎችን ሰላማዊ ጉዞ እና የባቡርን ጤናማ እንቅስቃሴ የሚያስተጓጉል ማናቸውም ድርጊት መፈጸም፤
5. ባቡር እንቅስቃሴ ከጀመረ በኋላ ለመሳፈር መሞከር፤
6. ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአቅመ ደካሞች፣ ለአረጋዊያን እና ለነፍስ ጡር ሴቶች ተብለው የተለዩ መገልገያዎችን ያለባቡር ሠራተኞች ፈቃድ መጠቀም፤
7. ሰክሮ፣ በአደንዛዥ ዕጽ ተመርዞ፣ ጫት እየቃመ ወይም ማንኛውንም ዓይነት ሲጋራ እያጨሰ በባቡር ላይ መሳፈር፤

8. በባቡር ጣቢያዎችም ሆነ በባቡሩ ላይ ተሳፍሮ እያለ ለሕግ ወይም ለመልካም ሥነ-ምግባር ተቃራኒ የሆነ ማናቸውንም ድርጊት መፈጸም፤
9. በባቡር ጣቢያም ሆነ በባቡር ላይ ተሳፍሮ እያለ የባቡሩን ጣቢያም ሆነ ባቡሩን ሊያቆሽሹ የሚችሉ ማናቸውንም ዓይነት ቆሻሻዎች መጣል፤
10. በባቡር ላይ ተሳፍሮ እያለ መቀመጫዎችን መረጋገጥ እና በባቡሩ አካል ላይ ጽሁፍ መጻፍ፡፡

## 23.<u>ለማንኛውም ሰው ስለተከለከሉ ነገሮች</u>

ለማንኛውም ሰው የሚከተሉትን መፈፀም የተከለከለ ነው፤

1. የባቡር እንቅስቃሴን የሚያደናቅፍ በባቡር እና በባቡር መሰረተ ልማት ላይ ጉዳት ማድረስ ወይም የባቡሩን እና የተሳፋሪዎችን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ማንኛውንም ተግባር መፈጸም፤
2. እግረኛ እንዲያቋርጥበት በተፈቀደ የባቡር ሀዲድ ላይ ሲያቋርጥ የባቡር ኦፕሬተር ሰራተኞችን ትዕዛዝ፣ የትራፊክ ምልክቶችንና ማመላከቻዎችን አለማክበር፤
3. ለእግረኞች ማቋረጫ ተብሎ በተከለለው ቦታና በተፈቀደው ጊዜ ብቻ ካልሆነ በስተቀር የባቡር ሀዲድን ለማቋረጥ መሞከር ወይም ማቋረጥ፤
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) በተደነገገው መሰረት ካልሆነ በስተቀር አጥር ቢኖረውም ባይኖረውም ለባቡር መሄጃ ብቻ ተብሎ ወደተከለለው ማናቸውም ስፍራ መግባትም ሆነ በባቡር ሀዲድ ውስጥ መጓዝ ወይም በባቡር የውጭ አካል ላይ መንጠልጠል፤
5. በባቡር ሀዲድ ላይ መቆም ወይም መጓዝ፣ ወደ ባቡር ሀዲድ ክልል፣ ዋሻዎች፣ ድልድዮች፣ የከፍታ መንገድ ክፍል፣ የመከለያ አጥር፣ ግድግዳ፣ እና የትኬት መቁረጫ መከለያ ስፍራዎች ዘሎ ወይም ሾልኮ መግባት፤
6. በተከለሉ የባቡር ሀዲዶች ውስጥ ወይም የባቡር መሰረተ ልማት ውስጥ እንስሳትን መንዳት ወይም መልቀቅ፤ በዋሻ መግቢያና መውጫ ላይ እንስሳትን ማቆም፣ ማከማቸት እና ማሰር፤
7. በባቡር ጣቢያዎች ውስጥ በሚገኙ መቀመጫዎች ላይ መተኛትም ሆነ ጽሁፍ መጻፍ፡፡

## [97]ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 30.የመተባበር ግዴታ

ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

### 31.መመሪያ የማውጣት ስልጣን

ይህን ደንብ ለማስፈጸም ሚኒስቴሩ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

### 32.ምልክቶችን ስለማክበር

ማንኛውም የባቡር ማስተር፣ አሽከርካሪ እና እግረኛ በዚህ ደንብ ሰንጠረዥ "ሀ" የተመለከቱትን የትራፊክ ምልክቶች እና ማመላከቻዎችን ማክበር አለበት።

### 33.ቅጣት

1. በሌሎች ሕጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ተላልፎ የተገኘ ሰው ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ "ለ" መሠረት ይቀጣል።
2. ትራንስፖርት ባለሥልጣን ወይም ትራፊክ ፖሊስ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ተላልፎ በተገኘ ሰው ላይ ተፈጻሚ የሚሆነውን ቅጣት እንዲፈጽም ለጥፋተኛው ወዲያውኑ በጽሁፍ ያሳውቃሉ፡፡

### 34.ቅሬታ አቀራረብ

1. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተደነገገው እንደጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሰው በዚህ ደንብ አንቀፅ 33 በተደነገገው መሰረት የተጣለበትን ቅጣት እንዲፈጽም በጽሁፍ ሲገለጽለት ወዲያውኑ ቅጣቱን ከፍሎ ቅሬታ ካለው ይህንኑ በሶስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ለማቅረብ ይችላል።
2. ባለሥልጣኑም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለቀረበው ቅሬታ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፤ ባለስልጣኑ የሚሰጠው ውሳኔም የመጨረሻ ይሆናል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ቅጣቱን ወዲያውኑ ለመክፈል የማይችል እግረኛ፣ ተሳፋሪ ወይም ሌላ ሰው መታወቂያው ተይዞ በአንድ ወር ውስጥ ቅጣቱን ለመክፈል ቃል እንዲገባ ይደረጋል፡፡

[97] የደንቡ ክፍል አራት እና አምስት አንቀጽ 24፣ 25፣ 26፣ 27፣ 28 እና 29 ድንጋጌዎች በ23/73 (2009) አ.1048 አንቀፅ 51(2) ተሽረዋል፡፡

4. ማንኛውም ኦፕሬተር ወይም የባቡር ማስተር ይህን ደንብ መሠረት በማድረግ በተወሰኑ ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ ሲኖረው ውሳኔው በተሰጠ በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ቅሬታውን ለማቅረብ ይችላል።
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሰረት ዋና ዳይሬክተሩ በሰጠው ውሳኔ ያልረካ ወገን ውሳኔው በተሰጠ በ20 የሥራ ቀናት ውስጥ ለሚኒስቴሩ ቅሬታውን ለማቅረብ ይችላል።
6. <u>**ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**</u>




   ይህ ደንብ ከዛሬ መስከረም 7 ቀን 2008 ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡




**አዲስ አበባ ጥቅምት 19 ቀን 2008 ዓ.ም**



**ኃይለማርያም ደሳለኝ**



**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስቴር**







## ሠንጠረዥ "ሀ"SCHEDULE "A"

| የባቡር የመንገድ ምልክቶች | | Railway Signs |
|---|---|---|
| 1. የማስጠንቀቂያ ምልክት | | 1. Warning Signs |
| መዝጊያ ያለው የባቡር ሀዲድ ማቋረጫ |  | Railway crossing with gate |
| መዝጊያ የሌለው የባቡር ሀዲድ ማቋረጫ |  | Railway crossing without gate |
| ተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ወይም ተደጋጋሚ የባቡር ሀዲድ ማቋረጫ ማስጠንቀቂያ | | Repeated warning or repeated railway crossing |
| ሀ. ወደፊት 240 ሜ. ርቆ የባቡር ሀዲድ ማቋረጫ መኖሩን የሚያመለክት |  | a. Railway crossing 240 m. ahead |
| ለ. ወደፊት 160 ሜ. ርቆ የባቡር ሀዲድ ማቋረጫ መኖሩን የሚያመለክት |  | b. Railway crossing 160m. ahead |





| | | |
|---|---|---|
| ሐ. ወደፊት 80 ሜ. ርቆ የባቡር ሀዲድ ማቋረጫ መኖሩን የሚያመለክት |  | c. Railway crossing 80m. ahead |
| የባቡር ሀዲድ ማቋረጫ |  | Railway Crossing |
| የባቡር ሀዲዱ ማቋረጫ ከላይ በኩል የኤሌክትሪክ ገመድ የተዘረጋበት ስለሆነ ከፍታቸው ትልቅ የሆነ ተሽከርካሪዎች በጥንቃቄ እንዲያልፉ |  | This railroad crossing has electrical wires overhead; high profiel vehicles should exercise caution |
| ከባለ አራት አቅጣጫ መንገድ በስተግራ በኩል የባቡር ሀዲድ ማቋረጫ አለ |  | There is railway crossing on the left side of the crossroad |

| | | |
|---|---|---|
| ከባለ አራት አቅጣጫ መንገድ በስተቀኝ በኩል የባቡር ሀዲድ ማቋረጫ አለ |  | There is railway crossing on the right side of the crossroad |
| የመብራት ምልክት ያለው የባቡር ሀዲድ ማቋረጫ<br><br>ቢጫ መብራት ሲበራ፡- ባቡር እየመጣ ስለሆነ የባቡር ማቋረጫ ክልል ውስጥ የገባ ተሽከርካሪ ቶሎ አቋርጠህ መውጣት ያልገባህ ከሆነ ቁመህ ባቡሩ እስኪያልፍ ጠብቅ<br><br>ቀይ መብራት ሲበራ፡- ባቡር እያለፈ ስለሆነ ቁም |  | Railway crossing with signal lights: When yellow light is on: a train is approaching therefore, vehicle began crossing rail shall speedly cross and those approaching rail shall stop ;<br><br>When red light is on: as the train is passing remain stopped until the train passed and signal turns off |

| | | |
|---|---|---|
| ሁለት የቀይ መብራት ምልክት ያለው የባቡር ሀዲድ ማቋረጫ<br>ቀይ መብራት ሲበራ፣ ባቡር እያለፈ ስለሆነ ቁም |  | Railway way crossing with flashing signal consisting of twin red light assembls:<br>When the red light is on stop and give way for the train |
| | | |
| 2. መረጃ ሰጭ ምልክቶች | | **2. Informative Signs** |
| ወደፊት የባቡር የሀዲድ ማቋረጫ አለ |  | There is railway crossing a head |
| ወደፊት መብራት ያለው የባቡር ሀዲድ ማቋረጫ ምልክት አለ |  | There is railway crossing flashing signals a head |
| የባቡር ሀዲዱ እና የተሽከርካሪ መንገዱ ከፍታ እኩል የሆነ ማቋረጫ ወደፊት አለ |  | There is low ground clearance railway crossing ahead |
| ወደፊት ከባለ አራት አቅጣጫ መንገድ ትይዩ በግራ በኩል የባቡር ሀዲድ ማቋረጫ አለ |  | There is parallel rail road crossing (Cross road) ahead |

| | | |
|---|---|---|
| ወደፊት በቀኝ በኩል ከሚታጠፈው መንገድ የባቡር ሀዲድ ማቋረጫ መንገድ አለ |  | There is parallel rail road crossing (Side road) ahead |
| 'T' ቅርጽ ካለው መንገድ ትይዩ የባቡር ሀዲድ ማቋረጫ መንገድ |  | There is parallel rail road crossing (T intersection) ahead |
| ሰያፍ የባቡር መንገድ ማቋረጫ |  | Skewed railway crossing |
| የባቡሩ ፍጥነት ከ80 ማይል በሰዓት በላይ ሊሆን ይችላል |  | Train's speed may exceed 80 M.P.H |
| የሚቀጥለውን የባቡር መንገድ ማቋረጫ ተጠቀም |  | Use next crossing |
| የባቡር ጣቢያ |  | Train Station |
| ከፊት ለፊት የባቡር ዋሻ አለ |  | Tunnel |

| 3. የሚቆጣጠሩ / የሚያስገድዱ ምልክቶች | | 3. Regulatory Signs |
|---|---|---|
| የጡርንባ ድምጽ ማሰማት የተከለከለ |  | Prohibition of Use audible warning appliance |
| በባቡር ሀዲድ ላይ ተሽከርካሪ ማሽከርከር የተከለከለ ነው |  | Driving vehicles on railway is prohibited |
| ጠቅላላ ከፍታቸው በሜትር በምልክቱ ላይ ከተመለከተው በላይ ለሆኑ ተሽከርካሪዎች የተከለከለ |  | Closed to vehicle of a total height exceeding that indicated in meter or the sign |
| በዚህ ማለፍ ክልክል ነው |  | Do not walk |
| ለእግረኞች የተከለከለ |  | Pedsterians prohibited |

| | | |
|---|---|---|
| ዘንጉ አግድም በተዘጋበት ጊዜ የባቡር ሀዲዱን ማቋረጥ ክልክል ነው |  | No crossing when the barricade is in clossed position |
| የዚህ ምልክት እስከሚያበቃበት ድረስ ባለው ቦታ ማቆም ክልክል ነው |  | No Parking |
| ቁም እና አሳልፍ |   | Stop and give way |
| ቅድሚያ ስጥ |  | You must give way to traffic on the intersecting |
| መግባት ክልክል ነው |  | Do not Enter |

**ሠንጠረዥ “ለ”**

| 1. እግረኞች ስለሚቀጡበት | | |
|---|---|---|
| ተ.ቁ | የጥፋቶች ዝርዝር | ቅጣት (በብር) |
| 1 | እግረኛ እንዲያቋርጥበት በተፈቀደ ሀዲድ ላይ ሲያቋርጥ የባቡር ኦፕሬተር ሠራተኞችን ትዕዛዝ፣ የትራፊክ ምልክቶችን እና ማመላከቻዎችን አለማክበር | 100.00 |

| | | |
|---|---|---|
| 2 | እግረኛ እንዲያቋርጥበት ባልተፈቀደ የባቡር ሀዲድ ላይ ማቋረጥ | 200.00 |
| 3 | ያለበቂ ምክንያት ሀዲድ ላይ መቆም ወይም መጓዝ | 200.00 |
| 4 | እግረኛ እንዲያቋርጥበት በተፈቀደ ሀዲድ ላይ እያቋረጠ እያለ የባቡር ኦፕሬተር ሠራተኞችን ትዕዛዝ፣ የትራፊክ ምልክቶችና ማመላከቻዎችን ሳያከብሩ እንስሳትን መንዳት ወይም ይዞ ማቋረጥ | 200.00 |
| 5 | ወደ ባቡር ሀዲድ ክልል፣ ዋሻዎች እና ድልድዮች፣ የከፍታ መንገድ ክፍል፣ የመከላከያ አጥር፣ ግድግዳ እና የትኬት መቁረጫ መከለያ ሥፍራዎች ዘሎ ወይም ሾልኮ መግባት | 200.00 |
| 6 | በተከለለ የባቡር ሀዲዶች ውስጥ ወይም የባቡር መሠረተ ልማት ውስጥ እንስሳትን መንዳት ወይም መልቀቅ፣ እና በዋሻ መግቢያና መውጫ ላይ እንስሳትን ማቆም፣ ማከማቸት እና ማሰር | 300.00 |
| **2. ተሳፋሪዎች ስለሚቀጡበት** | | |
| **ተ.ቁ** | **የጥፋቶች ዝርዝር** | **ቅጣት (በብር)** |
| 1 | ለአካል ጉዳተኛ፣ ለአረጋዊያን፣ ለአቅመ ደካማ እና ለነፍሰጡር ሴቶች በተለየው መቀመጫ፣ ሊፍቶችና ሌሎች መገልገያ መሣሪያዎች በባቡር ኦፕሬተር ሠራተኞች ሳይፈቀድለት መጠቀም | 50.00 |
| 2 | በባቡር ላይ ተሳፍረው እያሉ መቀመጫዎችን መረጋገጥ ወይም መቀመጫዎች ላይ መራመድ፣ ወይም በባቡር ውስጥ ወይም በባቡር ጣቢያ በሚገኙ መቀመጫዎች ላይ መተኛት | 50.00 |
| 3 | የባቡር ማስተር ወይም የባቡር ኦፕሬተር ሠራተኞች ትእዛዝ ወይም ስለባቡር አጠቃቀም የወጣ የአሠራር ደንብን አለማክበር | 100.00 |
| 4 | ለሕግ ወይም ለመልካም ሥነ-ምግባር ተቃራኒ የሆነ ማናቸውንም | 100.00 |

| | | |
|---|---|---|
| | ድርጊት መፈጸም | |
| 5 | በባቡር ጣሪያ፣ መስኮት፣ መግቢያና መውጫ በመሳሰለው ቦታ ላይ መንጠላጠል ወይም ተንጠላጥሎ መጓዝ | 100.00 |
| 6 | በባቡር ጣቢያዎችም ሆነ በባቡሩ ላይ ተሳፍሮ እያለ የባቡሩን ጣቢያም ሆነ ባቡሩን ሊያቆሽሹ የሚችሉ ማናቸውንም ዓይነት ቆሻሻዎች መጣል ወይም ማንኛውንም ዓይነት ሲጋራ ማጨስ | 100.00 |
| 7 | በዚህ ደንብ የተከለከሉ ዕቃዎችን እና እንስሳትን ይዞ ባቡር ላይ መሳፈር | 200.00 |
| 8 | ምንም ዓይነት አደጋ በሌለበት ሁኔታ የድንገተኛ አደጋ መሣሪያዎችን መጠቀም ወይም መነካካት | 300.00 |
| 9 | የደህንነት ምልክት፣ የእሳት አደጋ መከላከያ፣ የአደጋ ጊዜ መውጫ እና መረጃ ሰጭ ምልክቶችን ማበላሸት | 400.00 |
| 10 | በመፈንዳት እና በመቀጣጠል ወይም በማንኛውም ሁኔታ አደጋ ለማድረስ የሚችሉ ማንኛውንም ዕቃዎችን ይዞ ባቡር ላይ መሳፈር ወይም ለመሳፈር መሞከር | 5000.00 |
| **3. አሽከርካሪዎች ስለሚቀጡበት** | | |
| **ተቁ** | **የጥፋቶች ዝርዝር** | **ቅጣት (በብር)** |
| 1 | የባቡር ተሳፋሪዎች የተሽከርካሪ መንገድ አቋርጠው ወደ ባቡር ጣቢያ ሲገቡ እና ከባቡር ጣቢያ ሲወጡ ቅድሚያ አለመስጠት | 200.00 |
| 2 | የተሽከርካሪ መንገድ በሚያቋርጥበት ቦታ ላይ ተመድበው የሚሰሩ የባቡር ኦፕሬተር ሠራተኞች እና ትራፊክ ፖሊስ የሚሰጡትን ትዕዛዝ አለማክበር | 500.00 |
| 3 | ባቡር ጣቢያ ከፊት ወይም ከኋላ በ20 ሜትር ርቀት ውስጥ ተሽከርካሪ ማቆም | 500.00 |

| | | |
|---|---|---|
| 4 | እግረኞች እና ተሽከርካሪዎች የባቡር ሀዲዱን ከሚያቋርጡበት መንገድ ላይ በማንኛውም አቅጣጫ በ20 ሜትር ክልል ውስጥ ተሽከርካሪ ማቆም | 500.00 |
| 5 | በባቡር መሠረተ ልማት ላይ ጉዳት አድርሶ ሪፖርት አለማድረግ | 500.00 |
| 6 | የተሽከርካሪ መንገድ የባቡር ሀዲዱን በሚያቋርጥበት ቦታ ላይ የተበላሸን ተሽከርካሪ በአስቸኳይ አለማንሳት | 2000.00 |
| 7 | በባቡር መሠረተ ልማት ላይ ወይም በባቡር ላይ ጉዳት ማድረስ | 5000.00 |

| **4. የባቡር ማስተሮች ስለሚቀጡበት** | | |
|---|---|---|
| **ተ.ቁ** | **የጥፋቶች ዝርዝር** | **ቅጣት (በብር)** |
| 1 | ከተፈቀደው የግንባር መብራት ሀይል ውጭ የሆኑ መብራቶችን ወይም ፓውዛዎችን መጠቀም | 100.00 |
| 2 | የባቡር ማስተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ ኖሮት ፍቃዱን ሳይዝ ባቡር መንዳት ማድረግ | 100.00 |
| 3 | ተገቢው የባቡር ማስተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ኖሮት በወቅቱ ሳያሳድስ ባቡር መንዳት | 200.00 |
| 4 | ምንም ዓይነት አደጋ በሌለበት ሁኔታ የድንገተኛ አደጋ መሣሪያዎችን መጠቀም | 300.00 |
| 5 | የተሽከርካሪ መንገድ የባቡር ሀዲዱን በሚያቋርጥበት ቦታ ሲደርስ፣ ከዋሻ ሲወጣ እና ሲገባ እና ወደ ባቡር ጣቢያ ሲደርስ ወይም ከባቡር ጣቢያ በሚነሳበት ጊዜ ጡሩንባ አለማሰማት | 500.00 |
| 6 | ባቡር እየነዱ የግል ተንቀሳቃሽ ስልክ መጠቀም | 500.00 |
| 7 | ባቡር ከመቆሙ በፊት እና እየተንቀሳቀሰ እያለ የባቡር በሮችን መክፈት ወይም የባቡር በሮች ከመዘጋታቸው በፊት ባቡር | 500.00 |

| | | |
|---|---|---|
| | ማንቀሳቀስ | |
| 8 | ከመቆጣጠሪያ ማዕከል ከሚላኩ መልዕክቶች ውጭ የሆኑ ድምጾችን በጆሮ ማዳመጫ ማዳመጥ | 500.00 |
| 9 | ከባቡር ፍሰት ተቆጣጣሪ እና ከመረጃ ማዕከል የሚሰጠውን ትእዛዝ መጣስ | 2,000.00 |
| 10 | ጫት ቅሞ ወይም እየቃመ፣ ንቃትን የሚገድብ መድሃኒት ወስዶ፣ አደንዛዥ ዕጽ ወስዶ፣ አልኮል ጠጥቶ፣ ሰክሮ፣ በሰውነቱ ጤናማ ያለመሆን የተነሳ ወይም በድካም መንፈስ ውስጥ ሆኖ ባቡር መንዳት፣ | 5,000.00 |
| 11 | የባቡር ማስተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ ሳይኖረው ባቡር ኦፕሬት ማድረግ | 10,000.00 |

**5. የባቡር ኦፕሬተሮችን ስለሚቀጡበት**

| ተ.ቁ. | የጥፋቶች ዝርዝር | ቅጣት (በብር) |
|---|---|---|
| 1 | አስፈላጊ የሆኑ መልዕክቶችና የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥበትን የጊዜ ሰሌዳ አለማሳወቅ | 5,000.00 |
| 2 | ከተፈቀደለት የተሳፋሪ ብዛት እና የጭነት ልክ በላይ መጫን | 5,000.00 |
| 3 | ለጭነት ወይም ለተሳፋሪ ተስማሚ ባልሆነ ባቡር ወይም ፉርጎ ሰዎችን፣ ዕቃዎችን ወይም እንስሳትን ማጓጓዝ | 5,000.00 |
| 4 | ድንገተኛ ፍተሻ ሲደረግ የተገኘበትን ጉድለት እንዲያስተካክል በጽሁፍ ተገልጾለት ጉድለቱን ሳያስተካክል ባቡርን ለትራንስፖርት አገልግሎት ማሰማራት | 10,000.00 |
| 5 | ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ተገቢው የቴክኒክ ምርመራ ያልተደረገለት ወይም ለሥራ ብቁ መሆኑ ያልተረጋገጠ ባቡር ለሥራ ማሰማራት | 10,000.00 |

| | | |
|---|---|---|
| 6 | አግባብ ካለው አካል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳያገኝ እና አስፈላጊውን ምዝገባ ሳይፈጽም የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት | 20,000.00 |
| 7 | ተገቢው የባቡር ማስተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የሌለውን ሰው በባቡር ማስተርነት ማሰማራት | 20,000.00 |
| 8 | እድሜያቸው ከ10 ዓመት በታች የሆኑ ሕጻናትን እና የአዕምሮ ህሙማንን ያለአጋዥ ማሳፈር | 500.00 |

| 6. የባቡር መሠረተ ልማት ኦፕሬተሮች ስለሚቀጡበት | | |
|---|---|---|
| **ተ.ቁ** | **የጥፋቶች ዝርዝር** | **ቅጣት (በብር)** |
| 1 | በባቡር መሠረተ ልማት ውስጥ የሚተከሉ ወይም የሚለጠፉ አስፈላጊ የትራፊክ ምልክቶችና ማመላከቻዎችን አለመትከል | 5000.00 |
| 2 | ድንገተኛ ፍተሻ ሲደረግ የተገኘበትን ጉድለት እንዲያስተካክል በጽሁፍ ተገልጾለት ጉድለቱን ሳያስተካክል የባቡር መሠረተ ልማቱን ለአገልግሎት ማዋል | 10,000.00 |
| 3 | አግባብ ካለው አካል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳያገኝ እና አስፈላጊውን ምዝገባ ሳይፈጽም የባቡር መሠረተ ልማት ለአገልግሎት ማዋል | 20,000.00 |

| 7. ሌሎች የደንብ መተላለፎች | | |
|---|---|---|
| **ተ.ቁ** | **የጥፋቶች ዝርዝር** | **ቅጣት (በብር)** |
| 1 | በባቡር መሠረተ ልማት እና በባቡር ላይ ወረቀት መበተን፣ ስዕል መሳል ወይም ጽሁፍ መጻፍ | 200.00 |

| | | |
|---|---|---|
| 2 | በባቡር መሠረተ ልማት ውስጥ መጸዳዳት፣ ቆሻሻዎችን መጣል እና ልብስ ማስጣት | 300.00 |
| 3 | በባቡር ውስጥ፣ በባቡር ጣቢያ፣ የተሽከርካሪ መንገድ የባቡር መስመሩን በሚያቋርጡበት ቦታ፣ በባቡር መሠረተ ልማት ውስጥ ዕቃ ማከማቸት፣ የንግድ ሥራ ማካሄድ፣ ማስታወቂያዎችን መንገር | 500.00 |
| 4 | በባቡር መሠረተ-ልማት ወይም በባቡር ላይ ማስታወቂያ መለጠፍ | 2000.00 |
| 5 | አፈር፣ አሸዋ፣ ድንጋይ የመሳሰሉትን በባቡር ሀዲድ ላይ ማራገፈ ወይም እንዲራገፍ ማድረግና ማንኛውም ለባቡር ጉዞ አደናቃፊ የሆኑ ነገሮችን ማስቀመጥ | 5000.00 |
| 6 | በባቡር ጣቢያዎች ላይ የተገጠሙ መሣሪያዎችን፣ ባቡሮችን፣ ዋሻዎችን፣ የባቡር ሀዲዶችን፣ ንጣፎችን፣ የባቡር ሀዲድ መከለያ አጥሮችን እና ሌሎች ማንኛውም የባቡር መሠረተ ልማት አካላትን ማበላሸት፣ መንቀል፣ መገንጠል፣ መስበር ወይም መውሰድ | 5000.00 |
| 7 | የኤሌክትሮ ሜካኒካል እና የባቡር እንቅስቃሴ መከታተያ መሣሪያዎችን፣ ገመዶችን፣ የቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያዎችን፣ የምልክት ሥርዓት እና የኃይል ማስተላለፊያ ሥርዓትን፣ ማበላሸት፣ መንቀል፣ መገንጠል፣ መስበር ወይም መውሰድ | 5000.00 |

## አዋጅ ቁጥር 1074/2010

## የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ

በሰው ህይወትና በንብረት ላይ እየደረሰ ላለው የመንገድ ትራፊክ አደጋ አንዱና ዋነኛው መንስኤ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት ጉድለት ያለው በመሆኑ እና ይህንንም ሁኔታ በመለወጥ ብቃት ያላቸውን አሽከርካሪዎች ማፍራት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በአገር አቀፍ ደረጃ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት ወጥነት ያለው፣ ደረጃውን የጠበቀ እና ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ከማሽከርከር ልምድና ብቃት ማነስ ጋር ተያይዞ የሚደርስ የትራፊክ አደጋን ለመቀነስ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸውን መስፈርቶች ማሻሻል በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 1074/2010" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

   1. "ባለሥልጣን" ማለት የፌደራል የትራንስፖርት ባለሥልጣን ነው፤
   2. "የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ" ማለት ባለሞተር ተሽከርካሪዎችን ለመንዳት የሚያስችል በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤
   3. "የፌደራል መንጃ ፈቃድ" ማለት በእንካ ለእንካ መርህ (ሪሲፕሮሲቲ) መሠረት ለውጭ አገር ዜጎች፣ ወይም ለጉብኝት፣ ለንግድ ሥራ ወይም ለመንግስት ሥራ ወደ ውጭ አገር ለሚሄዱ ኢትዮጵያውያን ባለሞተር ተሽከርካሪ ለማሽከርከር የሚያስችል በዚህ አዋጅ በሚወጣ መመሪያ መሰረት የሚሰጥ መንጃ ፈቃድ ነው፤

4. “የውጭ አገር መንጃ ፈቃድ” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲዊ ሪፐብሊክ እውቅና ያለው የውጭ ሀገር መንግስት የሰጠው የመንጃ ፈቃድ ነው፣
5. “ኢንተርናሽናል መንጃ ፈቃድ” ማለት መስከረም 9 ቀን 1942 ዓ.ም ስዊስ ሀገር ጀኔቫ ላይ በተፈረመው የተባበሩት መንግስታት የመንገድ ትራፊክ ስምምነት መሠረት የተሰጠ መንጃ ፈቃድ ነው፣
6. “ፈቃድ ሰጪ አካል” ማለት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እንዲሰጥ በሕግ አግባብ የተቋቋመና በባለሥልጣኑ ውክልና የተሰጠው የፌደራል ወይም የክልል ትራንስፖርት ተቋም ወይም ማንኛውም የመንግስት ተቋም ነው፤
7. “ቀላል ተሳቢ” ማለት ከፍተኛ ክብደቱ ከነጭነቱ ከ 750 ኪሎ ግራም የማይበልጥ ተሳቢ ነው፤
8. “ማሽነሪ” ማለት ለግንባታ፤ ለግብርና፤ ለዕቃ ማንሻ ወይም ለቁፋሮ ሥራ አገልግሎት የሚውል የሰው ጉልበትን በማገዝ ሥራን የሚያፋጥን ባለጎማ ወይም ባለሰንሰለት እግር ያለው ማንኛውም በሞተር የሚንቀሳቀስ መሣሪያ ነው፤
9. “የሕክምና ተቋም” ማለት የሕክምና አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ የተሰጠው የሕክምና ተቋም ነው፤
10. “የወታደር የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ” ማለት በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 16 መሠረት የመከላከያ ሚኒስቴር የሰጠው የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ነው፤
11. “ሚኒስቴር” ማለት የትራንስፖርት ሚኒስቴር ነው፤
12. “ባለሞተር ተሽከርካሪ” ማለት በሜካኒካል ወይም በኤሌክትሪክ ኃይል እየተንቀሳቀሰ በመንገድ ላይ በመንኮራኩር የሚሄድ ማንኛውም ዓይነት ተሽከርካሪ ነው፤
13. “መንገድ” ማለት ለተላላፊ ክፍት ካልሆነ የግል መንገድ በስተቀር ተሽከርካሪዎች በተለምዶ የሚጠቀሙበትን ጎዳና፣ የከተማ መንገድ፣ አውራ ጎዳና፣ የገጠር መንገድ ወይም መተላለፊያ ነው፤
14. “የትራፊክ ተቆጣጣሪ” ማለት የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መከበራቸውን ለመቆጣጠር እና የትራፊክ ፍሰትን ለማስተናበር አግባብነት ባለው ሕግ ሥልጣን የተሰጠው ሰው ሲሆን፣ ትራፊክ ተቆጣጣሪ ፖሊስ እና የትራንስፖርት ተቆጣጣሪ ተብለው ይታወቃሉ፤

15. “ትራፊክ ተቆጣጣሪ ፖሊስ” ማለት የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መከበራቸውን ለመቆጣጠር እና የትራፊክ ፍሰትን ለማስተናበር አግባብነት ባለው ሕግ ሥልጣን የተሰጠው የፖሊስ አባል ነው፤
16. “የማሰልጠኛ ተቋም” ማለት በሕግ እውቅና ያለው መንግስታዊ ወይም የግል የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋም ሲሆን የቀጠራቸውን ወይም ለሚቀጥራቸው ሠራተኞች የማሽከርከር ሥልጠና ለመስጠት ፍቃድ የተሰጠው ማንኛውንም የግል ወይም የመንግስት ተቋምን ይጨምራል፤
17. “ትራንስፖርት ተቆጣጣሪ” ማለት የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መከበራቸውን ለመቆጣጠር በተለይም በመንገድ ላይ የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎችን የቴክኒክ ብቃት እንዲያረጋግጥና ከትራንስፖርት አስተዳደር ጋር በተያያዘ የወጡ መመሪያዎችን አፈፃፀም ለመቆጣጠር አግባብ ባለው አካል ሥልጣን የተሰጠው ሰው ነው፤
18. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
19. በዚህ አዋጅ በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር የሴትንም ይጨምራል፡፡

3. **ዓላማ**

የዚህ አዋጅ ዓላማ: -

1. አሽከርካሪዎች በቂ ችሎታ ኖሯቸው ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ተሽከርካሪን የሚያሽከረክሩ መሆኑን ማረጋገጥ፣
2. በአገር አቀፍ ደረጃ ደረጃውን የጠበቀ የማሽከርከር ብቃት መስፈርት መወሰን፣ ከማጭበርበር ከሙስና እና ከተንዛዛ አሠራር ነፃ የሆነ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ሥርዓት መፍጠር፣
3. የመንገድ ትራንስፖርት የትራፊክ ፍሰትንና የማሽከርከር ብቃትን የሚመለከቱ የሁለትዮሽና ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በማናቸውም የኢትዮጵያ መንገዶች ላይ በአሽከርካሪዎች መከበራቸውን ማረጋገጥ፣ ይሆናል፡፡

4. **የተፈፃሚነት ወሰን**

የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በማናቸውም የኢትዮጵያ መንገዶች ላይ ባለሞተር ተሽከርካሪዎችን ለሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎች በሚሰጡ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዶች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ተግባርና ኃላፊነት

5. **የባለስልጣኑ ተግባርና ኃላፊነት**

ባለስልጣኑ በሕግ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል: -

1. የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን መከታተል፤
2. በፈቃድ ሰጪው አካል መሟላት የሚገባቸውን ዝርዝር መስፈርቶች ማውጣት፤
3. ለፈቃድ ሰጭ አካላት እንደአስፈላጊነቱ የአቅም ግንባታ ድጋፍ መስጠት፤
4. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 መሠረት ለፈቃድ ሰጪው አካል የብቃት ማረጋገጫ ውክልና መስጠት፣ ተግባሩን በአግባቡ እያከናወነ መሆኑን መከታተል፣ ብቃት የሌለው ሆኖ ሲገኝ የተሰጠውን ውክልና ማገድ ወይም መሠረዝ፤
5. የአሽከርካሪ ብቃት ሥልጠና ለሚሰጡ ተቋማት የሚያስፈልገውን የካሪኩለም ዝግጅት ከቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት ጋር በመሆን ማዘጋጀት፤
6. የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ደብተር ጥራትን፣ ይዘትንና ቅርጽን መወሰን፣ የብቃት ማረጋገጫ ደብተሮችን በማሳተም በሀገር አቀፍ ደረጃ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ፤
7. የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጣቸውን እና ጥፋት የፈጸሙ አሽከርካሪዎችን ዝርዝር በአገር አቀፍ ደረጃ መዝግቦ መያዝ፤
8. የማሰልጠኛ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ማሟላት ያለባቸውን ሀገር አቀፍ መስፈርቶች በመመሪያ የመወሰን፤ ተግባራቸውን በአግባቡ እያከናወኑ ስለመሆናቸው ቁጥጥርና ክትትል የማድረግ፤ ብቃታቸው የተጓደለ ሆኖ ሲያገኘው በዚህ አዋጅ መሰረት የምስክር ወረቀታቸው እንዲታገድ ወይም እንዲሰረዝ የማድረግ፤
9. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በሀገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ የሚሆን የማሰልጠኛ ተቋማት የሥልጠና ታሪፍ መወሰን እና በሚኒስቴሩ ሲፀድቅ ተግባራዊ ማድረግ፤

10.የማሽከርከር ብቃት ሥልጠና የሚሰጡ የማሰልጠኛ ተቋማት፣ አሰልጣኞች እና የማሽከርከር ብቃት ማረጋገጫ ፈተና የሚሰጡ የፍቃድ ሰጪ አካላት ባለሙያዎች ሊያሟሏቸው የሚገቡ መስፈርቶችን እና ሊከተሏቸው የሚገቡ የሥነ-ምግባር መርሆዎችን እንዲሁም መስፈርቶቹን ሲያጓድሉ ወይም የሥነ-ምግባር መርሆዎቹን የሚጻረር ተግባር ሲፈጽሙ ሊወሰድባቸው የሚገቡ እርምጃዎችን በተመለከተ መመሪያ የማውጣት፤

11.በፌደራል ደረጃ የፌዴራል መንጃ ፈቃድ የመስጠት፤ የማደስ፤ በሕግ በተደነገገው መሠረት የማገድና የመሰረዝ፡፡

## ክፍል ሦስት

## አጠቃላይ ግዴታዎች

### 6. ስለ አሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት

1. ማናቸውም የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሲሰጥ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተደነገጉትን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡
2. ባለስልጣኑ ማንኛውም ፍቃድ ሰጪ አካል ማሟላት የሚገባውን መስፈርት ያወጣል፡፡
3. ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሚያወጣው መስፈርት መሟላቱን በማረጋገጥ ለፈቃድ ሰጪው አካል ውክልና ይሰጣል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እንዲሰጥ ሥልጣን የተሰጠው ፈቃድ ሰጪ አካል የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በሚቃረን መልኩ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሰጥቶ የተገኘ እንደሆነ ባለስልጣኑ ፈቃዱን ማገድ ወይም መሰረዝ ይችላል፡፡

### 7. የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ምድቦች

1. የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አመዳደብ ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ በተዘረዘረው መሠረት ይሆናል፡፡
2. ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድ ምድብ ውስጥ ከፍተኛውን የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት የሚቻለው በዚያው ምድብ ውስጥ ካለው አነስተኛ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድን በቅድሚያ በማግኘትና በየደረጃው በማሳደግ ነው፡፡

3. በአንድ ምድብ ውስጥ ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የሚቀይር ማንኛውም አሽከርካሪ ለደረጃው የተዘጋጀውን የንድፈ ሃሳብና የተግባር ሥልጠናና ፈተና መውሰድ አለበት፡፡
4. ማንኛውም የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የያዘ አሽከርካሪ የሌላ ምድብ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ማግኘት ከፈለገ ለምድቡ የሚሰጠውን ልዩ የንድፈ ሀሳብና የተግባር ሥልጠና እና ፈተና መውሰድ አለበት፡፡
5. ከማሽነሪ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በስተቀር ማንኛውም የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጠው ሰው በምድብ ውስጥ ከአነስተኛ ደረጃ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ሲያሳድግ ወይም ከአንድ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ምድብ ወደ ሌላ ምድብ ሲቀይር ቀድሞ የያዘውን የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ደብተር ተመላሽ ማድረግ አለበት፡፡
6. ማንኛውንም በአንድ ምድብ የሚገኝ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ያለው አሽከርካሪ በሌላ ምድብ የሚገኝ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት የሚችልባቸውን መስፈርቶች እና ሊወስዳቸው የሚገቡ የንድፈ ሀሳብና የተግባር ትምህርቶች እና ፈተናዎች ይዘትና መጠን በባለሥልጣኑ ይወሰናል፡፡
7. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (5) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም አሽከርካሪ ደረጃውን ሲያሳድግ ወይም ምድብ ሲቀይር አዲስ በሚሰጠው የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ላይ ቀድሞ ይዞት የነበረው የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ምድብና ደረጃ በሙሉ ሊያሽከረክር እንደሚችል ተገልፆ ይሰጠዋል፡፡

8. <u>ስለአሽከርካሪ ሥልጠናና ስለችሎታ ፈተና</u>

ማንኛውም ሰው የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት፡-

1. ባለስልጣኑ በሚያወጣው ሥርዓተ ትምህርት መሠረት ንድፈ ሃሣብንና ተግባርን ያዋሃደ ሥልጠና በማሰልጠኛ ተቋም መውሰድ አለበት፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን ሥልጠና እንዳጠናቀቀ የተሰጠውን የችሎታ ማረጋገጫ ፈተና ያለፈ መሆን አለበት፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም ሰው የአውቶሞቢል የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት በራሱ ወይም በቤተሰቡ ባለቤትነት የተያዘን ተሽከርካሪ በመጠቀም ከባለስልጣኑ ጊዜያዊ የማሰልጠን ፍቃድ በተሰጠው ሰው አማካኝነት ለመሰልጠን ይችላል፤
4. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) አፈፃፀም "ቤተሰብ" ማለት እስከ ሁለተኛ ደረጃ የሚቆጠር የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው ዘመድ ነው፤
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ሥልጠና ለሚሰጠው ሰው ጊዜያዊ የማሰልጠን ፍቃድ የሚሰጥበትን ዝርዝር ሁኔታ ባለስልጣኑ ይወስናል፤
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም አሽከርካሪ በታክሲ አገልግሎት የተመዘገቡ ተሽከርካሪዎችን ማሽከርከር የሚችለው፡-
   ሀ) አስረኛ ክፍልን ያጠናቀቀ ሆኖ የአውቶሞቢል ወይም የህዝብ ምድብ ቋሚ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ያለው ከሆነ፤ እና
   ለ) ባለሥልጣኑ ባዘጋጀው የሥልጠና ይዘት መሠረት ከፈቃድ ሰጭ አካል ልዩ ሥልጠና በመውሰድ የታክሲ የአሽከርካሪ የምስክር ወረቀት የተሰጠው እንደሆነ፤ ነው፡

## 9. <u>የማሰልጠኛ ተቋም ግዴታዎች</u>

1. ማንኛውም የማሰልጠኛ ተቋም
   ሀ) ባለስልጣኑ ያወጣውን መስፈርት ማሟላትና እንደአግባቡ በባለሥልጣኑ ወይም በፈቃድ ሰጪው አካል የተሰጠ የምስክር ወረቀትና አግባብ ባለው አካል የተሰጠ የንግድ ሥራ ፈቃድ መያዝ፣
   ለ) ሥልጠና በሚሰጥበት ጊዜ የትራፊክ ደህንነት ደንቦች በሚገባ መከበራቸውን ማረጋገጥ፣
   ሐ) ሥልጠናውን ባለስልጣኑ ባዘጋጀው መስፈርት መሰረት ማካሄድ፣ እና
   መ) የሥልጠና መረጃዎችን መያዝና በየጊዜው ለፈቃድ ሰጪው አካል ሪፖርት ማድረግአለበት፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የራሱን ሠራተኞች ወይም በአሽከርካሪነት ለመቅጠር ለመለመላቸው ሰዎች ብቻ የማሽከርከር ብቃት ሥልጠና እንዲሰጥ በባለስልጣኑ የተፈቀደለት የሕግ ሰውነት ያለው የማሰልጠኛ ተቋም የንግድ ፍቃድ እንዲኖረው አይገደድም፡፡

10.<u>የማስተማሪያ ተሽከርካሪ አነዳድ ሁኔታዎች</u>

1. የማስተማሪያ ተሽከርካሪ ሊነዳ የሚችለዉ አግባብ ባለው አካል ሲፈቀድ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው ቦታ ወይም አነስተኛ የትራፊክ እንቅስቃሴ በሚኖርበት መንገድ ላይ ሆኖ፡-
   ሀ) “ለማጅ” የሚል ምልክት ከተሽከርካሪው ፊትና በስተኋላ ተለጥፎ በ 50 ሜትር ርቀት ከፊት ለፊቱ ላለ ወይም ለተከታይ አሽከርካሪ በግልጽ  የሚታይ መሆን፣ እና
   ለ) ተሽከርካሪው በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ሁሉ ከለማጁ ጐን አሰልጣኝ መቀመጥ፣ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ለ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዕጩ አሽከርካሪዎች ለብቻቸው ራሳቸውን ችለው እያሽከረከሩ ስለሚሰለጥኑበት ሁኔታ ባለስልጣኑ ይወስናል፡፡
3. የማስተማሪያ ተሽከርካሪው ባለሁለት ወይም ባለሦስት እግር ሞተር ሳይክል ሲሆን፡-
   ሀ) “ለማጅ” የሚል ምልክት ከሞተር ሳይክሉ በስተኋላ ተለጥፎ ከ 50 ሜትር ርቀት ለተከታይ አሽከርካሪ በግልጽ የሚታይ መሆን፣
   ለ) ከለማጁ በስተኋላ በሞተር ሳይክሉ ኮርቻ የሚቀመጥ አሰልጣኝ መኖር፣ እና
   ሐ) ለማጁና አሰልጣኙ የአደጋ መከላከያ ቆብ የሚጠቀሙ መሆን አለበት፡፡

11.<u>ስለ መንዳት ፈተና</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 የተደነገገው ቢኖርም ለፈተና ሲሆን ለማጁ ብቻውን ራሱን ችሎ ማሽከርከር አለበት፡፡

12.<u>ተፈላጊ ዕድሜና ትምህርት</u>

የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት የሚያመለክት ማናቸውም ሰው፡-

1. ለሞተር ሳይክል ወይም ለአውቶሞቢል የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሲሆን፣ ቢያንስ የአራተኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቀና ዕድሜው ከ18 ዓመት ያላነሰ መሆን፣
2. ለባለ ሶስት እግር የአሽከርካሪ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሲሆን ቢያንስ የአስረኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቀና ዕድሜው ከ 20 ዓመት ያላነሰ መሆን፣
3. ለደረቅ I ወይም ለሕዝብ I የአሽከርካሪ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሲሆን ቢያንስ የአስረኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቀና ዕድሜው ከ 22 ዓመት ያላነሰ መሆን፣
4. ለደረቅ II፣ ለህዝብ II፣ ወይም ለፈሳሽ I የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሲሆን ቢያንስ አስረኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቀ፣ ዕድሜው ከ 24 ዓመት ያላነሰ፣ እና በተመሳሳይ ምድብ የደረቅ I፣ የሕዝብ I፣ ቋሚ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ኖሮት ከፈሳሽ I በስተቀር ቢያንስ የ አንድ ዓመት የማሽከርከር ልምድ ያለው መሆን፣
5. ደረቅ III፣ ለሕዝብ III፣ ለፈሳሽ II የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሲሆን ቢያንስ አስረኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቀ፤ ዕድሜው ከ 26 ዓመት ያላነሰ እና በተመሳሳይ ምድብ የደረቅ II፣ የህዝብ II፣ እና ቋሚ የፈሳሽ I የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ ኖሮት ቢያንስ የአንድ ዓመት የማሽከርከር ልምድ ያለው መሆን፤
6. ለማሽን ኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሲሆን ቢያንስ የአስረኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቀና ዕድሜው ከ 20 ዓመት ያላነሰ መሆን፤ አለበት፡፡

13.<u>የጤና ሁኔታ</u>

1. የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት የሚያመለክት ማናቸውም ሰው ባለሞተር ተሽከርካሪ በሚገባ ለማንቀሳቀስ ከሚያውክ ማንኛውም ዓይነት የአካል ጉዳት ወይም የጤና መታወክ ነፃ መሆን አለበት፡፡

2. ማንኛውም አመልካች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ መሠረት ባለሞተር ተሽከርካሪ ለማሽከርከር ብቁ መሆኑ፣ ባለሥልጣኑ ወይም ፈቃድ ሰጪው አካል ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ወይም ከጤና ቢሮ ጋር በመመካከር በሚያወጣው መስፈርት መሠረት በሚመረጥ የሕክምና ተቋም በሚደረግ ምርመራ ይረጋገጣል፡፡
3. ፈቃድ ሰጪው አካል በሕክምና ተቋም የምርመራ ውጤት ተቀባይነት ላይ ጥርጣሬ ካለው በሌላ የሕክምና ተቋም ድጋሚ ምርመራ እንዲደረግ ሊጠይቅ ይችላል፤ የኋለኛው የሕክምና ውጤት ከፊተኛው ጋር የሚጣጣም ከሆነም የመጨረሻ ይሆናል፡፡
4. በሁለት የሕክምና ተቋማት የተሰጠው የሕክምና ውጤት የተለያየ ከሆነ ፈቃድ ሰጪው አካል ለመረጠው ሦስተኛ የሕክምና ተቋም ተልኮ የሚሰጠው የሕክምና ውጤት የመጨረሻ ይሆናል፡፡

14.<u>ስለ አሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ማመልከቻ</u>

1. የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት ለፈቃድ ሰጪው አካል የሚቀርብ ማመልከቻ በግንባር ወይም በፖስታ ወይም በኤሌክትሮኒክስ መልዕክት ሊሆን ይችላል፡፡
2. ማናቸውም የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ማመልከቻ ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡-
   ሀ) የትምህርት ማስረጃ፤
   ለ) የልደት የምስክር ወረቀት ወይም ፓስፖርት ወይም በቀበሌ አስተዳደር የተሰጠ የነዋሪነት መታወቂያ ደብተር፤
   ሐ) የጤንነት ምርመራ ውጤት፤
   መ) በአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋም ወይም ፈቃድ በተሰጠው ሰው የሰለጠነ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰርተፊኬት ወይም ማስረጃ፡፡

15.<u>የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ስለመስጠት</u>

1. ፈቃድ ሰጪው አካል በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 መሠረት የቀረበለትን ማመልከቻ መርምሮ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8፣ 12 እና 13 ድንጋጌዎች የተመለከቱ መስፈርቶች መሟላታቸውን ካረጋገጠ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የሚወስድ ከሆነ ከህክምና ተቋማት ወይም በሕግ ሥልጣን በተሰጠው

አካል ተረጋግጦ የቀረበ ግዴታ ወይም ገደብ ካለ በፈቃዱ ላይ አስፍሮ የተጠየቀውን ምድብ ጊዜያዊ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚሰጥ ጊዜያዊ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ሁለት ዓመት ይሆናል፡፡
3. ጊዜያዊ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወደ ቋሚ የአሽከርካሪ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የሚቀየረው ባለፍቃዱ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ያስመዘገበውን የትራፊክ ጥፋትና የትራፊክ አደጋ ሪከርድ መሰረት በማድረግ ይሆናል፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም፡-
   ሀ) ማንኛውም አካል ጉዳተኛ የተሽከርካሪን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር ያለበትን ጉድለት ሊያካክስለት የሚችል ልዩ መሣሪያ የተገጠመለትን ባለሞተር ተሽከርካሪ ለመንዳት የሚያስችል የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል፤
   ለ) የውጭ አገር ወይም ኢንተርናሽናል መንጃ ፈቃድ ያለው ሰው ተመጣጣኙ ምድብ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እንዲሰጠው ሲያመለክትና ፈቃድ ሰጪው አካል፣
      (1) የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የሰጠው አገር የኢትዮጵያን የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በተመሳሳይ መልኩ የሚቀበል መሆኑን ሲያረጋግጥ፣
      (2) የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱ ትክክለኛነት በሚመለከተው አካል መረጋገጡንና ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ያላለፈ መሆኑን ሲያምንበት፣ እና
      (3) ተገቢው ክፍያ ሲፈጸምለት የተጠየቀውን ፈቃድ ይሰጣል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) (ለ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የውጭ አገር ወይም ኢንተርናሽናል መንጃ ፈቃድ ያለው ሰው ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ከገባበት ቀን አንስቶ እስከ አርባ አምስት ቀን ድረስ ወይም ፈቃዱ ፀንቶ የሚቆየው ከአርባ አምስት ቀን በታች ከሆነ ይኸው ቀን እስኪጠናቀቅ ድረስ ወደ ኢትዮጵያ መንጃ ፈቃድ መቀየር ሳያስፈልገው ማሽከርከር ይችላል፡፡

6. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚሰጥ ማንኛውም የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ፡
   ሀ) ጥራት፣ ይዘትና ቅርጽ በባለስልጣኑ የሚወሰን ሆኖ ለማጭበርበር ድርጊት ያልተጋለጠ እንዲሆን የሚያስችል አሠራር እንዲኖረው ማድረግ፤ እና
   ለ) የባለፍቃዱ ፎቶግራፍ የተለጠፈበት እንዲሁም የባለፍቃዱ የጽሁፍ ፊርማና የእጅ ጣቶቹ አሻራ ያረፈበት እንዲሆን ማድረግ፤ አለበት፡፡
7. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም አመልካቹ ቋሚ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ኖሮት ደረጃውን የሚያሳድግ ወይም በሌላ ምድብ የብቃት ማረጋገጫ የሚወስድ ከሆነ ፈቃድ ሰጭው አካል በዚህ አዋጅ አንቀፅ 14 መሠረት የቀረበለትን ማመልከቻ መርምሮ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 8፣ አንቀፅ 12 እና አንቀፅ 13 የተቀመጡ መስፈርቶች መሟላታቸውን ካረጋገጠ በኋላ ከህክምና ተቋም ወይም በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል ተረጋግጦ የቀረበ ግዴታ ወይም ገደብ ካለ በፈቃዱ ላይ አስፍሮ የተጠየቀውን ምድብ ቋሚ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

16.<u>ስለወታደር የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ</u>

1. የአገር መከላከያ ሚኒስቴር በመከላከያ ኃይል ውስጥ ለሚያገለግሉ ሠራተኞች የወታደር የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የመስጠት፣ የማደስ፣ የማገድና የመሰረዝ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡ ሆኖም፡-
   ሀ) ፈቃዱ "ለኦፊስዬል ወታደራዊ ጉዳይ ብቻ" የሚል መግለጫ የተጻፈበት ሆኖ የወታደር መለያ ቁጥር ሰሌዳዎች የተደረጉባቸውን የመከላከያ ኃይል ተሽከርካሪዎች ለመንዳት ብቻ የሚያገለግል ይሆናል፤
   ለ) የአገር መከላከያ ሚኒስቴር የተሰጠውን ሥልጣን በሥራ ላይ ሲያውል የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች መከተልና ማስፈጸም አለበት፤
   ሐ) ባለስልጣኑ የዚህ አንቀጽ ፊደል ተራ (ለ) ድንጋጌ መጠበቁን ለማረጋገጥ ከፈቃድ አሰጣጡ ጋር የተያያዙ የአገር መከላከያ ሚኒስቴር አሰራሮችና ሰነዶችን በማንኛውም ጊዜ ለመመርመር ይችላል፡፡
2. የወታደር የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዶች በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን መሥፈርቶችና ደረጃዎች የሚያሟሉ ሲሆንና ተገቢው ክፍያ ሲፈጸም በሲቪል የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዶች ሊለወጡ ይችላሉ፡፡

17.<u>የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይዞ ስለመገኘትና ስለማሳየት</u>

1. ማናቸውም ባለፈቃድ ባለሞተር ተሽከርካሪ በማንኛውም መንገድ ላይ በሚያንቀሳቅስበት ጊዜ ሁሉ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን ይዞ መገኘት አለበት፡፡
2. ማንኛውም ሰው በመንገድ ላይ ባለሞተር ተሽከርከሪ በማሽከርከር ላይ ሳለ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው የትራፊክ ተቆጣጣሪ ሲጠየቅ ተሽከርካሪውን በሥነ-ሥርዓት በማቆም የአሽከርከሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን የማሳየት ግዴታ አለበት፡፡

18.<u>የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድን ስለማሳረምና ስለመተካት</u>

1. በአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ላይ ከሰፈሩት መግለጫዎች መካከል የተሳሳተ ነገር መኖሩን እንዳወቀ አሽከርካሪው የብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን ለእርምት ማቅረብ አለበት፤ ይህም ሲሆን ስህተቱ ያጋጠመው በፈቃድ ሰጭው አካል ጥፋት ምክንያትነት ብቻ ካልሆነ በስተቀር ተገቢውን ክፍያ ባለፈቃዱ ይፈጽማል፡፡
2. የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የጠፋ፣ የተበላሸ፣ የማይነበብ ወይም በመግለጫዎቹ ላይ የተመለከቱት ጉዳዮች የተለወጡ እንደሆነ ባለፈቃዱ ምትክ ፈቃድ እንዲሰጠው ወዲያው ለፈቃድ ሰጭው አካል ማመልከት አለበት፡፡
3. ፈቃድ ሰጭው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ማመልከቻ ሲቀርብለት አመልካቹ ተገቢውን ክፍያ እንዲፈጽም ካስደረገ በኋላ ምትክ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡
4. ምትክ የተሰጠበትን የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መልሶ ያገኘ ሰው ተጨማሪ የሆነው ፈቃድ እንዲሰረዝና እንዲወገድ ወዲያው ለፈቃድ ሰጭው አካል ማስረከብ አለበት፡፡

19.<u>የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜና ስለማሳደስ</u>

1. ማንኛውም ቋሚ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ፀንቶ የሚቆየው ከተሰጠበት ቀን አንስቶ ለአራት ዓመት ይሆናል፡፡
2. ማንኛውም የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13 መሠረት የተደረገ የጤንነት ምርመራ ውጤት ሲቀርብና ተገቢው ክፍያ ሲፈጸም በእያንዳንዱ ዕድሳት ወቅት ለአራት ዓመት ይታደሳል፡፡

3. የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱ ባለቤት ፈቃዱን ለፈቃድ ሰጭው አካል ራሱ ወይም በሕጋዊ ወኪሉ አማካኝነት በማቅረብ ሊያሳድስ ይችላል፤ ሆኖም ለሁለት ተከታታይ ጊዜ በወኪል አማካኝነት ማሳደስ አይፈቀድም፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ባለቤት ዕድሜው ከሃምሳ አምስት ዓመት በላይ ከሆነ፣ ፍቃዱ በየሁለት ዓመት መታደስ አለበት፡፡
5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እና በዚህ አዋጅ አንቀፅ 15 (2) መሠረት የአሽከርካሪ ፈቃዱ ቋሚ ከሆነ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱ የአገልግሎት ጊዜው ካበቃ በኋላ ባለው አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ሳይቀይር ወይም ሳያሳድስ የቀረ አሽከርካሪ ፍቃዱ ቋሚ ከሆነ የተግባር ፈተና ተፈትኖ ሲያልፍ ይታደስለታል፤ ፍቃዱ ጊዜያዊ ከሆነ ደግሞ ከተግባር ፈተና በተጨማሪ ጊዜያዊ ፈቃዱን በያዘበት ዓመት የተመዘገበበት የጥፋት ሪከርድ ታይቶ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱ ይታደስለታል፡

20.**<u>የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ስለማገድና መሰረዝ</u>**

1. የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጠው ሰው በፈፀመው የትራፊክ ደንብን የመተላለፍ ጥፋት ሪከርድ ወይም በሌላ አጥጋቢ ምክንያት ላይ ተመስርቶ የጤንነት ሁኔታው ወይም የመንዳት ችሎታው አጥጋቢ አለመሆኑ ሲረጋገጥ ፈቃድ ሰጪው አካል የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን ማገድ ወይም ባለፈቃዱ የጤና ምርመራ እንዲያደርግ ወይም የችሎታ ማረጋገጫ ፈተና እንዲወስድ ወይም ሁለቱንም እንዲፈጽም ሊያስገድደው ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተካሄደው የጤና ምርመራ ወይም የችሎታ ማረጋገጫ ፈተና ውጤት የባለፈቃዱ የጤና ሁኔታ ወይም የመንዳት ችሎታ አጥጋቢ አለመሆኑን የሚያመለክት ሲሆን ወይም ባለፈቃዱ ያለበቂ ምክንያት የምርመራ ወይም የፈተና ውጤቱን በዘጠና ቀናት ውስጥ ሊያቀርብ ካልቻለ ፈቃድ ሰጪው አካል ፈቃዱን ሊሰርዘው ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በአሽከርካሪ የጥፋት ሪከርድ መሠረት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ውሳኔው በደረሰው በ 30 ቀናት ውስጥ ለሚኒስቴሩ ቅሬታውን ሊያቀርብ ይችላል፤ የሚኒስቴሩም ውሳኔ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሆናል፡
5. ማንኛውም የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የተገኘው በሀሰተኛ ማስረጃ፣ በማታለል ወይም በሌላ በማንኛውም ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ መሆኑ በባለስልጣኑ ወይም በፈቃድ ሰጭው አካል ሲረጋገጥ አጥፊው አግባብነት ባለው ሕግ መሰረት የሚጠየቅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ተሰጥቶ የነበረው የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰረዛል፡፡

## 21.<u>የፍቃድ ሰጭ አካላትን ፈቃድ ስለማገድና ስለመሰረዝ</u>

1. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 (4) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ፈቃድ ሰጪ አካል ይህን አዋጅና አዋጁን ተከትለው የወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን የተላለፈ እንደሆነ በተለይም፡-
   ሀ) በባለሥልጣኑ የወጣውን መስፈርት ለማያሟላ የማሰልጠኛ ተቋም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሰጠ ወይም ያደሰ፤
   ለ) ዕጩ አሽከርካሪው ሐሰተኛ የትምህርት፣ የጤናና የእድሜ ማስረጃ ማቅረቡን እያወቀ ወይም ማወቅ እየቻለ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈተና እንዲወስድ ያደረገ፣ ወይም የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እንዲሰጠው ያደረገ፤
   ሐ) በሀገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ እንዲሆን በባለስልጣኑ ከተዘጋጀው የጽሁፍና የተግባር ፈተና መመሪያ ውጪ ፈተና የሰጠ፤
   መ) ከባለስልጣኑ ወይም በባለስልጣኑ ውክልና ከተሰጣቸው አካላት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የሌላቸውን ወይም ፈቃዳቸው የታገደ፣ ወይም ያልታደሰ ፈታኞችን ተጠቅሞ ፈተና እንዲሰጥ ያደረገ፤ ወይም የተፈታኞች ብቃት እንዲረጋገጥ ያደረገ፤
   ሠ) የፍቃድ ሰጪ አካላት ሊያሟሏቸው ከሚገቡዋቸው መስፈርቶች ውስጥ አንዱን አጉድሎ የተገኘ፤

ረ) ብልሹ አሰራሮችንና ኪራይ ሰብሳቢነትን ለማስወገድ ተገቢውን እርምጃ ያልወሰደ፣ ወይም የሚቀርቡ የሕዝብ ቅሬታዎችን ተቀብሎና በአግባቡ አጣርቶ የእርምት እርምጃ ያልወሰደ፤ በተደጋጋሚ የሕዝብ ቅሬታ በሚቀርብባቸው የፍቃድ ሰጪው ሠራተኞችና ባለሙያዎች ላይ ቅሬታውን አጣርቶ ተገቢውን እርምጃ ያልወሰደ፤

ሰ) ለማሰልጠኛ ተቋም የተሰጠውን የምስክር ወረቀት እንዲያግድ ወይም እንዲሰረዝ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 22 (2) መሰረት በባለሥልጣኑ የተሰጠውን ትዕዛዝ ያልፈፀመ፤

ባለስልጣኑ ፍቃድ ሰጪው አካል ጥፋቶቹን ለማረምና ዳግም እንዳይከሰቱ ለማድረግ የሚያስችሉ ተገቢ እርምጃዎችን እንዲወሰድ ከማሳሰብ ጋር የእርምት እርምጃዎቹን ወስዶ ሪፖርት የሚያቀርብበትን ተገቢ ጊዜ በመወሰን የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡

2. ማንኛውም ፈቃድ ሰጪ አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት በተሰጠው ጊዜ ገደብ ውስጥ ተገቢውን እርምጃ ሳይወስድ የቀረ እንደሆነ ባለስልጣኑ ተገቢ ጊዜ በመወሰን ማስተካከያ እርምጃ እስከሚወስድ ለፍቃድ ሰጪ አካሉ የሰጠውን ፍቃድ ለማገድ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የጊዜ ገደብ ተሰጥቶት ማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ የእገዳ ትዕዛዝ የደረሰው ማንኛውም ባለፈቃድ እርምጃ ወስዶ ጉድለቱን ያላስተካከለ እንደሆነ ባለስልጣኑ ፈቃዱን ይሰረዛል፡፡
4. ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት የፈቃድ ሰጪ አካልን ፈቃድ ሲያግድ ከታገደው ፍቃድ ሰጪ አካል አገልግሎት የሚፈልጉ ዜጎች አገልግሎቱን ከባለሥልጣኑ ወይም ከሌላ ፍቃድ ሰጪ አካል በቀጣይነት የሚያገኙበትን አስፈላጊ ሁኔታ ማመቻቸት አለበት፡፡

22.<u>የማሰልጠኛ ተቋማትን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለማገድና ስለመሰረዝ</u>

1. ባለሥልጣኑ የማሰልጠኛ ተቋማት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 የተደነገገውን ግዴታ በአግባቡ እየተወጡ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችሉትን ዘዴዎች በመጠቀም በሚያደርገው ቁጥጥርና ክትትል ግዴታውን ሳያሟላ ባገኘው የማሰልጠኛ ተቋም ላይ በሕግ መሰረት እርምጃ ለመውሰድ ወይም እንደ አግባብነቱ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ለማገድ ወይም ለመሰረዝ ይችላል፡፡

2. ጥፋት የፈፀመው የማሰልጠኛ ተቋም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ያገኘው ከባለስልጣኑ ሳይሆን ከፍቃድ ሰጪው አካል የሆነ እንደሆነ እንደአግባብነቱ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን እንዲያግድ ወይም እንዲሰርዝ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን የሰጠውን ፍቃድ ሰጪ አካል ባለስልጣኑ ለማዘዝ ይችላል፡፡

23.<u>ክልከላ</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1. ማናቸውም ሰው ተገቢው የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሳይኖረው ማንኛውንም ባለሞተር ተሽከርካሪ በመንገድ ላይ መንዳት አይችልም፤
2. ማንኛውም የባለሞተር ተሽከርካሪ ባለቤት ወይም ባለይዞታ ተገቢው የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ያለው መሆኑን ሳያረጋግጥ ተሽከርካሪውን ሌላ ሰው እንዲነዳ መፍቀድ የለበትም፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

24.<u>ስለ ቅሬታ</u>

1. በዚህ አዋጅ መሠረት በተሰጠው ውሣኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ውሳኔው በደረሰው በሰላሳ ቀናት ውስጥ በየደረጃው ለሚመለከተው የክልልና የፌደራል ትራንስፖርት ቢሮ ወይም ባለስልጣን ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ቅሬታውን አቅርቦ በተሰጠው ምላሽ ያልረካ ማንኛውም ሰው ውሳኔው በደረሰው በሰላሳ ቀናት ውስጥ ለሚኒስቴሩ ቅሬታውን ለማቅረብ ይችላል፤ ሚኒስቴሩ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻው አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሆናል፡፡

25.<u>ቅጣት</u>

1. ይህን አዋጅ ተላልፎ የተገኘ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው ህግ ይቀጣል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የሞተር ሳይክል ወይም የባለሶስት እግር ምድብ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ያለው ማንኛውም አሽከርካሪ ከያዘው ምድብ ውጪ ሲነዳ ከተገኘ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እንደሌለው ተደርጎ ይቀጣል፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የሞተር ሳይክል ወይም የባለሶስት እግር ምድብ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሳይኖረው የሌሎች ምድቦች የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይዞ የሞተር ሳይክል ወይም ባለሶስት እግር ሲያሽከረክር ከተገኘ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እንደሌለው ተደርጎ ይቀጣል፡፡

26.**<u>የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>**

1. የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 600/2000 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም በአዋጅ ቁጥር 600/2000 መሠረት ወጥተው ሥራ ላይ የሚገኙ ደንቦች ሁሉ ከዚህ አዋጅ ደንጋጌዎች ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ በዚህ አዋጅ መሰረት እንደወጡ ተቆጥረው የፀኑ ይሆናሉ፡፡
3. ይህን አዋጅ የሚቃረን ሌላ ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

27.**<u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>**

ቀደም ሲል በነበሩ ሕጎች ተሰጥተው የነበሩ የባለሞተር ተሽከርካሪ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዶች ስለሚለወጡበት ሁኔታና ጊዜ ሚኒስቴሩ መመሪያ እስከሚያወጣ ድረስ ፀንተው ይቆያሉ፡፡

28.**<u>ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስችል ደንብ ያወጣል፡፡
2. የትራንስፖርት ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስችል መመሪያ ያወጣል፡፡

29.**<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት 7 ቀን 2010 ዓ.ም**

**ሙላቱ ተሾመ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## ሠንጠረዥ

## የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አመዳደብ

| ተ.ቁ | የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ምድብ | የብቃት ማረጋገጫ ፍቃዱ ለማሽከርከር የሚያስችለው የተሽከርካሪ አይነት |
|---|---|---|
| 1 | የሞተር ሣይክል የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ምድብ | ባለሁለት እግር ሞተር ሳይክል ተሽከርከሪ |
| 2 | ባለሶስት እግር የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ምድብ | ማንኛውንም ባለ ሶስት እግር ባለሞተር ተሽከርካሪ |
| 3 | የአውቶሞቢል የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ምድብ | እስከ 8 መቀመጫ ያለው ማንኛውም ዓይነት ተሽከርካሪ እና እስከ 10 ኩንታል የሚጭን ማንኛውም ተሽከርከሪ |
| 4 | የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገ ጫፈቃ ድምድብ | |
| | ደረጃ--- ሕዝብ I | እስከ 20 መቀመጫ ያለው ማንኛውም የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ እና በአውቶሞቢል የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ምድብ ሊያስነዳ የሚችል ማንኛውንም ተሽከርካሪ |
| | ደረጃ-- ሕዝብ II | እስከ 45 መቀመጫ ያለው ማንኛውም የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ እና በአውቶሞቢል የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ምድብ ሊያስነዳ የሚችል ማንኛውንም ተሽከርካሪ |
| | ደረጃ-- ሕዝብ III | ማንኛውም የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ እና በአውቶሞቢል የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ምድብ ሊያስነዳ የሚችል ማንኛውንም ተሽከርካሪ |
| 5 | የደረቅ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ምድብ | |

| | | |
|---|---|---|
| | ደረጃ - ደረቅ I | እስከ 35 ኩንታል የሚጭን የደረቅ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ እና በአውቶሞቢል የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ምድብ ሊያስነዳ የሚችል ማንኛውንም ተሽከርካሪ |
| | ደረጃ - ደረቅ II | ማንኛውንም ዓይነት የደረቅ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ያለ ተሳቢ፣ ከ18 ቶን የማይበልጥ ክብደትን የሚያነሱ ክሬን የተገጠመላቸው ተሽከርካሪዎች፣ እና በአውቶሞቢል የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ምድብ ሊያስነዳ የሚችል ማንኛውንም ተሽከርካሪ |
| | ደረጃ - ደረቅ III | ማንኛውንም ዓይነት የደረቅ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ተሳቢ ቢኖረውም ባይኖረውም፣ ማንኛውንም ክሬን የተገጠመለት ይሁን ያልተገጠመለት ተሽከርካሪ፣ እና በአውቶሞቢል የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ምድብ ሊያስነዳ የሚችል ማንኛውንም ተሽከርካሪ |
| 6 | የፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ምድብ | |
| | ደረጃ - ፈሳሽ I | እስከ 18, 000 ሊትር መያዝ የሚችል የፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ካለተሳቢ፣ እና በአውቶሞቢል የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ምድብ ሊያስነዳ የሚችል ማንኛውንም ተሽከርካሪ |
| | ደረጃ -- ፈሳሽ II | ማንኛውንም ዓይነት የፈሳሽ ጭነት ተሽከርካሪ ተሳቢ ቢኖረውም ባይኖረውም፣ እና በአውቶሞቢል የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ምድብ ሊያስነዳ የሚችል ማንኛውንም ተሽከርካሪ |
| 7 | የማሽነሪ ኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ምድብ | የማሽከርከር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱ የተሰጠበትን የማሽነሪ ዓይነትና ክብደት ብቻ |

## ደንብ ቁጥር 450/2011

## የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድና ተያያዥ አገልግሎቶች ክፍያን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀጽ 5 እና በአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 1074/2010 አንቀጽ 28(1) መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድና ተያያዥ አገልግሎቶች ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 450/2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ክፍያ**

   በአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 1074/2010 መሠረት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመስጠትና ተያያዥነት ላላቸው አገልግሎቶች የሚጠየቀው ክፍያ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ በተመለከተው መሠረት ይሆናል፡፡

3. **የተሻሩ ሕጎች**

   የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 262/2004 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

4. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሚያዚያ 17 ቀን 2011 ዓ.ም**

**ዶ/ር አብይ አህመድ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒሰትር**

## የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድና ተያያዥ አገልግሎቶች ክፍያ ሠንጠረዥ

| ተራ ቁ. | የአገልግሎት ዓይነት | ክፍያ ብር |
|---|---|---|
| 1. | የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሲሰጥ (ለሁሉም ምድብ) | 680 |
| 2. | የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ዕድሳት፣ ምትክ ወይም ኢንተርናሽናል መንጃ ፈቃድ (ለሁሉም ምድብ) | 620 |
| 3. | ለአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት ወይም የራሳቸውን ሠራተኞች ለሚያሰለጥኑ ሌሎች ተቋማት አዲስ ወይም ምትክ ፈቃድ ሲሰጥ | 5,175 |
| 4. | ለአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋም ወይም የራሳቸውን ሠራተኞች ለሚያሰለጥኑ ሌሎች ተቋማት አዲስ ወይም ምትክ ፈቃድ ሲታደስ | 2,570 |
| 5. | ለቴክኒሺያን አዲስ ወይም ምትክ የብቃት ማረጋገጫ ወይም ጊዜያዊ የማሠልጠን ፈቃድ ሲሰጥ | 435 |
| 6. | ለቴክኒሽያን የብቃት ማረጋገጨ ሲታደስ | 330 |

ለ/ የአየር ትራንስፖርት

## አዋጅ ቁጥር 432/1997

## የኢትዮጵያ የአቪዬሽን ሴኩሪት አዋጅ

በአየር ትራንስፖርት ደህንነት፣ አስተማማኝነትና ቅልጥፍና ላይ እየጨመረ የመጣውን የሕገ ወጥነት አደጋ መቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ፤

ኢትዮጵያ የተቀበለችዉን የቺካጎ ኮንቬንሽንና በአለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት የወጣውን የኮንቬንሽኑ አካል የሆነውን ተቀፅላ 17 ተግባራዊ ማድረግ በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀጽ 55/1/ መሠረት የሚከተለው ታዉጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ አቪዬሽን ሴኩሪቲ አዋጅ ቁጥር 432/1997" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ:-

   1. "ሕገ ወጥ ጣልቃ ገብነት" ማለት በበረራ ደህንነት ላይ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች በወጣው አዋጅ ቁጥር 31/1988 የተመለከተዉ ማናቸውም የወንጀል ድርጊት ነው፤
   2. "አይሮፕላን"[98] ማለት የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለ ሥልጣንን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 273/1994 የተሰጠው ትርጓሜ ይኖረዋል፤
   3. "ዛቻ" ማለት በፈንጂ ወይም በሌሎች አደገኛ ቁሳቁሶች የሚፈፀም በበረራ ወይም በመሬት ላይ በሚገኝ አይሮፕላን፣ በኤርፖርት አገልግሎት መስጫዎች ወይም በማንኛውም ግለሰብ ላይ ጉዳት እንደሚደርስ የሚገልጽ ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ ቢሆንም ባይሆንም በስም ወይም ያለስም የሚተላለፍ መረጃ ነው፤

[98] በ15/23 (2001) አ. 616 አንቀጽ 2(5) መሰረት "**አይሮፕላን**" ለሚለው ሀረግ የተሰጠው ትርጓሜ በዚህ አዋጅ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4. “አደገኛ ቁሳቁስ” ማለት በአይሮፕላን የመንገደኞች ክፍልም ሆነ በጭነት ማስቀመጫ የአይሮፕላኑ ክፍል ውስጥ ቢጫን የመንገደኞችን ጤንነት እንዲሁም የመንገደኞችንና የአይሮፕላኑን ደህንነት ስጋት ላይ የሚጥል ዓይነት ቁሳቁስ ነዉ፤
5. “ዓለም አቀፍ ኤርፖርት” ማለት በዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት አባል አገራት ውስጥ በዓለም አቀፍ በረራዎች በመነሻነትና በመድረሻነት የሚያገለግልና በውስጡ የጉምሩክ፣ የኢሚግሬሽን፣ የጤና ጥበቃ፣ የእንስሳትና የእጽዋት ኳራንቲንና ሌሎች የቁጥጥር ተግባራት የሚካሄድበት ኤርፖርት ነው፤
6. “ኦፕሬተር” ማለት በአይሮፕላን አገልግሎት በመስጠት ወይም በአይሮፕላን አገልግሎት የሚሰጡትን በመርዳት ተግባር ላይ የተሰማራ ማንኛውም ግለሰብ፣ ድርጅት ወይም ኢንተርፕራይዝ ነው፤
7. “ፍትሻ” ማለት ሕገ ወጥ ጣልቃገብነት ለመፈጸም የሚያገለግሉ መሣሪያዎችን፣ ፈንጅዎችን ወይም ሌሎች ቁሳቁሶችን ለይቶ ለማውጣትና ለማስቀረት በመፈተሻ መሣሪያዎች ወይም በእጅ የሚደረግ የሴኩሪቲ ቁጥጥር ነው፤
8. “ሴኩሪቲ” ማለት የቁጥጥር ስልቶችን፣ የሰዉ ኃይልንና ቁሳቁሶችን በማቀናጀት የሲቪል አቪዬሽን ሊደርስበት ከሚችል ማንኛውም ዓይነት ሕገ ወጥ ጣልቃገብነት የመከላከል ስራ ነው፤
9. “የሴኩሪቲ መፈተሻ መሣሪያ” ማለት የሲቪል አቪዬሽን እንዲሁም ፋሲሊቲዎቹን በተናጠል ወይም በተቀናጀ መልኩ ከሕገ ወጥ ጣልቃ ገብነት ለመከላከል የሚያገለግል የመፈተሻ መሣሪያ ነው፤
10. “የተከለከሉ ሥፍራዎች” ማለት ለሲቪል አቪዬሽን ሴኩሪቲ አመቺ አሠራር ሲባል መግቢያዎቻቸው በጥብቅ የተከለከሉ ወይም የሚጠበቁ በኤርፖርት የሚገኙ ሕንጻዎችን ፋሲሊቲዎች ናቸው፤
11. “የፀዳ ሥፍራ” ማለት በመንገደኞች የመፈተሻ ቦታና በአይሮፕላኑ መካከል የሚገኝና መግቢያው ጥብቅ ቁጥጥር የሚደረግበት ሥፍራ ነው፤
12. “የድንገተኛ ጊዜ እቅድ” ማለት በሕገወጥ ጣልቃ ገብነት ወቅት የመንገደኞችን፤ የበረራ ሠራተኞችን፣ ከአይሮፕላን ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸዉ ሠራተኞችንና የኤርፖርቱ ማህበረሰብን ደህንነት ለማረጋገጥ የተለያዩ ድርጅቶችን ኃላፊነትና የማወስዷቸውን እርምጃዎች የሚገልጽ እቅድ ነው፤

13.“ሚስጥራዊ ሰነዶች /ቁሳቁሶች” ማለት በሚመለከታቸዉ የመንግስት አካላት ሚስጥር ተብለዉ የታወቁ ሰነዶች ወይም ቁሳቁሶች ናቸዉ፡፡

**ክፍል ሁለት**

**የኃላፊነት ድልድል**

3. **የደህንነት ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን**[99]

1. የደህንነት ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን በተቋቋመበት ሕግ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የአቪዬሽን ሴኩሪቲ ሥራዎችን በበላይነት የማስፈፀም ሥልጣንና ተግባር በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የደህንነት፣ የኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን፡-
   ሀ) ለሕገወጥ ጣልቃ ገብነት አስፈላጊውን ምላሽ ይሰጣል፣ የኃይል እርምጃን ጨምሮ በበላይነት ይመራል፣ የማሳወቅ ተግባርን ይፈጽማል፤
   ለ) የሕገወጥ ጣልቃገብነትን ለመከላከል የፍተሻ፣ የክትትል እና የእጀባ ተግባራትን ያከናዉናል፤
   ሐ) በአገራዊና በኤርፖርት ደረጃ የድንገተኛ ጊዜ እቅድ ያዘጋጃል፤ ተግባራዊም ያደርጋል፤
   መ) በአይሮፕላንና በአይሮፕላን ማረፊያ ጣቢያዎች ላይ የሚሰነዘሩትን አደጋ የመጣል ዛቻዎች ወይም እንቅስቃሴዎች እየተከታተለ ይገመግማል፤ መረጃዎችን እንደአስፈላጊነቱ ለሚመለከታቸው አካሎችና አገሮች በማሰራጨት በሚወስዱትም እርምጃዎቸች ላይ የቅርብ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡
   ሠ) የኤርፖርቶች፣ የአይሮፕላኖች፣ የኤርፖርት ፋሲሊቲዎች፣ የበረራ መረጃ መሣሪያዎችና የተከለከሉ ሥፍራዎች ጥበቃና የሴኩሪቲ ቁጥጥርን በተመለከተ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፣
   ረ) በዚህ አዋጅ መሠረት ኃላፊነት የተሰጣቸዉ ወይም የሚመለከታቸው የተለያዩ መሥሪያ ቤቶችን ወይም ድርጅቶችን እንቅስቃሴ ለማስተባበር የሚያስችል

[99] በዚህ አንቀጽ ውስጥ የደህንነት፣የኢሚግሬሽንና የስደተኞች ጉዳይ ባለስልጣን በሚል የተገለጸው ባለስልጣኑ የተቋቋመበት አዋጅቁጥር 6/1988 በአዋጅቁጥር 19/55 (2005) አ. 804 አንቀጽ 29(1) ተሽሮ መስሪያ ቤቱ የብሔራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት ሆኗል፡፡ እንዲሁም በዚህ አዋጅ ውስጥ የደህንነት፣ የኢሚግሬሽንና የስደተኞች ጉዳይ ባለስልጣን ተብሎ የተገለጸው ሁሉ ብሔራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት ተብሎ ይነበባል፡፡

ስልት ይቀይሳል፣

ሰ) የሚመለከታቸው አካላት በዚህ አዋጅ ተለይቶ የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት መፈጸማቸውን ይከታተላል፤

ሸ) ሕገወጥ ጣልቃ ገብነት በሚፈጸምበት ወቅት ለመገናኛ ብዙኀን መግለጫ ይሰጣል፣ ከተለያዩ የዜና አገልግሎቶች ለሚቀርቡ ከአቪዬሽን ሴኩሪቲ ጋር የተዛመዱ ጥያቄዎች ምላሽና መግለጫ ይሰጣል፤

ቀ) ከዚህ አዋጅ ጋር የተጣጣመ የኤርፖርት አቪዬሽን ሴኩሪቲ መመሪያ ያወጣል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣

በ) የኤርፖርት አቪዬሽን ሴኩሪቲ መመሪያን በኃላፊነት የሚያስፈጽም የበላይ ኃላፊ ይሾማል፣

ተ) የአንድ አገር አየር መንገድ ኦፕሬተር ልዩ የሴኩሪቲ ጥንቃቄ ሲጠይቅ በጥያቄዉ መሠረት አስፈላጊውን ጥንቃቄና ድጋፍ ያደርግለታል፤

ቸ) በኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ላይ ሕገወጥ ጣልቃ ገብነቶች ሲፈጸሙ ጥቃቶቹን ወይም ድርጊቶቹን አስመልክቶ የዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ስለ ሪፖርት አቀራረብ ባወጣው ሥርዓት መሠረት ለድርጅቱ በጽሑፍ ሪፖርት ያቀርባል፤

ኀ) በየአገሮቹ ከሚገኙት የሲቪል አቪዬሽን ሴኩሪቲ አግባብ ያላቸው ባለሥልጣኖች ጋር ፈጣን እና አስተማማኝ የግንኙነት ሥርዓት ይዘረጋል፣

ነ) በዓለም አቀፍ ኤርፖርቶች አዳዲስ ሕንፃዎች፣ መንገዶች ወይም ፋሲሊቲዎች ሲገነቡ ወይም የነበሩት ሲለወጡ ዲዛይኑ የአቪዬሽን ሴኩሪቲ እርምጃዎችን በበቂ ሁኔታ ለማስፈጸም በሚያስችል መልኩ መሆኑን አረጋግጦ ያጸድቃል፤

ኘ) እንደአስፈላጊነቱ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመሆን የሲቪል አቪዬሽን ሴኩሪቲን የሚመለከት ብሔራዊ ፖሊሲና ሕግ ያመነጫል፣ የፀደቀዉን ፖሊሲና ህግ ለሚመለከታቸዉ አካላት ያሳዉቃል፤

አ) የዚህን አዋጅ ውጤታማነት በቀጣይነት ለማረጋገጥ እንዲቻል በየወቅቱ መረጃዎችን ይመዝናል፣ የስኬታማነት መስፈርት በማዘጋጀትና በመገምገም ተገቢዉን የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤ ያስወስዳል፤

ከ) በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ ኤርፖርቶች ለሚሰጡት የኤርፖርት ሴኩሪቲ አገልግሎቶች አስፈላጊ ድጋፍ ሰጪ መሣሪያዎችን እንዲሁም የስልጠና ፋሲሊቲዎችን ያሟላል፤

ኸ) የአየር መንገድ ኦፕሬተሮችን የሴኩሪቲ መመሪያ ከዚህ አዋጅ አንፃር ይገመግማል፤ ያጸድቃል፤

ወ) የኢትዮጵያ አቪዬሽን ሴኩሪቲ የሥልጠና ፕሮግራምና የሥልጠና መመዘኛ የአለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ያወጣዉን ስታንዳርድ ጠብቆ ያዘጋጃል፣ ሥልጠና ይሰጣል፣ ተመሳሳይ ስልጠና የሚሰጡ ድርጅቶችን የሥልጠና ፕሮግራም ይዘት ገምግሞ ያጸድቃል፣ ከሌሎች አገሮችና ድርጅቶች ጋር የሥልጠና መረጃ ይለዋወጣል፣ ይተባበራል፤

ዐ) የሴኩሪቲ መፈተሻ መሣሪያዎች በሚገዙበት ወቅት በተለይ የመንገደኛ ሻንጣዎች እና የሰዉነት መፈተሻ መሣሪያዎች በአገሪቱ የወጣዉን ደረጃ ያሟሉ መሆናቸዉን ያረጋግጣል፡፡

4. <u>**የአትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን በለሥልጣን**</u>

በዚህ አዋጅ መሠረት የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፦

1. በዚህ አዋጅ መሠረት ኃላፊነት የተሰጣቸው አካላት ኃላፊነታቸውን መወጣታቸውን እየተከታተለ በአለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት በተቀመጠው ደረጃ መሠረት መሠራቱን ኦዲት ያደርጋል የአፈፃፀም ሪፖርቱን ለደህንነት፣ ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን፣ ለኢትዮጵያ የአቪዬሽን ሴኩሪቲ ኮሚቴና ለሌሎች ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፣ በግኝቶቹ መሠረት የማስተካከያ እርምጃዎች በወቅቱ መወሰዳቸውን ያረጋግጣል፤
2. በኢትዮጵያ ውስጥ የተመዘገቡ የአየር መንገድ ኦፕሬተሮችንና የዓለም አቀፍ ኤርፖርቶችን የሴኩሪቲ መመሪያዎች ከዚህ አዋጅ ጋር በተጣጣመ መልኩ መቀረፃቸውን በመገምገም ለደህንነት፣ ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን አስተያየት ይሰጣል፤
3. የኢትዮጵያ አቪዬሽን ሴኩሪቲ የሥልጠና ፕሮግራም ይዘትንና የማሰልጠኛ ተቋማት የዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ስለሥልጠና ያወጣቸውን ደረጃዎችና ተመራጭ ሃሳቦችን የጠበቁ ስለመሆናቸው ይቆጣጠራል፤

4. በየኤርፖርቶቹ በሚቋቋሙት የኤርፖርት ሴኩሪቲ ኮሚቴዎች ውስጥ በአባልነት ይሳተፋል፤
5. ሕገወጥ ጣልቃ ገብነት የተፈጸመበት አይሮፕላን ባጋጠመ ጊዜ የማረፊያ ፈቃድና የኤር ናቪጌሽን አገልግሎት ይሰጣል፡፡

5. <u>**የፌዴራል ፖለስ ኮሚሽን**</u>

በሌሎች ሕጐች የተሰጠው ሥልጠንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን፡-

1. የሲቪል አቪዬሽን ለበረራ ደህንነት የሚያገለግሉ ተቋሞችና መሣሪያዎች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ይመረምራል፤
2. በተለያዩ የጥበቃ ዘዴዎች የኤርፖርቶችን ክልል፣ ተርሚናሎችን፣ ለበረራ ደህንነት የሚያገለግሉ ተቋሞችንና መሣሪያዎችን ይጠብቃ፤
3. ለበረራ ደህንነት አገልግሎት የሚውሉ ተቋሞችና መሣሪያዎች ላይ ሊቃጣ የሚችል ዛቻን ለመከላከል የክትትል ተግባራት ያከናውናል፣
4. የበኩሉን የድንገተኛ ጊዜ እቅድ በማዘጋጀት በደህንነት፣ የኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን ያስጸድቃል፤ ተግባራዊም ያደርጋል፤

6. <u>**የአገር መከላከያ ሚኒስቴር**</u>

በሌሎች ሕጐች የተሰጠዉ ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በድንገተኛ ጊዜ ዕቅድ መሠረት ይሳተፋል፣
2. የመከላከያ ኃይል የሲቪል ኤርፖርቶች የጋራ ተጠቃሚ ሲሆን የመተላለፊያ በሮችን በመቆጣጠርና በሌሎች የሴኩሪቲ ተግባሮች ከፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ጋር ይሳተፋል፡፡

7. <u>**የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት**</u>

በተቋቋመበት ሕግ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት፡-

1. በኤርፖርቶች አቪዬሽን ሴኩሪቲ መመሪያ ዝግጅት እና ተግባራዊነት ላይ ይሳተፋል፤
2. በኤርፖርት አቪዬሽን ሴኩሪቲ ኮሚቴ ውስጥ በአባልነት ይሳተፉ፣
3. የአዲስ ኤርፖርት ግንባታ ወይንም የነበረውን ለማሻሻል የግንባታ ሥራ ሲከናወን ዲዛይኑ የአቪዬሽን ሴኩሪቲን ፍላጐት ያገናዘበ ወይንም ያሟላ መሆኑን አረጋግጦ

ለደህንነት፣ ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን አቅርቦ ያስጸድቃል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤

4. የደህንነት፣ ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የኤርፖርት የድንገተኛ ጊዜ እቅድ ያዘጋጃል፤
5. የኤርፖርት ፋሲሊቴሽን መመሪያና ልዩ ልዩ የአሰራር ሥርዓቶች በሚያዘጋጅበትና ተግባራዊ በሚያደርግበት ወቅት ይህን አዋጅ መከተሉን ያረጋግጣል፡፡

8. **ኦፐሬተር**

ማናቸውም ኦፐሬተር ይህን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡትን መመሪያዎች ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

9. **የኢትዮጵያ የሲቪል አቪዬሽን ሴኩሪቲ ኮሚቴ**

1. የኢትዮጵያ የሲቪል አቪዬሽን ሴኩሪቲ ኮሚቴ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡
2. ኮሚቴው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

   ሀ) የደህንነት፣ ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን .................... ሰብሳቢ

   ለ) የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ................................................................ ፀሐፊ

   ሐ) የገቢዎች ሚኒስቴር[100] .................. ……………………………………………አባል

   መ) የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ............ ……………………………………………አባል

   ሠ) የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን............................................. አባል

   ረ) የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት....................................................... አባል

   ሰ) የኢትዮጵያ አየር መንገድ ኢንተርፕራይዝ[101]..........................................አባል

3. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ኮሚቴው ተጨማሪ አባላትን ከሚመለከታቸዉ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም ባለሙያዎችን በጊዜያዊነት ወይም በቋሚነት እንደአስፈላጊነቱ ሊያሳትፍ ይችላል፡፡
4. የኮሚቴ አባል የሆነ እያንዳንዱ መሥሪያ ቤት ወይም ድርጅት በበላይ ኃላፊዉ ወይም በምክትሉ ይወከላል፡፡
5. የኢትዮጵያ ሲቪል የአቪዬሽን ሴኩሪቲ ኮሚቴ፡-

   ሀ) በሲቪል አቪዬሽንና በአገልግሎት መስጫዎቹ ላይ ሊኖሩ የሚችሉ ስጋቶችን

[100] በ14/44 (2000) አ. 587 አንቀጽ 3(1) መሰረት የገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን ተብሎ ይነበባል፡፡
[101] 25/70 (2011) ደ.452 አንቀጽ 2(2) የኢትዮጲያ አየር መንገድ ግሩፕ በሚል ስያሜው ተሸሽሏል፡፡

ለመከላከል መወሰድ የሚገባውን የአቪዬሽን ሴኩሪቲ እርምጃ አስመልክቶ የደህንነት፣ ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣንን ያማክራል፣

ለ) ታምኖባቸዉ ተግባራዊ የሆኑትን ዕርምጃዎች አፈፃፀምና በየወቅቱ እየተለዋወጡ የሚመጡ አዳዲስ ስጋቶችን ይገመግማል፣ በአቪዬሽን ሴኩሪቲ መስክ የታዩትን የቴክኖሎጂ ለዉጦች የተሻሻሉትን የቴክኖሎጂ ግኝቶችንና ሌሎችንም ባጠቃላይ አየገመገመ ድክመት በታየባቸዉ ጉዳዮች ላይ የማሻሻያ የዉሣኔ ሃሳብ ያቀርባል፤

ሐ) አቪዬሽን ሴኩሪቲን በሚመለከት ኃላፊነት የተጣለባቸዉ ድርጅቶችና ወኪሎቻቸዉ በየጊዜዉ የሚከሰቱትን ስጋቶች ለመቋቋም በመካከላቸው ቅንጅታዊ አሠራር መኖሩን ያረጋግጣል፤

መ) የዚህ አዋጅ የማሻሻያ ሃሳቦችን ይመረምራል፤ እንዲጸድቅም የማሻሻያ ዉሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፣

ሠ) በኤርፖርት የሲቪል አቪዬሽን ሴኩሪቲ ኮሚቴ የሚቀረቡትን የማሻሻያ ሐሳቦች ይመረምራል፣ ለደህንነት፣ ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለስልጣን የውሳኔ ሐሳብ ያቀርባል፡፡

6. ኮሚቴዉ የራሱን የአሠራር መመሪያ ያወጣል፡፡

10. <u>የኤርፖርት አቪዬሽን ሴኩሪቲ ኮሚቴ</u>

1. የኤርፖርት አቪዬሽን ሴኩሪቲ ኮሚቴ የዓለም አቀፍ አገልግሎት በሚሰጡ ኤርፖርቶች እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ኤርፖርቶችም ይቋቋማል፡፡
2. የኤርፖርት አቪዬሽን ሴኩሪቲ ኮሚቴ፡-

ሀ) የአቪዬሽን ሴኩሪቲ እንዲጠናከር የደህንነት፣ ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣንን ያማክራል፤

ለ) በኤርፖርት ላይ የሚከናወኑትን የሴኩሪቲ እርምጃዎችና የአሰራር ሥርዓቶችን በተቀናጀ መልኩ ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>በሰዎችና ወደ አይሮፕላን በሚጫኑ እቃዎች ላይ የማድረግ ቁጥጥር</u>

11. <u>ስለፍተሻ አስፈላጊነት</u>

1. ማንኛውም መንገደኛም ሆነ የመንገደኛ ዕቃ ወደ አይሮፕላን ወይም በፍተሻ ወደ ጸዳዉ የመንገደኞች መቆያ ስፍራ ከመግባቱ በፊት መፈተሽ አለበት፡፡

2. የበረራ ሠራተኞች፣ የኤርፖርትና የአቪዬሽን ሠራተኞችን ሌሎች ሰዎች ከመፈተሻ ቦታው ወደ ጸዳው ሥፍራ ከማለፋቸው በፊት እንደመንገደኞች ሁሉ ይፈተሻሉ፡፡ ፍተሻዉም የእጅ ሻንጣን ያጠቃልላል፡፡
3. አይሮፕላን፣ አይሮፕላን ላይ የሚጫን ዕቃ፣ የፈጣን መልዕክት ጥቅልና ፖስታ የሴኩሪቲ ቁጥጥር ወይም ተገቢዉ ፍተሻ ይደረግበታል፡፡

12.**ልዩ የፍተሻ ሥርዓት**

1. የዲፕሎማቶች፣ የዲፕሎማቲክ ፖውችና የዲፕሎማቶች ሻንጣዎች አፈታተሸን በሚመለከት ኢትዮጵያ የፈረመቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተግባራዊ ለማድረግ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በሚወጡ መመሪያዎች መሠረት ይፈጸማል፡፡
2. ሚስጥርነታቸው እንደተጠበቀ በመንግሥት የሚጓጓዙ ዕቃዎች የሚፈተሹት ከማንኛውም መሣሪያዎችና አደገኛ ቁሳቁሶች ነፃ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን አጠራጣሪ ወይም ምንነቱ በትክክል ያልታወቀ ነገር ሚስጥራዊነት ባላቸው ቁሳቁሶች ውስጥ ቢገኝ በማንኛውም ኦፕሬተር መጓጓዝ አይኖርባቸዉም፡፡

13.**ከፍተሻ ነፃ ስለመሆን**

1. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስፈላጊውን የተለየ ሁኔታ ለማመቻቸት እንዲቻል ከፍተሻ ነፃ የሆኑ ሰዎች የጉዞ መረጃ ለደህንነት፣ ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለስልጣንና ለአየር መንገድ ኦፕሬተሮች አስቀድሞ ይገልፃል፡፡
2. መንግሥት መፈተሸ አይገባቸውም ብሎ አስቀድሞ የወሰነላቸዉ ግለሰቦች ከፍተሻ ነፃ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

14.**በግል ፍተሻ ስለሚደረግበት ሁኔታ**

ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው እቃዎች የያዙ፣ የልብ ምት ማስተካከያ መሣሪያ የተገጠመላቸው፣ የአካል ጉዳተኛ የሆኑ ወይም ሌሎች ፍተሻ የማያስፈልጋቸዉ መንገደኞች በግል ከሌሎች መንገደኞች እይታ በተከለለ ሥፍራ ሊፈተሹ ይችላሉ፡፡

15.**የተፈቀደ የጦር መሳሪያ ስለማጓጓዝ**

የህግ አስከባሪ ሠራተኛ ወይም ሌላ ሕጋዊ ፍቃድ ያለው ሰው በአይሮፕላኑ የመንገደኞች ክፍል ወይም ሻንጣ ውስጥ የጦር መሣሪያ ይዞ ሊጓዝ ይችላል፡፡

16.**በጥበቃ ወይም በአስተዳደራዊ ቁጥጥር ሥር የዋለ ሰው ስለማጓጓዝ**

1. በጥበቃ ወይም በአስተዳደራዊ ቁጥጥር ሥር የዋለ ሰው ወይም አእምሮዉ የታወከ መንገደኛ ስለሚጓጓዝበት ወይም ወደ መጣበት አገር ስለሚመለስበት ሁኔታ አጓጓዡ ወይም የሚመለከተው አገር ቅድሚያ እንዲያዉቀዉ ይደረጋል፡፡
2. የአየር መንገድ ኦፕሬተሮች በሕግ ጥላ ሥር ሆኖ የሚጓዝ መንገደኛን ደህንነት ለማረጋገጥ ሲባል ያለዉን ሕግ መሠረት አድርገዉ የአጓጓዝ ሥርዓቱን በየራሳቸዉ የሴኩሪቲ መመሪያ ዉስጥ በዝርዝር ማስቀመጥ አለባቸው፡፡

**ክፍል አራት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

17.**የአቪዬሽን ሴኩሪቲ ወጪ አሸፋፈን**

1. በዚህ አዋጅ የአቪዬሽን ሴኩሪቲን ለማስፈጸም ሥልጣን የተሰጠዉ አካል ወጪዎችን በሚመለከት ከመደበኛ ከደመወዝና ሌሎች የሥራ ማስኬጃ ወጪዎች በስተቀር የፋሲሊቲዎች ግዢ፣ ጥገናና ተያያዥ ወጪዎች እንዲሁም ተፈላጊ የግንባታ ሥራዎች በሙሉ ለሚያስተዳድራቸዉ ኤርፖርቶች በኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት ይሸፈናል፡፡
2. ድርጅቱ ያወጣውን ወጪ የዓለም ዐቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ተመራጭ ሃሳቦችን ተከትሎ ከተጠቃሚዎች ሊተካ ይችላል፡፡

18.**መመሪያ ስለማውጣት**

ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የደህንነት፣ ኢሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን መመሪያ ለማውጣት ይችላል፡፡

19.**ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ ሕጎች፣ መመሪያዎችና የአሠራር ልምዶች በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

20.**ቅጣት**

ይህን አዋጅ ተላልፎ የተገኘ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ይቀጣል፡፡

21.**አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከጥር 25 ቀን 19/1997 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥር 25 ቀን 1997 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 616/2001

## የሲቪል አቪዬሽን አዋጅ

የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣንን የቁጥጥር፣ የአስተዳደር፣ የቴክኒክና የአመራር ብቃት በማጠናከርና የተሻለ የሲቪል አቪዬሽን ቁጥጥር እንዲኖር በማድረግ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ከማንኛውም ስጋት ነፃ የሆነ፣ መደበኛ፣ ብቃት ያለውና ኢኮኖሚያዊ የሆነ የሲቪል አቪዬሽን ሥርዓትን የማስፈን ፍላጐትን ማሟላት እንዲቻል የአቪዬሽን ሕጐችን ማዋሃድና ዘመናዊና ከዓለም አቀፍ ደረጃዎች ጋር የተጣጣመ እንዲሆኑ ማድረግ በማስፈለጉ፤

የአቪዬሽን ደህንነትና ቁጥጥር የዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት በሚያወጣቸዉ ደረጃዎችና ተመራጭ ልምዶች መሠረት መተግበር ስላለበትና የሲቪል አቪዬሽን የቁጥጥር ተግባርን ማሳደግና የማያቋርጥ እድገቱን መደገፍ እንዲሁም ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች ተግባሮችን ማከናወን በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55/1/ መሠረት የሚከተለው ታዉጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የሲቪል አቪዬሽን አዋጅ ቁጥር 616/2001" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤[102]

   1. "አደጋ" ማለት ማንኛውም ሰው በአውሮፕላን ለመሄድ በማሰብ በአውሮፕላን ከተሳፈረበት ጊዜ ጀምሮ ሁሉም ሰው እስከሚወርድበት ድረስ ባለው ጊዜ ከአውሮፕላኑ እንቅስቃሴ ጋር ግንኙነት ያለው ሆኖ ወይም ሰው አልባ አውሮፕላን ከሆነ አውሮፕላኑ በረራን በማሰብ ለመንቀሳቀስ ከተዘጋጀበት ጊዜ ጀምሮ በበረራው መጨረሻ አውሮፕላኑ እስከሚያርፍበት እና ቀዳሚው የማንቀሳቀሻ ሲስተም እስከሚጠፋበት ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ:-

[102] በ26/27(2012) አ.1179 አንቀፅ 2(1) መሰረት ተሻሻለ፡፡

ሀ) በተፈጥሮ ምክንያት ወይም በራሱ ወይም በሌሎች ሰዎች ድርጊት ምክንያት ወይም ለመንገደኞች ወይም ለአውሮፕላን ሠራተኞች ከሚገባ ቦታ ውጭ በድብቅ ሲጓዝ ከሚደርስበት ጉዳት በስተቀር፤

1. በአውሮፕላን ውስጥ በመሆኑ፤
2. ከአውሮፕላኑ አካል ከተገነጠሉ አካላት ጋር ወይም ከአውሮፕላኑ በቀጥታ በመነካካቱ፤
3. አውሮፕላኑ በሚነሳበትና በሚያርፍበት ወቅት ወይም በመሬት ላይ እንቅስቃሴ በሚያደርግበት ወቅት ከሞተር ክፍሉ በሚያወጣው ከፍተኛ ፍጥነትና ሀይል ያለው የተቃጠለ አየር በቀጥታ በመጋለጡ፣ የሚያጋጥመው ከባድ የአካል ጉዳት ወይም ሞት፡፡

ለ) አውሮፕላኑ ጉዳት ደረሰበት ወይም አካላዊ ጥንካሬውን አጣ የሚባለው:-

1. የአውሮፕላኑ አካላዊ ጥንካሬ፣ ብቃት ወይም የበረራ ባህሪያቱን በከፍተኛ ደረጃ ሲጎዳ፡፡
2. አውሮፕላኑ ሞተር መጥፋት፣ መጎዳት፣ ከፍተኛ ጥገና ወይም መተካት ሲያስፈልገው ሲሆን ነገር ግን ጉዳቱ በአንድ ሞተር ላይ ብቻ ሲሆን እና በሽፋኑ ወይም በተጓዳኝ ደጋፊ፣ አጋዥ አካላት፣ በውልብልቢቶች፣ ክንፎቹ ጫፎች፣ በአንቴናዎች፣ ፕሮብስ፣ ቬንስ፣ ጎማዎች፣ ፍሬኖች፣ የጎማ መያዣ አቃፊዎች፣ የአውሮፕላን ፍጥነት ለመቀነስ አጋዥ መሣሪያዎች፣ ፓኔሎች፣ ላንዲንግ ጊር ዶርስ፣ የፊት መስታወት፣ የአውሮፕላኑ ሽፋን ላይ የሚታዩ (ትንንሽ መሰርጎዶች ወይም የተበሱ ቀዳዳዎች) ወይም በሄሊኮፕተር ከሆነ በሽክርክሪቱ ላይ የሚደርስ መጠነኛ ጉዳት፣ በጭራው ላይ በሚገኝ ሽክርክሪት ላይ የሚደርስ መጠነኛ ጉዳት፣ በሄሊኮፕተር ላይ ላንዲንግ ጊር እና ከጠጣር በረዶ ወይም ከወፍ ግጭት በአውሮፕላኑ ላይ የሚፈጠሩ ቀዳዳዎች ውጭ አውሮፕላኑ ላይ ከፍተኛ ጥገና ወይም የተጎዳውን አካል መተካት ሲያስፈልገው፡፡

ሐ) የአውሮፕላኑ መጥፋት ወይም ጨርሶ የማይደረስበት መሆን ነው።

2. “ኤርያል ሥራ” ማለት አንድን አውሮፕላን እንደ እርሻ፣ ግንባታ፣ ፎቶ ማንሳት፣ ቅየሳ፣ ቅኝት፣ ፈልጎ ማዳን፣ የኤርያል ማስታወቂያና በመሳሰሉ ልዩ አገልግሎቶች ላይ የሚያሰማራ የአውሮፕላን ኦፕሬሽን ነው፤
3. “አውሮፕላን ማረፊያ” ማለት በመሬት ወይም በውሃ ላይ የተከለለ ቦታ ሆኖ በውስጡ ማንኛውንም ህንጻዎችን፣ የተዘረጉ መሰረተ ልማቶችን እና መሳሪያዎችን ጨምሮ በሙሉ ወይም በከፊል ለአውሮፕላን ማረፊያ፣ እና መንቀሳቀሻ የሚያገለግል ቦታ ነው፡፡[103]
4. “የአየር አጓጓዥ” ማለት በመደበኛ ወይም በቻርተር በቀጥታ ወይም ቀጥታ ባልሆነ ኪራይ ወይም በሌሎች ስምምነቶች በአውሮፕላን የትራንስፖርት አገልግሎቶችን በክፍያ ወይም በኪራይ ለመስጠት የተሰማራ የአየር ኦፕሬተር ነው፤
5. “አውሮፕላን” ማለት አየር ከመሬት ገጽታ ጋር ከሚያደርገው መስተጋብር ውጭ ከገዛ አካሉ ጋር በሚያደርገው ግጭት የተነሳ በከባቢ አየር ዉስጥ ድጋፍ የሚያገኝ ማንኛውም በራሪ መሣሪያ ነው፡፡[104]
6. “አውሮፕላን ሞተር” ማለት ለአውሮፕላን ማንቀሳቀሻ በጥቅም ላይ የዋለ ወይም ሊውል የታሰበ ሆኖ ለሞተሩ ሥራና ቁጥጥር የሚያስፈልጉ ማናቸውም የዚሁ ክፍልና አካል የሚያጠቃልል ሲሆን ውልብልቢትን አይጨምርም፤[105]
7. “የአውሮፕላን ኦፕሬተር” ማለት በአውሮፕላን ኦፕሬሽን የተሰማራ ማንኛውም ሰው ነው፤
8. “የአየር ናቪጌሽን” ማለት አውሮፕላንን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ መምራት ሲሆን፣ አውሮፕኑን በአየር ላይ ባለ ጊዜ ትክክለኛ ቦታውን የማወቅ ተግባርን ይጨምራል፤
9. “የአየር ናቪጌሽን መገልገያ” ማለት አውሮፕላን ሲበር፣ ሲያርፍ ወይም ሲነሳ ለመቆጣጠር የሚያገለግል ማንኛውም ቦታ፣ የብርሃን መሣሪያ፣ የአየር ሁኔታ መረጃ ማሰራጫ፣ የሲግናል፣ የአቅጣጫ መፈለጊያ ወይም የሬዲዮ መገናኛ መሣሪያ ወይም ማንኛውም ሌላ መገልገያ ነው፤
10. “የበረራ መስመር” ማለት በባለሥልጣኑ ለአየር ናቪጌሽን የተመደበ የአየር ክልል ነው፤

[103] በበ26/27(2012) አ.1179 አንቀፅ 2(2) መሰረት ተሻሻለ፡፡
[104] በበ26/27(2012) አ.1179 አንቀፅ 2(3) መሰረት ተሻሻለ፡፡
[105] በበ26/27(2012) አ.1179 አንቀፅ 2(4) መሰረት ተሻሻለ፡፡

11.“የአየር አገልግሎት” ማለት በመደበኛነትም ሆነ አልፎ አልፎ የሚሰጥ የአየር ትራንስፖርት ወይም የኤርያል ሥራ አገልግሎት ነው፤

12.“የአየር ትራፊክ ቁጥጥር አገልግሎት” ማለት አውሮፕላን ከአውሮፕላን ወይም ከአደናቃፊ ነገር ጋር ግጭት እንዳይደርስበትና የአየር ትራፊክ እንቅስቃሴ በሚገባ እንዲካሄድና እንዲጠበቅ የማድረግ አገልግሎት ነው፤

13.“ለበረራ ብቁ መሆን” ማለት በባለሥልጣኑ በተወሰነው መሠረት አንድ አውሮፕላን ከአስፈላጊ አካላዊ ክፍሎቹና ተገጣሚ ዕቃዎቹ ጋር ተግባሩን በበቂ ሁኔታ ማከናወን መቻል ነው፤

14.“አፕሊያንስ” ማለት በበረራ ላይ ላለ አውሮፕላን ናቪጌሽን፣ ኦፕሬሽን ወይም ቁጥጥር የሚያገለግሉ ወይም ለማገልገል የታቀዱ መሳሪያዎች፣ ዕቃዎች፣ መገልገያዎች፣ የአዉሮፕላን ክፍሎች ወይም ተገጣጣሚ አካላት ሲሆኑ፣ ፓራሹቶችንና የአውሮፕላኑ፣ የሞተሮቹ ወይም የውልብልቢቶቹ ክፍሎች ያልሆኑ በበረራ ወቅት ከአውሮፕላኑ ጋር የተገጠሙ ወይም የተያያዙ የመገናኛ መሣሪያዎችንና ሌሎች ሥርዓቶችን ይጨምራል፤

15.“የተቀነሰ ዝቅተኛ የከፍታ መለያ የአየር ክልል” ማለት በቀጠናዉ የአየር ናቪጌሽን ስምምነት መሰረት በአውሮፕላኖች መካከል የ300 ሜትር ወይም 1000 ጫማ መለያ ተግባራዊ የሆነበት የአየር ክልል ነው፡፡

16.“የአቪዬሽን ባለሙያ” ማለት የሲቪል አቪዬሽንን ኦፕሬሽን ወይም የቴክኒክ ተግባር የሚያከናዉን ማንኛውም ግለሰብ ሲሆን፣

ሀ) በአዛዥ ፓይለትነት፣ በፓይለትነት፣ በመካኒክነት ወይም በበረራ ሠራተኞች አባልነት የሚሠራ ወይም አዉሮፕላኑን በበረራ ላይ እያለ የሚመራ ማንኛውንም ሰው፤

ለ) በአውሮፕላን፣ በአውሮፕላን ሞተሮች ወይም ዉልብልቢቶች ወይም አፕሊያንሶች የቴክኒክ ቁጥጥር ወይም ጥገና ተግባር ላይ በኃላፊነት የሚሰራ ማንኛውንም ሰው፣ ወይም

ሐ) በበረራ ተቆጣጣሪነት፣ የአየር ትራፊክ ተቆጣጣሪ ወይም በአውሮፕላን ዲስፓቸር መኮንንነት የሚሰራ ማንኛውንም ሰው፣ ይጨምራል፤

17.“ሲቪል አውሮፕላን” ማለት ማንኛውም የመንግስት ያልሆነ ሌላ አውሮፕላን ነው፤

18.“የንግድ በረራ” ወይም “የንግድ አየር ትራንስፖርት” ማለት መንገደኞችን፣ ጭነትን ወይም ፖስታን በክፍያ ወይም በኪራይ የሚያመላልስ የአውሮፕላን ኦፕሬሽን ነው፤

19.“የበረራ አባል” ማለት በበረራ ላይ ባለ አውሮፕላን ውስጥ የተወሰኑ ተግባረችን እንዲያከናውን በኦፕሬተሩ የተመደበ ሰው ነው፤

20.“አደገኛ ክልል” ማለት በአንድ በተወሰነ የአየር ክልልና የተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለአውሮፕላን በረራ አደገኛ የሆኑ እንቅስቃሴዎች የሚካሄዱበት አካባቢ ነው፤

21.“አደገኛ ዕቃ” ማለት በአየር በሚጓጓዝበት ወቅት ለጤና፣ ለበረራ ደህንነት ወይም ለንብረት አስጊ ሁኔታን የሚፈጥር ማንኛውም ዕቃ ነው፤

22.“የሀገር ውስጥ የአየር ትራንስፖርት” ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ቦታዎች መሃከል የሚከናወን የአየር ማመላለስ ተግባር ነው፤

23. “የኢትዮጵያ አውሮኘላን” ማለት በኢትዮጵያ የተመዘገበ ማንኛውም አውሮኘላን ነው፤

24.“የበረራ ሠራተኞች አባል” ማለት በበረራ ወቅት ለአውሮኘላን በረራ ሥራ ተፈላጊ በሆኑ ተግባሮች ላይ የተመደበ ፈቃድ ያለው የበረራ ሠራተኛ ነው፤

25.“የበረራ ወቅት” ማለት አንድ የበረራ ሠራተኞች አባል ሥራውን ከሚጀምርበት ጊዜ ጀምሮ አንድን በረራ ወይም ተከታታይ በረራዎቹን አጠናቅቆ ከሁሉም ተግባሮች ነፃ እስከሚሆንበት ያለው ጊዜ ነው፤

26.“የውጭ አገር አዉሮፕላን” ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ ያልተመዘገበ ማንኛውም አውሮፕላን ነው፤

27.“የውጭ አገር አየር አጓጓዥ” ማለት በኢትዮጵያ ግዛት ወይም የአየር ክልል ውስጥ በንግድ አየር ትራንስፖርት ተግባር ላይ የተሰማራ ኢትዮጵያዊ ያልሆነ የአየር አጓጓዥ ነው፤

28.“ጠቅላላ አቪዬሽን ኦፕሬሽን” ማለት ከንግድ አየር ትራንስፖርትና ከኤሪያል ሥራ ውጭ የተለየ የአቪዬሽን ሥራ ማለት ነው፤[106]

29.“በበረራ ላይ” ማለት መንገደኞች ከተሳፈሩ በኋላ የአውሮፕላኑ የውጭ በሮች ከሚዘጉበት ጊዜ ጀምሮ በሮቹ መንገደኞቹን ለማራገፍ እስከሚከፈቱበት ድረስ ያለ ጊዜ ነው፤ ባልተጠበቀ ሁኔታ ለማረፍ በሚገደድበት ጊዜ ግን የሚመለከታቸው

[106] በበ26/27(2012) አ.1179 አንቀፅ 2(5) መሰረት ተሻሻለ፡፡

ባለሥልጣናት ለአውሮፕላኑና በአውሮፕላኑ ውስጥ ላሉ ሰዎችና ንብረት ኃላፊነት እስከ ሚወስዱበት ጊዜ ድረስ በረራው እንደቀጠለ ይቆጠራል፤

30.“አለም አቀፍ አየር ትራንስፖርት” ማለት ከተወሰነ የኢትዮጵያ ቦታ ወደ ተወሰነ የውጭ አገር ቦታ ወይም ከኢትዮጵያ ተነስቶ በውጭ ሃገር በማረፍ ወደ ኢትዮጵያ የሚደረግ የአየር ትራንስፖርት ነው፤

31.“አዛዥ ፓይለት” ማለት አውሮፕላኑ በበረራ ላይ እያለ ለአዉሮፕላኑ ኦፕሬሽንና ደህንነት ኃላፊ የሆነ ፓይለት ነው፤

32.“ኤሮድሮም ኦፕሬተር” ማለት አንድን የአየር ማረፊያ አቅዶና ገንብቶ አውሮፕላኖች እንዲያርፉበትና እንዲነሱበት የሚያመቻች አካል ነው፡፡[107]

33.“ባለገደብ ቦታ” ማለት አንዳንድ ገደቦችን በማክበር አውሮፕላን እንዲበር ተፈቅዶ የተከለለ የአየር ክልል ነው፤

34.“የመለዋወጫ ዕቃ" ማለት የአውሮፕላን አካላትን ለመቀየር ወይም ለመጠገን የሚያገለግል ቁስ አካል ሲሆን የአውሮፕላን ሞተሮችን እና ውልብልቢቶችን ይጨምራል፤[108]

35.“የመንግሥት አዉሮፕላን” ማለት ለወታደራዊ፣ ለፖሊስ፣ ለጉምሩክ ወይም ለሌላ የሕግ ማስፈጸሚያ አገልግሎት የሚውል ማንኛውም አውሮፕላን ነው፤

36.“ኮንቬንሽን” ማለት እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 7 ቀን 1944 በቺካጎ የተፈረመው የዓለም አቀፍ የሲቪል አቪዬሽን ኮንቬንሽን ሲሆን፣

ሀ) በኮንቬንሽኑ አንቀጽ 94(ሀ) መሠረት ሥራ ላይ የዋለና በኢትዮጵያ የፀደቀ ማንኛውንም የኮንቬንሽኑ ማሻሻያ፣

ለ) ኮንቬንሽኖቹ አንቀጽ 90 መሠረት ተቀባይነተ ያገኘ ማንኛውንም ተቀጽላ ወይም የዚሁ ማሻሻያን፣ እና

ሐ) በኮንቬንሽኑ አንቀጽ 37 መሠረት በአለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት መሠረት በየጊዜው ተቀባይነት ያገኙና የተሻሻሉ ዓለም አቀፍ ደረጃዎችንና ተመራጭነት ያላቸው አሰራሮችን፣ ይጨምራል፤

37.“አጋጣሚ” ማለት ከአውሮፕላን አደጋ ሌላ የአውሮፕላን እንቅስቃሴን ደህንነት የሚያቃውስ ወይም ሊያቃውስ የሚችል ክስተት ነው፤

[107] በ26/27(2012) አ.1179 አንቀፅ 2(6) መሰረት ተሻሻለ፡፡
[108] በ26/27(2012) አ.1179 አንቀፅ 2(7) መሰረት ተሻሻለ፡፡

38.“የተከለከለ ቦታ” ማለት አውሮፕላን እንዳይበርበት ተወስኖ የተከለለ የአየር ክልል ነው፤

39.“ቅኝት” ማለት ለአየር ትራፊክ ቁጥጥር ዓላማ የራዳርንና ሌሎች መሳሪያዎችን ተጠቅሞ አውሮፕላን ያለበትን ትክክለኛ ቦታ ማወቅ ማለት ነው፡፡[109]

40.“ማጽደቅ” ማለት ይህ አዋጅ ለባለሥልጣኑ በሰጠው ሥልጣን መሠረተ መዉሰድ በሚገባዉ እርምጃ ምትክ በሌላ አገር የሲቪል አቪዬሽን የተወሰደ እርምጃን በጽሑፍ መቀበል ነዉ፤

41.“ትዕዛዝ ወይም ስርዓት” ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት ወይም በአዋጁ በሚወጣ ደንብ መሰረት በባለስልጣኑ የሚወጣ የጽሑፍ መመሪያ ነዉ፤

42.“ደንብ” ማለት ማንኛውም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጣ ደንብ ነው፤

43.“አባል አገር” ማለት የቺካጐ ኮንቬንሽን ተዋዋይ ወገን የሆነ አገር ነው፤

44.“ኢትዮጵያዊ ዜጋ” ማለት

ሀ) ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው ግለሰብ፣

ለ) አባላቱ ሁሉ ኢትዮጵያ የሆኑበት ሽርክና፣ ወይም

ሐ) በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተቋቋመና የተመዘገበ የንግድ ማህበር፣

ነው፤

45.“ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር” ማለት እንደቅደም ተከተሉ የትራንስፖርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው።[110]

46.ባለሥልጣን ማለት የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን ነው፤

47.ሰው ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

1. ይህ አዋጅ በሚከተሉት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፤

ሀ) በኢትዮጵያ ባሉ የሲቪል አውሮፕላን ማረፊያዎች፤

ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ በተቋቋሙ ወይም በሚሠሩ አየር አገልግሎት እና የጠቅላላ አቪዬሽን አገልግሎት ድርጅቶች፤

ሐ) በባለሥልጣኑ በተመዘገበ ማንኛውም አዉሮፕላን፤

[109] በ26/27(2012) አ.1179 አንቀፅ 2(8) መሰረት አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (38) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (39) ተጨምሮ ከንዑስ አንቀጽ (39 እስከ (46) ያሉት እንደ ቅደም ተከተላቸው ከንዑስ አንቀጽ (40) እስከ (47) ተሸጋሽገዋል፡፡

[110] በ26/27(2012) አ.1179 አንቀፅ 2(9) መሰረት ተሻሻለ፡፡

መ) በማንኛውም በኢትዮጵያ ክልል ውስጥ በሚገኝ የውጭ አገር አውሮፕላን፤

ሠ) በባለሥልጣኑ ፈቃድ በተሰጣቸው የአቪዬሽን ባለሙያዎችና ማሰልጠኛ ትምህርት ቤቶች፤

ረ) በኢትዮጵያ ውስጥ በአውሮፕላንና በአውሮፕላን መለዋወጫዎች ወይም አካሎች ዲዛይን፣ ፍብረካ፣ እድሳት፤ ጥገናና ማሻሻል ተግባር ላይ በተሰማሩ ድርጅቶች፤

ሰ) በኢትዮጵያ ባሉ የአየር ናቪጌሽን ፋሲሊቲዎችና አገልግሎቶች፡፡

2. በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር ይህ አዋጅ በመንግስት አውሮፕላን ላይ ተፈጻሚነት አይኖረዉም፤

3. [111]

## ክፍል ሁለት

## የሲቪል አቪዬሽን አስተዳደር

## ምዕራፍ አንድ

## ስለሚኒስቴሩ ሥልጣንና ኃላፊነት

4. **የሚኒስቴሩ ኃላፊነቶች**

ሚኒስቴሩ፣

1. ሲቪል አቪዬሽንን የሚመለከቱ የፖሊሲ ጉዳዮችን፣
2. በሲቪል አቪዬሽን ሲስተም ዉስጥ ሲቪል አቪዬሽንን ደህንነትና ሴኩሪቲ ማሳደግን፤
3. ለባለስልጣኑ መፈጸም ያለባቸዉን ክፍያዎች በተመለከተ የሚቀርብ አቤቱታን መርምሮ የመጨረሻ ውሣኔ መስጠትን፣ እና
4. በአጠቃላይ ባለሥልጣኑ ተግባሮቹንና ኃላፊነቶቹን በአግባቡ መወጣቱንና መፈጸሙን መቆጣጠርን፣

በሚመለከት ኃላፊነቶች ይኖሩበታል፡፡

5. **የአስቸኳይ ጊዜ ሥልጣን**

1. በመንግሥት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሲታወጅ ሚኒስቴሩ ማንኛውም አውሮፕላን ወይም የተወሰኑ ዓይነት አውሮፕላኖች በማንኛውም ወይም በተወሰነ የኢትዮጵያ የአየር ክልል እንዳይበሩ በትዕዛዝ ሙሉ በሙሉ ሊከለክል ወይም በትዕዛዙ ውስጥ በሚገለጹ ሁኔታዎች መሠረት ገደብ ሊያደርግ ይችላል፡፡

[111] በ26/27(2012) አ.1179 አንቀፅ 2(10) መሰረት ተሻሻለ፡፡

2. በመንግሥት በሚሰጥ ዉክልና መሠረት ሚኒስቴሩ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ መኖሩን ካረጋገጠ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታውን ለመቋቋም በሚያስችል መጠን በአጠቃላይ ወይም በልዩ ትዕዛዝ ማንኛውንም አውሮፕላን ወይም በአንድ ምድብ የሚካተቱ አውሮፕላኖችን ወይም ሰዎችን ለተወሰነ ወቅት ከማንኛውም የአዋጁ ድንጋጌ ነጻ ሊያደርግ ይችላል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የተላለፈ ትዕዛዝ በመፈጸሙ ወይም በትዕዛዙ መሠረት በቅን ልቦና በተወሰዱ እርምጃዎች ምክንያት ምንም ዓይነት ካሣ አይከፈልም፡፡

6. <u>የሥልጣን ውክልና</u>

1. ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን ሥልጣንና ኃላፊነቱን በከፊል ለባለሥልጣኑ በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡
2. ተቃራኒ ማስረጃ ከሌለ በስተቀር፣ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ የተሰጠውን ውክልና በሥራ ላይ ሲያውል የሚፈጽማቸው ተግባሮች በውክልናው መሠረት እንደተፈጸሙ ይቆጠራል፡፡

## <u>ምዕራፍ ሁለት</u>

## <u>ስለኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን</u>

7. <u>እንደገና መቋቋም</u>

1. የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን የራሱ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል፡፡
2. ባለሥልጣኑ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

8. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶችን እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ቦታዎች ሊያቋቁም ይችላል፡፡

9. <u>ዓላማ</u>

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፤

1. ቀልጣፋና ኢኮኖሚያዊ የአየር አገልግሎትና ጠቅላላ የአቪዬሽን አገልግሎት እንዲኖር የማድረግና የአየር አገልግሎት ደኅንነት በከፍተኛ ሁኔታ መጠበቁን የማረጋገጥ፤

2. የአገር ውስጥና የዓለም አቀፍ የአየር ማመላለሻ መስመሮች እንዲዘረጉና አስተማማኝና ዘለቄታ ያለው የአየር አገልግሎት እንዲኖር የማድረግ፤
3. የሲቪል አቪዬሽን ሕጐችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን እንዲሁም ኢትዮጵያ ተዋዋይ ወገን የሆነችባቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተግባራዊ የማድረግና የማስከበር፡፡

10. ሥልጣንና ተግባር[112]

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. የማንኛውንም አውሮፕላን መፈብረክ፣ ባለይዞታነት፣ በሥራ ላይ መዋል፣ ሽያጭ፣ ወደ ሀገር እንዲገባ መደረግ፣ ወደ ውጭ አገር መላክ ሕጋዊ መሆኑን ይቆጣጠራል፤
2. ለአቪዬሽን ባለሙያዎች የሥራ ፈቃድ ይሰጣል፤
3. የአውሮፕላን ማረፊያዎችን ደህንነት ለማረጋገጥ:-

   ሀ) የግንባታና ማስፋፊያ ሥራ ዲዛይን መርምሮ ያጸድቃል፡፡

   ለ) የአውሮፕላን ማረፊያዎችን ይመረምራል፣ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ የሥራ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፡፡
4. በኢትዮጵያ አየር ክልል ውስጥና ከኢትዮጵያ አየር ክልል ውጭ የአየር ትራፊክ አገልግሎት፣ የመገናኛ ናቪጌሽንና ቅኝት አገልግሎት እንዲሁም የኤሮኖቲካል መረጃ አገልግሎት ይሰጣል፡፡
5. የአውሮፕላን ማረፊያዎችን ይመረምራል፣ የሥራ ፈቃድም ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤
6. በኢትዮጵያ የአየር ክልል ውስጥና ከኢትዮጵያ የአየር ክልል ውጭ የአየር ትራፊክ፣ የናቪጌሽን፣ የኤሮኖቲካል መገናኛና መረጃ አገልግሎቶችን ይሰጣል፤
7. ለአየር አገልግሎትና ለጠቅላላ የአቪዬሽን አገልግሎት ሰጪዎች የሥራ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤
8. ማንኛውንም የሥራ ፈቃድ ወይም የምስክር ወረቀት በበቂ ምክንያት ይሠርዛል ወይም ያግዳል፤
9. መንገደኞች፣ ዕቃዎችና ፖስታዎች በአይሮፕላን የሚጓጓዙበትን ሁኔታ ይወስናል፤

[112] የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፆች 3፣ 4 እና 15 በ26/27(2012) አ.1179 አንቀፅ 2(11)(12) መሰረት ተሻሻለ፡፡

10.የአቪዬሽን ኢንዱስትሪ ስለሚያድግበት ሁኔታ ምርምር ያካሂዳል፣ ፕላንና ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ የአየር ክልሉንና ሌሎች ከአቪዬሽን ጋር የተያያዙ ፕሮጀክቶች ጥቅም ላይ ስለሚውሉበት ሁኔታ መመሪያ ያዘጋጃል፤

11.የአውሮፕላን በረራ የሚካሄድባቸውን ሥርዓቶችና ደረጃዎች ያወጣል፤

12. ለሕዝብ የሚሰጠው የአየር አገልግሎት ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ብቁና የተሟላ መሆኑን ያረጋግጣል፤

13.ማናቸውንም የሲቪል አውሮፕላን ከነመብቱ ይመዘግባል፣ የመለያ ምልክት ይሰጣል፣ የአይሮፕላን የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ የበረራ ብቁነተ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ አውሮፕላኑ የሚዉልበትን ተግባር ይወሰናል፣ አውሮፕላኑ የሚታደሰበትና የሚጠገንበትን ሁኔታ ይወስናል፤

14.የበረራ ብቁነታቸው ተረጋግጦ በኢትዮጵያ ለተመዘገቡ አውሮፕላኖች አግባብ ባለው አካል ውክልና ሲሰጠው የሬዲዮ ፈቃድ ይሰጣል፤

15.ለሚሰጠው የኤርናቪጌሽን አገልግሎት በዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ኮንቬንሽንና መመሪያዎች መሰረት ተመን አውጥቶ ክፍያ ይሰበስባል እንዲሁም ለበረራ ደህንነት ምርመራ፣ ቁጥጥር እና ክትትል ተግባር እና ማናቸውም ሌሎች አገልግሎቶች ከአየር መንገዶች እና ከኤርፖርቶች የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያፀድቀው ተመን መሰረት ክፍያ ይሰበስባል፡፡

16.በኢትዮጵያ ውስጥ የሚሠራባቸዉን የበረራ መስመሮች በመለየት ጥቅም ላይ የሚውሉበትን ሁኔታዎችና ወደ ኢትዮጵያ ግዛት የሚገቡትንና የሚወጡትን አውሮኘላኖች የበረራ ሁኔታዎች ይወስናል፤ ከሌሎች ከሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር በረራ የተከለከለባቸዉን፣ ገደብ የተደረገባቸውንና የአደጋ ቦታዎችና የአየር መስመሮችን በመለየት ይወሰናል፣ ያስፈጽማል፤

17.በአየር ትራንስፖርት ዘርፍ በአደገኛ ቁሶች አጓጓዥነትና በላኪነት ሥራ ላይ ለተሰማሩ ሰዎች ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፡፡[113]

18.ከደንቦች፣ መመሪያዎችና ደረጃዎች አፈጻጸም ነፃ ስለማድረግ:-

[113] በ26/27(2012) አ.1179 አንቀፅ 2(13) መሰረት ከአዋጁ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ (16) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጾች (17 እስከ 33) ተጨምረው ነባሮቹ ንዑስ አንቀጾች (17 እስከ 19) እንደቅደም ተከተላቸው ከንዑስ አንቀጽ (34) እስከ (36) ሆነው ተሸጋሽገዋል።

ሀ) ኦፕሬተሩ ወይም የሥራ ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ወገን ወይም ከባለስልጣኑ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ወይም እንደ ሁኔታው የአቪዬሽን ተግባር ስልጣን የተቀበለ አካል ሲያመለክት በባለስልጣኑ መመሪያዎችን፣ ትዕዛዞችን፣ ሥርዓቶችን ትግበራ አስመልክቶ ጠያቂው አማራጭ የአሰራር ዘዴ አዘጋጅቶ ሲያቀርብ ባለስልጣኑ ለተወሰነ ጊዜ ነፃ ሊያደርገው ይችላል፡፡ ነፃ የሚደረግበት ሁኔታ በባለስልጣኑ መመሪያ ይወሰናል፡፡

ለ) ከላይ በፊደል ተራ (ሀ) መሰረት የተሰጠ ነፃ የመሆን መብት በማንኛውም መንገድ ከስድስት ወራት ያልበለጠ ሆኖ ጠያቂው ወይም አገልግሎት ሰጪው ከባለስልጣኑ የወጡ መመሪያ ወይም አሰራር በሙሉ ነፃ የሚሆንበት እና ነፃ የመሆን መብቱ አብቅቶ መመሪያውን ወይም አሰራሩን ሙሉ ለሙሉ መከተል የሚጀምርበት ጊዜ በጽሑፍ ተገልጾ መሰጠት ይኖርበታል፡፡"

19. አግባብነት ባለው ህግ መሰረት ውክልና ሲሰጠው ከተለያዩ አገራትና የኤሮኖቲካል ባለስልጣናት ጋር የአየር አገልግሎት ስምምነቶችን ይደራደራል፣ ይፈራረማል፡፡

20. ወደ ኢትዮጵያ እና ከኢትዮጵያ ውጭ መደበኛ በረራ ለሚያደርጉ አየር መንገዶች የክረምትና የበጋ ወቅት የበረራ ፕሮግራሞችን መርምሮ ያጸድቃል፡፡

21. በአውሮፕላን ማረፊያ ውስጥና ዙሪያ ያለውን የመሬት አጠቃቀም በተመለከተ ከሚመለከተው አካል ጋር በመማከር ይወሰናል፡፡

22. በዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ደረጃ የወጡና አገሪቱ የተቀበለቻቸውን የአቪዬሽን የበረራ ሴፍቲ ደረጃዎችና ተቀባይነት ያላቸውን አሰራሮች መሰረት በማድረግ የተጣጣመ ብሔራዊ የአቪዬሽን ሴፍቲ ፕሮግራም ያወጣል፤ በሚኒስቴሩ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

23. በሁሉም የአቪዬሽን አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የአቪዬሽን ሴፍቲ ሥራ አመራር ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

24. ብሔራዊ የአየር ትራንስፖርት ፋሲሊቴሽን ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ ያሻሽላል፣ በሚኒስቴሩ ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

25. የኤርፖርቶች አቪዬሽን ፋሲሊቴሽን ፕሮግራም ማስፈጸሚያ መመሪያ ያወጣል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

26.በኮንቬንሽኑ ውስጥ የተካተቱት ደረጃዎችና ተቀባይነት ያላቸው አሰራሮች በአግባቡ ስለመተግበራቸው በኦዲትና ኢንስፔክሽን ያረጋግጣል፣ የአፈጻጸም ሪፖርቱን ለሚኒስቴሩ፣ ለብሔራዊ አየር ትራንስፖርት ፋሲሊቴሽን ኮሚቴ እና ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርስ ያደርጋል፡፡

27.ከሲቪል አቪይሽን ፋሲሊቴሽን ጋር የተዛመደ ብሔራዊ የፖሊሲ ሃሳብ ያመነጫል፣ የማሻሻያ ሃሳብ ያቀርባል፣ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

28.የኤርፖርቶች ፋሲሊቴሽን ፕሮግራምን ይመረምራል፣ ያጸድቃል፡፡

29.ከብሄራዊ የአቪዬሽን ሴኪዩሪቲ ፕሮግራም መስፈርቶች ጋር የተጣጣመ የኤርናቪጌሽን አገልግሎትን፣ የአቪዬሽን ሴኪዩሪቲ ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ ይተገብራል፣ ያሻሽላል፡፡

30.በሀገሪቱ ውስጥ ተመዝግበው አገልግሎት ለሚሰጡ አየር መንገድ ኦፕሬተሮች እና የበረራ ሰራተኞች ሰርተፊኬት ይሰጣል፡፡

31.ከአቪዬይሽን ኢንደስትሪ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ ሥልጠና፣ የምርምር እና የማማከር አገልግሎት ይሰጣል፡፡

32.የምድር ላይ ድጋፍ አገልግሎት የሚሰጥበትን ሥርዓት ይወስናል፣ ይቆጣጠራል።

33.በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም በቺካጎ ኮንቬንሽን አንቀጽ 83 ቢ.አይ.ኤስ. መሠረት አግባብ ካለው የውጭ ኤሮኖቲካል ባለሥልጣን ጋር በሚደረግ ስምምነት ባለስልጣኑ:-

ሀ) በኢትዮጵያ ተመዝግቦ በሌላ ሀገር ውስጥ በኪራይ፣ በቻርተር ወይም በሌላ ተመሳሳይ ስምምነት ኦፕሬት የሚያደርግን አውሮፕላን አስመልክቶ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሥራውንና ተግባሩን ለተጠቀሰው ሀገር በሙሉ ወይም በከፊል ያስተላልፋል፡፡

ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ በኪራይ፣ በቻርተር ወይም በሌላ ተመሳሳይ ስምምነት ኦፕሬት የሚደረግ በውጭ ሀገር የተመዘገበ አውሮፕላንን አስመልክቶ የመዝጋቢውን ሀገር የሲቪል አቪዬሽን ባለስልጣን ስራውንና ተግባሩን እንዳስፈላጊነቱ በሙሉ ወይም በከፊል ይቀበላል፡፡

ሐ) የሦስተኛ ወገን ሀገሮች የኃላፊነት ማስተላለፍን በተመለከተ በቺካጎ ኮንቬንሽን አንቀጽ 83 ቢ.አይ.ኤስ. መሰረት ከተፈራረሙና ይህን አንቀጽ

በመንግስታቸው አጸድቀው የኃላፊነቱን መተላለፍ ካሳወቁት የኦፐሬተሩን ሀገር ስምምነት ሊቀበለው ይችላል፡፡

34.ለሚሰጠዉ ፈቃድና አገልግሎት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያጸድቀዉ ተመን መሠረት ክፍያ ይሰበስባል፤

35.አይሮፕላን ለሲቪል አቪዬሽን ሥራ በሚዉልበት ጊዜ በድምፅ፣ በንቅናቄ፣ በአየር ብክላ ወይም በማናቸውም ምክንያት በሕብረተሰቡ ላይ ወይም በአካባቢው ላይ የሚፈጥረው ችግር በተቻለ መጠን እንዲቀንስ እርምጃ ይወስዳል፤

36.ይህን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡትን ደንቦችና መመሪያዎችን እንዲሁም ሲቪል አቪዬሽንን በሚመለከት ኢትዮጵያ ተዋዋይ ወገን የሆነችባቸዉን ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ተግባራዊ ያደርጋል፣ ያስከብራል፤

37.የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፤ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣ እንዲሁም ክርክሮችን ለግልግል ማቅረብ ይችላል፤

38.ዓላማውን ለማሳካት የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል፡፡

11.<u>የባለሥልጣኑ አቋም</u>

ባለሥልጣኑ፣

1. በመንግሥት የሚሾሙ ዋና ዳይሬክተርና እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይክተሮች፣ እና
2. ለሥራው የሚያስፈልጉት ሠራተኞች፣ ይኖሩታል፡፡

12.<u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሆኖ ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የባለሥልጣኑን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፣
   ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 የተመለከቱትን የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባሮች ሥራ ላይ ያዉላል፤
   ለ) የባለሥልጣኑን የሥራ ፕሮግራምና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤
   ሐ) ለባለሥልጣኑ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

መ) ሲቪል አቪዬሽንን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን እያዘጋጀ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያዉላል፤

ሠ) የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ ዓላማ ተከተሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት የባለሥልጣኑን ሠራተኞች ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤

ረ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ባለሥልጣኑን ይወክላል፤

ሰ) የባለሥልጣኑን ዓመታዊ የሥራ አፈፃፀምና የሂሣብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤

ሸ) በሚኒስትሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ይፈጽማል፡፡

3. ዋና ዳይሬክተሩ ለባለሥልጣኑ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልገው መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለባለሥልጣኑ ኃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

13.<u>ስለሥልጣን ውክልና</u>

ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሥልጣንና ተግባሩን ብቃት ላላቸው ሌሎች አካላት በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፤ ሆኖም የአየር ኦፕሬተሮች፣ የኤርያል ሥራ ወይም የጠቅላላ አቪዬሽን ኦፕሬተሮችና የጥገና ተቋሞች ራሳቸውን ለመቆጣጠር በሚያስችል መልክ አለመወከላቸዉ መረጋገጥ አለበት፡፡

14. <u>በጀት</u>

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የባለሥልጣኑ በጀት በመንግሥት ከሚመደብ ገንዘብና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 (15) መሠረት ከሚሰበሰብ የፈቃድና የአገልግሎት ክፍያ የተውጣጣ ይሆናል፡፡
2. የባለሥልጣኑ የፋይናንስ አስተዳደር የሚመራው በፌዴራል የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 57/1989 እና በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ይሆናል፡፡

15.<u>ስለሂሣብ መዛግብት</u>

1. ባለሥልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፡፡
2. የባለሥልጣኑ የሂሣብ ሰነዶችና ገንዘብ ነክ መዛግብት በዋናው ኦዲተር ወይም በእርሱ በሚወከሉ የሂሣብ መርማሪዎች በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

## ክፍል ሦስት
## የአዉሮፕን ምዝገባ

### 16.ምዝገባና ምልክት

1. ማንኛውም ሰው አንድን የሲቪል አውሮፕላን፣
   ሀ) የተመዘገበ ካልሆነ፣ እና
   ለ) የዜግነትና የምዝገባ ምልክቶች ግልጽና የሚታይ ሆኖ በአውሮፕላኑ ላይ የተቀባ ወይም የተጣበቀ ካልሆነ በስተቀር፣
   
   በኢትዮጵያ አየር ክልል ውስጥ ማብረር አይችልም፡፡
2. የኢትዮጵያ አውሮፕላን የዜግነትና የምዝገባ ምልክቶች ባለሥልጣኑ በሚወስነው መሠረት በአውሮፕላኑ ላይ መቀባት ወይም መለጠፍ አለበት፡፡

### 17.የአውሮኘላን ዜግነት

1. በኢትዮጵያ የተመዘገበ አዉሮኘላን የኢትዮጵያ ዜግነት ይኖረዋል፡፡ ምዝገባዉ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥም በሌላ አገር ሊመዘገብ አይችልም፡፡
2. በሌላ አገር የተመዘገበ አዉሮኘላን የመዝጋቢዉ አገር ዜግነት እንዳለው ይቆጠራል፡፡ ምዝገባዉ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥም በኢትዮጵያ ሊመዘገብ አይችልም፡፡

### 18.የምዝገባ ሥርዓትና መሥፈርቶች

ባለሥልጣኑ በኢትዮጵያ ውስጥ ብሔራዊ የሲቪል አውሮፕላን አመዘጋገብ ሥርዓትንና መሟላት ያለባቸውን መስፈርቶች ይወስናል፤ በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፡፡

### 19.የምዝገባ ምስክር ወረቀት

1. ባለሥልጣኑ ለመዘገበዉ አውሮፕላን ባለቤት የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡
2. የአውሮኘላን ባለቤትነትን በሚመለክት በሚነሳ ክርክር የምዝገባ ምስክር ወረቀት የባለቤትነት ማስረጃ ሆኖ ይቆጠራል፡፡
3. የአውሮፕላን ምዝገባ የምስክር ወረቀት በዚህ አዋጅ ክፍል ስምንት ድንጋጌዎች መሠረት በባለሥልጣኑ ሊታገድ ወይም ሊሠረዝ ይችላል፡፡

### 20.በአዉሮፕላን ላይ ያለ መብትን የሚመመለከቱ ሰነዶችን ስለመመዝገብ

1. ባለሥልጣኑ በኢትዮጵያ በተመዘገበ የሲቪል አወሮኘላን ወይም በኢትዮጵያ ለተመዘገበ አውሮፕላን አገልግሎት በሚውል ሞተር፣ ውልብልቢት፣ መለዋወጫ

ወይም አፐሊያንስ ላይ ያለን መብት ወይም ጥቅም የሚመለከቱ ሠነዶች የሚመዘገቡበትን ሥርዓት ያቋቁማል፡፡

2. ማንኛውም በአውሮፕላን ወይም በአውሮፕላን መሣሪያ ላይ የተፈፀመ ዓለም አቀፍ የጥቅም ምዝገባ በኢትዮጵያ በተመዘገበ አውሮፕላን ላይ ጥቅም ያላቸው ወገኖች ጥቅማቸውን በባለሥልጣኑ ዘንድ በማስመዝገብ ረገድ ያለባቸውን ግዴታ ቀሪ አያደርገውም።
3. ባለሥልጣኑ የአውሮፕላንና የአውሮፕላን መሣሪያዎች ጥቅምን በሚመለከት ኢትዮጵያ ተዋዋይ ወገን የሆነችባቸው አለም አቀፍ ስምምነቶችን ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ ሥርዓቶችን ሊወስን ይችላል፡፡

21.**<u>ሰነዶችን ያለማስመዝገብ ውጤት</u>**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 20 (1) መሠረት የሰነዶች ምዝገባ ሥርዓት ከተቋቋመ በኋላ በማንኛውም በባለሥልጣኑ የተመዘገበ አውሮፕላን፣ የአውሮፕላን ሞተሮች፣ ውልብሊቢተች፣ አፕሊያንስ ወይም መለዋወጫ ዕቃዎች ላይ ያለን መብት ወይም ጥቅም የሚነካ የውል ሰነድ በባለልጣኑ ካልተመዘገበ በስተቀር ተፈፃሚ የሚሆነው በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መካከል ብቻ ይሆናል፡፡

22.**<u>ተፈጻሚነት የላቸው ሕጐች</u>**

ተዋዋዮቹ ወገኖች በተቃራኒው መስማማታቸው በሰነዱ ውስጥ ካልተገለጸ በስተቀር የማንኛውም የተመዘገበ ሠነድ ተፈፃሚነት በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ይወሰናል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የሲቪል አቪዬሽን ደህንነት ቁጥጥር</u>

### <u>ምዕራፍ አንድ</u>

### <u>አጠቃላይ የደኅንነት ድንጋጌዎች</u>

23.**<u>ደህንነትን ስለማጎልበት</u>**

1. ባለሥልጣኑ፣
   ሀ) በኮንቬንሽኑ የተካተቱትን ደረጃዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ሥርዓቶችን፣ እንዲሁም
   ለ) የሲቪል አቪዬሽን ደህንነትን በአጥጋቢ ሁኔታ የተጠበቀ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ሥርዓቶችንና ደረጃዎችን፣

በየጊዜው በማውጣትና በማሻሻል የሲቪል አዉሮፕላን በረራ ደህንነትን የማጎልበት ሥልጣንና ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

2. ባለስልጣኑ ሥርዓቶችንና ደረጃዎችን ሲያወጣና በዚህ አዋጅ መሠረት የምስክር ወረቀቶችን ሲሰጥ፣ የአየር ኦፕሬተሮች ለሕዝብ ጥቅም ሲባል እጅግ በጣም ከፍተኛ የደህንነት ደረጃዎችን ጠብቀው የሙያ ግዴታቸውን መወጣት ያለባቸው መሆኑን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

24.<u>የበረራ ብቁነት የምስክር ወረቀት</u>

1. ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ ወይም በተመዘገበበት አገር ሕግ መሠረት የበረራ ብቁነት የምስክር ወረቀት ያልተሰጠውን አውሮፕላን በኢትዮጵያ የአየር ክልል ውስጥ ማብረር አይችልም፡፡
2. በሌላ አገር የተመዘገበ አውሮፕላንን በተመለከተ የተሰጠው የበረራ ብቁነት የምስክር ወረቀት በኢትዮጵያ ውስጥ ሕጋዊ ሆኖ ተቀባይነት የሚኖረው የምስክር ወረቀቱ የተሰጠበት መመዘኛ በኮንቬንሽኑ ከወጡ መነሻ ደረጃዎች ጋር እኩል ወይም የሚበልጥ ሲሆን ነው፡፡
3. ባለሥልጣኑ ለደህንነት አጠባበቅ አስፈላጊ ሲሆን በበረራ ብቁነት የምስክር ወረቀት ላይ የምስክር ወረቀቱ የሚቆይበትን ጊዜ፣ አውሮፕላኑ ጥቅም ላይ የሚውልበትን የአገልግሎት ዓይነትና ሌሎች ግዴታዎችን፣ ሁኔታዎችን፣ ገደቦችና መረጃዎችን ሊያሠፍር ይችላል፡፡
4. ባለሥልጣኑ የሰጠውን የበረራ ብቁነት የምስክር ወረቀት መዝግቦ መያዝ አለበት፡፡

25.<u>የጥገና ተቋሞችና የኢቪዬሽን ማሠልጠኛ ትምህርት ቤቶች</u>

1. ባለሥልጣኑ የጥገና ተቋሞችንና የሲቪል አቪዬሽን ትምህርት ቤቶችን የፈቃድ አሠጣጥና የሥራ ሁኔታቸውን የሚመለከቱ መመሪያዎችን የማውጣትና ለእነዚህ ተቋሞችና ትምህርት ቤቶች ፈቃድ የመስጠት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡
2. ባለሥልጣኑ፤

   ሀ) የበረራ ወይም የአዉሮኘላንና የአውሮኘላን ሞቶር ዉልበሊቢትና አፕሊያንስ ጥገና ስልጠና እንዲሰጡ የተፈቀደላቸዉ የሲቪል አቪዬሽን ትምህርት ቤቶችን የኮርሶቻቸዉን ብቃት፣ የመሣሪያዎቻቸዉን አመቺነትና ለበረራ ብቁ መሆን እንዲሁም የአስተማሪዎቻቸውን ብቃት፣ እና

ለ) የአውሮፕላንና የአውሮፕላን ሞተር፣ ዉልብሊቢትና አፕሲያንስ ለመጠገን የተፈቀደላቸውን ተቋሞች የመሥሪያ ቦታዎቻቸውን፣ የመሣሪያዎቻቸውን፣ የአሠራር ዘዴዎቻቸውንና የጥገና ባለሙያዎቻቸን ብቃት በተመለከተ ፈተና መስጠትና ደረጃቸውን መወሰን ይችላል፡፡

3. ባለሥልጣኑ የአቪዬሽን ማሰልጠኛ ትምህርት ቤቶች ማቋቋምና ለእነዚሁ ምሩቃን የምስክር ወረቀት መስጠት ይችላል፡፡

## 26. የመገናኛ መሣሪያዎች

1. ማንኛውም ሰው አውሮኘላኑ በተመዘገበበት አገር ሕግ መሠረት የተፈቀደና የተገጠመለት የሬዲዮ መሣሪያ ካልኖረዉና ባለሥልጣኑ ባወጣቸው ደረጃዎችና ሥርዓቶች መሠረት አዉሮፕላኑን ናቪጌት ማድረግ የሚያስችል ግንኙነት ማድረግ ካላስቻለ በስተቀር በኢትዮጵያ የአየር ክልል አውሮፕላኑን ማብረር አይችልም፡፡
2. ባለሥልጣኑ በኢትዮጵያ በተመዘገበ አዉሮፕላን ላይ ስለሚገጠሙ የሬዲዮ መሣሪያዎች ተከላ፣ ጥገናና አጠቃቀም ሥርዓት ያወጣል፡፡

## 27. የጉዞ መዝገብ

1. አዉሮኘላኑ የተመዘገበበት አገር ሕግ በሚያዘው መሠረት ስለአውሮፕላኑ፣ ስለበረራ ሠራተኞቹና ስለጉዞው ዝርዝር ሁኔታ የሰፈረበት መዝገብ ካልያዘ በስተቀር ማንኛውም ሰው በኢትዮጵያ የአየር ክልል አውሮፕላኑን ማብረር አይችልም፡፡
2. ይህንን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችን፣ መመሪያዎችን ወይም ትዕዛዞችን በመተላለፍ ምክንያት በሚመሠረት ክስ በጉዞ መዝገብ ውስጥ የሰፈሩት መግለጫዎች ማስተባበያ ማስረጃ ካልቀረበባቸው በስተቀር በመዝጋቢዉ ሰውና በአውሮፕላኑ ባለቤትና ኦፕሬተር ላይ ማስረጃ እንደሆኑ ይቆጠራሉ፡፡
3. ባለሥልጣኑ በኢትዮጵያ ለተመዘገቡ አዉሮኘላኖች ተፈጻሚ የሚሆን የጉዞ መዝገብ ፎርም ያዘጋጃል፡፡

## 28. በአውሮፕላን መያዝ ያለባቸው ሠነዶች

1. ማንኛውም ሰው የሚከተሉት ሰነዶች በአዉሮፕላኑ መያዛቸውን ካላረጋገጠ በቀር በኢትዮጵያ የአየር ክልል አውሮፕላኑን ማብረር አይችልም፤
   ሀ) የምዝገባ ምስክር ወረቀት፤
   ለ) የበረራ ብቁነት ምስክር ወረቀት፤
   ሐ) የያንዳንዱ የበረራ ሠራተኛ የአቪዬሽን ባለሙያ የምስክር ወረቀት፤

መ) የጉዞ መዝገብ፤

ሠ) የአውሮፕላን ሬዲዮ ፈቃድ፤

ረ) መንገደኞች ካሉ ወይም ጭነት ካለ፤ የመንገደኞች ዝርዝር ወይም የጭነት ማኒፌስት፤

ሰ) የበረራ መመሪያ፤ እና

ሸ) የንግድ በረራ በሆነ ጊዜ የአየር ኦፕሬተር የምስክር ወረቀት፡፡

2. በሌላ አገር በተመዘገበ አውሮፕላን ውስጥ የሚገኙ ሠነዶች ከዚያ አገር መስፈርት ጋር የሚጣጣሙ መሆን አለባቸው፤ ሆኖም ባለሥልጣኑ ሠነዶቹን አስቀርቦ የመመርመር ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

29.<u>የኦፐሬተሮችና የአቪዬሽን ባለሙያዎች ኃላፊነት</u>

1. ማንኛውም የአየር ኦፐሬተር የምስክር ወረቀት ባለቤት አውሮፕላኑና ለሲቪል አቪዬሽን ጥቅም የሚውሉ መሣሪያዎች በየጊዜው ምርመራና እድሳት የሚደረግላቸውና ኦፐሬሽኑ በዚህ አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት በወጡ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ትዕዛዞች መሠረት የሚፈፀም መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

2. ማንኛውም የአቪዬሽን ባለሙያ የምስክር ወረቀት ባለቤት በምስክር ወረቀቱ የተመለከቱትን ሥልጣኖችና ገደቦች እንዲሁም ከሥራው ጋር የተያያዙ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦች፤ መመሪያዎችና ትዕዛዞች የማክበርና የመፈጸም ኃላፊነት አለበት፡፡

3. ማንኛውም የሲቪል አቪዬሽን ሥራ የሚያከናዉን ሰው ሥራውን የሚመለከቱትን የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ትዕዛዞች የማክበርና የመፈጸም ኃላፊነት አለበት፡፡

4. በዓለም አቀፍ በረራዎች መነሻቸው ወይም መድረሻቸው ኢትዮጵያ ለሆኑም ሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚካሄዱ የንግድ አየር ትራንስፖርት በረራዎች ጭነት ወይም ጓዝ የሚያቀርብ ወይም የሚቀበል ሰው በኮንቬንሽኑና አደገኛ ዕቃዎችን ደህንነቱ በተጠበቀ መንገድ በአየር ማጓጓዝን በተመለከተ የአለም አቀፍ የሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ባወጣው ቴክኒካዊ መመሪያ መሠረት ጭነቶቹን ወይም ጓዞቹን የማስረከብ ወይም የመረከብ ኃላፊነት አለበት፡፡

30.<u>ቁጥጥር ስለማድረግ</u>

1. ባለሥልጣኑ፣

ሀ) በማንኛውም የሲቪል አውሮፕላን ኦፕሬተር ጥቅም ላይ የሚውሉ አውሮፕላኖችና የአውሮፕላን ሞተሮች፣ ውልብለቢቶችና አፕሊያንሶች ደህንነታቸው በተጠበቀ ሁኔታ መገኘታቸውን ለማረጋገጥ እነዚህኑ በሚመለከቱ ሠነዶች ላይ ጭምር ቁጥጥር የማድረግ፣ እና

ለ) የእነዚህን ዕቃዎች ቁጥጥርና እድሳት በተመለከተ እያንዳንዱን ኦፕሬተር የማማከር፣

ሥልጣንና ኃላፊነት ይኖረዋል።

2. ባለሥልጣኑ በማንኛውም ኦፕሬተር ለሲቪል አቪዬሽን ጥቅም ላይ የዋለ ወይም እንዲውል የታሰበ ማንኛውም አውሮፕላን ወይም የአውሮፕላን ሞተር፣ ውልብለቢት ወይም አፕሊያንስ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ኦፕሬሽን ላይ ሊውል አለመቻሉን ሲረዳ ይህንኑ ለኦፕሬተሩ በማሳወቅ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ኦፕሬሽን ላይ ሊውል መቻሉን እስከሚያረጋግጥ ድረስ ጥቅም ላይ እንዳይውል ያግዳል፡፡

3. ባለሥልጣኑ የዚህን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ትዕዛዞች መከበር ለማረጋገጥ፣

ሀ) ፈቃድ ያገኙ የጥገና ድርጅቶችን፣ የአቪዬሽን ሥልጠና ትምህርት ቤቶችንና የአየር ኦፕሬተሮችን፣

ለ) ኤርፖርቶች፣ የአየር ናቪጌሽን ፋሲሊቲዎችንና የኤርፖርት ሴኩሪቲን፣ እንዲሁም

ሐ) በዚህ አዋጅ ወይም በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መያዝ ያለባቸውን ሰነዶች፣

የመቆጣጠር ሥልጣንና ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

4. ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጁ መሠረት የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው የአቪዬሽን ባለሙያዎችን በየጊዜው እንደገና ሊፈትን ይችላል፡፡

31. <u>**ቁጥጥር ለማድረግ የመግባት መብት**</u>

1. በአግባቡ የተወከለ ማንኛውም የባለሥልጣኑ ኢንስፔክተር በዚህ አዋጅ አንቀጽ 30 መሠረት ለሚደረግ ቁጥጥር ዓላማ፣

ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥ በአገልግሎት ላይ ወደአለ ማናቸውም የሲቪል አውሮፕላን፣

ለ) በየትኛውም ቦታ በአገልግሎት ላይ ወደአለ በኢትዮጵያ ወደ ተመዘገበ

አውሮፕላን፤

ሐ) ወደ ማንኛውም የአየር ኦፕሬተር ይዞታ፤

መ) ወደ ማንኛውም የጥገና ተቋም ወይም የስልጠና ትምህርት ቤት፣

ሠ) ወደ ማናቸውም አውሮፕላን ማረፊያ፣ የአየር ናቪጌሽን ፋሲሊቲ ወይም የኤርፖርት ሴኩሪቲ፣

መግባት ይችላል፡፡

2. ማንኛውም ኢኒስፔክተር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወደተጠቀሰወ አዉሮኘላን ወይም ይዞታ ለመግባት ከባለሥልጣኑ የተሰጠውን መታወቂያ ወረቀት ማሳየት አለበት፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተጠቀሱት አገልግሎቶች የተሰማራ ማንኛውም ሰው ለኢንስፔክተሮች ተገቢውን ትብብር የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

32.<u>የምስክር ወረቀትንና ፈቃድን ስለማገድና መሠረዝ</u>

ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 30 መሠረት በተካሄደ ቁጥጥር ወይም ፈተና ወይም በሌላ ዓይነት ምርመራ ምክንያት ለሲቪል አቪዬሽን ደህንነት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠን ማንኛውንም የምስክር ወረቀት በሙሉም ሆነ በከፊል በዚህ አዋጅ ክፍል ስምንት ድንጋጌዎች መሠረት የሚያግድ ወይም የሚሠርዝ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

33.<u>ማፅደቅ</u>

ባለሥልጣኑ የምስክር ወረቀትና ፈቃድ የመስጠትና ቁጥጥር የማድረግ ኃላፊነቶቹን ለመወጣት የተለየ እርምጃ ከመውሰድ ይልቅ ደህንነትን ለማስጠበቅ ሲባል ያስፈልጋሉ ብሎ የሚወስናቸው ሁኔታዎችና የሚከተሉት ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው የሌላን አገር ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን ተግባራትን ሊያፀድቅ ይችላል፤

1. የአቪዬሽን ባለሙያዎችና የበረራ ብቁነት የምስክር ወረቀቶችን አሰጣጥና ፀንቶ መቆየትን በሚመለከት ስለሚወሰዱ እርምጃዎች ሌላዉ አገር የኮንቬንሽኑ ፈራሚ መሆኑንና በኮንቬንሽኑ መሰረት ግዴታዎችን የሚያሟላ መሆኑ መረጋገጥ ያለበት መሆኑ፤

2. በአየር አጓጓዥ ፈቃድ ላይ ተፈፃሚነት ያላቸዉ እርምጃዎችን በሚመለከት ባለስልጣኑ በተለየ ሁኔታ ለመወሰንና ደጋፊ ሰነዶችን መጠየቅ የሚችል መሆኑ፤

3. የአየር ኦፕሬተር የምስክር ወረቀት አሰጣጥና ፀንቶ መቆየትን በሚመለከት አባል አገሩ በኮንቬንሽኑ መሠረት ግዴታውን የማይወጣ ስለመሆኑ የሚጠቁም መረጃ የሌለ መሆኑን ባለሥልጣኑ ያረጋገጠ መሆኑ፡፡

34.<u>በረራን ስለመከልከል</u>

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ አንድን ኦፐሬተር ወይም የበረራ ሠራተኛ አውሮፕላንን ኦፐሬት ከማድረግ ለመከልከል ይችላል፣

1. አውሮፕላኑ ለበረራ ብቁ ካልሆነ፣
2. የበረራ ሠራተኛው በረራውን ለማከናወን ብቃት ከሌለው ወይም የአካሉ ወይም የአእምሮዉ ሁኔታ የማያስችለዉ ከሆነ፣
3. ኦፐሬሽኑ በአውሮፕላን ውስጥ ወይም በመሬት ላይ ባሉ ሰዎች ወይም ንብረት ላይ አደጋ እንደሚያደርስ የሚያሰጋ ከሆነ፣
4. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችን፣ መመሪያዎችን ወይም ትዕዛዞችን ለማስከበር ወይም በማንኛውም ፍርድ ቤት የተሰጠን ትዕዛዝ ለማስፈጸም አውሮፕላኑን ወይም የበረራ ሠራተኛን እንዳይንቀሳቀስ ማድረግ አስፈላጊ ከሆነ፡፡
5. የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ባለስልጣኑ አንድን ኤሮድሮም ኦፕሬተር ለመዝጋት ይችላል:-[114]

   ሀ) አየር ማረፊያው አውሮፕላን ለማሳረፍ እና/ወይም ለማስነሳት ብቁ ሆኖ ሳይገኝ፣

   ለ) በባለስልጣኑ ኢንስፔክተር የተገኘው ጉድለት ለአውሮፕላኑ እንቅስቃሴ አዳጋች ሆኖ ሲገኝ፣

   ሐ) ያለበትን የሴፍቲ ችግር እንዲያስተካክል በተደጋጋሚ የተሰጠውን ምክረ-ሃሳብ ካላሟላ፡፡

35.<u>ክልከላ</u>

1. ማንኛውም ሰው የሚከተሉትን ከፈፀመ ሕገወጥ ተግባር እንደፈፀመ ይቆጠራል፣

   ሀ) የፀና የበረራ ብቁነት የምስክር ወረቀት ሳይኖር ወይም የምስክር ወረቀቱን ድንጋጌዎች በመተለለፍ ማንኛውንም የሲቪል አውሮፕላን ኦፕሬት ማድረግ፣

[114] በ26/27(2012) አ.1179 አንቀፅ 2(14) መሰረት አዲስ የገባ ድንጋጌ ነው፡፡

ለ) አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስችለው የአቪዬሽን ባለሙያ የምስክር ወረቀት ሳይኖረው ወይም የምስክር ወረቀቱን ድንጋጌዎች በመተላለፍ ማንኛውንም የአቪዬሽን ባለሙያ ሥራ መሥራት፤

ሐ) በተቀጠረበት ሥራ ላይ ለመሠማራት የሚያስችል የአቪዬሽን ባለሙያ የምስክር ወረቀት የሌለውን ሰው እንደ አቪዬሽን ባለሙያ ቀጥሮ ማሠራት፤

መ) የኦፕሬተር የምስክር ወረቀት ሳይዝ ወይም የምስክር ወረቀቱን ድንጋጌዎች በመተላለፍ በአየር ኦፕሬተርነት መሥራት፤

ሠ) በዚህ አዋጅ መሠረት በባለሥልጣኑ የወጣውን መመሪያ ወይም የተሰጠውን ትእዛዝ በመተላለፍ የሲቪል አቪዬሽን አዉሮፕላንን ኦፕሬት ማድረግ፡፡

2. በዚህ አዋጅ መሠረት ለሲቪል አቪዬሽን ድርጅት የተሰጠ የምስክር ወረቀትን ድንጋጌዎች መተላለፍ ወይም የምስክር ወረቀት መያዝን በተመለከተ በዚህ አዋጅ መሠረት የወጣ ማንኛውንም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ትእዛዝ መተላለፍ ክልክል ነው፡፡

36.አደገኛ ዕቃዎችን በአየር ስለማመላለስ

ባለሥልጣኑ አደገኛ ዕቃዎችን በአየር በማመላለስ ረገድ የኮንቬንሽኑ 18 ድንጋጌዎችና የአለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ቴክኒካዊ መመሪያዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን ይቆጣጠራል፡፡ አስፈላጊ ሲሆንም በቴክኒካዊ መመሪያዎቹ ላይ የሚደረጉ ልዩነቶችን ኢትዮጵያን በመወከል ማቅረብ ይችላል፡፡

37.የአቪሽን ሴኩሪቲ

ባለሥልጣኑ የአቪዬሽን ሴኩሪቲን በተመለከተ በኢትዮጵያ የአቪዬሽን ሴኩሪቲ አዋጅ ቁጥር 432/1997 የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## የአውሮፕላን የአየር ሥርዓት

38.የአየር ሥርዓት

1. ባለሥልጣኑ በኮንቬንሽኑ መሠረት በየጊዜው ከሚወጡት ሥርአቶች ጋር በተቻለ መጠን የሚጣጣም በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ተፈሚ የሚሆን በበረራ ላይ ያለን አውሮፕላን እንቅስቃሴ የሚወስን የአየር ሥርዓት ያወጣል፡፡

2. ማንኛውም ሰው በባለሥልጣኑ የወጣውን የአየር ሥርዓት ሳያከብር በኢትዮጵያ የአየር ክልል ውስጥ አውሮፕላን ማብረር አይችልም፡፡

3. ማንኛውም ሰው በኢትዮጵያ የተመዘገበን አውሮፕላን በሌላ አገር የአየር ክልል በዚያ አገር ተፈጻሚ የሚሆነውን የአየር ሥርዓት ሳይከተል ማብረር ወይም በኮንቬንሽን መሠረት የወጡትን ሥርዓቶች ሳይከተል በአለም አቀፍ ባህር የአየር ክልል ማብረር አይችልም፡፡

39.<u>የተከለከሉ፣ የተገደቡ ወይም አደገኛ የሆኑ ክልሎች</u>

1. ማንኛውም አውሮፕላን አዛዥ ፓይለት የኢትዮጵያን አየር ክልል አቋርጦ ሲበር ወይም በአየር ክልሉ ሲንቀሳቀስ የተወሰኑትን የአየር መስመሮች ትራፊክ በባለሥልጣኑ ወይም በአየር ተቆጣጣሪው የተፈቀዱትን መከተልና ወደተከለከሉ፣ ገደብ ወደተደረገባቸው ወይም አደገኛ ተብለው ወደተሰየሙ ክልሎች ውስጥ ከመግባት መታቀብ አለበት።[115]
2. ከተፈቀዱት የአየር መስመሮች የወጣ ወይም ወደተከለከለ፣ ገደብ ወደተደረገበት ወይም አደገኛ ወደተባለ ክልል የገባ አውሮፕላን ያልተፈቀደ ኦፕሬሽን እንዳደረገ ይቆጠራል፡፡ በዚህ ዓይነቱ ያልተፈቀደ ኦፕሬሽን ላይ የሚገኝ አዛዥ ፓይለት ወዲያውኑ የማረሚያ እርምጃዎችን በመውሰድ ወደተፈቀደው መስመር መመለስና በሚወሰንለት ሥፍራ እንዲያርፍ የሚሰጠውን ትእዛዝ ጨምሮ በሚመለከታቸው ባለሥልጣናት የሚሰጡትን ልዩ መመሪያዎች ያለማወላወል ተከትሎ መፈጸም አለበት፡

40.<u>የኢትዮጵያን አየር ክልል አቋርጦ ወይም በውስጡ ስለሚበር የውጭ አዉሮፕላን</u>

1. መደበኛ በሆነ የዓለም አቀፍ የአየር አገልግሎት ያልተሰማራ የውጭ አገር ሲቪል አውሮፕላን ለባለሥልጣኑ በቅድሚያ ሳያሳውቅ የኢትዮጵያን የአየር ክልል አቋርጦ ወይም በውስጡ ለመብረርና ለማረፍ አይችልም፡፡
2. ማንኛውም የውጭ አገር አየር አጓጓዥ ከባለሥልጣኑ በተሰጠው ፈቃድና በፈቃዱ ውስጥ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ካልሆነ በስተቀር ኢትዮጵያን አቋርጦ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ መደበኛ የሆነ ዓለም አቀፍ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ሊሰጥ አይችልም፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) የተደነገገዉን የተላለፈ የውጭ አገር ሲቪል አውሮፕላን በኢትዮጵያ አየር ኃይል ተገዶ ለቀጣይ ምርመራ በተወሰነ ኤርፖርት እንዲያርፍ ሲደረግ ይችላል፡፡

[115] በ26/27(2012) አ.1179 አንቀፅ 2(15) መሰረት ተሻሻለ፡፡

4. ተገዶ እንዲያርፍ የተደረገ የውጭ አገር ሲቪል አውሮፕላን ሊለቀቅ የሚችለው የተወሰነበትን የገንዘብ ቅጣት ወይም ሁኔታው የሚጠይቀውን ሌላ ቅጣት ከፈፀመ በኋላ ከባለሥልጣኑ በሚሰጥ የመልቀቂያ ፈቃድ መሠረት ብቻ ይሆናል፡፡
5. የመንግሥት አውሮፕላንን በተመለከተ መልቀቂያና የጉዞ መቀጠሉ ውሳኔ የሚሰጠው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

41.<u>የኦፐሬሽን ቴክኒካዊ ሁኔታዎች</u>

1. ባለሥልጣኑ በኮንቬንሽኑ መሠረት በየጊዜው ከሚወጡት ሥርዓቶች ጋር የሚጣጣም የአየር ኦፕሬተር የምስክር ወረቀት ባለቤቶች የሚያካሂዱትን ኦፕሬሽን ቴክኒካዊ ሁኔታዎች የሚወስን ሥርዓት ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሱት ቴክኒካዊ ሁኔታዎች የአየር ኦፕሬተር የምስክር ወረቀት ባለቤት በሆኑ ኦፕሬተሮች በትክክል መፈፀማቸውን ለማረጋገጥ ቁጥጥር ያደርጋል፡፡
3. የኦፕሬሽን ቴክኒካዊ ሁኔታዎችን አለመከተል በዚህ አዋጅ ክፍል ስምንት ድንጋጌዎች መሠረት ያስቀጣል፡፡

42.<u>አደገኛ በረራ</u>

ማንኛውም አውሮፕላን በማንኛውም ሰው ወይም ንብረት ላይ አደጋ ሊያደርስ በሚችል አኳኋን ማብረሩ ከተረጋገጠ የአውሮፕላኑ አዛዥ ፓይለት ወይም አውሮፕላኑን በኃላፊነት ያንቀሳቀሰ ረዳት ፓይለትና የአውሮፕላኑ ባለቤት ወይም ተከራይ በዚህ አዋጅ ክፍል ስምንት መሠረት ይቀጣሉ፡፡

43.<u>የተቀነሰ ዝቅተኛ የከፍታ መለያያ ባለበት አየር ክልል ውስጥ የሚከናወን ኦፕሬሽን</u>

1. ማንኛውም ኦፕሬተር፣
   ሀ/ አውሮኘላኑ የተመዘገበበት አገር ኦፕሬሽኑን እንዲያካሂድ በአግባቡ የፈቀደለት፣ ወይም
   ለ/ በልዩ ሁኔታ ምክንያትና ደህንነትን በበቂ ደረጃ ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ገደቦችን በማድረግ ኦፕሬሽኑ እንዲከናወን በባለሥልጣኑ የተፈቀደለት፣

   ካልሆነ በስተቀር የተቀነሰ ዝቅተኛ የከፍታ መለያያ ተግባራዊ በሆነበት የአየር ክልል ውስጥ የውጭ አገር አውሮኘላንን ኦፕሬት ማድረግ አይችልም፡፡

2. ማንኛውም ሰው፣
   ሀ) ኦፕሬተሩና የኦፕሬተሩ አውሮፕላን በዚህ አዋጅ መሠረት በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ውስጥ የተቀመጡትን የበረራ ብቁነትና የኦፕሬሽን የፈቃድ ሁኔታዎችን ያከበሩ መሆኑ፣ እና
   ለ) ኦፕሬሽኑ እንዲካሄድ ባለሥልጣኑ የፈቀደ መሆኑ፣

   ካልተረጋገጠ በስተቀር በኢትዮጵያ የተመዘገበ ሲቪል አውሮኘላንን የተቀነሰ ዝቅተኛ የከፍታ መለያየ ተግባራዊ እንዲሆን በተወሰነበት የአየር ክልል ውስጥ ማብረር አይችልም።

## 44.የአየር ሥርዓትን መተላለፍ

ማንኛውም አዛዥ ፓይለት፤ ወይም አወሮፕላኑን በኃላፊነት የሚያንቀሳቅስ ረዳት ፓይለት፡-

1. ማንኛውንም አውሮፕላን የኢትዮጵያን የአየር ክልል በማቋረጥ ወይም በውስጡ ሲያበር የኢትዮጵያን የአየር ሥርዓቶች ከተላለፈ፣
2. በኢትዮጵያ የተመዘገበን አውሮፕላን የውጭ አገርን የአየር ክልል በማቋረጥ ወይም በውስጡ ሲያበር በዚያ አገር ተፈፃሚነት ያላቸውን የአየር ሥርዓቶች ከተላለፈ፣ ወይም
3. በኢትዮጵያ የተመዘገበን አውሮፕላን የአለም አቀፍ ባሕርን የአየር ክልል በማቋረጥ ሲያበር በኮንቬንሽኑ የተመለከቱትን የአየር ሥርዓቶች ከተላለፈ፤

   በዚህ አዋጅ መሠረት ጥፋተኛ ተደርጎ ይቀጣል፡፡

## ምዕራፍ ሦስት
## ስለ አቪዬሽን ባለሙያዎች

## 45.ለአቪዬሽን ባለሙያ ስለሚሰጥ የምስክር ወረቀት

1. ማንኛውም ተፈላጊው ሙያ ያለው ሰው የአቪዬሽን ባለሙያ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠዉ ባለሥልጣኑን በማመልከቻ ሊጠይቅ ይችላል፡፡
2. ባለሥልጣኑ አመልካቹ ከተጠየቀው የአቪዬሽን ባለሙያ የምስክር ወረቀቱ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ተግባራት ለማከናወን አስፈላጊው ችሎታ ያለውና ጤንነቱ የተሟላ መሆኑን አጣርቶ ካረጋገጠ በኋላ የምስክር ወረቀቱን ይሰጠዋል፡፡

3. ባለሥልጣኑ የዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት አባል የሆነ የውጭ አገር ቀደም ሲል የሰጠውን የአቪዬሽን ባለሙያ ምስክር ወረቀት አመልካቹ ከተጠየቀው የምስክር ወረቀት ጋር ግንኙነት ያላቸውን ተግባራት ለማከናወን አስፈላጊው ችሎታ ያለውና ጤንነቱ የተሟላ መሆኑን በሙሉም ሆነ በከፊል የሚያረጋግጥ ማስረጃ አድርጐ ሊቀበለው ይችላል፡፡
4. የምስክር ወረቀቱ ባለሥልጣኑ የሲቪል አቪዬሽንን ደህንነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ ናቸው ብሎ የሚወስናቸዉን ድንጋጌዎችና የአካል ብቃት ማረጋገጫ ምርመራዎችን ሊይዝ ይችላል፡፡
5. ባለሥልጣኑ የበረራ አባላትን ወይም የአዉሮፕላንና የአዉሮፕላን ሞተሮች፣ ዉልብልቢቶችና አፕሊያንሶች ጥገና ባለሙያዎችን የማሰልጠንና የመቆጣጠር ኃላፊነት ያለባቸውን ጨምሮ ለአቪዬሽን ባለሙያዎች የሚሰጡትን የምስክር ወረቀቶች ዓይነትና የሚሰጡበትን መሥፈርት የሚወስን ሥርዓት ሊያወጣ ይችላል፡፡
6. በሌላ አገር የተሰጠ የአቪዬሽን ባለሙያ የምስክር ወረቀትን በተመለከተ ባለስልጣኑ የማጽደቂያ የምስክር ወረቀት ሊሰጥ ይችላል፡፡

46.<u>ክልከላ</u>

1. ማንኛውም ሰዉ በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ ወይም የፀደቀ የአቪዬሽን ባለሙያ የምስክር ወረቀት ካልያዘ በስተቀር በኢትዮጵያ በተመዘገበ አውሮፕላን የበረራ አባል ሆኖ መብረር አይችልም፡፡
2. ማንኛውም ሰው፣
   ሀ) በዚህ አዋጅ ወይም አውሮፕላኑ በተመዘገበበት አገር ህግ መሰረት የተሰጠ የአቪዬሽን ባለሙያ ምስክር ወረቀት ካልያዘ፣
   ለ) ምስክር ወረቀቱ በሌላው አገር የተሰጠው በኮንቬንሽኑ መሠረት ከወጡት መነሻ ደረጃዎች ጋር እኩል በሆነ ወይም በበለጠ መስፈርት መሠረት ካልሆነ፣ እና
   ሐ) ተመጣጣኝ የኢትዮጵያ የምስክር ወረቀት ያልተከለከለ ሰው ካልሆነ፤

   በስተቀር በኢትዮጵያ አየር ክልል በሌላ አገር በተመዘገበ አውሮፕላን የበረራ አባል በመሆን ሊበር አይችልም፡፡

3. ማንኛውም ሰው የአቪዬሽን ባለሙያ የምስክር ወረቀት ቢሰጠውም በምስክር ወረቀቱ ላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎችና ገደቦች መሠረት ካልሆነ በስተቀር በአውሮፕላን ኦፕሬሽን ወይም ጥገና ወይም በማንኛውም ሌላ ተግባር ላይ መሠማራት አይችልም።

47.<u>የበረራ አባላት</u>

1. ባለሥልጣኑ፣
   ሀ) የአውሮኘላኑን ዓይነት፣ የውስጥ አቀማመጥ፣ የበረራውን ርዝመት፣ አውሮኘላኑ የተሰማራበትን የአገልግሎት መስክና ሌሎች ሁኔታዎችን ከግንዛቤ በማስገባት በኢትዮጵያ ለተመዘገበ አውሮፕላን ሥራ አስፈላጊ የሚሆኑ የበረራ አባላትን አደረጃጀት፣ ስብጥርና አነስተኛ ቁጥር ይወስናል፤
   ለ) የበረራ አባላትን ከፍተኛውን የሥራ ሰዓትና አስፈላጊ የዕረፍት ጊዜያትን ጨምሮ የአሠራር ደረጃና የሥራ ሁኔታዎችን ይወስናል፡፡
2. የበረራ አባላት ለበረራው አይነት በተወሰነው ደረጃና ሁኔታዎች መሠረት የተሟሉ ካልሆነና እያንዳንዱ የበረራ አባል ለሚፈጽመው ተግባር የሚጠየቁ ደረጃዎችንና ሁኔታዎችን የሚያሟላ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም በረራ ሊደረግ አይችልም፡፡
3. ማንኛውም የአየር ኦፐሬተር የምስክር ወረቀት ባለይዞታ በበረራ አባላቱ ላይ ተፈጻሚ የሚያደርጋቸውን የሥራ ሁኔታዎች በባለሥልጣኑ እንዲጸድቁለት ማቅረብ አለበት፡፡

48.<u>አዛዥ ፓይለትና ተተኪ አዛዥ ፓይለት ስለመመደብ</u>

ማንኛውም የአየር ኦፐሬተር ለእያንዳንዱ የበረራ ክፍል ብቁ የሆነ የበረራ ሠራተኞች አባልን እንደ አዛዥ ፓይለትና አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜም ተተክቶ የሚሠራ ብቃት ያለውን ሌላ የበረራ ሠራተኞች አባል እንደ ምክትል አዛዥ ፓይለት መመደብ አለበት፡፡

49.<u>የአዛዥ ፓይለት ኃላፊነት</u>

1. የአውሮፕላን አዛዥ ፓይለት አውሮፕላኑ በሮቹ ከተዘጉበትና የመነሳት እንቅስቃሴ ለማድረግ ከተዘጋጀበት ጊዜ አንስቶ በረራው ተጠናቆ በመጨረሻ እስከሚቆምበትና የአውሮፕላኑ ዋነኛ አንቀሳቃሽ ክፍሎች የሆኑት ሞተሮች እስከሚጠፉበት ጊዜ ድረስ ለአውሮኘላኑ፣ ለበረራ ሠራተኞቹ፣ ለመንገደኞቹና በአውሮኘላኑ ውስጥ ለሚገኝ ጭነት ደህንነት ኃላፊ ይሆናል፡፡

2. ማንኛውም አዛዥ ፓይለት የአየር ሥርዓቶችን፣ በአየር ትራፊክ ተቆጣጣሪዎች የሚሰጡ ተገቢ መመርያዎችንና በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ትዕዛዞች መሠረት የሚወስኑ ተፈላጊ ሁኔታዎችን መከተልና መፈጸም አለበት፡፡
3. ማንኛውም አዛዥ ፓይለት ተግባሩን በማከናወን ላይ እያለ የአውሮፕላኑን ወይም በአይሮፕላኑ ውስጥ የሚገኙ ሰዎችን ወይም ንብረቶችን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል የሙያ ግዴታው በሚጠይቀው መሠረት በፈጸመው ድርጊት ምክንያት ለሚከሰት ጉዳት በግሉ ተጠያቂ አይሆንም፡፡
4. ባለሥልጣኑ ለደህንነት አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በአዛዥ ፓይለት ላይ ተጨማሪ ግዴታዎችንና ኃላፊነቶችን ሊጥልበት ይችላል፡፡

## ምዕራፍ አራት

## የኤሮኖቲካል አገልግሎቶች

### 50.የኤርናቪጌሽን አገልግሎት[116]

1. ባለሥልጣኑ በኮንቬንሽኑ መሠረት በየጊዜው ከሚወጡት ሥርዓቶች ጋር በተቻለ መጠን የሚጣጣሙና በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ተፈጻሚ የሚሆኑ የአየር ትራፊክ ቁጥጥር ሥርዓቶችን ያወጣል፡፡
2. ባለሥልጣኑ በኢትዮጵያ ውስጥ ለኤሮኖቲካል ጠቀሜታ ብቻ የሚውል የሬዲዮ መገናኛና የናቪጌሽንና የቅኝት ፋሲሊቲዎች የመትከል፣ የማስተዳደርና የመጠገን ሥልጣን ይኖረዋል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና በሚኒስትሩ ሲፈቀድ በቀጠና ወይም በአህጉር ደረጃ ሲቪል አቪዬሽንን በተመለከተ በሚፈጠሩ የመገናኛ ሥርዓት ተቋሞች ውስጥ በመሳተፍ የመገናኛ ሥርዓቶች ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡፡
3. ባለሥልጣኑ በብሔራዊ ደረጃ ወይም በቀጠና ትብብር አማካይነት የመገናኛ፣ የናቪጌሽንና የቅኝት መረቦችን በተገቢው ቴክኖሎጂ ላይ ተመሥርቶ ማቋቋምና ማካሄድ ይችላል፡፡
4. ባለሥልጣኑ የአየር ናቪጌሽን ፋሲሊቲዎችንና ሠራተኞችን በሚመለከት ተፈጻሚ የሚሆኑና በተቻለ መጠን በኮንቬንሽኑ መሠረት ከወጡ ደረጃዎችና ተመራጭነት ካላቸው አሠራሮች ጋር የሚጣጣሙ ሥርዓቶችና ደረጃዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

---

[116] በ26/27(2012) አ.1179 አንቀፅ 2(16) መሰረት ተሻሻለ፡፡

5. ባለሥልጣኑ በሲቪል አቪዬሽን መስክ በኢትዮጵያ አየር ክልል የሚከናወኑ ተግባሮችን በሚመለከት ተፈጻሚ የሚሆኑ ቋሚ የኤሮኖቲካል መረጃዎችን እንዲሁም በኮንቬንሽኑ መሠረት ተፈላጊ የሆኑ የኤሮኖቲካል ካርታዎችና ቻርቶችን አሳትሞ ያሰራጫል፡፡

51.**የበረራ መስመሮችን ስለመሰየም**

1. ባለሥልጣኑ በኢትዮጵያ ኦፕሬት የሚያደርጉ የሲቪል አውሮፕላኖች የሚያልፉበትን የበረራ መስመር ይሰይማል፣ እንዲሁም ከሚመለከታቸው የመንግሥት ባለሥልጣናት ጋር በመተባበር የተከለከሉ፣ ገደብ የተደረገባቸውንና አደገኛ ቦታዎችን ሊሰይም ይችላል፡፡
2. ባለሥልጣኑ በዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት የአሠራር ደረጃዎችና በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ የአውሮፕላን ማረፊያዎች ውስጥ በሚያገለግሉ ተገቢ የናቪጌሽን አጋዥ መሣሪያዎች ላይ ተመሥርቶ የበረራ መዳረሻ፣ መቃረቢያና መነሻ ሥርአቶችን ያወጣል።

52.**የአየር ናቪጌሽን ፋሲሊቲ ደህንነት ደረጃዎች**

ባለሥልጣኑ የአየር ናቪጌሽን ፋሲሊቲዎች ኦፕሬሽንን በሚመለከት ተፈጻሚ የሚሆኑ መነሻ የደህንነት ደረጃዎችን ያወጣል።

**ምዕራፍ አምስት**

**ስለአውሮፕላን ማረፊያዎች**

53.**የምስክር ወረቀትና ፈቃድ አስፈላጊነት** [117]

1. ማንኛውም ሰው በሚመለከተው አካል የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲሁም በባለሥልጣኑ የኦፕሬሽን ፈቃድ የምስክር ወረቀት ወይም ሌላ ሕጋዊ ማስረጃ ካልተሰጠውና በተሰጠው ፈቃድ ውስጥ በተመለከቱት ድንጋጌዎችና ገደቦች መሠረት ካልሆነ በስተቀር የአውሮፕላን ማረፊያ ኦፕሬት ሊያደርግ አይችልም፡፡
2. በአውሮፕላን ማረፊያ ኢንቨስት ለማድረግ መብት ያለው ማንኛውም ሰው የአውሮፕላን ማረፊያ ኦፕሬሽን ፈቃድ የምስክር ወረቀት ወይም ሌላ ሕጋዊ ማስረጃ እንዲሰጠው ለባለሥልጣኑ ማመልከቻ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

---

[117] በ26/27(2012) አ.1179 አንቀፅ 2(17) መሰረት የአዋጁ አንቀፅ 53 ርዕስ ተሰርዞ "የምስክር ወረቀትና ፈቃድ አስፈላጊነት" በሚል ሐረግ የተተካ ሲሆን በዚሁ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1)፣ (2)፣ (4) እና (5) "ኦፕሬሽን ፈቃድ" ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ ‹‹የምስክር ወረቀት ወይም ሌላ ሕጋዊ ማስረጃ›› የሚል ሐረግ ተጨምሯል፡፡

3. ባለስልጣኑ የቀረበለትን ማመልከቻ መርምሮ አመልካቹ በዚህ አዋጅና በአዋጁ መሰረት በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ደህንነቱ የተጠበቀ የአውሮፕላን ማረፊያ ኦፕሬሽን ለማካሄድ በሚገባ የተዘጋጀና ብቃት ያለው መሆኑን ካረጋገጠ በኃላ ፍቃዱን፣ የምስክር ወረቀቱን ወይም ሌላ ህጋዊ ማስረጃ ይሰጠዋል፡፡[118]
4. ማንኛውም የአውሮፕላን ማረፊያ ኦፐሬሽን ፈቃድ የምስክር ወረቀት ወይም ሌላ ሕጋዊ ማስረጃ የንግድ አየር ትራንስፖርት ደህንነትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ድንጋጌዎችን ሁኔታዎችንና ገደቦችን እንደአስፈላጊነቱ መያዝ ይችላል፡፡
5. ባለሥልጣኑ ለሕዝብ ጥቅም ተቃራኒ ይሆናል ብሎ ካላመነ በስተቀር፣ ማንኛውም የአውሮፕላን ማረፊያ ኦፐሬሽን ፈቃድ የምስክር ወረቀት ወይም ሌላ ሕጋዊ ማስረጃ፤
   ሀ) የእሳት አደጋ መከላከያና ማዳኛ መሣሪያዎችን ጨምሮ ለአውሮኘላን ማረፍ፣ መነሳት ወይም በመሬት ላይ እንቅስቃሴ ለማድረግ ወደሚያገለግሉ ማንኛውም የአውሮፕላን ማረፊያው ክፍል በፍጥነት መዝለቅ የሚችሉ በቂ የሆኑ የደህንነት መሣሪያዎችን ኦፐሬሽንና ጥገና፤ እንዲሁም
   ለ) ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ይሆናሉ ብሉ የሚያምንባቸውን የመጀመሪያ ደረጃና የሁለተኛ ደረጃ ማረፊያ ሜዳዎች ሁኔታና ጥገና፣

   የሚመለከቱ ድንጋጌዎች፣ ሁኔታዎችና ገደቦችን ማካተተ አለበት፡፡
6. ባለስልጣኑ ይህን አዋጅና በአዋጁ መሰረት የወጡ ደንቦችን፤ መመሪያዎችና ትዛዞችን ለማስክበር ማንኛውንም የአውሮፕላን ማረፊያ የኦፕሬዬሽን ፈቃዱ፣ የምስክር ወረቀቱን ወይም ሌላ ህጋዊ ማስረጃ በዚህ አዋጅ ክፍል ስምንት ድንጋጌዎች መሰረት ማገድ ወይም መሰረዝ ይችላል፡፡[119]

54. **መመዘኛ**

1. ባለሥልጣኑ የአውሮፕላን ማረፊያ ኦፐሬሽን ፈቃድ ድንጋጌዎችንና ሁኔታዎችን ሲወስን የደህንነት፣ የሴኩሪቲና የአካባቢ ጥበቃ ተፈላጊ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ ማስገባትና እነዚህንም ተፈላጊ ሁኔታዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ሥርዓቶችን ማውጣት አለበት፡፡

---

[118] በ26/27(2012) አ.1179 አንቀፅ 2(18) መሰረት ተሻሻለ፡፡
[119] በ26/27(2012) አ.1179 አንቀፅ 2(19) መሰረት ተሻሻለ፡፡

2. ባለሥልጣኑ የሚያወጣቸው የኤርፖርት ግንባታ ሥርአቶችና ደረጃዎች በተቻለ መጠን በኮንቬንሽኑ ላይ ከተመለከቱት ደረጃዎችና ተመራጭነት ያላቸው አሠራሮች ጋር መጣጣም አለባቸዉ፡፡

55.<u>ስለመሰየም</u>

ባለሥልጣኑ፣

1. የሲቪል አቪዬሽን አውሮኘላን ማረፊያዎችንና በጊዜያዊ የሲቪል አውሮፕላን መነሻና መድረሻነት የሚያገለግሉ ቦታዎችን መሰየም፣
2. የአውሮኘላን ማረፊያ ደረጃዎችን ማውጣት፣ እና
3. በዓለም አቀፍ አየር ትራንስፖርት ለተሰማሩ አየር አጓጓዦች ጠቀሜታ የሚውሉ የተወሰኑ አዉሮኘላን ማረፊያዎችን እንደ ዓለም አቀፍ አዉሮኘላን ማረፊያ መሰየም፣ ይችላል፡፡

56.<u>በተፈቀድ አዉሮፐላን ማረፊያ ስለማረፍ</u>

ማንኛውም ሰው ባለሥልጣኑ ለአውሮኘላን ማረፊያና መነሻ እንዲያገለግል ከሰየመው አውሮኘላን ማረፊያ ወይም ጊዜያዊ ቦታ ውጭ ማንኛውንም የሲቪል አውሮፐላን ከአንድ አውሮኘላን ማረፊያ ወይም ጊዜያዊ ቦታ ወደሌላ አውሮኘላን ማረፊያ ወይም ጊዜያዊ ቦታ ኦፐሬት ማድረግ አይችልም።

57.<u>አደናቃፊ ነገሮችን ስለማንሳት ወይም ምልክት ስለማድረግ</u>

1. ባለሥልጣኑ በአውሮፐላን ማረፊያ አካባቢ ለበረራ ደህንነት አደናቃፊ ሊሆኑ የሚችሉ ግንባታዎች እንዳይገነቡ ወይም ሌሎች የሚጋርዱ ነገሮች እንዳይኖሩ ሊከለክል ይችላል፡፡
2. ባለሥልጣኑ፣
   ሀ) በአውሮፐላን ማረፊያ አጠገብ ባለ መሬት ላይ የሚገኙ አደናቃፊ ነገሮችን ማንሳትን ወይም ምልክት ማድረግን፣ እና
   ለ) ለአየር ናቪጌሽን ደህንነት ጠቀሜታ ያላቸው የማስጠንቀቂያ መብራቶችን ወይም ሌሎች የአየር ናቪጌሽን ደህንነት አጋዥ መሣሪያዎችን ከእነዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸውና በመሬት ውስጥም ሆነ በአየር ላይ የተዘረጉትን የቧንቧ፣ የስልክና የኃይል መስመሮች እና የመሳሰሉትን ማኖርንና መጠገንን፣

   የሚመለከቱ ሥርዓቶችና ደረጃዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

3. በአውሮፕላን ማረፊያ አቅራቢያ የሚገኝ ነገር ወይም የነገሩ ከፊል አካል፣
   ሀ) በባለሥልጣኑ አስተያየት ለአውሮፕላኖች በረራ አደናቃፊነቱ ወይም የሥጋት ምንጭነቱ ከተረጋገጠ፣ ወይም
   ለ) መጠኑ በኮንቬንሽኑ ወይም በሌሎች አግባብነት ባላቸው የዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ቴክኒካዊ መሥፈርቶች ውስጥ ከተመለከቱት ገደቦች በልጦ ከተገኘ፣

   ባለሥልጣኑ አደናቃፊው ነገር ለሚገኝበት ቦታ ባለቤት ወይም ባለይዞታ አደናቃፊው ነገር ወይም ከፊል አካል ተገቢ በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲነሳ ወይም በሚፈለገው መንገድ ምልክት እንዲደርግበት ማስጠንቀቂያ መስጠት ይችላል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ማስጠንቀቂያ የተሰጠው ባለንብረት ወይም ባለይዞታ በማስጠንቀቂያው መሠረት ካልፈፀመ ባለሥልጣኑ አደናቃፊ የሆነው ነገር ወይም ከፊል አካል እንዲነሳ ማድረግና ከዚሁ ጋር የተያያዙ ወጭዎችን ባለንብረቱ ወይም ባለይዞታው እንዲተካ ሊጠይቀው ይችላል፡፡

58.<u>መሬት ስለማግኘት</u>

1. ባለሥልጣኑ ወይም በባለሥልጣኑ የተሰየመ አካል ለአየር ናቪጌሽን አገልግሎትና የሬዲዮና የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎችና ዕቃዎችን ጨምሮ ለሌሎች ፋሲሊቲዎች የሚውል መሬት ያገኛል፡፡
2. መሬት ለሕዝብ ጥቅም ማዋልን በሚመለከት አግባብ ባለው ሕግ የተደነገገው ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>የአየር አገልግሎት ፈቃድ አሰጣጥ</u>

59.<u>የፈቃድ አስፈላጊነት</u>

ማንኛውም የአየር ኦፐሬተር ከባለሥልጣኑ የተሰጠው የፀና ፈቃድ ከሌለው በስተቀር በአየር አገልግሎት ሊሰማራ አይችልም።

60.<u>የአየር አገልግሎት ፈቃድ ዓይነቶች</u>

1. የሚከተሉት የአየር አገልግሎት ፈቃዶች በባለሥልጣኑ ሊሰጡ ይችላሉ፤
   ሀ) የአየር ትራንስፖርት ፈቃድ፤
   ለ) የኤርያል ሥራ ፈቃድ፤ እና

ሐ) የጠቅላላ አቪዬሽን ኦፕሬሽን ፈቃድ፡፡[120]

2. የአየር ትራንስፖርት ፈቃድ የሚሰጠው መደበኛና መደበኛ ላልሆኑ የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎቶች ይሆናል፡፡
3. የኤርያል ሥራ ፈቃድ የሚሰጠው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው ትርጓሜ ለሚሸፈኑ አገልግሎቶች ይሆናል፤ ሆኖም ማንኛውንም ካሜራ ይዞ የሚበር አውሮፕላንን በሚመለከት ፈቃድ የሚሰጠው ከሚመለከተው አካል የሴኪዩሪቲ ፈቃድ በቅድሚያ ሲያገኝ ብቻ ይሆናል፡፡
4. [121]

61. **የፈቃድ ማመልከቻ**

ማንኛውም በአየር አገልግሎት ለመሰማራት የሚፈልግ ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 60 (1) የተመለከተው አግባብ ያለው ፈቃድ እንዲሰጠው በባለሥልጣኑ በተወሰነው ሥርዓትና ፎርም መሠረት ማመልከቻውን ማቅረብ አለበት፡፡

62. **የፈቃድ አሰጣጥ መመዘኛዎች**

1. ባለሥልጣኑ የአገር ውስጥ የአየር ትራንስፖርት ወይም የኤርያል ሥራ ፈቃድ ሲሰጥ ሌሎች ሊታዩ የሚገባቸው ነገሮች እንደተጠበቁ ሆነው የፈቃድ ጠያቂውን ብቃትና ችሎታ፣ የበረራውን መድረሻና በመሃል አገልግሎት ሊሰጥባቸዉ የሚገቡ ቦታዎችን፣ አገልግሎት የሚሰጥበትን ፕሮግራምና የፈቃዱ መሰጠት ለሕዝብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማገናዘብ አለበት፡፡
2. ባለሥልጣኑ የዓለም አቀፍ አየር ትራንስፖርት ፈቃድ ሲሰጥ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተመለከተው በተጨማሪ ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸውን ዓለም አቀፍና የሁለትዮሽ ስምምነቶችን እንዲሁም ዓለም አቀፍ የርስበርስ መጠቃቀም ግንኙነቶችን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

63. **የፈቃድ አሰጣጥ ሁኔታዎች**

1. ማንኛውም በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ የሚጠይቅ የአየር አጓጓዥ በዚህ አዋጅ፣በዚህ አዋጅ መሠረት በወጣ ደንብ እና አግባብነት ባላቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የተደነገጉት የተለያዩ ኃላፊነቶች የሚያስከትሉትን አነስተኛ የክፍያ መጠን የሚሸፍን የመድን ዋስትና ፖሊሲ መያዝ አለበት፡፡

[120] በ26/27(2012) አ.1179 አንቀፅ 2(20) መሰረት ተሻሻለ፡፡
[121] በ26/27(2012) አ.1179 አንቀፅ 2(21) መሰረት ተሰረዘ፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን የመድን ዋስትና ፖሊሲ አለመያዝና ተፈጻሚነት ኖሮት እንዲቀጥል አለማድረግ ሊያስከትል ከሚችለው ማንኛውም ሌላ ቅጣት በተጨማሪ አውሮፕላን እንዳይበር ለማድረግና ለፈቃድ መታገድ ወይም መሰረዝ ምክንያት ይሆናል፡፡
3. ባለሥልጣኑ የአየር ትራንስፖርት ወይም የኤርያል ሥራ ፈቃድ በሚሰጥበት ጊዜ ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ሁኔታዎችና ገደቦች ከፈቃዱ ጋር እንዲያያዙ ማድረግ ይችላል፡፡
4. ማንኛውም የአየር ኦፐሬተር የምስክር ወረቀት የአየር ኦፕሬተሩ በንግድ አየር ትራንስፖርት እንዲሰማራ የተፈቀደለትን መድረሻና በመሃል ያሉ ማረፊያ ቦታዎችና የሚሰጠውን አገልግሎት እንዲሁም ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ከፈቃዱ ጋር እንዲያያዙ የተደረጉ ሁኔታዎችንና ገደቦችን መግለጽ አለበት፡፡
5. በመደበኛ ወይም ቻርተር በሚደረግ የዓለም አቀፍ የንግድ አየር ትራንስፖርት ለመሠማራት በተሰጠ ፈቃድ የበረራዉ መድረሻና በመሃል አገልግሎት ሊሰጥባቸዉ የሚገቡ ማረፊያ ቦታዎችን መግለጽ ካልተቻለ በረራው ሊከተል የሚገባውን አጠቃላይ የበረራ መስመር ወይም መስመሮች ብቻ መግለፅ ይችላል፡፡

64.<u>ታሪፍ</u>

1. ማንኛዉም የአየር አጓጓዥ ለሚሰጠዉ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት የክፍያ መጠንና አገልግሎቱ የሚሰጥባቸውን ሁኔታዎች ያካተተ ወቅታዊ የሆነ ታሪፍ ከሌለው በስተቀር በአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ሥራ ሊሠማራ አይችልም፡፡
2. ታሪፉ ባለሥልጣኑ በሚወስነው ፎርም የተዘጋጀና ዝርዝር መረጃ የያዘ መሆን አለበት፡፡ የዓለም አቀፍ የአየር ትራንስፖርትን በሚመለከት ተፈጻሚ የሚሆን ታሪፍ እስከተቻለ ድረስ በዓለም አቀፍ ደረጃዎች የተገለጸዉን ፎርምና ይዘት ያሟላ መሆኑን ባለሥልጣኑ ማገናዘብ አለበት፡፡
3. በባለሥልጣኑ እንዲመዘገብ ካልተደረገ በስተቀር ማንኛውም የአየር አጓጓዥ ወይም ወኪሉ ማንኛውንም መንገደኛ ወይም ዕቃ ማጓጓዝን አስመልክቶ በወቅቱ ሥራ ላይ በዋለው ታሪፍ ላይ ከተጠቀሰው ክፍያ በተለየ የዋጋ መጠን ወይም በታሪፉ ውስጥ ከተቀመጠው ድንጋጌ ወይም ሁኔታ ውጭ ለማጓጓዝ ስምምነት መፈጸም አይችልም፡፡

65.<u>የታሪፍ ምዝገባና እግድ</u>

1. በሕግ በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር ማንኛውም ታሪፉ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በአየር አጓጓዡ አማካይነት ለባለሥልጣኑ ቀርቦ መመዝገብ አለበት፡፡
2. ስምምነት የተደረሰባቸውና በሁለትዮሽ የአየር አገልግሎት ስምምነት መሠረት የፀደቁ ታሪፎች መመዝገብ አለባቸው፡፡
3. ባለሥልጣኑ በሥራ ላይ ያለ ታሪፍ አግባብ አይደለም፣ አድሏዊ ነው ወይም የሕዝብ ጥቅምን በማንኛውም መንገድ የሚፃረር ነው ብሎ ካመነ ሊያግደው ይችላል፡፡

66.<u>የማጓጓዝ ውል</u>

1. ማንኛውም ዓይነት የመንገደኛ ወይም የጭነት የአየር አገልግሎት በኪራይ ወይም በክፍያ ሲከናወን ለመንገደኛው ወይም ለአስጫኙ የሚሰጥ ትኬት ወይም የማስጫኛ ሠነድ የማጓጓዝ ውል ሁኔታዎችን መያዝ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለመንገደኛው ወይም ለአስጫኙ ትኬት ወይም የማስጫኛ ሰነድ ካልተሰጠው የአጓጓዡን ኃላፊነት የሚመለከቱ የውል ሁኔታዎችን እንዲያውቅ መደረግ አለበት፡፡ እነዚህ የውል ሁኔታዎችም በባለሥልጣኑ አስቀድመው የተመዘገቡ መሆን አለባቸው፡፡

67.<u>በአየር ትራንፖርት አገልግሎት ሽያጭ ሥራ ስለመሠማራት</u>

1. የአየር አጓጓዥ ካልሆነ ወይም በባለሥልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ሰው በሌላ ሰው በሚካሄድ የአየር ማጓጓዝ ሽያጭ ሥራ ላይ ሊሰማራ አይችልም፡፡
2. ባለሥልጣኑ በአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ሽያጭ ለተሰማሩ ሰዎች ፈቃድ አሠጣጥን የሚመለከት ሥርዓት ሊያወጣ ይችላል፡፡
3. ማንኛውም በአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ሽያጭ ተግባር ላይ የተሰማራ ሰው ባለሥልጣኑ በጽሑፍ ከሚያስታውቅበት ጊዜ ጀምሮ ከባለሥልጣኑ የሚሰጥ ፈቃድ መያዝ አለበት፡፡

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>በዕዳ የመጠየቅ ኃላፊነት</u>

68.<u>የአውሮፕላን ማረፊያ ኦፐሬተሮችና የአየር ናቪጌሽን አገልግሎት ሰጭዎች ኃላፊነት</u>

የአውሮፕላን ማረፊያ ኦፐሬተሮችና የአየር ናቪጌሽን አገልግሎት ሰጭዎች በአሠራር ቸልተኝነት በመንገደኞችና በጭነት ላይ ለሚያደርሱት ጉዳት የሚኖርባቸው

የኃላፊነት መጠን የሚወሰነው በአየር ማጓጓዣ ውል ላይ በሚመለከተው መሠረት ይሆናል፡፡

69.**<u>የአየር አጓጓዦች ለመንገደኞችና ጭነት የሚኖራቸው ኃላፊነት</u>**

በአውሮኘላን ላይ ወይም አውሮፕላን በማሳፈር ወይም በማራገፍ ሂደት በመንገደኞችና በጭነት ላይ ለሚደርስ ጉዳት የአየር አጓጓዦች ኃላፊነት የሚወሰነው ኢትዮጵያ አባል በሆነችባቸው በዓለም አቀፍ የሕግ ሠነዶች ውስጥ በሰፈሩ ሥርዓቶችና ገደቦች መሠረት ይሆናል፡፡

70.**<u>የአውሮፕላን ኦኘሬተሮች በመሬት ላሉ ሦስተኛ ወገኖች የሚኖራቸው ኃላፊነት</u>**

1. ማንኛውም የአውሮፕላን ኦፕሬተር አውሮፕላኑ በበረራ ላይ እያለ በአውሮፕላኑ ወይም በኦፕሬሽኑ ምክንያት ወይም በአውሮፕላኑ ውስጥ ያለ ሰው ወይም እቃ ወይም ከአውሮፕላኑ ጋር የተያያዘ እቃ በመውደቁ ምክንያት በመሬት ላይ ባለ የሶስተኛ ወገን ህይወት፣ አካል ወይም ንብረት ወይም አካባቢ ላይ ለሚደርስ ጉዳት ኃላፊ ይሆናል፡፡[122]
2. በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች በሥራ ላይ ማዋሉ እስከተረጋገጠ ድረስ በአውሮፕላን ማረፊያ ወይም በሌላ ቦታ ባለ ወይም በበረራ ላይ ባለ አውሮፕላን በድምፅና በመርገብገብ ምክንያት ወይም ከሞተሩ ውስጥ በሚወጣ የተቃጠለ አየር ግፊት ምክንያት ብቻ ለሚደርስ ችግር ኦፐሬተሩ በኃላፊነት አይጠየቅም፡፡

**<u>ክፍል ሰባት</u>**

**<u>ስለወንጀል ጥፋቶችና ቅጣቶች</u>**

71.**<u>የዳኝነት ሥልጣን</u>**

1. የኢትዮጵያ ፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚከተሉትን ጥፋቶች በሚመለከት የሚቀርቡ ጉዳዮችን በዳኝነት አይተው የመወሰን ሥልጣን ይኖራቸዋል፤
   ሀ) በኢትዮጵያ በተመዘገበና በማንኛውም ቦታ በተገኘ አውሮኘላን ላይ ወይም በውስጡ የተፈጸመ ማንኛውንም የወንጀል ጥፋት፤
   ለ) የአውሮኘላኑ ዜግነነት ግምት ውስጥ ሳይገባ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የተፈጸመ ማንኛውንም የወንጀል ጥፋት፤

[122] በ26/27(2012) አ.1179 አንቀፅ 2(22) መሰረት ተሻሻለ፡፡

ሐ) ተጠርጣሪ ጥፋተኛውን በውስጡ ይዞ ኢትዮጵያ ውስጥ ያረፈ አውሮፕላን ከኢትዮጵያ ግዛት ውጭ በበረራ ላይ ሳለ በአውሮፕላኑ ውስጥ የተፈፀመ ማንኛውንም የወንጀል ጥፋት፤

መ/ ዋነኛው የንግድ ቦታውን ኢትዮጵያ ውስጥ ባደረገ ወይም ዋነኛ የንግድ ቦታው ኢትዮጵያ ውስጥ ባይሆንም መደበኛ መኖሪያ ቦታው ኢትዮጵያ ውስጥ በሆነ ተከራይ የበረራ አባላትን ሳይጨምር በተከራየ አውሮፕላን ውስጥ የተፈፀመ ማናቸውንም የወንጀል ጥፋት፤

ሠ) ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝና ኢትዮጵያ ተዋዋይ ወገን በሆነችበት ዓለም አቀፍ ስምምነት መሠረት ለሌላ አገር ተላልፎ ባልተሰጠ ተጠርጣሪ ተፈጸመ የተባለን ማንኛውም የወንጀል ጥፋት፡፡

2. የወንጀል ክስ በኢትዮጵያ ውስጥ ለመመሥረት ሲባል በውጭ አገር የተፈፀመ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰ ማንኛውም የወንጀል ጥፋት በኢትዮጵያ ውስጥ እንደተፈጸመ ይቆጠራል፡፡

3. ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት የወንጀል ጥፋት ሊባል የሚችል ድርጊት በመፈጸሙ ወይም ማድረግ ያለበትን ባለማድረጉ በዚህ አዋጅ ወይም በሌላ ሕግ በኢትዮጵያ ውስጥ ወይም ከኢትዮጵያ ውጭ ክስ ቀርቦበት ከተፈረደበት ወይም ነጻ ከወጣ በተመሳሳይ ጥፋት በኢትዮጵያ ውስጥ እንደገና ሊከሰስ አይችልም፡፡

72.<u>በሲቪል አውፎኘላን ዉስጥ የተከለከሉትን ድርጊቶችን መፈጸም</u>[123]

1. ማንኛውም ሰው ሆን ብሎና ከህግ ውጭ በሆነ ሁኔታ፣

ሀ) በአውሮኘላን ውስጥ መፀዳጃ ክፍልን ጨምሮ በማንኛውም ቦታ ቢያጨስ፣ ወይም

ለ) በበረራ ላይ መጠቀም የተከለከሉ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎችን ሲጠቀም ቢገኝ፤ ከብር ሃምሳ ሺ በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአንድ ዓመት በማይበልጥ እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡[124]

2. ማንኛውም ሰው ሆነ ብሎና ከሕግ ውጭ በሆነ ሁኔታ በአውሮፕላን ላይ በተገጠመ የጭስ መቆጣጠሪያ ወይም ሌላ ከደህንነት ጋር የተያያዘ ዕቃ ያለ

[123] በ26/27(2012) አ.1179 አንቀፅ 2(24) መሰረት ንዑስ አንቀፅ 3 እና 4 አዲስ የገቡ ናቸው፡፡
[124] በ26/27(2012) አ.1179 አንቀፅ 2(23) መሰረት ተሻሻለ፡፡

አግባብ በመነካካት ቢያሰናክል ከብር 100,000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

3. ማንኛውም ሰው ሆን ብሎ አውሮፕላን በበረራ ላይ እያለ የሌዘር ጨረራ ወይም ሌላ ማንኛውንም ዓይነት ጨረራ ወደ አውሮፕላን በመልቀቅ እንቅስቃሴ ያወከ፣ አቅጣጫ ያሳተ ወይም ለአደጋ ወይም አጋጣሚ እንዲጋለጥ ያደረገ እንደሆነ እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡
4. ማንኛውም ሰው በንዑስ አንቀጽ (3) ላይ የተመለከተውን ድርጊት በቸልተኝነት የፈጸመ እንደሆነ እስከ አራት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

73.<u>አደጋ የደረሰበትን አውሮፕላን ክፍሎች ስለመዉሰድ</u>

ማንኛውም ሰው ሆን ብሎና ሥልጣን ሳይሰጠው አደጋ የደረሰበትን የሲቪል አውሮፕላን ማንኛውንም አካል ወይም አደጋው በደረሰበት አውሮፕላን ውስጥ የነበረ ማንኛውንም ንብረት ቢያነሳ፣ ቢደብቅ ወይም በይዞታው ሥር ቢያደርግ ከብር 100,000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

74.<u>ሪፖርት ማድረግና ሪከርድ መያዝን ስለመተላለፍ</u>

ማንኛውም ሰው፣

1. በዚህ አዋጅ ወይም በአዋጁ መሠረት በወጣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ትዕዛዝ መሠረት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ የሚገባውን ሪፖርት ሳያቀርብ ከቀረ፣
2. መያዝ ያለበትን ሪኮርድ ባለሥልጣኑ በወሰነው ፎርምና አኳኋን መሠረት ሳይዝ ከቀረ፣
3. ማንኛውንም ሪፖርት ወይም ሪኮርድ ከጥቅም ውጭ እንዲሆን ወይም እንዲለወጥ ካደረገ፣ ወይም
4. የተሳሳተ ሪፖርት ወይም ሠነድ ካቀረበ፣

ከብር 100,000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

75.<u>በአስቸኳይ ጊዜ የተሰጠን ትዕዛዝ ስለመጣስ</u>

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 (1) መሠረት በሚኒስቴሩ የተሰጠውን የአስቸኳይ ጊዜ ትዕዛዝ ከተላለፈ ጥፋተኛ እንደሆነ ተቆጥሮ ከብር 150,000

በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከሦስት ዓመት በማይበልጥ እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፤

**76.አጠቃላይ የወንጀል ድንጋጌዎች**

የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ በኢትዮጵያ አየር ክልል በሚበር አውሮፕላን ውስጥ የተፈጸመ የወንጀል ድርጊት በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት የሚያስቀጣ ይሆናል፡፡

**ክፍል ስምንት**

**አስተዳደራዊ የቅጣት እርምጃዎች**

**77.ጠቅላላ**

1. አስተዳደራዊ እርምጃ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችን፣ መመሪያዎችንና ትዕዛዞችን በመተላለፍ የሚፈጸሙ ጥፋቶችን በሚመለከት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 78 መሠረት የሚጣሉ የገንዘብ መቀጮዎችን እንዲሁም የምስክር ወረቀቶችንና ፈቃዶችን በከፊል ወይም በሙሉ ማገድና መሠረዝን ያካትታል፡፡
2. ባለሥልጣኑ አስተዳደራዊ የቅጣት እርምጃዎችን በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሠረት መወሰንና ማስፈጸም ይችላል፡፡

**78.በገንዘብ ስለሚፈጸሙ አስተዳደራዊ ቅጣቶች**

ስለወንጀል ኃላፊነት በዚህ አዋጅ ክፍል ሰባትና በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤

1. የዚህን አዋጅ አንቀጽ 40 (1) ወይም (2) የተላለፈ ማንኛውም የውጭ አገር ሲቪል አውሮፕላን ኦፕሬተር እስከ አምስት ሚሊየን የኢትዮጵያ ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፤[125]
2. ከንግድ አየር ትራንስፖርት ውጭ በሆነ ኦፕሬሽን የተሰማራ ማንኛውም የሲቪል አውሮፕላን ኦፕሬተር፣ የአቪዬሽን ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት፣ የአውሮፕላን ጥገና ተቋም፣ የአውሮፕላን ባለቤት ወይም ተከራይ፣ የአቭዬሽን ባለሙያ ወይም በአቭዬሽን ሥርዓት ውስጥ የኃላፊነት ድርሻ ያለው ማንኛውም ሰው የዚህን አዋጅ ድንጋጌ ወይም በዚህ አዋጅ መሰረት የወጣን ደንብ፣፤መመሪያ ወይም ትዕዛዝ ተላልፎ ሲገኝ እንደጥፋቱ ክብደት ከብር ሦስት መቶ ሺ በማያንስ እና ከብር

[125] በ26/27(2012) አ.1179 አንቀፅ 2(25) መሰረት ተሻሻለ፡፡

አራት መቶ ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፣ የዚህ ዓይነቱ መተላለፍ ቀጣይነት ካለው እያንዳንዱ ቀን እንደተለያየ ጥፋት ይቆጠራል፡፡[126]

3. በንግድ አየር ትራንስፖርት ኦፕሬሽን የተሰማራ ማንኛውም የሲቪል አውሮፕላን ኦፕሬተር የዚህን አዋጅ ድንጋጌ ወይም በዚህ አዋጅ መሰረት የወጣን ደንብ፣ መመሪያ ወይም ትዕዛዝ ተላልፎ ሲገኝ እንደ ጥፋቱ ክብደት ከብር አራት መቶ ሺ በማያንስ እና ከብር አምስት መቶ ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፣ የዚህ ዓይነቱ መተላለፍ ቀጣይነት ካለው እያንዳንዱ ቀን እንደተለያየ ጥፋት ይቆጠራል፡፡[127]

79.<u>ለባለሥልጣኑ ስለሚቀርብ ቅሬታና በባለሥልጣኑ ስለሚደረግ ምርመራ</u>

1. ማንኛውም ሰው የዚህን አዋጅ ድንጋጌ ወይም በአዋጁ መሠረት የወጣን ደንብ፣ መመሪያ ወይም ትዕዛዝ በመተላለፍ በማንኛውም ሰው የተፈጸመ ወይም መፈጸም ሲገባው ሳይፈጸም የቀረ ጉዳይን አስመልክቶ ቅሬታውን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ባለሥልጣኑ የቀረበው ቅሬታ ምርመራ ወይም እርምጃ ለመውሰድ የሚያበቃ ምክንያትን አይገልጽም ብሎ ሲያምን ተጨማሪ ማጣራት ሳያስፈልግ ቅሬታውን ወዲያውኑ ሊሰረዘው ይችላል፡፡
3. ባለሥልጣኑ የዚህን አዋጅ ድንጋጌ ወይም በአዋጁ መሠረት የወጣን ደንብ፣ መመሪያ ወይም ትዕዛዝ ሥራ ላይ ከማዋል ጋር በተያያዘና በሥልጣኑ ክልል ሥር በሚወድቅ ጉዳይ ላይ በማንኛውም ጊዜ በራሱ አነሳሽነት ምርመራ ለማካሄድ ይችላል፡፡
4. በባለሥልጣኑ ምርመራ የተገኙ የፍሬ ነገር ውጤቶች በጉልህ ማስረጃ የተደገፉ እስከሆኑ ድረስ የመጨረሻ ማረጋገጫ ይሆናሉ፡፡

80.<u>ስለምርመራ አካሄድ</u>

1. ባለሥልጣኑ ማንኛውንም አስተዳደራዊ እርምጃ ከመውሰዱ በፊት ሊወስደው ስላሰበው እርምጃ ለሚመለከተው ሰው ማሳወቅና የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር እርምጃው ሊወሰድ አይገባም የሚልበትን ምክንያት እንዲያስረዳ እድል መስጠት አለበት፡፡

---

[126] በ26/27(2012) አ.1179 አንቀፅ 2(26) መሰረት ተሻሻለ፡፡
[127] በ26/27(2012) አ.1179 አንቀፅ 2(27) መሰረት ተሻሻለ፡፡

2. ባለሥልጣኑ የሚያደርገው ምርመራ ለተገቢ የንግድ እንቅስቃሴ አፈጻጸምና ለፍትሕ መስፈን አመቺ በሆነ መንገድ መካሄድ አለበት፡፡
3. ማናቸውም የባለሥልጣኑ ሠራተኛ የግል ጥቅሙን በሚነካ የምርመራ ሂደት መሳተፍ የለበትም፡፡
4. ማንኛውም ምርመራዉ የሚመለከተው ሰው በምርመራዉ ሂደት ላይ ራሱ ወይም በጠበቃው አማካይነት ተገኝቶ ክርክሩን ሊያሰማ ይችላል፡፡
5. ባለሥልጣኑ ከብሔራዊ ጥቅም አኳያ የምርመራው ሂደት ለሕዝብ ክፍት እንዳይሆን ካልወሰነ በስተቀር በጉዳዩ ያገባኛል የሚል ማንኛውም ሰው ሲጠይቅ ለሕዝብ ክፍት መደረግ አለበት፡፡

81.<u>ማስረጃ ስለማስቀረብ</u>

1. ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 80 መሠረት በሚያደርገው የምርመራ ሂደት ምስክሮች እንዲቀርቡና የምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ እንዲሁም ምርመራው ከሚካሄድባቸው ጉዳዮች ጋር ግንኙነት ያላቸው ሠነዶች እንዲቀርቡ የማድረግ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡
2. በማስረጃነት የሚፈለጉት ምስክሮችና ሠነዶች ከማንኛውም ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኝ ቦታ ክርክር እንዲካሔድበት ወደ ተመረጠው ማንኛውም ቦታ እንዲቀርቡ ማድረግ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ መሠረት የተሰጠን ትዕዛዝ ተቀብሎ ያለመፈጸም እምቢተኝነት ሲያጋጥም ምስክሮቹ እንዲቀርቡና እንዲመሰክሩ እንዲሁም በማስረጃነት የሚፈለጉት ሠነዶች እንዲቀርቡ ለማስገደድ ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው ባለጉዳይ የፌዴራል ፍርድ ቤትን እርዳታ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

82.<u>የባለሥልጣኑ ውሳኔ</u>

ባለሥልጣኑ ማንኛውንም አስተዳደራዊ እርምጃ ለመውሰድ በሚወስንበት ጊዜ፤

1. የጥፋቱን ባህርይ፣ የተፈጸመበትን ከባቢያዊ ሁኔታ፣ ያስከተለውን ውጤት መጠንና አስከፊነት፣
2. ጥፋቱን የፈፀመውን ሰው የጥፋተኝነት ደረጃና ቀደም ሲል የፈጸማቸውን ጥፋቶች ታሪክ፣
3. የገንዘብ መቀጮን የሚመለከት ሲሆንም የአጥፊውን የመክፈል ችሎታና ሥራውን ለመቀጠል ባለው ችሎታ ላይ የሚያስከትልበትን ተጽዕኖ፣ እና

4. ሌሎች ከፍትህ አንፃር መታየት ያለባቸውን ጉዳዮች፣

ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

## 83.ስለይግባኝ

1. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 79 (4) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በባለሥልጣኑ ማንኛውንም የአስተዳደር እርምጃ ለመውሰድ የተሰጠ ትዕዛዝ ለሚመለከተው ሰው በደረሰው በአስር ቀናት ውስጥ አቤቱታ ሲቀርብ በሚኒስቴሩ እንደገና እንዲታይ ይደረጋል፡፡ የሚኒስቴሩ ውሳኔም የመጨረሻ ይሆናል፡፡
2. አቤቱታው እንደቀረበ ሚኒስቴሩ ቅጂውን ለባለሥልጣኑ መላክ አለበት፡፡ ባለሥልጣኑም ቅሬታው የቀረበበትን ጉዳይ በሚመልከት ምርመራ ሲካሄድ የተያዘውን መዝገብ ለሚነስቴሩ ማስተላለፍ አለበት፡፡
3. የባለሥልጣኑን ውሳኔ ለመቃወም መሠረት የተደረገው ማንኛውም የመከራከሪያ ነጥብ አስቀድሞ ለባለሥልጣኑ ቀርቦ የነበረ ካልሆነ ወይም ሊቀርብ ያልቻለው በበቂ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ለሚነስቴሩ ሊቀርብ አይችልም።
4. ባለሥልጣኑ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ መኖሩንና ለሲቪል አቪዬሽን ደህንነት ትዕዛዙ ወዲያውኑ እንዲፈጸም አስፈላጊ መሆኑን ለሚኒስቴሩ ካላስረዳና ትዕዛዙ ተግባራዊ እየሆነ እንዲቆይ በሚኒስቴሩ ካልታዘዘ በስተቀር በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚቀርብ ይግባኝ ማንኛውንም የባለሥልጣኑን ትዕዛዝ ተፈፃሚነት አግዶ ያቆየዋል፡፡

## 84.የአስተዳደራዊ እርምምጃ አፈጻጸም

1. ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የተወሰኑ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ለማስፈጸም ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 78 የተመለከተዉ የጥፋት ድርጊት ሲፈጸም በጥቅም ላይ የዋለው የሲቪል አውሮፕላን በባለሥልጣኑ ለተወሰነ መቀጮ ማስፈጽሚያነት በዕዳ ሊያዝ ይችላል፡፡
3. ማንኛውም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት መያዣ የሚደረግ አዉሮኘላን በባለሥልጣኑ ተይዞ በቁጥጥሩ ሥር ሊውል ይችላል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 85.ፋሲሊቴሽን

1. ባለሥልጣኑ በኮንቬንሽኑ አንቀጽ 22 መሠረት በኢትዮጵያና በሌሎች አገሮች መካከል የአየር ናቪጌሽን አገልግሎት ለማመቻቸትና ለማቀላጠፍ የሚያስችሉ አሠራሮች እንዲኖሩ ያደርጋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሱት አሠራሮች በተቻለ መጠን በኮንቬንሽኑ መሠረት ከወጡት ደረጃዎችና ተመራጭነት ካላቸው አሠራሮች ጋር መጣጣም አለባቸው፡፡
3. ባለሥልጣኑ ፋሲሊቴሽንን በተመለከተ ኢትዮጵያ ተዋዋይ ወገን የሆነችባቸውን አለም አቀፍ ስምምነቶች ተግባራዊነትና መከበራቸውን ይከታተላል፡፡ የክትትሉን ውጤትም ለሚመለከተው የመንግሥት አካል ሪፖርት ያደርጋል፡፡
4. በመድረሻና በመሄጃ ወቅት በክሊራንስ ተግባሮች ላይ የሚሳተፉ የተለያዩ አካላትን የተለያዩ ሥራዎች ለማቀናጀት የብሔራዊ ፋሲሊቴሽን ኮሚቴና የኤርፖርቶች ፋሲሊቴሽን ኮሚቴዎች እንደ አማካሪ አካላት ሆነው ይቋቋማሉ፡፡

86.<u>የሜትሮሎጂ አገልግሎት</u>

1. ባለሥልጣኑ የአውሮፕላን ኦፐሬሽንን ደህንነት፣ ኢኮኖሚያዊነትና ቀጣይነት ለማረጋገጥ እንዲሁም ኮንቬንሽኑን ተፈጻሚ ለማድረግ ሲባል አስፈላጊ ነው በሚለው ቦታና ሁኔታ ከብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ጋር በመስማማት የኤሮኖቲካል ሜቲዎሮሎጂ አገልግሎት እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡
2. ባለሥልጣኑ የኤሮኖቲካል ሜቲዎሮሎጂ አገልግሎት የሚሰጥበትን ሁኔታና ፋሲሊቲ ሊመረምርና የጥራት ደረጃውን ሊወስን ይችላል፡፡

87.<u>መፈለግና ማዳን</u>

1. ባለሥልጣኑ፣
   ሀ) በኢትዮጵያ የድንበር ክልል ውስጥ ለጠፋ ወይም ችግር ለደረሰበት አውሮፕላን የተፈለገውን እርዳታ የሚሰጡ የፈልጎ ማዳን ቡድኖችን ያቋቁማል፤
   ለ) አገልግሎቱን ሲሰጥ የሰው ኃይልና ንብረት በጋራ መጠቀም እንዲቻል መንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶችንና ሌሎች ድርጅቶችን ያስተባብራል፤
2. የጠፋው ወይም ችግር የደረሰበት አውሮፕላን በሌላ አገር የተመዘገበ ከሆነ የአዉሮኘላኑ ባለቤት ወይም የዚያ አገር ባለሥልጣናት ሁኔታዎች የሚጠይቁትን አስፈላጊ የእርዳታ እርምጃዎች ሁሉ እንዲወሰዱ ባለስልጣኑ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

ሆኖም የሚሰጠው ማናቸውም ዓይንት እርዳታ ሁልጊዜም ባለሥልጣኑ የሚቆጣጠረዉ መሆን አለበት፡፡

3. ባለሥልጣኑ ከሌላ አገር ጋር አዋሳኝ በሆነ አካባቢ ለጠፋ ወይም ችግር ለደረሰበት አዉሮፐላን ከሌላዉ አገር ወይም አለም አቀፍ ድርጅት የፈልጎ ማዳን እርዳታ ጥያቄ ሲቀርብለት ጥያቄዉን አጢኖ በፈልጎ ማዳኑ ተግባር ተሳታፊ መሆን ይችላል፡

88.[128]

89.<u>ሪፖርት የማድረግ ግዴታ</u>

1. የሲቪል አቪዬሽን ሠራተኞች፣
   ሀ) ይህንን አዋጅ ወይም በአዋጁ መሠረት የወጣን ደንብ፣ መመሪያ ወይም ትዕዛዝ የመተላለፍ ጥርጣሬ ሲኖር፣
   ለ) የሲቪል አቪዬሽን ደህንነትን የሚጐዳ ወይም ሊጎዳ የሚቻል ማንኛውም አጋጣሚ ወይም ድርጊት ሲኖር፣ ወይም
   ሐ) ማንኛውም የአውሮኘላን አደጋ ሲያጋጥም፣ ባለሥልጣኑ በሚፈልገዉ ጊዜና ፎርም መሠረት ሪፖርት የማድረግ ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡
2. ባለሥልጣኑ ማናቸውንም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የቀረበ ሪፖርት በአፋጣኝ መመርመርና የሚወሰድ ቀጣይ እርምጃም ካለ መወሰን ይኖርበታል፡፡

90.<u>የአገልግሎትና የፈቃድ ክፍያዎች</u>

1. በባለሥልጣኑ ወይም በባለሥልጣኑ ስም በኢትዮጵያ የአየር ክልል ውስጥ በበረራ ላይ ያለን አውሮፐላን በተመለከተ ለሚሰጡ የአየር ናቪጌሽን አገልግሎቶች ባለሥልጣኑ የአገልግሎት ክፍያ ሊያስከፍል ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚጠየቀዉ ክፍያ በባለሥልጣኑ ወይም በባለሥልጣኑ ስም፣
   ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥ በሚደረግ በረራ ወቅት ወይም በረራው በኢትዮጵያ ውስጥ ሲጀመር ወይም ሲያልቅ ወይም የበረራዉ ክፍል በኢትዮጵያ ውስጥ ሲደረግ የተሰጠ አገልግሎትን፣ ወይም
   ለ) በማንኛውም ኤርፖርት የተሰጠ አገልግሎትን፣

[128] በ22/84 (2008) አ. 957 አንቀጽ 28(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

የሚመለከት ሊሆን ይችላል፤

3. በባለሥልጣኑ የሚጠየቀው የፈቃድ ክፍያ በዚህ አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት በወጣ ደንብ በተደነገገው መሠረት ማንኛውንም ፈቃድ ወይም የምስክር ወረቀት መስጠትን፣ ማደስን፣ ማሻሻልን ወይም ማጽደቅን የሚመለከት ሊሆን ይችላል፡፡
4. የተመዘገቡት የአውሮኘላን ባለቤትና ኦፐሬተር አውሮኘላኑን አስመልክቶ ለተሰጠ አገልግሎት ክፍያ በአንድነትና በተናጠል ኃላፊ ይሆናሉ፡፡
5. ባለሥልጣኑ ለተመዘገበው የአውሮፐላኑ ባለቤት ወይም ኦፐሬተር ክፍያውን ከነወለዱ እንዲፈጽም በጽሑፍ ካስታወቀው በኋላ በማስታወቂያው በተገለጸው ጊዜ ውስጥ ባለዕዳው ግዴታውን ካልተወጣ አውሮፐላኑን ይዞ ሊያቆየው ይችላል፡፡
6. ባለዕዳው፣

   ሀ) ክፍያውን በጥሬ ገንዘብ ወይም በተረጋገጠ ቼክ ሲፈጽም፣ ወይም

   ለ) ባለሥልጣኑ በሚቀበለዉ ፎርም መሠረት የተዘጋጀና አውሮፐላኑ ተይዞ የቆየበትን የዕዳ መጠን የሚሸፍን ቦንድ ወይም ሌላ ዋስትና ሲያሲዝ፣

   ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት ይዞ ያቆየውን አውሮፐላን ይለቃል፡፡

## 91.የአዉሮፐላን እገዳ

1. በኮንቬንሽኑ አንቀጽ 27 ተራ ፊደል (ሐ) ያልተሸፈነ የአንድ አገር አውሮኘላን ወይም የአዉሮኘላኑ ክፍል በኢትዮጵያ ውስጥ ጥበቃ የሚደረግለትን የፈጠራ ሥራ፣ ዲዛይን ወይም ሞዴል ተላልፏል በሚል ያገባኛል የሚል ሰው ክስ ካቀረበ ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት አዉሮኘላኑ በኢትዮጵያ ውስጥ ሲያቋርጥ እንዲያዝና እንዳይንቀሳቀስ ሊያግድ ይችላል፡፡
2. የአውሮኘላኑ ባለቤት ከባለጉዳዩ ጋር ስምምነት ላይ የደረሰበትን ወይም ፍርድ ቤቱ በመጨረሻ ከሚፈርደዉ ጋር የሚመጣጠን ይሆናል ብሎ የሚወስነውን የገንዘብ መጠን ሲያስቀምጥ ወይም ዋስትና ሲሰጥ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተወሰነው የአውሮፐላኑ እግድ ይነሳል፡፡
3. የዚህን አዋጅ መከበር ለማረጋገጥ በባለሥልጣኑ የአዉሮኘላን እገዳ እንዲፈጸም የሚደረግበት ሁኔታ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ ሊደነገግ ይችላል፡፡

## 92.ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ባለሥልጣኑ ይህን አዋጅ በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሥርዓቶችንና ደረጃዎችን ያያዙ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

93.<u>የመመሪያዎች አወጣጥና ሕትመት</u>

1. ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ መሠረት ማንኛውንም መመሪያ ከማውጣቱ በፊት፣
   ሀ) የኢትዮጵያ የሲቪል አየር ትራንስፖርት ኢንዱስትሪን፣
   ለ) የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ተጠቃሚዎችን፣ እና
   ሐ) የሚመለከታቸው ሌሎች አካላትን፣
   ሊወክሉ ይችላሉ ብሎ የሚገምታቸውን ሰዎች ማማከር አለበት፡፡
2. ባለሥልጣኑ በየጊዜው የሚያወጣቸውን መመሪያዎች የማሳተም ኃላፊነት አለበት፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ማንኛውም መመሪያ የሚታተምበት ሁኔታ ባለሥልጣኑ በሚወስነው መሠረት ይሆናል፡፡

94.<u>የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>

1. የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 273/1994 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ፣ ትዕዛዝ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

95.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ የካቲት 5 ቀን 2001 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 957/2008

## የኢትዮጵያ የአውሮፕላን አደጋ እና የአደጋ አጋጣሚ ምርመራ አዋጅ

በአገሪቱ እያደገ የመጣውን የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ደህንነት ለማረጋገጥና የአደጋ ስጋትን ለመከላከል የአውሮፕላን አደጋን በገለልተኝነት በመመርመርና በመተንተን በመንስኤዎችና አስተዋጽኦ በሚያደርጉ ሁኔታዎች ላይ ወቅታዊ የጥንቃቄ ምክረ-ሃሳቦችን በመስጠት ቀጣይ አደጋና አጋጣሚዎችን የሚከላከል የአሰራር ሥርዓት መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤

አገሪቱ የገባቻቸውን ዓለም ዓቀፋዊ ግዴታዎች በተለይም እ.ኤ.አ በ1944 በወጣው የቺካጎ ኮንቬንሽን ተቀጽላ 13 መሠረት በዓለም አቀፍ ደረጃ የተቀመጠውን መስፈርት ለማሟላት የአውሮፕላን አደጋ እና የአደጋ አጋጣሚን የሚመረምር አካል የማቋቋም ኃላፊነት ያለባት በመሆኑ፤

የአውሮፕላን አደጋ እና የአደጋ አጋጣሚ ምርመራ የሚፈፀምበትንና የሚተገበርበትን ሥርዓት በሕግ መወሰን በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ የአውሮፕላን አደጋ እና የአደጋ አጋጣሚ ምርመራ አዋጅ ቁጥር 957/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

   1. "አውሮፕላን" ማለት በጠፈር ውስጥ በአየር ለመንሳፈፍ የሚያስችለውን ድጋፍ ከመሬቱ ገጽታ ሳይሆን ከአየሩ ሁኔታ የሚያገኝ ማንኛውም በራሪ መሣሪያ ነው፤
   2. "አደጋ" ማለት ማንኛውም ሰው በአውሮፕላን ለመብረር በማሰብ በአውሮፕላን ከተሳፈረበት ጊዜ ጀምሮ ሁሉም ሰው እስከሚወርድበት ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ከአውሮፕላኑ እንቅስቃሴ ጋር በተገናኘ የሚፈጠር ክስተት ሆኖ፡-

ሀ) በተፈጥሮ ምክንያት፣ በራሱ ወይም በሌሎች ሰዎች ድርጊት ምክንያት ወይም ለመንገደኞች ወይም ለአውሮፕላን ሠራተኞች ከሚገባው ቦታ ውጭ በድብቅ ሲጓዝ ከሚደርስ ጉዳት በስተቀር:-

1) በአውሮፕላኑ ውስጥ በመሆኑ፣ ወይም

2) ከአውሮፕላኑ አካል ጋር፣ ከአውሮፕላኑ ከተያያዙ ወይም ከተገነጠሉ አካላት ጋር በቀጥታ በመነካካቱ፣ ወይም

3) ለአውሮፕላኑ ጄት ፍንዳታ በቀጥታ በመጋለጡ የሚያጋጥም የሰው ሕይወት መጥፋት ወይም ከባድ የአካል ጉዳት፣ ወይም

ለ) በአውሮፕላኑ ሞተር ካዉሊንግስ ወይም ተጨማሪ ክፍሎች ላይ ከሚወሰን የሞተር ብልሽት ወይም በተሽከርካሪ አካሉ፣ ክንፉ ጫፍ፣ በአንቴናው፣ በጎማው ወይም በፍሬኑ ላይ ከሚደርስ ብልሽት ወይም በውጭ አካሉ ላይ ከሚደርሱ ትንንሽ ቀዳዳዎች ወይም ስንጥቆች በስተቀር:-

1) የአውሮፕላኑን የበረራ ባህርይ፣ የበረራ ብቃት ወይም አካል ጥንካሬ የሚያሳጣ፤

2) የተጎዳው የአውሮፕላኑ አካል ከባድ ጥገና እንዲደረግለት ወይም እንዲለወጥ የሚያስገድድ፣ የአውሮፕላን መጎዳት ወይም መበላሸት፣ ወይም

ሐ) አውሮፕላን መጥፋት ወይም ጨርሶ የማይደረስበት መሆን፣

ነው፤

3. “ከባድ የአካል ጉዳት” ማለት በአደጋ ምክንያት የደረሰ የአጥንት ስብራት፣ የአካል መጋጋጥ፣ የውስጥ አካል ጉዳት፣ ከ5 ፐርሰንት በላይ የሰውነት አካልን የሚሸፍን የሰውነት ቃጠሎ፣ የሰውነት መመረዝ ወይም የጨረር ጉዳት ወይም ከ48 ሰዓት በላይ በሆስፒታል የሚያስተኛ የአካል ጉዳት አይነት ነው፤

4. “ከባድ አደጋ አጋጣሚ” ማለት ከአውሮፕላን ኦፕሬሽን ጋር በተያያዘ ሁኔታ አደጋ የመድረስ ዕድሉ ከፍተኛ የነበረ አጋጣሚ ሆኖ ማንኛውም ሰው በአውሮፕላን ከተሳፈረበት ጊዜ ጀምሮ እስከሚወርድ ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ የሚደርስ ክስተት ነው፤

5. “አጋጣሚ” ማለት ከአውሮፕላን አደጋ ወይም ከከባድ የአደጋ አጋጣሚ ውጭ የአውሮፕላን እንቅስቃሴ ደህንነትን አስጊ ሁኔታ ላይ ሊያደርስ ወይም ሊጎዳ የሚችል ክስተት ወይም ሁኔታ ነው፤

6. “ክስተት” ማለት ከአውሮፕላን ኦፕሬሽን ጋር በተያያዘ ለደህንነቱ ክትትል ሳይደረግበት ቢቀር ለአውሮፕላን አደጋ፣ ለአደጋ አጋጣሚ ወይም ለአጋጣሚ መንስኤ ሊሆን የሚችል ሁኔታ ነው፤
7. “መንስኤ” ማለት ማንኛውም ለአደጋ፣ ለከባድ አጋጣሚ ወይም ለአጋጣሚ መነሻ ሊሆን የሚችል ድርጊት፣ አለማድረግ፣ ክስተት፣ ሁኔታ ወይም የእነዚህ ጥምረት ነው፤
8. “አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ሁኔታዎች” ማለት ማንኛውም ድርጊት፣ አለማድረግ፣ ክስተት፣ ሁኔታ፣ ምክንያት ወይም የእነዚህ ሁሉ ጥምረት ሆኖ እነዚህ ሁኔታዎች ቢጠፉ፣ ባይኖሩ ወይም ቢቀሩ የአውሮፕላን አደጋ ወይም አጋጣሚ የመከሰት ዕድሉን የሚያስቀር ወይም የሚቀንስ ወይም አደጋው ሊያደርስ ይችል የነበረውን የከፋ ጉዳት የሚቀንስ ሁኔታ ነው፤
9. “የአደጋ ምርመራ” ማለት አደጋን ለመቀነስ ዓላማ መረጃ ማሰባሰብን እና መተንተንን፣ ድምዳሜ ላይ መድረስን፣ የአደጋውን መንስኤ መወሰንን ጨምሮ እንደአስፈላጊነቱ የጥንቃቄ ምክረ-ሀሳብ መስጠትን የሚያካትት ሂደት ነው፤
10. “መርማሪ” ማለት የምርመራ ተግባርን ለማከናወን በአደጋ ምርመራ ቢሮ የተወከለ ባለሙያ የሆነ ሰው ነው፤
11. “የምርመራ ኃላፊ” ማለት የአደጋ ምርመራ ሥራን በኃላፊነት ለማስተባበር፣ ለመምራትና ለመቆጣጠር በሙያው የተመደበ ሰው ነው፤
12. “ሥልጣን የተሰጠው ተወካይ” ማለት በኢትዮጵያ የተመዘገበ አውሮፕላን በውጭ አገር አደጋ ሲደርስበት ምርመራ ላይ እንዲሳተፍ ኢትዮጵያን በመወከል ወይም ከኢትዮጵያ ውጭ የተመዘገበ አውሮፕላን በኢትዮጵያ ውስጥ አደጋ ሲደርስበት የመዘገበው ሀገር ወይም ሌላ የሚመለከተው ሀገር በኢትዮጵያ ውስጥ ለመሳተፍ በሙያው የተሰየመ ሰው ነው፤
13. “አማካሪ” ማለት በአደጋ ምርመራ ወቅት ስልጣን የተሰጠውን ተወካይ በሙያው ለማማከር የተመደበ ሰው ነው፤
14. “ተሳታፊ” ማለት ምርመራ በሚደረግበት ጉዳይ ላይ ጥቅም ያለውና በምርመራው ሂደት መሳተፉ ለቢሮው የምርመራ ግብ መሳካት ሙያዊ አስተዋጽኦ ማድረግ የሚችል መሆኑ ታምኖበት በምርመራ ሂደት እንዲሳተፍ በሚኒስቴሩ የተሰየመ ሰው ነው፤

15. “ታዛቢ” ማለት በደረሰው አደጋ ጥቅም ያለው አካል የወከለውና በምርመራው ላይ በታዛቢነት እንዲገኝ በቢሮው የተፈቀደለት ሰው ነው፤
16. “ጥቅም ያለው አካል” ማለት በአውሮፕላን አደጋ ወይም ከባድ አጋጣሚ ላይ ቀጥተኛ ጥቅም ያለው ሚኒስቴር፣ ባለስልጣን፣ መንግስታዊ ወይም መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው፤
17.“የአየር ትራፊክ ቁጥጥር ክፍል” ማለት የአየር ክልል፣ የመነሻና የመቃረቢያ አካባቢ ወይም የአውሮፕላን ማረፊያ ክልል ትራፊክን የሚቆጣጠር ክፍል ነው፤
18. “ኦፕሬተር” ማለት በአውሮፕላን ኦፕሬሽን የተሰማራ ወይም ለመሰማራት ጥያቄ ያቀረበ ሰው ነው፤
19.“ዋና አብራሪ” ማለት አውሮፕላኑ በረራ ላይ እያለ ለአውሮፕላኑ ኦፕሬሽንና ደህንነት ኃላፊ የሆነ ሰው ነው፤
20.“የበረራ አባል” ማለት በበረራ ወቅት በአውሮፕላን ውስጥ በኦፕሬተሩ ለሥራ የተመደበ ሰው ነው፤
21.“ኮንቬንሽን” ማለት እ.ኤ.አ ዲሴምበር 7 ቀን 1944 በቺካጎ የተፈረመው የአለም አቀፍ የሲቪል አቪዬሽን ስምምነት እና ተቀጽላዎች ናቸው፤
22.“ተቀጽላ 13” ማለት ከአውሮፕላን አደጋ እና ከአደጋ አጋጣሚ ምርመራ ጋር በተያያዘ ደረጃና የተመረጠ አሰራርን ያካተተ የዓለም ዓቀፉ የሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ኮንቬንሽን ተቀጽላ ነው፤
23.“ሰነድ” ማለት ማንኛውም የደብዳቤ ልውውጥ፣ መግባቢያ ሰነድ፣ መጽሐፍ፣ ዕቅድ፣ ካርታ፣ የተሳለ ንድፍ፣ ስዕላዊ ወይም ግራፍ፣ ፊልም፣ የድምፅ መቅጃ፣ ቪዲዮ ቴፕ፣ ኤሌክትሮኒክ መዛግብት እና መረጃ እና የእነዚህ ማንኛውም ቅጅ ነው፤
24.“መረጃ” ማለት በጥቅል ወይም በከፊል፣ በቃል ወይም በጽሑፍ ወይም የተቀዳና ከአደጋ ወይም ከከባድ አደጋ አጋጣሚ ጋር ግንኙነት ያለው ለቢሮው የተሰጠ መረጃ ነው፤
25.“የበረራ መመዝገቢያ ሳጥን” ማለት የአደጋ ወይም የአደጋ አጋጣሚ ምርመራ ሥራን የሚያግዝ ማንኛውም በአውሮፕላን ላይ የሚገጠም መመዝገቢያ መሣሪያ ነው፤
26.“የማጠቃለያ ረቂቅ ሪፖርት” ማለት በረቂቅ ሪፖርቱ ላይ አስተያየት እንዲሰጥበት፣ ሥልጣን ለተሰጠው ተወካይ እና በቢሮው እምነት በምርመራ ግኝቱ ላይ ቀጥተኛ

ጥቅም ላለው አካል በሚኒስትሩ አማካኝነት በምስጢር የሚላክ የምርመራ ረቂቅ ሪፖርት ነው፤

27. “የጥንቃቄ ምክረ-ሀሳብ” ማለት ተመሳሳይ የአውሮፕላን አደጋ ወይም የአደጋ አጋጣሚ ዳግም እንዳይከሰት ለመከላከል ሲባል የምርመራ መረጃን መሠረት አድርጎ በቢሮው የሚሰጥ የእርምት አስተያየት ነው፤
28. “አገር” ማለት የአለም አቀፉ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት አባል አገር ነው፤
29. “ንድፍ አውጭ አገር” ማለት የአውሮፕላን ንድፍ አውጥቶ ኃላፊነት በወሰደ ድርጅት የሚገኝበት ሥልጣን ያለው አገር ነው፤
30. “አምራች አገር” ማለት አውሮፕላን ገጣጥሞ አምርቶ ያወጣው ድርጅት የሚገኝበት ሥልጣን ያለው አገር ነው፤
31. “ክስተት የደረሰበት አገር” ማለት አደጋ ወይም ከባድ የአደጋ አጋጣሚ የተከሰተበት ሀገር ነው፤
32. “የኦፕሬተር አገር” ማለት ኦፕሬተሩ ሥራውን የሚያከናውንበት መደበኛ ቦታ ወይም የኦፕሬተሩ ቋሚ መኖሪያ አገር ነው፤
33. “የምዝገባ አገር” ማለት አውሮፕላኑ የተመዘገበበት አገር ነው፤
34. “ቢሮ” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 መሠረት የተደራጀ የኢትዮጵያ አውሮፕላን አደጋ ምርመራ ቢሮ ነው፤
35. “የቢሮ ኃላፊ” ማለት የቢሮውንና የአውሮፕላን አደጋ ምርመራ ስራን በበላይነት የሚመራ ባለሞያ ነው፤
36. “ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የትራንስፖርት ሚኒስቴር እና የትራንስፖርት ሚኒስትር ነው፡፡
37. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡
38. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለፀው የሴትንም ጾታ ይጨምራል፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በሚከተሉት ላይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል:-

1. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግዛት ክልል በሚደርስ የሲቪል አየር ትራንስፖርት አደጋ እና ከባድ የአደጋ አጋጣሚ፤

2. ሥራቸውን የሚያከናውኑበት የሌላ አገር ሕግ እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም ቦታ ያሉ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የተመዘገቡ የሲቪል አውሮፕላኖች፣
3. በማናቸውም ቴክኒካዊ ሥራዎች ማለትም የአየር ትራፊክ ቁጥጥር እና ተከላ፣ የኮሙኒኬሽን፣ የናቪጌሽን፣ የቅኝትና የሜትሮሎጂ መሣሪያዎች ኦፕሬሽንና ጥገና ጨምሮ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሲቪል አውሮፕላን ማረፊያ፡፡

4. **የአዋጁ ዓላማ**

የዚህ አዋጅ ዓላማዎች የሚከተሉት ይሆናሉ:-

1. የአውሮፕላን አደጋ እና የከባድ አደጋ አጋጣሚ ክስተቶችን ነጻና ገለልተኛ ሆኖ ምርመራ የማድረግ፣
2. በአቪዬሽን ክስተት ምርመራ የተረጋገጡ የደህንነት ጉድለቶችን የመለየት፣
3. የአውሮፕላን አደጋና የከባድ አደጋ አጋጣሚ ክስተት ምርመራን ጥፋትን ወይም ኃላፊነትን ለመፈረጅ ሳይሆን አደጋን በመከላከል ዓላማ የመፈጸም፣ እና
4. የተረጋገጡ የደህንነት ጉድለቶችን ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ የሚያስችሉ የጥንቃቄ ምክረ ሀሳቦችን የመስጠት፡፡

## ክፍል ሁለት

## የአውሮፕላን አደጋ ምርመራ ቢሮ

5. **መቋቋም**

የኢትዮጵያ የአውሮፕላን አደጋ ምርመራ ቢሮ (ከዚህ በኋላ "ቢሮ" እየተባለ የሚጠራ) በሚኒስቴሩ ውስጥ በዚህ አዋጅ መሠረት ተደራጅቷል፡፡

6. **የቢሮው አደረጃጀት**

ቢሮው:-

1. በሚኒስትሩ የሚሾም ቢሮ ኃላፊ እና
2. ለሥራው አስፈላጊ ባለሞያዎች፣

ይኖሩታል::

7. **የቢሮው ሥልጣንና ተግባራት**

ቢሮው ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1. የአውሮፕላን አደጋና የአደጋ አጋጣሚ ላይ የምርመራ ኃላፊን የመመደብ፣ ምርመራ የማካሄድ፣ የምርመራ ሥራውንና ሪፖርትን የመከታተል፣
2. ዓላማውን በሚገባ ለማሳካት የሚረዳው ሥልጣን የተሰጠው ተወካይ፣ አማካሪ ፣ ታዛቢ እና ተሳታፊ በሚኒስትሩ እንዲሰየም ሀሳብ የማቅረብ፣
3. ለምርመራ ተግባሩ የሚያስፈልገውን ማንኛውንም ሰው በአካል እንዲቀርብ በመጥራት የቃል፣ የጽሁፍ ወይም የሰነድ ማስረጃና ተያያዥ ነገሮች እንዲሰጠው የመጠየቅ፣
4. ያለ ገደብ ወደ አደጋ ቦታ የመግባትና ዙሪያውን በመቆጣጠር ማናቸውንም ቁሳቁሶችና ማስረጃዎች መመርመርና የመፈተሽ፣
5. በምርመራ ሂደት የተገኘን ወይም የተያዘን ማንኛውንም ንብረት ወይም የአውሮፕላን ስብርባሪ ለባለቤቱ የመመለስ ወይም የመልቀቅ ወይም የማስወገድ፣
6. ለሚመለከታቸው አካላት የምርመራ ግኝቱን መሠረት ያደረገ የጥንቃቄ ምክረ-ሀሳብ የመስጠት፣
7. ስለሰጠው የጥንቃቄ ምክረ-ሀሳብ አተገባበር ክትትል የማድረግና እንደአስፈላጊነቱ ተጨማሪ የጥንቃቄ ምክረ-ሀሳብ የመስጠት፣
8. የቅድመ ምርመራ፣ ጊዜያዊና የመጨረሻ የአደጋና የከባድ አደጋ አጋጣሚ ምርመራ ሪፖርቶችን ለሚኒስትሩ ያቀርባል፣
9. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች፣ በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንብና መመሪያዎችን፣ እንዲሁም ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸውን አግባብነት ያላቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች፣ ደረጃዎችና የተመረጡ አሠራሮችን የመተግበርና የማስፈጸም፣
10. ዓላማውን ለማሳካት የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን የማከናወን፡፡

## 8. <u>በጀት</u>

የቢሮው መደበኛ እና ለአደጋና ለከባድ ድንገተኛ አጋጣሚ ምርመራ የሚውል መጠባበቂያ በጀት በሚኒስትሩ በኩል ጥያቄ ሲቀርብ በመንግስት ይመደባል፡፡

## 9. <u>የቢሮ ኃላፊው ሥልጣንና ተግባር</u>

1. የቢሮው ኃላፊ የቢሮው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ የቢሮውን ሥራዎች በኃላፊነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የቢሮው ኃላፊ:-
   ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ (7) የተመለከተውን የቢሮውን ሥልጣንና ተግባር ሥራ ላይ ያውላል፣

ለ) የቢሮውን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

ሐ) የአውሮፕላን አደጋና የከባድ አደጋ አጋጣሚ የተመለከተ ፖሊሲ ሃሣብ አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲጸድቅም በሥራ ላይ ያውላል፤

መ) ለምርመራ ሥራ የሚያስፈልጉ ፋሲሊቲዎች እንዲሟሉ ያደርጋል፡፡

3. የቢሮው ኃላፊ ለቢሮው የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልገው መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለቢሮው ሠራተኞች ወይም ሥራ ኃላፊዎች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፤

10.<u>**የምርመራ ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር**</u>

የምርመራ ኃላፊው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1. በዚህ አዋጅ መሠረት ቢሮውን ወክሎ የተከሰተን የአውሮፕላን አደጋ ምርመራን ይመራል፤ ያከናውናል፡፡
2. ስለአደጋው ምርመራ ግኝት፣ ለአደጋው መንስኤና አስተዋጽኦ ስላደረጉት ምክንያቶች፣ ከምርመራው ጋር የተያያዙ የጥንቃቄ ምክረ-ሀሳቦች እና አጠቃላይ የምርመራ ሪፖርት ለቢሮው ያቀርባል፤
3. በምርመራ ሥራው ላይ የተመደቡ ሥልጣን የተሰጣቸው ተወካዮችን፣ አማካሪዎችን፣ ተሳታፊዎችን፣ ታዛቢዎችን በኃላፊነት ይመራል፡፡

11.<u>**የጥቅም ግጭት**</u>

የአውሮፕላን አደጋ እና የአደጋ አጋጣሚ ምርመራን የሙያ ገለልተኝነት እና የምርመራ ተዓማኒነት ለማረጋገጥ የቢሮው የምርመራ አባል የጥቅም ግጭት የሌለው መሆን አለበት፡፡

12.<u>**የሚኒስትሩ ሥልጣንና ተግባር**</u>

1. ሚኒስትሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

ሀ) የአውሮፕላን ትራንስፖርት አደጋ ምርመራ ተቀባይነት ባለው ደረጃ መሰረት መከናወኑን የማረጋገጥ፤

ለ) ከአውሮፕላን አደጋ እና የአደጋ አጋጣሚ ምርመራ ጋር የተያያዙ የፖሊሲ ሀሳቦችን

የማመንጨት፤

ሐ) የማጠቃለያ የምርመራ ሪፖርትን የማጽደቅና ለህዝብ ይፋ የሚደረግበትን ሁኔታ የመወሰን፤

መ) ቢሮው ተግባርና ኃላፊነቱን በሚገባ እንዲወጣ ድጋፍና ክትትል የማድረግ፤

ሠ) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የምርመራ ሥራን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ለሌላ አገር ወይም ቀጣናዊ የአደጋ ምርመራ ድርጅት ወይም አካል በውክልና የመስጠት፤

ረ) ሥልጣን የተሰጠው ተወካይን፣ ታዛቢን፣ ተሳታፊን እና አማካሪን ቢሮው እንዲመደብ አስተያየት ሲያቀርብ የመመደብ፤

ሸ) የቅድመ፣ ጊዜያዊና የመጨረሻ የአደጋና የከባድ አደጋ አጋጣሚ ምርመራ ሪፖርቶች ይፋ እንዲወጡ ማድረግ፡፡

2. ሚኒስትሩ በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን ሥልጣንና ተግባራት በከፊል ለቢሮው በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

## ክፍል ሦስት
## የምርመራ ሥልጣን እና ሥነ-ሥርዓት

### 13.የምርመራ ሥልጣን

1. ቢሮው ስለአውሮፕላን አደጋና ከባድ የአደጋ አጋጣሚ የደህንነት ምርመራ በተመለከተ ብቸኛ የመመርመር ሥልጣንና ኃላፊነት ይኖረዋል፤ ሆኖም በሚኒስትሩ ወይም ጥቅም ባለው አካል ካልተጠየቀ በስተቀር በአጋጣሚዎች ላይ ምርመራ አያደርግም፡፡
2. የቢሮው የአውሮፕላን አደጋ እና ከባድ የአደጋ አጋጣሚ ምርመራ ተግባር ሙያዊ እና ከማንኛውም ተጽዕኖ ነጻና ገለልተኛ መሆን አለበት፤ እንዲሁም የአስተዳደር ወይም የዳኝነት ሥርዓት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚከናወን የምርመራ ተግባር ውስጥ ጣልቃ አይገባም፡፡
3. ቢሮው ስለአውሮፕላን አደጋ መረጃ ሲደርሰው ምርመራውን ለማካሄድ የተሻለ የቴክኒክ ሙያ ያለውን ሰው ሊጠራ ይችላል፡፡
4. በሀገር መከላከያ የተከለሉ ወታደራዊ ስፍራዎች ውስጥ በሲቪል አውሮፕላን ላይ አደጋ ቢደርስ ቢሮው በመከላከያ ሚኒስቴር ካልተፈቀደለት በስተቀር ምርመራውን ማካሄድ አይችልም፡፡
5. የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች የፖሊስ ኃይል በሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚያከናውነውን የምርመራ ተግባር አይከለክልም፡፡

### 14.የምርመራ ሥነ ሥርዓት

1. ቢሮው ለአውሮፕላን አደጋና ከባድ የአደጋ አጋጣሚ ምርመራ የሚከተለው ሥነ-ሥርዓትና አሠራር አገሪቱ በኮንቬንሽኑ አንቀጽ 38 መሠረት ያለባትን ግዴታ፣ በኮንቬንሽኑ ተቀጽላ 13 ከተመለከቱ ደረጃዎችና ከተመረጡ የአሠራር ልማዶች ጋር ተዛማጅ መሆናቸውን ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ሁሉ እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡
2. ቢሮው ስለአቪዬሽን ክስተት ምርመራ ሥነ-ሥርዓት፣ ሪፖርት አቀራረብ አስመልክቶ ከመንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ይፈጥራል፡፡
3. የቢሮው የምርመራ ሥርዓት ጥፋትን ወይም የፍትሐ ብሔርና የወንጀል ኃላፊነትን ለማቋቋም ከሚደረገው ምርመራ በተለየ ሁኔታ የሚካሄድ ይሆናል፡፡

15.**<u>ስለምርመራ ኃላፊ ሥልጣንና ተግባራት</u>**

የምርመራ ኃላፊ በማንኛውም የአውሮፕላን አደጋና የአደጋ አጋጣሚ ምርመራ ወቅት የሚከተሉት ስልጣን ተግባራት ይኖሩታል:-

1. ምስክርን እና ማንኛውንም ለምርመራ አስፈላጊ የሆነን ሰው በመጥራት ቃለመጠይቅ በማድረግ መረጃ ማሰባሰብ፤
2. አግባብነት ያላቸውን ማናቸውም ነገሮች እና ማስረጃዎች ላይ በወቅቱ ምርመራ ማድረግ፤
3. አደጋው የደረሰበትንና ስብርባሪው ያለበትን ቦታ ያለገደብ የመግባትና በቁጥጥር ሥር የማድረግ፤
4. የበረራና የአየር ትራፊክ አገልግሎት ሪኮርድን ጨምሮ ማንኛውንም አግባብነት ያለውን ነገርና ማስረጃ ያለገደብ የማግኘት፤
5. ከክስተቱ ጋር የተያያዙ ማናቸውንም ምዝገባዎች ጨምሮ ክስተቱ የተፈጸመበትን ቦታ፣ አውሮፕላንንና የአውሮፕላኑን ማንኛውንም ክፍል እንዲጠበቅና እንዲያዝ የማድረግ፤
6. ከምርመራው ጋር ተያያዥነት ያላቸው ማናቸውንም ሰነዶች እንዲቀርቡለትና ቅጂ እንዲደረጉለት የመጠየቅ እንዲሁም ምርመራው እስኪጠናቀቅ ድረስ ይዞ የማቆየት፤
7. ከክስተቱ እና ከአውሮፕላን ኦፐሬሽን ጋር ቀጥተኛም ሆነ ቀጥተኛ ያልሆነ ተሣትፎ የነበረውን ማንኛውንም ሰው ለህክምና ምርመራ እንዲላክ የማድረግ፡፡

## ክፍል አራት
## ክስተቶችን ስለማሳወቅ፣ ማስረጃዎችን ስለመጠበቅ እና ማስረጃዎችን ይዞ ስለማቆየት

### 16. የአውሮፕላን አደጋ ስለማሳወቅ

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የአውሮፕላኑ ባለቤት፣ ኦፕሬተር፣ ዋና አብራሪ፣ ማንኛውም የበረራ አባል፣ ኤርፖርት፣ የአየር ትራፊክ ተቆጣጣሪ እንዲሁም የአውሮፕላን አደጋ ወይም ከባድ የአደጋ አጋጣሚ መከሰቱን ያወቀ ሰው መረጃውን ለማሰባሰብ እንዲቻል ወዲያውኑ በተገኘው ፈጣን የመገናኛ ዘዴ ለቢሮው ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ አግባብነት ላለው የመንግስት አካል ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው የግዴታ ሪፖርት ማቅረብ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በግዴታ ሪፖርት ያልተገኙ መረጃዎችን ለማሰባሰብ እንዲቻል ማንኛውም ሰው ለቢሮው ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ የመንግስት አካል በፈቃደኝነት ሪፖርት በማድረግ ማሳወቅ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት ሪፖርት ያደረገ ሰው ማንነቱ እንዳይታወቅ የሕግ ከለላ ይኖረዋል፡፡

### 17. ማስረጃን ስለመጠበቅ እና ይዞ ስለማቆየት

1. አደጋ የደረሰበት አውሮፕላን፣ ስብርባሪ አካል ወይም የአደጋ ቦታው ያልተፈቀደላቸው ሰዎች እንዳይደርሱበት መጠበቅ አለበት፡፡
2. የአውሮፕላን አደጋ ወይም ከባድ የአደጋ አጋጣሚ ሲከሰት ባለቤቱ፣ ኦፕሬተሩና የበረራ አባሉ በቢሮው በሌላ ሁኔታ እንዲጠበቅና እንዲቀመጥ እስከሚታዘዝ ድረስ ወይም በዚህ አዋጅ በሌላ መልኩ ካልተመለከተ በስተቀር በሰነድ ያሉ ማስረጃዎችን ጨምሮ ሪፖርት ከተደረገበት አደጋ ወይም ከከባድ አደጋ አጋጣሚ ጋር ተያያዥነት ያለው ማንኛውም ማስረጃ ባለበት ሁኔታ መጠበቅና ይዞ ማቆየት አለበት፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ የሰው፣ የንብረት ወይም የአካባቢ ደህንነትን ለመጠበቅ ሲባል ማንኛውም ሰው አስፈላጊ የሆነ እርምጃን እንዳይወስድ የሚከለክል ተደርጎ መወሰድ የለበትም፡፡

4. በዚህ አንቀጽ መሰረት የተደራጀ የምርመራ መዝገብ የምርመራው የመጨረሻ ሪፖርት ይፋ ከሆነበት ዕለት ጀምሮ ከ20 ዓመታት በቢሮው መጠበቅ አለበት፡፡

18.<u>የመረጃ ጥበቃ</u>

1. ቢሮው ምርመራ በሚያደርግበት ወቅት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጨምሮ ማንኛውንም ከምርመራ ጋር የተያያዙ ምዝገባዎች ከአደጋና ከከባድ አደጋ አጋጣሚ ምርመራ ውጭ ለሆነ ዓላማ መግለጽ አይችልም፤
   ሀ) በምርመራ ሂደት መርማሪው ከሰዎች የወሰዳቸው ማናቸውም መረጃዎች፤
   ለ) በአውሮፕላን ኦፕሬሽን ወቅት በነበሩ ሰዎች መካከል የተደረጉ ማናቸውም ግንኙነቶች፤
   ሐ) ከአደጋው ወይም ከባድ አደጋ አጋጣሚው ጋር ግንኙነት ያለው ሰው የህክምና ወይም የግል መረጃ፤
   መ) የኮክፒት የድምጽ ቅጂዎችንና የተገለበጡ መረጃዎች
   ሠ) ከአየር ትራፊክ ቁጥጥር ክፍል የተመዘገቡና የተገለበጡ መረጃዎችን፤
   ረ) የበረራ ምዝገባና ሌሎች በትንተና ወቅት የተገለጹ መረጃዎች፤
   ሰ) በረራ ላይ ያለ የኮክፒት ምስልን፣ የምስሉን የተወሰነ ክፍል ወይም የተገለበጡ መረጃዎችን፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱት መረጃዎች በማንኛውም ተሳታፊ ሰው ላይ በዲሲፕሊን፣ በፍርድ ቤት ወይም በሌላ የክርክር ሥርዓት በማስረጃነት ሊቀርቡበት አይችሉም፡፡

19.<u>የመርማሪዎች ማስረጃ</u>

1. የአውሮፕላን አደጋ መርማሪው ካከናወነው የአውሮፕላን አደጋ ምርመራ ጋር በተያያዘ ሌላ አካልን ጥፋተኛ ወይም ተጠያቂ ለማድረግ በፍርድ ቤት፣ አስተዳደራዊና በዲስፕሊን ጉዳዮች ምስክር ሆኖ አይቀርብም፡፡
2. አውሮፕላን አደጋ ምርመራ ማጠቃለያ ሪፖርት ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ የክርክር ሥርዓት ጥፋተኛነትን ወይም ተጠያቂነትን ለማቋቋም በማስረጃነት አይቀርብም፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ስለአውሮፕላን አደጋ ምርመራ ሪፖርት</u>

## 20.የቅድመ ምርመራ ሪፖርት

1. ቢሮው አደጋ የደረሰበት አውሮፕላን ክብደት ከ2,250 ኪሎ ግራም በላይ ከሆነ የቅድመ ምርመራ ሪፖርቱን ለሚኒስትሩ በማሳወቅ አውሮፕላኑ ለተመዘገበበት፣ አውሮፕላኑ ኦፕሬት ለሚደረግበት፣ አውሮፕላኑን አምራች ለሆነው እና የአውሮፕላኑን ንድፍ ላጸደቀው አገር፣ እንዲሁም ለአለም አቀፉ የሲቪል አቪዬሽን ድርጅት በ30 ቀናት ውስጥ መላክ አለበት፡፡
2. አደጋ የደረሰበት አውሮፕላን ክብደት ከ2,250 ኪሎ ግራም በታች ከሆነ ቢሮው የቅድመ ምርመራ ሪፖርቱን ለሚኒስትሩ በማሳወቅ ከአለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ለተጠቀሱት አገራት ሁሉ መላክ አለበት፡፡

## 21.የማጠቃለያ ረቂቅ ሪፖርት

1. የማጠቃለያ የምርመራ ሪፖርት ይፋ ከመድረጉ በፊት ቢሮው ስለምርመራ ግኝቱና የደህንነት ጉድለቶችን ያካተተ የማጠቃለያ ረቂቅ ሪፖርቱን ለሚኒስትሩ ያቀርባል፤ ሪፖርቱ በሚኒስትሩ በኩል ለእያንዳንድ ተሳታፊ እና ጥቅም ላለው አካል በሚስጥር ይላካል፡፡
2. በሚመለከታቸው አገራት መካከል የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር የምርመራ ረቂቅ ሪፖርት ላይ አስተያየት የመቀበያ ጊዜ 60 ቀን ብቻ ነው፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ቢሮው አስተያየት ከቀረበለትና አስተያየቱንም ማካተት አስፈላጊ መሆኑን ካመነ የማጠቃለያ ሪፖርት ከማውጣቱ በፊት አስተያየቱን ያካትታል፡፡
4. በተቀጽላ (13) በተመለከተው መሠረት የቀረበው አስተያየት በምርመራ ሪፖርት ውስጥ የማይካተት ከሆነ ከማጠቃለያ ሪፖርቱ ጋር ለብቻው በአባሪነት ይያያዛል፡፡

## 22. የማጠቃለያ ሪፖርት

1. ቢሮው የአውሮፕላን አደጋ ምርመራ ሥራውን በተቻለ ፍጥነት በ 12 ወራት ውስጥ በማጠናቀቅ የማጠቃለያ ሪፖርቱን በሚኒስትሩ አማካኝነት ለሚመከለታቸው አካላት በመላክ ለህዝብ ይፋ ይደረጋል፡፡
2. የአውሮፕላን አደጋ ምርመራ ግኝት ሪፖርት ጥፋትን ወይም ኃላፊነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ የሚያመላክት ቢሆንም እንኳን ሙሉ የአውሮፕላን አደጋ ምርመራ ሪፖርቱ ከመውጣት አይገደብም፡፡

23.**የጥንቃቄ ምክረ-ሀሳብ**

1. የአውሮፕላን አደጋ ምርመራው በማንኛውም ደረጃ ላይ ቢሆን አደጋን ለመከላከል አስፈላጊ የሆነ ማንኛውም የጥንቃቄ ምክረ-ሀሳብ እንዲተገበር ቢሮው ለሲቪል አቪዬሽን ባለስልጣንና ለሌላ ጥቅም ላለው አካል በፍጥነት መላክ ይችላል፡፡
2. ከቢሮው የጥንቃቄ ምክረ-ሀሳብ የደረሰው አካል ምክረ-ሀሳቡ በደረሰው በ90 ቀናት ውስጥ በምክረ-ሀሳቡ መሠረት ስለወሰደው እርምጃ ለቢሮው በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

24.**ድጋሚ ምርመራ ስለማድረግ**

ቢሮው የአውሮፕላን አደጋ ምርመራውን ካጠናቀቀ በኋላ አዲስ እና ወሳኝ ማስረጃ ከተገኘ በድጋሚ ምርመራ ማድረግ ይችላል፡፡

**ክፍል ስድስት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

25. **የፖሊስ ኃይል ወይም የጥበቃ አካል ግዴታ**

የአውሮፕላን አደጋ ምርመራ ኃላፊ አደጋ የደረሰበትን ቦታ፣ ዙሪያ፣ አውሮፕላኑን፣ የአውሮፕላኑን ስብርባሪ አካላት ተረክቦ እስከሚቆጣጠረው ድረስ አደጋው የተከሰተበት አካባቢ ያለ የፖሊስ ኃይል ወይም ማንኛውም ሥልጣን ያለው የጥበቃ አካል ባለበት ሁኔታ እና ተያያዥነት ያለውን ማስረጃ የመቆጣጠርና የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

26.**ጥፋቶች**

1. ማንኛውም ሰው:-

ሀ) የቢሮውን የአውሮፕላን አደጋ ምርመራ ተግባር የተከላከለ ወይም ያወከ፣

ለ) አደጋ ከደረሰበት አውሮፕላን አካል ወይም አደጋው ከደረሰበት አካባቢ ያለፈቃድ ማንኛውንም ንብረት ወይም ማስረጃ እያወቀ የወሰደ፣ ያጠፋ፣ የደበቀ፣ የለወጠ፣

ሐ) ለአውሮፕላን አደጋ የምርመራ ወይም የማጣራት ተግባር እያወቀ የሀሰት ወይም የሚያሳስት መረጃ የሰጠ፣ ወይም

መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16 መሠረት እያወቀ የሀሰት ወይም የሚያሳስት ሪፖርት ያቀረበ፣

እንደሆነ ጥፋተኛ ሆኖ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እስራት ወይም ከብር 500,000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

2. ይህን አዋጅ እና በዚህ አዋጅ መሠረት የወጣ ደንብን የተላለፈ ማንኛውም ሰው ጥፋተኛ ሆኖ ከብር 400,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

27.<u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም አስፈላጊ የሆነ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ሚኒስቴሩ ይህንን አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወጣ ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ሥርዓቶችንና ደረጃዎችን የያዘ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

28.<u>የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች</u>

1. የሲቪል አቪየሽን አዋጅ ቁጥር 616/2001 አንቀጽ 88 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ፣ ትዕዛዝ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

29.<u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

ይህ አዋጅ ተፈጻሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን በምርመራ ላይ ያለ ወይም የምርመራ ሥራው ተጠናቆ የማጠቃለያ ሪፖርት ያልተደረገበት ማንኛውም ጉዳይ ወደ ቢሮው ተላልፎ በዚህ አዋጅ መሠረት ፍጻሜ ያገኛል፡፡

30.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሀምሌ 5 ቀን 2008 ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## ሐ/ የባህር ትራንስፖርት

### ደንብ ቁጥር 1/1988

### ስለመርከብ ምዝገባ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 4/1987 አንቀፅ 5 መሰረት የሚከተለውን አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የመርከብ ምዝገባ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 1/1988" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ መርከብ ማለት በባህር ሕግ አንቀፅ 1 ላይ በተመለከተው ትርጓሜ የሚሸፈኑትን እንዲሁም በአገር ውስጥ ውኃዎች ላይ ለሚደረግ ትራንስፖርት የሚያገለግሉ መርከቦችንና በሞተር የሚሰሩ ጀልባዎችን ይጨምራል፡

3. **ምዝገባ**

   የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር[129] የመርከብ ምዝገባና ከዚሁ ጋር የተያያዙ ተግባሮችን ያከናውናል፡፡

4. **የምዝገባ ቦታ**

   አዲስ አበባ ወይም የሚመለከተው አካል የሚሰይማቸው ሌሎች የኢትዮጵያ ከተሞች የምዝገባ ቦታ (ፖርት ኦፍ ሬጅስተሬሽን) ሆነው የገለገላሉ፡፡

5. **ደንቡ የሚፀናበት ግዜ**

   ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታተሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የከቲት 5 ቀን 1988**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስቴር**

---

[129] በ22/12 (2008) አ. 916 አንቀጽ 9 (12) መሰረት የትራንስፖርት ሚኒስቴር ተብሎ ይነበባል፡፡

## ደንብ ቁጥር 37/1990

## የዕቃ አስተላላፊነት እና የመርከብ ውክልና ሥራ ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 4/1987 አንቀጽ 5 እና በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 67/1989 አንቀጽ 47 መሠረት ይህን ደንብ አወጥቷል ።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የዕቃ አስተላላፊነት እና የመርከብ ውክልና ሥራ ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 37/1990" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

   1. "ዕቃ አስተላላፊነት" ማለት በአገር ውስጥ ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕቃ ተቀባይን ወይም ዕቃ ላኪን በመወከል የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት፣ የወደብ ሥነ ሥርዐት እና ሌሎች ሥነ ሥርዓቶችን አስፈጽሞ የገቢ ወይም የወጪ ዕቃዎች በመደብ እንዲገቡ ወይም እንዲወጡ ማድረግ ሲሆን ዕቃን የማጓጓዝንና የማስረከብን ሥራ ይጨምራል፤
   2. "ዕቃ አስተላላፊ" ማለት በዚህ ደንብ መሠረት የዕቃ አስተላላፊነት ለመሥራት የንግድ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤
   3. "ወደብ" ማለት የፌዴራል ገቢዎች ቦርድ የሚወስነው ክልል ወይም ቦታ ነው፡
   4. "የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ማስፈጸም" ማለት ዕቃ ላኪዎችን ወይም አስመጪዎችን በመወከል በጉምሩክ ጣቢያ ውስጥ ለወጪ ወይም ለገቢ ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ማስፈጸም ነው፤
   5. "የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት" ማለት ወደ ሀገር የሚገባ፣ ወደ ውጭ ሀገር የሚላክ ወይም ተላላፊ ዕቃ ጉምሩክ ወደብ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ እንደአግባብነቱ አስመጪው እስከሚረከበው ወይም ከኢትዮጵያ እስከሚወጣ ድረስ የሚከናወን ማናቸውም ሂደት ነው፤
   6. "የወደብ ሥነ ሥርዓት ማስፈጸም" ማለት የወጪ ዕቃን በተመለከተ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ከተጠናቀቀ በኋላ በወደብ ዕቃው በመርከብ ላይ እስከሚጫንበት ወይም ገቢ ዕቃን በተመለከተ ዕቃው ከተራገፈ በኋላ ከወደብ እስከሚወጣበት ጊዜ ድረስ ለወጪ ወይም ለገቢ ዕቃ ማናቸውንም ሥነ ሥርዓት ማስፈጸም ነው፡፡

7. “ዕቃዎችን በአንድ ላይ ማቀናጀት” ማለት በአንድ ላይ ሊሆኑ የሚችሉ የተለያዩ ባለንብረቶች ዕቃዎችን በአንድ ሙሉ ኮንቴይነር አንድ ላይ የማሰባሰብ ተግባር ነው፤
8. “ሰዉ” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
9. “የተቆጣጣሪ ውክልና” ማለት ወደብ ውስጥ ያለ መርከብ ባለንብረትን በመወከል የባለመርከቡን ጥቅም ለመጠበቅ የመርከብ ወኪሉን ሥራ የመቆጣጠር ተግባር ነው፤
10. “መርከብ” ማለት ማናቸውም ለማሪታይም ትራንስፖርት አገልግሎት የሚውል ተንሳፋፊ የጭነት ወይም የሰው ማጓጓዣ መሣሪያ ሲሆን ጀልባን ይጨምራል ፤
11. “የመርከብ ውክልና” ማለት የመርከብ ባለንብረትን፣ ተከራይን፣ ወይም ኦፕሬተርን በመወከል መርከቡ የሚያጓጉዘውን ዕቃ ወይም መንገደኛ ማግኘትንና መመዝገብን በባህር ወደብ ላይ እና በአገር ውስጥ እንደአስፈላጊነቱ ለመርከቦች አገልግሎት መስጠትን፣ ዕቃ የመጫንና የማራገፍን፣ እንዲሁም ዕቃን አጓጉዞ የማከማቸትን ሥራ ማስተባበርን ይጨምራል፤
12. “የመርከብ ወኪል” ማለት በዚህ ደንብ መሠረት የመርከብ ውክልና ለመሥራት የንግድ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤
13. “የንግድ ሥራ ፈቃድ” ማለት በዕቃ አስተላላፊነት ወይም በመርከብ ውክልና አገልግሎት ሥራ ለመሠማራት ከንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡
14. “የውጭ ንግድ ረዳት” ማለት በንግድ ሕግ ከአንቀጽ 44 እስከ 62 እንደተተረጎመዉ የንግድ ወኪል፣ የንግድ ደላላ እና የኮሚሽን ወኪል ነው፡፡

3. <u>የዕቃ አስተላላፊነት ሥራ</u>

የዕቃ አስተላላፊነት ሥራ የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

1. የወደብ ሥነ ሥርዓት ማስፈጸም፤
2. የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ማስፈጸም፤
3. ዕቃዎችን በአንድ ላይ አቀናጅቶ የመላክ አገልግሎት መስጠት፤
4. የመጋዘን አገልግሎት መስጠትና ዕቃ የማድረስ፤
5. የዕቃ ማስተናገጃ መሣሪያዎች አገልግሎት መስጠት፤
6. የራሱ ትራንስፖርት ካለው እንደአጓጓዥ ሆኖ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት፤

7. ባለዕቃው ራሱ ማጓጓዣ ካላቀረበ በስተቀር፣ የራሱ ትራንስፖርት የሌለው እንደሆነ የትራንስፖርት አገልግሎት ተከራይቶ ዕቃውን ማጓጓዝ፣
8. የዕቃዎች ማጠን አገልግሎት መስጠት፣
9. ዕቃዎችን ማሸግ፣
10. ሠነዶችን ማዘጋጀትና መስጠት፣
11. የውጭ ንግድ ደንብና የሌተር ኦፍ ክሬዲት ትእዛዞችን ተግባር ላይ ማዋል፣
12. አመቺ ማጓጓዣ መምረጥ፣ የዕቃ ማጓጓዝ ስምምነት መዋዋል፣
13. የዕቃዎችን እንቅስቃሴ መከታተል፣
14. የዕቃ መተላለፍን በተመለከተ ምክር መስጠት።

4. **<u>የመርከብ ወክልና ሥራ</u>**

የመርከብ ዉክልና ሥሪ የሚከተሉትን ይጨምራል፣

1. ከተለያዩ የመርከብ ባለንብረቶች ጋር ግንኙነቶች በማድረግ ለመጫንና ለማራገፍ ስለሚመጡ መርከቦች አስፈላጊ መረጃዎችን በቅድሚያ ማጠናቀር፣
2. መርከቦች በየቀኑ ያሉበትን ሁኔታ በተመለከተ መግለጫ ማውጣትና ለላኪዎችና ላስመጪዎች መላክ፣
3. ለመርከብ ዕቃ የመፈለግ፣ የመደልደልና የማስተባበር አገልግሎት መስጠት፣
4. የመርከቦችን አመጣጥና አካሔድ ሁኔታ የማቀናጀትና የአገሪቱ የወጭ ንግድ ዕቃዎች ብቃት ባላቸው አጓጓዦች መስተናገዱን ማረጋገጥ፣
5. የወጭ ዕቃዎች መርከቡ ወደብ ከመድረሱ በፊት ወደብ ለመድረሳቸው መከታተል ፣ ዕቃዎች በመርከብ ላይ በአግባቡ መጫናቸውን ማረጋገጥ፣
6. ዕቃ አስመጪዎች ዕቃቸውን እንዲወሰዱ ማስታወቅ፣
7. የወደብ መጨናነቅን እንዲሁም የአገልግሎት መዘግየትን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ አግባብ ያላቸውን አካላት መርዳት፣
8. የመርከብ መከራየትን በተመለከተ ብቃት ያላቸውን መርከቦች ለመከራየት እንዲቻል ድጋፍ መስጠት፣
9. የመርከብ ዕቃ ማጓጓዣ ኪራይ መሰብሰብና የሒሳብ መግለጫ ሠነድ እንዲሁም የገቢና ወጪ መግለጫ ዝግጅት አገልግሎት መስጠት፣
10. የዕቃ መጫንና ማራገፍ አገልግሎት እና የዕቃ ተቆጣጣሪነት ተግባር ማስተባበር፣

11. ወደብ ውስጥ ለመርከቡ አስፈላጊ የሆኑ የተለያዩ አገልግሎቶችን ማለት ለመርከበ ሠራተኞች ምግብ ውሃ የመሳሰሉትን መስጠት ወይም የሚሰጥበትን ሁኔታ ማቀናጀት፤
12. ባሕረኞችን የማቀያየርና ወደ መጡበት የመመለስ አገልግሎት መስጠት፤
13. የመርከብ ዕቃ መጫኛ ሠነድ፣ የዕቃ ማስረከቢያ ሰነድ ማዘጋጀትና መስጠት እንዲሁም ሌሎች የመርከብ ሰነዶችን ማዘጋጀት፤
14. ባለዕቃዎች የሚያቀርቡት የክፍያ ጥያቄ እንዲፈጸም ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
15. የተቆጣጣሪ ውክልና አገልግሎት መስጠት፤
16. የኮንቴይነር እንቅስቃሴ መከታተል ።

5. <u>ስለፈቃድ አስፈላጊነት</u>

1. ማንኛዉም ሰው የዕቃ አስተላላፊነት ወይም የመርከብ ውክልና አገልግሎት ሥራ ለመሥራት በዚህ ደንብ መሠረት ፈቃድ ማውጣት ይኖርበታል፡፡
2. ማንኛውም ሰው በውጭ ንግድ ረዳትነት ፈቃድ የመርከብ ዉክልናና የዕቃ አስተላላፊነት ሥራ ለመሥራት በዚህ ደንብ መሠረት ፈቃድ ማውጣት ይኖርበታል፤
3. በዚህ ደንብ መሠረት የዕቃ አስተላላፊነት ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የጉምሩክ አስተላላፊነት ሥራ ፈቃድ እንደተሰጠው ይቆጠራል።

6. <u>ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች</u>

1. ለዕቃ አስተላላፊነት ሥራ ወይም ለመርከብ ውክልና ሥራ ፈቃድ ለማግኘት አመልካቹ፤
   ሀ) ኢትዮጵያዊ ዜጋ ወይም አንደኛው ወገን ለሚሰጠው ጥቅም ሌላኛው ወገን በተመሳሳይ አጸፋውን የሚሰጥበት ስምምነት ኢትዮጵያ የተፈራረመችበት አገር ሰዉ፤
   ለ) ለዕቃ አስተላላፊነት ከብር 1,500,000፤ ለመርከብ ወኪልነት ከብር 1,000,000 ወይም ሁለቱንም ሥራዎች ለማካሄድ ከብር 2,200,000 ያላነሰ መነሻ ካፒታል ያለው፤
   ሐ) እራሱ ወይም የቀጠረው ሰው በኢንተርናሽናል ትሪንስፖርት በተለይም በባሕር ትራንስፖርት ሥራ አስፈላጊው የሙያ ዕውቀትና ልምድ ያለው፤ ለዚህም ከትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር የችሎታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት

የሚያቀርብ፤

መ) በቴሌፎን፣ በፋክስ፣ በቴሌክስ እና በሌሎች ለሥራው አስፈላጊ በሆኑ ዘመናዊ የመገናኛ ዘዴዎች የተደራጀ ቢሮ ያለው፤እና

ሠ) የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩን መመሥረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ የሚያቀርብ መሆን አለበት፡፡

2. ለዕቃ አስተላላፊነት ሥራ የሚያመለክት አመልካች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ሐ) የተመለከተውንና ከጉምሩክ ባለሥልጣን በጉምሩክ አስተላላፊነት መሥራት የሚያስችለው የችሎታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማቅረብ አለበት፡፡

3. የጉምሩክ አስተላላፊነት ሥራ ፈቃድ ያለው አመልካች የችሎታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማቅረብ አያስፈልገዉም።

7. **<u>የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

1. የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ከዚህ በላይ በአንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (1) (ሐ) ለተጠቀሱት መስፈርቶች መመሪያ ያወጣል።

2. ሚኒስቴሩ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (1) (ሐ) የተጠቀሱትን መስፈርቶች ላሟላ አመልካች የችሎታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

8. **<u>የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በአንቀጽ 6 የተዘረዘሩት ተሟልተው ሲቀርቡለት የዕቃ አስተላላፊነት ወይም የመርከብ ውክልና የንግድ ሥራ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

9. **<u>የጉምሩክ ባለሥልጣን ሥልጣን</u>**

የጉምሩክ ባለሥልጣን በዕቃ አስተላላፊነት ሥራ ለሚሠራ ሰው የጉምሩክ አስተላላፊነትን በተመለከተ በጉምሩክ አስተላላፊነት ሥራ ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 155/1986 በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (1) (ሐ) መሠረት የችሎታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

10. **<u>የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሥልጣን</u>**

1. የመርከብ ዕቃ ማስጫኛ ሰነድ፣ በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 13 እንደተመለከተው፣ የመርከብ ወኪሉ የሚያዘጋጀውና የሚሰጠው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣዉ መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡

2. በእቃ አስተላላፊነትና በመርከብ ዉክልና ስራ የሚገኘዉንና የሚወጣዉን የዉጭ ምንዛሪ ቁጥጥር የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣዉ መመሪያ መሰረት ይፈጸማል፡፡

11. የችሎታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን ስለ ማገድና ስለመሰረዝ

አንድ እቃ አስተላላፊ ወይመ የመርከብ ወኪል ስራዉ የሚጠይቀዉን የሙያ ግዴታና ስነ-ምግባር ካላከበረ የችሎታ የምስክር ወረቀቱ ምስክር ወረቀቱን በሰጠዉ አካል ሊታገድበት ወይም ሊሰረዝበት ይችላል፡፡ ምስክር ወረቀቱን መታገዱን ወይም መሰረዙን የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እንዲያዉቀዉ ይደረጋል፡፡

12. የዕቃ አስተላላፊ ወይም የመርከብ ወኪል ተጠያቂነት

1. ዕቃ አስተላለፊ ወይም የመርከብ ወኪል ተግባሩን በጥንቃቄ ማከናወን አለበት፡፡
2. ዕቃ አስተላለፊዉ ወይም የመርከብ ወኪሉ ተግባሩን ባለማካናወኑ ጥፋት ቢፈጽም በተለይም እቃዉ ቢጠፋበት፣ ቢጎድልበት ወይም ዕቃዉን በወቅቱ ባያስረክብ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

13. የሌሎች ህጎች ተፈጻሚነት

የንግድ ምዝገባና ፍቃድ አዋጅ ቁጥር 67/1989[130]፣ የጉምሩክ ባለስልጣንን እንደገና ለማቋቋምና አሰራሩንም ለመወሰን የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 60/1989 እና ሌሎች አግባብነት ያላቸዉ ህጎች በዚህ ደንብ ላይ እንደአግባቡ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

14. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከሰኔ 12 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ 12 ቀን 1990 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስቴር**

[130] በ16/42 (2002) አ. 686 አንቀጽ 63(1) ሀ መሰረት የተሻረ ሲሆን ይህም አዋጅ በ22/101 (2008) አ. 980 አንቀጽ 51 (1) መሰረት እንደተሻሻለ ተሽሯል፡፡

## አዋጅ ቁጥር 549/1999

## የማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ

የተቀላጠፈ የማሪታይም ዘርፍ አገልግሎት ለአገር ልማትና ብልጽግና እጅግ አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ በተፋጠነ ሁኔታ ተሻሽሎና በተቀናጀ አደረጃጀት ተስፋፍቶ የበለጠና ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ በማስፈለጉ፤

በዘመናዊ የአሠራር ቴክኒክ ዘዴዎች በመጠቀም የደረቅ ወደቦችን፣ የባሕር ማመላለሻንና መልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አገልግሎትን መጠቀም እንዲቻል ለማድረግ፣ መርከቦችን፤ የባሕር ጉዞዎችንና ሌሎች የማሪታይም ዘርፍ አገልግሎቶችን በሚገባ መምራትና መቆጣጠር አስፈላጊ በመሆኑ፣ እንዲሁም የአገር ውስጥ የውሃ ኃብትን ለበለጠ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲውል ለማድረግ፣ እና

በተለያዩ መሥሪያ ቤቶች ሥር ተበታትነው ያሉትን ተግባራት በአንድ ላይ በማሰባሰብ በማሪታይም ዘርፍ የሚከሰቱ ችግሮችን ተከታትለው መፍትሔ የሚሰጥ፣ በአለም ዓቀፍ ባሕር ነክ ስምምነቶች ላይ በመመስረት አገራችን ግዴታዋን እንድትወጣ እና ልታገኝ የሚገባትንም ጥቅሞች ተከታትሎ በባለቤትነት የሚያስፈጽም ለትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር በቀጥታ ተጠሪ የሆነ መንግሥታዊ አካል ማቋቋም በማስፈለጉ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55/1/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/1999" ተብሎ ሊጠራ ይችላል፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም እንዲሰጠው ካላስገደደ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

1. “ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ማለት ነው፡፡[131]
2. “ባለሥልጣን” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 መሠረት የተቋቋመው የማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን ነው፡፡
3. “የባሕር ማመላለሻ አገልግሎት” ማለት በባሕር መንገደኛን፤ ጭነትን ወይም ፖስታን የማመላለስ አገልግሎት ነው፤
4. “ወደብ” ማለት ዕቃዎች ወደ ውጪ ሃገር የሚጫኑበትና ወደ ሃገር ውስጥ ሲገቡም የሚራገፉበት ቦታ ተብሎ አግባብነት ባለው ሕግ ተደንግጎ የተከለለ የጉምሩክ መ/ቤት ያለበት የባሕር ወይም ደረቅ ወደብ ሲሆን፤ በዚህ ክልል ውስጥና በአዋሳኙ ለዚሁ አገልግሎት የሚውሉትን ሕንፃዎች፤ድርጅቶችና መሣሪያዎች ይጨምራል፤
5. “የወደብ አገልግሎት” ማለት በወደብ ውስጥ ለሐመር መቆሚያ መስጠትን፣ ሐመር መጎተትን፣ የሐመር አገልግሎት መስጠትን፣ ዕቃዎችን በሐመር ላይ መጫንና ማራገፍን፣ ለጭነት ተሽከርካሪዎች መቆሚያ መስጠትን፣ የጭነት ተሽከርካሪዎችን መጎተተን፣ ዕቃዎችን በወደብ ውስጥ በጭነት ተሽከርካሪዎች ላይ መጫንና ማራፍን፣ ወዘተ በወደብ ክልል ውስጥ ዕቃን ማጓጓዝን፣ የእሳት አደጋ አገልግሎት መስጠትን፣ የመጋዘን አገልግሎት መስጠትንና የመሳሰሉትን ይጨምራል፤
6. “ባሕረኛ” ማለት በሐመር ላይ ተቀጥሮ ወይም ተመድቦ እንዲሠራ የተደረገ ማንኛውም ሰው ሲሆን አዛዡንና ለማጆችን ይጨምራል፤
7. “ለባህር ጉዞ ብቁነት” ማለት አንድ ሐመር በአሰራሩ፣ በአጫጫን እቅዱ፣ በስንቁና በባህረኞቹ ብቁና የተሟላ ሆኖ የተመደበበትን ተግባር ለማከናወን የሚችል መሆኑ በባለሥልጣኑ ሲረጋገጥ ነው፤
8. “ሐመር” ማለት በውሃ ላይ ለመጓጓዝ የሚያገለግል ማንኛውም ዓይነት መርከብ፣ ጀልባ፣ ታንኳ ወይም ሳንቡቃ ነው።

[131]የትራንስፖርትናመገናኛሚኒስቴር በሚል የተገለጸው በ22/12 (2008) አ. 916 አንቀጽ 9 (12) መሰረት የትራንስፖርት ሚኒስቴር ሆኗል፡፡ በዚሁም መሰረት በዚህ አዋጅ ውስጥ የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር በሚል የተገለጸው ሁሉ የትራንስፖርት ሚኒስቴር በሚል ይነበባል፡፡

9. “የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሥራ” ማለት ወጥ በሆነ የትራንስፖርት ውል መሠረት ቢያንስ በሁለት የተለያዩ የማጓጓዣ አይነቶች በመጠቀም በክፍያ አንድን ዕቃ ከአንድ የተወሰነ ቦታ ተርክቦ በማጓጓዝ ሌላ አገር ውስጥ ማስረከብን የሙያ ሥራ አድርጎ ጥቅም ለማግኘት ሲባል የሚሰራ ሥራ ማለት ነውለ፡፡

## ክፍል ሁለት

## የማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን

3. **መቋቋም**

ከዚህ በታች “ባለሥልጣን” እየተባለ የሚጠቀሰው የማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን ተጠሪነቱ ለትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር የሆነ የህግ ሰውነት ያለው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶችን በማናቸውም ቦታ ሊያቋቁም ይችላል፡፡

5. **ዓላማዎች**

ባለሥልጣኑ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፤

1. በገቢና ውጭ፣ ንግድ ኮሪደሮች የሚካሄደው የገቢና ወጪ ዕቃዎች እንቅስቃሴ ኢኮኖሚያዊ መሆኑን መቆጣጠር፣ በዕቅድ እንዲመራ ማድረግና ማስተባበር፣
2. የገቢና የወጪ ዕቃዎች የትራንዚት ጊዜ እንዲያጥርና ወጪው እንዲቀንስ፤ ዕቃዎች በወደቦች ላይ ጉዳት እንዳይደርስባቸው የሚመለከታቸው አካላት ተቀናጅተው እንዲሰሩ ማስተባበርና መምራት፤
3. የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት፣ የባሕርና የአገር ውስጥ ውሃ ትራንስፖርት በማንኛውም ረገድ የሚያድጉበትን መንገድ መፈለግ፡፡ የባሕር ማመላለሻ አገልግሎት ከፍተኛ ደኅንነት እንዲኖረው ማረጋገጥ፤ በአገሪቱ የዳበረና ቀጣይነት ያለው የማሪታይም ዘርፍ ክህሎት እንዲኖር ማድረግ፤
4. ከአለም ዓቀፍ የማሪታይም ዘርፍ ስምምነቶች ጋር በተያያዘ አገሪቷ መፈጸም ያለባትን ግዴታና ልታገኝ የሚገባትን ጥቅም ተከታተሎ ማስፈፀም፡፡

6. <u>ስልጣንና ትግባር</u>

ባለሥልጣኑ የተሰጡትን ዓላማዎች ከግቡለማድረስ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፤

1. በገቢና ወጪ ንግድ ኮሪደሮች የሚካሄደውን የገቢና ወጪ እቃዎች እንቅስቃሴ የአገሪቷን የገቢና ወጪ ዕቃዎች እንቅስቅሴ ኢኮኖሚያዊነትና ቀልጣፋነት ማረጋገጥ፣ መቆጣጠር፣ ማስተባበርና ለችግሮች አፋጣኝ መፍትሔ መስጠት፤
2. የገቢና ወጪ ዕቃዎች የትራንዚት ጊዜ እንዲያጥር የሚመለከታቸው አካላት ተቀናጅተው እንዲሰሩ መምራት፤ የባሕር ወደብ አጠቃቀምን በተመለከተ ለሚከሰቱ ችግሮች ተከታትሎ መፍትሔ መስጠት፣ መደራደር፣
3. በባሕር ወደቦች የራሱ የመርከብ መጠጊያ እንዲኖረው መጣር፣ የደረቅ ወደብ ግንባታና አገልግሎት ማስፋፋት፤ የገቢና ወጪ ዕቃዎች የትራንዚት የመርከብና ሌሎች ጭነቶች ዋጋ ለመደራደር የሚያስችል ክህሎት ማዳበር፤
4. ብሔራዊ የንግድ መርከብ እንዲጎለብት መጣር፣ አሰራሩን መቆጣጠር፤ ለባሕርና ለሃገር ውስጥ ውሃዎች ማመላለሻ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የሥራ ፈቃድ መስጠትና መቆጣጠር፤
5. የማንኛውንም ሐመር ሥራ፤ ይዞታ፤ አገልግሎት ላይ ማዋል፤ ሽያጭና ግዥ መቆጣጠር፤ ለባሕረኞ፤ ለሌሎች በሐመር ላይ ለሚሠሩ ሰዎች አስፈላጊውን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠትና ማደስ፤
6. ማናቸውንም የደረቅ ወደብ አገልግሎት መስጫ መሣሪያዎች ወይም መገልገያዎች መመርመርና መፍቀድ፤ የደረቅ ወደብ አገልግሎት፣ የሃገር ውስጥ ጉምሩክ ማስተላለፊያ ቦታዎችን አገልግሎቶች መቆጣጠር፤
7. በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሥራ መሰማራት ለሚፈልጉ ፈቃድ መስጠት፣ ማደስና መቆጣጠር፤
8. የደረቅ ወደቦችን፣ የወደብ ዕቃ አስተላላፊዎችን፤ የመርከብ ወኪሎችንና የጉምሩክ አስተላላፊነትን ሥራ መቆጣጠር፤ ዝርዝር መመሪያዎችን ማውጣት፣ ሥራቸውን ማስተባበር፣ አቅማቸውን ማጐልበት፤
9. ሚኒስቴሩን በማስፈቀድ ዓለም አቀፍ የማሪታይምና ትራንዚት አገልግሎት ስምምነቶች መደራደር፣ ደንቦች እንዲወጡ ወይም እንዲተገበሩ ማድረግ፣ አፈጻጸማቸውን መከታተል፤

10.በማሪታይም ዘርፍ አገልግሎት አሰጣጥ የግል ባለኃብቶች የተደራጀና የተቀናጀ ተሳትፎ እንዲኖርበት ማገዝ፣ በማሪታይም ዘርፍ የሚደራጁ ማህበራትን ሥራ መቆጣጠር፤ የማሪታይም ዘርፍን የሚመለከቱ የንግድ መረጃዎችን በትንታኔ በማስደገፍ ለተጠቃሚዎች ማቅረብ፤

11.በደረቅ ወደብ፣ አገልግሎት የተሰማሩ ድርጅቶች ለሚሰጡት ግልጋሎት የሚያስከፍሉትን ዋጋ ወይም ታሪፍ ማስወሰን፤ መንገደኞች፣ ዕቃዎችና ፖስታዎች በሐመር የሚጓጓዙበትን ሁኔታ መወሰንና መቆጣጠር፤

12.የደረቅ ወደቦችንና ሌሎችንም ውሃ ትራንስፖርት ነክ ጉዳዮችና ተግባሮች በማጥናት ኘላንና ኘሮግራም ማዘጋጀት፤ በሚፈቀደው ኘሮግራም መሠረት ደረቅ ወደቦችና ሌሎችንም የሐመር መገልገያዎች ማቋቋም፣ ማሻሻልና መጠገን፤

13.ደኅንነቱ የተጠበቀ፤ በቂ እና የተሟላ የደረቅ ወደብ የባሕር ማመላለሻና የወደብ አገልግሎቶች መኖራቸውን ማረጋገጥ፤ አስፈላጊው የባሕርና የየብስ መድን እንዲኖር ማድረግ፤

14.የወደብና የሐመር መዛግብትን መያዝ፤ ማናቸውንም ሐመር ከነመብቱ መመዝገብ፤ ለሐመር የመለያ ምልክት መስጠት፤ የሐመር ስምን መፍቀድ፤ የባሕር ጉዞ ብቁነት የምስክር ወረቀት መስጠት፤ ሐመር የሚሠራበትን፤ የሚውልበትን ተግባር፤ የሚጠበቅበትን፤ የሚታደስበትንና የሚጠገንበትን ሁኔታ መወሰንና መቆጣጠር፤

15.የባሕር መበከልን ወይም መቆሸሽን መቆጣጠር፤ ከሌሎች ከሚመለከታቸዉ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ጋረ በመተባበር ለሃገር ውስጥ ውሃ ማመላለሻ የተከለከሉ፣ አደገኛ ወይም ባለገደብ ቦታዎች መከለልና ማሳወቅ፤

16.ማንኛውም ሐመር ቢጠፋ ወይም በባሕር ላይ እንዳለ አደጋ በደረሰበት ጊዜ የፍለጋ፤ የማዳንና የአስቸኳይ ዕርዳታ ተግባሮችን ማስተባበር፤ የሐመር አደጋን መመርመር፤ የአደጋ ምርመራ ሪፖርት አዘጋጅቶ ማውጣት፤

17. የባሕር ትራንስፖርት ሙያ ማስተማሪያ ተቋማት፤ የሐመር ሥራ፤ ማደሻና መጠገኛ ድርጅቶች፤ እንዲሁም ሌሎች ለሐመር አገልግሎት የሚውሉ ክፍሎች እንዲቋቋሙ ማድረግ፤ ደረጃቸውን መመርመርና መወሰን፤ የችሎታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠት፤

18.ባለሥልጣኑ በወደብ ክልል ውስጥና እንዲሁም ለባሕር ጉዞ ለሚያበረክተው ማናቸውም አገልግሎቶች ተገቢውን ዋጋ፤ ኪራይ ወይም ሌላ ክፍያ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በኩል ለሚኒስትሮች ምክር ቤት በማቅረብ አፀድቆ ማስከፈል፡፡

19.በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ረቂቅ መመሪያዎችን አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ የማቅረብ፣ በየወቅቱ የሚያወጣቸውን መመሪያዎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሁሉ በግልጽ እንዲያውቁት ማድረግ።

20.ውል መግባት፤ መክሰስና መከሰስ፤ ክርክሮችን በግልግል መጨረስና ለሥራው እንደሚያስፈልገው ማንኛውንም ዓይነት ንብረት መግዛት፤ መሸጥ፤ ባለቤት መሆን፤ መከራየት ወይም ማከራየት፤

## ክፍል ሦስት

## አደረጃጀትና አስተዳደር

7. **የባለሥልጣኑ አቋም**

   1. ባለሥልጣኑ በሚኒስትሩ አቅራቢነት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾም አንድ ዋና ዳይሬክተርና ለዳይሬክተሩ ተጠሪ የሆነ አንድ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ይኖሩታል፤
   2. ባለሥልጣኑ ለሥራው አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

8. **የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር**

   ዋና ዳይሬክተሩ የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሲሆን የባለሥልጣኑ ሥራና አስተዳደር በሚገባ ለመከናወኑ የበላይ ኃላፊ ሆኖ በተለይ የሚከተሉትን ሥልጣንና ተግባር ይፈጽማል፡-

   1. ባለሥልጣኑ በሕግ በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት ገደብ ውስጥ ትእዛዞችን መረጃዎችንና የመሳሰሉትን እያዘጋጀ ማውጣት፤
   2. የሥራውን ፕላንና ፕሮግራም፤ እንዲሁም ዓመታዊ ዝርዝር በጀት እያዘጋጀ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ ሲፈቀድም ተግባራዊ ማድረግ፤
   3. ብሔራዊም ሆነ አለም ዓቀፍ የማሪታይምና ትራንዚት ንግድ ዘርፍ የሚመለከት ማንኛቸውንም ጉዳይ እየተከታተለና እያጠና በየጊዜው ሪፖርትና ሐሳብ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ፤
   4. የማሪታይም ዘርፍን የሚመለከቱ ልዩ ልዩ መረጃዎችንና እስታትስቲኮችን በቋሚ ሁኔታ መሰብሰብ፤

5. ተጠሪነታቸው ለእርሱ የሆኑትን የባለሥልጣኑን ኃላፊዎች መርጦ ለሚኒስቴሩ በማቅረብ ያሾማል፡፡
6. ሠራተኞችን በሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት መቅጠር፤ ማሳደግ፤ ማዛወር፤ ማስተዳደርና ከሥራ ማሰናበት፤
7. ለባለሥልጣኑ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ኘሮግራም መሠረት የሚያስፈልገው ገንዘብ ወጭ ሆኖ እንዲከፈል ማድረግ፤
8. የባለሥልጣኑ ገቢና ወጭ በቴክኒክ ረገድ የተፈጸሙትን ሥራና የሥራ እንቅስቃሴ የሚገልጽ የሒሳብና የሥራ መግለጫ ጽሑፍ በየሦስት ወር፤ እንዲሁም ዓመታዊ አጠቃላይ የሥራ ሪፖርትና በኦዲተር የተረጋገጠ የሒሳብ መግለጫ በየዓመቱ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ፤
9. ዋና ዳይሬክተሩ ለባለሥልጣኑ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልገው መጠን ከሥልጣኑና ከተግባሩ ለባለሥልጣኑ ሠራተኞች መወከል እና
10. ባለሥልጣኑ በሚከስበትም ሆነ በሚከሰስበት ማናቸውም ነገር ራሱ ወይም በነገረፈጁ አማካይነት የባለሥልጣኑ ወኪል ይሆናል፡፡

9. <u>ምክትል ዋና ዳይሬክተር</u>

ዋናውን ዳይሬክተር ይረዳል፣ ዋናውዳይሬክተር በሌለ ጊዜ ለዋናው ዳይሬክተር የተሰጡትን ሥራዎች ሁሉ ያከናውናል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ጉዳዮች</u>

10. <u>የገቢ ምንጭ</u>

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት የገቢ ምንጮችይኖሩታል፤

1. ከመንግሥት የሚመደብ በጀት ፤
2. በባለሥልጣኑ የሚሰበሰብ ዓመታዊ ክፍያ፤ የአገልግሎት ዋጋ፤ የመመዝገቢያ ክፍያ፤ የንብረት ኪራይ ወይም ሽያጭ፤
3. ከማናቸውም ወገን የሚሰጥ የገንዘብ ዕርዳታ፤ እና ተግባሩን ሲያከናውን ከሚያገኘው ማናቸውም ሌላ ገቢ ፡፡

11. <u>ስለበጀትና የበጀት አመት</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የባለሥልጣኑን በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት በማቅረብ ያፀድቃል፡፡

12.**<u>ስለሒሳብ መርማሪዎች</u>**

የባለሥልጣኑ የሒሳብ ሰነድ መዛግብትና ገንዘብ ነክ የሆነ ነገር ሁሉ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሾማቸው የሐሳብ መርማሪዎች በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

13.**<u>ከግብር ነፃ ስለመሆን</u>**

1. በዓለም አቀፍ የባሕር ትራንስፖርት አገልግሎት ላይ በተሰማሩ የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ ድርጅት ሐመሮች ባለቤትነት ምክንያት በሚገኝ ገቢ ላይ ማናቸዉም አይነት ግብር አይጠየቅም፤ ሆኖም ማናቸዉም በባለስልጣኑ የተመዘገበ ሐመር ፤

   ሀ/ ባለስልጣኑ የሚያስከፍለዉን ዓመታዊ የመርከብ ክፍያ፤

   ለ/ የአገልግሎት ክፍያና፤

   ሐ/ የሐመር መመዝገቢያ ክፍያ ይከፍላል፡

2. በኢትዮጵያ ንግድ መርከብ ድርጅት ወይም በባለሥልጣኑ በተመዘገበ ሐመር ላይ ተቀጥሮ በዓለም አቀፍ የባሕር ትራንስፖርት አገልግሎት ላይ የተሰማራ ባሕረኛ የሚያገኘው ደሞዝ ማናቸውም ዓይነት ግብር አይከፈልበትም፡፡

14.**<u>ክልከላ</u>**

ማንኛውም ሰው ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሥራ መሠማራት የባሕር ማመላለሻ አገልግሎት ማካሔድ፤ የባሕር ማመላለሻ አገልግሎት መስጠት፣ የወደብ ዕቃ አስተላላፊነት እና የመርከብ ወኪልነት ሥራ ማካሄድ፤ ሐመር መግዛት፤ መሸጥ፤ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ወይም ከአገር ውጭ ማስወጣት፤ ወይም በሐመር መገልገል ወይም ባሕረኛ መሆን አይችልም።

15.**<u>ስለትናንሽ ሐመሮች</u>**

ሚኒስትሩ የተለየ መመሪያ በማውጣት የዚህ አዋጅ ውሣኔዎች በትናንሽ ሐመሮች ላይ በሙሉ ወይም በከፊል ተፈፃሚ እንዳይሆኑ ለማድረግ ይችላል፡፡

16.**<u>አቤቱታ ስለማቅረብና ስለቅጣት</u>**

ሀ) ሚኒስቴሩ በማሪታይም ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ባለኃብቶችና ሌሎች ግለሰቦች ከፈቃድ አሰጣጥ እና ቁጥጥር ጋር በተያያዘ ባለሥልጣኑ በሚሰጠው ውሣኔ ላይ ለሚቀርብለት የይግባኝ አቤቱታ ተቀብሎ ውሣኔ ይሰጣል፡፡

ለ) ይህን አዋጅና በአዋጁም መሠረት የወጡትን ደንቦች የሚተላለፍ ማንኛዉም ሰው በወንጀለኛ መቅጫ ህግ መሠረት ይቀጣል፡፡

17.<u>የተሻሻሉና የተሻሩ ሕጐች</u>

1. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 471/1998 አንቀፅ 15 ሥር ወደብን በሚመለከት ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተሰጥቶ የነበረው ሥልጣንና ተግባር ተሽሮ ለባለሥልጣኑ ተላልፏል፡፡
2. ትራንስፖርትን ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 468/1997
   ሀ) አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 5 ከፊደል /ሀ-ሐ/ እንዳለ ተሽረዋል፡፡
   ለ) በአንቀጽ 23 ንዑስ ቁጥር /1/ ስር ባሕረኛን በተመለከተ ለትራንስፖርት ባለሥልጣን የተሰጠው ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሽሮአል፡፡

18.<u>ደንብና መመሪያ ስለማውጣት</u>

ይህን አዋጅ በሚገባ ለማስፈጸም፡-

ሀ) የሚኒስትሮች ምክር ቤት አስፈላጊ የሆኑትን ደንቦች ሊያወጣ ይችላል፡፡

ለ) ሚኒስቴሩ አስፈላጊ የሆኑትን መመርያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

19.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ 29 ቀን 1999 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## ደንብ ቁጥር 454/2012

## በማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን ለሚሰጡ አገልግሎቶች የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/1999 አንቀጽ 6(18) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ በማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን ለሚሰጡ አገልግሎቶች የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 454/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **በማሪታም ጉዳይ ባለሥልጣን ለሚሰጡ አገልግሎቶች የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ**

   የማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን በማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/1999 መሠረት ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚያስከፍለው ክፍያ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ በተመለከተው መሠረት ይሆናል፡፡

3. **የተሻረ ደንብ**

   ለማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን የሚከፈሉ የአገልግሎት ክፍያዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 274/2012 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

4. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

   ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

## አዋጅ ቁጥር 588/2000

## ደረቅ ወደብ ለባለዕቃው ስለሚኖረው ኃላፊነት ለመወሰን የወጣ አዋጅ

በባሕር ወደቦች ያለውን የወደብ መጨናነቅ ለመቀነስና በዕቃዎች ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለመከላከል እንዲሁም የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርትን አሠራር በሚገባ በሥራ ላይ ለማዋል የደረቅ ወደብን ሕጋዊ ኃላፊነት ከወቅታዊ ዓለም አቀፍ ሕጎች ጋር ማጣጣም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክሕገ መንግሥት አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "ደረቅ ወደብ ለባለ ዕቃው ስለሚኖረው ኃላፊነት ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 588/2000" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አግባብ የተለየ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

   1. "የደረቅ ወደብ" ማለት በሃገር ውስጥ ተለይቶ በተከለለ ቦታ የወደብ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት ነው፡፡
   2. "ዕቃ" ማለት ማንኛውም የወጪ ወይም የገቢ እቃ ሲሆን የቁም እንስሳትን፣ የዕቃ ማሸጊያዎችንና ኮንቴይነሮችን ይጨምራል፡፡
   3. "የወደብ አገልግሎት" ማለት የወጪና ገቢ ዕቃዎችን የመጫን፣ የማራገፍ፤ የማከማቸት፣ በኮንቴነር የማሸግና ከኮንቴነር የማውጣት እንዲሁም የኮንቴነር ማስተናገጃና ማከማቻ አገልግሎት መስጠት ሲሆን ከነዚሁ ጋር ተዛማጅ የሆኑ አገልግሎቶችን ይጨምራል።
   4. "ዋጋ" ማለት የወጪ ወይም የገቢ ዕቃ መሸጫ ወይም መግዣ ዋጋ ላይ የማጓጓዣ፣ የኢንሹራንስ፣ የታክስና ቀረጥ እና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ወጪዎች ተደምረው የሚገኘው ዋጋ ነው፡፡
   5. "ኤስ.ዲ.አር" በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 548/1999 አንቀጽ 2 (12) የተሰጠው ትርጓሜ ይኖረዋል።

3. **የተፈፃሚነት ወሰን**

የዚህ አዋጅ ደንጋጌዎች ማናቸውም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚቋቋም ማናቸውም የደረቅ ወደብ ለባለእቃዎች የመብት ጥያቄ የሚኖርበትን ሃላፊነት በሚመለከት ተፈፃሚ ይሆናሉ።

## ክፍል ሁለት

## የደረቅ ወደብ ሃላፊነት

4. **የኃላፊነት መሠረት**

   1. ማንኛውም ዕቃ በደረቅ ወደብ አስተዳደሩ ቁጥጥር ሥር እያለ ቢጠፋ፣ ጉዳት ቢደርስበት ወይም ዕቃ ማስረከብ በሚገባው ጊዜ ሳያስረከብ ቢቀር በኃላፊነት ይጠየቃል፡፡
   2. የተለየ ውል ወይንም ደንብ ከሌለ በስተቀር በዚህ አዋጅ አንቀፅ 8 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዕቃ ማስረከብ ዘገየ የሚባለው ደረቅ ወደቡ በውል ወይም በደንብ መሠረት በተመለከተው ጊዜ ውስጥ፣ ከቀረበለት ጊዜ ጀምሮ በ3 ቀን ጊዜ ውስጥ ማስረከብ ሳይችል ሲቀር ነው።
   3. ዕቃው የጠፋው ወይም ጉዳት የደረሰበት ወይም ርክክቡ የዘገየው በባለእቃው ወይም በአጓጓዡ ጥፋት ወይም በዕቃው የተለየ ባህሪ የተነሳ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑ ከተረጋገጠ የደረቅ ወደቡ ተጠያቂነት አይኖርበትም፡፡

5. **የኃላፊነት ወሰን**

   1. የጠፉ ወይም ጉዳት የደረሰበትን ዕቃ በሚመለከት የደረቅ ወደብ የሚኖርበት የኃላፊነት መጠን በዕቃው ዋጋ ልክ ይሆናል፤ ሆኖም በርክክቡ ወቅት የዕቃው ዋጋ በሰነድ ያልተገለፀ ከሆነ የሃላፊነቱ መጠን በዕቃው ክብደት ላይ ተመስርቶ በኪሎግራም ኤስ.ዲ.አር. 2.5 ይሆናል፡፡
   2. የዕቃ ማስረከብ መዘግየትን በሚመለከት የደረቅ ወደብ የሚኖርበት ሃላፊነት ዕቃውን በሚመለከት የተቀበለው የወደብ አገልግሎት ዋጋ በሁለት ተኩል /2.5/ ተባዝቶ በሚገኘው መጠን ልክ ይሆናል፡፡

6. **የተተወ ዕቃ**

   1. በደረቅ ወደብ ውስጥ የተቀመጠ ዕቃ እንደ ተተው ዕቃ የሚቆጠርበትን የጊዜ ገደብና ሊወሰድበት የሚገባውን እርምጃ በሚመለከት የጉምሩክ ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋምና አሠራሩን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 60/1989[132] /እንደተሻሻለ/ አግባብ ያላቸው ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
   2. የደረቅ ወደብ የተተወን ዕቃ በሚመለከት ለሰጠው አገልግሎት ዕቃው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ /1/ መሠረት ተሸጦ ከሚገኘው ገቢ ላይ ተቀናሽ ተደርጎ የመክፈል መብት ይኖረዋል፡፡

**ክፍል ሶስት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

7. **የይርጋ ጊዜ**

   1. በዚህ አዋጅ መሠረት የሚቀርብ የዕቃ ርክክብ ሆነ የሚጠየቅ ክፍያን በሚመለከት የሚቀርብ ክስ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ቀሪ ይሆናል፡፡
   2. የይርጋ ጊዜው መታሰብ የሚጀምረው፡-

      ሀ/ ደረቅ ወደብ ዕቃዎቹን ለመረከብ መብት ላለው ሰው በሙሉ ወይም በከፊል ካስረከበበት ወይም ማስረከብ ከሚገባው ቀን ወይም፣

      ለ/ ዕቃዎቹ በአጠቃላይ የጠፉ ከሆነ ደረቅ ወደብ ስለመጠየቅ መብት ላለው ሰው እቃዎቹ ስለመጥፋታቸው ካሳወቀበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡
   3. የተተወ ዕቃ ሽያጭ የተገኘ ቀሪ ገንዘብን በተመለከተ የዕቃው ባለቤት የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም የደረቅ ወደብ አገልግሎት ክፍያና ወጪዎች ተቀንሶ ተራፊ ገንዘብ ካለ ይህን የተረፈ ገንዘብ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ እንዲሰጠው ካልጠየቀ በቀር መብቱ በይርጋ ይታገዳል፡፡
   4. የይርጋ ጊዜው የሚጀምርበት ቀን በይርጋ ጊዜው ውስጥ አይካተትም፡፡

8. **ተፈፃሚ ስለማይሆኑ ህጎች**

   ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ ለዚህ አዋጅ አተገባበር ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

---

[132] ይህ አዋጅበ15/27 (2001) አ. 622 አንቀጽ 113 (1) የተሻረሲሆንይህምበ20/82 (2006) አ. 859 አንቀጽ 181 (1) የተሻረበመሆኑአንቀፁ በዚሁ አንቀጽ ተተክቶ የሚነበብ ይሆናል፡፡

9. **<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሐምሌ 7 ቀን 2000 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

*መ/ ፖስታና ቴሌኮሙኒኬሽን*

## አዋጅ ቁጥር 464/1997

## የቴሌኮሙኒኬሽን የኤሌክትሪክ ኃይል አውታሮችን ደህንነት ለመጠበቅ የወጣ አዋጅ

ፈጣን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድገት ለማምጣት የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎትና የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ወሳኝ ሚና ያላቸው በመሆኑና እነዚህንም ለማስፋፋት ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ ሚጠይቅ በመሆኑ፣

የቴሌኮሙኒኬሽንና የኤሌክትሪክ ኃይል አውታሮች በመላ ሀገሪቱ ተሰራጭው የሚገኙ ሲሆን በባሕሪያቸው ለጥቃት ድርጊት የተጋለጡ በመሆናቸውና አገልግሎቶቹ ለአፍታ እንኳ ቢቋረጡ በብሔራዊ ኢኮኖሚና ደህንነት ላይ የሚደርሰው ጉዳት እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ፣

የቴሌኮሙኒኬሽንና የኤሌክትሪክ ኃይል አውታሮች ከብሔራዊ ጥቅምና ደህንነት አንጻር የተለየ የሕግ ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55 /1/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የቴሌኮሙኒኬሽንና የኤሌክትሪክ ኃይል አውታሮችን ደህንነት ለመጠበቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር 464/1997" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉሙ የሚያሰጠዉ ካልሆነ ስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

   1. "የቴሌኮሙኒኬሽን አዉታር" ማለት ከቴሌኮሙኒሽን ሲስተም ጋር በተያያዘ አገልግሎት ላይ የዋለ ወይም እንዲውል የታቀደ ማናቸውም መሣሪያ፤ የመሣሪያው ተገጣሚ አካል፣ ሳተላይት፤ ኦፕቲካል ፋይበር፤ ታወር፣ ማስት፣ አንቴና፣ ሽቦ፣ ኬብል፤ ምሰሶ ወይም ማናቸውም እስትራክቸር ነው፣
   2. "የኤሌክትሪክ ኃይል አውታር" ማለት የኤሌክትሪክ ኃይል ከማመንጨትና ማስተላለፍ ሲስተም ጋር በተያያዘ አገልግሎት ላይ የዋለ ወይም እንዲውል የታቀደ ማናቸዉም መሳሪያ፤ የመሳሪያዉ ተገጣሚ አካል፤ ሽቦ፣ ኬብል፣ ምሰሶ ወይም ማናቸውም እስትራክቸር ነው፣
   3. "የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰጪ ድርጅት" ማለት በሕግ የተቋቋመና ከኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኤጀንሲ ፈቃድ አዉጥቶ የቴሌኮሙኒኬሽን ሥራ የሚሠራ ሰዉ ነዉ፡፡

4. “የኤሌክትሪክ ኃይል አቅራቢ ድርጅት” ማለት በሕግ የተቋቋመና ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኤጀንሲ ፈቃድ አውጥቶ የኤሌክትሪክ ኃይል የማቅረብ ሥራ የሚሠራ ሰው ነው፣
5. “ሰዉ” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

3. <u>ጥበቃ</u>

1. በመላ ሀገሪቱ የሚገኙ የቴሌኮሙኒኬሽንና የኤሌክትሪክ አውታሮች በዚህ አዋጅ መሠረት የተለየ ጥበቃ ተሰጥቷቸዋል፣
2. በየደረጃው ያሉ የፌዴራልና የክልል አስተዳደር አካላት ከቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰጪ ድርጅት እና ከኤሌክትሪክ ኃይል አቅራቢ ድርጅት ጋር በመተባበር በመላ ሀገሪቱ የተዘረጉ የቴሌኮሙኒኒኬሽንና የኤሌክትሪክ ኃይል አውታሮችን የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸዉ፣
3. ማንኛውም ፌዴራልና የክልል ከተማ አስተዳደር የግንባታ ፈቃድ ከመስጠታቸዉ በፊት በአካባቢው የቴሌሙኒኬሽን ወይም ኤሌክትሪክ ኃይል አውታር ስለመኖሩ እና ፈቃድ ጠያቂው አካልም ግንባታ ከማካሄዱ በፊት በቴሌኮሙኒኬሽን ወይም በኤሌክትሪክ አውታር ላይ ጉዳት የማይደርስ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸ፡፡

4. <u>ቅጣት</u>

የሀገር ደህንነትን ወይም ኢኮኖሚን በሚጎዳ ሁኔታ በቴሌኮሙኒኬሽን ወይም በኤሌክትሪክ አውታር ላይ የስርቆት ተግባር የፈፀመ ወይም ሆነ ብሎ ጉዳት ያደረሰ ወይም አገልግሎቱ እንዲቋረጥ ያደረገ ማንኛውም ሰው፣ አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ መሠረት የበለጠ የሚቀጣ ካልሆነ በስተቀር፣ ከ5 እስከ 20 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡ የወንጀል ድርጊቱ የተፈጸመው በቸልተኝነት ከሆነ ቅጣቱ ከ6 ወር እስከ 5 ዓመት የሚደርስ እስራት ይሆናል፡፡

5. <u>ተፈጻሚነት የማይኖራቸዉ ሕጎች</u>

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

6. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከሰኔ 23 ቀን 1999ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ 23 ቀን ዓ.ም.**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 1148/2011

## ስለ ኮሙኒኬሽን አገልግሎት የወጣ አዋጅ

የኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች በአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ዕድገት ላይ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው መሆናቸውን በመገንዘብ፤

መንግሥት የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት ለማሻሻል የቴሌኮሙኒኬሽን የገበያ ሥርዓቱን እንደገና ለማደራጀትና በውድድር ላይ የተመሠረተ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አቅርቦት እንዲኖር የወሰነ በመሆኑ፤

መንግሥት የቴሌኮሙኒኬሽን ገበያውን እንደገና ለማዋቀርና በቴሌኮሙኒኬሽን ገበያ ውድድርን ለማስፈን ያስቀመጠውን የፖሊሲ አቅጣጫ ለማሳካት ነፃ ግልፅ እና ተጠያቂነት ያለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55 (1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## አጠቃላይ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የኮሙኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148/2011 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

   1. "**ይግባኝ ሰሚ አካል**" ማለት በባለሥልጣኑ የተሰጠ ውሳኔ ላይ የቀረበ ይግባኝ ለማየትና ለመወሰን ዓላማ በዚህ አዋጅ የተቋቋመ አካል ነው፤
   2. "**የሥራ አመራር ቦርድ**" ማለት የባለሥልጣኑ የበላይ አስተዳዳሪ አካል ማለት ነው፤
   3. "**ብሮድካስተር**" ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ የብሮድካስት አገልግሎት እንዲሰጥ በኢትዮጵያ የብሮድካስት ባለሥልጣን ፈቃድ የተሰጠው አካል ነው፤
   4. "**ብሮድካስቲንግ**" ማለት የሬዲዮ እና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን ለሕዝብ በድምፅና በምስል ማስተላለፍ እና ማሰራጨት ነው፤
   5. "**የኮሙኒኬሽን አገልግሎት**" ማለት የቴሌኮሙኒኬሽን ማስተላለፊያ መስመር በመጠቀም የድምፅ፣ የምስል ወይም የዳታ እና ፖስታን በመጠቀም ቁሳዊ ይዘት

ያለው መልዕክት የማሰራጨት ወይም የመቀበል አገልግሎት ለሕዝብ መስጠት ሲሆን የብሮድካስቲንግ አገልግሎትን ግን አያካትትም፤

6. **"የመረጃ አገልግሎት"** ማለት መረጃን ለማመንጨት፣ ለማግኘት፣ ለማከማቸት፣ ለመለወጥ፣ ለማቀናበር፣ ለመጠቀም ወይም ቴሌኮሙኒኬሽንን በመጠቀም መረጃ እንዲገኝ ለማድረግ የሚያስችል አቅም የማቅረብ እና የኤሌክትሮኒክ ህትመትን የሚያካትት ሲሆን፣ ማንኛውንም እንዲህ ዓይነት ችሎታ ለቴሌኮሙኒኬሽን ስርዓት ወይም የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስተዳደር፣ ቁጥጥር ወይም አመራር መጠቀምን አያካትትም፤
7. **"ኢንተርኮኔክሽን"** ማለት የአንድ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ተጠቃሚዎች ከተመሳሳይ ወይም ከሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ተጠቃሚዎች ጋር እንዲገናኙ ወይም በሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የሚሰጡ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ የሚያስችል በተመሳሳይ ወይም ሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ጥቅም ላይ የዋሉ የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ አካላዊ፣ ቴክኒካዊ እና ምክንያታዊ ግንኙነት ማለት ነው፡ አገልግሎቶች በተሳተፉ አካላት ወይም የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ ተደራሽነት ባላቸው አካላት ሊቀርቡ ይችላሉ፤
8. **"ሚኒስቴር"** ወይም **"ሚኒስትር"** ማለት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ማለት ነው፣
9. **“ባለሥልጣን”** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀፅ 3 የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ባለሥልጣን ነው፣
10. **"የህዝብ ውይይት"** ማለት ባለሥልጣኑ በሥልጣን ወሰኑ ውስጥ ባሉ ጉዳዮች ላይ የህብረተሰቡን አስተያየት የሚሰማበት ሂደት ነው፤
11. **"ጉልህ የገበያ ድርሻ"** ማለት ለኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስፈላጊ የሆኑ መገልገያዎችን ወይም በገበያው ውስጥ ያለውን የገበያ ድርሻ አቅም በመጠቀም በኮሙኒኬሽን አገልግሎት ዋጋ ወይም አቅርቦት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ የማድረግ ችሎታ ነው፤
12. **"የባለድርሻ አካላት ምክክር"** ማለት ባለሥልጣኑ በማንኛውም ወገን ወይም የሕዝብ ጥቅም መብት ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር በሚችል በማንኛውም በሥልጣን ወሰኑ ውስጥ ባለ ጉዳይ ላይ ውሳኔ የሚሰጥበት ግልፅ ሂደት ነው፣

13."**ታሪፍ**" ማለት በቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ለቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች የሚጠየቅ ማንኛውም ክፍያ፣ ዋጋ ወይም ተመን ነው፤

14."**ቴሌኮሙኒኬሽን**" ማለት ድምፅ፣ ምልክት፣ ጽሁፍ፣ ምስል ወይም ማንኛውንም ዓይነት ሌላ መረጃ በኤሌክትሮመግነጢሳዊ ኃይል አማካኝነት በስልክ ሽቦ፣ በሬዲዮ፣ በብርሃን ሞገድ ወይም ኤሌክትሮመግነጢሳዊ ስልት ማሰራጨት፣ ማስተላለፍ ወይም መቀበል ሲሆን በማሰራጨቱ፣ በማስተላለፉ ወይም በመቀበሉ ሂደት ድምፁ፣ ምልክቱ፣ ጽሑፉ፣ ምስሉ ወይም መረጃው እንደገና መደራጀት ወይም በሌላ መንገድ ለውጥ የተደረገበት መሆኑ ልዩነት አያመጣም፤

15."**የቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያ**" ማለት ለቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት የዋለ ወይም ሊውል የታቀደ ማንኛውም መሣሪያ ሲሆን የመሣሪያውን ተገጣሚ አካል ይጨምራል፡

16."**የቴሌኮሙኒኬሽን መስመር**" ማለት ከቴሌኮሙኒሂኬሽን ስርዓት ጋር ለተያያዘ አገልግሎት የዋለ ወይም እንዲውል የታቀደ የስልክ ሽቦ፣ ኬብል፣ ማማ፣ አንቴና፣ ምሰሶ ወይም ማናቸውም ሌላ መሣሪያ ነው፤

17."**የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ**" ማለት ለቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አቅርቦት የሚውሉ የቴሌኮሙኒኬሽን መስመሮች እና ተዛማጅ የማዞሪያ ሥርዓቶች ስብስብ ነው፤

18."**የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር**" ማለት የቴሌኮሞኒኬሽን አገልግሎት ለመስጠት በዚህ አዋጅ መሰረት በባለስልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው ነው፤

19."**የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት**" ማለት ፈቃድ በተሰጠው አካል በቀጥታ ለሕዝብ ወይም ለቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች የሚሰጥ የቴሌኮሙኒኬሽን ማስተላለፍ አገልግሎት ነው፤

20."**ሁሉን አቀፍ ተደራሽነት**" ማለት በመልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ሳይገደብ በባለሥልጣኑ የተወሰነውን የጥራት ደረጃ የጠበቀ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት በተመጣጣኝ ዋጋ ለሁሉም ተጠቃሚዎች ማዳረስ ነው፤

21.**ኮሎኬሽን**" ማለት አንድ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ለአገልግሎት አቅርቦት የሚጠቀምባቸውን የኔትወርክ መሣሪያዎች ወይም ሥርዓቶች የሌላኛው የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የኔትወርክ መሣሪያዎች ወይም ሥርዓቶች የተገጠሙበት ስፍራ ላይ በሁለቱ መካከል በሚደረሰው ስምምነት መሠረት ቴክኒካዊ አግባብነት ባለው ቦታ በአንድ ላይ ማሰቀመጥ ነው፤

22.“**ሲም ካርድ**” ማለት የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ደንበኛ አገልግሎት ለማግኘት ከሚጠቀምበት የሞባይል ስልክ ቀፎ ወይም ሌላ መሣሪያ ጋር ተገጥሞ ከቴሌኮሙኒኬሽን ሥርዓቱ ጋር በመገናኘት ደንበኛው የቴሌኮሙኒኬሽን ግንኙነት እንዲያደርግ እና እንዲቀበል እንዲሁም የቴሌኮሙኒኬሽን ሥርዓቱን የደንበኛውን ማንነት እና መረጃ ለይቶ እንዲያውቅ የሚያስችል የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ደንበኛ ማንነት መለያ ነው፤

23.“**ብሔራዊ የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥር እቅድ**” ማለት ከቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አቅርቦት ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውል በባለሥልጣኑ የሚዘጋጅና የሚተዳደር የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥር እቅድ ነው፤

24.“**የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም**” ማለት ከ3 ኪሎ ኸርዝ እስከ 300 ጊጋ ኸርዝ የሚሸፍን የፍሪኩዌንሲ ኤሌክትሮመግነጢሳዊ ሞገድ ነው፤

25.“**ብሔራዊ የፍሪኩዌንሲ ድልድል እቅድ**" ማለት ከሬዲዮ ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አቅርቦት ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውል በባለሥልጣኑ የሚዘጋጅና የሚተዳደር የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም እቅድ ነው፤

26. **ቁጥር ማዛወር**” ማለት የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ደንበኞች በተመሳሳይ ቦታ ወይም ስፍራ የሚጠቀሙበትን የስልክ ቁጥር ሳይቀይሩ ከአንድ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ወደ ሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር መዛወር የሚችሉበት ሁኔታ ነው፤

27.“**የኢንተርኔት ፕሮቶኮል አድራሻ**” ማለት ለእያንዳንዱ ኮምፒዩተር፣ ፕሪንተር ፣ ስዊች፣ ራውተር ወይም ማንኛውም የኔትወርክ አካል የሆነ ሌላ መሣሪያ የሚሰጥ አግባብነት ያለው አሃዛዊ አድራሻ ነው፤

28.“**የዶሜይን ስም**” ማለት በአንድ ምድብ የሚካተት የኔትወርክ አካል አድራሻ መለያ ስም ነው፤

29."**የንጽጽር ችሎት**” ማለት ለአንድ የተወሰነ ፈቃድ በርካታ አካላት በሚያመለክቱበት ጊዜ በላቀ ሁኔታ ለህዝብ ጥቅም የሚሰጠው አመልካች የሚመረጥበት አሰራር ወይም ዘዴ ነው፤

30."**የደንበኛ መገልገያ መሣሪያ**” ማለት የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሩን ወይም የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰጭውን መሣሪያ ሳይጨምር ደንበኛው በሚገኝበት ቦታ ወይም ስፍራ ተገጥሞ ወይም ደንበኛው ይዞት እየተንቀሳቀሰ የቴሌኮሙኒኬሽን ግንኙነት ለማድረግ፣ ለመቀበል የሚጠቀምበት መሣሪያ ነው፤

31.**“ነፃና ገለልተኛ”** ማለት በአሰራር ተለይቶ የተቋቋመ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር ከማንኛውም ወገን ተፅዕኖ ነፃ ሆኖ በግልፅነት እና በተጠያቂነት የሚፈፅምና ውሳኔ የሚሰጥ የመንግስት ተቋም ነው፤

32.**“ኢንስፔክተር”** ማለት ባለፈቃዶች ይህን አዋጅ እና በአዋጁ መሰረት የወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን አክብረው መስራታቸውን የሚቆጣጠር በባለሥልጣኑ የሚመደብ ሰራተኛ ነው፤

33."**ሰው**" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

34.በወንድ ጾታ የተገለጸው ለሴት ጾታም በእኩል ያገለግላል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን መቋቋም

3. **መቋቋም**

1. የኢትዮጵያ የኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን (ከዚህ በኋላ "ባለሥልጣን" ተብሎ የሚጠራ) ራሱን የቻለ፣ የተሰጠውን ተልዕኮ ለማሳካት የሚያስችል ነፃና ገለልተኛ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡
2. የባለሥልጣኑ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል፡፡

4. **ዋና መስሪያ ቤት**

የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርን ጨምሮ በማናቸውም ስፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል፡፡

5. **ዓላማ**

የባለሥልጣኑ ዓላማ ተወዳዳሪ የገበያ ሥርዓትን በማበረታታት፣ የተጠቃሚዎችን ተደራሽነትና ፍላጎት ያሟላ፣ ጥራቱ የተጠበቀ፣ ቀልጣፋ፣ አስተማማኝ እና ኢኮኖሚያዊ አቅምን ያገናዘበ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት በመላ ሀገሪቱ እንዲስፋፋ ማድረግ ይሆናል፡፡

6. **የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር**

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የኮሙኒኬሽን አገልግሎት በመንግስት ፖሊሲ መሠረት ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ዕድገት ተገቢውን አስተዋጽኦ ሊያበረክት በሚችል መልኩ መካሄዱን ያረጋግጣል፤

2. የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፖሊሲዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤
3. በዚህ አዋጅ በተደነገጉ ባለሥልጣኑን የሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በራሱ ተነሳሽነት ወይም በሕዝብ ጥያቄ መሠረት ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር ያደርጋል፣
4. በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር በአግባቡ ለማከናወን ከማንኛውም ባለፈቃድ፣ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር፣ የፖስታ ኦፕሬተር ወይም ብሮድካስተር አስፈላጊ የሆነ መረጃ መጠየቅ ይችላል፤
5. ደረጃዎችን ለማዘጋጀት ኃላፊነት ከተሰጣቸው ተቋማት እና ከሌሎች አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የኮሙኒኬሽን አገልግሎት የሚሰጥበትን የቴክኒክ ደረጃ ይወስናል፤ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት የተወሰነለትን የጥራት ደረጃ ጠብቆ መሰጠቱን ይቆጣጠራል፤
6. በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሰረት ለኮሙኒኬሽን አገልግሎት የሚጠየቀውን ታሪፍ ይቆጣጠራል፤
7. የኮሙኒኬሽን አገልግሎት በመስጠት ሥራ ላይ ለሚሰማሩ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣ ፈቃድ ያሻሽላል፣ ያድሳል፣ ያግዳል ወይም ይሰርዛል፣
8. ከቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ ጋር ተገናኝተው ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚደረጉ የቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያዎች ዓይነት ይቆጣጠራል፤
9. በኢትዮጵያ ውስጥ ለንግድ፣ ለመንግሥት ፣ ለሃገር መከላከያ እና ለብሔራዊ ደህንነት ሥራዎች ጥቅም ላይ የሚውሉ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም አጠቃቀምን በተመለከተ ሚኒስቴሩን፣ የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣንን እና በኢትዮጵያ የስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂን በበላይነት ለመምራት ሥልጣን የተሰጠው ተቋምን ጨምሮ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ይፈቅዳል፣ ይቆጣጠራል፤
10. በዓለም አቀፍ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ደንቦች መሠረት በኢትዮጵያ የስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂን በበላይነት ለመምራት ሥልጣን ከተሰጠው ተቋም ጋር በመመካከር ለሳተላይት ምህዋር ቦታ ምዝገባ ያመለክታል፣ ያሳውቃል፣ ያስተባብራል፤
11. ብሔራዊ የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥር ፕላን ያዘጋጃል፣ ይመድባል፣ ያስተዳድራል፣ በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፣

12.የኢንተርኔት ፕሮቶኮል አድራሻና የሀገሪቱን የከፍተኛ ደረጃ ዶሜይን ጨምሮ የዶሜይን ስሞችን ይመድባል፣ ያስተዳድራል፣ በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፣

13.በተለያዩ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰጭዎች መካከል የሚኖረውን የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርኮች ኢንተርኮኔክሽን ይቆጣጠራል፣

14.የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ተጠቃሚዎችን መብት ያስጠብቃል፣

15.በኮሙኒኬሽን አገልግሎት ኦፕሬተሮች መካከል እንዲሁም በተጠቃሚዎች እና በኮሙኒኬሽን አገልግሎት ኦፕሬተሮች መካከል የሚነሱ ቅሬታዎችን ይመረምራል፣ አለመግባባቶችን ይፈታል፣

16.አካል ጉዳተኞች እና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ለኮሙኒኬሽን አገልግሎት የሚኖራቸውን ተደራሽነት የሚያግዙትን ጨምሮ አዳዲስ የኮሙኒኬሽን ቴክኒኮች እና ቴክኖሎጂዎችን ለማልማት እና ለመጠቀም የሚያስችሉ ምርምሮችን ያበረታታል፣

17.የኮሙኒኬሽን አገልግሎት መስጠት እና ማካሄድን በተመለከተ በፖሊሲና የሕግ ጉዳዮች ላይ መንግሥትን ያማክራል፣

18.ከሚመለከተው የመንግሥት አካል ጋር በመቀናጀት የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሬጉላቶሪ ጉዳዮችን በተመለከተ በዓለም አቀፍ ጉባዔዎች እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ዘንድ ኢትዮጵያን ይወክላል፣ የኮሙኒኬሽን አገልግሎትን በተመለከተ ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች አተገባበር ይከታተላል፤ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም አጠቃቀምን በተመለከተ ከአህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ይሠራል፣

19. በቴሌኮሙኒኬሽን መስክ የሚሰጥ የቴክኒክ ትምህርት እንዲስፋፋ ከትምህርት ተቋማት ጋር ይተባበራል፤

20.በአዋጁ ድንጋጌዎችና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት የፈቃድ ክፍያዎችን፣ ከኦፕሬተር የሚሰበሰቡ ክፍያዎችን እና ሌሎች የሬጉላቶሪ ክፍያዎችን ይወስናል፣ ይሰበስባል፣፤

21.የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች የቴሌኮሙኒኬሽን ዘርፍን በተመለከተ ኢትዮጵያ የተቀበለችውን ዓለም አቀፍ ግዴታዎች ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፤

22. የአዋጁ ድንጋጌዎች፣ የፈቃድ ሁኔታዎች እና በአዋጁ መሠረት በባለሥልጣኑ የወጡ መመሪያዎች መከበራቸውን ይከታተላል፣ ይመረምራል፣ ተፈጻሚነቱን ለማስከበር አስፈላጊ የሆኑ ውሳኔዎችን ይሰጣል፣
23. የዚህን አዋጅ አፈፃፀም በሚመለከት በብሮድካስተሮች ላይ ለሚቀርቡ ቅሬታዎች እና አለመግባባቶች ምላሽ ይሰጣል፣ ይፈታል፤
24. የዩኒቨርሳል አክሰስ የፋይናንስ ድጋፍ ማቋቋም እና ማስተዳደርን ጨምሮ የዩኒቨርሳል አክሰስ ግብን ይወስናል፣
25. የኢንፎርሜሽን ደህንነት፣ የመረጃ ግላዊነት እና ጥበቃን ያበረታታል፤
26. የኤሌክትሮኒክ ንግድ አስተማማኝ እንዲሆን የኤሌክትሮኒክ ፊርማን ጥቅም ላይ በማዋል በማንኛውም የኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚደረግ ግንኙነት እውነተኛነት እና አስተማማኝነት ያረጋግጣል፤
27. የንብረት ባለቤት ለመሆን፣ ውል ለመዋዋል እና በስሙ ለመክሰስ እና ለመከሰስ ይችላል፤
28. ዓላማውን ለማሳካትና አዋጁን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

7. <u>**የባለሥልጣኑ አደረጃጀት**</u>

ባለሥልጣኑ፡-

1. የሥራ አመራር ቦርድ፤
2. በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተር እና እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና እንደአስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

8. <u>**የሥራ አመራር ቦርድ አባላት**</u>

1. ባለሥልጣኑ ሰባት አባላት ባሉት የሥራ አመራር ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" ተብሎ የሚጠራ) ይመራል፡፡
2. ጠቅላይ ሚኒስትሩ የቦርድ አባላትን ይሾማል፤ ከቦርዱ አባላት መካከል አንዱን የቦርድ ሊቀመንበር ሆኖ እንዲያገለግል ይመድባል፡፡
3. የቦርዱ አባላት አራቱ ከመንግሥት ተቋማት፣ ሶስቱ ከግሉ ዘርፍ እና የትምህርት ተቋማት የሚመረጡ ይሆናል፡፡

9. <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የአዋጁን እና የባለሥልጣኑን ተግባራት አፈፃፀም ይቆጣጠራል፤
2. የባለሥልጣኑን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ እና በጀት እንዲሁም የሥራ አፈፃፀም ሪፖርቶች ይገመግማል፣ ያፀድቃል፤
3. የዚህን አዋጅ አፈፃፀም የሚመለከቱ የፖሊሲ ጉዳዮችን ይተገብራል፤
4. የዋና ዳይሬክተሩን ውሳኔዎች እና የሥራ እንቅስቃሴዎች ይገመግማል፤ ይቆጣጠራል፡፡

10.<u>የቦርድ አባላት የሚመረጡበት መስፈርት</u>

1. አንድ ሰው፡-
   ሀ) ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው፣
   ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት ኗሪ የሆነ፣
   ሐ) በባለሥልጣኑ የሥልጣን ወሰን ውስጥ ከሚገኝ ማንኛውም ተቋም ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ የፋይናንስ ጥቅም የሌለው፣
   መ) ከወንጀል ነፃ ከሆነ፤
   ሠ) በማንኛውም ጊዜ በሥነ-ምግባር ጉድለት ምክንያት ከኃላፊነት ያልተነሳ ከሆነ፣ የቦርድ አባል ሆኖ መሾም ወይም በአባልነት መቆየት ይችላል፡፡
2. የቦርዱ አባላት በፋይናንስ፣ በአካውንቲንግ፣ በሕግ፣ በተጠቃሚዎች ጉዳይ፣ በቴሌኮሙኒኬሽን ኢንጂነሪንግ፣ በብሮድካስቲንግ፣ በጋዜጠኝነት፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ በኢኮኖሚክስ፣ በሕዝብ አስተዳደር እና አግባብነት ባላቸው ተዛማጅ መስኮች ባሳዩት ብቃት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የተመረጡ ሊሆኑ ይገባል፡፡

11.<u>የቦርድ አባላት የሥራ ዘመን</u>

1. የቦርዱ አባላት የስራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የመጀመሪያው የቦርድ አባላት የሚያገለግሉበት የስራ ዘመን የተለያየ እንዲሆን ይደረጋል፡፡
3. ማንኛውም የቦርድ አባል ለሁለተኛው የአምስት ዓመት የሥራ ዘመን እንደገና ሊሾም ይችላል፡፡

12.የቦርድ አባላት ከአባልነት የሚነሱበት ሁኔታዎች

1. ጠቅላይ ሚኒስትሩ አንድን የቦርድ አባል በሚከተሉት ምክንያቶች ሊያነሳ ይችላል፣
   ሀ) በህመም ምክንያት ተግባሩን በአግባቡ ለመወጣት ካልቻለ፣
   ለ) ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት በወንጀል ጥፋት ተከሶ ቢያንስ የአንድ ዓመት እስራት የተፈረደበት ከሆነ፣
   ሐ) የዚህን አዋጅ የጥቅም ግጭት ድንጋጌዎች እያወቀ ጥሰት ከፈጸመ፣
   መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 ንዑስ-አንቀጽ (1) በተደነገገው መሠረት አባል ሆኖ ለማገልገል ብቁ የሚያደርጉ ሁኔታዎችን አሟልቶ መቀጠል ካልቻለ፡፡
2. ማንኛውም የቦርድ አባል በሞት ወይም ኃላፊነቱን በመልቀቁ ወይም ከኃላፊነቱ እንዲነሣ በመደረጉ ምክንያት የአባላት መጓደል በሚፈጠርበት ጊዜ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተተኪ የቦርድ አባል ይሾማል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሚሾመው አዲስ የቦርድ አባል የሚያገለግለው የተሰናባቹ የቦርድ አባል ቀሪ የአገልግሎት ዘመን እስኪጠናቀቅ ብቻ ይሆናል፡፡

13.ቦርዱ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት

1. ቦርዱ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ መሰብሰብ አለበት፡፡
2. ሊቀመንበሩ ለቦርዱ እና ለሕዝብ ከ 14 ቀናት በማያንስ ጊዜ አስቀድሞ በማሳወቅ ስብሰባ የመጥራት ሥልጣን አለው፡፡ ሆኖም ከ 14 ቀናት ባነሰ ጊዜ ውስጥ አስቀድሞ በማሳወቅ ቦርዱ እንዲሰበሰብ የሚያስገድዱ ሁኔታዎች ሲኖሩ ቢያንስ ከሌሎች ሁለት የቦርድ አባላት ስምምነት ካገኘ ሊቀመንበሩ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡
3. በቦርዱ በወቅቱ በማገልገል ላይ ካሉት አባላት መካከል ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤው እንደተሟላ ይቆጠራል፡፡
4. ሊቀመንበሩ በማይኖርበት ጊዜ ሌላ አባል ሊቀመንበር ሆኖ እንዲመራ መወከል ይችላል፡፡ ሊቀመንበሩ በሞት፣ ከኃላፊነት በመልቀቅ ወይም በመነሳት በማይኖርበት ጊዜ በጠቅላይ ሚኒስትሩ አዲስ ሊቀመንበር እስኪሾም ድረስ የተቀሩት የቦርድ አባላት ከመካከላቸው አንድ አባል እንደ ሊቀመንበር እንዲያገለግል በአብላጫ ድምፅ ሊመርጡ ይችላሉ፡፡፡

5. ቦርዱ በተገኙ አባላት አብላጫ ድምፅ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ሆኖም ውሳኔ እንዲሰጥበት በቀረበ ጉዳይ ላይ የአባላት ድምፅ እኩል በእኩል ከተከፈለ ሊቀመንበሩ ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፡፡

14. <u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ዋና ዳይሬክተሩ የባለሥልጣኑ ዋና ስራ አስፈፃሚ ሲሆን በቦርዱ በሚሰጠው መመሪያ እና በዚህ አዋጅ መሠረት የባለሥልጣኑን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፦
   ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባር ያከናውናል፤
   ለ) በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት የባለሥልጣኑን ሰራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤ ደመወዝና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን በተመለከተ የወቅቱን የገበያ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ አጥንቶ ለመንግስት ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፤
   ሐ) የባለሥልጣኑን ፕሮግራም እና በጀት በማዘጋጀት ለመንግሥት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤
   መ) ለባለሥልጣኑ በተፈቀደው በጀት መሠረት ወጪዎችን ያወጣል፤
   ሠ) በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰበሰቡ የንግድና ሌሎች ሚስጥራዊ መረጃዎችን ይጠብቃል፤
   ረ) ከሦስተኛ ወገን ጋር በሚደረግ ግንኙነት ሁሉ ባለሥልጣኑን ይወክላል፤
   ሰ) የባለሥልጣኑን የስራ እንቅስቃሴዎች እና የፋይናንስ ሪፖርቶችን በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ያቀርባል፡፡
3. ዋና ዳይሬክተሩ ለሥራው ቅልጥፍና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለባለሥልጣኑ ሌሎች ኃላፊዎች እና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

15. <u>የምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ከዋና ዳይሬክተሩ በሚሰጥ መመሪያ መሠረት
   ሀ) የባለሥልጣኑን ተግባራት በማቀድ፣በማደራጀት በመምራትና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛሉ፣፤
   ለ) የዘርፋቸውን ዕቅድ በማዘጋጀትና በማፀደቅ ተግባራዊ ያደርጋሉ፣

ሐ) በዋና ዳይሬክተሩ የሚሰጣቸውን ሌሎች ሥራዎች ያከናውናሉ፡፡

2. ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ተለይቶ ውክልና የተሰጠው ምክትል ዋና ዳይሬክተር ለዋና ዳይሬክተሩ የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

16.<u>የሚኒስቴሩ ተግባር</u>

ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ መሠረት የኮሙኒኬሽን ዘርፍ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ዕድገት የሚኖረውን ጠቀሜታ ለማረጋገጥ አጠቃላይ የዘርፍ ፖሊሲ የማዘጋጀት ተግባርና ኃላፊነት አለው፡፡

17.<u>በጀት</u>

1. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የባለሥልጣኑ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፦

   ሀ) በመንግሥት ከሚመደብ በጀት፣

   ለ) በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 6 (20) መሠረት ከሚሰበሰቡ የፈቃድና ሌሎች ክፍያዎች ፣

   ሐ) ሌሎች ምንጮች፡፡

2. የባለሥልጣኑ የፋይናንስ አስተዳደር የሚመራው በፌደራል የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር648/2001 (እንደተሻሻለ) እና በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ይሆናል፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው በጀት በባለሥልጣኑ ስም በሚከፈት የባንክ ሂሳብ ተቀማጭ ሆኖ የባለሥልጣኑን ሥራዎች ለማስፈፀም ወጪ ይሆናል፡፡

18.<u>ሂሳብ መዛግብት</u>

1. ባለሥልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

2. የባለሥልጣኑ የሂሳብ መዛግብትና ሌሎች የፋይናንስ ሰነዶች በፌደራል ዋና ኦዲተር ወይም የፌደራል ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>የፈቃድ መስፈርትና ሁኔታዎች</u>

19.<u>ስለ ኢንቨስትመንት</u>

1. በሌላ ሕግ የተደነገገ አዋጅ ወይም ደንብ ቢኖርም ማንኛውም የሀገር ውስጥ እና የውጭ ባለሃብት የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት፣ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ወይም የቴሌኮሚኒኬሽን ኔትወርክ ባለቤትነት ፈቃድ የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ምን ያህል አዲስ ኦፕሬተሮች እንደሚገቡ፣ በምን መልኩ እና መቼ ፈቃድ እንደሚሰጥ በመንግስት ይወሰናል፡፡

20.<u>የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ</u>

1. ማንኛውም ሰው ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ሳይኖረው የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ለመስጠት አይችልም፡፡
2. ባለሥልጣኑ የፈቃድ ጊዜውን ጨምሮ ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚወስነው የፈቃድ ሁኔታዎች መሠረት የፈቃድ ዓይነቶችን በመለየት የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ፈቃድ ይሰጣል፡፡
3. ባለሥልጣኑ ስለፈቃድ ማመልከቻ እና የእድሳት አሰራር ሥርዓቶችን ለማዘጋጀት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 35-38 መሠረት የባለድርሻ አካላት ምክክር ማካሄድ አለበት፡፡
4. ባለሥልጣኑ የፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት ሲዘረጋ፣ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ ሲሰጥ እና እንደ አስፈላጊነቱ የፈቃድ ሁኔታዎችን ሲያዘጋጅ የሚከተሉትን መርሆዎች በመከተል እና ግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል፦

   ሀ) ግልፅነት፣ ፍትሐዊነት እና ያለማዳላት፤

   ለ) ውጤታማ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ አጠቃቀምና አስተዳደር፣

   ሐ) በብሔራዊ የቁጥር ፕላን መሠረት ቁጥር መኖሩን፤

   መ) በኮሙኒኬሽን ኢንዱስትሪ ውስጥ ፍትሐዊ ውድድርና ኢንቨስትመንትን የማበረታታት ፍላጎት፤

   ሠ) ዘመናዊ፣ ጥራቱ የተጠበቀ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ተደራሽ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የማቅረብ ፍላጎት፣ ችሎታ፣ ብቃት እና አቅም፤ እና

   ረ) ባለሥልጣኑ እንደ አስፈላጊነቱ እና ብሔራዊ ጥቅምን ከግምት ውስጥ በማስገባት ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚወስናቸው ሌሎች መርሆዎች፡፡

21.<u>የፈቃድ ሁኔታዎች</u>

1. ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ (5) የተገለጸውን ዓላማ ለማሳካት የፈቃድ ዘመን እርዝማኔን ጨምሮ አስፈላጊ ናቸው ያለውን የኮሙኒኬሽን አገልግሎት የፈቃድ ሁኔታዎች መወሰን አለበት፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ የሚከተሉትን የፈቃድ ሁኔታዎች እንዲይዝ ሊደረግ ይችላል፡፡

ሀ) ባለፈቃዱ በመላ ሀገሪቱ አድልኦ በሌለው ዋጋ አገልግሎት ማቅረብ እንዳለበት፤

ለ) ባለፈቃዱ ከአገልግሎት ጋር የተያያዙ ክፍያዎችን እና ለተሰጠው አገልግሎት ተፈፃሚ የሚሆኑ ሌሎች የውል ሁኔታዎችን በፈቃዱ ውስጥ በተገለጸው ፎርም መሠረት ማሳወቅ እንዳለበት፣

ሐ) የአገልግሎት ታሪፍ ለመወሰን የሚያገለግሉ መመዘኛዎችን፣

መ) ባለፈቃዱ የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃዎችን ጨምሮ በፈቃዱ ውስጥ የተገለፁ የቴክኒክ ደረጃዎችን እና መስፈርቶችን ማሟላት እንዳለበት፡፡

3. ባለሥልጣኑ ለህዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 35-38 የተቀመጠውን የአሰራር ሥርዓት በመከተል ማንኛውንም የፈቃድ ሁኔታዎች በማንኛውም ጊዜ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

## ክፍል አራት
## የቴክኒክ ቁጥጥር

### 22. የቴክኒክ ደረጃዎች

1. ባለሥልጣኑ የደንበኛ መገልገያ መሣሪያዎችን ጨምሮ የሬዲዮኮሙኒኬሽን እና የቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያዎችን የሚመለከቱ የቴክኒክ ደረጃዎችን ይወስናል፡፡
2. ደረጃዎችን ለመወሰን የሚወጣ ማንኛውም መመሪያ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 35-38 መሠረት በሚካሄድ የባለድርሻ አካላት ምክክር መዘጋጀት እና በባለሥልጣኑ ድረ-ገጽ እና ለሕዝብ በቂ ግንዛቤ መስጠት በሚያስችሉ ሌሎች አግባብነት ያላቸው ዘዴዎች ይፋ መደረግ አለበት፡፡

### 23. የመሣሪያዎችን የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጥ

1. ባለሥልጣኑ ከቴሌኮሙኒኬሽን ሲስተሙ ጋር ከመገጠማቸው በፊት የባለሥልጣኑን የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ማግኘት የሚያስፈልጋቸውን የሬዲዮኮሙኒኬሽን እና የቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያዎች ዝርዝር በመወሰን ለሕዝብ ያስታውቃል፡፡
2. ባለሥልጣኑ ፈቃድ ባላቸው አገልግሎት ሰጪዎች፣ የመሣሪያ አምራቾች ወይም ፤ አስመጪዎች በሚቀርብ ጥያቄ መሰረት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ የሬድዮ ኮሙኒኬሽን እና የቴሌኮሙኒኬሽን መሳሪያዎችን በተመለከተ ፍተሻ ማካሄድ እና የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ሠርተፊኬት መስጠት አለበት፡፡

3. ባለሥልጣኑ የሬዲዮኮሙኒኬሽን እና የቴሌኮሙኒኬሽን መሳሪያዎችን የቴክኒክ ብቃት ለማረጋገጥ የሚከተሉትን መመዘኛዎች ማገናዘብ አለበት፦
   ሀ) በህይወት እና በጤንነት አደጋ ያለማድረስ ሁኔታዎች፤
   ለ) የመረጃ ጥበቃን ጨምሮ የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ ጥገና ሁኔታ፤
   ሐ) የኤሌክትሮማግኔቲክ መጣጣም ሁኔታ፤
   መ) የኤሌክትሮማግኔቲክ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ተገቢ አጠቃቀም ሁኔታዎች፤
   ሠ) በቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ እና በመሣሪያው መካከል የሚኖረው መጣጣም፤
   ረ) ባለሥልጣኑ በመመሪያ የሚወስናቸው ሌሎች መመዘኛዎች፡፡
4. የባለሥልጣኑ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ የሚያስፈልጋቸውን የሬዲዮ ኮሙኒኬሽን እና የቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያዎች ባለሥልጣኑ በቅድሚያ ሳይፈቅድ ማምረት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት ወይም ማከፋፈል የተከለከለ ነው፡፡
5. ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ በሚመርጣቸው ዓለም አቀፍ እውቅና ያላቸው የፍተሻ አካላት የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው የሬዲዮኮሙኒኬሽን እና የቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያዎች ማስመጣት እና መጠቀምን ለመፍቀድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 35-38 በተገለፀው መሠረት የባለድርሻ አካላት ምክክር ማካሄድ ይችላል፡፡

24. <u>የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም አስተዳደር</u>

1. ባለሥልጣኑ በኢትዮጵያ ውስጥ ለንግድ፣ ለመንግሥት፣ ለሀገር መከላከያና ለብሔራዊ ደህንነት ጥቅም ላይ የሚውሉ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ለመቆጣጠር፣ ለማቀድ፣ ለማስተዳደር እና ፈቃድ ለመስጠት ኃላፊ ይሆናል፡፡
2. ባለሥልጣኑ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ሲያስተዳድር ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን ወይም ያፀደቀቻቸውን አግባብነት ያላቸው ደረጃዎች እና የዓለም አቀፍ የቴሌኮሙኒኬሽን ሕብረት መስፈርቶችን እና የሬዲዮ ደንቦች በማክበር ይሆናል፡፡
3. ባለስልጣኑ በዓለም አቀፍ የቴሌኮሙኒኬሽን ሕብረት የሬዲዮ ሬጉሌሽን እና አግባብነት ያላቸው አህጉራዊ ስምምነቶች መሠረት ብሔራዊ የፍሪኩዌንሲ ድልድል ሠንጠረዥ ማዘጋጀት እና በየወቅቱ ማሻሻል አለበት፡፡
4. ባለሥልጣኑ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም አጠቃቀምን በተመለከተ በሀገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ ያስተባብራል፣ የሀገሪቱን ጥቅም በዓለም አቀፍ ደረጃ ያስጠብቃል፡፡

5. ባለሥልጣኑ ለኮሙኒኬሽን አገልግሎት አቅርቦት የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ፈቃድ አሰጣጥ እና አጠቃቀም መመሪያ ሲያዘጋጅ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 35 - 38 መሰረት አንድ ወይም ከዚያ በላይ የባለድርሻ አካላት ምክክር ማካሄድ ይችላል፡

25. **የፍሪኩዌንሲ ምደባ**

1. ባለሥልጣኑ ለቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት፣ ለሬዲዮኮሙኒኬሽን እና ለሬዲዮና ቴሌቪዥን ሥርጭት አገልግሎት የሚውል ፍሪኩዌንሲ ይመድባል፡፡
2. ባለሥልጣኑ የፍሪኩዌንሲ አጠቃቀምን በሀገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ ያስተባብራል፤ በትክክል ጥቅም ላይ መዋሉንም ይቆጣጠራል፡፡
3. በፍሪኩዌንሲ ለመጠቀም በቀረበ ማመልከቻ ላይ ለመወሰን የሀገሪቱ የወቅቱና የወደፊት ፍላጎት መገናዘብ ይኖርበታል፡፡
4. በተመደበ ፍሪኩዌንሲ የመጠቀም ፈቃድ በጊዜ ተወስኖ ለተለያዩ ሰዎች ሊሰጥ ይችላል፡፡
5. ለፍሪኩዌንሲ ምደባ በቀረቡ ማመልከቻዎች መካከል የጋራ መነጣጠል በሚኖርበት ጊዜ ባለሥልጣኑ ከማመልከቻዎቹ መካከል ለመምረጥ ተገቢ ነው ብሎ ያመነውን ዘዴ መጠቀም አለበት፡፡ ከዘዴዎቹ መካከል የጨረታ ውድድር፣ ዕጣ ወይም የንጽጽር ችሎት ሊካተቱ ይችላሉ፡፡

26. **የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ክፍያ**

1. ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 35-38 በተደነገገው አሰራር መሠረት የዚህን አዋጅ ዓላማ በሚያግዝ ሁኔታ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ሀብት ለኮሙኒኬሽን አገልግሎት አቅርቦት ለመጠቀም የሚያስችል የክፍያ መመሪያ ያዘጋጃል፡፡
2. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) መሠረት የክፍያ መመሪያ ሲያዘጋጅ ክፍያው ቢያንስ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማሟላቱን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፦
   ሀ) የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ሀብት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም የሚኖረውን ተገቢ ዋጋ የንግድ ዓላማ ካላቸው የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰጪዎች ለመሰብሰብ እና ባለሥልጣኑ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ሀብት ለማስተዳደር፣ ፈቃድ ለመስጠት እናለ መቆጣጠር የሚያወጣውን ወጪ ለመሸፈን መቻሉን፤
   ለ) ፍትሃዊ፣ አድልኦ የሌለበት እና ግልፅ በሆነ መንገድ የተዘጋጀ መሆኑን፤ እና

ሐ) በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ለማልማት እና ለማስፋፋት የሚያበረታታ መሆኑን፡፡

27. <u>ቁጥርና አድራሻ ስለመደልደል</u>

1. ማንኛውም ሰው በባለሥልጣኑ ፈቃድ እና በዚህ አዋጅ ለተፈቀደው ዓላማ ካልሆነ በስተቀር የቁጥር እና አድራሻ ሀብቶችን መጠቀም አይችልም፤
2. ባለሥልጣኑ በኢትዮጵያ ውስጥ ለቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት እና ለኢንፎርሜሽን አገልግሎት አቅርቦት የሚውሉ የቁጥር እና የአድራሻ ሀብቶች ማስተዳደር እና መቆጣጠር አለበት፡፡ ይህም ብሔራዊ የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥር ዕቅድ፣ የኢንተርኔት ፕሮቶኮል አድራሻ፣ የኢንተርኔት ዶሜይን ምዝገባ እና ማንኛውም የሀገሪቱን የቁጥርና የአድራሻ ሀብት ማካተት አለበት፡፡
3. ማንኛውም የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ባለሥልጣኑ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በመከተል በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ለቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አቅርቦት የቁጥር ሀብት የማግኘት መብት አለው፡፡
4. ባለሥልጣኑ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ለቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አቅርቦት ቁጥር የሚያገኙበትን የአሰራር ሥርዓት ይወስናል፡፡
5. ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 35 — 38 መሠረት አንድ ወይም ከዚያ በላይ የባለድርሻ አካላት ምክክር በማካሄድ የቁጥርና የአድራሻ ሀብት አስተዳደር እና አጠቃቀም መመሪያ ያዘጋጃል፡፡ መመሪያው የቁጥር ሀብቶች ለመጠቀም የቀረበውን ማመልከቻ በሙሉ ወይም በከፊል ውድቅ ለማድረግ የሚያስችሉ የሚከተሉትን ድንጋጌዎች ማካተት ይኖርበታል፡-

    ሀ) አመልካቹ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ካልሆነ

    ለ) የተጠየቀው የቁጥር ሀብት አጠቃቀም ከብሔራዊ ቁጥር ፕላኑ ጋር የማይጣጣም ከሆነ፤

    ሐ) የተጠየቀው የቁጥር ሀብት አጠቃቀም ከአዋጁ ድንጋጌዎች፣ ባለሥልጣኑ ካወጣው መመሪያ ወይም ማንኛውም በኢትዮጵያ ውስጥ ተፈፃሚነት ካለው ሕግ ጋር የማይጣጣም ከሆነ፤

    መ) የተጠየቀው የቁጥር ሀብት አጠቃቀም በብሔራዊ ደህንነት ወይም የሕዝብ መረጋጋት ላይ አደጋ የሚያስከትል ከሆነ፤

ሠ) አመልካቹ የቁጥር ሀብቱን በወቅቱ ወይም ውጤታማ በሆነ መንገድ የማይጠቀም ከሆነ፡፡

6. ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ መሠረት በፀደቀው መመሪያ የቁጥር ሀብት ለመጠቀም የቀረበውን ማመልከቻ ውድቅ በሚያደርግበት ጊዜ ማመልከቻውን ውድቅ ለማድረግ ያስቻለውን ምክንያት በመግለጽ ውሳኔውን በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡
7. አመልካቹ ባለሥልጣኑ የመጀመሪያውን ማመልከቻ ውድቅ ያደረገበትን ማንኛውን ሕጋዊ ወይም የቴክኒክ ጉድለቶች በማሟላት በቁጥር ሀብት ለመጠቀም የተስተካከለ ማመልከቻ ማስገባት ይችላል፡፡ ሆኖም አመልካቹ በአዋጁ መሠረት ባለሥልጣኑ ማመልከቻውን ውድቅ ያደረገበትን ውሳኔ በድጋሚ እንዲያየው መጠየቅ ወይም በውሳኔው ላይ ለይግባኝ ሰሚ አካል ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡
8. ባለሥልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 35 - 38 መሠረት የባለድርሻ አካል ምክክር በማካሄድ የኢንተርኔት ዶሜይን ምዝገባ መመሪያ የማውጣት ሥልጣን አለው፡፡
9. ባለሥልጣኑ በራሱ እየተቆጣጠረ ከአንድ ወይም ከዚያ በላይ ከሆኑ ድርጅቶች ጋር የሀገሪቱን የቁጥር እና የአድራሻ ሀብት ለማስተዳደር ስምምነት ሊፈጽም ይችላል፡፡

28.<u>የቁጥር ምዝገባ፣ አጠቃቀም እና ስለማዛወር</u>

1. ባለፈቃዱ የቁጥር መጠቀሚያ ፈቃድ ካገኘበት ጊዜ አንስቶ እስከ ሶስት ዓመት ጊዜ ድረስ ቁጥሮችን አቆይቶ መጠቀም እንዲችል ባለሥልጣኑ ሊፈቅድለት ይችላል::
2. ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 35- 38 መሠረት የቁጥር አጠቃቀም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡
3. ባለሥልጣኑ ሁሉንም የተመደቡ ቁጥሮች እና ለልዩ አገልግሎት የተወሰኑትን ወይም ተለይተው እንዲቀመጡ የተደረጉትን እና ቁጥር የተመደበላቸው ተጠቃሚዎችን ዝርዝር ያካተተ አጠቃላይ የቁጥሮች መዝገብ መያዝ አለበት፡፡ የቁጥሮች መዝገብ በፋይል ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ሊያዝ የሚችል ሲሆን ባለስልጣኑ የቁጥር መዝገቡን ለማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል ያለምንም ክፍያ ተደራሽ ማድረግ አለበት፡፡
4. ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 35 - 38 መሠረት የባለድርሻ አካላት ምክክር በማካሄድ ደንበኞች ቁጥራቸውን ሳይቀይሩ ከአንድ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ወደ ሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የሚዛወሩበት አሰራር በቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች መካከል ለመተግበር የሚያስችል መመሪያ ማውጣት አለበት፡፡

**29.የቁጥር ክፍያ**

1. ባለሥልጣኑ የዚህን አዋጅ ዓላማ በተሻለ ሁኔታ ለማስፈጸም ለቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት እና ለኢንፎርሜሽን አገልግሎት አቅርቦት የቁጥር ሀብቶች መጠቀሚያ ክፍያ ለመወሰን መመሪያ ያወጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) መሠረት ባለሥልጣኑ የሚያወጣው መመሪያ ክፍያው ቢያንስ የሚከተሉትን ማሟላቱን ማረጋገጥ አለበት፦
   ሀ) የቁጥር ሀብቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም የሚኖረውን ተገቢ ዋጋ የንግድ ዓላማ ካላቸው የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት እና የኢንፎርሜሽን አገልግሎት ሰጪዎች ለመሰብሰብ መቻሉን፣
   ለ) ፍትሃዊ፣ አድልኦ የሌለበት እና ግልፅ በሆነ መንገድ የተዘጋጀ መሆኑን፤ እና
   ሐ) በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት እና የኢንፎርሜሽን አገልግሎት ለማልማት እና ለማስፋፋት የሚያበረታታ መሆኑን፡፡

**30.የልዩ ቁጥር አገልግሎት ዓይነቶች**

1. ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 35- 38 መሠረት የባለድርሻ አካላት ምክክር በማካሄድ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች ለደንበኞቻቸው ማቅረብ የሚጠበቅባቸውን የልዩ ቁጥር የአገልግሎት ዓይነት ዝርዝር ለመወሰን ይችላል፡፡
   ሀ) የልዩ ቁጥር አገልግሎቶች የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡ የድንገተኛ አደጋ አገልግሎቶች፤
   ለ) የመረጃ እገዛ አገልግሎቶች፤
   ሐ) የኦፕሬተር እገዛ አገልግሎቶች፤
   መ) ለአካል ጉዳተኛ ደንበኞች አገልግሎቶች፣ እና
   ሠ) ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ናቸው ብሎ የሚያምንባቸው ሌሎች አገልግሎቶች፡፡
2. ባለሥልጣኑ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች የድንገተኛ አደጋ እርዳታ አገልግሎቶች ለደንበኞቻቸው እንዲያቀርቡ በሚወስንበት ጊዜ በመላ ሀገሪቱ ለስልክ አገልግሎት የተመደበ ብሔራዊ የድንገተኛ አደጋ እርዳታ ልዩ ቁጥር እንዲጠቀሙ በማድረግ የህዝብ ደህንነትን ማሳደግ እና ለድንገተኛ አደጋ እርዳታ አገልግሎት ተደራሽነት አስፈላጊ የሆኑ መሠረተ ልማቶች በመላ ሀገሪቱ በፈጣን ሁኔታ እንዲዘረጉ ማበረታታት ይጠበቅበታል፡፡

## 31.ቁጥጥር የማድረግ ሥልጣን

1. ባለሥልጣኑ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እና በዚህ አዋጅ መሠረት የሰጣቸው ውሳኔዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ ኢንስፔክተሮች ለመመደብ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተመደበ ኢንስፔክተር የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት በሚያካሂድ ድርጅት ውስጥ ወይም ማንኛውም የሬዲዮ መገናኛ መሣሪያ ይኖራል ብሎ ለማመን በቂ ምክንያት በሚኖረው ሥፍራ በሥራ ሰዓት ለመግባትና ቁጥጥር ለማድረግ ይችላል፡፡
3. ኢንስፔክተሩ ማንኛውንም የቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያ ለመመርመርና አግባብነት ያላቸውን ሰነዶች ለማየትና ቅጂው እንዲሰጠው ለመጠየቅ ይችላል፡፡
4. ኢንስፔክተሩ ቁጥጥር ወደሚያደርግበት ማንኛውም ስፍራ ከመግባቱ በፊት የመታወቂያ ወረቀቱን ማሳየት አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## ለቴሌኮሙኒኬሽን መስመር መሬት እና ሕንፃዎችን ስለ መጠቀም

## 32.በመሬትና ሕንፃ ስለመጠቀም

1. ማንኛውም የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ወደ ማንኛውም መሬት ወይም ህንፃ ከመግባቱ ከ10 ቀን በፊት የጽሁፍ ማስታዎቂያ ለመሬቱና ለህንፃው ባለይዞታ ወይም ባለቤት በመስጠት የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይችላል፡-
   ሀ) የቴሌኮሙኒኬሽን መስመር ከመሬት በላይና በታች ወይም በህንፃው ላይ ማሳለፍ፣ ማስቀመጥ ወይም መትከል፣
   ለ) የቴሌኮሙኒኬሽን መስመር ለመደገፍ ማንኛውንም ምሰሶ ማቆም፤
   ሐ) የቴሌኮሙኒኬሽን መስመር ለመደገፍ በመሬቱ ላይ ባለ ማንኛውም ነገር ላይ ቅስት ማያያዝ ወይም ማሰር፤
   መ) የቴሌኮሙኒኬሽን መስመር ሊጎዳ፣ እንቅፋት ሊሆን ወይም ጣልቃ ሊገባ የሚችል ማንኛውንም ዛፍ ወይም ቅርንጫፍ መቁረጥ፡፡
2. ማንኛውም የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር በግል ይዞታ ስር በሚገኝ መሬት ወይም ህንፃ ላይ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተዘረዘሩትን ተግባራት ሲያከናውን ለባለይዞታው ተገቢውን የመጠቀሚያ ክፍያ ይፈፅማል፡፡ የክፍያው መጠንም ባለሥልጣኑ በሚያወጣው የክፍያ መመሪያ መሰረት ይወሰናል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተቀመጠው ቢኖርም ማንኛውም ኦፕሬተር ባለሥልጣኑ በሚወስነው መሰረት የቴሌኮሙኒኬሽን በሚያወጣው መመሪያ አሰቀድሞ የተዘረጋ የቴሌኮሙኒኬሽን መስመርን መጠገን፣ ማሻሻል፣ መፈተሽ፣ መለወጥ ወይም ማንሳት ይችላል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተጠቀሰው መመሪያ በባለሥልጣኑ እስኪወጣ ድረስ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የተዘረጉ የቴሌኮሙኒኬሽን መስመሮችን የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሩ አግባብ ባለው ሁኔታ ለመሬት ባለይዞታው ወይም ለህንፃው ባለቤት በቅድሚያ በማሳወቅ ወደ መሬቱ ወይም ወደ ህንፃው በመግባት የቴሌኮሙኒኬሽን መስመር መጠገን፣ ማሻሻል፣ መፈተሽ፣ መለወጥ ወይም ማንሳት ይችላል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተቀመጠው ቢኖርም የመሬቱ ባለይዞታ ወይም የህንፃው ባለቤት ወደ ስፍራው እንዳይገባ ከከለከለው የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሩ ቅሬታውን ለባለሥልጣኑ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
6. የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር በዚህ አንቀፅ የተደነገገውን መብት ሲጠቀም በተቻለ መጠን በመሬቱ፣ በህንፃውና በአካባቢው ላይ አነስተኛ ወይም ዝቅተኛ ጉዳት የሚያስከትል መሆኑን ማረጋገጥ እና ላደረሰው ጉዳት ወይም ኪሳራ ለመሬቱ ባለይዞታ ወይም ለህንፃው ባለቤት ተገቢ እና በቂ ካሳ መክፈል አለበት፡፡
7. ማንኛውም የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር በመንግስት ይዞታ ስር ባለ መሬት ወይም ህንፃ ላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተዘረዘሩትን ተግባራት ሲያከናውን ለባለይዞታው ተገቢውን የመጠቀሚያ ክፍያ ይፈፅማል፡፡ የክፍያው መጠንም ባለሥልጣኑ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ መስተዳድርን ጨምሮ ከሚመለከታቸው የክልል መስተዳድሮች ጋር በመመካከር በሚያወጣው የክፍያ መመሪያ መሰረት ይወሰናል፡፡
8. በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሰረት በቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሩ እና በመሬቱ ባለይዞታ ወይም በህንፃው ባለቤት መካከል የሚነሱ ማንኛውም አለመግባባቶች በባለሥልጣኑ የሚወሰኑ ይሆናል፡፡

9. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (8) መሠረት በቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሩ ወይም በመሬቱ ባለይዞታ ወይም በህንፃው ባለቤት ቅሬታ በሚቀርብበት ጊዜ ባለሥልጣኑ ለሁለቱም ወገኖች የመሰማት ዕድል በመስጠት ተቃውሞውን መርምሮ ውሳኔውን በአስር ቀናት ውስጥ ማሳወቅ አለበት፡፡
10. በባለሥልጣኑ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን የባለሥልጣኑ ውሳኔ ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ በህግ ጉዳይ ላይ ለይግባኝ ሰሚ አካል ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

33. <u>ኮንስትራክሽን</u>

1. ማንኛውም የኮንስትራክሽን ወይም የቁፋሮ ሥራ ወይም ቋሚነት ያለው ስትራክቸር ግንባታ በቴሌኮሙኒኬሽን መስመር አቅራቢያ ከመከናወኑ በፊት የቴሌኮሙኒኬሽን መስመሩን የዘረጋውን የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ስምምነት ማግኘት ይኖርበታል፡፡
2. የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የስምምነት ጥያቄ ሲቀርብለት በሠላሳ ቀናት ውስጥ ምላሽ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡
3. የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሩ ያላግባብ ሳይስማማ በመቅረቱ ለባለስልጣኑ አቤቱታ ሲቀርብለትና ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) የተመለከቱት ሥራዎች በቴሌኮሙኒኬሽን መስመሩ ላይ ጉዳት የማያደርሱ ወይም የማያውኩ መሆናቸውን ሲያረጋግጥ ሥራዎቹ እንዲካሄዱ ሊፈቅድ ይችላል፡፡
4. ማንኛውም ኮንስትራክሽን ወይም ቋሚ የሆነ ስትራክቸር ግንባታ ከቴሌኮሙኒኬሽን መስመር ቢያንስ በሁለት ሜትር መራቅ አለበት፡፡
5. አስቀድሞ የተዘረጋ የቴሌኮሙኒኬሽን መስመርን የሚያውክ ማንኛውም ግንባታ እንዲነሳ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሩ ቢያንስ የሠላሳ ቀናት ማስጠንቀቂያ በመስጠት ባለቤቱን ወይም ባለይዞታውን ሊጠይቅ ይችላል፡፡
6. የግንባታው ባለቤት ወይም ባለይዞታ በተሰጠ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ውስጥ ግንባታውን ካላነሳ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተሩ ግንባታውን የማንሳት መብት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ስድስት

## የባለሥልጣኑ አሠራሮች

### 34. የባለሥልጣኑ የሕዝብ ውይይት የማድረግ ሥልጣን

1. ባለሥልጣኑ በራሱ ተነሳሽነት ወይም ፍላጎት ካለው አካል በጽሁፍ በቀረበ ጥያቄ መሠረት በዚህ አዋጅ በተሰጠው የሥልጣን ክልል ውሰጥ በሆኑ ማንኛውም ጉዳይ ላይ የሕዝብ ውይይት ሊያካሄድ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚካሄደው የሕዝብ ውይይት በውይይቱ ወቅት ከሚታየው ጉዳይ ሚስጥራዊነት ባህሪ የተነሳ ለህዝብ ይፋ መሆን እንደሌለበት በባለሥልጣኑ ካልተወሰነ በስተቀር ለሁሉም ሰው ክፍት መሆን አለበት፡፡
3. ባለሥልጣኑ በማንኛውም ሂደት የመረጃ ተደራሽነትን ከሕዝቡ የሚገድብበትን ምክንያት ማሳወቅ እና በተቻለ መጠን ሁሉም የውይይት መድረኮች ሙሉ በሙሉ ለሕዝብ ክፍት መሆናቸውን ለማረጋገጥ ጥረት ማድረግ አለበት፡፡

### 35. የባለሥልጣኑ የባለድርሻ አካላት ምክክር ሁኔታዎች

1. ባለሥልጣኑ በማንኛውም ወገን መብት ወይም የሕዝብ ጥቅም ላይ ተፅዕኖ ሊያሳርፍ በሚችል በማንኛውም በሥልጣን ወሰኑ ውስጥ ባለ ጉዳይ ላይ ውሳኔ በሚያስተላልፍበት ጊዜ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በጽሁፍ ብቻ እንዲቀርብ በማድረግ የባለድርሻ አካላት ምክክር ማካሄድ አለበት፡፡
2. ባለሥልጣኑ የባለድርሻ አካላት ምክክር ለማካሄድ ሲፈልግ እንደሚከተለው በሕዝብ ማስታዎቂያ ማሳወቅ አለበት፦
   ሀ) የሂደቱን መጀመር ማሳወቅ፤
   ለ) ከባለድርሻ አካላት ምክክር ጋር የሚያያዘውን ጉዳይ መለየት፤
   ሐ) የማመልከቻ መስፈርቶችን ጨምሮ አስተያየት መቅረብ የሚችልበትን ጊዜ መግለጽ፤
   መ) ፍላጎት ላላቸው አካላት አስተያየት ዝግጅት የሚረዱ ማንኛውንም የውይይት መነሻ ጽሁፍ ወይም ሌሎች መረጃዎችን መስጠት፤ እና
   ሠ) ባለሥልጣኑ እንደ ሁኔታው ተገቢ ናቸው ብሎ ያመነባቸውን ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎች፡፡

3. የባለድርሻ አካላት ምክክር ለማካሄድ የሚወጣው የሕዝብ ማስታወቂያ በባለሥልጣኑ እየታዩ ያሉ ጉዳዮች እና በባለድርሻ አካላት ምክክር ውጤት መሥረት ከባለሥልጣኑ የሚጠበቁ ውሳኔዎች ላይ ፍላጎት ላላቸው አካላት በቂ ግንዛቤ የሚሰጥ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡
4. ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ያዘጋጀውን ማንኛውም መመሪያ ከባለድርሻ አካላት ምክክር በተገኘው ውጤት መሠረት ለማፅደቅ፣ ለማሻሻል ወይም ለመሻር ይችላል፡፡
5. ባለሥልጣኑ የዚህን አዋጅ ዓላማ በተሻለ ሁኔታ ለማስፈፀም እርምጃ ባለመውሰድ ወይም በባለድርሻ አካላት ምክክር ውጤት መሠረት የደረሰበትን ግኝት ሪፖርት በማውጣት ጉዳዩን ሊቋጨው ይችላል፡፡
6. ባለሥልጣኑ ተገቢ ነው ብሎ ሲያምንበት በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ሊታዩ የማይችሉ ጉዳዮች መፍትሄ እንዲያገኙ ሕግ እንዲወጣ ሀሳብ ማቅረብ ወይም እንደ ሁኔታው አግባብ ሌላ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

36. <u>የባለሥልጣኑ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት</u>

1. ባለሥልጣኑ ማንኛውም የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ግልፅነት ባለው መንገድ መካሄዱን ማረጋገጥ አለበት፡፡
2. ባለሥልጣኑ ማንኛውንም መመሪያ ለማፅደቅ፣ ለማሻሻል፣ ለመሻር ወይም የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ለመተግበር ሲፈልግ በሕዝብ ማስታወቂያ ወይም በሌላ ተመሳሳይ ዘዴ ለሕዝብ በቂ መረጃ መስጠት አለበት፡፡
3. ባለሥልጣኑ ሊወስድ ስለሚያስበው ማንኛውም እርምጃ በተመለከተ የተሰጠው ሥልጣን የሚመለከታቸው አካላትን ጨምሮ ህብረተሰቡ እና ተጠቃሚዎች በጽሁፍ ወይም በቃል አስተያየት እንዲያቀርቡ በቂ ዕድል መስጠት አለበት፡፡
4. ባለሥልጣኑ በሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች በቀረቡ የጽሁፍ ወይም የቃል አስተያየቶች ላይ ህብረተሰቡ አስተያየት እንዲሰጥ ዕድል መስጠት አለበት፡፡

37. <u>የባለሥልጣኑ ውሳኔ</u>

1. ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ መሥረት ከባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር ጋር የሚጣጣሙ ማንኛውንም እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል፡፡
2. ባለሥልጣኑ በቀረበለት ማንኛውም ጉዳይ ላይ ምክንያቱን በመግለጽ በጽሁፍ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

3. የባለሥልጣኑ ውሳኔ በክርክሩ ጊዜ በቀረቡ የመከራከሪያ መረጃዎች እና ግንዛቤ በወሰደባቸው እውነታዎች ላይ ብቻ የተመሠረተ መሆን አለበት፡፡
4. የባለሥልጣኑ ውሳኔ በህብረተሰቡ የቀረቡ ሀሳቦችን እና ውሳኔውን ለመስጠት ያስቻሉትን ምክንያቶች በተገቢው ሁኔታ ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡፡
5. የባለሥልጣኑ ውሳኔ ማንኛውም ወገን የሚያቀርበውን ጥያቄ በሙሉ ወይም በከፊል ሊቀበለው፣ ውድቅ ሊያደርገው ወይም በተሰጠው የሥልጣን ወሰን አዋጁን በተሻለ ሁኔታ ለመፈፀም የሚያስችል ሌላ መፍትሔ ሊሰጥ ይችላል፡፡
6. ባለሥልጣኑ በሚሰጠው እያንዳንዱ ውሳኔ ላይ ህብረተሰቡ በቂ ግንዛቤ ማግኘቱን ለማረጋገጥ ውሳኔውን በራሱ ድረ-ገጽ እና ሰፊ የስርጭት ሽፋን ባላቸው ተገቢ ህትመቶች በይፋ ማሳወቅ አለበት፡፡

38. <u>የባለሥልጣኑ ውሳኔ በድጋሚ ስለሚታይበት ሂደት</u>

1. በባለሥልጣኑ ወይም በባለሥልጣኑ ሠራተኛ በተሰጠ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ወገን ባለሥልጣኑ ወይም ሠራተኛው የሰጠው ውሳኔ በባለስልጣኑ በድጋሚ እንዲታይለት መጠየቅ ይችላል፡፡
2. ባለሥልጣኑ ውሳኔው በድጋሚ እንዲታይ በተጠየቀበት ሁሉም ጉዳዮች ላይ ፍላጎት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በጽሁፍም ሆነ በቃል ሃሳባቸውን እንዲገልፁ ዕድል ለመስጠት ውሳኔው በድጋሚ በመታየት ላይ መሆኑን በይፋ ለህዝብ ማሳወቅ አለበት፡
3. ባለሥልጣኑ ውሳኔው በድጋሚ እንዲታይ የቀረበለትን ጥያቄ በከፊል ወይም በሙሉ ሊቀበለው ወይም ውድቅ ሊያደርገው ይችላል፤
4. ባለሥልጣኑ ውሳኔውን በድጋሚ እንዲያይ ለቀረበለት ጥያቄ ምላሽ ሲሰጥ ውሳኔውን ለመስጠት ያስቻለውን ምክንያት በመግለፅ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

39. <u>የይግባኝ ሰሚ አካል</u>

1. ሶስት አባላት ያሉት የይግባኝ ሰሜ አካል በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡
2. የይግባኝ ሰሚ አካል አባላት ለሶስት ዓመት የሥራ ዘመን እንዲያገለግሉ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሾማሉ፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም የመጀመሪያው የይግባኝ ሰሚ አካል አባላት የሚያገለግሉበት የስራ ዘመን የተለያየ እንዲሆን ይደረጋል፡፡
4. ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከይግባኝ ሰሚ አካል አባላት መካከል አንዱን የይግባኝ ሰሚ አካል ሊቀመንበር ሆኖ እንዲያገለግል ይሾማል፡፡

5. የይግባኝ ሰሚ አካል አባላት ለሁለተኛው የሶስት ዓመት የሥራ ዘመን እንደገና ሊሾሙ ይችላሉ፡፡
6. የይግባኝ ሰሚ አካል አባላት በሕግ፣ በቴሌኮሙኒኬሽን፣ በብሮድካስቲንግ ወይም ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው ዘርፎች ልምድ ያላቸው መሆን አለባቸው፡፡
7. የይግባኝ ሰሚ አካል ከባለሥልጣኑ ክፍያ ማግኘት አለባቸው፡፡ ነገር ግን ክፍያው በሥራ ዘመናቸው ሊቀነስ አይችልም፡፡

40. <u>ይግባኝ ሰሚ አካል ሥልጣንና ተግባር</u>

1. የይግባኝ ሰሚ አካል በባለሥልጣኑ የተሰጡ ውሳኔዎችን በይግባኝ ለመስማት ሥልጣን አለው፡፡
2. የይግባኝ ሰሚ አካል የሚቀርቡለትን ጉዳዮች የሚሰማበትና ውሳኔ የሚሰጥበትን የአሰራር ሥርዓት ማዘጋጀት አለበት፡፡
3. በባለሥልጣኑ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም አካል በሕግ ጉዳይ ላይ ብቻ ለይግባኝ ሰሚ አካል ይግባኝ ሊል ይችላል፡፡
4. ማንኛውም በባለሥልጣኑ ውሳኔ ላይ የሚቀርብ የይግባኝ ጥያቄ ውሳኔው ከሚፀናበት ቀን ጀምሮ በሠላሳ ቀን ውስጥ ለይግባኝ ሰሚ አካል መቅረብ አለበት፡፡
5. የይግባኝ ሰሚ አካል የባለሥልጣኑን ውሳኔ ያፀናበት፣ የሻረበትን ወይም እንደገና እንዲታይ ያዘዘበትን ምክንያት በማብራራት ውሳኔውን በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡
6. የዚህን አንቀጽ ድንጋጌዎች በተመለከተ ባለሥልጣኑ ውሳኔው የሚፀናበትን የተለየ ቀን በጽሁፍ ካላሳወቀ በስተቀር ውሳኔው ለሕዝብ ይፋ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡
7. የውሳኔውን ተፈፃሚነት ማዘግየት የፍትህና የአዋጁን ዓላማ በተሻለ ሁኔታ ለመተግበር የሚጠቅም ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር የባለሥልጣኑ ውሳኔ በድጋሚ እንዲታይ ቢጠየቅም ወይም ይግባኝ ቢቀርብበትም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
8. በይግባኝ ሰሚ አካል ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በስልሳ ቀናት ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሕግ ጉዳይ ላይ ብቻ ይግባኝ ማለት ይችላል፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

41. <u>ስለ የባለሥልጣኑ የጥቅም ግጭት መርህ</u>

1. ከባለሥልጣኑ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ዋና ዳይሬክተሩም ሆነ የሥራ አመራር ቦርድ አባል፣ የይግባኝ ሰሚ አካል አባል ወይም ማንኛውም የባለሥልጣኑ ሰራተኛ በራሱ ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ በሚችሉ በሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ መስራት አይችልም፡-
   ሀ) የራሱን የግል የፋይናንስ ጥቅም በሚመለከት፤
   ለ) የባለቤቱን ወይም ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጁን የፋይናንስ ጥቅም በሚመለከት፤
   ሐ) የራሱን የንግድ አጋር የፋይናንስ ጥቅም በሚመለከት፤
   መ) በኦፊሰርነት፣ በዳይሬክተርነት፣ በአጋርነት፣ በሰራተኝነት ወይም በባለአደራነት የሚያገለግለውን የማንኛውም ተቋም የፋይናንስ ጥቅም በሚመለከት፤ ወይም
   ሠ) በሥራ ለተቀጠረበት ወይም ለሥራ ቅጥር በድርድር ላይ የሚገኝበትን የማንኛውም አካል የፋይናንስ ጥቅም ጋር በሚገናኝ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) የተገለጹት ሁኔታዎች ሲኖሩ ማንኛውም የባለሥልጣኑ አካል ለጥቅም ግጭት ምክንያት የሆነውን ነገር መተው ወይም በጉዳዩ ውስጥ ላለመሳተፍ እራሱን ማግለል ይኖርበታል፡፡
3. በማናቸውም ሁኔታ እንኳን ቢሆን ዋና ዳይሬክተሩ፣ ማንኛውም የሥራ አመራር ቦርድ አባል፣ ማንኛውም የይግባኝ ሰሚ አካል አባል ወይም ማንኛውም የባለሥልጣኑ ሠራተኛ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚቆጣጠረው ማንኛውም ኩባንያ ቀጥተኛ የባለቤትነት ጥቅም ሊኖረው አይችልም፡፡

## <u>ክፍል ሰባት</u>

## <u>ኢኮኖሚያዊ ቁጥጥር</u>

42.<u>ስለ ኢንተርኮኔክሽን</u>

አንድ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ከሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የኢንተርኮኔክሽን ጥያቄ ሲቀርብለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ (43) በተመለከቱት መርሆዎች እና ሁለቱ ወገኖች በድርድር በሚስማሙበት የውል ሁኔታዎች መሠረት የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርኩን ከሌላኛው የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ኔትወርክ ጋር ቴክኒካዊ አግባብነት ባለው ቦታ ኢንተርኮኔክት የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

## 43.<u>የኢንተርኮኔክሽን የስምምነት ሁኔታዎች</u>

1. በቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች መካከል የሚደረግ ማንኛውም የኢንተርኮኔክሽን ስምምነት በዚህ አዋጅ እና በአዋጁ መሰረት ባለሥልጣኑ በየጊዜው ከሚያወጣው መመሪያ ጋር የተጣጣመ እና በጽሁፍ መሆን አለበት፡፡
2. የኢንተርኮኔክሽን የውል ስምምነት ሁኔታዎች በዋናነት በሁለቱ ወገኖች መካከል በሚደረስበት ስምምነት ይወሰናል፡፡ ሆኖም የሚከተሉት ሁኔታዎች በሚኖሩበት ጊዜ ባለሥልጣኑ በራሱ ወይም በአንዱ ወይም በሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች ሲጠየቅ ጣልቃ በመግባት ተፈፃሚነት ያለው ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡-
   ሀ) ስምምነቱ ወይም የስምምነቱ የውል ሁኔታዎች ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም ባለስልጣኑ ካፀደቃቸው ማናቸውም መመሪያዎች ጋር የሚቃረን ሆኖ ሲገኝ፣ ወይም
   ለ) ሁለቱ ወገኖች በተወሰኑ ጉዳዮች ስምምነት ላይ መድረስ ካልቻሉ ወይም ስምምነት ላይ ለመድረስ መዘግየት ሲኖር፣ ወይም
   ሐ) የሕዝብን ጥቅም ከግምት በማስገባት በአንዱ ወይም በሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች ጥያቄ ባይቀርብለትም የባለሥልጣኑ በራሱ ተነሳሽነት ጣልቃ መግባት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፡፡

## 44.<u>ኮሎኬሽን እና መሰረተ ልማት መጋራት</u>

1. የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ለሕዝብ አገልግሎት ለመስጠት ዓላማ ባለሥልጣኑ ጉልህ የገበያ ድርሻ አለው ብሎ ከለየው ሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ስፍራ ላይ መሣሪያዎቹ በኮሎኬሽን እንዲቀመጡለት ሊጠይቅ ይችላል፡፡
2. በኮሎኬሽን መሣሪያዎችን እንዲያስቀምጥ የተጠየቀው የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ቴክኒካዊ አግባብነት እስካለው ድረስ ጥያቄውን መቀበል አለበት፡፡
3. የኮሎኬሽን ቦታ አጠቃቀም በተመለከተ የሚኖረውን ክፍያ ሁለቱ ወገኖች በድርድር መስማማት አለባቸው፡፡
4. በኮሎኬሽን ስምምነት የንግድ ወይም የቴክኒክ ሁኔታዎች ላይ ሁለቱ ወገኖች ካልተስማሙ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 35 — 38 በተገለፀው መሠረት ተገቢ የስምምነት ሁኔታዎች ላይ መወሰን አለበት፡፡
5. ባለሥልጣኑ የቴክኒክ ደረጃ እና የንግድ ሁኔታዎችን ጨምሮ የኮሎኬሽን ቦታን በተመለከተ መመሪያ ያወጣል፡፡

6. የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ለመሥጠት ቋሚ እና ገባሪ መሠረተ-ልማቶችን በተቻለ መጠን እንዲጋሩ ይበረታታሉ፡፡
7. በባለሥልጣኑ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳለው የታመነበት የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ያለውን ቋሚ እና ገባሪ መሠረተ-ልማት ተገቢ ጥያቄ ላቀረበ ሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተር ማጋራት አለበት፡፡
8. መሰረተ-ልማት መጋራትን በተመለከተ የሚኖረውን ክፍያ ሁለቱ ወገኖች በድርድር መስማማት አለባቸው፡፡
9. በመሰረተ-ልማት መጋራት ስምምነት የንግድ ወይም የቴክኒክ ሁኔታዎች ላይ ሁለቱ ወገኖች ካልተስማሙ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 35-38 በተገለፀው መሠረት ተገቢ የስምምነት ሁኔታዎች ላይ መወሰን አለበት፡፡
10. ባለሥልጣኑ የቴክኒክ ደረጃ እና የንግድ ሁኔታዎችን ጨምሮ የመሰረተ-ልማት መጋራትን በተመለከተ መመሪያ ያወጣል፡፡
11. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (10) የተደነገገው ቢኖርም በባለሥልጣኑ ጉልህ የገበያ ድርሻ ያለው ስለመሆኑ ባይወሰንም ለማንኛውም የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተር የኮሎኬሽን ወይም የመሰረተ-ልማት መጋራት ጥያቄ ለማቅረብ የሚከለክል ሁኔታ የለም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ጥያቄ በሚኖርበት ጊዜ ሁለቱ ወገኖች በኮሎኬሽን ወይም የመሠረተ-ልማት መጋራት የንግድ እና የቴክኒክ ሁኔታዎች ላይ መደራደር አለባቸው፡፡

45. <u>ህጋዊ ታሪፍ</u>

1. ማንኛውም የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ለሚሰጠው አገልግሎት ሕጋዊ ክፍያ ማስከፈል አለበት፡፡ ሕጋዊ ተመኑ ፍትሀዊ፣ ተገቢ እና በተጠቃሚዎች መካከል አድልኦ የማያደርግ መሆን አለበት፡፡
2. በዚህ አዋጅ ወይም ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንደሌላቸው የተለዩ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች ታሪፍ ሕጋዊ እንደሆነ ይገመታል፣ ታሪፋቸውንም ለባለስልጣኑ ማቅረብ አይጠበቅባቸውም፡፡
3. ማንኛውም በባለሥልጣኑ በአንድ ወይም ከዚያ በላይ የአገልግሎት ገበያ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳለው የታመነ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የአገልግሎት ታሪፉን በግልፅ ማሳወቅ አለበት፡፡

4. በባለስልጣኑ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳለው የታመነ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ያወጣው ታሪፍ በባለሥልጣኑ እስኪፀድቅ ድረስ ተፈፃሚነቱ እንዲዘገይ ባለሥልጣኑ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡
5. ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 35 -38 በተደነገገው መሠረት በሚያፀድቀው መመሪያ በባለስልጣኑ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳለው በታመነ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የቀረበውን ታሪፍ ሕጋዊነት የሚወስንበትን ደረጃ እና የአሰራር ሥርዓት ያዘጋጃል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት የሚዘጋጀው ደረጃ እና የአሰራር ሥርዓት ወጪን ያካተተ መሆን አለበት፡፡ ባለሥልጣኑ ወጪን ሲገመግም ወደፊት ሊኖር የሚችለውን የወጪ ጭማሪ የዋጋ ዘዴ መጠቀም አለበት፡፡

46.<u>የባለሥልጣኑ ታሪፍ የመገምገም ሥልጣን</u>

1. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም ባለሥልጣኑ የማንኛውም ፈቃድ ያለው የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ታሪፍ ለመገምገም፣ ለመቆጣጠር እና ታሪፉ ሕጋዊ መሆኑን ለማረጋገጥ የታሪፍ ዝግጅት መመሪያ የማውጣት ሥልጣን አለው፡፡
2. ባለሥልጣኑ በራሱ ተነሳሽነት ወይም በማንኛውም ፍላጎት ያለው አካል ለቀረበ ማመልከቻ ምላሽ ለመስጠት የማንኛውም የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተር ታሪፍ ሕጋዊ መሆኑን ማጣራት ይችሳላል፡፡ ባለሥልጣኑ እንዲህ ዓይነት ማጣራት በሚያደርግበት ጊዜ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 35-38 በተደነገገው መሰረት የሚያዘጋጃቸውን መስፈርቶች በመጠቀም ይሆናል፡፡

47.<u>የገበያ ውድድር ቁጥጥር</u>

በሌላ ሕግ የተደነገገው ቢኖርም ባለሥልጣኑ በአጠቃላይ ወይም በተለየ ሁኔታ የኢትዮጵያን የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ገበያ በተመለከተ ለመወሰን፣ ለማስተዳደር፣ ለመቆጣጠር እና ማንኛውም ሰው ለውድድር ሕግና መመሪያ ተገዢ እንዲሆን ለማስፈፀም ብቸኛ ሥልጣን አለው፡፡

48.<u>የገበያ ውድድርን ስለመከላከል</u>

1. ማንኛውም የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተር በየትኛውም የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ገበያ ውስጥ ውድድርን በእጅጉ የመቀነስ ዓላማ ወይም ውጤት ባለው ማንኛውም ተግባር ላይ ተሳትፎ ከተገኘ ሕገ-ወጥ ድርጊት እንደፈፀመ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

2. ማንኛውም የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተር በየትኛውም የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ገበያ ውስጥ ውድድርን በእጅጉ የመቀነስ ዓላማ ወይም ውጤት ያለው ተግባር ለመፈፀም በማቀድ ካለ ሰው ጋር ስምምነት ከፈፀመ ሕገ-ወጥ ድርጊት እንደፈፀመ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡
3. ባለሥልጣኑ በራሱ ተነሳሽነት ወይም በማንኛውም ፍላጎት ያለው አካል ለቀረበ ማመልከቻ ምላሽ ለመስጠት የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተሮች በየትኛውም የኢትዮጵያ የቴሌኮሙኒኬሽን ገበያ ውስጥ ውድድርን በእጅጉ የመቀነስ ዓላማ ወይም ውጤት ባለው ማንኛውም ድርጊት ላይ መሳተፋቸውን ማጣራት ይችላል፡፡
4. ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 35 -38 በተቀመጡት የአሰራር ሥርዓት መሠረት ማንኛውም የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተር በየትኛውም የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ገበያ ውስጥ ውድድርን በእጅጉ የመቀነስ ዓላማ ወይም ውጤት ባለው ማንኛውም ድርጊት ላይ መሳተፉን ባረጋገጠበት ጊዜ፡-
   ሀ) ለወደፊቱ ከእንዲህ ዓይነት ተግባር እንዲቆጠብ ለቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተሩ ወይም አገልግሎት ሰጪው ትዕዛዝ ይሰጣል፤ እንዲሁም
   ለ) እንደሁኔታው አግባብ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 52 በተደነገገው መሠረት ቅጣት ወይም ሌላ እገዳ ይጥልበታል፡፡

49.<u>የዩኒቨርሳል አክሰስ አገልግሎት</u>

1. ባለሥልጣኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር በሚደረግ ምክክር መሰረት ለሀገሪቱ የኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች ዓመታዊ የዩኒቨርሳል አክሰስ ግብ ማዘጋጀት አለበት፡፡
2. ባለሥልጣኑ የዩኒቨርሳል አክሰስ ግብ በሚያዘጋጅበት ጊዜ የኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች በተለይ በገጠር እና ርቀት ባላቸው የሀገሪቱ አካባቢዎች በተቻለ መጠን ከፍተኛ ቁጥር ላላቸው ተጠቃሚዎች ተደራሽ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡
3. በኢትዮጵያ ውስጥ ለኮሙኒኬሽን አገልግሎት ዩኒቨርሳል አክሰስ ድጋፍ የሚውል የዩኒቨርሳል አክሰስ ፈንድ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡ የፈንዱ የገቢ መጠንና ምንጭ እንዲሁም ፈንዱ ስለሚተዳደርበት ሁኔታ በተመለከተ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

50.<u>የተጠቃሚዎች መብት ጥበቃ</u>

1. ባለሥልጣኑ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ተጠቃሚዎች መብት የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል መመሪያ የማውጣት ሥልጣን አለው፡፡
2. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የሚያወጣውን መመሪያ በአዋጁ አንቀጽ 35 -38 መሰረት የባለድርሻ አካላት ምክክር በማካሄድ ማፅደቅ አለበት፡፡
3. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) በተሰጠው ሥልጣን ሳይገደብ እያንዳንዱ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ተጠቃሚዎች ለቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሩ ወይም ለባለሥልጣኑ ቅሬታ ማቅረብ የሚችሉበትን ሥርዓት ጨምሮ የተጠቃሚዎችን መብት የሚደነግግ የሥነ-ምግባር ኮድ እንዲያዘጋጅ መጠየቅ ይችላል፡፡
4. ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 35 -38 መሠረት የባለድርሻ አካላት ምክክር በማካሄድ እያንዳንዱ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ያዘጋጀውን የሥነ-ምግባር ኮድ በጽሁፍ ውሳኔ ማፅደቅ አለበት፡፡
5. ባለሥልጣኑ በባለድርሻ አካላት ምክክር የተለዩ ጉዳዮች የተጠቃሚዎችን ፍላጎት ለመጠበቅ አስፈላጊ ሆነው ሲገኙ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሩ የሥነ-ምግባር ኮዱን በዚሁ መሠረት እንዲያሻሽል መጠየቅ ይችላል፡፡

## <u>ክፍል ስምንት</u>

## <u>ብሄራዊ ደህንነት እና ተፈፃሚነት</u>

51.<u>ብሄራዊ ድህንነት</u>

1. የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች ለደንበኞቻቸው የሚሰጡትን የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚሥጥራዊነት ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ሁሉ መፈፀም አለባቸው፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ከቴሌኮሙኒኬሽን ደንበኞች ጋር የተያያዙ መረጃዎች እንዲሰጠው ሲጠይቅ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች ማንኛውም ሥልጣን ያለው የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት ያስተላለፈውን ማንኛውንም ሕጋዊ ትዕዛዝ ማክበር አለባቸው፡፡

3. የወንጀል ምርመራ ወይም የሀገር ደህንነት ምርመራ ለማካሄድ ለተፈቀደለት የመንግሥት አካል ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በቴሌኮሙኒኬሽን ላይ ሕጋዊ ክትትል ማድረግ እንዲችል የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች ኔትወርካቸውን ተደራሽ ማድረግ አለባቸው፡፡ ይህን በማይፈፅሙ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች ላይ ባለሥልጣኑ ቅጣት ሊጥል፣ የተሰጣቸውን ፈቃድ ሊሰርዝ ወይም ሊያግድ ይችላል፡፡
4. ባለሥልጣኑ ብሔራዊ ደህንነትን ለመደገፍ ዓላማ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች የደንበኞች መረጃ ቋት በተሟላ ሁኔታ መያዝ እንዲችሉ፣ የሲም ካርድ ምዝገባ እንዲያከናውኑ እና ባለሥልጣኑ ደንበኞችን በተመለከተ የሚፈልጋቸውን መረጃ በያዘ ሁኔታ ብሄራዊ የደንበኞች መረጃ እንዲያደራጁ ለመጠየቅ ሥልጣን አለው፡፡

52. **ሕግ ማስፈፀም**

1. ባለሥልጣኑ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እና በዚህ አዋጅ መሰረት የሚያወጣቸውን ማናቸውም መመሪያ፣ የፈቃድ ሁኔታዎች፣ ያሳለፋቸውን ውሳኔዎች ወይም ሌሎች የቁጥጥር ማዕቀፎች እንደ አስፈላጊነቱ ከህግ አስከባሪ አካላት ጋር በመተባበር ለማስፈፀም ሥልጣን አለው፡፡
2. ባለሥልጣኑ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እና በዚህ አዋጅ መሰረት የሚያወጣቸውን ማናቸውም መመሪያዎች፣ የፈቃድ ሁኔታዎች ወይም ሌሎች የቁጥጥር ማዕቀፎች መከበራቸውን የመቆጣጠር ሥልጣን አለው፡፡ ቁጥጥሩ የባለሥልጣኑን ሠራተኞች መደበኛ የሥራ እንቅስቃሴዎችን ወይም ፍላጎት ባለው ማንኛውም አካል የቀረበ መረጃ ወይም ቅሬታን መሰረት ሊያደርግ ይችላል፡፡
3. ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 35 -38 የተመለከቱትን ግልፅ የአሰራር ሥርዓቶች መሰረት በማድረግ በማንኛውም ባለፈቃድ ላይ የቀረቡ ቅሬታዎችን ለመዳኘት እና የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች፣ በአዋጁ መሠረት የተቀመጡ የፈቃድ ሁኔታዎች ወይም ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ መሰረት የሚያወጣቸውን ሌሎች መመሪያዎች መጣስን በመገምገም እርምጃ የመውሰድ ሥልጣን አለው፡፡
4. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች፣ በአዋጁ መሠረት የተቀመጡ የፈቃድ ሁኔታዎች ወይም ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ መሰረት የሚያወጣቸውን ሌሎች መመሪያዎች የጣሰ ማንኛውም ሰው ላይ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሠረት የሚወስዳቸው እርምጃዎች የገንዘብ ቅጣት ወይም ካሳ መክፈልን ሊያካትት ይችላል፡፡

5. ባለሥልጣኑ የሚወስዳቸው እርምጃዎች እንደ አስፈላጊነቱ ፈቃድ መሰረዝን ጨምሮ ሌሎች አግባብነት ያላቸው ቅጣቶችን ሊያካትት ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ የሚወሰዱት እርምጃዎች ተመጣጣኝ፣ አድልኦ የሌለበትና ግልፅ መሆን አለባቸው፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (5) የተደነገገው ቢኖርም ፈቃድ ለማገድ ወይም ለመሰረዝ የሚያበቁ ሁኔታዎች እና ሌሎች አስተዳደራዊ ቅጣት የሚያስከትሉ የሕግ መተላለፍ ዓይነቶች እንዲሁም የቅጣት መጠን የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 53.ክልከላ

በቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ከተመደበ ሠራተኛ ወይም በባለሥልጣኑ ከተፈቀደለት ሰው በስተቀር ማንኛውም ሰው የቴሌኮሙኒኬሽን መስመርን ማገናኘት ወይም ማለያየት የተከለከለ ነው፡፡ ክልከላው የራሱን የቤት መገልገያ መሳሪያዎች የሚያገናኝ ወይም የሚያለያይ ሰውን አይመለከትም፡፡

### 54.ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ባለሥልጣኑ ይህን አዋጅ እና በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

### 55.የተሻሩ ሕጎች

የሚከተሉት በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፦

1. የቴሌኮሙኒኬሽን አዋጅ ቁጥር 49/1989 (እንደተሻሻለ)፤
2. የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 47/1991፤
3. የብሮድካስት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር533/1999 አንቀጽ 7 (6)፤
4. የፌደራል አሰፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀጽ 20(1) (ሐ)፣ (ኘ)፣ (ከ)፣ (ኸ) እና (ወ)፤

56.**<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ታትሞ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሀሴ 6 ቀን 2011**

**ሳህለ ወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጲያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዘዳንት**

# ክፍል ሃያ አራት

## ኮንስትራክሽንና ከተማ ልማት

## አዋጅ ቁጥር 177/1991

## ስለኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ምዝገባና ቁጥጥር የወጣ አዋጅ

የኮንስትራክሽን ሥራ ዘርፍን ለማጠናከር የሚያስችል ሁኔታዎችን ማመቻቸት በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ምዝገባና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 177/1991" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "ሚኒስቴር" ማለት የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር[133] ነዉ፤
2. "የኮንስትራክሽን መሣሪያ" ማለት ሚኒስቴሩ በመመሪያ የሚወስነው ለኮንስትራክሽን ሥራ እንዲያገለግል ሆኖ የተሠራ መሣሪያ ሲሆን በክልል ወይም ለፌዴራል መንግሥት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች ትራንስፖርትና መገናኛ ቢሮዎች በአዋጅ ቁጥር 14/84 የሚመዘገቡ የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችን አይጨምርም፤
3. "የባለቤትነት ወታወቂያ ደብተር" ማለት ለኮንስትራክሽን መሣሪያ ባለንብረቶች የሚሰጥ የባለቤትነት ማረጋገጫ ማስረጃ ነው፤
4. "መለያ ቁጥር" ማለት በኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ላይ የሚለጠፍ ፊደል ወይም ቁጥር ወይም ሁለቱም ነው፡፡

3. **ዓላማ**

የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ምዝገባና ቁጥጥር ዓላማዎች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

1. በመንግሥትና በግል ባለቤትነት የተያዙ የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችን መዝግቦ ለመያዝ፤

[133] 25/08 (2011) አ. 1097 አንቀጽ 9(10) የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚንስቴር ሆኗል፡፡

2. የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ለዋስትና መያዣና ለመሳሰሉት አገልግሎቶች የሚውሉበትን ሁኔታዎች ለማመቻቸት፤

4. **የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር**

ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

1. ለሥራዉ የሚያስፈልገዉን የሰው ኃይልና መሣሪያዎች ያደራጃል፤
2. የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችን ይመዘግባል፣ የባለቤትነት ደብተር ይሰጣል፣ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡም ሆነ ሲወጡ ይቆጣጠራል፤
3. ለኮንስትራክሽን መሣሪያዎች መለያ ቁጥር ይሰጣል፤ በመሣሪያዎቹ ላይ መለጠፉንም ይቆጣጠራል፤
4. የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ለምርመራ የሚቀርቡበትን ቦታና ጊዜ ይወስናል፤
5. የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችን ብቃት በመመርመር ማስረጃ ይሰጣል፤ ብቃት የሌላቸውን መሣሪያዎች ሥራ ላይ እንዳይውሉ ይቆጣጠራል፤
6. በዚህ አዋጅ በሚወጣ ደንብ በሚወሰነው መሠረት ለሚሰጠው አገልግሎት ዋጋ ያስከፍላል፡፡

5. **ደንብ ወይም መመሪያየማዉጣት ሥልጣን**

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የሚረዳ ደንብ ማውጣት ይችላል፤
2. ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጣዉን ደንብ ለማስፈጸም የሚረዳ መመሪያ ማውጣት ይችላል፡፡

6. **ቅጣት**

ይህን አዋጅ የተላለፈ ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት አግባብ ባለው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ[134] መሠረት ይቀጣል፡፡

7. **የተሻሩ ሕጎች**

የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣንን እንደገና ማቋቋሚያ (የማሻሻያን) አዋጅ ቁጥር 122/1997 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

---

[134] በ1996ቱ የወንጀል ህግ የተተካ በመሆኑ “የወንጀለኛ መቅጫ ህግ” በሚል የተገለጸው ድንጋጌ “የወንጀል ህግ” ተብሎ ይነበባል፡፡

8. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሰኔ 22 ቀን 1991 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ 22 ቀን 1991 ዓ.ም**

**ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 624/2001

## የኢትዮጵያ የሕንፃ አዋጅ

የሕዝብ ጤንነትና ደህንነት እንዲረጋገጥ ለማድረግ የሕንፃ ግንባታ ወይም የሕንፃ ግንባታ ማሻሻያና የአገልግሎት ለውጥን በተመለከተ በሀገሪቱ በአጠቃላይ ተፈፃሚ የሚሆን ዝቅተኛውን ደረጃ ለመወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ (3) የፌደራል መንግሥቱ የጤና፣ የትምህርት እንዲሁም የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሀገር አቀፍ መመዘኛዎችንና መሠረታዊ የፖሊሲ መለኪያዎች የማውጣትና የማስፈፀም ሥልጣን የተሰጠው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55 (1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ የሕንፃ አዋጅ ቁጥር 624/2001"ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

   1. "ሚኒስቴር" ማለት የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ነው፤[135]
   2. "ሕንፃ" ማለት ለመኖሪያ፣ ለቢሮ፣ ለፋብሪካ ወይም ለማናቸውም ሌላ አገልግሎት የሚውል ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ግንባታ ነው፤
   3. "የሕንፃ ሹም" ማለት ይህንን አዋጅ እንዲያስፈጽም በከተማ አስተዳደር ወይም በተሰየመ አካል የተሾመ ሰው ነው፤
   4. "የተመዘገበ ባለሙያ" ማለት ሥልጣን ባለው አካል ተመዝግቦ በዲዛይን ወይም በኮንስትራክሽን የባለሙያነት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ወይም በዲዛይን ወይም በኮንስትራክሽን የአማካሪነት የምዝገባ ምስክር ወረቀት የተሰጠው ድርጅት ነው፤

[135] በ25/08 (2011) አ. 1097 አንቀጽ 9(10) መሰረት የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

5. “የተመዘገበ የሥራ ተቋራጭ” ማለት ሥልጣን ባለው አካል ተመዝግቦ የሥራ ተቋራጭነት የምዝገባ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ድርጅት ነው፤
6. “ምደብ ‘ሀ’ ሕንፃ” ማለት በሁለት የኮንክሪት ወይም የብረት ወይም ሌሎች ስትራክቸራል ውቅሮች መካከል ያለው ርቀት 7 ሜትር ወይም ከዚያ በታች የሆነ ባለአንድ ፎቅ ሕንፃ ወይም ማናቸውም ከሁለት ፎቅ በታች የሆነ የግል መኖሪያ ቤት ነው፤
7. “ምደብ ‘ለ’ ሕንፃ” ማለት በሁለት የኮንክሪት ወይም የብረት ወይም ሌሎች ስትራክቸራል ውቅሮች መካከል ያለው ርቀት ከ7 ሜትር በላይ የሆነ ወይም ባለሁለት ፎቅና ከሁለት ፎቅ በላይ የሆነና በምደብ ‘ሐ’ የማይሸፈን ሕንፃ ወይም በምድብ ‘ሀ’ የተመደበ እንደሪልስቴት ያለ የቤቶች ልማት ነው፤
8. “ምድብ ‘ሐ’ ሕንፃ ማለት የሕዝብ መገልገያ ወይም ተቋም ነክ ሕንፃ፣ የፋብሪካ ወይም የወርክሾፕ ሕንፃ ወይም ከመሬት እስከ መጨረሻው ወለል ከፍታው ከ12 ሜትር በላይ የሆነ ማናቸውም ሕንፃ ነው፤
9. “ግንባታ” ማለት አዲስ ሕንፃ መገንባት ወይም ነባር ሕንፃን ማሻሻል ወይም አገልግሎቱን መለወጥ ነው፤
10. “አስጊ ሕንፃ” ማለት ግንባታው አስተማማኝ ያልሆነ ወይም በከፍተኛ ደረጃ ለእሳት አደጋ የተጋለጠ ወይም ለጤና ጠንቅ የሆነ ሕንፃ ነው፡፡
11. “የተሰየመ አካል” ማለት ይህ አዋጅ ከከተማ ክልል ውጪ ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ አዋጁን እንዲያስፈጽም በክልሉ የሚሰየም አካል ነው፤
12. “ሰነድ” ማለት ከሕንፃ ዲዛይንና ግንባታ ጋር በተያያዘ የሚያስፈልግ ወይም የተዘጋጀ ፕላን፣ ሪፖርት፣ የዋጋ ግምት ወይም ማንኛውም የቴክኒክ ጉዳይን የሚያስረዳ ሰነድ ነው፤
13. “የግል መኖሪያ ሕንፃ” ማለት ለአንድ ቤተሰብ መኖሪያነት የሚያገለግሉ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ክፍሎችና የመፀዳጃና የማብሰያ አገልግሎቶች ያሉት ሆኖ በመኖሪያው ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚገኝ የመኪና ማቆሚያንና ለመኖሪያነት የሚውሉ ከዋናው ቤት የተነጠሉ ክፍሎችን ሊጨምር ይችላል፤
14. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
15. “ፕላን” ማለት የአንድን ሕንፃ መጠን፣ ዓይነትና ስፋት እንዲሁም ሕንፃው የሚሠራበትን ቁሳቁስና የአገነባብ ዘዴን የሚያሳይ ንድፍ ወይም ሞዴል ሲሆን

የአርክቴክቸር፣ የስትራክቸር፣ የሳኒተሪ፣ የኤሌክትሪካል፣ የሜካኒካል፣ የእሳት መከላከልና የሌሎች ሥራዎችን ንድፍ ሊያካትት ይችላል፤

16.“ክልል” ማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 47 መሠረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

17.“የማስቆሚያ ትዕዛዝ” ማለት በአንድ የሕንፃ ግንባታ ቦታ የሚካሄድ ሥራ እንዲቋረጥ ወይም እንዲቆም በሕንፃ ሹም ወይም በሕንፃ ተቆጣጣሪ የሚሰጥ ትዕዛዝ ነው፤

18.“ፎቅ” ማለት በሁለት ወለሎች መካከል ወይም ከላይ ሌላ ወለል ከሌለ በወለሉና በኮርኒስ መሃል ያለው የሕንፃ ክፍል ነው፤

19.“የከተማ አስተዳደር” ማለት በሕግ ወይም በሚመለከተው መንግሥታዊ አካል ውክልና የከተማ አስተዳደር ሥልጣንና ተግባር የተሰጠው አካል ነው፤

20.“ከተማ” ማለት ማዘጋጃ ቤት የተቋቋመበት ወይም 2,000 ወይም ከዚያ በላይ የሕዝብ ቁጥር ያለውና ከዚህ ውስጥ ቢያንስ 50 በመቶ የሚሆነው የሰው ኃይል ከግብርናውጭ በሆነ ሥራ የተሰማራ ሆኖ የሚገኝበት አካባቢ ነው፡፡

3. <u>**የተፈጻሚነት ወሰን**</u>

1. ይህ አዋጅ በሚከተሉት ላይ ተፈፃሚይሆናል፤

ሀ/ 10,000 እና ከዚያ በላይ ነዋሪዎች ባሏቸው ከተሞች፣

ለ/ የነዋሪዎቻቸው ቁጥር ከ10,000 በታች በሆነና ተፈፃሚ እንዲሆንባቸው በሚመለከተው ክልል በሚወሰኑ ሌሎች ከተሞች፣

ሐ/ ከከተማ ውጭ በሚገኙ ህዝብ የሚገለገልባቸው ሕንፃዎች፣ የኢንዱስትሪ ወይም የዘመናዊ እርሻ ተቋሞችና የሪልስቴት ሕንፃዎች፡፡

2. ይህ አዋጅ በሚከተሉት ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፣

ሀ/ አዋጁ በፀናበት ቀን ወይም ከዚያ በፊት በተጠናቀቀ ሕንፃ፣

ለ/ አዋጁ ከፀናበት ቀን በፊት በተሰጠ የሕንፃ ግንባታ ፈቃድ በመካሄድ ላይ በሚገኝ በማናቸውም ሕንፃ፣

ሐ/ ከሀገር ደህንነት ጋር በተያያዘ እና በሌሎች ምክንያቶች አዋጁ ተፈፃሚ እንዳይሆንበት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወሰን ሕንፃ፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) ድንጋጌ ቢኖርም፣

ሀ) ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በወጣ የሕንፃ ግንባታ ፈቃድ መሠረት በመካሄድ ላይ የሚገኝ ሆኖ ግንባታው ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን ጀምሮ በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ያልተጠናቀቀ ከሆነ፣

ለ) የአገልግሎት ለውጥ ጥያቄ የሚቀርብለት ህንፃ ሕንፃው ሲሰጠው ከታሰበው አገልግሎት አንፃር ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ፣

ሐ) የእድሳት ፈቃድ ጥያቄ በሚቀርብበት ህንፃ ላይ፣

የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል ይህ አዋጅ ተፈጻሚ እንዲሆንበት ማድረግ ይችላል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>አስተዳደር</u>

4. <u>**ማመልከቻና ፕላን ስለማቅረብ**</u>

   1. የግንባታ ሥራ ለማካሄድ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ለከተማው አስተዳደር ወይም ለተሰየመው አካል ማመልከቻ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
   2. ሕንፃን ለመገንባት የሚቀርብ ማመልከቻ የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል ለዚሁ ብሎ ባዘጋጀው ቅፅ መሠረት ሆኖ ይህም እንደ ሕንፃው ምድብ አይነት ዲዛይንና ሪፖርት የያዘ መሆን አለበት፡፡
   3. ከማመልከቻው ጋር በአዋሳኝ ባሉ ስፍራዎች የሚገኙ ዋና መንገዶችንና የታወቁ ቦታዎችን ስም የሚገልፁ መረጃዎች መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
   4. አመልካቹ ሕንፃ በሚገነባበት ቦታ ወይም በንብረቱ ላይ የይዞታ መብት እንዳለው የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
   5. የሚቀርቡት ሰነዶች በዚህ አዋጅ እና በሌሎች ህጎች የተመለከቱት መሟላታቸውን ለማረጋገጥ በበቂ ሁኔታ የተሟሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

5. <u>**የፕላን ስምምነት**</u>

   1. ግንባታ ለማካሄድ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የግንባታ ፈቃድ ለማግኘት ማመልከቻ ከማቅረቡ አስቀድሞ የፕላን ስምምነት ማግኘት ይኖርበታል፡፡
   2. የሕንፃ ሹሙ ለፕላን ስምምነት የቀረበለትን ማመልከቻ ከመረመረ በኋላ ከከተማው ፕላን ጋር የሚጣጣም ወይም የማይጣጣም ስለመሆኑ የጽሁፍ ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡

6. <u>**ፕላን ስለማስፀደቅ**</u>

1. የሕንፃ ሹሙ የቀረበለትን የፕላን ሠነድ በዚህ አዋጅና በሌሎች ሕጎች ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ጋር የተጣጣመ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ በዚህ አዋጅ ወይም በሌሎች ሕጎች ያልተካተቱ መመዘኛዎችን ምክንያት በማድረግ አንድ ፕላን እንዳይፀድቅ ማድረግ አይችልም፡፡
2. የሕንፃ ሹሙ የሚሰጠው አስተያየት የጎሉ ግድፈቶችን የሚመለከት ካልሆነና ተፈላጊው ማስተካከያ በሥራው ሂደት ወቅት በቀላሉ ሊደረግ የሚችል ከሆነ አስተያየቱን በማከል ፕላኑን ሊያፀድቀው ይችላል፡፡
3. የፀደቀ ፕላን በላይ ላይ "ፀድቋል" የሚል ማህተም የተደረገበት፣ የምዝገባ ቁጥርና የፀደቀበትን ቀን የያዘና የሕንፃ ሹም ፊርማ ያረፈበት መሆን ይኖርበታል፡፡
4. ከፀደቀው ፕላን ጋር አብረው የቀረቡት የማመልከቻ ቅፆች በቅፆች ውስጥ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው ክፍት ቦታ ላይ "ፀድቋል" የሚል ምልክት ተደርጐባቸው የምዝገባ ቁጥርና የፀደቀበት ቀን ይሠፍርባቸዋል፡፡ አስተያየት ካለ ለዚሁ በተዘጋጀው ክፍት ቦታ ላይ ሰፍሮ በሕንፃ ሹሙ ይፈረምበታል፡፡
5. ፕላን ከፀደቀ በኋላ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ መሠረት ማህተምና ፊርማ ያረፈበት የማመልከቻ ቅፅና በአባሪነት የተያያዘው ፕላን አንድ ቅጅ ለአመልካቹ ይመለስለታል፤ ሌላው በከተማው አስተዳደር ወይም በተሰየመው አካል ዘንድ ይቀመጣል።
6. ፊርማና ማህተም ያለበት የፀደቀ ፕላንና ማመልከቻ ቅጅ በሕንፃው መሥሪያ ቦታ በግልፅ እንዲታይ ሆኖ ይቀመጣል፡፡ የፀደቀውን ፕላንና የማመልከቻውን ዋናዎቹን ቅጅ በጥሩ ሁኔታ እንዲቀመጥ ማድረግና ግንባታው ከመጀመሩ በፊት ወይም ግንባታው በሚካሄድበት በማናቸውም ጊዜ በከተማው አስተዳደር፣ በተሰየመው አካል፣ በሕንፃ ሹሙ ወይም ሥልጣን ባለው ተቆጣጣሪ ሲጠየቅ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

7. <u>**የፕላን መገምገሚያ ጊዜ**</u>

የሕንፃ ሹም የቀረበለትን ሠነድ በመገምገም ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ማፅደቅ ወይም ውድቅ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

8. <u>**ፕላን ውድቅ ስለማድረግ**</u>

1. ከዚህ አዋጅና ከሌሎች ሕጎች ጋር የማይጣጣም የግንባታ ፕላን በሕንፃ ሹሙ ውድቅ ይደረጋል፡፡

2. ፕላኑ ውድቅ የሚሆን ከሆነ የህንፃ ሹሙ በማመልከቻው ላይ ባለው ክፍት ቦታ የተጣሰውን የህጉን ድንጋጌ በአጭሩ መግለፅ ይኖርበታል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ተጨማሪ ማብራሪያዎች በተለየ ወረቅት በመፃፍ ማያያዝ ይችላል፡፡
3. በሕንፃ ሹሙ ውድቅ የተደረገ ማመልከቻና ፕላን "ውድቅ ተደርጓል" የሚል ምልክትና ቀን እንዲሁም የሕንፃ ሹሙ ፊርማ ይሠፍርበታል፡፡
4. የቀረበው ፕላን ውድቅ ሲደረግ የሕንፃ ሹሙ ፊርማ እና ማህተም ያረፈበት ማመልከቻ አንድ ቅጅ እና የፕላኑ ሁለት ቅጂዎች ለአመልካቹ የሚመለስ ሲሆን የህንፃ ሹሙ ፊርማ እና ማህተም ያረፈበት የማመልከቻ ቅፅ አንድ ቅጂ በከተማው አስተዳደር ወይም በተሰየመው አካል ዘንድ ይቀመጣል፡፡

9. <u>**የግንባታ ፈቃድ**</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 መሠረት የፀደቀ ፕላን በግንባታ ፈቃድነት ያገለግላል፡፡

10. <u>**ፕላን ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ**</u>

1. የግንባታ ሥራው ካልተጀመረ አንድ የፀደቀ ፕላን የሚፀናበት ጊዜ የሚያበቃው ፕላኑ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ ስድስት ወር ካበቃ በኋላ ይሆናል፡፡
2. የግንባታ ሥራው ፕላኑ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ የተጀመረና ሥራው ያልተጠናቀቀ ከሆነ የፀደቀው ፕላን ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ የሚያበቃው ፕላኑ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ አምስት ዓመት ካበቃ በኋላ ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ ወይም /2/ በተገለፀው መሠረት ፕላን ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ሲያበቃ ጊዜው እንዲራዘም በዚህ አዋጅ መሠረት ፕላኑን እንደገና የማፀደቅ ጥያቄ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

11. <u>**የሕንፃ ሹም**</u>

1. እያንዳንዱ የከተማ አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል አስተዳደሩን ወይም አካሉን በመወከል የዚህን አዋጅና የሌሎችን ሕጎች ድንጋጌዎች ለማስፈፀም የሚያስችል አስፈላጊው የትምህርትና የሙያ ዝግጅት ያለው ሕንፃ ሹም ይሾማል፡፡
2. የሕንፃ ሹም ፕላን እንዲፀድቅ የሚቀርብ ማመልከቻን በመቀበል ከዚህ አዋጅና ከሌሎች ሕጎች ጋር ሙሉ በሙሉ የሚስማማ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ያፀድቃል፡፡
3. የህንፃ ሹም በከተማው ክልል ወይም በተሰየመው አካል አስተዳደር ክልል ውስጥ ያሉ ሕንፃዎች ከዚህ አዋጅና ከሌሎች ሕጎች ጋር የሚስማሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ቁጥጥር ያደረጋል፡፡

4. የህንፃ ሹም ተግባሩን ለመወጣት በከተማው አስተዳደር ወይም በተሰየመው አካል ሌሎች ሠራተኞች ሊታገዝ ይችላል፡፡ ሆኖም ፕላን ለማፀደቅ በሚቀርቡ ማመልከቻዎችና የምርመራ ሪፖርቶች ላይ ውሳኔ መስጠት የእርሱ ኃላፊነት ይሆናል፡፡
5. የህንፃ ሹም ይህ አዋጅ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተሰሩና አዋጁ ተፈፃሚ እንዳይሆንባቸው የተደረጉ ሕንፃዎች እንዲመረመሩ የማድረግና ለሕብረተሰቡ ደህንነት አስጊ ሆነው ከተገኙ እንዲፈርሱ ወይም እንዲስተካከሉ የማዘዝ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡
6. የህንፃ ሹም በስህተት በፀደቀ ፕላን መሠረት የተገነባ ህንፃ እንዲስተካከል የማዘዝ ሥልጣን ይኖረዋል፣ ሆኖም የማስተካከያ ሥራውን ለማዘዝ በቂ ምክንያት ሊኖረው ይገባል፡፡
7. የህንፃ ሹሙ ይህ አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡት ደንብና መመሪያዎች የተጣሉበትን ኃላፊነት በግል ጥፋት ምክንያት በአግባቡ ባለመወጣት በሶስተኛ ወገኖች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት በወንጀል ተጠያቂ የሚሆንባቸው ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው በፍትሐብሔር ህግ ድንጋጌዎች መሠረት በግል ተጠያቂ ይሆናል፡፡
8. የህንፃ ሹሙ ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ የሕንፃ ሹሙ የፈጸመው ጥፋት በፍትሐብሔር ድንጋጌዎች መሠረት የሥራ ጥፋት ነው ሊባል የሚችልበት ምክንያት ያለ እንደሆነ በሶስተኛ ወገኖች ላይ ለደረሰው ጉዳት የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል በሕግ መሠረት ተገቢውን ካሣ ከፍሎ አጥፊውን መልሶ ለመጠየቅ መብት አለው፡፡

12. <u>ውክልና</u>

1. የህንፃ ሹሙ ከፕላን ግምገማ ጋር በተያያዘ ራሱ በሙሉም ሆነ በከፊል ሊያከናውነው ያልቻለውን ሥራ ለሌላ አካል ወይም ለዚሁ ተግባር ለተሰየመ ሰው በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡
2. የህንፃ ሹም የተመሩለትን ማመልከቻዎች በተመለከተ በፅሑፍ አስተያየቱን ለከተማው አስተዳደር ወይም ለተሰየመው አካል ይልካል፣ እንዲሁም ተያይዘው በቀረቡት ሠነዶች ላይ ይፈርማል፣ እንዳአስፈላጊነቱም ማህተም ያደርጋል፡፡

3. የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል የፀደቁትን ወይም ውድቅ የተደረጉትን ሰነዶች በህንፃ ሹሙ ስም ይሰጣል፡፡
4. ፕላኖችን ለመገምገም የሚሰጠው ውክልና የቁጥጥር ተግባራትንም እስከማከናወን ድረስ ሊሰፋ ይችላል፡፡

13.ስለ ይግባኝ

1. እያንዳንዱ የከተማ አስተዳደር ወይም የተሰየመ አካል በዚህ አዋጅ መሠረት ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ተገቢው ሙያ ያላቸው አባላት የሚገኙበት የይግባኝ ሰሚ ቦርድ ያቋቁማል፡፡
2. ቦርዱ ግንባታዎችን በተመለከተ በህንፃ ሹም በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በይግባኝ አይቶ የመወሰን ሥልጣን ይኖረዋል፡፡ ቦርዱ ቴክኒክ ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

14.ትዕዛዝን አለማክበር

1. የህንፃ ሹም ባልፀደቀ ፕላን ለተገነባ ህንፃ ጥቅም ላይ የዋለው ፕላን የዚህን አዋጅ ወይም የሌሎች ህጎችን ድንጋጌዎች የሚጥስ ሆኖ ከተገኘ ህንፃው እንዲፈርስ ያደርጋል፡፡
2. በህንፃ ሹም ህንፃውን እንዲያፈርስ ወይም እንዲያነሳ የተሰጠውን ትዕዛዝ የህንፃው ባለቤት ያላከበረ እንደሆነ የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል ህንፃውን በማፍረስ ወይም በማንሳት ያወጣውን ወጪ ከባለንብረቱ ሊጠይቅ ይችላል፡፡
3. ተፈላጊው ማስታወቂያ ሳይሰጥ የተሰራን ሥራ ወይም የሥራውን የተወሰነ ክፍል ለምርመራ እንዲከፈት፣ እንዲነሳ ወይም በህንፃው ላይ ጉዳት በማያደርስ ሁኔታ እንዲፈርስ የህንፃ ሹም ሊያዝ ይችላል፡፡
4. የህንፃ ሹም የህንፃ አካልን ለማሻሻል ወይም ለመለወጥ የፀደቀ ፕላን ሳይኖር የተሰራን ሥራ እንዲስተካከል ማዘዝና ባለንብረቱ በትዕዛዙ መሠረት እስኪያስተካክል ድረስ በህንፃው ላይ የሚካሄድ ሌላ ሥራ እንዲቆም ማገድ ይችላል፡፡

15. ስለ ማስታወቂያ

1. በምድብ ‘ለ’ ወይም ‘ሐ’ ሥር የሚወድቅ ህንፃ ለመገንባት የፀደቀ ፕላን ያለው ሰው ግንባታው የሚካሄድበትን ጊዜ የሚያሳይ ማስታወቂያ ለሚመለከተው የህንፃ ሹም ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት በቀረበ ማስታወቂያ ላይ ህንፃ ሹም የሚሰጠው ውሳኔ የጊዜ ገደብ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡
3. የህንፃ ሹም እንደ ህንፃው ዓይነትና የአሠራር ሁኔታ ተጨማሪ ማስታወቂያዎች እንዲቀርቡ መጠየቅ ይችላል፡፡ እንደዚህ አይነት ሁኔታ ሲያጋጥም ማስታወቂያው የሚቀርብበት ጊዜና የሥራው ደረጃ በግልፅ ተቀምጦ ለአመልካቹ ከፀደቀው ፕላን ጋር በፅሁፍ እንዲደርሰው ይደረጋል፡፡
4. ከፀደቀው ፕላን ውጭ የተከናወኑ አንዳንድ ሥራዎችን እንዲያስተካክል ከህንፃ ሹም ትዕዛዝ የደረሰው ሰው የማስተካከያውን ሥራ እንዳጠናቀቀ ለህንፃ ሹሙ ማስታወቅ ይኖርበታል፡፡

16. <u>ስለ ተቆጣጣሪዎች</u>

1. የከተማ አስተዳደር ወይም የተሰየመ አካል ለህንፃ ሹምና በእሱ ቁጥጥር ሥር ለሚሰሩ ተቆጣጣሪዎች በልብስ ላይ የሚንጠለጠል ማንነታቸውን የሚገልፅ የመታወቂያ ወረቅት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡
2. የከተማውን አስተዳደር ወይም የተሰየመውን አካል መታወቂያ ወረቀት የያዙ ተቆጣጣሪዎች የግንባታ ሥራው ወደ ተጠናቀቀ ወይም በግንባታ ላይ ወደ አለ ህንፃ በማንኛውም የሥራ ሰዓት የመግባት ሥልጣን ይኖራቸዋል፡፡
3. ተቆጣጣሪዎች ይህን አዋጅ ወይም ሌሎች ሕጎችን በመተላለፍ የሚካሄድ ግንባታ እንዲቆም ትዕዛዝ መስጠት ይችላሉ፡፡ የማስቆሚያ ትዕዛዝ የሚሰጠው በሚዘጋጀው የቁጥጥር ሪፖርት ቅፅ ይሆናል፡፡
4. የህንፃ ሹም የዚህን አዋጅ ወይም የሌሎች ህጎች ድንጋጌዎችን በመተላለፍ የተሰራ ህንፃ የሚስተካከልበትን፣ የሚነሳበትን ወይም የሚፈርስበትን ጊዜ በመወሰን ውሳኔው ለህንፃው ባለቤት በፅሑፍ እንዲደርሰው ያደርጋል፡፡ የሚሰጠው የጊዜ ገደብ ከግንባታው ሂደትና ከሥራው ቅደም ተከተል አንፃር የትዕዛዙን አጣዳፊነት ግምት ውስጥ የሚያስገባ ይሆናል፡፡
5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (4) መሠረት የተሰጠውን ትዕዛዝ የህንፃው ባለቤት ሳይፈፀም የቀረ እንደሆነ የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል በባለቤቱ ኪሳራ ሥራው እንዲስተካከል፣ እንዲነሳ ወይም እንዲፈርስ ሊያደርግ ይችላል፡፡

17.**ስለቁሳቁስ**

1. የህንፃ ሹም ለግንባታው ያገለግላል ተብሎ በግንባታው ሥፍራ የተቀመጠ ወይም በህንፃው ሥራ ላይ የዋለ ጉድለት ያለበት ቁሳቁስ እንዲወገድ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡
2. ተገቢ ያልሆነ የግንባታ ቁሳቁስ መጠቀም ወይም የሥራው ጥራት ከሚጠበቀው በታች ወርዶ በመገኘት የተሰራ ሥራን ላለመቀበል እንደበቂ ምክንያት ሆኖ ሊቆጠር ይችላል፡፡
3. የህንፃ ሹም በሥራ ላይ የዋለ ወይም ሊውል የታቀደ ቁሳቁስን በተመለከተ የጥራት ምርመራ ምስክር ወረቀት እንዲቀርብ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

18.**የህንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ**

1. በምድብ 'ሐ' ሥር የሚመደብ አዲስ የተገነባ ህንፃ በዚህ አዋጅ መሠረት መስፈርቱን ማሟላቱ በፍተሻ ካልተረጋገጠና የመጠቀሚያ ፈቃድ ካልተሰጠ በስተቀር ህንፃው ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም፡፡
2. የህንፃ ሹም ደህንነቱ አስጊ አለመሆኑ ለተረጋገጠ እና በከፊል ለተጠናቀቀ ህንፃ የመጠቀሚያ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡
3. በዚህ አዋጅ የተመለከቱት መመዘኛዎች እንደተጠበቁ ሆነው የህንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ በህንፃ ሹም የሚሰጥበት የጊዜ ገደብ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡
4. የህንፃ ሹም የህንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ ሳይኖረው በምድብ 'ሐ' ህንፃ መጠቀም በጀመረ በማናቸውም ሰው ላይ ሕጋዊ እርምጃ መውሰድ ይችላል፡፡

19.**የፕላን መገምገሚያ ክፍያ**

1. ፕላንና ሌሎች ሰነዶች ቀርበው እንዲመረመሩ በሚያስፈልግበት ጊዜ የፕላን መገምገሚያ ክፍያ ይከፈላል፡፡ የክፍያው መጠን ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡
2. ተደጋጋሚ አህዶች በሚያጋጥሙበት ጊዜ የፕላን መገምገሚያ ክፍያ የሚጠየቀው ከእያንዳንዱ አህድ ዓይነት የአንዱን አህድ የወለል አጠቃላይ ሥፋት መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡
3. የፕላን መገምገሚያ ክፍያ የሚከፈለው ፕላን ለማፅደቅ ማመልከቻ በሚቀርብበት ጊዜ ይሆናል፡፡

4. ውድቅ የሆኑ ፕላኖች እንደገና ለማፀደቅ በሚቀርቡበት ጊዜ የፕላን መገምገሚያ ክፍያ በድጋሚ ይከፈላል፡፡ የክፍያው መጠን ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

20.**ስለ ፕላን ማፀደቂያ ክፍያ**

1. የህንፃ ሹም የህንፃ ግንባታ፣ ማስፋፊያ ወይም ማሻሻያ ሥራ ፕላን ለማፅደቅ ክፍያ ያስከፍላል፡፡ የክፍያው መጠን ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚመጣው ደንብ ይወሰናል፡፡
2. ተደጋጋሚ ወለሎችን ወይም አሀዶችን በሚመለከት የፕላን ማስፀደቂያ ክፍያ የሚጠየቀው የወለሉን አጠቃላይ ስፋት ድምር መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡

21.**ስለ ቁጥጥር ክፍያ**

1 ለቁጥጥር ሲባል ለሚደረግ ጉብኝት የህንፃውን ምድብ መሠረት ያደረገ የቁጥጥር ክፍያ ይከፈላል፡፡ የክፍያው መጠን ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ለምድብ ‘ለ’ እና ‘ሐ’ ህንፃዎች የሚጠየቅ ክፍያ ለምድብ ‘ሀ’ ህንፃዎች ከሚጠየቀው ክፍያ እንደ ቅደም ተከተላቸው ከአምስትና ከአሥር እጥፍ መብለጥ አይኖርበትም፡፡

22.**ስለ ተመላሽ ክፍያዎች**

1. የህንፃ ሹም ማንኛውም አገልግሎት ያልተሰጠበት ክፍያ ከአመልካች በሚቀርብ የፅሁፍ ጥያቄ መሠረት ተመላሽ እንዲሆን ማዘዝ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ክፍያ ተመላሽ እንዲሆን የሚቀርብ ጥያቄ ክፍያው ከተፈጸመበት ቀን አንስቶ ባለው የ6 ወር ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

23.**ስለ መቀጮ**

1. የከተማ አስተዳደር ወይም የተሰየመ አካል የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በሚተላለፉ የግንባታ ባለቤቶች ላይ አስተዳደራዊ መቀጮ መጣል ይችላል፡፡ የመቀጮው ልክ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የሚጣል የገንዘብ መቀጫ ጥፋተኛውን በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን ከመፈፀም ወይም በከተማው አስተዳደር ወይም በተሰየመው አካል ከሚወስዱ ተጨማሪ እርምጃዎች ነፃ አያደርገውም።፡፡

24.<u>ጊዜያዊ ግንባታዎች</u>

አመልካቹ በጊዜያዊ ግንባታነት ያሳወቀውን ግንባታ ለማካሄድ ማመልከቻ ያቀረበ እንደሆነ የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል ግንባታውን በዚህ አዋጅና በሌሎች ህጎች መሠረት እንዲያከናውን ጊዜያዊ ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል፡፡

25.<u>የአገልግሎት ለውጥ ስለማድረግ፣ ስለማስፋፋት፣ ዕድሳት ወይም ጥገና ስለማድረግ እና ስለማፍረስ</u>

1. የህንፃ ሹም ከዚህ አዋጅ ጋር እስከተጣጣመ ድረስ የህንፃ አገልግሎት ለውጥ የማድረግ፣ የማስፋፋት ዕድሳት የማድረግ፣ የመጠገን ወይም የማፍረስ ፈቃድ ይሰጣል፡፡
2. የአገልግሎት ለውጡ፣ የማስፋፋቱ፣ የማደሱ፣ የመጠገኑ፣ ወይም የማፍረሱ ሥራ መጠን ሰፊ የሆነ እንደሆነ የህንፃ ሹሙ ህንፃው የሚገኝበትን ነባራዊ ሁኔታ የሚያሳዩ ፕላኖችና በአዋጁ መሠረት መከናወኑን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ማናቸውም ሌሎች ትንታኔዎች ወይም ማስረጃዎች እንዲቀርቡለት መጠየቅ ይችላል፡፡
3. የአገልግሎት ለውጥ፣ የማስፋፋት፣ የማደስ፣ የመጠገን፣ ወይም የማፍረስ ሥራ በሚከናወንበት ጊዜ ለአዲስ ህንፃ ግንባታ የሚወሰዱ ጥንቃቄዎች ሁሉ ሊወሰዱ ይገባል፡፡
4. የህንፃ ሹም አስጊ ሕንፃን ለማፍረስ ፈቃድ ይሰጣል፡፡
5. ማንኛውም ሰው አንድን ህንፃ ሲያፈርስ ወይም ካፈረሰ በኋላ ሕዝብንና የአዋሳኝ ንብረቶችን ደህንነት ለአደጋ በሚያጋልጥ ሁኔታ መተው የለበትም፡፡
6. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ ቢኖርም የታሪካዊ ቅርስነት ዋጋ ያላቸው ህንፃዎችን ከመጠገን ወይም ከማስፋፋት በፊት ከሚመለከተው አካል የጽሁፍ ስምምነት መገኘት ይኖርበታል፡፡

26.<u>የተመዘገቡ ባለሙያዎችን ስለመቅጠር</u>

1. ለማንኛውም ህንፃ ህንፃው ለሚገኝበት ምድብ የሚጠየቁ የዲዛይን ዓይነቶች ለየሥራው በሚመጥኑ የተመዘገቡ ባለሙያዎች መሰራት ይኖርባቸዋል፡፡ ዝርዝሩ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡ የህንፃው ግንባታ እስኪጠናቀቅ ድረስም የባለሙያዎቹ ቁጥጥር ሊኖር ይገባል፡፡ የህንፃ ዲዛይኑን ቴክኒካል ሥራ የሚያስተባብረው አርክቴክቱ ይሆናል፡፡

2. የግንባታ ሥራው ሲጠናቀቅ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ ላይ የተጠቀሱት ባለሙያዎች የፈረሙበትና መጠናቀቁን የሚያረጋግጥ ምስክር ወረቀት ለህንፃ ሹሙ መቅረብ ይኖርበታል፡፡
3. ማንኛውም የምድብ 'ለ' እና 'ሐ' ህንፃዎች ግንባታ ዲዛይን ለማከናወን ውለታ የሚወስድ የተመዘገበ ባለሙያ በዲዛይን የተነሳ ሊደርሱ ለሚችሉ ጉዳቶች ዋስትና ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ለተለያዩ የህንፃ ምድቦች የሚሰጠው የዋስትና መጠንና አቀራረብ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

27.**<u>የተመዘገቡ ስራ ተቋራጮችን ስለመቅጠር</u>**

1. ህንፃ ለመገንባት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ለሚገነባው ህንፃ ምድብ የሚመጥን የተመዘገበ ሥራ ተቋራጭ መቅጠር ይኖርበታል፡፡ ዝርዝሩ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡
2. ማንኛውም የምድብ 'ለ' እና 'ሐ' ህንፃዎች ግንባታ ለማከናወን ውለታ የሚወስድ ሥራ ተቋራጭ ግንባታውን በሚያከናውንበት ወቅት በግንባታው የሥራ ጥራትና በጥንቃቄ ጉድለት ምክንያት ሊደርሱ ለሚችሉ ጉዳቶች ዋስትና ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ለተለያዩ የህንፃ ምድቦች የሚሰጠው የዋስትና መጠንና አቀራረብ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

28.**<u>የሥራ ተቋራጮችና የተመዘገቡ ባለሙያዎች ኃላፊነት</u>**

1. ማንኛውም የተመዘገበ ባለሙያ ወይም የሥራ ተቋራጭ፣ በዋና ወይም በንዑስ ሥራ ተቋራጭነት፣ ወይም ከፊል ውለታ በመውሰድ ያከናወነው የህንፃ ዲዛይን ወይም የግንባታ ሥራ ለሚያስከትለው ጉዳት በወንጀል ተጠያቂ የሚሆንባቸው ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው አሠሪው ለሆነው ሰው አግባብነት ባላቸው የፍትሐብሔር ህግ ድንጋጌዎች መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የሥራ ተቋራጭ ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት በሚገነባው ህንፃ ወይም የህንፃ አካል ላይ ለሚደርሰው የሥራ ጥራት ጉድለት ተጠያቂነቱ ሳይቀር ጉድለቱን የማስተካከል ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት

## የመሬት አጠቃቀም፣ ተጓዳኝ ጥናቶችና ዲዛይኖች

### 29. የመሬት አጠቃቀምና ተጓዳኝ ጥናቶች

በፌዴራል፣ በክልል ወይም በከተማ አስተዳደር የፀደቀ አገራዊ፣ ክልላዊ ወይም ከተማ ነክ አጠቃላይ ፕላን በዚህ አዋጅ በተካተቱና የመሬት አጠቃቀምንና ተጓዳኝ ጥናቶችን በሚመለከቱ ድንጋጌዎች ላይ የበላይነት ይኖረዋል፡፡

### 30. ዲዛይኖች

1. ማንኛውም ህንፃ ለሚገኝበት ምድብ የሚያስፈልጉ ዲዛይኖች ሊዘጋጁለት ይገባል፤
2. ማንኛውም ህንፃ ወይም የህንፃ አካል ተቀባይነት ባላቸው የህንፃ ዲዛይን ደንቦች መሠረት የተጠቃሚውንም ሆነ የሌሎች አካላትን ደህንነትን፣ ምቾትንና የተሟላ ግልጋሎትን ሊያረጋግጥ የሚችል ሆኖ ዲዛይን መደረግ አለበት፡፡
3. ማንኛውም ህንፃ የሰዎችን፣ የሌሎች ግንባታዎችንና ንብረቶችን ደህንነት በማያሰጋ መንገድ ዲዛይን መደረግና መገንባት አለበት፡፡

### 31. በግንባታ ወቅት መደረግ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎች

የዚህ አዋጅ አንቀጽ 30 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፤

1. ማንኛውም ግንባታ በግንባታው አካባቢ የሚንቀሳቀሱ ሰዎችን፣ የግንባታው ሠራተኞችን፣ የሌሎች ግንባታዎችን ወይም ንብረቶችን ደህንነት በማያሰጋ መንገድ ዲዛይን መደረግና መገንባት ይኖርበታል፣
2. ከግንባታ ጋር የተያያዘ ቁፋሮ የማንኛውንም ንብረት ወይም አገልግሎት ደህንነት ጉዳት ላይ የሚጥል ሲሆን የግንባታ ቦታው ባለቤት የንብረቱን ወይም የአገልግሎቱን ደህንነት ለመጠበቅ በቂ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፤
3. የተቆፈረው ጉድጓድ ክፍት ሆኖ የሚቆይ ሲሆን ወይም በጉድጓዱ ውስጥ መሠረት በሚገነባበት ጊዜ ባለቤቱ ወይም ቁፋሮውን ያካሄደው ሰው ጉድጓዱን ለደህንነት በማያሰጋ ሁኔታ መጠበቅ አለበት፤
4. ከግንባታ ጋር የተያያዘ ቁፋሮ የማንኛውንም ንብረት ወይም አገልግሎት ደህንነት አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል መሆኑ ሲገመት የግንባታ ቦታው ባለቤት በቅድሚያ የመከላከያ ዘዴዎችንና የጥንቃቄ እርምጃዎችን ለከተማው አስተዳደር ወይም ለተሰየመው አካል በማቅረብ የፅሁፍ ፈቃድ ማግኘት አለበት፤

5. ማንኛውም አዲስ የሚገነባ ህንፃ መሠረት ጭነት በነባር መሠረቶች፣ የአገልግሎት መስመሮች ወይም ሌሎች ሥራዎች ላይ ችግር የሚፈጥር መሆን የለበትም።

32. <u>በግንባታ ቦታ ላይ ስለሚከናወኑ ሥራዎች</u>

1. ማንኛውም ህንፃ ሲገነባ ወይም ሲፈርስ በሕዝብ ላይ አደጋ ወይም ከፍተኛ መጉላላት ሊያስከትል የሚችል ከሆነ የግንባታ ቦታው ባለቤት ሥራውን ከመጀመሩ በፊት አስፈላጊውን የመከላከያ ሥራ እንዲያከናውን በከተማው አስተደደር ወይም በተሰየመው አካል ሊጠየቅ ይችላል፡፡
2. አንድን ህንፃ ከመገንባት ወይም ከማፍረስ ጋር የተያያዘ ሥራ የከተማው አስተደደር ወይም የተሰየመው አካል ንብረት በሆነ ወይም በእርሱ ቁጥጥር ሥር ባለ ንብረት ጥንካሬ፣ ደረጃ፣ ደህንነት፣ ጥራት ወይም አቀማመጥ ላይ ትልቅ ለውጥ እንደሚያመጣ የከተማው አስተደደር ካመነ ባለቤቱ በሥራው ምክንያት ለሚያደርሰው ጉዳት መጠገኛ የሚውል ማስያዣ ወይም ዋስትና እንዲሰጥ ሊጠይቀው ይችላል፡፡
3. ከግንባታ ቦታ ክልል ውጪ የግንባታ ቁሳቁስ ወይም ተረፈ ግንባታ የተጠራቀመ ከሆነ የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል በጽሑፍ ማስታወቂያ በሚገለጽ የጊዜ ገደብ ውስጥ ባለቤቱ እንዲያነሳ ሊያዝ ይችላል፡፡
4. ማኛውም የግንባታ ቦታ ባለቤት ወይም ከህንፃ ግንባታ ወይም ማፍረስ ጋር የተያያዘ ስራ የሚሰሩ ሰዎች ሥራውን በሚያከናውኑበት ጊዜ በሥራው ቦታ ላይ እንደ አስፈላጊነቱ ጊዜያዊ መጠለያ ሊያሰሩ ይችላሉ፡፡
5. ማንኛውም የግንባታ ቦታ ባለቤት ወይም የህንፃ ግንባታ ወይም ማፍረስ ስራ የሚሰራ ሰው በሥራው ላይ ለሚሰማሩ ሰዎች የሚሆን ተቀባይነት ያለው የንጽህና ቦታ በግንባታ ሥፍራው ላይ ወይም በከተማው አስተዳደር ወይም በተሰየመው አካል ፈቃድ በሌላ ቦታ ላይ ሳያዘጋጅ የግንባታም ሆነ የማፈረስ ሥራውን መጀመርም ሆነ መቀጠል አይችልም፡፡ እንዲህ ያለው ዝግጅት እስኪደረግ ድረስ ሥራው እንዲቆም ይደረጋል፡፡
6. የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል በግንባታ ወቅት ሊወሰዱ የሚገባቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎች ለመከታተል የሚያስችል የአሠራር ስልት ሊቀይስ ይችላል፡፡

## 33.ስለ አርኪቴክቸር

1. ማንኛውም ክፍል ወይም ቦታ ጥቅም ላይ ለሚውልበት ዓላማ የሚመጥን ስፋት ያለው መሆን ይኖርበታል።
2. የማንኛውም መኖሪያ ቤት ወለል ስፋት አንድ መኖሪያ ክፍልና አንድ የተለየ መፀዳጃ ቤት ሊያሳርፍ ከሚችል መጠን ያነሰ መሆን የለበትም።
3. በማንኛውም የመኖሪያ ሕንፃ ውስጥ የሚገኝ የመኖሪያ ክፍል ወይም ለመኖሪያነት ወይም ለተቋምነት በሚያገለግል ሕንፃ ውስጥ ያለ የመኝታ ክፍል ከሰው ሰራሽ ብርሃን ማግኛ መንገድ በተጨማሪ የተፈጥሮ ብርሃን የሚያገኝበት ቢያንስ አንድ ክፍተት ሊኖረው ይገባል፡፡
4. ከመሬት ወለል ከ20 ሜትር በላይ ከፍታ ያለው ማንኛውም ህንፃ የአሳንሰር ወይንም ተመሳሳይ አገልግሎት ሊኖረው ይገባል፡፡
5. አሳንስሮች ያለማቋረጥ አገልግሎት እንዲስጡ መደረግ ይኖርባቸዋል፡፡

## 34.ስለ ስትራክቸር

1. ማንኛውም ህንፃና የህንፃው ክፍል ወይም አካል ተቀባይነት ባለው የህንፃ ዲዛይን ደንብ መሠረት ጥንካሬን፣ ተደላድሎ መተከልን፣ ለጥገና ሥራ አገልግሎት አመቺነትን፣ እንዲሁም ዘለቄታዊ አስተማማኝነትን ሊያረጋግጥ የሚችል ሆኖ ዲዛይን መደረግ አለበት፡፡ እንዲህ ያለው ግንባታ በአገልግሎት ዘመኑ ከተመደበለት ሸክም በላይ እስካልተጫነ ድረስ የስትራክቸር ችግር ሊታይበት አይገባም፡፡
2. ማንኛውም ግንባታ የሌሎች ግንባታዎችን ወይም ንብረቶችን ደህንነት በማያስጋ መንገድ ዲዛይን መደረግና መገንባት ይኖርበታል።

## 35.የኤሌክትሪክ መስመር ተከላ

ለአንድ ግንባታ የሚደረገው የኤሌክትሪክ መስመር ተከላ እንዲሁም ጥቅም ላይ የሚውለው ቁሳቁስ የደህንነት ደንቦችን የጠበቀና ከኤሌክትሪክ መስመር ተከላው ጋር በተያያዘ ምንም አይነት አደጋ በማያስከትል መልኩ መሠራት ይኖርበታል፡፡

## ክፍል አራት

## የውሃ አቅርቦትና ሳኒቴሽን

### 36.የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች ስለሚደረጉ ዝግጅቶች

1. በማንኛውም የሕዝብ መገልገያ ህንፃ ውስጥ በተሽከርካሪ ወንበር ለመንቀሳቀስ የሚገደዱትንና መራመድ የሚችሉ ሆኖ ደረጃ መውጣት የሚሳናቸውን ጨምሮ የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች የሚመች መጻረሻ መዘጋጀት አለበት፡፡
2. የመፀዳጃ ቤት ሊሠራበት በሚገባ በማናቸውም ህንፃ ውስጥ የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች የሚመቹና ሊደርሱባቸው የሚችሉ በቂ መጠን ያላቸው መፀዳጃ ቤቶች መኖር አለባቸው።

### 37.የውሃ አቅርቦት

1. ለሰዎች አገልግሎት የታሰበ ማንኛውም ህንፃ በቂ የውሃ አቅርቦት ሊኖረው ይገባል፡፡ የውሃ አቅርቦት ዝግጅቱ በቂ ሥርጭት እና የማከማቻ ዘዴ ሊኖረው ይገባል፡፡
2. የማንኛውም ግንባታ የውሃ አቅርቦት ዘዴ የጤና ደረጃውን የጠበቀ መሆን አለበት፡፡
3. የማንኛውም ግንባታ የውሃ አቅርቦት አሠራር ለምርመራና ለሙከራ የሚመች መሆን ይኖርበታል፡፡

### 38.የፍሳሽ አወጋገድ

1. አንድ ግንባታ በአቅራቢያው ተስማሚ የሆነ ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ዘዴ ሲኖረው የግንባታው ባለቤት የፍሳሽ መተላለፊያውን ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡
2. ማንኛውም ሰው በአቅራቢያው ተስማሚ የሆነ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ከሌለው ተቀባይነት ባለው ሌላ መንገድ ፍሳሹን ማስወገድ ይኖርበታል፡፡

### 39.ተቀባይነት የሌላቸውን ፍሳሾች መቆጣጠር

1. ማንኛውም ሰው ከመፀዳጃ አገልግሎት መስጫዎች የሚወጣን ፍሳሽ ቆሻሻ ወደማንኛውም የጎርፍ ማስወገጃ ቦይ ወይም በሌላ መልኩ ወደ ተገነባ የውሃ መስመር፣ ወንዝ፣ ምንጭ፣ ጎዳና ወይም ሌላ ስፍራ መልቀቅ ወይም እንዲለቀቅ መፍቀድ የለበትም፡፡
2. ማንኛውም ሰው የጎርፍ ውሀ በየትኛውም ቦታ ላይ ወደሚገኝ ፍሳሽ ማስወገጃ እንዲገባ ማድረግ ወይም መፍቀድ የለበትም፡፡

40.<u>የኢንዱስትሪ ዝቃጭ</u>

ማንኛውንም ፈሳሽ ወይም ጠጣር ነገር፣ አፈር የያዘን ውሃ ወይም ቆሻሻ ውሀን ሳይጨምር፣ ወደማንኛውም ፍሳሽ ማስተላለፊያ እንዲለቅ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የፍሳሽ ማከማቻን፣ ማጣሪያና የመጠን መለኪያን አካቶ ተጨማሪ የፍሳሽ ማስተላለፊያ ተከላ ወይም ሌላ ተጨማሪ ሥራ እንዲያከናውን ፈቃዱ ሲሰጠው በከተማው አስተዳደር ወይም በተሰየመው አካል የተጠየቀ እንደሆነ የዚህኑ ተከላ ፕላንና ሌሎች አስፈላጊ ዝርዝሮች ለከተማው አስተደደር ወይም ለተሰየመው አካል ማቅረብ አለበት፡፡

41.<u>ውሀ አልባ ቆሻሻ ማስወገጃ</u>

በውሃ አማካኝነት ቆሻሻ የማስወገጃ ግንባታ በሌለበት ቦታ ሌሎች ቆሻሻ ማስወገጃ ዘዴዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል ሊፈቅድ ይችላል፣ ሆኖም ኬሚካል ወይም ዝግ ቆሻሻ ማስወገጃ በሚኖርበት ጊዜ ቆሻሻውን ከዕቃው ለማስወገድ ተቀባይነት ያለው ዘዴ ሊኖር ይገባል፡፡

42.<u>የጎርፍ ውሀ ስለማስወገድ</u>

1. የማንኛውም ይዞታ ባለቤት በማናቸውም የአፈር ሥራ፣ ግንባታ ወይም ድልደላ ምክንያት ተጠራቅሞ የሚፈሰውን የጎርፍ ውሀ ለመቆጣጠርና ለማስወገድ ተቀባይነት ያለው ዘዴ ሊኖር ይገባል ፡፡
2. የማንኛውም ይዞታ ባለቤት ከዝናብ ውሃ የተወሰነው በይዞታው ውስጥ ሰርጎ እንዲቀር ተስማሚ ዘዴ መጠቀም አለበት፡፡

43.<u>የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ</u>

የመኖሪያ ቤትን ሳይጨምር ደረቅ ቆሻሻ የሚያመነጭ ማንኛውም ግንባታ የደረቅ ቆሻሻ ማከማቻ የሚቀመጥበት በቂ ቦታ ሊኖረው ይገባል፡፡

<u>ክፍል አምስት</u>

<u>እሳት መከላከልና የእሳት ማጥፊያ ተከላ</u>

44.<u>ጠቅላላ መስፈርት</u>

ማንኛውም የህዝብ መገልገያ ህንፃ ተቀባይነት ባለው የእሳት መከላከያ ዲዛይን መስፈርት መሠረት የእሳት አደጋን ሊቋቋምና የእሳት አደጋ ቢከሰት በተጠቃሚዎችና በአካባቢው ላይ የሚደርሰውን አደጋ ሊቀንስ በሚችል መልክ ዲዛይን ሊደረግና ሊገነባ ይገባዋል፡፡

45.**ስለእሳት ማጥፊያ ተከላ**

ፈቃድ ተገኝቶ የተተከለ ማንኛውም የእሳት ማጥፊያ የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል ከዘረጋው የውሃ መስመር ውሀ መጠቀም ይችላል፡፡ ሆኖም የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል አስፈላጊ ሆኖ የተገኘውን ቅድመ ሁኔታ በማስቀመጥ እንዲህ ያለው የእሳት ማጥፊያ፣

1. ከሌላ አማራጭ የውሃ መስመር፣ ወይም
2. በከተማው አስተዳደር ወይም በተሰየመው አካል እምነት በጤና ላይ ችግር ሊያስከትል በሚችል መልኩ ለሌላ አገልግሎት እስካልዋለ ድረስ ለመጠጥነት ከማያገለግል የውሃ መስመር፣ ውሀ እንዲጠቀም ሊፈቅድ ይችላል፡፡

46.**ስለእሳት መከላከያ የውሃ አቅርቦት**

ለማንኛውም የእሳት ማጥፊያ የሚውል የውሃ መስመር ዝርጋታ፡-

1. የእሳት መከላከያ መሣሪያውና የውሃ አጠቃቀም ከከተማው አስተዳደር ወይም ከተሰየመው አካል መስፈርት ጋር የሚስማማ መሆኑ ካልተረጋገጠ፣
2. ለከተማው አስተዳደር ወይም ለተሰየመው አካል በቅድሚያ ማመልከቻ ቀርቦ ፈቃድ ካልተሰጠ፣

   ሊከናወን አይችልም፡፡

## ክፍል ስድስት

## የህንፃ ሥራ ህጎችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ስለመጣስ

47.**የወንጀል ህጉ ተፈፃሚነት**

1. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በመተላለፍ የግንባታ ሥራ ፈቃድን በሚሰጡ የመንግሥት ኃላፊዎች እና ይህንኑ እንዲያከናውኑ ሃላፊነት በተሰጣቸው ሌሎች የመንግሥት ሠራተኞች፣ በተመዘገቡ ባለሙያዎች ወይም ሥራ ተቋራጮች፣ እንዲሁም በግንባታ ባለቤቶች የሚፈፀሙ ጥፋቶች በዚህ ክፍል ውስጥ በተመለከተው መሠረት ይወሰናሉ፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚህ ክፍል ውስጥ በተመለከቱ ጥፋቶች አፈጻጸምና የቅጣት አወሳሰን ረገድ አግባብነት ያላቸው የወንጀል ህጉ የጠቅላላ ክፍል ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት የተጠበቀ ነው፡፡

48.<u>የግንባታ ፈቃድን አላግባብ ስለመስጠት</u>

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የህንፃ ግንባታ ፈቃድ ለመስጠት ሥልጣን የተሰጠው የህንፃ ሹም ወይም ይህንኑ ተግባር እንዲያከናውን ኃላፊነት የተሰጠው ማንኛውም ሰው ሆን ብሎ፡-
   ሀ) አግባብ ባለው አካል የተሰጠ ህጋዊ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ለሌለው ሰው በቦታው ላይ ለሚከናወን ግንባታ የግንባታ ፈቃድ የሰጠ እንደሆነ፣ ወይም
   ለ) በአስረጂነት የቀረበው ሰነድ ህጋዊነት ሳይኖረው ለዚሁ ሰነድ ዕውቅና በመስጠት የተጠየቀውን የግንባታ ፈቃድ የሰጠ እንደሆነ፣ ወይም
   ሐ) ለፕላን ስምምነት የቀረበን ማመልከቻ ተቀብሎ ከከተማው ፕላን ጋር ለማይጣጣም የግንባታ ጥያቄ የግንባታ ፈቃድ የሰጠ ወይም በዚህ መሠረት ለተከናወነ ግንባታ የመጠቀሚያ ፈቃድ የሰጠ እንደሆነ፣

   ከአምስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እሥራት እና ከብር አሥር ሺህ በማያንስና ከብር ሀምሳ ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመስከተው ጥፋት የተፈፀመው በቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ ቅጣቱ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ በሚችል እሥራትና ከብር አንድ ሺ. እስከ ብር አምስት ሺ. በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይሆናል፡፡

49.<u>የመቆጣጠር ግዴታን ባለማክበር ህገወጥ ግንባታ እንዲከናወን ስለመርዳት</u>

1. ማንኛውም የህንፃ ሹም ወይም የግንባታ ሥራን የመቆጣጠር ኃላፊነት የተሰጠው ሌላ የመንግሥት ሠራተኛ ወይም ይህንኑ ተግባር ለማከናወን በውል ኃላፊነት የተሰጠው ሰው ሆን ብሎ በዚህ አዋጅ መሠረት ሊከናወን የሚገባውን የቁጥጥር ሥራ ሳያከናውን በመቅረት በህግ የተደነገጉትን የግንባታ ደንቦች ሳይከተል እየተከናወነ የሚገኘውን የግንባታ ሥራ ሳያስቆም ወይም እንዲቆም ሳያስደርግ ግንባታው የተጠናቀቀ እንደሆነ፣ ከአምስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከአሥር ሺህ ብር እስከ ሃምሳ ሺህ በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተው ጥፋት የተፈፀመው በቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ ቅጣቱ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ በሚችል እሥራትና ከብር አንድ ሺ. እስከ ብር አምስት ሺ. በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይሆናል፡፡

50.<u>ባለጉዳይን አላግባብ ማጉላላት</u>

ማንኛውም የህንፃ ሹም ወይም እርሱን በመወከል እንዲሰራ ኃላፊነት የተሰጠው ሌላ የመንግሥት ሠራተኛ ወይም በየደረጃው የተለያዩ መረጃዎችን ወይም ሰነዶችን ለመስጠት ኃላፊነት የተሰጠው የመንግሥት ሠራተኛ ባለጉዳይን ለመጉዳት ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከባለጉዳዩ የገንዘብ ወይም ሌላ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ያለ በቂ ምክንያት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲከናወኑ የተመለከቱትን ጉዳዮች ለማከናወን ፈቃደኛ ባለመሆን ከህግ ወይም ከተለመዱ የአሠራር ሁኔታዎች ውጪ ባለጉዳዩን ያጉላላ እንደሆነ፣ ከስድስት ወር እስከ ሦስት ዓመት ሊደርስ በሚችል ቀላል እሥራት እና ከብር አምስት መቶ እስከ ብር እስከ ሶስት ሺ በሚደርስ ገንዘብ ይቀጣል፡፡

51.<u>መረጃ ስለመደበቅና የተሳሳተ መረጃ ስለመስጠት</u>

1. ማንኛውም ከግንባታ ሥራ ጋር በተያያዘ የቦታ አጠቃቀምና ይዞታን፣ እንዲሁም በዚህ አዋጅ መሠረት ከግንባታ ሥራ አፈፃፀም ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መረጃዎች የማስፈር፣ ሰነዶችን የመያዝ ወይም የመጠበቅ፣ የሰነዶችን ትክክለኛነት የማረጋገጥ ወይም የመስጠት ኃላፊነት የተሰጠው የመንግሥት ሠራተኛ በጉዳዩ ጥቅም ያለውን ሰው ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌሎች ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማስገኘት በማሰብ፣
   ሀ) በሰነድ ያልተረጋገጠ መረጃ ወይም ሰነድ ከሚያስረዳው የተለየ መረጃ የሰጠ እንደሆነ፣ ወይም
   ለ) በትክክል መግለጽ ያለበትን ሁኔታ የሚያስገኘውን ውጤት ለማስቀረት ወሳኝነት ያለውን ፍሬ ነገር ያስቀረ እንደ ሆነ፣

   ከአምስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ እሥራት እና ከብር አሥር ሺህ እስከ ብር ሃያ ሺህ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡
2. የተሳሳተው መረጃ የተሰጠው መረጃው የሚያስከትለውን ጉዳት ለመረዳት የሙያ ዕውቀት ወይም የሥራው ኃላፊነት በሚፈቅድለት ሠራተኛ የሆነ እንደሆነ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ አሥራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር አሥር ሺህ እስከ ብር ሃምሳ ሺህ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተው ጥፋት የተፈፀመው በቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ ቅጣቱ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ በሚችል እሥራትና ከብር አንድ ሺ እስከ ብር አምስት ሺ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይሆናል፡፡

52. **ደረጃው የማይፈቅድለት ግንባታ ማከናወን**

ማንኛውም በግንባታ ሥራ እንዲሰማራ ፈቃድ የተሰጠው የህንፃ ሥራ ተቋራጭ በዋናነት ወይም በንዑስ ሥራ ተቋራጭነት አግባብነት ባለው አካል የተሰጠው የሙያ ደረጃ የማይፈቅድለትን ማንኛውንም የግንባታ ሥራ አከናውኖ የተገኘ እንደሆነ ወይም ማንኛውም አግባብ ካለው አካል የተሰጠ የሙያ ፈቃድ ሳይኖረው በባለሙያ ሊሰራ የሚገባውን ግንባታ ሠርቶ የተገኘ እንደሆነ ከአምስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እሥራት እና ከብር አምስት ሺህ እስከ ብር አሥር ሺህ ይቀጣል።

53. **ደረጃውን ያልጠበቀ ግንባታ ስለማከናወን**

1. ማንኛውም በግንባታ ሥራ እንዲሰማራ ፈቃድ የተሰጠው የህንፃ ሥራ ተቋራጭ በዋናነት ወይም በንዑስ ተቋራጭነት ሲሰራ፤
   - ሀ/ የግንባታው ዲዛይን የሚጠይቀውን የግንባታ ዕቃ ደረጃ ባለመጠበቅ የጥራት ወይም የጥንካሬ ደረጃውን ባላሟላ የግንባታ ዕቃ ወይም በሙያው ዘርፍ ተቀባይነት ያለውን አሰራር ሳይከተል የሰራ እንደሆነ፣ ወይም
   - ለ/ በዲዛይን ወይም በሌሎች የውለታ ሰነዶች በግልጽ የተመለከቱ የሥራ ሁኔታዎችን በባለሙያ ሊለዩ የሚችሉና ተገቢውን ሙያዊ ጥንቃቄ አድርጎ ቢሆን ኖሮ ሊታረሙ ይችሉ የነበሩ ስህተቶችን ሳያርም ወይም እንዲታረሙ ሳያደርግ ያከናወነው ግንባታ አደጋ ያስከተለ እንደሆነ፣

   ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እሥራት እና ከብር ሃምሳ ሺህ እስከ ብር መቶ ሺህ ድረስ ይቀጣል።
2. ማንኛውም የግንባታ ባለቤት፤
   - ሀ) ለሚያከናውነው ግንባታ የሚያስፈልገውን የዲዛይን ሥራ፣ ወይም በተሰራው ዲዛይን መሠረት የሚከናወነውን ግንባታ የሙያ ደረጃው በማይፈቀድለት ባለሙያ ያሰራ እንደ ሆነ፣ ወይም
   - ለ) የሚያከናውነው ግንባታ ደረጃ ከሚጠይቀው የግንባታ ቁሳቁስ ያነሰ የጥራት ደረጃ ያላቸው ቁሳቁሶች በጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደረገ እንደሆነ፣ ወይም

ሐ) ግንባታውን አግባብ ካለው አካል የመጠቀሚያ ፈቃድ ሳያገኝ ወይም ከተፈቀደው ውጪ ለሌላ አገልግሎት አውሎት የተገኘ እንደሆነ፣ ወይም

መ) በማንኛውም ሌሎች ሁኔታዎች ግንባታውን የሕዝብን ደህንነት አደጋ ላይ በሚጥል ሁኔታ ያከናወነ እንደሆነ፣

ከአምስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ እሥራት እና ከብር ሃያ ሺህ እስከ ብር ሃምሳ ሺህ ይቀጣል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ እና /2/ የተመለከቱት ጥፋቶች የተፈፀሙት በቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ ቅጣቱ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ በሚችል እሥራትና ከብር አንድ ሺ. እስከ ብር አምስት ሺ. በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይሆናል፡፡

54.<u>የአማካሪነት የሙያ ኃላፊነትን ስለመጣስ</u>

1. ማንኛውም የተመዘገበ ባለሙያ ሆን ብሎ በሙያው በግልጽ የሚታወቁ ጥንቃቄዎችን ባለማድረግ፤

ሀ/ የግንባታ ሥራው የሚጠይቀውን መሠረታዊ የጥንቃቄ ደረጃዎችን ያልጠበቀ ዲዛይን፣ ወይም ሌሎች የተሳሳቱ ተዛማጅ ሰነዶችን በማዘጋጀት፣ ወይም

ለ/ እንደግንባታ ሥራው ዓይነት ሊጠበቅ የሚገባውን የጥራት ደረጃ ደንቦች በመጣስ ለግንባታው ዕቃ ለሚያቀርብ ሰው ወይም ግንባታውን ለሚያከናውነው ሥራ ተቋራጭ ለዚሁ ግንባታው ሊውል ከሚገባው ያነሰ የጥንካሬ ወይም የጥራት ደረጃ ያለው የግንባታ ዕቃ እንዲያቀርብ ወይም አገልግሎት ላይ እንዲውል ፈቃድ ወይም ስምምነት በመስጠት፣ ወይም

ሐ/ ሙያው የሚጠይቀውን ሥነ ምግባር በመጣስ በግንባታ ሙያ ዘርፍ ተቀባይነት የማይኖረውን ወይም ከደረጃ በታች የሆነ ግንባታ እንዲከናወን ወይም የተሰራ ግንባታ ተቀባይነት እንዲያገኝ ስምምነቱን በመስጠት የሕዝብን ደህንነት ለአደጋ የሚያጋልጥ ግንባታ አገልግሎት ላይ እንዲውል ያደረገ እንደሆነ፣

ከአምስት ዓመት እስከ አሥራ አምስት ዓመት በሚደርስ እሥራት ወይም ከብር ሠላሳ ሺ. እስከ ብር ሃምሳ ሺ. በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተው ጥፋት የተፈፀመው በቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ ቅጣቱ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ በሚችል እሥራትና ከብር አንድ ሺ. እስከ ብር አምስት ሺ. በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይሆናል፡፡

55.<u>በመንግሥት ሰነዶች አላግባብ ስለመገልገል</u>

1. ማንኛውም በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን ለማስፈፀም የተመደበ የመንግሥት ሠራተኛ በሥራው አጋጣሚ ከእጁ ሊገቡ የቻሉትን የመንግሥት ወይም የህዝብ ሰነዶች በማጥፋት፣ በማበላሸት፣ በመደበቅ ወይም ወደሀሰት በመለወጥ፣ በመደለዝ ወይም በማሻሻል ወይም በከፊል ቃሉን በመቀነስ ወይም ሌላ በመጨመር እና የመሳሰሉትን ድርጊቶች በመፈፀም ለግል ጥቅም አገልግሎት በሚሰጡ አኳኋን የተገለገለባቸው ወይም ሌላ ሰው እንዲገለገልባቸው ያደረገ እንደሆነ ከአምስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር ሃያ ሺ. እስከ ብር ሃምሳ ሺ. በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል፡፡
2. ወንጀሉን የፈፀመው ሰው ከላይ የተገለፁትን ሰነዶችን የመያዝ ወይም የመጠበቅ፣ ወይም አያያዛቸውንና አጠባበቃቸውን ለመቆጣጠር ኃላፊነት የተሰጠው ሰው እንደሆነ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ ሀያ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር ሃያ ሺ. እስከ ብር ሃምሳ ሺ. በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተው ጥፋት የተፈፀመው በቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ ቅጣቱ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ በሚችል እሥራትና ከብር አንድ ሺ. እስከ ብር አምስት ሺ. በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይሆናል፡፡

56.<u>ስለሙያና ሥራ ፈቃድ ዕገዳ</u>

በዚህ ክፍል በተመለከቱት የህግ መጣስ ተግባሮች ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ የተመዘገበ ባለሙያ ወይም ሥራ ተቋራጭ በፍርድ ከተወሰነበት የእሥራት ቅጣት በተጨማሪ ጥፋተኛው ከአምስት ዓመት ጀምሮ ጥፋተኛ በተባለበት አንቀጽ እስከተመለከተው ከፍተኛ የእሥራት ዘመን ድረስ የሙያ ወይም የሥራ ፈቃዱ ይታገዳል፡፡

## <u>ክፍል ሰባት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

57.<u>የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅ በማስፈፀም ረገድ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. በአገር አቀፍ ደረጃ የሚሠራባቸው ልዩ ልዩ ኮዶችን ያዘጋጃል፣
2. ለየሕንፃ ምድቦቹ የሚያገለግሉ የዲዛይንና ኮንስትራክሽን ዘዴ መመሪያዎች ሞዴል ለክልሎች ያዘጋጃል፣
3. አዋጁ በክልሎችና በከተሞች ተከብሮ መፈፀሙን ይቆጣጠራል፣

4. ከሌሎች አግባብነት ካላቸው የፌዴራል መንግሥቱ አካላት ጋር በመቀናጀት ክልሎችና ከተሞች አዋጁን ለማስፈፀም እንዲችሉ የአቅም ግንባታና የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

58.<u>የክልሎች ሥልጣንና ተግባር</u>

ክልሎች ይህን አዋጅ በማስፈፀም ረገድ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል፣

1. የመመሪያዎቹ አስገዳጅነት ሙያዊ ወይም ሳይንሳዊ በሆኑ አሳማኝ ምክንያቶች ሊቀር የሚችል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከሌሎች ከዚህ አዋጅ ጋር ሳይቃረኑ በሥራቸው የሚገኙ ከተሞችን ተጨባጭ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት በከተሞቹ ተፈፃሚ የሚሆነው የዲዛይንና ኮንስትራክሽን ዘዴ መመሪያዎችንና መመዘኛዎችን ያወጣሉ፣
2. ይህ አዋጅ ከከተማ ክልል ውጪ ተፈጻሚ ለሚሆንባቸው አካባቢዎች አዋጁን የሚያስፈጽሙ አካላት ይሰይማሉ፣
3. በአቅም ማነስ ምክንያት የሕንፃ ሹም ሊመድቡ ባልቻሉ ከተሞች የሌላ ከተማ የሕንፃ ሹም በውክልና አዋጁን እንዲያስፈጽም ሊወሰኑ ይችላሉ፣
4. በየክልላቸው ውስጥ የሚገኙ ከተሞች አዋጁን ለማስፈጸም እንዲችሉ የአቅም ግንባታና የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡

59.<u>የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>

1. ስለከተማ ዞንና የህንፃ ሥራ ፍቃድ የወጣው አዋጅ ቁጥር 316/1979 ከአንቀጽ 8 እስከ 14 የተመለከቱት ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል።
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

60.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ አንድ ዓመት ካበቃ በኋላ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡[136]

**አዲስ አበባ ሚያዝያ 28 ቀን 2001 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

[136] በማረሚያ ቁጥር 4/2001 ታረመ፡፡

**ደንብ ቁጥር 243/2003**

**የሕንጻ ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በኢትዮጵያ ሕንጻ አዋጅ ቁጥር 624/2001 መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሕንጻ ደንብ ቁጥር 243/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሠጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. "ጊዜያዊ ግንባታ" ማለት የጊዜ ገደብ ተቀምጦለት የሚገነባ እና የተሰጠው የጊዜ ገደብ ሲጠናቀቅ የሚነሳ የሕንፃ ግንባታ ነው፤
   2. "የሕዝብ መገልገያ ሕንፃ" ማለት በርካታ እና የተለያዩ ተጠቃሚዎችን የሚስብ እንደ ቲያትር ቤት፣ የሕዝብ ቤተ መፃሕፍት፣ መሰብሰቢያ አዳራሽ፣ መዝናኛ፣ የትምህርት ተቋም፣ የህክምና አገልግሎት መስጫ፣ የገበያ ማእከል ወይም እነዚህን የመሳሰሉ በርካታ ህዝብ የሚገለገልበት ሕንፃ ነው፤
   3. "ትንታኔ" ማለት ፕላን ወይም ዲዛይን ለማዘጋጀት የሚሰራ ስሌት ወይም እነዚህን ለመደገፍ የሚዘጋጅ ማብራሪያ ነው፤
   4. "የፕላን ስምምነት" ማለት ለሕንፃ ግንባታ እንዲቀርብ ለሚዘጋጅ ፕላን ከከተማው ፕላን ጋር የተጣጣመ እንዲሆን የሚያስችለው መሆኑን በማረጋገጥ የሚሰጥ በአንድ ቦታ ሊገነቡ የሚችሉ ወይም ለቦታው ያልተፈቀዱ የአገልግሎት አይነቶችን፣ ለቦታው የተፈቀደ የሕንፃ ከፍታን፣ በቦታው አካባቢ የሚያልፉ የመሠረተ ልማት አውታሮችን፣ ነባራዊ እና የታቀዱ መጠኖችን ወይም ስፋቶችን የሚያሳይ የፕላን መረጃ ነው፤

5. “የፕላን ማሻሻያ” ማለት በነባሩ ፕላን ለሕንፃው ምድብ የተጠየቁ ፕላኖችን ትንታኔ ሙሉ ለሙሉ መከለስ ሳያስፈልግ የሚደረግ ማስፋፊያ ወይም ማሻሻያ ነው፤
6. “ሪል እስቴት” ማለት ለሽያጭ፣ ለኪራይ፣ ወይም ለሊዝ አገልግሎት እንዲውል የተገነባ ሕንፃ ነው፤
7. “የአገልግሎት ለውጥ” ማለት አንድ ሕንፃ ያለውን ነባር አገልግሎት በሌላ ዓይነት አገልግሎት መለወጥ ነው፤
8. “የግንባታ ፈቃድ” ማለት አንድ የሕንፃ ግንባታ ለማካሄድ ለሚፈልግ አካል ሕንፃውን ለመገንባት የሚያስችሉት ዝርዝር መስፈርቶች እንደተሟሉ በከተማው ሹም ተረጋግጦ ግንባታ እንዲካሄድ ፈቃድ መስጠቱን የሚገልጽ ማስረጃ ነው፤
9. “ማስታወቂያ” ማለት በሕንጻ ዲዛይን እና ግንባታ ወቅት የከተማ አስተዳደር፣ የተሰየመ አካል ወይም የህንጻ ሹም ለሕንጻው ባለቤት ወይም የህንጻው ባለቤት ለተጠቀሱ አካላት የሚያቀርበው የጥያቄ፣ የትእዛዝ፣ የመረጃ፣ የማስጠንቀቂያ ሠነድ ነው፤
10. “አዋጅ” ማለት የኢትዮጵያ ህንጻ አዋጅ ቁጥር 624/2001 ነው፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>አስተዳደር</u>

### 3. <u>ማመልከቻና ፕላን ስለማቅረብ</u>

1. በአዋጁ አንቀፅ 4 መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ፡-

   ሀ) የአመልካቹን ሙሉ ስምና አድራሻ፣

   ለ) ሕንጻው እንዲሰጥ የተፈቀደለትን አገልግሎት፣

   ሐ) ሕንፃው የሚገነባበትን ቦታ፣

   መ) የሕንፃውን ወለል ጠቅላላ ስፋት የሚገልጽ ሠንጠረዥ፣

   ሠ) የፕላን ስምምነት ማስረጃ፣

   ረ) የኮንክሪት ጣሪያ ላላቸው የምድብ “ሀ” ህንፃዎች የአርክቴክቸር፣ የስትራክቸር እና የኤሌክትሪክ ፕላን፣

   ሰ) የኮንክሪት ጣሪያ ለሌላቸው የምድብ “ሀ” ህንፃዎች የአርክቴክቸር እና የኤሌክትሪክ ፕላን፣

ሸ) ለሕንፃ ምድብ “ለ” የአርክቴክቸር፣ የስትራክቸር፣ የሳኒተሪ፣ የኤሌክትሪካል ፕላን እና የአፈር ምርመራና ስትራክቸር ትንታኔ ሪፖርት፣

ቀ) ለሕንፃ ምድብ “ሐ” ለህንፃ ምድብ “ለ ከተጠየቁት በተጨማሪ የእሳት አደጋ መከላከያ ፕላን፣

በ) ሊፍት እና ለአየር ዝውውር ሰው ሰራሽ አማራጮችን የሚጠቀሙ ህንፃዎች የኢሌክትሮ-መካኒካል ፕላኖች እና ትንታኔዎች፣

ተ) በአዋሳኝ ቦታዎች የሚገኙ ግንባታዎች ከመሬት በላይ እና በታች ያላቸው የወለል ብዛት እና ከጋራ ወሰን ያላቸው ርቀት፣ እና

ቸ) የሕንፃውን ፕላን ያዘጋጁ የተመዘገቡ ባለሙያዎች ሙሉ ስም፣ አድራሻ እና ፊርማ ያረፈበት የምዝገባ ምስክር ወረቀት ኮፒ፣

ጋር ተያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ተ) ላይ የተገለፀው የአዋሳኝ ቦታዎች መረጃ በከተማው አስተዳደር ወይም በተሰየመው አካል በሚዘጋጅ ቅፅ አጐራባቹን በማስሞላት የሚቀርብ ይሆናል፡፡
3. የግንባታ ፈቃድ በተጠየቀበት ይዞታ የአጐራባች ቦታ ላይ የሚገኝ ባለይዞታ ይዞታውን በሚመለከት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተጠቀሰውን ቅጽ የመሙላት ግዴታ አለበት፡፡
4. የሕንጻ አገልግሎት ለውጥ ወይም ማሻሻያ ለማድረግ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በአገልግሎት ለውጥ ወይም ማሻሻያ ከሚገኘው የሕንጻ ምድብ ጋር ተመሳሳይ ለሆነ አዲስ ሕንፃ የሚጠየቁትን ፕላኖች ከትንታኔያቸው ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡ የሕንጻው ፕላኖች ከሌሉ የነባሩ ሕንፃ ልኬት ተሰርቶ ከተለካበት አግባብ እና ከትንታኔያቸው ጋር መቅረብ ይኖርበታል።

4. **<u>የፕላን ስምምነት</u>**

1. የፕላን ስምምነት ለማግኘት ገንቢው የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል በሚያዘጋጀው ቅፅ ሊገነባ ያቀደውን ሕንፃ ከፍታና የአገልግሎት ዓይነት ገልፆ በመሙላት የይዞታውን ካርታ ዋናውንና ኮፒውን በማያያዝ ጥያቄ ማቅረብ አለበት፡፡

2. የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል አዲስ ህንፃ ለመገንባት ለተጠየቀ የኘላን ስምምነት፡-
   ሀ) የይዞታ ካርታ፣እና
   ለ) የተፈቀደውን የሕንጻ ከፍታ እና አገልግሎት ዓይነት የሚገልጽ፣
   የኘላን ስምምነት ይሰጣል፡፡
3. ነባር ሕንጻን ለማሻሻል ወይም አገልግሎት ለመለወጥ ለተጠየቀ የኘላን ስምምነት የከተማው አስተዳደር፡-
   ሀ) የይዞታ ካርታ፣ እና
   ለ) የተፈቀደውን የሕንፃ ከፍታ እና የአገልግሎት ዓይነት የሚገልጽ፣
   የኘላን ስምምነት ይሰጣል፡፡
4. የከተማ ኘላን በሌላቸው ከተሞች የሕንፃ ከፍታ እና የአገልግሎት ዓይነት አወሳሰን እና የኘላን ስምምነት አሰጣጥ ክልሉ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡
5. የሕንፃ ሹሙ በአዋጁና በዚህ ደንብ ውስጥ የተቀመጡትን የሕንፃ ምድብ መለያዎችን መሠረት በማድረግ ለግምገማ የሚቀርቡለትን ሕንፃዎች ምድብ ይወስናል።
6. የሕንፃ ሹሙ ለፕላን ስምምነት የቀረበለትን ማመልከቻ ከመረመረ በኋላ ከከተማው ፕላን ጋር የሚጣጣም ወይም የማይጣጣም ስለመሆኑ ምክንያቶቹን በመዘርዘር ከሦስት የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በጽሁፍ መልስ ይሰጣል፡

5. **<u>ፕላን ስለማስፀደቅ</u>**

1. በአዋጁ አንቀፅ 6 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የጎሉ ያልሆኑ ግድፈቶችን ለማረም በፕላን ላይ የሚሰፍሩ አስተያየቶች፡-
   ሀ) የፕላኑን ተነባቢነት የሚቀንሱ መሆን የለባቸውም፤
   ለ) ባልደበዘዘ፣ ከፕላኑ ሊጠፋ በማይችል ሁኔታ እና ፕላኑ ኮፒ ሲደረግ በኮፒው ላይ በሚወጡበት ሁኔታ መስፈር አለባቸው።
2. የጎሉ ያልሆኑ ግድፈቶች ዝርዝር በዚህ ደንብ መሠረት በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡
3. ከግንባታ ፈቃድ ጋር በግንባታ ቦታ ተቀምጦ ለግንባታ ክትትል የሚውል “ለቁጥጥር አገልግሎት ብቻ የሚያገለግል” የሚል ማህተም ያረፈበት የፀደቀ ፕላን ኮፒ ለገንቢው ይሰጣል፡፡

6. <u>የፕላን መገምገሚያ ጊዜ</u>

1. ለአንድ የሕንጻ ዓይነት የተዘጋጁ ፕላኖችን ለመገምገም የሚያስፈልገው ጊዜ፡-

ሀ) ከሪል እስቴት ውጪ ላለ በምድብ "ሀ" ስር ለሚካተት ሕንፃ የፕላኖች የመገምገሚያ ጊዜ ከአምስት የሥራ ቀናት፤

ለ) በምድብ "ለ" ስር ለሚካተት ሕንፃ የፕላኖች መገምገሚያ ጊዜ ከ7 የሥራ ቀናት፤ እና

ሐ) በምድብ "ሐ" ውስጥ ለሚካተት ህንፃ እና በምድብ "ለ" ውሰጥ ለሚካተቱ የሪል እስቴት ህንጻዎች ፕላኖች የመገምገሚያ ጊዜ ከ21 የሥራ ቀናት፤

የበለጠ መሆን የለበትም፡፡

2. በአንድ ሰው የሚቀርቡ እና በአንድ የፕሮጀክት ቦታ የሚገነቡ የሕንፃ ዓይነቶች ከአንድ በላይ ከሆኑ ለፕላን ግምገማ የሚያስፈልገው ጊዜ እንደየ ሕንፃ ዓይነቱ ለአንድ ህንፃ የሚያስፈልገውን ጊዜ ብዛት ሆኖ የጠቅላላው ፕላን መገምገሚያ ጊዜ ከ21 ቀናት መብለጥ የለበትም፡፡

3. ለየምድቡ የተሰጠው የፕላን መገምገሚያ ጊዜ የሚቆጠረው ፕላኖቹ ከቀረቡበት ጊዜ አንስቶ ነው፡፡

4. ከፕሮጀክቶቹ ስፋት ወይም ውስብስብነት የተነሳ ተጨማሪ የመገምገሚያ ጊዜ ለሚሹ ሥራዎች የሕንጻ ሹሙ ለከተማው አስተዳደር ወይም ለተሰየመው አካል በማቅረብ ተጨማሪ ቀናት መጠየቅ ይችላል፡፡

7. <u>ፕላን ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ</u>

1. የግንባታ ሥራው ሳይጀመር የጊዜ ገደቡ ያበቃ የፀደቀ ፕላን የፈቃድ ጊዜውን ለማራዘም የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት የሚኖረው በወቅቱ ለሕንፃ ሹሙ ግንባታው ያልተጀመረበት ምክንያት በጽሑፍ ተገልፆ እንደሆነና ይኸውም ምክንያት በሕንፃ ሹሙ ተቀባይነት ሲያገኝ ነው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ ተቀባይነት የሚኖረው ግንባታው ሳይጀመር የቀረው፡-

ሀ) ከወሰንተኛ ጋር የተፈጠረ ግንባታ መጀመር የማያስችል የድንበር አለመግባባት ሲፈጠር፤ ወይም

ለ) ለግንባታው የሚያስፈልጉ በከተማው አስተዳደር በኩል መሟላት የሚኖርባቸው የመሠረተ ልማት አውታሮች አለመሟላት፤ወይም

ሐ) ለግንባታው መጀመር መነሳት ያለባቸው ነባር የመሠረተ ልማት አውታሮች ሳይነሱ መቅረት፣ ወይም

መ) በቦታው ላይ አከራካሪ የይዞታ ይገባኛል ጥያቄ ሲቀርብ፣ ወይም

ሠ) በአገር አቀፍ ደረጃ በግልጽ የታወቀ የግንባታ ግብዓት አቅርቦት እጥረት ሲከሰት፣ ወይም

ረ) ከቁጥጥር ውጪ በሆኑ ሌሎች ምክንያቶች የተከሰተ፣

መሆኑ ሲረጋገጥ ይሆናል፡፡

3. ግንባታው ተጀምሮ ሥራው ሳያልቅ የጊዜ ገደቡ ላበቃ የፀደቀ ፕላን ፕላኑ ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ ለማራዘም የሚቀርብ ጥያቄ በሚከተሉት እና በወቅቱ ለሕንፃ ሹሙ በቀረበ የጽሁፍ ሪፖርት ምክንያቶች ከሆነ ተቀባይነት ይኖረዋል፡-

   ሀ) በአገር አቀፍ ደረጃ በግልጽ የሚታወቁ የግንባታ ግብዓቶች እጥረት መከሰቱ ሲረጋገጥ፣

   ለ) በዲዛይን ወቅት ባልታዩ እና በግንባታ ወቅት በታዩ የዲዛይን ስህተቶች ምክንያት የዲዛይን ማሻሻያ ሲያስፈልግ፣

   ሐ) የግንባታው ማጠናቀቂያ ከአምስት ዓመት በላይ እንደሆነ ሲታመን፣

   መ) የፍርድ ቤት ውሳኔ የሚጠይቁ ነገር ግን ውሳኔ ያላገኙ በእንጥልጥል ያሉ ሁኔታዎች መኖራቸው ሲረጋገጥ፡፡

4. በዚህ ደንብ በአንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ተቀባይነት ባገኙት ምክንያቶች ተጨማሪ ጊዜ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ፕላኑ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ፕላኑን ለመገምገም ከወሰደው ተጨማሪ ጊዜ ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት፡፡

8. <u>የግንባታ ፈቃድ</u>

የግንባታ ፈቃድ ሰነድ ተከታታይ የኮድ ቁጥር ያለው፣ የተሰጠበትን እና አገልግሎቱ የሚያበቃበትን ጊዜ የሚገልፅ ይሆናል፡፡

9. <u>በግንባታ ወቅት ፕላንን ስለማሻሻል</u>

1. በግንባታ ወቅት ለውጥ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ለውጡ ከመደረጉ በፊት ለውጡ የሚመለከተው የማሻሻያ ፕላን ተዘጋጅቶ በህንፃ ሹም መጽደቅ ይኖርበታል፡፡

2. የፀደቀው የማሻሻያ ፕላን በመጀመሪያ የፀደቀው ፕላን አካል ሆኖ ያገለግላል፡፡

3. በግንባታ ወቅት በህንጻ ሹሙ መፅደቅ ሳያስፈልጋቸው መሻሻል የሚችሉ የፕላን አካላት እና ዓይነቶች ይህንን ደንብ ተከትሎ በሚወጣ መመሪያ ይወስናሉ፡፡
4. የህንፃ ግንባታ ተጠናቆ የሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ ጥያቄ ከመቀረቡ በፊት የተደረጉ ለውጦችን ያካተተ ጠቅላላ ፕላን ተዘጋጅቶ በህንፃ ሹም መፅደቅ ይኖርበታል፡፡

10.<u>የሕንጻ ሹም</u>

1. በከተማ አስተዳደር ወይም በተሰየመው አካል የሚሾም የሕንፃ ሹም፣ በአርክቴክቸር፣ በሲቪል ምህንድስና፣ በኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂ እና በኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ወይም በተመሳሳይ ሙያ የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም ተመጣጣኝ ልምድ ያለው መሆን አለበት፡፡ ዝርዝር መመዘኛ መስፈርቶቹ በመመሪያ ይገለጻሉ፡፡
2. የሕንጻ ሹም በአዋጁ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት አዋጁ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተገነባና አዋጁ ተፈፃሚ እንዳይሆንበት የተደረገ ሕንፃ፡-
   ሀ) ሕንፃው አደጋ ሊያደርስ ስለመሆኑ መረጃ ሲደርሰው፤
   ለ) በሕንፃው ላይ በግልጽ የሚታይ የመሰንጠቅ፣ የመስመጥ ወይም የመዝመም ሁኔታ ሲስተዋል፤
   ሐ) ሕዝብን ለአደጋ ያጋልጣል ተብለው የሚገመቱ ሌሎች ሁኔታዎች ሲታዩ ሕንፃው እንዲመረመር ማድረግ ይችላል፡፡
3. የሕንፃ ሹም በሕንፃው ላይ በተደረገው ምርመራ ሕንፃው በሰውና በንብረት ላይ አደጋ የሚያስከትል መሆኑን ሲያምንበት በሙሉም ሆነ በከፊል እንዲፈርስ ወይም ማስተካከያ እንዲደረግለት ሊያዝ ይችላል፡፡

11.<u>አገልገሎት መግዛት</u>

1. የሕንፃ ሹሙ በአስተዳደሩ ውስጥ አንድን የተወሰነ ስራ ለመስራት የሚችል ባለሙያ የማይገኝ ሲሆን ይህንን ስራ ሊሰራ ከሚችል የተመዘገበ ባለሙያ ጋር አግባብ ባለው ህግ መሰረት በመዋዋል ሊያሰራ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ተዋውሎ የሚሰራው ባለሙያ ሥራውን በአዋጁ፣ በዚህ ደንብ እና በውሉ መሰረት የማከናወን ኃላፊነት አለበት፡፡

3. የሕንፃ ሹሙ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ተዋውሎ የሚሰራው ባለሙያ ኃላፊነቱን በሚገባ መወጣቱን የመከታተልና የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

12.<u>ትዕዛዝን አለማክበር</u>

1. የግንባታው ባለቤት በገባው ውለታ መሠረት የጊዜ ገደቡ ያበቃለትን ጊዜያዊ ግንባታ እንዲያፈርስ የተሰጠውን ትዕዛዝ ካላከበረ የከተማው አስተዳደር ግንባታውን በማንሣት ያወጣውን ወጪ ከባለንብረቱ በሕግ ሊጠይቅ ይችላል፡፡
2. የሕንጻ ሹሙ ከጸደቀ ፕላን ውጪ የተከናወኑ ሥራዎች የሚስተካከሉበትን አግባብ ለሕንፃው ባለቤት በጽሁፍ ገልያለት የማያስተካክል ከሆነ የሕንፃ ሹሙ ግንባታውን ማስቆም ይችላል፡፡
3. ከፀደቀ ፕላን ውጪ የተከናወኑ ሥራዎች እንዲስተካከሉ ከሕንፃ ሸሙ ትእዛዝ የደረሰው ሰው የማስተካከያ ሥራውን በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት ማከናወኑን ለሕንፃ ሹሙ በፅሁፍ ማስታወቅ ይኖርበታል።፡፡

13.<u>ማስታወቂያ</u>

1. ማንኛውንም በምድብ "ለ" እና "ሐ" የሚገኝ ሕንፃ ለመገንባት የፀደቀ ፕላን ያለው ሰው የየሥራው እርከን የሚጀምርበትን ጊዜ የሚገልጽ ማስታወቂያ የሥራ እርከንን ከመጀመሩ 5 የሥራ ቀናት አስቀድሞ ለሕንፃ ሹሙ በፅሁፍ ማቅረብ ይኖርበታል።
2. ለአዲስ ግንባታ ማስታወቂያ ሊቀርብባቸው የሚገባ የሥራ እርከኖች ቅደም ተከተል ከዚህ በታች በተመለከተው መሠረት ይሆናል፡-
   ሀ) የመሠረት ሥራ ለመጀመር የሚያስችል የቅየሣ ሥራ ሲያጠናቅቅ፤
   ለ) የመሠረት ኮንክሪት ሙሌት ሥራ ከመጀመሩ በፊት፤
   ሐ) በየደረጃው ያለ የወለል ኮንክሪት ሙሌት ሥራ ከመጀመሩ በፊት፤
   መ) የመጨረሻው የኮንክሪት ሙሌት ሥራ ከመጀመሩ በፊት፤
   ሠ) የውሃ አቅርቦት፣ የሳኒታሪ፣ የኤሌክትሪክ እና የኤሌክትሮ ሜካኒካል ገጠማ ተጠናቆ ፍተሻ በሚደረግበት ጊዜ፤
   ረ) እንደ ሥራው ዓይነት እና የአሠራር ዘዴ በሕንፃ ሹሙ የሚጠየቁ ተጨማሪ እርከኖች፡፡

3. ለነባር ግንባታ ማሻሻያ ወይም ማስፋፊያ እና ለማፍረስ ማስታወቂያ ሊቀርብባቸው የሚገቡ የሥራ እርከኖች ከግንባታ ፈቃድ ጋር ለገንቢው በጽሁፍ እንዲደርሰው ይደረጋል፡፡
4. የግንባታ ሁኔታቸው እስከፈቀደ ድረስ ለማሻሻያ ወይም ለማስፋፊያ ሥራ ማስታወቂያ የሚቀርብባቸው የሥራ እርከኖች ለአዲስ ግንባታ የሚቀርቡ የሥራ እርከኖችን መሠረት ያደረገ ይሆናል፡፡
5. ማስታወቂያ በሚቀርብባቸው የሥራ እርከኖች የህንጻ ሹሙ በግንባታ ቦታው ላይ በመገኘት ግንባታው በተሰጠው ፈቃድ መሠረት እየተከናወነ መሆኑን ይቆጣጠራል፡፡
6. ማንኛውም ዓይነት ማስታወቂያ ወይም ትዕዛዝ በጽሑፍ መሆን ይኖርበታል። በቃል የሚሰጥ ትዕዛዝ ተቀባይነት የለውም፡፡

14.<u>ቁጥጥር</u>

1. ግንባታ የሚያካሂድ ማንኛውም ሰው በግንባታ ቦታ የግንባታ ክትትል መረጃ መዝገብ ማዘጋጀት አለበት፡፡
2. የግንባታ ሥራው ወደተጠናቀቀ ወይም በግንባታ ላይ ወደሚገኝ ህንጻ የገባ ተቆጣጣሪ ስለገባበት ዓላማ እና ስለተመለከተው ሁኔታ በግንባታ መረጃ መዝገብ ላይ ማስፈር ይኖርበታል።
3. የግንባታ ማስቆሚያ ትዕዛዝ የሚሠጠው በግንባታ ክትትል መረጃ መዝገብ ላይ በማስፈር ወይም የቁጥጥር ሪፖርት ቅጽን በመሙላት ይሆናል፡፡
4. የማስቆሚያ ትዕዛዙ ቅጽ የግንባታውን አድራሻ፣ የግንባታውን ባለቤት ስም፣ የግንባታውን ፈቃድ ቁጥር፣ ከፈቃድ ውጪ የሆነው ግንባታ ያለበትን ደረጃ እና የተቆጣጣሪውን ሙሉ ስም ያካተተ መሆን አለበት፡፡
5. የሕንፃ ሹሙ ከህንፃ ተቆጣጣሪዎች ሪፖርት እና የማስቆሚያ ትዕዛዝ ሲቀርብለት በህንፃው ሥራ ላይ የተጣሱትን የህግ ድንጋጌዎች በመዘርዘር ህንፃው የሚስተካከልበትን ወይም የሚነሣበትን ወይም የሚፈርስበትን ጊዜ በመወሰን በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ለህንፃው ባለቤት በጽሑፍ እንዲደርሰው ማድረግ አለበት፡፡

15.<u>የሕንፃ ቁሳቁስ ጥራት ስለማረጋገጥ</u>

1. የሕንፃ ሹም በግንባታ ሥፍራ የተቀመጠ ወይም በሕንፃው ሥራ ላይ የዋለ ግብዓት በናሙና ፍተሻ ውጤቱ ተቀባይነት ካጣ እንዲወገድ ወይም በአጠቃቀሙ ላይ ማስተካከያ እንዲደረግ ትዕዛዝ መስጠት ይችላል፡፡
2. በግንባታ ግብዓት ጥራት ምክንያት ለሚደርስ ማንኛውም አደጋ ወይም ጉድለት የግንባታው ባለቤት ሃላፊነት አለበት፡፡

16.<u>የሕንግ መጠቀሚያ ፈቃድ</u>

1. በምድብ "ሐ" የሚመደብ ሕንፃ የግንባታ ሥራ ሲጠናቀቅ የሕንፃው ባለቤት የመጠቀሚያ ፈቃድ በማመልከቻ መጠየቅ ይኖርበታል፡፡ ለሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ የሚቀርብ የማመልከቻ ቅጽ፡-
   ሀ) የግንባታውን ባለቤት ሙሉ ስምና አድራሻ፣
   ለ) ግንባታው የሚገኝበትን አድራሻ፣
   ሐ) የህንፃው የአገልግሎት ዓይነት፣
   መ) የግንባታውን ፈቃድ ቁጥር፣
   ሠ) ግንባታው የተጀመረበትንና የተጠናቀቀበትን ቀን፣ እና
   ረ) ህንጻው በፕላኑ መሠረት ስለመሠራቱ ቁጥጥሩን ያደረገው የተመዘገበ ባለሙያ ያረጋገጠበትን ማስረጃ፣

   ማካተት አለበት፡፡
2. የሕንፃ ሹሙ የቀረበለትን ማመልከቻና ሰነዶች መርምሮ በ10 የሥራ ቀናት ምላሽ ይሰጣል፡፡
3. የሕንፃ ሹሙ የሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ ሳይኖረው በምድብ "ሐ" ሕንፃ መጠቀም በጀመረ በማናቸውም ሕንፃ ባለቤት ላይ በዚህ ደንብ አንቀፅ 44 መሠረት የገንዘብ መቀጫ የመጣል ወይም ሕንፃው የመጠቀሚያ ፈቃድ እስከሚያገኝ ጥቅም ላይ እንዳይውል የማድረግ ወይም ሁለቱንም እርምጃዎች መውሰድ ይችላል፡፡
4. የማሻሻያ ወይም የማስፋፋት ግንባታ ፈቃድ የማያስፈልገው በምድብ "ሐ" ሥር የሚመደብ ህንጻ ግንባታው ሲጠናቀቅ በግንባታ ፈቃዱ መሠረት መከናወኑ እና ፈቃድ ለተጠየቀበት አገልግሎት ብቁ መሆኑ ተረጋግጦ የመጠቀሚያ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል።

5. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀፅ (4) መሠረት የመጠቀሚያ ፈቃድ ማግኘት የሚገባቸው ሕንፃዎች ፈቃዱን የሚያገኙት ከአዲስ ሕንጻዎች የመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ጋር በተመሳሳይ መልኩ ይሆናል፡፡

17.<u>ጊዜያዊ ግንባታዎች</u>

1. ጊዜያዊ ግንባታ ለማካሄድ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ጊዜያዊ ግንባታ ለማካሄድ የፈለገበትን ቦታ ለጊዜያዊ ግንባታ ለመጠቀም የሚያስችል ፈቃድ ከከተማው አስተዳደር ወይም ከተሰየመው አካል ማግኘት ይኖርበታል፡፡
2. የጊዜያዊ ግንባታ ለማከናወን ቦታ የተፈቀደለት ሰው ለሚያከናውነው ጊዜያዊ ግንባታ ከሕንጻ ሹም ጊዜያዊ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡
3. የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ ለማግኘት ለሕንጻ ሹሙ የሚቀርብ ማመልከቻ፡-
   ሀ) የግንባታውን አገልግሎት የሚገልጽ ማብራሪያ፣
   ለ) የግንባታ ቦታውን በጊዜያዊነት ለመጠቀም ከከተማው አስተዳደር ወይም ከተስየመው አካል የተሰጠውን ማስረጃ፣
   ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ (ለ) የተጠቀሰውን ቦታ ለጊዜያዊ ግንባታ ለመጠቀም የተሰጠው ፈቃድ ሲያበቃ በምን መልክ እንደሚያስረክብ የተስማማበትን ሰነድ፣
   መ) ለምድብ "ሀ" ህንፃ የሚጠየቁ ማስረጃዎችን እና የፕላን ዓይነቶችን፣
   ጋር ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል፡፡
4. ለሕዝብ መገልገያነት እንዲውል ለሚጠየቅ ጊዜያዊ ግንባታ በምድብ "ሐ" ለሚገኝ ህንፃ የሚጠየቁ የግንባታ ፈቃድ ፕላኖች ወይም ዲዛይኖች በዚህ ደንብ አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ (ቀ) መሠረት መቅረብ አለባቸው፡፡
5. ጊዚያዊ ግንባታዎች የቋሚነት ይዘት በሌላቸው በቀላሉ ሊነቃቀሉ እና ሊነሱ በሚችሉ ቁሳቁሶች መገንባት አለባቸው፡፡
6. በሕንፃ ሹሙ የሚሰጠው ጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ የሚያገለግለው ቦታው ለጊዜያዊ ግንባታ እስከተፈቀደበት የጊዜ ገደብ ድረስ ነው፡፡
7. ቦታን ለጊዜያዊ ግንባታ ለመጠቀም የተሰጠ ፈቃድ እስከተራዘመበት ጊዜ ድረስ በቦታው ላይ ለተሰራው ግንባታ የተሰጠው የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ ጸንቶ ይቆያል፡

8. የጊዜያዊ ግንባታው መነሳትና ቦታው በጊዜያዊነት በተሰጠበት ወቅት በተደረሰው ስምምነት መሠራት መስተካከል እና ማስረከብ ይኖርበታል፡፡

18.<u>የአገልግሎት ለውጥ፣ ማስፋፋት፣ ዕድሳት ወይም ጥገና ስለማድረግ እና ስለማፍረስ</u>

1. ማንኛውም ሰው አንድን ህንፃ አገልግሎቱን ለመለወጥ፣ ለማስፋፋት፣ ለመጠገን ወይም ለማፍረስ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡
2. አንድን ህንፃ አገልግሎቱን ለመለወጥ፣ ለማስፋፋት ወይም ለመጠገን የሚቀርብ የፈቃድ ማመልከቻ ከሚከተሉት ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡-

   ሀ) የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ፤

   ለ) አዋሳኞቹን የሚያሳይ ፕላን፤

   ሐ) አዋጁ ተፈጻሚ ከሆነ በኋላ የተሰራ ህንጻ ከሆነ የግንባታ ፈቃድ፤

   መ) የሕንፃውን የቀድሞ ፕላን እና የተሻሻለውን ፕላን፤

   ሠ) ለህንፃ ምድቡ የሚጠየቁ ፕላኖች እና ትንታኔዎች፡፡
3. አንድን ህንፃ ለማፍረስ የሚቀርብ የፈቃድ ማመልከቻ ከሚከተሉት ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡

   ሀ) የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ፤

   ለ) የህንጻው ፕላን፤

   ሐ) ህንጻውን ለማፍረስ የታሰበበትን ምክንያት፤

   መ) በአጎራባች ይዞታዎች የሚገኙ ህንጻዎች ከፍታና ከሚፈርሰው ህንጻ ወሰን ያላቸውን ርቀት፤

   ሠ) የኤሌክትሪክ፣ የውሃ፣ የፍሳሽ፣ የቴሌፎን እና የሌሎች የመሠረተ ልማት መስመሮች በሚመለከታቸው ተቋማት እንደሚቋረጡ የተደረሰበትን ስምምነት የሚገልጹ ማስረጃዎች፤

   ረ) የጥንቃቄ አወሳሰድ ዘዴዎችንና የማፍረሱን ሂደት ቅደም ተከተል የሚያሳይ ትንታኔ፡፡
4. የማፍረስ ሥራ ለዚሁ ተብሎ በሚዘጋጅ ይህንን ደንብ ተከትሎ በሚወጣ መመሪያ መሠረት መከናወን አለበት፡፡
5. የአገልግሎት ለውጥ አንድን ነባር ሕንፃ ሙሉ ለሙሉ የሚያፈርስ ከሆነ የሚሰጠው ፈቃድ ስለአዲስ ግንባታ በዚህ ደንብ አንቀጽ 3 በተመለከተው መሠረት ይሆናል፡

6. የአገልግሎት ለውጥ፣ ማሻሻያ ወይም ማስፋፋት የተደረገበት ሕንጻ በምድብ “ሐ” ሥር የሚመደብ ከሆነ ሕንጻው ለአገልግሎት ከመዋሉ በፊት የመጠቀሚያ ፈቃድ ሊያገኝ ይገባል፡፡
7. የአገልግሎት ለውጥ፣ የማስፋፋት፣ የመጠገን ወይም የማፍረስ ሥራ ሲከናወን ለሥራው በሚመጥን የተመዘገበ ሥራ ተቋራጭ መከናወን ይኖርበታል፡፡

19.<u>**የተመዘገቡ ባለሙያዎችን ስለመቅጠር**</u>

1. አርክቴክቱ የሚያስተባብረው በአንድ ፕሮጀክት የዲዛይን ዝግጅት ወቅት በተለያዩ የተመዘገቡ ባለሙያዎች የተሰሩ ዲዛይኖች እርስ በርሳቸው እና ህንጻው ሲሰጠው ከታሰበው አገልግሎት አንጻር የተጣጣሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ይሆናል፡፡
2. ማንኛውም ሰው የሕንፃ ዲዛይን ሥራ ለማሰራት ሲያቅድ ከዚህ በታች በተመለከተው መሠረት ለምድቡ የሚጠየቁ ፈቃዳቸው ለሥራ ዘመኑ የታደሰ የተመዘገቡ ባለሙያዎች መቅጠር አለበት፤፡-
   ሀ) ለምድብ “ሀ” ለአርክቴክቸር እና ለኤሌክትሪክ፤
   ለ) ለምድብ “ለ” ለአርክቴክቸር፣ ለስትራክቸር፣ ኤሌክትሪክ፣ ለሳኒተሪ እና ለአፈር ምርመራ ሥራ፤ እና
   ሐ) ሊፍት እና ለአየር ዝውውር ሰው ሰራሽ አማራጮችን ለሚጠቀሙ ህንፃዎች ለኤሌክትሮ ሜካኒካል የዲዛይን ሥራ፤

   የተመዘገቡ ባለሙያዎች መቅጠር አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል ለምድብ “ሀ” ሕንፃ ስታንዳርድ ፕላኖች በተመዘገቡ ባለሙያዎች አዘጋጅቶ ለገንቢዎች በተመጣጣኝ ክፍያ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
4. የሕንፃ ዲዛይን የሚያዘጋጁ የውጭ ሀገር አማካሪዎች ህጋዊ ሰውነት፣ የሥራ ፈቃድ፣ የሚፈቀድላቸውን የፕሮጀክት መጠን እና የዋስትና ሽፋናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
5. የሕንጻ ፕላን ዝግጅት እና የቁጥጥር ሥራ ለማከናወን የሚቀጠሩ የተመዘገቡ ባለሙያዎች ደረጃ የሕንፃውን ምድብና የፕሮጀክቱን ግምት ታሳቢ በማድረግ በሚዘጋጅ መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

6. የህንፃ ዲዛይን ለማከናወን ውለታ የሚወስድ የተመዘገበ ባለሙያ ለምድብ “ለ” እና “ሐ” ህንፃዎች ለሚያዘጋጀው ዲዛይን በአዋጁ አንቀፅ 26 (3) መሰረት የሚያቀርበው የዋስትና መጠንና አቀራረብ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

| ተ ዚ ቁ | የሕንጻ ምድብ | የፕሮጀክት ግምት /ብር/ | የዋስትና መጠን (የፕሮጀክቱን ግምት) | የዋስትና መጠን ጣሪያ /ብር/ | የዋስትና ጊዜ | የዋስትና አቀራረብ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 አ ን ቀ ጽ ን ዑ | ከሪል እስቴት ውጪ ያሉ የምድብ “ለ” ህንጻዎች | 5,000,000 | 10 በመቶ | 500,000 | ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀበት ጊዜ አንስቶ እስከ አንድ ዓመት የሚቆይ | ከታወቀ የመድን ድርጅት፣ ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ በፊት |
| 2 አ ቀ 7 . | ለሪል እስቴት እና ለምድብ “ሐ” ሕንፃዎች | 2,500,000 | 20 በመቶ | 500,000 | ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀበት ጊዜ አንስቶ እስከ አንድ ዓመት የሚቆይ | ከታወቀ የመድን ድርጅት፣ ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ በፊት |
| | | 10,000,000 | 15 በመቶ | 1,500,000 | | |
| | | 20,000,000 | 10 በመቶ | 2,000,000 | | |

በ

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) የተመለከተው የመድን ሽፋን መስጫ ጊዜ በፍትሐብሔር ህጉ ስለማይንቀሳቀስ ንብረት የሥራ ውል የተመለከቱትን ድንጋጌዎች የሚነካ አይሆንም፡፡

8. ለዋስትና መጠን ስሌት የሚሆነው የፕሮጀክት ዋጋ ግምት የሚሰላው በህንጻው ጠቅላላ ስፋት እና የህንጻ ሹሙ አዘጋጅቶ በሚያቀርበው እና በከተማው አስተዳደር ወይም በተሰየመው አካል በሚፀድቀው የየምድቡ የካሬ ሜትር የግንባታ ዋጋ ስሌት መሠረት ይሆናል፡፡

20.<u>የተመዘገቡ የሥራ ተቋራጮችን ስለመቅጠር</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የምድብ "ሀ" ህንጻዎች ግንባታ ከሚመለከተው አካል የክህሎት የምስክር ወረቀት ባገኙ መለስተኛ ባለሞያዎች ሊገነባ ይችላል፡፡
2. የተመዘገቡ የሥራ ተቋራጮችን አቀጣጠር መስፈርት ይህንን ደንብ ተከትሎ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡
3. የተመዘገበ ሥራ ተቋራጭ በህንፃ ግንባታ ሥራ ለመሳተፍ ለዘመኑ የታደሰ የንግድ እና የሥራ ተቋራጭነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ሊኖረው ይገባል፡፡
4. የተመዘገቡ ሥራ ተቋራጮች ሊሳተፉ የሚችሉባቸው የፕሮጀክት መጠኖች ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡
5. በግንባታ ሥራ ላይ የሚሰማሩ የውጭ አገር ሥራ ተቋራጮች ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው መሆኑን፣ የተሰጣቸውን የሥራ ፈቃድ፣ የሚፈቀድላቸውን የፕሮጀክት መጠን እና የዋስትና ሽፋናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
6. የሕንጻ ግንባታ ለማከናወን ውለታ የሚወስድ ማንኛውም የተመዘገበ የሥራ ተቋራጭ ለምድብ "ለ" እና "ሐ" ህንፃዎች ግንባታ በአዋጁ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሚያቀርበው የዋስትና መጠንና አቀራረብ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

| ተ.ቁ | የሕንጻ ምድብ | የፕሮጀክት ዋጋ /ብር/ | የዋስትና መጠን (የፕሮጀክቱን ግምት) | የዋስትና መጠን ጣሪያ /ብር/ | የዋስትና ጊዜ | የዋስትና አቀራረብ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከሪል እስቴት | 10,000,000 | 20 በመቶ | 2,000,000 | ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀበ | ከታወቀ የመድን |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ውጪ ያሉ የምድብ "ለ" ህንጻዎች | | | | ት ጊዜ አንስቶ እስከ አንድ ዓመት የሚቆይ | ድርጅት፣ ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ በፊት |
| 2 | ለሪል እስቴት እና ለምድብ "ሐ" ሕንፃዎች | 10,000,000 | 30 በመቶ | 3,000,000 | ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀበት ጊዜ አንስቶ እስከ አነድ ዓመት የሚቆይ | ከታወቀ የመድን ድርጅት፣ ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ በፊት |
| | | 15,000,000 | 25 በመቶ | 3,750,000 | | |
| | | 25,000,000 | 20 በመቶ | 5,000,000 | | |

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) የተመለከተው የመድን ሽፋን መስጫ ጊዜ በፍትሐብሔር ህጉ ስለማይንቀሳቀስ ንብረት የሥራ ውል የተመለከተውን ድንጋጌ የሚነካ አይሆንም፡፡
8. ለዋስትና መጠን ስሌት የሚሆነው የፕሮጀክት ዋጋ ግምት የሚሰላው በህንጻው ጠቅላላ ስፋት እና የህንጻ ሹሙ አዘጋጅቶ በሚያቀርበው እና በከተማው አስተዳደር ወይም በተሰየመው አካል በሚፀድቀው የየምድቡ የካሬ ሜትር የግንባታ ዋጋ ስሌት መሠረት ይሆናል፡፡
9. የግንባታ ሥራው የዲዛይን ዝግጅቱን ሥራ የሚያጠቃልል ከሆነ የዋስትና መጠኑ እና አቀራረቡ ለግንባታ ሥራው በተመለከተው በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (6) መሠረት ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>የይግባኝ ሰሚ ቦርድ</u>

### 21.<u>የቦርዱ አመሠራረት</u>

1. የይግባኝ ሰሚ ቦርዱ ከከተማ አስተዳደር ወይም ከተሰየመው አካል እና ከሚመለከታቸው ተቋማት የተውጣጡ ቁጥራቸው እንደጉዳዩ ውስብስብነት እና እንደ ከተማው ደረጃ የሚወሰን ሆኖ ከ5 እስከ 7 አባላት ይኖሩታል፡፡
2. የቦርዱ የሥራ ዘመን ከከተማ አስተዳደሩ የሥራ ዘመን ጋር ተመሳሳይ ይሆናል፡፡

3. የይግባኝ ሰሚ ቦርዱ አባላት ስብጥር እንደሚከተለው ይሆናል፦

ሀ) የከተማው አስተዳዳሪ ...................... ሰብሳቢ

ለ) የሥራ ተቋራጮች ማህበር ተወካይ......አባል

ሐ) በከተማው ከሚገኝ የፍትህ አካል ወይም ከተመሳሳይ ተቋም የሚወክል የሕግ ባለሙያ.............................................................. አባል

መ) በከተማው ከሚገኙ የሠራተኛና የመምህራንና የወጣቶች ማኅበራት እና ከከተማ ነዋሪዎች የሚመረጡ ተወካዮች ................ አባላት

ሠ) ከተማው አስተዳደር ተወካይ ............................. ጸሐፊ

4. ማንኛውም ሰው በሕንፃ ሹሙ በተሰጠ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ላይ ቅሬታ ካለው የህንፃ ሹሙ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ በደረሰው በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለይግባኝ ሰሚው ቦርድ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡

## 22. የቦርዱ ስልጣንና ተግባር

በአዋጁ አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1. የይግባኝ ሰሚ ቦርዱ አቤቱታ በደረሰው በአሥራ አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ጉዳዩን የሚመለከትበትን ቀን፣ ሰዓትና ቦታ በመወሰን ለአመልካቹ ከአምስት የሥራ ቀናት በፊት ማሳወቅ ይኖርበታል፤

2. ቦርዱ ለሚቀርብለት የይግባኝ አቤቱታ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡ ሆኖም የጉዳዩ ባህሪ ተጨማሪ ጊዜ የሚጠይቅ ሆኖ ሲገኝ ለአንድ ተጨማሪ ወር ሊያራዝም ይችላል፤

3. ቦርዱ በቀረበለት ጉዳይ ላይ ውሳኔ ለመስጠት የሌሎች ባለሙያዎችን እገዛ መጠየቅ ይችላል፤

4. ቦርዱ በቀረበለት ይግባኝ ላይ የሚሰጠውን ውሳኔ ለአመልካቹ እና ለህንጻ ሹሙ በጽሁፍ ያሳውቃል፤

5. የከተማው አስተዳደር ለቦርዱ አባላት አበል ሊከፍል ይችላል፤

6. ቦርዱ ተጠሪነቱ ለከተማው አስተዳደር ይሆናል፡፡

## 23. የቦርዱ ስብሰባ

1. ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

2. ማንኛውም የቦርዱ ውሳኔ በድምፅ ብልጫ ይሰጣል፣ ሆኖም ድምፅ እኩል ለእኩል በሆነ ጊዜ ሰብሳቢው የሚደግፈው ሃሳብ የቦርዱ ውሳኔ ይሆናል፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ክፍል አራት

## የአገልግሎት ክፍያዎች

### 24. የፕላን ስምምነትና መገምገሚያ ክፍያ

1. ለሁሉም የህንጻ ምድቦች የፕላን መገምገሚያ ክፍያ ይከፈላል፡፡
2. የፕላን ስምምነት ለማግኘት ጥያቄ ሲቀርብ የከተማው አስተዳደር የአገልግሎት ክፍያ ብር 300 በማስከፈል ስምምነቱን ይሰጣል፡፡
3. ለግንባታ ጥቅም ላይ የሚውሉት ፕላኖች በከተማው አስተዳደር ተዘጋጅተው የሚሰጠው ስታንዳርድ ፕላኖች ከሆኑ ፕላኖቹን ለማግኘት የሚፈጸመው ክፍያ እንደ ፕላን መገምገሚያ ክፍያ ይቆጠራል፡፡
4. የፕላን መገምገሚያ ክፍያ በሚከተለው ሠንጠረዥ መሠረት የሚሰላ ሲሆን የፕሮጀክት ግምት የሚሰላው የሕንጻዎቹን ጠቅላላ የወለል ስፋት በካሬ ሜትር የግንባታ ዋጋ በማባዛት ይሆናል፦

| ተ.ቁ | የፕሮጀክት ግምት /በብር/ | የፕላን መገምገሚያ ክፍያ |
|---|---|---|
| 1 | እስከ 2,500,000 | የፕሮጀክቱን ግምት $\frac{1}{2000}$ |
| 2 | 2,500,000$^{+}$እስከ 5,000,000 | $1250 + \frac{1}{2500}(\text{የፕሮጀክት ግምት} - 2{,}500{,}000)$ |
| 3 | 5,000,000$^{+}$እስከ 10,000,000 | $2250 + \frac{1}{3000}(\text{የፕሮጀክት ግምት} - 5{,}000{,}000)$ |
| 4 | 10,000,000$^{+}$እስከ 20,000,000 | $3920 + \frac{1}{3500}(\text{የፕሮጀክት ግምት} - 10{,}000{,}000)$ |
| 5 | 20,000,000$^{+}$እስከ 50,000,000 | $6770 + \frac{1}{4000}(\text{የፕሮጀክት ግምት} - 20{,}000{,}000)$ |

| | | |
|---|---|---|
| 6 | ከ50,000,000 ብር በላይ | $14270 + \frac{1}{5000}(የፕሮጀክት\ ግምት - 50,000,000)$ |

5. የሕንጻ ሹ·ም ከተማው ከሚገኝበት ክልል የግንባታ ዋጋ በመነሳት ለፕሮጀክት ግምት ስሌት የሚሆን የየህንጻ ምድቡን የካሬ ሜትር ዋጋ በማዘጋጀት ለከተማው አስተዳደር ወይም ለተሰየመው አካል አቅርቦ ያፀድቃል፡፡ የተዘጋጀው የካሬ ሜትር ዋጋ እንደ አስፈላጊነቱ ሊከለስ ይችላል፡፡
6. በዚህ ደንብ በአንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው መሠረት በግዥ በተገኘ የተመዘገበ ባለሙያ አገልግሎት ሲሆን የፕላን መገምገሚያ ዋጋ አሸናፊው ባቀረበው ዋጋ መሠረት ይሆናል፡፡
7. ለፕላን ግምገማ የቀረቡ የሕንፃ አሀዶች ተመሳሳይ ከሆኑ የፕላን መገምገሚያ ክፍያ የሚሰላው የአንዱን ሕንፃ የግንባታ ሙሉ ዋጋ እና የሌሎቹን አሀዶቹ ጠቅላላ የግንባታ ዋጋ 10 በመቶ በመደመር ይሆናል፡፡
8. ውድቅ የሆኑ ፕላኖች ተስተካክለው እንደገና ለማፀደቅ በሚቀርቡበት ጊዜ የፕላን መገምገሚያው ክፍያ፡-

   ሀ/ ለምድብ “ሀ” ሕንፃ የመጀመሪያውን ክፍያ ግማሽ፤

   ለ/ ለምድብ “ለ” እና “ሐ” የመጀመሪውን ክፍያ 25 በመቶ፤

   ይሆናል፡፡
9. ፕላኑ ውድቅ የተደረገበት ምክንያት ቀደም ሲል ይኸው ፕላን ውድቅ በተደረገበት ጊዜ ሳይታይ በታለፈ ግድፈት ምክንያት ከሆነ ተስተካክሎ የሚቀርበውን ፕላን ለመገምገም ክፍያ አይጠየቅም፡፡
10. የፕላን ማሻሻያ ክፍያ ስትራክቸራል ፕላኑን እንዲለውጥ የሚያስገድድ ከሆነ ክፍያው በአዲስ ፕላን መገምገሚያ አከፋፈል መሠረት ይሆናል፡፡ ለሌሎች የፕላን ማሻሻያዎች የሚከፈለው የፕላን መገምገሚያ ክፍያ ለአዲስ ፕላን መገምገሚያ የሚጠየቀው ክፍያ 25 በመቶ ይሆናል፡፡

25.<u>**የፕላን ማስፀደቂያ ክፍያ**</u>

ለሁሉም የሕንፃ ዓይነቶች የፕላን ማስፀደቂያ ክፍያ መጠን ለፕላን መገምገሚያ የተከፈለው ክፍያ 10 በመቶ ይሆናል፡፡

26.**የቁጥጥር ክፍያ**

1. ለሕንጻ ግንባታ የሚደረግ የቁጥጥር ሥራ በዚህ ደንብ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ (2) ለተመለከቱት ሕንፃዎች በተቀመጡት የሥራ ደረጃዎች መሠረት ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው መሠረት ለሚደረግ የቁጥጥር ሥራ ለየምድቡ የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያ፡-

   ሀ) ለምድብ "ለ" ህንፃ ብር 400 እና

   ለ) ለምድብ "ሐ" ህንፃ ብር 800፤

   ይሆናል፡፡

27.**ተመላሽ ክፍያዎች**

1. ተመላሽ ክፍያ የሚባለው አገልግሎት ያልተሰጠበት ክፍያ ወይም ክፍያ የተፈፀመበት አገልግሎት አስፈላጊ ሆኖ ሳይገኝ ሲቀር ወይም አገልግሎቱ ከሚጠይቀው በትርፍነት የተከፈለ ክፍያ ነው፡፡
2. አገልግሎት ያልተሰጠበት ክፍያ እንዲመለስለት የሚጠይቅ ሰው ጥያቄውን ክፍያው የተፈጸመበትን የአገልግሎት ዓይነት እና ክፍያው ተመላሽ እንዲሆን የተጠየቀበትን ምክንያት በመግለጽ ክፍያ ከተፈጸመበት ደረሰኝ ኮፒ ጋር በማያያዝ ማመልከት አለበት፡፡
3. የተመላሽ ክፍያ አፈፃፀም በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት ይከናወናል፡፡

**ክፍል አምስት**

**የመሬት አጠቃቀም፣ ተጓዳኝ ጥናቶች እና ዲዛይኖች ዲዛይኖች**

28.**ዲዛይኖች**

1. ለየሕንፃ ምድቡ የሚዘጋጁት ፕላኖች ወይም ዲዛይኖች እንደሚከተለው ይሆናሉ፡-

   ሀ) ለምድብ "ሀ" ህንፃዎች፣

   1) የኮንክሪት ጣሪያ ላላቸው የአርክቴክቸር፣ የስትራክቸር እና የኤሌክትሪክ ፕላን፤

   2) የኮንክሪት ጣሪያ ለሌላቸው የአርክቴክቸር፣ እና የኤሌክትሪክ ፕላን፡፡

   ለ) ለምድብ "ለ" ሕንፃዎች የአርክቴክቸር፣ የስትራክቸር፣ የሳኒተሪ እና የኤሌክትሪካል ፕላን፤

   ሐ) ለምድብ "ሐ" ሕንፃዎች ለህንፃ ምድብ "ለ" ከተጠየቁት በተጨማሪ የእሳት መከላከያ ፕላንና ማብራሪያ፤

መ) ሊፍት እና ለአየር ዝውውር ሰው ሰራሽ አማራጮችን ለሚጠቀሙ ህንፃዎች የኤሌክትሮ ሜካኒካል ፕላኖች እና ትንታኔዎች፡፡

2. የምድብ "ሐ" ሕንጻዎች ፕላን ለአካል ጉዳተኞች የሚያመቹ የየወለሉ መዳረሻዎች ለአካል ጉዳተኞች የተመደቡ የመኪና ማቆሚያዎች እና በየወለሉ ለአካል ጉዳተኞች የሚመቹ መጸዳጃ ቤቶች ያሏቸው ሆነው መዘጋጀት አለባቸው፡፡
3. ከፍታቸው ከሃያ ሜትር በታች የሆኑ እና ለአካል ጉዳተኞች አገልግሎታቸውን ተደራሽ ማድረግ የሚችሉ የሕዝብ መገልገያ ሕንፃዎች ሊፍት ሳያስፈልጋቸው ሊገነቡ የሚችሉበት ሁኔታ በመመሪያ ይዘረዘራል፡፡
4. የባለመስታወት ግድግዳ ለሚገጠምላቸው ሕንጻዎች ነፀብራቁ በነዋሪው ላይ ችግር የማያስከትል መሆኑ በቅድሚያ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

29.<u>በግንባታ ወቅት መደረግ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎች</u>

የአዋጁ አንቀጽ 31 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፡-

1. ማንኛውም የሕንፃ ባለቤት አዲስ የሕንፃ ግንባታ ከመጀመሩ በፊት፡-

ሀ) በአካባቢው ቀደም ብሎ የተሠሩ ሕንፃዎችን እና የመሠረተ ልማት አውታሮችን አገልግሎት የሚያውኩ፤

ለ) የአካባቢውን ወይም አዋሳኙን ደህንነትና ጤንነት ስጋት ላይ የሚጥሉ እና

ሐ) የትራፊክ ፍሰትን የሚያስተጓጉሉ፤

ሁኔታዎችን ማስወገድና ተገቢው የጥንቃቄ እርምጃ እንዲወስድ ማድረግ አለበት፡፡

2. በምሽት የሚከናወን ግንባታ አካባቢውን የማያውኩ እና ለሌሊት ሥራ አመቺ እና አደጋ የማያስከትል ስለመሆኑ እየተረጋገጠ ከህንፃ ሹሙ ፈቃድ ሊሰጠው ይገባል፤
3. በአዋጁ አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ለሚሠሩ ግንባታዎች የሕንፃው ባለቤት የሚከተላቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎች በጽሁፍ እንደአስፈላጊነቱም በዲዛይንና በዝርዝር ትንታኔ በማስደገፍ ለሕንፃ ሹሙ በማቅረብ ይሁንታ ማግኘት ይኖርበታል፤
4. አጎራባቹ የቴክኒክ ዕውቀት ካለው በራሱ ከሌለው ደግሞ በሚወክለው ባለሙያ ገንቢው የሚያደርገው የቅድሚያ ጥንቃቄ ዝግጅት ንብረቱን ከአደጋ መከላከል

መቻሉ እንዲገለጽለት መጠየቅ እና በግንባታም ወቅት ከግንባታው ባለቤት ጋር በመነጋገር መከታተል ይችላል፤

5. ማንኛውም የሕንጻ ግንባታ ሥራ በሚከናወንበት ወቅት ጉዳት እንዳያደርስ፡-
   ሀ) የግንባታ ሥፍራውን ተቀባይነት ባላቸው ቁሶች መከለል፤
   ለ) በቁፋሮ ወቅት ከመሬት በታች ሊኖሩ የሚችሉ የመሠረተ ልማት መሥመሮች እንዳይጎዱ፤
   ሐ) በአካባቢው የትራፊክ እንቅስቃሴ ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ለመከላከል፤
   መ) ተቀጣጣይነት ያላቸውን የግንባታ ቁሳቁሶች በአያያዝ ጉድለት ለእሳት አደጋ እንዳይጋለጡ በማድረግ፤
   ሠ) በግንባታ ሥራ ላይ ለተሠማሩ ሠራተኞችና ጉብኚዎች የደህንነት መጠበቂያዎችን በማሟላት፤
   ረ) ለግንባታ የሚውሉ የኬሚካል ውጤቶች በአጠቃቀም ወቅት በሰው ሕይወትና ንብረት ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ፤ እና
   ሰ) ብናኝ፣ ጭስና አንጸባራቂ ጨረር የመሳሰሉ አዋኪ ነገሮች አካባቢውን እንዳይረብሹ፤

   ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፡፡

30. <u>በግንባታ ቦታ ላይ ስለሚከናወኑ ሥራዎች</u>

1. በአዋጁ አንቀፅ 32 ንዑስ አንቀፅ (3) መሠረት የተሰጠው ትዕዛዝ በጊዜ ገደቡ ውስጥ ባይከበር የከተማ አስተዳደሩ ወይም የተሰየመው አካል በራሱ የግንባታው ቁሳቁስ ወይም ተረፈ ግንባታ እንዲነሳ በማድረግ ወጪው እንዲተካለት በሕግ ይጠይቃል፡፡
2. ማንኛውም የግንባታ ወይም የማፍረስ ሥራ የሚያከናውን ሰው ለሚያከናውነው ሥራ፡-
   ሀ/ የእቃ ማከማቻ፤
   ለ) የሠራተኞች መፀዳጃ፤
   ሐ) የሠራተኛ ልብስ መቀየሪያ፤
   መ) የቢሮ አገልግሎት፤ እና
   ሠ) የሠራተኛ መመገቢያ ወይም ጊዜያዊ መጠለያዎችን፤

   በቅድሚያ ማሰራት አለበት፡፡

31.**<u>አርክቴክቸር</u>**

1. የአርክቴክቸር ፕላኖች በመሪ ፕላን እና በዝርዝር የአካባቢ ፕላኖች የተቀመጡ መስፈርቶችንና የአጎራባች ሕንፃዎችን ያገናዘቡ እንዲሆኑ መደረግ ይኖርበታል፡፡
2. ማንኛውም የሕንጻ ፕላን የአካባቢውን የአየር ፀባይ ሁኔታ ከግምት ያስገባ መሆን ይኖርበታል፡፡
3. የማንኛውም ሕንፃ የአርክቴክቸር ዲዛይን ለኃይል ቁጠባ አጠቃቀም ተገቢውን ትኩረት እንዲሰጥ መደረግ ይኖርበታል፡፡።

32.**<u>የኤሌክትሪክ መሥመር ዝርጋታ</u>**

1. የኤሌክትሪክ መስመር ፕላን ተከላና ዝርጋታ ተቀባይነት ባላቸው ኮድና ስታንዳርዶች እንዲሁም የሚመለከተው አካል በሚያወጣው መመሪያ መሠረት መፈጸም ይኖርበታል፡፡
2. ለሕንጻው አገልግሎት የሚውል በቂ የኃይል አቅርቦትና የተገልጋዩን ደህንነት ከስጋት ነጻ የሚያደርግ ደረጃውን የጠበቀ የአደጋ መከላከያና መቆጣጠሪያ መሣሪያዎች መገጠም ይኖርባቸዋል፡፡
3. በምድብ "ሐ" የሚካተቱ ህንጻዎች ከዋና የኃይል አቅርቦት መስመር ከሚገኘው ኃይል በተጓዳኝ ለዋና ዋና አገልግሎቶቻቸው የሚሆን አዋጪ በሆነበት ለታዳሽ የኃይል አቅርቦት ቅድሚያ በመስጠት አማራጭ የኃይል አቅርቦት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

33.**<u>ሊፍቶች</u>**

ሊፍቶች፡-

1. ያለማቋረጥ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ ከዋና የኃይል አቅርቦት መስመር በተጨማሪ የመጠባበቂያ ኃይል አቅርቦት ሊኖራቸው፣
2. በድንገተኛ የኃይል መቋረጥ ምክንያት ተገልጋዩን ወደ ሚቀጥለው ወለል የሚያደርሱ እና በሮቻቸው እንዲከፈቱ የሚያስችል ባትሪ ሊገጠምላቸው፣
3. የአካል ጉዳተኞችን ጨምሮ ለሁሉም ተገልጋይ ለአጠቃቀም ምቹ መሆን፣
4. በብልሽት ምክንያት አገልግሎት እንዳያቋርጡ እና አስተማማኝ አገልግሎት እንዲሰጡ በተገቢው ባለሙያ ክትትል፣ በተመሰከረለት ድርጅት ወቅታዊ ምርመራ፣ ጥገና እና ዕድሳት ሊደረግላቸው፣

ይገባል፡፡

34.**ለአካል ጉዳተኞች የሚደረጉ ዝግጅቶች**

1. ማንኛውም የሕዝብ መገልገያ ሕንፃ ወይም የሕንፃ ክፍል የአካል ጉዳተኞችን እንቅስቃሴ የሚገታ ወይም የሚገድብ መሆን የለበትም፡፡
2. በማምረቻ ህንጻዎች ውስጥ ለአካል ጉዳተኞች የሚያመች የልብስ መቀየሪያ፣ መታጠቢያ እና ሌሎችም አገልግሎቶች መሟላት አለባቸው፡፡
3. በከፊል የተጠናቀቁ የሕዝብ መገልገያ ሕንፃዎች ጥቅም ላይ ለማዋል ሲፈለግ መሟላታቸውን ከሚያረጋግጡ ሁኔታዎች አንዱ ለአካል ጉዳተኞች የሚያመቹ መሆናቸው ይሆናል፡፡
4. በማንኛውም የሕዝብ መገልገያ ሕንፃ ውስጥ አካል ጉዳተኞችን በየመዳረሻዎቹ ከእንቅፋት የሚጠብቋቸው እንዲሁም በመኪና ማቆሚያነት የተያዙላቸውን ስፍራዎች የሚያመለክቱ ዓለም አቀፍ ደረጃ ያላቸው ምልክቶች መደረግ አለባቸው፡፡

**ክፍል ስድስት**

**የውሃ አቅርቦትና ሳኒቴሽን**

35.**የውሃ አቅርቦት**

1. ለሰዎች አገልግሎት የሚውል ማንኛውም ሕንፃ የውኃ አቅርቦት እና ጥራት አገሪቱ የተቀበለቻውን ዓለም አቀፍ እና በአገር ውስጥ ተቀባይነት ያላቸውን ኮድና ስታንዳርዶች ያሟላ መሆን ይኖርበታል፡፡
2. ለማንኛውም ህንፃ የሚዘጋጁ ዲዛይኖች የውሃ አቅርቦት መስመሮች እና የመጠቀሚያ ቁሳቁሶች ቁጠባዊ የውሃ አጠቃቀምን መሠረት ያደረጉ መሆን አለባቸው፡፡
3. የውሃ ማጠራቀሚያ ጋኖችና የስርጭት መስመሮች ለቁጥጥር እና ለጽዳት ተደራሽ ሆነው መገንባት አለባቸው፡፡

36.**የፍሳሽ አወጋገድ**

1. ማንኛውም የፍሳሽ ቆሻሻ መውረጃ መስመሮች ፕላን በአዋጁ እና ተቀባይነት ባላቸው የህንጻ ኮድና ስታንዳርዶች መሠረት በተመዘገበ ባለሙያ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡

2. በአካባቢው ተስማሚ የሆነ ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ መስመር ካለ የሚገነባው ህንጻ የፍሳሽ ቆሻሻ መሥመር ከአካባቢው የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ጋር መገናኘት ይኖርበታል፡፡
3. ማንኛውም ህንጻ በአቅራቢያው ተስማሚ የሆነ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ከሌለው በከተማ አስተዳደሩ ወይም በተሰየመው አካል ተቀባይነት ባለው ሌላ መንገድ ፍሳሹን ማስወገድ ይኖርበታል፡፡
4. በግቢ ውስጥ የሚደረግ የፍሳሽ አወጋገድ እና ግንባታ የሚመለከታቸው አካላት ያወጡትን መስፈርቶች እንዲያሟላ መደረግ አለበት፡፡

37.<u>ተቀባይነት የሌላቸውን ፍሳሾች መቆጣጠር</u>

1. የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል ከመፀዳጃ የሚወጣን ፍሳሽ ከጎርፍ ማስወገጃ ቦይ ጋር እንዳይቀላቀል የሚከለክል ህጎች መከበራቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡
2. የጎርፍ ውሀ መስመር ወደ ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦይ ወይም ማጠራቀሚያ ውስጥ እንዳይገባ የሚቀመጡ የጥንቃቄ መንገዶች መከተላቸውን የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል ክትትል ማድረግ አለበት፡፡

38.<u>የኢንዱስትሪ ዝቃጭ</u>

1. ማንኛውም ሰው ፈቃድ ሳይሰጠው የኢንዱስትሪ ዝቃጭ ያዘለ ፈሳሽ ወይም ጠጣር ነገር ወደ ማንኛውም ፍሳሽ፣ ወንዝ ወይም ደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ መልቀቅ ወይም መጣል የለበትም፡፡
2. ከኢንዱስትሪዎች ወይም ከፋብሪካዎች የሚወጡ ዝቃጮች ብክለትን እንዳያስከትሉ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሊዘጋጅላቸውና ግምገማው በሚመለከተው አካል መፅደቅ ይኖርበታል፡፡
3. ያለውን ደረጃ ተከትሎ የተሠራ የዝቃጭ ማስወገጃ ወይም ማከሚያ ግንባታ በተፅዕኖ ግምገማ መሠረት በአግባቡ ስለመገንባቱ አገልግሎት ከመስጠቱ በፊት በሚመለከተው አካል መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

39.<u>የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ</u>

የአዋጁ አንቀፅ 43 እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1. ለደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያነት የሚመረጠው ቦታ ለቆሻሻ ማንሻ ተሽከርካሪዎች ተደራሽ መሆን ይኖርበታል፤

2. መርዛማ ደረቅ ቆሻሻ የሚያመነጩ የማምረቻ ተቋማት የተለየ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የማጠራቀሚያ እና የአወጋገድ ዘዴ መጠቀም አለባቸው፡፡

40.**<u>የጎርፍ ውሀን ስለማስወገድ</u>**

1. የማንኛውም ይዞታ ባለቤት የጎርፍ ውሀ ለማስወገድ ለዚሁ ተብሎ ወደተገነባ ዋና መስመር ማገናኘት ይኖርበታል።
2. የማንኛውም ይዞታ ባለቤት ከዝናብ ውሃ የተወሰነው በይዞታው ውስጥ ሠርጎ እንዲቀር በከተማ አስተዳደሩ ወይም በተሰየመው አካል የወጡ ህጎችንና በጥናት የተደገፉ ዘዴዎችን መጠቀም አለበት፡፡

**<u>ክፍል ሰባት</u>**

**<u>እሳት መከላከልና የእሳት ማጥፊያ ተከላ</u>**

41.**<u>ጠቅላላ መስፈርት</u>**

1. ማንኛውም ሕንፃ በህንፃው ላይ ሊደርስ የሚችልን የእሳት አደጋ ለመከላከል ለእሳት አደጋ መከላከያ ሠራተኞች መዳረሻ ሊኖረው ይገባል፡፡
2. በምድብ “ሐ” ለሚገኙ ሕንፃዎች የአደጋ ጊዜ ማስጠንቀቂያ እና በራሱ የሚሠራ የእሳት ማጥፊያ ሥርዓት ሊገጠምላቸው ይገባል፡፡
3. በምድብ “ሐ” ለሚገኙ ሕንፃዎች በአደጋ ጊዜ የማምለጫና የመውጫ አመላካቾች በግልጽ ቦታ እንዲታዩ ሆነው መዘጋጀት አለባቸው፡፡
4. ተቀጣጣይነት ባሕሪ ያላቸው የኬሚካል ውጤቶች ተገቢ ማከማቻ ቦታ ሊኖራቸው ይገባል፡፡
5. ከአምስት ወለል በላይ ከፍታ ላላቸው ሕንፃዎች ከዋናው መወጣጫ ደረጃ በተጨማሪ ከአደጋ ነፃ ወደሆነ መሬት የሚያወርድ የአደጋ ጊዜ ማምለጫ ደረጃ ሊኖር ይገባል፡፡
6. የአደጋ ጊዜ ማምለጫ መስመር በአደጋ ጊዜ በቀላሉ ማግኘት የሚቻልና ዓለም አቀፍ ምልክቶችን የሚጠቀሙ፣ የኃይል አቅርቦት በተቋረጠ ጊዜም የሚሰሩ የብርሃን አቅጣጫ ጠቋሚ አመልካቾች የተገጠሙለት እና ከመሰናክል ነፃ መሆን አለበት፡፡

42.**<u>የእሣት ማጥፊያ መሣሪያ ተከላ</u>**

1. የእሳት ማጥፊያ መሣሪያ ተከላ የሥራ ፈቃድና የሙያ ምስክር ወረቀት ባለው ሰው መከናወን አለበት፡፡

2. የእሳት ማጥፊያ መሥመሮች እና መሳሪያዎች በቀላሉ ለተጠቃሚ የሚታዩ እና አጠቃቀማቸውን በጉልህ የሚያሳዩ መግለጫዎች በአጠገባቸው የሚገኝ መሆን አለባቸው፡፡
3. የሚገጠሙት የእሳት ማጥፊያ መሣሪያዎች ደረጃቸውን የጠበቁ ስለመሆናቸው በሚመለከተው አካል የተረጋገጡ እንዲሁም በየጊዜው አስተማማኝነታቸው ፍተሻ የሚደረግላቸው መሆን አለባቸው፡፡
4. በማንኛውም የሕዝብ መገልገያ ሕንፃ ውስጥ ያለ የእሳት ማጥፊያ መሳሪያ በማንኛውም ጊዜ ለአጠቃቀም ዝግጁ መሆን አለበት፡፡
5. ማንኛውም የምድብ "ሐ" ህንፃ ባለቤት የእሳት ማጥፊያ ወይም መከላከያ መሣሪያዎችን ደህንነት እና የዕድሳት ጊዜ የሚያመለክቱ መረጃዎችን መዝግቦ በመያዝ ለሚመለከተው አካል ቁጥጥር ዝግጁ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

43.<u>የእሳት መከላከያ የውሃ አቅርቦት</u>

የእሳት አደጋ መከላከያ ውኃ መርጫ ቱቦ ተቀባይነት ያለው የግፊትና የአቅርቦት ደረጃ ያሟላ መሆን አለበት፡፡

## ክፍል ስምንት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

44.<u>አስተዳደራዊ መቀጮ</u>

1. የወንጀልና የፍትሐ ብሔር ኃላፊነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ አዋጁን ወይም ይህንን ደንብ በሚተላለፍ የግንባታ ባለቤት ላይ የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል እንደ ሕንፃው ደረጃ ከዚህ በታች የተመለከተውን አስተዳደራዊ መቀጮ መጣል ይችላል፦

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነቶች | የህንፃ ምድብ እና አስተዳደራዊ ቅጣት መጠን(ብር) | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ምድብ ሀ | ምድብ ለ | ምድብ ሐ |
| 1 | ፍቃድ የተሰጠበት ፕላን ማመልከቻ ኮፒ በግንባታ ቦታ አለመገኘት | ---------- | 2000 | 3000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 2 | የውስጥ አደረጃጀት /የግንባታ ቅድመ ዝግጅት/ ሳያሟሉ ሥራ መጀመር | ----------- | 2000 | 3000 |
| 3 | የተሰጡ የማስተካከያ ትእዛዞችን ካጠናቀቁ በኋላ አለማስታወቅ | 1000 | 2000 | 3000 |
| 4 | የተሰጡ ትእዛዞችን በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ አለማከናወን | 1000 | 2000 | 3000 |
| 5 | ከግንባታ ክልል ውጪ የተቀመጠን የግንባታ ቁሳቁስ ወይንም ተረፈ ምርት በሚሰጥ የጽሁፍ ማስታወቂያ መሠረት አለማንሳት | 1000 | 2000 | 3000 |
| 6 | ካለተቆጣጣሪ ማሰራት | ------------- | 3000 | 5000 |
| 7 | ካለማስታወቂያ ሥራ መጀመር | -------------- | 2000 | 4000 |
| 8 | ያለፈቃድ ዕድሳት ማድረግ | 2000 | 3000 | 5000 |
| 9 | ያለፈቃድ የማስፋፋት ሥራ ማከናወን | 2000 | 3000 | 5000 |
| 10 | ያለፈቃድ የማፍረስ ሥራ ማከናወን | 2000 | 3000 | 5000 |
| 11 | በግንባታ ወቅት መወሰድ የሚገባቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎች አለመውሰድ | ………… | 3000 | 5000 |
| 12 | የሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ ሳያገኝ መጠቀም | ………… | 3000 | 5000 |

2. ከዚህ በላይ በተመለከተው ሰንጠረዥ ውስጥ ያልተመለከቱ ጥፋቶች ተፈጽመው ሲገኙ የህንጻ ሹሙ እንደጥፋቱ ክብደት በሠንጠረዡ ለየህንፃ ምድቡ ከተመለከቱት ቅጣቶች ውስጥ ተመጣጣኝ ነው ብሎ ያመነበትን ቅጣት ይጥላል፡፡
3. የተፈጸመው ጥፋት በአዋጁ በተመለከቱት የወንጀል ድንጋጌዎች ስር የሚወድቅ ሆኖ ሲገኝ የሕንፃ ሹሙ ተገቢ ነው ብሎ የሚወስደው እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ በአጥፊው ላይ የወንጀል ክስ እንዲቀርብበት ለሚመለከተው አካል መምራት አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት የሚጣል የገንዘብ መቀጮ ጥፋተኛውን በዚህ ደንብ የተመለከቱትን ከመፈፀም ወይም በከተማው አስተዳደር ወይም በተሰየመው አካል ከሚወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎች ነፃ አያደርገውም፡

55.**_የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች_**

1. ከአዋጁ መውጣት በፊት በሥራ ላይ የነበሩ ኮድና ደረጃዎች ይህንን ደንብ እስካልተቃረኑ ድረስ በዚህ ደንብ መሠረት እንደወጡ ተቆጥረው አዋጁ በሚመለከታቸው ህንፃዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ከአዎጁ እና ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረኑ የኮድና ደረጃዎች ድንጋጌዎች ተሽረዋል፡፡

56.**_መመሪያ ስለማውጣት_**

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ይህንን ደንብ ለማስፈፀም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

57.**_ደንቡ የማፀናበት ጊዜ_**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 16 ቀን 2003ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## አዋጅ ቁጥር 370/1995

## የጋራ ሕንፃ ባለቤትነት አዋጅ

በከተሞች ያለውን የቤት አቅርቦትና የቤት ፍላጐት አለመጣጣም ለመቀነስ የከተማ ቦታን በግል ከመሸንሸን በተጨማሪ ሌሎች የከተማ ቦታ አጠቃቀም አማራጮችን ጐን ለጐን ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ፤

የከተማ ቦታን ወደላይ ወይም ጐን ለጐን የተሠሩ ቤቶችን ለሚይዝ የጋራ ሕንፃ ግንባታ ማዋል አነስተኛ የከተማ ቦታ የብዙ ሰዎች የጋራ ይዞታ እና መጠቀሚያ እንዲሆን በማድረግ የከተማ ቦታ አጠቃቀምንና የቤት አቅርቦትን በማሻሻል እንዲሁም የከተሞችን ውበት በመጠበቅ ረገድ የሚኖረውን ድርሻ በመረዳት፤

የግል አልሚዎችና የኅብረት ስራ ማኅበራት በጋራ ሕንጻ ግንባታ ለሚኖራቸው ከፍተኛ አስተዋጽኦ እና የጋራ ሕንጻ ቤት ለሚገዙ ወይም ለሌሎች በጋራ ሕንጻው ላይ ባለመብት ለሆኑ ሰዎች ምቹ ሁኔታ መፍጠር ለጋራ ሕንጻ ግንባታ ወሳኝ በመሆኑ፤

ለዚህም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሠረት ይህ አዋጅ ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጋራ ሕንጻ ቤት ባለቤትነት አዋጅ ቁጥር 370/1995" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

   1. "የጋራ ሕንጻ" ማለት ከመሬት ወደላይ ወይም ጐን ለጐን የተሠሩ በተናጠል የሚያዙ አምስትና ከአምስት በላይ ቤቶች እና በጋራ ባለቤትነት የሚያዙ የጋራ መጠቀሚያዎች ያሉት ለመኖሪያ ወይም ለሌላ አገልግሎት የሚውል ግንባታ ሲሆን ሕንጻው ያረፈበትን የቦታ ይዞታ ይጨምራል፤
   2. "የጋራ መጠቀሚያ" ማለት በተናጠል ከተያዙት ቤቶች ውጭ ያለ ማናቸውም የሕንጻው አካል ነው፣

3. "የጋራ ወጪ" ማለት የባለቤቶች ማህበርን አላማ እና ግዴታ ለማስፈጸም የሚደረግ ማናቸውም ወጪ እና በዚህ አዋጅ፣ በሕንጻው ማሳወቂያ የጋራ ወጪ ተብሎ የተደነገገዉ ነው፤
4. "የጋራ ትርፍ" ማለት የባለቤቶች ማህበር ከሚሰበስበው ገቢ ወጪው ተቀንሶ የሚገኘው ውጤት ነው፣
5. "አስመዝጋቢ" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 መሠረት ሕንጻ ያስመዘገበ ነው፤
6. "የሕንፃ ማሳወቂያ" ማለት የቤት ባለቤቶች ማኅበርን እና የእያንዳንዱን የቤት ባለቤት መብትና ግዴታዎች የሚወስን ሰነድ ሲሆን ማንኛውንም የሕንፃ ማሳወቂያ ማሻሻያ ይጨምራል፣
7. "የሕንጻ መግለጫ" ማለት የጋራ ሕንፃውን ስምና አድራሻ፣ የቤቶችንና የጋራ መጠቀሚያዎችን ወሰኖች፣ እንደዚሁም ከጋራ ሕንጻው አንፃር የጋራ መጠቀሚያዎች እና የእያንዳንዱ ቤት የሚገኝበትን ትክክለኛ ቦታ የሚያሳይ ሰነድ ሲሆን፣ ማንኛውም የሕንፃ መግለጫ ማሻሻያ ይጨምራል፣
8. "ለተወሰነ ቤት የተመደበ የጋራ መጠቀሚያ" ማለት ከጋራ መጠቀሚያ ውስጥ ለአንድ ወይም ለተወሰኑ ቤቶች አገልግሎት ብቻ የተመደበ የህንፃው አካል ነው፡፡
9. "የቤት ባለቤቶች ማህበር" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመ የጋራ ሕንጻ ቤት ባለቤቶች ማህበር ነው፣
10. "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፣
11. "መዝጋቢ አካል" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የምዝገባ ተግባር ለማከናወን የሚሰየም አስፈጻሚ አካል ነው፣
12. "ቤት" ማለት በሕንፃ ማሳወቂያና መግለጫ ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት የተመደ በአንድ ወይም ከአንድ በላይ ክፍሎች ያሉት የሕንጻው አካል ነው፣

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የጋራ ሕንጻ ምዝገባና የምስክር ወረቀት

4. **የጋራ ሕንጻ ምዝገባ**

   1. የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም የሕንጻ ባለቤት ወይም ወኪሉ ህንጻው በዚህ አዋጅ እንዲገዛ ፍላጐቱን በጽሁፍ ለመዝጋቢው አካል በመግለጽ የሕንጻ ማሳወቂያና መግለጫ፣ መተዳደሪያ ደንብና ውስጠ ደንብ ሲያቀርብ ሕንጻው ይመዘገባል፤
   2. የሕንጻ ማሳወቂያና መግለጫ፣ የመተዳደሪያ ደንብ እና ውስጠ ደንብ ይዘት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፣
   3. የሕንጻ ማሳወቂያና መግለጫ፣ መተዳደሪያ ደንቡና ውስጠ ደንቡ በመዝጋቢው አካል መጽደቅና መመዝገብ አለበት፡፡

5. **የምዝገባ የምስክር ወረቀት**

   በዚህ አዋጅ መሠረት ሕንጻው ሲመዘገብ ለአስመዝጋቢው የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

6. **የምዝገባ ውጤት**

   1. ሕንጻው፣ ሕንጻው ያረፈበት ቦታና ከዚሁ ጋር የተያያዙ መብቶች፣ ጥቅሞችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ይገዛሉ፣
   2. በህንጻ መግለጫ ላይ የተገለጸው ሕንጻ በቤቶችና በጋራ መጠቀሚያዎች ይከፋፈላል፤
   3. የቤት ባለቤቶች ማኀበር የሕግ ሰውነት ያለው አካል ሆኖ ይቋቋማል፡፡

7. **የሕንጻ ማሳወቂያና መግለጫ፣ መተዳደሪያ ደንብና ውስጠ ደንብ ስለማሻሻል**

   1. የሕንጻ ማሳወቂያና መግለጫ፣ መተዳደሪያ ደንብና ውስጠ ደንብ መሻሻል በቤት ባለቤቶች 2/3ኛ ድምጽ መጽደቅ አለበት፤
   2. በክፍል ባለቤቶች የጸደቀው የሕንጻ ማሳወቂያና መግለጫ፣ መተዳደሪያ ደንብና ውስጠ ደንብ ማሻሻያ ተግባራዊ የሚሆነው ለመዝጋቢው አካል ቀርቦ ሲመዘግብና ለዚሁም የምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማህበሩ ሲሰጠው ነው፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለ ባለቤትነት

8. **ስለ ቤት ባለቤትነት**

   1. በዚህ አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማናቸዉም ቤት ባለቤት በቤቱ ላይ የባለቤትነት መብት ይኖረዋል፣

2. በዚህ አዋጅ መሠረት የሚተዳደር የጋራ ሕንጻ አባል የሆነ ቤት በተናጠል ማናቸውም ሕጋዊ ተግባር የሚከናወንበት ነው፡፡

9. **ስለ ጋራ መጠቀሚያዎች**

1. በዚህ አዋጅ፣ በጋራ ሕንጻ ማሳወቂያ፣ በመተዳደሪያ ደንብና በውስጠ ደንብ የተወሰኑ ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም የጋራ ሕንጻ የቤት ባለቤት የጋራ መጠቀሚያዎችን አግባብ በሆነ መንገድ የመጠቀም መብት አለው፣
2. በጋራ መጠቀሚያዎች የመጠቀም መብት የማይከፋፈልእና ከእያንዳንዱ ቤት የባለቤትነት መብት ጋር የማይነጣጠል ነው፤
3. የእያንዳንዱ ቤት የባለቤትነት መብት በጋራ መጠቀሚያ ላይ የሚያስገኘው የማይከፋፈል መብት ድርሻ መቶኛ በሕንጻ ማሳወቂያ ይወሰናል፣
4. የእያንዳንዱ ቤት የባለቤትነት መብት በጋራ መጠቀሚያ ላይ የሚያስገኘው መብት ድርሻ የእያንዳንዱ ቤት አካል ሆኖ የሚታይና በቤት ላይ የሚፈጸመው ማናቸውም ሕጋዊ ተግባር የሚመለከተው ነው፣
5. በዚህ አዋጅ መሠረት ካልሆነ በቀር የጋራ መጠቀሚያዎች ሊከፋፈሉ አይችሉም፡፡

## ክፍል አራት

## ስለ የቤት ባለቤቶች ማህበር

10. **ስለማኅበሩ**

የቤት ባለቤቶች ማኅበር ትርፍ ለማግኘት ወይም ለመከፋፈል ሣይሆን ለአባላቱ የጋራ ጥቅም የተቋቋመ ማኅበር ነው፡፡

11. **ዓላማ**

የቤት ባለቤቶች ማህበር የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፤

1. የቤት ባለቤቶችን በመወከል የጋራ ሕንጻውን ማስተዳደር፤
2. የጋራ ሕንጻውን ነዋሪዎች ሰላምና ደህንነት ማስጠበቅ፤
3. የቤት ባለቤቶች፣ ቤቶችን የያዙ ሰዎች፣ የጋራ መጠቀሚያ ተከራዮች፣ ይህንን አዋጅ፣ የሕንጻ ማሳወቂያና መግለጫውን፣ መተዳደሪያ ደንቡንና ውስጠ ደንቡን ማክበራቸውን ማረጋገጥ፤
4. የቤት ባለቤቶችን የጋራ ጥቅም በመወከል አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን መፈጸም፡፡

12.**<u>የማኅበር አባልነት</u>**

ማንኛውም የጋራ ሕንጻ ቤት ባለቤት የቤት ባለቤቶች ማኅበር አባል ይሆናል፡፡

13.**<u>የማኅበሩ ሥልጣንና ተግባር</u>**

የቤት ባለቤቶች ማኅበር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. የሕንጻ ማሳወቂያና መግለጫ፣ መተዳደሪያ ደንብና ውስጠ ደንብ ማውጣት፣ ማሻሻል፣
2. በጀት መወሰን፣ ማሻሻል፣
3. የጋራ መጠቀሚያዎችን አጠቃቀም መወሰን፣
4. የጋራ መጠቀሚያዎችን ማከራየት፣ በዋስትና ማስያዝ፣ ማስተላለፍ፣
5. ቅጣት መዋጮና የአገልግሎት ክፍያዎችን መወሰን፣
6. ሠራተኞች መቅጠር፣ ማስተዳደር፣ ማሰናበት፣
7. የንብረት ባለቤት መሆን፣ በዋስትና ማስያዝ፣ ማስተላለፍ፤
8. ውል መዋዋል፣ መክሰስ፣ መከሰስ፣

14.**<u>የማኅበሩ ጠቅላላ ስብሰባ ሥልጣንና ተግባር</u>**

የቤት ባለቤቶች ማኅበር ጠቅላላ ስብሰባ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፤

1. የሕንጻ ማሳወቂያና መግለጫ እንዲሁም ማሻሻያ ማጽደቅ፣
2. መተዳደሪያ ደንብና ውስጠ ደንብ እንዲሁም ማሻሻያዎቹን ማጽደቅ፤
3. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን መምረጥ፣ መሻር፤
4. የማኅበሩን የሥራ ክንውንና የሂሣብ ምርመራ ሪፖርቶች መስማትና ውሳኔ መስጠት፤
5. በዚህ አዋጅ መሠረት የቤት ባለቤቶች ማኅበር ከሌላ የቤት ባለቤቶች ማኅበር ጋር እንዲዋሀድ ወይም ሕንጻው በዚህ አዋጅ መሠረት መተዳደሩ እንዲያበቃ መወሰን፤
6. ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት ማጽደቅ፤
7. በዳይሬክተሮች ቦርድ በሚቀርብለት ማናቸውም ጉዳይ ላይ ውሣኔ መስጠት፤

15.**<u>የቤት ባለቤቶች ማኅበር ስብሰባ</u>**

1. የቤት ባለቤቶች ማኅበር ዓመታዊ ጠቅላላ ስብሰባ ይኖረዋል፤
2. የቤት ባለቤቶች ማኅበር፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ በሚያደርገው ጥሪ መሠረት ሌሎች ስብሰባዎችን ያደርጋል፤
3. 25 ፐርሰንት (ሃያ አምስት በመቶ) የሆኑትን ቤቶች የያዙ የቤት ባለቤቶች የባለቤቶች ስብሰባ እንዲደረግ ከጠየቁ የዳይሬክተሮች ቦርድ የቤት ባለቤቶች ስብሰባ መጥራት አለበት፤

4. በማንኛውም ስብሰባ ከጋራ ሕንጻው ቤት ባለቤቶች 50 ፐርሰንት ሲደመር 1 (ሃምሳ በመቶ ሲደመር 1) እና በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፤
5. የቤት ባለቤቶች በቀጥታ ወይም በወኪል አማካኝነት ድምጽ ሊሰጡ ይችላሉ፤
6. በዚህ አዋጅ በሌላ ሁኔታ ካልተደነገገ በቀር የቤት ባለቤቶች ማኅበር ውሣኔ የሚያስተላልፈው በድምጽ ብልጫ ይሆናል፡፡ .

16.<u>የዳይሬክተሮች ቦርድ</u>

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ የቤት ባለቤቶች ማኅበር የአመራር አካል ነው፤
2. የመጀመሪያውን የዳይሬክተሮች ቦርድ በአስመዝጋቢው የሚሰየሙ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ዳይሬክተሮች ከቤት ባለቤቶች መካከል በባለቤቶች ይመረጣሉ፡

17.<u>የመጀመሪያው የዳይሬክተሮች ቦርድ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. የጋራ ህንጻዉ በዚህ አዋጅ መሰረት ከተመዘገበ በኋላ አስመዝጋቢዉ የመጀመሪያዉን የዳይሬክተሮች ቦርድ መሰየም አለበት፤
2. የቤት ባለቤቶች በአስመዝጋቢዉ በተሰየሙት የቦርድ አባላት ተጨማሪ የሚሆኑ አባላት ወይም ተተኪ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሊመርጡ ይችላሉ፤
3. በዚህ አንቀጽ መሰረት ምርጫ ስለሚከናወንበት ጊዜ፣ እና በመጀመሪያ የዳይሬክተሮች ቦርድ እና በተተኪዉ የዳይሬክተሮች ቦርድ መካከል ስለሚደረገዉ የስልጣን ሽግግር ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

18.<u>የዳይሬክተሮች ቦርድ ስልጣንና ተግባር</u>

የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡-

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የማኅበሩን ጠቅላላ ስብሰባ መጥራት፣ የስብሰባውን ቃለ ጉባዔ በጽሑፍ መያዝ፣
2. የሕንጻ ማሳወቂያና መግለጫ፣ መተዳደሪያ ደንብና ውስጠ ደንብ ማሻሻያ ማዘጋጀት፣ ሲጸድቅም በሥራ ላይ ማዋል፣
3. ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት ማዘጋጀት፣ ሲጸድቅም በሥራ ላይ ማዋል፣
4. የማኅበሩን መዛግብትና ሂሣብ መያዝ፣
5. የቤት ባለቤቶች ማኅበር ጠቅላላ ስብሰባ ውሣኔዎችን ማስፈጸም፣
6. የማኅበሩን የሥራ እንቅስቃሴ በሚመለከት ለጠቅላላ ስብሰባ ሪፖርት ማቅረብ፣
7. ሌሎች በጠቅላላ ስብሰባ የሚስጡትን ተግባራት ማከናወን፡፡

19.**ስለ መተዳደሪያ ደንብና ውስጠ ደንብ**

የቤት ባለቤቶች ማኅበር መተዳደሪያ ደንብና ውስጠ ደንብ ይኖሩታል።

20.**ኦዲተር**

1. የቤት ባለቤቶች ማኅበር ኦዲተር ይኖረዋል፣
2. የኦዲተር አሰያየም፣ ብዛት፣ ተፈላጊ ችሎታ፣ ተግባራትና ስንብት በደንብ ይወሰናል፡፡

**ክፍል አምስት**

**የጋራ ሕንጻ ቤትን ስለመሸጥና ማከራየት**

21.**በአስመዝጋቢው የሚደረግ ሽያጭ**

1. በዚህ አዋጅ መሠረት ሕንጻው ከመመዝገቡ በፊት ወይም ከተመዘገበ በኋላ የጋራ ሕንጻ ቤት ሽያጭ ውል ለመዋዋል ይቻላል፤
2. ሕንጻው ከመመዝገቡ በፊትም ሆነ በኋላ ከአስመዝጋቢው ላይ የጋራ ሕንጻ ቤት ለሚገዛ ማንኛውም ሰው አስመዝጋቢው መረጃ መስጠት አለበት፤
3. አስመዝጋቢው ለገዥው መረጃ እስከሚሰጠው ድረስ ገዥው በቤት ሽያጭ ውሉ አይገደድም፣
4. መረጃ ከአስመዝጋቢው የደረሰው ገዥ የባለሀብትነት ስም በስሙ ከመዛወሩ በፊት ለአስመዝጋቢው በጽሑፍ የውሉን መሠረዝ መግለጽ ይችላል፣
5. በመረጃ በተገለጹ ጉዳዮች ላይ መሠረታዊ ለውጥ ሲኖር አስመዝጋቢው በተሻሻለ መረጃ ለውጡን ለገዥው መግለጽ አለበት፡፡ በተሻሻለ መረጃ መሠረታዊ ለውጥ መኖሩን ሲገልጽለት ወይም ገዢው በራሱ መሠረታዊ ለውጥ መኖሩን ተረድቶ አስመዝጋቢው በተሻሻለ መረጃ ሳይገለጽለት ከቀረ ገዥው ለአስመዝጋቢው በጽሑፍ የውሉን መሠረዝ መግለጽ ይችላል፡፡
6. ሕንጻው ከመመዝገቡ በፊት የቤት ሽያጭ ውል የተዋዋለ አስመዝጋቢ በዉሉ የተመለከተዉን ሕንጻ ግንባታ ሳይዘገይ የማጠናቀቅና ሕንጻዉን የማስመዝገብ ግዴታ አለበት፡፡

22.**ቤቶችን ስለማከራየት**

1. ማንኛውም የቤት ባለቤት ሲያከራይ ወይም የቤት ኪራይ ውል ሲያድስ ለቤት ባለቤቶች ማኅበር በጽሑፍ መግለጽ እና የኪራይ ውሉን ሰነድ ወይም የኪራይ ውሉን ማደሻ ሰነድ አባሪ አድርጎ መስጠት አለበት፡፡

2. ማንኛውም የቤት ባለቤት የቤት ኪራይ ውል በማናቸውም ምክንያት ሲቋረጥ የውሉን መቋረጥ የሚያስረዳ ማስረጃ አባሪ በማድረግ የውሉን መቋረጥ ለቤት ባለቤቶች ማኀበር መግለጽ አለበት፡፡
3. ማንኛውም የቤት ባለቤት የቤት ኪራይ ውል ሲዋዋል ለተከራዩ የጋራ ሕንጻውን ማሳወቂያና መግለጫ መተዳደሪያ ደንብና ውስጠ ደንብ ቅጂ መስጠት አለበት፡፡

23.<u>አስቀድሞ ወደ ቤት ስለመግባት</u>

የሕንጻው ማሳወቂያና መግለጫ ከመመዝገቡና የቤት ባለቤትነት ስም ለገዢው ከመዛወሩ በፊት ገዥው ወደ ገዛው ቤት ስለመግባቱ፣ በዚህም ጊዜ ገዥው ስለሚከፍለው ክፍያ እና ስለአስመዝጋቢው ግዴታ በቤት ሽያጭ ውል ላይ ስምምነት ሊደረግ ይችላል፡፡

<u>ክፍል ስድስት</u>

<u>ስለ ጋራ ወጪዎችና ትርፍ</u>

24.<u>በባለቤቶች የሚደረግ መዋጮ</u>

1. የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የቤት ባለቤቶች የጋራ ወጪዎችን ለመሸፈን፣ በጋራ መጠቀሚያዎች ላይ ካላቸው የማይከፋፈል ጥቅም ጋር የሚመጣጠን መዋጮ ይከፍላሉ፣
2. የቤት ባለቤቱ በጋራ መጠቀሚያዎች ላለመጠቀም የወሰነ ቢሆንም፣ ወይም በማኀበሩ ላይ የይገባኛል ጥያቄ ያለው ቢሆንም ወይም በቤት ባለቤቶች ማኀበር፣ በመተዳደሪያ ደንብ ወይም በውስጠ ደንብ በጋራ መጠቀሚያዎች የመጠቀም መብቱ በከፊል ወይም በሙሉ የተገደበ ቢሆንም የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

25.<u>የመያዣ መብት</u>

1. የቤት ባለቤት የጋራ መዋጮውን በማይከፍልበት ጊዜ ማኀበሩ በባለቤቱ ቤትና በጋራ ጥቅሞች ድርሻው ላይ ባልተከፈለው መዋጮ መጠን የመያዣ መብት ይኖረዋል፡፡ ይህ የገንዘብ መጠን ክፍያው በተወሰነለት ጊዜ ባለመከፈሉ ምክንያት የሚኖረውን ወለድ እና ወጪዎችን ይጨምራል፣
2. የቤት ባለቤት መዋጮውን መከፈል ከነበረበት ጊዜ አንስቶ ባለው የሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ማኀበሩ በዚህ አዋጅ መሠረት በንብረቱ ላይ አለ የሚለውን የመያዣ መብቱን የሚያረጋግጥለት ምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ያልተመዘገበ እንደሆነ የማኅበሩ በመያዣ መብት የሦስት ወር ጊዜው ካለቀ በኋላ ተፈጸሚ አይሆንም፣
4. የማህበሩን የመያዣ መብት ለማረጋገጥ የሚሰጠዉ የምስክር ወረቀት የቤት ባለቤቱ ያልከፈለውን የመዋጮ መጠን እና መዋጮውን ለማስከፈል ሲባል ማኅበሩ ያወጣቸውን ልዩ ልዩ ወጪዎች ለይቶ ማመልከት ይኖርበታል፣
5. ማኅበሩ የመያዣውን መብት ከማስመዝገቡ በፊት ለሚመለከታቸው የቤት ባለቤቶች 15 ቀናት የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መስጠት አለበት፣
6. የቤት ባለቤቱ በዚህ አንቀጽ የሚፈልግበትን ክፍያ ከፍሎ ሲያጠናቅቅ ማኅበሩ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንዲመዘገብ በማድረግ ለቤት ባለቤቱ ሊሰጠው ይገባል፣
7. በዚህ አንቀጽ የተመለከተው የማኅበሩ የመያዣ መብት ከመንግሥት ግብርና ቀረጥ በስተቀር ከሌሎች የተመዘገቡም ሆነ ያልተመዘገቡ መያዣዎች ቅድሚያ ይኖረዋል፡፡

26.<u>የጋራ ትርፍ</u>

1. ማኅበሩ የሚያገኘው ማንኛውም ትርፍ የጋራ ወጪዎችን ለመሸፈን ይውላል ወይም በልዩ ተቀማጭ ሂሣብ ውስጥ ይቀመጣል፣
2. ማኅበሩ ካልፈረሰ በስተቀር ይህ ትርፍ በቤት ባለቤቶች መካከል አይከፋፈልም፡፡

27.<u>ስለጥገናና ዕድሣት</u>

1. በአደጋ ምክንያት የሚደርስ ጉዳትን ስለመጠገን፡-
   ሀ) በአደጋ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸውን ቤቶች፣ የጋራ መጠቀሚያዎችን እና የማኅበሩ ንብረቶች ማኅበሩ ማስጠገን አለበት፣
   ለ) በአደጋ ምክንያት የሚደረግ ጥገና ጉዳት የደረሰበትን አካል መጠገንን እና በአዲስ መተካትን ይጨምራል። ሆኖም በቤቶች ላይ የተደረገ ተጨማሪ ሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳትን መጠገንን አይጨምርም፣
   ሐ) ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም በአንድ ቤት ላይ የተደረገ ተጨማሪ ሥራ ዓይነትና መጠን የሚወሰነው በሕንጻ ማሳወቂያ በተቀመጠው የቤቶች ደረጃ የሚመለከተው ቤት ከተመደበበት የክፍል ደረጃ ጋር በማወዳደር ይሆናል፣
   መ) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ለ) ቢኖርም ሕንጻው ከመመዝገቡ በፊት በቤቶች ላይ የተደረገ ተጨማሪ ሥራዎች ቢኖሩ ማኅበሩ የማስጠገን ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

2. ስለ ዕድሣት፡-

   ሀ) ማኅበሩ የጋራ መጠቀሚያዎችን የማደስ ኃላፊነት አለበት፣

   ለ) እያንዳንዱን ቤት የማደስ ኃላፊነት የቤቱ ባለቤት ነው፣

   ሐ) ለተወሰኑ ቤቶች የተመደቡ የጋራ መጠቀሚያዎችን ማደስ፣ የጋራ መጠቀሚያዎቹ የተመደቡላቸው ቤቶች ባለቤቶች ኃላፊነት ነው፣

   መ) የማደስ ኃላፊነት በመደበኛ የንብረት አጠቃቀም የሚመጣን ማርጀት ወይም አገልግሎት መቀነስ ማስተካከልን ይመለከታል፡፡

3. ለክፍል ባለቤቶች የሚደረግ ዕድሣት፣

   ሀ) የጋራ መጠቀሚያን ወይም ቤትን የማደስ ኃላፊነት የቤት ባለቤት ከሆነና የቤት ባለቤቱ በቂ በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ይህንን ኃላፊነቱን ባይወጣ ማኅበሩ ዕድሳቱንበ ራሱ ሊያከናውን ይችላል፣

   ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ መሠረት ማኅበሩ ዕድሳት ሲያከናውን ወጪው ኃላፊነቱን ያልተወጣው የቤት ባለቤት የጋራ ወጪ ተጨማሪ ድርሻው ሆኖ ይታሰባል፡፡

28.<u>ስለ ልዩ ተቀማጭ ገንዘብ</u>

1. ማኅበሩ ለጥገናና እድሳት ራሱን የቻለ የተለየ ገንዘብ ማስቀመጥ እና ሲያስፈልግ ወጪ ማድረግ አለበት፣
2. ለዚህ ተቀማጭ ገንዘብ ማኅበሩ ከክፍል ባለቤቶች መዋጮ ይሰበስባል፣
3. በዚህ አንቀጽ የተመለከተው ተቀማጭ ገንዘብ የማኅበሩ ሀብት ነው፡፡ በዚህ አዋጅ መሠረት ካልሆነ በቀር ለቤት ባለቤቶች አይከፋፈልም፡፡

## <u>ክፍል ሰባት</u>

## <u>ስለ ማኅበራት ውህደት</u>

29.<u>ስለ ምዝገባ</u>

1. የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ የቤት ባለቤቶች ማኅበራት የተዋሃደ የሕንጻ ማሳወቂያና መግለጫ፣ መተዳደሪያ ደንብና ውስጠ ደንብ ለመዝጋቢው አካል በማስመዝገብ ሊዋሃዱ ይችላሉ፣
2. ውህደቱ ከመመዝገቡ በፊት በእያንዳንዱ ማኅበር የቤት ባለቤቶች 80 ፐርሰንት ድምፅ መጽደቁና ማኅበራቱን ለመወከል ሥልጣን ባላቸው ሰዎች መፈረሙ መረጋገጥ አለበት፣

3. ስለ ውህደቱ በሚጠራው ጠቅላላ ስብሰባ ለሚዋሃደው ማህበር የሚያገለግሉት የሕንጻ ማሳወቂያና መግለጫ፣ መተዳደሪያ ደንብና ውስጠ ደንብ በውህደቱ ላይ ውሳኔ ለመስጠት ለሚጠራው ጠቅላላ ስብስባ ቀርበው መጽደቅ አለባቸው፣
4. የሚዋሀዱት ማህበራት የመጨረሻ ዓመት የኦዲት ሪፖርት በንዑስ አንቀጽ 3 ላይ በተጠቀሰው ስብሰባ ላይ ለአባላት መገለጽ አለበት፡፡

30.<u>ምዝገባው የሚያስከትለው ውጤት</u>

1. ውህደቱን የመሠረቱት ማኅበራት በሙሉ ተዋህደው የተዋሀደ አንድ የቤት ባለቤቶች ማኅበር ይመሠረታል፣
2. ከውህደት በፊት የነበሩት ቤቶች እና የጋራ መጠቀሚያዎች የተዋሀደው ማኅበር ቤቶችና የጋራ መጠቀሚያዎች ሆነው ይቀጥላሉ፣
3. ከውህደቱ በፊት የነበሩት የእያንዳንዱ ማኅበር የሕንጻ ማሳወቂያና መግለጫ፣ መተዳደሪያ ደንብና ውስጠ ደንብ ተፈጻሚነታቸው ይቀራል፣
4. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 31 እንደተተጠበቀ ሆኖ፣ ከውህደቱ በፊት የነበሩት የእያንዳንዱ ማኅበር ዳይሬክተሮች በአንድ ላይ የተዋሀደው ማኅበር የመጀመሪያ ዳይሬክተሮች ይሆናሉ፣
5. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 31 መሠረት ምርጫ እስከሚከናወን የሚያገለግሉ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ኦዲተሮች በአባላት ይሰየማሉ፣
6. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 29 መሠረት ለጠቅላላ ስብስባ ቀርበው የጸደቁትና የተመዘገቡት የሕንጻ ማሳወቂያና መግለጫ የመተዳደሪያ ደንብ እና ውስጠ ደንብ የተዋሀደው ማኅበር የሕንጻ ማሳወቂያና መግለጫ መተዳደሪያ ደንብ እና ውስጠ ደንብ ሆነው ይቀጥላሉ፣
7. ውህደቱን የመሠረተው የእያንዳንዱ ማኅበር መብትና ግዴታዎች ለተዋሐደው ማኅበር ይተላለፋሉ፡፡

31.<u>ዳይሬክተሮችንና ኦዲተሮችን ስለመምረጥ</u>

የተዋሀደው ማኅበር የሕንጻ ማሳወቂያና መግለጫ፣ መተዳደሪያ ደንብና ውስጠ ደንብ በተመዘገበ በ90 ቀናት ውስጥ የተዋሀደው ማኅበር የቤት ባለቤቶች በጠቅላላ ስብስባ ለተዋሐደው ማኅበር የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትና ኦዲተሮች መምረጥ አለባቸው፡፡

## <u>ክፍል ስምንት</u>

## <u>የጋራ ሕንጻ በዚህ አዋጅ መሠረት መተዳደሩ ስለሚያበቃበት ሁኔታ</u>

32.<u>የቤት ባለቤቶች ፈቃድ</u>

ድምፅ በሚሰጥበት ጊዜ ቢያንስ 80 ፐርሰንት የሆኑት ቤቶች ባለቤቶች የጋራ ሕንጻው በዚህ አዋጅ መሠረት መተዳደሩ እንዲያበቃ በማለት ድምጽ ከሰጡ ማኅበሩ ይህንኑ የሚገልጽ የጽሁፍ ማስታወቂያ ለመዝጋቢው አካል ማቅረብ አለበት፡፡

33.<u>ከፍተኛ ዉድመት</u>

1. ቦርዱ በጋራ ሕንጻው ላይ ከፍተኛ ውድመት ደርሷል ብሎ በሚወሰንበት ጊዜ ጉዳዩን ለቤት ባለቤቶች ጠቅላላ ስብሰባ በማቅረብ ስለውድመቱ መጠን እና ከውድመቱ በኋላ ሕንጻው በዚህ ሕግ መገዛቱን ያቆም እንደሆነ ማስወሰን አለበት፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት በሚደረገው የባለቤቶች ስብሰባ ከ80 ፐርሰንት በላይ የሆኑት ቤቶች ባለቤቶች ሕንጻው በዚህ ሕግ መገዛቱ እንዲያበቃ ከወሰኑ ቦርዱ ይህንኑ የሚገልጽ የጽሁፍ ማስታወቂያ ለመዝጋቢው አካል ማቅረብ አለበት፣
3. የቤቶች ባለቤቶች በዚህ አንቀጽ በተገለጸው ድምጽ መጠን ሕንጻው በዚህ ሕግ መገዛቱን እንዲያቆም በማለት ካልወሰኑ ቦርዱ በቂ በሆነ ጊዜ ውስጥ ውድመቱ እንዲጠገን ማድረግ አለበት።

34.<u>ስለ ሽያጭ</u>

1. የጋራ ሕንጻው ወይም የተወሰነው የጋራ መጠቀሚያ በሚሸጥበት ጊዜ ይህ ሕግ በተሸጠው ሕንጻ ወይም የጋራ መጠቀሚያ ላይ ተፈጻሚ መሆኑ ያበቃል፣
2. ማኅበሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ በተደነገገው፣ መሠረት ሽያጭ ለማከናወን፣
   ሀ/ ድምጽ በተሰጠበት ዕለት 80 ፐርሰንት የሚሆኑትን፣ የቤት ባለቤቶች የአዎንታ ድምጽ እና፣
   ለ/ ሽያጩ ለተወሰኑ ቤቶች አገልግሎት ተለይተው የተሰጡ የጋራ መጠቀሚያዎችን የሚጨምር ከሆነ በተጨማሪ የጋራ መጠቀሚያው ተለይቶ የተሰጣቸው ቤቶች ባለቤቶችን የእያንዳንዳቸውን ፈቃደኝነት በጽሁፍ ማግኘት አለበት፡፡

35.<u>ለሕዝብ ጥቅም ንብረት ስለመውሰድ</u>

በሕግ መሠረት ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የተወሰደ የጋራ ሕንጻ ወይም የጋራ መጠቀሚያ በዚህ ሕግ መገዛቱ ያበቃል።

## 36.ከሽያጭና ከንብረት መወሰድ ስለሚገኝ ጥቅም

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 34 ወይም አንቀጽ 35 መሠረት የጋራ ሕንጻው ወይም የተወሰነው የጋራ መጠቀሚያ በመሸጡ ወይም በመወሰዱ የሚገኘው ጥቅም በጋራ መጠቀሚያዎች ላይ ባላቸው የመቶኛ ጥቅም ጋር ተመጣጣኝ በሆነ መጠን ለቤት ባለቤቶች ይከፋፈላል፣
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ቢኖርም የተሸጠው ወይም የተወሰደው ለተወሰኑ ቤቶች መጠቀሚያነት ብቻ ተለይቶ የተተወ የጋራ መጠቀሚያ በሆነ ጊዜ ጥቅሙ የሚከፋፈለው የጋራ መጠቀሚያው ተለይቶ በተሰጣቸው ቤቶች መካከል ብቻ ይሆናል፡፡

## 37.ስለ ምዝገባ

1. መዝጋቢው አካል በዚህ አዋጅ አንቀጽ 32 ወይም 33 መሠረት የሚቀርብለትን ማስታወቂያ መርምሮ በመመዝገብ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣
2. የምስክር ወረቀቱ እንደተሰጠ ይህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም የሚወጡ ሌሎች ሕጐች በሕንጻው ላይ ተፈጻሚነታቸው ያበቃል፡፡

## 38.ስለሀብት ክፍፍል

የጋራ ሕንጻው በዚህ አዋጅ መገዛቱ ሲያበቃ፣

1. የቤት ባለቤቶች ማህበር ሀብት በማኅበሩ ላይ የሚነሱ የገንዘብ ጥያቄዎችን ለመክፈል ይውላል፣
2. ቀሪው የማኅበሩ ሃብት በጋራ ጥቅማቸው መጠን ለቤት ባለቤቶች ይከፋፈላል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## የጋራ ሕንጻ ለመሥራት ስለሚደራጅ የመኖሪያ ቤት የኅብረት ሥራ ማኅበራት

## 39.አደረጃጀት

የመኖሪያ ቤት የኅብረት ሥራ ማኅበራት የጋራ ሕንጻ በመሥራት ዓላማ ሊደራጁ ይችላሉ፡፡

## 40.የሕብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 ተፈጻሚነት

1. የጋራ ሕንጻ ለመሥራት ለሚደራጁ የሕብረት ሥራ ማኅበራት ስለመኖሪያ ቤት የሕብረት ሥራ ማኅበራት በአዋጅ ቁጥር 147/1991 ዓ.ም የተደነገገው ተፈጻሚ ይሆናል፤
2. ሆኖም ሕንጻው በዚህ አዋጅ መሠረት ሲመዘገብ ይህ አዋጅ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**41. ሕንጻ ስለማስመዝገብ**

1. የጋራ ሕንጻው ግንባታ ሲጠናቀቅ የኅብረት ሥራ ማኅበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ሕንጻውን በዚህ አዋጅ መሠረት ያስመዘግባል፣
2. በዚህ አንቀጽ መሠረት ሕንጻውን ያስመዘገበው የሥራ አመራር ኮሚቴ የባለቤቶች ማኅበር የመጀመሪያ ቦርድ በመሆን በዚህ ሕግ ለቦርዱ የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣
3. በአዋጅ ቁጥር 147/1991 መሠረት የተመረጠው የቁጥጥር ኮሚቴ በዚህ አዋጅ መሠረት ኦዲተር ሆኖ ይሠራል፣
4. ሕንጻው በተመዘገበ በ90 ቀናት ውስጥ የቤት ባለቤቶች አዲስ የዳይሬክተሮች ቦርድና ኦዲተር ሊሰይሙ ይችላሉ፡፡

**ክፍል አሥር**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

**42. ደንብ ስለማውጣት**

የከተማ አስተዳደሮቹ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚረዳ ደንብ ለማውጣት ይችላሉ፡፡

**43. ስለ ሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት**

1. በ1952 ዓ.ም የወጣው የኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ሕግ ከቁጥር 1281 እስከ ቁጥር 1308 ያሉ ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ መሠረት በሚተዳደር የጋራ ሕንጻ ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም፣
2. ማንኛውም ሕግ፣ ልማድ ወይም አሠራር በዚህ አዋጅ በተደነገጉ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**44. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጳጉሜ 6 ቀን 1995 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 574/2000

## የከተማ ፕላን አዋጅ

የተመጣጠነና የተቀናጀ ብሔራዊ፣ ክልላዊና አካባቢያዊ ዕድገትን ለማድረግ ይቻል ዘንድ ፕላን ሳይኖራቸው ቁጥራቸው እየጨመረ የመጡ ከተሞችን ትክክለኛና ራዕይ ባለው የከተማ ፕላን መምራትና መቆጣጠር በማስፈለጉ፤

የመንግሥትም ሆኑ የግል ያገባኛል ባዮች አገር አቀፍ መስፈርቶችን በጠበቀ አኳኋን የከተማ ፕላን ሃሣብ ማመንጨትን፣ አዘገጃጀትንና አፈፃፀምን አስመልክቶ በሚደረገው የአሠራር ሂደት ውስጥ ሙሉ በሙሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር በማስፈለጉ፤

በግልም ሆነ በመንግሥት አካላት የሚከናወኑ የልማት ተግባራት የጠቅላላውን ሕብረተሰብ ጤንነትና የተፈጥሮ አካባቢን ደህንነት በማይጎዳ መንገድ እንዲሁም ተጠያቂነትን ባረጋገጠ መልኩ መከናወናቸውን መቆጣጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በሥራ ላይ ያሉት የከተማ ፕላን ሕግጋት አሃዳዊ በሆነ የመንግሥት ሥርዓት የወጡና አሁን ካለው ያልተማከለ አሰራር መንፈስ ጋር የማይጣጣሙ ከመሆናቸው የተነሳ ፌዴራላዊውን የመንግሥት አወቃቀርና በከተማ ፕላን ዝግጅትም ሆነ ተፈፃሚነት ረገድ ከተሞች ሊኖራቸው የሚገባውን ሚና በሚያመለክት ሁሉን አቀፍ ሕግ መተካት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የከተማ ፕላን አዋጅ ቁጥር 574/2000" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

   1. "ቻርተር ያለው ከተማ" ማለት በፌዴራል ወይም በክልል መንግሥት ሕግ አውጭ አካል በወጣ ቻርተር መሠረት የተቋቋመ ከተማ ነው፤

2. “ካሣ” ማለት በከተማ ፕላን አፈፃፀምና በሌሎች የልማት እንቅስቃሴዎች ምክንያት ጉዳት ለሚደርስበት ባለንብረት በካሣ ህግ መሰረት በገንዘብ፣ በአይነት ወይም በሁለቱም የሚከፈል ካሣ ነው፡፡
3. “የልማት ፈቃድ” ማለት በሚቀርብ ጥያቄ መሠረት በከተማ ክልል ውስጥ የልማት ወይም የማሻሻያ ሥራ ለማከናወን እንዲቻል ለመንግሥት ወይም ለግል አመልካች እንደ ሁኔታው ቻርተር ባለው ከተማ ወይም በከተማ አስተዳደር በጽሑፍ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤
4. “ንብረት ማስለቀቅ” ማለት ቻርተር ያለው የከተማ አስተዳደር ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ተመጣጣኝ ካሣ በመክፈል ማንኛውንም ንብረት ለማስለቀቅ የሚፈጽመው ተግባር ነው፤
5. “የሕዝብ ጥቅም” ማለት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ሕዝቦች በመሬት ላይ ያላቸውን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥና የከተማ ልማትን በቀጣይነት ለማጎልበት የፀደቀ የከተማ ፕላን ተፈፃሚ በሚሆንበት ጊዜ ቻርተር ያለው ከተማ ወይም የከተማ አስተዳደር በዚህ አዋጅ መሠረት “የሕዝብ ጥቅም” ብሎ የሚወስነው ነው፤
6. “የክልል መንግሥት” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተቋቋመ የክልል መንግሥት ነው፤
7. “የከተማ አስተዳደር” ማለት ቻርተር ያላቸውን ከተሞች ሳይጨምር በሌሎች ከተሞች ውስጥ እንደ ማዘጋጃ ቤት ያለ የከተማ አስተዳደርና አገለግሎት እንዲሰጥ የተቋቋመና ራሱን የቻለ አስተዳደራዊ አካል ነው፤
8. “ከተማ” ማለት ማዘጋጃ ቤት የተቋቋመበት ወይም 2000 ወይም ከዚያ በላይ የሕዝብ ቁጥር ያለውና ከዚህ ውስጥ 50 ፐርሰንት የሚሆነው የሰው ኃይል ከግብርና ውጭ በሆነ ሥራ የተሰማራ ሆኖ የሚገኝበት አካባቢ ነው፤
9. “ሚኒስቴር” ማለት የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ነው፤[137]
10. “ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

[137] በ25/08 (2011) አ. 1097 አንቀጽ 9 (10) መሰረት የከተማ ልማት እና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

3. **የተፈጻሚነት ወሰን**

   1. ይህ አዋጅ በአገሪቱ ውስጥ በሚገኙ ከተሞች ሁሉ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
   2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ ቢኖርም የክልል መንግስታት የየአካባቢያቸውን ሁኔታ መሰረት በማድረግ አዋጁ ደረጃ በደረጃ ተፈጻሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ ሊወስኑ ይችላሉ፡፡

4. **አላማዎች**

   ይህ አዋጅ የሚከተሉት ዋና ዋና አላማዎች ይኖሩታል፤

   1. በፕላን የሚመሩና የዳበሩ ከተሞች እንዲኖሩ ለማድረግ የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ መመስረት፤
   2. በከተሞች ውስጥ የሚከናወኑ የልማት እንቅስቃሴዎችን በመቆጣጠርና በማመቻቸት የአገሪቱ የኢኮኖሚያዊ ዕድገት እንዲሻሻል ማድረግ፤

## ክፍል ሁለት

## የከተማ ፕላን ስለማመንጨት እና ስለማዘጋጀት

5. **መሠረታዊ መርሆዎች**

   በዚህ አዋጅ መሠረት ማናቸውም የከተማ ፕላን የሚመነጭበት እና የሚዘጋጅበት ሂደት የሚከተሉትን መሰረታዊ መርሆች መከተል ይኖርበታል፤

   1. የፕላኖች ተወረድ መጠበቅ፤
   2. በአንድ አገራዊ ራዕይና የመስፈርት ደረጃ እንዲሰራና ተፈጻሚነት ያለው ሆኖ መገኘት፤
   3. የከተሞች የርስበርስ ትስስርና የከተማና ገጠር ግንኙነት ግምት ውስጥ ገብቶ መገኘት፤
   4. ውጤታማ የመሬት አጠቃቀምን ታሳቢ አድርጎ የከተሞችን ወሰን መከለል፤
   5. የሕዝብ ተሳትፎ፤ ግልፅነት እና ተጠያቂነት እንዲኖር በማድረግ የህብረተሰቡ ፍላጎት መሟላቱን ማረጋገጥ፡፡
   6. የሕዝብ ስርጭት የተመጣጠነ እና ስብጥር ያለው እንዲሆን ማበረታታት፤
   7. የማሕበረሰብና የአካባቢ ደህንነት መጠበቅ፤
   8. የታሪካዊና የባህላዊ ቅርሶች እንክብካቤና ጥገና ማግኘት፤
   9. የህዝብና የግል ፍላጎቶች ተጣጥሞ መገኘት፤
   10. ዘላቂ ልማትን የሚያረጋግጥ ሆኖ መገኘት፤

6. **<u>የከተሞች ወሰን</u>**

   1. ከተሞች የራሳቸው የተለየ ወሰን ይኖራቸዋል፡፡
   2. የከተሞችን ወሰን ማስተካከል በሚያስፈልግበት ወቅት የሚመለከታቸው የክልል መንግሥታት ያስተካክላሉ፣ ቻርተር ያላቸው ከተሞችም ወሰን በቻርተሩ ላይ ይመለከታል፡፡
   3. አንድ ከተማ በዚህ አንቀጽ እንደተመለከተው የራሱ የሆነ ወሰን ቢኖረውም አካባቢውን ይዞ እንዲለማ ለማድረግ ሲባል አግባብ ባለው የመንግሥት አካል የዕድገት ማእከል ሆኖ ሊመረጥና ዕውቅና ሊሰጠው ይችላል፡፡

7. **<u>የፕላኖች ደረጃ</u>**

   አገር አቀፍና ክልል አቀፍ በሆኑ የልማት ስትራተጂና እቅዶች ላይ ተመስርቶ የሚከተለው የፕላን ደረጃ ይኖራል፣

   1. ብሔራዊ የከተማ ልማት እቅድ፣
   2. ክልላዊ የከተማ ልማት ፕላን፣
   3. የከተማ ፕላን፡፡

8. **<u>የከተማ ፕላን ዓይነቶች</u>**

   የሚከተሉት የከተማ ፕላን ዓይነቶች በዚህ አዋጅ መሠረት እውቅና አግኝተዋል፣

   1. ከተማ አቀፍ መዋቅራዊ ፕላን፣ እና
   2. የአካባቢ ልማት ፕላን፡፡

9. **<u>የመዋቅራዊ ፕላን ትርጓሜና ይዘት</u>**

   1. መዋቅራዊ ፕላን በአጠቃላይ በአንድ ከተማ ክልል ደረጃ የተዘጋጀና የተነደፈ ሆኖ በማሕበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በአካባቢ ዘርፎች የተመጣጠነ የከተማ ልማት ለማስገኘት የሚያስችል ፊዚካላዊ እድገትን አስመልክቶ መኖር የሚገባቸውን መሰረታዊ ጉዳዮች የሚዘረዝርና ሕጋዊ ተፈፃሚነት ያለው ፕላን ሲሆን አባሪ የፅሑፍ ማብራሪያዎችን ይጨምራል፡፡
   2. ማንኛውም መዋቅራዊ ፕላን በዋነኛነት የሚከተሉትን ማመልከት አለበት፣

      ሀ) ከተማው የሚያድግበትን መጠንና አቅጣጫ፣

      ለ) ዋና ዋና የመሬት አጠቃቀም ምድቦች፣

      ሐ) የቤቶችን ልማት፣

መ) ዋና ዋና ማህበራዊና ፊዚካላዊ የመሰረተ ልማት አውታሮች የሚዘረጉበትንና የሚደራጁበትን ሥርዓት፤

ሠ) መልሶ የማልማት እርምጃን የሚጠይቁ የከተማውን አካባቢዎች፤

ረ) የአካባቢ ጥበቃ ነክ ጉዳዮችን፤

ሰ) የኢንዱስትሪ ዞንን፡፡

3. መዋቅራዊ ፕላን ተቋማዊ አደረጃጀትን፣ ሃብትንና የህግ ማዕቀፍን ያካተተ የአፈፃፀም እቅድ ይኖረዋል፡፡።

10.**<u>መዋቅራዊ ፕላን ፀንቶ ስለሚቆየበት ጊዜ</u>**

ማንኛውም መዋቅራዊ ፕላን ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ እስከ 10 አመት ፀንቶ የሚቆይ ይሆናል፡፡

11.**<u>የአካባቢ ልማት ፕላን ትርጓሜና ይዘት</u>**

1. የአካባቢ ልማት ፕላን በስትራቴጂያዊ አካባቢዎች ላይ በማተኮር አንድን የከተማ ክልል ለማሻሻል፣ ለማደስና ለማስፋፋት በመካከለኛ የዕቅድ ዘመን በጊዜ እየተከፋፈሉና እየተቀናጁ የሚከናወኑ የልማት ሥራዎችን የሚያሳይና የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ሕጋዊ ተፈጻሚነት ያለው የከተማ ፕላን ነው፡፡
2. የአካባቢ ልማት ፕላን የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ዋና ዋና ተግባራትን፣ የልማት ግቦችን፣ ማስፈጸሚያ ስልቶችን፣ የፈጻሚ አካላት ሚናን፣ ተፈላጊ ተቋሞችን፣ የአካባቢ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴን፣ የከተማ ዲዛይን መርሆችን፣ ተጨባጭ መስፈርቶችን፣ የአካባቢን ማዕቀፍ፣ በጀት እና ጊዜን በዝርዝር የሚያሳይ ይሆናል፡፡
3. ማንኛውም የአካባቢ ልማት ፕላን እንደየ አግባብነታቸው የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፤

ሀ) የመሬት አጠቃቀሙን አይነት ዞናዊ አመዳደብ፣ የሕንፃ ከፍታና የጥግግት መጠን፤

ለ) የአካባቢ መንገዶችና ዋና ዋና የመሠረተ ልማት አውታሮችን፤

ሐ) የትራንስፖርት ስርዓቱን አደረጃጀት፤

መ) የቤቶችን ዓይነትና የመንደሮችን አደረጃጀት፤

ሠ) የከተማ ማደስ፣ ማሻሻልና እንደገና መደልደል የሚጠይቁ የከተማውን አካባቢዎች፣

ረ) አረንጓዴ ቦታዎችን፣ ክፍት ቦታዎችን፣ የውሃ አካላትንና እንዲሁም ለጋራ አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉ ቦታዎችን፣

ሰ) አግባብነት ያላቸውን ሌሎች የአካባቢ ፕላን ነክ ጉዳዮችን፡፡

4. የአካባቢ ልማት ፕላን ለአፈጻጸሙ አስፈላጊ የሆኑትን ተቋማዊ አደረጃጀቶች፣ ሃብትና የመቆጣጠሪያ ድንጋጌዎች ያካተተ ዝርዝር የአፈጻጸም እቅድ ይኖረዋል፡፡

12.<u>የማስፈጸሚያ ጊዜ</u>

የአካባቢ ልማት ፕላን ተፈፃሚ የሚደረገው መዋቅራዊ ፕላኑ ፀንቶ በሚቆየበት ጊዜ ውስጥ ይሆናል፡፡

13.<u>የከተማ ፕላኖችን ስለማመንጨት</u>

1. መሟላት የሚገባቸው ፍላጎቶች ተለይተው ከመታወቃቸው አስቀድሞ ማናቸውም የከተማ ፕላን ዝግጅት መጀመር የለበትም፡፡

2. የሚመለከተው ማንኛውም መንግሥዊም ሆነ መንግሥታዊ ያልሆነ አካል በከተማ ፕላን ዝግጅት ወቅት ሊታይና ሊሟላ ይገባል የሚለውን ፍላጎት በደንብ በሚወሰነው ሁኔታና ሥርዓት መሠረት የማመንጨት መብት አለው፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የከተማ ፕላን የማመንጨት ሂደት ሊጀመር የሚችለው በሚመለከታቸው ቻርተር ባላቸው ከተሞችና የከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም በሚመለከታቸው የክልልና የፌዴራል አካላት አማካኝነት ይሆናል፡፡

14.<u>የከተማ ፕላኖችን የማዘጋጀትና የመከለስ ሥልጣንና ተግባር</u>

በማንኛውም ደረጃ ላይ የሚገኙ ከተሞች መዋቅራዊና የአካባቢ ፕላኖቻቸውን የማዘጋጀትና የመከለስ ወይም በተመሰከረላቸው የግል ወይም የመንግሥት ተቋማት እንዲዘጋጁላቸው ወይም እንዲከለሱላቸው የማድረግ ሥልጣንና ተግባር አላቸው፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

<u>ክፍል ሦስት</u>

<u>ፕላን ስለማጽደቅ፣ ስለማስተዋወቅ፣ ስለማስፈጸምና ስለማሻሻል</u>

15.<u>የሕዝብ ውይይት</u>

1. ፕላን ከመፅደቁ በፊት አመቺ በሆነ ስፍራ ሕዝቡ እንዲወያይበት ይደረጋል፡፡

2. የፕላን ዝግጅት ሂደቶቹና ውይይቶቹ ለጠቅላላው ሕዝብ በተለይም ለቀበሌ ምክር ቤቶችና ለሕዝባዊ ማህበራት ግልጽ እንዲሆኑና በበቂ ሁኔታ እንዲደርሱ ይደረጋል፡፡
3. አግባብነት ያላቸው ሃሳቦችና ተቃውሞዎች ፕላኑን ለማስተካከል እንደግብዓት ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

16.<u>የከተማ ፕላን ስለማጽደቅ</u>

1. የከተሞች መዋቅራዊና የአካባቢ ልማት የመጨረሻ ረቂቅ ፕላኖች በየከተሞቹ ምክር ቤቶች ውይይት ከተደረገባቸው በኋላ እንዲፀድቁና ለሚመለከታቸው የክልል ወይም የፌዴራል አካላት እንዲደርሱ ይደረጋል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም እንደአግባቡ የክልል መንግሥት ወይም የፌዴራሉ መንግሥት ከዚህ አዋጅ ከተደነገጉት መሠረታዊ መርሆዎች ጋር የማይጣጣም ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ የጸደቀ የከተማ ፕላንን የማገድ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

17.<u>የጸደቁ ፕላኖችን ስለማስተዋወቅ</u>

1. ቻርተር ያላቸው ከተሞችና የከተማ አስተዳደሮች ማንኛውንም የመገናኛ ዘዴ በመጠቀም የጸደቁ የመዋቅራዊና የአካባቢ ልማት ፕላኖችን ለሕዝብ በስፋት ያስተዋውቃሉ፡፡
2. በተጨማሪም የጸደቁ ፕላኖችን ፍላጎቱ ላላቸው ወገኖች እንዲደርሱ ያደርጋሉ፡፡

18.<u>የከተማ ፕላንን ስለማስፈጸም</u>

የከተማ ፕላን አፈፃፀም ግልጽ በሆነ የማስፈጸሚያ ስትራቴጂ፣ ደንቦችና መመሪያዎች እንዲሁም በተደራጀ አስፈፃሚ አካል የተደገፈ ይሆናል፡፡

19.<u>ስለከተማ ፕላን አፈፃፀም ኃላፊነት</u>

እያንዳንዱ ቻርተር ያለው ከተማ ወይም የከተማ አስተዳደር የፀደቀውን መዋቅራዊና የአካባቢ ልማት ፕላን ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ መሠረት የማስፈጸም ኃላፊነት አለበት።

20.<u>ፕላን የማስፈፀም ሥልጣን</u>

ማንኛውም ቻርተር ያለው ከተማ ወይም የከተማ አስተዳደር የከተማ ፕላንን በማስፈጸም ረገድ የሚከተለው ሥልጣን ይኖረዋል፤

1. ከመዋቅራዊና ከአካባቢ ልማት ፕላን ጋር የሚፃረሩ የልማት እንቅስቃሴዎችን የመቆጣጠርና የማስቆም፤
2. ካሣ በመክፈል የከተማ መሬት ይዞታን የማስለቀቅ፤
3. ፕላኑን ለማስፈጸም ባስፈለገ መጠን በፕላኑ ክልል ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የመንግሥት መስሪያ ቤቶችን፣ የልማት ድርጅቶችን፣ የአገልግሎት ሰጪ ተቋሞችን፣ የግል ድርጅቶችንና የሌሎች ያገባናል ባዮች እንቅስቃሴዎችን የማስተባበር፡፡

21.<u>ስለካሳ ክፍያ</u>

የከተማ ፕላን ለማስፈጸም ሲባል የከተማ መሬት ይዞታውን እንዲለቅ የተደረገ ማንኛውም ባለይዞታ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ካሣ ይከፈለዋል፡፡

22.<u>የከተማ ፕላኖችን ስለማሻሻልና ስለማስተካከል</u>

1. ማናቸውም የፀደቀ የከተማ ፕላን ፀንቶ የሚቆይበት ወይም የሚተገበርበት ጊዜ እንዳለቀ እንዲሻሻል ይደረጋል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የከተማ ፕላን ፀንቶ የሚቆይበት ወይም የሚተገበርበት ጊዜ ከማለቁ በፊት ሊሻሻል ይችላል።
3. የፀደቁ የከተማ ፕላኖች አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ የአንድን ከተማ ክፍል በሚመለከት ሊሻሻሉ ይችላሉ።

23.<u>የከተማ ፕላን የማሻሻልና የማስተካከል ሥልጣንና ተግባር</u>

ከተሞች ፕላኖቻቸውን የማሻሻልና የማስተካከል ወይም እንዲሻሻሉላቸውና እንዲስተካከሉላቸው የማድረግ ሥልጣንና ተግባር ይኖራቸዋል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልማትን ስለመፍቀድ</u>

24.<u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ “ልማት” ማለት በመሬት ላይ ወይም ከመሬት በታች የሚካሄድ የግንባታ፣ የምህንድስና፣ የማዕድን ወይም ሌላ ሥራ ወይም በማናቸውም መዋቅሮች ወይም መንደሮች የአገልግሎት ዘመን ላይ የሚደረግ ከፍተኛ ለውጥ ነው።

25.<u>ክልከላ</u>

1. አስቀድሞ የልማት ፈቃድ ካልተሰጠ በስተቀር በከተማ ውስጥ የልማት እንቅስቃሴ ማከናወን የተከለከለ ነው፡፡
2. ቻርተር ያላቸው ከተሞች ወይም የከተማ አስተዳደሮች ማናቸውም የልማት እንቅስቃሴ ያለልማት ፈቃድ በከተማ ክልል ውስጥ በሚከናወንበት ጊዜ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳሉ፡፡

26.<u>መሠረታዊ መርሆች</u>

በማንኛውም የልማት ሥራ ፈቃድ የመስጠት ሂደት የሚከተሉት መሠረታዊ መርሆዎች መከበር ይኖርባቸዋል፤

1. ቆጣቢና ዘላቂነት ያለው የመሬት አጠቃቀምን ማረጋገጥ፤
2. በአካባቢ ላይ የጎላ አሉታዊ ተጽእኖ ይኖራቸዋል ተብለው የሚገመቱ የልማት ፕሮጀክቶች በአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ጥናት መደገፋቸውን ማረጋገጥ፤
3. መሬት ለልማት በሚቀርብበት ወቅት በከተማው ፕላን መሠረት ተፈላጊ የመሠረተ ልማት አውታሮች እንዲሟሉለት ማድረግ፡፡

27.<u>የልማት ፈቃድ ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>

በአንድ ከተማ ውስጥ በልማት እንቅስቃሴ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም አልሚ ፈቃድ እንዲሰጠው ማመልከት አለበት፡፡

28.<u>የልማት ፈቃድ ስለመስጠት</u>

1. የሚመለከተው ቻርተር ያለው ከተማ ወይም የከተማ አስተዳደር የልማት ሥራ ፈቃድ መርሆዎችን መሠረት በማድረግ ያወጣቸውን ተፈላጊ መመዘኛዎች መሟላታቸውን አረጋግጦ የልማት ፈቃድ ይሰጣል፡፡
2. እንደ ሕንፃ ፈቃድ ያለ ተጨማሪ ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው የልማት ሥራዎች በፈቃድ አወጣጡ ሂደት ውስጥ በመዋሃድ እንደ አንድ ፈቃድ ሆነው ለአልሚው ይሰጣሉ፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

29.<u>የልማት ፈቃድ ጥያቄ ተቀባይነት ስለሚያጣበት ሁኔታ</u>

የልማት ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ ከዚህ በታች ከተመለከቱት ምክንያቶች በአንዱ ተቀባይነት ሊያጣ ይችላል፤

1. የቀረበው የልማት ዕቅድ ከፀደቀው የከተማው ፕላን ጋር የማይጣጣም ሆኖ ሲገኝ፤

2. የታቀደው ልማት በአካባቢውና በጠቅላላው ነዋሪ ህዝብ ላይ አሉታዊ ጫና ሊኖረው ይችላል ተብሎ ሲታመን፤
3. ልማቱ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ሕግ ከተደነገገ ማናቸውም ሌላ አስፈላጊ ሁኔታ ጋር ያልተጣጣመ መሆኑ ሲታወቅ።

30.<u>ፈቃድ ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ</u>

በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የሚሰጥ የልማት ፈቃድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ቻርተር ባለው ከተማ ወይም የከተማ አስተዳደር ይወሰናል፡፡

31.<u>የልማት ፈቃድን ስለማገድ</u>

1. ለማናቸውም አልሚ የተሰጠ የልማት ፈቃድ ያንኑ ፈቃድ በሰጠው ቻርተር ያለው ከተማ ወይም የከተማ አስተዳደር ካልሆነ በስተቀር በማንኛውም ሌላ አካል ሊታገድ አይችልም፡፡
2. የዚህ አይነቱን እገዳ የሚያስከትሉት ምክንያቶችና እገዳው የሚፈጸምባቸው ሁኔታዎች በሕግ ይወሰናል፡፡

32.<u>ስለ ማፍረስ ፈቃድ</u>

1. በማናቸውም ከተማ ክልል የሚከናወን መዋቅሮችን ወይም መንደሮችን የማፍረስ እንቅስቃሴ ፈቃድ፣ እንዲኖረው ያስፈልጋል፡፡
2. ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የክልል ወይም የፌዴራል መንግሥት አካላት በቅድሚያ የጽሁፍ ስምምነት ካልተገኘ በስተቀር በባህሪያቸው ለየት ያሉ መዋቅሮችን ለማፍረስ የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
3. ፈቃዱ የሚስጥባቸውም ሆነ የሚከለከልባቸው ሁኔታዎች፣ ስርአቶችና የአገልግሎት ክፍያዎች ዝርዝር በህግ ይወሰናል፡፡

33.<u>ስለ ተስማሚነት የምስክር ወረቀት</u>

1. አልሚው በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት የሚመለከተው ቻርተር ያለው ከተማ ወይም የከተማ አስተዳደር በሚሰጠው የተሰማሚነት የምስክር ወረቀት የልማት ፈቃድ የሚጠይቃቸው ሁኔታዎች መከበራቸው ይረጋገጣል፡፡
2. የተስማሚነት ምስክር ወረቀት የሚሰጥባቸውም ሆነ የሚከለክልባቸው ሁኔታዎችና ሥርዓቶች በሕግ ይወሰናሉ፡፡

34.<u>ስለ አገልግሎት ክፍያዎች</u>

ቻርተር ያለው ከተማ ወይም የከተማ አስተዳደር የልማት ወይም የማፍረስ ፈቃድ እንዲሁም የተስማሚነት የምስክር ወረቀት ለመስጠት ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ ሊያስከፍል ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፡፡

**ክፍል አምስት**

**ስለ ቦታ መረጃ**

35. ***የቦታ መረጃ የማግኘት መብት***

ፍላጎት ያለው ማንኛውም ወገን በአንድ ከተማ የስልጣን ክልል ውስጥ የሚገኝ ክፍለ ቦታ ስለሚለማበት ሁኔታ መረጃ የማግኘት መብት አለው፡፡

36. ***ስለ ቦታ መረጃ የምስክር ወረቀት***

1. በከተሞች የሥልጣን ክልል ውስጥ ስለሚገኝ ክፍለ ቦታ ጥያቄ ሲቀርብ የቦታ መረጃ የምስክር ወረቀት ሊሰጥ ይችላል፡፡
2. ማንኛውም የቦታ መረጃ የምስክር ወረቀት የሚከተሉትን ዝርዝሮች መያዝ ይኖርበታል፤
   ሀ) በከተማ ፕላን ደንቦችና በቦታ አጠቃቀም ረገድ ተፈላጊው ክፍለ ቦታ የሚገኝበት ሁኔታ፤
   ለ) በወቅቱ ያሉና ለወደፊቱ የሚታሰቡ የሕዝብ አገልግሎት መስጫ አውታሮች ይዞታና እነዚህን ለማሟላት የተጣሉ ግዴታዎች ሁኔታ፤
   ሐ) በክፍለ ቦታው ላይ ተፈጻሚነት ካለው የግብር አይነት ወይም ኪራይ ጋር የተያያዘ መረጃ፤
   መ) የአፈር አይነት፣ የመሬት መንቀጥቀጠና የጎርፍ አደጋ እንዲሁም ተፈላጊውን መረጃ ማግኘት እስከተቻለ ድረስ የክፍለ ቦታው ሌሎች አስፈላጊ ዝርዝሮች፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም በደህንነት ቀጠናነት የተከለሉና በደንብ የሚዘረዘሩ ሌሎች አካባቢዎችን አስመልክቶ የቦታ መረጃ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

37. ***የቅድሚያ ስምምነት ስለማስፈለጉ***

የአውሮፕላን ማረፊያዎችና ሌሎች ብሔራዊና አለም አቀፋዊ የመሠረተ ልማት አውታሮች፣ የባሕላዊ ቅርስ አካባቢዎች፣ የአርኪዮሎጂና የቱሪዝም መስህብ ስፍራዎች

የሚገኙበትን የከተማ ቦታ በሚመለከት የሚጠየቅ የቦታ መረጃ ምስክር ወረቀት አግባብ ካላቸው አካላት የጽሁፍ ስምምነት ካልተገኘ በስተቀር ሊሰጥ አይችልም፡፡

## 38. የምስክር ወረቀት ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ

የቦታ መረጃ የምስክር ወረቀት በሕጉ ለሚወሰን ጊዜ ፀንቶ ይቆያል፡፡

## 39. ስለአገለግሎት ክፍያዎች

ቻርተር ያለው ከተማ ወይም የከተማ አስተዳደር የቦታ መረጃ የምስክር ወረቀቶችን አዘጋጅቶ በሚስጥበት ጊዜ ተገቢውን ክፍያ ሊያስከፍል ይችላል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ከተማን መልሶ ስለማልማትና ስለ ልዩ ልዩ ገጽታዎቹ

## 40. ስለመልሶ ማልማት ወሰን

1. በዚህ አዋጅ መሠረት ከተማን መልሶ የማልማት ተግባር ማለት ከተማ ነክ ችግሮችን ለማቃለል፣ የኑሮ ደረጃን ለማሻሻልና የተፋጠነ የከተማ ለውጥና ብቃት ያለው የመሬት አጠቃቀምን ለማስገኘት ታስቦ የሚፈፀም ሲሆን የከተማ እድሳትን፣ ማሻሻልንና የመሬት እንደገና ድልደላን ያካትታል፡፡
2. ከተሞች የአስተዳደሮቻቸውን፣ የነዋሪዎቻቸውንና የአልሚዎቻቸውን ተነሳሽነት ተከትለው መዋቅራዊና የአካባቢ ልማት ፕላኖችን መሠረት በማድረግ እንደገና እንዲለሙና እንዲያንሰራሩ ይደረጋሉ፡፡

## 41. ከተማን ስለማደስ

በዚህ አዋጅ መሰረት ከተማን የማደስ ተግባር በአንድ ከተማ ውስጥ የሚታዩትን የፈራረሱ፣ ያረጁና የተተው መዋቅሮችን በከፊል ወይም በሙሉ በማስወገድ ምቹ የመኖሪያና የሥራ አካባቢ በማድረግ አላማ ላይ አተኩሮ የሚፈጸም ተግባር ነው፡፡

## 42. የከተማ እድሳትን ስለማከናወንና መምራት

1. የከተማ እድሳት በመዋቅራዊና የአካባቢ ልማት ፕላን ላይ በተመለከተው አካባቢ ማእቀፍ ላይ ተመስርቶና በበቂ ምክንያት ተደግፎ የሚታቀድና የሚፈጸም ይሆናል፡፡
2. የከተማ እድሳት ይከናወንበታል ተብሎ በታሰበ አካባቢ የሠፈሩ ነዋሪዎች እድሳቱ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በቅድሚያ ስለሁኔታው እንዲያውቁና እንዲመክሩበት ይደረጋል፡፡

3. የከተማ እድሳት የሚካሄደውና የሚመራው እንደ አግባቡ የክልልና የፌዴራል መንግሥታትን በማማከር፣ ከክልሎች ፈቃድ በማግኘትና ለጉዳዩ የሚገባውን ጥንቃቄ በማድረግ ቻርተር ባላቸው ከተሞች ወይም የከተማ አስተዳደሮች ኃላፊነት ይሆናል።
4. የከተማ እድሳት በሥራ ላይ የሚውልባቸው ሁኔታዎችና ሥርዓቶች በሕግ ይወሰናሉ፡፡

43. ከተማን ስለማሻሻል

በዚህ አዋጅ መሠረት ከተማን የማሻሻል ተግባር በአንድ ከተማ ውስጥ የሚታዩትን ዝቅተኛ ደረጃ ያላቸው መዋቅሮች በማደስና በከፊል በማስወገድ እንዲሁም የመሠረተ ልማትና ሌሎች አገልገሎት መስጫ አውታሮችን በመዘርጋት ወደምቹ ወይም ወደተሻለ የመኖሪያና የመሥሪያ አካባቢነት የማሻሻል ርምጃ ነው፡፡

44. የከተማ ማሻሻልን ስለማከናወን እና መምራት

1. የከተማ ማሻሻል መዋቅራዊና የአካባቢ ፕላንን በመከተል በሚመለከታቸው ቻርተር ባላቸው ከተሞች ወይም የከተማ አስተዳደሮች የሚፈጸምና የሚመራ ይሆናል፡፡
2. የከተማ ማሻሻል ተግባር የሚከናወነው የአካባቢ ገጽታን ለማሻሻል ብቻ ሳይሆን የነዋሪዎቹን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ለማሳደግ ጭምር ይሆናል፡፡
3. ከተማ የማሻሻል ሥራ የሚከናወንባቸው ሁኔታዎችና ሥርዓቶች በሕግ ይዘረዘራሉ፡፡

45. ቦታን እንደገና ስለመደልደል

1. በዚህ አዋጅ መሠረት ቦታን እንደገና የመደልደል ተግባር በተደራሽነት፣ በመጠን፣ በአቀማመጥና በዋና ዋና የመሠረተ ልማት አውታሮች አቅርቦት ረገድ የተመቻቹ ሆነው ውጤታማና ቆጣቢ የመሬት አጠቃቀምን የሚያረጋግጡ ቦታዎችን ለማስገኘት ሲባል ክፍለ ቦታዎችን የመከፋፈልና የማስተካከል ተግባር ነው፡፡
2. የመሬት ሀብትን በተሻለ ደረጃ ለሕዝብ ጥቅም ለማዋል ዓላማ ካልሆነ በስተቀር የከተማ ቦታን እንደገና የመደልደል ተግባር አይከናወንም፡፡

46. ተጣጥሞ ስለመገኘት

በተግባር ላይ እንዲውል የታሰበ ማናቸውም ቦታን እንደገና የመደልደል እቅድ ከከተማው የቦታ አጠቃቀም ፕላን ጋር ተጣጥሞ መገኘት ይኖርበታል፡፡

47. ቦታን እንደገና መደልደልን ስለማከናወንና መምራት

1. ቦታን እንደገና የመደልደል ተግባር የሚከናወነውና የሚመራው ጉዳዩ በሚመለከታቸው ቻርተር ያላቸው ከተሞች ወይም የከተማ አስተዳደሮች ይሆናል፡፡
2. ቦታ እንደገና የሚደለደልባቸው ዝርዝር ሁኔታዎችና ሥርዓቶች በሕግ ይወሰናሉ፡፡

## ክፍል ሰባት

## ልማትን ለጊዜው ስለማስቀምና ቦታ ስለሚገኝበት ሁኔታ

### 48. ልማትን ለጊዜው ስለማስቀም

በዚህ አዋጅ መሠረት ልማትን ለጊዜው የማስቀም ድርጊት የአንድ ከተማ ፕላን በዝግጅት፣ በክለሣ ወይም በመሻሻል ላይ በሚገኝበት ወቅት ቻርተር ያለው ከተማ ወይም የከተማ አስተዳደር አንድን አካባቢ ወይም ክፍለ ቦታ የማልማቱ እንቅስቃሴ ለጊዜው እንዲቆም ለማድረግ የሚያስችለው ሕጋዊ እርምጃ ነው፡፡

### 49. ልማትን ለጊዜው የማስቀም እርምጃ ስለሚወሰድባቸው ሁኔታዎች

የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ቻርተር ያለው ከተማ ወይም የከተማ አስተዳደር ማናቸውንም የልማት እንቅስቃሴ ለጊዜው የማስቀም ስልጣን ይኖረዋል፣

1. የማልማት ወይም የማፍረሱ ተግባር በዝግጅት፣ በክለሳ ወይም በመሻሻል ላይ የሚገኝ ማናቸውንም የከተማ ፕላን በሥራ ላይ እንዳይውል የማሰናከል ውጤት ይኖረዋል ተብሎ የተገመተ እንደሆነ፣
2. በመካሄድ ላይ የሚገኝ ልማት የአንድን ንብረት ዋጋ በማናር ለወደፊቱ የመሬት አጠቃቀም ለውጥ ቢያጋጥም ሊከተል የሚችለውን መሬት የማስለቀቅ እርምጃ እንደሚያውክ ከወዲሁ የተገመተ እንደሆነ፡፡

### 50. ክልከላ

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የልማት ሥራ ለጊዜው እንዲቆም በተደረገባቸው አካባቢዎች ውስጥ ለማናቸውም እንቅስቃሴ የልማትም ሆነ የማፍረስ ፈቃድ ሊሰጥ አይችልም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ሥር የተደነገገው ቢኖርም እንዲህ ያለው የልማት እንቅስቃሴ በዝግጅት፣ በክለሣ ወይም በመሻሻል ላይ ያለን የአንድ ከተማ ፕላን ተፈጻሚነት ለዘለቄታው በከፍተኛ ደረጃ የማያውክና በጣም አስፈላጊ መሆኑ ሲታመንበት ቻርተር ያላቸው ከተሞች ወይም የከተማ አስተዳደሮች የተጠየቀውን

የልማት ፈቃድ ሊሰጡ ወይም ቀደም ብሎ የተሰጠ ፈቃድ ተፈፃሚነት እንዲቀጥል ሊፈቅዱ ይችላሉ፤ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

51. ***ተፈጻሚነቱ ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ***

በደንብ የሚወሰነው ከፍተኛ የጊዜ ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም የልማት ሥራዎችን ለጊዜው የማስቆም እርምጃ ተፈፃሚ የሚሆነው የሚመለከተው የከተማ ፕላን ዝግጅት፣ ክለሳ ወይም ማሻሻል ሥራ እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ ይሆናል፡፡

52. ***መሬት ስለሚገኝበት ሁኔታና ስለመጠባበቂያ ይዞታ***

በማንኛውም ደረጃ ላይ ያሉ ከተሞች በዚህ አዋጅ መሠረት፤

1. በሥልጣን ክልላቸው ውስጥ ለሕዝብ ጥቅም የሚውል መሬት የማግኘትና መጠባበቂያ የመያዝ፣
2. ንብረት ማስለቀቅና ማፍረስን ለመቀነስ ሲባል በከተማ ፕላን ዝግጅት ወቅት መሬትን ለይቶ በመጠባበቂያነት የመያዝ መብትና ግዴታ ይኖራቸዋል፡፡

53. ***ስለመጠባበቂያ ቦታ ምድቦች***

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚያዝ የመጠባበቂያ ቦታ የሚከተሉት ምድቦች ይኖሩታል፤

1. የሕዝብ ጥቅምን ለሚመለከት ልማት የሚውል ወይም ለዚሁ አላማ ታስቦ የሚያዝ ቦታ፤
2. በከተማ ፕላን ዝግጅት ጊዜ ላልታዩና በአፈፃፀሙ ወቅት ለሚያጋጥሙ ሁኔታዎች የሚያዝ ቦታ፡፡

54. ***መሬት ስለሚገባቸውና መጠባበቂያ ስለሚያዝባቸው ሁኔታዎች***

ቻርተር ያላቸው ከተሞች ወይም የከተማ አስተዳደሮች ለሕዝብ ጥቅም የሚውል መሬት ለማግኘትና በመጠባበቂያነት ለመያዝ በሚፈልጉበት ጊዜ አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ባለይዞታዎችን ለማስለቀቅ ያላቸውን መብት ሊገለገሉበት ይችላሉ፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወስናል፡፡

## ***ክፍል ስምንት***

## ***ሥልጣንና ተግባራትን ስለማደላደል***

55. ***የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር***

የዚህን አዋጅ አፈፃፀም በሚመለከት ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. ከሚመለከታቸው የፌዴራል መንግሥት አካላት ጋር በመተባበር ብሔራዊ የከተማ ልማት እቅድ ያዘጋጃል፤
2. የከተማ ፕላኖች ከዚህ አዋጅ ጋር የሚጣጣሙ ስለመሆናቸው ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ በአገሪቱ ውስጥ የተመጣጠነና የተቀናጀ የከተማ ልማት መኖሩን ያረጋግጣል፤
3. ለክልል ከተሞችና ለፌዴራል መንግሥት ተጠሪ ለሆኑ ከተሞች የከተማ ፕላንን በሚመለከት የቴክኒክና የአቅም ግንባታ ድጋፍ ያደርጋል፤
4. የልማት አፈ.ቃቀድ ደንቦችን አጠቃላይ ተፈፃሚነት በብሔራዊ ደረጃ ይከታተላል፣ ይገመግማል፤
5. የከተማ ፕላንን የሚመለከቱ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ ፍላጎቱ ያላቸው ወገኖች እንዲያገኟቸው ያደርጋል፤
6. ለአማካሪዎች ፈቃድና ደረጃ ለመስጠት የሚረዱ መመዘኛዎችን ያዘጋጃል፤ በከተማ ፕላን አዘገጃጀት ሥራ ለሚሰማሩና በደረጃ አንድ ላይ ለሚመደቡ አማካሪዎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

## 56. የክልል መንግሥታት ሥልጣንና ተግባር

የዚህን አዋጅ አፈፃፀም በሚመለከት የክልል መንግሥታት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሯቸዋል፤

1. ከብሔራዊ የከተማ ልማት ዕቅድ የተጣጣሙ ክልል አቀፍ የከተማ ዕቅዶችን ማመንጨትና ማዘጋጀት፤
2. የከተማ ፕላኖች በአግባቡ ስለመፈፀማቸው ይከታተላሉ፤ ይገመግማሉ፤ ያረጋግጣሉ፤
3. ለክልሉ ልማት የጎላ ጠቀሜታ የሚኖራቸውን ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ከተሞችን የልማት ጥረቶች ያስተባብራሉ፤ ያቀናጃሉ፡፡

## 57. ለፌደራል መንግሥት ተጠሪ የሆኑ ከተሞች ሥልጣንና ተግባር

የዚህን አዋጅ አፈፃፀም በሚመለከት ለፌዴራል መንግሥት ተጠሪ የሆኑ ከተሞች የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሯቸዋል፤

1. እንደየአግባቡ ከክልልና ከአገር አቀፍ የከተማ ልማት እቅዶች ጋር የተጣጣሙ ከተማ አቀፍ መዋቅራዊና የአካባቢ ልማት ፕላኖችን ያዘጋጃሉ፣ ወይም እንዲዘጋጁ ያደርጋሉ፣ ይፈጽማሉ፤

2. የከተማ ፕላኖች በአግባቡ ስለመፈጸማቸው ይከታተላሉ፣ ይገመግማሉ፣ ያረጋግጣሉ፤
3. በሥልጣን ክልላቸው ውስጥ የሚከናወኑትን የልማት ተግባራት ይመራሉ፣ ይቆጣጠራሉ፤
4. የከተማ ቦታንና በላዩ ላይ የሚገኘውን የማይንቀሳቀስ ንብረት አስመልክቶ አስተማማኝና በስርአት የተደራጀ መረጃ እንዲኖር ያደርጋሉ፣ ጥያቄ ሲቀርብላቸውም መረጃ ይሠጣሉ፡፡

58. <u>ቅጣት</u>

1. ማናቸውም ሰው በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ያልተዘጋጁ ፕላኖች አግባብ ባላቸው አካላት ከመጽደቃቸው በፊት፣ ወይም በሚያጸድቀው አካል ማስተካከያ እንዲደረግባቸው የተወሰኑ ወይም እንዲታገዱ ወይም ለጊዜው እንዲቆሙ ውሳኔ የተሰጠባቸው ፕላኖች በሚመለከተው አካል ሳይጸድቁ ወይም ተገቢው ማስተካከያ ሳይደረገባቸው ተግባራዊ እንዲሆኑ ፈቃድ የሰጠ ወይም ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደረገ እንደሆነ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ በሚወሰነው መሰረት ይቀጣል፡፡
2. በዚህ አዋጅ የተመለከቱት እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም የልማት ፈቃድ ለመስጠት አግባብ ካለው አካል የልማት ፈቃድ ሳይሰጠው ማንኛውም የልማት ሥራ የሚያከናውን ሰው ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ በሚወሰነው መሠረት ይቀጣል፡፡

## <u>ክፍል ዘጠኝ</u>
## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

59. <u>የተሻረ ሕግ</u>

የከተሞች ፕላን አዘገጃጀትና አፈጻጸም አዋጅ ቁጥር 315/1979 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፤

60. <u>ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጐች</u>

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

61. **<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት 8 ቀን 2000 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## ክፍል ሃያ አምስት

## የከተማ ቦታና የገጠር መሬት አስተዳደር

## አዋጅ ቁጥር 1161/2011

## ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት፣ ካሣ የሚከፈልበት እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ አዋጅ

መንግስት ለሕዝብ አገልግሎት ለሚያከናውናቸው የልማት ሥራዎች መሬትን መጠቀም አስፈላጊ ስለሆነ፤

የአገሪቱ ከተሞች ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደጉና የነዋሪዎቹም ቁጥር እየጨመረ በመሄዱ በከተሞች ፕላን መሠረት ለመኖሪያ ቤት ግንባታ፣ ለመሠረተ ልማት፣ ለኢንቨስትመንትና ለሌሎች አገልግሎቶች የሚውል የከተማ መሬትን መልሶ ማልማት አስፈላጊ በመሆኑ፣ እንዲሁም በገጠር ለሚከናወኑ የልማት ሥራዎች መሬት አዘጋጅቶ ማቅረብ በማስፈለጉ፤

የመሬት ይዞታ እንዲለቅ ለተደረገ ባለይዞታ ተገቢና ተመጣጣኝ ካሣና የተነሽ ድጋፍ ለመክፈል ግምት ውስጥ መግባት የሚገባቸውን መሠረታዊ መርሆዎችን ለይቶ መወሰን በማስፈለጉ፤

ካሣውን የመተመን፣ የመክፈል እና ተነሺዎችን መልሶ የማቋቋም ሥልጣንና ኃላፊነት ያለባቸውን አካላት በግልጽ ለይቶ ለመወሰን በማስፈለጉ፤

በነባሩ ሕግ ያጋጠሙ የሕግ ክፍተቶችን ለማስተካከልና ሌሎች የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትን እና ካሣ የሚከፈልበት ሥርዓቱን ይበልጥ ውጤታማ የሚያደርጉ ድንጋጌዎችን ማካተት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ከይዞታ መነሳትና ካሳ ክፍያ ጋር ተያይዞ ስለሚኖር የቅሬታ አቀራረብና ውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት በግልጽ መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፤

የፌደራል መንግሥት የመሬት አጠቃቀም ሕግ የማውጣት ሥልጣን እንዳለው በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 51(5) በመደንገጉ፣

ለህዝብ ጥቅም ሲባል የሚለቀቅ ንብረትን በሚመለከት ተመጣጣኝ ካሣ በቅድሚያ እንዲከፈል በአንቀጽ 40(8) በመደንገጉ እንዲሁም ተነሺዎች በመንግስት ዕርዳታ እንዲቋቋሙ በአንቀጽ 44(2) የተቀመጠውን መሠረተ ሀሳብ በዝርዝር መደንገግ በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(2)(ሀ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

1. **አጭር ርእስ**

ይህ አዋጅ "ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት፣ካሣ የሚከፈልበት እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 1161/2011" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "የህዝብ ጥቅም" ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማትን ለማጎልበት የክልል ካቢኔ፤ የአዲስ አበባ፤ የድሬዳዋ ወይም አግባብ ባለው የፌደራል አካል በመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ወይም በልማት ዕቅድ ወይም በመሠረተ ልማት መሪ ፕላን መሠረት ለሕዝብ የተሻለ የጋራ ጥቅምና ዕድገት ያመጣል ተብሎ የተወሰ ነው፡፡
2. "የንብረት ካሣ" ማለት የመሬት ይዞታውን እንዲለቅ ለሚወሰንበት ባለይዞታ በመሬቱ ላይ ለሰፈረው ንብረት ወይም ላደረገው ቋሚ ማሻሻያ በዓይነት ወይም በገንዘብ ወይም በሁለቱም የሚከፈል ክፍያ ነው፡፡
3. "የልማት ተነሽ ካሣ" ማለት ባለይዞታው የመሬት ይዞታውን ሲለቅ በመሬቱ ላይ የመጠቀም መብቱ በመቋረጡ ምክንያት የሚደርስን ጉዳት ለማካካስ የሚከፈል ክፍያ ነው፡፡
4. "የልማት ተነሽ ድጋፍ" ማለት የመሬት ባለይዞታ ከመሬቱ በጊዜያዊም ሆነ በቋሚነት ሲነሳ ከአዲሱ አካባቢ ጋር መላመድ እንዲችል ከንብረት እና ከልማት ተነሽ ካሣ በተጨማሪ በዓይነት ወይም በገንዘብ የሚሰጥ ድጋፍ ነው፡፡
5. "የኢኮኖሚ ጉዳት ካሣ" ማለት ከቦታቸው ያልተነሱ ነገር ግን መሬት ለሕዝብ ጥቅም በመለቀቁ ምክንያት በመቀጠር ወይም በመነገድ ወይም በማከራየት እና ከመሳሰሉት ያገኙት የነበረ ገቢ በመቋረጡ ለሚደርስ ጉዳት የሚከፈል ካሣ ነው፡፡
6. "የማህበራዊ ትስስር መቋረጥና ሥነ-ልቦና ጉዳት ካሣ" ማለት ለተነሺ ከነበረበት አካባቢ በመነሳቱ የነበረው ማህበራዊ ትስስር በመቋረጡ የሚከፈል የማህበራዊ ትስስር መቋረጥ እና የስነ ልቦና ጉዳት ማካካሻ ክፍያ ነው፡፡
7. "መልሶ ማቋቋም" ማለት ለልማት ተብሎ በተወሰደው መሬት ምክንያት የሚያገኙት ጥቅም ለሚቋረጥባቸው ተነሺዎች ዘላቂ የገቢ ምንጭ እንዲኖራቸው የሚሰጥ ድጋፍ ነው፡፡

8. "ቀመር" ማለት ለህዝብ ጥቅም በሚለቀቅ መሬት ላይ ለሠፈረ ንብረት ወጥ የሆነ የካሣ ስሌት የሚሰራበት ዘዴ ነው፡፡
9. "ቋሚ ማሻሻያ" ማለት በይዞታው ላይ የምንጣሮ፣ ድልደላና እርከን ሥራ፣ ውሃ መከተር ሥራ እና የግቢ ንጣፍና ማስዋብ የመሳሰሉትን ሥራዎች ያጠቃልላል።
10. "የማቋቋሚያ ማዕቀፍ" ማለት ለህዝብ ጥቅም ሲባል ከመሬት ይዞታቸው እንዲነሱ ሲደረግ ዘላቂ የሆነ የገቢ ምንጭ ሊኖራቸው የሚያስችል የሥራ መርሐ ግብር ነው፡
11. "የወል ይዞታ" ማለት ከመንግሥት ወይም ከግል ይዞታነት ውጭ የሚገኝና የአካባቢው ማህበረሰብ ለግጦሽ፣ ለደንና ለማህበራዊ አገልግሎት በጋራ የሚጠቀሙበት የመሬት ይዞታ ነው፡፡
12. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47/1 የተመለከተው ማንኛውም ክልል ነው።
13. "የከተማ አስተዳደር" ማለት በሕግ የከተማ አስተዳደር ሥልጣንና ተግባር የተሰጠው አካል ነው፡፡
14. "መሠረተ ልማት" ማለት ከመሬት በላይ ወይም ከመሬት በታች ያለ መንገድ፣ የባቡር ሀዲድ፣ የአውሮፕላን ማረፊያ፣የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ የመስኖ፣የውሀ መስመር ወይም የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ሲሆን ሌሎች ተያያዥ ግንባታዎችንም ይጨምራል።
15. “የአገልግሎት መስመር" ማለት ለህዝብ ጥቅም ሲባል የሚለቀቅ መሬት ከመሬቱ በላይ ወይም ውስጥ የተዘረጋ የውሃ የፍሳሽ የኤልክትሪክ ወይም የስልክ መስመር ሲሆን ሌሎች ተመሳሳይ ስራዎችንም ይጨምራል፡፡
16. “ተነሺ” ማለት ለህዝብ ጥቅም መሬት በሚለቀቅበት ጊዜ በተለቀቀው መሬት ላይ ይኖሩ የነበሩ ባለይዞታ ተከራይ ተቀጥሮም ሆነ በግል ይሰራ የነበረ እና በጥገኝነት ይኖር የነበረን ይጠቀልላል፡፡
17. “አቤቱታ ሰሚ” ማለት በዚህ አዋጅ አፈጻፀም ላይ ለሚነሳ ቅሬታ የሚመለከት እና ውሳኔ የሚሰጥ አካል ነው
18. "ይግባኝ ሰሚ" ማለት አቤቱታ ሰሚ አካል የሰጠውን ውሳኔ በይግባኝ ተመልክቶ ውሳኔ የሚሰጥ አካል ነው፡፡

19. "እውቅና ያለው ገማች" ማለት ቋሚ ንብረቶችን ለመገመት አግባብ ባለው አካል እውቅና የተሰጠው ገማች አካል ነው፡፡

20. "አስቸኳይ ልማት" ማለት በመደበኛው የጊዜ ሰሌዳ መሄድ የማይችልና ለከፍተኛ ወጪ ሊዳርግ ወይም ከፍተኛ ገንዘብ ሊያሳጣ የሚችል መሆኑ ተረጋግጦ በመንግስት የተወሰነ የልማት አይነት ነው፣

21. "ውስብስብ መሰረተ ልማት" ማለት በተለመደው አሰራር የማይሰራ፣በአገር ውስጥ ባለው ባለሙያ የማይሰራ፣ እቃዎችም በክምችት የማይያዝበት፣ ከአገር ውጪ ግዥ የሚጠይቅ እና መሰል ስራ ሆኖ በመሰረተ ልማት ባለሙያ የተረጋገጠ እና በመሰረተ ልማት ተቋም ሀላፊ የፀደቀ ተጨማሪ ጊዜ የሚያስፈልገው የመሰረተ ልማት አይነት ነው፣

22. "ሀገራዊ ወይም ክልላዊ ፋይዳ ያላቸው ልማቶች" ማለት ለኢትዮጵያ እድገትና ትራንፎርሜሽን ከፍተኛ ለውጥ የሚያመጡ የልማት ፕሮጀክቶች ወይም የትብብር መስኮችን ለማስፋት በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ሀገሪቱ ከሌሎች ሀገሮች ለሚኖራት የተሻለ ግንኙነት መሰረት እንዲጥሉ የታቀዱ ልማቶች ናቸው፡፡

23. "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

24. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትን፣ ካሣ የሚከፈልበትንና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ በሚመለከት በመላ ሀገሪቱ በከተማም ሆነ በገጠር ተፈጻሚ ይሆናል።

## 4. መርሆዎች

1. የመሬት ይዞታ ለሕዝብ ጥቅም እንዲለቀቅ የሚደረገው በመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ወይም በከተሞች መዋቅራዊ ዕቅድ ወይም በመሠረተ ልማት መሪ ፕላን መሠረት መሆን አለበት፡፡
2. ለሕዝብ ጥቅም መሬት ሲለቀቅ የሚከፈል ካሣና የሚሰጥ የማቋቋሚያ ድጋፍ የተነሺዎችን የኑሮ ሁኔታ የሚያሻሽልና የሚያስቀጥል መሆን አለበት፡፡
3. በፌደራል መንግስትም ሆነ በክልል መንግስታት፣በአዲስ አበባ ወይም ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች ለሚከናወኑ የልማት ሥራዎች በአንድ አካባቢ ለሚገኙ ቦታዎች

ለሠፈረ ንብረት እና ተጓዳኝ ጥቅም ማጣት የሚከፈል የካሣ ነጠላ ዋጋ ተመን ተመሳሳይ መሆን አለበት።

4. ለሕዝብ ጥቅም መሬት እንዲለቀቅ ሲደረግ አሰራሩ ግልጽ፣አሳታፊ፣ ፍትሃዊ እና ተጠያቂነትን የተከተለ መሆን አለበት፡፡

## ክፍል ሁለት

## መሬት ለማስለቀቅ ስለሚፈፀም ሥነ-ሥርዓት

5. **የሚለቀቀው መሬት ለሕዝብ ጥቅም መሆኑን ስለመወሰን**

1. አግባብ ያለው የፌደራል አካል ወይም የክልሉ፤አዲስ አበባ ወይም ድሬዳዋ ካቢኔ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የተሻለ ልማት ያመጣል ብሎ በመሬት አጠቃቀም እቅድ ወይም በልማት እቅድ ወይም በመሠረተ ልማት መሪ ፕላን መሠረት የሚለቀቀውን መሬት ለሕዝብ ጥቅም መሆኑን ይወስናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሠረት ለመወሰን መሪ ፕላኑ ዝርዝር የማስፈፀሚያ ፕላን ሊኖረው ይገባል፡፡
3. ለሕዝብ ጥቅም መሬት እንዲለቀቅ ሲወስን ለካሣ እና መልሶ ማቋቋም የሚያስፈልግ በጀትና በጀቱ በማን እንደሚሸፈን አብሮ መወሰን አለበት፡፡
4. የመሬት ባለይዞታዎች በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 የተገለፀው መስፈርት ሳይሟላ መሬታቸው ለሕዝብ ጥቅም እንዲለቀቅ የሚሰጥ የሕዝብ ጥቅም ውሳኔ ላይ አቤቱታ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡
5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም እንደ አስፈላጊነቱ የክልሉ፣ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ካቢኔ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል መሬት ማስለቀቅ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣኑን ለከተማ ወይም ለወረዳ አስተዳደሩ በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

6. **መሬት የማስለቀቅ ሥልጣን**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 መሠረት ለሕዝብ ጥቅም እንዲለቀቅ ውሳኔ የተሰጠበትን መሬት የከተማው ወይም የወረዳው አስተዳደር መሬቱ የማስለቀቅ እና የመረከብ ሥልጣን አለው።

7. **ለባለይዞታዎች ቅድሚያ የማልማት መብት ስለመስጠት**

1. በከተማ ለመልሶ ማልማት በተከለለ ቦታ ውስጥ ያለ ባለይዞታ በፕላኑ መሠረት ይዞታውን በግልም ሆነ በጋራ ቅድሚያ የማልማት መብት አለው፡፡

2. የገጠር መሬት ባለይዞታ ለእርሻ ስራ የሚለቀቅ ሲሆን አቅሙ ካለው ይዞታውን በግልም ይሁን በቡድን በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ መሠረት ቅድሚያ የማልማት መብት አለው፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት ለተነሺው ቅድሚያ የማልማት መብት የሚጠበቅለት በፕላኑ መሠረት ለማልማት አቅም ማሳያ ማቅረብ ሲችል ነው፡፡
4. ቅድሚያ የማልማት መብት የሚሰጥበት ዝርዝር ሁኔታ እና አቅም ማሳያ መጠንና የጊዜ ገደብ በደንብ ይወሰናል፡፡

8. <u>መሬት የሚለቀቅበት ሥርዓት</u>

1. የከተማ አስተዳደር ወይም የወረዳ አስተዳደር መሬት ሲያስለቅቅ መከተል ያለበት ቅደም ተከተል፡፡-፡-
   ሀ) ተነሺዎች ከመነሳታቸው ቢያንስ ከአንድ ዓመት በፊት ስለልማቱ ዓይነት ጠቀሜታና አጠቃላይ ሂደት በማወያየት እንዲያውቁት ማድረግ አለበት፡፡
   ለ) በዚህ አንቀፅ ፊደል ተራ (ሀ) የተጠቀሰው ቢኖርም የሚመለከተው የፌደራል ወይም የክልል መንግሰት ሀገራዊ ወይም ክልላዊ ፋይዳ ላለው ለአስቸኳይ ልማት መሬት እንዲለቀቅ ከወሰነ ተነሺዎች ከአንድ ዓመት ባነሰ ጊዜ ስለልማቱ አይነት፣ ጠቀሜታና አጠቃላይ ሂደት በማወያየት እንዲያውቁት ሊደረግ ይችላል፡፡
   ሐ) እንዲለቀቅ በተወሰነው ቦታ ላይ ከሚገኙ ተነሺዎች ወይም ሕጋዊ ወኪሎች የባለመብትነት ማስረጃ እና ካሣ የሚከፈልባቸውን ንብረቶች የልኬትና የመጠን መረጃ መሰብሰብ አለበት፡፡ ተነሺዎች ስለልማቱ እንዲያውቁት ከተደረገ በኋላ የተጨመሩ ማናቸውም ንብረቶች ካሳ አይከፈልባቸውም፡፡
   መ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሐ" መሠረት የተሰበሰበውን መረጃ አጣርቶ ለልማት ተነሺ የሚሰጥ መብት ተጠቃሚነት ይወስናል፣ የካሣ መጠኑንም አስልቶ ካሣና ሌሎች ተያያዥ መብቶችን ክፍያ ይከፍላል፡፡
   ሠ) ለሕዝብ ጥቅም እንዲለቀቅ በተወሰነው ቦታ ላይ ለሚገኝ ተነሺ ወይም ሕጋዊ ወኪል የሚገባውን የካሣ መጠን እና/ወይም ምትክ ቦታ ስፋትና አካባቢን ወይም ቤት በመግለጽ በጽሁፍ የማስለቀቂያ ትዕዛዝ መስጠት
   ረ) የሚለቀቀው ይዞታ የመንግሥት ቤት የሰፈረበት ከሆነ የማስለቀቂያ ትዕዛዙ የሚደርሰው ቤቱን ለሚያስተዳድረው አካል እና ቤቱን ለተከራየው ሰው

ይሆናል፡፡

ሰ) ተነሺን ከቦታው ማስነሳት የሚችለው ለተነሺው ካሣ ከከፈለ እና ምትክ ቦታ ወይም ቤት ከሰጠ በኋላ መሆን አለበት፡፡

ሸ) መሬት የማስለቀቅ ስርዓት ዝርዝር አፈጻጸሙ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

2. ተነሺ ወይም ሕጋዊ ወኪሉ ባለመብትነቱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ወይም ሠነድ በገጠርም ሆነ በከተማ መሬት የማስተዳደር በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል በሚያወጣው መርሐ-ግብር መሠረት ማቅረብ አለበት፡፡

3. ተነሺው የካሣ ግምት በጽሁፍ እንዲያውቅ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ፡-

ሀ) በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ተገቢው ካሣ ካልተከፈለው በመሬቱ ላይ ከቋሚ ተክልና ግንባታ በስተቀር ሌሎች ሥራዎችን መስራት ይችላል፡፡

ለ) በስድስት ወር ካሣ ካልተከፈለው በመሬቱ ላይ ማንኛውንም በፕላን የሚፈቀድ እና ቀጣይ የቦታውን የልማት ወጪ በመንግስት ላይ የማያዛባ ሥራ መስራት ይችላል፡፡

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ "ሀ" እና "ለ" መሰረት የተሰራ ሥራ ወይም የተደረገ ለውጥ በካሣ ስሌቱ ውስጥ እንዲገባ መደረግ አለበት፡፡

4. የማስለቀቂያ ትዕዛዝ የደረሰው ባለይዞታ ትዕዛዙ በደረሰው በ30 (ሰላሳ)ቀናት ውስጥ ካሣ እና ምትክ ቦታ ወይም ቤት መውሰድ አለበት።

5. የማስለቀቂያ ትዕዛዝ የደረሰው ባለይዞታ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት በተቀመጠ ጊዜ ገደብ ውስጥ የካሣ ክፍያውን ካልወሰደ በከተማው ወይም በወረዳው አስተዳደር ስም በሚከፈት ዝግ የባንክ ሂሳብ እንዲቀመጥለት ይደረጋል።

6. ለባለይዞታ የሚሰጠው የመልቀቂያ የጊዜ ገደብ ካሣና ምትክ ቦታ ከተቀበለ ወይም ካሳው በዝግ ሂሳብ ከተቀመጠበት ቀን ጀምሮ ከ120 (መቶ ሀያ) ቀናት መብለጥ የለበትም፡፡

7. በሚለቀቀው መሬት ላይ ሰብል፣ ቋሚ ተክል ወይም ቋሚ የሆነ ሌላ ንብረት ከሌለ ባለይዞታው የልማት ተነሽ ካሣ ከተከፈለው በኋላ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ይዞታውን ለከተማ ወይም ለወረዳ አስተዳደር ማስረከብ አለበት፡፡

8. በሕገ-ወጥ መንገድ በተያዘ ቦታ ላይ ለሰፈረ ንብረት ካሣ መክፈል ሳያስፈልግ ለ30 (ሰላሳ) ቀናት የሚቆይ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወይም በቦታው በሰፈረው ንብረት ላይ በመለጠፍ እንዲለቀቅ ይደረጋል።

9. የማስለቀቂያ ትዕዛዝ የደረሰው ባለይዞታ ወይም ባለንብረት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) እና (7) በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያለ በቂ ምክንያት መሬቱን ካላስረከበ የከተማ ወይም የወረዳ አስተዳደሩ መሬቱን በራሱ ይረከባል፡፡ አስፈላጊም ሲሆን ለመረከብ የፖሊስ ኃይል ትብብር ሊጠይቅ ይችላል፡፡

9. <u>***መሬት እንዲለቀቅለት የተወሰነለት አካል ኃላፊነት***</u>

1. መሬት እንዲለቀቅለት የተወሰነለት አካል ለሥራው የሚፈለገውን መሬት መጠንና የሚገኝበትን ትክክለኛ ስፍራ የሚያሳይ ውሳኔ የተሰጠበት ማስረጃ ቢያንስ ሥራው ከመጀመሩ ከአንድ ዓመት በፊት ለከተማው ወይም ለወረዳው አስተዳደር ማቅረብ አለበት፡፡
2. መሬቱ ለሕዝብ ጥቅም እንዲውል ሲወሰን የመሬት ይዞታቸውን እንዲለቁ ለሚደረጉ ባለይዞታዎች የሚከፈለውን ካሣ እና የመቋቋሚያ ድጋፍ ወጪ እንዲሸፍን ከተወሰነ ገንዘቡን ለከተማው ወይም ለወረዳው አስተዳደር ገቢ ያደርጋል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ገንዘቡ ገቢ ተደርጎ ለተነሺዎች ካልተከፈለ የከተማው ወይም የወረዳው አስተዳደር መሬት አያስለቅቅም፡፡

10. <u>***የአገልግሎት መስመሮች ስለሚነሱበት ሥርዓት***</u>

1. የከተማው ወይም የወረዳው አስተዳደር በሚለቀቀው መሬት በላይ ወይም በታች የአገልግሎት መስመር መኖር አለመኖሩን የአገልግሎት መሥመር ባለቤት ለሆኑ ተቋማት ምላሽ እንዲሰጡበት በጽሁፍ ጥያቄ ማቅረብ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 መሠረት ጥያቄ የቀረበለት ተቋም ንብረት ካለው ለሚነሳው ንብረት ካሣ እውቅና ባለው ገለልተኛ ገማች በማስተመን ከነዝርዝር ማስረጃው ጥያቄው በደረሰው በ30 (ሰላሳ) ቀን ውስጥ በጽሁፍ ለጠያቂው አካል ይልካል።
3. የከተማው ወይም የወረዳው አስተዳደር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ግምቱ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ለባለ ንብረቱ የንብረቱን ግምት ካሣ ይከፍላል።

4. የአገልግሎት መስመሩ ባለቤት ክፍያው በተፈጸመለት በ60(ስልሳ) ቀናት ውስጥ ካሣ የተከፈለበትን የአገልግሎት መስመር አጠናቆ ማንሳትና መሬቱን መልቀቅ አለበት።
5. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 እንደተጠበቀ ሆኖ የአገልግሎት ባለቤት ክፍያው በተፈፀመ 120 (አንድ መቶ ሀያ) ቀናት ውስጥ ውስብስብነት ያላቸውን የመሰረተ ልማት መስመሮች አጠናቆ ማንሳትና መሬቱን መልቀቅ አለበት፡፡
6. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 እና 5 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ልማቱ ካልተነሳ በአንቀፅ 8 ንዑስ አንቀፅ 9 መሰረት በማስነሳት ይዞታው የሚወሰድ ሲሆን በወቅቱ ተገቢውን ስራ ያልተወጣ የመሰረተ ልማት ተቋም ለሚደርሰው ጉዳት ተጠያቂ ይሆናል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

## ክፍል ሶስት

## የካሳ አወሳሰን ምትክ አሰጣጥ እና መልሶ ማቋቋም

11. **ለህዝብ ጥቅም መሬት ሲለቀቅ ለተነሺዎች ስለሚከፈል ካሳ**

ለህዝብ ጥቅም መሬት እንዲለቀቅ ሲደረግ ለተነሺው ባለው የንብረትና የይዞታ መብት መሠረት የንብረት እና የልማት ተነሽ ካሣ ይከፈላል።

12. **የንብረት ካሣ**

1. የመሬት ይዞታን እንዲለቅ የሚደረግ ባለይዞታ በመሬቱ ላይ ለሚገኘው ንብረት እንዲሁም በመሬቱ ላይ ላደረገው ቋሚ ማሻሻያ ካሣ ይከፈለዋል።
2. በሚለቀቀው የመሬት ይዞታ ላይ ለሰፈረው ንብረት የሚከፈል ካሣ ንብረቱን ለመተካት የሚያስችል ይሆናል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ለሚነሳው ቤት የሚከፈለው አነስተኛ የካሣ መጠን እንደ የክልሉ፤እንደ አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ተጨባጭ ሁኔታ ወይም ክልሉ፤ አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ አስተዳደር በሚያወጣው ስታንዳርድ መሰረት ቢያንስ ዝቅተኛውን የቤት ደረጃ ሊያስገነባ የሚችል መሆን አለበት፡፡
4. በመሬት ይዞታው ላይ ለተደረገ ቋሚ ማሻሻል የሚከፈል ካሣ በመሬቱ ላይ የዋለውን ገንዘብና የጉልበት ዋጋ የሚተካ ክፍያ በአካባቢው ወቅታዊ ዋጋ ተሰልቶ ይሆናል።
5. ንብረቱ ከሚገኝበት ስፍራ ወደ ሌላ አካባቢ ተዛውሮ እንደገና ሊተከልና አገልግሎት ለመስጠት የሚችል ከሆነ የማንሻ፣ የማጓጓዣና መልሶ የመትከያ ወጪ የሚሸፍን ካሣ መከፈል አለበት፡፡

6. የተለያዩ ንብረቶች የሚሰሉበት የካሣ ቀመር እና ዝርዝር አፈፃፀማቸው በደንብ ይወሰናል።

## 13.ስለ የልማት ተነሽ ካሳ እና ምትክ ቦታ

1. በቋሚነት ስለሚነሳ የገጠር መሬት ባለይዞታ የሚሰጥ ካሳ እና ምትክ ቦታ፡-
   ሀ) የመሬት ይዞታውን በቋሚነት እንዲለቅ የሚደረግ የገጠር መሬት ባለይዞታ እንደ አከባቢው ሁኔታ ከተወሰደበት መሬት ተመጣጣኝ ምርት የሚያስገኝ ምትክ መሬት የሚገኝ ሲሆን ምትክ መሬት ይሰጠዋል፡፡
   ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ" መሠረት ተመጣጣኝ ምትክ መሬት የሚሰጠው ከሆነ መሬቱን ከመልቀቁ በፊት በነበሩት ሶስት ዓመታት ውስጥ በየዓመቱ ከመሬቱ ሲያገኝ ከነበረው ከፍተኛውን የአንድ ዓመት ገቢ በወቅታዊ ዋጋ ተሰልቶ የልማት ተነሽ ካሳ ይከፈለዋል፤
   ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ" መሠረት ተመጣጣኝ ምትክ መሬት የማይሰጠው ከሆነ መሬቱን እንዲለቅ ከመደረጉ በፊት በነበሩት ሶስት ዓመታት ውስጥ ከመሬቱ ሲያገኝ የነበረውን ከፍተኛ ዓመታዊ ገቢ በአስራ አምስት ተባዝቶ የልማት ተነሽ ካሳ መከፈል አለበት፡፡
   መ) ከመኖሪያ ቦታው የሚነሳ ከሆነ ክልሉ፤አዲስ አበባ ወይም ድሬዳዋ ከተማ አሰተዳደሮች በሚያወጡት መመሪያ የሚወሰን ምትክ ቦታ እና የልማት ተነሽ ድጋፍ መከፈል አለበት፡፡
   ሠ) በጊዜያዊነት ለሚለቀቅ መሬት የሚከፈል የልማት ተነሽ ካሣ በማንኛውም ሁኔታ በዘላቂነት ከሚከፈል የልማት ተነሽ ድጋፍ መብለጥ የለበትም፡፡
   ረ) የዚህ ንዑስ አንቀፅ ዝርዝር አፈፃፀም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡
2. በጊዜያዊነት ስለሚነሳ የገጠር መሬት ባለይዞታ የሚሰጥ የልማት ተነሽ ድጋፍ ካሳ:-
   ሀ) ይዞታውን ለተወሰነ ጊዜ እንዲለቅ ለሚደረግ የገጠር መሬት ባለይዞታ መሬቱ ከመለቀቁ በፊት በነበሩት ሶስት ዓመታት ውስጥ ያገኘው ከፍተኛ ዓመታዊ ገቢ መሬቱ እስከሚመለስ ድረስ ባለው ጊዜ ታስቦ የልማት ተነሽ ድጋፍ ካሣ

ይከፈለዋል፡፡

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ" የሚከፈለው የልማት ተነሽ ካሣ መሬቱ የነበረውን ምርታማነት ለመመለስ የሚወስደውን በአካባቢ የግብርና ተቋም የሚወሰን ተጨማሪ ጊዜ ታሳቢ ማድረግ አለበት፡፡

ሐ) መሬቱ ተመልሶ በፊት ይሰጥ የነበረውን አገልግሎት መስጠት የማይችል ከሆነ በቋሚነት እንደለቀቀ ተቆጥሮ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት የልማት ተነሽ ካሳ ወይም ምትክ ቦታ ይሰጠዋል፤

መ) መሬቱ በጊዜያዊነት በተለቀቀበት ጊዜ የተከፈለ የልማት ተነሽ ካሣ በዚህ ንኡስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሐ" መሠረት በቋሚነት እንዲለቀቀ ተቆጥሮ ከሚከፈል ካሳ ተቀንሶ ለተነሺው ልዩነቱ ይሰጠዋል፡፡

ሠ) በጊዜያዊነት ለሚለቀቅ መሬት የሚከፈል የልማት ተነሽ ካሣ በማንኛውም ሁኔታ በዘላቂነት ከሚከፈል የልማት ተነሽ ካሣ መብለጥ የለበትም፡፡

ረ) የዚህ ንዑስ አንቀፅ ዝርዝር አፈፃፀም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

3. ስለወል ይዞታ የልማት ተነሺ ካሣ

በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ለሚለቀቅ የወል ይዞታ የልማት ተነሽ ካሣ ስሌት እና አከፋፈል ሁኔታ ክልሉ፤አዲስ አበባ፤ድሬዳዋ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ሆኖ መመሪያው ሲወጣ፡-

ሀ) ለተወሰደው የወል መሬት የልማት ተነሽ ካሣ ስሌት የወል መሬቱ ይሰጥ የነበረውን ጥቅም ወይም ጥቅሙ የቀረባቸውን የአኗኗር ዘይቤ ወይም መተዳደሪያ መሠረት ያደረገ ሊሆን ይገባል።

ለ) የወል መሬቱ ተጠቃሚዎች በግልጽ መለየት አለበት፡፡

ሐ) በወል መሬቱ ላይ የሚገኙ የግልና የወል ንብረት መለየት አለበት፡፡

መ) የወል መሬት በመወሰዱ ምክንያት በካሣ የተገኘውን ገንዘብ ለማህበረሰቡ አባላት እኩል ሊከፈል ወይም በዓይነት ሊጠቀሙበት የሚችሉበትን መንገድ መቅረጽ አለበት፡፡

4. በቋሚነት ስለሚነሳ የከተማ መሬት ባለይዞታ የሚሰጥ ልማት ተነሽ ካሳ እና ምትክ ቦታ የከተማ መሬት ባለይዞታ ከይዞታው በቋሚነት ተነሺ በሚሆንበት ጊዜ

የሚከፈለው የልማት ተነሽ ካሣ እና የሚሰጠው ምትክ ቦታ በሚከተለው አግባብ ይሆናል፡-

ሀ) በቋሚነት ለሚነሳ የከተማ መሬት ባለይዞታ ምትክ ቦታ ወይም መኖሪያ ቤት በግዥ እንዲያገኝ ይመቻቻል፡፡

ለ) የሚሰጠው ምትክ ቦታ ከሆነ በቦታው ቤት እስኪገነባ ለሁለት ዓመት የሚኖርበት ቤት ያለኪራይ ይሰጠዋል ወይም ለፈረሰበት ቤት በወቅታዊ የኪራይ ግምት ተሰልቶ የሁለት ዓመት የልማት ተነሽ ካሣ ይከፈለዋል፡፡

ሐ) የሚሰጠው ምትክ ቤት ከሆነ ለፈረሰበት ቤት በወቅታዊ የኪራይ ግምት ተሰልቶ የአንድ ዓመት የልማት ተነሽ ካሣ ይከፈለዋል፡፡

መ) በዚህ ንኡስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ለ" እና "ሐ" የሚከፈል የልማት ተነሽ ካሣ መጠን ቢያንስ የአካባቢውን ዝቅተኛ የቤት ኪራይ ለመክራየት ከሚያስችል ያነሰ መሆን የለበትም፡፡

ሠ) ተነሺዎች በነበሩበት አካባቢ ለነበራቸው የማህበራዊ ትስስር መቋረጥና ለሚደርስ በየሥነ-ልቦና ጉዳት ማካካሻ ይከፈላቸዋል፡፡ መጠኑ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፤

ረ) የሚለቀቀው የሊዝ ይዞታ ከሆነ የሚሰጠው ምትክ ቦታ ከተለቀቀው መሬት በደረጃ እና በስፋት ተመጣጣኝ መሆን አለበት፡፡ ይህንን ለመፈፀም የማይቻል ከሆነ አማራጭ የአፈፃፀም ሁኔታ እንደየከተሞቹ ተጨባጭ ሁኔታ በመመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

ሰ) የምትክ ቦታ ወይም ቤት አሰጣጥ፣ የልማት ተነሽ ካሣ እና ተያያዥ ጉዳዮች ዝርዝር አፈፃፀም ክልሎች፣ አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳሮች በሚያወጡት መመሪያ ይወሰናል፡፡

5. በጊዜያዊነት ስለሚነሳ የከተማ መሬት ባለይዞታ የሚሰጥ የልማት ተነሽ ድጋፍ፦

ሀ) በጊዜያዊነት ለሚነሳ የከተማ ባለይዞታ ተነስቶ ለሚቆይበት ጊዜ ምትክ ቤት ወይም በወቅታዊ የኪራይ ግምት ተሰልቶ ተመጣጣኝ ቤት የሚከራይበት ክፍያ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

ለ) የከተማ ባለይዞታዎች በጊዜያዊነት በመነሳታቸው ምክንያት ላጡት ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ካሳ ይከፈላቸዋል፤የዚህ ንዑስ አንቀጽ ዝርዝር አፈፃፀም ክልሎች፤አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ አስተዳደሮች በሚያወጡት መመሪያ ይወሰናል፡፡

14.ገቢ በመቋረጡ ስለሚከፈል የኢኮኖሚ ጉዳት ካሣ

1. ለሕዝብ ጥቅም ቦታ. እንዲለቀቅ ከመደረጉ ጋር በተያያዘ ከይዞታው ሳይነሳ በጊዜያዊነት ወይም በዘላቂነት ሲያገኝ የነበረው ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለተቋረጠበት ሰው የጉዳት ካሳ የሚከፈል ሲሆን ካሳው ስለሚገባው ተጎጂ እና የጉዳት ካሣው መጠንና አይነት ክልሉ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፤
2. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 መሠረት የካሳዉን መጠንና ዓይነት ለመወሰን ከመቀጠር፣ ከንግድ፣ ከኪራይ ከእርሻ ውጪ መሬትን በመጠቀም የሚገኝ ገቢ እና የመሳሰሉ ዓመታዊ የተጣራ ገቢን ታሳቢ ሊያደርግ ይችላል፡፡

15.ከገጠር ወደ ከተማ ለተካለለ የከተማ አካባቢ ባለይዞታ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ስለመወሰን

1. ከገጠር ወደ ከተማ በተካለለ የአርሶ አደር ይዞታ ከመኖሪያ ቤቱ ለሚነሳ ባለይዞታ በክልሉ፤በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ ካቢኔ የሚወሰን ሆኖ የከተማውን ስታንዳርድ በመጠበቅ ከ500 (አምስት መቶ)ሜትር ካሬ ያልበለጠ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ መሰጠት አለበት።
2. ዕድሜው 18 ዓመትና ለሆነው የባለይዞታውን ገቢ በመጋራት አብሮ የሚኖር አርሶ ወይም አርብቶ አደር ልጅ የቦታ ስፋቱ የከተማውን አነስተኛ የመሬት ይዞታ ደረጃ የሆነ ለመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ መሰጠት አለበት፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም ለመኖሪያ የሚሰጠው ጠቅላላ የቦታ መጠን ከነበረው የመኖሪያ ይዞታ በላይ መሆን የለበትም፡፡
4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 የተገለፀው የመኖሪያ ይዞታ መጠን የባለይዞታው መኖሪያ ቤት ያረፈበትና የአጥር ግቢውን ይጨምራል።
5. የዚህ አንቀፅ ዝርዝሩ አፈፃፀም ክልሉ፣አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች በሚያወጡት መመሪያ ይወሰናል።

16.መልሶ ስለማቋቋም

1. የክልል መንግሥት፤የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ አስተዳደር ለካሣ ክፍያ እና ለመልሶ ማቋሚያ ፈንድ ያቋቁማል፤
2. ክልሎች፤አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች ተነሺዎችን በዘላቂነት ለማቋቋም የሚያስችል ማቋቋሚያ ማዕቀፍ የመቅረጽ ግዴታ አለባቸው፡፡

3. የከተማ ወይም የወረዳ አስተዳደር በተቀረፀው ማቋቋሚያ ማዕቀፍና በሚመደበው ማስፈጸሚያ በጀት ተነሺዎችን የማቋቋም ግዴታ አለበት፤
4. በገጠርም ሆነ በከተማ ለሕዝብ ጥቅም መሬት የሚለቀቀው ለኢንቨስትመንት ከሆነ ተነሺዎች ከኢንቨስትመንቱ የሼር ባለቤት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

5. በገጠርም ሆነ በከተማ የልማት ተነሺ በሼር ለመጠቀም ፍላጎት ኖሮት ባለሀብቱ ይህንን ለማድረግ የሚያስችለው ሁኔታ ካለ ባለሀብቱ ለተነሺዎች የኢኮኖሚ አስቻይ ተለዋጭ መፍትሄ በተነሺው፤በባለሀብቱ እና በአስተዳደሩ መሰጠት አለበት፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡
6. የመልሶ ማቋቋሚያ ማዕቀፍ ይዘትና ዝርዝር አፈፃፀም በደንብ ይወሰናል፡፡

17.<u>ንብረት ስለመገመት</u>

1. እንዲለቀቅ በሚፈለግ መሬት ላይ ለሚገኝ ንብረት ካሣ የሚወጣውን አገር አቀፍ ቀመር

   መሠረት በማድረግ በተመሰከረለት የግል ድርጅት ወይም ግለሰብ አማካሪዎች ይገመታል፡፡
2. የካሣውን መጠን የሚገምት የተመሰከረለት የግል ድርጅት ወይም ግለሰብ አማካሪዎች ከሌሉ ራሱን የቻለ በመንግሥት በተቋቋመ ተቋም ይገመታል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት የካሣውን መጠን የሚገምት ድርጅት ከሌለ የሚለቀቀው መሬት እንደሚገኝበት አካባቢ የሚመለከተው የወረዳ ወይም የከተማ

   አስተዳደር ተገቢው ሙያ ያላቸው አባላት የያዘ ገማች ኮሚቴ በማቋቋም የሚገመት ይሆናል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የሚቋቋመው ገማች ኮሚቴ ሥራውን የሚያከናውንበት የአሠራር ሥርዓት ክልሉ፤አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች በሚያወጡት መመሪያ ይወሰናል፡፡
5. የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1፣2 እና 3 ቢኖርም የሚነሳው ንብረት የተለየ እውቀት የሚጠይቅ ሲሆን አግባብ ባለው የመንግሥት ወይም የግል ድርጅት ሊገመት ይችላል።

6. የሚነሳው ንብረት የመንግሥት መሠረተ ልማት ወይም የአገልግሎት መስመር ከሆነ የካሣ ግምቱ የሚዘጋጀው በንብረቱ ባለቤት ይሆናል፡፡
7. የካሣ ግምት የሚሰላበት ነጠላ ዋጋ ቢበዛ በየሁለት ዓመቱ መከለስ አለበት፡፡

18.**<u>አቤቱታ ሰሚ አካል እና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ስለማቋቋም</u>**

1. ክልሎች፣አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች በዚህ አዋጅ መሠረት በሚሰጥ ውሳኔ ላይ ለሚቀርብ አቤቱታ አቤቱታ ሰሚ አካል እና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ማቋቋም አለባቸው፡፡
2. ክልሎች፣አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች አቤቱታ ሰሚ አካል እና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አስፈላጊ ነው ብለው በወሰኑት ከተሞቻቸው ሊያቋቁሙ ይችላሉ፡
3. የአቤቱታ ሰሚ አካል እና የይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አደረጃጀት ሥልጣንና ተግባር ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

19.**<u>አቤቱታ ስለማቅረብ</u>**

1. የመሬት ይዞታ ማስለቀቂያ ትዕዛዝ የደረሰው ወይም እንዲለቅ ትዕዛዝ በተሰጠበት ንብረት ላይ መብቴ ወይም ጥቅሜ ተነካብኝ የሚል ማንኛውም ተነሽ ትዕዛዙ በደረሰው በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ አቤቱታውን፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ለሚቋቋመው አቤቱታ ሰሚ አካል ማቅረብ ይችላል፤
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተጠቀሰው አካል የሚቀርብለትን አቤቱታ ከመረመረ በኋላ በ30(ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ውሳኔ በመስጠት ለተከራካሪ ወገኖች በጽሁፍ ያሳውቃል።

20.**<u>ስለ ይግባኝ</u>**

1. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 19 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን አቤቱታውን ለይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ውሳኔው በጽሁፍ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ማቅረብ አለበት፡፡
2. ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔው በጽሁፍ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በ30 (ሰላሳ) ቀን ውስጥ ይግባኝ ለክልል ከፍተኛው ፍርድ ቤት፣ በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ ከተሞች ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ማቅረብ

ይችላል። ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ይግባኝ ማለት የሚፈልግ ከሆነ ልማቱ እንዳይጓተት ቦታውን አስረክቦ ክርክሩን የመቀጠል መብት አለው፡፡

3. ተነሺው ንብረቱን በማስረከቡ እና በቅሬታ ምክንያት ካሳውን ባለመውሰዱ ለይግባኙ ክርክሩ የሚሆን በቂ ገንዘብ ከሌለው እና በዚህ ምክንያት የሚቸገር ከሆነ መንግስት ነፃ የህግ አገልግሎት የሚያገኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

21.**አቤቱቱ የቀረበበትን ቦታ ስለመረከብ**

1. የመሬት ማስለቀቅ ትእዛዝ የደረሰው ባለይዞታ በዚህ አዋጅ መሠረት አቤቱታ ያቀረበ ከሆነ የከተማው ወይም የወረዳው አስተዳደር ቦታውን መረከብ የሚችለው፡-
   ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት አቤቱታ አቅርቦ ውሳኔው ከፀና እና በተሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ሳያቀርብ ሲቀር፣ ወይም
   ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 20 ንኡስ አንቀጽ 2 መሠረት ይግባኙን ሳያቀርብ ሲቀር፣
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ አጸ ቢኖርም አቤቱታ የቀረበበትን ቦታ በሕገ ወጥ መንገድ የተያዘ ቦታ ከሆነ በቦታው ላይ የሰፈሩ ንብረቶች በማውጣት የተሰራ ግንባታ እንዲፈርስ በማድረግ የከተማው ወይም የወረዳው አስተዳደር መሬቱን መረከብ ይችላል፡፡

**ክፍል አራት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

22. **የፌደራል ተቋማት ሥልጣንና ተግባር**

በሌላ ሕግ ለሚኒስቴሩ የተሰጠ ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ:-

1. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር:-
   ሀ) ከተማን የሚመለከቱ የአዋጁ ድንጋጌዎች በከተሞች መከበራቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣
   ለ) የከተማ ተነሺዎችን በማቋቋም ሥራ ላይ ድጋፍ ያደርጋል፣
   ሐ) ክልሎች፣ አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተሞች አዋጁን ማስፈጸም እንዲችሉ የቴክኒክና አቅም ግንባታ ድጋፍ ያደርጋል፣
   መ) አዋጁን ለማስፈጸም መመሪያዎች በወቅቱ መውጣታቸውን ይከታተላል፣ ይደግፋል፡፡
   ሠ) በከተማ ማልማት ምክንያት የተነሱ ባለይዞታዎች ያሉበትን የኑሮ ሁኔታ

ጥናት ያካሂዳል፣ ለታዩ ችግሮች መፍትሄ ይሰጣል።

2. የግብርና ሚኒስቴር

ሀ) የገጠር መሬትን የሚመለከቱ የአዋጁን ድንጋጌዎች በክልሎች መከበራቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል

ለ) የገጠር ተነሺዎችን በማቋቋም ሥራ ላይ ድጋፍ ያደርጋል፣

ሐ) ክልሎች፣ አዲስአበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች አዋጁን ማስፈጸም እንዲችሉ የቴክኒክና አቅም ግንባታ ድጋፍ ያደርጋል፣

23.<u>የክልሎች፣ የአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ይህንን አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈፀም የሚወጣውን ደንብ እና መመሪያዎች በክልሉ፣ በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች ወይም ከተሞች እንዲፈጸሙ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣
2. የመልሶ ማቋቋሚያ ማዕቀፍ ይቀርጻል፣ ይተገብራል።ይህን ማዕቀፍ የሚተገብር እና የሚመራ ራሱን የቻለ ተቋም ይቋቋማል ወይም ካሉት ተቋሞች ይህንን ሀላፊነት የሚወጣ ይሰየማል፣
3. ከተሞችና ወረዳዎች አዋጁን ማስፈጸም እንዲችሉ የአቅም ግንባታ ድጋፍ ያደርጋል፡
4. በልማት ምክንያት የተነሱ አካላት ያሉበትን የኑሮ ሁኔታ ጥናት ያካሂዳል፣ለተለዩ ችግሮች መፍትሄ ይሰጣል፡፡

24.<u>የወረዳ እና የከተማ አስተዳደር ኃላፊነት</u>

1. ተነሺዎችን ስለልማቱ አይነት፣ጠቀሜታና አጠቃላይ ሂደቱ ላይ ግልጽ ውይይት በማድረግ እንዲሳተፉ ያደርጋል፣
2. መሬት እንዲለቁ ለተደረጉ ባለይዞታዎች ተገቢውን ካሣ ይከፍላል ወይም እንዲከፈል ያደርጋል፣
3. የመልሶ ማቋቋሚያ ማዕቀፍን ስራ ላይ ያውላል፣
4. ካሣ ተከፍሎበት እንዲለቀቅ በተወሰነ መሬት ላይ የሚገኘውን ንብረት በሚመለከት የተሟላ መረጃ ይይዛል፣
5. ተነሺ አርሶ እና/ወይም አርብቶ አደሮች ኑሮአቸው እንዲሻሻል የድጋፍና ክትትል ሥራዎችን ይሠራል፣
6. ተነሺዎችን የተመለከተ መረጃና ማስረጃ አደራጅቶ ይይዛል፡፡

**25.ተጠያቂነት**

በዚህ አዋጅ የተቀመጡ ግዴታዎችን በህጉ አግባብና በወቅቱ ያልተገበረ ማንኛውም ግለሰብ፣ ተቋም እና የተቋም ሀላፊ አግባብ ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**26.ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም ደንብ ያወጣል፡፡
2. ክልሎች፤ አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች ይህንን አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚወጣ ደንብ ለማስፈጸም መመሪያ ያወጣል፡፡

**27.የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

ይህ አዋጅ ከመፅደቁ በፊት ክስ ቀርቦባቸው ውሳኔ ያላገኙ ጉዳዮች በቀድሞው አዋጅ 455/1997 መሠረት ይስተናገዳሉ፡፡

**28.የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

1. ለህዝብ ጥቅም ሲባል መሬት የሚለቀቅበትንና ለንብረት ካሣ የሚከፈልበትን ሁኔታዎች ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 455/1997 በዚህ አዋጅ ተሽሯል።
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ አዋጅ ውስጥ ተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**29. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ መስከረም 12 ቀን 2012 ዓ.ም**

**ሳህለ ወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

# ደንብ 472/2012

## ለህዝብ ጥቅም ሲባል መሬት ሲለቀቅ ስለሚከፈል ካሳ እና ተነሺ ስለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 በአንቀጽ 5 እና ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትን፣ ካሣ የሚከፈልበትን እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1161/2011 አንቀጽ 26(1) መሠረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "ለህዝብ ጥቅም ሲባል መሬት ሲለቀቅ ስለሚከፈል ካሳ እና ተነሺ ስለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 427/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

   1. "አዋጅ" ማለት ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትን፣ ካሣ የሚከፈልበትን እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 1161/2011 ነው፤
   2. "ሰብል" ማለት በአንድ አዝመራ ወቅት የሚዘራ ወይም የሚተከል እና የሚሰበሰብ ማንኛውም እጽዋት ነው፤
   3. "የደረሰ ሰብል" ማለት በመሬት ላይ ተዘርቶ ወይም ተተክሎ የሚገኝና ሊሰበሰብ የሚችል ሰብል ነው፤
   4. "ቋሚ ተክል" ማለት ወቅቱን ጠብቆ ለዓመታት ምርት የሚሰጥ ተክል ነው፤

5. "ቤት" ማለት በገጠር ወይም በከተማ ለመኖሪያ፣ ለማምረቻ፣ ለንግድ፣ ለማህበራዊ ወይም ለሌላ አገልግሎት የተሰራ ወይም በመሠራት ላይ ያለ ማንኛውም ግንባታ ነው፡፡
6. "ወቅታዊ የአካባቢ የገበያ ዋጋ" ማለት ማንኛውም ንብረት በሚነሳበት ጊዜ ንብረቱ በሚገኝበት አካባቢ ባለው ገበያ ሊያወጣ ወይም ሊያስከፍል የሚችለው ዋጋ ነው፡፡
7. "ቅድሚያ የማልማት መብት" ማለት ለልማት በተፈለገ ቦታ ላይ በግል ወይም በጋራ ለቦታው በፀደቀው ዝርዝር የማስፈጸሚያ ፕላን መሰረት ለማልማት ቦታው ለሌላ አልሚ ከመሰጠቱ በፊት ለባለይዞታው የሚሰጥ የማልማት መብት ነው፡፡
8. "የተመዘገበ ባለሙያ" ማለት ስልጣን ባለው አካል ተመዝግቦ በዲዛይን ወይም በኮንስትራክሽን የባለሙያነት ወይም የአማካሪነት የምዝገባ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ነው፡፡
9. "ዝቀተኛ የቤት ደረጃ" ማለት በክልል ወይም በከተሞች ፕላን መሠረት ለመኖሪያ የተፈቀደ አነስተኛው የቤት ደረጃ ነዉ፡፡
10. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47(1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል እና የሲዳማ ክልል ነው፡፡
11. በአዋጁ የተሰጡት ትርጓሜዎች በሙሉ በዚህ ደንብ ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## ክፍል ሁለት

## መሬት ለማስለቀቅ ስለሚፈፀም ሥነ-ሥርዓት

### 3. የሚለቀቀው መሬት ለሕዝብ ጥቅም መሆኑን ስለማወያየት

በአዋጁ የህዝብ ጥቅም የመወሰን ስልጣን የተሰጠው አካል መሬቱ ለሕዝብ ጥቅም እንዲለቀቅ ከመወሰኑ በፊት በከተማ ወይም በወረዳዉ ዉስጥ የሚገኙ እንደ መሰረተ ልማት ዘርጊ ተቋማት፤ የፍትህ አካላት፤ ወጣቶች፣ ሴቶችና አካል ጉዳተኞች ላይ የሚሰሩ ተቋማት እና ከስራዉ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉ መሰል ባለድርሻ አካላት እና በሚለቀቀዉ መሬት ላይ መብት ያላቸዉ የልማት ተነሺዎችን ማወያየት አለበት፡፡

### 4. የልማት ተነሺዎች ዉይይት ስነ ስርዓት

በሚለቀቀዉ መሬት ላይ መብት ያላቸዉ የልማት ተነሺዎች ውይይት በሚከተለው ሥነ-ሥርዓት ይፈጸማል፡-

1. ጥሪው ለሁሉም የልማት ተነሺዎች በደብዳቤ መድረስ አለበት፤ ለመድረሱም ማረጋገጫ ሊኖር ይገባል፡፡

2. በመጀመሪያው ጥሪ የሚደረገው ውይይት መካሔድ ያለበት ቢያንስ ከልማት ተነሺዎቹ ሶስት አራተኛው በተገኙበት መሆን አለበት፡፡
3. በንኡስ አንቀጽ 2 በተደረገው ጥሪ ሶሰት አራተኛው ካልተገኙ ሁለተኛ ጥሪ ተደርጎ በዚህ ጥሪ ቢያንስ ግማሽ የሚሆኑት በተገኙበት ውይይት መካሔድ አለበት፡፡
4. በንኡስ አንቀጽ 3 በተደረገው ጥሪ ግማሽ የሚሆኑት ካልተገኙ ሶስተኛ ጥሪ ተደርጎ በተገኙት የልማት ተነሺዎች ውይይቱ ይደረጋል፡፡
5. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2፣ 3 እና 4 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ሀገራዊ ወይም ክልላዊ ፋይዳ ላለዉ አስቸኳይ ልማት መሬት እንዲለቀቅ ከተወሰነ ተነሺዎች ከመነሳታቸው ከ6 ወር በፊት ውይይቱ ይደረጋል፡፡
6. የልማት ተነሺዎች ዉይይት የጾታ የዕድሜና የአካል ጉዳት ሁኔታ ያገናዘበ መሆን አለበት፡፡ ዝርዝር አፈጻጸሙ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

5. <u>የአገልግሎት መስመሮች ስለሚነሱበት ስርዓት</u>
   1. መሬት ለሕዝብ ጥቅም በሚለቀቅበት ጊዜ የወረዳው ወይም የከተማው አስተዳደር:-
      ሀ) በሚለቀቀው መሬት ላይ የአገልግሎት መስመር መኖሩን ለማረጋገጥ ለሚመለከታቸው መሰረተ ልማት ተቋማት በጽሁፍ ጥያቄ ማቅረብ፣
      ለ) ጥያቄውን ለማቅረብ ተገቢው ቅድመ ዝግጅት መጠናቀቁን ማረጋገጥ አለበት፡፡
   2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1(ሀ) መሰረት በጽሁፍ ጥያቄ የደረሰው የአገልግሎት መስመር ባለቤት የንብረቱ ዝርዝር መረጃና የካሳ ግምቱን ጥያቄዉ ከደረሰዉ ቀን ጀምሮ ባሉት ሰላሳ የሥራ ቀናት ዉስጥ ቦታው እንዲለቀቅለት ለተወሰነለት አካል እና ለወረዳው ወይም የከተማው አስተዳደር በጹሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡
   3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት የቀረበው የካሳ ግምት ላይ ከፋዩ ቅሬታ ካለው ቅሬታውን የካሳ መጠኑ ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ ባሉት አሥር (10) የሥራ ቀናት ውስጥ ስልጣን ለተሰጠው አካል ማቅረብ አለበት፡፡
   4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3 መሰረት ቅሬታ የተፈጠረው በሁለት የአገልገሎት መስመር ባለቤት ተቋማት መካከል ከሆነ ቅሬታው የሚቀርበው ስልጣን ለተሰጠው አካል ይሆናል፡፡
   5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት የወረዳው ወይም የከተማው አስተዳደር ካሳውን ለአገልግሎት መስመሩ ባለቤት በሰላሳ (30) ቀናት ውስጥ መክፈል አለበት፡፡

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሰረት የአገልግሎት መስመሩ ባለቤት ክፍያው በተፈጸመለት በስልሳ (60) ቀናት ውስጥ ካሳ የተከፈለበትን የአገልግሎት መስመሩን አጠናቆ በማንሳት ወይም በማዛወር መሬቱን መልቀቅ አለበት፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የአገልግሎት መስመሩ የሚዛወር ከሆነ የመስመሩ ባለቤት ለማዛወር የተቀመጠውን ጊዜ ገደብ ማክበር ግዴታ የሚሆነው መስመሩ የሚዘረጋበት ቦታ ከሶስተኛ ወገን ንብረት ነጻ መደረጉን የወረዳው ወይም የከተማው አስተዳደር እንዲያውቅ ካደረገ ነው፡፡
8. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 6 እንደተጠበቀ ሆኖ የሚነሳው የአገልግሎት መስመር ውስብስብነት ያለው ከሆነ የአገልግሎት መስመሩ ባለቤት ክፍያው በተፈፀመ በ120 (አንድ መቶ ሀያ) ቀናት ውስጥ አጠናቆ ማንሳትና መሬቱን መልቀቅ አለበት፡፡
9. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 7 መሰረት የማስለቀቂያ ትዕዛዝ የደረሰው የአገልግሎት መስመር ባለቤት በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያለበቂ ምክንያት መሬቱን ነጻ አድርጎ ካላስረከበ የከተማ ወይም የወረዳው አስተዳደር መሰረተ ልማቱን ሙያው በአላቸው እዲነሳ በማድረግ መሬቱን ነጻ ያደርጋል፡፡ መስመሩን ያላነሳው የአገልግሎት መስመር ባለቤት ተቋም ለሚደርሰው ጉዳትና ለተጨማሪ ወጪው ተጠያቂ ይሆናል፡፡
10. ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል ተሸካሚ መስመር በሚያልፍባቸዉ ቦታዎች ለምሰሶ መትከያ በቋሚነት ከሚወሰደዉ ቦታ ዉጪ ያሉና ገደብ ወይም ክልከላ ለተጣለባቸዉ ይዞታዎች ካሳ አይከፈልም፡፡
11. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 10 ቢኖርም መስመር የሚያልፍባቸዉ ቦታዎች ላይ የሚገኝ ቋሚ ንብረት ካለ እና በዝርጋታ ወቅት የሚነሳ ከሆነ ካሳ መከፈል አለበት፡፡
12. መሬት እንዲለቀቀለት የተወሰነለት የመሠረተ ልማት ዘርጊ ተቋም ለካሳ ክፍያ የሚሆን ገንዘብ ለክልሉ፣ ለአዲስ አበባ ወይም ለድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ገቢ ማድረግ አለበት፡፡
13. ለመሰረተ ልማት ግንባታ በተፈቀደ ቦታ ላይ የሌላ ተቋም የአገልግሎት መስመር በሚኖርበት ጊዜ የካሳ ግምቱን ለአገልግሎት መስመሩ ባለቤት በቀጥታ በመክፈል ለወረዳው ወይም ለከተማዉ ማሳወቅ አለበት፡፡

6. <u>ካሳ የተከፈለበት መሬትን ወሰን ስለማስከበር</u>

1. ክልሉ ወይም አዲስ አበባ ወይም ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ገቢ የተደረገላቸዉን የንብረት ካሳ ገንዘብ ለባለንብረቶች ክፍያ በመፈጸም የወሰን ማስከበር ሥራ ማጠናቀቅ አለባቸው፡፡
2. የመሠረተ ልማት ዘርጊ ተቋማት መሰረተ ልማት ለመዘርጋት ውል ከመዋዋላቸው በፊት ካሳ የተከፈለበት መሬት ወሰን መከበሩን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

7. **<u>መሬት እንዲለቀቅለት የተወሰነለት አካል ኃላፊነት</u>**

1. የካሣ እና መልሶ ማቋቋም ወጪ ሸፍኖ መሬት እንዲለቀቅለት የተወሰነለት አካል የከተማ ወይም ወረዳ አስተዳደር የወጪዉን መጠን ካሳወቀበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ዉስጥ ገንዘቡን ለከተማዉ ወይም ለወረዳዉ አስተዳደር ገቢ ማድረግ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገዉ ቢኖርም በሁለት የአገልግሎት መስመር ባለቤት መካከል የካሳ ክፍያ የሚደረግ ከሆነ ለአገልግሎት መስመሩ ባለቤት ለሚነሳው ወይም ለሚዛወረው የአገልግሎት መስመር የካሳ ክፍያውን በሰላሳ ቀን ውስጥ ከፍሎ መክፈሉን ለከተማዉ ወይም ለወረዳዉ አስተዳደር ማሳወቅ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገገዉ ባለመፈፀሙ የመሬት ማስለቀቅ ሂደቱ ቢጓተት ኃላፊነቱ የመሬት ጠያቂዉ አካል ይሆናል፡፡
4. መሬቱ ከተለቀቀለት በኋላ በወቅቱ ባለማልማቱ ስለሚወሰድ እርምጃ ባለው የመሬት አስተዳደር ሕግ መሰረት የሚወሰን ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>ቅድሚያ የማልማት መብት</u>

8. **<u>ቅድሚያ የማልማት መብት አወሳሰን የወል ድንጋጌዎች</u>**

1. በባለይዞታዎች ቅድሚያ የማልማት ጥያቄ ሊቀርብ የሚችለው፡-
   ሀ) በልማት ፕላኑ መሰረት ቦታው በነባር ባለይዞታዎች መልማት የሚችል መሆኑ በወረዳ አስተዳደር ወይም በከተማ አስተዳደር ከተረጋገጠ፣
   ለ) ቦታዉ የተፈለገው ሀገራዊ ወይም ክልላዊ ፋይዳ ላለዉ ልማት፣ በመንግሥት ለሚሰራ መሰረተ ልማት፣ ለአገልግሎት መስመር፣ አረንጓዴ ቦታ ወይም ለዉስብስብ መሰረተ ልማቶች ካልሆነ፣
   ሐ) በቦታው ላይ የሚከናወነው ኢንቬስትመንት በግል ወይም በጋራ ለማልማት

የተፈቀደ ከሆነ፤

ነው፡፡

2. በግል ወይም በጋራ ቅድሚያ የማልማት ጥያቄ የሚቀርበው ቦታው ለልማት እንደሚፈለግ ከነዋሪዎች ጋር ውይይት ከተደረገበት ጀምሮ ባሉ 30 (ስልሳ) የሥራ ቀናት ውስጥ መሆን አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት ጥያቄ ካልቀረበ ነዋሪዎቹ ቅድሚያ የማልማት ፍላጎት እንደደሌላቸው ይቆጠራል፡፡
4. ቅድሚያ የማልማት ጥያቄን ተቀብሎ ውሳኔ የሚሰጥ አካልና የሚፈጽምበት አሰራር ስርዓት በመመሪያ ይወሰናል፡፡

9. <u>**በከተማ ቅድሚያ የማልማት መብት የሚፈቀድበት ሁኔታ**</u>

1. ለከተማ ባለይዞታዎች በግል ወይም በጋራ ቅድሚያ የማልማት መብት የሚፈቀደው፡-
   ሀ) ተነሺው ለልማት በተፈለገው ቦታ ላይ ህጋዊ ባለይዞታ ከሆነ፤
   ለ) በግል ለማልማት ተነሺው የያዘው የመሬት መጠን ቅርፅን ታሳቢ ሳያደርግ በዝርዝር ፕላኑ ከተቀመጠዉ አነስተኛ ስፋት እኩል ወይም በላይ ሲሆን፤
   ሐ) በጋራ ለማልማት የፈለጉት ባለይዞታዎች የያዙት የመሬት መጠን ቅርፅን ታሳቢ ሳያደርግ በድምሩ በዝርዝር ፕላኑ ከተቀመጠዉ አነስተኛ የሽንሻኖ መጠን እኩል ወይም በላይ ሲሆን፤
   መ) ቅድሚያ የማልማት ጥያቄ ያቀረቡት ይዞታ የመሬት አጠቃቀም አገልግሎት በዝርዝር ፕላኑ የተፈቀደ የመሬት አጠቃቀም አገልግሎት ሲሆን፤
   ሠ) በዝርዝር ፕላኑ መሠረት በግል ወይም በጋራ ለመገንባት አቅም እንዳላቸው መጠኑ በቦታዉ ለሚደረገዉ ግንባታ ከሚያስፈልገዉ ወጭ 10 በመቶ ያላነሰ የአቅም ማሳያ በዝግ ሂሳብ ሲያስቀምጡ ወይም የግል ገንዘብ ዝዉዉር ማስረጃ ወይም ከዚህ ገንዘብ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ንብረት ግምት በማስያዣነት ሲያቀርቡ፤
   ረ) የቦታዉ ነባር ባለይዞታ በግል ወይም በጋራ የሚያቀርበዉ የልማት ዕቅድ በቦታው ሊሰራ ከሚጠበቀው ልማት ዕቅድ አንጻር እኩል ወይም የተሻለ ልማት የሚያመጣ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

ሰ) ቦታው በተዘጋጀው ፕላንና በተቀመጠዉ የግንባታ የጊዜ ገደብ ዉስጥ በፕላን የተፈቀደውን ግንባታ ገንብቶ ለማጠናቀቅ ከተማዉ እና አልሚው ዉል ሲገቡ ይሆናል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (መ) የተደነገገው ቢኖርም የሚለማው ቦታ አገልገሎት ቅይጥ ከሆነ ቅድሚያ የማልማት መብት ጠያቂዎች ይዞታ የመሬት አጠቃቀም አገልግሎቱ ቅይጥ ወይም የመኖሪያ ወይም የንግድ ሊሆን ይችላል፡፡
3. በተናጠልም ሆነ በጋራ ቅድሚያ ለማልማት የጠየቁት ሴቶች ወይም አካል ጉዳተኞች ሲሆኑ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1(ሠ) የተጠቀሰዉን መሥፈርት የከተማዉ አስተዳደር የሴቶችንና አካል ጉዳተኞችን ልዩ ድጋፍ ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መልኩ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ዝርዝር አፈጻጸም በመመሪያ ይወሰናል፡፡

10.<u>በከተማ በመልሶ ማልማት በተከለለዉ ቦታ ላይ ቅድሚያ የማልማት መብት አወሳሰን</u>

1. የከተማ አስተዳደሩ ቅድሚያ ለማልማት ጥያቄ ላቀረቡ ተነሺዎች ውሳኔ ለመስጠት በአንቀጽ 7 እና 8 የተዘረዘሩት መሟላታቸዉን ማረጋገጥ አለበት፡፡
2. ለቦታው በተዘጋጀው ዝርዝር ፕላን የተፈቀደው የቁራሽ መሬት ብዛት እና ቅድሚያ የማልማት መብት ኖሯቸው ቅድሚያ ለማልማት ጥያቄ ያቀረቡ ተነሺዎች ቁጥር ተመጣጣኝ ካልሆነ በጋራ ተደራጅተዉ የሚያለሙበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡
3. ቅድሚያ የማልማት ጥያቄ ላቀረቡ ነባር ባለይዞታዎች የከተማ አስተዳደሩ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ መወሰንና የተወሰነውን ውሳኔ በ7 የስራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡
4. ቅድሚያ ለማልማት ጥያቄ ያቀረበ ባለይዞታ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (3) በተቀመጠዉ ጊዜ መልስ ካላገኘ ወይም በተሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ ካለዉ በዚህ ደንብ አንቀጽ 39 መሠረት ቅሬታዉን ማቅረብ ይችላል፡፡
5. ቅድሚያ የማልማት መብት የተሰጣቸዉ የማልማት ክትትልና ዉሳኔ አሰጣጥ ዝርዝር በመመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

11.<u>በገጠር ቅድሚያ የማልማት መብት አወሳሰን</u>

1. በገጠር ለግብርና ስራ ለልማት የሚፈለግ ቦታ ላይ ያሉ ባለይዞታዎች በፕላን የተፈቀደውን የግብርና ልማት በግል ወይም በጋራ ቅድሚያ የማልማት መብት

የሚሰጣቸዉ በዝርዝር ፕላኑና በተቀመጠዉ የልማት የጊዜ ገደብ ዉስጥ በግል ወይም በጋራ ለማከናወን ከወረዳዉ አስተዳደር ጋር ዉል ሲገቡ ይሆናል፡፡

2. ቅድሚያ ለማልማት ጥያቄ ላቀረቡ ተነሺዎች ውሳኔ ለመስጠት በዚህ ደንብ አንቀጽ 7 እና 8 የተዘረዘሩት መሟላታቸዉን መረጋገጥ አለበት፡፡
3. ለቦታው በተዘጋጀው ዝርዝር ፕላን የተፈቀደው የቁራሽ መሬት ብዛት እና ቅድሚያ የማልማት መብት ኖሯቸው ቅድሚያ ለማልማት ጥያቄ ያያቀረቡ ተነሺዎች ቁጥር ተመጣጣኝ ካልሆነ በጋራ ተደራጅተዉ የሚያለሙበት አማራጭ ይሰጣቸዋል፡፡
4. ቅድሚያ የማልማት ጥያቄ ላቀረቡ ነባር ባለይዞታዎች የወረዳ አስተዳደሩ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ መወሰንና የተወሰነውን ውሳኔ በ7 ሰባት የስራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡
5. ቅድሚያ የማልማት መብት የተሰጣቸዉ የማልማት ክትትልና ዉሳኔ አሰጣጥ ዝርዝር በመመሪያ ይወሰናል፡፡

12. <u>ቅድሚያ የማልማት መብት የተሠጠው ባለይዞታ ግዴታ</u>

1. ቅድሚያ የማልማት መብት ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ እስከ 6 ወር ጊዜ ዉስጥ አስፈላጊዉን ሁኔታ አሟልቶ ወደ ልማት መግባት አለበት፤
2. በዚህ ደንብ አንቀጽ 8 እና 9 የተቀመጠዉን ካላሟላ ካሳ ተክፍሎት መሬቱን ያስረክባል፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ያሏማለበት ምክንያት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከሆነ ተጨማሪ እስከ ሦስት ወር የሚደርስ ጊዜ ሊሰጠዉ ይችላል፤

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የካሣ አወሳሰን፤ አተማመንና ቀመር</u>

### <u>ንዑስ ክፍል አንድ</u>

### <u>የንብረት ካሳ አወሳሳንና ቀመር</u>

13. <u>ንብረት የሚገምት አካል</u>

1. የንብረት ግመታ ፍቃድ ባለው የግል ድርጅት ወይም ግለሰብ መከናወን አለበት፡፡
2. ፍቃድ ያለው የግል ድርጅት ወይም ግለሰብ ከሌለ፣ የክልሎች፤ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ መንግሥታዊ የሆነ ተቋም አቋቁመው የንብረት ካሳ ግምት ስራ ይሰራሉ፡፡

3. የሚቋቋሙት መንግሥታዊ ተቋማት እንደአስፈላጊነቱ ለአስተዳደር በሚያመች ቦታ ሊደራጁ ወይም ቅርንጫፍ ሊኖራቸው ይችላል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 እና 3 መሰረት የሚቋቋመው ገማች ተቋም የካሳ ክፍያና መልሶ ማቋቋም ስራ ከሚሰራው የስራ ክፍል ወይም ተቋም ተለይቶ መደራጀት አለበት፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 እና 3 መሰረት የሚቋቋመው የመንግስት የንብረት ካሳ ገማች ተቋም ሥራውን የሚያከናውንበት የአሠራር ሥርዓት በመመሪያ ይወሰናል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት ካሣውን የሚገምት ድርጅት ወይም ግለሰብ ወይም መንግሥታዊ ተቋም ከሌለ የወረዳው ወይም የከተማው አስተዳደር ገማች ኮሚቴ በማቋቋም የሚገምት ይሆናል፡፡
7. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 6 እንደተጠበቀ ሆኖ የንብረት ግመታ ስራ የሚሰራ በቂ የግል ድርጅት ወይም የሙያ ፈቃድ ያለዉ ግለሰብ መፍራታቸዉ እና መሟላታቸዉ ሲረጋገጥ የኮሚቴ ስራ እንዲቀር ይደረጋል፡፡

14.<u>ንብረት ገማች ኮሚቴ ስለማቋቋም</u>

1. የንብረት ገማች ኮሚቴ ሲቋቋም እንደሚገመተው ንብረት ዓይነት ተገቢው ሙያ ያላቸውን እንዲሁም ጾታንና ዕድሜን ግንዛቤ ዉስጥ ማስገባት አለበት፡፡
2. የሚገመተው ንብረት ባለበት ገጠር ወረዳ ወይም ከተማ ኮሚቴውን ለማዋቀር ተገቢ ሙያ ያላቸው ባለሙያዎች ማግኘት ካልተቻለ ከፍ ካለው የአስተዳደር እርከን ባለሙያ በመሳብ ወይም በክልል ደረጃ ኮሚቴ በማዋቀር ግምቱን እንዲሰራ ያደርጋል፡፡
3. የኮሚቴው አባላት የሙያና የጾታ ስብጥር እና ብዛት፤ ኮሚቴዉ ሥራውን የሚያከናውንበት የአሠራር ሥርዓትና ተያያዥ ጉዳዮች በመመሪያ ይወሰናል፡፡

15.<u>የንብረት ካሳ</u>

1. ለንብረት ካሳ ከመከፈሉ በፊት የተገመተዉ ግምት ለህዝብ ይፋ መሆን አለበት፡፡
2. የንብረት ግምት /ለህዝብ ለአምስት የስራ ቀን ይፋ ከሆነ በኋላ በከተማ ከንቲባ ወይም በወረዳ አስተዳዳሪው መፅደቅ አለበት፡፡
3. የሚነሳው ንብረት የመኖሪያ ቤት ከሆነ የሚከፈለው አነስተኛ የካሣ መጠን እንደየክልሉ፤ እንደ አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ተጨባጭ ሁኔታ ወይም ክልሉ፤

አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ባወጡት ደረጃ መሰረት ቢያንስ ዝቅተኛውን የቤት ደረጃ ሊያስገነባ የሚችል መሆን አለበት፡፡

4. የሚፈርሰው ንብረት በከፊል ከሆነና ባለይዞታው በቀሪው ቦታ ላይ ለመቆየት ከመረጠና ቀሪው ቦታ በሚዘጋጀው ዝርዝር ፕላን በቂ መሆኑ ተቀባይነት ካለው ለፈረሰው ንብረት ብቻ ካሣ ይከፈላል፡፡
5. ለልማት የተፈለገው ቦታ ሲወሰድ በቦታው ላይ ለመሰብሰብ የደረሰ ሰብል ካለ ባለንብረቱ በሚሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሰብስቦ ማንሳት አለበት፡፡
6. በአስቸኳይ ሁኔታ ቦታዉ የሚፈለግ ሲሆን ሰብሉ ለመሰብሰብ ያልደረሰ ከሆነ እንደደረሰ ተቆጥሮ የምርቱ መጠን በወቅቱ የአከባቢ የገበያ ዋጋ ተሰልቶ ለባለይዞታዉ ካሳ ተከፍሎት እንዲለቅ ይደረጋል፡፡
7. ካሳ የተከፈለባቸዉ ንብረቶች የካሳ ከፋዩ ንብረት ይሆናሉ፡፡

16.<u>የቤት ካሣ አተማመንና ቀመር</u>

1. የቤት ካሣ የሚሰላዉ:-

ሀ) የሚፈርሰው ቤት የግንባታ ቁስ ለመተካት የሚያስችል ወቅታዊ የገበያ ዋጋ እና በምትክ ቦታው ላይ ተመሳሳይ ቤት ለመገንባት የሚያስፈልግ የወቅቱን የባለሙያ እና የጉልበት ዋጋ፡፡

ለ) ከቤቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የግቢ ንጣፍና ማስዋብ፣ በረንዳ፣ ሴፕቲክታንክ ሌሎች ግንባታዎችን ለመስራት የሚያስፈልገውን የወቅቱ የአካባቢው የገበያ ዋጋ፤

ሐ) ቤቱ በመነሳቱ ምክንያት የተገነቡ የአገልገሎት መስመሮችን ለማፍረስ፣ ለማንሳት፣ መልሶ ለመገንባት፣ ለመትከልና ለማገናኘት የሚያስፈልጉትን ወጪዎች ግምት፤

ታሳቢ በማድረግ ይሆናል፡፡

2. የሚፈርሰው ቤት የግንባታ ቁስ በወቅቱ በገበያ የማይገኝ ከሆነ በተቀራራቢ ቁስ ዋጋ ይሰላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም የሚፈርሰው ቤት የተገነባው በሊዝ ይዞታ ላይ ከሆነና ተነሺው ምትክ ቦታ የማይፈለግ ከሆነ ከቤቱ ካሳ በተጨማሪ የከፈለው የቀሪ ዘመን የመሬት ሊዝ ክፍያ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

4. የቤት ካሣ የሚሰላው የሚፈርሰውን ቤት ለመተካት የሚያስችል ወቅታዊ የአካባቢው የካሬ ሜትር ወይም የነጠላ ዋጋ በማውጣት ይሆናል፡፡

| |
|---|
| ቤት ካሣ = የወቅቱ የግንባታ ወጪ + የመሬቱ ቋሚ ማሻሻያ ወጪ |

17.**አጥር ካሣ አተማመንና ቀመር**

የአጥር ካሣ የሚሰላው፡-

1. ከሚፈርሰው አጥር ጋር በዓይነቱ ተመጣጣኝ የሆነ አጥር በአዲስ ለመስራት የሚያስፈልገውን የወቅቱን የካሬ ሜትር ወይም የሜትር ኩብ ዋጋ በማስላት፤
2. የአጥሩን የግንባታ ቁስ በካሬ ሜትር ወይም በሜትር ኩብ መገመት የማይቻል ከሆነ ነጠላ ዋጋ በማውጣት ይሆናል፡፡

| |
|---|
| የአጥር ካሣ = የአጥሩ የካሬ ሜትር/ሜትር ኩብ<br>ነጠላ ዋጋ x የአጥሩ መጠን በካሬ ሜትር/ሜትር ኩብ |

18.**ተዛውሮ የሚተከል ንብረት ካሣ አተማመንና ቀመር**

1. ንብረቱ ከሚገኝበት ስፍራ ወደ ሌላ አካባቢ ተዛውሮ እንደገና ሊተከልና አገልግሎት መስጠት የሚችል ከሆነ የሚከፈለው የማንሻ፣ የማጓጓዣና መልሶ የመትከያ ክፍያዎች ንብረቱን የመንቀያ፣ የመጫኛ፣ የማውረጃ፣ የመቀጠያ እና ተያያዥ ወጪዎች ያካትታል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የካሳ ግምቱ ከመሰራቱ በፊት ንብረቱ ተዛውሮ መተከል የሚችልና የማይችል መሆኑ በባለሙያ መረጋገጥ አለበት፡፡
3. ንብረቱ ሲነሳ ጉዳት የሚደርስባቸው የንብረቱ ክፍሎች መኖራቸው በባለሙያ ከተረጋገጠ ለመተካት ወይም ለመጠገን የሚያስፈልግ ወጪ መከፈል አለበት፡፡

| |
|---|
| ተዛውሮ የሚተከል ንብረት ካሣ= የንብረቱ መንቀያ + የንብረቱ የማንሻ ወይም መጫኛ + የንብረቱ ማጓጓዣ + የማውረጃ + የንብረቱ መልሶ መትከያ እና ወይም የመቀጠያ ወጪ |

19.**የሰብል ወይም የአትክልት ካሳ አተማመንና ቀመር**

1. ሰብሉ ወይም/እና አትክልቱ ቦታው በሚለቀቅበት ወቅት የደረሰ ከሆነ ባለይዞታው በሚሰጠው የጊዜ ገደብ ሰብሉን ወይም አትክልቱን ሰብስቦ ሊወሰድ ይችላል፡፡

2. ቦታው በአስቸኳይ ከተፈለገና ሰብሉን ወይም አትክልቱ የደረሰ ሆኖ ለመሰብሰብ በቂ ጊዜ ካልተሰጠው በአካባቢው ከሚገኝ ተመሳሳይ ሰብል ወይም አትክልት የሚገኘውን የአንድ አመት የምርት መጠን በወቅታዊ የአካባቢው የገበያ ዋጋ ተሰልቶ ይከፈለዋል፡፡
3. ሰብሉ ወይም አትክልቱ የደረሰ ካልሆነ የሚከፈለው ካሳ ሰብሉ ወይም አትክልቱ ለመሰብሰብ ደርሶ ቢሆን ኖሮ ሊሰጥ የሚችለውን የምርት መጠንና ምርቱ ሊያወጣ ይችል የነበረውን ወቅታዊ የአካባቢው የገበያ ዋጋ መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በተደነገገው መሰረት ካሳ ሲሰላ ሰብሉ ወይም አትክልቱ ለመሰብሰብ እስኪደርስ ባለንብረቱ ሊያወጣ የሚገባዉ ወጪ ተቀናሽ ይደረጋል፡፡
5. የሰብል ተረፈ ምርት ካሳ የሚተመነው የተረፈ ምርቱን ወቅታዊ የአካባቢው የገበያ ዋጋ መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡
6. በአንድ የእርሻ ቦታ በአንድ አመት ውስጥ ከአንድ ጊዜ በላይ ምርት የሚመረት ከሆነ የአመቱ የእርሻ ቦታው የምርት መጠን በአመቱ ውስጥ የተመረተው ምርት ድምር ይሆናል፡፡

| |
|---|
| **ሰብል ካሳ** = (የቦታው ስፋት በሄክታር x የሰብሉ የአካባቢው ወቅታዊ የገበያ ዋጋ በኩንታል x በአንድ ሄክታር ስፋት ላይ የሚገኝ ምርት በኩንታል) + የመሬቱ ቋሚ ማሻሻያ ወጪ |
| **የሰብል ተረፈ ምርት ካሳ** = (የቦታው ስፋት በሄክታር x በአንድ ሄክታር የሚገኝ ተረፈ ምርት በኩንታል x የተረፈ ምርቱ የአካባቢው ወቅታዊ የገበያ ዋጋ በኩንታል) |

20. <u>ፍሬ የሚሰጥ ቋሚ ተክል ካሳ አተማመን</u>

1. ቦታው በሚለቀቅበት ወቅት የቋሚ ተክሉ ፍሬ የደረሰ ከሆነ ባለንበረቱ በሚሰጠው የጊዜ ገደብ ሰብስቦ ሊወስድ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት በሚሰጠው የጊዜ ገደብ አንስቶ መውሰድ ካልፈለገ ለንብረቱ ካሳ ይከፈለዋል፡፡

3. ቦታው በአስቸኳይ ከተፈለገና ለባለንብረቱ የደረሰውን የአንድ ዓመት ፍሬ ለመሰብሰብ በቂ ጊዜ የማይሰጥ ከሆነ በአካባቢው ከሚገኝ ተመሳሳይ ቋሚ ተክል የሚገኘው የአንድ አመት የምርት መጠን በወቅታዊ የአካባቢው የገበያ ዋጋ ተሰልቶ ይከፈለዋል፡፡
4. በንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቋሚ ተክሉን በደረሰበት ደረጃ ለማድረስ የወጣ ወጪ በወቅታዊ የአካባቢው የገበያ ዋጋ ተሰልቶ ይከፈላል፡፡

| |
|---|
| ፍሬ መስጠት የጀመረ ቋሚ ተክል ካሳ = (ከአንድ ዛፍ የሚገኝ የፍሬ መጠን በኪሎ X የአንድ ኪሎ የወቅቱ የገበያ ዋጋ X የዛፉ ብዛት) + ተክሉ በደረሰበት ደረጃ ለማድረስ የወጣ ወጪ + የመሬቱ ቋሚ ማሻሻያ ወጪ<br><br>ፍሬ መስጠት ያልጀመረ ቋሚ ተክል ካሳ= ተክሉ በደረሰበት ደረጃ ለማድረስ የወጣ ወጪ በወቅታዊ ዋጋ + የመሬቱ ቋሚ ማሻሻያ ወጪ |

21. **ፍሬ የማይሰጥ ቋሚ ተክል/ዛፍ ካሳ አተማመንና ቀመር**

1. በሚለቀቀው መሬት ላይ ፍሬ የማይሰጥ ተክል ወይም ዛፍ ያለው ባለንብረት በሚሰጠው የጊዜ ገደብ ሰብስቦ መውሰድ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ፍሬ የማይሰጥ ተክል ወይም ዛፉን በሚሰጠው የጊዜ ገደብ አንስቶ መውሰድ ካልፈለገ ለንብረቱ ካሳ ይከፈለዋል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ፍሬ የማይሰጥ ተክል ወይም ዛፉን ከወሰደ ለማስቆረጫና እና ማጓጓዣ ወጪዎች ያወጣው ወጪ ብቻ ይከፈላል፡፡
4. ቦታው በአስቸኳይ ከተፈለገና ዛፉን ለማንሳት በቂ ጊዜ ካልተሰጠው በአካባቢው ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ተሰልቶ ካሳ ይከፈለዋል፡፡
5. ፍሬ የማይሰጥ ተክል ወይም የዛፍ ካሣ የሚሰላው ፍሬ የማይሰጥ ተክል ወይም የዛፉን የወቅቱን የነጠላ ወይም የካሬ ሜትር በማውጣት ይሆናል፡፡
6. ፍሬ የማይሰጥ ተክል ወይም ዛፉ ለአገልግሎት ያልደረሰ ከሆነ ፍሬ የማይሰጥ ተክል ወይም ዛፉ በሚገኝበት ደረጃ ለማድረስ የሚያስፈልገውን ወጪ በወቅታዊ የአካባቢው የገበያ ዋጋ በማስላት ይከፈላል፡፡

**ፍሬ የማይሰጥ ቋሚ ተክል/ዛፍ ካሣ** = (ትልቅ ዛፍ በቁጥር X የአንድ ዛፍ ወቅታዊ የአካባቢው የገበያ ዋጋ) + (መካከለኛ ዛፍ በቁጥር X የአንድ ዛፍ ወቅታዊ የአካባቢው የገበያ ዋጋ) + (ዝቅተኛ ዛፍ በቁጥር X የአንድ ዛፍ ወቅታዊ የአካባቢው የገበያ ዋጋ) + (ችግኝ/ያልደረሰ ዛፍ በቁጥር X የአንድ ችግኝ/ያልደረሰ ዛፍ ወቅታዊ የአካባቢው የገበያ ዋጋ)+ የመሬቱ ቋሚ ማሻሻያ ወጪ

22.**የሣር ካሣ አተማመንና ቀመር**

1. በሚለቀቀው መሬት ላይ የሚገኘው ሣር ለመሰብሰብ የደረሰ ከሆነ የልማት ተነሺው በሚሰጠው የጊዜ ገደብ ሰብስቦ መውሰድ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ሳሩን ከወሰደ የማጨጃና የማጓጓዣ ወጪ ብቻ ይከፈላል፡፡
3. ቦታው በአስቸኳይ ከተፈለገና ሳሩን ለማንሳት በቂ ጊዜ ካልተሰጠው የሣሩ ግምት በአካባቢው ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ተሰልቶ ካሳ ይከፈለዋል፡፡
4. ሳሩ ለመሰብሰብ ያልደረሰ ከሆነ እንደደረሰ ተቆጥሮ ካሳ ይከፈላል፡፡

**የሣር ካሣ** = ሣሩ የሸፈነው የቦታ ስፋት በካሬ ሜትር X የካሬ ሜትር የሳር ምርት በወቅታዊ የገበያ ዋጋ + የመሬቱ ቋሚ ማሻሻያ ወጪ

23.**ለማዕድን ባለፈቃድ የሚከፈል ካሣ አተማመን**

1. ለማዕድን ሥራ በማዕድን ባለፈቃድ የተያዘ መሬት ሲለቀቅ የሚከፈለው ካሣ አግባብ ባለው የማዕድን ሕግ መሠረት ይሆናል፡፡
2. ማዕድን ለማውጣት ፈቃድ ባልተሰጠው አካል ለተያዘ የማዕድን መሬት ካሳ አይከፈልም፡፡

24.**ለመካነ መቃብርን ስለሚከፈል ካሣ አተማመንና ቀመር**

1. መካነ መቃብር ለማንሳት የሚከፈለው ካሣ መካነ መቃብሩን ለማንሳት፣ ተለዋጭ ማረፊያ ቦታ ለማዘጋጀት፣ አጽሙን ለማዘዋወርና ለማሳረፍ እንዲሁም ከዚሁ ጋር በተያያዘ ለሚደረግ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ሥርዓት ማስፈጸሚያ የሚያስፈልጉትን ወጪዎች ያጠቃልላል፡፡

2. መካነ መቃብር ያለበት ቦታ ለሕዝብ ጥቅም ሲፈለግ የመካነ መቃብሩ ባለቤት በሚሰጠው የጊዜ ገደብ እንዲያነሳ ተደራሽ በሆነ መንገድ እንዲያወቅ መደረግ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የመካነ መቃብሩ ባለቤት ካላነሳ መሬት የሚያስለቅቀው አካል አጽሙ በአግባቡ እንዲነሳና ተለዋጭ ቦታ ላይ እንዲያርፍ ማድረግ ይችላል፡፡

| |
|---|
| **የመካነ መቃብር ካሣ** = ለመካነ መቃብር ማንሻ ወጪ+ ተለዋጭ ማረፊያ ቦታ ማዘጋጃ ወጪ + አጽሙን ለማዛወሪያና ማሳረፊያ + ሃይማኖታዊና ባህላዊ ሥርዓት ማስፈፀ ወጪ |

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የልማት ተነሺ ካሳ አተማመንና ቀመር

### 25.የገጠር የልማት ተነሺ ካሣ አተማመን

1. የገጠር መሬት ባለይዞታ የአንድ ዓመት ገቢ ለማስላት በሚወሰደው መሬት ላይ አመቱን ሙሉ ሰርቶ ሲያገኝ የነበረውን ገቢ ታሳቢ መደረግ አለበት፡፡
2. የልማት ተነሺ ካሳ ሲሰላ ስሌቱ ከተጀመረበት ቀደም ብሎ በነበሩት ሶስት ተከታታይ ዓመታት በየዓመቱ ከመሬቱ ሲያገኝ ከነበረው ከፍተኛውን የአንድ ዓመት ገቢ መረጃ እንደየክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ አግባብነት ካላቸው ሕጋዊ ተቋማት የሚወሰድ ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው የይዞታው አመታዊ ገቢ ማስረጃ ካልተገኘ በአካባቢው ባለ ተመሳሳይ ይዞታና የመሬት ለምነት ደረጃ በሶስት ዓመት ከሚገኘው ከፍተኛው ዓመታዊ ገቢ ይወሰዳል፡፡
4. ከእርሻ መሬት በአካባቢዉ በሄክታር የሚገኘዉን ከፍተኛዉን አመታዊ ገቢ ለማስላት የአከባቢዉ የሄክታር የምርት መጠን መታወቅ አለበት፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት የገጠር ባለይዞታዉ ከመነሳቱ በፊት የሶስት አመት የየአመቱ ምርት መጠን በወቅታዊ ዋጋ ተሰልቶ ከእርሻ መሬቱ ሰብል ከማምረት የሚገኘዉ ገቢ መወሰድ አለበት፡፡
6. እንደየክልሎች ተጨባጭ ሁኔታ በመመሪያ የሚወሰን ለልማት የተፈለገውን መሬት በመጠቀም የሚያገኙ ሌሎች ገቢዎች በአመታዊ ገቢ ይደመራል፡፡

**26.<u>በቋሚነት ለሚነሳ የገጠር መሬት ባለይዞታ የልማት ተነሺ ካሳ አተማመንና ቀመር</u>**

1. ለልማት ተነሺው የሚሰጠው ምትክ ቦታ ከሆነና የሚነሳው የመኖሪያ ቤት ወይም የንግድ ቤት ከሆነ ተመጣጣኝ ምትክ ቤት ለሁለት ዓመት ያለኪራይ ይሰጠዋል ወይም ለፈረሰበት ቤት በወቅታዊ የኪራይ ግምት ተሰልቶ የሁለት ዓመት የልማት ተነሺ ካሣ ይከፈለዋል፡፡
2. በምትክ ቦታ ፋንታ ምትክ ቤት የሚሰጠው ከሆነ ለፈረሰበት ቤት በወቅታዊ የኪራይ ግምት ተሰልቶ የአንድ ዓመት የልማት ተነሺ ካሣ ይከፈለዋል፡፡
3. ወቅታዊ የኪራይ ግምቱ የተነሺውን የመኖሪያ ቤት መነሻ አድርጎ የሚሰላ ይሆናል፡ ፡
4. ዝቅተኛው የቤት ኪራይ፣ የቤት ኪራይ የካሬ ሜትር ዋጋ እና ዝቅተኛው የኪራይ ቤት ደረጃ በመመሪያ ይወሰናል፡፡
5. በቋሚነት ለሚነሳ የገጠር መሬት ባለይዞታ የልማት ተነሺ ካሳ ቀመር

| |
|---|
| ምትክ የእርሻ መሬት ላልተሰጠውና በቋሚነት ለሚነሳ የገጠር ባለይዞታ የልማት ተነሺ ካሳ = ዓመታዊ ገቢ x 15 |

**27.<u>በጊዜያዊነት ለሚነሳ የገጠር መሬት ባለይዞታ የልማት ተነሺ ካሳ ቀመር</u>**

| |
|---|
| ምትክ የእርሻ መሬት ላልተሰጠውና በጊዚያዊነት ለሚነሳ የገጠር ባለይዞታ የልማት ተነሺ ካሳ = በጊዜያዊነት የተለቀቀዉ መሬት በሄክታር x ዓመታዊ ገቢ በሄ/ር x የለቀቀበት ጊዜ መጠን በዓመት |

**28.<u>በቋሚነት ለሚነሳ የከተማ መሬት ባለይዞታ የልማት ተነሺ ካሳ አተማመንና ቀመር</u>**

1. ለልማት ተነሺው የሚሰጠው ምትክ ቦታ ከሆነና የሚነሳው የመኖርያ ቤት ወይም የንግድ ቤት ከሆነ ተመጣጣኝ ምትክ ቤት ለሁለት ዓመት ያለኪራይ ይሰጠዋል

ወይም ለፈረሰበት ቤት በወቅታዊ የኪራይ ግምት ተሰልቶ የሁለት ዓመት የልማት ተነሺ ካሣ ይከፈለዋል፡፡

2. ለልማት ተነሺዉ በምትክ ቦታ ፋንታ ምትክ ቤት የሚሰጠው ከሆነ ለፈረሰበት ቤት በወቅታዊ የኪራይ ግምት ተሰልቶ የአንድ ዓመት የልማት ተነሺ ካሣ ይከፈለዋል፡፡
3. ወቅታዊ የኪራይ ግምቱ የተነሺውን የመኖሪያ ቤት መነሻ አድርጎ የሚሰላ ይሆናል፡፡
4. ዝቅተኛው የቤት ኪራይ፣ የቤት ኪራይ የካሬ ሜትር ዋጋ እና ዝቅተኛው የኪራይ ቤት ደረጃ በመመሪያ ይወሰናል፡፡
5. በቋሚነት ለሚነሳ የከተማ መሬት ባለይዞታ የልማት ተነሺ ካሳ ቀመር

| |
|---|
| ምትክ ቦታ ለወሰደና በቋሚነት ለሚነሳ የከተማ ባለይዞታ የልማት ተነሺ ካሳ = የሚኖርበት ቤት ስፋት በካ. ሜ x የ1 ካሬ ሜ ወቅታዊ የቤት ኪራይ ዋጋ x 24<br><br>በምትክ ቦታ ፋንታ ቤት በግዢ ለተሰጠው በቋሚነት ለሚነሳ የከተማ ባለይዞታ የልማት ተነሺ ካሳ = የሚኖርበት ቤት ስፋት በካ.ሜ x የ1 ካ.ሜ ወቅታዊ<br><br>የቤት ኪራይ ዋጋ x 12 |

29. <u>በጊዜያዊነት ለሚነሳ የከተማ መሬት ባለይዞታ የልማት ተነሺ ካሳ አተማመንና ቀመር</u>

1. ዝርዝር አፈጻጸሙ በመመሪያ ይወሰናል፡፡
2. በጊዜያዊነት ለሚነሳ የከተማ መሬት ባለይዞታ የልማት ተነሺ ካሳ ቀመር

| |
|---|
| በጊዜያዊነት ለተነሳና ለሚቆይበት ጊዜ ምትክ ቤት ላልተሰጠው የከተማ ባለይዞታ የልማት ተነሺ ካሳ = የሚኖርበት ቤት ስፍት በካ.ሜ x የ1 ካሬ ሜ ወቅታዊ የቤት ኪራይ ዋጋ x የለቀቀበት ጊዜ መጠን (በወር) |

## <u>ንዑስ ክፍል አራት</u>

## <u>ተያያዥ ካሳዎች አተማመንና የካሳ ግምት ስለማሳወቅ</u>

30. <u>የማህበራዊ ትስስር መቋረጥና ሥነ-ልቦና ጉዳት ካሣ አተማመን</u>

1. የማህበራዊ ትስስር መቋረጥና የሥነ ልቦና ጉዳት ካሳ አንድ ጊዜ ብቻ ይከፈላል፡፡
2. የማህበራዊ ትስስር መቋረጥ ካሳ እና የሥነ ልቦና ጉዳት ካሳ መጠን በድምሩ ከ25ሺ.ህ እስከ 60ሺ.ህ ብር ሊከፈለዉ ይችላል፡፡

3. የማህበራዊ ትስስር መቋረጥና የሥነ ልቦና ጉዳት ካሳ የሚከፈለው ከነበሩበት ቦታ ከ5 ኪ.ሜ በላይ ርቀው ለሰፈሩ የልማት ተነሺዎች ነው፡፡
4. ከአንድ ሠፈር የልማት ተነሺዎች ከይዞታቸዉ ሳይነሱ የቀሩ ካሉ ለሚደርስባቸዉ የማህበራዊ ትስስር መቋረጥና የሥነ ልቦና ጉዳት ካሳ በሚመለከተዉ አካል ተረጋግጦ ሊከፈላቸዉ ይችላል፡፡
5. የማህበራዊ ትስስር ተፈጥሯል የሚባልበት ጊዜና ለልማት ተነሺዎች የሚሰጥ ተጨማሪ የሥነ ልቡና ምክር ድጋፍ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

31.<u>**የልማት ተነሺ ድጋፍ**</u>

1. የገጠር የልማት ተነሺ ድጋፍ ክልሎች በሚያወጡት መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡
2. የከተማ የልማት ተነሺ ድጋፍ የሚደረገዉ ምትክ ቦታ ለተሰጣቸዉ ቤቱን ገንብተዉ እስኪጨርሱ የሁለት ዓመት የቤት ኪራይ ይከፈላል፡፡
3. ምትክ ቤት ለተሰጣቸዉ የከተማ ልማት ተነሺዎች የአንድ ዓመት የቤት ኪራይ ግምት ይከፈለቸዋል፤
4. ለመንግስት ቤት ተከራዮች በአከራዩ በኩል የልማት ተነሺ ድጋፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋሉ፡፡
5. ልማት ተነሺ ድጋፍ የልማት ተነሺው በአዲሱ ቦታ ለመስፈር ለሽግግር ጊዜ የሚያስፈልግ የትራንስፖርት ወጭን ታሳቢ ሊያደርግ ይገባል፡፡
6. የልማት ተነሺ ድጋፍ አይነት እና መጠን በመመሪያይወሰናል፡፡

32.<u>**ካሳ ግምትና ክፍያን ስለማሳወቅ**</u>

1. ለባለይዞታዉ የሚከፈል ማንኛዉም ዓይነት ካሳ ዓይነቱና መጠኑ ተገልጾ በጹሑፍ ለባለይዞታዉ ይላካል፡፡
2. ባለይዞታዉ የትዳር አጋሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተላከዉ የካሳ ግምት ማሳወቂያ ጹሑፍ የደረሳቸዉ መሆኑን የላከዉ አካል ማረጋገጥ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 2 ማሳወቂያዉ የደረሳቸዉ ባለመብቶች ስለሚከፈለዉ ካሳ አከፋፈል የት እንደሚከፈልና በምን ዓይነት መንገድ እንደሚከፈል ከፋዩ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

<u>**ክፍል አምስት**</u>

<u>**የምትክ ቦታ ወይም ቤት አሰጣጥ እና ተነሺዎችን መልሶ ስለማቋቋም**</u>

33.**<u>የምትክ ቦታ ወይም ቤት አሰጣጥ</u>**

1. ተነሺዎቹ እማወራዎች፣ አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች በሚሆኑበት ጊዜ የምትክ ቦታ ወይም ምትክ ቤት ሲሰጥ አመቺና ተደራሽ የሆኑ ቦታዎች ቅድሚያ ሊታዩላቸዉ ይገባል፡፡
2. ምትክ ቤት የሚሰጠው ምትክ ቦታ ካልተሰጠው እና ተነሺው የቤቱን ዋጋ በአንድ ጊዜ ወይም የወረዳዉ ወይም የከተማ አስተዳደር በሚወስነዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ሲከፍል ነው፡፡
3. ለልማት የተፈለገው ቦታ ባለይዞታው ከያዘው ይዞታ ከፊሉ ሲሆን ተነሺው በቦታው ላይ መቅረት ከፈለገ መቅረት የሚችለው ቀሪው ቦታ ተነሺው ለሚፈልገው አግልግሎት በከተማው ዝርዝር ፕላን ተቀባይነት ካለው የቁራሽ መሬት መጠን ጋር እኩል ወይም በላይ ሲሆንና ምትክ ቦታ ካልተሰጠው ነው፡፡
4. የእድር ይዞታ ለልማት ሲለቀቅ ምትክ ቦታ የሚሰጠዉ ከግማሽ በላይ አባላቱ የሚነሱና በአንድ አካባቢ የሚሰፍሩ ከሆነ ነዉ፡፡
5. ለተነሺው የሚሰጠው ምትክ ቦታ ስሪት ተነሺው ለልማት የተፈለገውን ቦታ በያዘበት ስሪት መሰረት ይሆናል፡፡
6. ለቀበሌ መኖሪያ ቤት ተከራይ የልማት ተነሺዎች ምትክ የመኖሪያ ቤት ወይም መኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ይሰጣል፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 6 መሰረት ምትክ ቤት የሚሰጠው በግዢ ሲሆን ይህም በኪራይ ለመስጠት የማይቻልበት ሁኔታ መኖሩ ሲረጋገጥና በከተማው ካቢኔ ተቀባይነት ሲያገኝ ብቻ ነው፡፡
8. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 6 መሰረት መሬት የሚሰጠው መጠኑ በመመሪያ የሚወሰንና በሊዝ ስሪት በሊዝ መነሻ ዋጋ ይሆናል፡፡ ሆኖም የልማት ተነሺው መጠኑ በመመሪያ የሚወሰን የግንባታ አቅም ማሳያ ገንዘብ በዝግ ሂሳብ ማስቀመጥ አለበት፡፡
9. ለቀበሌ ንግድ ቤት ተከራይ ምትክ ቤት ለመስጠት ካልተቻለ ምትክ የመስሪያ ቦታ የሚሰጠው ሲሆን የቦታው መጠን በመመሪያ ይሆናል፡፡
10. የምትክ ቦታ ወይም ቤት አሰጣጥ እና ተያያዥ ጉዳዮች ዝርዝር አፈፃፀም በመመሪያ ይወሰናል፡፡

34.**<u>በጊዜያዊነት የተወሰደ መሬት ስለመመለስ</u>**

1. በጊዜያዊነት የተወሰደ መሬት በውሉ መሰረት ለባለይዞታዉ መመለስ አለበት፡፡
2. መሬቱን በወቅቱ መመለስ የማይቻልበት ሁኔታ መኖሩን የወረዳዉ ወይም ከተማዉ አስተዳደር ሲያረጋግጥ ለተጨማሪው ጊዜ ክፍያ ይከፈላል፡፡ ወይም ፈጽሞ መመለስ ካልተቻለ እንደ ቋሚ ተነሺ ተቆጥሮ ይስተናገዳል፡፡

35.<u>**የመልሶ ማቋቋሚያ ማዕቀፍ ይዘት**</u>

1. የመልሶ ማቋቋሚያ ፓኬጅ፤-

   የመልሶ ማቋቋም ፓኬጅ ሰነድ፡-

   ሀ) የፓኬጁ ይዘት መኖሪያ ቦታ ወይም ቤት፣ መስሪያ ቦታ፣ ገቢ ማስቀጠል፣ መንገድ፣ ጤና ጣቢያ፣ ትምህርት ቤት፣ የሃይማኖት ተቋም፣ ሥልጠና፣ ምክር አገልግሎት፣ ብድር አገልግሎት የመሳሰሉትን፣

   ለ) የፕሮጀክቱን አይነትና ያለውን ጠቀሜታ፤

   ሐ) በፓኬጁ ተጠቃሚ የሚሆኑትን ተነሺዎች ብዛት፤

   መ) ፓኬጁ መሰረት ያደረጋቸውን የፖሊሲ፣ የህግና ደንቦች ዝርዝር፤

   ሠ) ለተነሺዎች የሚደረገውን የድጋፍ አይነት፣ ከፕሮጀክቱ ተጠቃሚ የሚሆኑበትና ተግባራዊ የሚደረግበትን ዘዴ፤

   ረ) በተነሺዎችና ምትክ ቦታ በተሰጠበት አካባቢ በሚኖረው ማህረሰብ መካከል ሊፈጠር ለሚችለው ማንኛውም አይነት ጊዜያዊ ችግር በጊዜያዊነት መፍትሄ የሚሰጥበት ዘዴ፤

   ሰ) ተነሺዎችን የሚያሳትፍ የውይይት ዕቅድ፣ የሚሰሩ ስራዎችን ቅደም ተከተልና የጊዜ ሰሌዳ፤

   ሸ) የፓኬጁ አፈጻጸሙን የሚከታተሉበትንና የሚገመግሙበትን ሂደት ማካተት ይኖርበታል፡፡

2. ተነሺዎችን መልሶ ስለማቋቋም

   ሀ) ክልሎችና አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተሞች ተነሺዎችን በዘላቂነት ለማቋቋም የሚያስችል ፓኬጅ በመቅረጽ ስራ ላይ ያውላሉ፡፡

   ለ) የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደሩ በተቀረጸው ፓኬጁ ተነሺዎችን በማሳተፍ ቀጣይነት ያለው የገቢ ምንጭ እንዲኖራቸው የሚያስችላቸውን ድጋፍና ክትትል በማድረግ ማቋቋም ይኖርበታል፡፡

ሐ) አስፈጻሚው አካሉ የልማት ሥራው በሚሰራበት ወቅት ተነሺዎች በተቻለ መጠን የሥራ እድል እንዲያገኙ ማድረግ አለበት፡፡

መ) ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደሩ እድሜያቸው ከ18 አመትና ከዚያ በላይ የሆኑ ከወላጆቻቸው ጋር ተጠግተው የሚኖሩ የተነሺ ቤተሰብ አባላት በመልሶ ማቋቋም ፓኬጅ ማሳተፍ አለበት፡፡

ሠ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ላይ ለተጠቀሱ ተነሺዎችን ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደሩ በቂ ስልጠናና በመስጠት በፕሮጀክቱም ሆነ በተሰጠው ስልጠና መሰረት የስራ ዕድል መፍጠር አለበት፡፡

ረ) በመልሶ ማቋቋሚያ ፓኬጁ ለሴቶችን፣ ለአካል ጉዳተኞችን፣ ለወላጅ አልባ ህፃናትና ለአረጋውያን ቅድሚያ መሰጠት አለበት፡፡

ሰ) የሴቶችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚሰሩ አካላት በመልሶ ማቋቋም ፓኬጅ ላይ መሳተፍ አለባቸው፡፡

## ክፍል ስድስት

## ለኢንቬስትመንት በሚለቀቅ መሬት ስለተነሺዎች የሼር ባለቤትነት

### 36.የተነሺዎች የሼር ባለቤትነት ጥያቄን የሚያስተናግድ ተቋም ስለመወሰን

1. ክልሉ፣ አዲስ አበባና ድሬደዋ ከተማ አስተዳደር የልማት ተነሺዎችን የሼር ባለቤትነት ጥያቄ ተቀብሎ የሚያስተናግድ ተቋም ይሰይማሉ፤
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚሰየመው ተቋም:-

ሀ) የልማት ተነሺዎችን የሚያቋቁመው ተቋም አካል ወይም እራሱን የቻለ ሌላ ተቋም ሆኖ መደራጀት፣

ለ) የግል ባለሀብቱን የኢንቬስትመንት መሬት ጥያቄ ተቀብሎ ከሚያስወስነው የስራ ክፍል ወይም ተቋም የተለየ፣

ሐ) የተነሺዎችን የሼር ባለቤትነት መብት የማስከበርና ተጠቃሚ መሆናቸውን የመከታተልና የመደገፍ ሀላፊነት ያለው፣

መ) የልማት ተነሺዎች የሼር ባለቤት የሚሆኑበትን የአሰራር ስርዓት በመቅረጽ የሚሰራ፣

መሆን አለበት፡፡

### 37.የልማት ተነሺዎች በሼር የማልማት ፍላጎት ስለመለየትና ስለመወሰን

የልማት ተነሺዎች ከግል ባለሀብቱ ጋር የኢንቬስትመነት ሼር ለመግባት፡-

1. ለኢንቬስትመነት ከተፈለገው መሬት ላይ ተነሺ ከሆኑት ውስጥ ከባለሀብቱ ጋር በጋራ ለማልማት ፍላጎት ያላቸው መታወቅ አለባቸው፡፡
2. ሼር ለመግባት የሚፈልጉት ባለይዞታዎች ከካሳ እና ከሊዝ መብት ከሚኖራቸው ካፒታል ውስጥ ሼር ለመግዛት የወሰኑት የብር መጠን መለየትና መታወቅ አለበት፡፡
3. ከግል ባለሀብቱ ጋር በሽርክና ለመስራት ያላቸው የፋይናስ አቅም እንዲሁም ፍላጎት ተገምግሞ በሼር ተጠቃሚነታቸው የሼር ባለቤትነት ጥያቄን በሚያስተናግደው ተቋም መወሰን አለበት፡፡

38.<u>ለተነሺ የኢንቬስትመንት ሼር ጥያቄ የሚቀርብበትና የሚፈቀድበት አግባብ</u>

1. ለግል ባለሀብት ለኢንቬስትመንት በተፈቀደው መሬት ላይ የልማት ተነሺ ባለይዞታ የሼር ባለቤትነት ጥያቄ የሚቀርበው፡-

ሀ) ቦታው ለኢንቬስትመነት እንደሚፈለግ ከነዋሪዎች ጋር ውይይት ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ባሉ 90 (ዘጠና) የሥራ ቀናት ውስጥ መሆን አለበት፡፡

ለ) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 (ሀ) መሰረት ጥያቄ ካልቀረበ ባለይዞታው ቦታውን በሼር ለማልማት ፍላጎት እንደደሌለው ይቆጠራል፡፡

ሐ) የተነሺዎች የሼር ባለቤት እንሁን ጥያቄ አቀራረብና ዝርዝር አፈጻጸም በመመሪያ ይወሰናል፡፡

2. ለግል ባለሀብት ለኢንቬስትመንት በተፈቀደው መሬት ላይ የልማት ተነሺ ባለይዞታ የሼር ባለቤትነት መብት የሚኖረው፡-

ሀ) ለኢንቬስትመንት በተፈቀደው መሬት ላይ ሕጋዊ ባለይዞታ ከሆነ፣

ለ) ተነሺው ከካሳ እና ከሌሎች ገቢዎች በሚያገኘው የገንዘብ መጠን አክሰዮን በመግዛት የሼር ባለቤት ለመሆን ፈቃደኛ ከሆነ፣

ሐ) ለኢንቬስትመነት መሬቱን የጠየቀው ባለሀብት ተነሺዎች የሼር ባለቤት እንዳይሆኑ የሚከለክል በሕግ ተቀባይነት ያለው ምክንያት የሌለው መሆኑ በወረዳው ወይም በከተማው አስተዳደር ከተረጋገጠ፣

መ) በቦታው ላይ የሚከናወነው ኢንቬስትመንት በጋራ ለማልማት የተፈቀደ ከሆነ፣

ሠ) የልማት ተነሺ በሼር ለመጠቀም በወሰነው መሰረት ሌሎች የማቋቋሚያ ድጋፎች ተጠቃሚ እንደማይሆን ውል ከገባ፣

ረ) በቦታው ላይ የሚከናወነው ኢንቬስትመንት በጋራ ለማልማት የተፈቀደ ከሆነ፣

ነው፡፡

3. ኢንቬስትመንቱ የሼር ባለቤት እንሁን ጥያቄ ላቀረቡ ነባር ባለይዞታዎች የከተማ ወይም የወረዳው አስተዳደር በ30 ቀናት ውስጥ መወሰንና የተወሰነውን ውሳኔ በ7 የስራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡
4. የኢንቬስትመንቱ የሼር ባለቤት እንሁን ጥያቄ ያቀረበ ባለይዞታ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (3) በተቀመጠዉ ጊዜ ውስጥ መልስ ካላገኘ ወይም በተሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ ካለዉ በዚህ ደንብ አንቀጽ 39 መሠረት ቅሬታዉን ማቅረብ ይችላል፡፡
5. የሼር ባለቤት በመሆን እንዲያለሙ የተፈቀደላቸው ተነሺዎች የማልማት ክትትልና ዉሳኔ አሰጣጥ ዝርዝር በመመሪያ ይወሰናል፡፡

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 39. ቅሬታና አቤቱታ አፈታት

1. የመሬት ይዞታ ማስለቀቂያ ትዕዛዝ የደረሰው ወይም እንዲለቅ ትዕዛዝ በተሰጠበት ንብረት ላይ መብት ወይም ጥቅም አለኝ የሚል ማንኛውም ተነሺ ትዕዛዙ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ አቤቱታውን፣ በአዋጁ አንቀጽ 18 ንኡስ አንቀጽ 1 መሠረት ለሚቋቋመው አቤቱታ ሰሚ አካል ማቅረብ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 የተጠቀሰው አቤቱታ ሰሚ የሚቀርብለትን አቤቱታ በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ በመስጠት ለአቤቱታ አቅራቢዉ አካል በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 2 መሠረት አቤቱታ ሰሚዉ አካል በሰጠው ዉሳኔ ቅር የተሰኘ አቤቱታ አቅራቢ ዉሳኔዉ በደረሰዉ በ30 ቀናት ውስጥ ቅሬታዉን ለይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ማቅረብ ይችላል፡፡
4. ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ቅሬታ አቅራቢዉ ቅሬታዉን ካቀረበበት ቀን ጀምሮ 30 በቀናት ዉስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡
5. ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ አካል ዉሳኔው በጽሁፍ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በ30 የሥራ ቀናት ዉስጥ ይግባኙን ለክልል ለከፍተኛዉ ፍርድ ቤት፣ በአዲስ አበባና በድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮች ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

6. ክልሎች፣ አዲስ አበባና ድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮች አቤቱታ ሰሚ አካል እና የይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ካላቋቋሙ አቤቱታ ያለው ተነሺ አቤቱታውን ስረ ነገር ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡
7. ቅሬታ አቅራቢ ሴት ባለይዞታ ከሆነች ለምታቀርበዉ አቤቱታ ልዩ የሕግ ድጋፍ ሊደረግላት ይገባል፡፡
8. በሙያዉ ብቁ የሆኑ ሴት የህግ ባለሙያዎች በሚኖሩበት ጊዜ በአቤቱታ ሰሚም ሆነ በይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ዉስጥ ሴቶችን ማካተት ይገባል፡፡

40. <u>ስለ አቤቱታ ሰሚ አካል አደረጃጀት</u>

1. አቤቱታ ሰሚ አካል የራሱ ጽሕፈት ቤት የሚኖረው ሆኖ በየወረዳው ወይም በየከተማው አስተዳደር ይቋቋማል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚቋቋመው አቤቱታ ሰሚ አካል ከ 3 የማያንሱ አባላት የሚኖሩት ሲሆን ከዚህ ውስጥ ቢያንስ አንዱ የሕግ ባለሙያ መሆን ይኖርበታል፡፡
3. የአቤቱታ ሰሚው አካል ተጠሪነት ለወረዳው ወይም ለከተማው ምክር ቤት ይሆናል፡፡
4. የጉባኤዉ አባላት የስራ ዘመን በመመሪያ ይወሰናል፡፡

41. <u>ስለይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አደረጃጀት</u>

1. ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የራሱ ጽሕፈት ቤት የሚኖረው ሆኖ በየወረዳው ወይም በየከተማው አስተዳደር ይቋቋማል፡፡
2. ጉባኤው አግባብ ካላቸው አካላት የተውጣጡ ከ5 የማያንሱ አባላት የሚኖሩት ሲሆን ከዚህ ውስጥ ቢያንስ ሁለቱ የሕግ ባለሙያዎች መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
3. የጉባኤው ተጠሪነት ለወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት ወይም ለከተማው አስተዳደር ምክር ቤት ይሆናል፡፡
4. የጉባኤዉ አባላት የስራ ዘመን በወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት ወይም በከተማው አስተዳደር ምክር ቤት ይወሰናል፡፡

42. <u>የአቤቱታ ሰሚ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር</u>

አቤቱታ ሰሚ ጉባኤው፡-

1. ከይዞታ መነሳት ወይም ምትክ ቦታ ወይም ካሣ ወይም ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን በተመለከተ የቀረበለትን አቤቱታ የማየት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

2. ለውሳኔ አሰጣጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አግባብነት ያላቸውን አካላት በማዘዝ ሙያዊ አስተያየት የመቀበል እና ማስረጃ እንዲቀርብለት የማዘዝ ሥልጣ ይኖረዋል፡
3. የማስፈጸሚያ ዝርዝር ሥነ-ሥርዓት በመመሪያ ይወስናል፡፡
4. እንደአስፈላጊነቱ በመደበኛው የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት የተቀመጡ መርሆዎችንና የአሰራር ሥነ- ሥርዓቶችን ሊጠቀም ይችላል፡፡
5. ለሚሰጣቸው ውሳኔዎችና ትእዛዞች ተፈጻሚነት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የፖሊስ ኃይል ይጠቀማል፡፡

43.<u>የይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር</u>

ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው፡-

1. ከይዞታ መነሳት ወይም ምትክ ቦታ ወይም ካሣ ወይም ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን በተመለከተ የከተማው አስተዳደር ወይም የወረዳው አስተዳደር አቤቱታ ሰሚ አካል በሰጠው ውሳኔ ላይ የቀረበለትን አቤቱታ የማየት፣ ውሳኔ የማጽናት፤ የማሻሻል ወይም የመሻር ሥልጣን ይኖረዋል፡፡
2. ለውሳኔ አሰጣጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አግባብነት ያላቸውን አካላት በማዘዝ ሙያዊ አስተያየት የመቀበል እና ማስረጃ እንዲቀርብለት የማዘዝ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡
3. ዝርዝር ሥነ-ሥርዓት በመመሪያ ይወስናል፡፡
4. እንደአስፈላጊነቱ በመደበኛው የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት የተቀመጡ መርሆዎችንና የአሰራር ሥነ- ሥርዓቶችን ሊጠቀም ይችላል፡፡
5. ለሚሰጣቸው ውሳኔዎችና ትእዛዞች ተፈጻሚነት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የፖሊስ ኃይል ይጠቀማል፡፡

44.<u>የአቤቱታ ሰሚ ጉባኤ እና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ</u>

የአቤቱታ ሰሚ ጉባኤው እና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ተግባራቸውን ሲያከናውኑ የሚከተሉትን መርሆዎች ጠብቀው ይሰራሉ፡-

1. ነጻ እና ገለልተኛ አቋማቸውን ጠብቀው ይሰራሉ፡፡
2. የውሳኔ አሰጣጡ እና ውሳኔው የሚመለከተው የመንግሥት ተቋም እና አቤቱታ አቅራቢው አካል በሕግ ፊት እኩል መሆናቸውን እና ከአድሏዊነት የፀዳ መሆኑን ያረጋገጡ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡
3. ውሳኔዎች ሕግን እና ማስረጃን ብቻ መሠረት አድርገው እንዲሰጡ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

4. አሰማም ሂደቱ ግልጽ እና ማንኛውም ሰው ሊታደመው የሚችል እንዲሆን ያደረጋሉ፡፡

## 45. መረጃ ስለመስጠት

1. ግምት እንዲሰራ ሥልጣን የተሰጠው ተቋም፣ የተመሰከረለት ገማች ወይም አማካሪ፣ እና ገማች ኮሚቴ በአዋጁ እና በዚህ ደንብ መሠረት ንብረት ለመተመን አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች አግባብ ካላቸው የፌደራል፣ የክልል ወይም ሌሎች አካላት መጠየቅ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ጥያቄ የቀረበለት አካል የተጠየቁትን መረጃዎች መስጠት አለበት፡፡ የተጠየቁትን በእጁ ያሉ መረጃዎችን ካልሰጠ በአግባብ በአላቸዉ ሕጎች ተጠያቂ ይሆናል፡፡
3. በተጠየቁት አካላት ዘንድ መረጃዎቹ አለመኖራቸው ሲረጋገጥ ግምት እንዲሰራ ሥልጣን የተሰጠው አካል የአካባቢውን የንብረት ዋጋ ቅኝታዊ ጥናት ራሱ ያካሂዳል፡፡

## 46. መረጃ ስለመያዝ

1. ለአዋጁ እና ለዚህ ደንብ አፈጻጸም የወረዳው ወይም የከተማው አስተዳደር እንዲለቀቅ በሚወሰን መሬት ላይ የሚገኙትን ንብረቶች፣ የተከፈለ ካሣ እና ምትክ ወሳጆችን በሚመለከት መረጃ የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡
2. የመልሶ ማቋቋም ድጋፍ የሚያደርገው ተቋም ያቋቋማቸውን ተነሺዎች ዝርዝር መረጃ የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡
3. ግምት እንዲሰሩ ስልጣን የተሠጣቸው አካላት የካሳና ምትክ ዝርዝር መረጃዎች አደራጅተው የመያዝና በሚመለከተው አካል እንዲያቀርቡ ሲጠየቁ የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1፣ 2 እና 3 መሠረት የሚያዙ መረጃዎች በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ዘዴ ደህንነታቸው ተጠብቆ መያዝ አለባቸው፡፡

## 47. ስለግምት ሥራ ወጪዎች

ንብረት ለመገመት የሚከፈሉ ወጪዎችን በማንኛውም ሁኔታ ተነሺዎች እንዲከፍሉ አይገደዱም፡፡

48. ***መመሪያ የማውጣት ሥልጣን***

1. ክልሎች፣ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች ይህን ደንብ ለማስፈጸም መመሪያ ያወጣሉ፡፡
2. የሚወጣው መመሪያ የከተማና የገጠር መሬትን የተመለከተ መሆን አለበት፡፡

49. **የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ደንብና መመሪያዎች**

1. ለህዝብ ጥቅም ሲባል በሚለቀቅ መሬት ላይ ለሰፈረ ንብረት ስለሚከፈል ካሣ የወጣ የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 135/1999 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡
2. ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

50. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ 5 ቀን 2012 ዓ.ም**

**አብይ አሕመድ (ዶ/ር)**

**ኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

## አዋጅ ቁጥር 456/1997

## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ

የመሬት ባለቤትነት መብት የመንግሥትና የሕዝብ ብቻ መሆኑ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት በመረጋገጡ፣

በተለያዩ የሀገሪቱ የሥነ ምህዳር ቀጠናዎች ላይ ተመስርቶ ዘላቂ የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ በማውጣትና በመተግበር የተፈጥሮ ሀብቶችን በዘላቂነት በመጠበቅና በማልማት ለመጪው ትውልድ ማስተላለፍ በማስፈለጉ፣

በሀገሪቱ የሚገኙ የተለያዩ የገጠር መሬት ይዞታ ዓይነቶችን ማለትም በወል፣ በግለሰብ ገበሬ እና በፌዴራልና በክልል መንግሥታት ሥር የሚገኙ ይዞታዎችን በስፋት፣ በአቅጣጫና በመሬት የመጠቀም መብቶች ለመለየት የሚያስችል የመረጃ ሥርዓት መዘጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የግለሰብ ገበሬዎችን፣ የአርብቶ አደሮችንና የእርሻ ኢንቨስተሮችን ከማበረታታት አኳያ የሚታዩ ችግሮችን በመቅረፍ ምቹ የሆነ የገጠር መሬት አስተዳደር ሥርዓት መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፣

ጥምር የሰብልና የእንስሳት ምርት እንቅስቃሴ በሠፈነባቸው አካባቢዎች የአፈር መሸርሸርና የደን መመናመን አደጋ በመኖሩ አርሶ አደሩ አስፈላጊውን እንክብካቤ እንዲያደርግ በይዞታው የመጠቀም መብቱ እንዲጎለብትና እንዲጠናከር ምቹ የሕግ ሁኔታዎች መፍጠሩ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በአርብቶ አደሮች አካባቢ በአብዛኛው በጎሣ ላይ በተመሠረተው የወል የመሬት ይዞታ ስሪት ውስጥ ለተፈጥሮ ሀብት አያያዝና አጠቃቀም እንዲሁም የግል ባለሀብቶችን ከማበረታታት አኳያ ተስማሚ የገጠር መሬት አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን ለማስተዳደር ለክልሎች የተሰጠው ሥልጣን በሥራ ላይ የሚውለው የፌዴራል መንግሥቱ በሚያወጣው ህግ መሠረት መሆኑን የሕገ መንግሥት አንቀጽ 52 (2) (መ) ስለሚደነግግ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55 (1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

 ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/1997" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

 የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

 1. "የገጠር መሬት" ማለት ከማዘጋጃ ቤት ክልል ውጪ ወይም አግባብ ባለው ሕግ "ከተማ" ተብለው ከሚሰይመው ውጪ ያለ ማንኛውም መሬት ነው፣
 2. "የገጠር መሬት አስተዳደር" ማለት በገጠር መሬት ይዞታ ላይ ዋስትና የሚሰጥበት፣ የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ የሚተገበርበት፣ በገጠር መሬት ተጠቃሚዎች መካከል የሚነሱት ግጭቶች የሚፈቱበትና ማንኛውም የገጠር መሬት ተጠቃሚ መብትና ግዴታዎች የሚተገበሩበት እንዲሁም የባለይዞታዎች ማሳዎችን የግጦሽ መሬትን መረጃ በመሰብሰብና በመተንተን ለተጠቃሚዎች እንዲዳረሱ የሚደረግበት ሂደት ነው፣
 3. "የገጠር መሬት አጠቃቀም" ማለት የገጠር መሬትን በእንክብካቤ ይዞ ዘላቂነት ባለው መንገድ ለተሻለ ጠቀሜታ እንዲውል የሚደረግበት ሂደት ነው፣
 4. "የይዞታ መብት" ማለት ማንኛውም አርሶ አደር፣ ከፊል አርብቶ አደር እና አርብቶ አደር የገጠርን መሬት በግብርናና በተፈጥሮ ሀብት ልማት ተግባር ላይ ለማዋል፣ ለማከራየትና ለቤተሰቡ አባልና ለሌሎች በሕግ መብት ለተሰጣቸው ወራሾች ለማውረስ የሚኖረው መብት ሲሆን፣ በመሬቱ ላይ

በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ ንብረት ማፍራትና ይህንንም በመሬቱ ላይ ያፈራውን ንብረት መሸጥ፣ መለወጥና ማውረስንም ይጨምራል፣

5. “የቤተሰብ አባል” ማለት የይዞታ ባለመብቱን መተዳደሪያ ገቢ በመጋራት በቋሚነት አብሮ የሚኖር ማንኛውም ሰው ነው፣
6. “የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ” ማለት አካላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ የገጠር መሬት ሊሰጥ ከሚችለው የተለያዩ የመሬት አጠቃቀም አማራጮች መካከል የመሬት መጎሳቆልንና የአካባቢን ብክለት ሳያስከትሉ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚያስገኙት አማራጮች የሚወሰኑበትና ተግባራዊ የሚደረጉበት የአሰራር ዘዴ ነው፣
7. “አርሶ አደር” ማለት የገጠር መሬት የይዞታ መብት የተሰጠውና ከመሬቱም በሚያገኘው ገቢ እራሱን እና ቤተሰቡን የሚያስተዳድር የገጠሩ ሕብረተሰብ ክፍል አባል ነው፣
8. “አርብቶ አደር” ማለት የግጦሽ መሬትን በመያዝና ከቦታ ወደ ቦታ በመንቀሳቀስ በዋነኛነት እንስሳት በማርባትና ኑሮው ከእንስሳት ሀብት በሚገኘው ምርት ላይ የተመሠረተ የገጠሩ የሕብረተሰብ ክፍል አባል ነው፣
9. “ከፊል አርብቶ አደር” ማለት በዋነኝነት ከብት በማርባትና በተወሰነ ደረጃ ከእርሻ በሚገኝ ምርት ላይ ኑሮው የተመሠረተ የገጠር ህብረተሰብ ክፍል ነው፣
10. “አነስተኛ የይዞታ መጠን” ማለት ምርታማነቱ የአንድን አርሶ አደር ከፊል አርብቶ አደር እና አርብቶ አደር ቤተሰብ የምግብ ዋስትና ሊያረጋግጥ የሚችል የገጠር መሬት ይዞታ ወይንም ለሰብል እርሻ፣ ለቋሚ ሰብል፣ ለግጦሽ፣ ለመኖሪያ ቤትና ለጓሮ የሚበቃ የገጠር መሬት ይዞታ መጠን ነው፣
11. “አነስተኛ የግል ይዞታ” ማለት በአርሶ አደሮች ከፊል አርብቶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች ወይንም በሌሎች መብት በተሰጣቸው አካል በግል ይዞታ ስር ያለ የገጠር መሬት ነው፣
12. “የወል ይዞታ” ማለት የአካባቢው ነዋሪዎች በጋራ ይዞታነት ለግጦሽ፣ ለደንና ለሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶች እንዲጠቀሙበት በመንግሥት የተሰጣቸው የገጠር መሬት ነው፣
13. “የመንግሥት ይዞታ” ማለት በፌዴራል ወይም በክልል መንግሥት ተከልሎ የተያዘ እና ወደፊት የሚከለለው የገጠር መሬት የሚገልፅ ሲሆን፣ የደን

መሬቶችን፣ የዱር እንስሳትን ጥብቅ ቦታዎችን፣ የመንግሥት እርሻዎችን፣ የማዕድን መሬቶችን፣ ሃይቆችን፣ ወንዞችንና ሌሎችን በተመሳሳይ መልኩ የተያዙትን ያጠቃልላል፣

14.“የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር” ማለት በገጠር መሬት የመጠቀምን መብት ለማረጋገጥ አግባብ ባለው አካል የሚሰጥ ሰነድ ነው፣

15.“የመሬት ምዝገባ” ማለት በገጠር መሬት የመጠቀም መብትና ባለይዞታነት የሚገለፅበት የመረጃ ማሰባሰብና የማጠናቀር ሂደት ነው፣

16.“የመሬት መረጃ ሥርዓት” ማለት የገጠር መሬት ነክ መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በመተንተንና በአግባቡ እንዲያዙ በማድረግ ለተለያዩ ተጠቃሚ ክፍሎች የማሰራጨት ሥርዓት ነው፣

17.“አግባብ ያለው ባለስልጣን” ማለት የክልሎች ህገ መንግስት በሚፈቅደው መሠረት በክልሎች ውስጥ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ስርአት መስፈኑን ለመከታተል የተቋቋመ አካል ነው፣

18.“ሰው” ማለት የተፈጥሮ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

3. <u>የጾታ አገላለጽ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

4. <u>የአዋጁ ተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ በማንኛውም የገጠር መሬት ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ስለማረጋገጥ</u>

5. <u>የገጠር መሬት ስለማግኘትና ስለመጠቀም</u>

1. በመሬት አስተዳደር ሕግ መሠረት፡-

ሀ/ በግብርና ሥራ ለሚተዳደሩ አርሶ አደር፣ ከፊል አርብቶ አደር እና አርብቶ አደሮች የገጠር መሬት በነፃ እንዲያገኙ ይደረጋል፣

ለ/ ዕድሜው ከ18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነና በግብርና ሙያ ሊተዳደር የሚፈልግ ማንኛውም የሀገሪቱ ዜጋ በገጠር መሬት የመጠቀም መብቱ የተረጋገጠ ሆኖ እናትና አባታቸውን በሞት ወይም በሌላ ሁኔታ ያጡ ልጆች

18 ዓመት እስኪሞላቸው ድረስ በህጋዊ ሞግዚታቸው አማካኝነት በገጠር መሬት የመጠቀም መብት አላቸው፣

ሐ/ በግብርና ሥራ መሰማራት የሚፈልጉ ሴቶች የገጠር መሬት የማግኘትና የመጠቀም መብት አላቸው፣

2. ማንኛውም በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ያለው አርሶ አደር ከፊል አርብቶ አደር እና አርብቶ አደር ቤተሰብ አባል ከቤተሰቡ በስጦታ ወይም በውርስ ወይም አግባብ ካለው ባለሥልጣን የገጠር መሬት በይዞታ ሊያገኝ ይችላል፣

3. መንግሥት በመሬት ባለቤትነቱ የወል/የጋራ የገጠር መሬት ይዞታዎችን እንደአስፈላጊነቱ ወደ ግል ይዞታነት እንዲቀየሩ ሊያደርግ ይችላል፣

4. ለአርሶ አደሮች ለከፊል አርብቶ አደሮችና ለአርብቶ አደሮች ቅድሚያ በመስጠት፣

ሀ/ በግብርና ልማት ለሚሰማሩ ባለሀብቶች በፌዴራልና በክልል ደረጃ በወጡት የኢንቨስትመንት ፖሊሲዎችና ሕጎች መሠረት በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ይኖራቸዋል፣

ለ/ መንግሥታዊና መንግሥስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተቋማት ከልማት ዓላማቸው ጋር እየታየ በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ይኖራቸዋል፣

6. <u>የገጠር መሬትን ስለመለካት፣ ስለመመዝገብና ስለ ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር</u>

1. በግል፣ በወል፣ በመንግሥትና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ይዞታዎች ያሉ የገጠር መሬቶች እንደሁኔታው ባህላዊና ዘመናዊ የቅየሳ መሣሪያዎችን በመጠቀም የመሬት ስፋታቸውን በመለካት እንዲሁም የመሬት አጠቃቀማቸውና የለምነት ደረጃቸው በክልልና በየደረጃው በተቋቋሙ የመረጃ ማዕከላት እንዲመዘገቡ ይደረጋል፣

2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) የተዘረዘሩት የገጠር መሬት ይዞታዎች አግባብ ባለው ባለሥልጣን ተለክተው የይዛታ ድንበራቸውን የሚሳይ ካርታ ይዘጋጅላቸዋል፣

3. ማንኛውም የገጠር መሬት ባለይዞታ አግባብ ባለው ባለሥልጣን የሚዘጋጅና የመሬቱን ይዞታ ስፋት፣ አጠቃቀምና ሽፋን፣ የለምነት ደረጃና አዋሳኞቹን እንዲሁም ኃላፊነትና ግዴታን የያዘ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እንዲኖረው ይደረጋል፣

4. መሬቱ የባልና የሚስት የጋራ ከሆነ ወይም በሌሎች በጋራ የተያዘ ከሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ በሁሉም የጋራ ባለይዞታዎች ስም መዘጋጀት አለበት፣
5. የገጠር መሬት በማን ይዞታ ሥር እንደሚገኝ፣ ከማን መሬት ጋር እንደሚዋሰን፣ ደረጃው ምን ዓይነት እንደሆነ፣ ለምን አገልግሎት እንደሚውልና ባለይዞታው ምን መብትና ግዴታዎች እንዳሉበት የሚገልጽ መረጃ ተመዝግቦ አግባብ ባለው ባለሥልጣን እንዲያዝ ይደረጋል፣
6. በሊዝ ወይም በኪራይ የተያዘ የገጠር መሬት አግባብ ባለው አካል መመዝገብ አለበት፡፡

7. **<u>በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ፀንቶ ስለማቆይበት ጊዜ</u>**

1. የአርሶ አደሮች ከፊል አርብቶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች በገጠር መሬት የመጠቀም መብት የጊዜ ገደብ የለውም፣
2. የሌሎች ባለይዞታዎች በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ፀንቶ የሚቆይበት የጊዜ ገደብ በክልሎች የገጠር መሬት አስተዳደር ሕግ መሠረት ይወሰናል፣
3. የገጠር መሬት ባለይዞታ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል መሬቱን በመንግሥት እንዲለቅ ሲደረግ በመሬቱ ላይ ላደረገው ማሻሻያና ላፈራው ንብረት ተመጣጣኝ ካሣ ይከፈለዋል፡፡ ወይንም በለቀቀው መሬት ምትክ በተቻለ መጠን ሌላ ተለዋጭ መሬት እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡ የገጠር መሬት ባለይዞታ መሬቱን እንዲለቅ የሚደረገው በፌዴራል መንግሥት ከሆነ ከሚከፈለው ካሣ ተመን በፌዴራል የመሬት አስተዳደር ሕግ ይወሰናል፣ ባለይዞታው መሬቱን እንዲለቅ የሚደረገው በክልል መንግሥት ከሆነ ደግሞ የካሣ ተመኑ በክልሎች የገጠር መሬት አስተዳደር ሕግ ይወሰናል፡፡

8. **<u>በገጠር መሬት የመጠቀም መብትን ሰለማሰተላለፍ</u>**

1. የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የተሰጣቸው አርሶ አደሮች ከፊል አርብቶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች እነሱን በማያፈናቅል መልኩ ለሌላ አርሶ አደር ወይንም ባለሀብት እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ በጥናት ላይ ተመሥርቶ በክልሎች የገጠር መሬት አስተዳደር ሕግ በሚወሰን የጊዜ ገደብ ከይዞታቸው ላይ ለተፈላጊው ልማት በቂ የሆነ የማሳ ስፋት ማከራየት ይችላል፣

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚደረግ የገጠር መሬት ኪራይ ውል በመሬቱ የመጠቀም መብት ያላቸውን አባላት የጋራ ይሁንታ ማግኘትና አግባብ ባለው አካል ጸድቆ መመዝገብ አለበት፤
3. የገጠር መሬትን በጋራ ለማልማት የመሬት ባለይዞታው በመሬቱ የመጠቀም መብቱን ይዞ ከባለሀብት ጋር በሚገባው ውል መሠረት የልማት ሥራ ሊሠራ ይችላል፡፡ ውሉም አግባብ ባለው ባለሥልጣን ፀድቆ መመዝገብ አለበት፤
4. የገጠር መሬት በሊዝ የተከራየ ባለሀብት የመጠቀም መብቱን እንደዋስትና ለማስያዝ ይችላል፤
5. ማንኛውም ባለይዞታ በገጠር መሬት የመጠቀም መብቱን ለቤተሰቡ አባላት የማውረስ መብት አለው፤

9. <u>ስለገጠር መሬት ሽግሽግ</u>

1. የመሬቶች ባለይዞታዎቹ በሕይወት የሌሉና ወራሽ የሌላቸው ከሆኑ ወይም ባለይዞታዎቹ በሰፈራ ወይም በፍላጐታቸው በክልሎች የገጠር መሬት አስተዳደር ሕግ ከተወሰነው ጊዜ በላይ ከአካባቢው ለቀው የቆዩ ከሆነ በአካባቢው ለሚኖሩት መሬት አልባ ለሆኑ ወይም መሬት ላነሳቸው አርሶ አደሮች፣ ከፊል አርብቶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች በሽግሽግ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡
2. የመስኖ መሬትን በአግባቡና በፍታሃዊነት ለመጠቀም በመስኖ መሬት ላይ ሽግሽግ ሊካሄድ ይችላል፡፡
3. በአርሶ አደሮች ከፊል አርብቶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች ፍላጎትና ውሳኔ የገጠር መሬት ሽግሽግ ማካሄድ አማራጭ የሌለው ሆኖ ሲገኝ የመሬት ሽግሽጉ ከአነስተኛ የይዞታ መጠን በታች በማይሆንና የተፈጥሮ ሀብት መመናመንን በማያስከትል መልኩ ተግባራዊ መሆን አለበት፡፡
4. የገጠር መሬት ይዞታቸውን ለመስኖ አውታር ግንባታ ሲባል ለሚያጡ አርሶ አደሮች ከፊል አርብቶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች በአካባቢው ከሚዘረጋው የመስኖ ልማት ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የመሬት ሽግሽግ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

10. <u>የገጠር መሬት ተጠቃሚዎች ግዴታዎች</u>

1. የገጠር መሬት ባለይዞታው መሬቱን በአግባቡ የመጠቀምና የመንከባከብ ግዴታ አለበት፡፡ በመሬቱ ላይ ጉዳት ከደረሰ የመሬት መጠቀም መብቱን ሊያጣ ይችላል፡፡ ዝርዝሩም በክልል የገጠር መሬት አስተዳደር ሕግ መሠረት ይሆናል፣
2. የመስኖ ቦዮችና ሌሎች የመሠረተ ልማት አውታሮች በሚዘረጉበት ወቅት በባለይዞታው መሬት ላይ የሚያልፉ ከሆነ ይህንኑ የመቀበል ግዴታ አለበት፡፡
3. ባለይዞታው አግባብ ባለው ባለሥልጣን የገጠር መሬቱ እንዲለካ ወይም የቅየሳ ሥራ እንዲካሄድ ሲጠየቅ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡
4. ማንኛውም የገጠር መሬት ባለይዞታ በመሬቱ የመጠቀም መብቱን በፈቃዱ ሲተው አግባብ ላለው ባለሥልጣን የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

11.<u>የገጠር መሬት አነስተኛ ወለልን ስለመወሰንና ኩታ ገጠም ይዞታን ስለማበረታታት</u>

1. ቀደም ሲል የነበረው የአንድ ቤተሰብ ይዞታ ወይም ማሳ ስፋት እንዳለ ሆኖ፣ ወደፊት የሚሰጠው የማሳ ስፋት ከአነስኛው የይዞታ መጠን በታች መሆን የለበትም፡፡
2. የገጠር መሬት በውርስ በሚተላለፍበት ወቅት የሚተላለፈው የመሬት ይዞታ መጠን ከአነስተኛው የይዞታ መጠን በታች መሆን የለበትም፡፡
3. አነስተኛ ማሳዎች ለልማት አመቺ እንዲሆኑ በአርሶ አደሩ ሙሉ ፍቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የይዞታ ልውውጥ እንዲያደርጉ ይበረታታሉ፡፡
4. የይዞታ ልውውጥ ለማድረግ ፈቃደኛ የሆኑ ገበሬዎች ለመለዋወጥ ያሰቡትን የማሳ ስፋትና የለምነት ደረጃ በቀበሌው አስተዳደር ክልል ውስጥ የሚኖሩ ሌሎች ገበሬዎች እንዲያውቁት ለማድረግ መረጃዎቹ በቀበሌው አስተዳደር አማካይነት እንዲሰራጩ ይደረጋል፡፡
5. በሕብረተሰቡ ጥያቄና ተሳትፎ የሚከናወን የሠፈራና የመንደር ምሥረታ ፕሮግራም የመሬት ኩታ ገጠምነትን ዓላማ ያደረገ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

12.<u>የክርክሮች አወሳሰን</u>

የገጠር መሬት ይዞታ መብትን በተመለከተ ክርክር ሲነሳ ጉዳዩ በሚመለከታቸው ተከራካሪዎች በውይይትና ስምምነት እንዲፈታ ጥረት ይደረጋል፡፡ በስምምነት ሊፈታ ካልቻለ በተከራካሪ ወገኖች በተመረጠ ሽምግልና ወይንም በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር ሕግ በተደነገገው መሠረት ይወሰናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## በገጠር መሬት በአጠቃቀም ረገድ ስለተጣሉ ገደቦች

### 13.የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ ስለማወጣትና ስለተዳፋት፣ ቦሪቦርና ረግረጋማ መሬቶች አጠቃቀም

1. የአፈር ዓይነትን፣ የመሬት አቀማመጥን፣ የተዳፋትነት መጠንን፣ የአየር ፀባይን፣ የዕፅዋት ሽፋንን እና ሶሺዮ-ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን ባካተተ መልኩ ተፋሰስን መሠረት ያደረገ የመሬት አጠቃቀም መሪ ዕቅድ አግባብ ባለው ባለሥልጣን ወጥቶ ተግባራዊ ይሆናል፣
2. በላይኛውና በታችኛው የተፋሰስ ክፍል ባለተጠቃሚ ሕብረተሰብ መካከል ፍትሃዊ የሆነ የውሃ አጠቃቀም ሥርዓት እንዲኖር ይደረጋል፣
3. የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች በተከናወነባቸውና ቋሚ ተክሎች በለሙበት ማንኛውም ዓይነት የገጠር መሬት ላይ የልቅ ግጦሽ የአመጋገብ ሥርዓትን በመከልከል ደረጃ በደረጃ አጭዶ መመገብ ሥርዓት እንዲይዝ ይደረጋል፣
4. የመሬት ተዳፋትነታቸው ከ30 ፐርሰንት በታች የሆኑ የገጠር መሬቶች አያያዝ የአፈር ክለትን የሚቀንስና ውሃ የመሰብሰብን ስልት የተከተለ መሆን አለበት፡፡ ዝርዝሩ በክልሎች የገጠር መሬት አስተዳደር ሕግ ይወሰናል፣
5. የመሬት ተዳፋትነታቸው ከ31- 60 ፐርሰንት የሆኑ የገጠር መሬቶችን ለዓመታዊ ሰብሎች ልማት ለማዋል የሚቻለው ጠረጴዛማ እርከን በመሥራት ብቻ ነው፣
6. ተዳፋትነታቸው ከ60 ፐርሰንት በላይ የሆኑ የገጠር መሬቶች ለእርሻና ለልቅ ግጦሽ እንዳይውሉ ሆኖ ለዛፍ፣ ለቋሚ ተክሎችና ለእንስሳት መኖ ልማት እንዲውሉ ይደረጋል፣
7. በማንኛውም ተዳፋት የሚገኝና በጣም የተጐዳ የገጠር መሬት ለተወሰነ ጊዜ ከሰውና ከእንስሳት ንክኪ ተጠብቆ እንዲያገግምና ማገገሙ ሲረጋገጥ ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡ መሬቱን በአግባቡ ባለመንከባከብ የሚከሰት ጉዳት ካልሆነ በስተቀር ለመሬቱ ተጠቃሚ አርሶ አደሮች ከፊል አርብቶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች በክልሉ የመሬት አስተዳደር ሕግ መሠረት ለተጠቀሰው ጊዜ አማራጭ ይፈለግላቸዋል፣ ወይም ካሣ ይከፈላቸዋል፡፡

8. ቦረቦር የሆኑ የገጠር መሬቶች በግልና በአጐራባች ባለይዞታዎች፣ እንደአስፈላጊነቱም በአካባቢው ሕብረተሰብ ሥነ-ሕይወታዊ እና ፊዚካላዊ ሥራዎችን በመጠቀም እንዲያገግሙና ጥቅም ላይ እንዲውሉ መደረግ አለባቸው፣
9. በኮረብታማ አካባቢዎች ያሉ ቦረቦር የሆኑ የገጠር መሬቶች በወል እንዲሁም እንደየሁኔታው በግል ተይዘው እንዲያገግሙና እንዲለሙ ይደረጋል፣
10. ረግረጋማ የሆኑ የገጠር መሬቶች ያላቸው ብዝሀ ሕይወት እንዲጠበቁና እንደአስፈላጊነቱ ተስማሚ በሆነ የመሬት አጠቃቀም ስልት ጥቅም እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

14. <u>ለመንደር ምስረታና ለሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶች የገጠር መሬትን ጥቅም ላይ ስለማዋል</u>

የተሻለ የገጠር መሬት አጠቃቀም ሥርዓትን ለማስፈን የሚያስችል የሰፈራ፣ የመንደር ምሰረታና የማህበራዊ አገልግሎቶች የሚሰፋፉበት ስልት እንዲነደፍ ይደረጋል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

15. <u>በገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ላይ ጥናት ስለማካሄድ</u>

በገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ላይ ያሉ ችግሮችን በመለየትና ተገቢውን መፍትሄ በመፈለግ ላይ ያተኮረ የጥናት ሥርዓት እንዲዘረጋ ይደረጋል፡፡

16. <u>የፌደራል የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር[138] ኃላፊነት</u>

የፌዴራል ግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር

1. አግባብ ያላቸውን ባለሥልጣናት በማስተባበርና አስፈላጊውን የሙያ ድጋፍ በመስጠት ይህን አዋጅ የማስፈፀም ኃላፊነት አለበት፣
2. በሀገር አቀፍ ደረጃ የተሰበሰቡና በየጊዜው በክትትልና በግምገማ የሚገኙ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ አዳዲስ የፖሊሲ ሃሳቦች እንዲነደፉና አስፈላጊም ሲሆን በሥራ ላይ ያለው ፖሊሲ በየጊዜው እንዲሻሻል ያደርጋል፣
3. በክልሎችና በፌዴራል መካከል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት እዲንዘረጋ ያደርጋል፡፡

17. <u>የክልሎች ኃላፊነት</u>

[138] በ25/08 (2011) አ.1097 አንቀፅ 9(6) መሰረት የግብርና ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

1. እያንዳንዱ የክልል ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ዝርዝር ድንጋጌዎችን የያዘ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ህግ ያወጣል፣
2. ክልሎች የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ሥርዓትን የሚያስፈጽሙ ድርጅታዊ ተቋሞች በተዋረድ እንዲቋቋሙና የተቋቋሙትም እንዲጠናከሩ ማድረግ አለባቸው።

18.<u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማናቸውም ሰው ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም አግባብነት ካላቸው ባለሥልጣናት ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

19.<u>ስለቅጣት</u>

ማንኛውም ሰው ይህን አዋጅ ወይም አዋጁን ለማስፈፀም የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ጥሶ ሲገኝ አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ መሠረት ይቀጣል፡፡

20.<u>ስለተሻሩ እና ተፈጻሚ ስለማይሆኑ ህጎች</u>

1. የፌደራል መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 89/1989 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፣
2. ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ህግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን ጉዳዮች በተመለከተ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

21.<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሰኔ 8 ቀን 1997 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ 8 ቀን 1997 ዓ.ም.**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

# አዋጅ ቁጥር 721/2004

## የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የወጣ አዋጅ

*መሬት የመንግስትና የሕዝብ ንብረት ሆኖ የመሬት አጠቃቀም በሕግ እንደሚወሰን በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40 የተደነገገ በመሆኑ፤*

*በመላ ሀገሪቱ በሁሉም ክፍላተ-ኢኮኖሚዎችና ክልሎች በመመዝገብ ላይ ያለው ቀጣይነት የተላበሰ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት የከተማ መሬት ፍላጎትን በዘላቂነትና በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ እንዲመጣ በማድረጉና ይህም ሁኔታ ብቃት በተላበሰና ለፍላጎቱ ተገቢ የመሬት ሀብት አቅርቦት ምላሽ ሊሰጥ በሚችል አስተዳደር በአግባቡ መመራት ያለበት በመሆኑ፤*

*ለተሳለጠ፣ ለውጤታማ፣ ለፍትሐዊና ለጤናማ የመሬትና መሬት ነክ ንብረት ገበያ ልማት፤ ቀጣይነት ለተላበሰ የነፃ ገበያ ሥርዓት መስፋፋት፣ ግልጽና ተጠያቂነት ለሰፈነበት እንዲሁም የመሬት ባለቤቱንና የመሬት ተጠቃሚውን መብቶችና ግዴታዎችን ለማረጋገጥ የሚያስችል የመሬት አስተዳደር ሥርዓት ለመገንባት የመልካም አስተዳደር መኖር እጅግ መሠረታዊ ተቋማዊ ፍላጎት በመሆኑ፤*

*በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ* /2/ (ሀ) *መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡*

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ “የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የወጣ አዋጅ ቁጥር 721/2004” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

1. “ሊዝ” ማለት በጊዜ በተገደበ ውል መሠረት የከተማ ቦታ የመጠቀም መብት የሚገኝበት የመሬት ይዞታ ስሪት ነው፤
2. “የከተማ ቦታ” ማለት በከተማ አስተዳደራዊ ወሰን ክልል ውስጥ የሚገኝ መሬት ነው፤
3. “ከተማ” ማለት ማዘጋጃ ቤት የተቋቋመበት ወይም 2000 ወይም ከዚያ በላይ የህዝብ ቁጥር ያለውና ከዚህ ውስጥ 50 በመቶ የሚሆነው የሰው ኃይል ከግብርና ውጭ በሆነ ሥራ ላይ የተሰማራ ሆኖ የሚገኝበት አካባቢ ነው፤
4. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47(1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ነው፤
5. “የከተማ አስተዳደር” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወይም የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ነው፤
6. “አግባብ ያለው አካል” ማለት የከተማ ቦታን ለማስተዳደርና ለማልማት ሥልጣን የተሰጠው የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር አካል ነው፤
7. “የሕዝብ ጥቅም” ማለት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ሕዝቦች በመሬት ላይ ያላቸውን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥና ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማትን በቀጣይነት ለማጎልበት አግባብ ያለው አካል በከተማው ፕላን መሠረት የሕዝብ ጥቅም ብሎ የሚወስነው የመሬት አጠቃቀም ነው፤
8. “የከተማ ፕላን” ማለት ሥልጣን ባለው አካል የፀደቀና ህጋዊ ተፈፃሚነት ያለው የከተማ መዋቅራዊ ፕላን፣ የአካባቢ ልማት ፕላን ወይም መሠረታዊ ፕላን ሲሆን አባሪ የፅሁፍ ማብራሪያዎችን ይጨምራል፤
9. “ጨረታ” ማለት የከተማ የመሬት ይዞታ በገበያ የውድድር ሥርዓት በሚወጡ የውድድር መስፈርቶች መሰረት አሸናፊ ለሚሆነው ተጫራች የከተማ መሬት በሊዝ የሚተላለፍበት ስልት ነው፤
10. “ምደባ” ማለት በጨረታ ሊስተናገዱ ለማይችሉ ተቋማት የከተማ ቦታ በሊዝ የሚፈቀድበት ስልት ነው፤

11.“የሊዝ መነሻ ዋጋ” ማለት ዋና ዋና የመሰረተ ልማት አውታሮች የመዘርጊያ ወጪን፣ ነባር ግንባታዎች ባሉበት አካባቢ የሚነሱ ግንባታዎችና ንብረቶችን ለማንሳት የሚያስፈልገውን ወጪና ለተነሺዎች የሚከፈል ካሣን እና ሌሎች አግባብ ያላቸው መሥፈርቶችን ታሳቢ ያደረገ የመሬት የሊዝ ዋጋ ነው፤

12.“የችሮታ ጊዜ” ማለት መሬት በሊዝ የተፈቀደለት ሰው የመሬቱን የሊዝ ቅድመ ክፍያ ከከፈለ በኋላ በየአመቱ መከፈል ያለበትን መክፈል ከመጀመሩ በፊት ከክፍያ ነጻ ሆኖ እንዲቆይ የሚፈቀድለት የእፎይታ ጊዜ ነው፤

13.“ስታንዳርድ” ማለት የሽንሻኖ ስታንዳርድ ወይም የመሬትና መሬት ነክ መረጃ ስታንዳርድ ወይም ሌላ ማንኛውም ስታንዳርድ ነው፤

14.“ግንባታ መጀመር” ማለት በቦታው ላይ ለመስራት ከተፈቀደው ግንባታ ወይም ሕንፃ ቢያንስ የመሠረት ሥራ መስራትና የኮለን ግንባታ ለማከናወን የሚያስችሉ የኮለን ብረቶች የማቆም ሥራ ማጠናቀቅ ነው፤

15.“የመሠረት ግንባታ ማጠናቀቅ” ማለት በፕላኑ መሰረት የዋናው ግንባታ መሬት ተቆፍሮ ሙሉ በሙሉ አርማታ የተሞላ፣ የወለል ሥራው የተጠናቀቀና የመጀመርያው ወለል ግድግዳ ግንባታው የተጀመረበት ነው፤

16.“ግንባታን በግማሽ ማጠናቀቅ” ማለት፡-

ሀ/ ቪላ ሲሆን የመሠረቱን፣ የኮለኖችና ለጣሪያ ውቅር የሚያስፈልጉ ቢሞችን ሥራ ማጠናቀቅ፣ ወይም

ለ/ ፎቅ ሲሆን የመሠረቱንና ከጠቅላላው ወለሎች ውስጥ 50 በመቶ የሚሆኑትን የሶሌታ ሥራ ማጠናቀቅ፣ ወይም

ሐ/ ሪል ስቴት ሲሆን የሁሉንም ብሎኮች ግንባታ እንደአግባቡ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ሀ) ወይም (ለ) በተመለከተው ደረጃ ማጠናቀቅ፣

ነው፤

17.“ግንባታ ማጠናቀቅ” ማለት በሊዝ የተፈቀደ ቦታ ላይ እንዲገነባ የተፈቀደን ግንባታ በተሰጠው የግንባታ ፈቃድ መሰረት ሙሉ በሙሉ መሥራትና ዋና ዋና አገልግሎቶች ተሟልተውለት ለአገልግሎት ዝግጁ ማድረግ ነው፤

18.“ነባር ይዞታ” ማለት የከተማ ቦታ በሊዝ ስርዓት መተዳደር ከመጀመሩ በፊት በሕጋዊ መንገድ የተያዘ ወይም ሊዝ ተግባራዊ ከሆነ በኃላ ለነባር ይዞታ ተነሺ በምትክ የተሰጠ ቦታ ነው፤

19.“የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ቦታ” ማለት በመሬት አጠቃቀም ፕላን መሰረት ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ አገልግሎት የተከለለ ወይም የተዘጋጀ ወይም የተሰጠ ቦታ ነው፤

20.“ግዙፍ ሪል ስቴት” ማለት በከተሞች ውስጥ የሚታየውን የመኖሪያ ቤት ችግር ለመቅረፍ ለሽያጭ ወይም ለኪራይ አገልግሎት የሚውሉ ቢያንስ 1ሺ ያላነሱ ቤቶችን የሚገነባ የቤቶች ልማት ነው፤

21.“ልዩ ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸው ፕሮጀክቶች” ማለት ለኢትዮጵያ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ከፍተኛ ለውጥ የሚያመጡ የልማት ፕሮጀክቶች፡ ወይም የትብብር መስኮች ለማስፋት በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ሀገሪቱ ከሌሎች ሀገሮች ጋር ለሚኖራት የተሻለ ግንኙነት መሰረት እንዲጥሉ የታቀዱ ፕሮጀክቶች ናቸው፤

22.“ሚኒስቴር” ማለት የከተማ ልማትና የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ነው፤

23.“ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፣

24.ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል።

3. **የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ አዋጅ የከተማ ቦታን በሚመለከት በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ማናቸውም ከተሞች ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

## ክፍል ሁለት

## መሠረታዊ የሊዝ ድንጋጌዎች

4. **ጠቅላላ**

1. የከተማ ቦታን የመጠቀም መብት በሊዝ የሚፈቀደው ለህዝቡ የጋራ ጥቅምና ዕድገት እንዲውል ለማድረግ ይሆናል፡፡
2. የሊዝ ጨረታ አቅርቦትና የመሬት አሰጣጥ ስርዓቱ ግልጽነትና ተጠያቂነትን የተከተለ በማድረግ ሙስናንና ብልሹ አሰራርን በመከላከል ከአድሎ የጸዳ እንዲሆን መደረግ አለበት፡፡
3. ጨረታ የመሬትን የወቅቱን የልውውጥ ዋጋ የሚያስገኝ መሆን አለበት፡፡
4. የከተማ ቦታ አሰጣጥ ስርዓቱ የህዝቡንና የከተሞችን ጥቅም በቀዳሚነት በማስከበር የከተማ ልማትን በማፋጠንና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የዜጎችን ተጠቃሚነት በማረጋገጥ የሀገሪቱን ልማት ቀጣይነት የሚያረጋግጥ መሆን አለበት፡፡

5. <u>ከሊዝ ሥሪት ውጪ ቦታ መያዝና መፍቀድ ስለመከልከሉ</u>

1. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ድንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሰው የከተማ መሬትን በዚህ አዋጅ ከተደነገገው የሊዝ ሥርዓት ውጪ መያዝ አይችልም፡፡
2. ማንኛውም ሰው አግባብ ካለው አካል ፈቃድ ሳያገኝ በህጋዊነት ከያዘው ይዞታ ጎን ያለን የከተማ ቦታ አስፋፍቶ መከለልና መጠቀም አይችልም፡፡
3. ማንኛውም ክልል ወይም የከተማ አስተዳደር በዚህ አዋጅ ከተደነገገው ውጪ የከተማ መሬትን መፍቀድ ወይም ማስተላለፍ አይችልም፡፡
4. የክልሎች ካቢኔዎች ይህ አዋጅ ለተወሰነ ጊዜ ተፈጻሚ ሳይሆን እንዲቆይ የሚደረግባቸውን ከተሞች ሊወሰኑ ይችላሉ፡፡ ሆኖም አዋጁ ከጸናበት ቀን ጀምሮ በማንኛውም ከተማ ላይ ተፈጻሚ ሳይደረግ ሊቆይ የሚችልበት የመሸጋገሪያ ጊዜ ከአምስት ዓመት ሊበልጥ አይችልም፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /4/ የተመለከቱት ከተሞች በመሸጋገሪያ ጊዜው ውስጥ የከተማ ቦታን ሊሰጡ የሚችሉት በጨረታ ይሆናል፡፡ የጨረታው መነሻ ዋጋም የአካባቢው አመታዊ የቦታ ኪራይ ተመን ይሆናል፡፡

6. <u>ነባር ይዞታዎች ወደ ሊዝ ሥሪት ስለሚቀየሩበት ሁኔታ</u>

1. ነባር ይዞታዎች ወደሊዝ ሥሪት የሚቀየሩበት ሁኔታ ሚኒስቴሩ በሚያቀርበው ዝርዝር ጥናት ላይ ተመሥርቶ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ይወሰናል፡፡ ሆኖም የጥናቱ ሂደት የነባር ኪራይ ተመን መከለስን አይከለክልም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ነባር ይዞታዎች ወደሊዝ በሚቀየሩበት ወቅት በአገር አቀፍ ደረጃ ተፈጻሚ እንዲሆን በሚጸድቀው ስታንዳርድና በከተማው ፕላን መሠረት በሚደረግ ሽንሻኖ የሚቀነስ ወይም የሚጨመር የከተማ ቦታ ይዞታ ሲኖር፡-
   
   ሀ/ ከሚቀነሰው ይዞታ ላይ ለሚነሳ ንብረት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ካሣ ይከፈላል፣ ወይም
   
   ለ/ ለሚጨመረው ይዞታ የሚፈጸመው ክፍያ በሊዝ አግባብ ይስተናገዳል፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም በነባር ይዞታ ላይ የሰፈረ ንብረት ባለቤትነት ከውርስ በስተቀር በማናቸውም መንገድ ለሌላ ሰው ከተላለፈ ንብረቱ የተላለፈለት ሰው የቦታው ባለይዞታ ሊሆን የሚችለው በሊዝ ሥሪት መሰረት ይሆናል፡፡

4. አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድ የተያዙ ይዞታዎችን ሥርዓት ለማስያዝ ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የሚያወጧቸውን ደንቦች ተከትሎ ከከተሞች ፕላንና ከሽንሻኖ ስታንዳርድ አንፃር ተቀባይነት የሚያገኙ ይዞታዎች በሊዝ ሥሪት ይተዳደራሉ፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሰረት በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች የማስተካከሉ ሂደት ተፈፃሚ የሚሆነው ይህ አዋጅ ከሚጸናበት ቀን ጀምሮ ባለው የአራት ዓመት ጊዜ ውስጥ ብቻ ይሆናል፡፡
6. ነባር ይዞታና የሊዝ ይዞታ እንዲቀላቀል ጥያቄ ቀርቦ ይዞታው እንዲቀላቀል ከተፈቀደ ጠቅላላ ይዞታው በሊዝ ሥሪት ይተዳደራል፡፡
7. በዚህ አንቀጽ መሰረት ወደ ሊዝ ሥሪት የሚገቡ ይዞታዎችን በተመለከተ ተፈጻሚ የሚሆነው የሊዝ ክፍያ መጠን በአካባቢው የሊዝ መነሻ ዋጋ መሠረት ይሆናል፡፡

7. <u>የከተማ ቦታ በሊዝ ስለመፍቀድ</u>

የከተማ ቦታ በሊዝ እንዲያዝ የሚፈቀደው፡-

1. ከተማው ፕላን ያለው ሲሆን የፕላኑን የቦታ አጠቃቀም ድንጋጌ ወይም ከተማው ፕላን የሌለው ሲሆን ክልሉ ወይም የከተማ አስተዳደሩ የሚያወጣውን ደንብ በመከተል፤ እና
2. በጨረታ ወይም በምደባ ስልት፤

ይሆናል፡፡

8. <u>ለጨረታ ስለሚዘጋጁ የከተማ ቦታዎች</u>

አግባብ ያለው አካል፡-

1. ለጨረታ የተዘጋጁ የከተማ ቦታዎች ለሕዝብ ይፋ ከመደረጋቸው በፊት፡-
   ሀ) ከማንኛውም የይገባኛል ጥያቄ ነጻ መሆናቸውን፤
   ለ) የከተማውን ፕላን ተከትለው የተዘጋጁ መሆናቸውን፤
   ሐ) መሠረታዊ የመሠረተ ልማት አውታሮች አቅርቦት ያላቸው መሆኑን፤
   መ) ተሸንሽነው የወሰን ድንጋይ የተተከለላቸውና ልዩ የሽንሻኖ መለያ ቁጥር የተሰጣቸው መሆናቸውን፤
   ሠ) ሳይት ፕላንና ሌሎች አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች የተዘጋጁላቸው መሆናቸውን፤ እና

2. የጨረታው አፈጻጸም ግልጽነትና ተጠያቂነት ባለበት አሠራር የመሬቱን ትክክለኛ ዋጋ በሚያስገኝ መልኩ መከናወኑን፤

ማረጋገጥ አለበት፡፡

9. **ለጨረታ የተዘጋጀ የከተማ ቦታ መረጃዎች**

1. ለጨረታ የተዘጋጀ የከተማ ቦታን የሚመለከት መረጃ የቦታውን ደረጃ፣ የሊዝ መነሻ ዋጋና አግባብነት ያላቸው ሌሎች ዝርዝር መረጃዎችን መያዝ አለበት፡፡
2. ለጨረታ የተዘጋጀ የከተማ ቦታ የተለየ የልማት መርሃ-ግብርና የአፈጻጸም ሰሌዳ የሚያስፈልገው ከሆነ የልማት መርሃ-ግብሩና የአፈጻጸም ሰሌዳው በመረጃው ውስጥ እንዲካተት ይደረጋል፡፡

10. **ለጨረታ የሚቀርቡ የከተማ ቦታዎች ዕቅድን ለህዝብ ይፋ ስለማድረግ**

1. አግባብ ያላቸው አካላት፡-

ሀ) የመሬት አቅርቦት ፍላጎትንና ትኩረት የሚደረግባቸውን የልማት መስኮች መሰረት በማድረግ በየዓመቱ ለጨረታ የሚያወጡትን የከተማ ቦታ መጠን በመለየት ዕቅዳቸውን ለህዝብ ይፋ ማድረግ፤ እና

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 የተመለከቱትን መረጃዎች ሕዝቡ በቀላሉ ሊያገኛቸው እንዲችል ማድረግ፤

አለባቸው።

2. አግባብ ያላቸው አካላት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለህዝብ ይፋ ያደረጉትን እቅዳቸውን ተከትለው ወቅቱን የጠበቀ የመሬት አቅርቦት እንዲኖር የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው።

11. **የጨረታ ሂደት**

1. አግባብ ያለው አካል የሊዝ ጨረታ ለማካሄድ የጨረታ ማስታወቂያ ማውጣትና የጨረታ ሰነድ መሸጥ አለበት፡፡
2. የጨረታ ሰነድ ሽያጭ በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ ሁሉ በቀላሉ በሚያገኙበት አግባብ የሚፈፀም ይሆናል፤ ሆኖም አንድ ተጫራች ለአንድ ቦታ ከአንድ የጨረታ ሰነድ በላይ በመግዛት መወዳደር አይችልም፡፡

3. የጨረታ ማስከበሪያ መጠን በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች በሚወጡ ደንቦች የሚወሰን ሆኖ በማንኛውም ሁኔታ ከመሬቱ የሊዝ መነሻ ዋጋ ከአምስት በመቶ በታች ሊሆን አይችልም፡፡
4. ለመጀመርያ ጊዜ በወጣ የሊዝ ጨረታ ቢያንስ ሦስት ተወዳዳሪዎች ካልቀረቡ ጨረታው ይሰረዛል፡፡
5. በአቀረበው የጨረታ ዋጋና የቅድሚያ ክፍያ መጠን ላይ ተመሥርቶ ከፍተኛውን ነጥብ ያገኘ ተጫራች የጨረታው አሸናፊ ይሆናል፡፡
6. የጨረታ አሸናፊዎች ዝርዝርና ያገኙት የውድድር ውጤት በማስታወቂያ ሰሌዳ ለህዝብ ይፋ መደረግ አለበት፡፡
7. ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች በግል ለሚካሄዱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ ሆስፒታሎች፣ የጤና ምርምር ተቋማት፣ ባለ አራት ኮከብና ከዚያ በላይ ደረጃ ላላቸው ሆቴሎች እና ግዙፍ ሪል ስቴቶች የሚሆኑ ቦታዎችን በቅድሚያ በማዘጋጀት ቦታዎቹ በጨረታ አግባብ የሚስተናገዱበትን ሁኔታ ያመቻቻሉ፡፡
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተደነገገው ቢኖርም በጨረታው ለመሳተፍ የቀረበው አንድ ተጫራች ብቻ ቢሆንም ፕሮጀክቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (7) ሥር የሚወድቅ ከሆነ የማልማት አቅሙ አግባብ ባለው አካል ተረጋግጦ ይስተናገዳል፡፡

12. <u>በምደባ ስለሚሰጥ የከተማ ቦታ</u>

1. በሚመለከተው ክልል ወይም የከተማ አስተዳደር ካቢኔ እየተወሰኑ የሚከተሉት የከተማ ቦታዎች በምደባ እንዲያዙ ሊፈቀዱ ይችላሉ፦
   ሀ) ለባለበጀት የመንግስት መሥርያ ቤቶች ለቢሮ አገልግሎት የሚውሉ ቦታዎች፤
   ለ) በመንግሥት ወይም በበጎ አድራጎት ድርጅቶች ለሚካሄዱ ማህበራዊ የአገልግሎት መስጫ ተቋማት የሚውሉ ቦታዎች፤
   ሐ) በመንግስት ለሚካሄዱ የጋራ መኖርያ ቤቶች ልማት ፕሮግራሞች እና በመንግስት እየተወሰነ ለሚካሄዱ ለራስ አገዝ የጋራ መኖርያ ቤት ግንባታዎች የሚውሉ ቦታዎች፤
   መ) ለእምነት ተቋማት አምልኮ ማካሄጃ የሚውሉ ቦታዎች፤
   ሠ) ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ልማት የሚውሉ ቦታዎች፤

ረ) ከመንግሥት ጋር በተደረጉ ስምምነቶች ለኤምባሲዎችና ለአለምአቀፍ ድርጅቶች አገልግሎት የሚውሉ ቦታዎች፤

ሰ) በክልሉ ፕሬዚዳንት ወይም በከተማው አስተዳደር ከንቲባ እየታዩ ለካቢኔው ለሚመሩ ልዩ አገራዊ ፋይዳ ላላቸው ፕሮጀክቶች የሚውሉ ቦታዎች፡፡

2. በከተማ መልሶ ማልማት ፕሮግራም ምክንያት ተነሺ የሚሆን የነባር ይዞታ ባለመብት ምትክ ቦታ የማግኘት መብት ይኖረዋል።

3. በክልል ወይም በድሬዳዋ ከተማ የመንግስት ወይም የቀበሌ መኖሪያ ቤት ህጋዊ ተከራይ የሆነ ሰው በከተማ መልሶ ማልማት ፕሮግራም ምክንያት ተነሺ በሚሆንበት ጊዜ ተተኪ ቤት የሚያገኝበትን ሁኔታ ማመቻቸት ካልተቻለ የመኖሪያ ቤት መስሪያ የከተማ ቦታ በሊዝ መነሻ ዋጋ የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡ ሆኖም አግባብ ያለው አካል የሚወስነውን የአቅም ማሳያ ገንዘብ በዝግ የባንክ ሂሳብ ማስቀመጥ አለበት፡፡

4. በአዲስ አበባ ከተማ የመንግስት ወይም የቀበሌ መኖሪያ ቤት ህጋዊ ተከራይ የሆነ ሰው በከተማው መልሶ ማልማት ፕሮግራም ምክንያት ተነሺ በሚሆንበት ጊዜ የጋራ መኖሪያ ቤት በግዥ የሚያገኝበት ሁኔታ ይመቻችለታል።

5. የመንግስት ወይም የቀበሌ የንግድ ቤት ህጋዊ ተከራይ የሆነ ሰው በከተማ መልሶ ማልማት ፕሮግራም ምክንያት ተነሺ በሚሆንበት ጊዜ በሚመለከተው ክልል ወይም የከተማ አስተዳደር በሚወሰነው መሠረት ይስተናገዳል፡፡

13. **<u>የከተማ ቦታ ምደባ ጥያቄ አቀራረብ</u>**

የከተማ ቦታ በምደባ አማካይነት በሊዝ ለመያዝ የሚቀርብ ጥያቄ ከሚከተሉት ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡-

1. ጥያቄ ያቀረበው ተቋም የበላይ ተቆጣጣሪ አካል ወይም የዘርፍ አካላት የድጋፍ ደብዳቤ፤
2. በቦታው ላይ የሚከናወነው ፕሮጀክት ዝርዝር ጥናት፤ እና
3. ለፕሮጀክቱ ማስፈፀሚያ የተመደበለት በጀት ማስረጃ፡፡

14. **<u>የከተማ ቦታ የሊዝ ዋጋ</u>**

1. ማንኛውም የከተማ ቦታ የሊዝ መነሻ ዋጋ ይኖረዋል፡፡ የመነሻ ዋጋ ትመና ዘዴው በሚመለከታቸው ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች በሚወጡ ደንቦች መሠረት የየከተሞቹን ነባራዊ ሁኔታ መነሻ በማድረግ ይወሰናል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የተሰላውን የከተማ ቦታዎች የሊዝ መነሻ ዋጋ መሰረት በማድረግ የዋጋ ቀጠና ካርታ መዘጋጀት አለበት፡፡
3. የሊዝ መነሻ ዋጋ ወቅታዊነቱን ጠብቆ እንዲሄድ ቢያንስ በየሁለት ዓመቱ መከለስ አለበት፡፡

15. **<u>የችሮታ ጊዜ</u>**

1. የከተማ ቦታ በሊዝ የተፈቀደለት ሰው እንደ ልማቱ ወይም አገልግሎቱ ዓይነት የችሮታ ጊዜ ሊሰጠው ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በክ5ልሎችና በከተማ አስተዳደሮች በሚወጡ ደንቦች ይወሰናል፡፡
2. የችሮታ ጊዜ የሊዝ ውል ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ የሚታሰብ ሆኖ በማንኛውም ሁኔታ ከግንባታ ማጠናቀቂያ ጊዜ መብለጥ የለበትም፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>የከተማ ቦታ ሊዝ አስተዳደር</u>

16. **<u>የሊዝ ውል</u>**

1. በዚህ አዋጅ መሰረት የከተማ ቦታ በሊዝ እንዲይዝ የተፈቀደለት ሰው አግባብ ካለው አካል ጋር የሊዝ ውል መፈራረም ይኖርበታል፡፡
2. የሊዝ ውሉ የግንባታ መጀመርያ፣ የግንባታ ማጠናቀቅያ፣ የክፍያ አፈፃፀም ሁኔታ፣ የችሮታ ጊዜ፣ የውል ሰጪና የውል ተቀባይ መብትና ግዴታዎች እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ዝርዝር ሁኔታዎች ማካተት አለበት፡፡
3. የከተማ ቦታ በሊዝ እንዲይዝ የተፈቀደለት ሰው የሊዝ ውል ከመፈረሙ በፊት ስለውሉ ይዘት እንዲያውቅ ተደርጎ በቅድሚያ የሚከፈለውን የገንዘብ መጠን ገቢ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡
4. የሊዝ ውል የፈረመ ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 በተገለፀው መሰረት በስሙ የተዘጋጀ የሊዝ ይዞታ የምስክር ወረቀትና ቦታውን በመስክ ተገኝቶ የሚረከብ ይሆናል፡፡
5. አግባብ ያለው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሰረት ርክክብ የተፈፀመበት የከተማ ቦታ በሊዝ ውሉ መሠረት እንዲለማ መደረጉንና በየዓመቱ የሚከፈለው የሊዝ ክፍያ ወቅቱን ጠብቆ እየተፈጸመ ስለመሆኑ ክትትል የማድረግና የማረጋገጥ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

17. **<u>የሊዝ ይዞታ የምስክር ወረቀት</u>**

1. የከተማ ቦታ በሊዝ የተፈቀደለት ሰው የሊዝ ይዞታ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡
2. የሊዝ ይዞታ የምስክር ወረቀት የሚከተሉትን መግለጫዎች አካቶ መያዝ አለበት፣
   ሀ) ቦታ በሊዝ የተፈቀደለትን ሰው ሙሉ ስም ከእነአያት፤
   ለ) የቦታውን ስፋትና አድራሻ፤
   ሐ) የቦታውን የአገልግሎት ዓይነት፣ ደረጃና የፕሎት ቁጥር፤
   መ) የቦታውን ጠቅላላ የሊዝ ዋጋና በቅድሚያ የተከፈለውን መጠን፤
   ሠ) በየዓመቱ የሚፈጸመውን የሊዝ ክፍያ መጠንና ክፍያው የሚጠናቀቅበትን ጊዜ፤
   ረ) የሊዝ ይዞታው ፀንቶ የሚቆይበትን ዘመን፡፡

18. <u>የሊዝ ዘመን</u>

1. የከተማ ቦታ ሊዝ ዘመን እንደየከተማው የዕድገት ደረጃና የልማት ሥራው ዘርፍ ወይም የአገልግሎቱ ዓይነት ሊለያይ የሚችል ሆኖ ጣሪያው እንደሚከተለው ይሆናል፦
   ሀ) በማናቸውም ከተማ፡-
      (1) ለመኖሪያ ቤት፣ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ ለምርምርና ጥናት፣ ለመንግስት መሥሪያ ቤት፣ ለበጎ አድራጎት ድርጅትና ለሃይማኖት ተቋም 99 ዓመታት፤
      (2) ለከተማ ግብርና 15 ዓመታት፤
      (3) ለዲፕሎማቲክና ለዓለም አቀፍ ተቋማት በመንግሥት ስምምነት መሠረት ለሚወሰን ዓመት፤
   ለ) በአዲስ አበባ ከተማ፡-
      (1) ለትምህርት፣ ለጤና፣ ለባህልና ለስፖርት 90 ዓመታት፤
      (2) ለኢንዱስትሪ 70 ዓመታት፤
      (3) ለንግድ 60 ዓመታት፤
      (4) ለሌሎች 60 ዓመታት፤
   ሐ) በሌሎች ከተሞች፦
      (1) ለትምህርት፣ ለጤና፣ ለባህልና ለስፖርት 99 ዓመታት፤
      (2) ለኢንዱስትሪ 80 ዓመታት፤
      (3) ለንግድ 70 ዓመታት፤

(4) ለሌሎች 70 ዓመታት።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) የተደነገገው ቢኖርም፡-

ሀ) በባሕሪው ረዘም ያለ የሊዝ ይዞታ ዘመን ለሚጠይቅ የልማት ሥራ ወይም አገልግሎት ከተወሰነው ዘመን ጣሪያ ከግማሽ ሳይበልጥ ሊጨመር ይችላል፤

ለ) ለጊዜው በልማት ሥራ ጥቅም ላይ በማይውሉ የከተማ ቦታዎች ላይ ለሚቀርቡ የአጭር ጊዜ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተቋማት የቦታ ጥያቄዎች ከአምስት ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ በሊዝ ይስተናገዳሉ፡፡ እንደአስፈላጊነቱ ለተመሳሳይ ጊዜ ሊታደስላቸው ይችላል፡፡

19. <u>**የሊዝ ዘመን ዕድሳት**</u>

1. የሊዝ ዘመን ሲያበቃ በወቅቱ የሚኖሩትን የቦታውን የሊዝ መነሻ ዋጋና ሌሎች መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ ሊታደስ ይችላል፡፡ ሆኖም የሊዝ ዘመኑ ሊታደስ በማይችልበት ሁኔታ ለሊዝ ባለይዞታው ካሣ አይከፈልም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው መሠረት ባለይዞታው የሊዝ ዘመኑ ሊታደስለት የሚችለው የሊዝ ዘመኑ ሊያበቃ ከ10 እስከ 2 ዓመት እስኪቀረው ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ እድሳት እንዲደረግለት መፈለጉን አግባብ ላለው አካል በጽሑፍ ካመለከተ ብቻ ይሆናል፡፡
3. አግባብ ያለው አካል ማመልከቻው በቀረበለት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ውሳኔውን ለአመልካቹ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ውሳኔውን ሳያሳውቅ ቢቀር በእድሳት ጥያቄው እንደተስማማ ተቆጥሮ በወቅቱ በሚኖረው የሊዝ መነሻ ዋጋና ለአገልግሎቱ በሚሰጠው የሊዝ ዘመን መሰረት የሊዝ ውሉ ይታደሳል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት መልስ መስጠት የነበረበት የሥራ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ በዕድሳቱ ምክንያት የደረሰ ጉዳት ካለ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

20. <u>**የመክፈያ ጊዜ**</u>

1. የከተማ ቦታ በሊዝ የተፈቀደለት ሰው ወጪውን ለመመለስ የሚያስፈልገውን ጊዜ ግምት ውስጥ በማስገባት የሚወሰን የመክፈያ ጊዜ ሊሰጠው ይችላል፡፡
2. የቅድሚያ ክፍያ እንደየክልሉና የከተማ አስተዳደሩ ሁኔታ የሚወሰን ሆኖ ከጠቅላላ የቦታው የሊዝ ክፍያ መጠን 10 በመቶ ማነስ የለበትም፡፡

3. የቅድሚያ ክፍያው ከተከፈለ በኃላ የሚቀረው የሊዝ ዋጋ በመክፈያ ዘመኑ እኩል ዓመታዊ ክፍያ የሚፈጸም ይሆናል፡፡
4. በቀሪው ክፍያ ላይ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የማበደሪያ የወለድ ተመን መሠረት ወለድ ይከፈላል፡፡ የሚመለከተው አካል የየወቅቱን የማበደርያ ወለድ ተመን ተከታትሎ ወቅታዊ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡
5. ወቅቱን ጠብቆ በማይፈጸም ዓመታዊ ክፍያ ላይ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በዘገዩ የብድር ክፍያዎች ላይ በሚጥለው የቅጣት ተመን መሠረት መቀጫ ይከፈላል፡፡
6. የሊዝ ባለይዞታው የሊዝ ክፍያውን ለመክፈል በሚገባው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካልከፈለና የሦስት ዓመት ውዝፍ ካለበት አግባብ ያለው አካል ንብረቱን ይዞ በመሸጥ ለውዝፍ ዕዳው መክፈያ የማዋል ሥልጣን ይኖረዋል፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (5) የተደነገገው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ (1) ተራ ፊደል (ሀ) ወይም (መ) መሠረት ለባለበጀት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም ለሃይማኖታዊ ተቋም በምደባ በሚሰጥ የከተማ ቦታ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡ ሆኖም ባለበጀት የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ወይም ሃይማኖታዊ ተቋሙ በምደባ ያገኘውን መሬት ለማስለቀቅ የተከፈለውን ካሣ የሚተካ ክፍያ ይከፍላል፡፡

21. <u>በሊዝ የተያዘ የከተማ ቦታ አጠቃቀም</u>

1. የከተማ ቦታ ሊዝ ባለይዞታ በሊዝ ውሉ ውስጥ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ቦታውን ለተፈቀደለት አገልግሎት ጥቅም ላይ ማዋል አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የሊዝ ባለይዞታው የቦታውን አጠቃቀም ለመለወጥ አግባብ ላለው አካል ሊያመለክት ይችላል፡፡
3. አግባብ ያለው አካል የታቀደው የቦታ አጠቃቀም ከከተማው የመሬት አጠቃቀም ፕላን ጋር የማይጋጭ መሆኑን ሲያረጋግጥ ለውጡን ሊፈቅድ ይችላል፡፡

22. <u>ግንባታ ስለመጀመር</u>

1. ማንኛውም የሊዝ ባለይዞታ በሊዝ ውሉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ መሠረት ግንባታ መጀመር አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም እንደ ግንባታው ውስብስብነት እየታየ ክልሉ ወይም የከተማ አስተዳደሩ በሚያወጣው ደንብ መሠረት የግንባታ መጀመርያ ጊዜው ሊራዘም ይችላል፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የሊዝ ባለይዞታ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ግንባታውን ካልጀመረ ቦታውን ከተረከበበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን የሊዝ ክፍያና የጠቅላላውን የሊዝ ዋጋ ሰባት በመቶ መቀጮ እንዲከፍል ተደርጎ ቦታውን አግባብ ያለው አካል መልሶ ይረከባል፡፡
4. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የከተማ ቦታ ይዞታ የተፈቀደለት ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ግንባታ ካልጀመረ ለአቅም ማሳያ በዝግ የባንክ ሂሳብ ከተያዘው ገንዘብ ላይ ሦስት በመቶ ተቀጥቶ ቦታውን አግባብ ያለው አካል መልሶ ይረከባል፡፡
5. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ (1) ተራ ፊደል (ሀ)፣ (ለ)፣ (ሐ)፣ (መ) ወይም (ረ) መሠረት ቦታ የተፈቀደለት የሊዝ ባለይዞታ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ግንባታ ካልጀመረ የሊዝ ውሉ ተቋርጦ ቦታውን አግባብ ያለው አካል መልሶ ይረከባል፡፡

23. <u>**ግንባታ ስለማጠናቀቅ**</u>

1. ማንኛውም የሊዝ ባለይዞታ የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) ድንጋጌዎች ተከትሎ በሊዝ ውሉ ውስጥ በተመለከተው የጊዜ ገደብ መሠረት ግንባታውን ማጠናቀቅ አለበት፡፡
2. የግንባታ ማጠናቀቂያ የጊዜ ገደብ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

   ሀ) ለአነስተኛ ግንባታ 24 ወራት፤

   ለ) ለመካከለኛ ግንባታ 36 ወራት፤

   ሐ) ለከፍተኛ ግንባታ 48 ወራት፡፡
3. የግንባታ ደረጃዎች በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች በሚወጡ ደንቦች ይወሰናሉ፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም እንደ ግንባታው ውስብስብነት እየታየ ክልሉ ወይም የከተማ አስተዳደሩ በሚያወጣው ደንብ መሠረት የግንባታ ማጠናቀቂያ ጊዜው ሊራዘም ይችላል፡፡ ሆኖም ለግንባታ ማጠናቀቂያ የሚሰጠው ጠቅላላ ጊዜ በማንኛውም ሁኔታ፡-

   ሀ) ለአነስተኛ ግንባታ ከሁለት ዓመት ከስድስት ወር፤

ለ) ለመካከለኛ ግንባታ ከአራት ዓመት፣ እና

ሐ) ለከፍተኛ ግንባታ ከአምስት ዓመት፣ መብለጥ አይችልም፡፡

5. ማንኛውም የሊዝ ባለይዞታ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በተወሰነው የጊዜ ገደብ ግንባታውን ካላጠናቀቀ አግባብ ያለው አካል የሊዝ ውሉን በማቋረጥ ቦታውን መልሶ መረከብ ይችላል፡፡

6. የሊዝ ውል የተቋረጠበት ሰው በራሱ ከስድስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በቦታው ላይ የሠፈረ ንብረቱን ማንሳት አለበት፡፡ ለዚህም አግባብ ያለው አካል በፅሁፍ ማስጠንቀቅያ መስጠት አለበት፡፡

7. የሊዝ ባለይዞታው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) መሠረት ንብረቱን ካላነሳ አግባብ ያለው አካል፡-

   ሀ) ጅምር ግንባታው በፕላኑ መሰረት የተገነባ መሆኑን አረጋግጦ ግንባታውን ማጠናቀቅና መጠቀም ለሚችል ሰው በግልፅ ጨረታ ንብረቱን በመሸጥ ማስተላለፍ፣ ወይም

   ለ) ንብረቱን በራሱ ወጪ በማንሳት ከሊዝ ቅድሚያ ክፍያው ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት በምደባ የከተማ ቦታ ይዞታ የተፈቀደለትን ሰው የሚመለከት ሲሆን ለአቅም ማሳያ በዝግ የባንክ ሂሳብ ከተያዘው ገንዘብ ላይ ተሰልቶ ወጪውን ማስመለስ፣

   ይችላል፡፡

8. አግባብ ያለው አካል በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /7/ (ሀ) መሠረት ከሚፈጸም ሽያጭ ከሚገኝ ገቢ ላይ ሽያጩን ለማስፈጸም የወጡ ወጪዎችን ቀንሶ ተራፊ ገንዘብ ካለ ለባለመብቱ ተመላሽ ያደርጋል፡፡

## 24. የሊዝ መብትን ስለማስተላለፍና በዋስትና ስለማስያዝ

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተወሰነው የሊዝ ዘመንና በአንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቦታውን ለተፈቀደለት አገልግሎት ጥቅም ላይ የማዋል ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የሊዝ ባለይዞታ መብቱን ለማስተላለፍ ወይም በከፈለው የሊዝ ክፍያ መጠን በዋስትና ለማስያዝ ወይም በካፒታል አስተዋፆነት ለመጠቀም ይችላል፡፡

2. ማንኛውም የሊዝ ባለይዞታ የሊዝ መብቱን ግንባታ ከመጀመሩ ወይም ግንባታውን በግማሽ ከማጠናቀቁ በፊት ከውርስ በስተቀር ማስተላለፍ የሚችለው አግባብ ባለው አካል ቁጥጥር የሚደረግበት ግልጽ የሽያጭ ሥርዓትን በመከተል ይሆናል፡፡
3. የሊዝ ይዞታ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ሲተላለፍ፡-
   ሀ) የተፈጸመው የሊዝ ክፍያና የሊዝ ክፍያው በባንክ ቢቀመጥ ያስገኝ የነበረው ወለድ፤
   ለ) የተከናወነው ግንባታ ዋጋ፤ እና
   ሐ) የሊዝ መብቱ በመተላለፉ የተገኘው የሊዝ ዋጋ 5 በመቶ፤

ለሊዝ ባለመብቱ እንዲቀርለት ተደርጎ ልዩነቱ አግባብ ላለው አካል ገቢ ይደረጋል፡፡

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ማንኛውም የሊዝ ባለይዞታ ግንባታ ከመጀመሩ በፊት የሊዝ መብቱን በዋስትና ማስያዝ የሚችለው ከሊዝ የቅድሚያ ክፍያው ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ሊደረጉ የሚችሉ ተቀናሾች ታስበው በሚቀረው የገንዘብ መጠን ይሆናል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት የሊዝ መብቱን በዋስትና ያስያዘ ሰው የዋስትና ግዴታውን ባለመወጣቱ በዋስትና መያዣው ላይ የፍርድ አፈጻጸም ትዕዛዝ የተላለፈበት የእዳ ጥያቄ ከቀረበ አግባብ ያለው አካል የሊዝ ውሉን አቋርጦ መሬቱን በመረከብ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የሚደረጉ ተቀናሾችን አስቀርቶ ቀሪውን ለዋስትና ባለመብቱ ይከፍላል፡፡ ተራፊ ገንዘብ ካለም ለሊዝ ባለመብቱ ይመልስለታል፡፡
6. በሌላ አኳኋን ስምምነት ካልተደረገ በስተቀር በመሬት የመጠቀም መብት በዋስትና ሲያዝ ወይም ሲተላለፍ በመሬቱ ላይ የተገነባው ህንፃና ከህንፃው ጋር የተያያዙ መገልገያዎች መብት አብሮ ይያዛል ወይም ይተላለፋል፤ እንዲሁም ሕንፃና ከሕንፃው ጋር የተያያዙ መገልገያዎች በዋስትና ሲያዙ ወይም ሲተላለፉ በመሬት የመጠቀም መብቱም አብሮ ይያያዛል ወይም ይተላለፋል፡፡
7. ማንኛውም ሰው በመሬት የወቅት ጥበቃ የሚመጣን ጥቅም ለማግኘት በማሰብ በተደጋጋሚ ጊዜ ግንባታ ሳያጠናቅቅ የሊዝ መብቱን የሚያስተላልፍ ከሆነ የሚመለከተው አካል በማንኛውም የሊዝ ጨረታ እንዳይሳታፍ ሊከለክለው ይችላል፡፡

8. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሊዝ መብት በማናቸውም ሁኔታ ሲተላለፍ በሊዝ ውሉ የተመለከቱት የሊዝ ባለይዞታው ግዴታዎች በሙሉ ያለ ቅድመ ሁኔታ መብቱ ለተላለፈለት ሦስተኛ ወገን ይተላለፋሉ፡፡

25. **የሊዝ ይዞታ መቋረጥና የካሳ አከፋፈል**

1. የከተማ ቦታ የሊዝ ይዞታ፡-
   ሀ) ባለይዞታው በዚህ አዋጅ አንቀጽ21 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ቦታውን ጥቅም ላይ ካላዋለ፤
   ለ) ቦታው ለሕዝብ ጥቅም ተብሎ ለሌላ አገልግሎት እንዲውል ሲወሰን፤ ወይም
   ሐ/ የሊዝ ይዞታ ዘመኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ካልታደሰ፤

   ሊቋረጥ ይችላል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ (ሀ) ድንጋጌ ቢኖርም ቦታው ጥቅም ላይ ያልዋለው በፍትሐብሔር ሕጉ በተደነገገው መሠረት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑ ከተረጋገጠ አግባብ ያለው አካል ከአቅም በላይ በሆነው ምክንያት የባከነውን ጊዜ የሚያካክስ ተጨማሪ ጊዜ ሊፈቅድ ይችላል፡፡
3. የከተማ ቦታ የሊዝ ይዞታ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ (ሀ) መሠረት ሲቋረጥ ተገቢው ወጪና መቀጫ ተቀንሶ የሊዝ ክፍያው ለባለመብቱ ተመላሽ ይሆናል፡፡
4. የከተማ ቦታ የሊዝ ይዞታ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ (ለ) መሠረት ሲቋረጥ ባለይዞታው አግባብ ባለው ሕግ መስረት ተመጣጣኝ ካሣ ይከፈለዋል፡፡
5. የከተማ ቦታ የሊዝ ይዞታ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ (ሐ) መሠረት ሲቋረጥ ባለይዞታው እስከ አንድ ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ በቦታው ላይ ያሰፈረውን ንብረት በማንሳት ቦታውን አግባብ ላለው አካል መልሶ ማስረከብ አለበት፡፡
6. ባለይዞታው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ንብረቱን ካላነሳ የሚመለከተው አካል ቦታውን ከነንብረቱ ያለምንም ክፍያ ሊወስደው ይችላል፡፡ ለአፈፃፀሙም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ፖሊስን ማዘዝ ይችላል፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ (ለ) መሠረት የሊዝ ውል ሲቋረጥ የቦታው ርክክብ የሚፈፀመው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 31 በተደነገገው መሠረት ይሆናል፡፡

**ክፍል አራት**

## የከተማ ቦታ ስለማስለቀቅ

### 26. የከተማ ቦታ የማስለቀቅ ሥልጣን

1. አግባብ ያለው አካል ከቦታው ለሚነሳው ንብረት ተመጣጣኝ ካሣ በቅድሚያ እንዲከፈል በማድረግ የከተማ ቦታ ይዞታን ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የማስለቀቅና የመረከብ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በሚወሰድ እርምጃ ምክንያት ተነሺ ለሚሆነው ሰው መጠኑ በክልሉ ወይም በከተማው አስተዳደር የሚወሰን ምትክ ቦታ በከተማው ውስጥ ይሰጠዋል፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የከተማ ቦታ በሊዝ የያዘ ሰው የሊዝ ውሉን ባለማክበሩ፣ የቦታ አጠቃቀሙ ከከተማው ፕላን ጋር ሊጣጣም የሚችል ባለመሆኑ ወይም ቦታው መንግሥት ለሚያካሂደው የልማት ሥራ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር የሊዝ ዘመኑ ከማለቁ በፊት ይዞታውን እንዲለቅ አይደረግም፡፡
4. አግባብ ያለው አካል በሕገ ወጥ መንገድ የተያዘን የከተማ ቦታ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 27 መሠረት የማስለቀቂያ ትዕዛዝ መስጠትና ካሣ መክፈል ሳያስፈልግ የሰባት የሥራ ቀናት የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ብቻ ለባለይዞታው በአካል በመስጠት ወይም በቦታው በሠፈረው ንብረት ላይ በመለጠፍ የማስለቀቅ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

### 27. የማስለቀቂያ ትዕዛዝ

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የከተማ ቦታ ይዞታ እንዲለቀቅ ሲወሰን ይዞታው የሚለቀቅበት ጊዜ፣ ሊከፈል የሚገባው የካሣ መጠን እና ሊሰጥ የሚችለው የምትክ ቦታ ስፋትና አካባቢ ተጠቅሶ የማስለቀቂያ ትዕዛዝ ለባለይዞታው በጽሁፍ ይሰጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚሰጠው የማስጠንቀቂያ ጊዜ በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች በሚወጡ ደንቦች ይወስናል፤ ሆኖም በማንኛውም ሁኔታ ከ90 ቀናት ያነሰ ሊሆን አይችልም፡፡
3. የሚለቀቀው የከተማ ቦታ ይዞታ የመንግሥት ቤት የሰፈረበት ከሆነ የማስለቀቂያ ትዕዛዙ የሚደርሰው ቤቱን ለሚያስተዳድረው አካል ይሆናል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የማስለቀቂያ ትዕዛዝ የተላለፈበት ቤት ተከራይቶ ከነበረ ትዕዛዙ የደረሰው አካል የማስጠንቀቂያ ጊዜው ከማብቃቱ በፊት የኪራይ ውሉን ለማቋረጥ የሚያስችል እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

28. **የማስለቀቂያ ትዕዛዝን ወይም ማስጠንቀቂያን የሚመለከቱ አቤቱታዎች**

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የማስለቀቂያ ትዕዛዝ የደረሰው ወይም ትዕዛዝ በተሰጠበት ንብረት ላይ ያለ መብቴ ወይም ጥቅሜ ይነካብኛል የሚል ማንኛውም ሰው ትዕዛዙ በደረሰ በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ ያለውን አቤቱታ ከዝርዝር ምክንያቱና ማስረጃው ጋር አግባብ ላለው አካል ማቅረብ ይችላል፡፡
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ማስጠንቀቂያ የደረሰው ሰው ማስጠንቀቂያው በደረሰው በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ከዝርዝር ምክንያቱና ማስረጃው ጋር አግባብ ላለው አካል ማቅረብ ይችላል፡፡
3. አግባብ ያለው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሠረት የቀረበለትን አቤቱታ በአግባቡ በማጣራት ውሳኔ መስጠትና ውሳኔውን ለአቤቱታ አቅራቢው በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡ የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት ያላገኘ ከሆነ ምክንያቱ በግልጽ በውሳኔው ውስጥ መገለጽ ይኖርበታል፡፡

29. **አግባብ ባለው አካል ውሳኔ ላይ ስለሚቀርብ ይግባኝ**

1. አግባብ ያለው አካል በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ አቤቱታ አቅራቢ ውሳኔው በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ይግባኙን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 30 መሠረት ለተቋቋመው ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ጉባዔው የቀረበለትን ይግባኝ በ30 የሥራ ቀናት ውስጥ መርምሮ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡ የሰጠውን ውሳኔም ለተከራካሪ ወገኖች በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡
3. በካሣ ክርክር ላይ ካልሆነ በስተቀር ምትክ ቦታን ጨምሮ በሌሎች በሕግም ሆነ ፍሬ ነገር ክርክሮች ላይ ጉባዔው የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡
4. ጉባዔው ካሣን በሚመለከት በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ተከራካሪ ወገን ውሳኔው በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ለሚመለከተው የከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ወይም የከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በሌለበት ለሚመለከተው መደበኛ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ይግባኝ መቅረብ የሚችለው ይግባኝ ባዩ እንዲለቀቅ ትዕዛዝ የተሰጠበትን የከተማ ቦታ አግባብ ላለው አካል ካስረከበና ያስረከበበትን ሰነድ ከይግባኝ አቤቱታው ጋር አያይዞ ካቀረበ ብቻ ይሆናል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤት ይግባኙ በቀረበለት 30 የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡ የፍርድ ቤቱ ውሳኔም የመጨረሻ ይሆናል፡፡

30. **<u>ስለይግባኝ ሰሚ ጉባዔ</u>**

1. የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሣ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባዔዎች በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች ይቋቋማሉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተቋቋመ ጉባዔ የቀረበለትን ይግባኝ መርምሮ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የተሰጠ ውሳኔን የማጽናት፣ የማሻሻል ወይም የመሻር እና የሰጠውን ውሳኔ የማስፈፀም ሥልጣን ይኖረዋል፡፡
3. የጉባዔው ተጠሪነት እንደ አግባቡ ለክልሉ ወይም ለከተማው አስተዳደር ምክር ቤት ይሆናል፡፡
4. ጉባዔው አግባብ ካላቸው አካላት የተውጣጡ ከ5 የማያንሱ አባላት ይኖሩታል፡፡
5. ጉባዔው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አግባብነት ያላቸውን አካላት በማዘዝ ሙያዊ አስተያየት መቀበል ወይም ማስረጃ እንዲቀርብለት ማድረግ ይችላል፡፡
6. ጉባዔው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የፖሊስ ኃይል በማዘዝ የሚሰጣቸውን ውሳኔዎችና ትእዛዞች ማስፈፀም ይችላል፡፡
7. ጉባዔው ከሕግ በቀር ከማናቸውም ተጽዕኖ ነፃ ይሆናል፡፡
8. ጉባዔው ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ በመደበኛው የፍትሐብሔር ስነ-ሥርዓት ሕግ አይመራም፡፡ ሆኖም በክልሉ ወይም በከተማ አስተዳደሩ በሚወስን የተቀላጠፈ ስነ ሥርዓት ይመራል፡፡
9. የጉባዔው አባላት የስራ ዘመን በክልሉ ወይም በከተማ አስተዳደሩ ይወሰናል፡፡

31. **<u>ስለመረከብ</u>**

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ያለው አካል ማስለቀቂያ ትእዛዝ የተሰጠበትን ቦታ የሚረከበው የከተማ ቦታ ባለ ይዞታው ካሣ ከተከፈለው ቀን ወይም ካሣውን ለመቀበል ፈቃደኛ ካልሆነ ደግሞ ካሣው አግባብ

ባለው አካል ስም በዝግ የባንክ ሂሣብ ከተቀመጠበት ቀን ጀምሮ በ90 ቀናት ውስጥ ይሆናል፡፡ ሆኖም የተወሰነለትን ካሣ ያልተቀበለው ሰው ለመቀበል በፈለገ ጊዜ አግባብ ያለው አካል በባንክ የተቀመጠውን ገንዘብ መስጠት አለበት፡፡

2. አግባብ ያለው አካል የማስለቀቂያ ትዕዛዝ ወይም ማስጠንቀቂያ የተሰጠበትን መሬት የሚረከበው፡-

   ሀ) ትዕዛዙ ወይም ማስጠንቀቂያው የደረሰው ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሠረት አቤቱታ ሳያቀርብ ሲቀር፤

   ለ) አቤቱታ ቀርቦ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት አቤቱታውን ውድቅ የሚያደርግ ውሳኔ ሲሰጥ እና በውሳኔው ላይ ይግባኝ ሳይቀርብ ሲቀር፤ ወይም

   ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ይግባኝ ቀርቦ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ይግባኙን ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሲሰጥ፤

   ይሆናል፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም በሚለቀቀው መሬት ላይ ሰብል፣ ቋሚ ተክል ወይም ሌላ ንብረት ከሌለ የከተማ ቦታ ባለይዞታው የማስለቀቅ ትዕዛዝ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ የከተማ ቦታ ይዞታውን አግባብ ላለው አካል ማስረከብ አለበት፡፡

4. አግባብ ያለው አካል ቦታውን በሚረከብበት ጊዜ ኃይል መጠቀም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የፖሊስ ሃይል ማዘዝ ይችላል፡፡

5. በሕገ ወጥ መንገድ የተያዘ የከተማ ቦታ እንዲለቀቅ በሚደረግበት ጊዜ በቦታው ላይ ላለ ንብረት አግባብ ያለው አካል ተጠያቂ አይሆንም።

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 32. የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር

ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ይህ አዋጅ በሁሉም ክልሎች በሚገባ መፈጸሙን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤
2. ለክልሎችና ለከተማ አስተዳደሮች የቴክኒክና የአቅም ግንባታ ድጋፍ ያደርጋል፤

3. በሀገር አቀፍ ደረጃ የመሬትና መሬት ነክ መረጃዎችን በቴክኖሎጂ የማዘመንና የማናበብ ሥራዎች ይሰራል፤
4. ሀገር አቀፍ የመሬትና መሬት ነክ መረጃዎችን በተመለከተ ስታንዳርዶች ያወጣል፣ ተፈፃሚነታቸውን ይከታተላል፤
5. የዚህን አዋጅ ማስፈጸሚያ ሞዴል ደንቦች፣ መመሪያዎችና ማንዋሎች ያዘጋጃል፡፡

33. **የክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች ሥልጣንና ተግባር**

ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች፡-

1. በሁሉም ከተሞች ውስጥ የሚገኘውን መሬት በዚህ አዋጅ መሠረት ያስተዳድራሉ፤
2. ይህን አዋጅ በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦች እና መመሪያዎች ያወጣሉ፡፡

34. **የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ይህንን አዋጅ በማስፈጸም ረገድ የመተግበር ግዴታ አለበት፡፡

35. **ቅጣት**

1. የወንጀል ህጉ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር፡-

   ሀ) ማንኛውም ይህን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን ለማስፈፀም የተመደበ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ፡-

   (1) በዚህ አዋጅ ከተደነገገው ውጪ የከተማ ቦታን የፈቀደ እንደሆነ ከ7 እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር 40,000 እስከ ብር 200,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

   (2) የጨረታ መረጃዎችን ይፋ ባያደርግ፣ በጨረታ ሰነድ ሽያጭ ላይ ገደብ ቢጥል፣ የጨረታ ሂደቱን ቢያዛባ ወይም የጨረታ ውጤቱን ቢለውጥ ከ5 እስከ 12 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር 30,000 እስከ ብር 150,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

   (3) በዚህ አዋጅ ከተደነገገው ውጪ ፈፅሞ ከተገኘ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት መውሰድ የሚገባውን እርምጃ ሳይወስድ ከቀረ ከ5 እስከ 12 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር 30,000 እስከ 150,000 ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

ለ) ማንኛውም ሰው ይህን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በመተላለፍ የከተማ ቦታን አጥሮ ከያዘ፣ ግንባታ ካካሄደበት ወይም ከአዋሳኝ ይዞታው ጋር ከቀላቀለ ከ7 እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር 40,000 እስከ ብር 200,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

ሐ) ማንኛውም በከተማ ቦታ ሊዝ ጨረታ የሚወዳደር ሰው የሐሰት ማስረጃ ካቀረበ፣ መግለጽ የነበረበትን መረጃ ከደበቀ ወይም ከሌላ ተወዳዳሪ ጋር በመመሳጠር የሐሰት ውድድር ካደረገ ከ5 እስከ 12 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር 30,000 እስከ ብር 150,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

2. ማንኛውም ይህን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን ለማስፈፀም የተመደበ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱትን ጥፋቶች በቸልተኝነት ከፈጸመ ከ1 እስከ 5 ዓመት በሚደርስ እሥራትና ከብር 10,000 እስከ ብር 30,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

3. ማንኛውም በዚህ አንቀጽ የተመለከተን የወንጀል ድርጊት በመፈጸም የተገኘ ሀብት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተወርሶ አግባብ ያለው አካል እንዲረከበው ይደረጋል፡፡

36. **<u>የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>**

1. የከተማ ቦታ በሊዝ ስለመያዝን እንደገና ለመደንገግ የወጣው አዋጅ ቁጥር 272/1994 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

37. **<u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>**

1. ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች ቀደም ሲል ቀርበው በእንጥልጥል ላይ ያሉ የከተማ ቦታ ጥያቄዎችን በሚመለከት ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ በቀድሞው ህግ መሠረት ውሳኔ መስጠት አለባቸው፡፡

2. ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት አግባብ ባለው አካል የተፈረሙ የሊዝ ውሎችና በነዚሁ መሠረት የተከናወኑ ሥራዎች ህጋዊነታቸው ተጠብቆ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል፡፡

38. **አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ኅዳር 18 ቀን 2004ዓ.ም**

**ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዘዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 818/2006 ዓ.ም

## የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40(7) የተደነገገውን ዜጎች በመሬት ላይ ለሚገነቡት ቋሚ ንብረት የተጎናጸፉት የባለቤትነት እና በመሬት የመጠቀም መብታቸውን በከተሞች ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የከተማ መሬት ይዞታ መመዝገብ ለአገሪቱ ኢኮኖሚ አስተማማኝ መረጃን በማመንጨት ለሚፈለገው አገልግሎት ለማዋል ተቋማዊ መሠረት በመሆኑ፤ በተለይም የዜጎች ይዞታ መብት ዋስትና እንዲያገኝና የከተሞችን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አካባቢያዊ ልማት ማፋጠን አስፈላጊ በመሆኑ፤

ከመሬት እና ከማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር ተያይዞ የሚነሳውን ክርክር ለመቀነስ፣ ባለይዞታው በሕግ አግባብ ያፈራውን ሀብት መጠቀም የሚያስችለው ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለበት አስተማማኝ የሆነ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት እና በመንግስት የሚሰጡ አገልግሎቶች የተሳለጡ እንዲሆኑ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ከመሬት ይዞታ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መብቶች፣ ክልከላዎች እና ኃላፊነቶችን ለመመዝገብ የሚያስችል ወቅታዊ፣ ፈጣን፣ ከገበያ ልውውጥ ጋር የተጣጣመ የሕግ ማዕቀፍ በማውጣት የመሬትና የማይንቀሳቀስ ንብረት ለነጻ ገበያ የኢኮኖሚ ሥርዓት ግንባታ ያለውን አስተዋጾ ለማሳደግ፣ እንዲሁም ማንኛውም የመሬት ባለይዞታ በመሬት ላይ ላፈራው የማይንቀሳቀስ ንብረት በመሬት ይዞታው ውስጥ ዋስትና ማረጋገጫ እንዲኖረው ማድረግ በማስፈለጉ፤

የህጋዊ ካዳስተር መሠረታዊ መርሆዎች የሆኑትን የይዞታ ምዝገባን፣ በይዞታ ልውውጥ ጊዜ የባለይዞታን ይሁንታ ማግኘት፣ የይዞታ ምዝገባን ለሕዝብ ግልጽ ማድረግ እና ይዞታውንና ባለይዞታውን በመለያ ኮዶች መለየትን ሥራ ላይ ማዋል በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 55(2) (ሀ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 818/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

   1. "ከተማ" ማለት ማዘጋጃ ቤት የተቋቋመበት ወይም በህግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ከተማ ተብሎ የተሰየመ ስፍራ ነው፤
   2. "የከተማ መሬት" ማለት በማንኛውም ክልል የከተማ የአስተዳደር ወሰን ውስጥ የሚገኝ መሬት ነው፤
   3. "የመሬት ይዞታ" ማለት የሊዝ ሥሪት በሚመራበት ህግ መሰረት በሊዝ የተያዘ ወይም በሊዝ ህግ መሠረት እውቅና የተሰጠው የከተማ ነባር የመሬት ይዞታ ላይ የተገኘ የተጠቃሚነት መብት ነው፤
   4. "ከተማ አስተዳደር" ማለት በህግ የተቋቋመ ወይም አግባብ ባለው አካል በተሰጠ ውክልና የከተማ አስተዳደር ሥልጣንና ተግባር የሚያከናውን አካል ነው፤
   5. "ህጋዊ ካዳስተር" ማለት ለእያንዳንዱ ህጋዊ ወሰን ለተለየለት ይዞታ፣ የይዞታ መብት፣ ክልከላ እና ኃላፊነት የሚያመለክት መረጃ የያዘ፣ የይዞታውን ካርታ አጣምሮ የያዘ ወቅታዊ የመሬት ይዞታ መረጃ ሥርዓት ነው፤

6. “በሥልታዊ ዘዴ ይዞታን ማረጋገጥ” ማለት በአንድ የይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር ውስጥ በሚገኙ ይዞታዎች ላይ የነበረን መብት በመደዳው የማረጋገጥ ዘዴ ነው፤
7. “በአልፎ አልፎ ዘዴ ይዞታን ማረጋገጥ” ማለት በአንድ የይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር ውስጥ ቀደም ብሎ የነበረን የይዞታ መብት ለማረጋገጥ በባለይዞታ ጥያቄ መሰረት የሚተገበር የይዞታ መብት ማረጋገጥ ዘዴ ነው፤
8. “የጣቢያ ሽንሻኖ” ማለት በአንድ ከተማ ዝቅተኛ የአስተዳደር እርከን ሥር የሚገኝ መሬት ሆኖ ለጣቢያ ሽንሻኖ በተዘጋጀ ደረጃ መሰረት መንገዶችን እና መስመራዊ ገጽታዎችን ተከትሎ የሚነደፍ በውስጡ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆነ ይዞታዎችን የያዘ የፕላን ጣቢያ ነው፡
9. “የቁራሽ መሬት ልዩ መለያ ኮድ” ማለት በአንድ ከተማ ውስጥ የሚገኝ ነጠላ ይዞታ በብቸኝነት የሚለይበት የመሬት ይዞታ መለያ ኮድ ወይም ቁጥር ነው፡
10. “ካዳስተር ማውጫ ካርታ” ማለት በአንድ ከተማ ለሚካሄድ የይዞታ ማረጋገጫ ምዝገባ የተዘጋጁ የጣቢያ ሽንሻኖዎች ወይም የይዞታ ማረጋገጫ ምዝገባ ሰፈር ካርታዎች ሆነው የካርታ ስም አሰጣጥ ደረጃ ያለው ተከታታይ ስያሜ እና ቁጥር ኖሯቸው የሚዘጋጁ ካርታዎች ናቸው፤
11. “ቁራሽ መሬት” ማለት ወሰኑ በምድር እና በካርታ ላይ በግልፅ ተለይቶ የመጠቀም መብት የተረጋገጠለት ልዩ የመለያ ኮድ ያለው ነጠላ የመሬት ይዞታ ነው፤
12. “የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ቀጠና” ማለት በከተማ ዝቅተኛ አስተዳደር እርከን ውስጥ ከአንድ ሺ ያልበለጡ ቁራሽ መሬት ያሉት ሆኖ ከአምስት ያልበለጡ የይዞታ ማረጋገጫ ሠፈሮችን በጥምረት የሚይዝ፣ የቀጠና ልዩ ኮድ ያገኘ የይዞታ ማረጋገጫ አካባቢ ነው፤
13. “የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር” ማለት ስልታዊ የይዞታ ማረጋገጥ ትግበራ የሚከናወንበት በግልፅ በመስክና በካርታ ላይ የሚታወቅ በመስመራዊ ካርታ ወሰን፣ ተከታታይ ቁጥር እና መለያ ስያሜ ያለው የይዞታ ማረጋገጫ አካባቢ ነው፤
14. “የይዞታ መብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት” ማለት በመዝጋቢው ተቋም የሚስጥ ከመሬት ተጠቃሚነት የሚመነጭ የይዞታ መብትን የሚያረጋግጥ ሰነድ ነው፤

15. “የካዳስተር ቅየሳ” ማለት ማንኛውም የመሬት ይዞታ ወሰን ልኬት በመስክ ላይ በመገኘት በምድር ቅየሳ መሣሪያ አማካኝነት ወይም በፎቶግራሜትሪ ዘዴ ማከናወን ነው፤
16. “ልዩ ፈቃድ የተሰጠው ቀያሽ” ማለት በከተማ አስተዳደር ውስጥ ስልጣን ባለው አካል የካዳስተር ቅየሳ እንዲያከናውን ኃላፊነት የተሰጠው ቀያሽ ነው፤
17. “የካዳስተር ቀያሽ” ማለት የካዳስተር ቅየሳ እንዲያከናውን በተዘጋጀው የሙያ ምዘና ደረጃ መሠረት ስልጣን ባለው አካል የተመዘገበና ፈቃድ የተሰጠው የቅየሳ ባለሙያ ነው፤
18. “ምዝገባ” ማለት የመሬት ይዞታ መብት፣ ክልከላ እና ኃላፊነት በህጋዊ ካዳስተር መዝገብ የሚመዘገብበት ሂደት ነው፡
19. “አግባብ ያለው አካል” ማለት የፌደራል የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ወይም በክልል ደረጃ የተቋቋመ ወይም የተሰየመ የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ መዝጋቢ ተቋማትን የሚቆጣጠር አካል ነው፡
20. “መዝጋቢ ተቋም” ማለት በክልሎች አመቺ በሆነ አደረጃጀት የተቋቋመ ወይም የተሰየመ አግባብ ላለው አካል ተጠሪ የሆነ የከተማ መሬት ይዞታና የማይንቀሳቀስ ንብረት መረጃ ምዝገባ የሚያሄድበት ተቋም ነው፤
21. “የይዞታ አረጋጋጭ ሹም” ማለት በስልታዊ የይዞታ ማረጋገጥ ሂደት በይዞታ ማረጋገጫ ቀጠና ውስጥ የይዞታ ባለመብትነት እንዲያረጋግጥ በመንግስት የተሾመ እና በዚሁ ቀጠና የይዞታ መረጃን በኃላፊነት የሚያደራጅ ሰው ነው፤
22. “መዝጋቢ ሹም” ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የመሬት ይዞታ መብትን፣ ክልከላንና ኃላፊነትን እንዲመዘግብ እና ማረጋገጫዎችን እንዲሰጥ በክልል ወይም በከተማ አስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው ሰው ነው፤
23. “መሠረታዊ ካዳስተር ካርታ” ማለት በምድር ቅየሳ ወይም ከአየር ፎቶ የተዘጋጀ ካርታ ሆኖ በውስጡ የአስተዳደር ወሰን፣ አጥር፣ መንገድ፣ የህንፃ ወይም የቤት የወሰን መስመር፣ ወንዝ፣ ሃይቅ፣ የመሬት ገፅታ፣ ቋሚ የቅየሳ ነጥቦች ስርጭት እና መሰል ነባራዊ ሁኔታዎችን የሚያሳይ መነሻ ካርታ ነው፤
24. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 47(1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባንና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

25.“ሚኒስቴር” ማለት የከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ነው፤[139]

26.“ሰው” ማለት የተፈጥሮ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

27.ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ያካትታል፡፡

3. **የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ አዋጅ የከተማ መሬትን በሚመለከት በአገሪቱ ውስጥ በሚገኙ ሁሉም ከተሞች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

4. **የመሬት ይዞታ ምዝገባ ዓላማዎች**

የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባ የግል፣ የጋራ፣ የማህበራት፣ የመንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት በመሬት የመጠቀም መብት ወጥ በሆነ ደረጃ የሚያስጠብቅ ሆኖ፤ ከተሞች ያላቸውን መሬት ቆጥረው ማወቅ እንዲችሉ በማድረግ በአገር አቀፍ ደረጃ ተናባቢ የሆነ የመሬት ይዞታ መረጃ እንዲኖር እና አሠራሩ ከገጠሩ የመሬት ይዞታ አስተዳደር ጋር ተጣጥሞ አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመገንባቱን ሂደት ማገዝ፡ እና
2. የከተማ መሬት ይዞታ መብትን በምዝገባ በማረጋገጥ የባለይዞታውን የመሬት ይዞታ ተጠቃሚነት ዋስትና እና የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት መብትን እውቅና በመስጠት የከተሞችን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና አካባቢያዊ ልማትን ማፋጠን፡፡

5. **የመሬት ይዞታ ለማረጋገጥ መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች**

በከተሞች የመሬት ይዞታ መብትን ለማረጋገጥ፡-

1. የከተማው አስተዳደራዊ ወሰን መስመራዊ ካርታ ተዘጋጅቶለት አስቀድሞ መጽደቅ፣ እና
2. የከተማውን አስተዳደራዊ ወሰን ያገናዘበ በህግ አስገዳጅነት ያለው የከተማ ፕላን ሥልጣን ባለው አካል መጽደቅ፤

አለበት፡፡

---

[139] በ25/08 (2011) አ.1097 አንቀፅ 9(10) መሰረት የከተማ ልማት እና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሆኗል፡፡

## ክፍል ሁለት
## ህጋዊ ካዳስተር

6. ***መሠረቱ***

1. በመሬት ላይ ያለውን እውነታ የሚያመላክት የመሠረታዊ ካዳስተር ካርታ፣ የይዞታ ጠቋሚ ካርታ እና የካዳስተር ማውጫ ካርታ ከአገራዊ የጂኦደቲክ ቅየሳ መረብ በመነሳት በወረቀት ወይም በወረቀት እና በድጅታል ፎርም ይዘጋጃል፡፡
2. የመሬት ይዞታ ተጠቃሚነት መብት የተሰጠው ሰው በእያንዳንዱ ቁራሽ መሬት ያለውን መብት፣ ክልከላ እና ኃላፊነቱን የሚገልፅ ሰነድ በወረቀት ወይም በወረቀት እና በድጅታል ፎርም ይዘጋጅለታል፡፡
3. እያንዳንዱ ቁራሽ መሬት ልዩ መለያ ኮድ የሚሰጠው ሲሆን ይህም ኮድ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ያሉትን እርስ በርሳቸው ማስተሳሰር አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)፣ (2) እና (3) የተዘረዘሩት መሟላታቸው ተረጋግጦ በዚህ አዋጅ መሰረት ምዝገባ ሲካሄድ ህጋዊ ካዳስተር ይመሰረታል፡፡
5. ህጋዊ ካዳስተሩ በመዝጋቢ ተቋም ውስጥ ተደራጅቶ የሚቀመጥ ሲሆን ለመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ዋና ማስረጃ ሆኖ ያገለግላል፡፡

7. **ስለ ካዳስተር ካርታ**

1. ክልሎች ለካዳስተር የሚሆን መሰረታዊ መነሻ ካርታ እንዲዘጋጅ ማድረግ አለባቸው፡፡
2. የካዳስተር ካርታው በመዝጋቢው ተቋም አማካኝነት ይዘጋጃል፡፡
3. የካዳስተር ካርታ አስተዳደር ወሰኖችን፣ ቁራሽ መሬቶችን፣ መንገዶችን፣ የቁራሽ መሬት ልዩ መለያ ኮድ እና ጣቢያ ሽንሻኖን መሠረት ያደረጉ የይዞታ አድራሻዎችን እና የቦታ ስፋት መያዝ አለበት፡፡
4. የካዳስተር ካርታ ከከተማው የአስተዳደር ወሰን በመነሳት የሚዘጋጅ ሆኖ በየተዋረዱ ያሉ አስተዳደራዊ ወሰኖችን፣ የካዳስተር ማውጫ ካርታዎችን፤ የቁራሽ መሬት ወሰን እና ኮኦርድኔቶችን ይይዛል፡፡
5. በአንድ የካዳስተር ጣቢያ ውስጥ የሚገኙ የተረጋገጡ ቁራሽ መሬቶችን የሚያሳይ የካዳስተር ካርታ አገራዊ ደረጃን ጠብቆ የከተማውን የአስተዳደር ወሰን በሚሸፍን አግባብ እና በተከታታይ የካርታ ቅጠል ስያሜ እና ቁጥር እንዲይዝ ተደርጎ ይዘጋጃል፡፡

6. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚዘጋጅ የካዳስተር ካርታ የቁራሽ መሬት ወሰን ህጋዊነት ተለይቶ ከተለካ በኋላ በወረቀት ወይም በወረቀት እና በድጅታል ፎርም መዘጋጀት አለበት፡፡

8. **የቁራሽ መሬት ልዩ የመለያ ኮድ**

1. ማንኛውም ቁራሽ መሬት በአገራዊ ደረጃ መሰረት በየትኛውም የከተማ ቁራሽ መሬት ላይ የማይደገም ልዩ መለያ ኮድ ይኖረዋል፡፡
2. በአገራዊ ደረጃ መሠረት ጥቅም ላይ ከዋለ ልዩ የቁራሽ መሬት መለያ ኮድ ወጪ ቁራሽ መሬትን ለመለየት ሌላ መለያ ኮድ መጠቀም አይቻልም፡፡

9. **የይዞታ ጠቋሚ ካርታ**

የይዞታ ጠቋሚ ካርታ የቁራሽ መሬቱን ልዩ መለያ ኮድ፣ ቁመት፣ ስፋት፣ ልኬት፣ አቀማመጥ እና የቦታውን ቅርፅ፣ የቦታውን አድራሻ፣ አጎራባች ቁራሽ መሬቶችን፣ አዋሳኝ መንገድ፣ የቁራሽ መሬት የማዕዘን ምልክቶች፣ ኮኦርድኔት፣ የሰሜን አቅጣጫ እና መስፈርት መያዝ አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ሥርዓት

10. **መሠረቱ**

1. የመሬት ይዞታን የማረጋገጥ ሥራ በስልታዊ የመሬት ይዞታ የማረጋገጥ ዘዴ ለመጀመሪያ ጊዜ መካሄድ አለበት፡፡
2. ስልታዊ የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ በአንድ የይዞታ ማረጋገጥ ቀጠና እየተካሄደ እያለ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሌላ የይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር ላይ አልፎ አልፎ የመሬት ይዞታ የማረጋገጥ ዘዴ ሊተገበር ይችላል፡፡
3. የመሬት ይዞታን በስልታዊ ዘዴ የማረጋገጥ ሥርዓት ሲካሄድ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር ተብሎ በሚወሰነው በከተማው የአስተዳደር ወሰን ክልል ውስጥ ነዋሪውን ህዝብ በማሳተፍ የሚካሄድ መሆን አለበት፡፡
4. ማንኛውም የመሬት ይዞታ ወሰን በመስክ በሚደረግ የካዳስተር ቅየሳ ይረጋገጣል፡፡

5. የከተማ የመሬት አስተዳደር ተቋም ለእያንዳንዱ የመሬት ይዞታ ቀደም ብሎ የሰጠውን መብት፣ የመዘገበውን ክልከላና ኃላፊነት የሚመለከቱ ማስረጃዎች አደራጅቶ ለመዝጋቢው ተቋም ማስረከብ አለበት፡፡
6. በከተማ የአስተዳደር ወሰን ክልል ውስጥ የሚካተቱ የገጠር መሬት ባለይዞታዎች ማስረጃን በተመለከተ፣ መሬቱን ቀደም ብሎ ሲያስተዳድር የነበረው የገጠር መሬት የአስተዳደር አካል ማስረጃዎቹን በግልጽና በዝርዝር ለሚመለከተው የከተማ መሬት አስተዳደር ማስረከብ አለበት፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) መሠረት መረጃውን የተረከበ የከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታውን አረጋግጦ መረጃውን ለመዝጋቢው ተቋም ማስተላለፍ አለበት፡፡
8. በማንኛውም የመሬት ይዞታ ላይ ያለ መብት፣ ክልከላና ኃላፊነት በሚረጋገጥበት ወቅት በመሬት ይዞታው ላይ የመጠቀም መብትን ለመፍቀድ፣ ለማስተላለፍ፣ ለመከልከል ወይም ኃላፊነት ለመጣል ሥልጣን ባለው አካል የተሰጠ የሰነድ ማስረጃ ስለመኖሩ መረጋገጥ አለበት፡፡
9. የመሬት ይዞታን በማረጋገጥ ሂደት የተገኘ ውጤት የተደራጀና ምዝገባ ለማካሄድ ብቁ የሚያደርግ መሆን አለበት፡፡
10. የይዞታ ማረጋገጫ የሚከናወነው የአካባቢ ልማት ፕላን እና ህገወጥ ይዞታን ሥርዓት የማስያዝ ሥራዎች ተሟልተው በተጠናቀቁበት የይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር ላይ ብቻ ይሆናል፡፡
11. የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር የሚወሰነው ቅደም ተከተሉን በጠበቀ ሁኔታ በክልሉ ወይም በከተማ አስተዳደሩ አማካኝነት በሚወጣ የህዝብ ማስታወቂያ ይሆናል፡፡

11. <u>የመሬት ይዞታን የማረጋገጥ ሥርዓት አተገባበር</u>

1. በስልታዊ ዘዴ የመሬት ይዞታ የማረጋገጥ ሥርዓት በመንግስት ወጪ የሚተገበረው ለመጀመሪያ ጊዜ የህጋዊ ካዳስተር ሥርዓት ለመገንባት ብቻ ይሆናል፡፡
2. በስልታዊ ዘዴ የመሬት ይዞታ የማረጋገጥ ሥርዓት በክልሉ ወይም በከተማው አስተዳደር በሚወጣ የህዝብ ማስታወቂያ ከተወሰነው የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር ውጪ አይተገበርም፡፡

3. አልፎ አልፎ የመሬት ይዞታ የማረጋገጥ ሥርዓት የሚተገበረው ይዞታው እንዲረጋገጥለት የሚፈልገው ሰው ማመልከቻ ሲያቀርብና በክልሉ የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ ሲፈጽም ይሆናል፡፡

12.<u>ስለ መሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር እና ካዳስተር ማውጫ ካርታ</u>

1. በስልታዊ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሥርዓት ትግበራ ወቅት ለሚወሰነው የከተማው የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር ካርታ በከተማው አስተዳደር ምዝገባ ተቋም አማካኝት በቅድሚያ መዘጋጀት አለበት፡፡
2. የከተሞች የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር ማውጫ ካርታ እንዲዘጋጅ ሲታዘዝ፤ በአገር አቀፍ ደረጃ በተቀመጠው የካርታ ዲዛይን እና የካዳስተር ማውጫ ካርታ ስታንዳርድ መሠረት ተከታታይነቱን ጠብቆ መዘጋጀት አለበት፡፡

13.<u>በመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ሂደት ወቅት ስለሚታገዱ ጉዳዮች</u>

1. በአንድ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር የመሬት ይዞታን የማረጋገጥ ሂደት መጠናቀቁ ይፋ እስከሚደረግ ድረስ በማንኛውም ደረጃ የሚገኝ የይዞታ ስም ዝውውር ሳይተገበር እንዲቆይ ይደረጋል፡፡
2. በመሬት ይዞታ ማረጋገረጫ ሠፈር ውስጥ የሚከናወን የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ሥራ ከመጠናቀቁ በፊት በዚሁ የመሬት ይዞታ ላይ የሚቀርብ የወሰን ክርክር ወይም አስቀድሞ ቀርቦ ያልተወሰነ የወሰን ክርክር በማንኛውም አካል ውሳኔ ሊያገኝ የሚችለው የመሬት ይዞታ ማረጋገጥን ከሚተገብረው መዝጋቢ ተቋም በወሰን የማረጋገጥ ክርክር ስለተነሳበት ይዞታ ማስረጃ ሲያገኝ ብቻ ነው፡፡
3. በአንድ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር የማረጋገጥ ሥራው በሕዝብ ማስታወቂያ ይፋ ከመደረጉ በፊት በህግ ሥልጣን ባለው አካል የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ መኖሩ ሲረጋገጥ እገዳ የተደረገበት የአንድ የመሬት ይዞታ ባለመብት የማረጋገጥ ሥራ ሂደት እንዲቆም ይደረጋል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከተው እግድ የተሰጠው የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ሥራው በህዝብ ማስታወቂያ ይፋ ከተደረገ በኋላ ከሆነ የመሬት ይዞታ የማረጋገጥ ሥራው እገዳው በተሰጠበት ይዞታ ላይ እንዲቆም አይደረግም፡፡
5. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (4) አፈጻጸም ሲባል የይዞታ አረጋጋጭ ሹሙ ከመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር ሥራውን አጠናቆ መውጣት ያለበትን ጊዜ ክልሉ ወይም የከተማው አስተዳደር ይወሰናል፡፡

14.<u>በመሬት ይዞታ የመጠቀም መብት ስለማረጋገጥ</u>

1. በአንድ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር ውስጥ በመሬት ይዞታ የመጠቀም መብት የሚረጋገጠው ባለመብት ነኝ ባዩ ባቀረበው ማስረጃ እና መብቱን በፈቀደለት ተቋም ማስረጃ መካከል ልዩነት አለመኖሩ ሲረጋገጥ ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተገለጹ ማስረጃዎች መካከል ልዩነት ከተገኘ የሁለቱን ወገን ማስረጃዎች በተመለከተ በመሬት የመጠቀም መብት ለሚፈቅድ ህጋዊ አካል ውሳኔ እንዲሰጥበት መላክ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ጉዳዩ የተላከለት መብት ፈቃጅ ተቋም ለመዝጋቢው ተቋም በአስራ አምስት የስራ ቀናት ውሳኔውን ማሳወቅ አለበት፡፡
4. ተቃራኒ ሁኔታ መኖሩ እስካልተረጋገጠ ድረስ ማንኛውም የመጠቀም መብት ያልተፈጠረበት ቁራሽ መሬት ሁሉ የመንግሥት እንደሆነ ተቆጥሮ መሬቱን እንዲያስተዳድር ወይም እንዲያለማ ሥልጣን በተሰጠው አካል ጠያቂነት ይዞታው በስሙ ይረጋገጣል፡፡
5. ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች በአንድ ይዞታ ላይ ላላቸው መብት እንደ ጋራ ባለመብት ተመዝግበው እንደሆነ የመሬት ይዞታ አረጋጋጭ ሹሙ ስላላቸው የመብት ድርሻ ተቃራኒ ማስረጃ እስካልቀረበለት ድረስ እነዚህ ሰዎች የጋራ የመሬት ይዞታ ባለመብቶች በማድረግ የእያንዳንዱ ድርሻ እኩል እንደሆነ ግምት በመውሰድ ያረጋግጣል፡፡
6. ማንኛውም ሰው በመብት ፈቃጅ ተቋም ከተፈቀደለት እና በይዞታ ካስከበረው የቁራሽ መሬት ስፋት በላይ በያዘው የመሬት ይዞታ ላይ መብት እንዳለው ተደርጎ የመሬት ይዞታው አይረጋገጥለትም፡፡
7. የመሬት ይዞታ ወሰን በመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ሂደት በሚረጋገጥበት ወቅት በወሰኑ ላይ ልኬት ተካሂዶ በአዋሳኝ ባለይዞታዎች ስምምነትን በማግኘት ወይም ስምምነት ባልተገኘበት ጊዜ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17(1) መሠረት በተቋቋመው የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ቅሬታ ሰሚ ጉባዔ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት የሚተገበር ይሆናል፡፡
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት በመብት ፈቃጁ ውሳኔ ያላገኙ የመሬት ይዞታ ጉዳዮች፣ በመሬት ይዞታ የክርክር መዝገብ ውስጥ ተመዝግበው እንዲቆዩ ይደረጋሉ፡፡

15.በመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ሂደት ስለሚኖር ግዴታ

1. በመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ሂደት ወቅት በመሬት ይዞታው የመጠቀም መብት አለኝ የሚል ሰው ሲጠየቅና የሚመለከተው ሆኖ ሲገኝ ራሱ ወይም በሕጋዊ ወኪሉ አማካኝነት መገኘት አለበት፤ ሆኖም ባለመብት ነኝ ባዩ አለመገኘቱ የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ሥራን አያስቀርም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የመሬት ይዞታ አረጋጋጭ ሹም በመንግስት የስራ ሰዓት በማንኛውም የይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር ውስጥ ባሉ ይዞታዎች ውስጥ በመግባት ሥራውን ማከናወን ይችላል፡፡

16.በህዝብ ተሳትፎ የመሬት ይዞታ መብት ስለማረጋገጥ

1. ማንኛውም የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ሥራ ከመጀመሩ በፊት መዝጋቢው ተቋም በተመረጠው የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር ለሚገኙ ባለይዞታዎች ጥሪ አድርጎ ስለ ሂደቱ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ማድረግ አለበት፡፡
2. መዝጋቢው ተቋም በመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ሥራ ላይ ከህዝብ የተወከሉ ታዛቢዎችን ማሳተፍ አለበት፡፡
3. በእያንዳንዱ ዝቅተኛ የአስተዳደር እርከን ከአስተዳደሩ እና ከህብረተሰቡ የሚወከሉ አባላት የሚገኙበት የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ቅሬታ ሰሚ ጉባዔ ይቋቋማል፡፡ የቅሬታ ሰሚ ጉባዔው አደረጃጀትና አሰራር ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡
4. ማንኛውም ሰው የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ሂደቱ ላይ ሲፈለግና የሚመለከተው ሆኖ ሲገኝ የመሳተፍ መብት አለው፤ በሂደቱ ላይ የቃል ምስክርነት፣ የፅሁፍ ማስረጃ ወይም ሌላ ማናቸውም ከይዞታ ማረጋገጥ ጋር የተያያዘ ሰነድና መረጃ እንዲያቀርብ በተጠየቀ ጊዜ ማቅረብ አለበት፡፡
5. በክልሎች ደረጃ ባለው በቀበሌ፣ በወረዳ፣ በከተማ ወይም በዞን ደረጃ ባለው መዋቅር የይዞታ ማረጋገጥ ሂደት እንዲሳካ የሚያስተባብርና የሚደግፍ አማካሪ ኮሚሽን እንደአስፈላጊነቱ መቋቋም ይችላል፡፡ የኮሚሽኑ ተግባርና ኃላፊነት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

17.ስለቅሬታ አቀራረብና አወሳሰን

1. በመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር ውስጥ በሚከናወኑ የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርብለትን ቅሬታ በመቀበል መርምሮ ውሳኔ የሚሰጥ የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ቅሬታ ሰሚ ጉባዔ ይኖራል፡፡
2. በመዝጋቢ ተቋሙ የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ውሳኔ ቅሬታ ያደረበት ማንኛውም ሰው የማረጋገጥ ሂደቱ መጠናቀቅ ከታወቀበት ቀን ጀምሮ ባሉት አስራ አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ወደ መሬት ይዞታ ማረጋገጥ ቅሬታ ሰሚ ጉባዔ አቤቱታውን ማቅረብ ይችላል፡፡ የቅሬታ ሰሚ ጉባዔው የሚሰጠውን ውሳኔ ተከትሎ የይዞታ አረጋጋጭ ሹሙ ይዞታዎችን ማረጋገጥ አለበት፡፡
3. በመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ቅሬታ ሰሚ ጉባዔ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ለከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡
4. በከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ለከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡
5. የከተማ ፍርድ ቤቶች ባልተቋቋሙባቸው ከተሞች መደበኛ ፍርድ ቤቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)እና (4) የተጠቀሱት ጉዳዮችን የመወሰን ሥልጣን ይኖራቸዋል፡፡ በዚህ መልክ የሚቀርቡ ጉዳዮችን በተፋጠነ ጊዜ መወሰን የሚችሉ ችሎቶችን መደበኛ ፍርድ ቤቶች ማደራጀት አለባቸው፡፡

18.<u>የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ መጠናቀቁን ስለመግለጽ</u>

1. በአንድ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር ውስጥ የማረጋገጥ ሥራው የሚጠናቀቀው ለመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ቅሬታ ሰሚ ጉባዔ ቅሬታ ያልቀረበ እንደሆነ የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜ ገደብ እንዳበቃ ወይም ቅሬታ ሰሚ ጉባዔ ለቀረቡት ቅሬታዎች በሙሉ ውሳኔውን እንዳሳወቀ መሆን አለበት፡፡
2. በአንድ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር ውስጥ የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ሥራ ሲጠናቀቅ በህዝብ ማስታወቂያ መገለጽ አለበት፡፡

19.<u>የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ መዝገብ</u>

1. የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ መዝገብ የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ሂደት በመስክ ተረጋግጦ የሚመዘገብበት መዝገብ ሆኖ እያንዳንዱ የመሬት ይዞታ ቅጽ በወረቀት ወይም በወረቀት እና በድጅታል ፎርም መዘጋጀት ይኖርበታል። የቅጹ ይዘት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል፤

2. የመሬት ይዞታ የማረጋገጥ ሂደት ከተጠናቀቀ በኋላ የመሬት ይዞታ አረጋጋጭ ሹም ከመብት ፈቃጅ ተቋም የተቀበላቸውን የባለመብትነት ሰነዶች፣ የተፈረመበት የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ መዝገብ፣ የመሬት ይዞታ ወሰን ማካለያ ካርታ፣ ከመብት ፈቃጅ ተቋም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14(3) መሠረት የተገኘ ምላሽና ውሳኔ እንዲሁም የእያንዳንዱን ቁራሽ መሬት ቅጽ በማያያዝ ለመዝጋቢ ተቋም ማስረከብ አለበት፡፡

20.<u>የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ሰነዶች ለለማስተላለፍ</u>

1. በየመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር የይዞታ ማረጋገጥ ሥራ እንደ ተጠናቀቀ ይዞታው የተረጋገጠባቸው ሰነዶች በሙሉ ተደራጅተው ለመብት ምዝገባ መተላለፍ አለባቸው፡፡
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13(3) መሰረት የእገዳ ትዕዛዝ የተላለፈበት የመሬት ይዞታ ሥልጣን ባለው አካል እገዳው መነሳቱ እስኪገለጽ ድረስ በክርክር መዝገብ ውስጥ እንዲሰፍር ተደርጎ ወደሚቀጥለው ሂደት መተላለፍ አለበት፡፡

21.<u>የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ውጤት</u>

1. በመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ሂደት ህጋዊ ወሰን ተለይቶ በታወቀ ቁራሽ መሬት ላይ ያሉ መብቶች፣ ክልከላዎች እና ኃላፊነቶች የተረጋገጡባቸው ሰነዶች በሙሉ ምዝገባ ለማከናወን እርግጠኛ ማስረጃ ሆነው ያገለግላሉ፡፡
2. በስልታዊ የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ዘዴ የመሬት ይዞታው የተረጋገጠለት ማንኛውም ሰው የመሬት ይዞታ መብቱን በዚህ አዋጅ መሠረት የማስመዝገብ ግዴታ አለበት፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የካዳስተር የምድር መረጃ</u>

22.<u>ስለቅየሳ መሳሪያዎችና ቅየሳ</u>

1. የካዳስተር ቀያሽ ወይም ልዩ ፈቃድ የተሰጠው ቀያሽ ፍተሻና ቁጥጥር ተደርጎ ትክክለኛ መሆናቸው በተረጋገጡ የቅየሳ መሣሪያዎች ብቻ የቅየሳ ሥራ ማከናወን አለበት፡፡ ዝርዝሩ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በመሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡
2. የመሬት ይዞታ ልኬት በመስክ የሚከናወነው የካዳስተር ቅየሳ እንዲሰራ ልዩ ፈቃድ በተሰጠው ቀያሽ ወይም በካዳስተር ቀያሽ አማካኝነት ብቻ ይሆናል፡፡

3. የይዞታ ልኬት ቅየሳ የሚካሄደው ከአገር አቀፍ ጂኦዲቲክ ኔትወርክ በመነሳት የማዕዘን ችካሎችን በመትከል ወይም በፎቶግራሜትሪ ካርታ አሰራር ወይም በሁለቱ ጥምረት የተገኘውን የሰሜናዊ አግድመት እና የምስራቃዊ አግድመት ልኬት ንባቦች መሠረት በማድረግ መሆን አለበት፡፡
4. በመስክ በተካሄደ ቅየሳ መሠረት የመሬት ይዞታ ቁራሽ ወሰን ስፋትን ማስተካከል የሚጠይቅ ሲሆን አፈፃፀሙ ክልሎች በሚያመጡት መመሪያ ይወሰናል፡፡

## 23.<u>ስለካዳስተር ቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች እና የወሰን ምልክቶች</u>

1. የካዳስተር ወሰን ልኬት ለማካሄድ ጥቅም ላይ የሚውሉ የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች አተካከላቸው እና ጥቅም ላይ የሚውሉበት አግባብ ለዚህ ዓላማ ተብሎ በወጣ ስታንዳርድ መሠረት መሆን አለበት፡፡
2. ቅየሳ ልኬት የተደረገለት ቁራሽ መሬት ህጋዊ የይዞታ ወሰን ምልክቶች ማዕዘን ላይ በሚደረግ ችካል ወይም ሌላ በግልጽ የሚታይ ምልክትን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡ በመሬት ላይ ያረፈው የወሰን ምልክት በካዳስተር ካርታ ላይ ከሚታየው ወሰን ጋር መስፈርቱ በሚፈቅደው መጠን ተመሳሳይ መሆን አለበት፡፡
3. የካዳስተር ቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ መሠረት ጥበቃ ማግኘት አለባቸው፡፡

## 24.<u>የቅየሳ ንድፍና የመስክ ማስታወሻ</u>

ማንኛውም በመስክ የሚካሄድ የካዳስተር ቅየሳ የቁራሽ መሬቱን ይዞታ የወሰን መስመር ርዝመት በልኬት በማሳየት በንድፍ መግለፅ አለበት፡፡ ንድፉ የካዳስተር ቅየሳ ልኬት በተካሄደበት ተመሳሳይ ቦታና ጊዜ ከተዘጋጀ የመስክ ማስታወሻ ጋር አብሮ መያያዝ ይኖርበታል።

## 25.<u>ስለካዳስተር ቀያሽ</u>

1. የካዳስተር ቀያሽ ወይም ልዩ ፈቃድ የተሰጠው ቀያሽ የከተማ መሬት ምዝገባ ተቋም በሰጠው የሥራ ትዕዛዝ መሠረት የቅየሳ ሥራ ዝርዝር መረጃዎች ለተቋሙ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡
2. ቀያሹ ትክክለኛነታቸው ተፈትሾ ባልተረጋገጡ የቅየሳ መሳሪያዎች በመጠቀም የቅየሳ መረጃ በመሰብሰቡ ምክንያት በመሬት ባለይዞታው ላይ ወይም መሬቱ እንዲቀየስ ባዘዘው ተቋም ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ኃላፊ ይሆናል፡፡

## 26.<u>የመሬት ይዞታ ጣቢያ ጥራዝ</u>

በአንድ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር ባለ የጣቢያ ሽንሻኖ ውስጥ የሚያርፍ የቁራሽ መሬት ይዞታ ካርታ ጥራዝ በመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ስታንዳርድ መሰረት በወረቀት ወይም በወረቀት እና በድጅታል ፎርም እየተዘጋጀ የሚደራጅ እና ለውጦችም ካሉ በየጊዜው ወቅታዊ የሚደረጉበት ይሆናል፡፡

**ክፍል አምስት**

**ስለምዝገባ ሥርዓትና ውጤቱ**

**ንዑስ ክፍል አንድ**

**ስለምዝገባ ሥርዓትና ምዝገባ**

27.**የመሬት ይዞታን ለማስመዝገብ ማመልከቻ ስለማቅረብ**

1. በመሬት ይዞታ ላይ ጥቅም አለኝ የሚል ማንኛውም ሰው ይዞታውን ለማስመዝገብ ለመዝጋቢው ተቋም ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. የምዝገባ ማመልከቻው የሚቀርበው መዝጋቢው ተቋም ለዚሁ አገልግሎት ያዘጋጃቸውን ቅጾች በመሙላት እና የምዝገባ አገልግሎት ክፍያ በመፈጸም ይሆናል፡፡
3. በመሬት ይዞታ ላይ ያለን መብት ለማስመዝገብ የሚቀርብ ማመልከቻ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው ደንብ የተመለከቱ በመሬቱ የመጠቀም መብትን፣ ክልከላንና ኃላፊነት በግልፅ የሚያሳይ ሆኖ ከደጋፊ ማስረጃዎች ጋር ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል፡፡
4. የይዞታ ማረጋገጥ የተከናወነለት የይዞታ ባለመብት ለመብት ምዝገባ የሚያበቃ ማስረጃ ባገኘ በ30 የሥራ ቀናት ውስጥ በከተማ መሬት ይዞታ መዝጋቢ ተቋም ዘንድ ቀርቦ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ሠርተፍኬት እንዲሰጠው ጥያቄ ማቅረብ አለበት፡፡ ይህ ጥያቄ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያልቀረበ እንደሆነ

በክልሎች የተወሰኑትን የአገልግሎትና የመቀጫ ክፍያ ሲፈጽም ሰርተፍኬት እንዲሰጠው ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፡፡

28. <u>የምዝገባ ማመልከቻን ስለመቀበል</u>

1. መዝጋቢው ተቋም የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባ ማመልከቻ በተዘጋጀው ቅጽ መሠረት ተሞልቶ ሲቀርብለት በማህደር ውስጥ ለሚገባው ለእያንዳንዱ ማመልከቻ ቅደም ተከተሉን የጠበቀ ተራ ቁጥር ይሰጣል፡፡ የዚህን ግልባጭ የተቋሙን ማህተም በማስፈር፣ ቀን፣ ወር፣ ዓመት ምህረት፣ ሰዓት እና ደቂቃ በመጻፍ አንዱ ቅጂ ለአመልካቹ መሰጠት አለበት፡፡ በዚህ መልክ የተመዘገበ ጊዜ የምዝገባው ቅደም ተከተል ለመለየት ቁልፍ መነሻ ይሆናል፡፡

2. ሁለቱ የሚቃረኑ መብቶችን፣ ክልከላዎችንና ኃላፊነቶችን በአንድ የመሬት ይዞታ ላይ ለማስመዝገብ በተመሳሳይ ጊዜ ለመዝጋቢው ተቋም የሚቀርቡ ማመልከቻዎች ቢኖሩ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት የተወሰነ የውሳኔ ማስረጃ አስደግፎ ያቀረበው ሰው የምዝገባ ቅድሚያ ይሰጠዋል፡፡

29. <u>የምዝገባ ማመልከቻዎችን ስለማጣራት</u>

1. መዝጋቢው ተቋም አመልካቹ ለማስመዝገብ ያቀረበው ጥያቄ በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈፀም የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የሚጠይቁት መስፈርቶች ማሟላታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተጠቀሰው መሠረት መዝጋቢው ተቋም የማስረጃዎችን መሟላት ሲያጣራ አመልካች ያቀረበውን ሰነድ ውድቅ የሚያድረግ ውሳኔ የሚሰጥ ቢሆን አመልካቹ በዚህ ጉዳይ ላይ ያለውን ቅሬታ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ በሚወሰነው የቅሬታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት መሠረት ሲያቀርብ ታይቶ የሚፈታ ይሆናል፡፡
3. ከምዝገባ ማመልከቻዎች ጋር አባሪ ሆኖ የቀረበ ማንኛውም ሰነድ በመዝጋቢው ተቋም የተመዘገበ መሆኑ ብቻ ስለሰነዱ ህጋዊነት ማረጋገጫ ሊሆን አይችልም፡፡

30. <u>የሚመዘገብ የመሬት ይዞታ መብት፣ ክልከላ እና ኃላፊነት</u>

1. በመሬት ይዞታ የመጠቀም መብት በሚፈጠርበት ወቅት አግባብ ካለው የመንግሥት አካል ጋር በነባር የመሬት ይዞታ እና በሊዝ ይዞታ ውል ውስጥ የተመለከቱ መብቶች፣ ክልከላዎችና ኃላፊነቶች ይመዘገባሉ፡፡

2. በዚህ አዋጅ፣ አዋጁን ተከትሎ በሚወጣ ደንብና መመሪያ በሚፈቀደው መሠረት በሙሉም ሆነ በከፊል በሽያጭ፣ በስጦታ፣ በውርስ፣ በድርሻ መልቀቅ፣ በዓይነት መዋጮ ወይም በሌላ ህጋዊ መንገድ የተገኘ መብት፣ ክልከላና ኃላፊነት ይመዘገባል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተዘረዘሩትን መብቶች፣ ክልከላዎች እና ኃላፊነቶች ለማስቀረት፣ ለመቀነስ፣ ለመጨመር፣ ለመለወጥ ወይም ለማሻሻል በህግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የሚሰጡ ውሳኔዎች ወይም ትዕዛዞች ወይም ውሎች ይመዘገባሉ፡፡
4. መንግስት በሚወስነው መሠረት የመሬት ይዞታ መብት፣ ክልከላ እና ኃላፊነት በሰብ-ሊዝ ለማስተላለፍ የተደረገ ውል ይመዘገባል።
5. ከመሬት ይዞታው ጋር የተያያዘ ማንኛውም የመያዣ ውል ወይም የዕዳ ዕገዳ በመዝጋቢው ተቋም ዘንድ መመዝገብ አለበት፡፡
6. በመሬት አስተዳደር አገልግሎት ሥርዓት መሠረት የተፈቀዱ መብቶች፣ ክልከላዎችና ኃላፊነቶች ይመዘገባሉ፡፡

## 31.<u>ስለመዝገቦች አዘገጃጀት እና አጠባበቅ</u>

1. የመሬት ባለይዞታነት መብትን ለመመዝገብ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ መዝገብ፣ የመሬት ይዞታ መብት መዝገብ፣ የጋራ ህንፃ የመሬት ይዞታ መዝገብ፣ የዋስትና እና ዕዳ እገዳ መዝገብ፣ ወደ ከተማ የተካለለ የአርሶ አደር መሬት ይዞታ መዝገብ እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ መዝገቦች መዘጋጀት አለባቸው፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተመለከቱት መዝገቦች በወረቀት ወይም በድጅታል ፎርም መዘጋጀት አለባቸው፡፡
3. መዝጋቢው ተቋም የህጋዊ ካዳስተር መረጃ መዝገብ በወረቀትም ሆነ በድጅታል ፎርም ተዘጋጅቶ ባለበት ሁኔታ ከመረጃ ደህንነት ሥጋት ለመጠበቅ የሚያስችል ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) በተጠቀሰው መሰረት የሚዘጋጁ መዝገቦች የባለመብቱን ማንነት በአገር አቀፍ ደረጃ በብቸኝነት ለመለየት በሚያስችል አገራዊ ደረጃ መሠረት መዘጋጀት አለባቸው፡፡

## 32.<u>ስለወረቀት እና ድጅታል ምዝገባ</u>

1. በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 31(2) መሰረት በወረቀት የተደረገ ምዝገባና በድጅታል የተደረገ ምዝገባ እኩል ተቀባይነት ይኖራቸዋል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት በሁለቱም ምዝገባዎች መካከል ልዩነት ሲኖር ወይም አጠራጣሪ ሲሆን በወረቀት የተደረገው ምዝገባ በድጅታል ምዝገባ ላይ ገዥ ይሆናል፡፡
3. የወረቀት መዝገቡ ገዢ የሚሆነው የተቋሙ ማህተምና ስልጣን የተሰጠው ሃላፊ ፊርማ በእያንዳንዱ የምዝገባ ቅፅ ላይ ሲያርፍበት ነው፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## ስለመሬት ይዞታ መብት ምዝገባ ሰርተፍኬት እና የመዝጋቢያው ተቋም ኃላፊነት

### 33.የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ስርተፍኬት ስለመስጠት

1. በመዝጋቢው ተቋም የመሬት ይዞታውን ላስመዘገበ የመሬት ይዞታ ባለመብት ለሆነ ሰው ምዝገባው የተከናወነበት ቀን እና ዓመት ምህረት ተጠቅሶ፣ በመዝጋቢ ሹሙ ተፈርሞ እና የመዝጋቢ ተቋሙ ማህተም ያረፈበት የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት መስጠት አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚሰጥ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ሚኒስቴሩ አዋጁን ተከትሎ በሚያወጣው መስፈርት መሠረት የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡
3. የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት የጠፋበት፣ የተበላሸበት ወይም በተለያየ ምክንያት ከጥቅም ውጭ የሆነበት ማንኛውም ሰው በክልሉ የተወሰነውን አግባብ ያለውን ክፍያ ሲፈጽም ምትክ ሰርተፍኬት ሊሰጠው ይችላል፡፡

### 34.ስለሰብ-ሊዝ

የመሬት ይዞታ ባለመብት መንግሥት በሚወስነው መሠረት ከይዞታው ከፊሉን ወይም ይዞታውን በሙሉ ከሊዝ ዘመኑ ከፍሎ ለተወሰነው ጊዜ ወይም ለአጠቃላዩ

የሊዝ ዘመን ለሦስተኛ ወገን በሰብ-ሊዝ ካስተላለፈ ይኸው መብት፣ ክልከላና ኃላፊነት ተመዝግቦ የማረጋገጫ ሰርተፍኬት በሰብ-ሊዝ ለተላለፈለት ባለመብት ይሰጠዋል፡፡

35.<u>ስለመያዣ እና ዕዳ እገዳ</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 30(5) መሠረት የተመዘገበ የመሬት ይዞታን በተመለከተ መዝጋቢው ተቋም ማመልከቻ ሲቀርብለት የመያዣ ውሉን ወይም የዕዳ እገዳውን የሚያሳይ ማረጋገረጫ ይሰጣል፡፡
2. በዚህ አንቁጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በአንድ የመሬት ይዞታ ላይ መብት ያገኘ ማንኛውም ሰው መብቱን ለማስመዝገብ ሲቀርብ መብቱን ያስተላለፈለት ሰው ይህንኑ መብት ያገኘበትን ሰነድ አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

36.<u>የህጋዊ ካዳስተር መረጃን ለህዝብ ክፍት ስለማድረግ</u>

መዝጋቢው ተቋም የህጋዊ ካዳስተር መረጃን ለህዝብ ክፍት ማድረግ አለበት፡፡

37.<u>ከህጋዊ ካዳስተር መረጃን ስለማግኘት</u>

1. መዝጋቢው ተቋም መዝገቦችን ለመመርመር ወይም ቅጂዎችን ለመውሰድ በህግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ጥያቄ ሲቀርብለት በሥሩ ያሉትን መዝገቦች ባሉበት እንዲመረመሩ መፍቀድ ወይም የተመዘገቡ ሰነዶችን ግልባጭ መስጠት አለበት፡፡
2. መዝጋቢው ተቋም የሚሰጣቸው ማናቸውም ቅጂዎች የምዝገባ ሹሙ ወይም ቅጂዎችን እንዲሰጥ የተፈቀደለት ሰው ፊርማ ከሌለው፣ የተቋሙ ማህተም ካልተደረገባቸው፣ የመዝገቡ ግልባጭ የተሰጠበት ቀን፣ ዓመተ ምህረት እና ማጣቀሻ ቁጥር ካልተጻፈባቸው ዋጋ አይኖራውም፡፡
3. የህጋዊ ካዳስተር መዝገብ ከመዝጋቢው ተቋም ውጪ በማንኛውም አካል ጥያቄ መንቀሳቀስ የለበትም፡፡

38.<u>የመሬት ይዞታ መረጃን ወቅታዊ ስለማድረግ</u>

መዝጋቢው ተቋም የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች በህጋዊ ካዳስተሩ መዝገብ ላይ መመዝገብና የመሬት ይዞታ መረጃውን በየጊዜው ወቅታዊ ማድረግ አለበት፡፡

39.<u>ምዝገባውን ለባለይዞታው ስለማሳወቅ</u>

1. በአንድ የመሬት ይዞታ ላይ መብት ያገኘ ሰው መብቱን ያስመዘገበ እንደሆነ መብቱን ለማስመዝገብ ያቀረባቸው ሰነዶች ተቀባይነት ማግኘታቸውን

የሚያረጋግጥ ትክክለኛ ቅጂ ለባለይዞታው በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ይዞታው በተመዘገበበት አድራሻ አስመዝጋቢው ማሳወቅ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የማሳወቅ ግዴታ ያለበት ማንኛውም ሰው ግዴታውን ባለመወጣቱ ምክንያት በባለይዞታው ወይም በሶስተኛ ወገኖች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ኃላፊ ይሆናል፡፡

40.<u>የመዝጋቢው ተቋም ተጠያቂነት</u>

1. መዝጋቢው ተቋም በሰጠው የመሬት ይዞታ መብት፣ ክልከላና ኃላፊነት ምዝገባ ማረጋገጫ ማስረጃ ላይ በመደገፍ ሦስተኛ ወገኖች በቅን ልቦና በሚፈጽሙት ተግባር ምክንያት ለሚደርስባቸው ጉዳት መዝጋቢው ተቋም ተጠያቂነት አለበት፡፡
2. መዝጋቢው ተቋም ተጠያቂ ለሆነበት ጉዳይ በህገ ወጥ መንገድ ተጠቃሚ የሆነውን ማንኛውንም ሰው ወይም ጥፋት የፈጸሙ የራሱን ኦፊሰሮችና ሠራተኞች መልሶ የመጠየቅ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

41.<u>የዋስትና ፈንድ ስለማቋቋም</u>

1. ክልሎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 40(1) የተመለከተውን ኃላፊነት ለመወጣት የዋስትና ፈንድ ማቋቋም ይችላሉ፡፡
2. በክልል ደረጃ በሚወስነው መሠረት ለዋሰትና ፈንዱ ማቋቋሚያ እንዲሆን የመሬት ይዞታ ዝውውር ከተካሄደበት ግብይት የግብይቱን ዋጋ ከአንድ መቶኛ ያልበለጠ ተጨማሪ ክፍያ መዝጋቢው ተቋም ሊሰበስብ ይችላል፡፡
3. በክልል በሚወሰን መጠን ከዋስትና ፈንዱ ከፊሉ ለሕዝብ ልማት አገልግሎት ሊውል ይችላል፡፡
4. የዋስትና ፈንድ ማሰባሰብ አጀማመሩ፣ የአሰባሰብ ዘዴው ወይም የዋስትና ፈንድ ማሰባሰብ ሊቋረጥ የሚችልበት ሁኔታ በክልል ይወሰናል፡፡

## <u>ንዑስ ክፍል ሦስት</u>

## <u>የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባ ውጤት</u>

42.<u>ስለመሬት ተጠቃሚነት መብት እና የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ</u>

ተቃራኒ ሁኔታ መኖሩ እስካልተረጋገጠ ድረስ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 33 (1) መሰረት የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት የተሰጠው ማንኛውም ሰው በመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ላይ ለተጠቀሰው መሬት ባለይዞታ

እና በመሬት ይዞታው ላይ ላረፈው የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት እንደሆነ ይቆጠራል፡፡

43.**ቀድሞ ስለተመዘገበ መብት**

1. ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች በአንድ ባለይዞታ ሊመዘገብ የሚገባን መብት አግኝተው እንደሆነ በመሬት ይዞታ መብት መዝገብ ውስጥ በመጀመሪያ መብቱን ያስመዘገበው ሰው ቅድሚያ ይሰጠዋል፡፡
2. የሁለተኛው ሰው መብት በመጀመሪያ የተመዘገበውን ሰው መብት የሚቃረን ሆኖ እስከተገኘ ድረስ እንዲመዘገብ አይደረግም፡፡
3. ሆኖም ሁለተኛው ሰው የመሬት ይዞታ መብቱን ባስተላለፈለት ባለይዞታ ሰው ላይ ያሉት መብቶች የተጠበቁ ናቸው፡፡
4. የመሬት ይዞታ መብቶች፣ ክልከላዎች እና ኃላፊነቶች የተመዘገቡበት ጊዜ አንድ የሆነ እንደሆነ ወይም አንዱ ከአንደኛው በፊት ስለመመዝገቡ ማስረጃ የታጣ እንደሆነ በመዝገቡ ውስጥ የቅድሚያ መመዝገቢያ ቁጥር የተሰጠው ቅድሚያ ይኖረዋል፡፡

44.**በፍርድ ቤቶች የሚሰጥ ውሳኔ**

በመሬት ይዞታ ላይ የሚገኝ መብትን በተመለከተ መብቱን የሚያረጋግጡ፣ የሚያስተላልፉ፣ የሚለውጡ፣ የሚያስቀሩ ወይም የሚያግዱ ፍርዶች፣ ውሳኔዎች ወይም ትዕዛዞች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 40 መሠረት በመዝጋቢው ተቋም ላይ ተጠያቂነት ሊያስከትሉ የሚችሉት ፍርዱ፣ ውሳኔው ወይም ትዕዛዙ ንብረቱ በሚገኝበት ስፍራ በሚገኝ የመሬት ይዞታ መዝገብ ውስጥ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

45.**ምዝገባን ስለማስተካከል እና ስለመሰረዝ**

1. በዚህ አዋጅ መሰረት የተመዘገበ ማንኛውም ምዝገባ እንዲስተካከል በአስመዝጋቢው ሰው ሲጠየቅ፣ በፍርድ ቤት ወይም ሥልጣን ባለው አካል ሲወሰን ወይም መስተካከል በሚገባው ጉዳይ ላይ የሚያገባቸው ሰዎች ተስማምተው ጥያቄ ሲያቀርቡ እንዲስተካከል ሊደረግ ይችላል፡፡

2. በዚህ አዋጅ መሰረት የተመዘገበ ምዝገባ እንዲሰረዝ በፍርድ ቤት ወይም ሥልጣን ባለው አካል የተወሰነ እንደሆነ የመሬት ይዞታ መብት ክልከላና ኃላፊነት ከመዝገቡ ይሰረዛል፡፡
3. የተመዘገበ መብት፣ ክልከላና ኃላፊነት መዝጋቢው አካል በራሱ ውሳኔ ሊሠርዝ የሚችለው የተመዘገበው መብት፣ ክልከላና ኃላፊነት የተደረገው ለተወሰነ ጊዜ ሲሆንና ይህ የተወሰነ ጊዜ ያለፈ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡
4. መዝጋቢው አካል በራሱ ውሳኔ ምዝገባ እንዲስተካከል ወይም እንዲታረም ለማድረግ የሚችልባቸው ምክንያቶች እና ዝርዝር ሁኔታ በደንብ ይወሰናል፡፡
5. በመሬት ይዞታ የተመዘገበ መብት፣ ክልከላ እና ኃላፊነት ውስጥ የተደረገ ማንኛውም ማስተካከያና ስረዛ ይኸው ተግባር ከተፈፀመበት ጊዜ ጀምሮ ውጤት ይኖረዋል፡፡

46.<u>የተመዘገበውን መብት ስላለማወቅ</u>

1. ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 31(1) በተጠቀሱት መዛግብት ውስጥ ተመዝግቦ ለሕዝብ ክፍት የተደረገ መብት፣ ክልክላ እና ኃላፊነት መኖሩን አላውቅም ነበር ብሎ የሚያቀርበው መከራከሪያ ተቀባይነት የለውም፡፡
2. ይህ የተባለው አለማወቅ የደረሰው በተቋሙ ሰራተኛ ወይም በመዝገብ ሹም ወይም በተቋሙ ሃላፊ ከሆነ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) በተጠቀሰው ተከራካሪ ወይም ባለመብት ላይ ለደረሰው ጉዳት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

47.<u>ያለመመዝገብ የሚያስከትለው ውጤት</u>

በመሬት የመጠቀም ይዞታ መብት ወይም ይዞታ ላይ የሚገኝ የማይንቀሳቀስ ንብረት የባለቤትነት መብት በመሬት ይዞታ መዝገብ ውስጥ እስካልተመዘገበ ድረስ በማናቸውም ሰው ላይ መቃወሚያ መሆን አይችልም፡፡

<u>ክፍል ስድስት</u>

<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

48.<u>ቅጣት</u>

1. ይህን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን ለማስፈፀም የተመደበ ማንኛውም ኃላፊ፣ የመሬት ይዞታ መብት መዝጋቢ፣

የመሬት ይዞታ መብት አረጋጋጭ፣ የካዳስተር ቀያሽ፣ ልዩ ፈቃድ የተሰጠው ቀያሽ ወይም ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈፀም ከወጣው ደንብና መመሪያ ውጪ፡-

ሀ/ የመሬት ይዞታዎችን የማረጋገጥ ሥራ የሠራ እንደሆነ ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራትና ከብር 40,000 እስከ ብር 200,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፤

ለ) የመሬት ይዞታን የመዘገበ እንደሆነ ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራትና ከብር 40,000 እስከ ብር 200,000 ሊደርስ በሚችልመቀጮ ይቀጣል፡፡

2. በመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር ለሚሰሩ ሥልታዊ ዘዴ የይዞታ ማረጋገጥ ሥራዎች ትብብር እንዲያደርግ መጥሪያ ተሰጥቶት ያለበቂ ምክንያት ፈቃደኛ ያልሆነ፣ እንዲያቀርብ የተጠየቀውን ሰነድ ሳያቀርብ ከቀረ ወይም ወደ ይዞታ ለማስገባት ፈቃደኛ ያልሆነ ማንኛውም ሰው በቀላል እሥራት ወይም ከብር 1,000 እስከ ብር 3,000 በሚደርስ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

3. ህጋዊነት የሌለው ወይም የሀሰት ማስረጃ በመጠቀም ሆነ ብሎ መዝጋቢ ተቋሙን በማሳሳት ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ያስገኘ ወይም የሌሎች ሰዎችን የመሬት ይዞታ መብት፣ ክልከላና ኃላፊነት ላይ ጉዳት ያደረሰ ማንኛውም ሰው ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚያደርስ ጽኑ እስራትና ከብር 40,000 እስከ ብር 200,000 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

4. በዚህ አዋጅ መሠረት በሚደራጁ መዝገቦች ደህንነት ላይ ሥጋት ሊያስከትሉ የሚችሉ ሁኔታዎችን በመፍጠር የህጋዊ ካዳስተር መረጃ መዝገብ እንዲጠፋ ወይም እንዲጎዳ ያደረገ ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) ወንጀሉ ሆነ ተብሎ የተፈጸመ ሲሆን ከሰባት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራትና ከብር 100,000 እስከ ብር 1 ሚሊዮን በሚደርስ መቀጮ፤

ለ) ወንጀሉ በቸልተኝነት የተፈጸመ ሲሆን ከሶስት ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚያደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር 20,000 እስከ 150,000 ብር በሚደርስ መቀጮ፤

ይቀጣል፡፡

49.<u>የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

በሌሎች ህጎች የተመለከቱ ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆኖ ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ይህን አዋጅ እና አዋጁን ተከትለው የወጡ ደንቦች፣ መመሪያዎች እና ደረጃዎች በሁሉም ክልሎች በሚገባ መፈጸማቸውን ይከታተላል፤ ጉድለቶች ካሉ ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግ ያደርጋል፤
2. ለክልሎች የቴክኒክ ድጋፍ እና በህግ ማዕቀፎች ላይ የእውቀት እና የክህሎት አቅም እንዲፈጠር የሥልጠና ድጋፍ ይሰጣል፤
3. የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባንና ተዛማጅ መረጃን በተመለከተ አገር አቀፍ የመረጃ ማዕከል በመሆን ያገለግላል፡፡

50.<u>የክልል ሥልጣንና ተግባር</u>

በሌሎች ህጎች የተመለከቱ ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆኖ እያንዳንዱ ክልል የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ይህን አዋጅና አዋጁን ተከትለው የሚወጡ ደንቦችን፣ መመሪያዎችን እና ደረጃዎችን በሚገባ ለማስፈፀም በክልል ደረጃ አግባብ ያለው አካል እንዲሁም በከተሞች ደረጃ የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ተቋም እንዲቋቋም ወይም እንዲሰየም ያደርጋል፤
2. በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡት ደንብና መመሪያዎች በአግባቡ መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፤
3. በዚህ አዋጅና አዋጁን ተከትለው በወጡ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ደረጃዎች መሠረት አጠቃላይ ሥራውን ይመራል፤ ያስተባብራል፤
4. በዚህ አዋጅ መሠረት የመሬት ይዞታ ምዝገባ የሚጀመርባቸውን ከተሞች ደረጃ በደረጃ ይወስናል፤
5. ለምዝገባ እና ለሚሰጧቸው ሌሎች አገልግሎቶች መከፈል የሚገባውን ተገቢ የአገልግሎት ክፍያ መጠን ይወስናል፡፡

51.<u>የከተማ አስተዳደሮች ሥልጣንና ተግባር</u>

በሌሎች ህጎች የተመለከቱ ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆኖ የከተማ አስተዳደሮች የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል፡-

1. የህጋዊ ካዳስተር ምዝገባ መረጃ ብቸኛ አመንጪ ማዕከል በመሆን ያገለግላሉ፤
2. የምዝገባ መረጃዎችን አግባብ ላለው የክልል አካል እና ለፌደራል የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ያስተላልፋሉ፤
3. የህጋዊ ካዳስተር መረጃን በባለቤትነት ይይዛሉ፣ መረጃውን ያደራጃሉ፤ ያስተዳድራሉ፡፡

52.<u>ስለአገልግሎት ክፍያ</u>

1. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 11(1) እና አንቀጽ 55(5) እንደተጠበቁ ሆኖ አልፎ አልፎ የይዞታ ማረጋገጫ የአገልግሎት ክፍያ መጠን የሚወሰነው በወጪ መጋራት መርህ መሠረት ይሆናል፡፡
2. የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባን አስመልክቶ የሚፈጸም ክፍያ ተመን በፌዴራል መንግስት ከጸደቀው ቀመር ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት፡፡

53.<u>የመተባበር ግዴታ</u>

1. ማንኛውም ሰው ይህንን አዋጅ እና በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንብና መመሪያ በማስፈጸም ረገድ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡
2. ፍርድ ቤቶች፣ የፋይናንስ ተቋማት፣ ውል ለማዋዋል ሥልጣን የተሰጣቸው ተቋማት እና ገቢ ሰብሳቢ አካላት የሚያመነጩቸውን ከመሬት ይዞታ ጋር በተዛመደ መመዝገብ የሚገባቸውን መብቶችን፣ ክልከላዎችንና ኃላፊነቶችን የሚመለከቱ ማስረጃዎች በቀጥታ ለመዝጋቢው ተቋም መስጠት ወይም መዝጋቢው ተቋም ቀርቦ እንዲወስድ ማድረግ አለባቸው፡፡

54.<u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

55.<u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

በዚህ አዋጅ መሰረት ስልጣን የተሰጣቸው መዝጋቢ ተቋማት የመሬት ይዞታ ምዝገባን ለማከናወን በከተሞች ተቋቁመው መሉ በሙሉ ሥራቸውን እስኪጀምሩ ድረስ ነባሩ የከተማ መሬት ይዞታ አመዘጋገብ ሥርዓት የሚቀጥል ይሆናል፡፡

56.**<u>ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች</u>**

ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ህግ ወይም የአሰራር ልማድ በዚህ አዋጅ በተደነገጉ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

57.**<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት 14 ቀን 2006 ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**<u>ደንብ ቁጥር 323/2006</u>**

**<u>የከተማ ካዳስተር ቅየሳ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 818/2006 አንቀጽ 54(1) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

**<u>ክፍል አንድ</u>**

**<u>ጠቅላላ</u>**

1. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ ደንብ "የከተማ ካዳስተር ቅየሳ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 323/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **<u>ትርጓሜ</u>**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

1. "አዋጅ" ማለት የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 818/2006 ነው፤
2. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተሰጡ ትርጓሜዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፤

3. “ጂኦዴቲክ ኔትወርክ” ማለት የሶስት ማዕዘን የጂኦዴቲክ መቆጣጠሪያ ነጥብ ጥምረት ሲሆን የሚለካውም በምድራዊ ቅየሳ ነው፤
4. “የከተማ ጣቢያ” ማለት በአንድ ከተማ ዝቅተኛ እርከን ሥር የሚገኝ መሬት ሆኖ፣ ለከተማ ጣቢያ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት በዙሪያ ገጠም መንገዶችን እና መስመራዊ ገፅታዎችን ተከትሎ የሚከለል በውስጡ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ይዞታዎችን የያዘ ሥፍራ ነው፤
5. “ዳተም” ማለት ለቅየሣ ልኬቶች ሁሉ መነሻ ሆኖ እንዲያገለግል በብሔራዊ ደረጃ ተቀባይነት ያገኘ መነሻ ነጥብ ነው፤
6. “የካዳስተር ሹም” ማለት በከተማ ውስጥ ባለ የመሬት ይዞታ ምዝገባ ተቋም ውስጥ ወይም ተቋሙ በሚመዘግብበት የምዝገባ ከተማ ውስጥ የካዳስተር ቅየሳ ተግባርን እንዲመራ በክልል መንግሥት ወይም በከተማ አስተዳደር የተሾመ ሰው ነው፤
7. “የኢትዮጵያ ከፍታ ዳተም የልኬት መጠን” ማለት ከኢትዮጵያ ከፍታ ዳተም በላይና በታች ካለ ከቅየሳ ነጥብ አንፃር እኩል ወይም የተሻለ የልኬት መጠን የተደነገገለት ስታንዳርድ ነው፤
8. “ትክክለኛነት” ማለት በአንድ ቅየሳ ሥራ ላይ የቅየሳ ስታንዳርዱን ጠብቆ የተከናወነ ቅየሳ ነው፤
9. “የወሰን ምልክት” ማለት በይዞታ ወሰን ምልክት አሰራር ስታንዳርድ መሠረት የተቀመጠውን በመሬት ላይ የሚታይ የችካል፣ የአጥር ማዕዘን፣ የተተከለ ሚስማር ወይም የማይጠፋ ቀለም የተቀባ ድንጋይ ምልክት ነው፤
10. “ግሎባል ናቪጌሽናል ሳታላይት ሲስተም” ማለት ዓለም አቀፍ የናቪጌሽን ሳተላይት ሥርዓት ነው፤
11. “የቅየሳ ነጥብ ትክል ድንጋይ ወይም ሞኑመንት” ማለት የተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ ቁስ ወይም በተፈጥሯዊ ወይም ሰው ሰራሽ ቁስ ላይ የተመላከተ የቅየሳ ፕላን ምልክት ሲሆን ሥልጣን በተሰጠው ተቋም በቅየሳ ዘዴ የይዞታ ወሰንን ወይም ነጥብን ለመጀመሪያ ጊዜ ለመትከል ወይም በድጋሚ ለመትከል የተቀመጠ ድንጋይ ነው፤

12.“ብሔራዊ የጂኦዴቲክ መነሻ ነጥብ” ማለት በአገር አቀፍ ደረጃ ስልጣን በተሰጠው አካል የተመሠረተ የብሔራዊ የጂኦዴቲክ የምድር መቆጣጠሪያ ነጥቦች መረብ አካል የሆነና ለቀጣይ የቅየሣ ሥራ መነሻ ሆኖ የሚያገለግል ነው፤

13.“የተመሰረተ የቅየሳ ምልክት” ማለት የቅየሳ ምልክት ሆኖ በቅየሳ መዝገብ ላይ በስታንዳርድ ላይ በተቀመጠው አግባብ የአግድሞሽ የቅየሳ ልኬት ሆኖ የተመዘገበ ነው፤

14.“መንገድ” ማለት ማንኛውንም መንገድ፣ ጎዳና፣ መተላለፊያ ወይም መገናኛ ሆኖ አሁን በጥቅም ላይ የዋለ ወይም ሊሰራ የታቀደ ነው፤

15.“የቅየሳ ሰርተፊኬት” ማለት የቅየሳ ሥራ ትክክለኛነት በስታንዳርዱ መሠረት ለመሰራቱ የሚያመላክት ሰርተፊኬት ነው፤

16.“የከተማ መሬት ቅየሳ” ማለት የመሬት ቅየሳ ሆኖ፡-

ሀ) በከተማ መሬት አጠቃቀም ፕላን ክልል ውስጥ ያለ የመኖሪያ አካባቢ፣ የገጠር መኖሪያ አካባቢ፣ የንግድ ሥፍራ፣ የኢንዱስትሪ ሥፍራ፣ የአስተዳደርና የማህበራዊ ቦታዎች፣ የህዝብ መገልገያ ሥፍራ፤ ወይም

ለ) ማንኛውም የመኖሪያ ቤት ግንባታ፣ የገጠር መኖሪያ ግንባታ፣ የንግድ ወይም የኢንዱስትሪ መሰረተ ልማት ለማካሄድ የተፈቀደ መሬት ወይም ህጋዊ የልማት ፈቃድ በህጉ መሠረት ያላገኘ ሥፍራ፤ የሚከናወን ቅየሳ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## የካዳስተር ቅየሳና መረጃ

### 3. የካዳስተር ቅየሳ ሥርዓት ትግበራ መርሆዎች

1. ቅየሳ የሚካሄደው በሚከተሉት መርሆዎች ላይ በመመሥት ይሆናል፡-

ሀ) የቅየሳ መሳሪያ ጥራት ደረጃውን የጠበቀ እና ከዘመኑ ቴክኖሎጂ ጋር የሚጣጣም መሆኑ የተረጋገጠ መሆን አለበት፤

ለ) ዳተምን መነሻ ያደረገ እና አግባብነት ያለው ሆኖ ሲገኝ ደረጃቸውን ከጠበቁ የቅየሳ ነጥቦች መነሻ ወይም በመሬት የተቀመጡ የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች ትስስር ያደረገ መሆን አለበት፤

ሐ) የቅየሳ መነሻ ትክል ድንጋዮችን ወይም ሞኑመንት በአንጻራዊነት ቀድሞ ከነበራቸው ይዞታ አለመናጋቱን ማረጋገጥ አለበት፤

መ) ለመስክ ቅየሳ ሥራ የሚያገለግሉ ደረጃቸውን የጠበቁ ቅጾች መዘጋጀት አለባቸው፤

ሠ) የካዳስተር ቀያሹ የመሬት ቅየሳውን የወሰን ምልክት በመሬት ላይ አንድ ጊዜ ወይም በድጋሚ ማመላከት አለበት፤

ረ) ቅየሳውን አስመልክቶ አግባብ ያለው የቅየሳ ምልክት በመሬት ላይ መኖር አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ስር በተዘረዘሩት መርሆዎች መሠረት ለተካሄደበት የቅየሳ ሥራ የተሟላ የመስክ ማስታወሻና ቅየሳው የተካሄደበትን ምክንያት በሚጠይቀው አግባብ የቅየሳ ንድፍ መዘጋጀት አለበት፡፡

4. <u>የካዳስተር ቅየሳ ሥራ ቅድመ ሁኔታዎች</u>

የካዳስተር ቅየሳ ሥራ ከመጀመሩ በፊት የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፡-

1. ለካዳስተር ሥራ የሚሆን መነሻ የከተማ ካዳስተር መሰረታዊ ካርታ ሃገራዊ ስታንዳርድ ጠብቆ መዘጋጀቱ እና ለካዳስተር ቅየሳ ጥቅም ላይ የሚውል መሆኑ መረጋገጥ፤
2. ምዝገባ ተቋሙ ወደ ሥልታዊ የይዞታ ማረጋገጫ ሂደት ከመግባቱ በፊት የካዳስተር መሰረታዊ ካርታው ከመሬት ይዞታ ማህደሮች ጋር ተሳስሮ ለካዳስተር ቅየሳ ምቹ ሁኔታ ስለመፈጠሩ ማረጋገጥ፤
3. የካዳስተር ቀያሽ ወይም ልዩ ፈቃድ የተሰጠው ቀያሽ የካዳስተር ቅየሳን በምድር ቅየሳ መሳሪያዎች የሚያከናውን ከሆነ የቅየሳ መሳሪያዎች ትክክለኛነት በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል መረጋገጥ፤
4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) እና (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የካዳስተር ቅየሳ መረጃ መነሻው ከብሔራዊ የጂኦዴቲክ ኔትወርክ ጋር የተሳሰረና የተናበበ መሆኑ መረጋገጥ፡፡

5. <u>ቀያሹ የሥራ ትዕዛዝን ስለማሟላት</u>

1. ቀያሹ ማንኛውም የከተማ ካዳስተር የቅየሳ ጥያቄ በመዝጋቢው ተቋም ወይም በሚመለከተው ክፍል እንዲሰራ ሲታዘዝ ደረጃውን በጠበቀ አግባብ መፈጸም እና ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፡፡

2. ማንኛውም የመሬት ቅየሳ ስራ የሚሰራ አካል የቅየሳ ትዕዛዝ አቀባበልን፣ አተገባበርን እንዲሁም የቅየሳ መረጃዎች ሪፖርት አደራረግን በሕግ ሥልጣን በተሰጠው ተቋም በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት መፈጸም አለበት፡፡

6. **<u>በቅየሳ ሂደት የቀያሹ ኃላፊነት</u>**

1. ማንኛውም የካዳስተር ቀያሽ ወይም ልዩ ቀያሽ ራሱ ለሚሰራቸው ወይም በራሱ ኃላፊነት ለሚያከናውናቸው የካዳስተር ቅየሳ ሥራዎች ትክክለኛነት ሙሉ ኃላፊነት ይወስዳል፡፡
2. ማንኛውም የካዳስተር ቀያሽ የቅየሳ ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ የቅየሳው ሥራ በህዝብና በመንግስት አገልግሎት ሥር ባልተያዘ መሬት ላይ ሲሆን ሥራውን ከመጀመሩ አስቀድሞ ለባለመብቶቹ ወይም በሥራው ሂደት ሊነኩ ለሚችሉ አዋሳኝ የይዞታ ባለመብቶች ከ15 ቀናት በፊት ማሳወቅ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) በተጠቀሰው መሰረት ባለመብቶችን ማግኘት የማይቻል ሲሆን፣ የይዞታ ባለመብቶች እንዲያውቁት የወሰን ቅየሳ መርሃ ግብሩን የሚገልጽ ማስታወቂያ ይዞታው በሚገኝበት መሬት ላይ ሊታይ በሚችል ቦታ ከ15 ቀናት በፊት መለጠፍ አለበት፡፡
4. ማንኛውም የካዳስተር ቀያሽ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) ወይም (3) መሰረት ካሳወቀ በኋላ የጊዜ ገደቡ ሲጠናቀቅ የሥራ ትዕዛዝ በመያዝ በሌሎች ሕጎች የተቀመጡትን በመሬት የመጠቀም መብቶችን በማያዛባ መልኩ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የቅየሳ ሥራውን ሊያከናውን ይችላል፡፡

7. **<u>የቅየሳ ልኬት የጥራት ደረጃዎችን ስለመጠቀም</u>**

1. የቅየሳ ልኬት የጥራት ደረጃዎች በዘመኑ የቅየሳና ልኬት ቴክኖሎጂዎች ወይም መሣሪያዎች ላይ ተመስርቶ በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል በመመሪያ ወይም በስታንዳርድ መሠረት መፈፀም አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የካዳስተር ቅየሳን የሚያስፈጽመው የክልሉ መስተዳደር ወይም የከተማ አስተዳደር አካል በሚመርጠው የቅየሳ ልኬት ጥራት ደረጃ መሰረት ሥራው መሰራቱን ማረጋገጥ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት የካዳስተር ቅየሳው በምን አይነት የትክክለኛነት ደረጃ መሰራት እንዳለበት ካልተጠቀሰ፣ ቀያሹ በከተማው የመሬት

ይዞታ ምዝገባ ተቋም ካዳስተር ሹም ተቀባይነት ሊያገኙ የሚችሉ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

8. <u>**ይዞታን ስለመለካት**</u>

በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 6 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1. በተቋሙ ወይም በተገልጋይ ጥያቄ አዲስ ወይም ቀድሞ የተቀየሰን ይዞታ ወሰን ለይቶ ለማመላከት በካዳስተር ቅየሳ ሹም በሚሰጠው የስራ ትዕዛዝ መሰረት ቀያሹ የቅየሳ ስራ ማከናወን አለበት፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ቅየሳ በሚካሄድበት ወቅት ቀድሞ የተቀየሰው የይዞታ ወሰን ምልክት ትክክለኛ ያልሆነ ቦታ ማረፉን ወይም ቦታ መልቀቁን በበቂ ማስረጃ እስካልተረጋገጠ ድረስ ነባሩን የይዞታ ወሰን ምልክት እንደ እውነተኛ ወሰን አድርጎ ማወራረስ አለበት፣
3. ቀድሞ የተቀየሰን የይዞታ ወሰን ምልክት በድጋሜ በሚደረግ ቅየሳ ወቅት በመዝጋቢው ተቋም በመዝገብ ላይ ተመዝግቦ ከሚታወቀው ጋር ያለመጣጣም ሲያጋጥም፣ የካዳስተር ቀያሹ በቅየሳ ንድፉ ላይ የድንበሩን መዛነፍ በግልጽ በማመላከት ቅየሳውን ባደረገ በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ በጽሁፍ ሪፖርት ለመዝጋቢ ተቋም የካዳስተር ቅየሳ ሹሙ ማስተካከያ ሥራ እንዲሰራ ማማከር አለበት፣
4. የመሬት ይዞታ መዝጋቢው ተቋም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የጽሁፍ ሪፖርት በደረሰው በሁለት ወራት ውስጥ የማስተካከያ ሥራ መስራት አለበት፡፡

9. <u>**የቅየሳ መረጃ ስለማደራጀት**</u>

1. የካዳስተር ቅየሳ መረጃዎች በዚህ ደንብና አግባብነት ባላቸው የአሰራር ስታንደርዶች መሰረት በሚዘጋጁ ቅፆች መሞላት አለባቸው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተሞሉት መረጃዎች በካዳስተር ቅየሳ ሹም በኩል በሚዘጋጅ ወረቀት ወይም ዲጂታል ማህደር መደራጀት አለባቸው፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>የቅየሳ ልኬትና ስሌት</u>

10. <u>**የይዞታ ወሰን ልኬት**</u>

1. ቀያሽ የይዞታን ወሰን መለካት ያለበት በቀጥታ መስመር ልኬት ዘዴ ምክንያታዊና ተግባራዊ ሊሆን በሚችል አግባብ መሆን አለበት፡፡
2. ቀያሹ የይዞታ ወሰን ሲለካ የልኬት ትክክለኛነት ለማሳየት የልኬት ውጤት ምዝገባ እና የካዳስተር ቅየሳ ፕላን ሰርተፊኬት አዘጋጅቶ ማስፀደቅ አለበት፡፡
3. የልኬት ትክክለኛነት የተገኘበት መንገድ በስታንዳርዱ መሰረት መመላከት አለበት፡፡
4. የይዞታውን ቆዳ ስፋት በሄክታር ወይም በሜትር ካሬ ማሳየት መቻል አለበት፡፡

11. **<u>የፎቶ መረጃን በመጠቀም ልኬት ማካሄድ</u>**

1. ማንኛውም ቀያሽ የምድር ቅየሳ መሳሪያ ሳይጠቀም በፎቶግራሜትሪ ወይም ሪሞት ሴንሲንግ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ተመስርቶ የንድፍ ካርታ ትክክለኛነቱ በተረጋገጠ የካዳስተር መሰረታዊ ካርታ በመጠቀም የካዳስተር ቅየሳ ልኬቱን ማካሄድ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው ካርታ ለካዳስተር ቅየሳ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው ተፈላጊው የትክክለኛነት ደረጃ ከተቀመጠው መስፈርት እና ከተፈቀደው የቦታ ትክክለኛነት ስታንዳርድ ጋር እኩል ወይም በተሻለ ደረጃ ለመሆኑ የሚገልጽ የትክክለኛነት ሰርተፊኬት መኖሩ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው ዘዴ ጥቅም ላይ ከዋለ ቀያሹ በቅየሳ ፕላኑ ላይ የተሰራበትን ዘዴ ማመላከት አለበት፡፡

12. **<u>አስቀድሞ የተለካ የቁራሽ መሬት ካርታ ልኬት የሚለውጥ ቅየሳ</u>**

1. የሚካሄደው ቅየሳ አስቀድሞ የተለካ የቁራሽ መሬት ስፋትን ሊለውጥ እንደሚችል ታሳቢ ሲደረግ፣ ቀያሹ ለውጥ ይመጣበታል ተብሎ የታሰበውን መሬት ቅየሳ ልኬት ተገቢነት ካለው የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥብ ጋር በማስተሳሰር የቦታው ስፋት በቅየሳ ንድፉ ላይ በኮኦርዲኔት ወይም ዲግሪ ንባብና ርዝመት ልኬት ማመላክት አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በነባር የውሃ እና የኤሌክትሪክ ማሳለፊያ መስመር ምክንያት ከመሬት በታች በሌላ ባለይዞታ ላይ የመጠቀም መብት ሲፈጠር ወይም በባለይዞታ ላይ ሁለተኛ ወገን የመጠቀም መብት በህንፃ ውስጥ በነበረ የውሃ እና የኤሌክትሪክ ማሳለፊያ መስመር ሲፈጠር

እና ትክክለኛ ቦታው የት እንደሆነ ማመላከት ሳይቻል ሲቀር ግምታዊ ስፍራው በቅየሳው ንድፍ ላይ ሰፍሮ ማብራሪያው በቅየሳ ማስታወሻ ላይ መስፈር አለበት፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መነሻነት የቁራሽ መሬቱ ካርታ ልኬት ተገቢው ማስተካከያ መደረግ አለበት፡፡

13. <u>የቅየሳ መሳሪያ መስተካከል</u>

1. ለካዳስተር ቅየሳ ሥራ የሚውሉ የቅየሳ መሣሪያዎች በየዓመቱ በአምራቹ ድርጅት በተዘጋጀው ሰነድ ላይ በተቀመጠው የልኬት ትክክለኛነት መለኪያ ደረጃ መሠረት ቢያንስ አንድ ጊዜ ተመርምረው ካሊብሬት መደረግ አለባቸው፡፡
2. ማንኛውም ቀያሽ የሚጠቀምበትን የቅየሳ መሳሪያ ልኬት በመስክ በሚጠቀምበት ጊዜ ከቅየሳ መነሻ ነጥቡ ላይ በተደጋጋሚ ልኬት ወስዶ ያገኘው ውጤቱ ከተቀመጠለት የትክክለኛነት ወሰን በላይ ሲሆን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰውን የአንድ ዓመት ጊዜ መጠበቅ ሳያስፈልገው የቅየሳ መሳሪያውን በማስመርመር ካሊብሬት ማስደረግ አለበት፡፡
3. ማንኛውም ካዳስተር ቀያሽ የሚጠቀምበትን የቅየሳ መሳሪያ ምን ያህል የትክክለኛነት ደረጃ ውጤት እንደሚያመጣለት እርግጠኛ ካልሆነ መጠቀም የለበትም፡፡

14. <u>ግሎባል ናቪጌሽናል ሳታላይት ሲስተም መሳሪያን መጠቀምና ማዕዘናዊ ልኬት ስራን ስለማረጋገጥ</u>

1. ቅየሳው በግሎባል ናቪጌሽናል ሳታላይት ሲስተም ሥርዓት በሚጠቀም መሳሪያ በሚከናወንበት ጊዜ ቀያሹ የግድ መጠቀም ያለበት ውጤታማነቱ በተረጋገጠ ዘዴ ሆኖ ተፈላጊውን ትክክለኛነት በሚተገብረው የቅየሳ ዓይነት የሚያስገኝ መሆን አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ከ10 ሺህ ሜትር ርዝመት በላይ የወሰን ቅየሳ ልኬት ሲኖር ቀያሹ የማዕዘን ቅየሳ ሥራው በጂኦዴቲክ ቅየሳ ንባብ መሠራቱን ማረጋገጥ አለበት፤ ይህም ከግሎባል ናቪጌሽናል ሳታላይት ሲስተም ንባብ በማነፃፀር በ360 ዲግሪ ሙሉ የማዕዘን ልኬት ወይም ከአገራዊ የቅየሳ መቆጣጠሪያ መረብ ጋር የተነጻጸረ መሆን አለበት፡፡

3. ማንኛውም በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) ላይ የተጠቀሱ ንፅፅሮች በቅየሳ ንድፉ ላይ መመላከት አለባቸው፡፡
4. ማንኛውም ካዳስተር ቀያሽ ወይም ልዩ ፈቃድ የተሰጠው ቀያሽ ከራሱ ውጭ ማንኛውንም ማዕዘናዊ ልኬት በሌላ ቀያሽ አማካኝነት ወደ ንድፍ መቀየር የለበትም፡፡
5. የግሎባል ናቪጌሽናል ሳታላይት ሲስተም የቅየሳ መሳሪያ ጥቅም ላይ ሲውል ቢያንስ ትክክለኛ የኢትዮጵያ ከፍታ ዳተም የልኬት መጠን ያላቸው አራት የቅየሳ ነጥቦች አስቀድሞ ቅየሳው በሚካሄድበት አካባቢ መመስረት አለባቸው፡፡

15.<u>የልኬቶችን ትክክለኛነት ማረጋገጥ</u>

1. የቅየሳው አተገባበር ሥርዓት ከፈቀደ ካዳስተር ቀያሹ ሁሉንም ልኬቶች በማረጋገጥ፣ ከነጥብ በኋላ ሶስት ዴሲማል ማስቀመጥ በሚችል ደረጃ ምስራቃዊ እና ሰሜናዊ መስመራዊ ልኬቶችን በሁሉም አቅጣጫ በማካሄድ እና በሜትር በማስላት የተደረጉት ልኬቶች መዝጋታቸውን በማረጋገጥ ማከናወን አለበት፡፡
2. በከተማ ካዳስተር ቅየሳ ሥራ የተዘጋጀው መረጃ ትክክለኛነት በሁለት ወሰንተኞች መካከል አከራካሪ ሊሆን የሚችለው ካርታው ከተሰራበት መስፈርት መነሻ በማድረግ ሊፈጠር የሚችለውን ስህተት መቀበል ከሚቻልበት የስህተት ወሰን ስታንዳርድ መጠን በልጦ የተገኘ ሲሆን ብቻ ነው፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የቅየሳ መነሻ ነጥቦች አጠቃቀምና የቅየሳ ነጥብ ትክል ድንጋይ</u>

16.<u>ስለ ቅየሳ መነሻ ነጥብ</u>

1. የቅየሳ መነሻ ነጥብ ለመወሰን የሚያገለግል የቅየሳ ምልክት ለቀጣይ የቅየሳ ሥራ እንዲጠቅም ለማድረግ ለተፈለገው ቅየሳ ዓይነት ሲባል በተለየ ሁኔታ ምን አይነት መሆን እንዳለበት መወሰን አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚካሄድ ቅየሳ ዝርዝር ተግባራት በመመሪያ ይወስናሉ፡፡

17.<u>የከፍታ ቅየሳ ነጥቦች</u>

1. ማንኛውም የከፍታ ቅየሳ ከኢትዮጵያ ከፍታ ዳተም ልኬት ወይም ከሌላ ተቀባይነት ካገኘ መሰል ዳተም ጋር መተሳሰር አለበት፡፡

2. የከፍታ ዳተም በሁለት ትክክለኛ የኢትዮጵያ ከፍታ ዳተም ልኬት መጠን ባላቸው የከፍታ ቅየሳ ነጥቦች መካከል ባለ ዝግ ከፍታ ልዩነት መረጋገጥ አለበት፡፡
3. የተረጋገጠ ማንኛውም የከፍታ ልዩነት ወይም ለቅየሳ የተዘጋጀ ከፍታ ልኬት በስታንዳርድ ከተቀመጠው በትክክለኛነቱ እኩል የሆነ ወይም የተሻለ መሆን አለበት፡፡
4. የከፍታን ወይም የዝቅታን ወይም ሁለቱንም መጠን ለመወሰን በሚደረግ ቅየሳ ማንኛውም ቀያሽ የቅየሳ ልኬቱን ሲለካ ከሁለት ወይም ከሁለት በላይ በሆኑ የከፍታ ቅየሳ ነጥቦችን በማስተሳሰር መሆን አለበት፡፡ ሆኖም ከሁለት አንዱ ከሚቀየሰው መሬት ወሰን ውጭ መሆን አለበት፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት የቅየሳ ልኬት ሲፈጸም፡-
   ሀ) መነሻ ከሆነው የከፍታ ቅየሳ ነጥብ ከቁራሽ መሬቱ በ 300 ሜትር ርቀት ውስጥ የሚገኝ የቅየሳ ነጥብ ትክል ድንጋይ መሆን አለበት፤ ወይም
   ለ) ከሚለካው መሬት ወሰን ውጭ ነባር ቋሚ የቅየሳ ነጥብ መጠቀም በማይቻልበት ሁኔታ አዲስ የቅየሳ ነጥብ ከቁራሽ መሬቱ በ 300 ሜትር ርቀት ወሰን ውስጥ ይዘጋጃል፡፡

## 18.<u>የቅየሳ ምልክቶች ቅርጽ እና ቅጾች</u>

1. ዘላቂነት እና ቋሚነት ላለው የቅየሳ ሥራ የሚያገለግሉ የቅየሳ ምልክቶች ቅርጽ እና ቅጾች በአገር አቀፍ ደረጃ በሚመለከተው አካል በተዘጋጀ ስታንዳርድ መሰረት መሆን አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተዘጋጀ ስታንዳርድ በሌለ ጊዜ በካዳስተር ቅየሳ ሹም አጽዳቂነት መዝጋቢው ተቋም በሚያወጣው የመመዘኛ መስፈርት መሰረት ይሆናል፤ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

## 19.<u>የወሰን ምልክት ስለማድረግ</u>

1. በካዳስተር ቅየሳ ወቅት የወሰን ምልክቶች በችካልና አቅጣጫን በሚያሳዩ ምልክቶች መቀመጣቸው መረጋገጥ አለበት፡፡

2. የወሰን ማዕዘን ችካል ውፍረት እና ከፍታ በአገር ደረጃ ተፈፃሚ በሚሆን ስታንዳርድ በተቀመጠው ደረጃ መሠረት ለረዥም ጊዜ የሚያገለግል፣ የማይንቀሳቀስ እና በቀላሉ ሊታይ እና ሊገኝ የሚችል መሆን አለበት፡፡

20. **የወሰን ማዕዘናት እና ማጣቀሻ ምልክት**

1. የወሰን ማዕዘን ችካል እና ማጣቀሻ ምልክት በአንድ ቦታ ከተገኙ ቀያሹ በሁለቱ መካከል ያለውን አቀማመጥ እና ርቀት በማስላት መወሰን አለበት፡፡
2. ከዋናው ማጣቀሻ ሰነድ ጋር ያለመጣጣም ከተገኘ ቀያሹ ሌሎች ሰነዶችን በማገናዘብ የትኛው መወሰድ እንዳለበት መወሰንና የተከሰተውን ልዩነት ምንነት በቅየሳ ንድፍ ላይ በዝርዝር ማስቀመጥ አለበት፡፡

21. **የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦችን ስለማስተካከል**

1. ማንኛውም አዲስ የካዳስተር ቅየሳ ከፊሉን የመሬት ይዞታ ቀድሞ ከተመዘገበው መረጃ አንጻር የሚያናጋ ከሆነ የካዳስተር ቀያሹ እያንዳንዱን የወሰን ማዕዘን ምልክት ልኬት ከዚህ ቀደም መነሻ ሆኖ ካገለገለ እና ከይዞታ ወሰን ማዕዘን ምልክት ጋር ትስስር ከነበረው የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥብ መነሻ በማድረግ እያንዳንዱ የወሰን ማዕዘን ምልክት ትክክለኛ ቦታ ላይ ማረፉን ማረጋገጥ አለበት፡፡
2. ወሳኝ የሚባሉ የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች ከተበላሹ፣ ቀያሹ አዲስ ልኬት በማካሄድ የይዞታ ወሰን እና የወሰን ማዕዘናትን ለመወሰን ካስፈለገው፣ ኩታ ገጠም አጎራባች እና ከመንገድ ባሻገር በተቃራኒ ወገን ባሉ ክፉይ መሬቶች አጥሮች እና ሌሎች ቋሚ ምልክቶችን እንደ አስፈላጊነቱ በከፊል ወይም በሙሉ መረጃዎችን በመውሰድ መለካት ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሰረት ማሻሻያ በሚኖርበት ጊዜ ቀያሹ በከፊል ወይም በሙሉ ጥቅም ላይ የሚያውላቸውን መረጃዎች በመመርመር ትክክለኛ ትስስራቸውን በማረጋገጥ ቦታቸውን ማመላከት አለበት፡፡

22. **የቅየሳ መቆጣጠሪያ እና የወሰን ምልክት አጠባበቅ**

1. ለካዳስተር ሥራ የሚውል የቅየሳ መቆጣጠሪያ ምልክት ስልጣን በተሰጠው አካል በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ለጥበቃ ምቹ የሆነ መከላከያ ሊገነባለት እና የሕግ ጥበቃ ሊደረግለት ይገባል፡፡

2. የወሰን ምልክት ከተደረገ በኋላ የወሰን ምልክቱ ተጠቃሚ የሆኑ ባለይዞታዎች ወይም የሚመለከተው የአካባቢው የታችኛው እርከን የአስተዳደር አካል ደህንነቱን በተመለከተ የመከታተል እና ለውጥ ሲኖር ለመዝጋቢው ተቋም ሪፖርት የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

23.<u>የመስክ ልኬትና ርቀት አመዘጋገብ</u>

1. ማንኛውም ቀያሽ የይዞታን ወሰን ምልክት ሲለካ የወሰን ምልክቱን ቀድሞ ከነበረበት ቦታ በማያናጋ አኳኋን መለካት አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የተለካው የይዞታ ወሰን ተመዝግቦ በሰነድ ላይ ከተመላከተው የመሬት ይዞታ ወሰን ጋር እንደማይጣጣም ከታወቀ ቀያሹ አለመጣጣሙን በማስታወሻ በማስፈር የወሰኑን ርቀት ማረጋገጥና የሌላ አካል የይዞታ ወሰን ርቀት በመውሰድ አመላክቶ ያገኘውን ልኬት ከቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥብ ተነስቶ በንጽጽር ማረጋገጥ አለበት፡፡
3. የመሬት ይዞታን ወሰን ለመወሰን የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥብ በማይኖርበት ጊዜ ቀያሹ በቅየሳ ማስታወሻው ላይ ልኬቱን ለማከናወን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በቂ ልኬትን በቀድሞ ቦታው ለማካሄድ የሚያስችል መሬት ያለ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡ ሆኖም ኩታ ገጠም መሬት ወይም አጎራባች ክፍይ መሬት መግፋት እንደማይቻል ማመላከት አለበት፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ስለመስክ ማስታወሻ</u>

24.<u>የመስክ ማስታወሻ አዘገጃጀት</u>

የመስክ ማስታወሻ በስታንዳርዱ በተገለጸው መሰረት በምዝገባ ተቋሙ መዘጋጀት አለበት፡፡

25.<u>የመስክ ማስታወሻ መረጃን መሰብሰብ</u>

ቀያሹ የመስክ ማስታወሻ መረጃን ሲሰበስብ ልኬቶችን፣ የአየሩን ሁኔታና የልኬት አመዘጋገቡን ከሌሎች ጠቃሚ መረጃዎች ጋር በማመሳከር እና በማስተሳሰር

በስታንዳርዱ መሰረት መመዝገብ አለበት፡፡ እንዲሁም ለመስክ ማስታወሻ ጠቃሚ የሚባሉ ሌሎች መረጃዎችና ዶክመንቶች ከመስክ ማሰባሰብ አለበት፡፡

26.<u>በመስክ የሚሰበሰቡ ዲጂታል መረጃዎች</u>

1. ቀያሹ በመስክ የሚሰበስባቸውን ዲጂታል መረጃዎች ከሰበሰበ የሰበሰበውን ቅጅ በፋይል መረጃ አያያዝ ሥርዓት ተጠቅጥቆ ሲቀመጥ የተሟላ እና ትክክለኛ የቅየሳ ንድፍ ወይም ፕላን ማሠራት በሚችል መልኩ መሆን አለበት፡፡
2. ቀያሹ አስቀድሞ በሙሉም ሆነ በከፊል በግሎባል ናቪጌሽናል ሳተላይት ሲስተም የቅየሣ ልኬት ሥርዓት መረጃ መዝግቦ ከሆነ፣ በዲጅታል የተመዘገበው መረጃ የማነፃፀሪያው መነሻ ልኬት ወይም የቦታ አቀማመጥ መረጃው የኤሌክትሮኒክስ የቅየሣ መሣሪያ በሚጠይቀው ፎርማት መሠረት ቅርጹ ሳይቀየር የተሟላ እና ትክክለኛ የቅየሳ ፕላን መስራት በሚያስችል መልክ መጠበቅ አለበት፡፡

27.<u>በመስክ ማስታወሻ የጂኦዴቲክ ልኬት ንባቦችን መመዝገብ</u>

1. ማንኛውም ቀያሽ በመስክ ማስታወሻው ላይ የቅየሳ መነሻ ነጥብ መስመር እና አቅጣጫ ወይም ኦረንቴሽኑ የተወሰደበት የመጀመሪያ መነሻ ነጥብን ግልፅና በማያሻማ መልኩ ማመላከት አለበት፡፡
2. ቀያሹ የጂኦዴቲክ ንባብ የሚያካሂድ ከሆነ ቀን፣ ሰዓት እና አግባብ ያለው የቅየሳ መቆጣጠሪያ ላቲትዩድ እና በአጠቃላይ በቦታው ላይ ከተካሄደ የቅየሳ ንባብ ጋር መስፈር ይኖርበታል።
3. ሁሉም ማዕዘኖች እና አቅጣጫዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በዲግሪ፣ በደቂቃ እና በሰከንድ ደረጃ መገለጽና መመዝገብ አለባቸው፡፡ አቅጣጫዎቹም በሰአት አቆጣጠር አቅጣጫ መቀመጥ ወይም በግራድ ተነቦ መመዝገብ አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (3) የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው ቀያሹ ሌሎች ለዚሁ ሥራ ያገለግላሉ የተባሉትን መረጃዎች በግልፅ በሚነበብ መልኩ በመስክ ማስታወሻው ላይ መመዝገብ አለበት፡፡

28.<u>በመስክ ማስታወሻ የተያዙ መረጃዎችን ትክክለኛነት ስለማረጋገጥ</u>

በመስክ ማስታወሻ የተመዘገቡትን መረጃዎች ትክክለኛነት በተመለከተ ለማረጋገጥ ቀያሹ ሙሉ ስሙን ፊርማውን እና የተሰራበትን ቀን ማስፈር አለበት፡፡

<u>**ክፍል ስድስት**</u>

<u>**የቅየሣ ንድፍ**</u>

**29.የቅየሳ ንድፍ ቅፆች**

1. ማንኛውም ቀያሽ የካዳስተር ልኬት ሲያከናውን የቅየሳ ንድፍ ቅፆች መጠቀም አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጹ ቅፆች ሥልጣን ባለው አካል ለዚሁ ተግባር ተብለው የተቀመጡ ደረጃዎችን ጠብቀው መዘጋጀት አለባቸው፡፡

**30.የዳተም መረጃዎችን መመዝገብ**

1. ማንኛውም ቀያሽ የካዳስተር ልኬት ሲያከናውን የዳተም መረጃዎች ኮድ፣ ዞን፣ ኮኦርድኔት፣ መስፈርት እና የስህተት ወሰኑን አሟልቶ መመዝገብ አለበት፡፡

**31.የከፍታ መቆጣጠሪያ ነጥብ መመዝገቢያ ዘዴ**

በቅየሳ ፕላን ላይ የእያንዳንዱ ከፍታ መቆጣጠሪያ ነጥብ ተፈጥሯዊ ባህሪ ይዞታ እና የከፍታ ዋጋ እንዲሁም የከፍታ መቆጣጠሪያ ነጥብ የከፍታ ዋጋ ከመረጃ ሰጪው ባለስልጣን የተገኘበት ቀን መስፈር አለበት፡፡

**32.የመሬት ይዞታ ወሰኖችን ስለማመላከት**

የመሬት ይዞታ ወሰኖች ከማመላከት የቅየሳ ንድፉ በሚጠይቀው ወይም በሚፈልገው አግባብ ምልክቶችን፣ የወሰኑን ዓይነት፣ የተወሰደው ግድግዳ ከሆነ የጋራ መሆኑንና የወሰን መለያውን እና ሌሎች ጠቃሚ ነገሮች መመዝገብ አለባቸው፡፡

**33.የተፈጥሮ ክስተትን በይዞታ ወሰንነት ማሣየት**

የተፈጥሮ ክስተትን በይዞታ ወሰንነት የሚያሳይ የቅየሳ ንድፍ በወቅቱ በመሬቱ ላይ ያለውን ነባራዊ ሁኔታን የሚያሳይ ሆኖ መነደፍ አለበት፡፡

## ክፍል ሰባት

## ስለ ካዳስተር ካርታ አሠራር

**34.ስለካዳስተር ካርታ ዝግጅት**

1. መዝጋቢው ተቋም የካዳስተር ሥርዓት ለመዘርጋት አስቀድሞ የካዳስተር መሠታዊ ካርታ እንዲዘጋጅለት ማድረግ ወይም የተዘጋጀለትን መሠረታዊ ካርታ መጠቀም አለበት፡፡
2. የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር ካርታ በውስጥ የሚካተቱ ቁራሽ መሬቶችን ከልዩ የቁራሽ መሬት ኮዳቸው ጋር በካርታ ላይ በግልጽ ለማሳየት በሚመጥን መስፈርት የካዳስተር ካርታ ኢንዴክስን መሠረት አድርጎ ካርታው በስታንዳርዱ መሰረት መዘጋጀት አለበት፡፡

3. የካዳስተር ካርታ የሚመነጨው ከመሠረታዊ ካዳስተር ካርታ፣ መብት ፈጣሪው ተቋም በይዞታ ከገለፀው ሰነድ እውነታ እና በአዲስ መልክ የተወሰደው ልኬት ጥራቱን እና ተመጋጋቢነቱን የጠበቀ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ መሆን አለበት፡፡

35.<u>የይዞታ ካርታና የቁራሽ መሬት ልዩ መለያ ኮድ</u>

1. የቁራሽ መሬት ልዩ መለያ ኮዱ በየትኛውም የሀገሪቱ የከተማ ክፍል የማይደገም መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከገጠር ቁራሽ መሬት መለያ ኮድ ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት፡፡
2. የቁራሽ መሬት መለያ ኮዱ የሚተገበርበት ስታንዳርድ የገጠር ቁራሽ መሬት መለያ ኮድ አሰጣጥን ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፡፡
3. ጠቋሚ ካርታው የይዞታውን ልኬት፣ ኮዱን፣ መስፈርቱን፣ መረጃዎቹንና የተገናዘበውን የመስክ ማስታወሻ ባካተተ መልኩ መዘጋጀት አለበት፡፡

<u>**ክፍል ስምንት**</u>

<u>**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**</u>

36.<u>የቀያሽ ደረጃ እና ተጠያቂነት</u>

1. የካዳስተር ቀያሽ በሙያው እውቅና ከተሰጠው ተቋም የተመረቀ፣ የሙያ ምዘና አልፎ ተገቢውን የብቃት ደረጃ ሰርተፊኬት ያገኘ እና ከዚሁ ሙያ ጋር በቀጥታ ተያያዥነት ያለው ስራ ላይ ከሶስት ዓመታት ላላነሰ አገልግሎት የሰጠ፣ ባለፉት ሶስት ዓመታት ሥራ ላይ ስለመሆኑ ወይም የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና ለመውሰዱ ማስረጃ የሚያቀርብ መሆን አለበት፡፡
2. ልዩ ፈቃድ የተሰጠው ቀያሽ በሙያው ከታወቀ ተቋም ተምሮ የተመረቀ፣ የሙያ ምዘና ፈተና አልፎ ተገቢውን የብቃት ደረጃ ሰርተፊኬት ያገኘ እና ከዚሁ ሙያ ጋር በቀጥታ ተያያዥነት ያለው ሥራ ላይ አንድ አመት የሥራ ልምድ ያለው መሆን አለበት፡፡
3. ማንኛውም የካዳስተር ቀያሽ የቅየሳ ስራን እንዲያከናውን በተቀበለው ትዕዛዝ መሰረት የቅየሳ ሥራውን አሟልቶ እና ትክክለኛነቱን ጠብቆ ባያከናውን፣ በከፊል ቢያጓድል ወይም ቢያሳስት በዚህ ደንብ አንቀጽ 37(1) መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

4. ማንኛውም ልዩ ፈቃድ የተሰጠው ቀያሽ የተቀበለውን የሥራ ትዕዛዝ በተቀበለው መሰረት አሟልቶ እና ትክክለኛነቱን ጠብቆ ባያከናውን፣ ቢያጓድል ወይም ቢያሳስት በዚህ ደንብ አንቀጽ 37 (1) መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

37.<u>ደንብ ስለመተላለፍ</u>

1. የዚህን ደንብ ማናቸውንም ድንጋጌዎች፣ ይህንን ደንብ ተከትለው የወጡ መመሪያዎች፣ በመመሪያዎቹ መሠረት የሚወጡ የመንግስት አካል ሕጋዊ ትእዛዞችን እንዲሁም በሌሎች ሕጎች የካዳስተር ቀያሽን አስመልክቶ የተቀመጡ የሥነ ምግባር ኃላፊነቶችን አለመወጣት የሙያ ሥነ ምግባር ደንብ በመጣስ ያስጠይቃል፡፡
2. የቅየሳ ነጥብ እና የወሰን ምልክትን ከሥፍራው ያነሳ፣ ያዘዋወረ፣ በሐሰተኛ ሥፍራ ላይ የተከለ ወይም ወደ ሐሰተኝት የለወጠ ወይም እንዳይታወቅ ያጠፋ ማንኛውም ሰው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 688 መሠረት ተጠያቂ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የተነሳውን የቅየሳ ነጥብ ወይም የወሰንን ምልክት ወደ ነበረበት ለመመለስ የሚያስፈልገውን ወጪ እንዲሸፍን ይደረጋል፡፡

38.<u>ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

39.<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥቅምት 10 ቀን 2007 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## <u>ደንብ ቁጥር 324/2006</u>

## <u>የከተማ መሬት ይዞታ ማረጋገጥ እና ምዝገባ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 እና በከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 818/2006 አንቀጽ 54(1) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የከተማ መሬት ይዞታ ማረጋገጥ እና ምዝገባ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 324/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

   1. "አዋጅ" ማለት የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 818/2006 ነው፤
   2. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተሰጡ ትርጓሜዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፤
   3. "የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ" ማለት በአንድ ቁራሽ መሬት ላይ ያለ የመሬት ይዞታ መብትን በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት ማረጋገጥ ነው፤
   4. "የከተማ ጣቢያ" ማለት በአንድ ከተማ ዝቅተኛ አስተዳደር እርከን ሥር የሚገኝ መሬት ሆኖ ለከተማ ጣቢያ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት በዙሪያ ገጠም መንገዶችን እና መስመራዊ ገጽታዎችን ተከትሎ የሚከለል በውስጡ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ይዞታዎች የያዘ ሥፍራ ነው፤
   5. "የመሬት ይዞታ መብት ሰጪ ተቋም" ማለት በሚረጋገጠው ቁራሽ መሬት ላይ በህግ መሠረት መሬትን የመጠቀም መብት የመስጠት ሥልጣን የነበረው እና ያለው አካል ነው፤
   6. "የመሬት ይዞታ የክርክር መዝገብ" ማለት የይዞታ ማረጋገጥ ለጊዜው የማይከናወንባቸው የመሬት ይዞታዎች ሰነዶቻቸው እስኪረጋገጥ በጊዜያዊነት የሚቆዩበት መዝገብ ነው፤
   7. "የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ መዝገብ" ማለት በወረቀት ወይም በዲጂታል መዝገብ ደረጃ የሚዘጋጅ የቁራሽ መሬት ልዩ መለያ ኮድ የታወቀ የመሬት ይዞታ መብት እና ወሰን ተረጋግጦ የሚመዘገብበት መዝገብ ነው፤
   8. "የመሬት ይዞታ መብት መዝገብ" ማለት በወረቀት ወይም በወረቀትና በዲጂታል የሚዘጋጅ በልዩ የመለያ ቁጥር የታወቀ የእያንዳንዱ የይዞታ ተጠቃሚዎችን፣ መብት፣ ክልከላና ኃላፊነት የሚመዘገብበት መዝገብ ነው፤

9. “የማይንቀሳቀስ ንብረት” ማለት የከተማ መሬትንና በመሬቱ ላይ የሚገኘውን መሬት ነክ ንብረት፣ በመሬት ላይ በቋሚነት የተገነቡ ግንባታዎችን ወይም የተተከሉ ቋሚ ተክሎችን የሚያካትት ሲሆን ሌሎች ተነሽ ንብረቶች እንደሰብል፣ ሳር እና ቋሚ ያልሆኑ ተክሎችን አይጨምርም፤
10. “ሰብ ሊዝ” ማለት በኢንዱስትሪ ዞን የለማ የመሬት ይዞታ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በሊዝ ሥርዓት አግባብ ማከራየት ነው፤
11. “መደበኛ አድራሻ” ማለት የመሬት ይዞታው የሚገኝበት አድራሻ ሆኖ ከወረዳ በታች ቀጠና፣ ሠፈር፣ ጣቢያ እና የቤት ቁጥር የሚገለጽበት ነው፤
12. “አማካሪ ኮሚሽን” ማለት በዚህ ደንብ በአንቀጽ 29 መሠረት የሚቋቋም ኮሚሽን ነው፤
13. “የዋስትና ፈንድ” ማለት መዝጋቢ ተቋም ላረጋገጣቸውና ለመዘገባቸው የከተማ መሬት ይዞታዎች በተቋሙ ስህተት በተፈጠሩ የመሬት ይዞታ መብት መዛባቶች ምክንያት ለሚደርስ ጉዳት ካሣ ክፍያ እንዲውል በየጊዜው ከሚደረግ የከተማ መሬት ይዞታ የመጠቀም መብት ዝውውር ከግብይቱ ዋጋ አንድ መቶኛ ሳይበልጥ የሚሰበሰብ ክፍያ ነው፡፡

3. <u>**የምዝገባ ዓላማዎች**</u>

የመሬት ይዞታ ምዝገባ የሚከተሉ ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1. ከተሞች ያላቸውን የመሬት ሀብት ለይተው እንዲያውቁና የመሬት ይዞታው በማን፣ መቼ፣ ለምን አገልግሎት፣ በምን ሁኔታና ለምን ያህል ጊዜ እንደተያዘ ህጋዊ የሆነ መረጃ እንዲኖራቸው በማድረግ በመሬት ላይ ለሚያስተሳልፉት ውሳኔ ምቹ ሁኔታመፍጠር፣
2. የመሬት ይዞታ ባለመብት የሆነ ሰው በመሬት ይዞታው ላይ ያፈራውን ሀብት በዋስትና በማስያዝ ከከተሞች የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ እና አካባቢያዊ ዕድገት ውስጥ ተጠቃሚ እንዲሆን ማስቻል፤
3. የመሬት ይዞታ ላይ ያለን የተጠቃሚነት መብትን፣ የአገልግሎት አይነት በይዞታው ላይ ያለን የማይንቀሳቀስ ንብረት ልውውጥ ተቀባይነት ባለው ማስረጃ ላይ እንዲገነባ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር በሂደቱ ለሁሉም ሰው ግልጽነት የሚፈጠርበትን የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት;

4. በመብት ሰጪ ተቋም የተሰጠ የመሬት ይዞታ መብት፣ ክልከላ እና ኃላፊነት ከተሞች ዋስትና እንዲሰጡ በማድረግ የመሬት ይዞታን አስመልክቶ የሚነሳ ክርክር በመቀነስ ህብረተሰቡ የመሬት ይዞታ ተጠቃሚነት መብቱን አረጋግጦ ጊዜውን ለልማት የሚያውልበት አመቺ ሁኔታ መፍጠር፡፡

4. <u>***የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጥ መርሆዎች***</u>

1. በህግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል ውጭ መዝጋቢው ተቋም በመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ሂደት ያለን የይዞታ መብት ማሻሻል ወይም ያልነበረ አዲስ የመሬት ይዞታ መብት መስጠት አይችልም፡፡
2. የመሬት ይዞታ መብት የማረጋገጥ ሂደት በይዞታው ላይ ያለ መብት፣ ክልከላና ኃላፊነት አስቀድሞ ተረጋግጦ የሚመዘገብበት ሂደት በመሆኑ የባለይዞታው የመሬት ይዞታ መረጃ ከመሬት አስተዳደር የይዞታ መረጃ ጋር ተመሳሳይ መሆን ይኖርበታል፡፡
3. የመሬት ይዞታ መብት ይረጋገጥልኝ ጥያቄ ያልቀረበበት እና የማይንቀሳቀስ ንብረት ያላረፈበት መሬት የመሬት ይዞታ መብት ሰጪ ተቋም ስም እንዲመዘገብ ይደረጋል፡፡
4. መብት ጠያቂው ከመሬት ይዞታ መብት ይረጋገጥልኝ ጥያቄ ጋር በማስረጃነት አያይዞ ያቀረበው ሰነድ ለመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጥ ሂደት ብቁ ካልሆነ ሥልጣን ባለው የመሬት ይዞታ መብት ሰጪ ተቋም የመሬት ይዞታው መብት ትክክለኛነት ተረጋግጦ መቅረብ አለበት፡፡

5. ስለአንድ ቁራሽ መሬት ይዞታ መብት እና ወሰን በትክክልና በተሟላ ሁኔታ ተረጋግጦ በመዝጋቢው ተቋም የተመዘገበ መብት፣ ክልከላ እና ኃላፊነት መረጃ ለተመሳሳይ ሥራም ሆነ ለመሬት ይዞታ አስተዳደር አገልግሎት መሠረታዊ መነሻ ሆኖ ያገለግላል፡፡

<u>**ክፍል ሁለት**</u>

<u>**የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ሥርዓት**</u>

<u>**ንዑስ ክፍል አንድ**</u>

<u>**የመሬት ይዞታ መብት እና ወሰን ማረጋገጥ አተገባበር**</u>

5. **የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ሥርዓት ቅድመ ሁኔታዎች**

   1. በመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር ውስጥ የሚገኙ ሁሉም ቁራሽ መሬቶች በካዳስተር መሰረታዊ ካርታ ላይ ተለይተውና የራሳቸው መለያ ኮድ የተዘጋጀላቸው መሆን አለባቸው፡፡
   2. የመሬት ይዞታን ለማረጋገጥ በተመረጠው የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር ውስጥ ወይም በአጎራባች የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር ውስጥ የወሰን ልኬት ለማካሄድ የሚያስችል ከሁለት ያላነሰ የቅየሣ መቆጣጠሪያ ነጥብ መተከል ይኖርበታል፡፡
   3. ሥልጣን ካለው የመሬት ይዞታ መብት ሰጪ ተቋም በቁራሽ መሬት ላይ የተፈጠረውን መብት፣ ክልከላና ኃላፊነት ዓይነት የሚገልጽ የእያንዳንዱ ቁራሽ መሬት ማስረጃ በተዘጋጀው የርክክብ ሠነድ መሰረት ለመዝጋቢው ተቋም መተላለፍ አለበት፡፡
   4. መዝጋቢ ተቋሙ ከመሬት ይዞታ መብት ሰጪው ተቋም ጋር በመመካከር የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ሥራ የሚጀመርበትን አካባቢ ለቅድመ ዝግጅት እንዲረዳ በቅድሚያ ለይቶ ለከተማ መሬት አስተዳደር ተቋማት እና ለሚመለከታቸው አካላት ማሳወቅ አለበት፡፡

6. **በስልታዊ ዘዴ የመሬት ይዞታን ስለማረጋገጥ**

   1. ከተሞች የህጋዊ ካዳስተር ሥርዓትን በአጭር ጊዜ ለመገንባት በስልታዊ የይዞታ ማረጋገጥ ዘዴ የመሬት ይዞታን መብትና ወሰንን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡
   2. በስልታዊ የይዞታ ማረጋገጥ ዘዴ እንዲከናወን በተወሰነበት ቀጠና እና ሠፈር ውስጥ ይዞታ ያለው ማንኛውም ሰው ይዞታው እንዲረጋገጥለት የማመልከት ግዴታ አለበት፡፡

7. **በአልፎ አልፎ ዘዴ ይዞታን ስለማረጋገጥ**

1. የከተማ አስተዳደር የይዞታ ማረጋገጥ ሥራውን በስልታዊ ዘዴ ከማረጋገጥ በተጨማሪ በአልፎ አልፎ ዘዴ ለማከናወን ሲወስን ለሕዝብ ይፋ ማድረግ አለበት፡
2. ሥልታዊ የይዞታ ማረጋገጥ ከሚከናወንበት ቀጠናና ሠፈር ውጭ የሚገኙ ባለይዞታዎች በአልፎ አልፎ ዘዴ ይዞታቸው እንዲረጋገጥላቸው ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ፡፡
3. በአልፎ አልፎ ዘዴ የመሬት ይዞታው እንዲረጋገጥለት የሚጠይቅ ማንኛውም ሰው ለዚህ ዓላማ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላትና የተተመነውን የአገልግሎት ክፍያ በመፈፀም ጥያቄውን ማቅረብ አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረትመዝጋቢው ተቋም የአገልግሎት ክፍያን ለመተመን የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፦
   ሀ) የሰነድ ማሰባሰብ እና ማጣራት ሥራን፤
   ለ) የመስክ ወሰን የማረጋገጥ እና የቅየሳ ልኬትን፤
   ሐ) የመሬት ይዞታውን የማረጋገጥ ሥራ በተጠየቀው አግባብ ለመፈፀም ለህዝብ ማስታወቂያ የሚወጣ ወጪን፤
   መ) የሚረጋገጠው የመሬት ይዞታ ስፋት እና የገበያ ዋጋ ግምትን፤ እና
   ሠ) ስህተት ቢፈፀም በሌላ ወገን ላይ ሊያስከትል የሚችለውን የጉዳት ተጋላጭነት መጠን፡፡
5. በአልፎ አልፎ ዘዴ የመሬት ይዞታው የማረጋገጥ አገልግሎት ይሰጠኝ ብሎ ያመለከተ ባለይዞታ የአገልግሎት ክፍያውን አጠናቆ ከፍሎ አገልግሎቱን እንደማይፈልግ ቢያሳውቅ አገልግሎቱ ይቋረጣል፤ ነገር ግን ለተጠየቀው አገልግሎት ከተደረገው ክፍያ ለአገልግሎቱ የወጣው ወጪ ተቀንሶ ቀሪው ተመላሽ ይደረጋል፡፡
6. በአልፎ አልፎ ዘዴ የመሬት ይዞታ የማረጋገጥ አገልግሎት ለማግኘት የሚፈልግ አመልካች የያዘውን የመሬት ይዞታ ማስረጃ ፎቶ ኮፒ ከዋናው ጋር በማቅረብ ከተመሳከረ በኋላ ፎቶ ኮፒውን ማስረከብ አለበት፡፡
7. አመልካቹ የከተማ መሬት ይዞታ መብቱን ያገኘው በሽያጭ፣ በስጦታ ወይም በሌላ ህጋዊ መንገድ ከሆነ ከመብት ሰጪ ተቋም በኩል የስም ዝውውሩ ስለመፈጸሙ መረጋገጥ አለበት፡፡

8. <u>ስለ ይዞታ ማረጋገጫ ቀጠና እና ሠፈር</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 12(1) መሰረት በመዝጋቢው ተቋም ለተመረጠው የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ቀጠና እና ሠፈር ያዘጋጀው የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር ካርታ በተቋሙ ኃላፊ ፊርማ ከተረጋገጠ እና የተቋሙ ማህተም ካረፈበት በኋላ የመሬት ይዞታ አረጋጋጭ ሹሙ ተረክቦ ጥቅም ላይ ማዋል ይኖርበታል፡፡
2. በከተማው ለመሬት ይዞታ ማረጋገጫ የተመረጠው ቀጠና እና በሥሩ ያሉት ከአምስት የማይበልጡ ሰፈሮች ተከታታይ ቁጥርና መለያ ስያሜ ያላቸው መሆን አለባቸው፡፡
3. በአዋጁ አንቀጽ 2 (13) የተሰጠው ትርጉም እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ወረዳ በቀጠና ይከፋፈላል፣ አንድ ቀጠና በሠፈር ይከፋፈላል፣ አንድ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር ደግሞ ከ200 ቁራሽ መሬት ያልበለጠ መያዝ ያለበት ሆኖ እያንዳንዱ የይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር በከተማ ጣቢያ መከፋፈል አለበት፡፡

9. **የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር ካርታ**

1. የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር ካርታ በይዞታ የማረጋገጫ ቀጠና እና ሠፈር ውስጥ ያሉትን የቅየሣ መቆጣጠሪያ ነጥቦች ማሳየት ይኖርበታል፡፡
2. መዝጋቢው ተቋም የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር ካርታን በከተማ ካዳስተር ቅየሳ ደንብ በተቀመጠው መሠረት ያዘጋጃል፡፡
3. የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር ካርታው የይዞታ ማረጋገጫ ቀጠናና ሠፈር ወሰንን፣ በሚያሳይ መልኩ መሠረታዊ ካዳስተር ካርታን መነሻ በማድረግ መዘጋጀት አለበት፡፡

10. **በከተማ የተካለለ የአርሶ አደር መሬት ይዞታ ስለማረጋገጥ**

1. በከተማ የተካለለ የአርሶ አደር መሬት ይዞታ ለማረጋገጥ የመሬት ይዞታውን ሲያስተዳድር ከነበረው የገጠር የመሬት አስተዳደር አካል የቦታውን ስፋት፣ የባለይዞታውን የድርሻ መጠን፣ በይዞታው ላይ ያለውን መብት፣ ክልከላና ኃላፊነት በዝርዝር ለይቶ ለከተማ የመሬት መጠቀም መብት ሰጪ አካል የሰጠው ሰነድ መቅረብ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሠረት ማስረጃ ተሟልቶ ከቀረበ ወደ ከተማ የተካለለ የአርሶ አደር መሬት ይዞታ ይረጋገጣል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ሠነዱን የላከው አካል ባስረከበው ሠነድ ላይ በተጠቀሰው የመሬት ስፋትና በልኬት በተገኘው ስፋት መካከል ልዩነት

ከታየ፣ ይኸው ተገልጸ የመሬት ይዞታውን ሲያስተዳድር ለነበረው የገጠር የመሬት አስተዳደር አካል ውሳኔ እንዲሰጥበት የከተማው የመሬት ይዞታ መብት ሰጪ ተቋም መላክ ይኖርበታል፡፡

4. የከተማው የመሬት ይዞታ መብት ሰጪ ተቋም ወደ ከተማ የተካለለ የአርሶ አደር የመሬት ይዞታ መብትን አስመልክቶ የሚነሱ የሰነድ ማጣራት እና ማጣጣም ሥራዎችን በተመለከተ ጥያቄው በቀረበለት በአስር ቀናት ውስጥ ተገቢው ምላሽ መስጠት አለበት፡፡

11.<u>የጋራ ሕንጻ የመሬት ይዞታ ስለማጋገጥ</u>

የጋራ መኖሪያ ቤት ግንባታ የተካሄደበት ቁራሽ መሬት ሲረጋገጥ፡-

1. እያንዳንዱ ሰው ከአጠቃላይ የቦታው ስፋት ለቤቱ የሚደርሰው ተነጻጸሪ ድርሻ፤
2. እያንዳንዱ ሰው በጋራ ድርሻው ላይ ያለው መብት፣ ክልከላና ሃላፊነት፤
3. የጋራ መኖሪያ ቤቱ በህጋዊ ማህበር የሚተዳደር ከሆነ የጸደቀ የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብና ውስጠ ደንብ፤
4. አጠቃላይ የቦታው ስፋት እያንዳንዱ የቤት ባለቤት በድርሻው በሚደርሰው ይዞታ ላይ ያለው መብት፣ ክልከላና ሃላፊነት፤

መረጋገጥ አለበት፡፡

12.<u>ስለ ህብረተሰብ ተሳትፎ</u>

1. የይዞታ ማረጋገጥ ሥራዎች ከመጀመራቸው በፊት የከተማ ነዋሪ፣ የወጣቶች እና የሴቶች አደረጃጀቶችን በመጠቀም ስለከተማ መሬት ይዞታ ማረጋገጥ አስፈላጊነት እና ሂደት ውይይቶች በማካሄድ የጋራ መግባባት ላይ መደረስ ይኖርበታል፡፡
2. ከተሞች የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ሥራዎች በሚያከናውኑበት ወቅት ዓላማውን የማስተዋወቅ ሂደቱ፣ የቅሬታ አቀራረቡ እና የውሳኔ አሰጣጡ ላይ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራዎች መከናወን ይኖርባቸዋል፡፡
3. ለመሬት ይዞታ ማረጋገጥ የሚደረጉ የግንዛቤ መፍጠር ሥራዎች በተለዩ ቀጠናዎች እና ሠፈሮች በእቅድ ተይዘው መከናወን አለባቸው፡፡
4. ዝርዝሩ በመመሪያ የሚወሰን ሆኖ በስልታዊ ዘዴ የመሬት ይዞታ የማረጋገጥ ሥርዓት ለማከናወን ከይዞታ ማረጋገጫ ሠፈሩ የተመረጡ ሦስት ታዛቢዎች እንዲሳተፉ ይደረጋል፡፡

<u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>

## ስለ መሬት ይዞታ የይረጋገጥልኝ ጥያቄ

### 13. ስለ መሬት ይዞታ የይረጋገጥልኝ ጥያቄ ስለማቅረብ

1. ማንኛውም በመሬት ይዞታ የመጠቀም መብት ያለው ሰው የመሬት ይዞታ ይረጋገጥልኝ ጥያቄውን በራሱ ወይም በወኪሉ አማካኝነት ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ማቅረብ አለበት፡፡
2. የይረጋገጥልኝ ማመልከቻው የቀረበው በወኪል ከሆነ የውክልና ሥልጣን ማረጋገጫ ሰነድ ፎቶ ኮፒ እና ዋናውን ለማገናዘቢያ ማቅረብ አለበት፡፡
3. ጥያቄው የሚቀርብበት የመሬት ይዞታ የባለይዞታነት መብት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ባለድርሻዎች ካሉት የይረጋገጥልኝ ጥያቄው ቅጽ በሁሉም ባለድርሻዎች መሞላትና መፈረም አለበት፡፡
4. ማንኛውም በመሬት ይዞታው ላይ ጥቅም አለኝ የሚል ሰው መብቱን በተመለከተ የይረጋገጥልኝ ጥያቄ ማቅረብ አለበት፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የይረጋገጥልኝ ጥያቄ መቅረብ ሲገባው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ የመሬት ይዞታ ይረጋገጥልኝ ጥያቄ እንዳልቀረበበት ተመዝግቦ ከመሬት ይዞታ አስተዳደር በሚቀረበው በምሪት ወይም በሊዝ የመሬት ይዞታ መጠቀምያ መብት መረጃ መነሻ ይረጋገጣል፡፡
6. ከመሬት ይዞታ መብት ሰጪ ተቋም ማስረጃ የተሰጣቸው ይዞታዎች ሆነው ባለይዞታዎቹ አቅመ ደካማና አካል ጉዳተኛ በመሆናቸው የይረጋገጥልኝ ጥያቄ በአካል ቀርበው ካላቀረቡ ወይም ማቅረብ ያልቻሉ እንደሆነ የአካባቢው ታዛቢዎች በሚገኙበት ግለሰቦቹ ባሉበት ቦታ የይረጋገጥልኝ ጥያቄ ቅጽ እንዲሞሉ እና እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡

### 14. ስለ ማስረጃ አቀራረብ

1. ከመሬት ይዞታ መብት ሰጪ ተቋም ከሚገኘው የይዞታ መረጃ ውስጥ የሚገኙ የመብት፣ የክልከላና ኃላፊነት ማስረጃዎች ተለይተውና ትክክለኛነታቸው ተረጋግጦ ለመዝጋቢ ተቋም መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
2. ከይረጋገጥልኝ ጥያቄ ጋር መቅረብ የሚገባቸው ማስረጃዎች በመመሪያው ላይ በዝርዝር በሚገለጹት መሰረት መሆን አለበት፡፡

3. የይረጋገጥልኝ ማመልከቻ አቅራቢ ማመሳከር እንዲቻል የሰነዱን ቅጂ ከዋናው ጋር ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

15. <u>በአመልካቹ የቀረበ ሠነድ ስለማጣራት</u>

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 13(1) እና (2) ከሚቀርብ ጥያቄ ጋር የተያያዘው ማስረጃ ጊዜ ያላለፈበት፣ የሚነበብ እና ማህተሙ በግልጽ የሚታይ መሆኑ መጣራት ይኖርበታል፡፡
2. የመሬት ይዞታ ይረጋገጥልኝ ጥያቄ የሚስተናገደው የይረጋገጥልኝ ጥያቄው እንዲስተናገድ የሚያስችል ማስረጃ ከጥያቄው ጋር ስለመካተቱ ተጣርቶ እና ጉድለት ካለ አመልካቹ እንዲያሟላ ከተደረገ በኃላ ጥያቄው በቀረበበት ቅደም ተከተል መሠረት ይሆናል፡፡
3. የይዞታ አረጋጋጩ ሹም ከጥያቄ አቅራቢው ለቀረበለት በሰነድ የተደገፈ ጥያቄ ሰነዶቹን ስለመቀበሉ ለጥያቄ አቅራቢው ማስረጃ መስጠት ይኖርበታል፤ የሚሰጠው የማስረጃ ዓይነት በከተማ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ስታንዳርድ ይገለፃል፡፡
4. የመሬት ይዞታ ሰነድ በሚረጋገጥበት ወቅት ከሠፈሩ ነዋሪዎች መካከል በዚህ ደንብ በአንቀጽ 12(4) መሰረት የተወከሉ የህብረተሰቡ ተወካዮች በማጣራት ሂደት ስለመታዘባቸው በፊርማቸው ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

16. <u>ተቀባይነት ስለማይኖራቸው ሰነዶች</u>

የይዞታ አረጋጋጭ ሹሙ ከሚከተሉት ምክንያቶች አንዱ መኖሩን ሲያረጋግጥ የቀረበውን ሰነድ አልቀበልም ብሎ መመለስ አለበት፦

1. የይረጋገጥልኝ ጥያቄ አቅራቢው ያቀረበው ሰነድ የሐሰት ማስረጃ መሆኑ ከተረጋገጠ፤
2. ማስረጃው በግልጽ የማይነበብ ከሆነ፤
3. ማስረጃው ስርዝ ድልዝ ያለው ከሆነ፡፡

17. <u>ስለ ሕዝብ ማስታወቂያ አወጣጥ</u>

1. የክልል መንግስት በቅድሚያ የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ሥራ የሚጀመርባቸውን ከተሞች ዝርዝር ለሕዝብ ተደራሽ በሆኑ በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችና በሕዝብ ማስታወቂያ ያሳውቃል፡፡

2. የከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ የሚጀመርባቸውን አካባቢዎች እንዲሁም መዝጋቢው ተቋም በሚያዘጋጀው ቅደም ተከተል መሠረት የመሬት ይዞታ የማረጋገጡ ተግባር እንደሚፈጸም፣ የይዞታ ማረጋገጥ ምዝገባ ጥሪ ከመተላለፉ ከ15 ቀናት በፊት በሕዝብ ማስታወቂያ ይፋ ማድረግ አለበት፡፡
3. መዝጋቢ ተቋሙ ስለመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ሥራ መጀመር፣ የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ሥራ በሚሰራበት ሠፈሩ ውስጥ የሚለጠፍ ጥሪ ወረቀት እና የወሰን ማካለያ ማስታወቂያ በማስታወቂያ ሠሌዳ እና እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ዘዴዎችም ይገልፃል፡፡
4. በየቀጠናውና ሠፈሩ የሚወጣው የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ሥራ ማስታወቂያ ይዘት፣ የመሬት ይዞታ መብት ይረጋገጥልኝ ጥያቄ የሚቀርብበትን ቦታ፣ ሥራው የሚጀመርበትን ቀን፣ የማረጋገጥ ሥራው በይዞታነት በተያዘ ይዞታም ሆነ ባልተያዘ መሬት ላይ ሊቀርቡ ስለሚገባቸው የማስረጃ ዓይነቶች ያካተተ ሆኖ በመዝጋቢ ተቋሙ መገለጽ ይኖርበታል፤ ዝርዝር አፈፃፀሙ በመመሪያ ይገለጻል፡፡

## ክፍል ሦስት
## ስለሚረጋገጡ ጉዳዮች፣ ቅሬታ አቀራረብ እና የመሬት ይዞታ ማረጋገጥን ማጠናቀቅ
### ንዑስ ክፍል አንድ
### ስለሚረጋገጥ መብት፣ ክልከላና ኃላፊነት

#### 18. ስለሚረጋገጥ መብት

በአዋጁ አንቀጽ 29(1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፦

1. የይዞታ ባለመብት በመሬት የመጠቀም መብት ከሚሰጠው አካል ጋር ያደረገው ውል ካለ በውሉ ላይ የተጠቀሱት መብቶች፣ ክልከለላዎችና ኃላፊነቶች ይረጋገጣሉ፤
2. ሥልጣን ባለው አካል የተሰጠ የመሬት አጠቃቀም መብት፣ መያዣና ዕዳ እገዳ፣ የመተላለፊያ መንገድ፣ የመሬት አገልግሎት ዓይነት መቀየር፣ ታሪካዊ ቅርሶች እና በሌሎች የህግ አግባብ የተሰጡ ክልከላዎች ይረጋገጣሉ፡፡

#### 19. በመስክ ይዞታን ስለማረጋገጥ

1. ከባለይዞታው የቀረበው ማስረጃ የመሬት ይዞታ መብት ሰጪ ከሆነ ተቋም ከተገኘው ማስረጃ ጋር እና ከይዞታው ልኬት ጋር ልዩነት ያለው ከሆነ የመብት ሰጪው ተቋም የማጣራት ሥራ እንዲሰራበት ማስረጃው ተመላሽ ይደረጋል፡፡
2. የመስክ ሥራው በካዳስተር መሰረታዊ ካርታ መረጃ እና እንደአስፈላጊነቱ በመስክ ቅየሣ የሚከናወን ይሆናል፡፡
3. የቁራሽ መሬት ወሰንን ለማካለልና በመስክ ቅየሳ ሥራ በሚረጋገጥ ይዞታ ወሰን ውስጥ የሚገቡ ሁሉም ባለሙያዎች ማንነታቸውን የሚገልጽ የራሳቸውን መታወቂያና መለያ ዩኒፎርም መያዝና ሲጠየቁም መታወቂያ ካርዳቸውን ማሳየት አለባቸው፡፡

20.<u>ሳይረጋገጡ ስለሚቆዩ ይዞታዎች</u>

1. የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የከተማ መሬት ይዞታ ለጊዜው ሳይረጋገጥ ይቆያል፡-
   ሀ) በመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር ውስጥ የይዞታ ማረጋገጥ ስራ በህዝብ ማስታወቂያ ይፋ ከመደረጉ በፊት ሥልጣን ባለው አካል የተሰጠ የማገጃ ትዕዛዝ ካለና ይኸው ትዕዛዝ ስለመነሳቱ ማስረጃ ካልቀረበ በእገዳ ላይ ያለው የመሬት ይዞታ ለጊዜው ሳይረጋገጥ ይቆያል፣ ሆኖም የወሰን መረጃው ይሰበስባል፤
   ለ) የመሬት ይዞታ መብት ሰጪ ተቋም በላከው የይዞታ ሰነድ እና የመሬት ይዞታ ባለመብት ነኝ ባዩ ባቀረበው ሰነድ መካከል ልዩነት ሲፈጠር፣ እንዲሁም በሰነዶቹ እና በቁራሽ መሬት ልኬት መካከል በታየው ልዩነት ላይ መብት ሰጪ ተቋሙ ውሳኔውን መግለጹ አስፈላጊ ሆኖ ጥያቄ ቀርቦለት ለመዝጋቢ ተቋሙ እስኪገልጽ ድረስ ይኸው ቁራሽ መሬት ሳይረጋገጥ ይቆያል፤ በተጨማሪ ይህ ሁኔታ ለዚህ ዓላማ በተዘጋጀ የመሬት ይዞታ ክርክር መዝገብ ውስጥ እንዲመዘገብ ይደረጋል፤
   ሐ) የመሬት ይዞታ ባለመብት ነኝ ባይ የባለመብትነት ማስረጃ አቅርቦ ነገር ግን የመሬት ይዞታ መብት ሰጪ ተቋም ይህን የሚያስረዳ ነባር ሰነድ ለመዝጋቢው ተቋም ያላስረከበ ከሆነ፣ ባለመብት ነኝ ባዩ ያቀረበው ሰነድ ለመብት ሰጪ ተቋም ቀርቦ ተቋሙ ውሳኔውን ለመዝጋቢ ተቋም እስኪያሳውቅ ድረስ የመሬት ይዞታው ሳይረጋገጥ ይቆያል፤

መ) ወደ ከተማ የተጠቃለለን የገጠር መሬት በሚመለከት መሬቱን ያስተዳድር የነበረው አካል በላከው ሰነድ ላይ በተገለጸው የመሬት ስፋትና በመስክ ልኬት በተገኘው የመሬት ስፋት መካከል ልዩነት ከተገኘ፣ በተፈጠረው የመሬት ስፋት ልዩነቱ ላይ መብት ሰጪው አካል ውሳኔ እስኪሰጥበት ድረስ የመሬት ይዞታው ሳይረጋገጥ ይቆያል፤

2. ሳይረጋገጥ እንዲቆይ የተደረገ ይዞታን አስመልክቶ የሚመዘገብበት የመሬት ይዞታ ክርክር መዝገብ ይዘጋጃል፤ ያልተረጋገጠ ይዞታ መኖር ግን የአጎራባች ይዞታዎችን እንዳይረጋገጡ ምክንያት መሆን አይችልም፡፡

21.<u>የመሬት ይዞታ ስም ዝውውርን ስለማቆየት</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 13(1) መሠረት በአንድ ሠፈር ውስጥ ይዞታን የማረጋገጥ ሂደት መጠናቀቁ ይፋ እስከሚደረግ ድረስ በዚያ ሠፈር ውስጥ ያሉ ማናቸውም የከተማ መሬት ይዞታ ስም ዝውውር ሳይተገበር የሚቆይበት ጊዜ ከአምስት ወር ያልበለጠ ሆኖ እንደ ነባራዊ ሁኔታው በክልሉ ወይም በከተማ አስተዳደሩ በኩል ወደ ሥራ ከመገባቱ በፊት መወሰን እና ለህዝብ ይፋ መደረግ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተገለጸውን የጊዜ ገደብ ለመጠበቅ እንዲያስችል የይዞታ ማረጋገጫ ሠፈሩን የመሬት አቀማመጥ፣ አሰፋፈር እና የይዞታ ወሰን ባህሪ ከግምት ውስጥ ያስገባ ተገቢው ቅድመ ዝግጅት በመዝጋቢው ተቋም መደረግ አለበት፡፡

## <u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለቅሬታና ይግባኝ አቀራረብ እና አወሳሰን</u>

22.<u>ስለከተማ መሬት ይዞታ ማረጋገጥ ቅሬታ ሰሚ ጉባዔ</u>

1. በከተማ መሬት ማረጋገጥ ውሳኔ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን መርምሮ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን የሚኖረው የከተማ መሬት ይዞታ ማረጋገጥ ቅሬታ ሰሚ ጉባዔ (ከዚህ በኋላ “ጉባዔ” እየተባለ የሚጠራ) በቀበሌ ወይም በቀጠና አስተዳደር ደረጃ ይቋቋማል፡፡
2. የጉባዔው አባላት ከእያንዳንዱ ሠፈር የሚወከሉ አምስት እና ሶስት የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር አካላት ድምር ይሆናል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ከየሤፈሮቹ የሚወከሉ አባላት እንደ ይዞታ ማረጋገጫ ሠፈሮቹ ብዛት በነዋሪ ህብረተሰብ ከባለይዞታዎች የሚወከሉ ይሆናል፡፡
4. የጉባዔው አባላት መመልመያ መመዘኛ እና አሰያየም በመመሪያ ይወሰናል፡፡
5. የቀጠናው ጉባዔ የሥራ ቦታ በዝቅተኛው የአስተዳደር መዋቅር ጽሕፈት ቤት ውስጥ አስፈላጊ በሆነ መጠን ይደራጃል፡፡

23.<u>የጉባዔው ሥልጣንና ኃላፊነት</u>

1. ጉባዔው የሚከተሉት ሥልጣንና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-
   ሀ) በጽሁፍ የሚቀርቡለትን ቅሬታዎችና ማስረጃዎች ተቀብሎ በመመርመር በ15 ቀናት ውስጥ ውሳኔ የመስጠት፤
   ለ) ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት አስፈላጊውን ማስረጃ ከቅሬታ አቅራቢ፣ ከመሬት ይዞታ አረጋጋጭ ሹም እና ከሚመለከተው አካል እንዲቀርብለት የማድረግ፤
   ሐ) በቀረቡለት ማስረጃዎች ላይ ተመስርቶ ውሳኔ የመስጠት፤
   መ) ውሳኔውን ለቅሬታ አቅራቢው እና ለመሬት ይዞታ አረጋጋጭ ሹም እንዲሁም ለሚመለከተው አካል በጽሁፍ የማሳወቅ፡፡
2. ጉባዔው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በ15 ቀናት ውሳኔ ካልሰጠ ቅሬታ አቅራቢው ቅሬታውን ሥልጣን ላለው የከተማ ነክ ፍርድ ቤት ወይም ለመደበኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡
3. መዝጋቢ ተቋሙ በ15 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ያልሰጡ የጉባዔ አባላት ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡
4. በህዝብ የተመረጠ የጉባዔ አባል የመንግስት፣ የግል፣ የማህበራት ወይም መንግስታዊ ያልሆነ ተቋም ሰራተኛ ከሆነ ጉባዔው ሥራውን እስኪያጠናቅቅ ድረስ ጥቅማ ጥቅሙ ተጠብቆ ልዩ ፈቃድ የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡

24.<u>ስለይግባኝ አቀራረብና አወሳሰን</u>

1. ጉባዔው በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ሰው ውሳኔው በደረሰው በ15 ቀናት ውስጥ በአዋጁ አንቀጽ 17(3) መሠረት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፤ በዚህ ጊዜ ውስጥ ይግባኙን ካላቀረበ ግን ውሳኔው ተቀባይነት እንዳገኘ ይቆጠራል፡፡
2. ይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤት ይግባኙን መርምሮ ውሳኔውን ለይግባኝ ባይና ለመዝጋቢው ተቋም እንዲደርስ ያደርጋል፡፡ በዚህ ይግባኝ ምክንያት በአንድ

የይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር ውስጥ ያለ የይዞታ ማረጋገጥ ሂደት አይታገድም፣ ነገር ግን የመሬት ይዞታ የማረጋገጥ ሂደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ የፍርድ ቤቱ ውሳኔ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ይግባኝ ባይ ውሳኔው እንደደረሰው ለሚቀጥለው ደረጃ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኙን መርምሮ ውሳኔውን ለይግባኝ ባይ እና ለመዝጋቢ ተቋም ባሳወቀው መሰረት መዝጋቢው ተቋም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሦስት

## ስለመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ሥራ መጠናቀቅና ውጤት ማስተላለፍ

### 25.ስለመሬት ይዞታ ማረጋገጫ መዝገብ

1. የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ መዝገብ ለህጋዊ ካዳስተር መብት ምዝገባ መነሻ ሆኖ የመሬት ይዞታ መብትን አስመልክቶ የመብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ጥያቄ ሲቀርብ፣ ስልታዊ የመሬት ይዞታ ማረጋገጥን ተከትሎ ለመጀመሪያ የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባ ዋነኛ የመረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፡፡
2. ዝርዝሩ በመመሪያ የሚወሰን ሆኖ የመሬት ይዞታ ማረጋገረጫ መዝገብ የሚከተሉትን ዋና ዋና ዝርዝር መረጃዎችን ይይዛል፡-

   ሀ) የባለይዞታው ዝርዝር መረጃ፣

   ለ) የቁራሽ መሬት ዝርዝር መረጃ እና የመሬቱ አገልግሎት፣

   ሐ) በመሬት ይዞታ ላይ ስላለው መብት፣ ክልከላ እና ኃላፊነት፣

   መ) ከመብት ሰጪና ከባለይዞታው የቀረቡ ሰነዶች፡፡
3. ዝርዝሩ በመመሪያ የሚወሰን ሆኖ በወሰን አካላይ የሚሰበሰብና የሚሞላ መረጃ የሚከተሉትን ዋና ዋና መረጃዎች ይይዛል፡-

   ሀ) የቁራሽ መሬት የሚገኝበት አድራሻ፣

   ለ) ስለወሰኑ ዓይነት (አጥሩ በግንብ፣ በእንጨት፣ በእፅዋት፣ በተክል ድንጋይ፣ በድንጋይ ካብ ወይም ምንም የሌለው) ስለመሆኑ፣

   ሐ) የወሰን ስፋትና ርዝመት ማመላከቻ መስፈርት፣

   መ) የመሬት ይዞታ አገልግሎት፡፡

### 26.ስለማህደር አከፋፈትና አጠባበቅ

1. ማንኛውም የመሬት ይዞታ የተረጋገጠለት ሰው በከተማ ጣቢያ እና በቁራሽ መሬቱ ልዩ ኮድ መሠረት የይዞታ ማህደር እንዲከፈትለት መደረግ አለበት፡፡
2. የሚከፈተው ማህደር በወረቀት እና በዲጂታል የመረጃ ሥርዓት አደረጃጀት መሠረት መሆን አለበት፡፡
3. በማረጋገጥ ሂደት ውስጥ የመሬት ይዞታው የሚከፈል ከሆነ ወይም በመሬት ይዞታ መብት ሰጪ ተቋም ውሳኔ የሚቀላቀል ከሆነ ማህደሩም በቁራሽ መሬቱ ልዩ ኮድ መሰረት እንዲደራጅ መደረግ ይኖርበታል፡፡
4. ለእያንዳንዱ ቁራሽ መሬት የተከፈተ የወረቀት ማህደር ለብልሽት ወይም ለእሳት አደጋ በማይጋለጥበት መልኩ በአስተማማኝ ቦታ እንዲቀመጥ መደረግ አለበት፡፡
5. በይዞታ አረጋጋጭ ሹሙ ካልተፈቀደ በስተቀር ማንኛውም ማህደር ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ የለበትም፡፡
6. ማንኛውም ማህደር የራሱ የሆነ የመዝገብ መለያ ኮድ እንዲኖረው መደረግ አለበት፡፡
7. ማንኛውም ማህደር የማህደር ሥራ ለሚያከናውኑ ሠራተኞች ግልጽና ለክትትል በሚያመች መልኩ መደራጀት እና መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

27.<u>የመሬት ይዞታ መብት የማረጋገጥ ሥራን ስለማጠናቀቅ</u>

1. የመሬት ይዞታ መብት እና ወሰን ማረጋገጥ አስመልክቶ ችግር ሳይኖርባቸው የተረጋገጡ የመሬት ይዞታዎች በአዋጁ አንቀጽ 18(1) እና (2) በተደነገገው መሠረት የማረጋገጥ ሥራ መረጃዎች በግልጽ ለህዝብ ይፋ መደረግ አለባቸው፡፡
2. የመሬት ይዞታ መብት ወይም ወሰን የማረጋገጥ ችግር ያለበት የመሬት ይዞታ ያለበትን ችግር እና በተከታታይ የተሰጠ ውሳኔ ወይም የውሳኔ ለውጥ በተመለከተ በህዝብ ማስታወቂያ ይፋ መደረግ አለበት፡፡
3. የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ሥራ ላይ ቅሬታ ቀርቦ የቀጠና መሬት ይዞታ ማረጋገጥ ቅሬታ ሰሚ ጉባዔው ቅሬታ በቀረበበት ጉዳይ ላይ የሰጠውን ውሳኔ ሲያሳውቅ፣ የመሬት ይዞታ የማረጋገጡ ማጠቃለያ በጉባዔው ውሳኔ መሠረት መፈጸም አለበት፡፡
4. መዝጋቢው ተቋም ሰፊ ስርጭት ባላቸው የመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች ወይም የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የከተማ መሬት ይዞታ ማረጋገጥ ሥራው መጠናቀቁን ለህዝብ ማሳወቅ አለበት፡፡

28.**በመሬት ይዞታ መብት የተረጋገጠን ሰነድ ስለማስተላለፍ**

1. የአንድ የይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ሥራ እንደተጠናቀቀ መረጃው በወረቀት እና በዲጂታል መረጃ ሰነድነት ተለውጦ ለምዝገባ እንዲተላለፍ መደረግ አለበት፡፡
2. የይዞታ አረጋጋጭ ሹም ሰነዱን ለምዝገባ ተግባር ለተቋሙ ዋና መሥሪያ ቤት ከማስተላለፉ በፊት ሰነዱ መሟላቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡
3. የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር የመሬት ማረጋገጥ መረጃ ዋጋ የሚኖረው የቀጠናው አረጋጋጭ ሹም ሙሉ ስም፣ ፊርማ እና ማህተም ሲያርፍበት ነው፡፡

29.**የከተማ መሬት ይዞታ ማረጋገጥ አማካሪ ኮሚሽን**

1. የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ አማካሪ ኮሚሽን (ከዚህ በኋላ "ኮሚሽን" እየተባለ የሚጠራ) አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት የከተማ አስተዳደር የመዋቅር እርከን እንዲቋቋም ይደረጋል፡፡ በኮሚሽኑ ውስጥ የሚካተቱት ቁልፍ ባለድርሻ አካላት ሆነው እንደ ከተሞቹ ተጨባጭ ሁኔታ በክልሉ መንግስት የሚወሰኑ ይሆናል፡፡
2. ኮሚሽኑ በመንግስት መዋቅር ተዋረድ በፌደራል፣ በክልል፣ በዞን፣ በከተማ እና በወረዳ አስተዳደር ከፍተኛ አመራር ይመራል፡፡ በክልሉ በሚቀረፀው አግባብ የሚጠበቅበትን የከተማ መሬት ይዞታ ማረጋገጥ ተልዕኮ በየደረጃው የማሳካት ድጋፍ ይሰጣል፡፡
3. የኮሚሽኑ አባላት በየደረጃው ለሚፈጽሙት ድጋፍ፣ የሥራ ግምገማ እና ስብሰባዎች በክልሉ ወይም በከተማ አስተዳደር በተደነገገው መሠረት የስብሰባ አበል ከመዝጋቢው ተቋም ያገኛሉ፡፡
4. በከተማ እና በወረዳ ደረጃ ያለ ኮሚሽን በይዞታ ማረጋገጫ ቀጠናና ሠፈር ውስጥ የሚገኙ ባለይዞታዎች ይዞታቸው እንዲረጋገጥ እንዲያስደርጉ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ቅስቀሳ እንዲከናወን ያስተባብራል፡፡
5. በከተማ እና በወረዳ ደረጃ ያለ ኮሚሽን በመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ቀጠና እና ሠፈር የመሬት ይዞታ አረጋጋጭ አካል የድጋፍ ጥያቄ ሲቀርብለት በየደረጃው ባለው አወቃቀሩ ድጋፍ ይሰጣል፡፡
6. ባለድርሻ አካላት የማስተባበር ድጋፍ ሲጠይቁ ኮሚሽኑ የማስተባበሩን ሥራ ይመራል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፡፡

**ክፍል አራት**

## ስለከተማ መሬት ይዞታ መብት ምዝገባ

## ንዑስ ክፍል አንድ

## የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባ ማመልከቻ አቀራረብ

30.የመሬት ይዞታ መብት ለማስመዝገብ የማመልከቻ አቀራረብ

1. በአዋጁ አንቀጽ 27 መሠረት ማንኛውም በመሬት ይዞታ ላይ ጥቅም አለኝ የሚል ሰው ይዞታውን ለማስመዝገብ በራሱ ወይም በህጋዊ ወኪሉ አማካኝነት ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. በመንግስት አስተዳደር ሥር የሚገኙ የመንግስት ሕንፃ ያረፈባቸው መሬቶች፣ መንገዶች፣ ድልድዮች፣ ለአካባቢ ጥበቃ የተከለሉ ጥብቅ ቦታዎች፣ ተፋሰሶች፣ በመንግስት የተዘጋጁ የኢንዱስትሪ መንደሮች፣ የሚለሙና የለሙ በከተማው አስተዳደር ለሊዝ የሚቀርቡ መሬቶች የመሳሰሉትን ለማስመዝገብ በመንግስት ለሥራው ኃላፊነት በተሰጠው አካል አማካኝነት ማመልከቻ መቅረብ አለበት፡፡
3. ሁለትና ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች የጋራ ይዞታቸውን ለማስመዝገብ ሲፈልጉ በሁሉም ባለይዞታዎች ወይም በጋራ ወኪላቸው አማካኝነት ማመልከቻ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

31.የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባ ማመልከቻ ይዘት

1. የመሬት ይዞታ መብት ለማስመዝገብ የሚከተሉት መረጃዎች መዝጋቢው ተቋም ባዘጋጀው ቅጽ መሞላትና ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡-
   ሀ) የአመልካቹን ሙሉ ስምና አድራሻ፤
   ለ) የሚመዘገበው ቁራሽ መሬት ልዩ መለያ ኮድ፤
   ሐ) በከተማ መሬት ይዞታው ለመጠቀም ከመብት ሰጪው አካል የተሰጠ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ፣ የሊዝ የምስክር ወረቀት፣ የነባር ይዞታ ማስረጃ ወይም የኪራይ ውል፤
   መ) የመሬት ይዞታውና የቀረቡት ሰነዶች መረጋገጣቸውን የሚያሳይ ከይዞታ አረጋጋጭ ሹሙ የተሰጠ መተማመኛ ቅጽ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የምዝገባ ማመልከቻን የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው በመዝጋቢው ተቋም የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ማመልከቻውን ማቅረብ አለበት፡፡

32.የሰነዶች አቀራረብ

በዚህ ደንብ በአንቀጽ 31 መሠረት ለመሬት ይዞታ ምዝገባ የሚቀርቡ ማመልከቻዎች እንደሁኔታው ቢያንስ ከሚከተሉት ደጋፊ ማስረጃዎች ጋር ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡-

1. የምዝገባ ማመልከቻው የቀረበው በወኪል ከሆነ ህጋዊ የውክልና ማስረጃ፤
2. የሚመዘገበው ውል ወይም ሰነድ ከሆነ የዚሁ ውል እና ሰነድ ከዋናው ጋር የተመሳከረ ኮፒ፤
3. እንዲመዘገብለት የቀረበው ጥያቄ የመሬት ይዞታውን በተመለከተ ከፍርድ ቤት የተሰጠው ትዕዛዝ ወይም ፍርድ ከሆነ የትዕዛዙ ወይም የፍርዱ ዋናው ወይም ትክክለኛ ግልባጩ፣
4. ከማመልከቻው ጋር አባሪ ሆኖ የሚቀርብ ማንኛውም ሰነድ ከከተማው ሥራ ቋንቋ ውጪ የተዘጋጀ ሰነድ ሲሆን በህጋዊ አካል የተረጋገጠ ትርጉም፣
5. ለምዝገባው ሊጠቅሙ ይችላሉ ተብለው የሚታሰቡ ሌሎች ሰነዶች፡፡

33.<u>የምዝገባ ማመልከቻን ስለማጣራት</u>

1. መዝጋቢው ተቋም ለምዝገባ የቀረበ ማመልከቻ በተገቢው ቅጽ መሞላቱንና ደጋፊ ማስረጃዎች የተያያዙ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡
2. ለምዝገባ የቀረበ ማመልከቻ የሚጣራው እንደአመጣጡ ቅደም ተከተል ይሆናል፡፡
3. ለምዝገባ የቀረበ ማመልከቻ በመሬት ይዞታ ላይ ያለን መብት፣ ክልከላና ኃላፊነት በግልጽ የሚያመላክት መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡

34.<u>ተቀባይነት የሌላቸው ሰነዶች</u>

1. መዝጋቢው አካል ለምዝገባ ከቀረበው ማመልከቻ ጋር ተያይዞ የቀረበው ደጋፊ ሰነድ ወይም ማስረጃ፡-
   ሀ) የአመልካቹን የመሬት ይዞታ ተጠቃሚነት መብት በግልጽ በማያሻማ ሁኔታ የማያሳይ ወይም የማያረጋግጥ፤
   ለ) እርስ በእርሱ የሚቃረን ወይም የተዛባ፤ ወይም
   ሐ) ህጋዊነቱ በግልጽ አጠራጣሪ ወይም ጊዜ ያለፈበት፤

   ሲሆን ማመልከቻውን ተቀባይነት የለውም ብሎ ይመልሰዋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለምዝገባው የቀረበ ማመልከቻ ብቁ አይደለም ተብሎ ሲመለስ ለአመልካቹ በጽሁፍ ምክንያቱ መገለጽ አለበት፡፡

35.<u>መደበኛ አድራሻ ስለመምረጥ</u>

1. ለምዝገባና ከምዝገባ ጋር ተያይዘው ለሚነሱ ማናቸውም ጉዳዮች ሲባል የአንድ ሰው መደበኛ አድራሻ በስሙ የተመዘገበው የመሬት ይዞታ ያለበት ቦታ ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተጠቀሰው በተለየ ሁኔታ አንድ ሰው በከተማ ውስጥ በስሙ የተመዘገበው የመሬት ይዞታ ከአንድ በላይ በሚሆንበት ጊዜ የባለይዞታው መደበኛ አድራሻ የምዝገባ አገልግሎቱ ማመልከቻ የተጠየቀበት ቁራሽ መሬት ያለበት ይዞታ ላይ ያለ የማይንቀሳቀስ ንብረት የተሰጠው አድራሻ መደበኛ አድራሻው ሆኖ ይቆጠራል፡፡
3. ኤሌክትሮኒክስ አድራሻ ካለ በዚህ አድራሻ መረጃ ይላካል፣ መረጃው ለባለመብቱ መድረሱ ከተረጋገጠ ይህ አድራሻ እንደ ህጋዊ አድራሻ ይቆጠራል፡፡

<u>**ንዑስ ክፍል ሁለት**</u>

<u>**ስለምዝገባ፣ ስለሚመዘገቡ መብቶች፣ ግዴታዎች እና ኃላፊነቶች**</u>

## 36.<u>የምዝገባ መርሆዎች</u>

1. የማንኛውም ሰው ግልጽ የሆነ የመሬት ይዞታ መብት እና ይህንኑ መብት ተከትሎ የሚመጣው ክልከላ እና ኃላፊነት ይመዘግባል፡፡
2. የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባ የሚካሄደው በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል መብት ለተፈጠረላቸው የመሬት ይዞታዎች ነው፡፡
3. ማንኛውም የመሬት ይዞታ ምዝገባ ተቃራኒ ማስረጃ እስካልቀረበበት ድረስ ለይዞታው ተጠቃሚነት መብትና በይዞታው ላይ ለተገነባው የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት የመጨረሻ ማስረጃ ሆኖ ያገለግላል፡፡
4. ማንኛውም በመሬት ይዞታ ላይ ያለ መብት፣ ክልከላ እና ኃላፊነት ወይም ይህንኑ የሚነካ ድርድር መቃወሚያ ሊሆን የሚችለው ከተመዘገበ ብቻ ነው፡፡
5. ማንም ሰው በመሬት ይዞታ መብት መዝገብ ውስጥ የተመዘገበውን መብት ክልከላና ኃላፊነት አላውቅም በማለት ተጠቃሚ መሆን አይችልም፤ ሆኖም ይህ ያለማወቅ የተከሰተው በመዝጋቢው ተቋም ስህተት ወይም ጥፋት ከሆነ የመዝጋቢው ተቋም ኃላፊነት የተጠበቀ ነው፡፡
6. ማንኛውም በመሬት ይዞታ ላይ ያለ መብት፣ ክልከላ እና ኃላፊነት የሚመዘገበው የይዞታ ማረጋገጥ ሂደትን ሲያልፍ ነው፡፡

## 37.<u>የመሬት ይዞታ ተጠቃሚን ስለመመዝገብ</u>

የመሬት ይዞታ በሚመዘገብበት ጊዜ፡-

1. የግለሰብ ይዞታ ከሆነ በመሬት ይዞታ ተጠቃሚው ግለሰብ ስም፤
2. የጋራ ይዞታ ከሆነ በመሬት ይዞታው ተጠቃሚዎች ስም፤
3. በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ወይም ማህበር ከሆነ በህግ የሰውነት መብት በተሰጠው ድርጅት ሙሉ ስም፤
4. ለሕዝብ አገልግሎት የሚሰጡ የመሬት ይዞታዎች የሕዝብ የመሬት ይዞታ ተብለው በወቅቱ በስራ ላይ ባለው የከተማው የመሬት አጠቃቀም ፕላን መሰረት እንዲያስተዳድር ሥልጣን በተሰጠው የከተማ አስተዳደር ስም፤

በሚመለከተው ተቋም በኩል መመዝገብ ይኖርባቸዋል፡፡

38.<u>**የሚመዘገቡ መብቶች፣ ክልከላዎች እና ኃላፊነቶች**</u>

1. የከተማ መሬትን በሊዝ ወይም በነባር ይዞታ የመጠቀም መብትን እንዲሰጥ በህግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተሰጠ የመሬት ይዞታ ላይ ያለ ማንኛውም የመጠቀም መብት፣ ክልከላ እና ኃላፊነት ይመዘገባል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሠረት በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የተሰጠ የመሬት የመጠቀም መብት፣ ክልከላ እና ኃላፊነት ጋር በተያያዘ የውል ሰነድ እና የእግድ ጥያቄ ለማስመዝገብ የቀረበ ማመልከቻ ተቀባይነት ካገኘ የምዝገባ አካል ሆኖ በሁለት ወገኖች መካከል የተደረገ ህጋዊ እና የተፈጸመ የመሬት ይዞታ ውል እንደሆነ ይቆጠራል፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ በከተማ የመሬት ይዞታ መብት ሰጪ ተቋምና በማንኛውም ሰው መካከል የተደረገው የሊዝ ወይም የኪራይ ውል የምዝገባው ዋና መነሻ ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን ለወረቀትና ለዲጂታል መዝገብና ለአገልግሎት አሰጣጥ ሲባል ከውሉ ላይ የተመለከተ መብት፣ ክልከላና ኃላፊነት ይመዘገባል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የሚመዘገበው የመብት ማስተላለፍ በገደብ ወይም ያለገደብ ስለመሆኑ፣ ክልከላን በተመለከተ ዋስትና እና በዕዳ

ምክንያት እገዳ ስለመኖሩ፣ በኃላፊነት የሊዝ ክፍያና ቦታውን ለተፈቀደለት አገልግሎት መዋልን የሚመለከቱት ዝርዝሮች ይመዘገባሉ፡፡

39. <u>በሊዝ የተያዙ የመሬት ይዞታዎች ምዝገባ</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 30(1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሊዝ ሥርዓት መሠረት በከተማ መሬት የመጠቀም መብት ሰጪ አካል ተፈቅደው በሊዝ እንዲስተናገዱ ለተደረጉ ይዞታዎች የሚከተሉት መረጃዎች እየተረጋገጡ መመዝገብ ይኖርባቸዋል፦
   ሀ) የሊዝ ባለይዞታው ሙሉ ስም፤
   ለ) የሊዝ ቦታው ስፋትና አድራሻ፤
   ሐ) የሊዝ ቦታው አገልገሎት ዓይነት፣ ደረጃ፣ የከተማ ጣቢያ እና የቁራሽ መሬት ልዩ መለያ ኮድ፤
   መ) የቦታው ጠቅላላ የሊዝ ዋጋና በቅድሚያ የተከፈለውን መጠን፤
   ሠ) በየዓመቱ የሚፈፀመውን የሊዝ ክፍያመጠን፤
   ረ) የሊዝ ይዞታው ፀንቶ የሚቆይበትን ዘመን፡፡
2. በዚህ ደንብ በአንቀጽ 38(3) በተደነገገው መሰረት በከተማ መሬት የመጠቀም መብት ሰጪ አካል እና በመሬት ይዞታ ተጠቃሚው መካከል በተደረገው ውል ላይ የተዘረዘሩት መብት፣ ክልከላ እና ኃላፊነት መመዝገብ አለባቸው፡፡
3. በከተማ መሬት የመጠቀም መብት ሰጪውና በመሬት ይዞታ ተጠቃሚው መካከል የተደረገው የሊዝ ውል ሰነድ ከባለይዞታው ማህደር ጋር እንዲያያዝ ተደርጎ በመዝገብ ላይ ውሉ የተመዘገበበት ቀን እና ዓመተ ምህረት ይመዘገባል፡፡

40. <u>ነባር የመሬት ይዞታ የመጠቀም መብት ምዝገባ</u>

1. በመሬት የመጠቀም መብት እንዲሰጥ ሥልጣን በተሰጠው አግባብ ባለው አካል ፈቃድ መብት ተሰጥቶ በነባር ይዞታ ሥሪት የሚተዳደር መሬት ሲሆን የመሬት ይዞታዎች የሚከተሉት መረጃዎች ተረጋግጠው መመዝገብ ይኖርባቸዋል፡-
   ሀ) የመሬት ይዞታው ተጠቃሚ ሙሉ ስም፤
   ለ) የቦታው ስፋትና አድራሻ፤
   ሐ) የቦታው የአገልግሎት ዓይነት፣ ደረጃ፣ የከተማ ጣቢያ እና የቁራሽ መሬት ልዩ መለያ ኮድ፤
   መ) ዓመታዊ የኪራይ ክፍያ መጠን፡፡

2. መብት ሰጪ ተቋም የነባር መሬት ይዞታ ተጠቃሚዎች ሊኖራቸው የሚገባውን መብት፣ ክልከላ እና ኃላፊነት ወስኖ በሚልከው የውል ሰነድ ወይም ለዚሁ ተግባር ተብሎ በሚወጣ መመሪያ ላይ የሚገለጽ መብት፣ ክልከላ እና ኃላፊነት ተረጋግጦ ይመዘገባል፡፡

41.**<u>ለኢንዱስትሪ ዞን የለማ መሬት ይዞታ የሰብ ሊዝ ምዝገባ</u>**

1. ለኢንዱስትሪ ዞን የለማ መሬት ይዞታ ባለመብት መንግስት በሚወስነው መሰረት ከመሬት ይዞታው ከፊሉን ወይም በሙሉ፣ ለከፊል የሊዝ ዘመን ወይም ለአጠቃላዩ የሊዝ ዘመን ለሦስተኛ ወገን በሰብ-ሊዝ ያስተላለፈ እንደሆነ የሚከተሉት መረጃዎች ይመዘገባሉ፡-

   ሀ) ቁራሽ መሬት በሰብ-ሊዝ የተፈቀደለት ሰው ሙሉ ስም፤

   ለ) የይዞታ ስፋት እና አድራሻ፤

   ሐ/ የይዞታው አገልግሎት ዓይነት፣ ደረጃ፣ የከተማ ባቢያ እና የቁራሽ መሬት ልዩ መለያ ኮድ፤

   መ/ የይዞታውን ጠቅላላ የሰብ-ሊዝ ዋጋና የተከፈለውን የሰብ-ሊዝ መጠን፤

   ሠ/ የሰብ-ሊዝ ይዞታው ፀንቶ የሚቆይበትን ዘመን፡፡

2. ለኢንዱስትሪ ዞን የለማ መሬት ይዞታ በሰብ-ሊዝ የተላለፈለትና መብቱን አስመዝግቦ ሰርተፍኬት ያገኘ ማንኛውም ሰው ይህን መብቱን ለሌላ ሰው የማስተላለፍ መብት አይኖረውም፤ ነገር ግን ውል ማቋረጥ በፈለገ ጊዜ የኢንዱስትሪ ዞኑን ካለማው ሰው ጋር በገባው ውል መሰረት ያገኘውን የይዞ ታመብት ለመዝጋቢው ተቋም ተመላሽ ያደርጋል፡፡

42.**<u>የጋራ ሕንፃ ቤቶች የተገነቡባቸው የመሬት ይዞታዎች ምዝገባ</u>**

የጋራ ሕንፃ ቤቶች የተገነቡባቸው የመሬት ይዞታዎች ሲመዘገቡ የሚከተሉት መረጃዎች ተረጋግጠው መመዝገብ አለባቸው፡-

1. እያንዳንዱ የጋራ ሕንፃ ቤት ባለቤት ከአጠቃላይ የይዞታ ስፋት የሚደርሰው ተነፃፃሪ ድርሻ፤
2. አግባብ ባለው ህግ መሠረት የጋራ ሕንጻ ማህበር የተመሠረተ ከሆነ የፀደቀ የማህበሩ መመስረቻ ጽሑፍ እና መተዳደሪያ ደንብ እንዲሁም የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ያስቀመጣቸው ክልከላዎች እና ኃላፊነቶች፤

3. ከአጠቃላይ የይዞታው ስፋት እያንዳንዱ የቤት ባለቤት በሚደርሰው ድርሻ ይዞታ ላይ ያለው መብት፣ ክልከላ እና ኃላፊነት፡፡

43.<u>ከተማ ክልል የሚገኝ የአርሶ አደር መሬት ምዝገባ</u>

በከተማ ክልል የተካለለ የአርሶ አደር መሬት ይዞታ ሲመዘገብ የሚከተሉት መረጃዎች ተረጋግጠው መመዝገብ አለባቸው፡-

1. የቁራሽ መሬት ይዞታው ባለመብትና ተጠቃሚ አርሶ አደር ሙሉ ስም፤
2. የቁራሽ መሬቱ ስፋትና አድራሻ፤
3. የቁራሽ መሬት ይዞታው አገልግሎት ዓይነት፣ የቁራሽ መሬቱ ልዩ መለያ ኮድ፤
4. መሬቱን ሲያስተዳድር ከነበረው የገጠር ወይም የከተማ መሬት አስተዳደር አካል የተሰጠው መብት፣ ክልከላ እና ኃላፊነት፡፡

44.<u>የመሬት ይዞታ ተጠቃሚነት መብት ያልተፈጠረበት ይዞታ ምዝገባ</u>

1. የመሬት ይዞታ ተጠቃሚነት መብት ያልተፈጠረበት ይዞታ በመዝጋቢው አካል ተረጋግጦ የከተማን መሬት ለማስተዳደር ወይም ለማልማት ሥልጣን በተሰጠው አካልማመልከቻ ሲቀርብ ይዞታው በስሙ ይመዘገባል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የይመዝገብልኝ ማመልከቻ የከተማውን መሬት ለማስተዳደር ወይም ለማልማት ሥልጣን በተሰጠው አካል ሲቀርብ የማይንቀሳቀስ ንብረት ያላረፈበት እና ክፍት መሬት መሆኑ ተረጋግጦ ሲቀርብ የሚከተሉትን መረጃዎች እንዲይዝ በማድረግ በስሙ ይመዘገባል፡-

   ሀ) የይዞታውን ስፋትና አድራሻ፤

   ለ) የከተማ ጣቢያ እና የቁራሽ መሬቱ ልዩ መለያ ኮድ፤

   ሐ) የይዞታውን አገልግሎት እና ደረጃ፡፡

3. የመሬት ይዞታው የማይንቀሳቀስ ንብረት አርፎበት ባለመብቱን መለየት ወይም ለማግኘት አስቸጋሪ ሲሆን በከተማው መሬትን ለማስተዳደር ወይም ለማልማት ሥልጣን በተሰጠው አካል ማመልከቻ ሲቀርብ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከቱት መረጃዎች እንዲያካትት ተደርጎ በባለአደራነት በስሙ እንዲመዘገብ ይደረጋል፡፡

4. ህጎች በሚፈቅዱት መሠረት ባለመብት ነኝ ባይ ለ15 ዓመት ያልታወቀ ወይም የጠፋ እንደሆነ የመሬት ይዞታው በከተማው መሬትን ለማስተዳደር ወይም ለማልማት ሥልጣን በተሰጠው አካል ስም ይመዘገባል፡፡

45.<u>በተመዘገበ የመሬት ይዞታላይ የሚኖሩ ለውጦችን ስለመመዝገብ</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 30 እና በዚህ ደንብ መሠረት ተዘርዝረው የተመዘገቡትን መብት፣ ክልከላና ኃላፊነቶች ለመቀነስ፣ ለማሻሻል፣ ለማስተካከል ወይም ለማስቀረት በተዋዋይ ወገኖች መካከል የሚደረጉ ስምምነቶች፣ ስልጣን ካለው አካል የተሰጡ የዋስትና እና ዕዳና እገዳ ትዕዛዞች ወይም ውሳኔዎች እና በተዋዋይ ወገኖች መካከል የሚደረጉ የውል ማሻሻሎች ይመዘገባሉ፡፡
2. የዋስትና እና ዕዳ እገዳ የተያዘ የመሬት ይዞታ፣ በባለይዞታው ሰው ላይ በደረሰበት ኪሳራ ምክንያት ግዴታውን መወጣት ካልቻለ መያዣው በስሙ ለተመዘገበለት የፋይናንስ ተቋም ተላልፎ የስም ዝውውር ሊመዘገብለት ይችላል፡፡

46.<u>የሌሎች የመሬት ይዞታን የመጠቀም ወይም የማቋረጥ መብት ምዝገባ</u>

1. በአንድ የምዝገባ ፎርም የሌላ ባለይዞታን መሬት መጠቀምን ወይም ማቋረጥን አስመልክቶ የመግባብያ ውል ከተዘጋጀ መዝጋቢው ተቋም የሌሎችን መሬት ይዞታ መብት የመጠቀም ወይም የማቋረጥ መብትን አስመልክቶ በምዝገባ ሰነዱ የሚከተሉት መረጃዎች እንዲመዘገቡ ያደርጋል፦
   ሀ) የሌሎችን መሬት ይዞታ የመጠቀም ወይም የማቋረጥ መብት ተፅኖ ስር የሚወድቅ መሬት ተጠቃሚ ወይም በዚህ ጉዳይ መብት እንዲመዘገብለት የሚደረገው ባለይዞታ፤
   ለ) የሌሎችን መሬት ይዞታ የመጠቀም ወይም የማቋረጥ መብት ጫና ያረፈበት የሚመለከተው ቁራሽ መሬት፤
   ሐ) የምዝገባ ተቋሙ ተገቢ እና አስፈላጊ የሚላቸው ሌሎች ልዩ ጉዳዮች፡፡
2. የሌሎችን መሬት ይዞታ መብት የመጠቀም ወይም ማቋረጥ መብት ሊወሰን የሚችለው በከፊልም ሆነ በሙሉ ንብረቱ ከመሬት በላይ ወይም በታች ወይም በሁለቱም ሁኔታ ሲኖረው ነው፡፡

47.<u>የሌሎችን መሬት ይዞታ የመጠቀም ወይም የማቋረጥ መብት ምዝገባ፣ ማስተላለፍ እና አለመመዝገብ</u>

1. ለአገልግሎት አቅርቦት የሚውል የሕዝብ መሠረተ ልማት ከመሬት በታች የዋለ ንብረት ሆኖ ከመሬት ይዞታ ጋር ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው የተላለፈ እንደሆነ ቀደም ብሎ የተመዘገበ በሌሎች መሬት ይዞታ የመጠቀም ወይም የማቋረጥ መብትን መጣስ የለበትም፡፡
2. የሌሎችን መሬት ይዞታ የመጠቀም ወይም የማቋረጥ መብት ከአንድ ባለመብት ለሌላ ባለመብት የተላለፈ እንደሆነ መብቱ የተላለፈለት ሰው ማመልከቻ ሲያቀርብ በማመልከቻው መሰረት በስሙ ወይም ይህን አገልግሎት እንዲያስቀጥል በተላለፈለት አካል ስም ይመዘገባል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሌሎችን መሬት ይዞታ የመጠቀም ወይም የማቋረጥ መብት ያገኘ ሰው መብቱን የማዘዋወር ስምምነት በፈፀመ በ30 ቀን ውስጥ ማስመዝገብ አለበት፤ ሆኖም መብቱን ለማስመዝገብ መብቱ በተላለፈለት ሰው ጥያቄ ካልቀረበ የመብት ምዝገባው አይካሄድም፡፡
4. ከመሬት በታች ያለ መሠረተ ልማት አገልግሎት መስጠት ያቆመ ቢሆንም እንኳን ለዚሁ አገልግሎት ሲባል ከመሬት በታች ወይም በላይ ያለ የሌሎችን መሬት ይዞታ የመጠቀም ወይም የማቋረጥ መብት እንደተመዘገበ ይቆያል፡፡
5. ከመሬት በታች ያለ የሕዝብ መሠረተ ልማት ሲዘረጋና ሲመዘገብ በመሬት ይዞታው የመጠቀም መብት ያለውን ሰው ወይም አካል ንብረት በማይጎዳ ሁኔታ መፈጸም አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## በመዝጋቢው ተቋም የሚሰጡ አገልግሎቶች

### ንዑስ ክፍል አንድ

### በመዝጋቢ ተቋሙ የተመዘገቡ መብቶች፣ ክልከላዎች እና ኃላፊነቶች ላይ የሚነሱ የአገልግሎት ጥያቄዎች መስተንግዶ

### 48.በመሬት ይዞታ ላይ ለሚሰጡ አገልግሎቶች ስለሚቀርቡ ማመልከቻዎች

1. በመሬት ይዞታ ላይ ለሚሰጡ አገልግሎቶች የሚቀርቡ ማመልከቻዎች ለዚሁ ተብሎ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላትና ከአስፈላጊ ደጋፊ ሰነዶች ጋር ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡፡
2. በመሬት ይዞታ ላይ የሚሰጡ የአገልግሎት ዓይነቶች እና የማመልከቻ ማቅረቢያ ቅፆች ይዘት ይህን ደንብ ለማስፈፀም በሚወጣ መመሪያ ይወሰናሉ፡፡

**49.የስም ዝውውር**

ማንኛውም ሰው በተመዘገበው የመሬት ይዞታ ላይ ያለውን መብት በውርስ፣ በስጦታ፣ በሽያጭ ወይም በሌላ በማንኛውም ህጋዊ መንገድ ስመ ንብረቱን ማዛወር የሚችለው፡-

1. የተመዘገበ የመሬት ይዞታ ሆኖ የመጠቀም መብቱን ማስተላለፍ ያልተከለከለ ከሆነ፤
2. በተመዘገበ ክልከላና ኃላፊነት ውስጥ የተመለከቱ ዝርዝር ጉዳዮች ከተሟሉ፤
3. ንብረቱ እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ ያልታገደ ከሆነ፤
4. የስም ዝውውሩን ለመፈፀም የሚያስችሉ እንደአግባቡ ከሚከተሉት ሰነዶች አንዱ የቀረበ እንደሆነ፡-
   ሀ) በውል ወይም በአክስዮን መዋጮ የሚተላለፍ ከሆነ በተዋዋይ ወገኖችመካከል የተደረገ በሰነዶች ማረጋገጫ የጸደቀ የስምምነት ወይም የሽያጭ ውል፤
   ለ) በስጦታ ከሆነ በሰነዶች ማረጋገጫ የጸደቀ ማስረጃ፤
   ሐ) በድርሻ መልቀቅ ከሆነ የድርሻ መልቀቁ በሰነዶች ማረጋገጫ የጸደቀ ስምምነት፤
   መ) በሊዝ ህጉ መሰረት የመሬት ይዞታው ከነባር ይዞታ ወደ ሊዝ ሥሪትየሚዞር ከሆነ ከመብት ሰጪው ጋር የተደረገ የሊዝ ውል ስምምነት፤
   ሠ) አግባብ ካለው አካል ስመ ንብረቱ እንዲዛወር የተሰጠ ማስረጃ፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (4) የተዘረዘሩት ሲሟሉ እና አግባብ ያላቸው ክፍያዎች ሲፈፀሙ፡፡

**50.የዋስትና እና ዕዳ እገዳ ምዝገባና ስረዛ**

1. የዋስትና እና ዕዳ እገዳ ምዝገባ አገልግሎት ጥያቄ ከፍርድ ቤት፣ ከባንክ፣ ከኢንሹራንስ እና ሌሎች በህግ ስልጣን ከተሰጣቸው አካላት ሲቀርብ ምዝገባው ይከናወናል፡፡
2. በቀረበው ማመልከቻ መሰረት ከሊዝ ህጉ ጋር በማገናዘብ የዋስትና እና ዕዳ እገዳው የሚመዘገበው የሚከተሉት በቅድሚያ ሲረጋገጡ ይሆናል፡-
   ሀ) የመሬት ይዞታው አስቀድሞ የተመዘገበ ከሆነ፤

ለ) በመሬት ይዞታ መብት ሰጪው ተቋም የመሬት ይዞታውን ለዋስትና እና ዕዳ እገዳ በማስያዝ የትኛውንም ህጋዊ ተግባር ለመፈፀም የሚያስችል መብት ተፈጥሮ እንደሆነ፤ እና

ሐ) በተመዘገበው መብት፣ ክልከላ እና ሃላፊነት ላይ ያሉ ዝርዝር ጉዳዮች ባለይዞታው ያሟላ ከሆነ፡፡

3. እገዳ የተጣለበትን የመሬት ይዞታ አስመልክቶ እግዱን ከሰጠው አካል እገዳው እንዲነሳ ወይም እንዲሰረዝ የሚጠይቅ ደብዳቤ ሲቀርብ የእገዳ ምዝገባው ሊሰረዝ ይችላል፡፡

4. የከተማ መሬት ይዞታ ላይ በጊዜ ገደብ የተደረጉ እገዳዎችን በተመለከተ መዝጋቢው አካል ጊዜ ገደቡ ማለፉን ሲያረጋግጥ በራሱ ሥልጣን እግዱን መሰረዝ ይኖርበታል፡፡

51.<u>የመሬት ይዞታ መቀላቀልን ስለመመዝገብ</u>

ሁለትና ከሁለት በላይ የሆኑ አዋሳኝ ይዞታዎችን ቀላቅሎ ወደ አንድ ይዞታ ሥር በማድረግ መመዝገብ የሚቻለው የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸው ሲረጋገጥ ይሆናል፦

1. የመሬት ይዞታዎቹ አስቀድመው የተመዘገቡ ሲሆኑ፤
2. የመሬት ይዞታዎቹ ኩታ ገጠም ሲሆኑ፤
3. ከመሬት ይዞታዎች መካከል አንዱ ወይም ሁሉም የተገኙት በማይንቀሳቀስ ንብረት ግዢ፣ በስጦታ ወይም በውርስ ከሆነ የስም ዝውውሩ አስቀድሞ የተጠናቀቀ ሲሆን፤
4. የመሬት ይዞታዎች በዋስትና ዕዳና እገዳ መዝገብ ላይ የተመዘገቡ ከሆነ ዕዳና እገዳው አስቀድሞ የተሰረዘ ወይም የዋስትና እና ዕዳ እገዳ የጣለው አካል እንዲቀላቀሉ ስምምነቱን በጽሁፍ የተገለጸ ሲሆን፤
5. ይዞታዎች ሲቀላቀሉ የሚኖረው የመብት፣ የክልከላ እና ኃላፊነት መነሻው የኪራይ ይዞታ ወይም የተለያዩ የነባር እና የሊዝ ስሪት ይዞታዎች ከሆኑ ዝርዝር ሁኔታ ከመብት ሰጪው አካል በአዲስ መልክ ተዘጋጅቶ መብቱ፣ ክልከላው እና ኃላፊነቱ ተለይቶና ተረጋግጦ ሲቀርብ፡፡

52.<u>ይዞታን ስለመክፈልና መመዝገብ</u>

የመሬት ይዞታን ከሁለት ወይም ከዚያም በላይ ማካፈልና ማስመዝገብ የሚቻለው፡-

1. የመሬት ይዞታው አስቀድሞ የተመዘገበ እንደሆነ፤
2. በመሬት ይዞታው ላይ የተመዘገበ እዳና ዕገዳ ከሌለ ወይም እዳና ዕገዳው እንዲመዘገብ ያደረገው ተቋም ዕዳና እገዳው እንዲነሳ ስምምነቱን በጽሁፍ የገለጸ ከሆነ፤
3. ይዞታው መካፈል የሚችል ስለመሆኑ የመሬት አጠቃቀም ተቆጣጣሪ አካል ባወጣው ስታንዳርድ ተመሳክሮ ሲረጋገጥ፤
4. በተካፈለው ይዞታ ላይ ሊመዘገብ የሚገባው መብት፣ ክልከላ እና ኃላፊነት ተለይቶ ሲቀርብ፤

ይሆናል፡፡

53.<u>የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባ መረጃን ወቅታዊ ለለማድረግ</u>

የመሬት ይዞታ መብት መረጃን መዝጋቢው ተቋም ማሻሻል ወይም ወቅታዊ ማድረግ የሚችለው፡-

1. የመሬት ይዞታ መብት መረጃው እንዲሻሻል የቀረበበት የመሬት ይዞታ በመሬት ይዞታ መብት መመዝገቢያ መዝገብ ውስጥ ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑ ሲረጋገጥ፤
2. የመሬት ይዞታ መብት መረጃውን ለማሻሻል ወይም ወቅታዊ ለማድረግ የቀረበው ሰነድ ህጋዊ መሆኑ ሲረጋገጥ፤
3. በተመዘገበ የመሬት ይዞታ ላይ የተጠየቁ አገልግሎቶች መረጃውን የሚለውጡት ሆነው ሲገኙ፤ እና
4. የቀረበዉ መረጃ ትክክለኛነት እና ከይዞታዉ ማህደር ጋር መያያዙ ከተጣራ በኋላ በመዝጋቢ ሹሙ ሲፈቀድ፤

ይሆናል፡፡

## <u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>

## <u>የመሬት ይዞታ መዝገብ ማህደር አዘገጃጀት፣ አጠባበቅ እና የመረጃ አቅርቦት</u>

54.<u>የመሬት ይዞታ መዝገቦች አዘገጃጀት</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 31 (1) መሠረት የሚዘጋጁ የመሬት ይዞታ መዝገብ፣ የጋራ ሕንፃ የመሬት ይዞታ መዝገብ፣ ወደ ከተማ የተካለለ የአርሶ አደር መሬት ይዞታ መዝገብ እና የዋስትና እና ዕዳ እገዳ መዝገብ በወረቀት እና በዲጂታል መልክ ተዘጋጅተው የመሬት ይዞታ መብት፣ ክልከላ እና ኃላፊነት በጥቅል የሚመዘገብባቸው ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱት መዝገቦች በዋናነት የሚከተሉትን ይይዛሉ፦
   ሀ) የከተማ ጣቢያና የቁራሽ መሬት ልዩ መለያ ኮድ፤
   ለ) የባለቤቱ ወይም የባለይዞታው ስምና አድራሻ፤
   ሐ) መብት፣ ክልከላ እና ኃላፊነት፤
   መ) የመሬት ይዞታው ስሪት፤
   ሠ) የቁራሽ መሬት አገልግሎት እና ደረጃ፤
   ረ) የቁራሽ መሬት ርዝመት፣ ስፋት እና የይዞታው ማዕዘኖች ኮኦርዲኔት፤
   ሰ) ሌሎች በካዳስተር ቅየሳ ስታንዳርድ እና መመሪያ የሚገለጹ ዋና ዋና መረጃዎች፡፡

55.<u>**የዋስትና ዕዳ ዕገዳ መዝገብ**</u>

1. የዋስትና እና ዕዳ እገዳ መዝገብ ከፍርድ ቤት፣ ከባንክ እና ከሌሎች በህግ ሥልጣን ከተሰጣቸው አካላት የሚሰጡ ከመሬት ይዞታ ጋር የተያያዙ ክልከላዎች ለመመዝገብ በአዋጁ አንቀጽ 31(1) መሠረት ይደራጃል፡፡
2. የዋስትና እና ዕዳ እገዳ መዝገብ በዋናነት ሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፦
   ሀ) የመሬት ይዞታው ተጠቃሚ ሙሉ ስም፤
   ለ) የከተማ ጣብያና የቁራሽ መሬቱን ልዩ መለያ ኮድ፤
   ሐ) ዕዳ እገዳውን የሰጠውን አካል ሙሉ ስም፤
   መ) ዕዳ እገዳው እንዲመዘገብ የተጻፈው ደብዳቤ ቁጥር እና ቀን፤
   ሠ) የዕዳ እገዳው ምክንያት፤
   ረ) የዋስትናው የገንዘብ መጠን፤
   ሰ) ዕዳ እገዳው የተመዘገበበት ቀን፤
   ሸ) ዕዳ እገዳውን ምዝገባ የፈጸመው ሰው ስምና ፊርማ፤
   ቀ) ዕዳ እገዳው እንዲነሳ የተፃፈው ደብዳቤ ቁጥርና ቀን፤

በ) ዕዳ እገዳው እንዲነሳ ትዕዛዝ የሰጠው በህግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ስም፤

ተ) ዕዳ እገዳው የተነሳበት ቀን፤

ቸ) ዕዳ እገዳውን ስረዛ የመዘገበው ሰው ስምና ፊርማ፡፡

56. **ሌሎች መዝገቦች**

መዝጋቢው ተቋም ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተጨማሪ መዝገቦችን የክልሉን መንግስት በማስፈቀድ ሊያደራጅ ይችላል፡፡

57. **የመዝገቦች አጠባበቅ**

1. በወረቀትና በዲጂታል የሚዘጋጁ መዝገቦች የተፈጥሮም ሆነ ሰው ሰራሽ ጉዳት እንዳይደርስባቸው ተደርገው መጠበቅ አለባቸው፡፡
2. ዝርዝሩ በመመሪያ የሚወሰን ሆኖ በወረቀትና በዲጂታል ለሚዘጋጁ መዝገቦች አጠባበቅ አጠቃላይ የአጠባበቅ ሥርዓትና ተጨማሪ ኮፒ የሚቀመጥበት ወይም የባክ አፕ መረጃ አያያዝ ሥርዓት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

58. **የመረጃ ደህንነት እና ጥበቃ**

1. በፌዴራል፣ በክልል እና በከተማ ደረጃ ባሉ መዋቅሮች የሚቀረጸውና ተግባራዊ የሚደረገው የካዳስተር መረጃ መሠረተ ልማት ደህንነት በአገራዊ የኢንፎርሜሽን ደህንነት ፖሊሲ እና ስታንዳርድ ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፡፡
2. በፌዴራል፣ በክልል እና በከተማ ደረጃ ያሉ የህጋዊ ካዳስተር አስተግባሪ እና ተግባሪ ተቋማት የመረጃ ማዕከላቸውን እና መሠረተ ልማቱን ደህንነት ብቃት ለማረጋገጥ ምክንያታዊ በሚባል የጊዜ ወሰን በሚመለከተው አካል የማስፈተሽ እና ኦዲት የማስደረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡
3. የምዝገባ ተቋሙ የካዳስተር መረጃ ስርዓቱ መጠቀም ከመጀመሩ በፊት የመረጃ ጉዳት ወይም ውድመት ቢፈጠር መልሶ የማቋቋም አማራጭ መኖሩን በማረጋገጥ መሆን አለበት፡፡
4. የምዝገባ ተቋሙ በካዳስተር መረጃ መሠረተ ልማቱ ሥርዓት ውስጥ አስፈላጊ አካላዊ እና አመክንዮአዊ ተጋላጭነት ቁጥጥር ሥርዓቶች መተግበራቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

5. በወረቀት፣ በዲጂታል ወይም በዓለም አቀፍ የመረጃ መረብ ለማንኛውም ሰው በነፃ የሚለቀቁ የህጋዊ ካዳስተር መረጃዎች “ጥቅል መረጃ” ተብለው የተለዩት መሆን አለባቸው፡፡
6. ዝርዝር እና መሠረታዊ መረጃዎች ለሦስተኛ ወገኖች ሊሰጡ የሚችሉት በመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነጻነት አዋጅ መሠረት የባለ ይዞታውን ጥቅምና መብት የማይጋፉ እና የመንግስትንና የሕዝብን ጥቅምና ደህንነት አደጋ ላይ የማይጥሉ ሆነው ሲገኙ እና ጠያቂው አካል የአገልግሎት ክፍያ ሲፈጽም ይሆናል፡፡

59.**ስለ ማህደራት አደረጃጀት**

1. የመሬት ይዞታ መረጃ ማህደር የሚከፈተው የመዝጋቢው ተቋም የበላይ ኃላፊ ወይም እሱ የሚወክለው ሰው ትዕዛዝ ሲሰጥ ይሆናል፡፡
2. እያንዳንዱ ማህደር የሚደራጀው በአገር አቀፍ ደረጃ አንድን ቁራሽ መሬት ለመለየት በሚያስችል መልኩ የሚወጣውን ስታንዳርድ ተከትሎ ይሆናል፡፡
3. ለተጨማሪ ኮፒ ወይም ለባክ አፕ መረጃ አያያዝ አገልግሎት ከመዝጋቢው ተቋም ውጪ በተለየ ቦታ እንዲቀመጥ ካልተፈቀደ በቀር በማንኛውም ሁኔታ የመሬት ይዞታ ማህደር ከመዝጋቢው ተቋም ውጪ መቀመጥ የለበትም፡፡

60.**የሕጋዊ ካዳስተር መረጃ ቅጂ ስለማግኘት**

1. የህጋዊ ካዳስተር መረጃ ለሕዝብ ተደራሽ መሆኑን ተከትሎ የተመዘገቡ ሰነዶችን፣ ከመዛግብቱ ውስጥ የተያያዙ መረጃዎችን፣ ከሰነዱ የተውጣጡ መረጃዎችን፣ ከተመዝጋቢው ንብረት ጋር በጊዜያዊነት የተያያዙ ማስታወሻዎችን፣ የአንድን የተመዘገበ ንብረት ወይም ባለይዞታ የሚመለከት ማንኛውም መረጃ ግልባጭ እንዲሰጥ በህግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ወይም በመሬት ይዞታው ላይ ጥቅም ባለው ሰው ጥያቄ ሲቀርብ ቅጂው ይሰጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የመረጃ ቅጂ የሚሰጠው የአገልግሎት ክፍያ መከፈሉ ሲረጋገጥ ወይም ከክፍያ ውጭ መረጃውን እንዲያገኙ ለተፈቀደላቸው ተቋማት መሆኑ ተረጋግጦ ይሆናል፡፡
3. የአዋጁ አንቀጽ 37(3) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በህጋዊ ካዳስተር መዝገብ ውስጥ ያለውን መረጃ አስመልክቶ ጥያቄ ሲቀርብ ተቋሙ በማስረጃ የተደገፈ ምስክርነቱን ይሰጣል፡፡

4. የባለይዞታ ስም፣ የመሬት ይዞታ ስፋት፣ የመሬት ይዞታ አገልግሎት ዓይነት እና ደረጃ፣ የመሬት ይዞታ ዋጋ እና በመሬት ላይ ያለ ቋሚ ንብረት ዋጋ የሚመለከቱ የካዳስተር መረጃዎች በአግባቡ ከተደረጁ በኋላ ለሕዝብ ተደራሽ ይሆናሉ፡፡

## ክፍል ስድስት

## ስለ ሰርተፍኬት አሰጣጥ፣ ስለመሰረዝ፣ ስለማስተካከል እና ስለ ቅሬታ አቀራረብ

### ንዑስ ክፍል አንድ

### ስለ መሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት አሰጣጥ

61.የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት

1. የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት በአዋጁ አንቀጽ 33(2) መሠረት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መሥፈርት መሠረት የሚዘጋጅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉትን የሚያካትት ይሆናል፦
   ሀ) የተመዘገበውን የመሬት ይዞታ የሚያመለክትና በቀላሉ ለመለየት የሚያስችል ሚስጥራዊ ቁጥር በባር ኮድ፣ የምዝገባ ቁጥር፣ የከተማ ጣቢያ፣ የቁራሽ መሬት ልዩ መለያ ኮድ፣ የባለይዞታው መግለጫ፣ የይዞታው ስዕላዊ መግለጫ፣ የመሬት ይዞታው መብት መግለጫ እና የመዝጋቢ ሹሙ ፊርማ እና የመዝጋቢ ተቋሙ ማህተም፤
   ለ) የመሬት ይዞታው ባለመብት ግለሰብ ሙሉ ስም እስከ አያት ወይም የማህበራት እና የድርጅት ሲሆን ድርጅቱ በህጋዊ ሰውነት የተመዘገበበት ስም እና የተመዘገበበት ቁጥር፤
   ሐ) ሰርተፍኬቱ የተሰጠበትን ቀን፣ ወርና ዓመት ምህረት፣ የመዝጋቢ ሹሙ ወይም እሱ የወከለው ሰው ስም፣ ፊርማና የተቋሙ ማህተም፡፡
2. በምዝገባ ሹም ተፈርሞ እና የምዝገባ ተቋሙ ማህተም አርፎበት የተሰጠ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት በአዋጁ አንቀጽ 42 መሠረት የመሬት ይዞታ መብትን ለማረጋገጥ ማስረጃ ሆኖ ያገለግላል፡፡
3. የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬቱ ጥቅም ላይ በሚውልበት ጊዜ ባለይዞታው ወይም ህጋዊ ወኪሉ ባቀረቡት ያልተሟላ ማመልከቻ ምክንያት የፎርም አሞላል ስህተት ሲፈጠር ወይም ያልተሟሉ ህጋዊ ሥነ-ሥርዓቶች

ቢከሰቱ መዝጋቢ ሹሙ ስለሰርተፍኬቱ ትክክለኛነት ሌላ ማረጋገጫ እንዲቀርብ አይጠየቅም ወይም ሰርተፍኬቱ ጥያቄ ውስጥ አይገባም፡፡

62.**<u>የሰርተፍኬት አሰጣጥ</u>**

1. ማንኛውም የመሬት ይዞታ ባለመብት ላስመዘገበው የመሬት ይዞታ መብት፣ ክልከላ እና ኃላፊነት ማረጋጋጫ የሚሆን ሰርተፍኬት እንዲሰጠው ሲያመለክትና የአገልግሎት ክፍያ ሲፈጽም ይሰጠዋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚዘጋጁ ሰርተፍኬቶች፡-

   ሀ) በሊዝ አግባብ የተያዙና የተመዘገቡ የመሬት ይዞታዎች፤

   ለ) በሰብ ሊዝ የተያዙ ይዞታዎች የመጠቀም መብት፣ ክልክላ እና ኃላፊነቶች፤

   ሐ) በነባር ይዞታ የተያዙና የተመዘገቡ የመሬት ይዞታዎች፤

   መ) ወደ ከተማ ክልል የተካለሉ የአርሶ አደር የመሬት ይዞታዎች፤

   ሠ) ለጋራ መኖሪያነት በሪል እስቴት እና በኮንዶሚኒየም የተያዙ የመሬት ይዞታዎች፤

   ተብለው በአራት ዓይነት ተከፍለው የሚዘጋጁ እና የሚሰጡ ይሆናል፡፡

63.**<u>የሚዘጋጀው ሰርተፍኬት የቅጂዎች ብዛት</u>**

1. የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ኦሪጂናል እና ኮፒ በሚል በሁለት ቅጂዎች መዘጋጀት አለበት፡፡
2. ከተዘጋጁት ሁለት ሰርተፍኬቶች ውስጥ ዋናው ቅጂ ለባለይዞታው የሚሰጥ ሲሆን ኮፒው ከማህደሩ ጋር ተያይዞ መቀመጥ አለበት፡፡

64.**<u>የምትክ ሰርተፍኬት አሰጣጥ</u>**

1. በዚህ ደንብ መሰረት ተዘጋጅቶ የተሰጠ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት የጠፋበት፣ የተበላሸበት ወይም በተለያየ ምክንያት ከጥቅም ውጭ የሆነበት ማንኛውም ሰው መረጃው ለመጥፋቱ በአገር አቀፍ ደረጃ ሰፊ ሥርጭት ባለው ጋዜጣ ታውጆ ተቃዋሚ ካልተገኘ አግባብ ያለውን የአገልግሎት ክፍያ ሲፈጽም ምትክ ሰርተፍኬት ይሰጠዋል፡፡

2. በምትክነት በተሰጠ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ከስድስት ወር ቆይታ በኋላ ካልሆነ በስተቀር የመሬት ይዞታ መብትን ሌላ ሰው ማስተላለፍ አይቻልም፡፡
3. ለባለይዞታው ምትክ ሰርተፍኬት ከመሰጠቱ በፊት የመዝጋቢው ተቋም ድርሻ የሆነው ቅጂ ሰርተፍኬት ከማህደሩ ውስጥ መኖሩ መረጋገጥ አለበት፤ ምትክ ሰርተፍኬት ስለመሰጠቱም በዚያው ቅጂ ላይ መስፈር አለበት፡፡
4. ዝርዝር አፈጻጸሙ በመመሪያ የሚወሰን ሆኖ መዝጋቢው ተቋም ምትክ ሰርተፍኬት ስለመስጠቱ በአስር ቀናት ውስጥ በሕዝብ ማስታወቂያ ይፋ ማድረግ አለበት፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት
## ሰርተፍኬት ያገኘ ምዝገባን ከመዝገብ ስለመሰረዝ፣ ስለማስተካከል እና ስለ ቅሬታ አቀራረብ

### 65.ሰርተፍኬት ያገኘ ምዝገባን ከመዝገብ ላይ ስለመሰረዝ እና ማስተካከል

1. የአዋጁ አንቀጽ 45(3) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ መዝጋቢው አካል በራሱ ውሳኔ ምዝገባ እንዲስተካከል ወይም እንዲታረም ለማድረግ የሚችለው በተቋሙ ኦፊሰሮች የተፈጸመ የአጻጻፍ ወይም የአመዘጋገብ ስህተት መኖሩን ሲያረጋግጥ ይሆናል፡፡
2. ተዋዋይ ወገኖች በስምምነት በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ቀርበው የቀድሞ ውላቸውን ቀይረው ወይም ከተመዘገበው ውል ውስጥ የተወሰነውን አስተካክለው እንዲመዘገብላቸው ሲያመለክቱ ምዝገባው በመዝጋቢው ተቋም እንዲስተካከል ይደረጋል፡፡
3. መዝጋቢ ሹሙ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት መስተካከል አለበት ብሎ ሲወስን፡-
   ሀ) በተመዘገበው መሬት ይዞታ ላይ ጥቅም ያላቸውን ሰዎች እና ከስህተቱ ጋር በተያያዘ ጥቅማቸው የሚነካባቸውን በአድራሻቸው ማሳወቅ እና ከ15 ቀናት በኋላ ማስተካከያውን ተግባራዊ ማድረግ፤ እና
   ለ) መስተካከሉን በሚመለከት ጥቅም አለኝ የሚለው ሰው የሚያቀርበውን አስተያየት ወይም ተቃውሞ መቀበልና መስማት፤

   አለበት፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ማስታወቂያ የደረሰው ጥቅሙ የሚነካበት ሰው በ 15 ቀናት ውስጥ በከተማ ነክ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወይም የሚመለከተው መደበኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ በማቅረብ መዝጋቢ ተቋሙ ማስተካከያ እንዳያደርግ እንዲታገድ ሊያደርግ ይችላል፡፡
5. የምዝገባ ተቋሙ በመሬት ይዞታው ላይ ጥቅም አለን የሚሉትን ሰዎች ካሳወቀ እና ተቃውሞ ካልቀረበ ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝም ሆነ በሌላ አካል የእገዳ ውሳኔ ካልተላለፈ ከ 15 ቀናት በኋላ ማስተካከያውን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሰረት የተደረገው ማስተካከያ ለማገናዘብያ እንዲረዳ እና ማስተካከያ መደረጉን ለማሳየት እንዲቻል ማስተካከያ የተደረገበት ቀን ተጠቅሶ እና በመዝጋቢ ሹሙ ተፈርሞበት ለአስረጅነት መቀመጥ አለበት፡፡
7. መዝጋቢው ተቋም ማንኛውንም በስህተት በመዝገብ ውስጥ በተመዘገበ ምዝገባ ምክንያት የተገኘ መብትን የሚነካ ማስተካከያ ምዝገባ አያደርግም፡፡
8. ምዝገባ ሹሙ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (7) የተመለከተው ዓይነት ችግር ሲገጥመው ለከተማ ነክ ፍርድ ቤት ወይም ሌላ ለሚመለከተው መደበኛ ፍርድ ቤት ከማብራሪያ ጋር በማመልከት አግባብ ያለውን የህግ ድጋፍ ሊያገኝ ይችላል፡፡
9. መዝጋቢ ሹሙ የመሬት ይዞታ መብት ባለቤት ማንነት መግለጫን በመዝገብ ላይ መቀየር ወይም ማስተካከል የሚችለው በሚከተሉት ምክንያቶች ይሆናል፦
   ሀ) ስሙ በመዝገቡ ላይ የሰፈረው ሰው ወይም ህጋዊ ወኪሉ በጽሁፍ ሲያመለክት፤
   ለ) የምዝገባ ተቋሙ መረጃ በሚያደራጅበት እና በሚያዘጋጅበት ወቅት በመዝገቡ ላይ የተመዘገበውን ሰው የማንነት መግለጫ የሆነውን በስህተት ቀይሮት ወይም አስተካክሎ መዝግቦት ከሆነ፡፡
10. እንዲሰረዝ የተወሰነ የመሬት ይዞታ መብት፣ ክልከላ እና ኃላፊነት ከወረቀት መዝገቡ የሚሰረዘው፦
   ሀ) በጽሁፉ ላይ ከግራ የላይኛው ጠርዝ ተነስቶ ወደ ቀኝ የታችኛው ጠርዝ ከዳር እስከዳር አንድ ሰያፍ መስመር በማስመር፤

ለ) የተቋሙ ኃላፊ ሰነዱ የተሰረዘበትን ቀን በመጻፍ በተሰረዘው ጽሁፍ ፊት ለፊት ገጽ ላይ ከግራ ወደ ቀኝ ተሰርዟል የሚል ቃል በማስፈር፤ እና

ሐ) ምዝገባው እንዲሰረዝ ያዘዘውን አካል ወይም ውሳኔ የሰጠው ፍርድ ቤት ስም፣ የውሳኔው ማጣቀሻ ቁጥር እና ቀን በመዝገቡ ላይ በማስፈር፤

መሆን አለበት፡፡

66. <u>ስለ ቅሬታ አቀራረብ</u>

በዚህ ደንብ በተመለከተው መሠረት በአግባቡ አልተፈጸመልኝም፣ መጉላላት ደርሶብኛል ወይም ጉዳት ደርሶብኛል ወይም ሊደርስብኝ ነው የሚል ማንኛውም ሰው ጉዳዩ እንዲታይለት በዚህ ደንብ በአንቀጽ 67 መሠረት ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡

67. <u>የቅሬታ አቀራረብ ሥነሥርዓት እና ስለሚመረመርበት ሁኔታ</u>

1. ማንኛውም ሰው በተሰጠው የከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ አገልግሎት ቅሬታ ካለው በመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎቱን ለሰጠው ሰራተኛ መዝጋቢው ተቋም በሚያዘጋጀው የቅሬታ ማቅረብያ ማመልከቻ ላይ አስፍሮ እና በቀሪው ላይ አስፈርሞ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡ አገልግሎት የሰጠው ሰራተኛ በሁለት የሥራ ቀናት ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን ምላሽ በጽሁፍ መስጠት አለበት።
2. ሰራተኛው በሰጠው ምላሽ ያልረካ ቅሬታ አቅራቢ ቅሬታውን ለሰራተኛው የቅርብ ኃላፊ ያቀርባል፤ ኃላፊው የቀረበውን ጉዳይ መርምሮና ማጣራት አድርጎ በሶስት የስራ ቀናት ውስጥ አስፈላጊውን ምላሽ በጽሁፍ መስጠት አለበት፡፡
3. ቅሬታ አቅራቢው በቅርብ ኃላፊው በተሰጠው ምላሽ ያልረካ ከሆነ ለመዝጋቢው ተቋም ኃላፊ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፤ ኃላፊው ጉዳዩን ያየውን ሰራተኛ እና የቅርብ ኃላፊውን ምላሽ መርምሮ እና ተገቢውን ማጣራት አድርጎ ለቅሬታ አቅራቢው ምላሹን በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡
4. በአንድ የመሬት ይዞታ ላይ ጥቅም ባለው ቅሬታ አቅራቢ የቀረበው ቅሬታ ተጣርቶ በመዝጋቢ ተቋሙ የበላይ ኃላፊ የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ቅሬታ በቀረበበት የመሬት ይዞታ ላይ ማንኛውም ዓይነት በሕግ ውጤት

ያለው ተግባር እንዳይካሄድ እንዲታገድ ቅሬታ አቅራቢው በጽሁፍ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

5. የመዝጋቢው ተቋም ኃላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት የቀረበውን የእግድ ጥያቄ መነሻ በማድረግ ቅሬታው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከአምስት የሥራ ቀናት ለማይበልጥ ጊዜ በመሬት ይዞታው ላይ ማንኛውም ዓይነት በህግ ውጤት ያለው ተግባር እንዳይካሔድ ሊያግድ ይችላል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት በሚሰጥ እግድ ምክንያት የሚደርስ ጉዳት ቢኖር ቅሬታ አቅራቢው ኃላፊ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሰባት

## የመዝጋቢው ተቋም ተጠያቂነት እና የዋስትና ፈንድ ስለማቋቋም

### 68. የመዝጋቢው ተቋም ተጠያቂነት

1. በአዋጁ አንቀጽ 40 (1) እና (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የአዋጁን ሌሎች ድንጋጌዎች፣ ይህንን ደንብ እንዲሁም ይህንን ደንብ ተከትለው በወጡ መመሪያዎች መሠረት የተመዘገበ መብት፣ ክልከላ እና ኃላፊነት ላይ የተዘረዘሩ ጉዳዮችን በመተላለፍ የመዝጋቢው ተቋም ሹም በማንኛውም መንገድ የስም ዝውውር፣ መያዣና እዳ ዕገዳ፣ ይዞታን መክፈል ወይም መቀላቀል ምዝገባ የፈፀመ እንደሆነ እና በዚህም ምክንያት የደረሰ ጉዳት መኖሩ ሲረጋገጥ ተጠያቂ ይሆናል፡፡
2. በተመዘገበ መብት፣ ክልከላና ኃላፊነት ላይ የደረሰን የጉዳት ካሣ መጠን ለመወሰን የመሬት ይዞታው እና በመሬት ይዞታው ላይ የነበረው የማይንቀሳቀስ ንብረት ግምት በዚህ ደንብ በአንቀጽ 69(2) መሠረት የሚሰላው ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

### 69. የኃላፊነት መጠን

1. መዝጋቢው ተቋም የሚወስደው የኃላፊነት መጠን ከመሬት ይዞታውና በይዞታው ላይ ካረፈው የማይንቀሳቀስ ንብረት ዋጋ ግምት ሊበልጥ አይችልም።
2. የመሬት ይዞታውና የማይንቀሳቀስ ንብረት ግምቱ የሚሰላው መንግስት ለመሬት ይዞታ እና በይዞታው ላይ ለሚገኘው የማይንቀሳቀስ ንብረት ለታክስ

አከፋፈል ዓላማ የሚገምትበት ወቅታዊ የንብረት ዋጋ ግመታን መነሻ ያደረገ ይሆናል፡፡

3. መዝጋቢው ተቋም ከዋስትና ፈንዱ የከፈለውን ገንዘብ በሕገወጥ መንገድ ተጠቃሚ ከሆነው ሰው ተከታትሎ በሕግ አግባብ በማስመለስ እና ወደ ዋስትና ፈንዱ ገቢ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከተውን ግዴታ ያልተወጣ አግባብ ያለው የሥራ ኃላፊ ተጠያቂነት አለበት፡፡

70.<u>አስተዳደራዊ ጉዳዮችን ስለመመዝገብ</u>

1. መዝጋቢው ተቋም አስተዳደራዊ ጉዳዮችን ለመመዝገብ የሚያስችለውን መዝገብ በማዘጋጀት በመዝገቡ ውስጥ፦
   ሀ) የጉዳዩ ባለቤት፣
   ለ) የጉዳዩ ምንነት፤
   ሐ) ውሳኔ የተሰጠበትን ቀን፤
   መ) የውሳኔውን ፍሬ ነገር፤ እና
   ሠ) ውሳኔው የተሰጠበት የህግ መነሻ፤
   መመዝገብ አለበት፡፡
2. መዝጋቢው ተቋም ለአስተዳደራዊ ጉዳይ ባዘጋጀው መዝገብ ውስጥ ቁራሽ መሬትን አስመልክቶ የሚከተሉትን መረጃዎች ማካተት አለበት፦
   ሀ) መሬቱ በሊዝ ስሪት የተያዘ ከሆነ የሊዝ ባለይዞታውን ሙሉ ስም፤
   ለ) ቁራሽ መሬቱ የሚገኝበት አድራሻ፤
   ሐ) ቁራሽ መሬቱ የሚገኝበትን ወረዳ፣ ቀጠና፣ ሰፈር እና የከተማ ጣብያ
   መ) ከቁራሽ መሬቱ ጋር የተያያዘ መዝጋቢው ተቋም አስፈላጊ ነው ብሎ ያመነባቸውን ሌሎች መረጃዎች፡፡
3. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ለመዝጋቢው ተቋም ከቁራሽ መሬቱ ጋር በተያያዘ እንዲካተቱ የቀረቡ መረጃዎች በመሬት ይዞታ መዛግብቱ ውስጥ ቀደም ብለው ከተካተቱት ተጨማሪ ሆነው ከተገኙ መመዝገብ የለባቸውም፡፡

71.<u>የከተማ ነክ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሥልጣን</u>

የከተማ ነክ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአዋጁ አንቀጽ 17(3) መሠረት የቀረበለትን ይግባኝ ሰምቶ የምዝገባ ተቋሙ ማናቸውንም የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ እንዲያደርግ፣ የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ማስተካከያ እንዲያደርግ ወይም የሚያደርገውን የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ማስተካከያ እንዲያቆም ሊያዘው ይችላል፡፡

72.<u>ስለዋስትና ፈንድ</u>

1. የመሬት ይዞታ የሚያስተላልፍ ማንኛውም ሰው ክልሎች በሚወስኑት ተመን መሰረት ለሚያደርገው የመሬት ይዞታ ስም ዝውውር፣ ለኢንዱስትሪ ዞን የለማ መሬት በሰብ-ሊዝ ሲተላለፍ፣ በውል ሙሉ ወይም ከፊል የመሬት ይዞታ መብት ሲተላለፍ፣ በውርስ የመሬት ይዞታ ሲተላለፍ፣ በመያዣና ዕዳ እገዳ የመሬት ይዞታ ሲመዘገብ እና በልማት ምክንያት የመሬት ይዞታ እና የማይንቀሳቀስ ንብረት ካሳ ክፍያ ሲፈጸም ለዋስትና ፈንድ የሚውል ተጨማሪ ክፍያ ይፈጽማል።
2. ክልሎች የወሰኑትን የዋስትና ፈንድ የክፍያ ቀመር በሕዝብ ማስታወቂያ ለህብረተሰቡ ማሳወቅ አለባቸው።
3. የዋስትና ፈንድ ተጨማሪ ክፍያ ቀመርን በሚመለከት የከተማው ምዝገባ ተቋም አጥንቶ በህግ ይህን እንዲመራ ሥልጣን ለተሰጠው የክልል አካል ሲያቀርብ ሊሻሻል ይችላል፡፡
4. ጥናቱ የቀረበለት የሚመለከተው የክልል አካል ጥናቱ በቀረበለት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡
5. በየከተሞቹ የተጀመረው የዋስትና ፈንድ ማሰባሰብ ሊቋረጥ የሚችለው በህግ ይህን እንዲመራ ሥልጣን ለተሰጠው የክልል አካል የጥናት ውጤት ሲቀርብ በክልሉ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት ይሆናል፡፡
6. የዋስትና ፈንድ ማሰባሰብ እንዲቋረጥ ከተወሰነ በሕዝብ ማስታወቂያ ይፋ መደረግ አለበት፡፡

## <u>ክፍል ስምንት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

73.<u>ስለ ደንብ መተላለፍ</u>

ማንኛውም የመዝጋቢ ተቋም ኃላፊ፣ የመሬት ይዞታ መብት መዝጋቢ፣ የመሬት ይዞታ መብት አረጋጋጭ ወይም ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ በዚህ ደንብ ላይ ከተደነገጉት ወይም ይህንን ደንብ ተከትሎ ከወጣው መመሪያ ውጪ ቢፈጽም ወይም እንዲፈፀም ሲያደርግ በአዋጁ አንቀጽ 48(1) መሠረት በወንጀል መቀጣቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በሙያ ሥነ-ምግባር የዲስፕሊን ደንብ ይቀጣል፡፡

74.<u>የመሸጋገሪያ ደንጋጌ</u>

1. በከተሞች የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባ ሂደት በአዋጁ መሰረት ሥልጣን የተሰጠው መዝጋቢ ተቋም ተቋቁሞ ሙሉ በሙሉ በሰፈር ወይም በቀጠና፣ በወረዳ ወይም በከተማ ምዝገባውን አጠናቆ አገልግሎት መስጠት እስኪጀምር ድረስ ሥራ ላይ በነበረው ህግ እና የመሬት አስተዳደር አሰራር ወይም ክልሎች በሚወስኑት አደረጃጀት መሰረት ሥራው እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡
2. የሽግግር ጊዜው ከተሞቹ ያላቸውን የቆዳ ስፋት፣ ግምታዊ የመሬት ይዞታ ብዛት እና ቅድመ ዝግጅት ከግምት ውስጥ በማስገባት የክልሉ መንግስት ህጋዊ ካዳስተር ተግባራዊ እንዲሆን ከወሰነበት ጊዜ አንስቶ ይሆናል፡፡

75.<u>ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች</u>

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ ወይም የአሠራር ልማድ በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

76.<u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ 16 ቀን 2007 ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**